ከድኅነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ

# በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ፅሁፎች


አርታኢ

ሺፈራው በቀለ



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

Forum for Social Studies

# ከድኅነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ስትውልድ ማስተሳሰፍ

## በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ፅሁፎች

አርታኢ
ሺፈራው በቀለ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

© 2006 ዓ.ም. ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

አዲስ አበባ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፦ ቆንጅት በለጠ

ISBN 13: 978-99944-50-50-3

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲ
ፖ.ሳ.ቁ 25864 code 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ: www.fssethiopia.org.et

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም አስችኳይ ተቋማዊ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ፡፡

# ማውጫ


ምስጋና v

መቅድም vi

ቀዳሚ ቃል:- viii
ባህሩ ዘውዴ

መግቢያ:- xii
ሺፈራው በቀለ

**ክፍል ፩ ተቋም ግንባታ** xix

**ከበደ ፍሬ ሰንበት** ፣ ዘመናዊ ትምህርት በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ 1

**Semret Medhane**, National Air Carriers as Catalysts for Development: The Case of Ethiopian Airlines (ET) 25

**በትሩ አድማሴ**፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ምስረታና እድገት እስከ 1966 ዓ.ም. 47

**ተፈራ ደግፌ**፣ የባንክ እድገት ለአገሪቱ ግንባታ ያደረገው አስተዋጽኦ 63

**ተፈራ ኃይለ ሥላሴ**፣ የኢንዱስትሪና የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር እድገት 83

**ክፍል ፪ ዘመናዊ ሙያዎችን ማጐልበት** 109

**ነጋሽ ገብረማርያም**፣ ጆርናሊዝምና እድገት በኢትዮጵያ:- የግል ትዝታዎች 111

**ጥሩነህ ዜና**፣ የኢትዮጵያዊ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ አጀማመርና ሂደት (ከ1933-66) 157

**አስፋው ዳምጤ**፣ ትምህርት ፣ ባህልና እድገት:- የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት (1948-1996) 181

**መኰንን ተገኝ**፣ ተካ ኤገኖ፣ አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ተዋናይ 245

**ክፍል ፫ የተወረሱ ተግዳሮቶችን መቋቋም** 261

**ሽመልስ አዱኛ፣** ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983) 263

**ጠና አበረ፣** በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት

**ዘውዴ ገብረ ስላሴ፣** የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም አቀፋዊ ችግሮች 299

**ክፍል ፬ የሴቶች እንቅስቃሴ** 347

**እሌኒ መኩሪያና አለምሰገድ ህሩይ፣** የኢትዮጵያ ሴቶች በትምህርትና በስራ አለም (ከነጻነት እስከ አብዮት) 349

**ክፍል ፭ በእቅድ የመስራት ጅማሮ** 379

**አሸናፊ ሺፈራው፣** የኢኮኖሚ ፕላን በኢትዮጵያ መቼና እንዴት ተጀመረ? 381

**ደጃዝማች ወልደሰማአት ገብረወልድ፣** የአውራጃና የጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ሪፎርም (1955-1967) የግል ትዝታዎች 413

**መደምደሚያ** 475

**ስለደራሲዎቹ** 478

## ምስጋና

*ይህ መጽሀፍ ሲዘጋጅ አንዳንድ ድርጅቶችና ብዙ ሰዎች ትብብር አድርገዋል፤ ሁሉንም መጥቀስ ባይቻልም አንዳንዶቹን ማንሳት ተገቢ ነው። ከሁሉ በፊት የመጣጥፎቹ ደራሲዎች ሊመሰገኑ ይገባል፤ ጽሁፎቻቸውን ለማዘጋጀት ብዙ ለፍተዋልና። የቀድሞው የኤፍ.ኤስ.ኤስ. ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር፣ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፣ የውይይቱን መድረክ በማዘጋጀትና በኋላም ለዚህ መጽሐፍ ቀዳሚ ቃል በመጻፍ፣ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል፤ ምስጋና ይገባዋቸዋል። የኤፍ.ኤስ.ኤስ የአሁኑ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር፣ ዶ/ር ምህረት አየነው፣ መጽሀፉ እንዲታተም ከፍ ያለ ተነሳሽነት አሳይተዋል፣ የቀድሞው የኤፍ.ኤስ.ኤስ. የምርምርና የህትመት ጉዳዮች ዳይሬክተር ዶ/ር አስናቀ ከፍያለው፣ ከፍ ያለ ድጋፍ ሰጥተዋል፤ የኤፍ.ኤስ.ኤስ. የህትመት ኦፊሰር የሆኑት የወ/ሮ ቆንጅት በለጠ የማያቋርጥ ርዳታ፣ ማነቃቃትና ጉትጎታ ባይኖር ኖሮ ይህ መጽሐፍ የህትመት ብርሃን ማየቱ አጠያያቂ ይሆን ነበር፤ ለሁሉም፣ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።*

*ለመጽሐፉ ዝግጅትና ህትመት የገንዘብ እርዳታ ያደረገውን የሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም አስቾኳይ ተቋማዊ ድርጅት በእጅጉ ላመሰግን እወዳለሁ።*

***አርታኢው***

## መቀድም

ይህ መጽሀፍ የተለያዩ መጣጥፎች መድበል ነው፤ መጣጥፎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ.ኤስ.ኤስ) ባዘጋጀውና ከ1997-2000 ድረስ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ነበር፤ እያንዳንዱ ጽሁፍ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በውይይቱ ላይ የተነሱትን ጠቃሚ ሀሳቦች አካቶ ራሱን ችሎ እንዲታተም ተደርጓል፤ ይሁን እንጅ ከአንባቢዎች በተገኘው ግብአት መሰረት፣ ሁሉም ጽሁፎች አንድ ጋር ተሰባስበው፣ አርትኦት ተሰርቶባቸው እንዲታተሙ ስለተወሰነ እነሆ ቀርበዋል። የመጽሀፉ ርዕስ *ከድኅነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ* ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት <u>የተቋም ግንባታ</u> ሁሉንም መጣጥፎች የሚያገናኝ ክር መሆኑና ጸሀፊዎቹ በግንባታው ሂደት ውስጥ (በአንድም ደረጃም ሆነ በሌላ) ተካፋይ መሆናቸው ነው።

መጽሐፉ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ተደራጅቷል፤ ክፍል 2 ያለው አንድ ምዕራፍ ብቻ ቢሆንም፣ ጭብጡ (የሴቶች ጉዳይ) እጅግ ከፍ ያለ ስፍራ ስላለውና ከሌሎቹም ጭብጦች ስለሚለይ፣ ለብቻው እንዲሆን ተወስኗል። በኤፍ ኤስ ኤስ የውይይት መድረክ ላይ ከቀረቡት ጽሁፎች ውስጥ ሶስቱ አልታተሙም፤ ሁለቱ የአቶ ጌታቸው በቀለ (የባህር ክፍልን ማቋቋም) እና የአቶ ጌታቸው ማህተመስላሴ (አዲስ አበባን ለማሳደግ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የተደረገ ጥረት) ከዚህ በፊት ስለታተሙ፣ እንደገና ማሳተሙ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው፤ አንባቢ ከፈለገ፣ በየቤተ መጻህፍቱ ሊያገኛቸው ይችላል፤ ሶስተኛው የወ/ሮ ጽዮን ሚካኤል አንዶም ንግግር ሲሆን እሳቸውም በጽሁፍ ሳይሆን በቃል ስላቀረቡ ሊታተም አልቻለም።

ይህንን መጽሀፍ ስናዘጋጅ አንዱ ትልቅ ችግር የአማርኛ ሞግሼ ሆሄያት ጉዳይ ነው። ስለሞግሼ ሆሄያት አጠቃቀም፣ ሁሉንም የሚያስማማና መሪ ሊሆን የሚችል ማጣቀሻ መጽሀፍ የለም፤ ያለው አማራጭ ውሳኔውን ለደራሲው መተው ነው፤ በዚሀ የተነሳ፣ የሆሄያት አጠቃቀም ዝብርቅርቅ ያለ ሆኗል። ሌላው የአርትኦት ችግር፣ የተለያዩ ጸሀፊዎች የሚጠቀሙበት የአጻጻፍ ዘዴ ወይም ስታይል ነው። የሰዋስው ጉዳይም ያለቀለት ነገር አይደለም። አንዳንዴ የደራሲውን ስታይል ለመጠበቅ ሲባል አርትኦት በቅጡ ያልተካሄደባቸው ምእራፎች አሉ፤ እንደምሳሌ አድርጌ ልጠቅስ የምፈልገው፣ የመጨረሻውን፣ በደጃዝማች ወልደሰማእት ገብረወልድ የተጻፈውን መጣጥፍ ነው። የዚህ አይነት አጻጻፍ በ1940ዎቹ የተለመደ ነበር። ሶስተኛ ተግዳሮት ስርአተ ነጥቦችን ይመለከታል። የስርአተ ነጥቦች አጠቃቀምን አስመልክቶ፣ ልክ እንደ ሞግሼ ሆሄያቱ፣ በቋንቋው ሊቃውንት ዘንድ ሙሉ መግባባት የለም። ነጠላ ሰረዝንና ድርብ ሰረዝን የአማርኛ ሊቃውንት በተለያየ ሁኔታ ሲጠቀሙበት ይታያል።

በነዚህ ምክንያቶች፣ አንባቢ በየመጣጥፎቹ ውስጥ የሚያገኛቸው የሞግሼ ሆሄያት አጠቃቀም፣ የስርዓተ ነጥብ አሰፋፈር፣ የሰዋስው ሁኔታ የተለያዩ፣ አንዳንዴም የተዘበራረቁ ሆነው ሊያገኛቸው ይችላል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ለማቃናት አስቸጋሪ እንደሆነብኝ ይገነዘባል ብዬ አምናለሁ። ከዚህ ሌላ፣ አንባቢን እንዲረዳ በማለት፣ አስፈላጊ በመሰለኝ ስፍራ፣ ለአንዳንዶቹ መጣጥፎች ማብራሪያዎች ወይም ገለጻዎች ወይም ዋቤ መጻህፍት በግርጌ ማስታወሻ አስፍሬአለሁ።

***አርታኢው***

## ቀዳሚ ቃል

ታሪክ የለውጥና የቀጣይነት ኅብር ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ እንዳለ የሚቆይ ነገር የለም፤ ሙሉ በሙሉ የሚለወጥም እንዲሁ፡፡ በነበረው መሠረት ላይ አዲሱ ሲገነባ የቀድሞውን እሴትና የአዲሱን ክስተት በማቀናበር ኅብረተ-ሰባዊ ዕድገትን ማምጣት ይቻላል፡፡ አደጉ በተባሉት አገሮች፣ አብዮት የተካሄደባቸው ሳይቀር፣ የታየው ሁኔታም ይኸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ብዙውን ጊዜ በአርአያነት የሚጠቀሰው የእንግሊዝ ኅብረተ ሰብ ነው፡፡ የለውጥ ተምሳሌት የሆነው የኢንዱስትሪ አብዮት የተካሄደባት እንግሊዝ በሚያስደንቅ ሁኔታ ቀጣይነትም የሚታይባት አገር ናት፡፡ ይህም በጉልህ በሚታየው በዘውዳዊ ሥርዓቷ ብቻ አይደለም፤ በዕለት ዕለት ኑሮም ጭምር እንጂ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1983 ዓ.ም. ከሰባት ዓመት ቆይታ (እና ከብዙ የኑሮ ውጣ ውረድ) በኋላ ተመልሼ ወደ እንግሊዝ ስሄድ በእጅጉ የደነቀኝ ነገር ቢኖር በመሓል ለንደን በሚገኘው ረስል ስኲዌር ተብሎ በሚታወቀው ባቡር ጣቢያ የነበረው ቲኬት ሰብሳቢ ያው፣ በቀድሞ ኮሌጁ ካፌቴሪያ ‹‹ከሪ›› የተባለውን ሕንዳዊ ወጥ የምትጨልፈው ባልቴትም ያው ሆነው ማግኘቴ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም ብትሆን በተለይ በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ ቀጣይነት በአያሌው የሚታይባት መሆኗ እምብዛም አያጠያይቅም፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ ብዙ ማኅበራዊ እሴቶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል መረዳዳት፣ ታላቅንና አረጋውያንን ማክበር፣ ግብረ ገባዊ ጨዋነት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ቀጣይነት እምብዛም የማይታየው በፖለቲካ/ፖሊሲ ረገድ ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት ሀገሪቱ ሩብ ምዕተ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለቴ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ማካሄዷ ነው፤ መጀመሪያ በ1966፣ ቀጥሎ ደግሞ በ1983፡፡ ሁለቱም ለውጦች ያለፈውን ሥርዓት በመኰነን አዲስ ሰውና አዲስ ኅብረተ ሰብ ለመፍጠር ያለሙ ክስተቶች ነበሩ፡፡ በ1966 አብዮት ማግስት ‹‹አሮጌ›› መጻሕፍት መቃጠል አለባቸው፣ የለባቸውም በሚል ባንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ቋሚ ተጠሪና በታሪክ ምሁር መካከል የተካሄደውን አስገራሚ የቴሌቪዥን ክርክር ብዙዎቻችን የምናስታውሰው ጉዳይ ነው፡፡ በሁለተኛው የሥርዓት ለውጥ ዋዜማና ማግስትም እንዲሁ ቀደምት ሰነዶችና መዛግብትን እንደዋዛ የማየት አዝማሚያ ታይቶ ነበር፡፡ ባጠቃላይ የሥርዓት ለውጥ ሲደረግ ‹‹ከዜሮ ነው የምንጀምረው›› የሚል መርህ የሚሰፍን ይመስላል፡፡

ይሁን እንጂ በተለይ ከ1933 እስከ 1966 ያሉት ዓመታት እስካሁንም ከኛ ጋር ያሉ የዘመናዊት ኢትዮጵያ የሥልጣኔ አውታሮች የተመሠረቱበት ዓመታት ነበሩ፡፡ በስኬታማነቱ ባገሪቱ ውስጥ ምናልባትም ወደር የማይገኝለትና በአፍሪቃም ቀዳሚ ከሆኑት የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ተርታ ሊሠለፍ የበቃው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የተቋቋመው በ1938 ዓ.ም. ነው፡፡ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በዘመናዊ መልኩ የተደራጀው፣ የጋዜጠኝነት ሙያ መስፋፋት የጀመረው፣ ዘመናዊ የባንክ አገልግሎት መስጠት የተጀመረውም በነዚሁ ዓመታት ነው፡፡ በዚሁ ዘመንም ነው አሁን እንደገና

እያንሠራራ ያለውን የወባ መቅሠፍት በመቆጣጠር ረገድ አመርቂ ውጤት ሊመዘገብ የተቻለው፡፡

እንግዲህ ይህን እውነታ በማጤን ነው የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ፎረም ፎረ ሳሻል ስተዲስ) በ1997 ዓ.ም. ‹‹ከድኅነት ወደ ልማት፣ ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ›› በሚል ርዕስ አንድ የሕዝባዊ ውይይት መድረክ ለመጀመር የተነሣሣው፡፡ ድርጅቱ በ1990 በጥቂት ምሁራንና የሲቪል ማኅበረሰቡ መሪ ተዋናዮች አነሳሽነት ሲመሠረት ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሣው ፖሊሲ-ነክ ምርምር በማካሄድና በነዚህና በሌሎች መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ውይይት በማዘጋጀት መንግሥት በልማትና መልካም አስተዳደር መስክ ለሚያደርገው ጥረት አጋዥ ኃይል ለመሆን ነው፡፡ ምርምር እንደ በፊቱ በዩኒቨርሲቲ ቅፅር ታጥሮ የሚቀር ሳይሆን ለሕዝብና ለፖሊሲ አውጭዎችና አስፈፃሚዎች በቀላሉ መድረስ አለበት የሚል እምነት ነው የድርጅቱን መሥራቾች ያነሳሳው ሐሳብ፡፡ ድርጅቱ መጀመሪያ የሥራ መርሀ ግብሩን ሲቀርፅም አያሌ ፖሊሲ-ነክ የሆኑ የምርምርና የውይይት ርዕሶች የደረደረ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል አንዱ ይኸው ዕውቀትን ለትውልድ የማስተላለፍ ፕሮግራም ነበር፡፡

ሆኖም ድርጅቱ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በተለይ አንገብጋቢ በነበሩት የምግብ ዋስትና፣ የድኅነት ቅነሳና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ተጠምዶ ስለነበር ይህን ፕሮግራም ለሰባት ዓመታት ያህል ቅድሚያ ሊሰጠው አልቻለም ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ይህን ፕሮግራም ጥር 20 ቀን፣ 1997 ዓ.ም. አቶ ሽመልስ አዱኛ ‹‹ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)›› በሚል ርዕስ ባደረጉት ንግግር ጀምሯል፡፡ ፕሮግራሙ በዚህ የተጀመረውም አለምክንያት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያን ባለፉት ሃምሣ ዓመታት በእጅጉ ፈትኖ የያዛት ነገር ቢኖር የምግብ ዋስትና ጉዳይ በመሆኑ እንጂ፡፡ ስለዚህም ለዘመናት የኢትዮጵያውያንን ኑሮ ጎስቋላ አድርገው የቆዩትን ድርቅንና ረሀብን ለመጀመሪያ ጊዜ በተደራጀ መልኩ ለመቋቋም ታስቦ የተመሠረተውን የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የመሩት አቶ ሽመልስ አዱኛ ፕሮግራሙን እንዲቀድሱት ማድረጉ ተገቢ ነበር፡፡ ከዚያ በመቀጠልም በተለይ በአሁኑ ወቅት የመላ ኢትዮጵያውንን ትኩረት የሳበውን የአባይ ተፋሰሶች ጉዳይ በምሁርነታቸውም ሆነ በመንግሥት ባለሥልጣንነታቸው ብዙ ያሰቡበትንና የደከሙበትን ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴን በመጋበዝ ሕዝቡ በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ተችሏል፡፡

እንዲህ እያለ በየሁለት ወሩ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስምንት ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ፕሮግራሙ በ1999 መጀመሪያ ላይ ተገባዷል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ አመራር ፕሮግራሙ ከፍተኛ ተወዳጅነት ማፍራቱን በመገንዘቡ እንደገና ለሁለተኛ ዙር እንዲቀጥል በወሰነው መሠረት፣ ከመስከረም 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ግንቦት 8 ቀን 2000 ዓ.ም ተጨማሪ አሥራ አንድ ተናጋሪዎች ልምዳቸውን ሊያካፍሉና ለሕዝቡም ከፍተኛ ግንዛቤ

ሊያስጨብጡ ችለዋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ዙር የተጀመረው በታዋቂው አንጋፋ እንተርፕረነር ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ ነበር፡፡ እንዲህ እንዳሁኑ ከመቅፅበት ሚሊዮኔር ለመሆን በማይቻልበት ጊዜ፣ በረጅም ጊዜ ጥረትና ትጋት፣ ‹‹ከቡትቶ ወደ ሀብት ፀጋ›› (በእንግሊዝኛው አባባል "from rags to riches") ማደግ የቻሉት የተካ ኤገኖ የሕይወት ታሪክ ታዳሚውን በእጅጉ ያስደመመ ገድል ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የዙሩ ማሳረጊያ ደግሞ ከአብዮት በፊት አብዮተኛ የነበሩት የደጃዝማች ወልደ ሰማዕት ገብረ ወልድን የአስተዳደር ማሻሻል ጥረት ታሪክ ነበር፡፡

ለአብነት አንዳንዶቹን ንግግሮችና ውይይቶች ጠቀስን እንጂ፣ አድማጭ ጠቃሚ ትምህርት ሳያገኝበትና የሙያና የዕውቀት ቀጣይነትን በቅጡ ሳይገነዘብ የወጣበት ምሽት አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም አንዱ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው ጉዳይ የሚቀርቡት ጽሑፎችና የሚደረገውም ውይይት በአማርኛ መሆኑ ነበር፡፡ በተለይ ውይይቱ ለአብዛኛው ታዳሚ አፍ መፍቻ በሆነው በአማርኛ መሆኑ ብዙ ሐሳቦችና የተለያዩ አመለካከቶች እንዲንሸራሸሩ ረድቷል፡፡ ሌላው የፕሮግራሙን መሪዎች ሁልጊዜም ያስደንቅ የነበረው ጉዳይ፣ ጽሑፍ አቅራቢዎቹ ጽሑፋቸውን ለማሰናዳት ያሳዩ የነበረው ትጋትና ይወስዱት የነበረው ጥንቃቄ ነበር፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን በጥልቀት ከመመልከታቸውም በላይ ያለፉበትን ዘመን በስፋት ማተታቸው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ድርጅቱ ይህን ስብስብ በሚያዘጋጅበት ወቅት አንዳንዶቹን ጽሑፎች በተቻለ መጠን ትርጉማቸውንና የሐሳብ ፍሰታቸውን ሳያፋልስ በመጠኑ ለማሳጠር የተገደደው፡፡ ይህን ባያደርግ ኖሮ አሁን ለሕትመት የበቃው ጥራዝ ከዚህም የበለጠ ደጎስ ያለ ይሆን ነበር፡፡

የመርሀ ግብሩ መሠረታዊ ዓላማ ‹‹ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላላፍ›› በመሆኑ በተቻለ መጠን ያሁኑ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ተረካቢውም ትውልድ፣ ማለትም ወጣቱ፣ በዝግጅቶቹ እንዲሳተፍ ልዩ ጥረት ተደርጎ ነበር፡፡ ይህም ከሞላ ጎደል የተሳካ ለመሆኑ በየፕሮግራሙ የሚገኙት ወጣት ተሳታፊዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከቶም የማይረሳኝ ትውስታ፣ አቶ ጌታቸው ማኀተመ ሥላሴ ስለ አዲስ አበባ የዕድገት እንቅስቃሴ በተመለከተ (አሁን ሊተገበር በዝግጅት ያለውን የከተማ የባቡር አገልግሎት ፅንሰ ሐሳብ ጨምሮ) ንግግር ካደረጉ በኋላ በሪሰፕሽኑ ወቅት ዙሪያውን በወጣቶች ተከበው ያደርጉ የነበረው የሞቀ ውይይት ነበር፡፡ ይህ ታሪካዊ አጋጣሚ በቪዲዮ እንዲቀረፅ በማሰብ ለምሽቱ የቀጠርናቸውን ባለሙያዎች ዞር ዞር ብዬ ብፈልግ የአዳራሹ ውይይት እንደተጠናቀቀ ሄደው ኖሮ በሞባይል ካሜራዬ ከመቅረፅ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ይህንንም በማድረጌ ያ ፎቶ ጽሑፉ ታትሞ በሚሠራጭበት ወቅት ተገቢ ሥፍራውን ለማግኘት ችሏል፡፡

እንግዲህ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ አሁን አሰባስቦ ባንድ ጥራዝ ያሳተመው ሦስት ዓመት የፈጀውንና የአያሌ ኢትዮጵያውያንን ቀልብ የሳበውን የሕዝባዊ ውይይት መርሀ ግብር መነሻ የነበሩትን ሃያ የሚያህሉ ጽሑፎች ነው፡፡

የጽሑፎቹ እንዲህ ባንድ ጥራዝ ተሰባስቦ መቅረብ ቀደም ብለው በተናጠል በታተሙበት ወቅቱ ሁሉንም ላላገኙ አንባቢዎች ባንድነት እንዲያገኟቸው ይረዳሉ። ፖሊሲ አውጭዎችና አስፈፃሚዎችም በየተሰማሩበት ዘርፍ ቀደም ሲል የተደረጉትን እንቅስቃሴዎች እንዲያጤኑ በማገዝ፣ አገራችን ለምታደርገው የልማት እንቅስቃሴ አጋዥ ይሆናሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

*ባሕሩ ዘውዴ (ፕሮፌሰር)*

**የፎረሙ የቀድሞ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር**

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የትውስታ መጽሐፍ ነው፡፡ ትውስታውም ኢትዮጵያ ከነጻነት (1933) እስከ አብዮት (1966) ድረስ ባሉት አመታት ስለገነባቻቸው የልማት ተቋማት ነው፡፡ መጽሀፉ ተቋማቱ ለምን ተገነቡ? እንዴትስ ተገነቡ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡ እዚህ መጽሀፍ ውስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ምዕራፎች የተጻፉት በወቅቱ ተቋማቱን በመግንባት ስራ ላይ በተካፈሉ ሰዎች ነው፡፡ እያንዳንዱ ተካፋይ የተቋሞቹን ግንባታ በራሱ አነጋገር ቢገልጸውም፣ አላማው ባጭሩ በሀገሪቱ ተከታታይነት ያለው ዘላቂ ልማት ለማምጣት መሰረቱን በየመስኩ ለመጣል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ጉዳዩ ዞሮ ዞሮ ኢትዮጵያን ዘመናዊ ሀገር ማድረግ ነው፡፡

ዘመናይ የማድረግ እንቅስቃሴ ዝመናን (Modernization) ያመጣል፤ ዝመና ከመጣ በሁዋላ ዘመናዊነት (Modernity) ይሰፍናል፤ ዘመናዊነት ሲሰፍን አገራችን "ከሰለጠኑት" ወይም "ከለሙት" ወይም "ከአደጉት" አገሮች ተርታ ትመደባለች፡፡ ዝመናን የሚያስበውን፣ የሚያቅደውንና በሥራ የሚተረጉመውን መሪ አዘማኝ (Modernizer) ብሎ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ ለዚህ አይነቱ ለውጥ "ዝመና" የሚለውን ቃልና ተዛማጅ ጽንሰ ሀሳቦችን ብቻ ተጠቅሞ አያውቅም፡፡ ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ እንደሚባለው፣ የዝመና ሂደት የተጀመረው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አውሮፓውያን በመጀመሪያ ከቀያይ ህንዶች ጋር (በላቲንና በመካከለኛው አሜሪካ)፣ ቀጥሎ ከኤስያ ህዝቦች ጋር፣ በመጨረሻም ከአፍሪካውያን ጋር ስፋት ባለው መልክ መገናኘት ሲጀምሩና ጥልቅ ተጽእኖ ማሳረፍ ሲጀምሩ ነው፡፡ በዚያን ወቅት፣ የለውጡ ባህርይ ይገለጽ የነበረው "መሰልጠን" (to be civilized) "ማሰልጠን" (to civilize) በሚሉት ቃላት ሲሆን ዋናው ጽንሰ ሀሳብ "ስልጣኔ" (Civilization) ነበር፡፡ አፍሪካውያን ወይም ቀያይ ህንዶች ወይም የፓሲፊክ ደሴቶች ነዋሪዎች "ያልሰለጠኑ" ተብለው ሲፈረጁ (በእንግሊዘኛ savage or primitive የሚሉትን ቃላት ይጠቀማሉ)፣ አውሮፓውያንና ሰሜን አሜሪካኖች የሰለጠኑ ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ይህ አገላለጽ በቅኝ ግዛት ዘመን በሰፊው ስራ ላይ ውሏል፡፡ በአገራችንም እስከጣልያን ወረራ ድረስ የነበሩት ምሁራን፣ የመንግስትና የፖለቲካ ሰዎች የሚጠቀሙት እነዚያኑ ጽንሰ ሀሳቦች ነበር፡፡ እስከ 1928 ዓ.ም. ድረስ የተጻፉ መጻህፍት ውስጥ ስለስልጣኔ እና ስለመሰልጠን ብዙ ተብሏል፡፡ በዚያ ዘመን ተወልደው ያደጉ ሊቃውንት ወይም የፖለቲካ ሰዎች፣ አንዴ ስለለመደባቸው ከጣልያን በኋላ (ከ1933 ዓ.ም በኋላ) ቢሆንም የሚጽፉት፣ ያው እንደበፊቱ መሰልጠን፣ ስልጣኔ በተሰኙት ጽንሰ ሀሰቦች ዙሪያ ስለልማት ያላቸውን አስተሳሰብ አደራጅተው ማቅረብ ይቀናቸው ነበር፡፡ ምናልባት፣ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት፣ ከበደ ሚካኤል የተባሉ የስነጽሁፍ ሰው፣ የታሪክ ጸሀፊ፣ የልማት ሀሳቢ እና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ናቸው፡፡ ከጻፏቸው አያሌ መጻህፍት ውስጥ *ስልጣኔ ማለት ምንድንች? ጃፓን እንዴት ሰለጠነች? የስልጣኔ አየር* የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡ ከበደ ሚካኤል እነዚህን መጻህፍት በሚጽፉበት ጊዜ ዋናው ጽንሰ ሀሳብ፣ ልማት

(Development) ሆኖ ነበር፤ መሰልጠን/አለመሰልጠን የሚሉት ሀሳቦች ጊዜያቸው ያለፈባቸው ተደርገው ይቆጠሩ ነበር።

ትልቅ የጽንሰ ሀሳብ ለውጥ የመጣው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ መጀመሪያ አሜሪካኖች፣ ለጥቆ የተባበሩት መንግስታት፣ ልማት (Development) የተሰኘውን ቃል ተቀብለው ለአለም ሲያሰራጩት ነው። የምእራብ አገሮች “የለሙ” ሲባሉ፣ የአፍሪካ ፣ የኤስያና የላቲን አሜሪካ አገሮች (በመሀከላቸው እጅግ ሰፋፊ ልዩነት ቢኖርም) “ያልለሙ” ወይም Underdeveloped ፣ “ወደኋላ የቀሩ” ወይም backward ተብለው ተፈረጁ። በ1960ዎቹና 70ዎቹ “ያልለሙ” ወይም underdeveloped ፣ ወደሁዋላ የቀሩ ወይም backward የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ትክክል አይደለም ተብሎ ተተቸ፤ ይልቁንም ልክ እንደበፊቶቹ ጽንሰ ሀሳቦች (ያልሰለጠኑ ወይም primitive) የደቡብ ሀገሮችን የበታችነት ይጠቁማሉ በማለት የሰላ ሂስ ቀረበ፤ በዚህም ምክንያት፣ “ያልለማ” “በመልማት ላይ ያለ” (ወይም Developing) በሚሉት ቃላት ተተካ፤ እስካሁንም ድረስ በመልማት ላይ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ተቀባይነት አለው። ቢሆንም፣ በደቡብ ሀገሮች መሀከል አሁንም ሰፊ ልዩነት ስላለ፣ እጅግ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ የልማት ደረጃ ላይ ያሉትን አገሮች Least Developed Countries (LDCs) በማለት መፈረጅ የተለመደ ነው።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ፍጻሜ ተከትሎ ከመጣው ጽንሰ ሀሳባዊ ለውጥና የእውቀት እድገት ጐን ለጐን አዲስ ቲዎሪ ተፈልስፎ ለሶስት አሰርት ያህል የበላይነቱን ይዞ ቆይቷል፤ ይህም የዝመና ቲኦሪ (Modernization theory) የሚባለው ነው። የዝመና ቲኦሪን ደግሞ post modernism የሚለው በቅርብ አመታት ተካው። የዝመና ቲኦሪ የለውጡን ባህርይ ለመግለጽ የሚሞክር ነው። ለምንድነው የተወሰኑ የአለም አገሮች ወደኋላ የቀሩትና ለመዘመን የሚገደዱት? የለውጡስ ባህርይ ምንድነው? የዝመና ቲኦሪን ተንተርሰን እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክርም። እዚህ መጠቀስ ያለበት፣ ዝመና ተባለ ልማት፣ ለውጡ እጅግ ስር ነቀል፣ ሁሉንም የተወረሱ የኑሮ፣ የባህል፣ የርእዮተ ዓለም፣ የምርት፣ የውጊያ፣ የግንኙነት ዘርፎችን ወደጐን አድርጐ በቦታቸው “ዘመናዊ” የኑሮ፣ የባህል፣….ወዘተ ሁነቶችን የሚተካ መሆኑን ነው፤ ለውጡም አንዳንዴ አዝጋሚ፣ ሌላ ጊዜ ፈጣን፣ አንዳንዴ ሰላማዊ፣ ሌላ ጊዜ በግጭት የተሞላ ይሆናል። ባጭሩ፣ ዝመና “ለምዕራባዊነት” (Westernization) የተሰጠ ሌላ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በደቡብ የዓለም ክፍል የሚገኙ ማህበረሰቦች የኑሮ ሁኔታቸውን በሙሉ ቀይረው ከሰሜኑ በተወረሱ ቴክኖሎጂዎች ወይም በምርታቸው መተካት ነው። በአሁኑ ጊዜ አለም እጅግ እየተመሳሰለ መጥቷል። ከኒውዮርክ እስከ ሻንግሀይ፣ ከኖርዌይ እስከ ደቡብ አፍሪካ ሰው ቢጓዝ፣ የሚያገኛቸው ሰዎች የኑሮ ሁኔታ፣ የሚያርፍባቸው ሆቴሎች፣ የሚጠቀምባቸው ቴክኖሎጂዎች በሙሉ ተመሳሳይ ናቸው። ምናልባት ቢቀየር አለባበስና ቋንቋ ነው። አንዳንድ ማህበረሰቦች ልብስን የማንነት መገለጫ አድርገው ስለሚወስዱት፣ የወረሱትን የልብስ አይነት “በዘመናዊ” እስታይልና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አሰርተው ይለብሱታል፤ በተረፈ ሌላው ነገር ሁሉ ያው ነው። ይህ

የመመሳሰል ሂደት (Homogenization) የመነጨው ከዝመና ሲሆን ሙሉ Homogenization ለማምጣት የዓለም ህዝቦች ሁሉ መልማት አለባቸው፡፡ ልማት ደግሞ በአንዴ የሚደረስበት ሳይሆን ትውልዶች እየተፈራረቁ፣ እየወደቁ እየተነሱ፣ እየተፋለሙ እየተጋጩ፣ በመጓዝ የሚቀዳጁት ዋንጫ ነው፡፡ የልማት ሂደት የሚካሄደው ደረጃ በደረጃ ነው፤ ኢትዮጵያ ያለችው ገና ጅምሩ ላይ ነው፤ ይህም የሆነው የዝመናን ሂደት የጀመረችው በቅርቡ፣ ማለትም በ20ኛው ክፍለ ዘመን መሀከል ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ጋር ሲወዳደር፣ እጅግ ብዙ ሀገሮች በጣም ቀድመዋት ነበር ሂደቱን የጀመሩት፡፡ ለምሳሌ ቻይና የለውጡን ሂደት የተያያዘችው በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሲሆን፣ በምዕተ ዓመቱ ሁለተኛው አጋማሽ ላይ የባቡር መረብ፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች የገነባች አገር ነበረች፤ በ1880ዎቹ ነበር የሻንግሀይ የአክስዮን ገበያ (Stock exchange) የተቋቋመው፡፡ በቅርብ ካሉት ሀገሮች ግብጽን ብንወስድ፣ በ1800 መባቻ ላይ ዝመናን በምር እንደጀመረች በሰፊው ይታወቃል፡፡ አዘማኙ መሪም የታወቀው ሞሀመድ አሊ ፓሻ አል-ማሱድ ኢብን አጋ (እ.ኤ.አ 1805-1848) ሲሆን በኢትዮጵያ የእሱ አቻ አፄ ኃይለሥላሴ (1909-1922 እንደአልጋ ወራሽ፣1923-1967) ነበሩ፡፡ ምን ያህል ኢትዮጵያ ዘግይታ እንደጀመረች በዚህ ይታወቃል፡፡

ምናልባት በዚህ የተነሳ በ1960ዎቹ የተነሱት ወጣት ምሁራን የኢትዮጵያ ወደኋላ መቅረት በጣም ያሳስባቸው ነበር፤ መነሻቸው "ልማት ሂደት ነው፤ ዝመና የዘመናት ጉዞ ነው፤ ልማትም እንበለው ዝመና እንደ ህንጻ ግንባታ አንዱ በአንዱ ላይ እያከለ፣ በጡብ ላይ ጡብ እየገነባ፣ የሚሄድ እድገት ሲሆን የእድገቱም መጨረሻ የለሙት ሀገሮች ተርታ መግባት ነው፤" የሚለው አስተሳሰብ አይደለም፤ ለነሱ አፄ ኃይለሥላሴ ይመሩት የነበረው ስርአት "ወደኋላ የቀረ፣ የአረጀ የአፈጀ፣ የበሰበሰ የፊውዳሊዝም ስርአት ነው፤" ወይም ደግሞ "ስርአቱ ጨቋኝ፣ ኋላ ቀር፣ በዝባዥ ፊውደ ቡርዧ ስርአት ነው፤" የተሸኘው አመለካከት መነሻቸው ነበር፡፡ በዚህም አይነት አገላለጽ አቀረቡት በሌላ አይነት፣ ይዘቱ አንድ ነው፤ የሀሳባቸው መነሻና መድረሻ የስርአቱን ዳይናሚዝም አይቀበልም፤ ስርአቱ በመለወጥ ላይ የነበረ፣ እንዲያውም በረዥሙ የልማት ጉዞ የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የነበረ፣ በዚህ ጊዜ የሚደረጉት ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች የልማት መሰረቶችን መገንባት እንደሆነና ወደፊት የሚመጡት የኢትዮጵያ መንግስታት በዚህ መሰረት ላይ እንደሚገነቡ አያገናዝብም፡፡ ከሚነሱትና ከሚያጨቃጭቁት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ለምን አገሪቱ ወደኋላ ቀረች የሚለው ነበር፤ ለዚህ ጥያቄ በዘር ላይ ወይም በመደብ ላይ ወይም በሁለቱም ላይ የተዋቀረ መልስ ይሰጣሉ፤ ለአያሌ ምዕተ አመታት የሚገዛው አማራ ስለነበረ የአማራው ገዢ መደብ ትኩረቱ ብዝበዛ ላይ እንጂ ግንባታ ላይ ስለአልነበረ፣ አገሪቷ ወደኋላ ልትቀር ችላለች፡፡ ይህ አስተሳሰብ "መደብ" የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በመጠቀም በተመሳሳይ ሁኔታ ይገለጻል፤ "የፊውዳሉ የገዢ መደብ" ላይ ወቀሳው ሁሉ ይወድቃል፤ ነገሩን ለማባባስ "ብዙ ጊዜ ጦርነት በአገሪቱ መደረጉ" ይጠቀሳል፡፡ ይህ ትልቅ ሙግት በተማሪዎች

ንቅናቄ ጊዜ በስፋት ስለተገለጸና ደርግም ሆነ የኢህአዴግ መንግስቶች ተቀብለውት ስለሚያሰራጩት እጅግ ከፍ ያለ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የኢትዮጵያ ሁዋላ ቀርነት ሊያስደንቀን አይገባም፤ ሁሉም - እደግመዋለሁ ሁሉም- የጥቁር አፍሪካ ህብረተሰቦች “ሁዋላ ቀር” ነበሩ፡፡ በዛሬ ጊዜ አጠራራቸው ከሱማሊያ እስከ ሴኔጋል፣ ከኒጀር እስከ ደቡብ አፍሪካ የነበሩት ህብረተሰቦች ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ነበሩ ባይባልም፣ ከዳር እስከዳር፣ ከኢትዮጵያ የበለጠ ጨርሶ አልነበሩም፤ ከኢትዮጵያ የተሻለ የምርት፣ የትራንስፖርት፣ የጦርነት፣ የኑሮ ቴክኖሎጂ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያው ስርአት ምን ታይቶበት ነው ለወቀሳ የሚዳረገው? የአፍሪካውን ወገን ትተን ወደምስራቅ የኢትዮጵያ ጐረቤቶች ብንመለከት፣ አሁን ሳኡዲ አረብያ ተብሎ የሚጠራው ሀገር ማህበረሰቦችም ሆኑ አሁን የመን በመባል የሚታወቀው ሀገር ህብረተሰብ እንዲሁ “ሁዋላ ቀር” ተብለው ይፈረጁ ነበር፡፡ ባጭሩ የኢትዮጵያ “ሁዋላ ቀር” መሆን የሚያስደንቅም፣ የተለየም አልነበረም፡፡ ለምን “ሁዋላ ቀር’’ ሆነች የሚለው ጥያቄ ከተነሳም፣ መልሱ ኢትዮጵያ ተለይታ የምትጠይቅበት ምክንያት አለመኖሩን በአጽንኦት ከመለሱ በኋላ መልሱን ለማግኘት ጥያቄውና ምርምሩ በሰፊ መነጽር እንደሚከተለው መታየት አለባቸው - ለምንድነው የተወሰነው የአለም ክፍል (ማለትም አውሮፓ) ወደፊት እየገሰገሰ የሚሄድ ህብረተሰብና ስርአት የገነባው? በአንጻሩ ደግሞ ለምንድነው ሌሎቹ የተወሰኑ የአለም ክፍሎች (ማለትም የአፍሪካ፣ የላቲን አሜሪካ የቀያይ ህንዶች ህብረተሰብና ስርአት) ዘገምተኛ የነበሩት? ይህ ጽሁፍ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አይዳዳውም፡፡ ጥያቄዎቹ የተነሱት የጥናት መነሻ ለውጥ እንዲኖር ለመሟገት ነው፡፡ የጥናቱ መነሻ ኢትዮጵያ ዝመናን እንደግብጽ ወይም እንደ ህንድ ወይም እንደ ቻይና (ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል) ለምን ቀድማ አልጀመረችም የሚለው ጥያቄ አይደለም፤ ይህ ጥያቄ በሌላ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡- ኢትዮጵያ ዝመናን ስራዬ ብላ ለመያያዝ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ለምን ዘገየች? የዚህ ጥያቄ መነሾ ቀደም ብላ ጀምራ ቢሆን፣ አሁን ረጅም ጉዞ ተጉዛ እናገኛት ነበር የሚለው ህልዮታዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ለታሪክ ጥናት ወሳኙ ጉዳይ ህልዮታዊ አስተሳሰብ ሳይሆን መቼ? ምን ሆነ? እንዴት ሆነ? ለምን ሆነ? ይህስ ምን አስከተለ? የሚሉት የመርህ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዚህ አይነት መነጽር ስናይ፣ የሚከተለውን ታሪካዊ ስዕል እናገኛለን፡፡

በኢትዮጵያ የታሪክ መጻህፍትም ሆነ በተማረው ህዝብ በኩል ምኒልክን አዘማኝ አድርጐ መቁጠር የተለመደ ነው፤ ሀቆችም ይደረደራሉ፡- ቴሌግራም አስገቡ፤ የባቡር መስመር አዘረጉ፤ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከፈቱ፤ ወዘተ፣ ወዘተ፡፡ እነዚህ ሀቆች እውነት ቢሆኑም፣ እንደሚታወቀው ንጉሠ ነገሥቱ ይሄንን ሁሉ ሲያደርጉ ቀጣይነት ባለው መልኩ፣ ተጠንቶና ታቅዶ በዘዴ (systematically)፣ ራእይ ሰንቆ አገሪቱን “ማሰልጠን” ሳይሆን፣ እንደአመጣጡ በተበታተነና ባልተቀናጀ መልክ ነበር፤ ፈረንጆች እንደሚሉት የአፄ ምኒልክ እርምጃዎች

“Spontaneous reaction” ነበሩ። ስለዚህ፣ አፄ ምኒልክን አዘማኝ ማለት ይከብዳል፤ ነገር ግን አፄ ኃይለ ሥላሴ የስልጣን መንበሩን ከያዙ በኋላ ስለ ዝመና በረጅሙ ማሰብ ተጀመረ፤ በጉዳዩ ላይ ጽሁፎችም ይታተሙ ጀመር፤ ሃይለሥላሴም ሆኑ ባለስልጣኖቻቸው በአደባባይ ንግግራቸው ውስጥ ይኸንኑ ጭብጥ መጨመር አዘወተሩ፤ ጋዜጦች ሳይታክቱ ስለዝመና መጻፉን ተያያዙት። ይህ እንግዲህ በአስተሳሰብ ደረጃ ነው።

በተግባር ደረጃም፣ ኢትዮጵያን ለማዘመን ከ1910 አካባቢ ጀምሮ ያላሰለሰ ጥረት ይደረግ ጀመር፤ በዚህም የተነሳ ከ1913 እስከ 1928 ድረስ በተወሰኑ አካባቢዎች ፈጣን ለውጥ መታየት ጀመረ - እነዚህም አካባቢዎች አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሀረር ከተሞች ነበሩ። እንዲያውም፣ በከተሞቹ ውስጥ ለውጡ በተወሰኑ ቦታዎች እጅግ ፈጣን ነበር፤ ለምሳሌ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ በጊዜው አራዳ የሚባለው ሰፈር (ዛሬ ጊዜ ፒያሳ የሚሰኘው) እጅግ ፈጣን ለውጥ በሁሉም መስክ ያስመዘግብ ነበር። ይህንን ክስተት፣ አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች “enclave capitalism” ብለው ሰይመውታል። ይህንንም ደሴታዊ ካፒታሊዝም ብለን በአማርኛ ልናቀርበው እንችላለን። ዙሪያውን በቅድመ ዘመናዊ ህብረተሰብ የተከበበ ዘመናዊ ኤኮኖሚ ማለት ነው። ይህ ለውጥ ጠባብ የነበረው መንግስት በቂ ገንዘብና የተማረ የሰው ሀይል ስላልነበረው ነው። ከዚህ ጐን ለጐን መንግስት ከፍ ያለ ተቋም ግንባታ ላይ ተሰማርቶ ነበር፤ የለውጥ አየር ባገሪቱ፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻም ቢሆን እንኳ፣ መንፈስ ጀምሮ ስለነበር፣ ሰው ከአገር ቤት ወደ አደስ አበባ ሲመጣ “ጉድ” እያለ ይመለስ ነበር፤ እንኳን የሩቁ፣ የከተማውም ነዋሪ በለውጡ ፍጥነት መደነቁ አልቀረም፤ ይሁንና ይህ መጋጋል የጀመረ የለውጥ እንቅስቃሴ በጣልያን ወረራ ተቋረጠ።

ፋሽስቶች የቅኝ መንግስት (Colonial state) ለመመስረት ቢጥሩም፣ ሰፊ ጦርነት ተከፍቶባቸው፣ በመገንባት ላይ የነበረው ስርዓት በ1933 ከስሩ ተመንግሎ ወደቀ፤ ስለዚህ አፄ ኃይለሥላሴ ወደመዲናቸው ሲመለሱ የቅኝ መንግስት (Colonial State) መዋቅር ውስጥ አልገቡም። ከጥቂት ሕንጻዎች በቀር፣ የወረሱት ነገር አልነበረም፤ የጣልያንን ግምጃ ቤት ከነገንዘቡ አላገኙትም፤ የተረፋቸው ህንጻው ብቻ ነበር። የአርበኞች ሰራዊት፣ ንጉሥ ነገስቱን አጅቦ፣ አዲስ አበባ ሲገባ፣ የጣልያን ባንኮች ከተዘጉ ቢያንስ አራት ሳምንት አልፏቸዋል። አዲሱ መንግስት ከጣልያኖች ምንም ጥሪት ሳይረከብ፣ የአዲስ መንግስት ግንባታ ስራውን “ሀ” ብሎ ጀመረ። ተቋም ግንባታ እንደገና እንደ አዲስ ተጀመረ። ጥሩው ምሳሌ ትምህርት ቤት ነው።

የከበደ ፍሬ ሰንበት መጣጥፍ (ምዕራፍ 1) በደንብ እንደሚያሳየው በ1928 ዓ.ም. የትምህርት ቤቶች አሀዝና የተማሪዎች ቁጥር በእጅጉ ጨምሮ ነበር። ጣልያኖች ሲወጡ አንድም የሚሰራ የትምህርት ቤት ትተው ስላልሄዱ የትምህርት ተቋማት ግንባታ አሀዱ ብሎ መጀመር ነበረበት፤ ከዚያ በኋላ እድገቱ ፍጥነት አመጣ። ነጻነት ከተመለሰ ከአስር አመት በኋላ ኢትዮጵያ ባለሁለት ኮሌጆች ልትሆን ስትችል፣ አንዱ በሁዋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሆነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነበር፤ ሌላው የምህንድስና ኮሌጅ ነበር፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1936 ተከፍቶ በጥቂት አመታት ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባና በትላልቅ አውራጃ ከተሞች ተከፍተዋል፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም አሀዝ በጣም አድጐ ሆኖ ነበር። ስለሆነም፣ የትምህርትን ስፋት እንደሂደት ስናየው እድገቱ እጅግ ፈጣን ነበር ማለት ይቻላል።

በእድገቱ ፈጣንነት የምንደመመው መንግስት የነበረው ገቢ አነስተኛ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ነው። አቶ ከበደ በጻፉት ምዕራፍ ውስጥም ሆነ በአቶ አሸናፊ መጣጥፍ (የኢኮኖሚ ፕላን) ውስጥ ቁልጭ ብሎ እንደሚታየው፣ በዚያን ጊዜ የመንግስት ገቢ እጅግ አነስተኛ እንደነበረ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሰለጠነ የሰው ሀይል ገና አልተፈጠረም፤ ይህንንም ለማፍራት ወጣቶች ባጭር ጊዜ ውስጥ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንዲሰለጥኑ ወደ እንግሊዝ፣ አሜሪካና ፈረንሳይ ሲላኩ፣ አልፎ አልፎም ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገሮችና ወደሊባኖስ ይላኩ ነበር። በዚህ ሁኔታ ነበር የተቋም ግንባታ ስራ የተካሄደው። መሰረቱ ሲጣልና ህንጻው ሲሰራ በሁኔታው አስገዳጅነት ከውጭ በመጡ ጠበብት (experts) ስራው መሰራት ነበረበት፤ ይህንንም ሁኔታ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከኮሌኔል ስምረት መድሃኔ፣ ከአቶ በትሩ አድማሴ እና ከአምባሳደር ጥሩነህ ዜና መጣጥፎች መረዳት ይቻላል። በልዩ ልዩ ምክንያት ወረቀት የሚያቀርብ ሰው ማግኘት አልተቻለም እንጂ እንደ ኤፍ.ኤስ. ኤስ. ፍላጐት ቢሆን ኖሮ፣ ስለመብራት ሀይል ድርጅት፣ ስለ አውራ ጐዳና፣ ስለስነጥበብ ተቋማት (ስዕል፣ ቲያትር፣ ሙዚቃ፣ ስነጽሁፍ፣ ሲኒማ)፣ ስለህግ ቀረጻ ሂደት (Codification) ሰፋፊ ጽሁፎች እንዲቀርቡ ታስቦ ነበር።

በልማት ሂደት ውስጥ ምዕራፎች አሉ ብለናል፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ የትውውቅ ወቅት ነው፤ ይህንንም ፈረንጆቹ በሌጣው Encounter ወይም Cultural Encounter የሚሉት ነው። ማለትም አንድ የአፍሪካ ህብረተሰብ (ጥቁር አፍሪካን እንደምሳሌ ብንወስድ!) ከምእራብ አለም ጋር የሚገናኝበት፣ የምእራብን አለም የቴክኖሎጂ መራቀቅ የሚገነዘብበት፣ ይህንንም ቴክኖሎጂ (በአንድ መልኩ ወይም በሌላ መልኩ እየመረጠ) ለራሱ የሚያስገባበት ዘመን ነው። ከዚህ ቀጥሎ ጉዞው ውስብስብ ቢሆንም (ብዙው ዓለም ቅኝ ግዛት ይሆናል!) በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚደረገው ተመሳሳይ ነው:- ደረጃ በደረጃ ዝመናን ማስገባት ሲሆን አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ተግዳሮት የተቋማት ግንባታ ነው፤ እነዚህ ተቋማት የተለያዩ ገጽታዎችና ባህርዮች አሏቸው - ብዙዎቹ መስሪያ ቤቶች ናቸው፤ የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶችም (ለምሳሌ ባንክ፣ የፖስታ ወይም የቴሌ ድርጅት) አሉበት፤ ህንጻ ኖሯቸው የማይታዩ ነገር ግን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ተቋማትም መገንባት ነበረባቸው፤ ከነዚህ ውስጥ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የፍትህ ስርአት ግንባታ ነው። የፍትህ ስርዓቱ ባንድ በኩል፣ ግዝፈት ያላቸው፣ የሚታዩ የሚዳሰሱ፣ ተቋማት ሲኖሩት (ፍርድ ቤት ፣ አቃቤ ህግ፣ ፖሊስ ወዘተ...)፣ በሌላ በኩል የማይታዩ የማይዳሰሱ፣ ይሁንና እጅግ ወሳኝ የሆኑ ተቋማት - የፍትህ ብሄር ፣ የወንጀል፣ የንግድ፣ የትራፊክ

ወዘተ ሕጐች - አሉት። እነዚህ ሁሉ - የሚታዩትም፣ ሆኑ የማይታዩት - መገንባት ነበረባቸው። ሀገሪቱ - ነጻ ሀገርም ሆነች (እንደ ኢትዮጵያ፣ ቻይና፣ ታይላንድ፣ ኢራን፣ አፍጋኒስታን)፣ ቅኝ ግዛትም ሆነች፣ እነዚህ ተቋማት በዘዴና በእቅድ መቋቋም ነበረባቸው። ይህ ምእራፍ ሀገሪቱን ለሚ አገር (developing country) ተርታ ያሰልፋታል። ከዚህ በኋላ ሀገሪቱ ወደ መካከለኛ ገቢ አገር፣ ከዚያም ወደለሙት አገሮች መዳረሻ (Emerging Economies) ማለትም እንደዛሬ ጊዜዎቹ ህንድ፣ ቻይና፣ እንዶኔዢያ፣ ታይላንድ ወዘተ እየተሸጋገረች በመጨረሻም የለሙት አገሮች አባል (ማለት እንደ ጃፓን) ትሆናለች። በአፄ ሀይለስላሴ ጊዜ ኢትዮጵያችን ገና ጉዞ ጀምራ ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ (ማለትም ለሚ አገሮች ተርታ የገባችበት ወቅት) ነበረች፤ እዚህ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት መጣጥፎች ያ ጊዜ ምን ዓይነት እንደነበር ይዘግባሉ፤ ይተርካሉ። በአብዛኛው ተራኪዎቹ የታሪኩ አካል የነበሩ ስለሆነ ትረካው፣ የታሪክ አጥኚዎች ቀዳማይ ምንጭ (Primary source) የሚሉት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያን የዝመና ሂደት ለማጥናት ይጠቀሙበታል የሚል ተስፋ አለን። ነገር ግን ሌላው አንባቢ ጽሁፎቹን እንደምስክርነት ቢወስዳቸው ጥሩ ይሆናል። ስለዚያ ዘመን የተሻለ ግንዛቤ ሊያገኝ ይችላልም ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የለውጡን ፍጥነት፣ ስፋትና ጥልቀትም ሊገነዘብበት ይችላል የሚል እምነት አለን።

# ክፍል ፩
# ተቋም ግንባታ

# ዘመናዊ ትምህርት በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ

*ከበደ ፍሬ ሰንበት*

## *መግቢያ*

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች

*ለአንድ አገር የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ እድገት የትምህርት ወሳኝነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ የታወቀ ነው። ኢትዮጵያ የራሷ ፊደል ያላት አገር ስትሆን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትምህርት መስጫ ማዕከል ሆና ለብዙ ዘመናት ሠርታለች። የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ ትምህርት በመስጠት እንዳገለገሉ የሚገመት ሲሆን፣ ትምህርት ቤቶቿም በየቤተክርስቲያኑ እና በየገዳማቱ ተሠራጭተው ትልቅ ቁም ነገር ሲሰሩ ኑረዋል። ቀደም ሲል የሚሰጠውም ትምህርት በመሠረቱ የሃይማኖት ትምህርት ሲሆን፣ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ፊደል መቁጠር፣ በኋላም ማንበብ፣ በመጠኑም መጻፍና በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉትን የጸሎት መጻሕፍትና ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነውን በቃል ማጥናት፣ ማለትም ዳዊትን መድገም የመሳሰሉት ነበር። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በየቤተክርስቲያኑ የሚገኙ ሲሆን በየጊዜው የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን የመመልመያና ማሠልጠኛ ማዕከል ሆነው እና በአገሪቱ ውስጥ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲስፋፋና እንዲቀጥል እንደሞተር ኃይል ሆነው ለዘመናት አገልግለዋል።*

*አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ትንሽ መጻፍና ማንበብ ሲችሉ ትምህርት የሚያቋርጡ ሲሆን፣ ትምህርታቸውን የሚቀጥሉት ግን ወደተለያዩ የቤተክርስቲያን የትምህርት መስኮች በመግባት ማለትም ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ መጻሕፍት ቤት በመግባት፣ በእያንዳንዱ ወስጥ የሚገኙትን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዘርፎች ይማራሉ። በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት አዋቂ ለመሆን ከሁለት ዓመት ያላነሰ ጊዜ የሚፈጅ እንደነበር ይታወቃል።*

*ትምህርት የሚሰጠው በግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ፣ ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ መጻፍና ማንበብ የሚችለው ሕዝብ ቁጥር በጣም ጥቂት ነበር። በጊዜው ከነበሩት የመንግሥት ባለሥልጣናት እንኳን በቀላሉ ማንበብና መጻፍ የሚችሉት ብዙ አልነበሩም። አንዳንዶቹ እንዲያውም ስማቸውን ከመፈረም በስተቀር ማንበብና መጻፍ አይችሉም ነበር። በሴቶች በኩልም መጻፍና ማንበብ የሚችሉት በየቤታቸው የተማሩት በጣት የሚቆጠሩ የአንዳንድ ባለሥልጣናት ቤተሰቦች አባል የነበሩ ናቸው። ዘመናዊ ትምህርት በአገሪቱ ውስጥ መስጠት ከተጀመረበት ጊዜ በፊት መጻፍና ማንበብ የማይችለው ሕዝብ ቁጥር ከ90 ከመቶ በላይ እንደነበር ይገመታል።*

## **የቁራን ትምህርት ቤቶች**

*በየቤተክርስቲያኑ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሌላ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው በማዕከላዊ፣ በምስራቅና በምዕራብ ክልል የቁራን ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን በአረብኛ ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በመጀመሪያዋቹ አሥራ ዘጠነኛው መቶ ዓመታት ቻርለስ ጆንስተን የተባለ አገር ጎብኚ በአንድ ቦታ ሰፍረው የማይኖሩ ብዙ ሶማሌዎችና ደንከሎች አረብኛ ማንበብና መጻፍ ይችሉ እንደነበር ዘግቧል፡፡ ሞሐመድ ሙክታር የተባለ ግብፃዊ በኋለኛው አሥራ ዘጠነኛው መቶ ዓመታት በሐረር ግንብ ውስጥ በሚገኙት የቁራን ትምህርት ቤቶች ትምህርት መስፋፋቱን ዘግቧል፡፡ ሕጻናት በትንንሽ የቁራን ትምህርት ቤቶች ማንበብና መጻፍ በቀን ሲማሩ ብዙ ጎልማሶች ደግሞ በማታ ትምህርት በሃይማኖት መሪዎች አማካኝነት የእስልምና ሕግ ይማሩ እንደነበር ገልጿል፡፡ እንዲሁም ሌላ አገር ጎብኚ የፈረንሳይ ሰው በጅማ ይገኙ የነበሩ ብዙ ሙስሊሞች ቁራንን በአረብኛ ማንበብ ይችሉ እንደነበር ገልጿል፡፡*

## **የአውሮፓ ሚሲዮናውያን ትምህርት ቤቶች**

*ከፖርቱጋል ጋር ግንኙነት የተጀመረው አህመድ ግራኝ የንጉሥ ልብነ ድንግልን ግዛት በወረረበት በ16ኛው መቶ ዓመት ነበር፡፡ ፖርቱጋሎች የግራኝን ጦር ድል ለማድረግ በተደረገው ትግል ላበረከቱት አስተዋጽኦ ኢትዮጵያን ወደ ሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታይነት ለመለወጥ ትብብር እንዲደረግላቸው ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በመጠኑ የተሳካለት የሮማ ካቶሊክ ተከታይ ነበረው ጀስዊታዊው ፔድሮ ፖኤስ* (Pedro Paes) *ባገሪቱ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የፖርቱጋሎችን ልጆች ለማስተማር በትግራይ ውስጥ ፍሬሞና በተባለ ቦታ ትምህርት ቤት መክፈት መቻሉ ነበር፡፡ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1617 ዓ.ም. ፍሬሞና ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ፖርቱጋላውያን አንድ የሃይማኖት ትምህርት ማስተማሪያ ተቋም የነበራቸው ሲሆን አሥራ ስድስት ፖርቱጋላውያን ተማሪዎች የተማሩበት ነበር፡፡ እንዲሁም በወቅቱ የታወቁ የሁለት ኢትዮጵያውያን ልጆች በዚህ ተቋም በዚህ ውስጥ ገብተው በመማር ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በየቤታቸው ውስጥ ለተወሰኑ የአካባቢው ልጆች ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ እነዚህ ሚሲዮናውያን በደምቢያ ባቋቋሙት አንድ የሃይማኖት ተቋም ውስጥ 34 ወጣቶችን ያሰለጥኑ የነበረ ሲሆን በአንድ ሌላ ትምህርት ቤት ጎጃም ውስጥ 35 ልጆች ማንበብና መጻፍ ሲማሩ የነበረው በፖርቱጋል ቋንቋ እና በአማርኛ ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ሱስኒዮስ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት በመለወጥ ሕዝቡ ይህንኑ ሃይማኖት እንዲከተል ማስገደድ በመጀመራቸው ተቃውሞ እየበዛባቸው ስለሄደና ዙፋናቸውን ለልጃቸው ለፋሲለደስ እ.ኤ.አ በ1632 ለቀው የልጃቸውን አርአያ በመከተል ካቶሊክ መሆናቸውን አውግዘው ወደ ቀድሞ እምነታቸው ወደ ኦርቶዶክስነት ተመለሱ፡፡ ፋሲለደስም ጀሱቶችን ከአገር አስወጥተው መጻሕፍቶቻቸውን እንዲቃጠሉ አደረጉ፡፡ በማያያዝም ከቀይ ባህር አስተዳዳሪዎች ጋር በመገናኘት የካቶሊክ ቀሳውስት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ*

እንዲያደርጉ ከስምምነት ላይ ደረሱ። የተጀመረውም የካቶሊኮች ትምህርት ተቋረጠ።

ፒተር ሄይሊንግ የተባለ ጀመርናዊ ሉተራን ሚሲዮናዊ በንጉሡ በመጀመሪያ አገዛዝ አካባቢ ኢትዮጵያ የገባ ሲሆን በቤተመንግሥት መልካም አቀባበል ከተደረገለት በኋላ ሙሉ ጊዜውን ወጣቶችን በግሪክኛና በእብራይስጥኛ ቋንቋዎች ማስተማር ጀመረ። በሥራውም ዝነኛ እየሆነ መጥቶ ብዙ የተከበሩ የከፍተኛ ባለሥልጣናት ጭምር ልጆቻቸውን እንዲያስተምር የማድረግ ክብር አገኘ። ይሁንና የእሱም ሀይማኖት ኦርቶዶክስ አለመሆኑ ሲረጋገጥ እንኳን ትምህርቱ ሊቀጥል ራሱ በሞት እንዲቀጣ ተደርጓል። አገሪቱ ከዛ በኋላ የውጭ ጣልቃ ገብነት በመፍራት ለሁለት መቶ ዓመታት ራሷን በማግለል የሚሲዮናውያንን እንቅስቃሴ አግዳ ቆየች።

## የሚሲዮናውያን ትምህርት እንደገና መጀመርና የዘመናዊ ትምህርት ፍንጭ መታየት

ከአውሮፓ ጋር የነበረው ግንኙነት እንደገና የተጀመረው በመጀመሪያው 19ኛ መቶ ዓመት ነበር። ከዚህም በኋላ ብዛት ያላቸው የፕሮቴስታንትና የሮማ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን በማስተማር ሥራ ላይ መሠማራት ጀመሩ። አይዘንበርግ እና ክራፕፍ (Isenberg and Krapf) የተባሉ ሁለት ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ሸዋ ውስጥ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1830 የወንዶች ልጆች ትምህርት ቤት ከፍተው ሲያስተምሩ የነበረ ሲሆን ከብዙ ጊዜ በኋላ ደግሞ ፍላድ (Flad) የተባለ የፕሮቴስታንት ሰው በመጀመሪያ አዖራ (Awora) ከተባለ ቦታ በኋላም መቅደላ ውስጥ ያስተምር ነበር። በተጨማሪ የዚሁ ሰው ሁለት ጓደኞች ብራንዴይስ እና እስታይግለር (Brandies and Staigler) አንድ ትንሽ ትምህርት ቤት ዳርና በተባለ ቦታ አቋቁመው ነበር፤ በአማርኛ ትምህር ይሰጥበት የነበረው የዚህን ትምህርት ቤት ሥራ የተሳካ ለማድረግ ከላይ ስሙ የተሰጠው አይዘንበርግ (Isenberg) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሃይማኖት ትምህርት ጋር ያልተያያዙ አንድ የንባብና አንድ የጂዮግራፊ መጻሕፍት እ.ኤ.አ. በ1841 እና በሚቀጥለው ዓመት አንድ የዓለም የታሪክ መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋ እንዲታተሙ አደረገ። በዚህ አቅጣጫ ያለውን ፍላጎት በማንፀባረቅ የስዊድን ወንጌላዊ ሚሲዮን ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1866 በምጽዋ የመጀመሪያውን የሚሲዮን ትምህርት ቤት ያቋቋመ ሲሆን ላዛሪስቶች ቀደም ብለው በ1847 በአሊቴና አንድ የወንዶች ልጆች ትምህርት ቤት ከፍተው ነበር።

## ወጣት ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ወደ ውጭ አገሮች መሄድ መጀመር

ከውጭ አገሮች ጋር ግንኙነት እየቀጠለ በመሄድ እ.ኤ.አ በ19ኛው መጀመሪያ መቶ ዓመት አካባቢ በተለያዩ መንገዶች ጥቂት ወጣት ኢትዮጵያውን ለትምህርት ወደ ውጭ አገሮች መሄድ ጀመሩ። ከነዚህም ውስጥ ማህደረ ቃል የተሰኘ አንድ ወጣት ለፌብቨር (Lefebvre) በሚባል ፈረንሳዊ አማካይኝነት ወደ ፓሪስ ተወስዶ በአንድ ጄስዊት ተቋም ከተማረ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር

በመሄድ በግሉ ትምህርቱን ቀጥሎ በኋላም ግብጽ በመሄድ ተምሯል። ሌላ ሊጠቀስ የሚችል ከአርመንና ከኢትዮጵያዊ የተወለደ ምርጫ ወርቄ ይባል የነበረ ወጣት ወደ ቦምቤ በመሄድ በአንድ የሚሲዮን ትምህርት ቤት ሒንዱስታን እና እንግሊዝኛ ተምሯል። ወንድሙ ብሩ ወርቄ ደግሞ ለብዙ ዓመታት እንግሊዝ አገር ከመማሩም ሌላ በእንግሊዝኛ እና አረብኛ ቋንቋዎች የተካነ ነበር። ሦስቱም ወጣቶች በአስተርጓሚነት ለአፄ ቴዎድሮስ ያገለገሉ ሲሆን በኋላም ለተተኪያቸው ለአፄ ዮሐንስ ተላልፈው ሠርተዋል። እ.ኤ.አ በ1868 ዓመተ ምህረት ከመቅደላ ጦርነት በኋላ እንግሊዞች ወርቅነህ የሚባል የአራት ዓመት ሕፃን ወደ ሕንድ አገር በመውሰድ እድሜው ሲደርስ ላሖር ውስጥ የሕክምና ትምህርት ሲከታተል ቆይቶ በኋላም እንግሊዝ አገር በኤድንብራና ግላስጎው በከፍተኛ ደረጃ ሰልጥኗል። ዶክተር ወርቅነህ ማርቲን ወደ ትውልድ አገሩ ተመልሶ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዘመናዊ ሐኪም ለመሆን በቅቷል።

በተጨማሪም በተለያዩ ሚሲዮናውያን አማካኝነት ብዛት ያላቸው ወጣቶች ወደ ልዩ ልዩ አገሮች በመሄድ ተምረዋል። ደጃኮቢስ (De Jacobis) የተባለ የካቶሊክ ጳጳስ እ.ኤ.አ. በ1847 ዓ.ም. 23 ወጣቶች ወደ ሮማ በመውሰድ የሃይማኖት ትምህርት እንዲከታተሉ አድርጓል። እንዲሁም 18 ወጣቶች ወደ ፈረንሳይ አገር በመውሰድ ተመሳሳይ የሃይማኖት ትምህርት እንዲማሩ አድርጓል። ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ስዊዘርላንድ በዛ ያሉ ወጣቶች የሄዱ ሲሆን የሚከታተሉት የትምህርት ዓይነት ግን በአብዛኛው የሃይማኖት ትምህርት ነበር። ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላም በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው አገራቸውን አገልግለዋል። ከነዚህም ውስጥ ወርቅነህ ማርቲን፣ የታወቁት የአፄ ምኒልክ ጊዜ ባለሥልጣናት ግራዝማች ዮሴፍ እና ከንቲባ ገብሩ ደስታ (በኋላም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ያገለገሉ) ይገኙባቸዋል።

### ዘመናዊ ትምህርት በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን

የሚሲዮናያውያን ትምህርት ዓላማ የኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ሃይማኖት ለመለወጥና እነርሱም ሌሎችን ለመለወጥ እንዲችሉ ለማድረግ ነበር። በጊዜው ለነበሩ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የአገሪ መሪዎች ግን ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ሌላ የሚታያቸው አዲስ ዓይነት ትምህርት ቤቶች አልነበሩም። በጊዜው አፄ ቴዎድሮስን የማረከው አዲስ የትምህርት ዓይነት የውትድርና ትምህርት ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ የውትድርና ትምህርት መማር እንዳለባቸው በማመን አሠልጣኞች እንዲላኩላቸው የእንግሊዝን መንግሥት ጠየቁ። እንዲሁም በመሣሪያ ጥገናም ችሎታ ያላቸው አሠልጣኞች እንዲላኩላቸው የጠየቁ ሲሆን ንጉሡ ነገሥት ከመሆናቸውም በፊት ጥቂት ቱርኮች፣ አንድ የግሪክ ክልስና እና ሌላ ዶሚኒዮ (Dominio) ይባል የነበረ የኢጣለያን ክልስ ወታደሮቻቸውን በዘመናዊ ውትድርና ትምህርት እንዲያሰለጥኑ ቀጥረዋቸው የነበረ ሲሆን በኋላ በኃላፊነቱ ቤል (Bell) ይባል

የነበረ በአገር ጎብኚነት መጥቶ ለነበረ እንግሊዛዊ ሰው ሰጥተውት ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ከውጪ የሚመጡት አሠልጣኞች አስተምረው ወደ አገራቸው መመለስ አለባቸው ሲሉ እምነታቸውን ገልጸዋል።

## ዘመናዊ ትምህርት በአፄ ምኒልክ ዘመን

አፄ ቴዎድሮስ በትምህርት ላይ የነበራቸው እምነት በቤተ መንግሥታቸው የነበሩትን ወጣቱን ምኒልክ በማሳመኑ፣ አድገው አልጋው ላይ ሲመጡ የዘመናዊ ኢትዮጵያ አስተዳደር መሥራች ንጉሠ ነገሥት እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል። በምዕተ ዓመቱ የመጨረሻው አሥርት አካባቢ ተማሪዎችን ወደ ውጭ አገር ለትምህርት በመላክ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መሪ ለመሆን በቅተዋል። ሦስት ተማሪዎች፣ በኋላም የታወቁ ምሁራን፣ ደራሲ አፈወርቅ ገብረየሱስን ጨምሮ፣ አልፍሬድ ኢልግ (Alfred Ilg) በሚባል የንጉሠ ነገሥቱ የስዊስ አማካሪ አማካኝነት ወደ ስዊዘርላንድ ተላኩ። ለጥቂት ጊዜ ኑኡቻቴል (Neuchatel) ከሚባል ስፍራ ከቆዩ በኋላ ወደ ኢጣልያ በማምራት ቱሪን (Turin) ውስጥ ተማሩ። በተጨማሪም ስድስት ወጣት ኢትዮጵያውያን ዝነኛውንና የታወቁትን ተክለ ሃዋርያትን ጨምሮ ከሌላ የመንግሥት ባለሥልጣን ጋር ወደ ሩሲያ (Russia) ተላኩ። በጊዜው ሩሲያ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን የምትከተል ሀገር ሆና የምትታወቅ ስለነበረችና በምኒልክ ዘመንም የኢጣሊያንን ወረራ ደጋፊ ስላልነበረች በጊዜው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት በአክብሮትና በወዳጅነት የሚያዩዋት አገር ነበረች። ቢያንስ ሁለት ተማሪዎች ደግሞ ወደ ጀርመን የሄዱ ሲሆን ዶክተር ወርቅነህ ማርቲን ለተወሰነ ጊዜ ወደ በርማ በመሄድ ቆይተው ስለነበር ወደዚያው አምስት ወገኖቻቸው ኢትዮጵያውያን ወስደው እንዲማሩ አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችተውላቸዋል። የንጉሠ ነገሥቱን ስሜትና ፍላጎት የመጀመሪያው የአሜሪካን መልእክተኛ እስኪነር የተገነዘቡ በመሆናቸው ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ወደ አሜሪካ ለትምህርት መላክ አስፈላጊ ስለመሆኑ ተወያይተዋል። አፄ ምኒልክም ዘመናዊ ትምህርት ወጣቶቻችን መማር አለባቸው ያሉትን በመጥቀስ የንጉሠ ነገሥቱን ፍላጐት አሜሪካዊው መልእክተኛ አንጸባርቀዋል።

የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመጀመሪያዎቹ ሃያኛው ክፍለ ዘመን አፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥታቸው ውስጥ የከፈቱት ትምህርት ቤት ነው። ይህ የትምህርት ተቋም ይመራ የነበረው የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በሆኑት በቀኛዝማች ይብሳ ሲሆን ተማሪዎችም ወጣት የቤተመንግሥት አገልጋዮች ነበሩ። የሚማሩትም ንባብ፣ የእጅ ጽሑፍ፣ የሃይማኖት ትምህርት፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሕግ፣ ግዕዝና መልካም ጠባይ ነበር።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ይህ የመጀመሪያው ትምህርት ቤት በቂ አለመሆኑን በመገንዘብ መምህራን ከውጭ አገር ለማስመጣት ወሰኑ። ነገር ግን ከቤተክርስቲያን በኩል ተቃውሞ ስለተነሳባቸው በተለይም ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ የተቃውሞው ተካፋይ በመሆናቸው ጉዳዩን ለማርገብ ሲሉ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ግብፃውያን መምህራንን መመልመል

እንዳለባቸው ወሰኑ፡፡ በዚሁ መሠረት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1906 አሥር ግብጻውያን መምህራን ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሲሆን አዲስ አበባ፣ ሐረር፣ አንኮበር እና ደሴ ሊመደቡ ችለዋል፡፡

ሌላው ትምህርት ቤት ማለትም ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት (Ecole Imperial Menelik II) የሚባለው የመጀመሪያው የመንግሥት ትምህርት ቤት በመሆን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1907 ዓ.ም. በንጉሠ ነገሥቱ ተከፈተ፡፡ በግብጽ ውስጥ በጊዜው የነበረውን ሁኔታ በመከተል የማስተማሪያው ቋንቋ ፈረንሳይኛ ሲሆን እንግሊዝኛ፣ ጣሊያንኛ እና አማርኛ በተጨማሪ ተማሪዎቹ ይማሩ ነበር፡፡ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ጂምናስቲክና ሌሎች የስፖርት ትምህርቶችም ይሰጡ ነበር፡፡ ትምህርት ቤቱ አማርኛን መጻፍና ማንበብ ለሚችል ሁሉ ክፍት ነበር፡፡ ምግብና ማደሪያም በነጻ ይሰጥ የነበረ ሲሆን ትምህርት መማር እድሜ አይገድበውም ነበር፡፡

በዚሁ ዓመት አፄ ምኒልክ በተጨማሪ በክፍለ ሀገር ደረጃ ሐረር ውስጥ አንድ ሌላ የመንግሥት ትምህርት ቤት አቋቋሙ፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ከግብጽ ከመጡ መምህራን ማህል አንዱ ሃና ሣሊብ (Hana Salib) የተባለ በዲሬክተርነት ተመድቦ እንዲሰራ ሾሙ፡፡

ከነዚህ ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ በ1907 በፈረንሳይ ኮሚኒቲ አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ነበር፡፡ የተቋቋመው ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ሲሆን እስከ 1910 ዓ.ም. ካገለገለ በኋላ ከአሊያንስ ፍራንሴዝ ተወስዶ ኤኮል ፍራንሴዝ በኦፊሴል እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1912 ዓ.ም. ተከፈተ፡፡ ትምህርት የሚሰጠው በፈረንሳይኛ የነበረ ሲሆን በቀን አንድ ሰዓት ያህል የአማርኛ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡

ከሃይማኖት ጋር ያልተያያዙ መጻሕፍት ለመማሪያ አስፈላጊነታቸው የታወቀ ሲሆን በዘመነ ምኒልክ የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት ተቋቁሟል፡፡ በጊዜው በውጭ አገር ትምህርታቸውን ከተማሩት ሰዎች አንዱ አቶ ሚካኤል ብሩ የመጀመሪያውን የሂሳብ መጽሐፍ ጽፈው ያሳተሙና የመጀመሪያውን አእምሮ የተሰኘውን የአማርኛ ጋዜጣ ያቋቋሙ ሰው ነበሩ፡፡

### የአፄ ምኒልክ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ያስከተለው የአጭር ጊዜ ክፍተት

አፄ ምኒልክ እ.ኤ.አ. በ1913 በመሞታቸው የትምህርት መስፋፋት ለጊዜው ተሰናክሎ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሚሲዮን ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ጀመሩ፡፡ ላዛሪስቶች በዚያን ወቅት ሁለት የወንዶች ትምህርት ቤቶች በአሊቴና እና በጉሉ እንዲሁም ሁለት የልጃገረዶች ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባና በአሊቴና ያካሂዱ ነበር፡፡ ትምህርት የሚሰጠው በፈረንሳይኛና በአማርኛ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ የሚሰጠውም ትምህርት ሙሉ በሙሉ በነጻ ነበር፡፡ ካፑቺንስ (Capuchins) የተሰኙ የካቶሊክ ሚስዮናውያን ደግሞ 14 የመዋዕለ ሕጻናት፣ 24 የአንደኛ ደረጃና 7 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያካሄዱ እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ፡፡ ከብዙ ጥቃቅን

ከከተማ ወጣ ያሉ የመንደር ትምህርት ቤቶች ሌላ፣ ከፍ ከፍ ያሉ ሌሎች የሮማ ካቶሊካውያን ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋና በሶፊ (Sofi) ይገኙ ነበር።

የሉተራን ሚሲዮኖችም በበኩላቸው ጥረት አድርገዋል። የስዊድን ኤቫንጄሊካል ሚሲዮን ስምንት ትምህርት ቤቶች ያካሄድ እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ። ትልቁ ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ይገኝ የነበረ ሲሆን ትምህርት የሚሰጠውም በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ነበር። የሚሰጡትም የትምህርት ዓይነቶች የሃይማኖት ትምህርት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ሂሳብ፣ ጂኦሜትሪ፣ መዝሙርና ጂምናስቲክ የነበሩ ሲሆን በተለይ ልጃገረዶች ስፌት በእጅ ሙያነት ይማሩ ነበር። ወላጆች እንደየአቅማቸው ለልጆቻቸው ትምህርት እንደሚከፍሉ መረጃዎች ይገልጻሉ። የስዊድን የመጽሐፍ ቅዱስ ተልእዕኮ ወዳጆች (Swedish Friends of the Bible Mission) የተሰኘ ማህበር ከሦስት ትምህርት ቤቶች በተጨማሪም አንድ ትምህርት ቤት ለወንዶች ልጆች እና አንድ ትምህርት ቤት ለልጃገረዶች አዲስ አበባ ውስጥ እንደነበራቸው ይታወቃል።

የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች አንድ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እና አንድ አነስ ያለ ትምህርት ቤት በአዲስ ዓለም ነበራቸው። ትምህርት የሚሰጠው በነጻ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ የነበረ ሲሆን ወላጆች የምግብና የመኝታ ወጪዎችን ብቻ እንዲሸፍኑ ይደረግ ነበር። የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ንባብ፣ የእጅ ጽሕፈት፣ ሂሳብ፣ የጤና ትምህርት፣ ሥዕል መሳል፣ ጂምናስቲክ እና መዝሙር እንደነበር ይታወቃል።

በዚሁ ዘመን ትምህርት ይሰጡ ከነበሩት ሚሲዮናውያን የመጨረሻዎቹ የሰሜን አሜሪካን የፕሬስቢቴሪያን ቤተክርስቲያን (Presbyterian Church) አባላት ሲሆኑ ሰዮ (ወለጋ) ውስጥ ትምህርት በኦሮምኛ ብቻ የሚሰጥበት ተቋም ነበራቸው።

በጊዜው የሚሲዮናውያን ትምህርት ቤቶች ቢስፋፉም ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ተመርቀው የሚወጡት፣ አፄ ምኒልክ ከከፈቷቸው ትምህርት ቤቶች ከሚወጡት አንጻር ሲታይ፣ ከተራ የጽሕፈት ሥራ ሌላ ለመሥራት የማይችሉና የአርበኝነት ስሜት የሌላቸው ናቸው በማለት በመንግሥት አካባቢ በጊዜው የነበረውን አመለካከት አሸብር ገብረሕይወት ገልጸውታል።

## ዘመናዊ ትምህርት በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት

ራስ ተፈሪ መኮንን እ.ኤ.አ. በ1916 ዓ.ም. አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሲሆኑ ለመንግሥት ሥራ ሁሉ ኃላፊ ሆነው መሥራት ጀመሩ። ይህም በቅድመ ኢጣልያን ወረራ ዘመን በኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክና በአጠቃላይም በሥልጣኔ በር ከፋችነቱ ትልቅ ስፍራ የነበረው የትውስታ ዘመን ነው። እርሳቸው ራሳቸው የምኒልክ ትምህርት ቤት ተመራቂ ሲሆኑ ትምህርት ለማስፋፋት የነበራቸው ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ ነበር። እ.ኤ.አ በ1923 ዓ.ም.

የራሳቸውን ማተሚያ ቤት በማቋቋም *ብርሃንና ሰላም* የተሰኘ ጋዜጣና የተለያዩ ትምህርታዊ ጽሑፎች እንዲታተሙ አደረጉ፡፡

እ.ኤ.አ. በ1925 ዓ.ም. ብዙ ተቃዋሚዎች ቢያጋጥሟቸውም የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን ከፈቱ፡፡ ተቃውሞው የቀድሞ አመለካከት ከነበራቸውና ዘመናዊ ትምህርትን ከሚጠሉ ባለሥልጣናት የመነጨ ነበር፡፡ ይህም ተቃውሞ የትምህርት ቤቱን መከፈት ለተወሰነ ጊዜ አዘግይቶታል፡፡ በትምህርት ቤቱ የመክፈቻ ንግግራቸው ላይ ለአገሪቱ የሚደረግ ከንቱ የቃላት ውዳሴ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን፣ የሕዝቡ ፍላጎትና ጩኸት ግን ትምህርት ለማግኘት እንደሆነና ያለትምህርትም ነጻነት ተጠብቆ መኖር እንደማይቻል አስገነዘቡ፡፡ ስለዚህ የእውነተኛ አርበኝነት ምልክት ትምህርት ቤቶችን መክፈት መሆኑን አበክረው ገለጹ፡፡ የእድገትና የሥልጣኔ መነሻው ትምህርት እንደመሆኑ እርሳቸው በምሳሌነት ትምህርት ቤት በመክፈት ችሎታው ያላቸው ሁሉ የእርሳቸውን አርአያነት እንዲከተሉ አሳሰቡ፡፡ በመክፈቻ ካሰሙዋቸው ምክር ጠቀስ መመሪያዎች የሚከተለው አንዱ ነበር፡-

> *ለኢትዮጵያ ነፃነትና ጽናት ወሰንዋን ጠብቆ አሳፍሮ አስከብሮ ለማኩራትና ለሕዝቧ ልብ የታመነ ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ መሣሪያው ትምህርት መማር ነው፡፡ ተማሪ ቤት ለማቆምና ልጆቻችሁ ያልሆኑ ተማሪዎችን ለመርዳት ልጆቻችሁንም እንዲማሩ ማድረግ ኢትዮጵያን ለሚወድ ሁሉ ይገባል፡፡ በንግግር አሁን ማንም ሰው ሲጠይቁት አገሬን ኢትዮጵያን እወዳለሁ የማይል የለም፡፡ ለሀገሬ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ነኝ የሚል ሰው ሁሉ የወዳጅነቱን ምልክት ለማሳየት ተማሪ ቤት መርዳትና የሚቻለውም ተማሪ ቤት መሥራት ልጁን ማስተማር የሚገባ ነገር ነው፡፡*[1]

የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የተሠራው በ430 000 ማርተሬዛ ብር እንደነበር ይታወቃል፡፡ ትምህርት ቤቱ ከምኒልክ ትምህርት ቤት በስፋት የበለጠና ዘመናዊም ነበር፡፡ የሚሰጠውም ትምህርት በይበልጥ ወደፈረንሳይኛ ያዘነበለ እንደነበር ነው መረጃዎች የሚገልጹት፡፡ ለተከታታይ ዓመታት የትምህርት ቤቱ ዲሬክተሮች ፈረንሳውያን የነበሩ ሲሆን ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ብቃታቸውን ለማወቅ በየዓመቱ የፈረንሳይን መንግሥት ፈተና ይወስዱ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሁለት የትምህርት መስጫ ቋንቋዎች የነበሩ ሲሆን አንደኛው ፈረንሳይኛ ሲሆን ሌላኛው እንግሊዝኛ ነበር፡፡ የፈረንሳይኛውን የሚከታተሉት 124 ተማሪዎች ሲሆኑ እንግሊዝኛውን 76 ነበሩ፡፡ ይህም እ.ኤ.አ ከ1928-9 የነበረው ሁኔታ ነው፡፡ አብዛኞዎቹ መምህራን ፈረንሳዮችና ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሊባኖሳውያን ነበሩ፡፡ የሚሰጡትም የትምህርት ዓይነቶች ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ፣ አረብኛ፣ ሂሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ታሪክ፣ ጂምናስቲክና ስፖርት ነበሩ፡፡ ያስተምሩ ከነበሩት የውጭ አገር መምህራን ሌላ

---

[1] *የክብር ሠላምታ* ከሚል መጽሔት የተወሰደ ጥቅስ

አማርኛና በዝቅተኛ ክፍሎች ፈረንሳይኛ ጀማሪ ተማሪዎች የሚያስተምሩ ኢትዮጵያውያን መምህራን ነበሩ፡፡

ሀብት ወይም ብቃት ያላቸው ቤተሰቦች ልጆች በአዳሪነት ለመማር የሚከፍሉት ዘጠኝ ማርተሬዛ ብር የነበረ ሲሆን ችሎታው የሌላቸው ግን ለምግባቸውና ለማደሪያቸው ሳይከፍሉ በነጻ ይማሩ ነበር፡፡ እንዲያውም በኋላ ለእያንዳንዱ ተማሪ ለየወሩ የሚሆነው የወጪ ሂሳብ መክፈል ተጀምሮ ነበር፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት የተማሪዎችን ወጪ ለመሸፈን ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ ትምህርት በሰፊው የሚቃወሙትን ወገኖች ለማሸነፍ በጊዜው የተወሰደ ርምጃ ነው፡፡

## የትምህርት ታክስ መጀመር

የትምህርት ወጪዎችን ለመሸፈን እ.ኤ.አ. በ1926 ዓ.ም ከመቶ 6 በገቢና በወጪ ንግድ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት ታክስ ተጣለ፡፡ እ.ኤ.አ ከ1929-30 ባለው ጊዜ 163,874 ማርተሬዛ ተሰበሰበ፡፡

በእነዚሁ ዓመታት ውስጥ የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤትና አንድ ሌላ ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ተከፈቱ፡ ሁለቱም በፈረንሳይኛ ነጻ ትምህርት መስጠት ጀመሩ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በክፍለ ሀገር ደረጃ በደሴ፣ በድሬዳዋ፣ በጅጅጋና በለቀምት እ.ኤ.አ በ1928 እና በ1929 ባሉት ጊዜያት አራት ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ፡፡ ደሴ ውስጥ የተከፈተው ትምህርት ቤት የሚያስተምረው በፈረንሳይኛ የነበረ ሲሆን ድሬዳዋ ውስጥ የተከፈተው በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ በቀሪዎቹ ሁለት ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያው ቋንቋ እንግሊዝኛ ነበር፡፡

## የመጀመሪያው የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር መቋቋም

እ.ኤ.አ. በ1930 ዓ.ም. ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ክብረ በዓል በኋላ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት መስፋፋት ጀመረ፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ ዋና ዓላማ ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ለመመሥረት እንደመሆኑ የመጀመሪያውን የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር አቋቋሙ፡፡ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተመራቂ የነበሩት ክቡር ብላቴን ጌታ ሳሕሌ ፀዳሉ የመጀመሪያው የትምህርት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡

ዓፄ ኃይለሥላሴ፣ ከትምህርት ታክስ በተጨማሪ ከጠቅላይ ግምጃ ቤት ገቢ ውስጥ ሁለት ከመቶ ለትምህርት እንዲመደብ አደረጉ፡፡ በዚሁ ጊዜ አካባቢ ንጉሠ ነገሥቱ ወታሮች ማንበብና መጻፍ እንዲማሩ ትዕዛዙ ሰጡ፡፡ ካህናትም ሕጻናትንና ወጣቶችን በማስተማር እንዲሳተፉ አሳሰቡ፡፡

በዚሁ ጊዜ ፕሮፌሰር ኧርነስት ወርክ የሚባሉ ጥቁር አሜሪካዊ ቀደም ብለው መስኪንግሀም ኮሌጅ (Mukingham College) ውስጥ ያስተምሩ የነበሩ ምሁር በትምህርት አማካሪነት ተሾሙ፡፡ በመቀጠልም እኚህ ምሁር የአገሪቱ የትምህርት መዋቅር ስድስት ዓመት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ ስድስት ዓመት

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና አራት ዓመት የዩኒቨርስቲ ትምህርት እንዲሆን ሲሉ ሀሳብ አቀረቡ። የሚሰጠውም ትምህርት በመምህራን ስልጠናና በእርሻ ትምህርት ላይ ልዩ ትኩረት እንዲያደርግ አሳሰቡ። ይሁን እጂ ይህንን የትምህርት መዋቅር ፕላን በሥራ ላይ ለማዋል በቂ መምህራን የሉም ሲሉም ችግሩን ገለጹ።

ችግሮች ቢኖሩም ቀጥሎ በነበሩት አምስት ዓመታት ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ታሪክ ያልታየ የትምህርት እድገትና መስፋፋት ሊታይ ችሏል። በዋናው ከተማ ሰባት እና በክፍለ ሀገራት ስምንት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሊከፈቱ ችለዋል። ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሊሴ (Lycée Haile Sellassie I) የቴክኒክና የቋንቋ ትምህርት ሥልጠና ለ100 ያህል ተማሪዎች በመስጠት ሥራውን ጀመረ። ትምህርት የሚሰጠው በፈረንሳይኛ ሲሆን የትምህርቶቹም ዓይነቶች ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ሲቭል እንጂነሪንግ፣ የእንስሳት ጤና ትምህርት (Veterinary Science) እና ዘመናዊ የቋንቋዎች ትምህርት ነበሩ።

እ.ኤ.አ. በ1931 ግርማዊት እቴጌ መነን በስማቸው የሚጠራ አንድ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ከፈቱ። የልጃገረዶቹ ተማሪዎች ቁጥር እ.ኤ.አ. በ1935 ዓ.ም 80 የደረሰ ሲሆን ትምህርት ይሰጥ የነበረው በፈረንሳይኛ ሆኖ በተከታታይ የትምህርት ቤቱ አመራር አባላት ፈረንሳዊ ሴቶች ነበሩ። ተማሪዎቹም የአንደኛ ደረጃን ትምህርት ሲያከናውኑ የፈረንሳይ መንግሥት ሰርቲፊኬት ለማግኘት ፈረንሳይ ለጋሲዮን ውስጥ ፈተና ይሰጣቸው ነበር። ለተማሪዎቹ የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ሥዕል፣ ባልትናና ጂምናስቲክ እንደነበሩ ይታወቃል።

እ.ኤ.አ. በ1932 ዓ.ም. አባትና እናት ለሌላቸው 100 ለሚያህሉ ወንዶች ልጆች ትምህርት ቤት የተከፈተ ሲሆን የሚማሯቸውም የትምህርት ዓይነቶች ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የብረታ ብረት ሙያና ጫማ ሥራ እንዲሁም ሌሎችም የሙያ ትምህርቶች ነበር። እ.ኤ.አ በ1934 ዓ.ም አንድ የመምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት፣ አንድ የወንዶች እስካውት ትምህርት ቤት ተከፍተው የነበሩ ሲሆን ትምህርት የሚሰጠው በፈረንሳይኛ መሆኑ ታወቋል። በዚሁ ጊዜ አንድ የሥዕል ትምህርት ቤት (Academie des Beaux Arts) ስራውን ጀምሮ የነበረ ሲሆን ትምህርት ቤቱ የሚመራው ፓሪስ ውስጥ በተማረው በኢትዮጵያዊው ሠዓሊ በአቶ አገኘሁ እንግዳ ነበር።

በየክልሉም ትምህርት እየተስፋፋ በመሄድ በፈረንሳይኛ ትምህርት ይሰጥባቸው የነበሩ ትምህርት ቤቶች በአሰበ ተፈሪ፣ በጎንደር፣ በደብረ ማርቆስ፣ በአድዋና በመቀሌ ተከፍተዋል። በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ አገር ሕብረተሰብ አባላት ልጆች ማስተማሪያ ግሪኮች፣ አርመኖችና ሕንዶች የየራሳቸውን ትምህርት ቤቶች ከፍተዋል።

በዚሁ መልክ ትምህርት እየተስፋፋ ከመሄዱም በተጨማሪ መንግሥት

ለትምህርት መላኩ ላይ እየገፋበት ሄደ። መንግሥት እየከፈለ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች ከሚልክባቸው የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ውስጥ ግብጽ፣ ሊባኖስ፣ ሱዳን ይገኙባቸው የነበረ ሲሆን ከእነዚሁ አገሮች ተነስተው ብዙዎች ለዩኒቨርስቲ ትምህርት ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይሄዱ ነበር። ሌሎች በቀጥታ ከኢትዮጵያ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይሄዱ እንደነበር ይታወቃል። በአንድ ወቅት ቢያንስ 20 ተማሪዎች ወደ ግብጽ፣ ይህንኑ የሚያህል ቁጥር ወደ ሊባኖስና ግማሽ ደርዘን ያህል ወደ ሱዳን ሄደዋል። ትልቅ ቁጥር የያዙት ወደ ስልሳ ገደማ የሆኑ ወደፊት የአገሪቱ ሚኒስትሮች የሚሆኑትን ጭምር ያካተተ ቡድን ወደ ፈረንሣይ፣ ሃያ ያህል ወደ እንግሊዝ አገር፣ አሥር ወደ እስዊዘርላንድ፣ ዘጠኝ ወደ አሜሪካና ዘጠኝ ወደ ኢጣልያን፣ ሁለት ወደ ጀርመን፣ ሁለት ወደ ቤልጂየምና አንድ ወደ እስፔይን ተልከዋል። የሚማሩዋቸው የትምህርት ዓይነቶች መድኃኒት፣ የእንስሳት ሳይንስ (Veterinary Science)፣ ምህንድስና፣ የሕግ ትምህርት፣ የመምህርነት ሙያ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ስነጽሁፍ፣ ስዕል፣ ጋዜጠኝነት፣ አውሮፕላን መንዳትና ሚሊተሪ ሣይንስ የነበሩ ሲሆን ከሰላሳ ያላነሱ በፈረንሣይ አገር በውትድርና ትምህርት ሰልጥነው ተመልሰዋል። ከነዚህ መንግሥት ከላካቸው ተማሪዎች ሌላ ወደ አርባ የሚያህሉ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች በሚሲዮናውያን ወጪ ወደ ቫቲካንና ሃያ አምስት የሚያህሉ ቤተ እሥራኤላውያን በይሁዳውያን ርዳታ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ አገሮች ለትምህርት ሄደዋል። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶች የሃይማኖታቸውን ትምህርት የተከታተሉ ሲሆን አብዛኞዎቹ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች (መድኃኒት፣ ሕትመት፣ ሽመና፣ አናጢነትና ሜካኒክነት ወ.ዘ.ተ) መማር ችለዋል።

ከኢጣልያን ወረራ በፊት የዘመናዊ ትምህርት መሠረት ተጠናክሮ የተጣለበት ጊዜ የነበረ ሲሆን ተከፍተው የነበሩት ትምህርት ቤቶች የሚያስተናግዷቸው ተማሪዎች ማንም ኢትዮጵያዊ ገብቶ የሚማርባቸው ነበሩ።

ከኢጣልያን ወረራ አሥር ዓመት ገደማ በፊት ጀምሮ ማንበብና መጻፍ የሚችለው ሕዝብ ቁጥር እያደገ ሄዶ ስለነበር በዛ ሳለ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ክሪስቲን ሳንድፎርድ የሚባሉ የውጭ አገር ዜጋ በዚሁ ዘመን ማንበብና መጻፍ የሚችለው ሕዝብ ቁጥር ማደጉን ሲገልጹ «እ.ኤ.አ. በ1920 በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ማንበብና መጻፍ የሚችል ወንድ ልጅ ሲገኝ በመገረም የተለየ ሆኖ ይታይ የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1935 ግን በዚሁ ሕብረተሰብ ውስጥ በአማርኛ ፊደላት በመጠቀም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ወንዶች ጎልማሶችና ልጆች በጣም ጥቂት ነበሩ» ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ይህን የክርስቲን ሳንድፎርድ አስተያየት ያነበቡ አንድ እንግሊዛዊ ሰው እ.ኤ.አ. በ1932 ማንበብና መጻፍ የሚችለው ሕዝብ በጣም ከፍተኛ ነው ባይባልም በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ካሉት ሌሎች አገሮች ጋር ሲታይ ግን በእውነትም ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታ እድገት እየታየ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። በተጨማሪም አንድ ኤሪክሰን የተባሉ የስዊድን ሚሲዮናዊ ከዚህ አባባል ጋር በመስማማት «ማንበብ የሚችሉ ሰዎች ቁጥር መጨመሩ የተረጋገጠ ነው» ካሉ

በኋላ ፍርሀታቸውን ደግሞ ሲገልጹ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ የሚማሩ ወጣቶች «በአብዛኛው የከተማ ፍቅር ስለሚያድርባቸው ወደመንደራቸው የሚመለሱት ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ነው የሚሆነው» ሲሉ አስተያየታቸውን አክለው ሰጥተዋል፡፡ ለዚህ ውጤት የተደረሰው ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸው ከኢጣልያን ጦርነት በፊት ሕብረተሰቡን ለመለወጥ ትምህርት በፍጥነት እንዲስፋፋ ስለሚያበረታቱ ነበር፡፡

## ትምህርት በጣልያን ወረራ ዘመን

እ.ኤ.አ. የ1935 ዓ.ም. የኢጣልያን ወረራ ተጀምሮ የነበረውን የትምህርት መስፋፋት ገታው፡፡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሙሉ የተዘጉ ሲሆን ሥራቸውን ያላቆሙት ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ብቻ ነበሩ፡፡ የተዘጉት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው ወደ ጣልያን ልጆች ማስተማሪያ ትምህርት ቤትነት እንዲለወጡ ተደረገ፡፡ የጊዜው የፋሺስት ጣሊያኖች ዓላማ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ብዙ ዜጎቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ለማድረግ ስለነበር ለአገሬው ሕዝብ ሳይሆን ለዜጎቻቸው ትምህርት ቤቶች ማስፋፋት እንዳለባቸው በማመን ይህንኑ ዓላማ ለመተግበር መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ልጆች ባይማሩ የሚያሳስባቸው ጉዳይ ስላልነበረ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን በሁለት በመክፈል የአካዳሚክና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች በማለት ለኢጣልያን ልጆች ማስተማሪያ አደረጉት፡፡

ከጣልያን ወረራ በፊት የማስተማሪያ ቋንቋ አማርኛ የነበረ ሲሆን ከወረራው በኋላ አዲስ የትምህርት መመሪያ በማውጣት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ኤርትራ ውስጥ ይደረግ እንደነበረው እስከ 4ኛ ክፍል እንዲማሩ ቢበዛ ከ6ኛ ክፍል በላይ ትምህርት እንዳይሰጣቸው በመወሰን የማስተማሪያ ቋንቋ በአማራ አውራጃዎች አማርኛ፣ በትግራይ ትግሪኛ፣ በአዲስ አበባ አማርኛና ኦሮምኛ፣ በሐረርጌ ኦሮምኛና ሐረሪኛ፣ ኦሮሞዎች በሚኖሩባቸው አውራጃዎች በከፋ ኦሮምኛና ለከፊቾ፣ በሶማሌ ሱማሊኛ እንዲሆን የሙስሊም ሕብረተሰብ ባሉባቸው አካባቢዎች ትምህርት ቤቶች ሁሉ በተጨማሪ በአረብኛ እንዲጠቀሙ ተወስኖ የየአካባቢዎቹ ገዥዎች ሌሎች ተጨማሪ የማስተማሪያ ቋንቋዎች ሲያስፈልጋቸው ሥራ ላይ እንዲያውሉ ሥልጣን ተሰጣቸው፡፡

ትምህርት ፖሊሲው መሠረቱ ፖለቲካ የነበረ ሲሆን የኢትዮጵያ ልጆች ከኢጣልያን ልጆች ጋር አብረው መማር አይችሉም ነበር፡፡ ፖልሰን ኒውማን (Polson Newman) የተባሉ ታዛቢ እንደገለጹት ተማሪዎች ለሮማው ንጉሠ ነገሥትና ለዱቼ ታማኝ እንዲሆኑ መስበክ የትምህርቱ አንደኛው ዋና ዓላማ ነበር፡፡ የማስተማሪያ መጻሕፍት ለዚሁ ዓላማ በሚስማማ መልክ በማዘጋጀት ከዚህ በታች ያለውን መፈክር ያካትቱ እንደነበር ፖሊሰን ኒውማን ይገልጻሉ፡፡ «እናንተ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ በታላቂቱ የኢጣልያን ሕዝብ ሥር በመሆናችሁና በጥፋተኞች ላይ የቅጣት ውሳኔ ሰጭ አካል ሥር በመሆን የምትሠሩ በመሆናችሁ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል፡፡» «ትኩር ብሎ በጥልቀት

እየተመለከተ ለሚገመግማችሁ ለዱቼ (Duce) ክንዳችሁን ወደ ላይ ከፍ በማድረግና እጃችሁን በመዘርጋት… 'እኔ ሁልጊዜ ትዕዛዝህን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ' በማለት ድምጻችሁን ጎላ በማድረግ አሰሙ» የሚሉ የፖለቲካ መፈክሮችን ያካተተ ትምህርት ይሰጥ እንደነበር አስተያየት ሰጪው ገልጸዋል።

የትምህርቱ ይዘት ወጣቶችን ለኢጣልያን አገልጋይነት ማዘጋጀት ሲሆን ጥልቀት ያለው ትምህርት እንዳይሰጥ የትምህርቱ ፖሊሲ ትኩረት እንደነበር ፖልሰን ኒውማን ገልጸውታል። ይኸው ስብከት ይሰጥባቸው የነበሩት ትምህርት ቤቶች የተከፈቱት የመንግሥት ትምህርት በቶች ባልነበሩባቸው በጥቂት የክልል ከተማዎች ሲሆን በጣልያኖች የቅርብ ቁጥጥር ይደረግባቸው የነበሩ ናቸው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ኒውማን እንዳሉት ትምህርት ይሰጥባቸው የነበሩት ቋንቋዎች ኢጣልያንኛና የአካባቢ ቋንቋዎች የነበሩ ሲሆን መምህራኑ በአብዛኛው ኤርትራውያን ቄሶችና መነኩሳት የነበሩ ሲሆን ተቆጣጣሪዎቹ ጣሊያኖች ነበሩ። ትምህርት የሚከታተሉት ተማሪዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ እንደነበር የጣሊያኖች ሪፖርት የሚገልጽ ሲሆን ትምህርት አቋርጠው ወደ ቤታቸው የሚመለሱትና ለአስተርጓሚነት ሥራ ትምህርት የሚያቋርጡ ብዙ ነበሩ። ይሰጥ የነበረውም ትምህርት እጅግ በጣም ዝቅተኛና ጥራት የጎደለው እንደነበር እንግሊዛዊው ጆርጅ እስቲር (George Steer) ገልጸውታል። ለጣሊያን ተሰልፈው የነበሩት የየአካባቢው ተወላጅ ወታደሮች ማንበብና መጻፍ የሚችሉት ከመቶ አምስት እንደማይበልጡ ታውቋል። ይሁን እንጂ በአገሪቱ ውስጥ የጣልያኖች ገብቶ መኖርና በጣሊያንኛ ቋንቋ ማስተማር መሞከሩ ብዙ የጣሊያንኛ ቃላት ወደ የአካባቢው ቋንቋዎች ሠርገው መግባታቸው በቀላሉ የሚታይ ክስተት እንደነበር ታውቋል።

### ከወራሪው ጣልያን ድል መመታት በኋላ ትምህርት በኢትዮጵያ

ከጣሊያን ወረራ በፊት ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ብዙ ጥረት በመደረግ ላይ የነበረ ሲሆን ተከፍተው የነበሩት ትምህርት ቤቶች ሥራ በድንገት በወረራው ምክንያት ሊቋረጡ ችለዋል። የሚያሳዝነው በውጭ አገር ሆነ በአገር ውስጥም ተምረው የነበሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን በወረራው ጊዜ መገደላቸው ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ ከጣሊያን ድል መመታት በኋላ በ1933 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ መንግሥትን መልሶ ለማቋቋም ሆነ ትምህርት መስጠትን ለመጀመር ከባዶ መነሳት ግድ ሆኖባቸው ነበር። ሁሉም ነገር የተጀመረው እንደ ታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ይህ ወቅት በዓለም አቀፍ ጦርነት ምክንያት የብዙ አገሮች ኢኮኖሚ የተጎዳበት ጊዜ ስለነበር ኢትዮጵያን እንደገና መልሶ ለማቋቋም እርዳታ ለማግኘት የማይቻልበት ወቅት ነበር። አገሪቱ የነበራት አማራጭ ወደፊት ለመራመድ የራሷን ጥረት ዋንኛው መንገድ አድርጎ መከተል ብቻ ሆኖ የነበረ ሲሆን ቀስ በቀስ ግን ያደጉት አገሮች ኢኮኖሚ ማገገም ሲጀምር ድጋፍ ማግኘቷ እየጨመረ መሄድ ጀመረ።

ነፃነቷን ካስከበረች በኋላ በ1936 ዓ.ም. የነበረው የትምህርት በጀት ብር 879,413 ብቻ ነበር፡፡ በ1937 ዓ.ም. ደግሞ ወደ ብር 1,772,451 ሊያድግ ችሏል፡፡ በየጊዜው የትምህርት በጀት ቀስ በቀስ እያደገ በመሄድ በ1941 ዓ.ም. የነበረው የትምህርት በጀት ብር 10,530,797 ደርሶ ነበር፡፡ በ1943 የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ቁጥር 425 ሲሆን የተማሪዎች ቁጥር 79,533 ነበር፡፡ ከዚህ ውስጥ የልጃገረዶች ቁጥር 11,370 ብቻ እንደነበር ታውቋል፡፡

ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በ1939 ዓ.ም. የመሬት የትምህርት ታክስ ታወጀ፡፡ በተጨማሪም ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከሚገባ በማንኛውም ዕቃ ላይ ለትምህርት የሚውል ተጨማሪ ታክስ ተደነገገ፡፡

ከወራሪው ጣሊያን ድል መመታት በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ማለትም ከ1936 ዓ.ም. እስከ 1943 ዓ.ም. የነበረው የእያንዳንዱ ዓመት በጀት በዝርዝር ሲታይ እንደሚከተለው ነበር፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1936 ዓ.ም. | ብር | 879,413 |
| 1937 ዓ.ም. | " " | 1,772,451 |
| 1938 ዓ.ም. | " " | 6,963,397 |
| 1939 ዓ.ም. | " " | 8,107,363 |
| 1940 ዓ.ም. | " " | 10,178,600 |
| 1941 ዓ.ም. | " " | 10,530,797 |
| 1942 ዓ.ም. | " " | 10,336,105 |
| 1943 ዓ.ም. | " " | 10,319,545 |

### የትምህርት አስተዳደር ሥርዓት

በጊዜው የትምህርትና ሥነ ጥበብ ቦርድ የነበረ ሲሆን ኃላፊነቱም የትምህርትን እድገት መገምገምና የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የሚያዘጋጃቸውን ፖሊሲዎች አጥንቶና መርምሮ ያመነባቸውን ማጽደቅ ሲሆን በሥራ ላይ ማዋሉ ግን የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነበር፡፡

በየጠቅላይ ግዛቱ የነበሩት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚተዳደሩት ከየጠቅላይ ግዛቱ በሚሰበሰበው የትምህርት ታክስ የነበረ ሲሆን ይህም በትክክል መፈጸሙን ለመከታተል የተለያዩ የትምህርት መመሪያዎች ለመስጠት እያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት የራሱ የትምህርት ቦርድ ነበረው፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር በማዕከላዊ ደረጃ ባለው የትምህርት ቦርድ ሲጸድቅለት የየጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቢሮ በሥራ ላይ የሚያውለውን በጀት ያስተላልፍ ነበር፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና በዋናው ከተማ የነበሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ወጪ የሚሸፈነው በማዕከላዊ ደረጃ ከሚገኝ በጀት ነበር፡፡

## ከነጻነት በኋላ የጥቂት ዓመታት የትምህርት ተሳትፎ

### አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ከ1-4ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከ5-8ኛ መካከለኛ ደረጃ፣ ከ9-12ኛ ክፍል ሁለተኛ ደረጃ በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ በአንደኛ ደረጃ አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ የነበረ ሲሆን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጥ ነበር፡፡ እንግሊዝኛ ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ነበር፡፡

በ1945 ዓ.ም. 412 የመንግሥት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን በሚቀጥለው ዓመት ግን የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር 62,387 ደርሶ እንደነበር ታውቋል፡፡ በዚሁ ዓመት (1946) የነበሩ ያስተማሪዎች ቁጥር 1541 ሲሆን የመምህርና የተማሪ ጥምርታ 1፡40 ነበር፡፡

መምህራን የሚሠለጥኑት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀን ትምህርት ቤትና በግርማዊት እቴጌ መነን የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት ሲሆን ትምህርት ቤቶች ለእረፍት ሲዘጉ የሙያ ትምህርት ኮርስ ይሰጥ ነበር፡፡

### መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

እነዚህ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ከ1-4 ክፍል ትምህርት ቤቶች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የእነዚህ ደረጃ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ከ8ኛ ክፍል በኋላ አገር አቀፍ ፈተና (National Examination) ይወስዱ ነበር፡፡ ፈተናውን ያለፉት ተማሪዎች በተለያዩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድበው ትምህርታቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡ በጊዜው የነበሩት ማዕከላዊ ትምህርት ቤቶች ቁጥር 119 እንደነበር ይታወቃል፡፡ በ1946 ዓ.ም. በእነዚህ 119 ትምህርት ቤቶች ያስተምሩ የነበሩ መምህራን እና የትምህርት ቤት ዲሬክተሮች 344 ኢትዮጵያውያንና 172 የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ፡፡

### ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ያሉት ክፍሎች መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያካትቱት የአካዳሚክ፣ የቴክኒክ፣ የንግድ (Commercial)፣ የግብርና (Agricultural)፣ እና የሙያ (Vocational) ትምህርት ዘርፎች ነበሩ፡፡ በሐረር ውስጥ ይገኙ ከነበሩት የመምህራን ማሠልጠኛና መድሐኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሌላ የጂማና የአምቦ የእርሻ ትምህርት ቤቶች፣ የጎንደር የጤና ጣቢያ እና በአዲስ አበባ የሚገኙ 7 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን ሌሎች በየጠቅላይ ግዛቱ የሚቋቋሙ ነበሩ፡፡ የአካዳሚክ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል ትምህርት ከፈጸሙ በኋላ የለንደን ዩኒቨርስቲ የጠቅላላ ትምህርት የምስክር ወረቀት እ.ኤ.አ. እስከ 1960 ዓ.ም. ድረስ የለንደን የሁለተኛ ደረጃ

ማጠናቀቂያ ፈተና (London University General Certificate of Education Examination) ይወስዱ ነበር፡፡[2]

በ1947 ዓ.ም. በአካዳሚክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 77 የውጭ አገር መምህራንና የትምህርት ቤቶች ዲሬክተሮች በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ይሠሩ ነበር፡፡ በመከፈት ላይ ላሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ 67 የውጭ አገር መምህራን እንደሚያስፈልጉም በጊዜው በእቅድ ሊያዝ ተችሏል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በይበልጥ ለማስፋፋት ለከፍተኛ ትምህርት ብቃት የሚኖራቸው ተማሪዎች ቁጥር በ1953 ዓ.ም. 525 መድረስ እንዳለበት በዕቅድ ተይዟል፡፡

#### የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚገቡባቸው በሐረር የሚገኘው የእርሻና ሜካኒካል ትምህርት ኮሌጅ (College of Agriculture and Mechanical Arts)፣ የኢንጂነሪንግ ኮሌጅ (College of Engineering)፣ የሕንጻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (Institute of Building Technology)፣ የቴክኒክ ኢንስቲትዩት (Technical Institute)፣ የባህር ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት (Marine Training Institute)፣ የጦር ኃይል ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት (Military Training Institue)፣ የጎንደር የሕዝብ ጤና ኮሌጅ እና ማሠልጠኛ ማዕከል (Gondar Public Health College and Training Centre)፣ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ (Universty College of Addis Ababa) ነበሩ፡፡ ከነዚህም ሌላ በጂማ ሌላ ኮሌጅ ለመክፈት ታስቦ ነበር፡፡

#### በውጭ አገር የሚማሩ ተማሪዎች

አገር ውስጥ ከሚሰጠው የከፍተኛ ትምህርት ሌላ ብዙ ተማሪዎች ከኢትዮጵያ ውጭ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በ1957 ዓ.ም. አካባቢ በውጭ አገር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ 400 ያህል ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከ300 በላይ ለሚሆኑት የትምህርት እስኮላርሽፕ የሚሰጠው የትምህርት ሚኒስቴር ነበር፤ አብዛኛዎቹም የሚማሩት በእንግሊዝ አገር እና በአሜሪካ እንደነበር ታውቋል፡፡

### የመምህራን አቅርቦት እና የውጭ እርዳታ

ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረው (በዓለም ታሪክ አንጻር ሲታይ) በኢትዮጵያ ብዙ ዘግይቶ ሲሆን፣ ከላይ እንደተገለጸው፣ በአፄ ምኒልክ ዘመን የተጀመረው ዘመናዊ ትምህርት በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የጣሊያን ወረራ እስካደናቀፈው ጊዜ ድረስ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶት ወደፊት በመራመድ ላይ ነበር፡፡ በወረራው

[2] ይህ የለንደን ፈተና ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው በ1939 ዓ.ም. ነበር፡፡ ይህም የተደረገው፣ ገና በአገሪቱ ውስጥ ይህንን ፈተና ለማዘጋጀት የሚችል ተቋም ስላልነበረ ነው፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በ1943 ዓ.ም. ሲከፈት የሁለተኛ ደረጃ ፈተና የማዘጋጀት ሀላፊነት ቢሰጠውም

ምክንያት የተማረ ሰው እጥረት ችግር በመኖሩ ከጣሊያን ድል መመታት በኋላ የተገኘውን የትምህርት ውጤት ለማግኘት በውጭ አገር መምህራን መጠቀም የግድ ነበር፡፡

በጊዜው ተቀጥረው ያገለግሉ የነበሩት የውጭ አገር የግል መምህራን እና የትምህርት አስተዳዳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ከተባበሩት መንግሥታትና ከወዳጅ አገሮች ይገኝ በነበረው ድጋፍ ጭምር የሚመጡ መምህራንም ነበሩበት፡፡ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታም ይሰጡ ነበር፡፡ በተለይም ከአሜሪካ የፓይንት ፎር ፕሮግራም፣ ከእስዊድን የቴክኒክ ተራድኦ አስተዳደር እና ከእስዊድን እና ኢትዮጵያ ቴክኒክ አስተዋጽኦ (Swdish Ethiopia Technical Mission) ከፍ ያለ ድጋፍና ርዳታ ተገኝቷል፡፡ ከተባበሩት መንግሥታት በጣምራ የገንዘብ ድጋፍ ተቀጣሪ የውጭ አገር ሰዎች ሌላ በዚሁ ጊዜ እ.አ.አ በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ 369 የውጭ አገር መምህራንና አስተዳዳሪዎች እንደነበሩ ታውቋል፡፡

### ኢትዮጵያውያን መምህራን

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር 2080 ሲሆን የከፍተኛ ተቋማት መምህራን ግን የውጪ አገር ሰዎች ነበሩ፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን ማሠልጠኛ የትምህርት ፕሮግራም መሠረት በየተቋሙ የሚሰጠው ሥልጠና የሚወስደው ጊዜ እንደሚከተለው ነበር፡፡

- የአራት ዓመት የስልጠና ጊዜ በሐረር መምህራን ማሠልጠኛ[3]፣
- የአራት ዓመት የስልጠና ጊዜ በአዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመላላሽ ትምህርት ቤት፣
- ልዩ የአንድ ዓመት ስልጠና በአዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመላላሽ ትምህርት ቤት፣
- ልዩ የአንድ ዓመት የእጅ ሥራ ስልጠና በግርማዊት እቴጌ የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት፣
- የትምህርት ኮርስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፣ እንዲሁም
- በክረምት፣ ትምህርት ቤቶች ለእረፍት ሲዘጉ፣ ለስድስት ሳምንታት በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቱ ለአካዳሚክና ለእጅ ሥራ መምህራን፣ ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አስተማሪዎችና ለትምህርት ቤቶች ድሬሰሮች የሚሰጥ ስልጠና ነበር፡፡

[3] ሐረር መምህራን ማሠልጠኛ አጀማመሩ አዲስ አበባ ነበር፤ ይህ ተቋም የተወሰነ ቁጥር የላቸውን መምህራንን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ካሰለጠነ በኋላ ወደ ሐረር እንዳዛወር

## ከትምህርት ሚኒስቴር ውጪ በሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚሠጡ ስልጠናዎች

ከላይ ከተጠቀሱት የሥልጠና ዓይነቶች ሌላ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ለየት ላሉ ኮርሶች በአስተዳደርና በትምህርት ዘርፍ በውጭ አገር ስልጠና ይሰጣቸው ነበር፡፡

ለአስተዳደር አመቺነት ሲባል ከትምህርት ሚኒስቴር ሌላ በሌሎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና የሥራ ዘርፎች የሚተዳደሩ የትምህርት ዘርፎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም የአየር ኃይል፣ ሲቪል አቪዬሽን እና ቴሌኮሙኒኬሽን ሠራተኞቻቸውን ለማሰልጠን ትምህር ቤቶችና የማሠልጠኛ ማዕከላት ነበሯቸው፡፡ ለፖሊስ ካዴቶች፣ ለሕዝብ ጤና ሠራተኞች፣ ለነርሶችና ለድሬሰሮች መሥሪያ ቤቶቻቸው የየራሳቸው ልዩ ልዩ የማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች ነበራቸው፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ የግርማዊት እቴጌ መነን የእጅ ሥራ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት የሚተዳደረው በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነበር፡፡ በጂማና በአምቦ የእርሻና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች የሚተዳደሩት በእርሻ ሚኒስቴር ነበር፡፡

### የግል ትምህርት ቤቶች

ክርስቲያን ሚሲዮናውያን የትምህርት ሚኒስቴርን ሥርዓተ ትምህርት በመከተል ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ብዙ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአገሪቱ የትምህርት ስርዓት በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ገብተው ትምህርታቸውን ለመከታተል ይችሉ ነበር፡፡ በአሊያንስ ፍራንሴዝ እና በሊሴ ገብረ ማርያም የትምህርት ተቋማት አማካኝነት የፈረንሣይ የባሕል ትስስር ወይም ግንኙነት ሊጠብቅ ችሏል፡፡ ብሪቲሽ ካውንስል በባሕልና በትምህርት መስክ ለረጅም ዓመታት እርዳታ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን የመንግሥት ትምህርት ቤት ለሆነው የጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በእርዳታ መምህራንን ይመድብ ነበር፡፡ ጥራት ያለው ትምህርት በአዲስ አበባ ውስጥ የሚሰጡ የአርመን፣ የእንግሊዝ፣ የግሪክ፣ የሕንድ እና የእስካንዲኔቪያን ሐገሮች ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን በዋናነት ትምህርት ቤቶቹ አገልግሎት የሚሰጡት ለራሳቸው ሕብረተሰብ ልጆች ሲሆን የእንግሊዝ ትምህርት ቤት ግን እስከ ዛሬም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ሲያስተምር ኖሯል፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘውን ናዝሬት የልጃገረዶች ትምህርት ቤትን ያቋቋሙት የካቶሊክ ሲስተሮች ነበሩ፡፡ ትምህርት ቤቱ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር እውቅና የነበረው ሲሆን በየጊዜው 6 ካቶሊክ ሲስተሮች (ማለትም አንድ ፈረንሳያዊት ዲሬክተር፣ 3 ካናዳውያን፣ አንድ የአሜሪካ ዜጋ እና ሌላዋ ከቺሊ ሲሆኑ)፣ ከአገር ውስጥ የተቀጠሩ ደግሞ ሦስት ኢትዮጵያውያን፣ ከነዚህ ሌላ አንድ ግብፃዊ፣ አንድ ሕንዳዊ፣ አንድ ማልታዊ

እና ሌሎች አውሮፓውያን በመምህርነት አገልግለዋል። አሥራ ዘጠኝ የልዩ ልዩ አገር ዜጎች ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ይማሩ ነበር።

የኢትዮጵያ ሴቶች የበጎ አድራጎት ማህበር ያቋቋመው ትምህርት ቤት እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ይሰጥ የነበረው ትምህርት የትምህርት ሚኒስቴርን ሥርዓተ ትምህርት የተከተለ እንደነበር ይታወቃል።

### የጎልማሶች ትምህርት

ለጎልማሶች የማታ ትምህርት በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኙ ትምህርት ቤቶችና በአዲስ አበባ ይሰጥ ነበር። በማታ በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የአርት ፋኩልቲ፣ በአሜሪካ ኢንስቲትዩት፣ በብርሃን ዛሬ ነው ኢንስቲትዩትም ብዙ ጎልማሶች ትምህርታቸውን ይከታተሉ ነበር።

የአሜሪካን ኢንስቲትዩት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ ጥቂት የአሜሪካ በጎ አድራጊ ዜጎች የተቋቋመ ነው። የተቋቋመውም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1946 ዓ.ም. ነበር። የአሜሪካን የኢንፎርሜሽን ሰርቪስ አዲስ አበባ ውስጥ የንባብ ቤት አገልግሎት ከማጥኛ ክፍል ጋር የሚሰጥ ሲሆን አዳራሹም ትምህርታዊ ፊልም ለማሳያና እና ለተሳታፊዎች አልፎ አልፎም በተጋባዦች ለሚደረጉት ንግግሮች ሲያገለግል ቆይቷል። የብሪቲሽ ካውንስል ቤተ መጻሕፍት ተመሳሳይ አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል። በተመሳሳይም የመስኮብ ቤተ መጻሕፍትም ተመሳሳይ አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል።

### መሠረተ ትምህርት ለሁሉም

መሠረተ ትምህርት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲዳረስ ሰኔ 1946 ዓ.ም. የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የትምህርት ቦርድ አጽድቆት የጊዜው አንዱ የትምህርት ፖሊሲ ሆነ። መሠረታዊ ትምህርት ለሁሉም (Basic Education for All) የታቀደው ለአራት ዓመት ትምህርት ሲሆን አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ነበር። ሆኖም ግን ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ሲገቡ ትምህርት መጀመር ያለባቸው በራሳቸው በቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን እንዳለበት በጥናት መልክ በጊዜው የቀረበ ቢሆንም በሥራ ላይ ግን አልዋለም። ጥናቱም አማርኛ የትምህርት መስጫው ቋንቋ እንዲሆን በዝቅተኛ ክፍሎች መጀመር እንዳለበት ገልጿል።[4]

### ማጠቃለያ

ከጣሊያን ወረራ በኋላ ከባዶ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ብዙ ጥረት የተደረገ መሆኑ ከላይ በዝርዝር ተገልጿል። ለዚህ ብዙ እና ወሳኝ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ኃይለ ሥላሴ የተለየ ስፍራ

[4] Ministry of Education and Fine Arts, "A Ten-year Plan for the Controlled Expansion of Ethiopian Education, Addis Ababa," June 1955 (1947 E.C.), p.93.

ሊሰጣቸው የሚገባ ነው። የርሳቸውንም አርአያነት በመከተል የሚመለከታቸው ሁሉ የተቻላቸውን ሁሉ ሲያደርጉ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ የትምህርት ቤቶችን እድገት በቅርብ ለመከታተል ይችሉ ዘንድ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴርነት ሥልጣን እርሳቸው እንደያዙት ለብዙ ጊዜ ቆይቷዋል። ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ በማነቃቃትና ትምህርት ቤት የገቡትንም ተማሪዎች መማራቸውን ለማረጋገጥ በማንኛውም ጊዜ በድንገት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ጉብኝት ያደርጉ ነበር። ክፍል ውስጥ በመግባት የመምህራን የትምህርት አሰጣጥና የተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል በመጎብኘት አስተያየታቸውንና ጥያቄም ካላቸው ጥያቄያቸውን ለትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች አቅርበው መልሳቸውን በጥሞና ያዳምጡ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ አዳሪ ትምህርት ቤቶችም ውስጥ በምግብ ሰዓት እየተገኙ ፍራፍሬ ለተማሪዎች በማደል ስለምግባቸውም ጥራትና በቂ መሆን ይጠይቁ ነበር። ችግር ካለ መፍትሄ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ይሰጡ ነበር። ለገና በዓል በአዲስ አበባ የሚገኙ ተማሪዎች ወደ ቤተ መንግሥት በመሄድ የገና ስጦታ ይሰጣቸው ነበር።

ወደ ውጭ አገር ለከፍተኛ ትምህርት የሚሄዱ ተማሪዎች ቤተመንግሥት ድረስ በመሄድ ማነቃቂያ ንግግር ተደርጎላቸው መመሪያ ከተሰጣቸው በኋላ እጅ ነስተው ይመለሱ እንደነበር የታወቀ ነው። ተምረው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱም እንኳን ደህና መጣችሁ ለመባል ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርበው መመሪያ ጭምር ይሰጣቸው ነበር።

አገሪቷ ያላትን ችሎታ መሠረት በማድረግ በበጀት፣ በሰው ኃይል፣ በትምህርት መሣሪያ በአጠቃላይም በአቅም ግንባታ ከፍተኛ ድጋፍ ለትምህርት ቤቶች በመስጠቱ (ከነበረው ችግር አንጻር ሲታይ) አመርቂ ውጤት ሊታይ ችሏል።

ይህ ትኩረት የተሰጠው ለአንደኛና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይሆን ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመገኘት ሽልማት እና የምስክር ወረቀት በመስጠት የዜጎች ትምህርት ለአገሪቱ ልማት እድገት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያንፀባርቅ ያደርጉ ነበር።

ከዚህም በላይ እንደተገለጸው ከፍተኛ ትምህርትም እንዲስፋፋ ብዙ ጥረት በጊዜያቸው ተደርጓል። የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሲሆን የኮሌጁን መሠረት የጣሉት መጋቢት 13 ቀን 1942 ዓ.ም. ነው። በኦፊሴላዊ ስነ ሥርዓት የተመረቀው ግን ጥር 17 ቀን 1944 ዓ.ም. ነበር። ለዚሁ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በ1953 ዓ.ም. ከአባታቸው የወረሱትን የመኖሪያ ቤታቸው የነበረውን የገነተ ልዑል ቤተመንግሥት አስረክበዋል።

## የአንደኛ፣ የመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እድገት

ከጣሊያን ድል መመታት በኋላ በኢትዮጵያ ትምህርትን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት ትልቅ እድገት ተመዝግቧል። በ1950ዎቹ መጨረሻ እና በ1960ዎቹ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ የትምህርት ቤቶችና የተማሪዎች ብዛት እንደሚከተለው ነበር፡-

| አስተዳደር | የአንደኛ ደረጃ | | መለስተኛ ደረጃ | | ሁለተኛ ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ት/ቤቶች | ተማሪዎች | ት/ቤቶች | ተማሪዎች | ት/ቤቶች | ተማሪዎች |
| የመንግሥት | 1190 | 471,077 | 233 | 63,405 | 52 | 48,303 |
| የቤተ ክህነት እና የእስልምና | 181 | 26,152 | 6 | 887 | 3 | 515 |
| የግልና ሚሲዮን | 926 | 158,295 | 102 | 8829 | 40 | 4182 |
| ድምር | 2297 | 655,524 | 341 | 75,121 | 95 | 53,00 |

ምንጭ፡- ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን ሰኔ 26 ቀን 1963 ዓ.ም.

## በጊዜው የተከሰቱ ችግሮች

በዚህ ዓመተ ምህረት ለትምህርት ከደረሱት ልጆች ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመማር እድል ያገኙት (Participation rate) 15.7 በመቶ የሚያህሉት ብቻ ነበሩ። የመማር እድል በገጠርና በከተማ መካከል የነበረው ክፍተት የባሰ እንደነበር የትምህርት መረጃዎች ያሳያሉ። በአውራጃዎች መካከል ይታይ የነበረው የተሳትፎ ልዩነት ከ0 እስከ 28 ከመቶ ነበር።

ለነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ምክንያት ከነበሩት ችግሮች ዋነኛው የበጀት ድልደላ እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ። ከነበረው ጠቅላላ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በጀት ከመቶ አርባ አንድ (41%) በላይ የሚመደበው ለሸዋ፣ ለአዲስ አበባ እና ለኤርትራ እንደነበር መረጃዎች ይገልጻሉ። እነዚህ ደግሞ በጠቅላላው በአገሪቱ ውስጥ ለትምህርት ከደረሱት ልጆች ውስጥ ከመቶ ሃያ አምስቱ (25%) ብቻ የሚገኙባቸው ነበሩ። ለዚህ ሁሉ መንስዔው የተስተካከለ ፕላን እና ፖሊሲ ያልነበረ በመሆኑ እንደነበር ታውቋል።

ሌላው ችግር በጠቅላላው ለትምህርት ከሚመደበው በጀት ውስጥ ከመቶ ሃምሳው (50%) ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚውል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከመቶ ሰላሳ ሁለት (32%) ያህሉ በ1ኛ እና በ3ኛ ክፍል መካከል ትምህርታቸውን ለሚያቋርጡ ልጆች የሚወጣ ገንዘብ እንደነበር ታውቋል።

## በ1966 ዓ.ም. የነበረው አጠቃላይ የትምህርት ሥርጭትና እድገት

ከጣሊያን ወረራ በኋላ የነበረውን ችግር ለመቋቋም በተደረገው ጥረት ለትምህርት ብዙ አስተዋጽኦ ተደርጓል። በጊዜው በአገሪቱ ብዙ የተማረ የሰው

ኃይል አለመኖር፣ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ መሆን፣ ሌሎችንም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት መልሶ ለማቋቋም የነበረውን ሰፊ ሥራ ታሳቢ በማድረግ፣ በትምህርት በኩል የተገኘው ውጤት ከፍተኛ ነበር ለማለት ይቻላል። በ1966 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርትን ሳይጨምር የትምህርት ቤቶች የተማሪዎችና የመምህራን (በየደረጃው) ብዛት እንደሚከተለው ነበር።

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤቶች | የተማሪዎች ብዛት | የመምህራን ብዛት | የትምህርት ቤቶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አፀደ ሕፃናት | 7570 | 190 | 77 |
| 2. | አንደኛ ደረጃ | 859,000 | 18,600 | 2,754 |
| 3. | መካከለኛ ደረጃ | 101,800 | 3,220 | 420 |
| 4. | ከፍተኛ ደረጃ | 81,300 | 2,960 | 112 |
| 5. | ልዩ ትምህርት | 522 | 40 | 6 |
| 6. | የቴክኒክና ሙያ | 5,500 | 550 | 59 |
| 7. | የአንደኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና | 3,100 | 190 | 10 |

## የተማሪ አስተማሪ ጥምርታ

አንድ መምህር ስንት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ማስተማር እንዳለበት ፖሊሲ ሊኖር ይገባል። ቀደም ሲል ምንም ዓይነት ፖሊሲ አልነበረም። ከጊዜ በኋላ ግን አንድ መምህር በአንደኛ ደረጃ በክፍል ውስጥ ሃምሳ ተማሪዎችን ማስተማር እንዳለበት መመሪያ ወጥቶ ነበር። በ1966 ዓ.ም. የነበረው የመምህር ተማሪ ጥምርታ ግን እንደሚከተለው ነበር።

| | | |
|---|---|---|
| 1) | አፀደ ሕፃናት | 40:1 |
| 2) | አንደኛ ደረጃ | 46:1 |
| 3) | መለስተኛ 2ኛ ደረጃ | 32:1 |
| 4) | መካከለኛ ደረጃ | 27:1 |
| 5) | ልዩ ትምህርት | 13:1 |
| 6) | ቴክኒክና ሙያ | 10:1 |
| 7) | የአንደኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና | 16:1 |

አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ከመጠን በላይ ብዛት ያላቸው ተማሪዎችን ማስተማር ሲኖርበት ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል። በተቻለ መጠን የተማሪ አስተማሪ ጥምርታ ተመጣጣኝ መሆን አለበት። ብዙ

የተማሪው ቁጥር ደግሞ በጣም አነስተኛ ሲሆን መምህሩ መሥራት የሚገባውን ያህል ሥራ አልሠራም ማለት ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ለትምህርት የተመደበው በጀት እንደባከነ ይቆጠራል፡፡

## የትምህርት ይዘት (ካሪኩለም)

ከ1966 ዓ.ም. በፊት የነበረው የትምህርት ይዘት ብዙ ችግር ነበረበት፡፡ ከጣሊያ ወረራ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት በየደረጃው የነበሩ መምህራንና አስተዳዳሪዎች የውጭ ዜጎች ነበሩ፡፡ በትምህርት ሚኒስቴርና በየጠቅላይ ግዛቱም የውጭ አገር ሰዎች የትምህርት አማካሪዎችና አስተዳዳሪዎች የነበሩ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው ትምህርት የአገሪቱን የተለያዩ ችግሮች ለመቅረፍ ታስቦበት የተዘጋጀ አልነበረም፡፡ የሚሰጠው ትምህርት ሰለጠኑ ስለሚባሉት አገሮች ማጥናትና ለማወቅ መሞከር ላይ በይበልጥ ያተኮረ ነበር እንጂ ስለኢትዮጵያ በማወቅና ችግሮቿን በመፍታት ወደፊት የምትራመድበትን መንገድ በመሻት ላይ ያተኮረ አልነበረም፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፍጻሜ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት የሚሰጠው ፈተና ከእንግሊዝ አገር የሚመጣ ነበር፡፡

በዚህም የተነሳ በጊዜው ተማሪዎች ስለአገራቸው ሳይሆን በይበልጥ የሚያውቁት ስለውጭ አገር ታሪክ፣ ባሕል፣ ሥልጣኔ፣ እምነት ወ.ዘ.ተ. ነበር፡፡ በጊዜው አሜሪካንና አውሮፓን ለስልጡንነት በምሳሌነት በመውሰድ ኢትዮጵያን በኋላ ቀርነት ብቻ በምሳሌነት መውሰድ የተለመደ ነበር፡፡ የብዙ ዘመን የሰፊ ታሪክ ባለቤት እና ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች አገር መሆኗን የሚገልጽ ለአገሪቱ ወጣቶች የሚሰጥ ትምህርት እምብዛም ነበር፡፡ ትምህርቱም በማሰብና በመመራመር ላይ ያተኮረ ሳይሆን በይበልጥ በቃል ጥናት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህም ሊያስከትል የቻለው ኢትዮጵያዊነትን ዝቅ አድርጎ የማየት አባዜ ሊሆን ችሏል፡፡

እነዚህንና ሌሎች የትምህርት ችግሮችን ለመቅረፍ የትምህርት ዘርፍ ጥናት (Education Sector Review) በብዙ ኢትዮጵያውያን ምሁራንና የውጭ አገር ጠበብቶች (Experts) ከተካሄደ በኋላ እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 8 እስከ 13 ቀን 1972 ዓ.ም. አፍሪካ አዳራሽ ውስጥ የመጨረሻ የጥናቱ ግምገማ፣ ማሻሻያና ማጽደቂያ ስብሰባ ተካሂዷል፡፡ ስብሰባውን የከፈቱት ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ፡፡ የስብሰባው ተካፋዮች 86 ኢትዮጵያውያን ምሁራንና 61 የውጭ አገር ምሁራንና ተመልካቾች ነበሩ፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ መሠረተ ትምህርት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚዳረስበትን መንገድ ለመቀየስና ጥራት ያለው የሁለተኛ እና የከፍተኛ ትምህርት አቅጣጫ ለማሳየት ነበር፡፡ ይሁንና፣ በአብዮቱ መፈንዳት ምክንያት፣ ጥናቱ ስራ ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡

## ማጣቀሻዎች

1. ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን፣ «የኢትዮጵያ የትምህርት ዓላማዎች»፣ 1963 ዓ.ም.
2. Long-term Planning Committee, “A Ten-year Plan for the Controlled Expansion of Ethiopian Education,” Addis Ababa, 1955.
3. R. Pankhurst, “The Foundations of Education, Printing, Newspaper, Book Production, Libraries and Literacy in Ethiopia,” *Ethiopia Observer* VI, (1962).
4. David Abner Tallbot, *Haile Selassie I Silver Jubilee (The Story of Significant Events in the Life of Ethiopia under Emperor Haile Selassie I, Covering the First 25 years of His Region)*, The Hague, 1955.
5. Tekeste Negash, *Rethinking Education in Ethiopia*, Uppsala: Nordiska Afrikainstitutet, 1996.
6. Various documents on Education Sector Review of 1972, Addis Ababa.

# National Air Carriers as Catalysts for Development: The Case of Ethiopian Airlines (ET)

*Semret Medhane (Col. Ret.)*

## Introduction

At the outset, let me state that what I have to say to you comes from my own personal experience and that all opinions and conclusions arrived at have no official character. At the same time, however, I take full responsibility for them and stand to be corrected if convinced otherwise. For many, it is a forgone conclusion that air forces are created to wage war and airlines to render transport. I am here tonight to try and point out that the transfer of aviation technology, whether military or civil, has contributed greatly for the development of our country. Aviation has served as the sole gateway for our landlocked country, hemmed as it was by former colonial territories of France, Italy and the U.K., some of whom have carried over the less than friendly postures of the colonial powers. Without a vibrant aviation sector, not only will our country suffer adverse economic consequences but Addis Ababa will also lose its role as an African metropolis. For the UNECA, the AU, and hosts of NGO's and diplomatic missions will certainly leave. It is such considerations and acute concern for my country's wellbeing that forces me to voice what may be offensive to some ears. I beg the pardon of those that may find my conclusions and proposed solutions offensive, or even naïve, for I know no better. I thank you in advance for lending me your ears, and eyes. A special thank you is due to the staff at ET, headed by Mrs. Emebet Tesfaye, who made available a complete data of ET's 60 years performance.

## Transfer of Technology

### *Background*

Even my sketchy knowledge of recent Ethiopian history convinces me that the country's rulers have sought the transfer of modern technology upon the realization of this ancient country's military weakness and economic underdevelopment. Most of all, knowledge was required to bring about a healthy growth not only to consolidate their own rule but also to ensure the betterment of their people.

In the late fifties, in the process of translating for an English history researcher, I was fortunate to have been exposed to several Amharic letters of our Emperor Tewodros to Queen Victoria of the British Empire. Emperor Tewodros was requesting not just military assistance to stave off threats to his country but also machines, which he had learned existed in Her Majesty's Empire, that plough and harvest many times faster than hosts of peasants. Interestingly, he also asked that knowledgeable individuals should accompany those “fire machines” so that they would instruct his subjects on their operation. He did not stop there. He went on to specify that his subjects should be taught not just to operate and repair those machines when they broke down, but also to manufacture spare parts for sustained operation. Indeed, he wanted his subjects to be able, in time, to manufacture the machines themselves in order for him not to be a burdensome ally of Her Majesty's Government. Astoundingly, as a quid pro quo, Emperor Tewodros offered the mutual support of two Christian empires, whose shared values and respect for human rights ought to be emulated by others, his country having abolished slavery in order to please God.

At that time, I was pursuing my studies to become an aeronautical engineer at the Imperial College of City & Guilds Institute of London University. I could not help but wish that Emperor Tewodros were alive to see that his wishes were starting to be fulfilled, admittedly not as quickly and as easily as he had wished or expected. He was seeking the transfer of knowledge through developmental assistance from Great Britain. The assistance never came. He was a century and a half ahead of his time. What came instead was an invasion, led by Lord Napier of Maqdala, which caused Emperor Tewodros to commit suicide. To my mind, the lesson to be learned from this tragic episode is that "Ask and ye shall be given" does not always hold in our earthly empires. On the contrary, Ethiopia should struggle persistently and leverage all assets at her disposal to acquire knowledge that is essential to improve her national wellbeing.

That successive rulers of Ethiopia, often against strong conservative resistance, were expending such efforts is a fact. Emperor Menilik's introduction of the railway, the telephone, and other similar innovations is adequate testimony. The conviction of our sovereigns that transfer of knowledge is essential for development is corroborated in a negative manner by Italian colonial policy in the Horn of Africa. To deprive the local population of this essential ingredient for development, Italy limited the level of academic education for the indigenous population to only four years during its half a century rule of present-day Eritrea and southern Somalia. In acquiring practical skills, the indigenous populations were limited to being helpers or "aiutanti" to Italian skilled personnel. To achieve this same end, Italy all but eliminated the few educated Ethiopians upon

occupying Ethiopia in 1936. My father was one of the survivors of this purge. Indeed, knowledge is recognized as the essential element for development by all, whether their motive is to transfer or to deny it.

One could ask why the efforts of our sovereigns did not yield the kind of results that have been obtained in Japan and lately in the Tiger Economies of Southeast Asia. It would take better brains than mine to identify all the weaknesses that have caused our backwardness. However, I feel certain that one weakness, perhaps the greatest one, is the political instability that has prevailed in our country in the past several centuries. Our inability to sustain positive developmental policies during changes of rulers or governments must have been perpetuated by the fact that such changes were invariably implemented through armed conflicts. The lack of peaceful transition, irrespective of the good intentions of those engaged in armed conflict to achieve change, has not only retarded accumulation of knowledge but also has bled collectively acquired knowledge through the exodus of educated and skilled personnel. It has not only retarded investment but also diminished our capacity to absorb it.

### *The TWA connection*

In the post World War Two era, Emperor Haile Sellassie faced the same dilemma of how to survive as a technologically backward country. Even as late as 1952, on the eve of our unification with Eritrea, I remember the venerable but pro-Italian weekly magazine, *Time*, proclaiming that, unified or not, we have not a single native engineer of any kind inside or outside our country. At the time, I was a SAAB B-17 bomber pilot who landed the first Imperial Ethiopian Air Force (IEAF) warplane at Asmara airport. The Italian-generated rumor in Asmara was that the pilots of IEAF were Swedes. It was necessary to put up an air show for the population, taxiing the aircraft with our heads sticking out of the bombers' cockpits in full view of the spectators, to dispel the low morale created by the rumor. It was to take a little longer to rectify the total absence of engineering capability in the country.

The country had been not only humiliated but also nearly obliterated by the superior technology that Fascist Italy possessed, especially air power. Hence, the transfer of knowledge to Ethiopians became our Emperor's highest priority. Ethiopia's bitter experiences as a landlocked country dictated that air transport be developed, without which the inflow of experts to transfer knowledge and the outflow of Ethiopians to acquire it at the rate required, would be nearly impossible. Also, in order not to experience again the helplessness of being bombed at will by an enemy, by high explosives, incendiaries and mustard gas,

the building of an Ethiopian air force was a must. Aversion to colonial powers in Africa, as well as many other good reasons, dictated that the establishment of an air force and an airline be entrusted to countries that have no colonial ambitions on Ethiopia or colonial history in Africa. The establishment and running of the airline was to be entrusted to Americans, and it materialized thanks to President Delano Roosevelt's deviation from the USA's Monroe Doctrine. Likewise, the establishment of the air force was assigned to the Swedes. Discussions were started with the USA and Sweden in 1945.

While attending the founding conference of the United Nations in San Francisco in 1945, delegates from Ethiopia took side trips to Washington DC to seek assistance from the US State Department for the establishment of an airline. According to verbal communication to me by two members of the team that undertook this task, namely H.E. Aklilu Habtewold, now deceased, and H.E. Ato Minase Lemma, now residing in Washington DC, TWA was persuaded by President Truman's administration to undertake the operation of the airline under commercial consideration. Hence, in December 1945, just months after the end of the 2nd World War, Ethiopian Airlines was established with the enormous capital outlay (then for Ethiopia) of half a million US dollars. Demobilized pilots and technicians from American forces that had fought in the 2nd World War were engaged by a TWA management team. The airline started operation in April 1946 with purchased war surplus C-47 or DC3 aircraft. Concurrently, Count Carl von Rosen, a Swede, led the establishment of the IEAF.

It was understood from the beginning that airline operations should be undertaken on sound commercial principles. Except for tax concessions for expatriate employees of ET, which was rescinded some twenty years later, no subsidy was provided to the airline. Non-payment of landing fees to the Civil Aviation Authority, which by some was considered a form of subsidy but was actually granted in view of the airline maintaining most domestic airfields, was rescinded a little while after that. No additional capital was ever injected by the Ethiopian government, except for 22 million US dollars in the early eighties as compensation for damages caused by government action. ET's present huge assets were accumulated by reinvestments of part of its profits to maintain growth. Nominal dividends were paid.

*From the Gooney-Bird to the Boeing B767 and going-on to the Dreamliner*

1. The twin piston engine and propeller-driven DC3 or Gooney-Bird seated 30 passages or carried 3 tons of cargo. Its most valuable attributes were that it could be put into operation relatively cheaply and that it did not need paved runways to land and take off. Hence, not only did it connect Ethiopia internationally, from Cairo in the north to Nairobi in the south as well as from Khartoum in the west to Aden in the east within our region, but it also connected the interior of the country. It helped to open the country for trade and development. Some fifty airports scattered throughout the country, mostly residual values of the Italian occupation, were used to build a domestic air transport network. It also served as a unifying factor for the nation by serving as a tool of the central government in the hinterland. From the initial year's uplift of 8,000 passengers, the uplift rose nearly threefold to 22,000 in the fifth year of operation. All allocated yearly losses continued to decline throughout the first three years of operation. Beyond the fifth year, yearly profits of less than half amillion Ethiopian Birr were being realized. The irreplaceable Gooney-Bird served ET for forty-six years before it was retired in 1993.

2. The bigger and faster twin piston engine and propeller-driven Convair-240 was introduced in 1950. Consequently, the route structure was expanded in all four directions. Its jet-assisted take-off would give it better payload from the high altitude of its home base. By 1955, passenger uplift had again increased three-fold to 67,000. Profits remained of the same order as in previous years. The Convair-240 served fifteen years before its retirement in 1965.

3. After a failed experiment with the competing Convair Constellation, which caught fire and crashed without loss of life near Khartoum in 1957, the four piston-engine and propeller-driven Douglas DC6B was introduced. Again, the route structure was expanded in all four directions. By 1960, passenger uplift had increased to 104,000, just over 50% over the 1955 figure or about 10% per year. Profits in the order of one million Ethiopian Birr started to be realized. The Douglas DC6B served twenty-nine years before its retirement in 1986.

4. In 1960, the four fan-jet engine Boeing 720B was bought, but its introduction was delayed for two years due to delay in infrastructure construction at Bole International Airport. The sixties saw the operation by ET of the Boeing 720B/707C and yet another expansion of the route

structure in all four directions. By 1965, 5 years later, passenger uplift had increased to 178,000, some 70% over the 1960 figure or about 12% per year. Passenger uplift was 232,000 by 1970, 245,000 by 1975 and 291,000 by 1980. Operating profits in the range of five million Ethiopian Birr started being realized.

5. During the heyday of Jumbo-jets in the late sixties and seventies, for lack of smaller sized long-range second generation jet equipment that would have been more suitable for the traffic flowing over ET's network, the service life of ET's B720/707 was extended to the eighties. By 1965 and 1970, passenger uplift of 231,000 and 245,000 was realized with improving profitability. Hence, for over two decades, the Boeing 720B/707C was ET's workhorse for its international routes and for numerous wet-leases that ET undertook to survive the lean years in the seventies. The type went on to serve a total of forty-three years before its retirement in 2004.

6. The introduction of the three fan-jet engine Boeing 727 in 1979 and the twin fan-jet engine Boeing 737 ten years later did not best meet ET's objectives, but it served to develop medium and short haul routes. By 1980, passenger uplift was nearly 300,000 but profits and cumulated company assets were on the decrease due to the prevailing unstable environment. The Boeing 727 served eighteen years before its retirement in 1997. During much of this period, ET suffered from its owner government’s disfavor while successfully resisting the imposition of Soviet equipment that were less fuel efficient and of inferior passenger appeal compared to available western equipment. The B-737 continues to serve to this day and beyond, having been upgraded to third generation attributes.

7. In 1984, the second-generation twin fan-jet Boeing B767, nicknamed the poor-man's jumbo-jet, was introduced. Again, the route structure was expanded in all four directions and passenger uplift increased to 510,000 by 1985 and to 586,000 by 1990. Operating profits of the order of 50 million Ethiopian Birr started being realized. This equipment type continues as ET's workhorse to this day and beyond. Starting in the early eighties, an attempt was made to develop the domestic traffic and make the domestic network financially viable by replacing the Gooney Bird. The DHC-6 was introduced in 1985, the ATR-42 in 1988 and the F-50 in 1996. But, to this day, the domestic service is subsidized by the international one.

8. To replace the aging 707/720 fleet, the second-generation narrow-bodied Boeing B757 was introduced in 1990. Passenger uplift increased by just

25% to 730,000 by 1995 and by 30% to 942,000 by the year 2000. Profits started to decline after peaking at 250 million Ethiopian Birr. By 1999, losses of considerable magnitude were being sustained due to the prevailing radicalized management practices imposed by the owner government.

9. The introduction of 12 upgraded B767-300 and B737-700 and the relatively more stable management of ET has created and maintained an upward swing by the first decade of the 21st century. In spite of the worsening climate that played havoc with the global air transport industry, passenger uplift reached an all time high of 1,552,000 and operating profit rose to 377 million Ethiopian Birr by 2005. These two types of aircraft are likely to enjoy an extended service life to well after the B787 has entered service with ET, destined to be its launch customer.

10. In 2004, decision was taken to acquire and orders placed for ten Boeing Dreamliners or B-787. An expansion as well as deepening of the route structure is being attempted in ET's Vision-2010. Radically changed air transport environment appears to have favored the construction of third-generation long haul equipment suitable for serving thin routes point to point. ET's thinnest and longest routes of any regular scheduled air carrier can at last be competitively served, although it would be by “hubbing” over its home base and not point to point due ET's heavy reliance on sixth freedom traffic rights. Barring unforeseen circumstances, the projected yearly passenger uplift by the year 2010 under ET’s Vision 2010 plan is 3.5 million and profits of 75 million USD on a revenue of 950 million USD.

## The Struggle for Ethiopianization

### *Flight Operations*

1. While Ethiopian Airlines started commercial operation in 1946 with American aircrews, the IEAF started as a flying school simultaneously. Ethiopian pilots were given basic flight training on the all metal SAAB Safir which had retractable tricycle landing gears, flaps and, on later versions, propeller pitch control. At that time, the SAAB Safir was considered too complex for basic training by most air forces including the Swedish Air Force. But, the performance of Ethiopian trainee pilots, who had no previous exposure to mechanical vehicles (some could not even ride a bicycle), was so good that this assumption was dispelled. Operational training was undertaken on the SAAB B-17 and the Fairey Firefly in the late forties and fifties. When the USA started assisting Ethiopia in building

an air force, the North American T-28, Lockheed T33, North American F-86F and the Northrop F-5A&B were introduced in the sixties and seventies.

2. Ethiopian pilots were released from the IEAF to ET starting in 1951 and continue trickling in to this day. I was among this first group of pilots proposed by the IEAF, along with Captain Alemayehu Abebe, who subsequently became the first Ethipian captain. But during the interview, I declined the offer, to the surprise of Ato Tecle Rorro, the Civil Aviation Director at the time, and Captain Vic Harrell, the ET General Manager. I remember the latter saying loudly: “You will fly 100 hrs each month and earn fourfold of what you earn here”. I persistently shook my head to the delight of General Aseffa Ayene, my mentor and later commander of the IEAF. My brother Captain Addamu Medhane was among the first batch to be released from the IEAF. But his group arrived from the UK with commercial airline pilot's licenses, a few months after Capt. Alemayehu's batch had earned their licenses in the country.

3. However, the healthy growth of ET could not be accommodated by the meager supply of pilots from the IEAF. Nor was the continued hiring of American pilots economical for ET's operation. During my first year as Deputy General Manager of ET, after my negotiations with the IEAF to expand its existing flying school to accommodate ET's trainee pilots requirement failed, ET started its own flying school in late 1964. This development was not in line with the previously accepted philosophy that the Ethiopian government ought to provide trained personnel to ET so that its operation would be on the basis of sound commercial principles. Further, ET's pilot requirement did not warrant a large enough flying school that could operate efficiently and the assumption that foreigners would come to train as pilots in Ethiopia to increase volume for efficiency was ridiculed at the time. But, ET's operation became more cost-effective from the input of Ethiopian pilots and foreign students flocked to the school, boosting trainee numbers and thereby rendering the school efficient. The ensuing record demonstrates that operating under sound commercial principles require taking different paths in different countries of varying economic and social environment. The performance of ET's Flying School over the years has been laudable. It has trained nearly 800 pilots, nearly half of whom have been expatriates from 37 countries of Africa, Asia and Europe.

4. ET's flight operations maintained an enviable safety record for many years, except for a period of turmoil in the country in the late seventies and the ensuing disruption of proper management. It sustained high efficiency

financially and otherwise. The high investments required to train and maintain cockpit crew dictated that, the national pride requirement of operating a high tech industry having been satisfied, already trained American captains be retained up to their mandatory retirement age of 60 years.

### *Maintenance*

1. In an effort to satisfy the initial assumption of sound commercial principles, the Ethiopian government opened an Aviation Technical School with ICAO assistance. Together with the IEAF, the school started supplying technicians to ET. Again, following a similar path to that of pilot training, ET opened its own technical school in 1967. ET's technical school, like its pilot training school, quickly gained an enviably good international reputation and acceptance by ICAO, USA-FAA, UK-CAA and French-BV enhanced its image and facilitated its work. Among innovations that won laudable reputation for the school was its deployment of hands-on training on airworthy equipment. ET's technical school has, as of today, trained 2130 technicians, 1431of whom are expatriates from numerous countries that have become loyal customers.

2. Technical Services became ET's lifesaver, not just by ensuring safe and regular flights but also by providing its services at relatively low cost. Maintenance and overhaul services rendered to other operators grew to reduce significantly ET's own maintenance costs. Its repair and overhaul activities covered all aspects of restoration of flying hours and repair of damaged parts. These activities included overhaul of jet and piston engines, airframes, avionics, etc. at costs well below the industry average. Additionally, maintenance and repair work accomplished for other carriers brought in revenues that, in the form of overhead credits, further reduced maintenance costs of ET's equipment.

### *Commercial & Financial*

1. In these and other sectors, the government high schools, commercial colleges and universities supplied a steady stream of applicants who underwent rigorous skills training at ET's schools before being hired. They continued their development to supervisory levels and beyond.

2. The competitive edge that ET enjoys, both in service quality and economical operation, comes from this largest group of employees.

***Management***

1. The most important aspect of human resource development for ET has been its management staff. The skill, dedication and integrity requirements are greatest for this group since correct deployment of resources is the key for success. As such, this group was the last to be Ethiopianized, with me becoming the first to assume the post of General Manger in 1971, ET's 25th year of service to the nation. The important consideration behind this decision was not to Ethiopianize for the sake of political prestige but to gain for ET and the country a stable and economical management resource, while improving on the qualities of the above-mentioned three essential elements.

2. Starting in the sixties, to reach and maintain a comfortable level of redundancy in management resource, in-house and external management courses were offered to supervisors and above. Career development and management trainee programs were launched. These programs continue, except for weakness in the career development sector, averting dire consequences from the brain drain that has afflicted our nation of late.

ET's Ethiopianization programs were methodical and from the ground up, focusing on productivity and quality. Its continuous application created a process that continues to supply qualified personnel long after all expatriates have departed. I have not come across any other airline that trains nearly all of its aspirant employees before they are hired. In my opinion, this process is the single most important element that enabled ET to survive obstacles that no airline should be made to face. Among these obstacles are: low volume of own traffic, politically motivated high-jacking of airplanes, revolutionary environment that destabilized proper management and started off the huge brain drain, as well as all other obstacles faced by normal airlines that are failing, including its mentor of thirty years, TWA. To date, ET has hired and trained over 15,000 employees of its own, all of whom have gained not only the professional skills required to carry out their functions but, perhaps more importantly, have become more conscious citizens with worldwide exposure. Their influence on their extended family members and others must have had manifold benefits.

## ET as a vehicle for national integration

### *Opening of the Ethiopian interior*

1. ET's services to such otherwise inaccessible corners as Tepi, Waka, Masselo, Gode, and assigning to and hiring employees from such places have provided more than essential transportation links to the interior. ET's services have helped to create awareness of our whole national entity among all segments of our societies. It has also symbolized the visible presence of the central government in remote areas of the country, often transporting government officials and their instruments for administration and rule.

2. But there has been a controversial side to this. As owners of the airline, governments have provoked political opposition groups into sabotaging ET’s civil air transport operation. Government use of ET’s air services to transport military hardware and personnel in times of conflict, although limited to and from non-combat areas, has aggravated the situation.

## ET as an African airline

### *"Bringing Africa Together"*

1. While most African airlines plied the North-South or Europe to Africa routes, ET kept on investing in the developments of routes that directly connected African countries. One can assume that this policy of ET, faithfully applied over the years even when the going was extremely tough, was the primary factor that attracted the UNECA to Addis Ababa. This reward, followed closely by the installation of OAU’s headquarters in Addis Ababa in 1963, made it mandatory for ET to continue developing its African network. Embassies and NGOs followed in the footsteps of the OAU and UNECA, gaining for Addis Ababa the designation of Africa’s political capital. While ET continues to reap rewards from its home base, the city’s fate - and indeed the county’s welfare - are also linked to the existence of a strong and growing ET.

2. Over the past two decades, African business traffic has overtaken the value of western leisure traffic in importance to ET’s revenue. The flow of business traffic to the Middle East and Asia without transiting European capitals is a direct consequence of services availed by ET to the African continent, with immediate onward connections to the East.

3. No other air-carrier serves as many African cities as ET does. ET has brought Africa together and plans to strengthen this aspect in the coming years with all its available resources.

4. To survive the global competition they face and to ameliorate the environment that they work in, African airlines needed to take well-considered and agreed-upon group actions. ET has been at the forefront in developing cooperation among African airlines through the formation and consequent work of the African Airlines Association (AFRAA).

## The Challenges of African Aviation

### *The genesis of AFRAA*

The early stages of de-colonization in Africa brought about new leaders whose visions for the continent included attaining economic progress through group action. Since institutions for inter-state cooperation existing at the time did not fully satisfy the ambitions of the under-developed states in Africa, new means for coordinating plans and actions were sought. Because of their efforts, the United Nations Economic Commission for Africa (UNECA) came into being and was headquartered in Addis Ababa. A new institution to coordinate policies, plans and actions of African States towards their eventual complete integration, the Organization for African Unity (OAU), followed suite in 1963; it was also headquartered in Addis Ababa. Through these and other organizations, representatives of independent African entities struggled to right wrongs, isolate distasteful practices and promote policies conducive for their development. An aspect of this struggle was the efforts of African airline delegates to oust South Africa Airways (SA), the national airline of the then distasteful State, from the International Air Transport Association (IATA). It is in this environment that AFRAA was conceived.

An African walkout from the proceedings of the IATA General Assembly in 1963 in Rome yielded the opposite result: it left SA, the culprit, securely inside. African air-carrier executives, including myself, attending the IATA General Assembly in 1964 in Bogota (Colombia) met in a hotel room to devise ways of achieving, in their area of competence, the isolation of the apartheid regime. Their meetings continued in Addis Ababa, chaired by me, and in Abidjan, chaired by the Senegalese Sheik Fall, finally achieving an amendment to the IATA Articles of Association. The amendment opened a door for governments to influence IATA membership through their actions in the International Civil Aviation Organization (ICAO). As fate would have it, however, the first IATA member casualty of this amendment became the Taiwanese national carrier. SA

remained immune, since ICAO never terminated South Africa's membership.

Flushed with this modest success and, more importantly, accustomed to discussing mutual problems with a view to finding acceptable solutions, African member airlines of IATA decided to establish their own forum to coordinate their air transport policies and in general ensure their collective well being. Their meetings continued until the seventh session, in Accra (Ghana) in 1968. That effectively became the founding conference of AFRAA. An illustration of the problems that dog African air transport happened during this founding conference. The de facto chairperson, the Chief Executive Officer (CEO) of Ghana Airways, was removed from his office by the Ghanaian head of state during the first day of the conference. I, as co-chairman, brought the work to conclusion on the second day. What followed is history. Overcoming fragile political and at times non-conducive environments, AFRAA succeeded not only in holding its AGAs (Annual General Assemblies) every year but also in organizing the numerous meetings of specialized committees that make each AGA Annual General Assemblies) effective.

Early achievements included getting chief executives of fifteen, eventually thirty-five, African airlines and their key staff to table their visions for African development, identify obstacles in their path and devise cooperative means of achieving the desired objectives. Perhaps the greatest challenge in this respect was the maintenance of continuity of cooperative programmes in the face of constant changes of chief executives of airlines as well as the consequent changes in expert staff. Mostly, African governments, in the course of exercising their perceived rights to make political appointments, induced such changes. Measures to promote togetherness, such as the AFRAA soccer league and cabin service contest, were instituted. Ironically, their success over a decade planted the seed for their discontinuance, as enhanced competitive spirit threatened growth of cooperative measures. Against all odds, good advices in technical, commercial, legal and regulatory areas were being submitted yearly by AFRAA for implementation by member airlines. Through the observer status in the OAU that it acquired in 1976, AFRAA provided relevant inputs towards harmonizing state policies as regards African air transport.

### *Is Pan-African Airways only a dream?*

As decades fly past, the realization that intra-Africa trade is the key to African air transport development sinks in deeper. The formation of regional trade groupings, which depend on sound transport infrastructure to realize their goal, is an encouraging factor for the development of air transport. Sound regional

networks, which would constitute a strength for an African air industry, can grow only if air transport service is reliable enough and could be priced reasonably to meet regional trade needs. Such routes, merged with competitively operated intercontinental routes of African airlines, can be the foundation for a sound African airline industry. African economic development needs sound air transport, but air transport itself needs a thriving African economy to remain a viable industry.

For such an air transport scenario to evolve and to remain in the forefront, undivided attention ought to be given to the development of African human resources, most importantly management resources, to ensure a motivated and quality workforce. Only with such manpower deployment can a proper match of equipment in all relevant fields of air transport production be made. With judicious utilization of the generated financial revenue, Africans can produce competitive air services at cost levels that will satisfy their regional needs while giving them adequate margin to compete on intercontinental routes. Workforce productivity at par with that of the industrialized world, offering services at wages of the developing world, is needed to build the basis for sound African air traffic growth. Therefore, throttling down the drain of skilled and competent human resources from Africa as well as sustained investment in human resource development must take first priority. This state can be achieved by maintaining environments that are conducive for workforce retention, and not by coercive action. Collectively, African governments have to succeed in creating the stability required for the sustained investment indicated above before an African air transport industry can come into its own.

The recent spate of failures of national and multinational African airlines does not augur well for the realization of a Pan-African Airways. Indeed, lack of a successful continental model anywhere in the world casts doubt on the viability of such a concept for continental development. Instead, joint ownership of viable airlines by governments and private institutions centered on the surviving airlines appears to be gaining ground. Several examples are in evidence, including the one being attempted by ET in Ghana. It remains to be seen whether these developments will eventually lead to the creation of a Pan-Africa Airways. But, the sheer diversity of the obstacles that have to be overcome to realize that dream makes its attainment unlikely, at least in my lifetime. The failure of Air Afrique, East African Airways and Central African Airways has sent a clear message that attempts to create a Pan African Airways by African governments will not meet with easy success. Indeed, these failures may indicate that a Pan African Airways dream, if ever realized, could quickly turn into a nightmare.

## Lessons for the Present and Future

### *Peace, Stability, Awareness and Teamwork*

1. In examining the performance of ET over the past 60 years, one can not fail to notice that its performance has drastically plunged during violent social and political changes at its hub, requiring years to recover to previous levels. One such occurrence was in the seventies and another in the nineties, both with lasting consequences. Even the present confrontation over parliamentary election results has initiated telltale signs of damage in the form of booking cancellations to the country, of about 20% from some origins. Although ET takes mitigating actions automatically when such losses occur, one could conclude that ET could not have thrived otherwise, and may in fact have disappeared like so many other airlines, in the absence of peace and stability in the country. An example of the mitigating action taken by ET in the seventies, when revolution and civil wars hit the country, is the deployment of ET's equipment and manpower resources in the service of other countries. Deciding ahead of its European competitors, ET succeeded in wet-leasing its B-707C fleet to IranAir, Saudia and other airlines. The wet-leased capacity was of equal magnitude to that deployed for ET's own business, indicating that half of the then ET's three thousand employees were supported by services to airlines of oil rich countries. Consequently, although its own business had received crippling bashes, ET saved itself with its precious manpower almost intact. This gave the incumbent government time to learn of the adverse consequences of their actions and change course before the complete demise of ET became inevitable.

2. The importance of ET's hub for the country's growth is immeasurable, for Addis Ababa is not only the political capital of Ethiopia but is also;

    - the only gateway to this land locked country,
    - its commercial and industrial center, and
    - the transportation and communication hub to all its regional states.

    In addition to the above major characteristics, Addis Ababa is well on its way to becoming the political capital of Africa. An awareness of this fact by all sectors of the society, especially by the many layered administrations, is a must for the continuation of the services Addis Ababa renders the nation. If

Addis Ababa deteriorates, the country will suffer heavily both economically and politically.

3. Bole and other international airports are vital segments of the whole picture. As such, all Ethiopian entities functioning in this domain, be they government entities or merchants and user air-carriers, including ET, must understand that their fates are tied to one another. They must work as a team to satisfy all present and future users of the facility, inspiring the feeling of “Yichalal” (“It can be done!”) on employees of all segments and inducing them to perform better than any competing air transport hubs in the region. Meeting, or even exceeding, the expectations of the airborne traffic, be it passenger or cargo, that utilize our airports should be their number one priority. Low performance by this informal team, whether induced by an indifferent bureaucracy, or malpractice and greed by commercial entities, or plain thievery by employees of all categories, will have severely adverse consequences not only for ET but also for Addis Ababa and Ethiopia. The extent of possible damage being horrendous, all segments of society, including the government and judiciary, should continuously take proper actions to ensure that our airports earn and retain an enviable reputation for efficiency and friendliness.

### *Consistent use of sound commercial policies by ET*

1. ET must be allowed to exercise sound commercial principles at all times. It ought to be free of political intervention by governments except for long term strategy consideration. Damaging political decisions taken in the seventies affecting management and unionized workforce alike, operating standards, equipment choice, should remain part of a history that should never be repeated. The ill-advised radical management philosophy imposed by the owner government in the nineties has also done harm to ET's ability to serve the country, despite the good intentions of the perpetrators. The country's interests are best served by allowing dedicated professionals to exercise their trade not only unencumbered but with encouragement and appreciation of the work being performed by them. Governments have a vital role in shaping and maintaining ET's performance in line with the country's vital interests. Of crucial importance is keeping the gates of Ethiopia open to the world at large and to the African region in particular, and this function can be achieved only with a virile and growing ET.

2. The selection, training and motivation of ET’s manpower should follow a set pattern that will lead to a work ethics and productivity of employees that


equals the best in the industry, while maintaining a payroll structure related to the county's environment. The other major elements of airline costs, such as fuel, aircraft, insurance and capital offer disadvantageous conditions owing to ET's low traffic volume and miniscule operation. For example, with the possible exception of the recent B-787 purchase as a launch customer, ET has in the past paid much higher prices for each of its new airplanes and paid higher interests for borrowed capital than any of its major European competitors. It continues to pay higher prices for fuel due to its meager uplift at each of its numerous stations save Addis Ababa. What, with operations in politically volatile regions beset with security concerns and meager safety-enhancing infrastructure, ET has long ago ceased to enjoy insurance rates as an adjunct to TWA. Employee productivity happens to be the only area where ET can have a margin for survival. ET's employees must understand this inescapable truth and support a viable policy in this respect if their airline is not to go the way others have gone in front of our very eyes. Employees must also realize that, should such a calamity happen, they would be the first to suffer and they would be responsible for having brought damage to their country far greater than the damage they have incurred.

3. That the value of ET goes well beyond the direct material benefits emanating from its operation should be well understood by the leadership of not just the City, State, and Federal governments, but also by those who aspire to lead in all segments of the society. To give an order of magnitude to this statement, ET's earnings of 2005 amounting to 4.3 billion Ethiopian Birr is expected, at even a conservative estimate, to more than double and rise to nearly 10 billion Ethiopian Birr per year by the year 2010. Most of these amounts come from sources outside Ethiopia. When we deduct expenses incurred for non-local elements such as fuel, aircraft, etc. we can still appreciate the sizable contribution to the local economy that this represents. It is of the order of several billion Ethiopian Birr per year in hard currency. The damage that would be caused to the national economy by the failure of ET would be in the tens of billions of Ethiopian Birr, quite apart from the disastrous political consequences**.** Our political, civic, religious and business leaders ought to take such a scenario to heart and act to ensure that ET and the vital elements that go with it are nurtured in the county's interest.

## Annex: Five Year Operational and Financial Data, 1946-2001

| | 1946/47 | 1950/51 | 1955/56 | 1960/61 | 1965/66 | 1970/71 | 1975/76 | 1980/81 | 1985/86 | 1990/91 | 1995/96 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ASK('000)** | | | | 261,348 | 674,513 | 1,082,873 | 1,240,550 | 1,383,906 | 2,034,693 | 2,684,777 | 3,222,841 | |
| **RPK (000)** | 4,865 | 16,847 | 49,275 | 105,151 | 233,888 | 314,681 | 454,371 | 722,626 | 1,090,676 | 1,474,215 | 1,837,681 | 2,688,636 |
| **ATK (000)** | | | 13,534 | 33,606 | 84,253 | 132,988 | 140,679 | 192,484 | 375,309 | 603,247 | 679,364 | 858,656 |
| **Load Factor** | | | | 40.2 | 34.7 | 29.1 | 36.6 | 52.2 | 53.6 | 54.9 | 57.0 | 60.3 |
| **REVENUE (000)** | 1,106 | 3,675 | 9,719 | 23,436 | 46,217 | 59,097 | 96,654 | 213,763 | 376,109 | 643,327 | 1,642,844 | 2,361,559 |
| **EXPENSE (000)** | 1,704 | 3,524 | 8,980 | 19,493 | 41,329 | 62,085 | 89,072 | 210,074 | 330,065 | 584,478 | 1,478,974 | 2,292,707 |
| **OPER.Profit (000)** | (598) | 151 | 739 | 3,943 | 4,888 | (2,988) | 7,582 | 3,689 | 46,044 | 58,849 | 163,870 | 68,852 |
| **NET-PROFIT** | (598) | 157 | 700 | 3,039 | 2,997 | (4,220) | 4,335 | 70 | 14,477 | 18,809 | 58,317 | 55,138 |
| **No. of employee** | 146 | 377 | 593 | 895 | 1,833 | | 2,828 | 2,950 | 3,380 | 3,421 | 3,309 | |
| **pax no** | 8,000 | 22,347 | 67,023 | 104,067 | 177,586 | 231,907 | 245,465 | 290,917 | 509,620 | 585,517 | 730,460 | |

National Air Carriers as Catalysts for Development:  The Case of Ethiopian Airlines (ET)



# የኢትዮጵያ ቴሌኮምዩኒኬሽን ምሥረታና ዕድገት እስከ 1966 ዓ.ም

*በትሩ አድማሴ*

### መቅድም

ቴሌኮምዩኒኬሽን ከሰው ልጅ መገናኛዎች አንዱና በቅርብ ዘመን የመጣ ቢሆንም ባለፈው 1000 ዓመት ከተፈለሰፉት በሺህ ከሚቆጠሩ የሰው ልጅ መገልገያዎች በጥቅሙ ከመጀመሪያዎቹ ደረጃ ላይ የሚመደብ ነው። ባለፈው ሺህ ዐመት ከተፈለሰፉት በቀጥታ ጥቅም ላይ በመዋላቸውም ሆነ ወይም ለሌላ ፍልስፍናና ግኝት ፈር ከከፈቱት መሠረታዊ ፍልስፍናዎች፣ አንድ ምሁር በዋናነት 10 ምረጥ ቢባል፣ በአስሩ ውስጥ፣ ኤሌክትሪክ፣ ቴሌግራፍ፣ ራዲዮ እና ትራንሲስተር ያካትታል። ዛሬ ብዙዎቻችን የምናውቀው ከቴሌግራፍ ይበልጥ ቴሌፎንን ቢሆንም፣ ከላይኛው ምርጫ ውሰጥ ያልተካተተው፣ ቴሌፎን በቴሌግራፍ ፍልስፍና ላይ ስለተመሰረተ ነው።

የቴሌኮምዩኒኬሽን ትርጉም "የሩቅ መገናኛ" ማለት ሲሆን፡ ቴሌግራፍ፣ ቴሌፎን ፣ ራዲዮ፣ ከሮድካስቲንግ፣ ቴሌቪዥን፣ ፋክስ፣ እና ማንኛውንም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሞገድ ወይም ጨረር አማካይነት በሩቅ የሚያገናኘውን ሁሉ ይሸፍናል።

በጊዜ ወደኋላ መለስ ብለን የጥንቱ ኮምዩኒኬሽን ምን እንደሚመስል እንየው። መልእክትን ከቦታ ቦታ ለማስተላለፍ ከፈጣን ሩዋጭና ከፈረስ የተሻለ አማራጭ አልነበረም። ዛሬ የማራቶን ሩጫ የምንለው የተጀመረው መልእክት በፍጥነት ለማድረስ ነበር። በ 490 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ዳሪዮስ የሚባለው ታላቁ የፋርስ ንጉሥ ግሪክን ለመያዝ ዘምቶ ማራቶን በሚባለው ቦታ ከባድ ጦርነት ተኪያሒዶ ብዙ ግሪኮች አልቀው ጦርነቱን ድል አደረጉ። ይህንኑ ዜና በፍጥነት አቴና ለማድረስ ፊዲፔዲስ የተባለ ፈጣን ሩዋጭ 42 ኪሎሜትር ወደአቴና ሮጦ ደስ ይበላችሁ አሸነፍን ብሎ እየጮኸ እንደደረሰ ሞተ ይባላል። ሌላው የሩቅ መገናኛ ዘዴ እሳት ማንደድ፣ከበሮ መደለቅ፣ ጢስ ማጤስ ነበር።

የሳይንስ ምርምር እየተስፋፋ ቴሌስኮፕ ከተፈለሰፈ በኋላ በ 18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ሴማፎር የሚባል መገናኛ ዘዴ በፈረንሳይ አገር ተጀምሮ ኤውሮጳ በሰፊው ተጠቅመውበታል። አሠራሩም በፎቆችና በኮረብታዎች ላይ ረጂም ምሰሶ በሰው ቅርጽ ተክሎ፣ ለእጆቹ አቅጣጫ በፊደሎች ኮድ ወስኖ በሩቅ በቴሌስኮፕ ምልክት ማንበብ ነበር። በናፖሊዮን ጦርነት ዘመን በሰፊው ተጠቅመውበታል። በጥሩ ቀን አስከ 10 ኪሎሜትር ርቀት ማንበብ እንደሚቻል ይነገራል። እኔም ተማሪ ቤት ቦይስካውት በነበርኩበት ጊዜ በኮዱ ተጠቅሜበታለሁ።

ዛሬ ቴሌኮምዩኒኬሽን የምንለው ተፈጥሮውም አሠራሩም ከዚያን በፊት ከተሞከረው ሁሉ የተለየ ነው። የሚሰራው በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሞገድ

(ጨረር) ሲሆን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው የሚተላለፈው በአንድ አካል አማካኝነት፣ (ለምሳሌ ሺቦ)፣ ወይም ያለምንም አካል ዕርዳታ በህዋው (በስፔስ) ነው። ፍጥነቱ ሶስት መቶ ሺህ ኪሎሜትር በሴኮንድ ሲሆን፣ የተፈለሰፈውም የዛሬ 175 ዓመት ነው። በአሜሪካና በኤውሮፓ የቴሌግራፍ ሥራ በ 1832፣ እንዲሁም ቴሌፎን በ 1870 ተጀመረ።

## ከምኒልክ እስከ ፋሺስት ጦርነት (1886 - 1928)

የምዕራባውያንን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ባላቸው አርቆ አስተያየት ዳግማዊ ምኒልክ በ 1886 ዓም፣ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ የቴሌግራፍ/ቴሌፎን መስመር መዘርጋት አስጀምረው በ1888/89 ሥራ ላይ ዋለ። ይህም በምዕራብ፣ ማለት በኤውሮፓና በአሜሪካ፣ የቴሌፎን አገልግሎት በጥቅም ላይ በዋለ በ16 ኛ ው ዓመት መሆኑ ነው። እንዲሁም፣ በዚሁ ዓመት የባቡር መንገድ ከጅቡቲ አስከ አዲስ አበባ ከዚያም አልፎ እስከ ከፋ እንዲዘረጋ ውል አደረጉ።

ከአድዋ ጦርነት በኃላ ከኢጣሊያ ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት (1888 ዓ ም፣) ከአስመራ በአድዋ፣ መቀሌ፣ ኮረም፣ መርጦ፣ ደሴ፣ ወረኢሉ፣ አንኮበር አድርጎ እስከ አዲስ አበባ የቴሌግራፍ/ቴሌፎን መስመር ዝርጋታ በ1894 ተጀምሮ በ1897 አለቀ። አከታትሎም ከወረኢሉ፣ በደብረ ታቦር፣ ይፋግ አድርጎ ወደ ጎንደር ኢትዮጵያውያን በውጭ ባለሙያዎች እየተረዱ መስመሩን ዘረጉ። አላማው አገሩን በሙሉ በቴሌፎን/ቴሌግራፍ አገልገሎት ለመሸፈን ስለነበር ምዕራብ ኢትዮጵያን ለማዳረስ አዲስ መስመር ከአዲስ አበባ በገነት - አዲስ ዓለም አድርጎ ኖኖ ደረሰ። ኖኖ ከአምቦ ምዕራብ የምትገኝ አንዲት ከተማ ነበረች። ኖኖን የመገናኛ ማእከል በማድረግ፣ ከኖኖ ወደ ነቀምቴ - ጂማ/ጂረን -ጎሬ -ጋምቤላ - ወዘተ ...ተዘረጋ። እንዲሁም ከአዲስ አበባ በስልጢ - ከምባታ - ወላይታ ወደ ሲዳሞ ተቀጠለ። የመገናኛው ሥራ እየቀጠለ በ1928 170 ከተሞችና መንደሮች ቴሌግራፍ/ቴሌፎን አገልግሎት ተጠቃሚ እንደነበሩ ተዘግብዋል። በ 1924 ዓ.ም ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ቴሌኮምዩኒኬሽን ህብረት (ITU) አባል ሆነች።

የዓለም አቀፍ ቴሌኮምዩኒኬሽን ህብረት (ITU) ከመጀመሪያዎቹ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አንዱ ነው። በ1857 በፓሪስ በ27 የኤውሮፓ አገሮች ስምምነት ተቋቋመ። በ1957፣100 ዓመቱ ፓሪስ ሲከበር ኢትዮጵያን ወክዬ ተገኝቻለሁ። በዚያ ዓመት የመጀመሪያዋ የመገናኛ ሳተላይት ወደ ጠፈር ተተኩሳ በሙከራ ላይ ነበረች። ስምዋም ኧርሊ በርድ (Early Bird) ይባላል። በዚችው ሳተላይት አማካይነት የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኡታንት ለስብሰባው በኢንተርኮንቲኔንታል ቴሌቪዥን ለመጀመሪያ ጊዜ ንግግር አደረጉ። ከዚያ በፊት ቴሌቪዥን ውቅያኖስን አቋርጦ መድረስ አይችልም ነበር። ብዙ ዝርዝሩ ውስጥ ሳንገባ፣ያለ የዓለም አቀፍ ቴሌኮምዩኒኬሽን ህብረት (ITU) ዛሬ የምናውቀው የዓለም የቴሌኮምዩኒኬሽን ግንኙነት አይቻልም ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል።

ዳግማዊ ምኒልክ ምንም እንኳን አውሮፓን ባያዩ በሰሙት ለአገር ዕድገት ለሕዝባቸው ሥልጣኔ ይጠቅማል ብለው ብዙ አዳዲስ ነገርና ሥራ ኢትዮጵያ

አስገብተዋል:: ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ መጽሐፋቸው እንደ ገለጹት፣ ከአድዋ ጦርነት በኃላ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያን ነፃነት ለዐለም ከአስታወቁ በኃላ ከመንግስታት ግንኙነት እያደረጉና የውጭ አገር ነጋዴዎችን በፍቅር እየሳቡ አዲሱ የስልጣኔ ሥራ በአገራቸው እንዲገባ አደረጉ::ብዙ አዳዲስ ነገርም ገባ:: እስከ 1900 ድረስ በቁጥርም 61 ይሆናል:: ለምሳሌ በ1892 በስልክ ሽቦ በያገሩ መነጋገር ተጀመረ:: ይህም በሕዝቡ እንደ ተአምራት ተቆጠረ:: በ1896 ደግሞ ከፈረንጅ አገር የሰርኪስ ባቡር አስመጡ:: አዲስ አበባ ደርሶ ስለታየ የዘመኑ ድንቅ ሆኖ ከረመ:: ባቡሩም በእሳት ኃይል በውሃ እንፋሎት የሚነዳ ነው:: የተሰጠውም ስም ባመጣው በሙሴ ሳርኪስ ነው:: በዚያን ጊዜ አዝማሪም እንዲህ ብሎ ገጠመ፣

ባቡሩ ሰገረ ስልኩም ተናገረ፣

ምኒልክ መልአክ ነው ልቤ ጠረጠረ::

የኢትዮጵያ ቴሌኮምዩኒኬሽን እስከ ጣልያን ጦርነት መጀመሪያ በመጠኑ እየተስፋፋና እየተሻሻለ በ1928፣ 170 ከተሞች ወይም የቴሌግራፍ/ቴሌፎን ጣቢያዎች፣ በ 7000 ኪሎሜትር መስመር ተገናኝተው አገልግሎት እንደሚያገኙ ተዘግቧል:: በዚህ ጊዜ ትልቁ እርምጃ ለመጀመሪያ ግዜ ራዲዮ ኢትዮጵያ መግባት ነው::

ሁላችንም እንደምናውቀው ራዲዮ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የሚተላለፈው እስከዚያ ጊዜ እንደነበረው በሺቦ አማካኝነት ሳይሆን በህዋው ነው:: ከራዲዮ መፈልሰፍ በፊት ቴሌግራፍ ባሕርን አቋርጦ መድረስ አይችልም ነበር:: የጣሊያኑ ተወላጅ ጉልየልሞ ማርኮኒ በ 1889 ዓም በራዲዮ ቴሌግራፍ ማስተላለፍ ችሎ ፍልስፈናውን አስመዘገበ:: በ 1893 በራዲዮ አማካይነት ከኤውሮፓ ወደ አሜሪካ አትላንቲክን አቋርጦ ቴሌግራም ደረሰ:: የራዲዮ ቴክኖሎጂ እየተፋጠነ በ1912 የድምፅ፣ በ 1926 የቴሌቪዥን ብሮድካስት በአሜሪካና በኤውሮፓ ተጀመረ:: እንዲሁም አዲስ አበባ አንዳንድ ለጋሲዮኖች ለያገራቸው መገናኛ ከ 1922 ዓም ጀምሮ ራዲዮ አቆሙ::

የኢትዮጵያ መንግሥት ራዲዮ ለማቆም ጨረታ አውጥቶ ከአሸናፊው አንሳልዶ ከተባለ የጣሊያን ኩባንያ ጋር በ 1923 ውል ተፈራርሞ የጣቢያውን የመሠረት ደንጊያ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ሐምሌ 14 ቀን 1923 ዓ ም አኖሩ:: ከደንጊያው እንደምናየው ዛሬ ራዲዮ የምንለውን "ያለሺቦ ቃል የሚያሳልፍ መኪና" ብለውታል:: ሕዝብ ግን ንፋስ ስልክ አለው፤ ስፈሩም ንፋስ ስልክ ተብሎ ቀረ::

የራዲዮ መቋቋም ውል በተፈረመ በሁለተኛው ዓመት ሥራው በመጠናቀቅ ላይ እያለ፣ መንግሥት ሲረከብ ኢጣሊያኖች ባልሆኑ የውጭ ባለሙያዎች ሥራው እንዲካሄድ ስለ ፈለገ፣ የጣሊያኑ ኩባንያ በዚህ ባለመስማማት ሥራውን ሆን ብሎ አዘገየው:: በዚህ ምክንያትና በጊዜው የነበረውን የፖሊቲካ ሁኔታ በመገምገም በአስቸኳይ ጊዜያዊ ራዲዮ ጣቢያ ማህል አዲስ አበባ በዕቴጌ ሆቴል አካባቢ ተቋቋመ:: ያቋቋሙትም ፈራንክ ሐመር የተባሉ የስዊድንና ኤሚል ኢብሌንስኪ የተባሉ የፈረንሳይ መሀንዲሶች ነበሩ:: ያ ጊዜያዊ ራደዮ ጣቢያ

*ኃይሉ አነስተኛ ቢሆንም፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የራዲዮ ቴሌግራፍ ቀጥታ ግንኙነት ከካይሮ፣ ከጂቡቲ እና ከኤድን ጋር በ 1926 ጀመረች፡፡ የኢጣሊያኑም ኩባንያ አላማው እንዳልተሳካ ሲገነዘብ በ 1927 ዓ ም የንፋስ ስልክን ራዲዮ ጣቢያ ስለ አስረከበ ቀጥታ የራዲዮ ቴሌግራፍ ግንኙነት ከሎንዶን ጋር ተመሠረተ፡፡ በሎንዶንም አማካኝነት ከዓለም በሙሉ መገናኘት ተቻለ፡፡*

*ጊዜያዊ ራዲዮ ጣቢያውን ከአቋቋሙት አንዱ ፍራንክ ሐመር የራዲዮ ትምህርት ቤት በ 1925 ከፍተው 30 ወጣቶች ማሰልጠን ጀመሩ፡፡ ወጣቶቹ በ 1928 የጣሊያን ጦርነት ወቅት በቴሌግራፊስትነት ላገራቸው ከፍተኛ ሚና በጦር ሜዳ ተጫውተዋል፡፡*

*አንድ ቀን (1960 ዓ.ም)፣ ጸሐፊዬ ሚስተር ፍራንክ ሐመር የሚባሉ ሊያነጋግሩኝ መምጣታቸውን ነገረችኝ፡፡ ስሙን በፊት የሰማሁት መሰለኝ፤ ግን በምን ግንኙነት እንደሆነ ለጊዜው ግር አለኝ፡፡ ምን አይነት ሰው እንደሆኑ ስትገልጥልኝ ማን እንደሆኑ ገባኝ፡፡ ተቀብያቸው በሰፊው የጥንቱን ተጨዋወትን፡፡ ከዱሮ ተማሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘት እንድረዳቸው ጠየቁኝ፡፡ የሚያስታውሱትን ያህል ስሞቻቸውን ነገሩኝ፡፡ ከሰጡኝ ስሞች የማውቃቸው ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው ደጃዝማች አሰጋኸኝ፣ ጀነራል መርዕድ መንገሻ (የመንግስቱ ነዋይን መፈንቅለ መንግሥት ያከሸፉት) ነበሩበት፡፡ በቴሌኮምዩኒኬሽን ሕዝብ ግንኙነት በኩልና በጊዜው አረጋዊ በነበሩ ሰዎች ዕርዳታ በከፊል ተማሪዎቻቸውን አግኝተን ግብዣ አደረግንላቸው፡፡ ከጨዋታቸውም በዘያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በይበልጥ ለመገንዘብ ቻልን፡፡*

*የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ጦር ግምባር በሚዘምትበት ጊዜ በመስከረም 1928 በንፋስ ስልክ ራዲዮ የመጀመሪያው ብሮድካስት ተጀመረ፡፡ አፄ ኃይለሥላሴ መስከረም 2 ቀን 1928 ስለ ፋሺስት ጦርነት ለዓለም ብሮድካስት አደረጉ፡፡ በጦርነቱ መንስኤ የዓለም ጋዜጠኞች አዲስ አበባ በብዛት መጥተው በሶስት ወር ውስጥ በዱቤ የላኩት የቴሌግራፍ መልእክት ዋጋ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ሲሆን፣ ይህም ገንዘብ ራዲዮ ጣቢያውን ለማቋቋም ከወጣው በላይ ነበር፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሎንዶን በስደት በነበሩበት ዘመን፣ ኬብል ኤንድ ዋይርሌስ የሚባል ድርጅት ለጋዜጠኞቹ ዱቤ ሀላፊ ስለነበር ገንዘቡን እንዲከፍል በፍርድ ቤት ከሰው እንዲከፍል ከተወሰነ በኋላ በይግባኝ ውሳኔውን አሻረው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ብሪታኒያ የጣልያንን ይዞታ አውቃ ስለነበረ ገንዘቡ የሚከፈለው ለጣልያን ንጉሥ ነው ተባለ፡፡*

*እስካሁን፣ በዓለምና በኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽንን አጀማመር፣እንዴት እየተስፋፋ አገልግሎቱ ለሰው ልጅ ጥቅም እንደዋለ፣ ቴክኖሎጂውም ምን እንደሚመስል ባጭሩ ለማስረዳት ሞክሬአለሁ፡፡ እዚህ ላይ ባገራችን አስተዳደሩና አገልገሎቱ ከ1886 እስከ 1928 እንዴት እንደነበር ማብራሪያ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡*

## አስተዳደር

*የፖስታ አገልገሎት ቀደም ብሎ በ1884 ተቋቁሞ ስለነበር፣ ቴሌግራፍና ቴሌፎን በ1886 ሲጀመር የፖስታ፣ ቴሌግራፍና ቴሌፎን የበላይ አስተዳደር ለግቢ ሚኒስትሩ ተሰጠ:: ድርጅቱን በቀጥታ የሚያስተዳድሩ የውጭ ባለሙያዎች ነበሩ:: የኢትዮጵያ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ማዕከላዊ አስተዳደር የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ሚስተር ስቴቨኒን (ፈረንሳዊ)፣ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ፖስታ፣ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ማዕከላዊ ቢሮ ተብሎ ሚስተር አልፍሬድ ኢልግ (ስዊስ፣ የዐፄ ምኒልክ፣ የቅርብ አማካሪ)፣ በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ፖስታ፣ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር ተብሎ በሚኒስትሩ ስር ሚስተር ሊዮ ሽፍነ (ፈረንሳዊ) ሲያስተዳድሩት ቆይተዋል::*

*የግቢ ሚኒስትሩ በየለቱ ጠዋት በቴሌግራፍና በቴሌፎን የተገኘውን ያገሩን ሁኔታ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርቡ ነበር ይባላል::*

*ዓፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን ወደፊት ለማራመድ በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት የአገሪቱን ጠቅላላ አመራርና አስተዳደር መዋቅር በኤውሮፓ አኳሁዋን ለማድረግ በ 1900 የሚኒስትሮች ምክር ቤት አቋቁመው 10 ሚኒስትሮች ሾሙ:: ከተሾሙት ውስጥ አስረኛው ልጅ በየነ ይመር የሚባሉ "የፖስታ ቴሌግራፍ ቴሌፎን ሹም" የሚል ስልጣን ተሰጣቸው::*

## አገልግሎት

*አገልጎሎቱ ዛሬ ከምናውቀው ደረጃ እጅግ ቢርቅም በዘመኑ እንደተአምር የሚቆጠር ነበር:: ቀደም ብሎ በነበረው ሁኔታ መልእክት ለመለዋወጥ ብዙ ሳምንታት ወይም ወሮች የሚወስደው ጊዜ ወደ ጥቂት ሰዐታት ዝቅ ማለቱ እንደ ተአምር ቢታይ አያስደንቅም:: በጊዜው ቴክኖሎጂና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጦት ምክንያት አገልግሎቱ ብዛትም ጥራትም ይጎድለዋል:: ሆኖም በተለይ ለመንግሥት አስተዳደርና ደህንነት ጊዜው በሚፈቅደው ደረጃ የላቀ አስተዋጽዎ አበርክቷል::*

*ዝርዝር ታሪፍ ከአንዱ ጣቢያ ወደ ሌላው ለሚተላለፍ ቴሌግራምና ቴሌፎን ወጥቷዋል:: ለምሳሌ ከአንድ ጣቢያ ወደ አዲስ አበባ ለመነጋገር ለ 5 ደቂቃ ከ 1 ብር 4 መሀለቅ አይበልጥም:: ለቴሌገራም ደግሞ በቃል ከ 1 እስከ 3 መሀለቅ ያስከፍላል[1]::*

*የመስመር ጥበቃና ጥገና ሀላፊነት የተሰጠው መስመሩ የሚያልፍበት መሬት ባለቤት ነበር:: መስመሩ እንጨት ምሰሶ ላይ የታሰረ ሺቦ በመሆኑ ለጥገናውም*

---

[1] *1 ብር በ 2 አላድ፣ በ 4 ሩብ፣ በ 8 ትሙን፣ በ 16 መሀለቅ፣ በ 32 ቤሳ ይመነዘራል:: ብሩ በዚያን ጊዜ ጠገራ ብር* (Silver) *ይባልም ነበር፤ ወረቀት ሳይሆን ብር ስለሆነ፣ የራሱ የሆነ ዋጋም ነበረው:: ለብዙ ጊዜ ያለሽርፍራፊ ሲያገለግል ቆይቶ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ከላይ የተገለጹት ሽርፍራፊዎች ተቀርጸው በስራ ላይ ዋሉ::*

ብዙ ቴክኒክ አያስፈልገውም። ሺቦውም የብረት (metal) እንደሆነ ይነገራል። ብረት ደግሞ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ ችሎታው ደካማ ስለሆነ የሚተላለፈው ድምፅ ብዙ ርቆ ሳይሔድ ይደክማል። ስለዚህ ኦፐሬተሮች እየተቀባበሉ ቃሉን እየደገሙ ለሚቀጥለው ያስተላልፋሉ። ቴሌግራሙ መጨረሻው ጣቢያ ከደረሰ በኋላ ለአድራሻው ከመሰጠቱ በፊት ከላኪው ጣቢያ ጋር በመናበብ የቴሌግራሙ ትክክለኛነት ይረጋገጣል። ለመናበቡም ተጨማሪ ክፍያ አለው። በዚህ አሰራር ሁኔታ ብዙ መልእክት በተወሰነ ጊዜ ማስተላለፍ አይቻልም።

## የዓለም አቀፍ ማኅበረተኛነት

በ1884 የፖስታ አገልግሎት ከአቋቋሙ በኋላ፣ አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ የዓለም ፖስታ አንድነት ማህበር (UPU) እንድትሆን ከ 1885 ጀምሮ ደጋግመው ጥያቄ ለስዊዝ ፕሬዜዳንት አቀረቡ። ሆኖም ኢትዮጵያ አባል የሆነችው በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን በ1918 ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ቴሌኮሙኒኬሺን የዓለም አቀፍ ቴሌኮምዩኒኬሽን አንድነት ማኅበር (ITU) አባል የሆነችው በ 1924 ነው።

## 1928 - 1933 በፋሺስት ይዞታ

ከ40 ዓመት በላይ የተደከመበት መስመርም ሆነ ራዲዮ በጦርነቱ ምክንያት ወደመ። ግን ስርጭቱ እንደ ቀድሞው ብዙ ከተሞች ባይሸፍንም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ጣሊያኖች ትላልቅ ከተሞች የሚያገናኘውን መንገድና ቴሌፎን መስመር በዘመኑ ደረጃ በተሻሻለ ሁኔታ ሠሩ። ለምሳሌ ለአዲስ አበባ - አስመራ፣ አዲስ አበባ - ጂማ፣ አዲስ አበባ - ደብረ ማርቆስ መስመሮች የባለ ብዙ መዳብ ሺቦ በብረት ምሶሶ ላይ ዘረጉ። እንደ ሺቦው ብዛት በአንድ ጊዜ ምርከት ያሉ ሰዎች በቀጥታ ማነጋገር ይችላሉ። በተጨማሪም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ባለ 1500 እና በአስመራ 1200 መስመር ኦቶማቲክ ማዞሪያዎች ስላቆሙ የአዲስ አበባና አስመራ ቴሌፎን ደንበኞች ከተማ ውስጥ በቀጥታ በመደወል ሊገናኙ ችለዋል። ከዚያ በፊት ከተማ ውስጥም መነጋገር የሚቻለው በኦፐሬተር አገናኝነት ነበር። በጣሊያን ይዞታ ዘመን መገናኛ የነበራቸው ከተሞች 96 ቢደርሱም በጦርነቱ ምክንያት ብዙዎች ከአገልግሎት ውጭ ነበሩ። በ 1928 ግን 170 እንደነበሩ ከላይ ተጠቅሰዋል።

እንዲሁም አንድ የብሮድካስቲንግ ጣቢያ አዲስ አበባ (ጂማ መንገድ ላይ) በ1929 አቁመዋል። ይህንኑ ብሮድካስቲንግ ጣቢያ ቢያረጂም እስከ 1953 ተጠቅመንበታል።

## ከነፃነት በኃላ በፖስታ ቴ ቴ ሚኒስቴር (1933 -1945)

ጣሊያኖች የዘረጉትን የመዳብ ሺቦ አልፎ አልፎ አርበኞች ቢቆርጡትም ጉዳቱ ከባድ አልነበረም። ትልቁ ጉዳት የደረሰው በእንግሊዞች ጦር ሠራዊት ነው። የተዘረጋው መስመር አብዛኛው ባለ 8 የመዳብ ሺቦ ነበር ይባላል። መዳብ በጣም ውድ ስለሆነ (በተለይ በጦርነት ጊዜ)፣ እንግሊዞች በመስመር 2 ሺቦ ብቻ

በመተው ስድስቱን እየጠቀለሉ ወሰዱት። በአካባቢው ሕዝብም ተጨማሪ ጉዳት ደርሶበታል።

በዚህ ሁኔታ እንዳለ፣ ሚያዚያ 27 1933 ዓ.ዔ ኃይለ ሥላሴ ተመልሰው መንግሥታቸውን ሲአቋቁሙ፣ የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር አስተዳደሩን ተረከበ። በጥቂት የውጭ ዜጎች እየታገዘ የቴሌኮሙኒኬሽንን አገልግሎት መልሶ ሊያቋቁም ቢሞክርም በገንዘብና በሰለጠነ የሰው ኃይል እጦት ምክንያት በ1945 ከሞላ ጎደል አገልግሎት የነበራቸው ከተሞች 65 ብቻ ነበሩ። በነበረበት ሁኔታ አገልግሎቱ እየቀነሰ እንጂ እየጨመረ አለመሔዱን በመገንዘብ መንግሥት መሥራች አባል የሆነበትን የዓለም ባንክን፣ ለእርሻ፣ ለመንገድ፣ ለቴሌኮምዩኒኬሽንና ለኢንዱስትሪ መልሶ ለማቋቋምና በመጠኑም ቢሆን ለማስፋፋት በ1942 ዕርዳታ ጠየቀ። ባንኩም ባለሙያዎች ልኮ ጥናቱን አካሒድዋል፤ ቴሌኮምዩኒኬሽንን በተመለከተ አቋሙንና አገልገሎቱን መርምሮ መልሶ የማቋቋም ፕሮግራምና ፕሮግራሙን ሥራ ላይ የሚያውልና ወደ ፊት የሚያስፋፋ፣ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለው ቀልጣፋ ድርጅት አስፈላጊነትን ገልጾ፣ ለውጭ አገር ቴሌኮምዩኒኬሽን ድርጅት ለተወሰነ ዘመን በስምምነት እንዲሰጥ በ 1943 አሳሰበ። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን በጥናቱ ሲስማማ በምንም ረገድ ለውጭ ድርጅት እንዲሰጥ አልፈቀደም። ከፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር ለይቶ፣ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በሕግ አቋቁሞ፣ የውጭ ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ቀጥሮ ለማሠራት ወሰነ። በዚሁ መሰረት "***የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት*** *የቴሌኮምዩኒኬሽን* ***ቦርድ***" በሚል ስያሜ ድርጅቱ በአዋጅ ቁጥር 131/1945 ጥቅምት 5 1945 ተቋቋመ። የአዋጁ ዓላማ በአንቀጽ 5 እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡-

> ቦርዱ የተቋቋመበት ጉዳይ የኢትዮጵያን የቴሌኮምዩኒኬሽን ማከናወኛዎች መልሶ ለማቋቋም፣ ለማስፋፋት፣ ለማደስና ለመጠገን፣ በቴሌኮምዩኒኬሽን ሥራ ጥቅም ለማስገኘት፣ እንዲሁም የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት በሚነኩ ጉዳዮች ሁሉ በኢትዮጵያና በማናቸውም ሌላ ስፍራ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ስም ተወክሎ ለመሥራትና ለአሁኑና ለወደፊቱ ለቦርዱ ሥራ የሚሆኑ ሠራተኞች ለማሰልጠን የሚቻልበትን ዘዴና ማሰልጠኛውንም ትምህርት ቤት ለማዘጋጀት ነው።

በተሰጠው ቻርተር መሰረት ጠቅላላ ፖሊሲ በርዕሰ ብሔሩ ለሚሾሙ ከ 5 ለማያንሱ ከ 7 ለማይበልጡ የቦርድ ዲሬክተሮች ተሰጥቷል። ዲሬክተሮቹ የሚሾሙት (በልምድ እንደታየው) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልክ ከቴሌኮምዩኒኬሽን ጋር ግንኙነት ካለው መሥሪያ ቤት ሲሆን፣ የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስትር በዲሬክተርነት ሊቀ መንበር ነው። ፖሊሲውን ለማስፈጸም በዋና ሥራ አስኪያጅ ለሚመራው መስሪያ ቤት ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷል። ቦርዱ በድምፅ በእኩል ቢከፈል ሊቀመንበሩ ያለበት ወገን ያሸንፋል። ከዚያ ውጭ የተለየ ሥልጣን ሚኒስትሩ በቦርዱ ላይ የለውም።

## የቴሌኮምዩኒኬሽን ቦርድ ዘመን (1945 - 1966)

### በውጭ ዜጎች ሲቋቋምና ሲተዳደር (1945 - 1953)

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጉዳት ካልደረሰባት ከስዊድን ብዙ የቴሌኮሙኒኬሽን ሠራተኞች፣ ከዋና ሥራ አስኪያጅ ጀምሮ እስከ ቴክኒሺያኖች (ጸሐፊዎችም ጭምር) በ1945 በቅጥር ከአስመጣ በኃላ መሥሪያ ቤቱን አቋቁሞ፣ ይጠቅሙኛ ል ብሎ የሚፈልጋቸውን ሠራተኞች ከፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር መርጦ እንዲወስድና ሥራውን እንዲጀምር ሚስተር እንግማር ኖርበርግ ለሚባለው ስዊድናዊው ዋና ሥራ አስኪያጅ መንግሥት አስረከበው:: ከፖስታ ቴቴ ሚኒስቴር (ቴሌፎንና ቴሌግራፍ) 696 ኢትዮጵያውያንና 4 የውጭ ዜጎች፣ በጠቅላላው 700 ሰዎች መርጦ፣ 92 የውጭ ዜጎች (ስዊድናዊያን) ጨምሮ ሥራውን እ.ኤ.አ. ጃኑዋሪ 1 1953 (ታህሣስ 22 1945) በይፋ ጀመረ:: ከኢትዮጵያኖቹ ውስጥ ከጥቂት ቴክኒሺያኖች በስተቀር የቴሌኩምዩኒኬሺን እውቀት ያለው አቶ ገብርኤል ቴዎድሮስ የሚባል ሰው ብቻ ነበር::

በየካቲት 1943 መልሶ ማቋቋሚያ የ3 ዓመት ፕሮግራም ብድር ውል ከዓለም ባንክ ጋር መንግሥት ተፈራርሞ፣ የድርጅቱ መቋቋም በመዘግየቱ፣ ድርጅቱም ከቆመ በኃላ በአዋጁ የተጠቀሱት ጉዳዮች በመንግሥት በኩል በጊዜው ሥራ ላይ ሳይውሉ በመቆየታቸው፣ ብድሩን ሥራ ላይ ለማዋል የተጀመረው በየካቲት 1946 ነው:: ይሔውም ድርጅቱ በተቋቋመ በዓመቱ መሆኑ ነው::

የሥራው መጀመሪያ ያደረገው በጊዜው የነበረውን ያረጀ፣ በጥገና ጉድለትና በመለዋወጫ እጦት ከአገልግሎት ውጭ የሆነውን መልሶ በማቋቋም ጥቅም ላይ ለማዋል ቢሆንም፣ ጅምሩን በፍጥነት ለማጠናቀቅ በገንዘብ እጦት ምክንያት አልቻለም:: የሆነ ሆኖ በጊዜው የነበረው የመንገድ፣ የትራንስፖርት፣ የገንዘብ ችግር ፕሮግራሙን በመጠኑ ያዘግይበት እንጂ ብዙ አህዮችና በቅሎዎች በመግዛት የረጂም መስመሮችንና ማዞሪያዎችን ጥገና በብዛት ለማከናወን ችሏል::

ቦርዱ ሲቋቋም ከባንክ ብድርና ከመንግሥት ተውጣቶ የተሰጠው ካፒታል ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ (6,750,000) ቢሆንም፣ ይህንኑ ገንዘብ ጥቂት በጥቂት ለማግኘት ብዙ ዓመት ወስዷል:: ይህ ገንዘብ ታቅዶ የነበረው ለሶስት ዓመት መልሶ ማቋቋምና ቀደምትነት ለሚሰጠው አዲስ ሥራ ነበር:: ነገር ግን ከ 1945 እስከ 1953 ሌላ ምንም ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት አልተቻለም:: በተጨማሪም ለቦርዱ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን ከቀድሞው የተለመደ አሠራርና ከባለሥልጣናት ጋር ሊጣጣም ስላልቻለ፣ ይልቁንም ዋናው ሥራ አስኪያጅ የውጭአገር ሰው በመሆናቸው ከቦርዱ በይበልጥም ከሚኒስትሩ ጋር አለመግባበት ተፈጠረ:: ይህም የቦርዱን ዓላማ በፕሮግራሙ መሰረት እግቡ ለማድረስ እንቅፋት ሆነ::

በዚህ ምክንያት የመጀመሪያው የ3 0መት ፕሮግራም ከ1945 አስከ 1953 ያለምንም ተጨማሪ ፈንድ፣ ቦርዱ ከገቢው በሚገኘው ገንዘብ እየታገዘ ሥራውን በማካሔድ ብዙ መሰረታዊ ተቅዋምና አገልግሎት አበርክትዋል::

## የኔ ወደ መስርያ ቤቱ መግባት

እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቴሌኮምዩኒኬሽን ጋር ግንኙነት ያደረግሁት በ ነሐሴ 1947 ዓም ነው።

ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው በነበረው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮተቤ በሚገኘው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት) ተማሪ ሆኜ በሰኔ 1942 የለንደን ማትሪኩሌሽን ፈተና በዲስቲንክሽን ስላለፍሁ ከሌሎች ተመሳሳይ ውጤት ካላቸው 9 ተማሪዎች ጋር ተመርጠን በጥቅምት 1943 ወደ እንግሊዝ ሀገር ተላክን[2]። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምሩቃን እየበዙ ስለሔዱ ቀደም ብሎ እንደሚደረገው መንግሥት ሁሉንም ውጭ አገር ልኮ ለማስተማር አቅም ስላነሰው በ 1943 ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ለመክፈት የሚዘጋጅበት ወቅት ነበር።

በኅዳር 1947፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከዓለም ጦርነት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዩናይትድ ኪንግደምን ሲጎበኙ፣ እኔ በሎንዶን ዩኒቨርሲቲ የመጨረሻ ዓመቴ ነበር። በብሪታኒያ የነበርነውን ተማሪዮች ሁሉ ኤምባሲ የቡፌ ራት ጋብዘውን እንደ ተራ ሰው ሁነው ሲያነጋግሩን ከእኩለ ሌሊት በላይ ቆየን። ለምሳሌ በንግግራቸው በ ***እኛ*** *ፈንታ* በ ***እኔ*** ይጠቀሙ ነበር። *"እንዲህ ተሰብስባችሁ ሳያችሁ ብዙ ትመስላላችሁ፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያ ውቅያኖስ ውስጥ እንደተበተነ እፍኝ ጠጠር ናችሁ"* አሉ።

የእልፍኝ አስከልካያቸው፣ ለማነጋገር የምትፈልጉ ሁሉ ስማችሁን ስጡኝና በተራ አነጋግሯቸው ስላሉን እኔም ተመዘገብኩ።

በዚያን ዘመን አንድ ተማሪ ከዩኒቨርሲቲ ሲመረቅ ወደ አገሩ ካልተመለሰ ስኮላርሺፑ ይቋረጣል። እኔ የምመረቀው በዚያው ዓመት በሰኔ 1947 ስለነበር ወደ አገሬ ጨርሼ ከመመለሴ በፊት በኢንዱስትሪ ውስጥ በከፊል እየሠራሁ ቢዚኔስ ማኔጅሜንት፣ ኤኮኖሚክስና ፋይናንስ አጥንቼ ብመለስ የበለጠ ጠቃሚ መሆኔን ገልጬ፣ በተጨማሪም ባገሩ ውስጥ ያለውንም ስለማላውቅ ቤተሰቤም ሰለናፈቁኝ ከምረቃው በኋላ አገሬ ደርሼ እንድመለስ ብጠይቅ «*ታዲያ ፕራቲኩን እዚያው አገራችን መጥተህ አታደርገውም?*» ቢሉኝ፣ «*ጃንሆይ የአገሬ ፕራቲክ መኪናውን እንዴት እንደማሠራው ነው፤ እዚህ ግን መኪናውን እንዴት እንደምሠራ ነው*» አልኳቸውና፡ በፈገግታ ፈቀዱልኝ።

በነሐሴ 1947 መጥቼ ያን ጊዜ ኮኔል ይባል የነበረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አባ ሳሙኤልና ቆቃ የሚገኙትን ትናንሽ የኃይል ማመንጫዎች ጎበኘሁ። እንዲሁም ቴሌኮሙኒኬሽን ሒጂ ከመጀመሪያው ዋና ሥራ አስኬያጅ ሚስተር እንግማር ኖርበርግ ጋር በሰፊው ተወያየን። ስለትምህርቴም በዝርዝር ጠይቆኝ ከስዊድን

---

[2] ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1936 ዓ.ም. ስታቋቁም፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማካሄድ የሚያስችሉ አያሌ ቁሳቁሶች ገና አልተሟሉም ነበር። ከነዚህም መሀከል፣ ካሪኩለም፣ መማርያ መጻህፍት፣ ለየደረጃው ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያውያን መምህራን አለመኖርና የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና አለመኖር ይገኙበታል። ስለዚህ፣ ተማሪዎቹ በ1939 ዓ.ም. የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ፣ የእንግሊዝ ሀገር ፈተና እንዲፈተኑ ተደረገ።

*ጋር አንድ ዐይነት መሆኑን ገለጸልኝ:: ከዚያም ወዲያው ሥራ እንድጀምር ጋበዘኝ:: በርሱም በኩል ያለውን ችግር: በመጠኑ አጫወተኝ::*

*ኮተቤ 2ኛ ደረጅ ትምህርት ቤት ከነበሩ ጓደኞቼ በብዛት ተቀጥረው፣ ሃይኮማንድ ኮርስ የተሰኘ ትምህርት ለሁለት ዐመት ወስደው በናፍቆት ሥራ በመጀመር ላይ ነበሩ:: ሁኔታው አስደሳች መስሎ ቢታየኝም ያሰብኩትን ፕሮግራም ለመፈጸም በጥቅምት መጀመሪያ ወደ ሎንዶን ተመለስኩ::*

*ሎንዶንና ልዩ ልዩ ከተሞች ውስጥ ፕሮግራሜን አጠናቅቄ በሚያዝያ 1949 አዲስ አበባ ተመለስኩ:: ሥራ ለመጀመር ጥቂት ወራት ፈጀ:: እኔ ለመሥራት የምፈልገው ቴሌኮምዩኒኬሽን ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ተመድበህ ሥራ ስለተባልኩ ነበር:: በመጨረሻ በእኔ ፍላጎት መሠረት ቴሌኮምዩኒኬሽን ተመድቤ እንድሠራ፣ ደሞዜም ኢትዮጵያ ከገባሁበት ቀን ጀምሮ እንዲከፈል በጽሕፈት ሚኒስቴር ታዘዘ:: በዚያን ጊዜ የነበረው ሁለተኛው የስዊድን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሚስተር አረቪድ ሉንድኩስት፣ ላልሠራሁበት ጊዜ ደሞዝ መክፈሉ ቅር ቢሰኝም፣ ትዕዛዙ ከየት እንደመጣ በመገንዘብ ሳያንገራግር ከፈለ::*

*እኔ ስቀጠር በራዲዮ ዋና ክፍል በመሐንዲስነት እየሠራሁ በከፊል ቴሌኮምዩኒኬሽን ኢኒስቲትዩት እንዳስተምር ተመደብኩ:: ከዚያ ቀጥሎ አዲስ የተቋቋመው የአቃቂ በሰቃ ራዲዮ መቀበያ ጣቢያ ሀላፊ ሆንኩ:: ለጣቢያው ሠራተኞች መኖሪያ ቤት ተሰርቶላቸዋል፤ ሀላፊው ግን ከአዲስ አበባ እየተመላለሰ ይሠራል:: በዚያን ጊዜ አቃቂ ትንሽ መንደር ስለነበረች የሚረባ ምሳ አይገኝም:: መኪና ከነነዳጁ አለኝ፤ ግን በመንገዱ መጥፎነት አዲስ አበባ ደርሶ መልስ 3 ሰዓት ስለሚፈጅ ጦም መዋሉን መረጥሁ:: ከወራት በኃላ አንድ የክልስ ቤተሰብ ተዋውቄ ገንዘብ እየከፈልኩ ማለፊያ ምግብ አገኘሁ:: ቀጥሎም ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ተዛውሬ የራዲዮ ክፍል ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆንኩ:: አለቃዬ ማሪኖስ የሚባል ግሪክ ሽማግሌ፣ ሙያው የራዲዮ ፍሪኴንሲ ማኔጅሜንት ነበር እንጂ የኢንጂነርነት ዕውቀት አልነበረውም::*

*ወደ ዋናው የቴሌ ታሪክ ልመለስና እስኪ መጀመሪያ በአዲስ መልክ በቦርድ ከተቋቋመበት ከ 1945 ጀምሮ እስከ 1953 ሥራው ምን እንደሚመስልና በተሰጠው ዓላማስ እንዴት እንደተራመደ ልየው:: ዋናው ሥራአስኪያጅ ሚስተር እንግማር ኖርበርግ፣ መጀመሪያ ሳውቀውም፣ ከቴሌ ሰራተኞች እንደተረዳሁትም፣ በጣም ንቁና ኃይለኛ ሠራተኛ ነበር:: በነበረው ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአህያና በበቅሎ ትራንስፖርት እየታገዘ ብዙ የተዘጉትን ጣቢያዎች ብዙ ሺህ ኪሎሜትር መስመሮች በመጠገን መልሶ አቋቁሙዋል:: በአዲስ አበባ ዘመናዊ ማዞሪያ ተክሏል፤ ቴሌ ኢኒስቲትዩት አቁሞ ሁለተኛ ደረጃ የፈጸሙ ተማሪዎች በቴክኒክ፣ በአስተዳደር፣ በፋናንስ፣ በአካውንቲንግ አሰልጥኖ ሥራ አስጀምሮአል::*

*መሥሪያ ቤቱ በ1945 ሲቋቋም ለሶስት ዓመት የመልሶ ማቋቋምና ማስፋፋት ፕሮግራም ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር* (6,750,000) *ታቅዶ የነበረው ገንዘብ በማለቁና ተጨማሪም ባለመገኘቱ፣ ሥራ አስኪያጁም ከቦርዱና በይበልጥም ከሊቀ መንበሩ (ሚኒስትሩ) ባለመስማማት ከሥራው ተሰናብቶ*

ሁለተኛው ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ሉንድኩኢስት ተቀጥሮ የመስፋፋቱ ሥራ በጣም ቀዝቅዞ ነበር:: ሉንድኩኢስት ቀዝቃዛና ሁሉም ነገር እንደ ሁኔታው ይቀጥል ባይ እንጂ የቦርዱን አላማ እግቡ ለማድረስ የሚታገል ሰው አልነበረም:: ስለዚህ ድርጅቱ ከሥራው በሚገኘው ገቢ ጥገናና በጣም አስፈላጊ የሆኑ ማስፋፊያ እየሠራ እስከ 1952 ቆይቶ ኮንትራክቱ ባለመታደሱ ተሰናበተ:: ቦርዱም ለስዊድን ቴሌኮምዩኒኬሽን ከሉንድኩኢስት የተሻለ ሥራ አስኪያጅ እንዲላክላቸው ቢጠይቁም፣ የተሻለ የለንም ብለው መለሱላቸው:: በዚህ ገዜ በርከት ያሉ በኢንጂነሪንግ እና በሌላም ሙያ ከልዩ ልዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በብዛትም ከአሜሪካ፣ የተመረቁ ኢትዮጵያውያን ቴሌ ገብተው ነበርና፣ለይስሙላ ሥራ ቢሰጣቸውም ውሳኔ የሚደረገው በውጭዎቹ ሰዎች ስለሆነ ከፍ ያለ ቅሬታ ተፈጥሯል::

ከዓለም ባንክ ጋር በነበረው ስምምነት ቦርዱ ባንኩን ሳያማክር ዋና ሥራ አስኪያጅና የፊናንስ ሀላፊ መሾም አይችልም:: ከኢትዮጵያውያኖቹ ሊቀጥር ቢፈልግም የሚበቃ የሥራ ልምድ የላቸውም ይባላል:: ቴሌ ካሉት የስዊድን ከፍተኛ ሀላፊዎች መምረጥ ለቦርዱ ግዴታ ሆነ:: ለምርጫው ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችሉ 3 ነበሩ::

ሚስተር ፍሪስክ ዋና መሀንዲስ፣ ብዙ ዓመት ቴሌ የሠራ፣

ሚስተር ሚረንፎርሽ የፊናንስ ሥራ አስኪያጅ፣ ብዙ ዓመት ቴሌ የሠራ፣

ሚስተር ኸርማን ሩድ የራዲዮ ዋና ክፍል ሥራ አስኪያጅ፣ ቴሌ 1 ዓመት የሠራ፣

እኔ በዚያን ጊዜ 4 ዓመት ቴሌ ሠርቼ ስለነበር ሶስቱንም ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ:: ፍሪስክ ጀርጃራ ብጤ፣ ምንም ነገር ውስጥ ጠልቆ የማይገባ፣ የሚቀርብለትን የትጋ ልፈርም ባይ ነው:: ሚረንፎርሽ በፊናንስ ከፍ ያለ ችሎታ ያለው፣ ሠርቶ የማይደክም፣ ማታ ወደ ቤቱ ሲሔድ በመኪናው ፋይል ጭኖ የሚሔድ፣ ከቤተሰቡ ሥራውን የሚያስቀድም ሲሆን፣ ነገር ግን የበታቹ 2 እና 2 = 4 ቢለው ራሱ ካላረጋገጠ አይቀበልም:: ኸርማን ሩድ አንድ ዓመትም ቢሆን አለቃዬ ሆኖ ሠርተናል:: ከሌሎችም ጋር ሲሠራ መዝኘዋለሁ:: መርህ ያለው፣ በኢትዮጵያውን ሙሉ እምነት ያለው፣ በየጊዜው ብዙ አዲስ ሀሳብ አመንጪ ነው::

ምርጫውን በተመለከተ ቦርዱ በግል ጠርቶ ሀሳቤን በጠየቀኝ ጊዜ ከዚህ በላይ የዘረዘርኩትን አስረዳሁ:: ሩድ ከኅዳር 1953 ጀምሮ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነ:: እዚህ ላይ መለስ ብለን ቦርዱ ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ታህሣስ 1953 የተሰራውን እንመልከት::

## 1945 - 1953 የተሀድሶ ፕሮግራም (1ኛ ፕሮግራም)

የዚህ ፕሮግራም የመጀመሪያው አላማ መልሶ ማቋቋም ሲሆን ገንዘቡ ሲገኝ በመቋቋሚያው የተዘረዘረውን መፈጸም ነበር:: በካፒታል መልክ መነሻ ገንዘብ የተሰጠው ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀምሳ ሺ ብር (675000) ለ3 ዓመት

ሲሆን ያንኑም ገንዘብ በሙሉ ለማግኘት ረዘም ያለ ጊዜ ወስድዋል። ሆኖም በራሱ ገቢም እየታገዘ በ8 ዓመት ውስጥ ከዚህ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሥራዎች ፈጽሟል፡-

1. በፋሺስት ጦርነት የወደሙትን የመገናኛ አውታሮች መልሶ ማቋቋም፣
2. የቴሌ ኢንስቲቱዩት ከፍቶ ኢትየጵያውያንን ማሰልጠን፣
3. በአዲስ አበባ ኦቶማቲክ ማዞሪያ ማስፋፋት፣
4. ለ12 ከተሞች የተለያየ መጠን ያላቸው ማዞሪያ ማቋቋምና 6 ማዞሪያዎች ማስፋፋት፤
5. ልዩ ልዩ የቴሌግራፍ መሳሪያዎችና የራዲዮ መገናኛዎች ለአገር ውስጥና ለኢንተርነሽናል አገልግሎት ማደራጀት፣
6. ለጣቢያዎች ማቋቋሚያና ለሠራተኞች መኖሪያ ቤት ሕንጻዎች ማሠራት።

የ8 ዓመት የሥራ ውጤት ከዚህ እንደሚከተለው በሁለት መስፈርት ሲለካ፣ በተለይ በጊዜው የነበረው የገንዘብና ያስተዳደር ችግር ሲታወስ፣ ጥሩ ውጤት እንዳስመዘገበ ይታያል።

| መስፈርት | 1945 | 1953 | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በመቶ |
|---|---|---|---|
| የአገልጎት ማዕከል ብዛት | 65 | 168 | 12.6 |
| የቴሌፎን ደንበኞች ብዛት | 3640 | 8973 | 11.9 |

አብዛኛው ሥራ የመልሶ ማቋቋም በመሆኑ ዓመታዊ ዕድገቱ ከፍ ብሎ ይታያል።

## በኢትዮጵያውያኖች ሲተዳደር (1953-1966)

ይህ ዘመን ኢትዮጵያውያኖች በየዘርፉ ከፍተኛ ኃላፊነት የተቀበሉበትና እውነተኛ ሥልጣን የጨበጡበት ጊዜ ነው።

በ1953 3ኛው ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ሩድ እንደ ተሾመ የመጀመሪያ ሥራ ያደረገው የድርጅቱን አስተዳደር መዋቅር በእኛ ኢትዮጵያውያን እንዲጠና እና የ3 አመት የልማት ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለማስፈጸሚያ ገንዘብ ማግኘት ነበር። በፊት የነበረው መዋቅር ማዕከላዊነትን ያጠነከረና ለየክፍሉ የተሰጠው የሥልጣን ውክልና እጅግ ጠባብ በመሆኑ ጥቃቅኑን ጉዳይ ሁሉ ወደ በላይ ስለ ሚመራ ለቀልጣፋ ሥራ ምቹ አልነበረም።

አዲሱ መዋቅር ሀላፊነትና ሥልጣንን በማያሻማ ሁኔታ በየደረጃው በዝርዝር ከፋፍሎ፣ ቀልጣፋና ኤኮኖሚያዊ አሠራር ዘረጋ። በዚህም አሠራር መጀመሪያ የዋናው መሥሪያ ቤትን የሥራ ድርሻ ለይቶ፣ ሐገሩን በ6 ክፍለ ሐገር ከፋፍሎ፣ የደንበኞች አገልግሎትና የጥገና ሥራዎች ለየክፍለ ሐገሩ ሰጠ።

የዋናው መሥሪያ ቤት ድርሻ የሚከተሉትን ያካትታል፡- ፖሊሲ፣ ፕላን፣ ፕሮግራም፣ ፊናንስ፣ ዕቃ ግዥና ማደራጃ፣ አስተዳደር፣ እንጂነየሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ትምሕርት፣ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ቴሌኮምዩኒኬሽን የመንግሥት ውክልና ናቸው።

ዋናው መሥሪያ ቤት በ6 ዋና ክፍል ተቋቁሞ ዝርዝር ኃላፊነትና ሥልጣን ተሰጠው። የዋና ክፍል ሥራ አስኪያጆችና የክፍለ ሐገር ሥራ አስኪያጆች ተሾሙ። መጀመሪያ በቀጥታ ለዋናው ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ሆኑ፤ ከጥቂት ጊዜ በኃላ ደግሞ ከዋናው ሥራ አስኪያጅ ስር ለአስተዳደርና ለቴክኒክ ሁለት መምሪያ ተቋቋመ። ምክትል ሥራ አስኪያጅም ተሾመ። በኅዳር 1959 ሚስተር ሩድ ኮንትራቱን ፈጽሞ ሲሰናበትና ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራአስኪያጅ ሲሾም ድርጅቱ በሙሉ በኢትዮጵውያን ተያዘ።

**ዋና ክፍሎች**

| | |
|---|---|
| አስተዳር | ራዲዮ |
| ፊናንስ | ቴሌፎን |
| ኦፐሬሽን | ዕቃ ግዥና ማደራጃ |

እንደ ጊዜውና ሁኔታው መዋቅሩ ጥቂት በጥቂት ቢሻሻልም መሰረታዊ ለውጥ አላደረገም።

ከ1954 ጀምሮ በየተራ የዋና ክፍል ሥራ አስኪያጅ፣ የመምሪያ ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ካገለገልሁ በሁዋላ፣ ከታህሣስ 1959 አስከ ሰኔ 1966 ዋና ሥራ አስኪያጅነቱን ከሚስተር ሩድ ተረክቤ ለኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ።

በዚሁ ዘመን መስሪያ ቤቱ በቦርድ አመራር ከተቋቋመ ጀምሮ ከሚቆጠሩት የመስፋፋት ፕሮግራሞች፣ 2ኛውና 3ኛው እያንዳንዱ የ3 ዓመት፣ 4ኛና 5ኛው፣ የ5 ዓመት፣ ቀርጾ አራቱንም ፕሮግራሞች ፈጽሞ፣ 5ኛው የ5 ዓመት ፕሮግራም ሲጀምር የ1966 አብዮት ፈነዳ።

የልማት ፕሮጀክት ከዝርዝር ጥናት መነሻ ከተቀረጸ በኃላ፣ ፕሮጀክቱን በሥራ ለመተርጎም የገንዘብ አበዳሪ ስለሚያስፈልግ ለዓለም ባንክ ጥያቄ ቀረበ። ባንኩም ከዚህ በፊት ለመጀመሪያው ፕሮግራም ያበደረው ጥሩ ውጤት ያመጣ መሆኑን፣ አሁንም የአስተዳደሩ መዋቅር እና ተሻሽሎ የተቀረጸውን ፕሮግራም በመመርመር፣ የሰውን ችሎታና ኃይል በማገናዘብ የተጠየቀውን ፈቀደ። በሥራው ውጤት በመደሰት ለተከታታዮቹ ፕሮግራሞችም መንግሥት ከፈቀደ አስፈላጊውን ብድር ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር።

በ1943/44 ቴሌን መልሶ ለማቋቋም መጀመሪያ ብድር በተጠየቀ ጊዜ የዓለም ባንክ ፈቃደኛ አልነበረም፤ ምክንያቱም እንደ ቴሌኮምዩኒኬሽን ያለ ድርጅት በንግድ መልክ ተቋቁሞ ሊሠራ የሚችል በመሆኑና ባንኩ የሚያበድረው እንደ ትምሕርት፣ ጤና ጥበቃ፣ መንገድ ሥራ በመሆኑ ነው። የሆነ ሆኖ ከብዙ

*ሙከራ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በባንኩ ታሪክ የቴሌኮምዩኒኬሽን ብድር ለኢትዮጵያ ሰጠ፡፡ የሰጠው ብድር ያመጣውን ውጤት ከተገነዘበ በኋላ ለሌሎች በመልማት ላይ ላሉ አገሮችም ሲያበድር በውጤት መገምገሚያው የኢትዮጵያን ቴሌ እንደ መለኪያ አደረገው፡፡ ስለዚህ መንግሥት አምኖበት ብድሩን ከደገፈው፣ ባንኩ ለቴሌኮምዩኒኬሽን ቦርድ ብድር ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነ፡፡ የባንኩ ድጋፍ ይህ ብቻ አልነበረም፤ በሚሰጠው የብድር ውል ላይ ቦርዱን የሚደግፍ ብዙ ሁናቴ አስገብቷል፤ ለምሳሌ መንግሥትም ሆነ ባለሥልጣን የቦርዱን ሒሳብ በጊዜው መክፈል እንዳለበት፣ ለቦርዱ በሕግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት እንዳይኖርበት፣ ወዘተ፡፡ የመንግሥትና የባለሥልጣናት የቴሌ ሒሣብ በየሶስት ወር ለባንኩ ለማቅረብ በብድሩ ውል ተቀጥላ ስምምነት ተጽፏል፡፡ ሀሳቡን በመደገፍ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ሒሣብ ካልተከፈለ የቤተ መንግሥቱን ጭምር ቁረጡ ብለዋል፡፡ በድርጊትም ታይቷል፡፡*

*አዲሱ የኢትዮጵያውያን ማኔጅሜንት፣ ከጥር 1953 እስከ ጥር 1966፣ ሁለት እያንዳንዱ የ3 ዓመትና ሁለት እያንዳንዱ የ5 ዓመት በጠቅላላው 4 የልማት ፕሮግራሞች በተከታታይ አዘጋጅቶ የመጀመሪያ ሶስቱን በሥራ አውሎ፣ አራተኛው ሲጀመር አብዮቱ ስለፈነዳ ወደ ፊት ተላለፈ፡፡*

*የፕሮግራሞቹ መሰረታዊ አላማ የአገሩን ቴሌኮምዩኒኬሽን በጊዜው በነበረው ዘመናዊ መሳሪያዎች እያስፋፉ ቀልጣፋና ርካሽ አገልግሎት ላገር ውስጥም ሆነ ለአለም አቀፍ ግንኙነት ማዘጋጀትና በየጊዜው በሚፈጠረው ቴክኖሎጂም እየተጠቀሙ ሥራ ላይ ማዋል ነበር፡፡ በ13 ዓመት ውስጥ የተሠራው ዝርዝር ብዙ በመሆኑ እዚህ ላይ መጥቀስ ያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ በአዳዲስ ቴክኖሎጂ የተጀመሩትን እና ታላላቅ ሥራዎችን ጠቅሶ፣ ውጤቱን በፊት በተጠቀምንበት መስፈርት ማሳየት ይሻላል፡፡*

***ዋና የሥራ ውጤቶች***

1. *በከፍተኛ የራዲዮ መሳሪዎች ብዙ ቀጥታ የኢንተርኔሽናል ቴሌፎን ግንኙነት ተከፈተ፤ ከዚያ በፊት ከሰሐራ በታች ያሉ የአፍሪቃ አገሮች እርስ በርሳቸው ቀጥታ የቴሌፎን ግንኙነት አልነበራቸውም፤*
2. *የቴሌክስ አገልገሎት ተጀመረ፤*
3. *አቶ ተረፈ ራስወርቅ በፈለሰፈው ታይፕ ቴሌክስን በግዕዝ ፊደል ተጀመረ፤*
4. *ብዙ ኦቶማቲክ ማዞሪያዎች በብዙ ከተሞች ተቋቋሙ፣ ተስፋፉ፤*
5. *የክፍለ ሀገር ረጂም መስመሮች በብዛት ተሰሩ፤*
6. *የራዲዮ ቴሌግራፍ እና ቴሌክስ አገልግሎት ተስፋፋ፤*
7. *የማይክሮዌቭ ራዲዮ ተከላ ከአዲሰ አበባ እስከ ምጽዋ አልቆ፣ ወደ ሐረር፣ ጂማ፣ አዋሳ ተጀመረ፤*

**8.** **የትራንዚት ማዞሪያዎች ተተክለው ለመጀመሪያ ጊዜ የአዲስ አበባ - ደሴ - አስመራ - ምፅዋ - ናዝሬት - ድሬዳዋ ነዋሪዎች በቀጥታ እየደወሉ እርስ በርስ መገናኘት ቻሉ፤ ይህንንም ንጉሠ ነገሥቱ መርቀው ከፈቱ፤**

**9.** **የአዲስ አበባ (ጌጃ ዴራ)፣ አስመራ፣ ሐረር ሚዲዮም ዌቭ ብሮድካስት ራዲዮ ጣቢያዎች ተቋቋሙ፤**

**10.** **ራዲዮ ፎቶ፣ ቮይስ ካስት አገልግሎት ተጀመረ፤**

**11.** **በቴሌ ማይክሮ ዌቭ ራዲዮ ቴሌቪዥን ከአዲስ አበባ እስከ አስመራ ደረሰ፤**

**12.** **በአንድ ጥንድ ሺቦ አንድ ሰው ብቻ ባንድ ጊዜ በሚነጋገርበት መስመር ላይ ኬሪየር የሚባል ቴክኖሎጂ በማስገባት ተጨማሪ 12 ሰዎች እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፤**

13. **በሕንፃ ረገድ አዲስ አበባ የሚገኙት ታላላቅ ሕንፃዎችና በየክፍለ ሐገሩ ብዙ ህንፃዎች ተሠሩ፤**

**14.** **የአዲስ አበባን ዕድገት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በሚቀጥለው 20 እና 30 ዓመት ለማዞሪያ ያስፈልጋሉ ተብለው በጥናት የተደረሰባቸው 11 ቦታዎች ታውቀው አንዳንዶቹ አስቀድመው ተገዙ:: ብዙዎቹም በአሁኑ ጊዜ ማዞሪያ ተሠርቶባቸዋል::**

| መስፈርት | | የፕሮግራሙ ዘመን ዓመት | የአገልግሎት ማዕከል ብዛት | የቴሌፎን ደንበኞች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| | ጥር 1953 | | 168 | 8 973 |
| | ጥር 1966 | 13 | 343 | 46 245 |
| 2ኛ እስከ 4ኛ ፕሮግራም (የኢትዮጵያውያን) | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በመቶ | | 5.64 | 13.44 |
| | ጥር 1966 | | 343 | 46 245 |
| | ሰኔ 1983 | 17.5 | 512 | 133 091 |
| 5ኛና 6ኛ ፕሮግራሞች (ደርግ ዘመን) | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በመቶ | | 2.32 | 6.23 |

**የ5ኛው ፕሮግራም የተቀረጸውም ለ5 ዓመት፣ ለማስፈጸሚያም የብድር ውል ተፈርሞ ውሉም በፓርልያሜንት ጸድቆ ሥራ ሲጀመር አብዮት ፈነዳ:: በአብዮት ዘመን ደግሞ 6ኛ ፕሮግራም ተካሔደ:: በጠቅላላው ዕድገቱ በፊት ከነበረው ከግማሽ በታች ወርድዋል::**

**የሰው ኃይል፡-**

የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልገሎት በቦርድ ከተቋቋመ ጀምሮ የሠራተኛ አቀጣጠር፣ መብትና ዕድገት፣ የሥራ ክትትል፣ በዘመናዊ መልክ ተቋቁሟል:: ቅጥር በግልጽ ውድድር ሲሆን፣ እያንዳንዱ ሠራተኛ ሥራውንና ሃላፊነቱን እንዲያውቅ ይደረጋል:: በየ 6 ወር እየተገመገመ ውጤቱ ይከማቻል:: በቂ ውጤት ካለው ዓመታዊ የደሞዝ ጭማሪ በስኬሉ መሠረት ያገኛል:: ሥራው አጥጋቢ ካልሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል:: ዋናው ዓላማ ለማስፈራራት ሳይሆን ሥራውን እንደግል ንብረቱ ቆጥሮ እንዲሠራ ማበረታቻ ነው:: እዚህ ላይ በተለይ መጠቀስ የሚገባው ቴሌኮምዩኒኬሽን ለሴቶች ሥራ በሰፊው የከፈተ የመጀመሪያው ድርጅት መሆኑን ነው:: በጽንስና በወሊድም ሰፋ ያለ ዕረፍትና እንክብካቤ ይሰጣቸዋል:: መሥሪያ ቤቱ የራሱ ክሊኒክ አለው:: በሆስፒታልም ነጻ ሕክምና ይሰጣል:: ኢንሹራንስ፣ ክሬዲት ዩኒዮን አቋቁሟል:: የጡረታ ፈንድም ተቋቁሟል::

ከፍተኛ ሀላፊነት ቦታ ያሉት ቀድመው ይገባሉ፤ አምሽተው ይወጣሉ:: በበአል ቀን ብዙ ጊዜ ቢሮ ይገባሉ:: በጠቅላላው የሠራተኛው መንፈስ ቤቱ የራሴ ነው ብሎ የሚያስብ ይመስል ነበር:: ለምሳሌ ያህል ሁለት አጋጣሚዎችን ልጥቀስ::

አንድ ምሽት በ5 ሰዓት አካባቢ ከጊዮርጊስ በላይ በሚገኘው የቦርዱ ትራንስፖርት አገልግሎት ክፍል በኩል ሳልፍ የግቢውም የቢሮውም መብራት በሙሉ በርቷል:: በራፉ ላይ የነበረውን ዘበኛ ብጠይቅ *አልወጡም እኮ እየሠሩ ነው* አለኝ:: በማግስቱ ጠዋት ሀላፊውን በቴሌፎን ብጠይቀው *ቀን ሥራ ስለበዛብን ሪፖርታችንን ለመጨረስ አምሽተን ነው* አለኝ::

አንድ ቀን ደግሞ፣ የትራንስሚሽን ባለሙያዎች አምሽተው ትራፊኩ በቀነሰበት ጊዜ መሣርያ ሲመረምሩ፣ ከሱሉልታ ጣቢያ ጋር ግንኙነት በድንገት ተቋረጠ:: እንዴት በድንገት ይቋረጣል ሌቦች መስመሩን ቆርጠውት ይሆናል፣ ለፖሊስ ብንነግር መፍትሔ አናገኝም:: የኬብሉ መቋረጥ የዓለም አቀፍ ግንኙነትን በሙሉ ያቋርጣል:: እኛው እርምጃ እንውሰድ በማለት በቮክስ ቫገናቸው ተነስተው ወደ ሱሉልታ ገሰገሱ:: ተራራው ማህል ሲደረሱ ካሚዮን ቆሞ ሌቦቹ ኬብሉን እየቆረጡ ይጭናሉ:: እንደ ደረሱ አራቱንም ጎማ በሽጉጥ ሲመቱት ሌቦቹ ነፍሴ አውጭኝ ብለው በጭለማ ተበታተኑ:: በዚያ ዘመን የነበረው የሥራ ፍቅርና መንፈስ ዛሬም አለ/የለም የሚለውን ጥያቄ ለአንባቢው እተወዋለሁ::

በዘመኑ በነበረው ሁኔታ፣ እንደ ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች የቴሌም ሠራተኞች በማሕበር እንዲደራጁ ሕግ አይፈቅድም:: ሆኖም ቦርዱ የሠራተኛውን መብት በሙሉ ይጠብቃል::

ከፖስታ ቴ ቴ ሚኒስቴር ወደ ቴሌኮሙኒኬሽን ከተዛወሩት ውስጥ፣ በኋላም በዝቅተኛ ደረጃ (እንደ ጽዳት ሠራተኞች) የተቀጠሩት፣ ማንበብ መጻፍ አይችሉም ነበር:: ደሞዝ በጣት አሻራ ፊርማ ይቀበላሉ:: ሠራተኛውን በሙሉ ሊተሬት ለማድረግ (ማንበብና መጻፍ የሚችል ለማድረግ) በትዕዛዝ ሳይሆን በፈቃዳቸው ለጥቅማቸው እንዲያደርጉት በማሰብ፣ ለትምሕርታቸው

እንዲከፈልላቸው፣ ፈተናቸውን ሲያልፉ የደሞዝ እድገት እንዲያገኙ ተደረገ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ የቴሌ ሠራተኞች በሙሉ ሊተሬት ሆኑ::

ባለሙያዎች በትርፍ ጊዜያቸው ከፍተኛ ትምሕርት እንዲከታተሉ ይበረታታሉ:: የቴሌኮምዩኒኬሽን ኢንስቲትዩት ምሩቃን ሁለት ዓመት ካገለገሉ በኋላ ብዙዎቹ ዩኒቨርስቲ ሶስተኛ ዓመት ላይ ይገባሉ:: ሲመረቁም በፈቃዳቸው ቴሌ ይመለሳሉ::

## ማጠቃለያ

የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት ኢትዮጵያ መግባት ከጀመረበት ከ1886 ዓ.ም እስከ ደርግ አብዮት (1966) ድረስ የነበረው እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት እንደ ታሪክ ይታያል:: ከ 1886 እስከ 1945 በግቢ ሚኒስቴርና በፖስታ ቴ ቴ ሚኒስቴር ሥር ቆይቷል:: በመሀሉ ግን ፋሺስት ጣሊያን ከ1928 እስከ 1933 አስተዳድሮታል:: ጦርነቱ ሲጀመር በ1928 አገሩ ውስጥ 170 ከተሞች (የቴሌግራም/ ቴሌፎን ጣቢያዎች)፣7000 ኪሎሜትር ያህል የስልክ ረጂም መስመሮች ነበሩ:: ነፃነት ሲመለስ 96 ከተሞች ብቻ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በመሰረቱ ቢሆኑም በከፊል ችግር ነበረባቸው:: ከ1933 እስከ 1945 ባለው ጊዜ የፖስታ ቴ ቴ ሚኒስቴር ተረክቦ መልሶ ለማቋቋም ገንዘብም የሰለጠነ የሰው ኃይልም ለማግኘት ባለመቻሉ የአገልግሎት ጣቢያዎቹ ተቀንሰው በ 1945 65 ደረሱ::

ባለበት ሁኔታ መቀጠል አለመቻሉን መንግሥት ተገንዝቦ፣ ራሱን ችሎ በትርፍ መልክ ለሚሠራ የመንግሥት ተቋም፣ ከሙሉ ሥልጣን ጋር፣ ያለመንግሥት ጣልቃ ገብነት እንዲሠራና፣ በቴሌኮሙኒኬሽን ረገድ፣ ባገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ መንግሥትን የሚወክል *የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የቴሌኮምዩኒኬሽን ቦርድ* ስያሜ መነሻ ካፒታል ሰጥቶ በሕግ አቋቋመ::

ቦርዱ ከ1945 አስከ 1953 በውጭ ዜጎች መሪነትና ባለሙያዎች መልሶ የማቋቋምና በተሰጠው አነስተኛ ገንዘብ እስከቻለ ድረስ አዲስ ሥራ አከናወነ:: ከነበረበት ችግር ጋር ሲተያይ አጥጋቢ ውጤት አስመዝግቧል::

ከ 1953 እስከ 1966 የአብዮት ፍንዳታ፣ ወጣት ኢትዮጵያውያን ድርጅቱን ለ 13 ዓመት አካሒደውታል:: በዘመኑም ከፍ ያለ ውጤት ተመዝገቧል:: የ 13 ዓመት አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በመቶ 13.44 ነበር:: በዚህ ዕድገት ሁኔታ ቢቀጥል ዛሬ 3 ሚሊዮን ደንበኛ ይደርስ ነበር::

# የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ

*ተፈራ ደግፌ*

## መግቢያ

እንደሚታወቀው ለመጀመሪያ ጊዜ ባንክ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በ1898 ዓ.ም. ነው። ይህ "የአቢሲኒያ ባንክ" "Bank of Abyssinia" (የዛሬው ዘመናዊ ባንክ ሳይሆን) አጼ ምኒልክ በእንግሊዞች ትብብር አቋቁመው በ1923 ዓመት ገደማ በኢትዮጵያ ባንክ የተተካው ነው። በነፃነት ማግስት ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተቋቋመ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተተኪ ወራሽ ድርጅት ሆኖ ቀጠለ።

እኛ ያለፍንበት ዘመን ከአሁኑ ጋር ሲተያይ ብዙ ልዩነት አለው። አያሌ ዓመታት ስለአለፉ ብዙ ለውጥም ስለተደረገ ውጤቱን ማወዳደር ያስቸግራል። በእኛ ጊዜ ባንኮች እየተወዳደሩ የሚሰሩት አብዛኛውን በራሳቸው ውሳኔ ነበር። የብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር ብዙውን ጊዜ የሚፈጸመው ከባንኮቹ ጋር በመመካከርና በመግባባት ነበር። በዚህ ዓይነት ነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጽኑ መሰረት ላይ ሊዋቀር የበቃው።

ስለዚህ ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው በ1934 ዓ.ም. ከተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ ጀምሮ ወራሹ ድርጅት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያደረገውን አስደናቂ እድገት ላይ ነው። በኢትዮጵያ ባንኮች ውስጥ የፈጸምኩት አገልግሎት ከ1934 እስከ 1968 ዓ.ም. ድረስ በመሆኑ ጽሁፌ ከነዚህ ዓመታት አያልፍም።

## የመጀመሪያ ትምህርት

የተወለድኩት ሰኔ 8 ቀን 1918 ዓ.ም. ሸዋ ጠቅላይ ግዛት አንኮበር አውራጃ አንበሴ በሚባል ቀበሌ ነው። አባቴ አቶ ደግፌ በላይነህ እናቴ ወይዘሮ እርገጫቸው (እማማ እታባ) ገብረ ማርያም ናቸው። የአደግሁት ገንዳውሃ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ነው።

ሰባት ዓመት ገደማ ሲሆነኝ ለትምህርት ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ታላቋ አክስቴ ወይዘሮ ጌጤ ገብረማርያም ዘንድ አረፍኩ። አንድ ቄስ ቤት ፊደል ከቆጠርኩ በኋላ አሊያንስ ፍራንሴዝ በሚባል የፈረንሳይኛ ትምህርት ቤት ገብቼ ዘመናዊ ትምህርት ጀመርኩ።

ሁለት ዓመት ያህል እንደተማርኩ በ1928 ዓ.ም. ፋሺስት ኢጣሊያ አገራችንን ከወረረ በኋላ የአሊያንስ ፍራንሴዝ ትምህርት ቤት ስለተዘጋ ትምህርቴ ተቋርጦ ቀረ።

በአምስቱ የፋሺስት ኢጣሊያ ወራራ ዘመን ጥገኛ ሆኜ የኖርኩት ሌቭድሮዝዶቭስኪ የሚባሉ የሩሲያ ስደተኛ ጄኔራል ቤት ነው። ልጃቸው ማዳም አሌክሳንድራ ዳቤራት የታወቁ የጥርስ ሐኪም ነበሩ። በተላላኪነት፣ ጥቃቅን ሥራ በመሥራትና ልጃቸውንም በማጫወት ነው ያደግሁት። ከልጃቸው ጋር በመማር ሩሲያኛ እና ኢጣሊያንኛ ቋንቋ ለመማር በቃሁ። በነዚህም ቋንቋዎች ብዙ መጻሕፍት ለማንበብ ቻልኩ።

በ1933 ዓ.ም. በታላቋ ብሪታኒያ ጦር ዕርዳታ ነጻነታችን ከተመለሰ በኋላ የሚረዱኝ የፈረንጅ ቤተሰብ በሙሉ በጠላትነት ከአገር ስለተጋዙ መጠጊያ አጣሁ። የትምህርትም ዕድል ስላልገጠመኝ ሥራ ፈልጌ ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ በአስተርጓሚነት ተቀጠርኩ። በዚያን ጊዜ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ሚሸል ባንኩል የሚባሉ የመስኮብ ስደተኛ ነበሩ። አንድ ዓመት ያህል ሲንጀር ኩባንያ እንደሰራሁ የመማር ጉጉት ስለነበረኝ ሥራውን ለመተው ወሰንኩ።

አጋጣሚ ሆኖ አዲስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (State Bank of Ethiopia) ቋንቋ የሚያውቁ ሠራተኞች እየፈለገ ይቀጥራል ሲባል ሰምቼ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ማመልከቻ አቀረብኩ። በቀጠሮው ዕለት ሚስተር ሐይሊግ የሚባሉ ተባባሪ ሥራ አስኪያጅ አነጋገሩኝ። ሚስተር ሐይሊግ የሃንጋሪ ተወላጅ መስኮብ ቤተሰብ ዘንድ ስሠራ ያውቁኝ ስለነበረ ያለአንዳች ማመንታት ባንክ እንድቀጠር ፈቀዱ። በ1936 ዓ.ም. በ18 ዓመቴ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ በጸሐፊነት (Filing Clerk) ተቀጠርኩ። ሥራ ስጀምር ነው የማላውቀው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቅ ያለው። ወዲያውኑ ከጓደኞቼ ጋር ተሰብስበን በብሪቲሽ ካውንስል በተከፈተው ብሪቲሽ ኢንስቲትዩት በተባለው የማታ ትምህርት ቤት እንግሊዘኛ ለመማር ተመዘገብን። ባንክ አንድ ዓመት ተኩል ከሠራሁ በኋላ ከሌሎች ወጣት ሠራተኞች ጋር ተመርጬ ትምህርቴን ለማሻሻል ኮተቤ ወደሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተላክሁ። በየጊዜው ልዩ ፈተና እየተሰጠን የለብ ለብ ትምህርቱን በአንድ አመት ካጠናቀቅሁ በሁዋላ የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ የነፃ ትምህርት ዕድል ሰጥቶኝ ለከፍተኛ ትምህርት ካናዳ ተላክሁ፡፡

ስለዚህ በ1938 ዓ.ም. ለከፍተኛ ትምህርት ካናዳ ከተላኩት የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች አንዱ ነበርኩ። መጀመሪያ ያመራሁት ካልጋሪ አልበርታ ወደሚገኘው የንግድ ኮሌጅ (Garbutt Business College) ነበር። ባንድ ዓመት ውስጥ ትምህርቱን ጨርሼ ዲፕሎማ ለመቀዳጀት በቃሁ። ወዲያውኑ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ለመቀጠል ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ (UBC) በ1939 ዓ.ም. ተመዘገብኩ። ኮሜርስ ፋኩልቲ በየአመቱ የበጋ ትምህርት ጭምር እየወሰድኩ በ1942 ዓ.ም. ቢ.ኮም ወይም ባችለር ኦፍ ኮሜርስ (የንግድ ትምህርት ባችለር) ዲግሪ ተቀበልኩ። ሁለት ዓመት የሕግ ትምህርት ተከታትዬ በ1945 ዓ.ም. አገሬ ተመልሼ የባንክ አገልግሎቴን

ቀጠልኩ። አገር ውስጥና ጎረቤት አገርም በሚገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቅርንጫፎች፣ በጸሐፊነት ደረጃ ጀምሬ የባንኩ ነገረ ፈጅ በመሆን፣ በ1953 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለመሆን በቃሁ። ከ1956 እስከ 1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ከ1966 እስከ 1968 ዓ.ም. ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋና አዛዥ (Governor)፣ በመሆን አገልግያለሁ።

## የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አመሰራረት

እኔ ተቀጥሬ የባንክ ሥራ የጀመርሁበትን ሁኔታ ከገለጽኩ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንዴት እንደተቋቋመ መግለጽ አስፈላጊ ይመስለኛል። የኢጣሊያን ወረራ ተወግዶ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና በመቋቋም ላይ ሳለ፣ የእንግሊዝ መንግስት ፍላጐት የባንክና የገንዘብ ስርጭት ከእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪቃው የቅኝ አገዛዝ ጋር ተቀላቅሎ እንዲተዳደር ነበር። ግፊትም ታደርግ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ተነጥላ የራሷን ባንክ ለማቋቋም ስትነሳ ብዙ ችግር ገጥሟት ነበር።

ይህንን ችግር በውስጥ ምክርና ድፍረት ተወጥቶ፣ መንግስት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን በ1934 ዓ.ም. በአዋጅ አቋቋመ። በዓመቱ ሠራተኛው ተሰባስቦ ሥራውን ለመጀመር በቃ። በጦርነቱ ጊዜ የታላቋ ብሪታኒያን የጦር ሠራዊት ተከትሎ መጥቶ የኢጣሊያን ባንኮችን አስወግዶ የባንኩን ሥራ ተረክቦ የሚያስተዳድረው ባርክሌይስ ባንክ (Barclays Bank D.C.& O) ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ይህንን የእንግሊዝ ባንክ ተክቶ ነው ሥራውን የጀመረው። ባንኩ የተዋቀረው የማዕከላዊ ባንክንና የንግድ ባንክን ሥራ አጣምሮ እንዲሠራ ነው። ሥራውን ሲጀምር አብዛኞቹ የባንኩ ሠራተኞች የውጪ አገር ዜጎች ነበሩ። ብዙዎቹ ከኢጣሊያን ወረራ በፊት የቀድሞው የኢትዮጵያ ባንክ ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው። በእኛ ጊዜ ሠራተኛው ሲቀጠር ስልጠናና ማለማመጃ ሥርዓት አልነበረም። ሠራተኛው ሌላውን እያየ ነበር የሚለማመደው። ሁሉም ስለሚተዋወቅ መረዳዳት፣ በሥራው ውጤት መተባበር፣ የማወቅ ፍላጎት ጎልቶ ይታይ ነበር። ሁላችንም የመማር ጉጉት ስለነበረን በራሳችን ወጪ ከካይሮ ድረስ በፖስታ በመላላክ የሂሳብ ሥራ ትምህርት እንማር ነበር። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እውቀታችን ደካማ ስለነበር የሚያውቀው የማያውቀውን ይረዳ ነበር። በዚህ ዓይነት የባንኩ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ የገጠር ቅርንጫፎች መከፈት ጀመሩ። የእነዚህ ቅርንጫፎች ኃላፊዎችም የውጭ ዜጎች ነበሩ። ተራ ሠራተኞቹ ግን ሥራውን የሚለማመዱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በ1937 ዓ.ም. አሜሪካን አገር በሚስጥር ተዘጋጅቶ አዲስ የኢትዮጵያ ብር ገንዘብ ታውጆ ወጣ። በዚህ ዓይነት ነው የኢጣሊያ ሊሬና የምስራቅ አፍሪካ ሺሊንግ በአዲሱ የኢትዮጵያ ብር የተለወጠው። የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የባንክ ሥራው ቀስ በቀስ ነው እየሰመረ የሄደው። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት

ከባንክ ውጭ ለገንዘብ ሚኒስቴር ብዙ ልዩ ልዩ አገልግሎት አበርክቷል። አዲስ አበባ፣ ጂቡቲ፣ አሰብ የባሕር ትራንዚት አገልግሎት ይሠራ ነበር። የለገሃርን ጉምሩክ መጋዘን ያስተዳድር ነበር። አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ከፍቶ ለትምባሆ ሞኖፖል ሲጃራ በካርቶን ያከፋፍል ነበር። በአስረኛ ዓመቱ ነው (የባንኩ ስልጣን በአዋጅ እየተጠናከረ ሲሄድ) ወደ ዋናው የባንክ ተግባሩ የዞረው። ቅርንጫፎች በጠቅላይ ግዛት ዋና ዋና ከተሞች ተከፈቱ፤ በዚህ ዓይነት የባንክ አገልግሎት በመጠኑ መሰራጨት ጀመረ። በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ የባንኩ ደንበኞች የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። በብድርም በኩል አብዛኛው መንግሥት ነክና በውጭ አገር ሀብት የተቋቋሙ ድርጅቶች ነበሩ።

## የባንኩ ስልጠና መስፋፋት

በ1937 ዓ.ም. በወጣው የሕጋዊ ገንዘብ አዋጅ ባንኩ ባለሙሉ ሥልጣንና ብቸኛ የኢትዮጵያ ብር አሳታሚና አከፋፋይ ሲሆን የብሔራዊ ባንክ ሥልጣንን ተጎናጸፈ። ከዚህ ቀጥሎ፣ በኅዳር 21 ቀን 1939 ዓ.ም. በወጣ አዋጅ መሰረት የማሪያ ቴሬዛ ብር ያለው ሁሉ ባንክ እያቀረበ እንዲመነዝር ታወጀ።

ምንዛሪው አንድ ማሪያ ቴሬዛ ብር በአንድ ተኩል የኢትዮጵያ ብር ነበር። እንዲሁም ባንኩ ከነሐሴ ወር ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የውጪ ምንዛሪ (foreign exchange) ብቸኛ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሆነ። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ንግድ መስፋፋት ጀመረ። ዋናው የውጭ ንግድ የሚካሄደው (በጅቡቲና በኤደን ባንኮች ያለው ሁሉ) በባንክ በኩል ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንደ ንግድ ባንክ ሆኖ ሲሠራ መጀመሪያ የሚሰጠው አገልግሎት የተንቀሳቃሽ ሂሳብና የገንዘብ ማዛወር/ማስተላለፍ ሥራ ነበር። ሥራው እየደረጀ ሲሄድ ነው ተደራቢ ሥልጣን የተሰጠው። በ1938 ዓ.ም. የቁጠባ ሂሳብ (Saving Account) አገልግሎት መስጠት ጀመረ። የባንኩን ሥራ ለህዝቡ ለማለማመድና በባንኩ ላይ እምነትን ለመፍጠር ብዙ ዓመት ፈጅቷል። ገንዘቡን በጉድጓድ እየቀበረ ማስቀመጥ የለመደን ኅብረተሰብ ቀስ በቀስ እየመከሩ ባንክ አስቀምጥ ብሎ ማግባባት ቀላል አልነበረም። ብድርን በሚመለከት ደግሞ ንብረቱን አስይዞ መበደር የሚፈራውን ጀማሪ ነጋዴ ማሳመን፣ ገንዘብን በባንክ በኩል ማስተላለፍ ማስለመድ ከፍተኛ ትግል ነበር። ዘመናዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲጀምር ትምህርትም እየተስፋፋ ሲሄድ፣ ኢትዮጵያውያን ሥራውን እየተላመዱ የባንኩን አመራር እስከመያዝ በቁ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሁለገብ ድርጅት ሆኖ ጠቅላላ የባንክ አገልግሎትን ማስፋፋት ጀመረ። የማዕከላዊ ባንክ ሥራው የተወሰነ ነበር፤ ምክንያቱም አገር ውስጥ ይሠሩ የነበሩት የውጭ አገር ባንኮች አነስተኛ

ነበሩ። አንዱ አዲስ አበባ ተቋቁሞ የነበረው የፈረንሳይ ባንክ ደ ላንዶሽን (Banque Del'Indochine) የወኪል ጽሕፈት ቤት ነው። ሁለት ሌሎች ባንኮች አስመራ የነበሩት ባንኮ ዲ ሮማ (Banco Di Roma) እና ባንኮ ዲ ናፖሊ (Banco di Napoli) የሚባሉ የውጭ አገር የባንክ ቅርንጫፎች ነበሩ። የእነዚህ አነስተኛ ድርጅቶች የባንክ ሥራ በጣም የተወሰነ በመሆኑ የመንግሥቱ ባንክ የቁጥጥር ሥራ ቀላል ነበር።

ሌላው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተግባር የመንግሥት ተጠሪና ወኪል ሆኖ መሥራት ነበረ፤ ይኸውም በመንግሥት ስም ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልና መክፈል ነበር። ሲያስፈልግ ደግሞ ብድር የመስጠት ስልጣን ነበረው። ባንኩ ገንዘብ የማሳተምና የማሰራጨት፣ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ሀላፊነትም ነበረው። በዚህ አይነት ነው የንግድ ባንክና የማዕከላዊ ባንክ ሥራውን አጣምሮ ለሀያ አመታት ሲሠራ የቆየው።

### የካርቱም ቅርንጫፍ መከፈት

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ውጭ አገር የሚሠሩ ሁለት ቅርንጫፎች ነበሩት። የመጀመሪያው የትራንዚት ሥራ የሚሠራው የጂቡቲ ቅርንጫፍ ነበር። ሁለተኛው ለባንክ አገልግሎት ሱዳን አገር የተቋቋመው የካርቱም ቅርንጫፍ ነበር።

የባንኩን የካርቱም ቅርንጫፍ አመሰራረትና ይሰጠው የነበረውን የባንክ አገልግሎት አጀማመር ባጭሩ ለመግለጽ ያስቸግራል። መነሻው በክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ (በዚያን ጊዜ የንግድና የኢንዱስትሪ ምክትል ሚኒስትር የነበሩ) የሚመራ የንግድ ልኡክ እኤአ በ1957 ወደ ሱዳን መላክ ነው። እኔም የልኡኩ አባል ሆኜ ሄድኩ። የልኡኩ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የነበረው ንግድ የሚዳብርበትን ዕቅድ ማጥናትና የንግድ ውል መደራደር ስለነበረ፣ ለዚህ ዓላማ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ ካርቱም ቢከፈት የሁለቱን አገሮች የጋራ ንግድ እንደሚረዳ ስለታመነበት ጥያቄው ለሱዳን መንግስት ቀረበ። የሱዳን መንግሥትም ቅርንጫፉ ካርቱም እንዲቋቋም ፈቀደ።

የንግድ ልኡኩ ተመልሶ ሪፖርት አቅርቦ ከተፈቀደ በኋላ ለታቀደው የባንክ ቅርንጫፍ ብቁ የሆነ የሥራ አስኪያጅ በአስቸኳይ ተመርጦ እንዲቀጠር ባንኩ ታዘዘ። በጊዜው የነበሩት አሜሪካዊ የባንኩ ገዥ ሚስተር ጆርጅ ሬይ (George Rea) በሥራው የሰለጠነ ኢትዮጵያዊ የለም በማለት የአንድ እንግሊዝ ዜጋ ስም አቀረቡ። ለታቀደው ዓላማ የውጭ ዜጋ አይበጅም ተብሎ የባንኩ ምርጫ ውድቅ ሆነ።

በዚያን ጊዜ እኔ የሲቪል አቪዬሽን ዋና ዲሬክተር ሆኜ እሰራ ነበር። ከዚያ ተጠርቼ የካርቱም ቅርንጫፍ የባንኩ ሥራ አስኪያጅ ተብዬ በጽሕፈት ሚኒስቴር ማዘዣ ተሾምሁ። ከዚያም በኋላ ከምክትል ሥራ አስኪያጁ ከአቶ

ከበደ ሡረቀ ብርሃን ጋር ሆነን ቅርንጫፉን ለማቋቋም ሱዳን ተላክን። ካርቱም እንደደርስን በከተማው መሐል አዲስ የሚሠራ ሕንፃ ውስጥ ቅርንጫፉን ለማቋቋም የውል ድርድር ጀመርን።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የንግዱ ክፍል ቅርንጫፍ ካርቱም የተከፈተው በ1950 ዓ.ም. ከዋናው መሥሪያ ቤት አራት ኢትዮጵያውያን ኃላፊዎች ተመርጠው ተልከው ነው። ለቅርንጫፉ የሚስማሙ ሱዳናውያን እየመለመልን ቀጥረን ማሰልጠን ጀመርን፤ በተቻለ መጠን የባንኩ ገጽታ አፍሪቃዊ እንዲሆን ጥረት አደረግን። ባጭር ጊዜ ብዙ ደንበኞች አፍርተን ባንኩ ተወዳጅ ሆነ። ካርቱም የሚኖሩ ብዙ ኤርትራዊ ወይዛዝርት ስለነበሩ የቅርንጫፉ ደንበኞች ሆኑ። የባንኩ ሙሉ ስም ለአረብኛ ተናጋሪዎች ስለሚያስቸግር ደንበኞቻችን ቅርንጫፉን በወዳጃዊ አጠራር "ባንክ አል ሐበሺ" ብለው ሰየሙት።

በዚያን ጊዜ ሱዳን ውስጥ ስድስት የውጭ አገር ባንኮች ነበሩ። ሦስቱ የምዕራባውያን ባንኮች፣ ማለት ባርክሌይስ ባንክ፣ ኦቶማን ባንክና ክሬዲ ሊዎኔ ነበሩ። የመካከለኛው ምሥራቅ ባንኮች ደግሞ፣ የአረብ ባንክ፣ ባንክ ምስርና የሱዳን ንግድ ባንክ ነበሩ። የግብፅ ብሔራዊ ባንክ (The National Bank of Egypt) በሱዳን ውስጥ የማዕከላዊ ባንክ ተግባርን ሲሠራ ቆይቶ በሱዳን ባንክ ተተካ። ብቸኛው አፍሪካዊ ባንክ የእኛ ቅርንጫፍ ነበር። እነዚህን የደረጁ ባንኮች እየተወዳደረ የእኛ ባንክ በሦስት ዓመታት ውስጥ ብዙ ደምበኞች ለማፍራትና አትራፊ ለመሆን በቃ።

የባንካችን የካርቱም ቅርንጫፍ ለኢትዮጵያ የባንክ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የባንክ ውድድር ሥራ ለአገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት ምን ያህል እንደሚጠቅም ራሳችን እየሠራን ነው የተማርነው። ስለዚህ በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ በአገር ውስጥ ለባንክ አመራር ብቁ ሆነው ያገለገሉ አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊ የባንክ ባለሞያዎችና ኃላፊዎች ካርቱም ቅርንጫፍ እየሠሩ በቂ ልምምድ ያገኙ ናቸው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ማንሳት ይበቃል። ከበደ ሡረቀብርሃን፣ መስፍን በለጠ፣ ታደሰ አበበ፣ ስሜ ታከለ፣ ቸርነት በየነ፣ ተሳለ ወርቁ፣ ኢማም ቢ. ፌሎውስ፣ ጌታቸው ደስታ እና በላይነሽ ማንደፍሮ ነበሩ። ሁሉም ታዋቂ የባንክ ባለሙያዎች ሆነው እያንዳንዳቸው በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንክ ውስጥ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ የደረሱ ናቸው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካርቱም ቅርንጫፍ አስር ዓመት ያህል ካገለገለ በኋላ በጄኔራል ኒሜሪ ዘመነ መንግሥት እኤአ በ1969 የግል ባንኮች ሁሉ በሱዳን መንግሥት ሲወረሱ የእኛም ቅርንጫፍ አብሮ ተወረሰ።

## ባንኩን የውጭ አገር ዜጎች ሲያስተዳድሩት

አሁን ስልሳ አራት ዓመታት ካለፉ በኋላ ወደ ኋላ እየተመለከቱ ሁኔታዎችን በትክክል እያነጻጸሩ ማስረዳቱ ያስቸግራል። በጠቅላላው እኤአ ከ1942 አንስቶ እስከ 1959 ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዢዎች የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። የሚመጡት በልዩ የሥራ ኮንትራት እየተቀጠሩ ነበር። የባንኩ የሥራ አስፈጻሚና የውስጥ አስተዳዳሪዎችም የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን በከፊል ስልጣን መጋራት የጀመሩት አቶ የወንድ ወሰን መንገሻ ምክትል ገዥ ሆነው እ.ኤ.አ በ1959 ዓመተ ምህረት ሲሾሙ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን ያገለገሉት የውጭ አገር ዜጎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| ሚስተር ሲ. ኤስ. ኮሊየር | 1942-1943 |
| ሚስተር ጆርጅ ኤ. ብርላወርስ | 1949-1952 |
| ሚስተር ጃክ ቤኔት | 1944-1948 |
| ሚስተር ደብልዩ ኤች ሮዜል | 1953-1955 |
| ሚስተር ኒል ፔሪ | 1955 |
| ሚስተር ጆርጅ ሬይ | 1956-1959 |

በ1960 እ.ኤ.አ ክቡር አቶ ምናሴ ለማ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ተጠባባቂ ገዥ ሆነው ተሾሙ (በወቅቱ የመንግሥት ኦዲተር ነበሩ)። የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ኢግናሲዩስ ሜንዚስ የሚባሉ የሕንድ ተወላጅ ነበሩ። የባንኩን የውስጥ አስተዳደርም በኢትዮጵያውያን ለማስጨበጥ ታስቦ በ1953 አጋማሽ ላይ (እ.ኤ.አ 1961 አ.ም.) እኔ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ በመሾም የተካሁት እኚህኑ ሕንዳዊ ሥራ አስኪያጅ ነበር። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ነው የባንኩ ሥራ አስኪያጆች ሁሉ በኢትዮጵያውያን መተካት የጀመሩት።

በየድርጅቱ ውስጥ ብዙ የውጭ አገር ዜጎች ስለነበሩ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክን ለመምራት ብቁ አይደሉም የሚሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ከተረከብን በኋላ ሥራው ሳይዛነፍ በደንብ መቀጠሉ ብዙዎችን ሳያስደንቅ አልቀረም። እርግጥ ነው የውጭ ዜጎች የሆኑ አማካሪዎችና አንዳንድ ረዳቶች ነበሩ። በባንኩ ድጋፍ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያው የአክሲዮኖችና የገንዘብ ሰነዶች መሻሻጫ ገበያ ተቋቋመ። የባንኩ ዓመታዊ ሪፖርት መግለጫ ተሻሽሎ መታተም ጀመረ። ስለዚህ የብድር እድገት፣ የቅርንጫፎች መስፋፋት፣ የዓመት ገቢው ከፍተኛ እድገት የታየው በመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ማለት በ1953፣ በ1954 እና በ1955 ባንኩ በኢትዮጵያዊያን የበላይ መሪነት በሚካሄድበት ዘመን ነበር።

የአገር ውስጥ ንግድ መንቀሳቀስ ሲጀምር ልማቱን ለማበረታታት ቀስ በቀስ የባንክ አገልግሎትም በየከተማው መሰራጨት ጀመረ። የተሟላ የባንክ አገልግሎት በአዲስ መልክ ለማቋቋም እቅድ ወጣ። ይህ የባንክን አቋም የማሻሻል እቅድ ሰፊ ጥናት እንደሚያስፈልገው ታውቆ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (International Monetary Fund) አንድ አዋቂ ተቀጥሮ በገለልተኝነት የአገሪቱን ሁኔታ ካጠና በኋላ በዓመቱ ጥናቱን አጠናቆ አቀረበ። የቀረበው ጥናት፣ አገሪቱ ውስጥ የባንክ አገልግሎት እንዲስፋፋ ከተፈለገ፣ የግል ባንኮች መቋቋም አስፈላጊ ስለሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የባንክ ሞኖፖል መሰረዝ አለበት በማለት አሳሰበ። በዚህ ሀሳብ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሁለት ተከፍሎ አንዱ ማዕከላዊ ባንክ (የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሆነው) ሌላው ደግሞ የንግድ ባንክ፣ እንዲቋቋሙ ተወሰነ። ቀጥሎም፣ አዲስ የባንክ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለፓርላማ ቀረበና "ስለገንዘብና የባንክ ሥራ አዋጅ" በሚል ርእስ በሐምሌ ወር በ1955 ዓ.ም. ታውጆ ወጣ።

### የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ ለሁለት መከፈል

አዋጁ ከወጣ በኋላ የባንኩ ሀብትና ሠራተኛ በሁለቱ ድርጅቶች መሐከል ተደላድሎ በስድስት ወር ውስጥ ተጠናቀቀ።

ሀ/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማዕከላዊ ባንክን ሥራዎች ሁሉ አጠቃልሎ እንዲሠራ በልዩ አዋጅ ተቋቋመ።

ለ/ እ.ኤ.አ ከ1943 እስከ 1963 (ከ1936 እስከ 1955 ዓ.ም) የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሲሠራቸው የቆየውን የንግድ ባንክ ተግባሮች በንግድ ሕግ መሠረት ግላዊ ኩባንያ ሆኖ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ (አክሲዮን ኩባንያ) እንዲሠራው ተደረገ። በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ባንክ ባለአክሲዮኖች አምስት ነበሩ። ዋናው የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኖ አራቱ ደግሞ መንግሥታዊ ድርጅቶች ነበሩ። በአዋጅ ለብሔራዊ ባንክ ከተላለፈው ውጪ የቀረው የኢትዮጵያ መንግስት ባንክ ንብረት፣ ስልጣን፣ ጥቅምና ልዩ መብት ሁሉ በወራሽነት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተላልፏል። በዚህ መሠረት አዲስ አበባ የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ከነሂሳባቸው ወደ ንግድ ባንክ ተዛውረዋል።

የመንግሥት ባንክ ንብረትና ሠራተኛ በሁለቱ አዲስ ድርጅቶች መሐከል ተደላድሎ ሲያልቅ፣ በታህሣሥ ወር 1956 ዓ.ም. ክቡር አቶ ምናሴ ለማ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ሆነው ተሾሙ። እኔ ደግሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅና የብሄራዊ ባንክ የቦርድ አባል ሆኜ ተመረጥኩ። በተጨማሪ ለመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሁለቱ የመንግሥት ባንኮች ተባብረው እንዲሠሩ ታስቦ አቶ ምናሴና አቶ የወንድ ወሰን (የባንኩ ገዥና ምክትል ገዥ) የንግድ ባንክ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆኑ፡፡ እኔ

ደግሞ የብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባልነቴን ለቅቄ ሌላ ሰው ተተካ። ነገር ግን፣ የጥቅም ግጭት ያመጣል በሚል እሳቤ አቶ ምናሴም የንግድ ባንክ ቦርድ አባልነትን እ.አ.አ. በ1969 እንዲለቁ ተደረገ።

ብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንክ በአዲስ መልክ ተለይተው ሥራቸውን የጀመሩት እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 1 ቀን 1964 (1956 ዓ.ም.) ነው። በዚህ አይነት ነው የባንክ ሥራ በአገራችን ተደላድሎ ለመስፋፋት የበቃው። አዲሱ የባንክም አዋጅ በ1955 ዓመተ ምህረት እንደወጣ፣ ወዲያውኑ የግል ባንኮች ማለትም የአዲስ አበባ ባንክ፣ ባንኮ ዲ ሮማ (ኢትዮጵያ) እና ባንኮ ዲ ናፖሊ (ኢትዮጵያ) ለባለሀብቶች አክሲዮን እንዲሸጡ ስለተፈቀደላቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ ተቋቁመዋል፡፡ የማንኛውም የግል ባንክ ባለቤትነት ቢያንስ ቢያንስ አምሳ አንድ በመቶ (51%) ኢትዮጵያዊ እንዲሆን የባንኩ አዋጅ ያስገድደናል።

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቋቋም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1956 ዓ.ም. እንደ ግል ኩባንያ ሆኖ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሰረት ሲቋቋም የመሰረቱት አምስት ባለአክሲዮኖች ነበሩ። እነዚህም አምስት መንግሥታዊ ድርጅቶች ነበሩ። መንግሥትን ወክሎ ዋናውን ድርሻ የያዘው የገንዘብ ሚኒስቴር ነው። አራቱ ደግሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና መብራት ኃይል ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ ሲሚንቶ ኮርፖሬሽን ሲሆኑ እያንዳንዳቸው አንድ አክሲዮን ይዘው ባለቤት ሆነዋል፡፡ የባንኩ መነሻ ካፒታል 20,000,000 ብር ነበረ።

በግል መልክ የተቋቋመው መንግሥታዊው የንግድ ባንክ ከግል ባንኮች ጎን ለጎን ነፃ በሆነው ውድድር መንፈስ ሥራውን እየተሻማ የቀለጠፈ የባንክ አገልግሎት በማበርከት የአገሪቱ ኤኮኖሚ እንዲዳብር አስተዋጽኦ አድርጓል። በ1960ዎቹ አስር ዓመታት የአገሪቱ ኤኮኖሚ ሰፊ እድገት ያሳየበት ዘመን ነበር። ዘመናዊ የግል እርሻዎች የተስፋፉበት፣ ሰፋፊ የቡና ተክል የለማበት፣ እንዲሁም የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ እና ቡና በብዛት ወደ ውጭ አገር መላክ የተጀመረበት ዘመን ነበር። በዚህ የአገሪቱ እድገት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

ባንኩ በአዲስ መልክ ሥራውን እንደጀመረ ዋና እቅዱ ሠራተኞቹን ማሰልጠንና የባንክ ቅርንጫፎቹን ማስፋፋት ነበር። ቅርንጫፎቹን የማስፋፋት እቅዱ ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ቢያስከትልም ከፍተኛ የግል ቁጠባ ሂሳብና ተቀማጭ ገንዘብ ለማሰባሰብ ረድቷል። እንደሚታወቀው የአገር ልማት እቅዶች ግባቸውን እንዲመቱ ከተፈለገ ሕዝባዊ ተሳትፎ፣ ኅብረተሰባዊ ድጋፍና በቂ መዋዕለ ንዋይ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በ1960ዎቹ

ዓመታት ከመንግሥታዊ ድጋፍ ጋር የግል ዘርፍ እየተስፋፋ በመምጣቱ የአገር ውስጥና የውጭ ንግድ እንዲዳብር ባንኩ ረድቷል።

አርባ ዓመት ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስታውሰው በእኛ ዘመን ባንኩ በማደግ ላይ ስለነበረ ሠራተኛው በባንኩ የነበረውን እምነት ለማጠናከር በተቻለ መጠን አመራሩ ሠራተኛውን እያሰለጠነ የሚሾመው ከነባር ሠራተኛው እየመረጠ ነበር። በዚያን ጊዜ በባንኩና በሠራተኛው መሐከል የነበረው ግንኙነት ጤናማ የአባትና የልጅ ግንኙነት መሰል ስለነበረ ባንኩ የሠራተኛውን የሥራ ብቃት ለማሳደግና የሙያ እድገት ለማረጋገጥ ያስተምር፣ ያሰለጥንና ያበረታታ ነበር። በአጠቃላይ ሲታይ "እኔ ለድርጅቱ፤ ድርጅቱ ደግሞ ለእኔ" የሚል የመተሳሰብ ስሜት እንደነበረ በጊዜው የነበሩ ሠራተኞችና የባንኩ ደንበኞች ይመሰክራሉ፤ ያወሳሉ።

የባንኩ አስተዳደር በኢትዮጵያዊነቱ እየተመካ የሥራ ጥራቱን በማሻሻል ትጋትን፣ ትዕግስትን፣ ብቃትንና ቆራጥነትን ለማንፀባረቅ ይጥር ነበር። በተቻለ መጠን እውነት፣ ጨዋነት፣ ታማኝነት እንዲሰፍን ጥረት ያደርግ ነበር። የዘወትር የሥራ አክብሮትና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት መከበር ዋና ዓላማው ነበር። ይህ ነው ባንኩ በጽኑ መሰረት እንዲገነባ የረዳው። ምርታማነቱን ከፍ ለማድረግ እንዲያስችለው ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን ማካሄድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነበር። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደተቋቋመ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረታችንን ለሟሟላት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የምንቀበላቸውን አዳዲስ ተቀጣሪዎችንና ቀደም ሲል የነበሩትንም ሰራተኞች ከባንኩ አሰራር ጋር ለማስተዋወቅና አዳዲስ እውቀቶችና ብልሃቶች ለማስጨበጥ የሚረዳ የባንክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ከፈትን፡፡ ይህም የሰራተኞቻችንን የሙያ ብቃት በማሳደጉ ባንኩ በየጊዜው ላስመዘገባቸው ከፍተኛ የሥራ ውጤቶች ዋናው ምክንያት ከመሆኑ ሌላ፣ በሃገሪቱ ያሉትን የገንዘብና የመድን ተቋማት የሰው ኃይል እጥረት ለመሸፈን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉና በማድረግም ላይ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን መሰል የማሰልጠኛ ተቋም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሳይወሰን በኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በአውራ ጎዳና፣ በኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለስልጣን፣ በቴሌኮሚዩኒኬሽንና በሌሎችም ድርጅቶች በመቋቋሙ ለተቋማቱ መሰረት ገንብቶላቸዋል፡፡

## የሠራተኛው ስልጠና

የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ከነጻነት ማግስት ሲመሰረት የባንክ ትምህርት የተማረ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። የሰለጠነ የሰው ሀይል ለመገንባት መሰረት የሆነው በ1938 ዓመተ ምህረት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ወጣት ሠራተኞቹን መርጦ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲልክ ነው። በዚያን ጊዜ ለትምህርት የተላኩት አስራ አንድ ሠራተኞች ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው። ወደ ካናዳ የተላክነው መጀመሪያ እኔ፣ ከዚያም ቀጥሎ ተስፋ ዮሐንስ

ሐጎስና ይላላ ይብሳ ነበሩ። ወደ ሲዊስ አገር እና በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር የተዛወሩት አጥናፉ መንግሥቱ፣ ደበበ ሀብተዮሐንስ፣ መስፍን በለጠ፣ ታደሰ አበበ፣ ሥዩም አረሩ፣ ሥዩም ስብሐት፣ ነጋሳ ቶሌራና የሺጥላ አምበሉ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ተምረው ሲመለሱ ሦስቱ ወደ ሌላ መንግሥት ሥራ ተደለደሉ። አምስቱ ደግሞ፣ ማለት አጥናፉ፣ደበበ፣መስፍን፣ታደሰና የሺጥላ በባንክ ሥራቸው በመቀጠል ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ የባንክ ባለሙያ ሊሆኑ ችለዋል። ካናዳም የተላክነው እንዲሁ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የተላክንበትን ትምህርት አጠናቀን ስንመለስ ባንኩ አድጎ ሠራተኛው በርክቶ ቆየን። ስለዚህ ለቀረው ሠራተኛ ሁሉ ትምህርትና የባንክ ስልጠና እንዲያገኝ በእኛ ጉትጎታ ጥናት ተጀመረ። ሠራተኛው በየደረጃው የማታ ትምህርት እንዲከታተል ታስቦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ውስጥ በባንኩ እርዳታ የማታ ትምህርት የሚያስተምሩ ምሁራን ተቀጠሩ። የባንክ ሠራተኞች ከጀመሩ በኋላ ከሌሎችም መንግሥታዊ ድርጅቶች ብዙ የማታ ተማሪዎች ተመዘገቡ። በባንክ ድጋፍ የተጀመረው የማታ ትምህርት ፕሮግራም ተስፋፍቶ በኋላ የተለያዩ ዲፕሎማዎችንና ዲግሪዎችን የሚሰጥ የዩኒቨርስቲው ኤክስቴንሽን ትምህርት ፕሮግራም ሆኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሥራው እየተስፋፋ ቅርንጫፎቹ እየበረከቱ ሲሄዱ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ከንግድ ትምህርት ቤት ምሩቃን መቅጠር ጀመረ። የሰለጠነ የሰው ኃይል የእድገት መሠረት በመሆኑ የባንኩን የሰው ኃይል ለማጠናከር ባንኩ የራሱን ማሰልጠኛ ተቋም ለማቋቋም ወስኖ በ1955 ዓ.ም. የለንደን የባንክ ባለሙያዎች ተቋም (The London Institute of Bankers) ዋና ጸሐፊ የነበሩትን ሚስተር ሞሪስ ማግራን (Mr. Maurice Megarah) በመጋበዝ አስጠንቶ ለባንክ ድርጅቶች ተስማሚ የሆነ የባንክ ጥናት ተቋም (Institute of Banking Studies) ከፈተ። ይህ ነው ከዓመታት በኋላ አንድ ወጥ የሆነ የባንክና የመድህን ማሰልጠኛ ተቋም የሆነው።

የባንክ ስልጠና ተቋማት መኖር ብዙ ጠቀሜታ አለው። አንደኛው የሠራተኞቹን ምርታማነት ስለሚያጠናክር ወጪውን በመቀነስ ድርጅቱን ለውድድር ብቁ ያደርገዋል። ሁለተኛውና መሰረታዊ ሆኖ የሚታየኝ የነዚህ ዓይነት የስልጠና ጥረቶች ከፍላጎታችንና ከአቅማችን ጋር የተመጣጠነ የአሠራርና የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከል ከመሆኑ ሌላ የሀገራችንን እድገት ከማያዛልቅ የውጭ ጥገኝነት አላቆ አገር- በቀል በሆነና ዘላቂነት ሊኖረው በሚችል መሰረት ላይ ሊገነባ መቻሉ ነው።

በተጨማሪም ይኸ ስልጠና የሠራተኞቹን የሙያ ብቃት በማሳደጉ፣ ባንኩ በየጊዜው ላስመዘገባቸው ከፍተኛ የሥራ ውጤቶች ዋናው ምክንያት ከመሆኑ ሌላ፣ በአገሪቱ ያሉትን የገንዘብና የመድን ድርጅቶች የሰው ኃይል እጥረት ለመሸፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የዘወትር የባንክ አሠራር

የረቀቀ በመሆኑ በዚህ ዓይነት በየዘርፉ የሚሰጥ የማሰልጠኛ ተቋም በእኛ ጊዜ እንደጠቀመው አሁንም በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል።

በዚህ ዓይነት ስልጠና የባንክ ሙያውን ብቻ ሳይሆን ከሙያው ጋር አብረው መሄድ ያለባቸውን ቁም ነገሮች፣ ማለትም ትዕግስትንና ሰፊ የሆነ አመለካከትን፣ ለበጎ ምግባር መጨነቅን፣ ትክክለኛ የሆነ የባንክ ደምበኛና ሠራተኛ አያያዝን ማሰብና ማዳመጥ ነበር። ከአገር ውስጥ ስልጠናው በተጨማሪ ብቁ የሆኑት ሥራ አስኪያጆችና የአመራር ኃላፊዎች እየተመረጡ አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ኢጣሊያና እንግሊዝ አገር በሚገኙት ታላላቅ ባንኮች ከእኩዮቻቸው ጋር እየሠሩ እንዲለማመዱ ይላኩ ነበር። ከሥራው ልምምድ በላይ ከመሰል አገሮች ከሚመጡ የባንክ ዋና ሥራ አስኪያጆችና የብድር መምሪያ ኃላፊዎች በሚሰጡ ሴሚናሮች ላይም ይሳተፉ ነበር። በዚህ ዓይነት እውቀታቸውን ለማዳበርና ከመሰል ባለሙያዎችም ጋር ለማወዳደር ዕድል ነበራቸው።

የነበረውን የሥልጠና ዘዴ ይኸንን ያህል የምዘረዝረው በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ የባንክ አሰራር በፈጣን እርምጃ እየተለወጠ የሚሄድ በመሆኑ፣ ዘመናዊውን የአሰራር፣ የአስተዳደር እና የአመራር ዘዴዎችን በመቅሰም፣ ስልቱ ሠራተኛውን ተዋህዶት የሙያ ብቃትና ቀልጣፋነት እንዲኖረው ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል።

### የንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ ምረቃ

የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ እ.ኤ.አ. ኅዳር 16 ቀን 1915 ዓ.ም. በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመርቆ ሲከፈት ከባንኩ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሁሉ ታሪካዊ ግርማ የተሞላበት አስደሳች ጊዜ ነበር። በዚሁም የምረቃ ሥነ ሥርዓት ከብዙ የውጭ አገር የመጡ የባንክ ባልደረቦች ተገኝተውበት ነበር። ከእነዚህም መካከል፣ ከ1944 እስከ 1949 የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዥ የነበሩት ሚስተር ጆርጅ ኤ. ብላወርሰን፣ በዚያን ጊዜ የኒው ዮርክ ፌደራል ሪዘርቭ ባንክ ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑትና ከ1953 እስከ 1957 የቀደመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ገዥ የነበሩት ሚስተር ዋልተር ኤች ሮዜል፣ እና በአርጀንቲና የፈርስት ናሺናል ሲቲ ባንክ ኦፍ ኒው ዮርክ ምክትል ፕሬዚደንት የነበሩትና ከ1945 እስከ 1949 የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሚስተር ቪ. ኦፕሮል የንግድ ባንኩ የክብር እንግዳ በመሆን ተገኝተዋል፡፡

የንግድ ባንክ እያደገ የሚሄድ ለመሆኑ በሚገባ የሚያመለክተው ጎብኝዎችን የሚያስደስትና ከተለመደው ውጭ በሆነ አኳኋን የተቀየሰው የባንኩ ክብ

ሕንፃ ከብዙዎች አድናቆት ማትረፉ ነው፡፡[1] በዚህ የባንክ ምረቃ በዓል ላይ ከታደሉት የመታሰቢያ ስጦታዎች በተለይ የተቀረጹት የብርና የመዳብ መታሰቢያ ሜዳዮች፣ እንዲሁም በዚህ ዕለት የወጡት የማስታወሻ የፖስታ ቴምብሮች ውብ በመሆናቸው እጅግ በላቀ አኳኋን ደስ ብሎት ያልተቀበለ ሰው አልነበረም።

## የ25ተኛው እና የ30ኛው ዓመት ክብረ በዓል

የንግድ ባንክ በኅዳር ወር 1961 የልደት በአሉን "የብር ኢዩቤልዩ" በድምቀት አክብሯል። ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ይባል የነበረውና አሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሆነው የተቋቋመበትን ሃያ አምስተኛ ዓመት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት አክብሯል፡፡ ባንኩ በዘመናዊ ዕቅድ በተሠራው ሕንጻውና በቅርንጫፎቹ አማካይነት የጊዜውን ሁኔታ በመከተል ለደንበኞቹ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት ንጉሠ ነገሥቱ እየዞሩ በመጎብኘት ስላዩት በጣም ተደስተው ነበር። የቀደመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የአሁኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለቱም በኢትዮጵያ ውስጥ የአገሪቱ ኤኮኖሚ እንዲዳብርና በተለይም የንግድ፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ሥራ ይበልጥ እንዲስፋፉ ባለፈው 25 አመታት ውስጥ እርዳታ አድርገዋል። ይሁን እንጂ፣ የባንኩን አገልግሎት ለአብዛኛው ሕዝብ ለማዳረስ ብዙ እንደሚቀር እሙን ነው።

ባንኩ ያስገኘውን ፍሬ በመመልከት ለባንኩ እድገት የደከሙትን የቀድሞዎቹን ሹማምንት የባንኩ ወዳጆች ሁሉ አስታውሰው አመስግነዋቸዋል። በተለይም ከንግድ ባንኩ ጋር ተባባሪ በመሆን የረዱትን በልዩ ልዩ አገሮች የሚገኙትን ወዳጅ ባንኮች የንግድ ባንክ ምስጋና አቀርቦላቸው ነበር።

አጥብቄ የማስታውሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለየ ድምቀት በ1967 ዓ.ም. ያከበረውን የ30ኛውን ዓመት ክብረ በዓል ነው። አጋጣሚ ሆኖ በ 1967 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና የዓለም ባንክ (World Bank) ዓመታዊው ስብሰባ ናይሮቢ ከተማ የተደረገበትን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም፣ የበዓሉን ቀን አሸጋሽገን እንዲገጥም አደረግንና ከታወቁ ባንኮች ጋር በመጻጻፍ፣ ወደ አንድ መቶ

---

[1] ይህ ክብ ህንጻ፣ ከመከላከያ ሚኒስቴር ትይዩ እና ከብሄራዊ ባንክ ህንጻ ጋር ተያይዞ የሚገኘው የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ነው፤ ከስነ ህንጻ ሙያ (Architecture) አንጻር ሲገመገም፣ እውነትም እጅግ ያማረና የከተማው አንዱ ውብ ህንጻ ነው፡፡ Heran Sereke-Berhan and Shiferaw Bekele, "Fluorescence of the Arts in the 'New Flower' (Addis Ababa) before 1974" in *Continuity and Chaigen Threee Generations of Ethiopian Artists* (Florida: University of Florida Samuel p. Harn Museum of Art, 2007); Nikolaus Knebel, *Addis Modern: Re- discovering the 1960s Architecture of Africa's Capital City* (Addis Ababa; Goethe Institute & ElABC, 2013).

የሚሆኑ ከባንካችን ጋር ቅርብ ግንኙነት የነበራቸውን የባንክ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ ከናይሮቢ የመልስ ጉዟቸውን በአዲስ አበባ በኩል እንዲያደርጉ አግባብተን፣ ለባንካችን በዓል ጋበዝናቸው።

በዚህ አጋጣሚ ነው የአውሮፓና የአሜሪካ ታላላቅ የባንክ ፕሬዚደንቶች አገራችንንና ባንካችንን በመጎብኘት የንግድ ባንክን በዓለም መድረክ ታዋቂ ድርጅት ሆኖ እንዲታወቅ ያደረጉት። እንግዶቹ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ አውሮፕላን ተከራይተን በተቀነባበረ ፕሮግራም ባህር ዳርን፣ ጎንደርን ላሊበላንና ሐረርን አስጎበኘናቸው። በሄዱበት ሁሉ የባንኩን ኃላፊዎች ቀልጣፋነት እና የገጠር ቅርንጫፎቹን ዘመናዊነት በማየት አደነቁ። ባንኩም ይበልጥ ታዋቂና ዝነኛ መሆን ቻለ።

ጎብኝዎቻችን፣ በተለይ ደግሞ የተገረሙት፣ የባንኩ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነበር፤ በዚያን ጊዜ አፍሪካ ውስጥ የነበሩት ባንኮች አብዛኞቹ የሚመሩት በውጭ አገር ዜጎች ስለነበር ነው። በተጨማሪ የንግድ ባንክ ጎብኝዎችን እጅግ ያስደሰታቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ እንግዶቹን ቤተ መንግሥት ተቀብለው ብዙዎቹን በማነጋገር የተለየ የሻምፓኝ ግብዣ ስላደረጉላቸው ነበር።

### የቅርንጫፎች መስፋፋት

በ1960ዎቹ ባንኩ ከፍ ባለ ፍጥነት ቅርንጫፎች ከፍቷል። በየከተማው አዳዲስ የባንክ ቅርንጫፎች መከፈት በአገር ውስጥ ንግድ እንዲሰራጭ ረድቷል። ከሌሎች የግል መሰል ድርጅቶች ጋር እኩል በመወዳደር ሥራውን እያሰራጨ ሕዝብን በመርዳት ሀገሪቱ ለምታደርገው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጠቃሚ አገልግሎት አበርክቷል። ለህዝብ አገልግሎት መስጠቱ ጠቃሚ ቢሆንም ገንዘብ ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ ውሎ ትርፍ እንዲያስገኝለት መጣሩም ተግባሩ ነው። ይህ ዓላማ ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ከማስገኘቱም ሌላ የድርጅቱን የሥራ ክንውን የቀለጠፈና የተሟላ ያደርገዋል።

የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን አውታር ከጊዜ ወደ ጊዜ በማስፋፋት ባንኩ የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎትና የንግድ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በአገሪቱ ውስጥ እንዲሰራጭ በማድረግ ረድቷል። ይህ አይነቱም የሥራ አገልግሎት ለልማት መሠረታዊ ዓላማ የሆነውን የእርሻ፣ የንግድና የመገበያያ አቋም በበለጠ ሊያሻሽለውና ሊለውጠው ችሏል።

አዳዲስ ቅርንጫፎች የሚከፈቱት አማካይ ስፍራዎችን በማጥናት ነው። በጥናቱም የሚካተተው የንግድ እንቅስቃሴ፣ የኢንዱስትሪ እድገትና የሕዝብ ብዛት ነበር። የባንክ ቅርንጫፎች የሚከፈቱት ይህን አሟልተው በሚገኙ አማካይ ስፍራዎች ነበር። በዚህ በተፋጠነ እርምጃ ቅርንጫፎቹን አከታትሎ በመክፈት፣ በ1961 ዓመተ ምህረት ገደማ የባንኩ የቅርንጫፎች ቁጥር 65

ደርሶ ነበር። ምንም እንኳን የቅርንጫፍ አውታር በመዘርጋት የሚወጣው የካፒታል ውጪ፣ ገንዘብና የሠራተኞች ስልጠና ከባድ ሆኖ ቢገኝም ወደፊት ለባንኩ ተቀማጭ ሀብት መሆኑ አያጠራጥርም።

ቅርንጫፎች ለመክፈት የተደረገው እሽቅድምድም ህዝቡ ዘንድ የሚገኘውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በቅርንጫፎቹ አማካይነት ገንዘብ ለሚሹ ተበዳሪዎች ብድር ለመስጠትም ነበር። በየጠቅላይ ግዛቱ የራሳቸው ቤትና ቦታ ላላቸው ሰዎች እና በአነስተኛ የንግድና የኢንዱስትሪ ሥራ ላይ ለተሰማሩት ሁሉ ገንዘብ በማበደር ጠቃሚ አገልግሎት አበርክቷል። ይህም እርምጃ ቀስ በቀስ በኢኮኖሚ አቋም ላይ ለውጥ ማስገኘቱ ግልጽ ነው።

ምንም እንኳ ባንኩ የነበረበት ውድድር ብርቱ ቢሆንም የባንኩ የክፍለ ሀገር መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ባበደሩትም ሆነ ሊሰበስቡ በቻሉት ገንዘብ ላይ እድገት ለማሳየት ችለዋል። ይኸም ሲወርድ ሲዋረድ አሁን ባለበት ደረጃ አድርሶታል። ስለዚህ ባንኩ አገሪቱ ውስጥ ራቅ ካሉ ቦታዎች ሁሉ ግንባር ቀደም ሆኖ ቅርንጫፎች መክፈቱን ለዓመታት አላቋረጠም።

በአገር ውስጥ የተቋቋሙት የባንክ ቅርንጫፎች ሲበረክቱ ለአስተዳደርና ለሥራ ቅልጥፍና በሚያመችና ለመገናኛ በሚቀል አኳኋን ቅርንጫፎቹን በክፍለ አገር ደረጃ አዋቀርን። ቀድሞ የነበሩትንና አዲስ የሚቋቋሙትን የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ደረጃ በደረጃ በማሰባሰብ ለመምራት በሚያስችል «አማካይ አስተዳደር» (Regional Area) አደረግናቸው፡፡ ይህ ድልደላ ለቁጥጥር የሚያስችል ሆኖ ለዘለቄታው እድገት መልካም መሰረት ሆነ።

ንጉሠ ነገሥቱ የባንኩን መስፋፋት ይደግፉ ነበር። ክፍለ አገር ሲጎበኙ አዲስ የተቋቋመውን የባንኩን ቅርንጫፍ መመረቅ ደስ ይላቸው ነበር። አንዱን ቅርንጫፍ ሲመርቁ ካደረጉት ንግግር እጠቅሳለሁ።

> ...የባንክ አዋጅን ካወጅን ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በባንክ አሠራር ብዙ መሻሻል ተደርጓል። ባንኩ ከተቋቋመ ጀምሮ ባከናወነው ሥራ ስሙን በመልካም እያስጠራ ለመራመድ ችሏል። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ የባንክ ድርጅት ኢትዮጵያ የምታደርገውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሁሉ በማበረታታት መልካም ስምና ዝና ማትረፉ ግልጥ ነው። ለወደፊትም የመሻሻል እርምጃ በዚህ አኳኋን እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን።

## የንግድ ባንክ ጥገኛ ድርጅቶች

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባንድ በኩል ተወዳዳሪዎቹን ለመቋቋም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚው የሚያስፈልገውን እርዳታ ሁሉ ለማድረግ፣ የጀርመን ባንኮችን ሞዴል በመከተል ሁሉንም ዓይነት የባንክ አገልግሎት የመስጠት ዝንባሌ እየተከተለ ነበር። ይህንንም የምናደርገው በቀጥታ

ወይም በጥገኛ ድርጅት፣ ሲያስፈልግም በዘርፍ ኩባንያዎች አማካይነት ነበር። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አብዛኛውን አክሲዮን በመያዝ ያቋቋማቸው ጥገኛ ኩባንያዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

### 1. የኢትዮጵያ ንብረት ማልሚያ ኩባንያ አክሲዮን ማኅበር

የኢትዮጵያ ንብረት ማልሚያ አክስዮን ማኅበር የንግድ ባንክ ጥገኛ ኩባንያ ሆኖ የተቋቋመው በሐምሌ ወር 1959 ነው። እንደተቋቋመ የተረከበው የቀድሞ መንግሥት ባንክ በቁጠባና ብድር ክፍል ለቤት ማሠሪያ የሰጠው ሞርትጌጅ ብድርና በልዩ ልዩ ዓይነት ሥራ በሰው ዋስትና የተሰጠ ብድር ነበር።

የቤትና የሕንፃ ሥራ እየጨመረ የሚሄድ እንቅስቃሴ ነው። ችግሩን ለመቋቋም የንብረት ማልሚያ ኩባንያ የሚሰጠውን ብድር ማጠናከር ያስፈልግ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሊሆን የሚችለው የኩባንያው የገንዘብ አቋም ሲደረጅና ሲጠናከር፣ የሕዝቡ የቁጠባ ልምድ ሲደረጅ ነው።

ጥገኛ ኩባንያው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ንብረት በመሆኑ ድርጅቱ ራሱን ችሎ እንዲተዳደር ለማድረግ ባንኩ በተቻለ መጠን ይጥር ነበር። ይህንንም ዓላማ በመከተል ከአንድ ዝነኛ ከሆነ የኢጣሊያን ቁጠባ ድርጅት ጋር ልዩ ስምምነት አድርጎ ነበር። በስምምነቱም መሠረት ይህ የውጭ አገር ድርጅት የንብረት ማልሚያ ኩባንያው በሚያደርገው ሰፊ የሥራ ፕሮግራም ተካፋይ እንዲሆን ሲደረግ ኩባንያውም ስሙን በመለወጥ "የቁጠባና የንብረት ማልሚያ ድርጅት (ኮርፖሬሽን)" ተብሎ እንዲጠራ ተወስኖ ሥራ ላይ ዋለ። በዚህ ርዳታ መሠረት በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት ድርጅቱ መልካም እድገት አስመዘገበ።

የኢትዮጵያ የቁጠባና የንብረት ማልሚያ ድርጅት (ኮርፖሬሽን) የብድር ሥራው ሲጠናከርና ራሱን ችሎ መስፋፋት ሲጀምር የራሱን ሕንፃ ሠንጋ ተራ ሰፈር አውራ ጎዳና ባለሥልጣን ሕንፃ አጠገብ አሠርቶ ሲጠናቀቅ ሚላን የሚገኘው ታላቅ የኢጣሊያን የቁጠባ ባንክ (Cassa di Risparmio delle Province Lombarde) ሕንፃን ለማጌጥ የሚረዳ የቢሮ ዕቃና መሳሪያ በእርዳታ መልክ አቀረበ። አዲሱ ሕንፃ ተመርቆ የተከፈተው በ1964 ዓ.ም. የላይቤሪያው ፕሬዚደንት ክቡሩ ዶክተር ቶልበርት ኢትዮጵያን ሲጐበኙ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሁለቱ በተገኙበት ደማቅ ክብረ በዓል ነበር።

### 2. የንግድ ተጠሪ ማህበር

ባንኩ አንድ "ኮሜርሻል ኖሚኒስ" (ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር) በሚል ስም ድርጅት አቋቁሟል። ድርጅቱ በአገሪቱ ሕግ መሠረት የግለሰቦች ወይንም የኩባንያዎች ወኪል ወይም ተጠሪ በመሆን አክሲዮን እንዲገዛና እንዲሸጥ፣ በአንድ ወይም በሌላ መልክ የሚቀርቡትን የገንዘብ ግዴታዎች በመቀበል፣ በመያዝ፣ በማስተዳደርና በመሸጥ ደንበኞቹን እንዲያገለግል

ተቋቁሟል። ከዚህም በላይ በአደራ የተሰጡትን ንብረቶችና የሙት ሀብቶች በሟቹ ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት በማስተዳደርና በማከፋፈል የአደራ ጠባቂነትን፣ የኑዛዜ አስፈጻሚነትን ወይም የንብረት አስተዳዳሪነትን ሥራ ሁሉ ተቀብሎ ደንበኞቹን እንዲያገለግል ተደርጓል።

ንብረት በአደራ የማስተዳደር ክፍል ለማኅበራዊ ኑሮአችን ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ በመሆኑ ሕዝቡ ጥቅሙን እያወቀ ሲሄድ አገልግሎቱ ይስፋፋል ብሎ በመገመት ነበር ተጠሪው ድርጅት የተቋቋመው። በጥናታችን መሠረት የሞቱ ሰዎችን ንብረት በማሰባሰብና ሂሳባቸውን በማዘጋጀት ባንኩ የሚሰጠው አገልግሎት የማያቋርጥ በመሆኑ ጠቃሚነቱ የታወቀ ነው። ነገር ግን የ1966 አብዮት በግል ንብረት አያያዝ ከፍተኛ ለውጥ ስላመጣ የድርጅቱ ሥራ ውስን ሆኖ ቀረ፡፡

### 3. የባሕርና የትራንዚት አገልግሎት (አ.ማ.)

የባሕርና የትራንዚት አገልግሎት (አክሲዮን ማህበር) የባንኩ ጥገኛ ድርጅት ሆኖ የተቋቋመው እ.ኤ.አ. በ1968 ዓመት ላይ ነበር። ሥራው ከኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የተወረሰ ነው። የማኅበሩ ካፒታል 500,000 ብር ሲሆን የንግድ ባንክና የንብረት ማልሚያ ድርጅት አንድነት የማኅበሩን ካፒታል 80% ድርሻ ሲይዙ የቀረው ድርሻ ደግሞ የፈረንሳይና የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩባንያ ነበር።

ይህ ኩባንያ ቀድሞ በጂቡቲ፣ በአዲስ አበባና በአሰብ ከተሞች በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ፣ በኋላም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ይካሄድ የነበረውን የትራንዚት የዕቃ መላክና የመጋዘን ሥራ (Bonded Warehouse) ተረክቦ ያከናውን ነበር። ኩባንያው የተመሰረተው፣ ወደፊት ሥራው እየተስፋፋ ሲሄድ፣ ለንግድ ባንክ ደንበኞችና ለሌሎችም እንዲሰጥ ሲሆን፣ ይህም በሸቀጥ አስመጪነትና ላኪነት ሥራ ለተሰማሩት ሁሉ ጠቃሚ አገልግሎት በጅቡቲ፣ በአሰብና በምፅዋ ወደቦች ለሚጠቀመው ሁሉ በጣም ጠቃሚ አገልግሎት ይሆናል ተብሎ ተገምቶ ነበር። ከአብዮቱ በኋላ እቅዱ ተለወጠ። በደርግ አገዛዝ ዘመን ማኅበሩ ከሌሎች ከተወረሱ የትራንዚት ድርጅቶች ጋር ተዋሀዶ አንድ ብቸኛ የመንግሥት የባሕር አገልግሎትና የትራንዚት ድርጅት ሆኖ ሥራውን እንዲቀጥል ተደረገ።

## የነበረው የኢኮኖሚና የንግድ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለመገመት በጊዜው የነበረውን የእድገት ደረጃ ማስታወስ ይረዳል።

በእኛ ዘመን አገሪቱ ስትከተል የነበረው በአመዛኙ የነፃ ገበያ ሥርዓትን ነበር፤ ዘላቂ ጥቅሟን የሚንከባከብና በተወጠነለት የእድገት አላማ የምትመራበት ሥርዓት ነበራት። አገሪቷ የነበራትን አነስተኛ ወረት ከውጭ

ከሚገኝ እርዳታና ብድር ጋር አቀናጅቶ ከፍተኛ እድገት ሊያመጡ በሚችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያውል በየአምስት ዓመቱ የሚዘጋጅ የልማት ፕላን ነበራት። በ1950ዎቹ መባቻ ላይ የተጀመረው ይህ የአምስት ዓመት ፕላን በዘመኑ የማይናቅ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና እድገት አሳይቷል። በተለይም በሁለተኛውና በሦስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ዘመናት አገሪቷን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ይረዳሉ ተብለው የተቋቋሙ ፋብሪካዎች እያደጉና እየጎለበቱ ሄደዋል፤ በመንግሥት አካላትና በንግዱ ኅብረተሰብ መሐከል ከፍተኛ የመተጋገዝና የመረዳዳት መንፈስና ፍላጎት ተፈጥሮዋል። ይህ ትብብርም የማይናቅ እድገት አምጥቷል።

በንጉሡ ዘመን የነበረው የኢኮኖሚ ይዞታ "የጠራ ውድድር" ባይሆንም፣ የግል ንብረት መርህ የሰፈነበት ወቅት ነበር። በሚሰጠው የአጭርና የረጅም ጊዜ ብድር የንግድ ባንክ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። አገር ውስጥ ከነበሩት ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች እና የንግድ ድርጅቶች አብዛኞቹ ከባንኩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። ለሥራ ማስኬጃ፣ ለዕቃ ማከማቻና ለውጭ ንግድ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ (ኦቨርድራፍት) ወይም በቋሚ ብድር የማይጠቀም ኩባንያ አልነበረም ማለት ይቻላል። እርግጥ ነው በጊዜው የነበሩት ባለሀብቶች አብዛኛዎቹ የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። ባንኩ ብድር ሲሰጥ የሚያመዛዝነው የዋስትናውንና የሥራ ብቃቱን ነበር።

በአሁኑ ጊዜ የብድሩን አሃዝ ማንሳቱ አይጠቅምም፤ የኢንዱስትሪዎቹን ስምና ተግባር እጠቅሳለሁ፦ የዳርማርና የአስኮ ኩባንያ የቆዳ ማልፊያና የጫማ ፋብሪካዎች፤ የድሬዳዋ፣ የባሕር ዳር፣ የዲያባኮ፣ የላዛሪዲስ፣ የባራቶሎ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፤ የኮካ ኮላ፣ የሣባ ጠጅ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስና የሜታ አቦ የቢራ ፋብሪካዎች ሁሉ የባንኩን ድጋፍ ይፈልጉ ነበር። በንግዱም በኩል የባንኩ ድጋፍ ወሳኝ ነበር። ከታላላቅ አስመጪ ኩባንያዎች ቤስ፣ ሚቸልኮት፣ ፖል ሪየስ እና ሰፈሪያን የባንኩ ደንበኞች ነበሩ፡፡ ከቡና ላኪዎች መሀከል ከድር ኤባን፣ ኮታሪን፣ ተድላ ደስታን እና ኪዳኔ በየነን አስታውሳለሁ፡፡

የንግድ ባንክ ለሕዝብ ከሚያቀርበው የባንክ አገልግሎት ሌላ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር የሀገር ውስጥ መጠነኛ የአክሲዮን ገበያ አቋቁሞ ነበር። ይህንን የአገር ውስጥ የአክሲዮን ገበያ ለማስፋፋት ብዙ እቅድ ነበረው። ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ገንዘባቸውን ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ባንኩ ያበረታታ ነበር። ባለሀብቶች የአክሲዮንን ጥቅም ተረድተው ገንዘባቸውን በዚህ ተግባር ላይ ካላዋሉ ደንበኛ የካፒታል ገበያ ሊስፋፋ አይችልም። በዚህ ዓይነት ጥቂት መሻሻል ቢታይም፣ ገንዘቡን አክሲዮን ግዢ ላይ ለማዋል የሚፈልገው ሕዝብ ብዙ ምርጫ እንዲኖረው ለማድረግ በገበያው ላይ የሚሸጡትንና የሚገዙትን አክሲዮኖች ማብዛት ያስፈልጋል።

ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት በዚያን ዘመንና በተለይም ከ1955 እስከ 1965 ዓ.ም. ድረስ በነበሩት አስር ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የልማት ተግባራት ተካሂደዋል። በእነዚህ ዓመታት የተሠሩትን ሥራዎች ሳስታውስ ሁለት ቁም ነገሮች ውል ይሉብኛል። አንደኛው፣ በመንግስትና በንግዱ ኅብረተሰብ መካከል የአላማ አንድነት መኖሩ ከታመነበት እና እነዚህ ሁለት አካላት ይህንን በመሰለ የትብብርና የአላማ አንድነት ከተሣሩ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ አገሪትዋ ከፍተኛ ለውጥ ልታስመዘግብ መቻሏ ነው። ሁለተኛው፣ በዚያን ጊዜ የነበረው የልማት ጥረት ቢቀጥል ኖሮ እያልኩ አንዳንዴ የሚመጣብኝ ቁጭት ነው።

አንዳንዴ ወዳለፈው ዘመን መለስ ብዬ ስመለከት በእኛ የሥራ ዘመን የጎደለው ቆራጥነት ይመስለኛል። በነበረን ሰፊ የአስተዳደር ስልጣን በድፍረት ብዙ ሊሠራ ይችል ነበር። ሲያስፈልግም አስረድተን፣ ጠቀሜታውን አሳውቀን፣ ሽንጣችንን ገትረን ብንከራከር ኖሮ የተሻለ ለውጥ አምጥተን የተሻለ አገር ለተተኪው ትውልድ እናስረክብ ነበር።

የአገሮችን የኢኮኖሚ ዳርና ድንበር ለማፈራረስና ዓለምን አንድ ወጥ ለማድረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ በእጅጉ እየተፋፋመ ነው። ስለዚህ የዛሬው የምርት ዓለም እኛ ከነበርንበት በጣም ተለውጧል። እኛ ስንመካባቸው የነበሩት አስተማማኝና ፈጣን የግንኙነት መስመሮች ኋላ ቀር ሆነዋል። ዛሬ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ መረጃ የሚተላለፈው ከመቅፅበት ሆኗል። ገዥና ሻጭ፣ ባንክና ደንበኛ፣ ለመገናኘት በደላላና ባገናኝ መማሰኑ ቀርቶ ኢንተርኔትን ወደ ማገላበጥ ተለውጧል።

በአሁኑና በእኛ ዘመን ያለው ትልቅ ልዩነት የገበያ ጉዳይ ነው። በአገራችን የነበሩት ኢንዱስትሪዎች ተግዳሮት እና በግብርናው ዘርፍ የነበረው ችግር የምርት ሳይሆን የገበያ እንደነበር የታወቀ ነው። ገበያን ለማስፋፋት አገር ውስጥ ብዙ ጥረት ነበር።

### መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሕዝባዊ አገልግሎት አላማው ንጉሣዊ ድጋፍ ነበረው። አፄ ኃይለ ሥላሴ ለባንኩ ልዩ አስተያየት ነበራቸው። የባንኩን ቅርንጫፍ በመረቁ ቁጥር በሚያደርጉት የምረቃ ንግግር ላይ በባንኩና በሕዝቡ መሐከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ሲናገሩ “የሕዝብ በጎ ፈቃድና መተማመን በየዕለቱ መረጋገጥ አለበት” ይሉ ነበር። በተለይ በ1960 ዓ.ም. የአዲስ ከተማውን ዋና ቅርንጫፍ ሲመርቁ እንዲህ ብለው ነበር፦

> በኢትዮጵያ የባንክ አዋጅ ከአወጅን ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በባንክ አሠራር ብዙ መሻሻል ተደርጓል። ባንኩ ከተቋቋመ ጀምሮ ባከናወነው ሥራ ስሙን በመልካም እያስጠራ ለመራመድ ችሏል። ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ባንክ ድርጅት ኢትዮጵያ የምታደርገውን የኢኮኖሚ

> እንቅስቃሴ ሁሉ በማበርታት መልካም ስምና ዝና ማትረፉ ግልጥ ነው። ለወደፊትም የመሻሻል እርምጃ በዚህ አኳኋን እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን።

መቼም በዚህ ዓለም ሁሉ ነገር ሰው እንዳሰበው አይሆንምና በ1966 ዓ.ም. ያልታሰበ ለውጥ መጣ። ድንገት አብዮት ፈነዳ፤ የነበረው ንጉሣዊ ሥርዓት ፈረሰ። መሬት የመንግሥት ሆነ፤ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ተወረሰ። የግል ባንኮችና የመድን ድርጅቶች ተወርሰው በብሔራዊ ባንክ ስር ተሰባሰቡ። የንግድ ድርጅቶችና የግል ፋብሪካዎች ሁሉ ወደ መንግሥት ይዞታ ተዛወሩ። በወደቀው ሥርዓት ስር በአመራር ላይ የነበረው ኅብረተሰብ ከፊሉ ተገደለ፤ ገሚሱ ታሰረ፤ ሌላው ከሥራ ተባረረ፤ አንዳንዱ ደግሞ ተሰደደ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ከዚህ የለውጥ ትርምስ አላመለጠም።

በደርግ ዘመን ማዕከላዊ የኢኮኖሚ አሠራር የተንሰራፋበት ጊዜ ስለነበረ ባንኮቹን ሥራ በሚያጨነግፍ ሞኖፖል አስሮ በመያዝ፣ ቁጥጥሩ ተጠቃሎ ለብሔራዊ ባንክ ተሰጠ። በደርግ አገዛዝ ዘመን ድርጅቶች በነፃ እንዳይንቀሳቀሱ የሚያደርገው ቁጥጥር ጠበቀ፤ ቅርንጫፎች የሚቋቋሙት በገበያ ጥናት መሆኑ ቀርቶ፣ በባለሥልጣናት ፍላጎትና ትእዛዝ ሆነ። የብድር ፖሊሲው የታቀደው የነበረውን ሶሻሊስታዊ ሥርዓትን ለማጠናከር ነበር። በዚህ ከባድ ተጽዕኖ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ፈራርሶ ከፍተኛ ውድቀት ደረሰበት።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2003 ዓመት የ60ኛ ዓመቱን ክብረ በዓል ሲያከብር በጊዜው የነበሩት የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ ገዛኸኝ ይልማ፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አመሰራረት አንስቶ ባንኩ የገጠመውን የእድገት ውጣ ውረድ አውስተው፣ ያለፉትንም የባንኩን ባለሙያዎች አስታውሰው፣ በሚቀጥሉት ቃላት አሞግሰዋቸዋል፦ "ታሪክ ከማይረሳቸው ከእነዚህ ቀደምት የባንክ ባለሙያዎች መስዋዕትነትን፣ የዓላማ ጽንዓትን፣ ለአገር አሳቢነትን፣ ተቆርቋሪነትን፣ ታማኝነትን እኛ በአዲሱ ዘመን የምንገኝ ዜጎች ልንማር ይገባናል" ብለው ደምድመዋል።

እኔም ጽሁፌን በሚከተለው ሃሳብ እደመድማለሁ። የዛሬ ስምንት ዓመት በ1991 ዓ.ም. ለአቢሲኒያ ባንክ ምረቃ ተጋብዤ በመጣሁበት ጊዜ ለጦቢያ መጽሔት ቃለ ምልልስ ሰጥቼ ነበር። መደምደሚያው ላይ ላገሬ ያለኝን ራዕይና ምኞት ተጠይቄ የሰጠሁትን መልስ አዘጋጆቹ አጠቃልለው እንዲህ ብለው መዝግበውት ነበር፦ "እኔ ለኢትዮጵያ የምመኘው ከጦርነት ውጥረትና ከሚያስከትለው ጥፋት አምልጠን በመልማት ላይ እንዳሉት ሌሎች አገሮች ወደ ልማቱና ማህበራዊ እድገት እንድትደርስ ነው። ለዚህ ደግሞ ራዕይ ያለው አመራር፣ ተግባብቶ የሚኖር ህዝብ፣ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ የሚኮራና አገሩን የሚያስከብር ዜጋ መኖር ወሳኝ ነው።" ብዬ ነበር። አሁንም ምኞቴና ፀሎቴ ይኸው ነው።

# የኢንዱስትሪ እና የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር እድገት

*ተፈራ ኃይለ ሥላሴ*

## *መግቢያ*

የጽሁፌ ርእስ ሁለት ሰፋፊና በይዘታቸው የተለያዩ ጭብጦችን የሚመለከት ስለሆነ፣ በዚህ በአንድ መጣጥፍ በበቂ ጥልቀት እመረምራቸዋለሁ ለማለት አልደፍርም:: ቢሆንም የምችለውን ያህል በሁለቱም ላይ መሰረታዊ የሆኑትን ጉዳዮች ለመዳሰስ እሞክራለሁ::

የመጀመሪያው ጭብጥ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች አስተዳደር (Labour Administration) ሁለተኛው ደግሞ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች አስተዳደር ይሆናል:: እነዚህን የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች የአስተዳደር ሥርዓቶች በተቻለ መጠን ከዓለም የሥራ ድርጅት (International Labour Organization) ድንጋጌዎችና (Conventions) በመልማት ላይ ካሉ አገሮች፣ በተለይም ከአፍሪካ አገሮች ተሞክሮ ጋር፣ እንደሁኔታውና አግባቡ በማነፃጸርና በማገናዘብ ለማቅረብ እሞክራለሁ::

የኢንዱስትሪ ሠራተኞች አስተዳደር የሚባለው የኢንዱስትሪ ግንኙነትን (Industrial Relation)፣ የሥራና የሰው ኃይል አስተዳደርንና (Employment and Manpower Administration) የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ አገልግሎትን (Labour Inspection Service) ስለሚያጠቃልል፣ እነዚህን ሦስት የሥራ ዘርፎች ከዚህ ቀጥለን እናያለን::

## የኢንዱስትሪ ግንኙነት

የኢንዱስትሪ ግንኙነት ከኢንዱስትሪ መስፋፋትና እድገት ጋር ተገናዝቦ የሚታይ ጉዳይ ነው:: ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ መስፋፋት የጀመረበት ጊዜ ከሌሎች አገሮች፣ በተለይ በቅኝ ግዛት አስተዳደር ስር ከነበሩ የአፍሪካ አገሮች፣ የእድገት ታሪክ ጋር ሲነፃጸር እጅግ አጭር ሆኖ ይታያል:: ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ቀርቶ ለብዙ ሺ ዘመናት የኖረውን የመንግሥት መስተዳድር እንኳ በሥራ ዓይነት መደልደልና ሠራተኞችን በደሞዝ ማስተዳደር፣ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመን የተጀመረ ቢሆንም፣ በተወሰነ ደረጃ በተግባር መተርጎም የተጀመረው ግን በዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነበር:: በግሉም ክፍለ ኢኮኖሚ እንደ ባንክ፣ ወፍጮ፣ ማተሚያ ቤት እና ሆቴል የመሳሰሉ አገልግሎቶች ብቅ ብቅ ማለት ቢጀምሩም ሠራተኞች የሚተዳደሩበት በመንግሥት ደረጃ የወጣ ሕግ አልነበረም:: አሠሪው በመሰለው ደሞዝና የሥራ ሁኔታዎች ሠራተኛ የሚያስተዳድርበት አካሄድ ነበር የሰፈነው:: የኢንዱስትሪ መስፋፋት ገና በለጋነት እድሜ ስለነበር፣ የሠራተኞችን የመደራጀት መብትን፣ ቅጥርን፣ ስንብትን፣ ደሞዝን፣ የሥራ ሰዓትንና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን

በህግ መወሰን በጊዜው ከነበረው የመንግሥት መስተዳድር የንቃተ ህሊና ደረጃ አንፃር ሲታይ የሚታሰብና ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አልነበረም፡፡ በተለይም የባርያ ስርዓት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ በጣት በሚቆጠሩ ተቋማት ውስጥ ለሚሠሩ አነስተኛ ቁጥር ለነበራቸው ሠራተኞች ደንብ ማውጣት የማይታሰብና እንደ ቅንጦት የሚቆጠር ነበር፡፡ ስለዚህ፣ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የነበረው ግንኙነት የጌታና የሎሌ ነበር፡፡

በንግሥተ ነገሥታት ዘወዲቱ ዘመነ መንግሥት (1909-1922 ዓ.ም.) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን በማደራጀትና የሥራ መመሪያ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ለውጥ የታየ ከመሆኑም በላይ፣ በተለይ ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን የአውሮፓ አገሮች ጉብኝት (1916 ዓ.ም.) በኋላ፣ ዘመናዊ ሥልጣኔ ወደ አገር ለማስገባት እና ለመስተዳድሩ ዘመናዊ ቅርጽ ለመስጠት በየሥራ መስኩ የውጭ አገር ባለሙያዎችን በመመደብ ብዙ እንቅስቃሴ ይደረግ ነበር፡፡ በተጨማሪም፣ በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብቸኛ ነፃ አገር ስለነበረችና ይኸውም በዓለም መድረክ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ በጊዜው በነበሩት የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ማህበርተኛ ሆኖ ለመግባት ጥረት ይደረግ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት፣ አገራችን በ1915 ዓ.ም. የዓለም መንግሥታት ማኅበር (the League of Nations) እና የዓለም የሥራ ድርጅት አባል ሆነች፡፡ ምንም እንኳ የእነዚህ ድርጅቶች፣ በተለይም የዓለም የሥራ ድርጅት አባል መሆን፣ የሠራተኛ ን መብት ለመጠበቅ ግዴታ የሚያስከትል ቢሆንም ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ሠራተኞችን መብት ለማስጠብቅ ደንብ አላወጣችም፡፡

አልጋ ወራሹ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ፣ የአገራቸውን አስተዳደር ሌሎች አገሮች ከደረሱበት የመንግሥት አስተዳደር ደረጃ ትይዩ ለማድረግ በነበራቸው ፍላጎት፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕገ መንግሥት ማውጣታቸው ሥር ነቀል ለውጥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕገ መንግሥቱ መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን በተመለከተ ድንጋጌዎች ቢኖሩትም፣ የሠራተኞችን መብት የሚጠብቁ አንቀጾችን አላከተተም፡፡

## የጠላት ወረራ ዘመን (1928-1933)

ጣልያን ኢትዮጵያን ወርራ በነበረችበት አምስት ዓመታት ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከቀድሞው በበለጠ መስፋፋታቸው አሌ የሚባል አይደለም፡፡ ጠላት ለጦሩና ለሰፋሪ ዜጎቹ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ለማምረት ሲል የምግብ፣ የመጠጥ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የሲሚንቶ፣ የሸክላ፣ የእንጨት መሰንጠቂያዎች እና የመሳሰሉትን የማምረቻ ድርጅቶች አቋቁሟል፡፡ አገሪቱንም ለመቆጣጠር አውራ ጎዳናዎች በብዛት መቀደዳቸው ለብዙ ሰዎች የሥራ እድል ቢከፍትም የሠራተኞች መብት ግን አልተጠበቀም፡፡ በማኅበር የመደራጀት መብትም አልነበራቸውም፡፡ ለዚያውም የጣልያን የቅኝ አገዛዝ መርህ በዘር ልዩነት ላይ የተመሰረተ ስለነበር፣ ሠራተኛው ሰብእናው ይገሰስ፣ መብቱም ይደፈር ነበር፡፡

በዚያን የወረራ ዘመን ኢንዱስትሪ በዓይነትና በቁጥር ቢጨምርም፣ በአሠሪና በሠራተኛ ግንኙነት ረገድ ከቁጥር የሚገባ ጠቃሚ ተሞክሮ ትቶ አላለፈም።

## ጠላት ድል ከሆነ በኋላ[1]

ጣልያን ድል ሲሆን ቀድሞ አዲስ አበባን የተቆጣጠረው የእንግሊዝ የጦር ሠራዊት ነበር። ጦሩ በአጋጣሚው ተጠቅሞ፣ ቁጥራቸው በእራሱ በእንግሊዝ መንግሥት ታውቆ፣ ያልተመዘገቡ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተነቅለው ወደ እንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ወደ ኬንያና ወደ ታንዛኒያ ወስዷል። ኤርትራም በእንግሊዝ ጦር ስር ስለነበረች፣ ወደዚያም የተላኩ ድርጅቶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ አንድ ማተሚያ ቤት ከሐረር ተነቀሎ ተወስዶአል። እንዲሁም አንድ የቃጫ ፋብሪካ፣ በመካሄድ ላይ ለነበረው ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይጠቅማል በሚል ሰበብ፣ ከአዲስ አበባ ወደ ታንዛኒያ ተልኳል። የደቡብ አፍሪካም ጦር አዲስ አበባን ከእንግሊዝ ጦር ጋር አብሮ ይዞ ስለነበር፣ እርሱም አንድ የምህንድስና ተቋም ነቅሎ ወስዷል። በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በእንግሊዝ ጥበቃ ሥር እንደነበር የሚቆጠርበት ሁኔታ ስለነበር፣ የንብረት ዘረፋውን ለመቋቋም ሮሮ ከማሰማት ያለፈ ጉልበትና ተሰሚነት አልነበረውም። ቢሆንም፣ ሮሮ ስለበዛ የጠላት ንብረትን እየመረመረ ለጦርነት የሚውለውን እንዲለይ፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና የእንግሊዝ ጦር ወኪሎች የሚገኙበት፣ የጋራ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደረገ። የኮሚቴው አባላት አብዛኛዎቹ እንግሊዞች ስለነበሩ፣ ዘረፋውን ኢትዮጵያውያኑን በማሳተፍ፣ ሕጋዊ ከማስመሰል ባሻገር፣ ሊያስቀረው አልቻለም። በዚህ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የራሱ ህልውና እንኳን አስጊ ሁኔታ ላይ ስለነበር፣ የጠላት ንብረት ዘረፋውን ለመግታት የሚችልበት ኃይል አልነበረውም።

ከእንግሊዝ ጦር ዘረፋ የተረፉት ተቋማት ነበሩ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ መሰረት የሆኑት። እነዚህን በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች የተሰራጩትን ድርጅቶች መንግሥት በባለቤትነት ማስተዳደር ስለነበረበት፣ የሠራተኞች ማስተዳደር ጉዳይ ለመጀመሪያ ጊዜ በቀጥታ ይመለከተው ጀመር፤ ስለሆነም፣ የፋብሪካዎች መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 58/1936 በ1936 ዓ.ም. አወጣ። አዋጁን የማስፈጸም ኃላፊነትና ሥልጣንም ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጠ።

አዋጁ ፋብሪካዎች ስለሚሰሩበት ሁኔታና በውስጣቸው የሚተከሉት መሣሪያዎች በሠራተኞች ላይ አደጋ እንዳያደርሱና ለጤናቸውም ጠንቅ እንዳይሆኑ መመሪያ ማውጣትና በተግባር መተርጐማቸው ላይ ያተኮረ ነበር። በተጨማሪም የሥራ ሰዓትንና ሌሎችንም የሥራ ሁኔታዎችን በደንብ እንዲወስን ለሚኒስቴሩ ሥልጣን ቢሰጠውም፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ በ1952

[1] ለተጨማሪ ንባብ፣ የሚከተለውን መጽሀፍ ይመለከቷል፦ ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፣ *ኢትዮጵያና ብሪታኒያ:የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ1798 -1966 ዓ.ም.* (አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣1999)

ዓ.ም. እስከ ወጣበት ድረስ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ምንም ዓይነት ደንብ አላወጣም::[2] የፋብሪካዎች ቁጥር እየጨመረ ቢሄድም፣ የሠራተኞችን የሥራ ሁኔታዎች የሚደነግጉና የሥራ ክርክሮች የሚፈቱበት ሥርዓት በማቋቋም ረገድ ለ16 ዓመታት ያህል ምንም ዓይነት እድገት አልታየም:: ይህም ሁኔታ የሚያሳየው፣ የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነት በኢኮኖሚ እድገት ላይ ያለውን ወሳኝ ሚና አለመረዳት፣ ወይም አብዛኞቹ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ወይም በከፊል የመንግሥት ስለነበሩና መንግሥትም የአሠሪንና የመንግሥትን ተግባሮች አጣምሮ በመያዙ ከጥቅም ግጭት የተነሳ ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠት ነው፣ የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል::

ይሁንና፣ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች አስተዳደር ጉዳይ ትልቅ መሰረት የጣለው የፍትሐ ብሔር ሕግ በ1952 ዓ.ም. ስለወጣ ከዚህ ቀጥለን እናየዋለን::

## የፍትሐ ብሔር ሕግ የአሠሪዎችንና የሠራተኞችን መብቶችና ግዴታዎችን እንዴት እንደደነገገ

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ፣ በ1936 ዓ.ም. ታውጆ እስከ 1952 ዓ.ም. ድረስ በሥራ ላይ የዋለው እና ስድስት አንቀጾች ብቻ የያዘው የፋብሪካዎች አዋጅ ይዘት ዝርዝርነትና ጥልቀት ይጐድለዋል። በዚህ ላይ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የአዋጁን ዓላማ ተከትሎ ዝርዝር ደንቦች ባለማውጣቱ የሠራተኞችን መብት በማስጠበቅና መልካም የኢንዱስትሪ ግንኙነት እንዲሰፍን በማድረግ በኩል የሚገባውን ያህል አላደረገም::

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመልካም የኢንዱስትሪ ግንኙነት መሰረት የጣለው የፍትሐ ብሔር ሕግ ነው::[3] በዚህ ሕግ፣ አገልግሎት መስጠትን የሚመለከቱ ውሎች፣ ከቁጥር 2512-2597 ድረስ ያሉት፣ የተዋዋዮችን (የአሰሪና የሰራተኛ) መብቶችንና ግዴታዎችን ደንግጓል::[4] ድንጋጌዎቹ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግንኙነት መሰረት ጥለዋል:: ዐዋጁ የጌታና የሎሌ ግንኙነት የነበረውን በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ተክቶታል:: በተለይ በአሠሪው መልካም ፈቃድና ችሮታ ይተዳደር የነበረው ሠራተኛ ከአሠሪው ጋር በእኩልነት ደረጃ መብቱን የሚያስጠብቅበትና ግዴታውንም የሚፈጽምበት ሁኔታ ተመቻችቶለታል::

ስለውል አፈጻጸም፣ የኅብረት ስምምነት ስለማድረግ፣ ስለ ደሞዝ፣ ስለ ልዩ ፈቃዶች፣ በሥራ ጊዜና ቦታ ስለሚደርስ አደጋ፣ በሙያ ሥራዎች ላይ ስለሚደርስ በሽታ፣ ውልን ስለማቋረጥ፣ ከሥራ በመሰናበት ስለሚከፈል ካሣ፣ ስለ ሥራ ማቆም አድማ፣ ስለ ሥራ መዝጋትና ስለ ሌሎችም የሥራ ሁኔታዎች የወጡት ዝርዝር ድንጋጌዎች የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነትን

---

[2] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት፣ *የፍትሐ ብሔር ሕግ- ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. (ነጋሪት ጋዜጣ ቁ.* ፯ ፲፱፶፯ ዓ.ም. ፣ በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ፣ 1952)

[3] *ዝኒ ከማሁ*::

[4] *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ 531-549 ይመለከቷል::

*ለማሻሻል የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዐዋጁ መደበኛውን የቀኑንና የሳምንቱን የሥራ ሰዓቶች አለመወሰኑ፣ ሠራተኛውን ለብዝበዛ አጋልጦታል፡፡ በሌላ በኩል፣ የኢንዱስትሪ ሰላም ለማስፈን መሰረት የሚሆነው የሥራ ክርክር የሚፈታበት ሥርዓት ባለመቋቋሙ፣ በሥራ ውል ምክንያት የሚነሱ ክርክሮች እንደሌላው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ ሆነዋል፡፡ ሌላው የዐዋጁ ግድፈት፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይን የሚከታተልና የሚያስፈጽም የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አለማቋቋሙ ነበር፡፡ በተጨማሪም፣ ሠራተኞች በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 406[5] መሰረት የሞያ የሥራ ማኅበር (ሰንዲካ)* (Labour/Trade Union) *ማቋቋም ቢችሉም፣ ህጉ የማህበሩን ተግባራት ስላልደነገገና አሠሪውም ማህበሩን አውቆ ከእርሱ ጋር ስለ ሥራ ሁኔታዎች እንዲደራደር የሚያስገድደው ድንጋጌ ባለመኖሩ፣ የኅብረት ስምምነት እንዳይዳብር ማነቆ ሆኖአል፡፡ በዚህ ላይ፣ ሠራተኞች በሥራ ሁኔታዎች ላይ የሚያነሱትን ክርክር አሠሪው ለመፍታት ከቅን ልቦና ጉድለት ፈቃደኛ ባይሆን፣ ሠራተኞች በሥራ ማቆም መብት በመጠቀም የሚያስገድዱበት መብት ስለሌለ፣ ሁኔታው አምባገነን ለሆነ አሠሪ አመቺ ነበር፡፡*

*በኢንዱስትሪ ዓለም አሠሪዎችና ሠራተኞች በማህበር ተደራጅተው የሚያደርጉት የጋራ ውይይት የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰ ከፍተኛና ወሳኝ ሚና እንዳለው የተረጋገጠ ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ቁጥር 406 የሠራተኞችና የአሠሪዎች ማኅበራት መቋቋምን ቢፈቅደም ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተግባሮቻቸው፣ መብቶቻቸውና ግዴታዎቻቸው ስለአልተገለጹ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በቁጥር 49/1954 ዓ.ም. የወጣው ድንጋጌ (ኋላ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ ቁጥር 210/1956 ዓ.ም.) በሥራ ላይ እስከ ዋለ ድረስ የተቋቋሙት የሠራተኞች ማኅበራት የመረዳጃ ማኅበራት ሁነው ከመንቀሳቀስ ያለፈ በሥራ ክርክር ከአሠሪዎች ጋር ስለ ሥራ ሁኔታዎች ተደራድረው የኅብረት ስምምነት ያደረጉበት አጋጣሚ አልነበረም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የነበረው ጉድለት በአሠሪና በሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ እንዴት እንደተሟላ ወደፊት የምናየው ይሆናል፡፡*

## *የኢንዱስትሪ መስፋፋት የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይን ለመደንገግ አስገዳጅ ስለመሆኑ*

*ከጠላት በተወረሱትና በግለሰቦች ሥር በሚተዳደሩት ኢንዱስትሪዎች ላይ አዳዲስ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መጨመራቸውና በ1950ዎቹ አሰርት የቅኝ ግዛት የነበሩ የአፍሪካ አገሮች ነፃ ወጥተው በመንግሥት መስተዳድርና በሠራተኛ ሕግ ረገድ ለውጥ በማሳያታቸው፣ በኢትዮጵያ የመንግሥትና የኢንዱስትሪ ሠራተኞች አስተዳደር ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማድረጋቸው አልቀረም፡፡ ሌላው ቢቀር፣ የውጭ አገር መዋዕለ ነዋይ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ለመሳብ፣ ነፃ ከወጡ አገሮች የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ሕጎች*

[5] *ዝኒ ከማሁ፡፡*

ጋር የሚስተካከል ሕግ ማውጣት፣ የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ የሚጠይቀው ነበር:: በተጨማሪም የ1953 ዓ.ም. የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ብዙ የአስተዳደር ቅሬታዎችን አደባባይ ስላወጣቸው መንግሥት በየሥራ መስኩ ከጊዜው የእደገት ደረጃ ጋር የሚመጣጠኑ ለውጦች ማድረግ ግድ ሆነበት:: ከእነዚህ ሁኔታዎች ይበልጥ፣ መንግሥት በ1949 ዓ.ም. የአምስት አመት የኤኮኖሚ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ጀምሮ ስለነበረ፣ የእድገት ማነቆ የሆኑትን ማስወገድ የአገሪቱን የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል በሚገባ ለመጠቀም አስፈላጊነቱ ግንዛቤ አግኝቶ ነበር:: በዚህ ላይ የሠራተኛው ብዛት እየጨመረ ስለሄደና መብቱ እንዲከበርለት የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች መስተናገድ እንደሚገባቸው መንግሥት ስለተገነዘበ፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይን በ1954 ዓ.ም. የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር በኃላፊነት እንዲመራው አደረገ:: ሚኒስቴሩም የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት፣ አንድ ንዑስ ክፍል አቋቁሞ፣ በማህበራዊ ጉዳይ በማስተርስ ዲግሪ የተመረቁ ሁለት ባለሙዎችን ከጥቂት ረዳቶች ጋር መደበ:: በተጨማሪም ከዓለም የሥራ ድርጅት አንድ የሕግ ባለሙያ እንዲመደብ አድርጐ፣ ቀደም ሲል በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጽፎ የነበረውን የአዋጅ ረቂቅ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና ከዓለም የሥራ ድርጅት ቃል ኪዳኖች ጋር በማገናዘብ የተሻሻለ የአሠሪና የሠራተኛ አዋጅ ረቂቅ እንዲያዘጋጅ አደረገ::

## የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅና ደንቦች ስለ መውጣታቸው

የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቋቋመው ክፍል ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ አገሮችን ተሞክሮዎችና መሰረታዊ[6] ከሚባሉት የዓለም የሥራ ድርጅት ቃል ኪዳኖች፣ በተለይም Convention No. 87 (Concerning Freedom of Association and the Protection of the Right to Organize) እና Convention No. 98 (Concerning the Application of the Principles of the Right to Organize and Bargain Collectively) መሰረት አድርጎ፣ ያረቀቀው የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ድንጋጌ ቁጥር 49/1954 ዓ.ም. ቀርቶ፣ ምክር ቤቱ ከእረፍት ተመልሶ ሥራውን ሲጀምር ድንጋጌው ሥሙ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ ቁጥር 210/1956 ተብሎ ተሻሽሎ ተተካ:: ከዚህ ቀጥሎ በፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ያለተካተቱትን የሥራ ሰዓትና የትርፍ ሰዓት ክፍያን እንዲሁም የሕዝብ በዓላትን፣ የዓመት ፈቃድንና ሌሎችንም የሥራ ሁኔታዎችን በማሻሻል ስለሠራተኛ የሥራ ሁኔታ የ1957 ዓ.ምን ደንብ (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 302/1957 ዓ.ም.) አወጣ::

---

[6] መሰረታዊ የተባሉት ቃል ኪዳኖች የሚከተሉት ናቸው:- Convention No. 87 (Freedom of Association and the Right to Organize), Convention No.98 (the Right to Organize and Bargain Collectively), Conventions No.110 and 111(Concerning Discrimination in Employment and Occupation), Conventions No. 29 and 105 (Forced Labour), Conventions 138 and 182 (Child Labour).

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ መሠረት የጣለ፣ የዓለም የሥራ ድርጅትን መሠረታዊ የሠራተኞች መብቶችን ጠብቆ የተዘጋጀ፣ ሕግ ነበር፡፡ የዐዋጁ ዋና ዓላማ በማኅበር የተደራጁ አሠሪዎችና ሠራተኞች ከመንግሥት ጋር በመመካከርና በቡድን በመሥራት፣ የኢንዱስትሪ ሰላም የሚያሰፍኑበት፣ የሠርቶ አዳሪው ሕዝብ መብቱና ሰብዕናው ተጠብቆ ምርታማነቱ የሚዳብርበት፣ ስርዓት ለመዘርጋት ነበር፡፡ የሥራ ሁኔታዎችንም በሚመለከት መንግሥት እንደሁኔታው አነስተኛውን ወይም ከፍተኛውን የሥራ ሁኔታ መነሻ ወይም መድረሻ ሲወስን፣ አንድ አሠሪ ወይም የአሠሪዎች ማኅበር ከሠራተኞች ማኅበር ጋር በመደራደር በኅብረት ስምምነት የሥራ ሁኔታዎች የሚያሻሽሉበት ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የኅብረት ስምምነት ለማድረግ የሚችሉ ወገኖች የሚደራደሩባቸውን ጉዳዮች፣ ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ወዘተ... በግልጽ በማስቀመጡ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበር ኃላፊነትና ተግባር ግልጽ ሆኗል፡፡

ሌላው የዐዋጁ ትልቅ አስተዋጽኦ የሥራ ክርክር ሳይጓተት የሚወሰንበት ስርዓት ማቋቋሙ ነበር፡፡ ማናቸውንም የሥራ ክርክር፣ መጀመሪያ አሠሪውና የሠራተኞቹ ማኅበር በሰላምና በመግባባት በውይይት እንዲፈቱት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና በማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ በእርቅ እንዲወሰን ይደረጋል፡፡ በእርቅ ክርክሩን መቁረጥ ካልተቻለ፣ የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ወይም ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ያቀርባል፤ ቦርዱም በፍሬ ነገሩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ የቦርዱ ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት የሚለው ወገን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ችሎት ይግባኝ የማለት መብት ሲኖረው፣ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የዓለም የሥራ ድርጅት የሚከተለውን የሦስትዮሽ ትብብርን መሠረት አድርጎ የተቋቋመ ሲሆን በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አቅራቢነት አምስት አባላት በንጉሠ ነገሥቱ የሚሾሙበት ነበር፡፡ ከአባለቱም ሦስቱ በመንግሥት፣ አንዱ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ አንዱ ደግሞ በኢትዮጵያ የአሠሪዎች ማኅበር የሚመረጡ ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥት የአሠሪና የሠራተኞች ወኪሎች፣ በተለይ ሠራተኞች በሥራ ሁኔታዎችና ተገቢ ባልሆኑ የሥራ አፈጻጸሞች ላይ፣ በእኩልነት ተቀምጠው ለመዳኘት መብቃታቸው፣ በኢንዱስትሪ ግንኙነት ሥር-ነቀል ለውጥ ነበር፡፡

ሌላው በኢንዱስትሪ ግንኙነት መሠረታዊ ለውጥ የተደረገው ሠራተኞች በማኅበር እንዲደራጁ መፈቀዱ ነው፡፡ በ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47፣ «ማናቸውም የኢትዮጵያ ዜጋ በሕገ መንግሥቱ መሰረት ማናቸውንም ዓይነት ሥራ እየሠራ ለመኖር ማናቸውንም ዓይነት ማኅበር ለማቋቋምና በማናቸውም ማኅበር አባል ለመሆን መብት አለው፡፡» በማለት የደነገገ ቢሆንም ስለአፈጻጸሙ በግልጽ የተመለከተ መመሪያ ባለመውጣቱ፣

ሠራተኞች ሕገ መንግሥቱ በሰጣቸው መብት ለመጠቀም አልቻሉም:: በሕገ መንግሥቱ መሠረት የወጣው የ1952 ዓ.ም. የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 406፣ የሙያ ሥራ ማኅበር (ሰንዲካ):-

(፩) የአባሎቻቸውን የገንዘብ ጥቅም ለመከላከል ወይም ላንድ ለተወሰነ የሞያ ሥራ እንደራሴ ለመሆን የተቋቋሙ ስብሰባዎች፤ የሙያ ሥራ ማኅበሮችን (ሰንዲኮችን) በሚመለከቱ ልዩ ሕጎች የሚመሩ ናቸው::

(፪) እነርሱን የሚመለከቱ ልዩ ሕጎች ባይኖሩም እነዚህ ስብሰባዎች እንደ ተራ ማኅበሮች ተገምተው በዚህ ምዕራፍ ሕጋውያን ደንቦች የሚመሩ ይሆናሉ:: በማለት ይደነግጋል::[7]

ይህ ድንጋጌ የሠራተኞች ማኅበሮች ሕጋዊ ተግባራት ለማከናወን እንዲችሉ በቂ ድጋፍ ስላልሰጣቸው፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ እስከወጣበት ድረስ፣ በዚህ ድንጋጌ የተመዘገቡ ማኅበራት በመረዳጃ ማኅበር ስም ከመንቀሳቀስ ያለፈ በአሠሪዎች ታውቀው የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ያስከበሩበት ሁኔታ አልነበረም:: የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ ማኅበራት የሚመዘገቡበትንና ተግባራቸውን በግልጽ በማውጣቱ፣ እንዲሁም ዐዋጁን የሚያስፈጽም መስሪያ ቤት ተለይቶ ኃላፊነቱን እንዲይዝ በመደረጉ በአጭር ጊዜ ውስጥ አብዛኛው ሰርቶ አደር በማኅበር ለመደራጀት በቅቷል::

## የኅብረት ድርድርና ስምምነት ስለማድረግ

የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበሮች ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2516፣ «አሠሪዎች ወይም የአሠሪዎች ስብሰባ ባንድ ወገን፤ የሠራተኞች ስብሰባ በሌላ ወገን፤ ከኅብረት ስምምነት ውስጥ እነዚህኑ የሚመሩ የእያንዳንዳቸው የሥራ ውል የሚያደርጉበትን ሁኔታዎች መወሰን ይችላሉ::»[8] በማለት መሠረቱን ቢጥልም ሕጉን የሚያስፈጽም አካል ተለይቶ ባለመታወቁና የአሠሪና ሠራተኛ ማኅበራት ለኅብረት ድርድርና ስምምነት እንግዳ በመሆናቸውና መብታቸውን በሚገባ ባለመረዳታቸው በዚህ ረገድ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ እስከታወጀበት ድረስ አንድም የተመዘገበ የሕብረት ስምምነት አልነበረም::

መሰረታዊ የሥራ ሁኔታዎች (minimum labour conditions) በፍትሐ ብሔር ሕግ ባለመወሰናቸው፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ በሥራ ላይ መዋል ሲጀምር የኅብረት ስምምነት ለማድረግ ስላላመቸ፣ ተጨማሪ ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 302/1957 ደንብ ወጣ:: ደንቡ ስለቀኑና የሳምንቱ የሥራ ሰዓቶች፣ የሳምንቱ የእረፍት ቀን፣ የሕዝብ በዓላት፣ ልዩ ፈቃዶች፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያና ስለሌሎችም የሥራ ሁኔታዎች እንደ አግባቡ መነሻውን ወይም መድረሻውን ስለ ወሰነ፣ የኅብረት ስምምነት ድርድር

[7] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 86

[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 532::

ለመጀመር አመቻ:: ተዋዋዮች ወገኖች መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎችን ለሠራተኛው በሚጠቅም መልኩ በድርድር የሚያሻሽሉበት ሥርዓት ተዘረጋ::

የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ በአንድ ተቋም ሥር ተደራጅቶ አንድ ወጥ አመራር እንዲኖረው የዓለም የሥራ ድርጅት ይገፋበት ስለነበር፣ ሐሳቡ በብዙ መንግሥታትም ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ፣ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ ወይም የአሠራር ነፃነት ተሰጥቶት በኤጀንሲ መልክ መዋቀር ስላለበት፣ ኢትዮጵያም የዓለም የሥራ ድርጅት አባል እንደመሆኗ ይኸንኑ የአደረጃጀት ስልት መከተል አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት (Employment Administration) በ1954 ዓ.ም ተቋቋመ::

## የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት መቋቋም

የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ ጥናት ሲደረግ ሥራውን የሚመራ ተቋም፣ በአጠቃላይ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይን ማለትም የኢንዱስትሪ ግንኙነት፣ የሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር እና የሥራ ሁኔታዎች መቆጣጠሪያ አገልግሎት ተሟልተው በተጓዳኝ በአንድ አመራር ሥር ካልተጠቃለሉ፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ እንዳለፉት ዘመናት አለውጤት መክኖ እንዳይቀር የሚያስችል የአሠራር ነፃነት ያለው መሥሪያ ቤት ማቋቋም አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በትዕዛዝ ቁጥር 26/1954 ተቋቋመ:: መሥሪያ ቤቱ የአስተዳደር ነፃነት ኖሮት በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ተቆጣጣሪነት የራሱ በጀትና ሠራተኞች ተመደቡለት::

የሥራ ጉዳይ (employment) ትኩረት ያልተሰጠው የሥራ መስክ ነበር:: ሆኖም የኢንዱስትሪ ማደግና መስፋፋት እንዲሁም የመንግሥትም አስተዳደር እያደገ ሲሄድ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በሙያ ዓይነትና በመጠን ተለይቶ ባለመታወቁ ኢኮኖሚውና አስተዳደሩ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ይገጥማቸው ጀመር:: በአንድ በኩል እጥረት ሲታይ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የተማረ የሰው ኃይል ጭምር ሥራ አጥ መሆኑ፣ የሰው ኃይል ፍላጎት ከትምህርትና ከማሰልጠኛ ተቋማት ውጤት ጋር አለመገናዘባቸውን በገሀድ አወጣው:: በዚህ ላይ አገሪቱ በአምስት ዓመት ፕላን መሥራት ጀምራ ስለነበር የሰው ኃይል ስልጠናንና የኢኮኖሚውን ፍላጎት ማጣጣም ግድ ሆነ::

የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ዋና ዓላማ፣ የኢኮኖሚውንና የአገር አስተዳደሩን የሰው ኃይል ፍላጎት ያገናዘበ የትምህርትና የሥልጠና ሥርዓት ለመጣል፣ የሥራ አጥነትን ችግር ለማቃለልና ለማስወገድ የሚቻልበትን ዘዴ ለማመልከት፣ የሥራ ገበያውን (employment/labour market) ለማስተካከል፣ የሚረዱ መረጃዎች መሰብሰብና ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ማቅረብ ነበር:: እነዚህንም ተግባሮች ለማከናወን ቁጥራቸው ከአስር በላይ ለሚሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቋቋሙ በቅድሚያ የሚስፈልጋቸውን የሰው ኃይል፣ የሙያ ስብጥርና ብዛት ለሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እንዲያስታውቁና የሠራተኞች ምልመላቸውንም በተቻለ መጠን ከመንግሥት የአሠሪና የሠራተኛ ማገናኛ ጽሕፈት ቤቶች ወይም ከመንግሥት ፈቃድ ከተሰጣቸው የግል የአሠሪና

የሠራተኛ ማገናኛ ጽሕፈት ቤቶች አማካይነት እንዲያደርጉ ማበረታታት ነበር። እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ፈቃድ ስለማያስፈልጋቸው፣ በትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ኢትዮጵያውያን ሊሠሯቸው የሚችሉ የሥራ መደቦች በውጭ አገር ዜጎች መያዛቸው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ ስለነበር፣ በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው ይህን የተዛባ ሁኔታ ለማስተካከል፣ በመጀመሪያ ደረጃ ማናቸውም የሥራ እድል ተፈላጊው የትምህርት ችሎታና የሥራ ልምድ ላላቸው ኢትዮጵያውያን ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ማድረግ የመንግሥት ግዴታና ኃላፊነቱ ስለሆነ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የመስጠትና የመንፈግ ሥልጣን ተሰጠው።

የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት መሠረታዊ ዓላማው አሠሪው ለሚፈልገው የሥራ መደብ ተፈላጊው ትምህርት/ሥልጠና፣ ችሎታና የሥራ ልምድ ያለው ዜጋ ከአገር ውስጥ ሲጠፋ ብቻ ነው። አሠሪው ይህንን ግዴታውን መወጣት የሚችለው በመገናኛ ብዙኃን ማስታወቂያ በማውጣት ከሥራ ገበያው የሚፈልገውን ሠራተኛ ለማግኘት አለመቻሉን ሲያረጋግጥ ነበር። የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤትም የሥራ ፈቃዱን ሲሰጥ አሠሪውን የውጭ አገሩን ዜጋ የሚተካ ኢትዮጵያዊ ለማሠልጠን ግዴታ አስገብቶ ነበር። ይህም ሥርዓት ለብዙ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል ከመክፈቱም በላይ እንደ ሼል ኢትዮጵያ ለመሳሰሉ ተራማጅ ድርጅቶች በውጭ አገር ዜጎች የተያዙ የሥራ መደቦችን በኢትዮጵያውን የሚተኩበት እቅድ (Ethiopianization Programme) አውጥተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለብሔራዊ ፕላንና ለማሠልጠኛ ተቋማት የሚጠቅሙ መረጃዎች መሰብሰብና ተንትኖ ለሚመለከታቸው ወገኖች ማቅረብ ከሥራ ኃላፊነቱ ዐቢይ ክፍል ስለነበር ኢንዱስትሪዎች በብዛት በሚገኙባቸው ከተሞች፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና በአሥመራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመክፈት፣ አገልግሎት ማቅረቡን በስፋት ቀጠለ።

በሠራተኛ ጉዳይ ላይ የመንግሥት፣ የአሠሪዎችና የሠራተኛ ማህበሮች ወኪሎች እየተገናኙ ሀሳብ የሚለዋወጡበት መድረክ አስፈላጊ በመሆኑ ከማዕከል አንስቶ የሠራተኛ ጉዳይ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች የሥራ አማካሪ ኮሚቴዎች የሚቋቋሙባቸው ሁኔታዎች ተመቻችተው በሥራ ላይ ማዋል ተጀምሮ ነበር። ሌላው የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ያተኮረበት የሙያ ሥልጠና ነበር። በሥራ ላይ ለተሠማሩ ለአሠሪዎችና ለሠራተኞች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አስፈላጊ በመሆኑ በተለይ የአጭር ጊዜ የሙያ ሥራ ሥልጠና የሚሰጥበት አመቺ ሁኔታ ተመቻችቶ ነበር። በዚህ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ የነበረው የትናንሽ ድርጅቶች ባለቤቶች በቂ የሥራ አመራር ልምድና ችሎታ ሳይኖራቸው፣ በፍላጎት ብቻ ተነስተው፣ ያቋቋሟቸው ድርጅቶች ተገቢው የሥራ አመራር ክህሎት ቢታከልባቸው፣ ምርታማ ከመሆን አልፈው፣ ለብዙ ሠራተኞች ተጨማሪ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ስለሚችሉ፣ ይህንን የኋላ ቀርነት ሁኔታ ለመለወጥ በተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅትና (United

Nations Development Programme/UNDP) **በዓለም *የሥራ ድርጅት* እርዳታ በ1961 *ዓ.ም. የሥራ አስኪያጆች ማሠልጠኛ ድርጅት*** (Centre for Entrepreneurship and Management) **በአዲስ አበባ ተቋቁሞ በሥራ አመራር፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በግዥና ሽያጭ ወዘተ. የአጭር ጊዜ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት ከመስጠቱም በላይ ምርምርና ጥናት ያደርግ ነበር፡፡**

**ሌላው ችግር እንደሚታወቀው፣ አብዛኛው በኢንዱስትሪዎች የተሰማራው የሰው ኃይል ከገጠር የፈለሰና ተፈላጊው ክህሎት የሌለው ስለነበር፣ በአጭር ጊዜ ስልጠና የክህሎት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ፣ በዓለም *የሥራ ድርጅት* እርዳታ *የመርሀ ሙያ ማሰልጠኛ ድርጅት*** (Vocational Training Centre) **በአዲስ አበባ ተቋቁሞ ጠቃሚ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡**

**በአጠቃላይ *የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ* ቤት *መቋቋም የሥራ* ገበያውን ለማስተካከል፣ *ሥራና ሠራተኛን* በማገናኘት *የሥራ* ዕድል ለመፍጠርና *የሥራ* አጥነትን ችግር ለመፍታት፣ *የሙያ ሥ*ልጠና በመስጠትና *የሠራተኛ* ጉዳይ *መረጃዎችን* በማሰባሰብና ለተጠቃሚ ወገኖች በማቅረብ *መሠረት* ጥሏል፡፡ በተለይ አንደኛውና ሁለተኛው የአምስት ዓመት ብሔራዊ ፕላኖች በመረጃ እጥረት ረገድ የገጠማቸው ችግር ትልቅ ማነቆ እንደነበር የፕላኖቹ ግምገማዎች በማሳየታቸው፣ ለተከታታይ ፕላኖች በመረጃ እጥረትና ጥራት አኳያ የነበረውን ክፍተት ለማረም የጠቅላይ ስታትስቲክስ ጽህፈት ቤት ቢቋቋምም፣ በተለይ *የሠራተኛ ጉዳይ መረጃ*** (labour statistics) **ችግር አልተወገደም ነበር፡፡ ፕላኖቹም ሲዘጋጁ በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል በሙያ ደልድሎ የሚያሳይ ስታቲስቲክስ ካለመኖሩም በላይ በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማራውን የሰው ኃይል ብዛት የሚያሳይ መረጃ ጉድለት ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ *የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ* ቤት መቋቋም ይህንን ጉድለት ለማስተካከል እንደመሆኑ፣ በ1962 *ዓ.ም.* በኢትዮጵያ *ታሪክ ለመጀመሪያ* ጊዜ በኢንዱስትሪዎች የተሰማሩትን *ሠራተኞች* በሙያ ድልድል የሚያሳይ ጥናት** (A Survey of the Occupational Pattern of Employment in Ethiopia, 1962 E.C.) **ተደረገ፡፡ ጥናቱ ከመከላከያና ከደህንነት በስተቀር *የመንግሥት መሥሪያ* ቤቶችን፣ ማዘጋጃ ቤቶችን፣ በቻርተር የሚተዳደሩ *መሥሪያ* ቤቶችንና ከአስር በላይ *ሠራተኞች* የሚያስተዳደሩ ኢንዱስትሪዎችን የሚሸፍን ነበር፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በ70 ከተማዎች ሲሆን፣ 5000 ሕዝብ የሚገኝባቸውንም ከተሞች የሚጨምር ነበር፡፡ በጥናቱ የተሸፈኑት ተቋማት 272,432 *ሠራተኞች* የሚያስተዳድሩ ሲሆኑ፣ ከነዚህ ውስጥ 6,078 የውጭ አገር ዜጎች እንደነበሩ በጥናቱ[9] ተመልክቷል፡፡ ጥናቱ በመንግሥት አስተዳደርና በኢንዱስትሪ የተሰማራውን የሰው ኃይል በሙያ ደልድሎ ለማሳየት መሰረት ከመሆኑም በላይ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኋላም ለተተኩት መንግሥታት ትቶ ያለፈው ተሞክሮ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡**

---

[9] "A Survey of the Occupational Pattern of Employment in Ethiopia, 1962 E.C." Manpower Research and Statistics Section, Department of Labour, Ministry of National Community Development.

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሠራተኛ ጉዳይን በሁለንተናዊ ይዘቱ በማደራጀትና የኢንዱስትሪ ሰላም በማስፈን ምርታማነት እንዲጨምርና የሥራ ገበያው በሥርዓት እንዲመራ ለፖላንና ለስልጠና ግብአት የሚረዱ መረጃዎች አሰባስቦና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማቅረብን ትኩረት ሰጥቶት ነበር፡፡ ቢሆንም በልዩ ልዩ የሠራተኛ ጉዳይ ላይ የሚወጡ ሕግጋት፣ ደንቦችና ሌሎችም ሕጋዊ ውሳኔዎች መፈጸማቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም አስፈላጊነት ጉልቶ ስለታየ፣ በ1957 ዓ.ም. በሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ስር በትዕዛዝ ቁጥር 37/57 ዓ.ም. የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መሥሪያ ቤት (Labour Inspection Service) ሲቋቋም፣ በ1958 ዓ.ም. ደግሞ ስለ ሥራ ሁኔታዎች ደረጃ ስለመወሰንና ስለማስፈጸም የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 232/58 (A Proclamation to Provide for the Establishment and Enforcement of Labour Standards) ወጣ፡፡ እነርሱንም ከዚህ ቀጥለን እንዳስሳቸዋለን፡፡

## የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መሥሪያ ቤት መቋቋም

የሥራ ቦታዎች፣ የሥራ መሣሪዎችና አካባቢዎች ሠራተኛውን ለአካል ጉዳት፣ ለሙያ ሥራ በሽታና ለሞት እንዳያጋልጡት የሚቆጣጠር ክፍል በ1936 ዓ.ም. በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውስጥ እንደነበር ቀደም ሲል መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ አንድ ወጥ በሆነ መልክ በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ በተቋቋመው በአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መሥሪያ ቤት ተጠቃሎ ነበር፡፡ መሥሪያ ቤቱም የሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች፣ ደንቦች፣ የኅበረት ስምምነቶቹና ውሳኔዎች መፈጸማቸውን እንዲሁም የሥራ ቦታዎችና በውስጣቸውም የሚገኙት ወይም የተተከሉት መሣሪያዎች በሠራተኞች ላይ ያካል ጉዳት፣ የሙያ ሥራ በሽታ ወይም የሕይወት እልፊት እንዳያስከትሉ መቆጣጠር ኃላፊነቱ ነበር፡፡ መንግሥት መሥሪያ ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በሚገባ ለመፈጸም የሚያስችለው በጀትና የሰው ኃይል መድቦለት ነበር፡፡ መንግሥት አንድ ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት በማቋቋሙ አሠሪዎችና ሠራተኞች ሕግጋትን፣ ደንቦችንና ኅብረት ስምምነቶችን አክብረው ተልዕኳቸውን በማድረስ ለአገር ልማትና ብልጽግና የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ ለአሠሪና ለሠራተኛ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶት እንደነበር ያሳያል፡፡

የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መሥሪያ ቤት እራሱን እንዳደራጀ በ1958 ዓ.ም. ስለ ሥራ ሁኔታዎች ደረጃ አወሳሰንና አፈጻጸም ያዘጋጀው የሕግ ረቂቅ ታወጀ፡፡ ዐዋጁ የበላይ መሥሪያ ቤቱን (የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን) የሥራ ሁኔታ፣ የአማካሪ ቦርዱን እና የራሱን የተቆጣጣሪውን መሥሪያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት፣ እንዲሁም የተቆጣጣሪዎቹን ተግባራት ለይቶ በማያሻማ መልክ ማስቀመጡ የሙያ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት አስችሎታል፡፡ የአሠሪዎችንም ኃላፊነት ከዚያ ቀደም

ባልተለመደና ባልታወቀ መልክ ዘርዝሮታል። ከነዚህም መካከል አደጋ ስለመከላከል ደንግጓል፤ አደጋ ሲደርስ ወዲያው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መሥሪያ ቤት የማስታወቅና ለሠራተኛውም አደጋንና የሙያ ሥራ በሽታን የሚሸፍን መድን እንዲገባ ያስገድደዋል። በተጨማሪም፣ አካለ መጥን ያላደረሱ ልጆች የሚቀጠሩበት የሥራዎች ዓይነትንና የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከት ልዩ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ የአሠሪዎች ግዴታ ሆኖ ተደንግጓል። ዐዋጁ ያከተታቸው ጉዳዮች የዓለም የሥራ ድርጅት ያወጣቸው መስፈርቶችና መመሪያዎች ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው የተዘጋጁ በመሆናቸው የኢትዮጵያን የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ሕግጋትን በማስፈጸም ረገድ ያለውን አቅም ከሌሎች በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ አገሮች አፈጻጸም ጋር በአቻ ደረጃ አስቀምጦታል። በኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ የተሰማራው ሠራተኛ ከአፍሪካ አገሮች ጋር እንኳ ሲወዳደር አነስተኛ[10] መሆኑና ስርጭቱም በአመዛኙ በአዲስ አባባ፣ በአሥመራና በድሬድዋ ላይ መከማቸቱ ቁጥጥር ለማካሄድ አመቺ ነበር።

የዐዋጁ ሌላው ጠንካራ ጎኑ፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ሕጎች ሲረቀቁና የወጡትም በሥራ ላይ ሲውሉ ስለሚያጋጥሙ የአፈጻጸም ችግሮች ሐሳባቸውን የሚገልጹበት መድረክ መፍጠሩ ነበር። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት የሥራ ክርክርን በመፍታትና የሥራ ገበያውን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መረጃዎች በመሰብሰብ፣ የኢንዱስትሪን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማርካት፣ የማሰልጠኛ ተቋማት የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርታቸውን ከሃገሪቱ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር ስለ ሚያጣጥሙበት ሁኔታ እንዲመክሩ በሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ኮሚቴ እንዲያገለግሉ ዕድል እንደተሰጣቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ከዚህ ቀጥሎ የአሠሪዎችና የሠራተኞች በማኅበራት የመደራጀት ሂደት ይመረመራል።

## አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበራት ስለ መደራጀታቸው

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ማኅበር የማቋቋም መብት ቢሰጥም የ1952 የፍትሐ ብሔር ሕግ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራትን ተግባርና ኃላፊነታቸውን ባለመግለጹና ተመዝግበው የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጥቅሞቻቸውን የሚያስጠብቁበት ሥርዓት ካለማቋቋሙም በላይ በተለይ የሠራተኞች ማኅበራትን እንደሌሎች የመረዳጃ ማኅበራት ስለቆጠራቸው በ1954 ዓ.ም. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ድንጋጌ እስከ ወጣ ድረስ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት አልነበሩም ማለት ይቻላል። ድንጋጌው እንደወጣ አሠሪዎችና (በተለይ) ሠራተኞች በማህበራት ለመደራጀትና ሕጋዊ እውቅና አግኝተው ለመመዝገብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። በሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤትም በኩል ድንጋጌውን (በኋላ ዐዋጅ ቁጥር 210/1956 ዓ.ም.) ለማስፈጸም ቀናነት ስለነበር፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው ከ60,000-70,000 የሚደርሱ አባላት የነበሯቸው 109 የሠራተኞች ማኅበራትና አንድ የአሠሪዎች

[10] ከዚህ ምእራፍ መጨረሻ የሚገኘውን ሠንጠረዥ 1 ይመለከቷል።

ማኅበር ተመዘገቡ፡፡ በ1966 ዓ.ም 80,000 አባላት የነበሯቸው 167 የሠራተኞች ማኅበራት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር አባላት ሆነው ነበር፡፡

ሕጉ የሚፈቅደው ከ50 በላይ ሠራተኞች ቀጥሮ በሚያስተዳድር የንግድ ወይም የማምረቻ ወይም የአገልገሎት ሰጪ ወይም በግንባታ ተቋም ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በማኅበር እንዲደራጁ፣ ከ50 በታች ሠራተኞች በሚገኙበት ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ደግሞ በተመሳሳይ የሥራ መስክ ከተሰማሩ ድርጅቶች ሠራተኞች ጋር ተደባልቀው ማኅበር እንዲያቋቁሙ ነው፡፡ በዚያን ዘመን የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከገጠር ፈልሰው ከመምጣታቸውም በላይ የመሃይምነቱም መጠን እስከ 95 በመቶ የሚደርስ ስለነበር ብዙዎች በማኅበር በመደራጀት መብታቸውን በሚገባ ተጠቅመውበታል ለማለት አያስደፍርም፡፡

ሌሎች በማኅበር መደራጀት ላይ ንቁ ተሳትፎ ያልነበራቸው ትንሽ በትምህርት ደረጃ ከሠርቶ አደሩ ከፍ ብለው የሚታዩ የአየር ትራንስፖርት፣ የባንክ፣ የመድንና የመሳሰሉ ድርጅቶች ሠራተኞች (White-collar workers) ነበሩ፡፡ ከሌሎች የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ጋር አንድ ግንባር ለመፍጠርም ሆነ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር አባል ለመሆን ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ዝንባሌ በሌሎችም አገሮች የሠራተኞች ማኅበራት እንቅስቃሴ የታየ ነበር፡፡ ለምሳሌ የ አሜሪካን የወዝ አደር ፌዴሬሽን ወይም American Federation of Labour (AFL) ክህሎት የሌላቸውን ሠራተኞች በማግለሉ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ኮንግሬስ ወይም Congress of Industrial Organizations (CIO) ተቋቋመ፡፡

## የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅህበራት መቋቋም

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት በመሥሪያ ቤት ወይም በኩባንያ ደረጃ ከተቋቋሙ በኋላ በ1955 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌደሬሽን ተመሠረተ፡፡ የማኅበሩም ዓላማ የሠራተኞች ማኅበራት እንዲደራጁ ማበረታታት፣ ለማኅበራት መሪዎችና ለአባላት ስለ ሠራተኞች ማኅበራት አስተዳደርና አመራር ትምህርትና የኅብረት ድርድር ሲደረግ የሙያና የሕግ አገልግሎት መስጠት፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሠራተኞችን በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች መወከል ነበር፡፡ ማኅበሩ እነዚህን የሙያ ችሎታ የሚጠይቁ አገልግሎቶች ለመስጠት ልምድና ዝግጅት አልነበረውም፡፡ ይህንንም ድክመቱን የሚሸፍኑለት አራት የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ቀጥሮ ሁለቱን ወደ አሜሪካን አገር በመላክ በኢንዱስትሪ ግንኙነት አስመርቆ በአገልግሎት ላይ አውሏቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር እንደተቋቋመ ራሱን ከማደራጀት ቀጥሎ ቅድሚያ የሰጠው ለሠራተኞች ማኅበራት መሪዎች ሥልጠና ነበር፡፡ የሥልጠና ፕሮግራሙን ለማካሔድ በሙያና በድርጅት አቋሙ ባለመጠናከሩ በርዕዮተ ዓለም ከሚመስለው ዓለም አቀፍ ነፃ የሠራተኞች ማኅበራት ኅብረት (International Federation of Free Trade Unions /ICFTU) ጋር በመተባበር ለ40

*የሠራተኞች ማኅበራት መሪዎችና ለራሱም የአመራር አካላት ጭምር በአዲስ አበባ በ1955 ዓ.ም. የስልጠና ፕሮግራም አካሂዷል። በተጨማሪም ከልዩ ልዩ ማኅበራት ለተውጣጡ ለ50 አባላት በሠራተኛ ማኅበራት ሥራ የሰባት ሳምንታት ስልጠና በማታ ሰጥቶአል። እንዲሁም በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ድጋፍ የዓለም የሥራ ድርጅት ለኢትዮጵያ ሠራተኞች መሪዎች (ለማኅበራት የአመራር አካላት) አባላት በአዲስ አበባ፣ በአስመራ፣ በድሬዳዋ፣ በባሕር ዳርና በሌሎችም ማኅበራት በተቋቋሙባቸው አካባቢዎች ስለ ማኅበራት ኃላፊነትና ግዴታ፣ ስለ ኅብረት ክርክርና ስምምነት፣ ስለ ሥራ ክርክርና ስለ ሌሎችም ጉዳዮች ትምህርት ሰጥቷል። በተከታታይ ከ800 ላላነሱ መሪዎችና አባላት የዓለም የሥራ ድርጅትም ሥልጠና ሰጥቷል[11]። ሥልጠናው የማኅበራት መሪዎችንና የአባላትን እይታ ከማስፋትና ኃላፊነታቸውንም ከማሳወቁም ባሻገር የሠራተኞች ማኅበራት መሃይምነትን ለማጥፋት በግምባር ቀደምነት መታገል እንዳለባቸው አስገንዝቧቸዋል።*

## *የመንግሥት፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ግንኙነት*

*የመንግሥት ባለሥልጣኖችና አሠሪዎች በሥራና በማኅበራዊ ኑሮ የሚገናኙበት መንገድ ስለነበር ተባብሮ ለመሥራት አዳጋች አልነበረም። እንግዳው ነገር የሠራተኞች ማኅበራት መሪዎች ከመንግሥት ሹሞችና ከአሠሪዎች ጋር በእኩልነት በሥራ ሁኔታዎች ላይ ሐሳብ ተለዋውጠውና ተከራክረው ስምምነት ላይ የሚደርሱበት መድረክ መፍጠር ነበረ።*

*መንግሥት የአሠሪና የሠራተኞች ወገኖችን የሚያቀራርቡና በጋራ የሚያሳትፉ ሕጎችና ደንቦች በማውጣት ብቻ ሳይወሰን ለኢንዱስትሪ ሰላም የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ አመራር መስጠት ነበረበት። ከሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር አንስቶ እስከ ተራ ሠራተኞች ድረስ ቀና አስተሳሰብና በጎ አመለካከት ስለነበር፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ግንኙነት እንዲሰምር ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግና የትርፍ ጊዜያቸውንም ሳይቀር በመሰዋት የሚያገለግሉ ዜጎች ነበሩ። ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚመለመሉት አብዛኛዎቹ የዩኒቬርሲቲ ምሩቃን በመሆናቸው፣ የኢትዮጵያ ሠራኞች ማህበርም የሙያ አገልግሎት እንዲሰጡት ምሩቃንን በመቅጠሩና የአሠሪዎች ማኅበርንም በዋና ፀሐፊነት የሚመሩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ስለነበሩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች ማኅበራት መካከል መግባባትና መልካም የሥራ ግንኙነት ፈጥረው ነበር።*

*ሆኖም በአንድ ወቅት፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር በሰርቶ አደሩ ላይ ብዙ በደል ደርሶበታል በሚል ሰበብ፣ ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ ውሳኔ አስተላለፈ። የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሥራ ክርክር ካለ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዐዋጅ መሰረት፣ አቤቱታቸውን ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ እንዲያቀርቡና በሕጋዊ መንገድ እንዲከራከሩ በቃልና በጽሑፍ ምክር ቢሰጥም፣*

[11] ILO, Report on Workers Education in Ethiopia, 1964.

አመራሩ ግትር አቋም በመያዙ የአድማ ውሳኔውን ለመለወጥ ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣ የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ መሥሪያ ቤት በጉዳዩ ጣልቃ ገባ። የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አስቀደሞ ሲከላከል የነበረው የሕዝብ ደህንነት ጣልቃ በመግባት ጉዳዩን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይወስደው ነበር። የደህንነቱ መሥሪያ ቤት የአድማው ውሳኔ እንዲነሳ ብቻ ሳይሆን የማኅበሩ ፕሬዝዳንት ስልጣኑን እንዲለቅ፣ ባይለቅ ግን አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ፣ አቋሙን ግልጽ አደረገ። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ የሥራ ክርክር መሆኑ ቀረና ፀጥታ የማስከበር ጉዳይ ሆነ። ማህበሩም የሕግ ድጋፍ ስላልነበረው፣ ወዲያው ለደህንነት ጥያቄ ሽብረክ አለ። ፕሬዝዳንቱ ሥራውን ካልለቀቀ እርምጃ እንደሚወሰድበት ተነግሮት ስለነበር፣ ሥራውን ለቀቀ፤ የሥራ ማቆሙም አድማ ተጨናገፈ። ማኅበሩ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ ሲወስን በሥራ ሰበብ ወደ አስመራ ሄዶ የነበረው የማኅበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ የፕሬዝዳንትነቱን ቦታ ያዘ። በጊዜው የነበሩ የሠራተኛ ማኅበራት የውስጥ ፖለቲካ ተመልካቾች፣ ፕሬዝዳንቱ ሥልጣን በሚፈልጉ የአመራር አካላት ተገፋፍቶ ከመንግሥት ጋር የማያስፈልግ ውዝግብ ውስጥ እንደገባ ይተቻሉ። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር መንግሥትን ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ለመፈታተን ያደረገው ከንቱ ሙከራ ትምህርት በመሆኑ፣ የነጉሠ ነገሥት መንግሥቱ ከስልጣን እስከተወገደበት ድረስ አሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ለሕግ ተገዥ ነበሩ።

በአሠሪዎችና በሠራተኞች ማኅበራት መካከል የነበረው ግንኙነት ከድርጅት ወደ ድርጅት ይለያይ ነበር። በትላልቅ ፋብሪካዎች፣ ማለትም በወንጂና በሸዋ የስኳር ፋብሪካ፣ በኢንዶ ኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ በድሬዳዋ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ በባህር ዳር የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ በስሚንቶ ፋብሪካዎች፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ በሼል ኩባንያና በሌሎቹም ትላልቅ ድርጅቶች፣ የሥራ ክርክሮች በመግባባትና በመቻቻል የሚፈቱበት ሁኔታ እየተለመደ ሄዶ ነበር። በአነስተኛ ድርጅቶች፣ በተለይ በሥራ አመራር ዕውቀት ማነስ የተነሳ፣ የግሪክ፣ የአርመን፣ የሕንድና የዐረብ ዜጎች፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን፣ በባለቤትነት የሚያካሄዱአቸው ድርጅቶች፣ ውስጥ የሠራተኞችን ወኪሎች ወይም መሪዎች በእኩልነት ተቀብለው ማነጋገሩን እንኳን እንደውርደት የሚቆጥሩ፣ ማኅበራትን ለማፍረስ መሪዎቹን የሚያጉላሉና የሚደልሉ ነበሩ። በሠራተኞችም በኩል ኃላፊነትንና ግዴታን ካለመረዳት የሚታየው ሥራን የማቀዝቀዝና የማቆም ሕገወጥ ድርጊት በሂደት መቃለል ጀምሮ ነበር። የኢንዱስትሪ ሰላምም አዘውትሮ የሚታወከው በአብዛኛው በአነስተኛ ድርጅቶች ውስጥ ነበር።

የወንጂና የሸዋ የስኳር ፋብሪካ በማኔጅመንት እና የሠራተኞች ማኅበር በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ሁኔታዎች ላይ ተደራድረው የኅብረት ስምምነት ማድረጋቸው ለሌሎች አሠሪዎችና ማኅበራት መልካም ምሳሌ በመሆኑ በታላላቅ ድርጅቶችና ማኅበራት መካከል የኅብረት ስምምነቶች ተፈረሙ። ስምምነቶቹም የኢንዱስትሪ ሰላም የሚሰፍንበት መሰረት ጥለዋል።

የሠራተኞች ማኅበራትና አሠሪዎች በጋራ እየተመካከሩ ለኢንዱስትሪ ሰላምና (ብሎም) ለአገር ልማት በቡድን የመሥራት ባህል እንግዳ ነገር በመሆኑ፣ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ከአሠሪዎችና ከሠራተኞች ማኅበራት ጋር በመተባበር አዲሱን ዘዴ ለማስጨበጥ በየጊዜው የሥልጠና ፕሮግራም እያካሄደ፣ ከሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች ጋር ለማስተዋወቅ የሚያደርገው ጥረት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም:: በዚህ ረገድ፣ መንግሥትም ልዩ ትኩረት በመስጠት የአሠሪዎችና የሠራተኞች የአመራር አካላት በውጭ አገር ጉብኝት እንዲያደርጉና በተለይም አንድ ወር ያህል በሚቆየው በዓለም የሥራ ድርጅት ዓመታዊ ጉባዔ ላይ እንዲካፈሉ፣ ለኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌደሬሽንና ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ለእያንዳንዳቸው የአንድ ልዑክ የአየር ትራንስፖርትና የውሎ አበል ወጪ በመክፈል ወደ ጀኔቭ ይልክ ነበር:: በጉባዔው ላይ በሚያደርጉት ተሳትፎና ግንኙነት፣ በተለይ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር እይታውን በማዳበር በኩል በእጅጉ ተጠቃሚ ሆኖአል:: የውጭ ግንኙነት ሰፋ ባለ መልክ ከዚህ ቀጥሎ ይብራራል::

## የኢትዮጵያ ሠራተኞችና የዓለም ሠራተኞች እንቅስቃሴ

የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ለረጅም ዘመናት በማኅበር ባለመደራጀቱ፣ በዓለም ውስጥ ይደረግ ከነበረው የሠራተኞች እንቅስቃሴ ተገልሎ በመላ ዓለም የነበረው የሠራተኞች እንቅስቃሴ ተካፋይ መሆን ቀርቶ፣ በአፍሪካ አህጉር እንኳ፣ በተለይ በ1960ዎቹ ዓመታት፣ የጋለ እንቅስቃሴ መኖሩን የሚያውቅበት ሁኔታ አልነበረም:: በብዙ አገሮች፣ የሠራተኛው እንቅስቃሴ የመንግሥትን የፖለቲካ አቅጣጫ እየተከተለ የሚያስተጋባ ነበር:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ናዚዝምና ፋሺዝም ያደረሱት ጥፋት እንዳይደገም፣ የዓለም መንግሥታት (ኢትዮጵያን ጨምሮ)፣ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበርን ሲያቋቁሙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በምዕራቡ ዓለምና በምሥራቅ አገሮች የነበሩ የሠራተኞች ማኅበራት እ.ኤ.አ በ1945 ዓ.ም. በብሪታንያ የሠራተኞች ማኅበር ኮንግረስ (United Kiagdom Trade Union Congress) መሪነት የዓለም የሠራተኛ ማህበሮች ፌደሬሽንን (World Federation of Trade Unions /WFTU) ሲያቋቁሙ፣ ከአሜሪካ የአሜሪካ የወዝአደር ፌዴሬሽን ወይም American Federation of Labor (AFC) አፈንግጦ ራሱን ከWFTU ሲያገል፣ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ኮንግሬስ ወይም Congress of Industrial Organizations (CIO) የሚባለው የሠራተኞች ማኅበር ደግሞ የዚሁ ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል ሆነ::

የዓለም የሰራተኛ ማህበሮች ፌዴሬሽን (WFTU) ዓላማ የሠራተኛውን ሕዝብ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መብቶቹን ማስጠበቅ ሲሆን፣ በተጨማሪም የጦርነት መነሾዎችና ጦርነት ጠፍተው በዓለም ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነበር:: ይሁን እንጂ፣ አብዛኛዎቹ በቅኝ ግዛት ቀምበር ስር የነበሩት የአፍሪካ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ነፃ ካልወጡ፣ በዓለም ሰላም ሊኖር አይችልም የሚለው አስተሳሰብ በአመዛኙ የድርጅቱ አባላት ዘንድ ተቀባይነት አገኘ:: ድርጅቱ፣ በዚህ አቋሙ ብቻ ሳይወሰን፣ ለሕዝቦች ጭቆና ምክንያት

በሆኑት በኢምፔሪያሊዝምና በቅኝ አገዛዝ ላይ አሉታዊ አቋም በመያዙ የቅኝ ገዥዎች መንግሥታትን አስቀየመ:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሰላምን ለማስፈን የነበረው የጋለ ስሜትና ለአንድ ዓላማ የመሥራት ፍላጎት ቀረና በርዕዮተ ዓለም ላይ የተመሰረተ የእርስ በእርስ ንትርክ በመጠናከሩ፣ የምእራብና የምሥራቅ ጎራ የሆኑት አገሮች የሠራተኞቸ ማኅበራት አብረው ለመሥራት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ::

እ.አ.አ. በ1949 ዓ.ም. የምዕራባዊ አገሮች የሠራተኞች ማኅበራት ከዓለም የሠራተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን (WFTU) ተገንጥለው፣ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይና በአሜሪካን የሠራተኞች ማኅበራት መሪነት ዓለም አቀፍ ነፃ የሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽንን (International Confederation of Free Trade Unions, ICFTU) አቋቋሙ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ WFTU እና ICFTU የምዕራብና የምሥራቅ ጎራ መንግሥታት (የቀዝቃዛውን ጦርነት) ፍልሚያ ውስጥ በመግባታቸው፣ ትግሉ በምዕራብና በምሥራቅ ጎራ መካከል ተጧጧፈ:: ሁለቱም ወገኖች ነፃነታቸውን ያገኙ አገሮችን ወደ የጎራቸው ለማስገባት የሚያደርጉት ትግል በሠራተኛውም ዓለም ተንፀባርቆ WFTU እና ICFTU የልዩ ልዩ አገሮችን የሠራተኞች ማኅበራት አባላት ለማድረግ መሯሯጡን ተያያዙት:: ትግሉ አፍላ ላይ በነበረበት ወቅት በኢትዮጵያ የሠራተኞች ማኅበራት ባለመደራጀታቸው ከጎራ ጉትቻ ውስጥ ለመግባት አልቻሉም::

ቀዝቃዛው ጦርነት እየተፋፋመ ሲሔድ፣ በተለይ ICFTU በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በእስያና በሌሎችም አህጉራት ቅርንጫፎች ከፍቶ ፀረ-ኮሚኒዝም ዘመቻ በማካሄዱ፣ ከሠራተኞች ጥቅም የበለጠ በፖለቲካ ላይ በማተኮሩ፣ የምዕራብ መንግሥታት የፖለቲካ ተቀጽላ ድርጅት ስለአስመሰለውና አሜሪካኖችም ፀረ-ኮሚኒዝም ትግሉን በረቀቀ መንገድ ለመምራት እ.ኤ.አ በ1964 ዓ.ም. CIO ከ ICFTU አባልነቱን አቋርጦ ከ AFL-CIO[12] እና ከCIA ጋር አንድ ግንባር ፈጥረው African American Labour Centre (AALC) የተባለ ድርጅት መሰረቱ:: ድርጅቱ በአፍሪካ አገሮች የሠራተኛ መሪዎችን በማሠልጠን፣ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት፣ ኮምዩኒዝም በሠራተኞች ማኅበራት ውስጥ እንዳይስፋፋ ይከላከል ነበር ::

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር እንደተቋቋመ ተሽቀዳድመው ግንኙነት የጀመሩት AALC እና ICFTU ነበሩ:: እነዚህ ሁለት ድርጅቶች በመተባበር የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ወደ ኮሚኒስት ጎራ እንዳይገባ ከማድረጋቸውም በላይ የማኅበሩን መሪዎች በማሰልጠን በቁሳቁስና በገንዘብ ከመደገፋቸውም በላይ በተለይ AALC የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበርን ዋና ጽሕፈት ቤት ሕንፃ በ1962 ዓ.ም. አሰርቶለት በንጉሠ ነገሥቱ አስመርቋል::

[12] The American Federation of Labor and Congress of Industrial Organization

## የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርና የሌሎች የአፍሪካ አህጉር የሠራተኞች ማኅበራት እንቅስቃሴ

የአፍሪካ አገሮች በቅኝ ግዛት አስተዳደር ሥር ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ፣ ምንም እንኳ በመብታቸውና በእንቅስቃሴአቸው ላይ ገደብና ቁጥጥር ቢኖርባቸውም፣ በዘርና በቀለም ልዩነት ላይ የተመሰረቱ የሠራተኞች ማኅበራት ማቋቋም ይፈቀድላቸው ነበር:: ማኅበራቱም የቅኝ ገዥዎቻቸው አገሮች ማኅበራት ተቀጽላ እንዲሆኑ ስለሚደረጉ፣ በመጀመሪያ የ WFTU፣ በኋላ ድርጅቱ ሁለት ላይ ሲከፈል፣ የICFTU አባላት ሆነው ነበር:: ነፃ የወጡት የአፍሪካ አገሮች መንግሥታትና የሠራተኞች ማኅበራት የነፃነት ትግል አቀራርባቸው ስለነበር አንዳንዶቹም ማኅበራት የገዥው ፓርቲ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ወይም የቅርብ አጋር የሆኑበት አጋጣሚ ነበር:: በተለይ በምዕራብ አፍሪካ አገሮች የጋናና የጊኒ-ኮናክሪ፣ ከሰሜን አፍሪካ ደግሞ የግብጽ፣ ሠራተኞች ማኅበራት የመንግሥቶቻቸውን የፖለቲካ አቋም የሚከተሉ ስለነበር፣ በምዕራብና በምሥራቅ ጎራዎች ከሚደገፉት ከICFTU እና ከWFTU ገለል ለማለት፣ የመላ አፍሪካ የሠራተኞች ማኅበራት ፌደሬሽንን (All Africa Trade Union Fedaration/ AATUF) በ1951 ዓ.ም. አቋቁመው ብዙዎቹን የICFTU አባለትን አስኮበለሉ:: ማኅበሩም ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም አቋም ይዞ መንቀሳቀስ ቀጠለ:: በሌላ በኩል፣ የቱኒዝያ፣ የዩጋንዳ፣ የኬንያና የሞሮኮ የሠራተኞች ማኅበራት ሌሎች መሰሎቻቸውን አገር አቀፍ ማኅበራት ጨምረው በ1959 ዓ.ም. የአፍሪካ የሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽንን (African Trade Union Confederation /ATUC) አቋቋሙ::

የአፍሪካ የሠራተኞች ማኅበራትም፣ ልክ እንደለሙት አገሮች ማኅበራት በርዕዮተ ዓለም በሁለት ጎራ ተከፍለው በተፎካካሪነት መንቀሳቀሳቸውን ቀጠሉ:: የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርም ገና እንደተቋቋመ የአፍሪካ ሠራተኞች ጎራ ውስጥ ከመግባት የICFTU አባል ሆነ:: የICFTU የአፍሪካ ቅርንጫፉን በአዲስ መልክ ለማደራጀት የኢትዮጵያንና የላይቤሪያን አገር አቀፍ ማኅበራት ይዞ ተንቀሳቀሰ:: የኢትዮጵያ የሠራተኞች ማኅበር ከ AATUF ጋር እና ከ ATUC ጋር በገለልተኛነት በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጥረት እ.አ.አ. በ1973 ዓ.ም. ሁለቱ ማኅበራት ተዋህደው የአፍሪካ የሠራተኞች ማኅበራት ኅብረትን (Organization of African Trade Union Unity /OATUU) አቋቋሙ:: የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርም የዚሁ አህጉራዊ ድርጅት አባል ሆኖ ነበር::

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር፣ ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ከሌሎች የአፍሪካ የሠራተኞች ማኅበራት ጋር ሲነጻጸር፣ ገና ለጋ ስለነበር፣ ትኩረቱ የአመራር አባላትን ማሰልጠንና መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎችን ማስከበር ላይ ሳለ የ1966 ዓ.ም. አብዮት ተቀጣጠለ::

የመነግስት ሰራተኞች አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በቅርጽና በይዘት እያደጉ እንደመሄዳቸው፣ ሠራተኞቹ የሚተዳደሩበትን

ደንብ የማውጣት ጉዳይ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። ሠራተኞች በደሞዛቸው መተዳደር እንዳለባቸው ከመወሰኑ በስተቀር የሥራ ሁኔታዎችን ማለትም ደሞዝን፣ የሥራ ሰዓትን፣ ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ወዘተ. የደነገገ ደንብ አልነበረም። በእርግጥ በንጉሠ ነገሥቱ የሚሾሙት ተመሳሳይ ጥቅማ ጥቅም ቢኖራቸውም በጽሕፈት ሚኒስቴር ትእዛዝ የማይቀጠሩት ብዙኃን ሠራተኞች የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥት ሠራተኞች ትእዛዝ ቁጥር 23/1954 ዓ.ም. እስኪወጣ ድረስ ለ21 ዓመታት ያህል በልምድና በዘፈቀደ ይተዳደሩ ነበር።

የመንግሥት ሠራተኞችን አንድ ወጥ በሆነ ደንብ የማስተዳደር አስፈላጊነቱ ስለታመነበት፣ የመንግሥት ሠራተኞች ጠቅላይ መሥሪያ ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥር ተቋቋመ፤ ደንብም ወጣ። እነዚህንም ከዚህ ቀጥለን በየፈርጃቸው እንመረምራቸዋለን።

## የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መበራከትና የሠራተኛው ብዛት በዓይነትና በመጠን በመጨመሩ፣ እንዲሁም የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ዓለም አቀፍ ግንኙነት በመስፋፋቱ፣ የሠራተኛውን አስተዳደር ዘመናዊ መልክ ማስያዝ ግዴታ ሆነ። በተለይም በቅኝ ግዛት ቀምበር ስር የነበሩት ግዛቶች እንኳ የመንግሥት ሠራተኞችን አስተዳደር በኃላፊነት የሚመሩ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች የሚያስተዳድሩባቸው ደንቦች ሲኖሯቸው፣ ለአያሌ ዘመናት በነፃነት የኖረች አገር አለ ደንብ ሠራተኞቿን ማስተዳደሯን (በጊዜው በነበረው አስተሳሰብ) የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚቀበለው እውነታ አልነበረም። ሆኖም፣ ይህንን ደካማ ጎን ለመሸፈን የኢትዮጵያ መንግስት በተባበሩት መንግሥታት ባለሙያዎች እና በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች አስጠንቶ በ1954 ዓ.ም. በትእዛዝ ቁጥር 23/1954 ዓ.ም. የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት አቋቋመ። መንግስት ለጥቆም፣ የሠራተኞችን ማስተዳደሪያ ዝርዝር ድንጋጌዎች የያዘ ደንብ በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ 265/1955 ዓ.ም. አወጣ።

የመሥሪያ ቤቱም ዓላማ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች በአንድ ወጥ ደንብና ሥርዓት የሚተዳደሩባቸውን የሥራ ሁኔታዎችን (የሠራተኛ አቀጣጠር፣ ስንብት፣ ደሞዝ፣ ደረጃ ምደባ፣ የደረጃ እድገት፣ ፈቃድ፣ የሥራ ሰዓት፣ ወዘተ.)፣ የዲሲፕሊን ማስከበሪያ ሥርዓትን፣ የሠራተኛ ማሰልጠኛ ደንቦችንና መመሪያዎችን በተመለከተ ጥናት እያደረገ ለመንግሥት አቅርቦ ማስፈቀድና አፈጻጸማቸውንም የመከታተል ኃላፊነት ነበር። መሥሪያ ቤቱም በንጉሠ ነገሥቱ በሚሾሙ የበላይ ኮሚሽነርና ሁለት ኮሚሽነሮች የሚመራ ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበር። ማናቸውም የመሥሪያ ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው በኮሚሽነሮች ጉባዔ ነበር።

የመሥሪያ ቤቱ መቋቋምና የተሰጠው ኃላፊነት በኢትዮጵያ መንግሥት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የመንግሥት ሠራተኞችን መብቶችንና ግዴታዎችን ዘርዝሮ በማቅረብ እንደ አንድ ትልቅ እመርታ የሚቆጠር መሰረታዊ ለውጥ ነበር:: መሥሪያ ቤቱ የማንኛውንም፣ ከረዳት ሚኒስትር በታች በሆነ የሥራ መደብ ላይ የተመደበ፣ ሠራተኛ ቅጥርና እድገት የመፍቀድ ብቸኛ መብት ነበረው:: የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ሠራተኛ ለመቅጠርም ሆነ የደረጃ እድገት ለመስጠት በቅድሚያ የእርሱን ስምምነት ማግኘት ነበረባቸው:: ይህም በመሆኑ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በአምቻ ጋብቻ ይፈጸም የነበረውን ቅጥር፣ እድገትና ሹመት ለመቆጣጠር አስችሏል::

የሠራተኛ ቅጥር በማስታወቂያ ወጥቶ፣ ምልመላውም የመንግሥት ሠራተኞች ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ውስጥ በተቋቋመ የቀጣሪው መሥሪያ ቤት ወኪል በአባልነት በሚገኝበት የቅጥር ኮሚቴ ተካሂዶ በችሎታ፣ በትምህርት፣ በሥራ ልምድ፣ በስነ ምግባር፣ የላቀው ተወዳዳሪ ይቀጠራል:: የሠራተኛ ምልመላና ቅጥር እንዲሁም የደረጃ እድገት በችሎታ (merit) ላይ መመስረታቸው በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር መሠረታዊ ለውጥ ነው::

የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ከኃላፊነቱ አንዱ የሠራተኞችን የሥራ ደረጃ መወሰን ነበር:: በዚህ አኳያ የተጣለው መሰረት ደሞዝና እድገት የሚወሰኑት በሥራው ምደባ (position classification) ላይ እንዲሆኑ በማድረጉ የመንግሥት ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ አንድ አይነት ደሞዝ እንዲከፈሉ አድርጓል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደሞዝ ስኬል መውጣቱም የሠራተኛውን መብት ለማስጠበቅ የሚቻልበት ሁኔታ ፈጥሯል::

ሌላው አዲስ ለውጥ የታየበት፣ ለሠራተኛው የልምምድ ስልጠና በመስጠት ምርታማነቱን ለማሳደግና የደረጃ እደገት እድሉም በአንድ ሥራ መደብ ተወስኖ የማይቀርበት ሁኔታ መመቻቸቱ ነበር:: እንደሌሎች አገሮች የመንግሥት ሠራተኞች ማሰልጠኛ ማዕከል ባይኖርም የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ከሚመለከተው መሥሪያ ቤት ጋር በመተባበር የሚፈጸምበትን መንገድ ቀይሷል::

የሠራተኛ ምልመላ፣ ቅጥር፣ ደሞዝና የደረጃ እድገት ስርዓት እንደመያዛቸው፣ ሠራተኛ ከሥነ ሥርዓት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ የሚታረምበት ወይም እንደጥፋቱ ክብደት ከሥራ የሚገለልበትና መብቱም በስሜትና በማን አለብኝነት እንዳይነካ የሚጠበቅበት፣ የዲሲፕሊን ማስፈጸሚያ ስርዓት ተቋቁሟል:: ቀጣሪው መሥሪያ ቤት በሚወስደው እርምጃ ላይ ገደብ ተደርጎበት ቀለል ባሉ ጥፋቶች ብቻ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል:: ከባድ ጥፋት ግን በመርማሪ ተጣርቶ፣ በመስሪያ ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተወስኖ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲጸድቅ በሥራ ላይ ይውላል:: የመሥሪያ ቤቱን ውሳኔ ሠራተኛ ው ካልተቀበለው በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ውስጥ ለተቋቋመው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል:: የፍርድ ቤቱንም ውሳኔ ካልተቀበለ፣ ለኮሚሽነሮች ጉባዔ ማቅረብ ይችላል:: ይህ

የዲሲፕሊን ማስፈጸሚያ ሥርዓት የሠራተኛው መብት በሹሞች የሚረገጥበትን ሁኔታ ለመቆጣጠር አስችሏል።

የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ደንብ መውጣቱ፣ በተለይ የሠራተኛ ቅጥርን፣ እድገትን፣ ደሞዝን፣ ዝውውርን፣ ልዩ ልዩ ፈቃድን፣ ቅጣትን፣ ስልጠናን፣ ወዘተ. በመሳሰሉ የሥራ ሁኔታዎች ላይ ሥር ነቀል ለውጥ አድርጓል። ሠራተኛውም ተግባሩንና ኃላፊነቱን፣ እንዲሁም መብቱንና ግዴታውን በመረዳት ሥራውን የሚያከናውንበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮለታል። በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ለኢንዱስትሪ ሠራተኞች፣ በማኅበር ተደራጅተው በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች አባል በመሆን ኃሳብና ውሳኔ የመስጠት መብት ሲሰጥ፣ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች ግን በማኅበር ተደራጅተው ሐሳባቸውን የሚገልጹበትና በውሳኔም አሰጣጥ የሚካፈሉበትን እድል ነፍጉአቸዋል።

## የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አገልግሎት መሥሪያ ቤት መቋቋም

የ1950ዎቹ ዘመናት በመንግሥት አስተዳደር ብዙ መሰረታዊ ለውጦች የተደረጉባቸው ዘመናት ነበሩ። በዚሁ ዘመን ነበር የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች፣ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት፣ እንዲሁም ዳኞች የጡረታ መብት ያገኙት። ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መንግሥት እንደሰጠው የሚያሳየው፣ የጡረታን ጉዳይ የሚከታተልና የሚያስፈጽም መሥሪያ ቤት በሚኒስቴር ደረጃ በ1950 ዓ.ም. ማደራጀቱ ነው። በሂደት ልምድ እያካበተ ሲሄድ፣ በ1954 ዓ.ም. ደግሞ የመንግሥት የጡረታ አገልግሎት ጉባዔን በቻርተር (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 250/1954 ዓ.ም.) አቋቋመ። ጉባዔውም ከመንግሥት ሠራተኞች ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ጋር ሆኖ በኮሚሽነሮች ሲተዳደር፣ የእለት ተእለት ሥራው በኮሚሽነሮቹ በሚሾም ሥራ አስኪያጅ እንዲመራ ተደረገ። ተቋሙ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲሰራ ከቆየ በኋላ፣ የጡረታ ሚኒስቴር የሚል ስያሜ አግኝቶ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ፣ በ1994 ዓ.ም. በትዕዛዝ ቁጥር 46/1954 ዓ.ም. ፈረሰ።

ለመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ መብት የተሰጣቸው፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ለአገለገሉ ሰዎች የጡረታ አበል አከፋፈል በወጣው ድንጋጌ ቁጥር 46/1953 (ኋላ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/ የ1955 ዓ.ም. ተብሎ የተሻሻለው) መሰረት ነበር። አዋጁ ለብዙ ዘመናት የሠራተኛውና የቤተሰቡ ስጋት የነበረውን ከባድ የማኅበራዊ ችግር አስወገደለት። የጡረታ እድሜ የወንድ 60፣ የሴት ደግሞ 55 ሆነ። ማናቸውም የጡረታ እድሜ የደረሰ ሠራተኛ የሚጦረው፣ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ አዋጅ (ቁጥር 199/1955 ዓ.ም.) በደነገገው መሰረት ከወር ደሞዙ 4 በመቶ እንዲሁም አሠሪው ደግሞ 6 በመቶ በማዋጣት ከአስር ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ከሰጠ ጡረታ የማግኘት መብቱ ስለሚጠበቅለት ነበር። በሥራ ላይ በሚደርስ አደጋ ወይም ከሙያ ሥራ በሚነሳ በሽታ ለመሥራት ባይችል የእድሜ ጣራ እስኪሞላ

ሳይጠብቅ ጡረታ ይሠጠዋል፡፡ ዳሩ ግን፣ ሠራተኛው በአደጋ ወይም በበሽታ ምክንያት ቢሞት፣ ለባለቤቱና ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ለሆኑት ልጆቹ፣ እንዲሁም የእርሱ ጥገኞች ለሆኑት ወላጆቹ፣ የጡረታ መብት ይጠበቅላቸው ነበረ፡፡ ከዚህም በላይ፣ በሕመምና በቀላል አደጋ ምክንያት ሠራተኛው ላልሠራበት ለተወሰነ ጊዜ ደሞዙ እንዳይቋረጥበት ሲደረግ የአካል ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ካሳም የማግኘት መብት ነበረው፡፡

ስለጡረታ የወጡት ደንቦች ከጊዜው የአገሪቱ ኢኮኖሚ ጋር የተገናዘቡ ከመሆናቸውም በላይ የዓለም የሥራ ድርጅት ስለ ማኅበራዊ ዋስትና ባወጣው ቃልኪዳን (ILO, Social Security Minimum Standards Convention No. 102, 1952) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ውስጥ ስድስቱ ማለትም የሕክምና እንክብካቤ (Medical Care)፣ በሕመም ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ (Sickness Cash Benefit)፣ በሥራ አጥነት ጊዜ የሚሰጥ ጥቅም (Unemployment Benefit)፣ የወሊድ ጥቅም (Maternity benefit) ፣ ጡረታ (Pension) ፣ በሥራ ላይ የሚደርስ የአካል ጉዳት ካሳ (Employment Injury Benefit)፣ የቤተሰብ ጥቅም (Family Benefit) ፣ ለአካለ ስንኩላን የሚሰጥ ጥቅም (Invalidity Benefit)፣ እና ለጥገኞች የሚሰጥ ጥቅም (Survivors Benefit) በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ተጠቃልለዋል፡፡ የቀሩት ሦስቱ ማለትም የሕክምና እንክብካቤ፣ በሥራ አጥነት ጊዜ የሚሰጥ ጥቅምና የቤተሰብ ጥቅም በለሙት አገሮች እንኳ በጥቂት አገሮች ብቻ ነው በማኅበራዊ ዋስትና የተጠቃለሉት፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የማኅበራዊ ዋስትና በተደላደለ መሰረት ላይ አርፎ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

## ማጠቃለያ

ከጣልያን በኋላ የነበረው ጊዜ፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የኢንዱስትሪ ግንኙነትን፣ የሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደርንና የሥራ ሁኔታዎችን የመቆጣጠሪያ አገልግሎትን አስመልክቶ መሠረት የጣለበት ዘመን ነበር፡፡ አሠሪዎችና ሠራተኞች የሚተዳደሩባቸው ሕጎችና ደንቦች ከማውጣቱም በላይ፣ በሚዘጋጁበት ጊዜም፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት የኮሚቴዎችና የቦርዶች አባላት በመሆን ሀሳባቸውንና አቋማቸውን የሚገልጹበት መድረክ ፈጥሮ በተግባር አውሏል፡፡ የሥራ ክርክርን ለመዳኘት፣ የመንግሥት፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ተጠሪዎች በእኩልነት የሚወስኑበት ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የሥራ ሁኔታዎችን በመወሰን ረገድ፣ መንግሥት (እንደ አግባቡ) መነሻውን ወይም ጣራውን ሲወስን፣ አሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ደግሞ ይህን በህብረት ክርክርና ስምምነት እንዲያሻሽሉ መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ ላይ አሠሪዎችና ሠራተኞች በማኅበራት እንዲደራጁ፣ መንግሥት በመሪዎች ምርጫና በውስጥ ሥራቸው ጣልቃ ሳይገባ፣ ሕጋዊ ዓላማቸውን በነፃነት የሚያከናውኑበት ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል፡፡ ሕጎችና ደንቦች መውጣታቸውና የኅብረት ስምምነቶች መደረጋቸው፣ ለተፈጻሚነታቸው ማረጋገጫ ስላልሆነ ሥልጣኑና ኃላፊነቱ ተለይቶ በሁሉም ዘንድ የታወቀ የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ተቋቁሞ ነበር፡፡ እንዲሁም

የሠራተኞችን መብት የበለጠ ለማስፋት፣ የመነሻ ደሞዝ ለመወሰንና የማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ሁለት ጥናቶች በዓለም የሥራ ድርጅት ተጠናቅቀው ተግባራዊ የሚሆኑበት ዘዴ እየታየ ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የኢንዱስትሪን ሰላም ለማስፈን፣ ምርታማነትን ለማሳደግና የውጭና የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለመሳብ፣ በነበረው ፍላጎት (ከሥልጣን ጨርሶ በተወገደበት ወቅት) የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን በባጀትና በሰው ኃይል የተጠናከረ፣ በከፍተኛ ኮሚሽነር የሚመራ፣ መሥሪያ ቤት አድርጎት ነበር። መንግሥት በአንድ በኩል፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት በሌላ በኩል ለኢንዱስትሪ ሰላምና ለኢኮኖሚ እድገት በቡድን የመሥራት ልምድ ማዳበር ጀምረው ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የመንግሥቱን መስተዳድርና የመንግሥት ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ሥርነቀል ሕግና ደንብ አውጥቶ ተግባራዊ አድርጓል። በዚህ ረገድ የመንግሥት ሠራተኞች ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የጡረታ ኮሚሽን ተቋቁመው የሠራተኛውን መብት ከቅጥር አንስቶ እስከ እድሜ ልኩ እንዲጠበቅ ሲያደርጉ፣ ሕይወቱም ሲያልፍ፣ ለባለቤቱ እና (እድሜያቸው አስራ ስምንት አመት እስኪሞላ ድረስ) ለልጆቹና ለጥገኛ ወላጆችም ተገቢውን አበል ይከፈል ነበር። የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች የጡረታ አገልግሎት ማግኘታቸው ለኑሯቸው ትልቅ መድን ሆኗቸዋል። ከዚህ የተገኘው ልምድና ተሞክሮ ነበር የንጉሠ ነገሡቱን መንግሥት በኢንዱስትሪ ለተሰማሩት ሠራተኞች የማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎት ለማቋቋም ጥናት ለማድረግ ያደፋፈረው።

ምንም እንኳ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች የጡረታ መብት ማግኘታቸው በጥቅም አንጻር ከኢንዱስትሪ ሠራተኞች የተሻለ ሁኔታ ላይ ቢያስቀምጣቸውም፣ በሌላ በኩል፣ ደግሞ በማኅበር የመደራጀት መብት፣ በሥራ ሁኔታዎችና በዲሲፕሊን ጉዳይ ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ወይም በውሳኔ አሰጣጥ የሚካፈሉበት መድረክ አለማግኘታቸው ብዙ ትግል ማድረግ እንደነበረባቸው ያሳያል።

ማናቸውም ለውጥ ሲደረግ፣ በተለይም ለውጡ ለዘመናት ሲሠራበት የነበረውን ባህልና የማኅበራዊ ግንኙነት የሚለውጥ ሲሆን፣ የሚገጥመው ተቃውሞ ቀላል አይሆንም። የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች የሚተዳደሩበትና መብታቸውም የሚጠበቅበት ስርዓት ሲያቋቁም፣ ብዙ ድካም እንደነበረበት ማስተዋል የሚያዳግት አይመስለኝም። ትልቁ ቁም ነገር ከእኛ በፊት የነበሩት ከተውት ያስተዳደር ቅርስ ምን እንማራለን? እኛስ ለተተኪው ትውልድ ምን ጨምረንና አዳብረን እናወርሰዋለን ? የሚለውን መርህ በተግባር መተርጎሙ ላይ ነው።

## በተመረጡ የአፍሪካ አገሮችና በኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ የተሰማራውን የሰው ኃይል የሚያነጻጽር ሰንጠረዥ

### ሰንጠረዥ 1

| አገር/ግዛት | እርሻ | ማእድንና ደንጊያ ማምረት | ማምረቻ | ግንባታ | ኤሌክትሪክ ውሀ ጋዝ | ንግድ | ትራንስፖርትና መገናኛ | አገልግሎት | ሌሎች | ጠቅላላ የሠራተኞች ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 37330 | 3503 | 74675 | 15057 | 2288 | 24518 | 17119 | 97942 | -------- | 272432 |
| አልጀሪያ | 603850 | 14019 | 112555 | 76210 | 5626 | 68457 | 55409 | 138161 | 223153 | 1297440 |
| ኬንያ | 1426761 | 11478 | 375017 | 90668 | 16182 | 126006 | 142249 | 563038 | 855 | 2752254 |
| ሞሮኮ | 247218 | 6015 | 45920 | 17710 | 1946 | 22242 | 35993 | 157581 | -------- | 534733 |
| ናይጄሪያ | 352855 | 18115 | 98225 | 76315 | -------- | 22880 | 32635 | 109170 | 18010 | 728205 |
| ታንዛኒያ | 42680 | 53630 | 31574 | 111208 | 8816 | 56565 | 45052 | 123882 | 2191 | 475578 |
| ዩጋንዳ | 213092 | 12182 | 21326 | 10438 | -------- | 11800 | 7891 | 152729 | 1083 | 430541 |
| ማላጋሲ | 51525 | 3449 | 30701 | -------- | 8646 | 10378 | 86558 | -------- | | |

♦የመረጃ ምንጮች፡- For Ethiopia:Survey of Occupational Pattern of Employment in Ethiopia,1962 E.C. , Department of Labour of the Imperial Ethiopian Government. For other African countries: African Regional Conference, *Relations between Employers and Workers*, ILO, Geneva, 1960.

# ክፍል ፪
# ዘመናዊ ሙያዎችን ማጐልበት

# ጆርናሊዝምና እድገተ በኢተዮጽያ፡- የግል ተዝታሦት

*ነጋሽ ገብረ ማርያም*

የማህበራዊ ጥናት መድረክ ይቺን አጭር ጽሁፍ እንዳቀርብ ስለጋበዘኝ ደስታና
መንፈሳዊ ኩራት ይሰማኛል፡፡ በአሜሪካን አገር አራት አመት ያህል የጋዜጠ
ኝነት ትምህርት ከተከታተልኩ በኋላ በማስታወቂያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት 1
ዓመት ሠርቻለሁ፡፡ አራቱን አመት ያገለገልኩት *የአዲስ ዘመን ጋዜጣ* ዋና
አዘጋጅ ሆኜ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ምክትል ዋና
ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ለአንድ አመት ያህል የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
ዋና ስራ አስኪያጅ ነበርኩ፡፡ ሹመቴን የደረደርኩት ከዚህ ትምህርትና የስራ
ልምድ የአካበትኩት ተሞክሮ ይቺን ጽሁፍ ለማቅረብ ድፍረት ሰጥቶኛል
ለማለት ያህል ነው፡፡ ጽሁፉ የሚያተኩረው ከሐምሌ 16 ቀን 1953 ዓ.ም
ጀምሮ *የአዲስ ዘመን ጋዜጣ* ዋና አዘጋጅ ሆኜ ስሰራ በአጋጠሙኝ አንዳንድ
ትዝታዎችና ፈታኝ በሆኑ የሙያ ጥያቄዎች ላይ ይሆናል፡፡

የማህበራዊ ጥናት መድረክ ሥራ መሪዎችና አስተባባሪዎች፤ ከጋዜጣ ሥራ
ለብዙ ዓመታት የተለየሁትን የ80 ዓመት አዛውንት ይችን ጥናት እንዳቀርብ
እንዴት ጋበዙኝ ብዬ ሳሰላስል አንድ ያነበብኩት ነገር ትዝ አለኝ፡፡ አንድ
አርኪዎሎጂስት ያገባች የውጭ አገር ሴት ለምን አርኪዎሎጂስት እንዳገባች
ተጠየቀች፡፡ «አርኪዎሎጂስት ያገባሁት እኔ እያረጀሁ ስሄድ ባሌ እየወደደኝ
ይሄዳል ብዬ ነው» በማለት የሰጠችው መልስ አይረሳኝም፡፡

እኔ ይቺን ጥናት እንዳቀርብ የተጠየቅሁት በሁለት ምክንያት ሳይሆን
አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አድሮብኛል፡፡ አንደኛው፣ በመጠኑም ቢሆን በውጭ
አገር ዘመናዊ የጋዜጠኝነት ሙያ ተምረው ከተመለሱት ጋዜጠኞች መካከል
(ከመጀመሪያዎቹ ማለት ይቻላል) አንዱ በመሆኔ፣ የዛሬ 45 ዓመት ገደማ
የጋዜጠኝነት ስራ ምን ይመስል እንደነበር እንዳወጋ ነው፡፡ ወግ ደግሞ
በሀገራችን የተለመደ የሽማግሌ የስራ ድርሻ ሆኖ ኖሯል፡፡ «ማን ይናገር የነበረ
ማን ያርዳ የቀበረ» ደህና አባባል ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት፣ የዛሬ 45 ዓመት *የአዲስ ዘመን ጋዜጣ* ዋና አዘጋጆች
ከነበርነው ጋዜጠኞች መካከል በህይወት የምገኘው እኔ ብቻ በመሆኔ (ሌላ
በህይወት ያለ ሰው ከተገኘ ይቅርታ እጠይቃለሁ) በወቅቱ የነበረውን የሚዲያ
ስራ በዓይነ ህሊና በመቃኘት ኑዛዜዬን ለተተኪው ትውልድ ተናግሬ እንዳልፍ
ዕድል ለመስጠት ይሆናል፡፡ ስራው አድካሚ ስለመሰለኝ ግብዣውን ለመቀበል
ለጊዜው ባንገራግርም፣ በመጨረሻ የተቀበልኩት በደስታ ነው፡፡

በማስታወቂያ ሚኒስቴር የተቀጠርኩት በ1952 ዓ.ም ነበር፡፡ *በኢትዮጵያ
ሔራልድ ጋዜጣ* ለጥቂት ወራት ከሠራሁ በኋላ በወቅቱ የማስታወቂያ
ሚኒስቴር የነበሩት ክቡር ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሃዋርያት፣ «መሻሻል
የሚገባው ብዙ አንባቢ ያለው *አዲስ ዘመን ጋዜጣ* ነው፡፡ ይህን ጋዜጣ አንተ
ለምን ለማሻሻል አትሞክርም?» ሲሉኝ፣ ራሴን የማውቅበትና የምፈትንበት

ሥራ ይሆናል በማለት ይህን ብርቱ ሃላፊነት የተቀበልኩት ያላንዳች ማቅማማት ነበር፡፡ ሆኖም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የተረዳሁት ሥራውን ተረክቤ በቲዎሪ የተማርኩትን ሙያ በተግባር ለመተርጐም መፍረምረም ስጀምር ነው፡፡ ጋዜጣውን ለማሻሻል የነበረው አመቺ ሁናቴ ግልፅ ሆኖ ቢታየኝም፣ በተቃራኒው ደግሞ የአንድን ጋዜጠኛ የሙያ ብቃት ጐልቶ እንዳይታይ የሚያደርጉት መሰናክሎች በመንግስት ፖሊሲ ብቻ የተገደቡ አልነበሩም፡፡ በሀገራችን ለፕሬስ ስራ አመቺ ሁናቴ ነበር ያልኩት፣ ህዝቡ ሊያውቃቸውና ትምህርት ሊያገኝባቸው ይችላል ያልኳቸው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የባህል ጉዳዮች ዘርፈ ብዙ መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የአንባቢውን ህዝብ እንዲሁም የአድማጩን ንቃተ ህሊና በማዳበርና የአስተሳሰብ አድማሱን በማስፋት ረገድ ሚዲያው የሚጫወተው ሚና ከ እስከ የማይባል መሆኑን እንደኔ በመምህርነት ያገለገለ ሰው ሊጠፋው አይችልም፡፡

ከመጀመሪያውም ቢሆን፣ ጋዜጠኛ ለመሆን የፈለግሁበት አንዱ ምክንያት፣ ገና በልጅነት ዕድሜዬ በመምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በጊዜው ይሰጥ የነበረውን ኮርስ ተከታትዬ አስተማሪ ሆኜ ስለነበር፣ ወጣቱን ማስተማር ለሐገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት መፋጠን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገባኝ ስለነበረ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ የጋዜጠኝነት ትምህርት ብማር ለሰፊው ህዝብ ሊዳረስ የሚችል የማይናቅ አገልግሎት እሰጣለሁ ብዬ አምን ነበር፡፡ የዕድገትና የልማት ስራ ሲታሰብ ሚዲያው ሕዝቡን በመቀስቀስና በማሳተፍ ለተሻለ ህይወት እንዲጣጣር ዓይን-ከፋች መሆኑ ይታወቃል፡፡

ጋዜጠኛ ለመሆን የፈለግሁበት ሌላው ምክንያት ደራሲ ለመሆን እመኝና እጓጓ ስለነበር ነው፡፡ የአያሌ ደራሲያንን የህይወት ታሪክ ስመለከት፣ ለአብዛኞቹ የደራሲነትን በር የከፈተላቸው የጋዜጠኝነት ሙያ መሆኑን ራሳቸው ይመሰክራሉ፡፡ በጋዜጠኝነት ሥራ ላይ ቆይተው በኋላ ደራሲና ከፊሎቹም የኖቤል ሽልማት ተሸላሚ የሆኑ ብዙዎች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል፡- ዎልት ዊትማን፣ ሲንክሌር ሊዊስ፣ ኧርነስት ሀሚንግዌይ፣ ጆን እሽታይንቤክ፣ አልቤር ካምዩ…ወዘተርፈ ይገኙበታል፡፡ ከታላላቅ የሀገር መሪዎችም፡- ዊንስተን ቸርችል፣ ማሃትማ ጋንዲ፣ ጀዋህራል ኔህሩ… ጋዜጠኞችና ደራሲያን ነበሩ፡፡

በእኛም አገር ደረጃ ቢሆን፣ በጋዜጠኝነትና በደራሲነት ከታወቁት ሰዎች መካከል፣ ብላታ ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ ብርሃኑ ዘርይሁን፣ በዓሉ ግርማ፣ አሀዱ ሳቡሬ፣ ማዕረጉ በዛብህ፣ ማሞ ውድነህ፣ ጳውሎስ ኞኞ እና ዘውዴ ረታ እንደምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

*አዲስ ዘመን ጋዜጣ መታተም* ከጀመረበት ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ለሃያ ዓመት ያህል በዋና አዘጋጅነት ስራውን የመሩት ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበሩ፡፡ ብላታ ለረጅም ዘመን የሠሩበት ጋዜጣ በመሆኑ «የአዲስ ዘመን አባት» በመባል እንዲታወቁ አድርጓቸዋል፡፡ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ በጋዜጠኝነት የሠሩት *በአዲስ ዘመን* ጋዜጣ ላይ ብቻ አልነበረም፡፡ በሌሎችም ጋዜጦችና መፅሔቶች ላይ በመስራት የጋዜጠኝነት ልምድና ሙያ ያካበቱ የቤተ ክህነት ሊቅ እንደነበሩ ይታወቃል።

ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ *ለአዲስ ዘመን* ጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት እንዴት ተመረጡ? ጋዜጣው መሻሻል ያስፈልገዋል ከተባለ እሳቸው ጋዜጣውን ለማሻሻል የተቸገሩበት ምክንያት የዘመናዊ ጋዜጠኝነት ሙያ ስላልነበራቸው ነው? ወይስ የመንግስት ፖሊሲና የሣንሱር ማነቆ አላፈናፍን ብሏቸው ይሆን? ከሆነስ ሆነና ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ማን ነበሩ? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የህይወት ታሪካቸውን መመልከቱ አንድ ፍንጭ እንደሚሰጠኝ አምኜ ከዜና መዋዕላቸው የሚቀጥለውን መረጃ ሰበሰብሁ።

ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ዮሐንስ ደባልቄ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ያድንቁሽ መኩሪያ በ1887 ዓ.ም ተወለዱ። የተወለዱበት ክፍለ ሀገር ሸዋ ሲሆን፣ ወረዳው ጅሁር፣ የቀበሌው ልዩ ስም ጐበላ ነበር። እናታቸው በሞት የተለዩዋቸው ወልደ ጊዮርጊስ ገና የአምስት ዓመት ልጅ ሆነው ነበር።

በተወለዱበት አቅራቢያ ጃል በሚባለው ስፍራ ያስተምሩ ከነበሩት ከአባ ወልደ ዮሐንስ ንባብና የቃል ትምህርት ተምረው ዳዊት ከደገሙ በኋላ፣ አባታቸው ወደ አዲስ አበባ ይዘዋቸው መጥተው ከሊቀ ጳጳሱ ከአቡነ ማቴዎስ ማዕረገ ድቁና ተቀብለዋል። ከዚያም ወደ ሐገራቸው ተመልሰው በጐበላ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በድቁና ያገለግሉ ነበር።

ለትምህርት ብርቱ ፍላጐት ስለነበራቸው ሶምሳ ወደተባለ ስፍራ (በተጉለት ወረዳ) ሄደው በሶምሣ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያስተምሩ ከነበሩት ከደብተራ በየነ ዜማ ማጥናት ጀመሩ። ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከር ኮላሽ ወደተባለ አምባ ሄደው በሰማዕቱ በቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ያስተምሩ ከነበሩት ከአለቃ ተስፋ የቤተልሄም ዜማ  አጠኑ።

«ትምህርትና ምናኔ ከአባት፣ ከእናት፣ ከወገን ዘመድ ተለይቶ ሲይዙት ይወዳል» የሚለውን መርህ ተግባራዊ በማድረግ የሚሄዱበትን ሥፍራ በውል ሳያውቁትና ከወላጅ ዘመድ ሳይማከሩ ጉዞ ጀመሩ። መንገድ ላይ ከአገኙዋቸው ነጋዴዎች ጋር በመጓዝ ወረይሉ ደረሱ። ወረይሉ አለቃ ፀጋ ከተባሉ ሊቅ ትምህርት ቤት ገብተው የዜማውን ትምህርት ቀጠሉ።

«አንደበቴ የሠለጠነውና እጄም ብዕር የጨበጠው በዚሁ ሀገር ነው» ይላሉ ብላታ። «ከዚያ በፊት ጽህፈት አልሞከርሁም ነበር።» ምክንያቱንም ሲናገሩ፣ «በዚያን ጊዜ እንኳን ተማሪዎችና አስተማሪዎችም ቢሆኑ ለፅህፈት እምብዛም የማይጣጣሩ በመሆናቸው ነው። ነገር ግን አንዳንድ ቁም ፀሃፊዎች መኖራቸው የሚታበል አይደለም። እንዲሁም አንዳንድ ክታብ ከታቢዎች ያድናል እያሉ የሚቦጫጭሩት የጥንቆላ ፅህፈትም እንደነበረ የታወቀ ነው። ብልሁን ህዝብ የሚያሞኙበት አስማት ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ እንደ ታላቅ ቁም ነገር አድርገው ይኮሩበት እንደነበር የሚታወስ ነው» ይላሉ ብላታ። ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወረይሉ  በነበሩበት ወቅት በእጅጉ ያስመረራቸው የነበረው ሥራ ማታ ማታ አኮፋዳ ይዘው በየመንደሩ ለልመና መንከራተታቸውና ከውሾች ጋር ያደርጉት የነበረው ግብግብ ነበር።

ወጣቱ የቆሎ ተማሪ አለቃ ፀጋ ዘንድ እየተማሩ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍና የመፅሀፈ ሃዲሣትን ትርጓሜ አጠኑ። በዚህ ትምህርት ቤት 3 አመት ከተማሩ በኋላ በወረይሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ያስተምሩ ከነበሩት ገብረ ሚካኤል ከሚባሉ መምህር ቅኔ ተምረው በስምንት ወር ቅኔ ተቀኙ። በኋላም አቋቋም ለመማር ወደ አለቃ ፀጋ ዘንድ ተመልሰው ሄዱ።

በ1909 ዓ.ም ወደ ዋድላ ደላንታ ሄደው በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ደብር ከአለቃ ውቤ የቅኔ ትምህርታቸውን ከአጠናከሩ በኋላ በጭንጋ አቦ ቤተክርስቲያን ያስተምሩ በነበሩት በአለቃ ብዙ መሪነት የተለያየውን የቅኔ ጐዳና ዘለቁበት።

የብላታ ትምህርት በዚህ አላበቃም። ወደ በጌምድር ሔደው ደንቢያ ወረዳ አቻራ ማርያም ቤተክርስቲያን ያስተምሩ ከነበሩት ከአለቃ ገብረ እግዚአብሔር ዝማሬ መዋስዕትና ቀኝ ጌታ ላቀው ዘንድ አቋቋም አጠኑ። ደንቢያ ለበርበሬ አዝመራ ያመች ስለነበረ ብላታ በሙያተኝነት እየሠሩ ያገኙትን በርበሬ በሠላሳ ብር ሸጠው ጐንደር ከተማ ገቡ። ጐንደር ውስጥ አለቃ ኀሩይ ፈንታ የተባሉ የታወቁ ሊቅ በበዓታ ደብር ያስተምሩ ስለነበር፣ በእሳቸው መምህርነት ብላታ የመፃህፍተ ሃዲሳትን ትርጓሜ አጣጥመው አወቁ።

አለቃ ኀሩይ ፈንታ ቀደም ሲል በንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ፣ በኋላም በራስ ጉግሳ ችሮታ ቀለብ እየተሰጣቸው የጉባኤ ትምህርት አስፋፍተው ያስተምሩ ስለነበረ ብላታ በዚህ ጉባኤ ላይ እየተገኙ በቅኔ ምስጢር የመራቀቅ ችሎታቸውን አዳበሩ። በሊቃውንቱም ጉባኤ ላይ የመሳተፍ ዕድል አገኙ። አራት ዓመት ያህል በአለቃ ኀሩይ ጉባኤ ሲካፈሉ ቆይተው፣ የሐዲስን ትርጓሜ ጠንቅቀው አወቁ። በቤተ ክህነት ትምህርት የተጓዙበትን መንገድና ያሳለፉትንም ፈተና ስናስበው ብላታ የዕድሜ ልክ ተማሪ ነበሩ ለማለት ይቻላል።

በ1916 ዓ.ም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የአለቃ ኀሩይን የሊቅነት ዝና ሰምተው ከተማሪዎቻቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አደረጉ። መጓጓዣም ገንዘብ ላኩላቸው። ከአለቃ ኀሩይ ጋር ወደ አዲስ አበባ ከመጡት ተማሪዎች አንዱ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ነበሩ። አለቃ ኀሩይ በቤተ መንግስቱ ውስጥ ማረፊያ ተሰጥቷቸው የመፃህፍተ ሐዲሣትን ምስጢር ያስፋፉ ነበር።

በ1918 ዓ.ም አለቃ በዛብህ የተባሉ ሊቅ የቅዱስ ቄርሎስን መፅሀፍ ተርጉመው እንዲታተምላቸው ልዑል አልጋ ወራሽን ጠየቁ። አልጋ ወራሹም የቅዱስ ቄርሎስ መፅሀፍ ትርጓሜ አስቸጋሪ እንደሚሆን ከተናገሩ በኋላ ትርጉሙን የሚገመግሙ ሊቃውንት አዘዙ። ለዚህ ስራ የታዘዙት ሊቃውንት አለቃ ኀሩይ ፈንታ፣ አለቃ ለማ ኃይሉ (የመንግስቱ አባት ይመስሉኛል)፣ ሊቄ ገብረክርስቶስ ሲሆኑ፣ በታዛቢነት አለቃ በዛብህና መልአከ ገነት ክፍሌ (ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ) ነበሩ። የዚህ ጉባኤ ፀሐፊና ቃለ ጉባኤ መዝጋቢ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ሆኑ።

የትርጉሙ ሥራ ተጠናቅቆ ለልዑል አልጋወራሽ ሲቀርብ፣ ሊቄ ገብረክርስቶስ ብላታ ትጉህ ሰራተኛና ባለሙያ መሆናቸውን ተናገሩ። አልጋ ወራሹም ብላታ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ይታተሙ የነበሩትን መፃህፍት እንዲመረምሩና ስህተቱንም እንዲያርሙ ፈቀዱ።

ከ1917 ዓ.ም ጀምሮ በአቶ ገብረ ክርስቶስ በኋላም በአቶ ማህተመ ወርቅ እሸቴ ይዘጋጅ የነበረው *የብርሃንና ሠላም* ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ በመሆን የጋዜጠኝነት ሥራቸውን ጀመሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ *ከሣቴ ብርሃን ለልበ ጠቢባን* ለተሰኘው ወርሀዊ መፅሄት የፅሁፍ አቀናባሪ ሆነው ሠርተዋል። ብዙ መፃህፍትም ደርሰዋል። መስከረም 17 ቀን 1926 ዓ.ም ግርማዊ ጃንሆይ ባለሁለት ወርቅ ጥብጣብ ካባና ቀሚስ ከጃኖና ከወርቅ ሜዳይ ጋር ሸልመዋቸዋል። ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ በ1919 ዓ.ም ሚያዚያ 27 ቀን ወይዘሮ ዋካ ድንቄን በህግና በስጋ ወደሙ አግብተው የሰባት ልጆች አባት ሆነዋል። የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውስጥ ፋሺስቶች ባደረሱት ዕልቂት ብላታ በአፈሣ ተይዘው በእስር ቤት ተጉላልተዋል። ጠላት ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን በአዲስ አበባ ውስጥ 'Ufficio Stampa e Propaganda' (የፕሬስና የፕሮፓጋንዳ መስሪያ ቤት) የተባለ መስሪያ ቤት አቋቁሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እና ቀደም ሲል በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግስት የነበረውን አገዛዝ በማጥላላትና በመንቀፍ ፕሮፓጋንዳ ያሠራጭ ነበር። ፕሮፓጋንዳው የሚነዛው በሬዲዮ፣ *የቄሣር መንግስት መልክተኛ* በተባለ ጋዜጣና *የሮማ ብርሃን* ተብሎ በተሰየመ ወርሀዊ መፅሄት ነበር። የቄሳር መንግስት ለፕሮፓጋንዳው ሥራ ዋና መሳሪያ አድርጐ የተጠቀመባቸው ሰዎች ነጋድራስ (በኋላ አፈ ቄሣር) አፈወርቅ ገብረ የሱስ፣ አቶ ከበደ ሚካኤል፣ አቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝና ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ እንደነበሩ ይታወቃል። በ1933 ዓ.ም ጃንሆይ ከስደት ተመልሰው፣ ጣሊያኖች ያቋቋሙትን መስሪያ ቤት መንግስት ተረክቦ ሥራ ሲጀምር፣ የሚዲያ ባለሙያዎች በማስፈለጋቸው አቶ አምደ ሚካኤል ደሣለኝና ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ በጋዜጠኝነት ሥራ እንዲመደቡ ተደርጓል።

በ1953 ዓ.ም እኔ *የአዲስ ዘመን* ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኜ ስራ እንደጀመርኩ፣ በጋዜጣው የመጀመሪያ ገጽ ላይ ከጃንሆይ ንግግር በስተቀር፣ ወይም ጃንሆይን የሚመለከት ዜናና ሐተታ እንዲሁም ፎቶግራፍ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ፅሁፍ እንደማይታተም ከብላታና ከሠራተኞቹ ተነገረኝ። ይኸ መመሪያ ከተማርኩት ትምህርትና በውጭ ሀገር ከተመለከትኩት የጋዜጣ ሥራ ጋር ስለማይጣጣም አንድ አስቸጋሪ ፈተና ከፊቴ እንደተደቀነ ተረድቼ ነገሩን በጥሞና አሰብኩት።

የጋዜጣ ስራ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ስለምገነዘብ፣ ሥራው አይቻልም ብሎ እጅን አጣምሮ ከመቀመጥ ይልቅ የሚቻለውን ያህል እየሠሩ መመሪያውንና ሳንሱሩን በሂደት ለመሻር መሞከር ቀና አስተሳሰብ መስሎ ታየኝ።

ጋዜጣው የሚመራበት ፖሊሲ በፅሁፍ ተሰጥቶ ይሆናል ብዬ ፈልጌ ነበር። የካቲት 7 ቀን 1927 ዓ.ም የታወጀው ህግ መፃህፍትና ጋዜጦች ለማሳተምና ማተሚያ ቤቶችን ለማቋቋም በቅድሚያ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ፈቃድ ማግኘት እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ይኸ መስሪያ ቤት ጋዜጦችና መጻህፍት ያለፈቃድ እንዳይታተሙና እንዳይሸጡ የመከልከል ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር።

በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው ህገ መንግስት አንቀፅ 41 በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት መኖሩን ገልጾ፣ አፈፃፀሙ በህግ እንደሚወሰን ደንግጓል። ህገመንግስቱ፣

የመንግስት የሉአላዊነት ስልጣን የንጉሠ ነገሥቱ መሆኑን፣ ሚኒስትሮችን የሚሾሙትና የሚሽሩት ጃንሆይ መሆናቸውን፣ በሀገሪቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን የጃንሆይ መሆኑንና ማናቸውም ነገር የሚወሰነው በንጉሠ ነገሥቱ መሆኑን ይገልፃል። ፓርላማውንም የመሰብሰብና የመበተን ሥልጣን ነበራቸው። የህግ መወሰኛው ምክር ቤት አባላት የሚመረጡትና የሚሾሙት በጃንሆይ ነበር። የፓትሪያርክ ሹመት በጃንሆይ መጽደቅ ነበረበት። በአጠቃላይ አነጋገር የህግ አውጪው፣ የህግ ተርጓሚውና የህግ አስፈፃሚው አካላት በንጉሠ ነገስቱ ሥልጣን ስር ስለነበሩ፣ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ በጋዜጣው ሥራ ላይ ተፅዕኖ እንደነበረው ለመጥቀስ እፈልጋለሁ። እያንዳንዱ የሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሚኒስትሮችና በከፍተኛ ባለስልጣናት ቢመራም፣ ለሹማምንቱ «የበላይን ሳላማክር» በማለት ከተጠያቂነት የሚያመልጡበት መንገድ ከፍቶላቸው ነበር። ይኽ ሁናቴ ለፕሬስ ሥራ ምንኛ አስቸጋሪ እንደነበረ መረዳት አያዳግትም።

በ1958 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገቡትና በኢትዮጵያም ውስጥ የሚታተሙት ፅሑፎች የህዝብን ሞራል የማያበላሹ ወይም የህዝብን ፀጥታ የማያናጉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሐላፊነት ለማስታወቂያ ሚኒስቴር የተሰጠ መሆኑን ያመለክታል።

በየዕለቱ ከምናደርገው የስራ ክንውን እንደተረዳሁት ሚዲያው ይመራ የነበረው በፅሁፍ በተሠጠ መመሪያ ሳይሆን፣ በስልጣን ላይ ያለው ሚኒስትር ወይም ሹም በሚሰጠው የቃል ትዕዛዝ ነበር።

የሚኒስቴሩን መስሪያ ቤት ቀደም ሲል ከመሩት ሹማምንት መካከል አቶ ተስፋዬ ተገኝ፣ አቶ ክብረት አስታጥቄ፣ አቶ (በኋላ ብላታ) መርስኤ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ብላታ ግርማቸው ተክለ ሀዋርያት፣ አቶ ሠረቀ ብርሃን ገብረ እግዚእ፣ አቶ አምደ ሚካኤል ደሣለኝና አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ጥቂቶቹ እንደነበሩ ይታወቃል።

መኮንን ሀብተ ወልድ በቃል ሰጥተውት የነበረው መመሪያ ከሞላ ጐደልም ቢሆን የሌሎቹ መመሪያ ምን እንደሚመስል ስለሚያመለክት ለአብነት ያህል ገልጨዋለሁ። ይኽ የቃል መመሪያ የተገኘው አንጋፋው ጋዜጠኛ ክቡር አቶ አህዱ ሳቡሬ *የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ፍፃሜና የደርግ አነሣስ* በሚለው አንደኛ መፅሀፍ ከመዘገቡት ፅሁፍ ነው።

> መኮንን ሀብተ ወልድ እኛ ዘንድ በመጡ በጥቂት ሳምንቶች ውስጥ በጋዜጣና ማስታወቂያ መስሪያ ቤት ከእሳቸው በታች ሆኖ የጋዜጣውን፣ የሬዲዮኑንና በጠቅላላው የኘሮፓጋንዳውን ስራ በቅርብ የሚከታተል፣ የሚቆጣጠር፣ በሬዲዮ የሚነገረውን ዜናም ሆነ በጋዜጣ የሚወጣውን ፅሁፍ የሚመረምር ሰባት አባላት የሚገኙበት የሣንሱር ቦርድ ተቋቋመ። የቦርድ አባላት 1. ታደሰ አበበ 2. ከበደ አስፋው 3. ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ 4. ያሬድ ገ/ሚካኤል 5. መኮንን ወርቅ አገኘሁ 6. አድማሱ ባድማ 7. አህዱ ሳቡሬ ነበሩ።
>
> ቦርዱ በተቋቋመ ጊዜ የሥራውን ጠባይና የሐላፊነቱን ክልል በደንብ የሚገልፅ የፅሁፍ መመሪያ አልተሰጠውም። ሚኒስትሩ በመጀመሪያው

የቦርዱ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ገለፃ በሬድዮ የሚነገረውና በጋዜጣ የሚወጣው ማናቸውም አይነት ወሬ፣ ፅሁፍ፣ አስተያየት፣ ሐተታ፣ ዲያሎግ ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት በጥንቃቄ መመርመርና መመዘን ያለበት መሆኑን ጠቅሰው፤ … «ትልቅ አደራ ነው የተሰጣችሁ። በቅርብ ቀን ግርማዊነታቸው ፊት ትቀርባላችሁ። አንድ መጥፎ ወሬ ቢነገርና ህዝብ ጆሮ ቢደርስ ጉዳቱ ትልቅ ነው በማለት አስጠነቀቁ።…

ማናቸውም ወሬና ፅሁፍ ቦርዱ ፊት ሲቀርብ ከፀጉር ስንጠቃ በከፋ አካኋን እየተመረመረ ልዩ ልዩ ትርጉም እየተሰጠውና አቃቂር እየወጣለት ፈተናውን ከሚያልፈው የማያልፈው ወሬና ፅሁፍ ነበር የሚበዛው…[1]

ፖሊሲውን ወይም መመሪያውን ለማስለወጥ ባይቻልም ቅሉ፤ ለጊዜው እኔ አሻሽለዋለሁ ብዬ ዕቅድ ያወጣሁለትን ስራ ያስተጓጐለብኝ በጋዜጣው የቅንብር ቴክኒክ ላይ ገደብ የሚጥለው የሚቀጥለው መመሪያ ነበር፦

የጋዜጦቹ የመጀመሪያው ገፅ ስድስቱ አምዶች በሙሉ ከቤተ መንግስቱ ተራ ወሬ ጀምሮ በተቻለ መጠን የግርማዊነታቸውን ህይወትና ስራ በሚጠቃቅሱ ፅሁፎችና ፎቶግራፎች እንዲሸፈኑ ማድረግ የአዘጋጆቹ ዋና ኃላፊነት መሆኑ ለብላታ ወልደ ጊዮርጊስ በጥብቅ ተገልጾላቸዋል።[2]

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ትዕዛዝ አልበቃ ብሎ፣ ይላሉ አቶ አህዱ፣ «በየበዓላቱ የሚነሱት ፎቶግራፎች በጋዜጣም ሆነ በመጽሄት ከመውጣታቸው በፊት በትልቅ ኢንቨሎፕ ውስጥ ታሽገው ወደ ቤተ መንግስት እየተላኩ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ በአንድ አይተዋቸው ኤክስ ምልክት ያደረጉባቸው ፎቶግራፎች ብቻ እንዲወጡ ትዕዛዝ በመስጠታቸው አዲሱን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ነበር በየአቅጣጫው የሚጣደፈው»[3]

የሣንሱሩ ጉዳይ በአማርኛ የሚታተሙትን ጋዜጦችና መጽሄቶች ብቻ አልነበረም የሚመለከተው። በእንግሊዝኛ የሚፅፉትም ጋዜጠኞች ይኸው ችግር እንደ ነበረባቸው ዊልያም ሲድ የተባሉ ጋዜጠኛ «ሳንሱር በኢትዮጵያ» ‘Censorship in Ethiopia’ በሚል ርዕስ October 7 ታትሞ በወጣው ማንቼስተር ጋርድያን *Manchester Guardian* ጋዜጣ የሚቀጥለውን አስፍረዋል፦

- የጃንሆይን ስም ጠቅሶ የሚፃፍ ማናቸውም ፅሁፍ ተውላጠ ስም ሳይቀር በካፒታል ፊደል እንዲፃፍ፤
- በማንኛውም ፅሁፍ የጃንሆይ ስም መጠቀስ ካለበት ከእሳቸው በፊት የሌላ ሰው ስም እንዳይወጣ፤
- በህይወት የሚገኝ ሰው ፎቶግራፍ ከሞተ ሰው ጋር አብሮ መታተምና መውጣት እንደሌለበት፤

[1] አህዱ ሳቡሬ፣ *የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ፍጻሜና የደርግ አነሳስ*፣ (አዲስ አበባ፣ የታተመበት አመት አልተገለጸም)፣ ገጽ 102-3

[2] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* 110

[3] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* 119

- በጅምላ ብዙ ሰዎች የያዘ ፎቶግራፍ በጋዜጣ ሲወጣ ከመካከላቸው በሞት የተለየ ሰው ካለ ፎቶግራፉ መታተም እንደሌለበት ጽሁፉ ይገልፃል።

እኔ እንደሚመስለኝ የዚህ አይነቱ መመሪያ የሚወጣው በቤተ መንግስቱ ትዕዛዝ ሳይሆን የስራውን ባህሪ በማያውቁ ባለስልጣኖች ወይም እንወደድ ከሚሉ የሳንሱር ባለሙያዎች ነው።

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሃዋርያት *አዲስ ዘመንን* አሻሽለው ብለው ሃላፊነቱን የሰጡኝ የመንግስት ፖሊሲ ወጥሮ የሚይዝ መሆኑና የባለሙያዎች እጥረት መኖሩ ጠፍቷቸው ሳይሆን፣ ከፈረንጅ አገር እየተማረ የሚመጣ ሰው ሐገራችን ሲደርስ ምን አይነት ፈተና እንደሚያጋጥመው «አርአያ» በተሰኘው መፅሀፋቸው የተገለፀ መሆኑን ሊያስታውሱኝ ፈልገው ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ ሳያድርብኝ አልቀረም።

*የአዲስ ዘመንን* ጋዜጣ ለማሻሻል በህግና በመመሪያ እንዲሁም በአሠራር ልምድ የተወሳሰበ ችግር መኖሩን ባምንም፣ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት አንዳንድ ነገር ማሻሻል እንደምችል እርግጠኛ ነበርኩ። የአንድ ጋዜጣ ተግባር ኢንፎርሜሽን ማቅረብ፣ በንግዱ ሙያ ከተሠማራ ውድድሩን ተቋቁሞ ህልውናን መጠበቅ፣ እንዲሁም ህብረተሰቡን ማገልገልና ማዝናናት ነው።

በጋዜጠኝነት ትምህርት ቤት ከተማርኩት የዜና አፃፃፍ ቴክኒክ አንዱ ዜናንና አስተያየትን (fact & opinion) ለይቶ መፃፍ ነው። ዜና ዕውነተኛና ነባራዊ (objective) መሆን አለበት ከተባለ፣ የሪፖርተሩን ስሜታዊነት፣ አድላዊነትና ወገናዊነት ሳያንፀባርቅ ፍሬ ነገሩን እንዳለ ወይም (በአዲሱ ቋንቋ) እንደወረደ ማስፈርን ይጠይቃል። በዚህ አይነት የአፃፃፍ ቴክኒክ ከንቱ ውዳሴና ማናቸውንም ነገር ያለአግባብ አጋንኖ ማቅረብ ይወገዳል የሚል ዕምነት አለ። የታየው ይኸው ነው፤ የተናገሩት ይኸንን ነው፤ በማለት ተጨባጩን ነገር (fact) ለማስቀመጥ ይረዳል።

አስተያየትም በተመደበለት የአስተያየት ገፅ ላይ ይጻፋል። ሲፒ ስኮት (C.P. Scott) የተባለ እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ «አስተያየት ርካሽ ነው፤ fact ግን ክቡርና የተቀደሰ (ውድ) ነገር ነው» ሲል የፃፈው ለዚህ ነው። የጋዜጣው ልሳን የሆነው ርዕሰ አንቀፅ የሚሰፍረው በዚሁ በአስተያየት ገጽ ላይ ነው። በዜና አፃፃፍና በሥነ ፅሁፍ ወይም በተውኔት አፃፃፍ መካከል ግልፅ የሆነ የዓላማ፣ ወይም የተልዕኮ እንዲሁም የይዘትና የአቀራረብ ልዩነት አለ።

*በአዲስ ዘመን* ጋዜጣ፣ እነዚህን ልዩነቶች ጠብቆ ዜናውን ማቅረብ ቢቻል፣ ጋዜጣውን በማሻሻል ረገድ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እንደተደረገ አድርጌ እቆጥረው ነበር። በዜና አፃፃፍና በሥነ ፅሁፍ መካከል ስላለው ልዩነት ዝርዝር የሆነውን ጉዳይ በማንሳት አንባቢን እንዳላሰለች ስለ አላማውና ስለ አፃፃፉ ቴክኒክ ብቻ እጽፋለሁ።

የሥነ ፅሁፍ አፃፃፍ አላማ አንባቢን እያዝናና እና እያማለለ ልብ በመስቀል፣ ዝርዝር ከሆነው ጉዳይ ተነስቶ ወደ ጡዘቱ፣ ቀጥሎም ወደ ውጤቱ የሚመራ የአፃፃፍ ሥልት ነው፡፡ ይኸ ሒደት በልብ ወለድና በተውኔት አፃፃፍ ሲከሰት እንደምናየው የኢንፎርሜሽኑ ወይም የሚስጥሩ መጋረጃ የሚከፈተው በመጨረሻ ነው፡፡ የዜና ዓላማ በቀጥታ ኢንፎርሜሽን መስጠት ነው፡፡ የክስተቱ ወይም የድርጊቱ ውጤት በዜናው የመጀመሪያ አንቀፅ ወይም አረፍተ ነገር ይገለፃል፡፡ የዚህ አይነቱ የዜና አፃፃፍ ሥልት በተፈጥሮ ወይም በግብታዊነት ለምንጠይቃቸው ስድስት ጥያቄዎች መልስ ይሰጠናል፡፡ ዓላማው ኢንፎርሜሽን መስጠት ስለሆነ አንባቢ ማወቅ የሚፈልገውን ነገር ወዲያው አፍርጦ በመናገር የዜናውን ምንነት ያሳውቃል፡፡ እንደመርዶ ነጋሪ ዙሪያ ዙሪያውን አይዞርም፤ ሞቷል ብሎ ነው የሚጀምረው፡፡ በዜናው የመክፈቻ አንቀፅ ማን? ለምን? ምን? የት? መቼ? እንዴት? ለተሰኙት ስድስት ጥያቄዎች መልስ ስለሚሰጥ የዜናውን ምንነት ለማወቅ የዜናውን ዝርዝር ጉዳይ ማንበብ አይጠይቅም፡፡


ጆሴፍ ሩድያርድ ኪፐሊንግ (1865-1936) የተባለው የእንግሊዝ ደራሲና ገጣሚ ጋዜጠኛ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ለስድስቱ ጥያቄዎች መልስ የሚያስገኝ አንቀጽ ምን ያህል ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኘው በሚቀጥሉት ስንኞች እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡

I have six honest men
They taught me all I knew,
Their names are where & what & when and how
& why  and who.

ወደ አማርኛ ሲተረጐም፡-

*የማውቀውን ሁሉ እኔን ያስተማሩኝ*
*ስድስት አገልጋዮች ታማኝ ሰዎች አሉኝ፡፡*
*እስቲ ልንገራችሁ እንዲህ ነው ስማቸው*
*እንዴት? ወዴት ? መቼ? ምን? ለምን? ማን? ናቸው፡፡*

ከዚህ በላይ በፅሁፍ ለመግለፅ የተሞከረውን የዜና አፃፃፍ ሥልት በሥዕላዊ መንገድ ማመልከት ይቻላል፡፡ ዜና ሲፃፍ በአናቱ በቆመ ፒራሚድ ይመሰላል፡፡ሥነ ፅሁፍ ደግሞ በትክክለኛው ፒራሚድ ይወከላል፡፡




በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዜናውን በተፈለገው ገፅ ላይ በዚህ መልክ አቀነባብሮ ለመፃፍ የክቡር አቶ መኮንንን መመሪያ ቀስ እያልን መናድ ነበረብን፡፡ ሌላው ችግር የእኛ የጋዜጠኞቹ ችሎታ ውስንነት መሆኑን ልንሸሽግ አንችልም፡፡ አብረውኝ እንዲሰሩ የተመደቡልኝ የስራ ባልደረቦቼ መሠረታዊ የሆነ የጋዜጠኝነት ትምህርት የተከታተሉ አልነበሩም፡፡ ከተለያየ የስራ መስክ የመጡና ሐተታ የመፃፍ ልምድ ያካበቱ ስለነበሩ፣ እኔ በአሰብኩት መንገድ ጋዜጣውን ለማዘጋጀት ምኞትና ትዕግስት ብቻውን በቂ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ሪፖርተሮቹ የሚያቀርቡት አንዳንድ ፅሁፍ የሣንሱሩን ማነቆ ለማለፍ ስለማይችል መንፈሳቸው ተረጋግቶ በየቦታው እየተሯሯጡ ዜና ለማሰባሰብ የነበራቸው ፍላጐት እያደር እየተዳከመ ሲሄድ ይታየኝ ነበር፡፡ የትራንስፖርቱም ችግር እንዳለ ሆኖ ነው፡፡

የዕለቱን ጋዜጣ ለማዘጋጀት ቀኑን በሙሉ ሠርተን ሰዓቱ ተርፎን አያውቅም፡፡ ፅሁፉ ወደ ማተሚያ ቤት ከተላከ በኋላ የስራ ባልደረቦቼን መሠረታዊ የሆነ የጋዜጠኝነት ትምህርት ለማስተማር እሞክር ነበር፡፡ የጋዜጠኝነት ትምህርት ተምሮ የሙያው ባለቤት ለመሆን መንገዱ ሁለት ነው፡፡ አንዱ የጋዜጠኝነት ሙያ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ገብቶ ሙያውን መማር ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ የአንድ ጋዜጣ ድርጅት ሰራተኛ ሆኖ በስራው ላይ የቆየ ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች የአፃፃፉን ስልትና አርትኦት፣ እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርቱ የሚጠይቀውን ሙያ መማር ነው፤ እየሠሩ መማር ማለት ነው፡፡ የጋዜጠኝነት ሙያ ቲዎሪውን ብቻ በመማር የሚጨበጥ ሙያ አይደለም፡፡ የማያቋርጥ የማንበብና የመጻፍ ልምድ ማዳበር ይጠይቃል፡፡

በሀገራችን ውስጥ በዘመናዊ የጋዜጠኝነት ሙያ ሠልጥነው እየሠሩ የሚያስተምሩ ወይም የሚያሳዩ ባለሙያዎች ስላልነበሩ በወቅቱ ይኸ ዕድል ለሁላችንም ሊደርስ አልቻለም። በዚህም ምክንያት በዚያን ጊዜ ሪፖርተሮቻችን በራሳቸው ጥረት ሐተታ ፀሐፊ ከመሆን አላለፉም ማለት ይቻላል። አብረውኝ ይሰሩ ከነበሩት ጋዜጠኞች መካከል አሳምነው ገብረ ወልድን፣ ጋረደው ደምሴን፣ ጳውሎስ ኞኞን፣ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲሣሣን፣ አየለ ኪዳኔንና ያሬድ ገብረ ሚካኤልን አስታውሳለሁ። በአሁኑ ወቅት አሳምነው ገብረ ወልድ፣ ጳውሎስ ኞኞና ያሬድ ገብረ ሚካኤል በህይወት የሉም። ሀብተ ጊዮርጊስ ዲሣሣ ከአብዮቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት ዘብጥያ ወርዷል ሲሉ ሰምቻለሁ። እዚህ የፃፍኩት ነገር ዕውነት መሆኑን ለመመስከር ጋረደውና አየለ ይበቁኛል!

የጋዜጣው የመጀመሪያ ገጽ ለዜና የተመደበ ሆኖ ሳለ የግርማዊነታቸውን የውሎ ድርጊትና ፎቶግራፍ ብቻ ይዞ ይውጣ ማለቱ ጋዜጣውን ለማሻሻል ከታሰበው ዓላማ ጋር ሊጣጣም አልቻለም። የማናቸውም ጋዜጣ የመጀመሪያ ገጽ የዕለቱ ዋና ዋና ዜናዎች የሚሰፍሩበት የትርኢት መድረክ ከመሆኑም በላይ፣ የዜናው ትልቅነትና አንስተኛነት በተዋረድ የሚመደብበት ነው። የዜናው ርዕስና የሚያስፈልገው የአምድ መጠን የሚወሰንበት ስለሆነ፣ የዜናው ማሳያና መሸጫ (tells & sells) መድረክ ነው። የዜናው አቀማመጥ የአንባቢን ዓይን መማረክ ይኖርበታል።

ዜናውንና ፎቶግራፉን መምረጥ፣ የርዕሱ ኮርና ዜናው በገጹ ላይ የሚሰፍርበትን ሥፍራ መወሰን፣ ከውጭ የሚመጡ ፅሁፎችን መምረጥ፣ ፅሑፉን መቀበልና አለመቀበል፣ የአዘጋጁ ኃላፊነት ሆኖ ሳለ፣ የአቶ መኮንን መመሪያ አጉል ልማድ ጥሎብን ሄዷል። ይህንን የቆየ ልማድ በአንድ ጊዜ ለመለወጥ መሞከር መኮንን ሀብተ ወልድንና ወልደ ጊዮርጊስን፣ ምናልባትም ከእነሱም አልፎ ጃንሆይን ጭምር ያስቆጣ ይሆናል የሚል ስጋት ነበረን።

በመጀመሪያ ጊዜ ሥራውን ሀ ብዬ ስጀምር የፃፍኩት ርዕሰ አንቀፅ አስተያየት መሆኑ እየገባኝ በመጀመሪያው ገፅ ላይ አወጣሁት። ይህንን ርዕሰ አንቀፅ ለናሙና ያህል አባሪ አንድ አድርጌ ከዚህ ጽሑፍ ጋር አያይዤዋለሁ። በሂደትና ውሎ በማደር የመጀመሪያውን ገፅ ለዜና መድበን፣ ሁለተኛው ገፅ የአስተያየት መስጫ ገፅ እንዲሆን አደረግን። በሁለተኛው ገጽ ላይ የአዘጋጁ ስም፣ የጋዜጣው መታወቂያ ርዕስ (name – plate or masthead) አድራሻና የአንባቢዎች ደብዳቤ ይታተም ጀመረ። በዚህ ጋዜጣ ላይ የአዘጋጁ ስም ሲጻፍ የመጀመሪያው ጊዜ ነበር። በእንግሊዝኛው ቋንቋ Editorial ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል እንዲፈልጉልኝ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስንና ሊቀ ሥዩማን አክሊሉን ጠይቄ «ርዕሰ አንቀፅ» የሚል ስም ስለሰጡኝ በጋዜጣው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሠፈረ። እስከአሁንም *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ ብቻ ሳይሆን የግል ጋዜጦችም በዚህ ርዕስ ይጠቀሙበታል።

በውጭ አገር አንዳንድ ጋዜጦች «ርዕሰ አንቀፅ» አይፅፉም፡፡ ርዕሰ አንቀፅ የፃፉ እንደሆነ ሂስና አስተያየት ስለሚፅፉ፣ ጠላት እናፈራለን፤ ማስታወቂያ አናገኝም ይላሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች እንደፈሪ ነው የሚቆጠሩት፡፡

ግርማዊነታቸው ኢትዮጵያን የዘመኑ ሥልጣኔ ተቋዳሽ እንድትሆን ያደረጉትን አስተዋፅኦና ጠላትም ከሀገራችን እንዲባረር የተሚገቱበትን የትግል መድረክ በማስታወስ በጋዜጣው ላይ ይፃፍ የነበረው ምስጋናና ውዳሴ በህዝቡ ዘንድ አሰልቺ ነገር ሆኖ የታየበት ጊዜ አልነበረም፤ ቢኖርም በግልፅ የሚነገርበት ጊዜ አላገጠመኝም፡፡ ከቤተ መንግስቱም ሆነ ከባለስልጣኖቹ አካባቢ «ይኸም በዛ» የሚል የቅሬታ ድምፅ ሲነገር ሰምቼ አላውቅም፡፡ እርግጥ ነው ወጣቱ ትውልድ የራሱ የሆነ አቋም ነበረው፡፡

መኮንን ሀብተ ወልድ የሰጡት መመሪያ አለምክንያት አልነበረም የሚል ግምት አለኝ፡፡ የቤተ መንግስቱን ፍላጐትና የህዝቡን ስሜት በትክክል ያውቁት ስለነበረ ሊሆን ይችላል፡፡

ይኸንን በምን አወቅህ ብትሉኝ አህዱን ዋቤ አቀርባለሁ፡፡ አህዱ እንዲህ ይላሉ፡-

> አፄ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ከተመለሱበት ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት ጋዜጦች (አዲስ ዘመን፣ ሰንደቅ አላማችንና ሄራልድ) ላይ የሚወጡ አብዛኞቹ ፅሁፎች የእሳቸውን ስም፣ ስራ ክብርና ታሪክ አለመጠን አጉልተውና አስፍተው በሚገልጡ የምስጋና (የውዳሴ) ቃላት ተሞልተው ማየት እጅግ የሚወዱ መሆናቸው በጋዜጣና ማስታወቂያ መስሪያ ቤት ታውቆ የቆየ እንደመሠረታዊ ባህል የሚታይ በስራም ሲፈፀም የኖረ ነገር ነበር፡፡[4]

በዚያን ዘመን የነበሩ የውጭ ሀገር ሰዎች በትችትም ሆነ በሽሙጥ ሲናገሩ «ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት ጋዜጦች አሏቸው፡፡ በአንዱ ንጉሠ ነገሥቱን ያመሰግኑበታል፡፡ በሁለተኛው ጣሊያንን ይሰድቡበታል» እያሉ ይሳለቁብን ነበር፡፡

ወልደ ጊዮርጊስ ጋዜጣውን ለሀያ ዓመታት ሲያዘጋጁ የተቸገሩበት ምክንያት እየገባኝ ከሄደ በኋላ፣ ለአጭር ጊዜ ጉብኝት ወደ ውጪ አገር ሄዱ፡፡ የሣንሱሩን ሥራ ተጠባባቂ ሆነው እንዲያከናውኑ በእሳቸው ስፍራ ሻምበል አጥናፉ መኮንን ተተኩ፡፡

ሻምበል አጥናፉ እኔ የምፅፈው ርዕሰ አንቀፅ አልጣማቸውም መሰለኝ እንደመሰላቸው እየሠረዙና ሌላ ቃላት እየተኩ፣ ቆንጠጥ የሚያደርገውን እያለዘቡ፣ ያትሙት ጀመር፡፡ ይኸ አሠራር ስላልጣመኝና በእጅጉ ስለከነከነኝ የእኔ ስም በጋዜጣው ላይ ታትሞ እንዳይወጣ አደረግሁ፡፡ ይኸ አድራጐቴ ከድፍረት ተቆጠረብኝና በየሳምንቱ ሚኒስትሩ ቢሮ በምናደርገው ስብሰባ ላይ ቀርቤ ምክንያቱን እንዳስረዳ ብላታ ግርማቸው አዘዙኝ፡፡

እኔ የምፅፈውን ርዕሰ አንቀፅ ሻምበል አጥናፉ እያረሙ ከእኔ አስተሳሰብ ውጪ የሆነ ነገር ይታተማል፡፡ ሻምበሉ የፅሁፉን ጥርስ ጥርሱን እያወለቁ ባዶ ድድ

[4] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* 268

እንዲታይ እያደረጉ ነው የሚል ቃል ሰነዘርኩ:: ብላታ ግርማቸው ለማናቸውም ነገር መልስ ለማግኘት የሚቸግራቸው ሰው አልነበሩም:: በእኔ አነጋገር ትንሽ ከአሰቡበት በኋላ «አቶ ነጋሽ የዕሁፌ ጥርስ እየወጣ ድዱ ብቻ ነው የሚታተመው የሚል አነጋገር አምጥቷል:: እኔ እንደሚታየኝ ካልተስተካከለና ከአገጠጠ ጥርስ ንፁህ ድድ ይሻላል» አሉ::

ይኸም እንደመመሪያ ተቆጥሮ *አዲስ ዘመን* ለብዙ ዓመታት ንፁህ ድዱን ሲያሳይ ቆይቷል:: አንድ ጋዜጣ አሳትሞ ለማሰራጨት የብዙ ሰዎችን ትብብርና ጥረት ይጠይቃል:: የሥነ ፅሁፍ ዝግጅት ክፍል ዜናውንና ኢንፎርሜሽኑን ፈልጐ ሲፅፍና አርቲክሎችን ሲያቀርብ፣ የማስታወቂያና የህትመቱ ክፍል በተመደበለት ገጽ ላይ የታዘዘውን ሥራ ሲያከናውን የዕለቱ ጋዜጣ ስራ አልቆ ወደ አልጋው ሂደ ይባላል:: ይኸ ሁሉ ዝርዝር ጉዳይ አዘጋጁን ስለሚመለከት የሥራው ድርሻ ቀላል ሊሆን አይችልም::

የጃንሆይን ፎቶግራፍና በየቀኑ ያከናወኗቸውን ተግባራት በቤተ መንግስቱ የተመደበው ሪፖርተር እየፃፈ ስለሚያቀርብ፣ ጋዜጣው ላይ ኘሮቶኮሉን ጠብቆ በስተራስጌ ይወጣል:: ከዘመናዊ ጋዜጣ አፃፃፍ አንፃር ይኸም አንዳንድ የቴክኒክ ችግር ያስከትላል:: የዕለቱ ታላቅ ዜናና ፎቶግራፍ መስፈር ያለበትን ስፍራ ለማስያዝ ቢታሰብም፣ ቅድሚያ ለቤተ መንግስቱ ዜና ስለሚሰጥ የሙያውን ጥያቄ አውቆ መርሳት ወይም መተው ግድ ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፎቶግራፍ ከአንድ ሚኒስትር ፎቶግራፍ ግርጌ ማውጣት ክብረ-ነክ ስለሚሆን የጋዜጠኛው ሙያ በ2ኛ ደረጃ መታሰብ ነበረበት::

አንድ ጋዜጣ የራሱ የሆነ ፐርሰናሊቲ ብቻ ሳይሆን የተለየ የአፃፃፍ ቴክኒክ እንዲኖረው የተደረገው አለምክንያት አልነበረም:: 1ኛ/ የዜናውን ምንነት በርዕሱና በዜና መክፈቻው አንቀፅ ማወቅ ስለሚያስችል ነው:: በዜና አፃፃፍ ድግግሞሽን ያስቀራል:: 2ኛ/ በጋዜጣው ላይ የቦታ እጥረት ቢያጋጥም ወይም ዜናው ከተፈለገው በላይ ቢረዝም፣ ዜናውን እንደገና መፃፍ ሳያስፈልግ በቀጥታ ዝርዝር ጉዳዩን ከግርጌ ቆርጦ ማስቀረት ይቻላል:: 3ኛ/ የዚህ አይነቱ የጋዜጣ አፃፃፍ ቴክኒክ ሪፖርተሩ ዜናውን ቶሎ ለመፃፍ ያስችለዋል፤ ችግር አይኖርበትም:: ዜናውን ለማስረዘም ቢፈለግ ዜናው እንዳለ ሆኖ በዝርዝር ጉዳዩ ላይ ማከል ይቻላል::

ዘመኑ የቴክኖሎጂ ጥበብ የተስፋፋበት፣ የጥድፊያና የጊዜ ሽሚያ ያለበት እንደመሆኑ መጠን፣ አንባቢው 50 እና 100 ገጽ ጋዜጣ አንብቦ ለመረዳት ጊዜ ስለሚወስድበት ርዕሱንና የመክፈቻውን አንቀፅ ብቻ ተመልክቶ የጋዜጣውን ይዘት ሊረዳ ይችላል::

በመንግስት ጋዜጣ ላይ ተቀጣሪ ሆኖ መስራት ከግል ጋዜጣ ፖሊሲና አሠራር የተለየ ባህርይ እንዳለው ቀደም ብዬ ብገነዘብም፣ ባለስልጣኖቹን ጥቃቅኑ ነገር ሁሉ እንደሚያስከፋቸውና እንደሚያሳስባቸው ሳይ በዚህ ሥራ ምን ያህል እንደምገፋበት ራሴን አበክሬ እጠይቅ ነበር::

በጊዜው የነበረኝ ዕድል የታዘዝኩትን እየሠራሁ መቆየት አሊያም ወደውጭ ሐገር ተመልሼ እየሠራሁ መማር እንደነበር ሳላስብበት አልቀረሁም:: ይኸንን ሃሳብ እያወጣሁና እያወረድኩ እያለሁ ወዳጄና የትምህርት ቤት ጓደኛዬ

የነበረው አቶ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ወደ ሩሲያ ሄደን ለመማርና ለመስራት እንደምንችል ነገረኝ። ዮሐንስ በዚያን ጊዜ ጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ስለሚያስተምር በትምህርት ሚኒስተር በኩል ለጋዜጠኝነት ሥራ ስኮላርሺፕ መምጣቱን ያውቅ ነበር። ጥያቄያችን በትምህርት ሚኒስትር በኩል ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ሩሲያ ለመሄድ በዝግጅት ላይ እንዳለን በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ አምደ ሚካኤል ደሣለኝ የእኔን ስም ከሊስቱ ላይ ሠርዘው ሌላው ጓደኛችን እንዲሄድ አደረጉ። መቀየሜ አልቀረም። ነገሩ «ጥንቸል ዘልላ ዘልላ ወደ መሬት» እንደሚባለው ሆነና ምንም ለማድረግ አልቻልኩም።

እኔን ለምን እንዳስቀሩኝ ለመረዳት አልቻልኩም። ምናልባትም ከሚኒስትሩ የሚሰጠኝ መልስ ለስራ ታስፈልጋለህ የሚል እንደነበር ከነበረው ልምድ ለመናገር እችላለሁ። ዮሐንስ ወደ ሞስኮ ሄዶ ሁለት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ በጤና መታወክ ምክንያት ህይወቱ አልፎ አስከሬኑ ወደሐገሩ ተላከ። የትውልድ ሐገሩ ደሴ ስለነበረ የቀብሩ ስነ ስርዓት እዚያ ተፈፅሟል።

በዜና አሰባሰብ በኩል ያጋጥመን የነበረውን ችግር መጥቀሱ አስፈላጊ ይመስለኛል። ዜና ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አንድ ትርጉም ለመስጠት እንደሚያስቸግር አውቃለሁ። እንደየሀገሩ ልማድ፣ ባህልና የዕድገት ደረጃ ለአንዱ ሀገር ዜና የሚባለው ለሌላው ሀገር ዜና ላይሆን ይችላል። ለተማረ ሰው ዜና የሚሆነው ለመሀይም ዜና ላይሆን ይችላል። ለሴቶች ዜና የሚሆነው ለወንዶች ዜና አይሆንም። ለዚህ ለአሁኑ ስራ ያህል ዜና ማለት አያሌ አንባቢዎችን የሚስብ፣ ወቅታዊና ትክክለኛ የሆነ ትርጉም የሚሰጥ ኢንፎርሜሽን ነው እንበል። ዜና አንባቢ የሚፈልገውና ጥቅም አገኝበታለሁ የሚልበት ኢንፎርሜሽን ነው።

በጊዜው የነበሩት አንዳንድ ባለስልጣናት ሹመትና ኃላፊነት ሲሰጣቸው ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ይቸገሩ ነበር። በአንድ ፊት በህገ መንግስቱ እንደተደነገገው ተጠሪነታቸው ለንጉሡ ነገሥቱ ስለሚሆን፣ ሁሉን ነገር «የበላይ አካል» ሳያውቀው ለጋዜጠኛ ኢንፎርሜሽን መስጠት ይጨንቃቸው ነበር። ባጠ ፋም ባለማም የእኔ ኃላፊነት ነው ለማለት ስለማይደፍሩ አንድ ነገር ለመናገር እየሰጉ «ልማከርበት» በማለት ቀጠሮ ያበዛሉ። ያለሙያው በሥልጣን ላይ የሚመደብ ሹም ጋዜጠኛ አታሳዩኝ የሚልበት ጊዜ ነበር። ጸሐፊዋ ቢሮ ተቀምጣ ስብሰባ ላይ ናቸው፤ ዛሬ ስራ በዝቶባቸዋል፤ ወደግቢ ተጠርተው ሄደዋል፤ ስለምትል የዜናው ወቅታዊነት ይቀራል፤ ያልፋል። ወሬው በከተማው ውስጥ ተነግሮና የተሳሳተ መስመር ይዞ በየመሸታ ቤቱ ስለሚወራ ከዚያ በኋላ ዜና መሆኑ ይቀራል።

ባለስልጣኖቹ ለጋዜጠኛ ኢንፎርሜሽን እንዲሰጡ የሚያስገድድ ህግ አልነበረም። እኛ ኢትዮጵያውያን ሂስን በፀጋ የመቀበል ልምድ ያካበትን ሰዎች አይደለንም፤ አብዛኞቻችን በሰው ማፌዝ እንወዳለን እንጂ በራሳችን የመሳቅ ልምድ የለንም፤ በአሽሙር፣ በለበጣ፣ በቅኔ መናገር ስለምንወድ ግልፅነት ይጐድለናል፤ ይኸም ከመጥፎ ባህሪያችን አንዱ ይመስለኛል።

መጽሀፍ፣ ሙዚቃ፣ ሥዕልና ፊልም መተቸት ለጋዜጠኛ የተፈቀደ መብት ነው። የሥራውም ባለቤት የሆነ ደራሲ፣ ሙዚቀኛም ሆነ ሰዓሊ ሥራውን ለህዝብ የሚያቀርበው ይወደድልኛል ወይም ይጠላብኛል ብሎ አምኖ ስለሆነ ሂሱን በፀጋ መቀበል ይጠበቅበታል። ጋዜጠኛው የደራሲውን ወይም የሙዚቀኛውን (ፊልምም ሊሆን ይችላል) ሥራ ከመተቸት ፈንታ የባለሙያውን የግል ህይወት ቢተች በስም ማጥፋት ይጠይቅበታል።

በዲሞክራሲ ሥርዓትና በኘሬስ ነፃነት በሚያምኑ አገሮች ደራሲያን ሥራዬ ተተቸ በማለት ፍርድ ቤት አይሄዱም። በሀገራችን ሥራው ወይም መስሪያ ቤቱ የተነቀፈበት ሃላፊ ስሜቱ በቀላሉ ይነካና ከማኩረፍ አልፎ ለማጥቃትና ለመበቀል ይነሳል። የጋዜጣ አዘጋጅ በነበርኩበት ዘመን በየጊዜው የሚያጋጥመኝ አስገራሚ ነገር ይሄ ነበር። በጋዜጣ ተሰድቤያለሁ፤ ክብሬ ተነክቷል፤ የሰው መሳቂያና መሳለቂያ ሆኛለሁ የሚል ተቆርቋሪ በጋዜጣው መልሶ ይሳደባል እንጂ ወደ ፍርድ ቤት ሄዶ በህግ ለመካስ አይፈልግም። ተሰደብኩ ባዩ በተራው ስድቡን ያዥጐደጉደዋል። የመልስ መልስ ሲፃፉ ሶስተኛው ወገን ከዳር ቆሞ «ነገረው አይደለም!» እያለ ጠቡን ያባብሰዋል። በዚህ ምክንያት ጋዜጣው አንባቢ ቢያገኝም፣ የሚከራከሩበት ርዕሰ ጉዳይ ለህዝብ ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ብሎ መወሰን ያስፈልግ ነበር። አንድ የታወቁ ባለስልጣን ተውኔት ይጽፉና በመድረክ ይታያል።[5] አቶ አሀዱ ሳቡሬ ተውኔቱን በማስመልከት ሒስ ይጽፋሉ። ሒሱ ባለስልጣኑን አላስደሰተም። ከጥቂት ቀናት በኋላ አቶ አሀዱ አንድ ወዳጃቸው ሲያገባ ከዕድምተኞቹ አንዱ ሆነው የመልስ ግብዣ ይደረግበት ወደነበረው ወደ ባለስልጣኑ ቤት ይሄዳሉ። የተውኔቱ ፀሀፊ አቶ አሀዱን ሲያዩ እዚያ ሁሉ አጀቢ ፊት ተኮሳትረው «በጋዜጣ እንደዚያ ሰድበኸኝ አሁን ደግሞ እንጀራዬን ልትበላ ቤቴ ድረስ መጣህ ?» ይሏቸዋል። የባለስልጣኑ አነጋገር በባህላችን ቅር የሚያሰኝ ቢሆንም፤ «የተንገበገቡለትን እንጀራ አልማርኩትም» በማለት አቶ አሀዱ ስድቡን እያረረ ሣቀ የባህር ማሽላ ያደርጉታል። ቀደም ሲል ለማስረዳት እንደሞከርኩት የሀሳብ ልዩነትን ማስተናገድና በፀጋ መቀበል ገና ልንማረው የሚገባ ባህል ወይም ልማድ ይመስለኛል።

በውጪ ሐገር ስሜ በጋዜጣ ጠፍቷል፤ ክብሬ ተነክቷል፤ የህዝብ መሳቂያና መሳለቂያ ሆኛለሁ፤ ወይም በዚህ ፅሁፍ ምክንያት ሥራዬ ተበድሏል፤ ዕቅዴ ታጉሏል፤ የሚል ሰው ወደ ፍርድ ቤት ሔዶ ክስ ይመሠርታል። ፍርድ ቤቱ ከሳሽ ተበድሏል ብሎ ከአመነበት ዳጐስ ያለ ካሣ ያሰጠዋል። የሚከፈለው ካሣ ቀላል አለመሆኑን ለማመልከት ያህል 3 ምሳሌዎች እጠቅሳለሁ። እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም ቪክቶር ፍያዜል (Victor Fiazell) የተባለ ሰው በመጠጥ ኃይል እየተሽነፉ መኪና የሚያሽከረክሩ ሰዎች ክሱ እንዲነሣላቸው ጉቦ (ሙስና) ይቀበላል በማለት የዳላስ ቴሌቪዥን ስሜን አጥፍቶ ዜና አሠራጭቷል የሚል ክስ ይመሠርታል። ፍርድ ቤቱ ከሳሹ ተበድሏል በማለት 58 ሚሊዮን ዶላር ካሣ እንዲከፈል በይኗል። አፈፃፀሙ በምን እንዳለቀ አላውቅም። እ.ኤ.አ 1990

[5] የተውኔቱ ደራሲ ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ነበሩ፤ መኰንን ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በምኒስትርነት፣ በጠቅላይ ምኒስትርነት እና በህግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት አገልግለዋል። በ1955 ዓ.ም. አረፉ።

ዓ.ም «ፊላደልፊያ ኢንኳየረር» የተባለው ጋዜጣ በስም ማጥፋት ክስ 6 ሚሊዮን ዶላር ካሣ ከፍሏል፡፡ የአሜሪካ ፕሬዝዴንት የነበሩት ቴዎዶር ሩዝቬልት (Theodore Roosevelt) ሰካራም ናቸው በማለት *ዲትሮይት ኒውስ* (Detroit News) የተባለ ጋዜጣ ይወነጅላቸዋል፡፡ ፕሬዝዳንቱ ስሜን አጥፍቷል በማለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀርባሉ፡፡ ጋዜጣው ይቅርታ ጠይቆ እርማት ቢያደርግም ሩዝቬልት ክሱን አላነሳም ተበድያለሁና መካስ አለብኝ በማለት ሙግቱን ቀጠሉ፡፡ የፍርድ ቤቱንም ምክር ለመቀበል አልፈለጉም፡፡ ፍርድ ይሰጠኝ አሉ፡፡ ፍርድ ቤቱ የ6 ሣንቲም ካሣ ፈረደላቸው፡፡ በዚህ ውሳኔ ፕሬዝዳንቱ አጥፊው ጋዜጣ ተረትቷል ብለው በመደሰታቸው ካሣውን ተቀብለው ፋይሉ ተዘግቷል፡፡

የእኛ ፍርድ ቤት 58 ሚለዮን ብር ካሣ ያስከፍል አንልም፡፡ በስም መጥፋት ምክንያት የተበደለ ሰው ሰብአዊ መብቱ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ የጋዜጠኞችን ሥራ የሚገድበውና ለቅጣትም የሚዳርገው አስቸጋሪ ህግ የስም ማጥፋት ህግ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

*የአዲስ ዘመን ጋዜጣ* ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ ዕለታዊ ስለሆነ በተለያዩ ምክንያቶች በቂ የሀገር ውስጥ ዜና ለማግኘት እንቸገር ነበር፡፡ የውጭ ሀገር የዜና ወኪሎች የሚሸጡልንን ዜና እየተረጐምን እናወጣለን፡፡ አንባቢያን የሚጽፏቸው መጣጥፎች ፖሊሲውን የሚቃረኑ ወይም ለምንም የማይጠቅሙ ይሆኑና ሳይታተሙ ይቀራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች ቢሮ ድረስ እየመጡ ይቆጣሉ፡፡ ቁጣቸውን በትዕግስት እንድንቀበል የሚያደርገን «ጽሁፍ የራስ፣ ሚስት ግን የሰው ደስ ትላለች፤» የሚለው የቻይናዎች አባባል ነበር፡፡

ዜና የሚቃረምባቸው ሥፍራዎች ፍርድ ቤቶች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ አየር መንገዶች፣ የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ሪፖርተሮቻችን ሲቀናቸው ከእነዚህ ሥፍራዎች አንዳንድ ዜና ይዘው ይመጣሉ፡፡ ሪፖርተሮቹ ዜና ለማግኘት በየመሥሪያ ቤቱ ደጅ ሲጠኑና ሹማምንቱን ሲለሚመጡ ውለው ምንም ኢንፎርሜሽን ሳይዙ ወደ ቢሮ በሚመለሱበት ጊዜ የመንዜውን ገበሬ ብሶት እንዲህ እያሉ ያዜማሉ፡-

ጨርቄ ፊቷን ነጪት ዘመድ እንደሞታት
ለእያንዳንዱ ቱኪ (ጭቃሹም) ስቋጥር ስፈታት!

ዜና ምን ማለት እንደሆነ ውሱንና አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ስለማይገኝለት የሪፖርተሮችን ችሎታ መፈታተኑ አይቀርም፡፡ የጋዜጠኝነት ሥራ የጀመረ አንድ ሪፖርተር ዜና ዕፎ እንዲያመጣ ሃላፊነት ይሰጠዋል፡፡ ትዕዛዙ ለአንድ ጉባኤ ንግግር የሚያደርግ ሰው ስላለ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በትክክል ተከታትሎ ዜናውን እንዲያቀርብ ነበር፡፡ ንግግር የሚያደርገው ሰው መድረክ ላይ ወጥቶ ንግግሩን ሲጀምር ያልተጠበቀ ጠላት ተኩሶ ይገድለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሪፖርተሩ የማስታወሻ ደብተሩን አጣጥፎ ወደ ቢሮ ይመለሳል፡፡

«ዜናውን አመጣህ?» ሲል አዘጋጁ ይጠይቃል፡፡

«አላመጣሁም» ይላል ሪፖርተር፡፡

«ለምን ?»

«ተናጋሪውን አንድ ሰው ተኩሶ ስለገደለው የተናገረው ነገር የለም» ይላል:: የሰውዬው መገደል ትልቅ ዜና እንደነበር አልታየውም::

*አዲስ ዘመን* የሚጠቀምበት ሌላው የዜና ምንጭ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ነበር:: በየጠቅላይ ግዛቱ ርዕሰ ከተሞች የተመደቡት ሪፖርተሮች (አብዛኞቹ ለማለት ይቻላል) የሙያ ብቃታቸው አጠያያቂ ነበር:: በአዲስ አበባ ለቤተ መንግስቱ ወሬ ከፍ ያለ ክብር እንደሚሰጠው ሁሉ በየጠቅላይ ግዛቱ የሚሾሙት ባለስልጣናት የአገሩን ፀጥታ አስጠበቁ፤ ግብር እንዲሰበሰብ አደረጉ፤ በማለት እየተወደሱ በስልክ የሚላከው ወሬ ውሎ አድሮ አሰልቺ መሆኑ አልቀረም:: የገበሬው ችግር፣ የባለ ዕርስቱ ተፅዕኖ፣ የመሬት ላራሹ ጉዳይ፣ የፍትህ መጓደል፣ ጠቅላላው የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ቀውስ የዜና ምንጭ መሆኑ ቢታወቅም የሪፖርተሩ ውሱን ችሎታና  የመንግስት ሣንሱር ማዕቀብ ማድረጋቸው አልቀረም::

የጋዜጠኝነት  መሠረታዊ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ የዜናን ባህርይና ምንነት ለመተንተን የሚረዱ ጠቃሚ የሆኑ መስፈርቶች ይዘረዘራሉ:: የዜናው ወቅታዊነትና ቅርብነት ፣ የዜናው ክብደትና ትልቅነት፣ የሚያስከትለው ልብ ሰቀላ፣ ከዚህ ቀደም ያልታየና ያልተሰማ ወይም ያልተለመደ መሆኑ፣ ግጭትን የሚያስከትል ባህሪ እንዳለው (የሀሳብና የአካል ግጭት)፣ የጾታ ቅራኔ፣ ስሜትን የሚቀሰቅስ የዜና አይነት መሆኑና የዕድገት ሂደትን የሚያመለክት መሆኑ - በእነዚህ ባህሪያት ዙሪያ እየተሽከረከረ የሚቀርብ ኢንፎርሜሽን በዜናነት ሊፈረጅ ይችላል:: ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ባለመተዋወቅ የተነሳ በዜና አገልግሎት በኩል የሚቀርቡልንን ሀተታዎች ወደ ዜና ስንመልስ  ተጨባጭ ፍሬ ነገር (fact) ይጐላቸው ነበር::

*በአዲስ ዘመን* የምናቀርበው አንዳንድ ዜና ባለስልጣኖቻችንን የሚያሳጣ መስሎ ሲታያቸው የጃንሆይን ሁሉ-ገብ የሆነ ሥልጣን በማንተራስ አስቀድመው አቤቱታ ማቅረብ የተለመደ ዘዴ ነበር:: አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል:: በአንድ ወቅት በሱማሊያና በኬንያ ድንበር አካባቢ የኮሌራ በሽታ መከሰቱን የሚገልፅ ዜና በሮይተርስ የዜና ወኪል ተሰራጨ:: ይኸ ወረርሺኝ ነገ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊገባ ስለሚችል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ምን አይነት ቅድመ ዝግጅት አድርጓል የሚል ፅሁፍ አስተላለፍን::

በጊዜው የነበሩት የጤና ጥበቃ ሚኒስትር የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ህዝብን ከማሸበርና ስጋት ላይ ከመጣል በስተቀር ፣ እንዲሁም ቱሪስቶች ወደ አገራችን እንዳይገቡ ከማድረግ በስተቀር፣ ፋይዳ የለውም በማለት ለጃንሆይ አቤቱታ አቀረቡ:: የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ጃንሆይ ፊት ተጠርተው «ሥራውን አልቻልከው እንደሆነ ሌላ ሰው ይደረግበት» በመባላቸው ሚኒስትሩ በጣም አዝነው ሲበሳጩ እንደነበር አስታውሳለሁ::

ሚኒስትሩን የሚከስሱት ሰዎች አቤቱታ ሲያቀርቡ እንዲያው በደፈናው አልነበረም:: የማስታወቂያ መሥሪያ ቤት መንግስትና ህዝብ እንዲያገለግል ጃንሆይ ያቋቋሙት መስሪያ ቤት መሆኑን ጠቅሰው፣ ጋዜጠኞቹም የመንግስት ደሞዝ እየበሉ መንግስትን የሚያሣጣ ስራ ይሠራሉ በማለት ክሱን አሳምረው ነው የሚያቀርቡት:: እነዚህ ሰዎች በአብዛኛው እነማን ነበሩ? አንጋፋው

ጋዜጠኛ ክቡር አቶ አሀዱ ሳቡሬ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የማስታወቂያ ሚኒስትር ሆነው ወደ ቤተ መንግስት እየተጠሩ ቀጥና ተግሣፅ ይደርስባቸው ስለነበር አሳጮቹ እነማን እንደነበሩ እንዲህ በማለት ያስተዋውቁናል፡፡

እነዚህ ሰዎች «እበላ ባይ፣ አድርባይ፣ አስመሳይ የሆኑ በቤተመንግስቱ አካባቢ የሚርመሰመሱ፣ ቀጣፊዎችና መልቲዎች ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተቆርቋሪዎችና አሳቢዎች በመምሰል የሚፈፅሙት የተንኮል ሥራ መሆኑን አውቅ ነበርና ጃንሆይ በመቆጣታቸው አልተደነቅሁም» በማለት ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡

ማተሚያ ቤቱም የሚያስከትለው ችግር ቀላል አልነበረም፡፡ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሲታተም እንደአሁኑ ጊዜ በኮምፒዩተርና በኦፍሴት (offset) መሣሪያ እየታገዘ አልነበረም የሚሠራው፡፡ እያንዳንዱ ፊደል በእጅ እየተለቀመ፣ ጊዜ በሚወስድና አዝጋሚ በሆነ አሠራር ነበር የዕለቱ ሥራ የሚከናወነው፡፡ ከጊዜ በኋላ «ሞኖ ታይፕ» የተሰኘ የህትመት መሣሪያ በመምጣቱ በመጠኑም ቢሆን ሥራው ሊቃለል ችሏል፡፡ ከእኔ በፊት በነበረው አሠራር የዕለቱ ዜና፣ ኢንፎርሜሽንም ሆነ ማስታወቂያ፣ ወደ ህትመት የሚላከው በጋዜጣው ገጽ ላይ የት ቦታ እንደሚወጣ ሳይገለፅ፣ እርዝማኔውና እጥረቱ ሳይለካ ስለነበረ፣ የርዕሱ አምድና ወሬ ከተለቀመ በኋላ የጋዜጣው ገጽ ሁሉንም ፅሁፍ ሳይዝ ይቀርና ይበተናል፡፡ ይኸንን ችግር ለማስቀረትና የገጹንም አቀማመጥ መልክ ለማስያዝ «ዱሚ» መሥራት ያስፈልግ ነበር፡፡ በታይፕ የተፃፈው ፅሁፍ በህትመት መሣሪያ ከመለቀሙ በፊት እያንዳንዱ ወሬና ሥዕል በጋዜጣው ገጽ ላይ ምን ያህል ስፍራ እንደሚሰጠው በሂሳብ እየተሠራ መቅረብ ነበረበት፡፡ እዚችም ላይ እኔ ትንሽ አስተዋፅኦ ማድረጌ አልቀረም፡፡

በማተሚያ ቤቱ በኩል የነበረው ሌላው ችግር ለህትመቱ ሥራ የሚያገለግሉት ፊደላት ብዙ ያገለገሉ ስለነበሩ አንዷ እግር አንካሣ ሌላዋ ወልካሣ ይሆኑና የህትመቱ ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ ከአራሚዎቹ አምልጣ ወይም ተዘልላ የምትወጣ ፊደል ያልተጠበቀ ውዝግብና ችግር ትፈጥራለች፡፡ ለምሳሌ ያህል /ስ/ የምትለዋ ፊደል «ሳ» ብትሆን «ለ» «ላ» ሆና ብትታተም አሳፋሪ የሆነ ችግር ይከሰታል፡፡ ወይም አንዷ ፊደል እስከጭራሹ ትዘለልና ምድር ቁልቢጥ ትሆናለች፡፡ ለምሳሌ ያህል ግርማዊነታቸው ብለን ስንፅፍ አንድ ፊደል የተዘለለችበት ጊዜ አጋጥሟል፡፡ የዚህ አይነት ስህተት ታትሞ ሲወጣ ባለስልጣኖቹ ሆነ ተብሎ የተደረገ እየመሰላቸው ሠራተኞቹን ለማስቀጣትና ሃላፊነታቸውን ለማስወረድ ይሯሯጡ ነበር፡፡ በፈረንጁ ዓለም ሰው ይሳሳታል የሚለው አባባል ግንዛቤ ስለተሰጠው Honest mistakes ስህተት የመስራት ነፃነት በሚለው ስርዓት ውስጥ ይካተታል፡፡ To err is human to forgive divine እንደሚባለው፡፡

በማተሚያ ቤቱ ውስጥ የተለያየ መጠን ያላቸው ለርዕስ የሚያገለግሉ ፊደላት በብዛት ስላልነበሩ የጋዜጣውን ትዕይንተ-ገጽ ለማሳመር ችግር ነበረብን፡፡ የእርማቱን ሥራ ማታ ማታ የሚሠሩት የቤተ ክህነት ሰዎች ነበሩ፡፡ ብላታ

ወልደ ጊዮርጊስ አይተውት እኔም በአዘጋጅነቴ ተመልክቼው ወደ ማተሚያ ቤት የሚላከውን ፅሁፍ አራሚዎቹ ለሚኒስትሩ ስልክ ደውለው የራሳቸውን አስተያየትና የመሰላቸውን የይሆናል ትርጉም አክለው ወሬው እንዳይታተም ማድረግ ይችሉ ነበር፡፡

የመንግስት ጋዜጣ አይነተኛ ባህሪው በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት ልሣን ወይም አፈቀላጤ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በህዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ከግል ጋዜጣ ይሻላል ለማለት ያስቸግራል፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት በህዝብ ዘንድ ምን ያህል ተወዳጅነት አለው? የሚለው ጥያቄ በጋዜጣውም ሥራ ላይ ይንፀባረቃል፡፡ የጋዜጣ አንዱ ተግባር መንግስት የሚያወጣውን ህግና ፖሊሲ ከህዝብ ጋር ማስተዋወቅ ነው፡፡ ለህዝቡ ደህንነት፣ ለማህበራዊና ለኢኮኖሚ ዕድገት ሲባል የሚዘረጉትን የዕድገት አውታሮች፣ ዕቅዶችንና ተግባራዊነታቸውን ያብራራል፡፡ ጉድለታቸውንም ይጠቁማል፡፡ ያሳስባል፡፡ ይወቅሳል፡፡ መልካም ስራ ሲሰራ ያመሰግናል፡፡

የግል ሚዲያ ባለበት አገር መንግስት የህዝቡን ህገ መንግስታዊ መብት እንዲጠብቅ፣ ፍትህና ርትዕ እንዳይጓደል አለአግባብ የሆነ ድርጊት እንዳይፈፀም፣ ህዝቡን ወክሎ ይሟገታል፡፡ ዋናው ችግር መንግስት ለህዝብ ቆሚያለሁ ሲል የግሉም ሚዲያ ለህዝቡ የማስበው እኔ ነኝ ማለቱ ነው፡፡ እውነተኛው ማን እንደሆነ ሊመሰክር የሚችለው ተጠቃሚው ህዝብ ራሱ እንደሆነ መታወቅና መታመን አለበት፡፡

መንግስት ለራሱ ሲል የሚያደርገውን አድሎአዊነት አስወግዶ ሚዲያው ትክክለኛና ሚዛናዊ የሆነ ሥራ ለመስራት የሚችለው ከመንግስት እጅ ተላቅቆ ለኩባንያ ወይም ለግለሰቦች ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡ ይኸ በውጪው አለም የታወቀና የተለመደ አሠራር ነው፡፡ የግል ጋዜጣ የንግድ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ለህዝቡ መስጠት የሚገባውን አገልግሎት ቸል በማለት በንግዱ ስራ ላይ የሚያተኩርበት ጊዜ ያጋጥማል፡፡ የዚህ አይነቱን ስህተት እንዲታረም አንባቢው ህብረተሰብ፣ የፍትሐ ብሔሩና የወንጀለኛው መቅጫ ህጐች፣ የንግድ ህግ፣ የፕሬስ ካውስልና የፕሬስ ህግ፣ የመሳሰሉ ተቋሞች ከፍ ያለ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በተለያየ ምክንያት አንባቢው ህዝብ ደንበኛነቱን የሚነፍገው ጋዜጣ ዕድሜው አጭር እንደሚሆን አያጠያይቅም፡፡

በመንግስት ጋዜጣ ላይ የሚሠሩ ሪፖርተሮች ከሣንሱርና ከህሊናቸው ጋር እየተሟገቱ የሚያቀርቡት ራስን በራስ ሣንሱር ያደረገ ሪፖርት ነባራዊ (objective) ወይም የተመዛዘነ ሊሆን አይችልም፡፡ ይኸንን ችግር ከነበረን ተሞክሮና ልምድ ለመናገር ይቻላል፡፡

በሐገራችን ውስጥ የመንግስት ጋዜጣ ብቻ በነበረበት ዘመን፣ ጋዜጠኛው አላሠራም ብላችሁኛል በማለት ሥራውን ለቅቆ ራሱንና ቤተሰቡን ማስራብ ስለማይፈልግ ከዓመት ዓመት የማትጨምረውን አነስተኛ የወር ደሞዝ እየተቀበለ የጡረታ ጊዜውን ሲጠብቅ ይቆያል፡፡ የደሞዙን ሲሶ የምትሆን የጡረታ አበል አስመድቦ ከሥራ ይሰናበታል፡፡ ከዚያ በኋላ ምን አይነት ህይወት እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም፡፡

እኔ የጡረተኛው ህብረተሰብ አባል ስለሆንኩኝ ጡረተኛ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አውቃለሁ። በ«ብሌን» መፅሄት «በድጹ ይስቃል» በሚል ርዕስ ያሠፈርኳት ይህች ግጥም የምታስተላልፈው መልዕክት ስለሚኖራት ከዚህ ፅሁፍ ጋር አባሪ አድርጌ (አባሪ ሁለት) አቅርቤያታለሁ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት መውደቂያው እየተቃረበ ሲሄድ ጃንሆይም ሆኑ ባለስልጣኖቻቸው ሥጋት ላይ መውደቃቸው አልቀረም። በተለይ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ዶ/ር ተስፋዬ ገብረ እግዚአ ለፕሬስ ክፍል ይሰጡት የነበረው መመሪያ ከሣንሱርነትም አልፎ ጋዜጠኞቹ ምንም ነገር እንዳይጽፉ እጃቸውን የፊጥኝ አስሮ የሚያስቀምጥ መመሪያ ነበር። ለትዝብቱ ያህል መመሪያውን ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ፡-

> *ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚቀርብ ማስታወሻ*
>
> *ግርማዊ ሆይ፣*
>
> *የሚከተለው ለአቶ ተገኝ የተሻወርቅ፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የተሰጠ መመሪያ ነው።*
>
> *ስለ ፕሬስ ድርጅት ኃላፊነትና ስለ ጋዜጦች አመራር ጉዳይ ስብሰባ እያደረግን ብዙ ጊዜ ተነጋግረንበታል። በተለይም ህዳር 29/1964 ዓ.ም እርስዎና ዋና አዘጋጆች በተገኙበት በጋዜጦች የሚወጡትን ስህተቶች ስለመቀነስ ዘዴ አንዳንድ ውሳኔ ተደርጓል።*
>
> *እነዚህን ውሳኔዎች በሥራ ላይ ለማዋል ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር የተመለከቱት መመሪያዎች ተሰጥተዋል»*

ይልና ከዚሁ ጋር በማያያዝ በጋዜጣ ሊገለጡ የማይገባቸው በሚል ርእስ ሥር የሚከተሉት አበይት ጉዳዮች ሰፍረው እናገኛቸዋለን፡-

> *1. የንጉሠ ነገሥቱን አገዛዝና ዘውድ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥት የሚነካ፣ 2. የንጉሳውያን ቤተሰቦችንና የሚኒስትሮችን ክብር የሚነካ፣ 3. የሥራ ፈት ብዛት፣ 4. የአሠሪና ሠራተኛ ግጭት፣ 5. የተማሪዎች ሁከት፣ 6. የግብር ጭማሪ፣ 7. የኑሮ ውድነት፣ 8. የደመወዝ ጭማሪና የመንግሥት ሠራተኞች የሚገልጡት ቅሬታ፣ 9. አድማን የሚመለከት ጽሁፍ፣ 10. ስለ መሬት ስሪት ፣ 11. ወታደራዊ ጉዳይ (ስትራቴጂክ ቦታዎች የወታደር ደመወዝና የሠራዊቱ በጀት ወ.ዘ.ተ) ፣ 12. የሃይማኖት ልዩነት፣ 13 የጐሣ ልዩነት፣ 14. አንዱን የውጭ አገር መንግሥት አቋም የሚነካ፣ 15. የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን አቋም የሚነካ፣ 16. የኢትዮጵያን ሕዝብ ሞራል ዝቅ የሚያደርግ፣ 17. የኢትዮጵያን አንድነት የሚለያይ፣ 18. የሴተኛ አዳሪዎችን ብዛት የሚገልጽ፣ 19. የለማኞችን ብዛት የሚገልጽ፣ 20. ብልግናን የሚገልጹ ጽሐፎች፣ 21. የኢትዮጵያን በጀት የሚመለከት ጽሐፍ፣ 22. መንግሥት ያወጣውን ፕላን ያለአግባብ የሚተች ጽሑፍ፣ 23. የሰውን ስም ያለአግባብ የሚያጐድፍ፣ 24. የኢትዮጵያን የኑሮ ደረጃ ከሌሎች አገሮች ጋር በመጥፎ ሁኔታ የሚያወዳድር፣ 25. የሌላውን አገር የሶሺያል ፍልስፍና (አይዲኦሎጂ) ለማስፋፋት የሚሞክር ጽሑፍ፣ 26. የፓርላማ አባሎች በየጊዜው የሚያደርጉትን ክርክር የሚያብራራ*

> *ጽሑፍ፣ ልዩ መመሪያ ካልተሰጠ በቀር ከላይ የተዘረዘሩት አርዕስተ ነገሮች በጋዜጣ አይገለጡም። የጊዜው ሁኔታ ለሚያስከትለው ጉዳይ ልዩ መመሪያ ይሰጣል።*
>
> ጥር 30 ቀን 1964 ዓ.ም
>
> *ታዛዥ አገልጋይዎ*
>
> *ዶ/ር ተስፋዬ ገብረ እግዚእ*

*ከመንገዴ ወጣሁ መሰለኝ! ወደጋዜው ልመለስ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ በመንግስት በጀት የሚንቀሳቀስ ቢሆንም የዛሬ 45 ዓመት የማስታወቂያ ሚኒስቴር የአመት በጀት ከ6 ሚሊዮን ብር በታች እንደነበር አስታውሳለሁ። ጋዜጣው አንባቢን እንዲስብ አድርጐ ለማቅረብ መስሪያ ቤቱ ገንዘብ የለኝም ስለሚል ከሳንሱሩ ጋር እነዚህ ጥቃቅን የሆኑ የስራ መሰናክሎች እየተጨመሩ የጋዜጠኛውን ሞራል ያላሽቁት ነበር።*

*ብርቱና ብልህ የሆነ ጋዜጠኛ ጠላትም ወዳጅም የለውም የሚል አነጋገር አለ። የሚጽፈው ዜና እውነትን፣ ሚዛናዊነትን፣ ትክክለኛነትንና ተአማኒነትን አጠ ቃሎ የተላበሰ ስለሚሆን፤ አንባቢው ሕዝብ ያምነዋል፤ ያከብረዋል። ምናልባትም ይፈራዋል።*

*ቀደም ሲል እንደተገለፀው እኛ ያቀረብነው ፅሁፍ በጋዜጣ አልወጣልንም በማለት ቅሬታ የሚያሰሙ አንባቢያን ብዙ ቢሆኑም፣ የህዝቡ ፍላጐት ከመንግስቱ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን መሆኑን የማያውቁ ብዙዎች ነበሩ። በዚሁ መጠን ደግሞ በጋዜጣው የሚወጣው ፅሁፍ የኛን ዕምነትና አላማ አላንፀባረቀም፤ እንዲያውም የማይፈለግ ነገር ነው አትማችሁ ያወጣችሁት የሚሉን ነበሩ። በዚህ መልክ ተቆጥተው ሊጣሉን ከመጡት መካከል የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችንና የፖሊስ ባለስልጣናትን አስታውሳለሁ።*

*በ1961 ዓ.ም ገደማ ይመስለኛል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መንግስትን የሚቃወም ፅሁፍ በበራሪ ወረቀቶች እያባዙ በከተማው አውራ ጐዳናዎች ላይ ይበትኑ ነበር። ይህንን የቅስቀሳ ወረቀት የሚበትኑት አመፅን ለማነሳሳትና የጃንሆይን መንግስት ለማፍረስ ነው በማለት የህዝብ ደህንነትና የፀጥታ መሥሪያ ቤት ለአገር አስተዳደር ሚኒስቴር የሚበተነውን ወረቀት ያቀርባል።*

*በዚያን ጊዜ የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ክቡር ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ህይወት ነበሩ። ሚኒስትሩ ጋዜጠኞችን ጠርተው ተማሪዎቹ ሠላምን ለማደፍረስና ሁከት ለመፍጠር የሚበትኑት ወረቀት በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ ጥፋት እንዲደርስ የሚጋብዝ ነው። በእነዚህ ተማሪዎች ላይ መንግስት ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑ ተገልጾ በጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ እንዲፃፍ የሚል ትዕዛዝ ሰጡ። እኔ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ተገኝ የተሻወርቅ በሄራልድ ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ጻፍን።*

ጋዜጣው ለህዝብ ከተሰራጨ በኋላ 5 የሚሆኑ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ Crocodiles (አዞዎች) የሚል የህቡዕ ስም የተሰጣቸው ፣ እሳት ጐርሰው እሳት ለብሰው ብርሃንና ሰላም ህንፃ ውስጥ ይገኝ ወደነበረው ቢሮአችን ይመጣሉ::

እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኔ ማለድ ብዬ ቢሮ አልገባሁም ነበር:: የሰንደቅ አላማችን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበሩት አቶ ያሬድ ገብረ ሚካኤል ዘንድ ሄደው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣውን ርዕሰ አንቀጽ የፃፈውን ሰው እንፈልጋለን በማለት ያፈጡባቸዋል:: አቶ ያሬድ የጋዜጣው አዘጋጅ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይመጣሉ ስላሉአቸው ተማሪዎቹ እንመለሳለን ብለው ይሄዳሉ:: በዚህ ጊዜ ያሬድ ፖሊስ ይጠሩና ቢሮአቸው ውስጥ ያቆዩታል::

እኔ ቢሮ ስገባ ተማሪዎቹ ለደህና ነገር የመጡ ስላልመሰላቸው ፖሊስ መጥራታቸውን ይነግሩኛል:: መጠንቀቅም እንዳለብኝ ይመክሩኛል:: የአቶ ያሬድ አነጋገር ስላሰጋኝ ሽጉጤን ከመኪና ውስጥ አምጥቼ ጠረጴዛዬ መሳቢያ ውስጥ አስቀምጬ ተማሪዎቹን በመጠባበቅ ላይ እንዳለሁ፣ አንድ ወዳጄ ሊጠ ይቀኝ ይመጣል:: ስለተማሪዎቹ ስንነጋገር የታተመውን ጋዜጣ እየመረመረ አስተያየቱን ለሚኒስትሩ የሚያቀርበው የስራ ባልደረባችን ይመጣና የተማሪዎቹን ዛቻ ሰምቼ ነው የመጣሁት ይለኛል::

በተማሪዎቹና በእኔ መካከል ሊፈጠር የሚችለው ሙግት ከክርክር አልፎ ወደትንቅንቅ ቢያመራ ሁለቱ ሰዎች በገላጋይነት ያግዙኝ ይሆናል በማለት ሁለቱን ሰዎች ከቢሮው ወጥተው እንዲሄዱ አልገፋፋኋቸውም:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተማሪዎቹ ተከታትለው ቢሮዬ ይገባሉ:: በቁጣና በትዕቢት መንፈስ እንደመጡ ሁኔታቸው ይናገር ነበር:: የእንግዳ መቀበያው ሶፋ ስላልበቃቸው ተጨማሪ ወንበር አቀረብንላቸው::

አንዱ ተማሪ «እዚህ ጋዜጣ ላይ የተፃፈው ርዕሰ አንቀጽ የአንተ የግል አስተያየት ነው? ወይስ የመንግስት መግለጫ ነው?» በማለት ቆጣ ብሎ ጠየቀኝ:: ከአነጋገሩ ትግሬ ወይም ኤርትራዊ ይሆናል ብዬ ገመትኩ:: ጥያቄው እንደትዕዛዝ አይነት ስለሆነብኝ መልስ ቶሎ አልሰጠሁትም:: ተማሪዎቹን በዓይኔ እየቃኘሁ የምናገረውን ሳሰላስል ሁለተኛው ተማሪ ቀጠል አደረገና «እዚህ ጋዜጣ ላይ የተፃፈው ርዕሰ አንቀጽ እኛ ሰላም ለማደፍረስና ሁከት ለመፍጠር እንደተነሳሳን አድርጐ ነው የሚገልፀው:: ይኸ መግለጫ የመንግስት ነው ወይስ ያዘጋጁ የግል አስተያየት በማለት ሁኔታውን ለማወቅ ፈልገን ነው የመጣነው» አለ ለዘብ ባለ አነጋገር::

«እንደምታውቁት ይኸ የመንግስት ጋዜጣ ነው:: የመንግስት ጋዜጣ ማለት ደግሞ የመንግስት ልሣን ነው:: ርዕሰ አንቀጹ የመንግስት ፖሊሲ የሚንፀባረቅበት መሆኑን የምታውቁ ይመስለኛል» አልኳቸው::

«ይኸ ፅሁፍ ብዙ ስህተት አለበት» አለ ሶስተኛው::

«ምንድነው ስህተቱ?» አልኩት::

«እኛ በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ ጥፋት እንዲደርስ ወይም አመፅ እንዲፈጠ ር ቅስቀሳ አላደረግንም::»

«እኛ ለሀገሪቱ መልካም አስተዳደርና ፍትሀዊ የሆነ ዳኝነት ያስፈልጋል ነው ያልነው» አለ አራተኛው።

«የህዝብ መብት መከበር አለበት ነው ያልነው» አምስተኛው ነው እንዲህ ያለው።

«ይኸ ርዕሰ አንቀጽ የተፃፈው እናንተ ለበተናችሁት የቅስቀሳ ወረቀት መልስ እንዲሆን ነው። የተፃፈው በመንግስት ትዕዛዝ ነው። እናንተ ጽፋችሁ የበተናችሁትን ወረቀት እንደቀላል አድርጋችሁ የገመታችሁ መሰለኝ። እንደምታውቁት በሠላም የማይመጣ ለውጥ በአመፅ መምጣት አለበት ነው የሚለው ፅሁፉ።»

ከ5ቱ አንዱ «እርስዎ ለውጥ ፈላጊ መሆንዎን እንሰማለን። ሐሳባችንን ሊደግፉን በተገባ ነበር» አለ ፈገግ ብሎ። የልጁን አነጋገር አልጠላሁትም። በአዲሱ አነጋገር ትንሽ ሞቅ አለኝ! አዎን የለውጥ ፈላጊ ነኝ እንዳልል ሊጠይቀኝ የመጣው እንግዳና የሣንሱሩ ሠራተኛ እያዳመጡ ናቸው። አይደለሁም እንዳልል ተማሪዎቹን ማስቀየም አልፈለግሁም። የለውጥ ፈላጊ መሆኔን በሆዴ ይገቼ «መቼም ለውጥ የሚመጣው በሂደት ነው» ብዬ ተልካሻ ምክንያት ሰጠሁ። ተማሪዎቹ የፈለጉትን መልስ ከአገኙ በኋላ ሳያመሰግኑኝ እየተጉማለሉ ወደ ተገኝ የተሻወርቅ ቢሮ አመሩ። ተገኝ የሄራልድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር።

«እነዚህ ተማሪዎች እነማን እንደሆኑ ታውቋቸዋላችሁ?» ሁለቱን ሰዎች ጠየቅሁ።

«ሁለቱን የማውቃቸው ይመስለኛል» አለ የሥራ ባለደረባዬ። «ከዳር ተቀምጦ የነበረው ዋልልኝ ይመስለኛል። መካከል የነበረው ጥላሁን ግዛው ሳይሆን አይቀርም።»

ተማሪዎቹ ተገኝ ቢሮ ገብተው ያቀረቡት ጥያቄ እኔን ከጠየቁኝ የተለየ እንዳልነበረ ሰምቻለሁ። ሆኖም ተገኝ እንደኔ አልፈራቸውም። አቋሙን አስተካክሎ «እናንተ እነማን ሆናችሁ ነው ይኸንን ጥያቄ የምትጠይቁኝ» በማለት ስለአፈጠጠባቸው እየዛቱና እየተሳደቡ መሄዳቸውን ሰማሁ።

ተማሪዎቹ እጆቻችንን ለመጠምዘዝ እቢሮ ድረስ መጥተው መሄዳቸውን ሚኒስትሩ ወዲያው ሰሙ። የተገኝ መልስ ተገቢና ትክክለኛ መልስ እንደነበረ፤ የእኔ መልስ እንዳልተወደደልኝ ተነገረኝ። ተገኝ የተሻወርቅ በሥልጣንም ሆነ በዕድሜ ከማይመጥኑት የጃንሆይ ሹማምንት ጋር በደርግ ጁንታ እንደተረሸነ ይታወቃል። በእነሱ ቋንቋ ተመትቷል። ተገኝ ወዳጄና የሥራ ጓደኛዬ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ በምን ምክንያት እንደተገደለ ለማወቅ አልቻልኩም። እርግጥ ነው የደርግ ባሕሪና ተግባር ሲያሰኘው ገድሎ በኋላ ምክንያቱን እንደምንም ፈላልጐ በሚዲያ መናገር ነበር። «በሥልጣን መባለግ» በሚል የደፈና አነጋገር ለሐገሪቱ ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደረጉና ወደፊትም ሊያደርጉና ሊጠቅሙ ይችሉ የነበሩትን አያሌ ባለስልጣናት ያለፍርድ አጥፍቷቸዋል።

ቀደም ባለው ዘመን በውጭ ሐገር ጋዜጣ ላይ ይሠሩ የነበሩ ክሪቲኮችና ሐተታ ፀሐፊዎች፣ ጋዜጠኞች ቢባሉም ምድባቸው ከደራሲያን ጋር ነበር። በአሁኑ ዘመን ጋዜጠኝነትና ደራሲነት ሁለት የተለያዩ ሙያዎች መሆናቸው

እየታመነበት መጥቷል፡፡ እንደጋዜጠኞች ይጠቀሱ ከነበሩት ደራሲያን መካከል፡- ደፎ (Defoe) ፣ ስዊፍት፣ አዲሰን፣ ስቲል፣ ፊልዲንግ እና ሳሙኤል እንደምሣሌ ይጠቀሳሉ፡፡

ከጋዜጠኝነት ወደ ደራሲነት ለመሸጋገር የጋዜጠኝነት ሙያ ምን ያህል አስተዋፅኦ ያደርጋል? የሚል ጥያቄ በየጊዜው ይነሣል፡፡ የጋዜጠኝነት ሥራ በየዕለቱ አዲስ ምርት እንደሚያመርት ፋብሪካ ይቆጠራል፡፡ እንደ ፋብሪካ አንድ አይነት ምርት አያቀርብም፡፡ ጋዜጠኛው በየዕለቱ አዲስ ኢንፎርሜሽን ይሰበስባል፡፡ በየዕለቱ ከተለያዩ ምሁራንና ተራ ሰዎች ጋር ይወያያል፡፡ ለሰዎች ከሚያቀርበው ቃለ መጠይቅ አዲስ ትምህርት ይቀስማል፡፡ ከተለያዩ የሙያ መስኮች ከሚሰበስባቸው ዕውቀት ሰጪ ከሆኑ ኢንፎርሜሽኖች የራሱን ችሎታና የአስተሳሰብ አድማስ ያሰፋል፡፡ ፈረንጆች እንደሚሉት ስለ ብዙ ነገሮች ጥቂት ጥቂት ስለሚያውቅ Jack of all trades, master of none ይሆናል፡፡

ጋዜጠኛው ሥራው ነውና ሳያሰልስ ስለሚጽፍ ራሱን ለመግለጽ የሚያስችለውን የሙያ ብቃት ያዳብራል፡፡ ዜናና ኢንፎርሜሽን የሚጽፈው ለተማረውና ለሊቁ ብቻ ሳይሆን ለጀማሪ አንባቢና ለተራው ሰው ጭምር ስለሆነ የሚጠቀምባቸው ቃላትና አረፍተ ነገሮች አጫጭርና በቀላሉ ለአንባቢ የሚገቡ ናቸው፡፡

ጋዜጠኛው በየዕለቱ የሚያነጋግራቸውን ሰዎች ባሕርይ፣ ፊሊጥ፣ ልምድና የሰውነት እንቅስቃሴ ይመለከታል፡፡ ጋዜጠኛው ወደ ደራሲነት ሲሸጋገር እነዚህ ጥናቶች በሚጽፋቸው ልብወለዶችና ተውኔቶች ውስጥ ለሚስላቸው ባሕሪያት የሚጠቅሙ ሞዴሎች ይሆኑታል፡፡

መጽሐፍ ማንበብና ሳያሰልሱ መጻፍ የጋዜጠኛውን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበሩም በላይ ብዕሩንም ያሰላዋል፡፡ ያተባዋልም፡፡ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ጋዜጠኛ የነበሩ ሰዎች የታወቁ ደራሲያንና የኖቤል ሽልማት ተሸላሚዎች የሚሆኑት፡፡

በነገራችን ላይ በጋዜጠኝነት ትምህርት ቤት ለተማሪው ከሚመደብለት ጠቅላላ ጊዜ ሠልጣኙ ለጋዜጠኝነት ትምህርት የሚያውለው አንድ አራተኛውን ወይም አንድ ሶስተኛውን ብቻ ነው፡፡ የተረፈው ጊዜ የሚመደበው ከሶሶት እስከ አራት ዓመት ለሚፈጀው ጠቅላላ ትምህርት መሆኑ ይታወቃል፡፡ እያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ ወይም የጋዜጠኝነት ሙያ ማሠልጠኛ ኢንስቲቲውሺን የራሱ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ቢኖረውም፣ የጋዜጠኝነት ትምህርት የሚባለው የፕሬስ ታሪክ፣ የፕሬስ ሕግ፣ የሥነ ምግባር ትምህርት፣ የዜና አሰባሰብ ዘዴ፣ ሪፖርት የመጻፍ፣ አርትኦትና ርዕሰ አንቀጽ መጻፍ እንዲሁም መጣጥፍ መጻፍ፣ የጋዜጣውን ተነባቢነት ለማሳመር ዜናውንና ሥዕሉን በትዕይንተ ገጹ ላይ ማስቀመጥ (layout) መቻል ወዘተ ነው፡፡ ጋዜጠኛው ከዚሁ ጋር ሊያጠና የሚሞክረው ትምህርት ጂኦግራፊ፣ የፖለቲካ ሣይንስ፣ ኢኮኖሚ፣ ቋንቋና ሶሲዮሎጂ ሊሆን ይችላል፡፡

እኔ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ 15 ዓመት ያህል ሳገለግል ግርማዊነታቸው ፊት ሶስት ጊዜ ቀርቤያለሁ፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ የቀረብኩት ከፈረንጅ አገር እየተማሩ የሚመጡ ወጣቶች ጃንሆይ ፊት እየቀረቡ እጅ መንሳት የተለመደ

ሥርዓት ስለነበረ ይኸው ዕድል ደርሶኝ አንድ አሥር ከሚሆኑ «መጤዎች» ጋር ወደታላቁ ቤተ መንግሥት በሄድኩበት ጊዜ ነበር፡፡

ቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ውስጥ ጃንሆይ ቁመው ተማሪዎቹን ተራ በተራ ያነጋግሩ ነበር፡፡ በአካባቢው ይታይ የነበረው ሥርዓትና ፎርማሊቲ አስገርሞኝ አንድ እጄን አገጬ ላይ አስደግፌ ጥግ ይዤ ቆሜ ነበር፡፡ ግርማዊነታቸው ፊት አደግድጐ ያስተናብር የነበረ አንድ የዕልፍኝ አስከልካይ ከወዲት መጣ ሳይባል እጄን ከአገጬ ላይ መንጥቆ በማሽቀንጠር አፍጥጦ ተመለከተኝ፡፡ ይታዘዝ ወይም በራሱ ፈቃድ ያድርገው አልገባኝም፡፡ ከመደንገጤ የተነሳ እጄን የማስቀምጥበት ሥፍራ ጠፋኝ! ወደኊን - ወደኋላ - ፊት ለፊት? መቼም እኪሴ ውስጥ አልከትተው! ይኸ ድንገተኛ ገጠመኝ የጃንሆይ እንግዳ መሆኔን አስረስቶ የቤተ መንግሥቱ ሥነ ሥርዓት የማያዝናና መሆኑን እንዳውቅ የመጀመሪያ ትምህርት ሆነኝ፡፡

ይኸ ድርጊት ሌላም ታሪክ እንዳስታውስ አደረገኝ፡፡ በቤተመንግሥቱ አልፎ አልፎ ሰፊ ግብዣ ይደረጋል፡፡ ግብዣ በሚደረግበት ጊዜ የመከላከያ ሠራዊት፣ ጥሪ የተደረገላቸው ባለሥልጣትና ግብዣው ሲተርፍ ተጋፍቶ ለመግባት ዕድል ያጋጠመው ሁሉ የሚጋበዝበት ጊዜ ነበር፡፡ የወረገኑን ሠንጋ ጮማ ተመግቦና የቤተመንግሥቱን የማር ጠጅ ጠጥቶ ከግብዣው አዳራሽ የሚወጣ ሁሉ የግብዣውን አይነት እጅግ በሚያጐመዥ መልኩ ያወራዋል፡፡ ሰክሮም እየወደቀና እየተነሳ በትርኢት የሚያሳይ ሰው ነበር፡፡ የዚህ ግብዣ ተቋዳሽ ለመሆን የግቢውን አስተናባሪዎችና በር ጠባቂዎች ደጅ የማይጠና አልነበረም፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ከባድ መኪና ያሽከረክር የነበረ አንድ ኤርትራዊ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ሲያልፍ ሕዝቡ ወደ ግብዣው ሥፍራ ለመግባት በሩ ላይ ሲጋፋ ይመለከታል፡፡ ምክንያቱን ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ግብዣውን ለመቅመስ ስለጓጓና ሁኔታውንም ለማየት ስለፈለገ መኪናውን አቁሞ ብርቱ በሆነው በከባድ መኪና አሽከርካሪ ጡንቻ የተሰለፈውን ሕዝብ ግራና ቀኝ እየገላለጠ አዳራሹ በራፍ ሲደርስ ሥነ ሥርዓት አስከባሪው «አትጋፋ» ይልና በያዘው አርጩሜ ትከሻው ላይ ሾጥ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው ግፊያውን ተወት አደረገና che cosa é questa? Aperetivo? አለ ይባላል፡፡ ይኸ አፔሬቲቭ መሆኑ ነው? ማለት ነው ፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት የቀረብኩት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ስለ ልዑል መኮንን መታሰቢያ ሆስፒታል (የአሁኑ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል) በተጻፈ ሐተታ ምክንያት ነበር፡፡ ጽሑፉን የጻፉት ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ነበሩ፡፡ መልዕክቱ ሆስፒታሉ በልዑል መኮንን ስም ቢጠራም የሚታከምበት ሕዝቡ ስለሆነ የሆስፒታሉን ማሠሪያ መዋጮ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ በርትቶ እንዲያዋጣ የሚያሳስብ ጽሑፍ ነበር፡፡

ቤተ መንግስት ትጠራለህ ስባል እየተቻኮልኩ ነበር ወደዚያ የሄድኩት፡፡ በዚያን ዘመን ወደቤተ መንግሥት የሚጠራ ሰው አንድም ለሥራ፣ አልያም ለተግሣጽ፣ ሲቀና ደግሞ ለሹመት ስለነበረ፣ ልቤ እየተሸበረ ነበር ንጉሠ ነገሥቱ ፊት የቀረብኩት፡፡ እየደጋገምሁ ለጥ ብዬ እጅ ከነሳሁ በኋላ «ስለ ልዑል መኮንን መታሰቢያ ሆስፒታል የተጻፈውን ጽሑፍ አንተነህ የጻፍከው?» ሲሉ ጠየቁኝ፡፡

«እኔ አይደለሁም ጃንሆይ። ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው» አልኩኝ።

«አንብበኸዋል ?» አሉኝ።

«አዎን ጃንሆይ» አልኩኝ።

«አንተ መቼ ነው እንደዚህ የምትጽፈው? » አሉኝ።

«እየተማርኩ ነው ጃንሆይ» አልኩኝ።

«በል ሂድና ወልደ ጊዮርጊስን ጥራው» አሉኝ።

ለጥ ብዬ እጅ ነሣሁና ወጣሁ።

ቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ እጅ ለመንሣት፣ ግምባር ለማስወጋትና ደጅ ለመጥናት ብዙ ባለሥልጣናት ተኮልኩለው ነበር። ጃንሆይ ፊት ቀርቦ የሚወጣ ሰው ተሹሞ እንደሆነ የሚስመው ይበዛል። ጃንሆይ ተቆጥተውታል ወይም ሽረውታል ከተባለ የሚያውቁት ወዳጆቹ ሁሉ ፊታቸውን ያዞራሉ ሲባል እሰማ ነበር። የእኔ አይነቱ ሰው ለቁጣም ሆነ ለሹመት የሚያበቃ ዕውቅና ስላልነበረኝ ነው መሰለኝ ለምን ተጠራህ? ብሎ የጠቀየኝ ሰው አልነበረም። እነሱ እኮ ታላላቅ ባለሥልጣኖች ነበሩ።

ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ስለ ልዑል መኮንን መታሰቢያ ሆስፒታል የጻፉት ጽሑፍ በይዘቱ እውነት ቢሆንም፣ ሕዝቡ እስከዚያ ቀን ድረስ የከፈለው ገንዘብ በውል ባይገለጥ ነው እንጂ እንኳን አንድ ሆስፒታል ሌላም ይሠራ ነበር የሚል የሕዝብ ጉምጉምታ ስለነበረ ይኸ ርዕሰ ጉዳይ የሕዝቡን ጥያቄ ካላካተተ ሚዛናዊነት ይጐድለዋል ብዬ ስለአሰብኩ እኔን እምብዛም አላጓጓኝም ነበር።

ለሶስተኛ ጊዜ ጃንሆይ ፊት የቀረብኩት ጃንሆይ የተወለዱበት 80ኛ አመት በሚከበርበት ዕለት ነበረ። ልደታቸውን በማስመልከት ለጃንሆይ አንዳንድ ጥያቄ አቅርበን ዜና ለመጻፍ እንፈልጋለን በማለት በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ ጌታቸው መካሻን ጠየቅን። ጃንሆይ በቅድሚያ እንዲመለከቷቸው ጥያቄዎቹ ለሚንስትሩ ተሰጡ። ግርማዊነታቸው ጥያቄዎቹን ለመመለስ ፈቃደኛ መሆናቸው ከተነገረን በኋላ አምስት የምንሆን ጋዜጠኞች ወደ ኢዮቢልዩ[6] ቤተ መንግሥት ሄድን። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቢሯቸው ውስጥ ተቀምጠው ነበር። የጥያቄዎቹ መልሶች ጐላ ጐላ ባሉ ፊደላት ተጽፈው ጠረጴዛ ላይ መቀመጣቸውን በሩቅ ተመለከትኩ።

የሥራ ጓደኞቼ ጥያቄያቸውን በየተራ አቅርበው መልስ ከተሰጠባቸው በኋላ የእኔን ጥያቄ እንዲህ ስል አቀረብኩ። «ስለ ግራማዊነትዎ ገናናነትና አርቆ አስተዋይነት መጽሐፍ የሚጽፉ የውጭ ሐገር ደራሲያን ከጃንሆይ በኋላ ኢትዮጵያ ምን ይበጃት ይሆን? በሚል ጥያቄ መጽሐፋቸውን ይደመድማሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ግርማዊነትዎ የሚሰጡን አስተያየት አለ?»

[6] ኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት በዛሬ ጊዜ ብሄራዊ ቤተመንግስት የሚባለው ነው፤ በ1948 አልቆ ሲመረቅ ኢዮቤልዩ ቤተመንግስት የሚል ስም የተሰጠው፣ በዚያ ወቅት ለሚከበረው የንጉሰ ነገስቱ 25ኛው የዘውድ በአል (ማለት የብር ኢዮቤልዩ በአል) መታሰቢያ እንዲሆን ነበር።

«ጋዜጠኛ ማለት» አሉ ግርማዊነታቸው መልስ ሲሰጡ፣ «መጻፍ ብቻ አይደለም። የሐገራችንን ታሪክ ማንበብ ያስፈልጋል። ሕገ መንግስቱን ማወቅ ተገቢ ነው። . . . ከሆነስ ሆነና ይህን ጥያቄ የውጪዎቹ ፈረንጆች ይጠይቁ እንጂ እናንተ ናችሁ የምትጠይቁን» አሉና በቁጣ መንፈስ ተናገሩ። በዚህ ገዜ የጃንሆይን ፊትና ሁናቴ እየተመለከቱ ክፉውንና ደጉን ለይተው የሚያውቁት አስተናባሪዎችና በአካባቢው የነበሩት ባለሥልጣናት «ውጡ! ውጡ!» እያሉ በማዋከብ ወደበሩ ሸኙን። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ እዚያው ነበሩ። ፊታቸውን ስመለከት ኮስተር ብለው ስላዩኝ ይኸንን ጥያቄ በማቅረቤ የተደሰቱ አልመሰለኝም።

ለጃንሆይ የቀረበላቸው ጥያቄና የተሰጠው መልስ በሚዲያ እንዲነገር ተደረገ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ አስመሳዮችና መሀል ሰፋሪዎች ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው «ጋዜጠኛው ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ሊያሳስትዎት አስቦ ነው። አልጋዬን የሚወርሰው እገሌ ቀርቶ እገሌ ነው ቢሉ ይህቺ ሐገር ተበጠበጠች ማለት አይደለም» በማለት አካኪ ዘራፍ ከማለታቸውም በላይ «እርስዎ ካልቀጧቸው እኛ እንቅጣቸው» ይላሉ ። እንግዲህ ያለፍርድ ሳይገድሉህ (lynch ሳያደርጉህ) ነፍስህን አውጣ ሲል አንድ ወዳጄ በስልክ ነገረኝ። ወዲያው መለስ አድርጌ ጃንሆይ እኛ ፈቅደን ነው ስላሉ አምልጠሃል ስላለኝ ጭንቀቱ ለቀቀኝ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጥያቄው ወቅታዊና አግባብ ያለው ነበረ። አንደኛ የጃንሆይ ዕድሜ 80 ዓመት በመድረሱ «ንጉሥ ከሞቱ በማን ይሟገቱ» የሚለውን የአበው አባባል የሚመለከት በመሆኑ ነው። ሁለተኛ በአፍሪካ አህጉር መሣሪያ የጨበጠ የ፶ አለቃ ሁሉ ለሕዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል በሥልጣን ኮርቻ ላይ ቂጥጥ የሚልበት ዘመን ስለነበረ ከጃንሆይ የጠበቅሁት ቀና መልስ ከዚህ የተለየ ነበር።

የፓርላማው መኖር፣ እሳቸው ያስተማሩዋቸው ወጣቶች በትምህርት እየታነጹ ለሃላፊነት የሚያበቃቸው ሙያ ተላብሰው መገኘት፣ ሥልጣኑ በሕግ የተገደበና ከጊዜው ጋር የሚሄድ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ለሐገሪቱ አስፈላጊ እየሆነ መምጣት፣ የዲሞክራሲ ኢንስቲቲውሽንስ መሠረት የሆኑ የሥልጣኔ አውታሮች መዘርጋት ወዘተ. . . ይጠቅሳሉ ብዬ ጠብቄ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ ነው፣ ያስመሰግናል ተብሎ የተፃፈ ጽሑፍ ያልታሰበ ትርጉም ይሰጠዋል። አንዳንድ ጊዜ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ባለመኖሩ በዳበሳ የሚጻፍ ሐተታ በማስታወቂያ ሚኒስትር ላይ ተግሣጽና ቁጣ ያስከትላል። በዚህ ጊዜ ጋዜጠኛው በደሞዝ ይቀጣል፤ ወይም ከአንዱ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላው ክፍል ይዛወራል።

ጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ ፍርድ ቤት ቀርበው ያሰሙትን የመከላከያ ክርክር በማስመልከት አቶ አህዱ ሳቡሬ በጻፉት ሪፖርት ምክንያት ተግዘው ወደ አርሲ ክፍለ ሐገር ተልከው ነበር። በጊዜው ምናልባት በአንድ ጋዜጠኛ ላይ የደረሰ ከፍተኛው ቅጣት ይኸ ሳይሆን አይቀርም። በሚዲያ በተነገረ ስህተት ወይም ሆነ ተብሎ በቀረበ ሪፖርት ምክንያት ከላይ ከተጠቀሰው ቅጣት አልፎ የታሠረ ወይም የተገደለ ሰው መኖሩን አላስታውስም። በሐገራችን ውስጥ የጻኘነት ሥራ ከአድላዊነትና ከሙስና የፀዳ ነበር ለማለት ባይቻልም ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበረበት ጊዜ ነው ለማለት ይቻላል።

አንድ ጋዜጠኛ በጻፈው ጽሑፍ ወይም በሌላ ምክንያት መገደል የተጀመረው በደርግ ዘመነ መንግሥት ነበረ፡፡ ተገኝ የተሻወርቅ፣ በዓሉ ግርማና ወርቁ ተገኝን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል፡፡

ወርቁ ተገኝ ዜና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ በሪፖርተርነት የሚሠራ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሩቅ ነበር፡፡ ጥሩ ፀሐፊ መሆኑን ሁላችንም የምንመሰክርለት ወጣት ነበረ፡፡ የደርግ ምክትል ሊቀመንበር የነበሩት ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ለምን እንደተገደሉ ደርግ ምክንያቱን በሚገልጽበት ጊዜ ሐተታውን የጻፈው ወርቁ ነበር፡፡ ይህንን ጽሑፍ በትኩረት ለተመለከተው ሰው አጥናፉ አባተ መገደላቸው ቀርቶ ሊመሰገኑበት ይገባል የሚል ትችት በማስከተሉ የደርግ ባለሥልጣናት ያለመደሰታቸውን ሰምቻለሁ፡፡ የሆነ ሆኖ ዜናው ከተሠራጨ ከአንድ ሁለት ቀናት በኋላ ወርቁን ኢህአፓ ገደለው የሚል መርዶ ተነገረን፡፡

በአሁኑ ጊዜ የወርቁን ዘመዶች አግኝቼ እውነቱን ለማረጋገጥ አልቻልኩም፡፡ እዚህ ጥርጣሬ ላይ የደረስኩት የከፋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ የነበሩት የፖሊስ ኮሎኔል በኢህአፓ ተገደሉ ተብሎ አስከሬናቸው ዮሴፍ መካነ መቃብር ሲያርፍ ዲምብልቢ የተባሉት የእንግሊዝ ጋዜጠኛ የቀብሩን ሥነ ሥርዓት በቪዲዮ እንዲቀርጹ ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡ ጋዜጠኛው አገራቸው ከደረሱ በኋላ ደርግ የሚጠረጥራቸውንና የማይፈልጋቸውን ሰዎች እየገደለ ኢህአፓ ነው የገደላቸው ማለት አምጥቷል በማለት ዜናውን ለዓለም አሰራጭተውታል፡፡ በዚህ ሪፖርት ደርግ ተቆጥቶ ጋዜጠኛው ሁለተኛ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ መከልከሉን አስታውሳለሁ፡፡ ዲምብልቢ «በኢትዮጵያ ውስጥ የተደበቀው ርሃብ» የተባለውን የወሎን የርሃብ ፊልም አንስተው በመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም ያሳወቁ ጋዜጠኛ ናቸው፡፡

የደርግ ጁንታ የለውጥ ሐዋሪያት የሚላቸውን ካድሬዎች ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር እየላከ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በሥጋትና በፍርሃት እንድንዋጥ፣ በጥፍራችን ቆመን እስክንሄድ ያስፈራሩን ነበር፡፡ ከእነዚህ መካከል ሻለቃ ፍሰሐ ገዳን፣ ሻለቃ ተካልኝ ባልቻንና ሻለቃ ናደው ዘካሪያስን የማያስታውስ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠራተኛ ያለ አይመስለኝም፡፡ የወታደር ኃይል በአፈሙዝ ተጽዕኖ ሥልጣን በያዘባቸው የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ አገሮች የጋዜጠኝነት ሥራ በምላጭ ጠርዝ ላይ እየረገጠ እንደሚሄድ እግር በጥንቃቄ መራመድን ይጠይቅ ነበረ፡፡ የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉ የአያሌ ጋዜጠ ኞችን ስም ኢንተርናሽናል ኘሬስ ኢንስቲቲውት የተሰኘው የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት መዝግቦ ለታሪክ አስቀምጦታል፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናልም ብዙ ማስረጃ ሰብስቧል፡፡

ጋዜጠኞችና ደራሲያን በሚሠሩት ሥራ መስዋዕትነት መክፈል የጀመሩት ዛሬ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ1637 ዓ.ም William Prynn የተባለ የእንግሊዝ ደራሲ ንግሥቲቱን የሚነቅፍ መጽሐፍ ጽፈሃል ተብሎ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ የዕድሜ ልክ እሥራት ይፈረድበታል፡፡ ዳኞቹ ይኸ ቅጣት በቂ መስሎ ስላልታያቸው ሁለት ጆሮዎቹ እንዲጐመዱ አዝዘው ቅጣቱ ተፈጽሞበታል፡፡ ይኸን ምሣሌ የጠቀስኩት ቅጣቱ ያልተለመደ ስለመሰለኝ ነው፡፡

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኜ ያጋጠመኝን ችግር ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስታውሰው፣ በፈረንጅ አገር የተማርኩትን የፕሬስ ነፃነትና የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዳለ ወርሰን በሐገራችን ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንችል ነበር ወይ? የሚለው ጥያቄ የሚያነጋግር ሆኖ አገኘዋለሁ፡፡ የፊውዳል ሥርዓት ለዘመናት ተንሠራፍቶ ሲሰሠራበት በነበረ አገር፣ ሥልጣኑ ባልተገደበ የንጉሠ ነገሥት መንግሥትና የፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን በነበራቸው አገረ ገዢዎች ይመራ የነበረ ሕዝብ በነበረበት አገር፣ ከተማረው ይልቅ የመሃይሙ ህዝብ ብዛት 90 በመቶ በነበረበት አገር፣ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ልማዶችና ባህሎች በነበረበት አገር፤ የተለያዩ ሃይማኖቶችና አጓጉል ልምዶች ባልተለያት አገር፣ የፈረንጁ ዓለም ለዘመናት ሲገለገልበት የቆየውን ኢንስቲቲውሺን በቀላሉ ወርሰን ሕዝቡን የሉአላዊነት ሥልጣን ባለቤት ማድረግ ይቻል ነበር? ፕሬሱ የሥልጣኔውን ሂደት ብቻውን ሊያራምደው ይችል ነበር? ወይስ አሁን እንደደረስንበት ዘመን የፕሬስ ዕድገት ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣ ታሪካዊ ሒደት ነበር? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ በአሉታ የሚመለስ ከሆነ በሚዲያ ሥራ ተሰማርተን ስናጉመተመትና ስንፍረመረም የቆየነው ሰዎች የታሪክን ሂደት አናውቅም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ «ቦ ጊዜ ለኩሉ» የሚለውን ምሳሌ ማጤን ነበረብን፡፡

የፕሬሱን ዕድገት ሒደት የገታው ምን እንደነበረ ለማወቅ ከዩኔስኮ ጥናት አንድ መሠረታዊ የሆነ ትምህርት መቅሰም ነበረብን፡፡ የአንድ ሀገር ዕድገት የሚፋጠነው የኤኮኖሚ ዕድገት ቢቀድም ነው ወይስ የኮሚዩኒኬሺን ዕድገት ቢቀድም? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ዩኔስኮ አንድ ጥናት አድርጎ ነበር፡፡ ጥናቱ የደረሰበት ድምዳሜ ሁለቱም የዕድገት አውታሮች በአንድነት አብረው ማደግ እንዳለባቸው ይጠቁማል፤ በመካከላቸው የተቀራረበ ትስስር እንዳለ ይገልጻል፡፡ በሌላ አነጋገር የፕሬስ ዕድገት አዝጋሚ መሆኑ ቀርቶ ሒደቱ የተፋጠነ እንዲሆን የሐገሪቱ የኤኮኖሚ ዕድገት ወሳኝነት አለው፡፡

በተለይ የግሉ ፕሬስ በተፋጠነ እርምጃ ሊያድግና ሊጠነክር የሚችለው የገበያ ኤኮኖሚ ሲኖርና የማስታወቂያ እንቅስቃሴ ሲስፋፋ ነው፡፡ በውጪ ሐገር አንድ የግል ጋዜጣ ውድድሩን ተቋቁሞ ሕልውናውን ለመጠበቅ የሚችለው ከጋዜጣው ጠቅላላ አምድ 60% የሚሆነውን ለማስታወቂያ ሲሰጥና 40% የሚሆነውን ስፔስ ለጽሑፍ መድቦ መሥራት ሲችል ነው፡፡ በሐገራችን ይህን ያህል ማስታወቂያ ማግኘት ቀላል አይሆንም፡፡ ምናልባት የግል ጋዜጦች ሊያድጉና ሊጠናከሩ የሚችሉት ትንንሽ ጋዜጦች በተናጠል ለማደግ ከሚሞክሩ ይልቅ የተወሰኑት አንድ አይነት ውህደት ፈጥረው ካፒታላቸውንና የሰው ኃይላቸውን ያጠናከሩ እንደሆነ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለዚህም ቢሆን ማስታወቂያ ወሳኝነት አለው፡፡

በሐገራችን የፕሬስ እድገት አዝጋሚ ነበር ለማለት የምንችለው፣ ከጠቅላላው ከሐገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ዕድገት ተለይቶ ማደግ የሚችል ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ ይኸ አይቻልም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የእያንዳንዱ ሰው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ100 የአሜሪካ ዶላር ያነሰ ነው የሚል ግምት አለ።[7] እንደ ዩኔስኮ ገለጻ ከሆነ በአያሌ አፍሪካ ሐገሮች ለአንድ ዕለታዊ ጋዜጣ መግዣ በዓመት የሚከፈለው ዋጋ እያንዳንዱ ሰው በዓመት ከሚያገኘው የነፍስ ወከፍ ገቢ በ10% ይበልጣል።

በተለያዩ ሀገሮች ብዙ ጋዜጦች ያሏቸው እንግሊዛዊው፣ ሎርድ ቶምሶን በታዳጊ ሀገሮች የሚያጋጥሙትን የፕሬስ ችግሮች አስመልክተው የሚሰጡት ምክር አለ። ነፃነታቸውን ከጊዜ በኋላ ያገኙ ታዳጊና ኋላቀር ሀገሮች መንግሥታቸው እምብዛም የፀና አይደለም። መሪዎቻቸውም ከልምድ ማነስ የተነሣ ስህተት ሊሡሩ ይችላሉ። የእነዚህ አገሮች ጋዜጠኞች የፕሬስ ነፃነት ልምድና የዳበረ የሙያ ብቃት ስለማይኖራቸው የሚጽፉት ሂስ ለአመጽና ለመፈንቅለ መንግሥት ይዳርጋል። ምንም እንኳን የመጨረሻው ግብ የፕሬስ ነፃነት ተግባራዊነት ቢሆንም፣ ይኸ በሂደት እስኪረጋገጥ ድረስ ፕሬሱ መጠነኛ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል። በሠለጠነው ዓለም ከብዙ ዘመን ትግል በኋላ የተገኘውን የፕሬስ ነፃነት ከውጭ ሐገር እንዳለ ገልብጦ በእነዚህ አገሮች እንዲሠራ ለማድረግ መሞከር ያስቸግራል። ይኸ አከራካሪ ነጥብ ሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ ለፕሬስ ዕድገት እንቅፋት የሚሆኑት የመንግሥት ፖሊሲና የአሠራር ችግሮች ወይም የልምድ ማነስ ብቻ አይደሉም። በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወት እንዲሁም በፖለቲካ አመራር ኋላ ቀር መሆን የራሱ የሆነ አስገዳጅ ተፅእኖ እንደሚያደርግ መገንዘብ ያስፈልጋል።

የሐገራችን ፕሬስ አሁን ከሚገኝበት የዕድገት ደረጃ የላቀ ሆኖ መገኘት ነበረበት ማለት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እውነታዎች ከጠቅላላው የሐገሪቱ ዕድገት ደረጃ ጋር ያለማመዛዘን ይሆናል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ነፃነት ከወረቀት አልፎ በተግባር ሲተረጐም መመልከት ራሱ ለሚዲያ ዕድገት እንደ አንድ ትልቅ እመርታ የሚታይ መሆኑ አሌ የሚባል አይደለም። አሁን ለሚታየው የፕሬስ ዕድገት ምክንያት ሆኗል ብዬ የምገምተው የመንግሥት መለዋወጥ፣ የተማረው ሕዝብ እየተበራከተ መምጣት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋትና መራቀቅ፣ ወዘተ.. ይመስለኛል።

የፕሬስ ነፃነት ማለት ጋዜጠኛው እንደልቡ ተዘዋውሮ የሰበሰበውን ኢንፎርሜሽን ለተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ወይም ባለሥልጣን ሳያሳይና ማስፈቀድ ሳያስፈልገው አትሞ የማሠራጨት ነፃነት ነው ብለናል። ይህም ሆኖ ጋዜጠኛው አትሞ ለሚያሰራጨው ጽሑፍ ሃላፊነቱን የመውሰድ ግዴታ አለበት፤ ምክንያቱም ለጋዜጠኛው የተሰጠው መብት ከሌላው ዜጋ መብት የተለየ ስላልሆነ በሚጽፈው ጽሑፍ የሌሎችን መብት ከመዳፈር መታቀብ

[7] በአሁኑ ጊዜ (ግንቦት 2005)፣ አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ሶስት መቶ ሰባ ዶላር ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

እንዳለበት በፍትሐ ብሄሩና በወንጀለኛው መቅጫ ሕግ ተደንግጓል። (ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 580 ይመልከቱ)

በሌላ መልኩ ደግሞ የግል ጋዜጣ መፈቀዱ ራሱ የፕሬስን ነፃነት የሚያመለክት ስለሆነ የዲሞክራሲን ሥርዓት እከተላለሁ የሚል መንግሥት ሊገድበው የማይገባ መሠረታዊ መብት ነው።

«ሥርጭታቸው ከአንድ ክልል ወሰን ስለማያልፉ የፕሬስ ሥራዎች» በሚል ርዕስ በመጋቢት ወር 1994 ዓ.ም የወጣ መረጃ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ወቅት[8] 95 የግል ጋዜጦች እና 16 መጽሔቶች በድምሩ 112 የኘሬስ ውጤቶች በኢትዮጵያ ውስጥ እየታተሙ ይሠራጫሉ። እነዚህ ጋዜጦችና መጽሔቶች በአማርኛ፣ በኦሮሞኛ፣ በትግርኛ፣ በእንግሊዘኛና በአረብኛ ቋንቋዎች ይታተማሉ።

ገና ብቅ ከማለታቸው ወዲያው የሚከስሙ አንዳንድ ጋዜጦች አሉ። በአቅም ማነስ ምክንያት ተፈላጊነታቸው አነስተኛ በመሆን፣ መብትና ግዴታቸውን በውል ባለማወቅና በተለይም ከላይ እንደተጠቀሰው የሐገሪቱ የገበያ ኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ለሚዲያው የደም ሥር የሆነውን የማስታወቂያ ሽያጭ ሊያደፋፍርና ገቢ ለማስገኘት ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል።

ሌሎችም ችግሮች አሉ። በሌሎች አገሮች በሣንቲም ደረጃ የሚገዙ ጋዜጦች በሐገራችን በሕትመቱና በወረቀቱ ዋጋ መናር ምክንያት እስከ ሶስት ብር መሸጥ ጀምረዋል[9]። የአንድ ወዝ አደር የዕለት የምሣ ዋጋ እንደማለት ነው።

የፕሬስ ሥራ መስፋፋት ለጠቅላላው የሐገሪቱ ኤኮኖሚና ማህበራዊ፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ ዕድገት መሻሻል ያለው ከፍተኛ አስተዋጽኦ የተመሰከረለት ነው። መንግሥት በሕትመት ወረቀት ላይ የሚጥለው ግብር፣ እንዲሁም በፖስታ፣ በቴሌኮሚዩኒኬሽንና በዜና አገልግሎት የሚሰጠው ግልጋሎት ለፕሬሱ በተመጣጠነ ዋጋ እንዲገኝ ማድረግ ይጠበቅበታል። አንድ ጋዜጣ ሊያገኘው ከሚገባው ገቢ፣ 40% የሚሆነውን የሚከፍለው ለሕትመት ወረቀት ስለሆነ መንግሥት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የዚህ ጥናት ጭብጥ «ጆርናሊዝምና ዕድገት በኢትዮጵያ፣ የግል ትዝታዎች ከ1952 ዓ.ም. ጀምሮ» በሚል ሲሆን በውይይቱ ጊዜ ከተነሱት ነጥቦች አንዱ ለዕድገቱ ወይም ለልማቱ ሂደት በቂ ትኩረት አልሰጠም የሚል ነው። ዕድገት የሚለውን ቃል በሁለት አቅጣጫ ማጤን ያስፈልጋል። የፕሬስ ወይም የሚዲያ ዕድገት እመርታ ሊታይ ይገባል። ሁለተኛው የዕድገት ትርጉም ሚዲያው ለሀገሪቱ ጠቅላላ የኤኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ዕድገት ያደረገው አስተዋጽኦ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዚህ ጥናት ውስጥ ተካትቷል።

ልማትና ዕድገትን በተመለከተ የሚዲያ ተግባር የህዝቡን ንቃተ-ህሊና ማዳበርና እንዲሁም የአስተሳሰብ አድማሱን ማስፋት ይሆናል። ህዝቡ ለዘመናት

[8] ይህ አሀዝ የሚገልጸው፣ ይህ የአቶ ነጋሽ ጽሁፍ በፎረም ፎር ሶሻል ሳይንስ ስብሰባ ላይ የቀረበበትን ዘመን (1997 እና አካባቢው) ነው።

[9] በአሁኑ ወቅት (ግንቦት 2005 )፣ የጋዜጣ ዋጋ በአማካይ ከ5 እስከ 7 ብር ሆኗል፤ ነገር ግን፣ እሁድ እሁድ የሚወጣው *ሪፖርተር* ጋዜጣ 10 ብር ይሸጣል።

ሲገለገልበት የነበረውን የቆየ ልምድና አሰራር ለውጦ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጥበብ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ የኑሮ ደረጃውንም እንዲያሻሽል ሚዲያው የማይናቅ ሚና ይጫወታል።

የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ሥልጣኔ እንዲፋጠን የሚዲያው ቀስቃሽነትና አነሳሽነት የማይካድ ቢሆንም፣ በሌላ መንገድ ደግሞ ለሚዲያው ዕድገት የኤኮኖሚ ዕድገት ያስፈልጋል። ለዚህ ነው የኤኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፕሬስ እድገት እጅ ለእጅ ተያይዘው አብረው ማደግ አለባቸው የሚባለው።

የገበያ ኢኮኖሚ አድጎና ተስፋፍቶ እንቅስቃሴ ካልታየ ማስታወቂያ የለም፤ ማስታወቂያ ከሌለ ሚዲያው አያድግም፤ ሚዲያው ህዝቡ ለተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲነሳሳና እንዲጓጓ መንፈሱን ካላነቃቃ፣ የኢንፎርሜሽንና የትምህርት ተጠቃሚ ካላደረገ፣ የዕድገቱ ሂደት ይገታል ወይም በእጅጉ አዝጋሚ ይሆናል።

የፕሬስ ዕድገት አንድ አስተማማኝ ከሆነ የዕድገት እመርታ ላይ ደርሷል የሚባለው (takeoff stage)፣ ከምን ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆን ዩኔስኮ አንድ መስፈርት አውጥቷል። ይኸ መስፈርት፣ የጋዜጣ ሥራ አስተማማኝ ከሆነ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው ከሐገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ 20% የሚሆነው ማንበብና መጻፍ ሲችልና እንዲሁም ከመላው የሐገሪቱ ህዝብ 10% የሚሆነው ቁጥሩ 50,000 ወይም ከዚህ በላይ ሕዝብ በሚይዙ ከተሞች ውስጥ መኖር ሲችል ነው ይላል። ሌላም መስፈርት በዩኔስኮ ጥናት ተጠቅሷል። ቢያንስ 10 ጋዜጦች፣ አምስት ራዲዮኖችና ሁለት የሲኒማ ቤት መቀመጫዎች ለ10 ሰዎች ማገልገል ሲችሉ ነው።

በአሁኑ ወቅት በሐገራችን የሚታተሙት የግል ጋዜጦች በይዘታቸው ትኩረት የሚሰጡት አንገብጋቢ መስሎ ለታያቸው ለፖለቲካው መድረክ ይመስለኛል። የኤኮኖሚው፣ የማህበራዊና የባህሉ ጉዳይ ገና አልተነካም ለማለት ይቻላል።

የግል ጋዜጣ የሚቋቋመው ለንግድ ጭምር ስለሆነ ዓይን የሚወጋና ለጆሮ የሚከብድ ዜና (sensational) አንባቢን ይስባል። የሆነ ሆኖ ሚዲያው የተሟላ አገልግሎት መስጠት የሚችለው የአንባቢውን ፍላጐት የሚያንጸባርቁና ከዕለት ኑሮው ጋር ለተቆራኙ ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ ሃሳቦችንና መርሆዎችን ማቅረብ ሲችል ይመስለኛል።

ጋዜጠኞቻችን በየጊዜው እየተከሰሱ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። ይቀጣሉም። ለዚህ ቅጣት የሚዳረጉት በተከሰሱበት ጉዳይ እየተረቱ ነው ወይስ የፖለቲካ ውሣኔ እየተወሰደባቸው ነው ለማለት የሚችለው ፍርድ ቤቱ ነው። እንደ ሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ከአስፈፃሚው አካል ተጽዕኖ ውጭ መሆን ይኖርበታል። የዲሞክራሲ ሥርዓት ተግባራዊ ሆኗል የሚባለው በሕግ አውጪው፣ በሕግ ተርጓሚውና በሕግ አስፈፃሚው መካከል check and balance ሲኖር ነው።

ስለ ፕሬስ ነፃነት ሲወሳ እንደመብት የሚቆጠሩ፣ በከፊል ገደብ የሚጣልባቸውና በፍጹም የሚከለከሉ ተብለው የሚዘረዘሩ ግዴታዎች አሉ። ሁሉንም በዝርዝር ለማቅረብ ባይቻልም ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ።

ጋዜጠኛው እንደ መብት አድርጎ የሚጠቀምባቸው ነፃነቶች (Rights)፦

- የሚያዘጋጀውን ጽሑፍ ለሳንሱር ወይም ለተቆጣጣሪ ሳያሳይ ማተም፤
- የጋዜጣውን ይዘት መወሰን፣ መፍቀድ ወይም አለመፍቀድ፤
- እንደልቡ እየተዘዋወረ ኢንፎርሜሽን ወይም ዜና መሰብሰብ፤
- የሕዝብ ጉዳይ የያዙ መዛግብትን መመልከት፤
- ፖሊስ የዕለት ሁናቴዎችን የሚመዘግብበትን ዶኪዩመንት ማየት፤
- ሲኒማዎችን፣ ፊልሞችን፣ መጻሕፍትን፣ ተውኔቶችንና ለሕዝብ የሚቀርቡ ትርኢቶችን መተቸት፤
- ሕዝባዊ ስብሰባዎች ሲደረጉ ከተራው ሕዝብ የተለየ ፈቃድ ተሰጥቶት የጋዜጠኝነት ተግባሩን ያለ ችግር ማከናወን እንዲችል ዕድል ማግኘት፤
- ለሕዝብ ጠቃሚ የሚሆኑ ክስተቶችን አስመልክቶ ከዜናው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ፎቶግራፍ ማንሳት፤
- ሥራቸውንና ሃላፊነታቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች የመንግሥትን ባለሥልጣኖች መተቸትና ሂስ መጻፍ፤
- በድርጅቱ ወይም በጋዜጣው ሠራተኞች የሚሰበሰቡ ጽሑፎችና ፎቶግራፎች ባለመብት መሆን፤
- ጋዜጣው ላይ እንዲወጡ የሚመጡትን ማስታወቂያዎች የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት፡፡

በገደብ የተሰጡ መብቶች (Privileges)፦

- የስም ማጥፋት ክስ ሲመሠረትበት በገደብ በተሰጠ መብት(Privileges) የመከላከል መብት፤
- በፖስታ ቤት ለሚልካቸው ጋዜጦች ከተለመደው ክፍያ ያነሰ የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል መብት፤
- በአንዳንድ ሥፍራ (ክልል) የሐሰት ኢንፎርሜሽን ከሚሰጡ ሰዎች የመጠበቅ የሕግ ከለላ ወይም ጥበቃ የማግኘት መብት፤
- አንድ የኢንፎርሜሽን ምንጭ በሚስጥር የሰጠውን መግለጫ እንዲናገር ያለመገደድ መብት፡፡

በሕግ ገደብ የተጣለባቸው ግዴታዎች (Restrictions)፦

- ፕሬሱ እያተመ ለሚያሰራጫቸው ጽሑፎች ሃላፊነትን የመውሰድ ግዴታ አለበት፤
- የስም ማጥፋት ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሄሩና በወንጀለኛ መቅጫው ስለታወጁ (ወንጀለኛ መቅጫ አንቀጽ 580) የጋዜጠኛው መብት ተገድቧል፤

- ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች ወንጀል ሲፈጽሙ (በአንዳንድ ሥፍራ) ስማቸው በሚዲያ እንዳይገለፅ ተገድቧል፤
- ብልግናና አስነዋሪ የሆኑ ቃላት እንዳይታተሙ ይገድባል፤
- የኮፒ ራይት ሕግ መጠበቅ ስላለበት ጋዜጠኛውን ይገድበዋል፤
- ጋዜጠኛው በሚያዘጋጀው ዜና ከጉዳዩ ጋር ምንም አግባብ የሌለውን ግለሰብ የግል መብት ከመዳፈር ይገድባል፤
- በፍርድ ቤት የተያዘ አንድ ጉዳይ ገና በሒደት ላይ እያለ ነፃ አስተያየት ወይም ሂስ መፃፍ አይፈቀድም፤
- ሰላምን የሚያደፈርስና አመጽን የሚያነሳሳ ጽሑፍ ይከለክላል፤
- ሐገሪቱ በጦርነት ላይ ሆና ለጦርነት በሚደረገው ዝግጅት ጋዜጣው ጣልቃ ገብቶ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ለውትድርና እንዳይሰለፍ ቅስቀሳ ማድረግ በሕግ የተከለከለ ነው፤
- በጦርነት ጊዜ ለጠላት አመቺና ድጋፍ ሰጪ የሆነ ኢንፎርሜሽን መጻፍ አይፈቀድም፤
- ገንዘብን፣ ቴምብርንና የመንግሥት ቦንድን የመሳሰሉ ነገሮችን በማተም እትሞቹ ሕዝብን ለማጭበርበርና መልሶ ለማተም አመቺ እንዲሆኑ አድርጐ ማቅረብ የተከለከለ ነው፤
- አሳሳች የሆኑና ከዕውነት የራቁ ማስታወቂያዎችን ሆነ ብሎ አትሞ ማቅረብ የተከለከለ ነው፤
- ማስታወቂያዎችን ዜና አስመስሎ ማቅረብ በፖስታ ቤት በሁለተኛ ደረጃ የክፍያ ተመን እንዲላኩ የተሰጠውን ፈቃድ ከማሰረዙም በላይ፣ ቅጣት ስለሚያስከትል ከዚህ አድራጐት መታቀብ አለበት።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ 15 ዓመት ስሰራ ከአጋጠመኝ ችግር ይልቅ በደርግ ዘመነ መንግሥት ሶስት ዓመት ሠርቼ ከሥራዬ ጋር በተያያዘ ምክንያት የደረሰብኝ በደል ምንጊዜም አይረሳኝም።

ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አብዮቱ የተዋጠላቸውና ያልተዋጠላቸው በማለት ይሾምና ይሽር፣ ያስርና ይፈታ ነበር። እኔን ከዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅነት አንስቶ፣ ትንሽ ደጅ ካስጠናኝ በኋላ፣ የከተማ ልማት የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ ሆኜ እንድሠራ መደበኝ። ሹመት ሳይሆን ሽረት እንደነበር ገብቶኛል። በእኔ ሥፍራ አቶ በዓሉ ግርማ ተሾመ። በዓሉ ጥቂት ቆይቶ የሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት ቋሚ ተጠሪ የሚል ሹመት ተሰጠው። ወደ ባለሥልጣኖቹም ደረጃ ከፍ ከአደረጉት በኋላ የጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ንግግር ፀሐፊ (ghost writer) ሆኖ ነበር።

እኔ ወደ ከተማ ልማት መሥሪያ ቤት እንደተዛወርኩ «ልማተ ከተማ» የተሰኘች (News letter) በስቴንሲል የምትዘጋጅ ዜና ማሰራጫ አቋቁሜ በየወሩ ለመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞችና ለጋዜጠኞችም ትታደል ነበር። ይዞታዋ

የሚያተኩረው መሥሪያ ቤቱ በሚያወጣቸው መመሪያዎችና በሚሠራቸው የቁጠባ ቤቶች እንዲሁም በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ነበር።

በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የተሰገሰጉት የኢህአፓና የመኢሶን አባላት ስለነበሩ እኔና እኔን የመሳሰሉ «ተፈናቃዮች» በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ሽኩቻ ሳይገባን ዜናን እንደዜናነቱ፤ ቃለ መጠየቁንም እንደ አስፈላጊነቱ እናቀርብ ነበር። የኢህአፓ፣ የመኢሶን፣ የወዝ ሊግ ወዘተ... አባል እየተባባሉ ውስጥ ውስጡን በሚያካሂዱት ዘመቻ አንዱን ወገን ስለሥራው ጠይቄ ስፅፍ ሌላው የተዘነጋ እየመሰለው ለሚኒስትሩ አቤቱታ ያቀርባል። ሚኒስትሩ ክቡር አቶ ዳንኤል ታደሰ እኔ ከፖለቲካው ቡድን ውጭ መሆኔን ስለሚያውቁ በፖለቲካ ጥገኝነት የሚከሱኝን ሰዎች አይቀበሏቸውም ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን መኢሶኖች ተጠራርተው በየአቅጣጫው ዱር ገቡ። ብዙዎቹ እየታደኑ ሲያዙ ሚኒስትሩና ሌሎችም ወዴት እንደደረሱ እስከዛሬ ድረስ የማውቀው ነገር የለም። በዚያን ጊዜ ወደዱር ከገቡት ሰዎች መካከል አንዱ አቶ አበራ የማነ አብ እንደነበር አስታውሳለሁ። በአቶ አበራ የማነ አብ ሥፍራ ተተክቶ የማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ የሚሠራው ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ነበረ። ኃይሉ ወደዱር የገቡትን ሰዎች አስመልክቶ ለሠራተኛው በአደረገው ንግግር የመኢሶኖች «መፈርጠጥ» አብዮቱን ያጠራዋል እንጂ አያደክመውም በማለት ገለጻ አደረገ። ይህንኑ ንግግር በልማተ ከተማ ጋዜጣ ስጽፍ «ፈረጠጠ» የሚለውን ቃል በጥቅስ ምልክት ውስጥ አመለከትኩ። ኃይሉ ተቀየመ። ፈረጠጠ የሚለውን ቃል በጥቅስ ምልክት ውስጥ ያደረግኸው ቃሉን አጉልተህ ለማሳየት ነው? እኔ የምፈራ ሰው አይደለሁም አለኝ። ፍርሃቱን ምን እንዳመጣው አላውቅም። ወጣቶቹ የፖርቲ ቡድን ፈጥረው እርስ በእርሳቸው ይፋጁ ስለነበረ፣ ከሥጋት የተነሣ የተናገረው መሰለኝ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በባምቢስ ሱፐርማርኬት አካባቢ መኪና ውስጥ ተቀምጬ እያለሁ ሶስት ሰዎች መሣሪያ ወድረው ወደእኔ መጡ። ሰዓቱ ከምሽቱ ወደ ሶስት ሰዓት ገደማ ይሆናል።

«ካሣ የተባለው ባልደረባችን ቆስሏል ስለተባለ ወደዚያ ይዘውን ይሂዱ» አሉ። ሶስቱም መሳሪያቸውን ደግነው ብኛል። ኢህአፓ ይሁኑ ካድሬዎች አላውቅም። «ብዙ መኪና ቆሟል እኔን ለምን ጠየቃችሁኝ?» እያልኩ ሳቅማማ፣ ከሶስቱ ሰዎች በዕድሜ አነስ ያለው እንደ እናንተ ያሉ አድሃሪዎች እያሉ ይቺ አገር መቼም አትሻሻልም አለ። ወዲያው «ውጣ ከመኪና ውስጥ» አለኝ። እኔን ከመኪናዋ ውስጥ አስወጥተው ቁልፉን ከተቀበሉኝ በኋላ መኪናዋን ይዘዋት ሄዱ።

እኔም ድንጋጤው ሲለቀኝ በአካባቢው ወደሚገኘው የቀበሌ ጽሕፈት ቤት ሄጄ የደረሰብኝን በደል አመለከትኩ። በማግስቱ ጠዋት መኪናዬ ከፍተኛው ጽሕፈት ቤት ቆማ ስለነበር የከፍተኛው ሹም ቁልፉን ከሰጠኝ በኋላ መኪናዬን ይዤ እንድሄድ ፈቀደ። አቤቱታ ለማቅረብ ሞከርኩ። ሰውዬው ገላመጠኝ። ከእነመኪናዬ ያስረኛል ብዬ ስለሰጋሁ ወደቢሮ ሄጄ የፖሊስ ተጠሪ ለነበሩት ለኮሎኔል ሩንዳሣ አቤቱታ አቀረብኩ።

«ከእነዚህ ሰዎች ጋር አይጣሉ» የሚል ምክር ሰጡኝ ሩንዳሣ። «ጊዜና ሥፍራ ፈልገው ይበቀሉዎታል።» ለኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ አቤቱታ አቀረብኩ። «ስብሰባ ላይ አነሳዋለሁ» አለኝ። ለፍትህ መታገል ትርጉም እንደሌለው ገባኝ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በትንባሆ ፋብሪካ አጠገብ የሚገኘው ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ሊቀ መንበር የነበረው ከሰተ የሚባል ካድሬ፣ ትንሣኤ የምትባል ሌላ ካድሬና እንዲሁም ኃይለ ማርያም የሚባል ታጣቂና ባምቢስ አጠገብ መኪናዬን ሲነጥቁኝ በሹፌርነት ይዟት የሄደው ሰው አራት ሆነው በመኪና በመከታተል እቴጌ ሆቴል አቅራቢያ መሣሪያ ወድረው አስቆሙኝ።

«ነጋሽ ገብረማርያም እርስዎ ነዎት?» አለ ከሰተ።

«አዎን፣» አልኩት።

«ልማተ ከተማ የምትባለው ጋዜጣ አዘጋጅ ነዎት?»

«አዎን።»

«ፈረጠጠ ብለው የጻፉትን አስታውሳለሁ፣» አለኝ።

«ኃይሉ የተናገረውን ቃል ነው የጻፍኩት፤» አልኩት።

ከሰተ ወደ ከተማ ልማት መሥሪያ ቤት እየመጣ ከእነ ኃይሌ ፊዳ ጋር ሲገባና ሲወጣ አየው ነበር። ንግግር የለንም።

«አንዳንድ ጥያቄ ልንጠይቅዎት እንፈልጋለን። ወደ ቢሮ እንሂድ!» አለና እኔ እነሱ መኪና ውስጥ እንድገባ አዘዘኝ። ባምቢስ አጠገብ መኪናዬን እየነዳ የወሰዳት ልማደኛው ካድሬ ይመስለኛል እኔ መኪና ውስጥ ገባ።

07 ቀበሌ ጥሩ ስም እንደሌለው ሰምቻለሁ። ከእናንተ ጋር አልሄድም ብዬ ብከራከር የሚሰጠው ዳኝነት ምን እንደሆነ ቀደም ብዬ ተረድቼዋለሁ። ቀበሌው ጽሕፈት ቤት ስንደርስ ወደ መመርመሪያው ክፍል አስገብተው «የማንኛው ፖለቲካ ድርጅት አባል ነዎት?» አለኝ ከሰተ።

እኔ የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆኔን ነገርኩት።

«እሺ ይኸንን እንተወውና መትረየስ ደብቀዋል ሲባል ሰምቻለሁ» አለኝ።

«የምን መትረየስ ? ከስሙ በስተቀር መትረየስ ምን እንደሆነ አላውቅም» አልኩት። «እንኳንስ መትረየስ ሊኖረኝ።»

«መሣሪያ አልነበረዎትም?»

«ፊሎቨር ጠመንጃና የአደን ጠመንጃ ነበረኝ። ለደርግ አስረክብያለሁ» አልኩት።

«አሁን ምንም መሣሪያ የለዎትም?» አለ።

«ሽጉጥ አለኝ። ፈቃድም አለኝ» አልኩት።

«ማን ፈቀደልዎ?»

«ደርግ »

«እንዴት ፈቀደልዎ?»

«ሸጉጤ ከሌሎቹ መሣሪያዎቼ ጋር በአሠሳው ተወስዶ ነበረ። ሌሎች እንደሚያደርጉት ሽጉጡ እንዲመለስልኝ ለሚኒስትሩ ማመልከቻ ጻፍኩ። እሳቸው ለደርግ ስላመለከቱ ሽጉጡ ተመልሶልኛል።»

የደርግ ወታደሮች የአዲስ አበባን ከተማ እያሰሱ መሣሪያ ሲሰበስቡ እኔ ወደ ናዝሬት ሄጄ ነበረ። መሣሪያውን ያስረከቡት ቤተሰቦቼ ናቸው። ወደ ናዝሬት ስሄድ የወሰድኳት አነስተኛ የብሬታ ሽጉጥ አልተመዘገበችም ነበር። ፈቃድ አልነበራትም። ፈቃድ ከነበረው ሽጉጥ ጋር አብሬ ካዝና ውስጥ አስቀምጫት ስለነበር ሽጉጡን ሄደን እናምጣ ስላለኝ የዚያችን ሽጉጥ ታሪክ ነገርኩትና «በአንዱ ሽጉጥ ከታመንኩ ይቺን ቀስ ብዬ ፈቃድ አወጣላታለሁ ብዬ ነበር፤ ጊዜ ባለማግኘቴ ፈቃድ አላወጣሁም» በማለት አንድ ደካማ ምክንያት ሰጠሁ።

ወደ 07 ቀበሌ ይዘውኝ በመጡት ካድሬዎች በመሣሪያ ታጅቤ ቤቴ ስደርስ ሽጉጦቹን ከአስረከብኳቸው በኋላ «ቢሮ ደርሰው መሣሪያውን አስመዝግበው ይመለሳሉ» ተባልኩና ወደ ቀበሌ 07 እንደገና ተወሰድኩ።

በዚህ ቀበሌ ውስጥ ቁጥራቸው በርከት ያሉ በኢህአፓነት የተወነጀሉ ወጣቶችና የአውራ ጎዳና ባለሥልጣናት ታፍገውበታል። እኔን ምርመራው ክፍል አስገብተው እግሬን በኮሬንቲ ገመድ እየገረፉ «የደበቅሽውን መትረየስ አውጣ» ይሉኝ ጀመር። የሌለው ከወዴት ይወጣል! ድብደባቸውን ሲያበቁ አሥር ሰው እንድትይዝ በተሠራች ክፍል ውስጥ ከሠላሳ እሥረኛ ጋር ታፍኜ እንድሰቃይ አደረጉ። አንድ ነፍሰ ገዳይ ወጣት እጆቼ በሰንሰለት ታስረው ከእኛው ጋር ይሰቃይ ነበር።

በምገረፍበት ጊዜ የጩኸትና የእርዳታ ድምፅ እንዳላሰማ ነው መሰለኝ ወይዘሮ ትንሣኤ አፌን በቆሻሻ ጨርቅ እያፈነች መትረየሱን ከደበቅህበት አውጣ ትለኝ ነበር።

ገራፊዎቼ ቴዎድሮስና ቢንያም የሚባሉ ሁለት ወጣቶች ነበሩ። እንደሰማሁት ከሆነ ሁለቱም የኢህአፓ የገዳይ ጓዶች ምልምል እጩዎች ሆነው የተያዙ ናቸው። እኛን በማሰቃየት የእነሱ ኃጢአት እንዲሠረይላቸው የሚደክሙ ርህራሄ የሌላቸው ወጣቶች ስለነበሩ በሚሠሩት የማሰቃየት ተግባር የሚደሰቱ ይመስሉ ነበር።

የአውራ ጐዳና ባለሥልጣናት ሲገረፉና ሲደበደቡ ሰንብተው ከቁስላቸው ሲያገግሙ ሞት እንዳይመጣ ፈጣሪያቸውን ይማለዱ ነበር። እኔ ከመታሠሬ በፊት አንዳንድ ጭምብል የለበሱ ካድሬዎች ወይም ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ከጨለመ በኋላ በመጠጥ ፈረስ ተጭነው በመምጣት እሥረኛውን ከእሥር ቤት እየጐተቱ በማውጣት የብዙ ሰዎች ነፍስ ያጠፉ እንደነበር ሰምቻለሁ።

በእሥር ቤቱ ውስጥ ሀያ ስድስት ቀን ትኋንና ቁንጫ እየላሰኝ፣ ምንጣፍና ፍራሽ በሌለው የሲሚንቶ ወለል ላይ ስተኛ ከሰነበትኩ በኋላ፣ የታሠርኩበት ምክንያት የአብዮቱ ሂደት እንዲገባውና ፈቃድ የሌለው ሽጉጥ በመያዙ ነው ተብዬ በአማላጅ ብዛት ተፈትቻለሁ።

*ከእሥር ቤት ያሰናበተኝ የፍርድ ሸንጐ ሊቀመንበር ነው የሚባል ሰው ነበር። ፈቃድ የሌለው ሽጉጥ በመያዝ 500 ብር ቅጣት የተበየነብኝ መሆኑ ከተነረገኝ በኋላ አንዱ ሽጉጥ ፈቃድ እንዳለው አስታውሼ ሽጉጡ እንዲመለስልኝ ጠየቅሁ። «ይኼ ሰውዬ ጤና የለውም» ብሎ ወደ እሥር ቤት እንድመለስ ስለአዘዘ አፌን በመሐረቤ አፍኜ እጅ ነስቼ ወጣሁ።*

*ሕጋዊ የሆነ የመንግሥት ካርኒ እያለ «አቶ ነጋሽ ገ/ማርያም በተከሰሱበት ጉዳይ የመቀጫ ገንዘብ 500 ብር ተቀብያለሁ» የሚል ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 የሚል ማህተም ያለበት ነጭ ወረቀት ተሰጥቶኛል። ለማስረጃነት ያህል ከዚህ ጋር አባሪ አድርጌ አቅርቤዋለሁ። ወይዘሮ ትንሣኤ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለፈፀመችው በደል 17 ዓመት በእሥር እንድትቀጣ ፍርድ ቤት መወሰኑን በሬዲዮ ሲነገር ሰምቻለሁ። ከሰተስ? ገና ጠይቄ መረዳት አለብኝ።*

*ከሰተ የአንድ ባላጋራዬ ዘመድ መሆኑ ከጊዜ በኋላ ተነግሮኛል። እሷን ለማስደሰት ይሆን የገረፈኝ? ቢሆንስ ምን ማድረግ እችል ነበር?*

*የደርግ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን በደልና እልቂት ታሪክ ፀሐፊዎች በቸልታ የሚያልፉት አይመስለኝም። ዛሬ በእሥር ላይ የሚገኙ የደርግ ባለሥልጣናት በአብዮቱ ስም የብዙ ሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ ምክንያት ሆነዋል[10]። ሃላፊነቱ የእነሱ ነው ወይስ አይደለም ብሎ መወሰን የፍርድ ቤቱ ፈንታ ቢሆንም፣ የአንዳንዶቹ የወንጀል ድርጊት በአቃቤ ሕግ ክስ እየተጣራ ውጤቱ በሚዲያ ሲነገር እሰማለሁ። አንዳንዶቹ ቀን ቅዱስ ሌት እርኩስ እየሆኑ የፈፀሙትን ወንጀል በሬዲዮ ስንሰማ ከመገረም አልፈን እንደነግጣለን።*

*ደርግ መሣሪያ አስታጥቆ ሕዝቡን እንደፈለጋቸው እንዲያጉላሉ ያዘመታቸው ካድሬዎች በሠላማዊ ግለሰቦች ላይ ይፈጽሙት የነበረው ወንጀል በአሰቃቂነቱ ወደር አይገኝለትም ነበር። አንዳንዶቹ በሠፈሩት ቁና ባይሠፈሩም ቅሉ ከጥፋታቸው እንዲማሩ ትምህርት እየተሰጣቸው ነው።*

*በቂም በቀል ተነሳስተው ያጉላሉኝ ካድሬዎች እኔው የነገርኳቸውን ፈቃድ ያልነበረውን ሽጉጥ የወንጀሉ መነሻ በማስመሰል ለፈፀሙብኝ በደል ምክንያት አድርገው ተጠቅመውበታል። መሣሪያ የመያዝ ልምድ የነበረኝ ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ቢሆንም፣ የደርግ ጁንታ መሣሪያዬን ነጥቆ እኔን በማስገረፍ የልጆች መጫዎቻ አድርጎኛል። «ጉብዝና ጊዜና ሥፍራ ይጠይቃል» የሚለውን አባባል እንዳምን ትምህርት አግኝቼበታለሁ።*

*አዲስ ዘመንን ጋዜጣ ለማሻሻል የአደረግሁት ሙከራ ከጊዜው በፊት የተጣለብኝ ብርቱ ሃላፊነት እንደነበረ ሚዲያን አስመልክቶ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የታየው ለውጥ ምስክር ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ማናቸውም በሠላም መንገድ የማይመጣ ለውጥ በአመጽና በመፈንቅለ መንግሥት እንደሚመጣ ከታሪክ መማር ይቻላል።*

---

[10] የደርግ አባላት የነበሩት ባለስልጣናት፣ ለብዙ አመታት ከተከራከሩ በኂላ፣ ፍርድ ቤቱ የሞት ፍርድ በይኖባቸው ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ መንግስት በምህረት ለቋቸዋል።

ሐገራችንንና ወገናችንን በየተሰለፍንበት የሙያ ዘርፍ ለማገልገል ምን አይነት ሙከራ አድርገናል? የሚለው ጥያቄ እያንዳንዳችን ልናጤነውና ልናስብበት የሚገባ ጥያቄ ነው፡፡ ሕይወት አጭር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ገና በለጋ ዕድሜያቸው የሚቀጠፉትን ኢትዮጵያውን ስናይ፣ ከምንጊዜውም ይበልጥ ራሳችንን ለመጠ በቅና ጊዜያችንንም እርባናና ፋይዳ ባለው ተግባር ላይ ለማዋል መድከም ያለብን ይመስለኛል፡፡

All of us are not here

There are those who are gone

But we go on and on

በማለት አንድ ባለቅኔ የጻፈውን ስመለከት ነገ ዛሬ የሆነ ይመስለኛል፡፡

ሁላችን የለንም አያ፤ ስንቱ ሄዷል

ተፈጥሮ ነውና ጉዞው ይቀጥላል-ይቀጥላል እንደማለት ነው፡፡

ጋዜጠኛ ለመሆን የፈለግሁት፣ ደራሲ ለመሆን እመኝ ስለነበር ነው ብያለሁ፡፡ በዚህም ሥራ ቢሆን ምኞቴን በተግባር ለመተርጐም የተጋሁበት አልመሰለኝም፡፡ በዕድሜዬ በከንቱ ያጠፋሁትን ጊዜ ሳስብ እራሴን አበክሬ እወቅሰዋለሁ፡፡ የእኔው ዕድል ያጋጠመው አንድ ፈረንጅ የጻፈው ቃል እኔንም ይወክላል ብዬ አስባለሁ፡፡ «I had an ambition to become a writer, but destiny willed otherwise and made me a nobody instead.» ደራሲ ለመሆን ብርቱ ምኞት ነበረኝ፡፡ የሕይወት ዕጣ ፈንታ ሆነና አልባሌ ሆኜ ቀረሁ እንደማለት ነው፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ቤትና ርስት እንደማይመለስ እቅጩን ቢነግረንም፣ መሣሪያ ገዝተን በሕጋዊ ፈቃድ ራሳችንንና ንብረታችንን መጠበቅ እንችላለን ብለን የምንጓጓ ሰዎች ነበርን፡፡ ይህንን ፍላጐታችንን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲያውቁልንና እንዲፈቅዱልን *በአዲስ ዜና* ጋዜጣ አመልክቻለሁ፡፡ (ማመልከቻው ከዚህ ጋር አባሪ ሁለት ሆኖ ቀርቧል፡፡)

ይቻላል ወይም አይቻልም የሚል መልስ አልተገኘም፡፡ ምናልባት የእኔ ስህተት መሪዎች ሲባሉ የአናሣ ዜጐቻቸውን ጥያቄ ግምት ውስጥ አስገብተው በቢሯቸው በኩል መልስ ይሰጣሉ ብዬ ማመኔ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይኸ ጥያቄ የእኔ ጥያቄ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ታላላቅ የሐገር መሪዎች የእናንተንም ችግር እናደምጣለን እያሉ መልስ የሚሰጡት፡፡ ዜጐችና መሪዎች የሚገናኙበት አንዱ ድልድይ ይኸ ስለሆነ፡፡ ለዚህ ነበር ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መኪናቸውን አውራ ጐዳና መካከል እያስቆሙ የዜጐቻቸውን አቤቱታ የሚቀበሉት፡፡ እኔም እስከ ዛሬ ድረስ የአዎንታ ወይም የአሉታ መልስ እየተጠ ባበቅሁ ነኝ፡፡ ጥያቄዬ የማያሳስብና የሞኝ ጥያቄ ከሆነብኝ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

በመጨረሻ በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ሆነ ተቃዋሚ ኃይሎች በሰላና በተራቀቀ የፖለቲካ ሥልት ሲወዛገቡ እንሰማለን፡፡ ጋዜጣም እናነብባለን፡፡ ይኸ በእጅጉ መራራና አሳዛኝ የሆነ የፖለቲካ ግብግብ ለደሀው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ የዕድገት ጐዳና ለመቀየስና በእጅጉ አሳፋሪና አስፈሪ ከሆነ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ ለማውጣት

ይሆን? ወይስ ለሥልጣን ሲባል የሚከፈል የሞት ሽረት መስዋዕትነት ነው? የዚህን ጥያቄ መልስ የሚያውቁት ፖለቲከኞቹና እግዚአብሔር ብቻ ነው ማለቱ ትክክል ይመስለኛል፡፡

ለሐገራችን ደህንነትና ለብሔራዊ ክብራችን የምንቆረቆር ከሆነ በጐሣና በቋንቋ ተከፋፍለን ራሳችንን በራሳችን ለማጥፋት ከምንሽቀዳደም ይልቅ ለተሻለ ሕይወትና የኑሮ ደረጃ በመታገልና በመረባረብ ለዘመናት ሲያሰድበንና ሲያሳፍረን ከኖረው የድህነት አረንቋ ለመላቀቅ ቆርጠን መነሳት አለብን፡፡ እዚህም ላይ ሚዲያው ወሳኝ የሆነ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡

በታሪካችንም ሆነ በዘመናዊ ሥልጣኔያችን የተኩራራንና የታፈርን ሕዝቦች ለመሆን ከተፈለገ ከያንዳንዳችን የሐገርና የሕዝብ ፍቅር፣ ኢትዮጵያዊነት፣ ይዋል ይደር የማይባል Commitment ይጠበቃል፡፡

አሊስ ዱዌር ሚለር (Alice Duer Miller) የተሰኘች ደራሲ The White Cliffs በተሰኘው መጽሐፏ አገሬን እወዳለሁ ማለት እስከምን ድረስ እንደሆነ በሁለት ስንኞች እንዲህ ትለናለች፡-

I have seen much to hate here,
Much to forgive,
But in a world where England is finished and dead,
I do not wish to live.

እንግሊዝ በሚለው ቃል ፈንታ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ብተካበት ትርጉሙ እንዲህ ይነበባል፡-

*ይቅርታ የሚያሻው የሚያስጠላ ነገር*
*ብዙ ግፍ ተሠርቷል በዚች በእኛው ሐገር*
*ግን ኢትዮጵያ አልቆላት ወድማ ከማያት*
*መኖር አልመኝም ይሻለኛል ሞት፡፡*

ይኸ ለድርድር የማይቀርብ እምነትና ብርቱ አቋም የሁላችንም የሕይወት መርህ (credo) እንዲሆን እመኛለሁ፡፡

# አባሪ አንድ

## <u>ርዕስ አንቀጽ</u>

### ***<u>ልደት ምንድነው?</u>***

*ልደት ማለት መወለድ፣ መውጣት፣ መገለጥ፣ መከሠት ወይም መገኘት መሆኑን የኢትዮጵያ ሊቃውንት አብራርተው ያትታሉ፡፡*

*ልደት ልማድንና ባህልን ተደግፎ የሚከበር ቀን እንደመሆኑ መጠን ሠልጥነዋል በሚባሉት አገሮች ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የተወለደበትን ቀን ያስታውሳል፡፡ ያከብረዋልም፡፡*

*የዕድሜውን ብዛት እንዲያስታውሱት የተደረደሩትን ነዳጅ ሻማዎች አጥፍቶ፣ ብስኩቱን ቆርሶ፣ የዘመድ የወዳጅን መልካም ምኞት ከተቀበለ በኋላ፣ ራሱን እንዲህ ሲል በመመራመር ይጠይቀዋል፡፡ ከመወለድ ወደ ማደግ፣ ከማደግ ወደ መብሰልና ወደ መደርጀት እነሆ ደርሻለሁ፡፡ ልኖረው ከተፈቀደልኝ ዘመን በየ* 12 *ወሩ አንድ ዓመት በፍጥነት እየተቀነሰ ይሄዳል፡፡ በዕድሜዬ ውስጥ ሕሊናን የሚያረካ ልብን የሚያኮራ ምን የተለየና ቀዋሚ የሆነ ሥራ ሠራሁ ካቻምና ምን ሠራሁ? አምናስ ? ዘንድሮስ. . .*

በአገራችን ውስጥ ብዙዎቻችን ልዩ ልዩ የበዓል ቀናትን ጠንቅቀን ስንጠብቅ የልደታችንን ቀን ሳናውቀውና ሳናከብረው እንረሳለን፡፡ (እንሞታለን)

*የሆነ ሆኖ መወለድ ማንም የሚያደርገው የተፈጥሮ ግብር ሲሆን ራሳችንን ለታላቅ ሙያ መፍጠር፣ ወይም ትሩፋት ለሞላበት አገልግሎት ማዋል ለልባችን ኩራት ለመወለዳችንም ምክንያት እንደሚሆን አይጠረጠርም፡፡*

*ዛሬ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የልደት በዓል ስናከብር የሚገጥመን የመመራመር ጥያቄ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ግርማዊነታቸው ምን ሠሩ? የሚል ጥያቄ አይደለም፡፡ የዚህ ጥያቄ መልስ በየዕለቱ በምናየው ሥራ ተገልጾአል፡፡ የሚገጥመን ጥያቄ ኢትዮጵያን አሁን ከምትገኝበት ደረጃ ለማድረስ አንድ ሰው ምን ያህል የመሪነት ተግባር፣ የአስተያየት ጥልቀት፣ የማይገታ የሕሊና ትግል፣ የማይበገር ቆራጥነት ይዞ መነሳት አለበት ብለን ነው፡፡*

*የጃንሆይ ልደት የኢትዮጵያ ልደት ነው፡፡ እንዲያውም ጃንሆይ ለራሳቸው የሚገባውን ውለታ፣ ክብርና ምሥጋና ለኢትዮጵያ ይሰጥ በማለት «የዛሬውን የልደቴን በዓል ስትጠባበቁት በነበረው በኢትዮጵያ ልደት እለውጠዋለሁ» ብለው የተናገሩትን ቃል ሳናስታውሰው አናልፍም፡፡*

*ዛሬ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የግርማዊነታቸውን ዕለተ ልደት በሚያከብርበት ቀን ልደት ምንድነው? ከአንድ ሰውስ የሚጠበቀው አገልግሎት እስከምን ድረስ ነው? እያለ ራስን መጠየቅና መመራመር ግዴታ ይሆንበታል፡፡*

## አባሪ ሁለት

## ***በድዱ ይስቃል***

ጥሮ ተኛ ሁሉ አበሉ አነስተኛ፣
ብሶቱን ያሰማል ሲቀመጥ ሲተኛ።
ደጉ ጊዜ አለፈ፣የዛሬው ይቅር፣
ጧት ቁርሱን ሳይበላ ማታ ጦም ማደር።
አሉና እንጋጠጡ እግዜርን ፍለጋ፣
ጌታዬ አታጋልጠኝ ለረሃብ አለንጋ።
ብለው ተማጠኑ፣ የነገውን ፈሩ፣
የባሰም ይኖራል ብለው ጠረጠሩ።
የትዬ-ለሌ ነው የሸመታው ጣጣ፣
50 ብር ተሸርፋ ለስንቱ ልትወጣ።
ምኑን ከምን ላርገው እናንተው ፍረዱ፣
ይቅር ሥጋ ቅቤው ጥሬው መወደዱ።
አሉና ጠየቁ፣ እንድናጽናናቸው፣
ከኛ መልስ ታጣና ዝም ስላልናቸው፣
ልጆቻችሁ ሁሉ አሜሪካ ናቸው?
አሉና ጠየቁ የደላን መስሏቸው።
አሁንም መልስ አጡ፣ ሁሉም ይቆዝማል
ትንፋሽ መጨረስ ነው መንግሥትን ማን ያማል።
አምስት ልጆች አሉኝ ፣ የላቸውም ሥራ፣
ሁሉን ግዛ ባዮች ሰምተዋል ሲወራ።
ብለው ተካከዙ ጡር ቢኖር ነው አሉ፣
ሲመሽ መንገላታት ውለታ እንዳልዋሉ።
እኔ መሃይም ነኝ፣ ልጆቼ አይማሩ፣
የምከፍለው ታጥቶ ገንዘብ በየወሩ።
የፈረንጅ ውራጅ ሰልቫጅ ባይኖር ኖሮ
እርቃናችን ነበርን እኛማ ዘንድሮ።

**ሕክምና አናውቅም መድኃኒት አንገዛ**
**ደቂሶን ይሄዳል ህመሙ እንደዋዛ፡፡**
**አበሏ ተተክላ አትወርድ፣ አትወጣ፣**
**እግዚኦ ማለት ነው፤ ምፅዓት እስኪመጣ፡፡**
**ብለው ተናገሩ፤ አድማጩም ተስማማ፣**
**የኤም ትዳር ያው ነው እያለ እያቅማማ፡፡**
**ተመስገን እንበለው ጥርሳችን ረግፏል፣**
**በልቶ ካልተሳቀ ቢያገጥ ምን ያደርጋል?**
**ብለው ፈገግ አሉ ጥርስ አልባ ነበሩ፣**
**እንደሡራ አይገድል ሆነና ነገሩ፡፡**
**ሁሉንም ተናግረው ልንሄድ ስንነሳ፣**
**አንዲት ቃል ጨመሩ፣ መቼም አትረሳ፡፡**
**«ጡረተኛ ሁሉ ሲሄድ ያስታውቃል፣**
**አንጀቱ ተጣብቆ በድዱ ይስቃል»**

አባሪ ሶስት

***<u>ግልጽ ደብዳቤ</u>***

ለክቡር ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ

- *ሽጉጥ ለመግዛት የፈቃዱ  ጉዳይ ችግር እየፈጠረብን ነው*

*ክቡር ሆይ*

*እያንዳንዱ አትዮጵያዊ የእድገት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት እንዲሁም የንብረት መብት እንዳለው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ* 14፣15፣16፣26፣40 *ተረጋግጧል።*

*እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ መብቶች ተግባራዊ መሆን የሚችሉት እያንዳንዱ ዜጋ ሕይወቱን፣ ነፃነቱን፣ ንብረቱን ለመጠበቅና ለማስከበር የሚያስችለው ብቃት ሲኖረው ነው።*

*የሀገራችንን ልማድና ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንቃኝ፤ እያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወቱንና ንብረቱን ጠብቆ የኖረው በፖሊስ ጥበቃና አጋርነት ብቻ አልነበረም። ግለሰቡ ተበድሮም ሆነ ተለቅቶ ወይም የቤት እንስሳት ሸጦ አንድ አሮጌ መሣሪያ በመግዛት አጥሩን ዘልሎ፣ ታማኝ ውሻውን ገድሎ ሊዘርፈው የመጣውን ወስላታ ይፋለመዋል። ሌባና ወንበዴውም ሆነ ባለንብረቱ መሣሪያ እንዳላቸው ስለሚተዋወቁ «እዚያም ቤት እሳት አለ» በማለት ሁለቱም ባላንጣዎች ተፈራርተውና ተከባብረው በሠላም ኖረዋል።*

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

*በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይመራ የነበረው የደርግ ጁንታ መሣሪያችንንና ንብረታችንን (ቤትና መሬት) ነጥቆ ሕይወታችንና መብታችን እንዲደፈር በማድረጉ፤ የመኖር ዋስትናችን ድህነታችን ብቻ ሆኖ ቆይቷል። የቤቱና የመሬቱ ጉዳይ እስከ አሁን ድረስ ምሁራኑን እያነጋገረ መሆኑ አይዘነጋም።*

*ዛሬ በሽምግልና ዕድሜ ላይ የምንገኝ አዛውንቶች ለሐገራችን ዕድገትና ነፃነት ተቆርቋሪ በመሆን እንደየአቅማችን አስተዋጽኦ ማድረጋችን አይካድም። አንድ አሮጌ መሣሪያ ለመያዝ የቀየ ልምድና በዕድሜ የሰከነ ትዕግሥት አለን። በአካባቢያችን ሕብረተሰብ ዘንድም በጐ አመለካከት ያልተነፈግን ዜጐች በመሆናችን መንፈሳዊ ኩራት ይሰማናል።*

*አሮጌ መሣሪያ እንደ ክቡር ዕቃ መቆጠሩ ቀርቶ ተራ መገልገያ በሆነበት በአሁኑ ወቅት ሕይወታችንንና ንብረታችንን የምንጠብቅበት ሽጉጥ ለመግዛት የፈቃዱ ጉዳይ ችግር እየፈጠረብን ነው። በተለይም እኛ አዛውንቶች አባረን የማንይዝ፣ ሸሽተን የማናመልጥ፣ ተናንቀን የማንጥል በመሆናችን የስለትም ሆነ*

*የጦር መሣሪያ ከያዙ ሌቦችና ዘራፊዎች* (ወስላቶች) *ጋር መታገል እያስፈራንና በእጅጉ እያሳሰበን ነው*፡፡

*ፖሊስ የያንዳንዱን ግለሰብ ሕይወትና ንብረት ለመጠበቅ እንደማይችል ሌሊቱን በሙሉ እያደቡ የሚዘዋወሩት ሌቦች ሳይቀሩ ያውቁታል*፡፡

*ያለ መንግሥት ፈቃድ* በስውር የሚገዛ *መሣሪያ* ከጥቅሙ ይልቅ *ሥጋቱ* ስለሚያመዝን፣ ሕጋዊ በሆነ *መንገድ* አሮጌ *መሣሪያ* ገዝተን ሕይወታችንንና ንብረታችንን እንድንጠብቅ፣ አስፈላጊውንም ፎርማሊቲ አሟልተን ግብሩን እየከፈልን ደካማው ጉልበታችን የመንፈስ ጥንካሬ እንዲያገኝ ለማድረግ እንድንችል የጊዜው ሁናቴ ግድ ብሏል፡፡

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

በእጅጉ ውስብስብ የሆነውን የኢትዮጵያ የኤኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ችግር ለመፍታት ብርቱ ኃላፊነት ተሸክመው ከፍ ያለ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ይቺ አነስተኛ የሆነች የግል ጉዳይ ክቡርነትዎ ዘንድ በመቅረቧ ውድ ጊዜዎን መሻማቴ ተሰምቶኛል፡፡ ዳሩ ግን በአገራችን የሥልጣን ተዋረድ ከታች ወደ ላይ ዳገት እየቧጠጡ ከመውጣት ይልቅ፣ ከላይ ወደታች ቁልቁለቱን እየተንደረደሩ መውረዱ እንደባህል ሆኖ ሲሰሠራበት የቆየ ዘይቤ መሆኑን በማስታወስ ይቺን ግልጽ ደብዳቤ ከመጻፍ የተሻለ አማራጭ መንገድ ስላጣሁ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡


ከታላቅ አክብሮት ጋር

*ነጋሽ ገ/ማርያም*

*አዲስ ዜና መጋቢት* 3/95

## አባሪ አራት

### ደረሰኝ



6.10.70

6-10-70

# የኢትዮጵያ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ አጀማመርና ሂደት
# (1933 - 66)

*ጥሩነህ ዜና*

ኢትዮጵያ በመልክአ ምድርዋ አቀማመጥ የተነሳ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነቷ የጐላ ሰለነበር፣ ከጥንት ጀምራ፣ በወቅቱ ከነበሩ ታላቅ ከሚባሉ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ነበራት። በዚህ መሰረት፣ ጥንታዊት ኢትዮጵያ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ከባይዛንታይን፣ ከፋርስና ከግብጽ መንግሥታት ጋር ቅርብ ግንኙነት እንደነበራት በታሪክ ተመዝግቧል። ከአክሱም መውደቅ በኋላም ቢሆን የኢትዮጵያ ነገስታት ከግብጽ፣ ከፖርቹጋል፣ ከሩሲያና ከሌሎች አገሮች ጋር፣ በተለያዩ ምክንያቶች፣ አልፎ አልፎ ግንኙነት ሲፈጥሩና ሲተባበሩ እንደነበረ የሚታወቅ ነው። የቀይ ባህር አካባቢ ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ የእስልምና ተከታይ በሆኑ ሀይላት እጅ በመውደቁ፣ የኢትዮጵያ ነገስታት ከውጭ መንግስታት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየተዳከመ ሄዶ እንደገና ሊያንሰራራ የቻለው፣ በ1869 ዓ.ም የስዊዝ ካናል ከተከፈተ በኋላ እንደነበር እሚታወቅ ነው።[1] የስዊዝ ካናል ከተከፈተ ወዲህ፣ የቀይ ባህር አካባቢ ለአውሮፓውያን የኢኮኖሚና የንግድ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታን በማግኘቱ፣ አገሮቹ አካባቢውን ለመቀራመትና ለመቆጣጠር ቻሉ።

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት አካባቢውን ከተቀራመቱ የአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች ጋር፣ የአገራቸውን ዳር ድንበርና ህልውናዋን ለማስጠበቅ ሲሉ፣ የተለያዩ ግንኙነቶች ሲያደርጉ ቆይተዋል። ሆኖም በተቋም የተደገፈ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ፍንጭ የታየው፣ አጼ ምኒልክ የመንግሥት አስተዳደር በዘመናዊ መዋቅር እንዲዘረጋና የአገሪቱ ዲፕሎማሲ በተቀነባበረ መልክ በሥርአት እንዲራመድ፣ ካቢኔ መሥርተው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሾሙበት እ.አ.አ በ1907 ዓም ነበር። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ በኤደን፣ በጅቡቲ፣ በካርቱምና በእየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ከፈተ። እንዲሁም የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ መዋቅር እየተጠናከረ መራመድ ሲጀምር፣ በተለይ በ1920ዎቹና በ1930ዎቹ ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በለንደን፣ በፓሪስ፣ በሮምና በካይሮ ሌጋሲዮኖች ሲከፈቱ፣ በጄኔቫ የሚሲዮን ጽሕፈት ቤት ተቋቋመ[2]። በዚህ ሁኔታ፣ በጥሩ ጅምር ላይ የነበረውን የዲፕሎማሲውን እንቅስቃሴ የማዘመኑ ሂደት በጣሊያን ወረራ ምክንያት

---

[1] Robert L Hess, *Ethiopia: Modernization of Autocracy (*London: Cornell University Press, 1970), pp.31-34.

[2] ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ «የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ይዘትና ሂደት።» (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀና ያልታተመ ሰነድ፣ አዲስ አበባ 1996 ዓ.ም.) ገጽ 14።

ተቋረጠ፡፡ በመሆኑም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እንደገና በሰው ኃይል ተደራጅቶና በውጭ ያሉ ለጋሲዮኖች ተጠናክረው የተገኙት ኢትዮጵያ ነፃነቷን ከተቀዳጀች ከ1941 ጀምሮ እንደሆነ ብዙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በለጋሲዮን ደረጃ የነበሩ የኢትዮጵያ የውክልና ተቋማት ወደ ኤምባሲ ደረጃ ከፍ ከማለታቸውም በላይ በበርካታ መዲናዎች አዳዲሶች ሊከፈቱ ችለዋል፡፡ በሰው ኃይል ረገድም የነበረው ችግር ቀስ በቀስ እየተሻሻለ ሄዷል፡፡ በንጉሱ ዘመን የተሾሙ 84 አምባሳደሮች የነበራቸውን የትምህርት ደረጃ ብንመለከት የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ ያላቸው 22፣ ወታደራዊ ትምህርትና ዲፕሎማ የነበራቸው 31 ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ሰርቲፊኬት፤ የቤተክህነት ትምህርት እና የትምህርት ደረጃቸው ያልተገለጸላቸው ነበሩ፡፡[3] ከጦርነቱ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ባለስልጣኖችም በማንኛውም መለኪያ ቢሆን ለቦታው ተገቢ የሆኑ በዘመናዊ ትምህርት የገፉና ያገራቸውን ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ጽኑ አላማ የነበራቸው ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል ፋሽስት ጣልያን ከኢትዮጵያ ከተባረረች በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትን የመሩት ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታእዛዝ፣ ብላቴን ጌታ ኤፍሬም ተወልደ መድህን፣ የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ሲረቀቅ አስተዋጽኦ ያደረጉትና በኤርትራ ጉዳይ በተመድ መድረክ የታገሉት ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ፣ በአፍሪካ አንድነት ምሥረታ ጥሩ ሚና የተጫወቱት አቶ ከተማ ይፍሩና ዶክተር ምናሴ ኃይሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሁኔታ፣ በንጉሠ ነገሡቱ ዘመን፣ በተለይም ከ1933 ጀምሮ፣ የዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ ዘመናዊ መልክ እየያዘ መሄዱ ግልጽ ቢሆንም፣ የሚታዩ ችግሮችም ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል ዋንኛው የመሥሪያ ቤቱ ሥልጣን ተጠቃሎ በንጉሰ ነገሥቱ እጅ መውደቁ ነበር፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሮች የሚሾሙት በእሳቸው መልካም ፈቃድ ከመሆኑም በላይ ሪፖርት የሚያደርጉት ቀጥታ ለእሳቸው በመሆኑ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና በኤምባሲው መካከል ያለው ግንኙነት የተዛባ ነበር፡፡ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ በአንዳንድ አቢይ የፖሊሲ ውሳኔዎች አንጻር የሚጫወተው ሚና ውስን እንደነበረ ይታወቃል፡፡ መሥሪያ ቤቱ የአገሪቱን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የሩቅና የቅርብ አላማዎችና ግቦች ነድፎ ለተግባራዊነቱ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን፣ የንጉሡንና የሌሎች ባለስልጣናትን ጉብኝት ሲያዘጋጅ፣ ብዙ ጊዜውን እንደሚያጠፋ፣ በወቅቱ የነበሩ ዲፕሎማቶች ይመሰክራሉ፡፡

ንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይን ሥራ በቅርብ የሚከታተሉትና አቢይ ጉዳዮችን ለመፈጸም የሚጠቀሙት የዲፕሎማሲ ፈለግ፣ ከመሪዎች ጋር ፊት ለፊት በሚደረግ ግንኙነት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በውጭ አገር በርካታ ጉብኝቶች አድርገዋል፡፡ ንጉሡ በዘመናቸው ከመቶ በላይ የውጭ አገር ጉብኝቶች

[3] ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ «የኢትዮጵያ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሮች፣ አምባሣደሮች፣ ልዩ መልእክተኞችና ሚኒስቴሮች ዝርዝርና አጭር የሕይወት ታሪክ» (ያልታተመ ገጽ የሌለው)፡፡

እንደአደረጉና ከውጭም 63 ርዕሰ ብሄሮችና ርዕሰ መንግሥታት ኢትዮጵያን እንደ ጉበኙ የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ[4]::

ነገር ግን ከጉዟቸው ብዛት ጋር የሚመጣጠን ብሔራዊ ጥቅም ለኢትዮጵያ ህዝብ አስገኝተዋል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አይደለም:: በተለይም፣ በኤኮኖሚ ልማት አንጻር፣ ኢትዮጵያ ከውጭ ስታገኝ የነበረው እርዳታ፣ አገሪቱ ከምእራብ አገሮች፣ በተለይም ከአሜሪካ ጋር ከነበራት ቅርበት አንጻር ሆነ አሜሪካ ለሌሎች ወዳጅ ለሆኑ የአፍሪካ አገሮች ከምትሰጠው እርዳታ ጋር ሲነጻጸር፣ ከሚገመተው እጅግ ያነሰ ነበር:: እ.አ.አ ከ1966 እስከ 1970 ድረስ ባሉት ጊዜአት፣ የአሜሪካ መንግስት ወዳጅ ለሆኑ የአፍሪካ አገሮች፣ ማለት ለናይጀሪያ፣ለሞሮኮ እና ለቱኒዚያ (ለእያንዳንዳቸው) የሰጠው የኤኮኖሚ እርዳታ በየአመቱ በአማካኝ 43 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ሲሆን ኢትዮጵያ በዚህ ወቅት ከአሜሪካ ያገኘችው የልማት እርዳታ 21.84 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማለትም ከዚህ በላይ ለተጠቀሱ አገሮች ከተሰጠው እርዳታ ከግማሽ በታች ነበር[5]:: እርግጥ ነው፣ ጉብኝቶቹ የንጉሰ ነገስቱን አለምአቀፋዊ ዕይታን አጎልብተዋል:: ዝናቸውንና ክብራቸውን አሳድገዋል:: እንዲሁም የኢትዮጵያ መሪ እንደመሆናቸው፣ በሄዱበት ሁሉ የአገሪቱ ስም በመገናኛ ብዙኃን በመሰራጨቱ፣ አገሪቱንም አለምአቀፍ ኮሚዩኒቲው እንዲያውቃት አድርገዋል:: ስለሆነም፣ በወቅቱ የአለም ህዝብ ስለኢትዮጵያ የነበረው መልካም ግንዛቤ፣ በአገር ውስጥ የነበረውን ድህነትና ኋላቀርነትን ያላገናዘበ ነበር::

የኢትዮጵያ የወቅቱ ዲፕሎማሲ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ችገሮች ያሉበት ቢሆንም፣ በርካታ ብሄራዊ ጠቀሜታ ያላቸው አቢይ ጉዳዮችን አከናውኗል:: ከነዚህም መካከል፣ ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ለማላቀቅ የተደረገው ትግል ቅድሚያ ሥፍራ ከሚይዙ የዲፕሎማሲ ክንዋኔዎች አንዱ ነው::

## የእንግሊዝ ወታደራዊ ግዛት በኢትዮጵያ

የእንግሊዝ መንግሥት፣ ጣሊያንን ከኢትዮጵያና ከአካባቢው ለማስወጣት፣ የአጼ ኃይለ ሥላሴ በቦታው መገኘት ያለውን ጠቀሜታ በመገመት፣ ንጉሱ በሱዳን በኩል ከእንግሊዝ ወታደር ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ወስኖ ነበር:: በዚህ መሠረት፣ ንጉሡ ከእንግሊዝ ወታደሮች ጋር በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ቢገቡም፣ ከኬንያ ወደ አዲስ አበባ የተንቀሳቀሰው የደቡብ አፍሪካን፣ የህንድን፣ የናይጀሪያን፣ የጋናን፣ የቤልጅግንና የፈረንሳይን ወታደሮች ያቀፈው የእንግሊዝ ሠራዊት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በአጭር ጊዜ ውስጥ የጣሊያንን ሠራዊት በማሸነፍ፣ አዲስ አበባ የገባው፣ ከንጉሡ አንድ ወር ቀደም ብሎ ነበር::

---

[4] በሪሁን ከበደ፣ *የአፄ ኃይለሥላሴ ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1993)፣ ገጽ 145::

[5] Tekeda Alemu, "The Unmaking of Ethio-American Military Relations: Foreign Policy towards the Ethiopian Revolution," (Ph.D. Dissertation, Clare Monts Graduate School, 1985), pp.130-144.

ንጉሠ ነገሥቱ፣ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት በቸርችልና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሆኑት በኤደን በተሰጣቸው ቃል መሰረት፣ ነፃይቱን ኢትዮጵያ ለመገንባት አዲስ አበባ ቢገቡም፣ የእንግሊዝ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ኃላፊዎች፣ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እንግሊዝ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ እንድትቆጣጠር ያስገድዳሉ የሚለውን አቋም በመያዝ፣ ንጉሱ ስልጣን እንደሌላቸው ገለፁላቸው:: በነዚህ ባለስልጣናት አስተሳሰብ ሊቢያ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያና የጣልያን ሱማሌ የጠላት ግዛቶች ስለሆኑ፣ የሰላም ንግግር በእንግሊዝና በጣሊያን መካከል እስኪደረግ ድረስ፣ በእንግሊዝ ቁጥጥር ውስጥ መቆየት አለባቸው::

እንግሊዞች በጣሊያን ላይ ጦርነት ባወጁበት ወቅት፣ የኢትዮጵያን ቅኝ ግዛትነት እውቅና አንስተው እንደነበርና ይህንንም በማረጋገጥ፣ እ.አ.አ. በ1941 የካቲት 4 ቀን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ኤደን በሕግ መምሪያ ምክር ቤት (በሀውስ ኦፍ ኮመንስ) ቀርበው፣ የኢትዮጵያን ነፃ መንግስት መመለስ የእንግሊዝ መንግስት እንደሚቀበል አረጋግጠው ነበር:: በዚህ ሁኔታ፣ ለንደን ባለው መንግስትና አዲስ አበባ ባሉት ወታደራዊና ሲቪል ባለሥልጣናት መካከል፣ ሰፊ የሐሣብ ልዩነት ተፈጥሮ የነበር ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ላይ በተጨባጭ ይንጸባረቅ የነበረው ግን የወታደሩ ክፍል ፍላጎት ነበር ::

ንጉሡ አዲስ አበባ እንደገቡ፣ 7 ሚኒስትሮችንና የሸዋን ጠቅላይ ገዥን በሾሙበት ወቅት፣ ጄኔራል ላሽ የተባሉ በአዲስ አበባ የእንግሊዝ ምክትል የፖለቲካ ኃላፊና የወታደር አዛዥ፣ ጃንሆይ ሹመት ለመስጠት ሥልጣን እንደሌላቸው እና እንግሊዝ ከጣሊያን ጋር የሰላም ስምምነት እስክትፈራረም ድረስ፣ አፄ ኃይለስላሴ የንጉሠ ነገስትነት ስያሜያቸውን ሆነ ሥልጣናቸውን ለመያዝ እንደማይችሉ ገልጸውላቸው ነበር[6]::

በዚህ ሁኔታ፣ የእንግሊዝ ወታደራዊ ኃይል፣ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካከል በ1934 ሁለት ውሎች እስኪፈረሙ ድረስ፣ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት መልክ ገዝቶ ነበር ለማለት ይቻላል:: ጣልያንን ከአገሩ አስወጥቶ ሙሉ ነጻነቱን ለመቀዳጀት ለጓጓው ህዝብ ይህ የእንግሊዝ ወታደራዊ አገዛዝ እጅግ የሚያበሳጭ ነበር:: በተለይም፣ እንግሊዞች በገቡላቸው ቃል መሰረት ወደ ዙፋናቸው ቶሎ በመመለስ፣ ህዝቡን ለማረጋጋትና የፈረሰውን የመንግሥት መዋቅር ለመገንባት የተቻኮሉ ንጉሥ ከፍተኛ የፖለቲካ ፈተና እንዳጋጠማቸው ግልጽ ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግስት በእንግሊዝ ወታደራዊ አገዛዝ ላይ ያለውን ግዙፍ ቅሬታ በመገንዘብ፣ እንግሊዞች ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለወደፊት ስለሚኖረው ግንኙነት፣ 1934፣ ሁለት ስምምነቶችን ተፈራረሙ:: በስምምነቱ መግቢያ ላይ ኢትዮጵያ ነፃ አገር መሆንዋን የሚጠቅስ አንቀፅ ቢኖርም ቀጥለው

---

[6] መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ (ተርጓሚ)፣ ጆን ስፔንሰር (ደራሲ)፣ *ጥርስ ውስጥ የገባች ሀገር* ፣(አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም) ገጽ 147-161::

የተዘረዘሩ በርካታ ዋና ዋና አንቀጾች ኢትዮጵያ አሁንም በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር መሆኗን የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል፣ ለእንግሊዝ አምባሳደር ከሌሎቹ ውጭ መንግስታት ተወካዮች ይበልጥ ክብር እንደምትሰጥ፣ የእንግሊዝ ዜጎች ለኢትዮጵያ መንግስት የፖለቲካና የህግ አማካሪዎች፣ የፖሊስ አዛዦች፣ አስተማሪዎችና የፍርድ ቤት ዳኞች በመሆን እንደሚሰሩ፣ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሳይፈቅድ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በወታደራዊ ጉዳይ ከሌላ የውጭ አገር መንግስት ጋር ምንም አይነት ስምምነት ለማድረግ እንደማይችል የሚዘረዝሩ ይገኙበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ ወታደራዊ ስምምነቱ እንግሊዝ በአዲስ አበባና በቀሩት ትላልቅ ከተሞች ወታደራዊ ቁጥጥር እንድታደርግ የሚፈቅድ ነበር፡፡ በኦጋዴን፣ በሀውድ እና በተጠበቀው ክልል (Reserved Area) የእንግሊዝ ቀጥተኛ ቁጥጥር እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡ የእንግሊዝ አውሮፕላኖችን በአገሪቱ አየር ላይ ለመብረር ብቸኛ ባለመብት አድርጓቸዋል፡፡ ኢኮኖሚውን በተመለከተ የእንግሊዝ የምስራቅ አፍሪካ ሽልንግ የአገሪቱ ኦፊሴላዊ ገንዘብ ሆኖ እንዲያገለግል ይፈቅዳል፡፡ ገቢና ወጪ ንግድ ቁጥጥር የሚደረገው ከለንደን ሲሆን ወደ ውጪ ከሚላከው ዕቃ የሚገኘው የውጪ ምንዛሪ የሚገባው ለእንግሊዝ መጠባበቂያ ነበር[7]፡፡እነዚህ የተዘረዘሩ የስምምነቱ አንቀጾች የሚያሳዩን፣ ከ1934 በኋላም ቢሆን፣ ኢትዮጵያ በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ስር እንደነበረች ነው፡፡

ይህ ስምምነት ተለውጦ ኢትዮጵያ ሙሉ ነጻነትዋን እንድትጎናጸፍና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሰፈነውን የኢኮኖሚና የስነ ልቦና ችግር ለመፍታት፣ ፈታኝ የሆነ የዲኘሎማሲ እንቅስቃሴ መደረግ እንዳለበት፣ የኢትዮጵያ መንግስት በውል ተገንዝቦት ነበር፡፡ ነገር ግን፣ መፍትሄው እንዲህ ቀላል አልነበረም፡፡

## ከእንግሊዝ ተፅዕኖ ለመላቀቅ የተደረገ የሁለት ፈር (Two Track) ዲፕሎማሲ

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን፣ በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ምክንያት የተፈጠሩትን ባለ ብዙ ፈርጅ ችግሮች ለማስወገድ፣ ሶስት ዓቢይ ጉዳዮች መፈፀም እንደነበረባቸው በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ እነዚህም፣ ከእንግሊዝ ጋር በ1934 ዓ.ም. የተደረጉትን ሁለት ስምምነቶች የሚተካ ሌላ ውል መፈራረም፣ የምስራቅ አፍሪካን ሽልንግ የሚተካ ብሔራዊ ገንዘብ ማውጣት እና ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ ወታደራዊ ተፅእኖ ሊያወጣ የሚችል የመሳሪያ እርዳታ ማግኘት ነበሩ፡፡ የተጠቀሱትን አላማዎች ለማሳካት የኢትዮጵያ አቅም እጅግ ውስን እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በወቅቱ እየተካሄደ በነበረው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ ኢኮኖሚው ያልደቀቀበት እና የአፍሪካን ሀገሮች እንደ ቅርጫ ተከፋፍሎ የመግዛት ልምድና ዓላማ ያልነበረው

---

[7] ላጲሶ ጌ. ድሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም ፣1900-1966* (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም) ገጽ 130-131፡፡

ኃያል አገር አሜሪካን እንደሆነ በመገንዘብ፣ ንጉሠ ነገስቱ ኢትዮጵያን የዚች አገር የቅርብ ወዳጅ ለማድረግ ቁርጥ ፍላጐት አድሮባቸው ነበር፡፡ አሜሪካን በበኩሏ፣ ኢትዮጵያ ከሶስቱ ጦረኛ ሀገሮች የአንዱን ወረራ ተዋግታ በማሸነፍ የመጀመሪያዋ ነፃ ሀገር በመሆንዋ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያን በአውሮፖና በመካከለኛው ምሥራቅ ለሚካሄደው ጦርነት የምግብ አቅርቦት ምንጭ እንድትሆን ለማድረግና የአሜሪካን ጦር ሠራዊት ከአስመራ ወጣ ብሎ የመገናኛ ኮር እንዲሆን ያሰበውን የመልእክት የመቀበያና የመመሳጠሪያ ጣቢያ እውን ለማድረግ ስትል፣ ለመቅረብና ለመርዳት ፍላጐት ማሣየት ጀምራ ነበር[8]፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የአሜሪካን መንግሥት፣ በተለይም ፕሬዝዳንት ሩዝቬልት፣ ከአጼ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ከኢትዮጵያ ወገን በከንቲባ ገብሩ ደስታ፣ በሀኪም ወርቅነህ፣ በተለይም በጦርነቱ ወቅት በዶ/ር መላኩ በያን፣ በአሜሪካን በኩል በነ William H. Ellis (ታዋቂ ነጋዴ), Rabbi Arnold Josiah Ford, W.E.B. Du Bois (ተቀዳሚ የጥቁር አንድነት ሊቃውንት), Col.John C Robinson (በማይጨው በኢትዮጵያ ጎን ሆኖ የተዋጋ) ግለሰቦች ጥረት፣ በከፍተኛ ደረጃ ያደገውን የአሜሪካ ጥቁሮች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያላቸውን አንድነትና ሶሊዳሪቲ በውል የተረዱ ይመስላል፡፡ለዚህ ነው በ1934 ፕሬዝዳንቱ ለንጉሱ  በጻፉት ደብዳቤ፦

> It is a source of much satisfaction to me and to the people of the United States that your country, which fought so courageously against the ruthless enemy, has regained its independence and self-government. The steadfast friendship of the American people and their sympathy with you in your period of trial will continue to be manifest during the day of reconstruction now facing your country.[9]

በማለት የአሜሪካን መንግሥት ሳይጨምር ህዝቡ (አፍሮ- አሜሪካኖች) ኢትዮጵያ በተወረረችበት ወቅት ሰለአሳየው ሶሊዳሪቲ ገልጸዋል፡፡

በዚህ ሁኔታ፣ ቀደም ብሎ ከጦርነቱ በፊት ተጀምሮ የነበረውን ግንኙነት ለማጠንከር፣ በሁለቱ መንግሥታት መካከል መግባባት ቢኖርም፣ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ይፋዊ መንገድ ግን አልነበረም፡፡ በወቅቱ፣ እንግሊዝ በኢትዮጵያ የነበረውን የመገናኛ መስመር በሙሉ ተቆጣጥራ ነበር፡፡ አሜሪካኖች በአዲስ አበባ የነበረውን ሌጋሲዩን እንደገና ለመክፈት ፈልገው፣ እንግሊዞች በቆንስላ ጄኔራል ብቻ እንዲሆን በማለት ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል፡፡ የአሜሪካን ሌጋሲዩን በአዲስ አበባ የእንግሊዝን ተፅእኖ አልፎ ከተቋቋመም በኋላ ቢሆንም፣ ከአሜሪካ ጋር ውጤታማ ግንኙነት ሲደረግ የነበረው ንጉሱ ለፕሬዝዳንት ሩዝቬለት በሚጽፏቸው ደብዳቤዎች እና በልዑካን ልውውጥ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ከአሜሪካን ጋር ውጤታማ ግንኙነት የተጀመረው በግንቦት

[8] መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ፣ *ጥርስ ውስጥ የገባች ሀገር*፣ ገጽ 147-161፡፡

[9] Negussay Ayele, *Ethiopia and the United States*.(The Season of Courtship, Volume 1) (Ocopy.com. USA, 2003), p.169.

*1935 ዓ.ም. በልጅ ይልማ ደሬሳ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑክ፣ በሆት እስፕ ሪንግ ቨርጀንያ በተካሄደው የዓለም የምግብ ድርጅት ስብሰባ ለመካፈል፣ ወደ አሜሪካ በሄደበት ወቅት ነበር፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ልዑክ ከአሜሪካን የውጭ ጉዳይ እና የገንዘብ ሚኒስትሮች፣ እንዲሁም ከፕሬዝዳንት ሩዝቤልት ጋር የተወያየባቸው ጉዳዮች አያሌ ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-*

1) *የኢትዮጵያ ብር የሚባል አዲስ ገንዘብ ለማውጣት የሚያስችል 4,525, 000 ግራም ብር* (Silver) *በብድር እንዲሰጣት፣*
2) *ከእንግሊዝ ጋር የተደረገውን የ1934 ስምምነት የሚተካ ስምምነት እንዲደረግ አሜሪካን በእንግሊዝ ላይ ግፊት እንድታደርግ፣*
3) *የኢትዮጵያ የባንክ፣ የገንዘብና የንግድ እንቅስቃሴዎች ከእንግሊዝ ቁጥጥር ነጻ እንዲወጡ የቴክኒክ እርዳታ እንዲደረግላት ነበር፡፡*

*እነዚህ ጥያቄዎች በቀረቡበት ወቅት፣ አሜሪካኖች በኢትዮጵያ ውስጥ እንግሊዝ የምትከተለውን የቅኝ ግዛት ፖሊሲ እንደማይደግፉ የሚያስረዱ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከአቶ ይልማ ጋር ቀደም ብለው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ስለተደረገው ወይይት፣ ለፕሬዝዳንት ሩዝቤልት እንደሚከተለው ገልፀው ነበር፡-*

> *እንግሊዞች በሚያዝያ ወር 1941 አዲስ አበባን ከያዙ በኂላ ኢትዮጵያን በጠላት እንደተያዘች አገር አድርገው አስተዳድረዋታል በማለት ሚስተር ደሬሳ የገለፁት እውነት ነው፡፡ በእጃችን ያለው ማስረጃ የሚያመለክተውም በዚህ ጊዜ ውስጥ እንግሊዞች ሀገሪቱን ረግጠው ማስተዳደራቸውን ነው፡፡ ስለዚህም ጃንሆይ እና ብዙ የካቢኔ ሚኒስትሮቻቸው አስመራ ለሚገኘው ቆንስላችን ግልፅ እንዳደረጉት ከእነዚህ እንግሊዛውያን በተቻለ ፍጥነት ለመገላገል ቁርጥ ሀሣብ ይዘዋል በማለት አስረድተዋል[10]፡፡*

*ከዚህ በላይ የተመለከትነው የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሚስተር ሀል ለፕሬዝዳንት ሩዝቬልት ያደረጉት ሪፖርትና አሜሪካንን የመሰለ ታላቅ ሀገር መሪ የአንድ ደሀ አፍሪካዊ አገር ሚኒስትር ተቀብለው ማነጋገራቸው፣ አሜሪካኖች ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ የቅኝ ግዛት ተፅእኖ በማላቀቅ በአሜሪካን ተፅእኖ* (sphere of influence) *ሥር ለማድረግ እንደወሰኑ፣ ወይንም ፅኑ ፍላጐት እንደነበራቸው፣ የሚያመለክት ነበር፡፡*

*ኢትዮጵያ በወቅቱ፣ ለአሜሪካኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ስታስተላልፍ የነበረችው ሌሎች ጉዳዮች፡-*

- *ዘመናዊ መከላከያን ለመገንባት የሚያስችል ወታደራዊ እርዳታ ማግኘት፣*
- *ኤርትራን መልሶ የኢትዮጵያ አካል በማድረግ ነፃ እና ዘለቄታ ያለው የባህር በር ማግኘት፣*

[10] *መንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ ገጽ 218፡፡*

- *የአሜሪካን ኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ማበረታታት፣ የሚሉትን እና ሌሎችን ያጠቃለለ ነበር።*

*እ.አ.አ በ1945 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከፕሬዝዳንት ሩዝቬልት ጋር በስዊዝ ቦይ ላይ ተገናኝተው በተነጋገሩበት ወቅት፣ ካነሷቸው ነጥቦች መካከል፣ የጦር መሳሪያ ዕርዳታ፣ የባህር በርና የኤርትራ ጉዳይ፣ የኦጋዴንና የአዲስ አበባ ጅቡቲን የባቡር መንገድ ከእንግሊዝ ቁጥጥር ስለማላቀቅ፣ እንዲሁም በፓሪስ የሰላም ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ ለመካፈል እንድትችል፣ የአሜሪካን እርዳታ እንዲደረግላት የሚጠይቅ ነበር[11]። እነዚህ፣ ንጉሡ በየጊዜው ያነሷቸው የነበሩት ጉዳዮች፣ ቀስ በቀስ ተፈጻሚነት አግኝተው በመጨረሻ ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ተጽዕኖ ለመላቀቅ ቻለች። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው፣ ኢትዮጵያ፣ በአንድ በኩል፣እንግሊዞችን በትዕግስት እያስታመመች፣ በሌላ በኩል ከእንግሊዝ በተሻለ ሁኔታ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የወታደራዊ ዕርዳታ ሊሰጥ ወደሚችል ኃያል ወዳጅ በመጠጋትና ከጎኗ በማሰለፍ እንደ ሆነ ነጻነቷን ልታረጋግጥ የቻለችው፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ግልፅ ያደርጋሉ።*

*እዚህ ላይ፣ ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ጋር በ1942 በተፈራረመችው ስምምነት አንቀፅ 12 መሰረት የ3 ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ሰጥታ ውሉን ልትሰርዝ ስትችል፣ ለምን በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ስር ሆና ቆየች የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። መልሱ ባጭሩ፣ ይህን ለማድረግ የወቅቱ የአገሪቱ ሁኔታ የሚፈቅድ አልነበረም። ስምምነቱ ባይኖር ኖሮ እንግሊዝ መላውን ኢትዮጵያ የጠላት ግዛት ነው በማለት ልትይዝ የምትችልበት ሁኔታ ነበር። አልያም በማዕከላዊ መንግሥት ላይ ቅሬታ የነበራቸውን ሕዝቦች በማነሳሳት ወይንም ያለ በቂ ምክንያት ቢሆንም አንዳንድ የኢትዮጵያን ግዛቶች ልትይዝ ትችላለች የሚል ፍርሀት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ፣ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንደምንመለከተው፣ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት እንግሊዞች ሊያከሽፉ ይችላሉ የሚልም ስጋት ስለነበረ ነው።*

*ችግሮቹ እነዚህ ብቻ አልነበሩም። በወቅቱ ያለውጭ እርዳታ በጦርነት የፈረሰውን የመንግስት መዋቅር ለመገንባት አስቸጋሪ እንደነበር ለሁሉም ወገን ግልፅ ነበር። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጦርነቱ በፊትም ቢሆን እጅግ በጣም ደካማና ይህ ነው የሚባል ገቢ ከቀረጥ ለመሰብሰብ የሚያስችል አልነበረም። በጦርነቱ ዋዜማ (በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1927) መንግስት ከተለያዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብ የሰበሰበው ጠቅላላ ገቢ 2,426,476 ብር ብቻ የነበረ ሲሆን ወጭውም ከገቢው የተለየ አልነበረም። ከነፃነት በኋላም የነበረው ኢኮኖሚም ብዙ ለውጥ አላሣየም[12] ።በወቅቱ ሰለ ነበረው ሁነታ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ለመርማሪ ኮሚሽን በአቀረቡት ጽሁፍ ሲገልጹ «እስታሁን ያለነው በነሱ (እንግሊዝ) ገንዘብ እርዳታ ባመት 12 ሚሊዮን ፓውንድ ተዛ እየሰጡን ነበር።*

[11] ላጲሶ ጌ. ድሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* ፣ ገጽ 216።
[12] *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 133፣136፣154።

ገና በመቋቋም ላይ ነበርን የልማትና የታክስም ጉዳይ ገና መጀመሩ ነበር» በማለት አብራርተዋል።

በፖለቲካና በፀጥታ ረገድም የነበረው ሁኔታ እምብዛም የሚያወላዳ አልነበረም። ከጦርነቱ በፊት ዘመናዊ ወታደራዊ ኃይል በማቋቋም ረገድ የተደረገው ጥረት በጦርነቱ ምክንያት ዋጋ ቢስ ሆኖ ነበር። ከጦርነቱ በፊት የነበሩ ጥቂት የሠለጠኑ ወታደሮች ከጠላት ጋር ሲዋጉ አብዛኛዎቹ ተሰውተዋል። በመሆኑም የሀገሪቱ ሠራዊት አባላት ዘመናዊ መሣሪያና ስልጠና እምብዛም ያልነበራቸው ከአርበኞች ከስደተኞች እና ከሌሎች ከተለያዩ ክፍሎች የተሰባሰቡ ነበሩ ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፣ በወቅቱ በጐጃም፣ በትግራይ (እራያና አዘቦ)፣ በሐረርና በሌሎች አካባቢዎች የማዕከላዊ መንግስትን ፖሊሲ የሚቃወሙ ሕዝባዊና በአንዳንድ አካባቢም በመሣፍንት የተመሩ ዓመፆች ተቀስቅሰው ከፊሎቹ በእንግሊዝ ጦር ኃይል እርዳታ እንደተደመሠሡ ይታወቃል[13]። በእነዚህና በመሣሠሉ ባለ ብዙ ፈርጅ ችግሮች ተወጥሮ የነበረው መንግስት በእንግሊዝ ጦር ኃይል ላይ ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚቸገር ለመገመት አያዳግትም።

የአሜሪካን እርዳታ የተፈለገው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ የውጭና የውስጥ ችግሮችን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ለማዳበር ነበር። ከአሜሪካ ጋር የተጀመረው ግንኙነት ፍሬያማ እየሆነ በመምጣቱና በአንፃሩም የ1934 ስምምነት መፍረስ አስፈላጊነት እየጐላ በመሄዱ፣ ስምምነቱ ከ3 ወር በኋላ እንደማይፀና እና የስምምነቱ ወቅት ከማለቁ በፊት ድርድር ተጀምሮ የፊተኛው ስምምነት በአዲስ እንዲተካ የሚጠይቅ ማስታወሻ ግንቦት 17 ቀን 1936 ለእንግሊዝ ለጋስዮን ቀረበ።

የተጠቀሰው ማስታወሻ ለእንግሊዝ በተሰጠበት ወቅት፣ ኢትዮጵያ አሜሪካኖችን ጠይቃ የነበረውን የጥሬ ብር ብድር እና የጦር መሣሪያ እርዳታ እንድታገኝ የሚያስችል ስምምነት ተደርጎ የነበረ ከመሆኑም በላይ፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በቅርብ ሆኖ የሚያጠና የአሜሪካን ኤክስፐርቶች ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ተወስኖ ነበር። ከዚህም በላይ፣ አሜሪካኖች የኢትዮጵያ ነፃነት ተጠብቆ እንዲቆይ የነበራቸውን ፍላጎት ለእንግሊዝ መንግስት ገልፀው ነበር።

እንግሊዝ ቀድሞ የነበረው ውል በ3 ወር ጊዜ እንደሚሠረዝ ኢትዮጵያ ያቀረበችውን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ፣ አዲስ ውል የሚደራደር ቡድን መስከረም 16 ቀን 1937 ላከች። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ፣ በእንግሊዝ ተረቆ የቀረበው ረቂቅ ስምምነት መጠነኛ መሻሻል ተደርጐበት ፀደቀ። በስምምነቱ መሠረት፣ የእንግሊዝ አምባሳደር የዲኘሎማቶች ቀዳሚ መሆኑ ቀረ። ኢትዮጵያ የሌላ አገር ዜጐች የሆኑ የውጭ አማካሪዎችን ለመቅጠር ያላት

[13] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* **154**።

መብት ታወቀ:: የእንግሊዝ ወታደራዊ ቡድን ከምስራቅ አፍሪከ ዕዝ ወጥቶ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ጦር ሚኒስቴር እንዲሆን ስምምነት ተደረሰ[14]::

ይህ ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ተጽዕኖ ነጻ ለመውጣት በድፕሎማሲ መስክ የተጫወተችው የሁለት ፌር ድፕሎማሲ፣ አንድ አቢይ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችን በቅድሚያ በማዘጋጀት ረገድ ሆነ ትክክለኛውን ጊዜ ጠብቆ እርምጃ ከመውሰድ አንጻር ሲገመገም፣ የተዋጣለትና በሳል የዲፕሎማሲ ጥበብ የተንጸባረቀበት ነው::

የተጠቀሰው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ቢሆንም ኦጋዴንና የተጠበቁ ክልሎች በእንግሊዝ ሥር እንዲቆዩ በማድረግ፣ በኦጋዴን እስከአሁን ላለው ችግር የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል:: በአዲሱ ውል መሰረት ኦጋዴንና የተጠበቁ ክልሎችን በተመለከተ የተደረገው ስምምነት የሚከተለውን ይላል ፡-

> በጦር ቃል ኪዳን ወዳጅነቷ መሠረት ለጦርነቱ የተሳካ አፈፃፀም አስተዋጽኦ ለማድረግ በማሰብና በግዛቱ ያላት መብት ሳይነካ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገስት መንግስት ይህ ስምምነት ፀንቶ በሚቆይበት ዘመን ከስምምነቱ ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ እንድትመለከተው ኦጋዴንና የተጠበቁ ክልሎች በመባል የሚታወቀው የኢትዮጵያ ግዛት በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ስር እንዲቆይ ተስማምተዋል[15]::

እርግጥ ነው፣ ስምምነቱ የተጠቀሱት ግዛቶች በማያወላወል ሁኔታ የኢትዮጵያ ግዛት መሆናቸውን አረጋግጧል:: ኢትዮጵያንም ከተያዘች የጠላት ግዛትነት ከፍ አድርጎ የእንግሊዝ የጦር ቃል ኪዳን ወዳጅ ሀገር መሆኗን አስገንዝቧል:: ሆኖም ግን፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደምንመለከተው፣ በእንግሊዝ ይዞታ ምክንያት በተፈጠሩ ሁኔታዎች የተነሳ ኦጋዴንና የተጠበቀው ክልል ለኢትዮጵያ የችግር ምንጭ ሆነው ቀርተዋል::

## የእንግሊዝ ይዞታ ለኦጋዴን ችግር ምንጭ

በ1937ቱ ዓ.ም. የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ስምምነት አንቀፅ 7 መሠረት፣ የኦጋዴን ክልል በእንግሊዝ አስተዳደር ስር የሚቆየው የውሉ ዘመን ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሆኖ፣ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት በኋላ ግን፣ የ 3 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሚቋረጥ ነበር:: ኢትዮጵያ ስምምነቱን የሚተካ አዲስ ስምምነት ረቂቅ አዘጋጅታ ለእንግሊዝ መንግስት የሰጠችው በ1939 ዓ.ም. ነበር:: ነገር ግን ከእንግሊዝ መልስ ሳይመጣ ለብዙ ጊዜ ዘገየ:: በዚህም ምክንያት እንግሊዝ በ1940 ዓ.ም በሁለቱ አገሮች መካከል በተፈረመው ሌላ ስምምነት

---

14 መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርኢያ፣ ጥርስ ውስጥ የገባች ሀገር፣ ገጽ 199፣204::

15 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 209::

መሠረት ኦጋዴንን ለቃ ብትወጣም ሀውድንና የተጠበቁትን ግዛቶች እንደያዘች የሶማሊያ ቅኝ ግዛቶችዋን ለቃ እስከወጣች ጊዜ ድረስ ቆይታለች፡፡

እንግሊዞች የ1937 ዓ.ምን ስምምነት በዘላቂ ስምምነት ለመተካት ያስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ የተጠበቀውን ክልልና ሀውድን እንድትለቅ የሚጠይቅ ነበር፡፡ ይህን ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ ለመቀበል ዝግጁ ያለመሆኗን በማያወላውል ቃል ስላረጋገጠች ባዲሱ ስምምነት ረቂቅ ላይ ሊደረግ ታስቦ የነበረው ውይይት ለብዙ ጊዜ ተቋርጦ ሊቆይ ችሏል፡፡

እንግሊዝ የጣሊያን ሱማሌላንድን እና ኦጋዴንን በሙሉ ይዛ ታላቋ ሱማሊያን ለመፍጠር በ1930ዎች የነደፈችውን ዕቅድ የጣሊያን ሱማላንድ ዜጐች ተቀብለውት በወቅቱ ለተግባራዊነቱ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት እንግሊዝ በራሷ ስም የምትጠራው የእንግሊዝ ሱማሊያ በታላቋ ሱማሊያ እንዳትዋጥ ስጋት አድሮባት ነበር፡፡ የእንግሊዝ ሱማሊላንድ ከመዋጥ ተርፋ ለብቻዋ የምትቆይ ከሆነ ግን የአገሪቱ ዜጎች ከብቶቻቸውን ውሃ ለማጠጣትና ግጦሽ ለማብላት እንዲችሉ ክልሎቹን (ሀውድንና የተጠበቀ ክልል) ከኢትዮጵያ ገንጥለው ከሱማሊላንድ ጋር መቀላቀሉ አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ ነገር ግን ይህን ዓላማ ለማሟላት እንደማይቻል ኢትዮጵያ በገለጸችው ጠንካራ አቋም ተገንዝበዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሲጎተት የቆየው ስምምነት በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካከል የተፈረመው በ1948 ነበር[16]፡፡

እንግሊዝ፣ ከፓሪስ የሰላም ስብሰባ ወቅት ጀምራ፣ የኤርትራን ጉዳይ ከኦጋዴን ጋር በማቀናጀት፣ ኢትዮጵያ ኤርትራንና የምትፈልገውን የባሕር በር የምታገኘ ው፣ ኦጋዴንን ለእንግሊዝ የለቀቀች እንደሆነ ነው የሚለውን ሃሣብ ስታራምድ ቆይታለች፡፡ የ1937 ዓ.ም. ስምምነትን የሚተካ አዲስ ስምምነት በሚደረግበት በ1948 ዓ.ም. የኤርትራ ጉዳይ ከሞላ ጐደል መፍትሔ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገችው የ1940 ዓ.ም. ስምምነት መሠረት የኦጋዴንን ግዛት በከፊል ለቃ ወጥታለች፡፡ በመጨረሻም ሀውድና የተጠበቀው ክልል የኢትዮጵያ ግዛት መሆናቸውን አረጋግጣለች፡፡

በሁኔታዎች አጋጣሚነትና በትጋት ባደረገችው የዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ኢትዮጵያ፣ እንግሊዝ እንደጠበቀችው ኤርትራን ለማግኘት ስትል፣ ለኢትዮ ጣሊያን ጦርነትና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነውን ኦጋዴንን ለእንግሊዝ እንድትለቅ የሚያስገድድ ሁኔታ ሳይፈጠር ቀርቷል፡፡ በመሆኑም፣ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድም ያደረገችው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ውጤት ያለውና ባሸናፊነት ለመውጣት የቻለችበት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አሜሪካንን በማግባባት በጎኗ ባታሰልፍ ኖሮ ከእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ተላቃ፣ የተወሰዱባትን ግዛቶች ለማስመለስ ባለምአቀፍ ደረጃ ጠንክራ ለመዋጋት፣ አቅም እንደማይኖራት ለመገመት

[16] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 367፡፡

የሚያስቸግር አይደለም:: እንዲሁም፣ ቀጥለን እንደምንመለከተው፣ ኢትዮጵያ በኤርትራና በሌሎች ጉዳዮች ውጤት ያገኘቸው በአሜሪካን እርዳታ እንደሆነ ግልጽ ነው::

ያም ሆኖ፣ እንግሊዞች በተከታታይ ለአስራ አራት አመታት የተጠቀሱ አካባቢዎችን ይዘው በመቆየታቸው እና አካባቢውን ለቀው ሲወጡ ግዛቶቹን ለኢትዮጵያ በማስረከባቸው በአካባቢው ህዝብ ላይ የተፈጠረው የስነ ልቦና ሁኔታና ትክክለኛ ያልሆነ ግንዛቤ፣ በጣሊያን ሶማሊያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ወሰን በመሬት ላይ ምልክት ያልተደረገበት ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ፣ ኦጋዴን ባለፉት 40 ዓመታት በኢትዮጵያና በሱማሊያ መካከል ለተደረጉ ከፍተኛ ጦርነቶች መንስኤ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ እስከ አሁን ድረስ በአካባቢው ለሚከሰቱ ውዝግቦች እና ደም ያፋሰሱ ግጭቶች መሰረታዊ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል::

ዛሬም ቢሆን፣ ይህን በውጭ ኃይል በሁለቱ ህዝቦች መካከል የተፈጠረውን ያለመተማመንና ጥላቻ ለማስወገድ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የተደረጉ በርካታ እርምጃዎችን በማደናቀፍ፣ በአካባቢው የንጹኃን ደም መፍሰስ እንዲቀጥል ለማድረግ፣ የኤርትራ መንግሥትና አክራሪ ኃይላት ሌት ተቀን እየሠሩ ናቸው:: ስለሆነም፣ የችግሩን ምንጭ በውል መረዳቱ ያለፈውን የዲፕሎማሲ ጥረት እንድናደንቅና ትምህርትም እንድንቀስም ከማስቻሉም በላይ ዛሬም የነበሩ ክፍተቶችን በመጠቀም በልማት ጎዳና የጀመርነውን መልካም ጉዞ ለማሰናከል የሚፍጨረጨሩ ፅኩይ ኃይሎችን ደባ ለማክሸፍ ተጨማሪ መሣሪያ ሆኖ ያገለግለናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው በተመሳሳይ ምክንያት ትኩረት የምናደርገው ጽሁፉ በሚያጠቃልልበት ዘመን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጥረት ያደረገችበት የኤርትራ ጉዳይ ነው::

## የኤርትራ ጉዳይ በፓሪሱ የሰላም ስብሰባ (እ.አ.አ. 1947)

የኤርትሪያ ጉዳይ፣ ከጦርነቱ በኋላ፣ በአለም አቀፍ መድረክ በዝርዝር መታየት የጀመረው በፓሪስ የሰላም ስብሰባ ላይ ነበር::

ከተሸናፊ አገሮች ጋር የሠላም ውል ለመፈራረም በፓሪስ በተጠራው ስብሰባ በጦርነቱ ከተካፈሉ ሀገሮች ውስጥ (ከአራቱ ኃያላን በተጨማሪ) የተመረጡ 17 ሀገሮችን ያጠቃለለ ነበር:: ኢትዮጵያም በዚሁ ስብሰባ እንድትካፈል ከተመረጡ አገሮች አንዷ ነበረች::

ኢትዮጵያ በዚህ ስብሰባ ባደረገችው ንግግር፣ ያለውዴታቸው በግዴታ በኮሎኒያሊስት ጣሊያን ተገንጥለው የተወሰዱትን ግዛቶች (በተለይም ኤርትራ) ወደ እናት ሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ አሳስባለች::

በዚህ ስብሰባ ፍፃሜ ጣልያን የድሮ ቅኝ ግዛቶቿን በገዛ ፍቃድዋ እንድትለቅና በተለያዩ ሀገሮች ላይ ላደረሰችው ጉዳት የ360,000,000 የአሜሪካን ዶላር የጦር ካሣ እንድትከፍል በተወሰነው መሠረት ተስማምታ የዕርቁን ውል ለመፈረም ተገዳለች፡፡ ኢትዮጵያ በስብሰባው በመካፈል፣ ጣልያንን ወግተው ድል ካደረጉ ሀገሮች ጋር፣ የዕርቁ ውል ፈራሚ ሆናለች፡፡ እንዲሁም ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ በፈፀመችው ግፍ 25,000,000 ዶላር ካሳ አግኝታለች፡፡ የተዘረፉ ቅርሶቿ እንዲመለሱላት አስወስናለች፡፡ ግብፅና ጣሊያን ያቀረቡትን የግዛትና የኮሎኒያሊስቶች ጥያቄ በማክሸፍ ረገድ የበኩሏን ሚና ተጫውታለች[17]፡፡

በፓሪሱ ስብሰባ ውሳኔ መሠረት ኃያላን መንግሥታት በየአገሮቹ (ማለት በኤርትራ፣በሊቢያና በጣልያን ሶማልያ)፣ እየተዘዋወረ የህዝቡን ፍላጐት አጣርቶ ሀሳብ የሚያቀርብላቸው፣ አንድ የመርማሪ ኮሚሽን አቋቋሙ፡፡

በዚህ መሠረት ወደ ኤርትራ የሄደው ቡድን፣ የህዝቡን ስሜት ለማወቅ፣ የልዩ ልዩ ፖርቲ መሪዎችን አነጋግሮና እንዲሁም በግብጽና በሌሎች ያገባናል በሚሉ አገሮች ተዛዋውረው ያገኙትን መረጃ በመንተራስ ያቀረቡት አስተያየት፣ እንደየ አገሮቹ የፖለቲካ አመለካከት የተለያየ ነበር፡፡ በመሆኑም ኃያላኑ መንግስታት በጉዳዩ ላይ መስማማት ስላቃታቸው የኤርትራ ጉዳይ መስከረም 1941 ዓ.ም. በሚከፈተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት 3ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲቀርብ ተስማሙ[18]፡፡

## የኤርትራ ጉዳይ በተመድ መድረክ

ኤርትራንና ሌሎች የጣሊያን ቅኝ ግዛቶችን በተመለከተ በእንግሊዝ የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ ቀጥለን የምንመለከታቸውን ሀሳቦች ያዘለ ነበር፡፡

የሊቢያ ሶስቱም አውራጃዎች (ሲረናይካ፣ ፌዘንና ትሪፖሊታኒያ)፣ ከ10 ዓመት በኋላ በአንድነት ተዋህደው፣ የሊቢያ ነፃ መንግስት ሆነው ይቋቋማሉ፡፡ እስከ አስር አመት ድረስ ግን ሲረናይካ በታላቂ ብርታኒያ፣ ፌዘን በፈረንሳይ፣ እንዲሁም ቲሪፖሊታኒያ በጣሊያን ሞግዚትነት ይተዳደራሉ፡፡ ሱማሊያ፣ በጣሊያን ላልተወሰነ ጊዜ ስትተዳደር ከቆየች በኋላ፣ ነፃ መንግስት የመሆን እድል ይሰጣታል፡፡ ኤርትራ፣ ቀደም ብሎም እንደተገለጸው፣ ከምእራብ ቆላ በስተቀር ቀሪዎቹ ከኢትዮጵያ ጋር ይዋሀዳሉ፤ የምዕራብ ቆላ አውራጃዎች ግን የወደፊት እድላቸው ተጠንቶ ይወሰናል የሚል ነበረ፡፡

---

[17] ዘውዴ ረታ፣ *በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የኤርትራ ጉዳይ (1941-1963 እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር)*፡ 4ኛ ዕትም (አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ 1998 ዓ.ም) ገጽ 73፡፡

[18] *አክሊሉ ሀብተወልድ ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ጽሑፍ፣ (መስከረም 10፣1967) ገጽ 31-33*

የኢትዮጵያ ልዑክ መሪ የእንግሊዝን ረቂቅ አበክረው ነቀፉ:: የአቶ (በኋላ ጸሐፌ ትእዛዝ) አክሊሉ ሀብተወልድ ተቃውሞ የከረረበት ምክንያት፣ እራሳቸው እንደገለፁት፣ ኢጣሊያን ወደ ሞቃዲሾ የቅኝ ግዛቷ ተመልሳ ሱማሊያን ታስተዳድር በሚለው አስተያየት የተነሳ ነበር::

የእንግሊዙ ልዑክ መሪ ለኢትዮጵያ ለሰጡት በጐ ድጋፍ ያገኙት ነቀፋ እጅግ እንደአሳዘናቸው ሲገልፁ፣ የታላቋ ብሪታኒያ መንግስት የኢትዮጵያ ወዳጅ ባይሆን ኖሮ በአራቱ ኃያላን ጉባኤ ላይ መስኮብና ፈረንሣይ ኤርትራ ለጣሊያን ተመልሣ እንድትሰጥ ያደረጉት ጥረት አይፈርስም ነበር ብለዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ረቂቅ ወሳኔ በዋናው ኮሚቴ ፀድቆ ለጉባዔው በቀረበበት ወቅት የኤርትራ ጉዳይ በ37 ሀገሮች ተደግፎ ቢያልፍም፣ በጣሊያን ሞግዚትነት እንዲቆዩ የተባሉትን ግዛቶች በተመለከተ፣ ትሮፖሊታኒያ ሀይቲ በመጨረሻ ደቂቃ ሀሣቧን በመለወጥ ተቃዋሚ በመሆኗ፣ እንዲሁም ሱማሊያ በሀይቲና በላይቤርያ ምክንያት ሁለት ድምጽ ብቻ ስለጐደላቸው፣ ውሳኔው በአጠቃላይ ውድቅ ሆኗል[19]:: ሦስቱ ጉዳዮች በአንድ ውሳኔ ታስረው የቀረቡ በመሆናቸው፣ ከጉዳዮቹ መካከል አንዱ በቂ ድምጽ ሳያገኝ ቢቀር፣ ሌሎቹ አብረው ይወድቃሉ::

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሁኔታ፣ የኤርትራ ጉዳይ በተመድ ሦስተኛ ጉባኤ ሳይቋጭ ቀርቶ ለአራተኛ ጠቅላላ ጉባዔ በቀረበበት ወቅት ሁኔታዎች በእጅጉ ተለዋውጠው ነበር:: ጣሊያን ቅኝ ግዛቶችዋን መልሳ ለመያዝ ያደረገችው ጥረት በ3ኛው ጠቅላላ ጉባዔ በመክሸፉና ለወደፊቱም እንደማይሳካላት በመገመት፣ ኤርትራና ሊቢያ በቀጥታ ነፃነታቸውን እንዲጎናጸፉ፣ ሱማሊያ ለተወሰነ ጊዜ በጣሊያን ሞግዚትነት ከተዳደረች በኋላ ነፃነቷን እንድታገኝ፣ የሚል አቋም ያዘች:: በኢትዮጵያ በኩልም፣ የፖለቲካ ሁኔታ እንደሚለዋወጥ በመገመት፣ የአገሮችን ድጋፍ ለማሰባሰብ ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ በነበረው የዲፕሎማቲክ ውክልና ዕጥረትና ድክመት የተነሣ ይህ ነው የሚባል ውጤት ተገኝቷል ለማለት አይቻልም::

በመሆኑም ሊቢያ እ.አ.አ ከጥር 1 ቀን 1952 (ከታህሣስ 1944 ዓ.ም.) በፊት ነፃነቷን እንድታገኝ፤ ሱማሊያን ግን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ጣሊያን በሞግዚትነት ካስተዳደረቻት በኋላ ነጻነቷን እንድታቀዳጃት፣ ኤርትራን ደግሞ በተመለከተ አምስት አባላት ያሉበት ኮሚቴ ተሰይሞ፣ ወደዛች አገር ተልኮ፣ የህዝቡን ፍላጐት አጣርቶ ያቅርብ የሚል ውሳኔ ጉባኤው አጸደቀ:: ይህ ውሳኔ ለጣሊያንና ለደጋፊዎቿ ከፍተኛ ድል ያስመዘገበ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን በተመለከተ ቀደም ብሎ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ የነበረውን የኤርትራ ጉዳይ እንደገና ጥሬ አድርጎታል[20]::

---

[19] ዘውዴ ረታ፣ *በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት*፣ ገጽ 98-100 ፣172-73::
[20] *ገዘ ከማሁ*፣ ገጽ 263::

ለኮሚሽኑ አባልነት የተመረጡት ፖኪስታን፣ ጓቲማላ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ በርማ (ዛሬ ማይናማር) እና ኖርዌይ ነበሩ። የኢትዮጵያ ልዑክ፣ በግልፅ የጣሊያን ደጋፊ የሆኑት ፓኪስታንና ጓቲማላ እንዳይመረጡ፣ አበክረው ቢጠይቁም ሰሚ አላገኙም።

ያም ሆኖ፣ ልዑኩ በአዲስ አበባ ሆነ በኤርትራ ጥሩ አቀባበል ተደርጐለት፣ የተላከበትን ተግባር በሚገባ ፈፅሞ ተመልሷል። የኮሚሽኑ አባላት በኤርትራ በነበሩበት ወቅት የማህበር ፍቅረ ሀገር አባላትን ጣሊያን በገንዘብ በመግዛት ከማህበሩ ለማስከዳትና ማህበሩን ለማዳከም የአደረገውን ጥረት በማክሸፍ ካለፈው ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ ያላቸውን ፍላጐት ለመግለፅ ችለዋል። ይህም እንዲሆን ከማህበሩ መሪዎች ጋር በከፍተኛ ቁራጥነት ተልእኳቸውን የፈፀሙት ኮሎኔል ነጋ ሀይለ ሥላሴ በአስመራ የኢትዮጵያ ላይዘን ኦፊሰር እንደሆኑ በርካታ መረጃዎች ያሳያሉ። እሳቸውና የአንድነት ማህበር መሪዎች እንደ ደጃዝማች በየነ ባራኪ፣ አቶ ተድላ ባይሩ ሼህ ሱሊማን አልዲን፣ አህመድ ሠይድ እና የመሳሰሉ ባይኖሩ ኖሮ ኤርትራን በፌዴሬሽንም ቢሆን ከኢትዮጵያ ጋር ለማገናኘት እንደማይቻል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መድረክ ላይ ከተደረጉ ሁኔታዎች ለመገንዘብ አያዳግትም።

ኮሚሺኑ በአዲስ አበባና በኤርትራ ዞሮ የህዝብ ተወካዮችንና የመንግስት ባለሥልጣናትን እንዲሁም ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ አገሮችን (እንግሊዝን፣ አሜሪካንና ግብፅን) ካነጋገረ በኋላ ኒውዮርክ ተመልሶ ያቀረበው ሪፖርት ሁለት አይነት ነበር። እነዚህም፦

> *ፓኪስታንና ጓቲማላ «ለኤርትራ ጉዳይ ትክክለኛው መፍትሄ ፡ አገሪቱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የበላይ መሪነት ለ10 ዓመታት በሞግዚት አስተዳደር ከቆየች በኋላ ነፃነቷን ማግኘት ብቻ ነው» ሲሉ ደቡብ አፍሪካ ፡ በርማና ኖርዌይ ያቀረቡት አስተያየት የሚመሣሠል ቢሆንም አንድ አይነት አልነበረም።*
>
> *ኖርዌይ፣ ከምዕራቡ ቆላ በስተቀር፣ ሌላው የኤርትራ ግዛት በሙሉ ከኢትዮጵያ አስተዳደር ጋር እንዲዋሀድ ስትል፣ ደቡብ አፍሪካና በርማ በበኩላቸው ፌዴሬሽኑን በመደገፍ በሰጡት አስተያየት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ህይወቷን የምታስተሳስረው በህግ በተመሰረተ ፌዴሬሽን ከሆነ በውስጥ ሆነ በውጭ አመለካከት ትክክለኛ ሚዛን ያለው ፍርድ ሆኖ ተቀባይነትን ያገኛል የሚል ነበር።*

በዚህ መሠረት በፌዴሬሽን መፍትሄ ላይ የተመሰረተውና በአሜሪካንና በሌሎች 14 አገሮች ተባባሪነት የቀረበው ረቂቅ ውሳኔ እ.አ.አ ታህሣሥ 2 ቀን 1950 ዓ.ም. (ህዳር 1943) ለአምስተኛው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ፣ ከ60 አባል አገሮች በ46 ድምፅ ተደግፎ፣ ለማለፍ ችሏል። ውሳኔው በዚህ ሁኔታ ከፍተኛ ድምጽ ለማግኘት የቻለበት ምክንያት የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲን አችሰን በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ጭምር እራሳቸው ወንበር ይዘው ባደረጉት ክርክርና ከስብሰባውም ውጭ ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ ባደረጉት ጥረት

እንደነበር ለማንም የተሰወረ አልነበረም:: በተለይም፣ ውሳኔውን ተባብረው ካቀረቡ 14 አገሮች ውስጥ ሰባቱ የጣሊያን ደጋፊ የነበሩ የላቲን አሜሪካን አገሮች መሆናቸውን ስንገነዘብ፣ አሜሪካኖች ድጋፍ ለማሰባሰብ ምን ያህል እንደጣሩ ግልፅ ይሆንልናል::

ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ጉዳይ የፌዴራል መፍትሄ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሲወሰን፣ የፌዴራል ህገ መንግስት እንዲያዘጋጁ የተመረጡት የቦሊቪያ ተወላጅ አንሴ ማቲያንሶ ባዘጋጁት ህገ መንግስት መሠረት የፓርላማ አባላት ተመርጠው ሥራቸውን ጀመሩ:: በፓርላማው የፀደቀውን ህገ መንግስት እ.አ.አ ነሐሴ 1952 ዓ.ም. (ነሀሴ 1944) ንጉሰ ነገስቱ በፊርማቸው ስላፀደቁት፣ ፌዴሬሽኑ እስከ ፈረሰ ጊዜ ድረስ በስራ ላይ ውሏል[21]::

የኤርትራ ጉዳይ ከሞላ ጎደል በተሳካ ሁኔታ ሊደመደም የቻለው በመጀመሪያ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውና በአንድነት ፓርቲ የተመራው የኤርትራ ህዝብ ባደረገው ጥረት ነው:: ንጉሰ ነገስቱም፣ ኢትዮጵያ ከሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምራ ቀስ በቀስ እያጣች የሄደችውን በቀይ ባህር መተላለፊያ በሮች ላይ የነበራትን መብትና ጥቅም ለማስከበር፣ በተለይም በአፄ ምኒልክ ዘመን ለጣሊያን የተላለፉ የኢትዮጵያ ግዛቶችን በማስመለስ፣ አብዛኛው የኤርትራ ህዝብ ወንድም ከሆነው ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለመቀላቀል ያደረገውን ትግል ፍሬአማ እንዲሆን የጣሩ፣ እንዲሁም ለአንድ አገር ህልውና መጠበቅ ሆነ የኢኮኖሚ እድገት የባህር በር ያለውን ወሳኝ ሚና ተረድተው የታገሉና ውጤት ያስገኙ መሪ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ታሪክ ያስታውሳቸዋል:: በተመድ የኢትዮጵያ ልዑክም (በተለይም በኤርትራ ጉዳይ ላይ 700 ሰዓት የፈጀ ንግግር በተመድ መድረክ እንዳደረጉ ለመርማሪ ኮሚሽን በአቀረቡት ጽሑፍ የገለጹት አክሊሉ ሀብተ ወልድ) በከፍተኛ የአገር ፍቅር፣ አመቺ ባልነበረ መድረክ ያደረጉት ተጋድሎ የሚደነቅ ነበር:: ከሁሉም በላይ፣ አሜሪካንና እንግሊዝ በአንድነት በኢትዮጵያ ጎን ባይቆሙ ኖሮ የኤርትራ ጉዳይ ገና በጠዋቱ በፓሪስ ስብሰባ ወቅት ከኢትዮጵያ እጅ ባመለጠ ነበር::

ይህ በከፍተኛ ደረጃ ለኢትዮጵያ ህልውና መጠናከር የጎላ አስተዋጽኦ ያደረገው የአሜሪካን ድጋፍ ለምን እየመነመነ እንደሄደ ቀጥሎ እንመለከታለን::

## የኢትዮጵያ እና የአሜሪካ ግንኙነት መቀዝቀዝ

አሜሪካን በአስመራ ከተማ ቃኘው የሬድዮ መገናኛን፣ በምፅዋ ላይ ደግሞ የመርከቦች መገልገያን፣ እንዲሁም በአገሪቱ የትኛውም ክፍል የመብረር ልዩ ፍቃድ እንድታገኝ፣ እ.አ.አ በ1955 ከኢትዮጵያ ጋር ውል መፈራረሚ የሚታወቅ ነው::

[21] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 371::

በዚህ ስምምነት ምክንያት፣ ኢትዮጵያ ከአሜሪካን የመሣሪያና የቴክኒክ ተራድኦ እንድታገኝ አስችሏታል:: በአሜሪካን እርዳታ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር፣ ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች ሁሉ የተሻለ ወታደራዊ ኃይል ለመገንባት ችላለች::

ኢትዮጵያ በዚሁ በ1940ዎቹ ውስጥ ባለው ጊዜ ኤርትራንና ኦጋዴንን መልሳ በማዋሀድ ለረዥም ዓመታት ተቋርጦ የነበረውን የባህር በር ለማግኘትና በቅኝ ገዥዎች ተውስደውባት የነበሩትን ግዛቶቿን ለማስመለስ የቻለችው አሜሪካኖች በጎንዋ በመቆማቸው ጭምር ነበር:: ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ውጤት ያስገኘበትና በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የነበረው ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሠበት ወቅት ነበር፡

ነገር ግን ይህ መልካም ሁኔታ ቀስ በቀስ ተለውጦ ከ1970ዎች መግቢያ ጀምሮ እየተበላሸ መሄድ ጀመረ:: ይህ ለምን እንደ ሆነ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በ1955 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በመቀላቀሏ የተበሳጩ የአረብ አገሮች በግብፅ እየተመሩና በሶቭየት ሕብረት እየተረዱ ኤርትራ እንድትገነጠልና ኦጋዴንን የሚያካትተውን የታላቋ ሱማሊያ መቋቋም እውን እንዲሆን የፕሮፓጋንዳ እና የሠርጐ ገብ ዘመቻ እንዲጧጧፍ አደረጉ::

እንዲሁም በግብፅና በሶሪያ ድጋፍ የመገንጠል ፍላጐት የነበራቸው ተቃዋሚዎች በ1953 በካይሮ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባርን በማቋቋም ሳውዲ አረብያን ጨምሮ የሌሎች አረብ አገሮችን እርዳታ ለማግኘት ቻሉ::

ከሶቭየት ሕብረት፣ ከቻይና፣ ከሶሪያና ከደቡብ የመን ወደ ኤርትራ የጦር መሣሪያ መጉረፍ ጀመረ:: የአረብ አገሮች ለኤርትራ ተቃዋሚዎች የሚያደርጉትን እርዳታ፣ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ከኢትዮጵያ ጋር ፍፁም ከተዋሀደች በኋላ፣ በእጥፍ ከፍ አደረጉ[22]::

እንዲሁም፣ የሶቭየት ሕብረት ቀደም ብላ ለሶማሊያ መስጠት የጀመረችው የጦር መሳሪያ እርዳታ ከ1960ዎች መግቢያ ጀምሮ እየናረ ሄደ:: በተለይም በ1961 በሶማሊያ መፈንቅለ መንግስት ከተደረገ ወዲህ ሁለቱ አገሮች ግንኙነታቸውን በበለጠ በማጠናከር በ1964 የሶቭየት ህብረት ለሶማሌ ወታደራዊና የኢኮኖሚ ዕርዳታ ከፍ ለማድረግና ሶማሊያም ለሶቭየት ህብረት በበርበራ የአየር ማረፊያ እና የወደብ አገልግሎት እንድትጠቀም የሚያስችል ስምምነት ተፈራረሙ:: በዚህ ስምምነት መሰረት የሶቭየት ህብረት የሶማሊያ ወታደራዊ ብቃት በአፍሪካ የላቀ እንዲሆን ለማድረግ ወሰነች:: በዚህን ወቅት የኢትዮጵያ ወታደራዊ ሀይል ከሶማሊያ በቁጥር በዕጥፍ የሚበልጥ ቢሆንም ገሚሱ በኤርትራ የተመደበ ከመሆኑም በላይ በታጠቀው የመሳሪያ ዘመናዊነት ከሶማሊያ ጋር ሲነፃፀር ደካማ ነበር::

---

[22] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* **371**::

በዚህም ምክንያት በአፍሪካ ቀንድ ያለው የወታደራዊ ኃይል ሚዛን ወደ ሶማሊያ ማጋደሉ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉአላዊነት ላይ ስጋት አስከተለ። ንጉሠ ነገሥቱ በአፍሪካ ቀንድ የተፈጠረውን ወታደራዊ ሚዛን መዛባት በ1965 አሜሪካንን በጎበኙበት ወቅት፣ ለፕሬዝዳንት ኒክሰን የሁለቱን አገሮች የወታደራዊ ኃይል በማነጻጸር እንደሚከተለው ገልጸው ነበር። ኢትዮጵያ 20 ታንክ ሲኖራት ሶማሊያ 200 ታንኮች፣ ኢትዮጵያ 54 ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ሶማሊያ 310፣ ኢትዮጵያ 24 ፀረ አይሮፕላን መሳሪያ ሶማሊያ 170፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ያረጀ ሲሆን ሶማሊያ በ17 የተለያዩ የጦር አይሮፕላኖች የተደራጀ እንደሆነ አትተዋል[23]።

ፕሬዚደንቱ ንጉሠ ነገሥቱ ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፣ "We have great difficulties with aid. We will again ask Congress for a substantial appropriation, but I must honestly say to you that getting it will be difficult" **ብለዋል**።[24] **ይህ** የፕሬዚደንቱ አነጋገር አዎንታዊ ነው የሚባል አልነበረም።

ፕሬዝዳንቱ የተጠየቀውን መሳሪያ ለኢትዮጵያ ለመስጠት የተለያዩ ችግሮች እንደሚገጥማቸው ተገንዝበዋል። ኢትዮጵያን በተመሳሳይ ሁኔታ ማስታጠቅ በአፍሪካ ቀንድ ላይ የሁለቱን ኃያላን ወታደራዊ ውድድር ያባብሳል ብለው ከመስጋታቸው በተጨማሪ የአሜሪካን ኮንግረስ በወቅቱ ለአገሮች የሚሰጥ ወታደራዊ ዕርዳታ እንዲቀንስ የኒክሰን አስተዳደርን ወጥሮ የያዘበት ወቅት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የሳተላይት ቴክኖሎጂ በማደጉ የቃኘው ኮሚዩንኬሽን ጠቀሜታ ቀንሶ ስለነበር ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ እንዲጨምር ለማድረግ በቂ ምክንያት አልነበረም።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ሁኔታዎች የሚያሳዩን በወቅቱ የሶቭዬት ህብረት በቀይ ባህርና በአፍሪካ ቀንድ የበላይነት ለመጎናፀፍ ከፍተኛ ግፊት ስታደርግ በአንፃሩ አሜሪካ ወደኋላ በማፈግፈግ ላይ እንዳለች ነው።

የኢትዮ-አሜሪካ ግንኙነት በእንዲህ እያለ ነበር የ1974 አብዮት የፈነዳው። ከለውጡ በኋላም ቢሆን አሜሪካኖቹ በኢትዮጵያ ከንጉሱ በኋላ የሚመጣው አመራር በአሜሪካን ላይ ጎጂ አመለካከት አይኖረውም ብለው ስለገመቱ፣ ደርግን በክፉ አይን እንዳልተመለከቱ፣ አስተዳደሩ በጉዳዩ ላይ ሲለዋወጥ የነበረው የውስጥ ማስታወሻዎች ያሳያሉ። በነዚህ ማስታወሻዎች እንደተንጸባረቀው፣ ንጉሡ ያረጁና ፈላጭ ቆራጭ በመሆናቸው ለውጥ ለማምጣት የተዘጋጀ መንግሥት በኢትዮጵያ ሥልጣን መያዙ፣ መልካም እንደሆነ ተጠቅሷል። በዚህም ምክንያት ንጉሰ ነገስቱ ጠይቀዋቸው ያልሰጡዋቸውን መሳሪያ ጭምር ለደርግ ለመስጠት ተስማምተው ነበር። የኢኮኖሚ እርዳታም በንጉሱ ጊዜ

[23] Tekeda Alemu, "The Unmaking of Ethio-American Military Relations," pp.130-146.

[24] US State Department, *US State Department Memorandum of Conversation 1873- 74.* (Archives of the State Department)

ከነበረው እንደሚጨምር አስታውቀው ነበር። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ አልዘለቀም። በህዳር ወር 1967 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት ያለፍርድ በመገደላቸው በሁለቱ አገሮች መካከል ማደግ ጀምሮ የነበረው መልካም ግንኙነት ጋብ አለ። በዚህ መሰረት ለኢትዮጵያ ሊሰጥ የነበረው የመሳርያ ዕርዳታ የፖለቲካ ሁኔታው ግልጽ እስከሚሆን ድረስ እንደሚቆም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። እንደዚሁም በሂደት ላይ የነበረው የኢኮኖሚ እርዳታ ስምምነቶችም ለጊዜው ታገዱ።

ይህ በእንዲህ እያለ፣ ከኤርትራ ነጻ አውጭ ድርጅቶች ጋር የሚደረገው ጦርነት በመፋፋሙ ደርግ 25 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያወጣ መሳሪያ በአፋጣኝ ለመግዛት የአሜሪካንን መንግስት ጠየቀ። ከደርግ ለቀረበው የመሳሪያ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ለአሜሪካኖቹ ቀላል አልነበረም፤ ምክንያቱም በአካባቢው ያሉ የአረብ አገሮች በወቅቱ አሜሪካን ለኢትዮጵያ መሳሪያ እንዳትሸጥ ማሳሰብ ጀምረው ነበር። ከዚህ ባሻገር ያለፍርድ የተገደሉት የቀድሞ መንግስት ባለስልጣኖች ጉዳይ በአሜሪካን ኮንግሬስና በህዝቡ አካባቢ የፈጠረው መጥፎ ሁኔታ አልተረሳም ነበር።

በሌላ በኩል የተጠየቀውን መሳሪያ መከልከል የወታደራዊውን መንግስት ወደ ሶቭየት ካምፕ እንዲገባ የሚያስገድድ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን አንድነት በጥያቄ ውስጥ የሚከት በመሆኑ የሚደገፍ አልነበረም። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ምክንያት ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረግ ወይንም መቀበል ስላልተፈለገ ከተጠየቀው 25 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሳሪያ ውስጥ የ7 ሚሊዮን ዶላር የጦር መሳርያ ለመስጠት ተስማሙ[25]።

ከ1968 አጋማሽ ጀምሮ ደርግ ለዘብተኛ አቋም የነበራቸው የራሱ አባላት ላይ በሞት የማስወገድ እርምጃ በመውሰድ ወደ ግራ የሚያደርገውን ዝንባሌ እያጠናከረ መጣ። በአሜሪካኖችም ላይ የህዝብ መገናኛዎች በመጠቀም የማጥላላት ዘመቻ አጠናከረ። በዚህ ምክንያት አሜሪካኖች የፖሊሲ ለውጥ ባያደርጉም ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ወታደራዊና ሌሎች እርዳታዎችን መቀነስ ጀመሩ። እንደዚሁም የኢትዮጵያን አብዮት ለማዳከም ሱዳንንና ሳውዲ አረብያን የመሳሰሉ ወግ አጥባቂ አገሮች የሚያደርጉትን ሴራ መደገፍ ጀመሩ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም በ1969 ዓ.ም በወቅቱ የደርግ ሊቀመንበር በነበሩት በጀኔራል ተፈሪ በንቲ እና በሌሎች በእሳቸው ተቃዋሚዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ በአገሪቱ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ለመሆን ቻሉ። ለጥቆም በሶሻሊስቱ ካምፕና በመንግስቱ መካከል የተጀመረው ግንኙነት በፍጥነት እየተጠናከረ ሄደ። ከዚህ በኋላ በሚያዝያ ወር በኢትዮጵያ የአሜሪካን ወታደራዊ ተቋሞች እንዲዘጉ ኮሎኔል መንግስቱ አዘዙ። አሜሪካም በአጸፋው ለኢትዮጵያ ለመሳርያ ግዥ የምትሰጠውን ብድር ከመከልከልም በላይ ኢትዮጵያ

[25] Tekeda Alemu, "The Unmaking of Ethio-American Military Relations," pp.130-146.

ቀደም ብላ የገዛቻቸውን ሆነ በግዥ ሂደት ላይ ያሉ 40 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ የጦር መሳሪያዎች እንዳታገኝ አደረገች[26]::

እንግዲህ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት እንዲህ በዘቀጠበት፣ በመሀል አገር የፖለቲካ ቀውስ በሰፈነበት፣ በኤርትራ የተጀመረው ጦርነት ባልቀዘቀዘበት ወቅት ነበር የታላቋን ሶማሊያ አላማ ማሟላት አሁን ነው በማለት ሶማሊያ በኦጋዴን ላይ ከፍተኛ ጥቃት የከፈተችው:: በ1969 አጋማሽ አካባቢ የሶማሊያ ሰራዊት ጅጅጋን ያዘ፤ የአዲስ አበባ ጂቡቲ የባቡር መስመር ተቋረጠ፤ ሶማሊያ ከኦጋዴን አልፋ ሲዳሞን ፣ባሌን ፣አርሲንና ሀረርጌን አጠቃሎ እስከ አዋሽ ያለው መሬት ሁሉ የታላቋ ሶማሌ ነው በማለት አወጀች::

ኢትዮጵያ በቂ መሳሪያ በማግኘት ይህንን ማዕበል ለመቋቋም ወደ አሜሪካ፣ እስራኤል እና ቻይና ያደረገቸው ሩጫ የተፈለገውን ውጤት ስላልሰጠ በመጨረሻ ፊቷን ወደሶቭየት ህብረት አዞረች:: ሊቀመንበር መንግስቱ በ1969 በሞስኮ ካደረጉት ጉብኝት በኋላ የሶቭየት ህብረት ኢትዮጵያን፣ ሁለት ቢሊዮን በሚያወጣ የጦር መሳሪያ፣ ባጭር ጊዜ አስታጠቀች:: እንዲሁም በአንድ ሌተና ጀኔራል እና በሦስት ብርጋዴየር ጀኔራሎች የሚመራ የሶቭየት ወታደራዊ አማካሪዎች ቡድንና ፤የኩባና የየመን ወዶ ዘማቾች ወደኢትዮጵያ ላከች::[27] በዚህ ወታደራዊ ድጋፍ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በአገሪቱ ህልውና ላይ ከጣሊያን ወረራ ቀጥሎ በዘመናዊ ታሪኳ ከፍተኛ የተባለውን ወረራ በማክሸፍ ኢትዮጵያን ከከፍተኛ ውድቀት ሊያድን ሲችል፣ በሌላ በኩል ጦርነቱን የመሩት ሊቀመንበር መንግስቱ በኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ሊሆኑ ቻሉ:: ቀደም ብሎ የጀመሩትንም የሶሻሊስት ፈለግ በማጠናከር ሙሉ በሙሉ ወደ ሶሻሊስት ካምፕ ገቡ:: በመሆኑም ለረጅም ጊዜ የቆየው የኢትዮጵያና የአሜሪከ ወዳጅነት በዚህ ሁኔታ ተጠቃለለ:: ኢትዮጵያ፣ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው፣ በ1960ዎች መግቢያ ጀምሮ እያሽቆለቆለ የሄደውን የኢትዮጵያና የምዕራብ አገሮች (በተለይም የአሜሪካና የእንግሊዝ) ግንኙነት ያስከተለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቋቋም ስትል ግንኙነቷን ከአፍሪካና ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር ማጠናከር ጀመረች::

በመሆኑም ቀጥለን በወቅቱ ኢትዮጵያ ከአፍሪካና ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር በዓለም አቀፍ መድረክ የተጫወተችውን ሚና እንመለከታለን::

## ኢትዮጵያ ወደ ታዳጊ አገሮችና ወደ አፍሪካ ፊቷን ማዞርዋ

በ1888 በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያ የወቅቱ ትልቅ የአውሮፓ ኮሎኒያሊስት አገር ላይ የተቀዳጀችው ከፍተኛ ድል ለአፍሪካ ሕዝቦች ታላቅ ክብርና ኩራት

[26] ገዘኒ ከማሁ፣ ገጽ፣120፣325፣ 362፣ 364::

[27] ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ «የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ይዘትና ሂደት::» (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀና ያልታተመ ሰነድ፣ አዲስ አበባ፣ 1976)

ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ፈለግ በመከተል ለነፃነታቸው እንዲታገሉ በመቀስቀስ መልካም አርአያ መሆኑ በታሪክ የተመዘገበና አሁንም የሚጠቀስ ነው።

በ1928 ፋሽስት ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የከፈተው የግፍ ወረራ የዓለምን ሕዝብ በሙሉ ቢያሳዝንም ኢትዮጵያ ለደረሰባት ጥቃት ጥልቅ ሐዘንና መቆርቆር የተሰማቸው አፍሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲሁም በካሪብያንና በአሜሪካ የሚገኙ ጥቁሮች ነበሩ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ አንዳንዶቹም ወደ አገራችን መጥተው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን በመሰለፍ ጠላትን መዋጋታቸው ለተቆርቋሪነታቸው ዓይነተኛ ምሥክር ነው።

ከአምስት ዓመት የፋሽስት ወረራ በኋላ፣ ኢትዮጵያ በእራሷ ልዩ ልዩ ችግሮች ተወጥራ ስለነበር፣ በአፍሪካ የጋራ ጉዳዮች የተጫወተችው ሚና አነስተኛ ነበር ለማለት ይቻላል። ሆኖም እያደር የራሷ ችግር በመቃለሉ መገለሏን በማሻሻል በወቅቱ ነፃ የነበሩት የአፍሪካ አገሮች፣ ማለት ግብፅ፣ ላይቤሪያ፣ ሞሮኮ፣ ሱዳን፣ ጋና ወዘተ.. በ1950 አክራ ላይ ባደረጉት የመጀመሪያው የመላ አፍሪካ ነፃ አገሮች ስብሰባ ኢትዮጵያ ተገቢ ቦታዋን በመያዝ የሚጠበቅባትን አስተዋጽኦ አበርክታለች።

እንደዚሁም፣ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚክ ኮሚሽን በአፍሪካ እንዲቋቋም የአፍሪካ ነፃ መንግሥታት በዚህ ወቅት ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውታለች። እንደ አቶ ከተማ ይፍሩ ያሉ የዘመኑ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለስልጣኖች የአገሪቱን የአፍሪካ ዲፕሎማሲ ሚና ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። እነዚህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ለኢትዮጵያ አፍሪካዊነት በይበልጥ ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ በአፍሪካ የምታራምደው ፖሊሲና የምትወስደው አቋም ከምንጊዜውም ይበልጥ ተደማጭነት እንዲኖረው ለማድረግ በተቻለ መጠን ጥረዋል። የጥረቱም ውጤት ለዘመናችን የኢትዮጵያ አፍሪካዊነት ገጽታ የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ኢትዮጵያ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብ አፍሪካ ነፃነት ንቅናቄ (የAFMESCA) አባል በመሆን የሚፈለገውን የሞራል፣ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የማቴሪያል ድጋፍ በመስጠት አብዛኞዎቹ የአካባቢው አገሮች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ረድታለች። በኮንጐ (የዛሬዋ ኮንጐ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ) ከ1952 - 1956 ድረስ በተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት የአገሪቱን አንድነት፣ ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር በተባበሩት መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ ሥር የተሰለፉ አራት ባታሊዮን ወታደሮች ከማሰማራቷም በላይ ጠቅላላውን የተባበሩት መንግሥታትን ሰላም አስከባሪ ኃይል በአዛዥነት የመሩት የኢትዮጵያ ጄኔራሎች ነበሩ። ይኸውም ተሳትፎና አመራር ኢትዮጵያ በአፍሪካ ጉዳዮች የምትጫወተውን ሚና በማጉላት ለዲፕሎማሲዋ ግንባታ የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በሌላም በኩል፣ በቀድሞው የዓለም መንግሥታት ማሕበር አባልነትዋ በመጠቀምና ከላይቤሪያ ጋር በመተባበር የናሚብያን ጉዳይ ለዓለም ፍርድ ቤት አቅርባ የተጠቀሰችውን አገር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሞግዚትነት ሊያስተዳድር የሚገባ ለመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዲበይን በመጠየቅ ለአፍሪካ ነፃነት የምታደርገውን ተጋድሎ በግልጽ አስመዝግባለች፡፡

አፍሪካ ሙሉ ነፃነትዋን እንድትቀናጅ አንድነት እንደሚያስፈልጋትና አንድነቷም የሚጠናከረው የውጭ ተፅእኖን ስታስወግድ ብቻ መሆኑን ተገንዝበው አፍሪካውያን ያላሰለሰ ትግል ቢያካሂዱም በአንዳንድ የአስተሳሰብ ልዩነቶች የተነሳ ሞንሮቪያና ካዛብላንካ በመባል የታወቁ የፖለቲካ ቡድኖች በመፈጠራቸው መጠነኛ ችግር መከሰቱ ይታወሳል፡፡ ግብፅ ፣ ጋና፣ ጊኒ፣ ማሊ፣ ወዘተ. እና እነዚህኑ የመሳሰሉት ተራማጅ አገሮች (የካዛብላንካ ቡድን ይባሉ ነበር) አህጉሩ በአፋጣኝ የፖለቲካ ውህደት ማድረግ አለበት ሲሉ እንደ ናይጀሪያ ፣ ሱዳን፣ ላይቤሪያ፣ ሶማልያ፣ ቱኒዝያ፣ ወዘተ. ያሉት (የሞንሮቪያ ቡድን ይባሉ ነበር) የኤኮኖሚ ትብብር ቅድሚያ እንዲሰጠው አቋም ያዙ፡፡ ይህን መከፋፈል ለማስወገድ፣ ኢትዮጵያ ብዙ የዲፕሎማቲክ ጥረት ካደረገች በኋላ አስታራቂ ቻርተር በማቅረብና በዓለም ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈ የዲፕሎማቲክ ዘመቻ በማካሄድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ1955 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ እንዲመሠረት አድርጋለች፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄና የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በመመሥረትና በማጠናከር የተጫወተችው ሚና ምዕራባውያን ከጎንዋ በማፈግፈጋቸው የተፈጠረውን ክፍተት በከፊሉም ቢሆን ሊሸፍን ችሏል፡፡

ሆኖም ኢትዮጵያ የምዕራባውያንን መልካም እይታ ለማግኘት ስትል በመካከለኛው ምስራቅና ወሳኝ በሆኑ ጸረኮሎኒያሊስት ጥያቄዎች አንጻር የወሰደቻቸው አቋሞችና አንዳንድ አገሮች ለብሔራዊ ጥቅማቸው ሲሉ አገሪቱን ጸረ እስላም አድረገው ለማቅረብ ካደረጉት ጥረት ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያ በአካባቢው አቅማቸው እየጐላ በመሔድ ላይ ያሉ የአረብ አገሮች ዘንድ በመልካም አይን እንዳትታይ አድርጓታል፡፡ ይህ ጎጂ ሁኔታ ዛሬም ሆነ ለወደፊቱ ያገሪቱን ህልውና የሚጎዳ መሆኑ ታውቆ የጎላ እንቅስቃሴ መደረግ እንዳለበት የምንገነዘበው ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ከባህር ማዶ የመጡ ፈረንጆች አፍሪካን ሲቀራመቱ እኔ ዝም ብዬ ልመለከት አልችልም በማለት አፄ ምኒልክ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ከመሠረቱ በሁዋላ በፊት ባሉት ዘመናት ያገሪቱን ህልውና አጠያያቂ አድርገው የነበሩ ችግሮች የተከሠቱት በምሥራቅ በሶማሊያ፣ በሰሜን በኤርትራ በኩል እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ይህም አጭር ጽሁፍ ከ1933 - 66 ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ዋና ትኩረት የነበረው በኤርትራና በኦጋዴን ላይ መሆኑን በማብራራት ከላይ የተጠቀሰውን ያረጋግጣል፡፡

ሌላው በጽሁፉ ውስጥ የተመለከትነው በኢኮኖሚ ድክመቷና በአገር ውስጥ በነበሩት የፖለቲከ ችግሮች ምክንያት በኢትጵያ በስልጣን ላይ የነበረው መንግስት ያገሪቱን ህልውናና ስልጣኑን ለማረጋገጥ ባንድ ወይንም በሌላ ኃያል መንግስት ትከሻ መደገፍ እንደነበረበት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ጎጂ ወይንም ጠቃሚ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱት የውጭ ኃይል በሚያድርገው ግፊት ወይንም ድጋፍ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ አርበኞች ጣልያንን ከአገራቸው በማባረር ረገድ የተጫወቱት ሚና ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖር ቢሆንም፣ በእንግሊዝ የተመራው የኮመንዌልዝ ሰራዊት ከንጉሱ ቀድሞ አዲስ አበባ በመግባት ነጻ አውጪ ነኝ በማለት ኢትዮጵያን ለአራት አመታት በሞግዚትነት አስተዳድሮ ነበር፡፡ እንግሊዝ የኢትዮጵያን የፖለቲካ፣ የጸጥታ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የፍትህና የኢኮኖሚ መስኮች በመቆጣጠር ያደረገችውን ጫና ለማስወገድ የተቻለው የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ጎን በመሰለፉ ነበር፡፡ ንጉሱ አሜሪካንን በጎናቸው ለማሰለፍ ያደረጉት ያልተቋረጠ ጥረት ባይሳካላቸው ኖሮ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በመቀላቀል የባህር በር ለማግኘት ያደረጉት ጥረቶች ዋጋ ቢስ እንደሚሆኑ በወቅቱ በተ.መ..ድ መድረክ ከነበረው የኃይል አሰላለፍ ሁኔታ ለመገንዘብ የሚያስቸግር አይደለም፡፡

በ1960ዎች ጀምረው ምዕራባውያን በተለያዩ ምክንያቶች ከጎናችን በማፈግፈጋቸው የኢትዮጵያ ህልውና እንደገና አጠያያቂ መሆን ጀምሮ በሌላ ሃያል መንግስት ድጋፍ ችግሮችን ለማቃለል እንደተቻለ ብዙዎቻችን የምናውቀው የትላንትና ታሪክ ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያን የሚጎዱ ሆኑ የሚጠቅሙ ጉዳዮችን በመተግበር ረገድ የውጭ ኃያላን መንግስታት የተጫወቱት ሚና ባገሪቱ የዲፕሎማሲ ታሪክ ጉልህ ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የወቅቱ ዲፕሎማሲ የውጭ አጋዥ ኃይልን በማፈላለግ ያገሪቱ ህልውናና የነበረው መንግስት ስልጣን እንዲረጋገጥ በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡ በሌላ በኩል ግን ሀገሪቱን ለዘመናት ተጠናውቶ የኖረውን የኢኮኖሚ ድክመትና የውስጥ የፖለቲካ ችግሮች በማቃለል አገሪቱ በራሷ እንድትተማመን ለማድረግ ዲፕሎማሲው የተጫወተው ሚና የሳሳ ነበር፡፡

ከሀያላኑ መንግስታት ኢትዮጵያ በወቅቱ ያገኘችው ጠቀሜታ በርካታ እንደሆነ የሚካድ አይደለም፡፡ ነገር ግን በአንድ ሃያል መንግስት መተማመን የራሱ የሆነ ጉዳት አለው፡፡ ከጎኔ ኃያል አለ ብሎ መኩራራት ከሌሎች መካከለኛና እኩያ ከሆኑ መንግስታት ጋር አጋርነት የመፍጠር ጥረትን ያዳክማል፡፡ ኢትዮጵያም በወቅቱ የዚህ አይነት ችግር ታይቶባታል፡፡ በተለይም ከኢትዮጵያ ህዝብ ሰላሳ ሶስት በመቶ የሚሆነው የእስልምና ተከታይ ሆኖ ሳለ፣ በጥናቱ እንደተመለከትነው፣ አንዳንድ የአካባቢ አገሮች ኢትዮጵያን እንደክርስቲያን ደሴት በመቁጠር የሚያደርጉትን ጫና ለማስወገድ፣ በውስጥም ሆነ በውጭ የተወሰደ እርምጃ እጅግ ደካማ ነበር ፡፡

የምዕራባውያን በተለይም የአሜሪካ ድጋፍ እየመነመነ መሄዱን በመገንዘብ የንጉሡ ነገሥቱ መንግስት ከ1960ዎቹ ጀምሮ በገለልተኛ አገሮች ንቅናቁና በአፍሪካ የፖለቲካ መድረክ ጉልህ ሚና በመጫወት ክፍተቱን ለመሸፈን ጥሯል፡፡ በዚህ ረገድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረትና ዋናው ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን ውጤታማና አኩሪ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በአንጻሩም በምስራቅ አፍሪካ በሶቭየት ህብረት ድጋፍ የተፈጠረውን የወታደራዊ ኃይል ሚዛን መዛባት ለማስተካከል ከአሜሪካን ውጪ የጦር መሳሪያና የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት የተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት እምብዛም የተሳካ አልነበረም፡፡ በመሆኑም በአሜሪካን ድጋፍ ላይ ተመስርቶ ኃያል ሲመስል የነበረው የንጉሡ ነገሥቱ መንግስት የአሜሪካን ድጋፍ ማጣቱ ለድክመቱና ለውድቀቱ  አንዱ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

# ትምህርት፣ ባህልና ዕድገት፡-

# የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት (1948-1996)

*አሰፋው ዳምጤ*

የተወለድኩት፣ መጋቢት 10 ቀነ 1927፣ በአዲስ አበባ ከተማ ደጃች ውቤ ሰፈር፣መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት ቅጥር ግቢ ዛሬም በሚገኝ ቤት ውስጥ ነበር። አባቴ አቶ ዳምጤ ናደው የማተሚያ ቤቱ ባልደረባ የነበሩ ሲሆን፣ እናቴ ወይዘሮ ፈለቀች እርገጤ የሚባሉ ነበሩ። ለዚያ ዘመን ምናልባት አስደናቂው ነገር፣እናቴ ማንበብና መጻፍ ሲችሉ፣ አባቴ ግን በወቅቱ አይችሉም ነበር!! ኋላ እኔ ሳውቅ ግን አማርኛ ማንበብና መጻፍ ይችሉ ነበር፤ የመንግሥት ንብረት የሚባል መሥሪያ ቤት ባልደረባም ነበሩ። እናታቸውን «ትኮተልካለህ ብለሽ እንዳልማር ከልክለሽኝ፣ ከኀደኞቼ በታች አደረግሽኝ» እያሉ ሲያማርሩዋቸው ብዙ ጊዜ ሰምቻቸዋለሁ። እኔንም «ፈረንጅ ሀገር ሄደህ ትምህርትህን ሳትጨርስ ሥራ መያዝ የለም» ይሉኝ ነበር።

የ1929ኙ የየካቲቱ ጭፍጨፋ ሳቢያ ወላጆቼ ከአዲስ አበባ ከወሰዱኝ በኋላ እስከ 1936 አልተመለስኩም። ከሸሽት መልስ እናቴ አባት ዘንድ (25 ኪሎ ሜትር ከአዲስ አበባ በስተምሥራቅ) ነበር የኖርኩት። 7ኛ ዓመቴ ላይ እዚያው፣ ያገራችንን ትምህርት (እስከ ዳዊት ደገማ)፣ አባ እርገተ ቃል የሚባሉ መነኩሴ ተቀጥረው፣በአያቶቼ ቤት ተማርኩ። አዲስ አበባ እንደመጣሁ ዘመናዊ ትምህርት ቤት አልገባሁም፤ ከእናቴ ጋር (ዛሬ የአፍሪካ አዳራሽ ከሚገኝበት አካባቢ) ተቀምጬ፣አረጋዊው አለቃ ገብረ ኪዳን (የእንጀራ አባቴ አባት) እና መሪጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ (የግቢው ገብርኤል ካህን) ዘንድ ‹‹ዳዊት›› ከለስኩ።

ከመሪጌታው ተማሪ ቤት የደረስኩለት፣ ሁለት ትላልቅ ተማሪዎች (ኋላ ታዋቂ ድምፃዊና የቲያትር ባለሙያ የሆነው፣ ኢዩኤል ዮሀንስ እና ታምራት የሚባል የመሪጌታው ልጅ) በእግር ብረት ታስረው ዜማ ሲማሩ ነበር። «አንማርም ብለው እየጠፉ ስላስቸገሩ ነው» ታስረው፣ ድጓ ይሁን ጾመ ድጓ የሚማሩት የሚል ወሬ ሰማሁ። ከወራት በኋላም፣ ኢዩኤልን፣ አንድ ከፍተኛ የመንግሥት ሹም ገብርኤል ሲቀድስ ድምፁን አድንቀው ሀገር ፍቅር ቀጠሩት፣ የሚል ወሬ መስማቴ ትዝ ይለኛል።

ሚያዝያ 26 ቀን 1938 ወደ ወላጅ አባቴ ዘንድ (ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ከሚገኘው ሰፈር) ተዛውሬ፣ በክረምቱ ሥዕል ተማሪ ቤት አስገቡኝ። ትምህርት ቤቱ የሚገኘው፣ ከሰፈሬ ቅድስት ማርያም አልፈን ቁልቁል ስንወርድ፣ መንገዱ መጨረሻ ፊትለፊት (ትራፊክ መብራቱ ዘንድ) ነው። ኋላ አሜሪካን ኢኒስቲቲዩት ተብሎ የዶክተር ታልቦት *(የኢትዮፕያን ሄራልድ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበሩት)* እንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ትምህርት ቤት የነበረ

ሲሆን፣ በመጨረሻም ፣ዶርዜ ሀይዞ የሚባል ድርጅት የነበረበት፣ ትልቅ አዳራሽ ያለው ቤት ነበር፡፡

በዚያን ወቅት ዝንባሌዬና ትኩረቴ በሚገጣጠሙ የፊደል ዘሮች ላይ ማተኮር እንጂ፣ የተሣሉ የሰው ምስሎችን አስመስሎ መሣል አይስበኝም ነበር፡፡ አይሆንልኝምም ነበር፡፡ መምህራኑ፣ ወረቀት፣ እርሳስና ላጲስ ይሰጡንና፣ እዚያ ከነበሩት መጠነ ትልልቅ የነገሥታትና የመኳንንት የቀለም ቅብ ምስሎች፣ ደስ ያለንን አስመሰለን ‹‹እንድንቀዳ›› ይነግሩናል እንጂ የሚያስተምሩን ነገር አልነበርም፡፡ ሁሉም የየራሳቸውን ሥዕል ብቻ ነበር የሚሥሉት፡፡

ከመምህራኑ ትዝ የሚሉኝ የማነ ብርሃን ተንበሌ ብቻ ሲሆኑ፣ ከተማሪዎቹ የማስታውሳቸው ደግሞ፣ እንደ ከዋክብት ይቆጠሩና የርሳቸው ልጆችም የነበሩት ፣ሠረቀ እና አሰፋ የማነ ብርሃን እንዲሁም አሥራት ወልደ መድኅን ነበሩ፡፡ ሌላው ተማሪ አካሉ ወልደ ሚካኤል የነበረ ሲሆን፣ የማስታውሰው በደጃዝማች ገብረ ማርያም ትምህርት ቤት እንደገና ተገናኝተን፣ ከዚያም በኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት አብሮኝ ዘመናዊ ትምህርት ገበታ ላይ እስከ መጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ድረስ በመቀጠላችን ነው:: (አካሉ ኋላ በጂኦግራፊ የዶክትሬት ዲግሪውን አግኝቶ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ለብዙ ዓመታት አገልግሏል::)

## የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

ዘመናዊ ትምህርት ቤት የገባሁት ጥቅምት 9 ቀን 1939 ፣ በዚያን ጊዜ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ይባል በነበረው፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣በጀማሪዎች ክፍል (ኬ/ኤ) ነበር፡፡

በዚያ የትምህርት ዓመት በትምህርት ገበታ ላይ ከተገኘሁበት ጊዜ ያልተገኘሁበት ይበልጥ ነበር፡፡ ከእኔ በዕድሜ በጣም ከፍ ያለ የነበረው የንጀራናቴ ልጅም አብሮኝ ነበር የገባው፡፡ የሚያስተምሩን የፈረንጅ ፊደል ቀጠራ ስላልጣመው ትምህርቱን የጠላው ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ፣ ትምህርት ቤት ከመሔድ በከተማ መዞርን ይመርጥ ነበር፡፡

እኔም፣ ‹‹የእንግሊዝኛ›› ፊደሎቹን የምንማርበት አዝጋሚ ፍጥነት እና ፊደሎቹም ሁለት ሦስቱ ተገጣጥመው የሚነበቡበት ፈሊጥ እንደ አማርኛዎቹ ቀጥተኛ አለመሆኑን ስገነዘብ፣ ቶሎ ንባብ የመቻል ፍላጎቴ ላይ ውሃ ነበር የቸለሱበት፡፡ ሆኖም፣ የመጻሕፍት፣ የመጽሔቶችና የውጭ ጋዜጦች መደብር ባለቤት የነበረው ሚስተር ጃኖፑሎስ የወላጅ አባቴ ወዳጅ ስለነበረ፣ *ስቴፕ ባይ ስቴፕ* የምትል ትንሽ የእንግሊዝኛ መማሪያ መጽሐፍ ከእርሱ ዘንድ በነምሳ ሳንቲም ገዝቼ ነበርና፣ የሚያውቁትን እየጠየቅሁ፣ በጎን ‹‹ራሴን ማስተማር›› ጀምሬ ነበርና ተስፋ አልቆረጥኩም፡፡

ነገር ግን፣ የክፍሉ ትምህርት ብዙ ያመልጠኛል የሚል ሥጋት ይህን ያህልም አልነበረኝም፡፡ በዚህ ላይ፣መምህራኑ ይቀያየሩ ነበር፡፡ የመጀመሪያው

የማስታውሰው አስተማሪ ሚስተር ሽዳድ (እንደዚያ ነበር ተማሪ የሚጠራው) የሚባል ሱዳናዊ ነበር፡፡ ከርሱ ሌላ በየጊዜው የሚገቡ ኢትዮጵያውያን መምህራን ነበሩ፡፡ አስተማሪው ክፍል ሲገባ፣ ‹‹ዛሬ ምን ላስተምራችሁ?›› የሚል ጥያቄ ነበር የሚያቀርብልን፡፡ ታዲያ አብዛኛው ተማሪ አብዛኛውን ጊዜ፣ ‹‹ኤ ቢ ሲ ዲ!›› ይላል ጮክ ብሎ፡፡ አልፎ አልፎ ብቻ ‹‹ቁጥር!›› የሚለው ድምፅ ያይልና ያንን እንማር ነበር፡፡ ስለዚህ፣ የንጀራ ወንድሜን ከመንገድ የ‹‹እንቅርና እንዙር›› ሐሳብ አምርሬ አልቃወምም ነበር፡፡

ደግሞም፣እርሱ እናቱና አያቱ የሚሰጡት ‹‹ብዙ ፍራንክ›› ስለነበረው፣ ታሪክና ምሳሌ የሚለውን መጽሐፍ እንዲገዛ ‹‹ደጅ ጥናት›› ይዤለሁ፤ እና ‹‹አሁን ያለኝ ለቴምር ወይ ለስኳር ብቻ ነው፤ ሌላ ጊዜ ታሪክና ምሳሌን ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮፕያን ላይፍ የሚለውንም እንገዛለን›› እያለ እያጉዋጉዋኝ፣ ከርሱ አልለይም ነበር፡፡ በዚህ ላይ ስኳር መቃሙና ቴምር መብላቱንም አልጠላሁም፡፡

እንዲያውም አንድ ጊዜ፣‹‹የልጅ ወታደሮች ተማሪ ቤት አለ ብለው አንድ ዘመዴ ነገሩኝ፤ በየወሩ የኪስ ገንዘብ ይሰጣሉ፤ ትምህርቱም ከዚህ ይበልጣልና ለምን እዚያ አንገባም፤›› ብሎኝ እዚያ ለመግባት ተነሥተን እምድር ባቡር ጣበያ ጎን ከሚገኘው የወታደሮች ሰፈር ሔድን፡፡ አንድ ከእኔ ምንም ያህል ከፍ የማይል (እኔ 12ኛ ዓመቴን ገና አልደፈንኩም ነበር) ልጅ አግኝተን፣ ለመቀጠር መፈለጋችንን ስንነግረው፣ እዚያ ሳይሆን 11ኛ ሻለቃ ሔደን እንድንጠይቅ ነገረን፡፡ የት እንደሆነ አናውቅም ነበርና ጠየቅነው፤ ‹‹አውሮኘላን ማረፊያውጋ ነው›› አለን፡፡ ሁለታችም የአውሮኘላን ማረፊያው የት እንደሆነ ባለማወቃችን ነገሩ ቀረ፤ በየወሩ መጽሐፍ የመግዣያ የኪስ ገንዘቤም አብሮ!

ከዚህም በላይ፣ እናቱ እናት ዘንድ ገላን ርስታቸው በሰበብ አስባቡ እየሔድን እንከርም ነበር፡፡ ያማች ልጅ መስተንግዶውም አያያዙም አማላይ ነበር፡፡ ሆኖም፣ በለጠቀው ዓመት (1940) ወደ አንደኛ ክፍል መግባት ችዬ ነበር፡፡

ይኸ ሊሆን የቻለውም፣ በአዲሱ የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤቱ አዲስ ዲሬክተር (አሜሪካዊው ዶክተር ካርማይክል) የቀድሞውን ዲሬክተር (ግብጻዊውን ሙሴ ሳሊምን) ተክቶት ነበር፡፡ እኔ እና ወንድሜ እንደልማዳችን ከመክፈቻው ቀናት አሳልፈን ስንሔድ፣ ተማሪዎች ክፍላቸው ሲገቡ እውጭ የቀረነውን በሙሉ ሰብስቦን፣ ያለፈው ዓመት ትምህርት ቤት ሲዘጋ ሰርቲፊኬት የተቀበላችሁ እና አሁን የያዛችሁ እዚያ ተሰለፉ ሲባል፣ እኔ ሔጄ ተሰለፍኩ፤ እሱ ስላልነበረው ከመሰሎቹ ጋር ተባረረ፡፡

በዛው ዓመት፣ ማለት በ1940 ዓ.ም የኔ ትምህርት ቤት (ማለት የደጃዝማች ገብረ ማርያም ትምህርት ቤት) አቡዋሬ በሚባለው ሠፈር ከሚገኘው ወንድና ሴት ተማሪዎች ይማሩበት የነበረበት ትምህርት ቤት ጋር ተዋሕዶ ስሙም ተቀይሮ ኮከበ ጽባሕ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተብሎ፣ ዛሬ በሚገኝበት ቅጥር ግቢ (ቀበና ድልድይ አካባቢ) ዳግማዊ ልደቱን አገኘ፡፡ በወቅቱ እስከ 6ኛ ክፍል ብቻ ነበር ትምህርት የሚሰጠው፡፡ ደግሞም፣

በዚያን ወቅት፣ ወንድ እና ሴት ተማሪዎች በአንድ ገበታ ላይ የሚያስተምር፣ ብቸኛው ትምህርት ቤት ነበር።

የተዋሐደው ትምህርት ቤት ዲሬክተር የሆነው፣ እላይ እንደጠቀስኩት፣ ከዩኤስኤ ኦክላሆማ ክፍለ ሀገር በዚያው የትምህርት ዓመት መጥቶ ሙሴ ሳሊም ይባል የነበረውን የቀድሞ ግብጻዊ ዲሬክተር ተክቶ፣ የደጃዝማች ገብረ ማርያም ትምህርት ቤትን መምራት ጀምሮ የነበረው፣ ዶክተር ፔሪ ካርማይክል የሚባለው ምሁር ነበር። የአቡዋሬው ትምህርት ቤት ዲሬክተር የነበሩት የወለጋ ተወላጅ አቶ ነገሮ፣ ግርማ ሞገስ የነበራቸው ሽበቶ አረጋዊ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ በአስተዳደሩ አካባቢ አላየኋቸውም። ይህ ዝውውር የሆነው፣ በመጋቢት ወር መጨረሻ ወይም በሚያዝያ ወር መጀመሪያ 1940 ዓ.ም ነበር።

የትምህርት ቤቱ ባንዲራ ሲሰጥ፣ ትልልቆቹ ተሰልፈው ከጃንሆይ ሲቀበሉ፣ እኔ (ያኔ የ13 ዓመት ዕድሜ ብሆንም) ገና የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩና፣ በበዓሉ ላይ መገኘቴ ዛሬ ትዝ አይለኝም ። ንጉሠ ነገሥቱ የትምህርት ቤቱን አርማ ሲሰጡ የተናገሩትን ትክክለኛ ቃል ግን፣ ቆይቶ ፍሬ ከናፍር ከሚለው መጽሐፍ ቅጽ አንድ አግኝቼዋለሁ። የሚከተለው ነው፡-

> *ሰው ሠርቶ እንዲበላ ከፈጣሪው ታዟል። ለመሥራት መሣሪያ ያስፈልገዋል። ትምህርትና ቅንነት የመኖሪያችን መሠረቶች ናቸው። ለየታደልንበት ተፈጥሮ መሣሪያ የምናገኘው ከትምህርት ስለሆነ በሩ ተከፍቶ ይጠራችኋል። በምታገኙት ትምህርት እግዚአብሔርን መፍራት፣ አገራችሁን መርዳት ማንም ሊፍቀው የማይችል ዕዳ ነው። ይህን እንድትፈጽሙ፣ ይህ ሰንደቅ ዓላማ ምስክር ይሁንባችሁ።*
>
> *ሚያዝያ* 27 *ቀን* 1940

ዲሬክተሩ ዶክተር ካርማይክል፣ ከ1942 ጀምሮ በትምህርት ቤቱ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና በ1944 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እርከኖችን እየጨመረ በመሔድ በ1947 እስከ 12ኛ ክፍል መማር የሚያስችል፣ በሁሉም መልኩ የተሟላ፣ የአንደኛ፣ የመለስተኛ እና የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አደረገው። ከዚህም በላይ፣ ለሀገሪቱ የትምህርት እድገት አስፈላጊ የሆኑትን የማስተማር፣ ትምህርት ቤቶችን የመምራትና ለትምህርት ጥራት ሒደቱ ግብአቶች የሚሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ባለሙያዎች (የትምህርት ቤት ዲሬክተሮች፣ ሱፐርቫይዘሮች እና እንስፔክተሮች) የሚያፈልቅ ትምህርት ቤት አደረገው።

በ1948 ግን፣ የ2ኛ ደረጃን እርከኖች አሙዋልቶ፣ ከዚህ ትምህርት ቤት ከ14 የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በቀጥታ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ (አ.አ.ዩ.ኮ) ለመጀመሪያ ጊዜ ሦስት ተማሪዎች አስገባ። አካሉ ወልደ ሚካኤል፣

አበራ ተሰማና እኔ ነበርን። ከቀሩት ምሩቃን መካከል አምስቱ ምሕንድስና ኮሌጅ ገቡ። ይህ ኮሌጅ በዚያ ጊዜ የአ.አ.ዩ.ኮ. አካል አልነበረም።

ከኮከበ ጽባሕ አራተኛው ሆኖ ከእኛ ጋር ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ የገባው፣ቀደም ሲል ተለይቶን ለሁለት ዓመት ያህል እያስተማረ የነበረው፣ ተፈራ ኃይለ ሥላሴ (በኋላ አምባሳደር) ነበር። አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ የገባነው፣ የትምህርት ቤታችን የመጀመሪያዎቹ ምሩቃን ብንባልም፣ ለኮሌጁ ግን የስድስተኛ ዙር አዲስ ገቢ ተማሪዎች አባላት ሆነን ነበር።

## ሕይወት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

በሀገሪቱ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቅቀን፣ የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ሁለት ፈተናዎችን ዐልፈን፣ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ለ6ኛ ዙር ለገባነው በአጠቃላይ፣ ያ ዓመት በሕይወታችን ጉዞ ላይ ዐቢይ ምዕራፍ የከፈተ ብቻ ሳይሆን፣ ለሀገሪቱ ታሪክም አዲስ ሊሰኝ የሚችል ምዕራፍ የጀመረ ዓመትም ነበር ማለት ይቻላል።

ያኔ ለኛ ኮሌጅ መግባት ማለት ከአንድ የትምህርት እርከን ደረጃ ወደ ሌላ (ማለትም ከ12ኛ ወደ 13ኛ) መሸጋገር ወይም የመማሪያ ተቋም ወይም የቦታ ለውጥ ማለት ብቻ አልነበረም። ቀላል ያልነበረ የሥነ ልቡና እና የአመለካከት ለውጥ አብሮት ነበረ። ያኔ፣ አንድ ተማሪ 12ኛ ክፍልን አጠናቆ የኮሌጅ ተማሪ ሆነ ማለት፣ ከልጅነት ወደ ዐዋቂነት፣ ከእንዳሻው አድራጊ፣ ቦራቂ ልጅ ወደ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ተሸጋገረ ማለት ነበር።

ይህ አስተሳሰብ የወላጆችና የአዋቂዎች ብቻ ሳይሆን፣ተማሪው ራሱ አምኖ ተቀብሎት የሚመራበት ነበር። ተማሪው ራሱ፣ በራሱ ላይ የኃላፊነት ስሜት እንዲጭን የሚያደርግ ሁኔታ ነበር የሚገጥመው። በኮሌጅ ይገኙ የነበሩ ቀደምቶቹም በአርአያነታቸው የሚያሳድሩበት ይኸንኑ መንፈስ ነበር።

የኮሌጅ የመለዮ ልብሱን ለብሶ ከቅጥር ግቢው ሲወጣ፣ ጠባዩ እና ሁኔታው ሁሉ ልክ እንዳዋቂ መሆን አለበት። በአድናቆት ተመልካቹም ብዙ ስለሆነ፣ በሚናገረው እና በሚያደርገው ነገር ሁሉ ጠንቀቅ ማለት ይጠበቅበት ነበር።

የኮሌጅ መሪዎችም አያያዝ ይኸንኑ የሚያጠናክር ነበር። ለምሳሌ፣ገና እንደገባን፣ትምህርታችንን "ሀ" ብለን ከመጀመራችን አስቀድሞ፣ አዲሶቹ ተማሪዎች ባንድነት በምግብ ቤቱ አዳራሽ ተሰብስበን፣ የኮሌጁ ፕሬዚዳንት (ዶ/ር ሉሴየን ማት)፣ የአርት ፋክልቲ ዲን (ሚስተር ቦድዋ)፣የሳይንስ ፋክልቲ ዲን (ሚስተር ጉዋ) እና የተማሪዎች ዲን (ሚስተር ቤላ)፣ በየተራ ንግግር ሲያደርጉልን፣ በቀጥታም በተዘዋዋሪም ያስገነዘቡን ይኸንኑ ‹‹አዲሱን›› አንጻራዊ ቦታችንን ነበር።

ከዚያ ስብሰባ ሌላው የማይረሳኝ ትውስታ፣ በኮሌጁ ውስጥ የእኛን የአዲስ ገቢዎቹን ስፍራ ሲያስረዱን፣ በተለይ የተማሪዎች ዲን ያሉት ነው፡-

> እዚህ የተሰባሰባችሁት ተማሪዎች በሙሉ የየትምህርት ቤቶቻችሁ ከዋክብት ነበራችሁ። በየትምህርት ቤቶቻችሁ ያለውን ተማሪ ሁሉ እናንተ አዘቅዝቃችሁ ስትመለከቱ፣ ተማሪው ደግሞ አንጋጦ ሽቅብ ነበር እናንተን የሚያያችሁ። እዚህ ግን፣ አዲሶቹ እናንተ ከመሆናችሁም ሌላ፣ የሚበልጡዋችሁ እንጂ የምትበልጡዋቸው ተማሪዎች የሉም። ወደላይ የምታዩትና ወደታች የሚያያችሁ እንጂ፣ ወደታች የምታዩት እዚህ የለም። ግን መረበሽ የለባችሁም፤ ይህን ዐውቃችሁ፣ በውስጣችሁ ደረጃችሁን እስከተቀበላችሁ ድረስ፣ ችግር አይገጥማችሁም ነበር ያሉን።

ውጪ እንዳለው ዓለም፣ በዚህ በአእምሮ መኳንንት መንደርም ቀዳሚ እና ተከታይ መኖሩን ገና ከመነሻው ማስገንዘባቸው ነበር! በውስጤ ያኔ ለራሴ ያልኩት፣ ቀድሞና ተከትሎ የመግባት ነገር እንጂ የችሎታ ብልጫ አይደለምና፣ ይሽ ሁሉ ምን ማለት ነው? የሚል እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ንግግሩ አንዳችም ተጽእኖ አላሳደረብኝም ነበር።

ያ ዓመት፣ለሀገሪቱም አዲስ ምዕራፍ ጀማሪ ነበር ብያለሁ። እኛ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በገባን በወሩ፣ ማለትም ጥቅምት 23 ቀን 1948፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የደፉበት 25ኛ ዓመት (የብር ኢዩቤልዩ) በዓል የተከበረበት ወቅት ነበር። በመሆኑም፣ አንደኛ፣ የተሻሻለው እና ሁለተኛው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የታወጀበት፣ ሁለተኛ፣ በልማት ረገድ በልዩ ልዩ መስኮች ሀገሪቱ ያደረገቺውን እንቅስቃሴ እና ውጤቱን የሚያሳይ ሁለገብ ትርኢት (ኤግዚቢሽን) ከያኔው አውሮፕላን ማረፊያ በስተምዕራብ፣ ያኔ በነበረው እጅግ ሰፊ ሜዳ ላይ የቀረበበት ዓመትም ነበር።

የመጀመሪያው፣ማለትም የተሻሻለው ሕገ መንግሥት፣ ከ1948 ጀምሮ እስከ 1966 ለታወጁት ሕጎች ሁሉ መሠረት ከመሆኑም በላይ፣ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በሕዝብ ድምፅ እንዲመረጡ የደነገገ ነበር። ይሽ አሁን ሲነገር ቁምነገሩ እምብዛም ላይታይ ይችል ይሆናል። ነገር ግን፣ በወቅቱ ከነበረው አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር እና ተመራጮቹ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ፣ በተለይም በ1960ዎቹ፣ የተጫወቱት ሚና ሲታይ፣ ቀላል እርምጃ እንዳልነበረ ግልጽ ነው። ሁለተኛው፣ ማለትም የምርቶች ትርኢቱ ደግሞ (የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ የተደረገው ጥረት ውጤት ሲታይ)፣ በተገኘው ውጤት የመበረታታት፣ በአናሳነቱ የመቆጨት ስሜት በመቀስቀስ፣ ለሥራ የማነሣሣት ሚና እንዲጫወት የታለመ ስለነበረ፣ለልማት የነበረውን ንቃተ ህሊና ይጠቁማል።

በሥራ ውጤታቸው ብልጫ ላገኙና ላሳዩ ሽልማት (ማለትም ዕውቅና) መስጠቱም ይሽንኑ የሚያጠናክር ይመስለኛል። በጥበባት ዘርፍ የነበረው እንቅስቃሴም ግፊት ሳይሰጠው አላለፈም። በዚሁ ዓመት በርካታ መጻህፍት

ታትመው እናገኛለን። የሙገሳ ግጥሞች በዝተው መቅረባቸውንም እንገነዘባለን።[1]

በዚያ ክብረ በዓል ሳቢያ የሥዕል ውድድርም ተደርጎ ነበር። ይህ ደግሞ፣ሁለተኛ ለወጣው ለ18 ዓመቱ ወጣት ለእስክንድር ቦጎስያን የወደፊት የሙያ አቅጣጫ መወሰን እና ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥዕል እድገት ሒደት፣ አስተዋጽኦ አደረገ፤ አውሮፓ ሔዶ የዘመናዊ ሥዕል ጥበብን እንዲቀስም የዕድል በር ከፈተለት። አንደኛ የወጣው ደግሞ፣ ዛሬ በዓለምም ዕውቅ የሆነው እና ያኔ ተምሮ ከአውሮፓ ተመልሶ የነበረው ወጣቱ ሠዓሊ፣ አፈወርቅ ተክሌ እንደ ነበር መጠቆም ተገቢ ይመስለኛል።

እዚች ላይ ሳይገለጽ መታለፍ የማይገባው ቁምነገር፣ ጃንሆይ የጥበባት ዘርፎች እድገትን በቅርብ ይከታተሉና ያበረታቱ የነበረ መሆኑ ነው። ይኸ ሐቅ እስከ 1966 ድረስ የታየ ነገር ነው። በአንድ ሠዓሊ የግል ትርኢት ላይ ወይም ባንድ የሙዚቃ ባለሙያ ኮንሰርት ላይ ከተጋበዙ ይገኙ ነበር። እርሳቸውን ተከትሎ ደግሞ የካቢኔ ሚኒስትሮች፣ የውጭ አገር አምባሳደሮች እና መኳንንት፤ መሳፍንትና ሌሎችም ይገኙ ነበርና፣ የጥበቡ ባለሙያ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ስለሚያገኝ፣ ቶሎ ታዋቂ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነበር።

ወደ 6ኛው ዙር የአዲስ አበባ ዩኒቬርስቲ ኮሌጅ ገቢዎች ወደነበርነው ወጣቶች ጉዳይ ከማተኮሬ በፊት ደግሞ፣ ከራሴ እይታ ስለ ተቋሙ ጥቂት ልበል።

ኮሌጁ በ1943 ሲከፈት፣ በኮከበ ጽባሕ ቀ.ኃ.ሥ. ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ መሆኔን እንጂ መከፈቱን ያኔውኑ መገንዘቤን አላስታውስም። ሆኖም፣ እዚያው ሚያዚያ 27 አደባባይ ላይ በምሥራቃዊ ደቡብ በኩል፣ የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወይም ወወክማ) የሚገኝበት የአርበኞች ሕንፃ ነበር። ስፓርትን ይዞ፣ የሙዚቃ፣ የንግግር፣ የክርክር እና ሌሎችም ልዩ ልዩ ትምህርታዊ የሆኑ የምሽት ኘሮግራሞች ይዘጋጁበትና ይካሔዱበት ነበር።

የኮከበ ጽባሕ ተማሪዎች ተመላላሾች እንጂ፣ ለምሳሌ፣ እንደ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዳሪዎች ስለአልነበርን፣ ከትምህርት ቤታችን 11 ሰዓት ላይ ስንለቀቅ፣ በነዚህ ኘሮግራሞች ሳቢያ ወደ ወወክማ ጎራ ማለት ለምደን ነበር።

ይኸን አስመልክቶ እንደገና የምመለስበት ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ አልገባም። ወወክማን እዚህ ያነሣሁት፣ የግቢው አጥር በአንድ በኩል ከአደባባዩ ጋር የተያያዘውን እና ከመንገዱ ባሻገር የነበረውን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅን መኖር፣ እንዴት በሒደት ልገነዘብ እንደቻልኩ ለመጠቆም ብቻ ነው።

---

[1] እዚህ ላይ፣አማርኛ ወደ ጽሑፍ ቋንቋነት የተሸጋገረው ለዐፄ ዐምደ ጽዮን፣ለልጅ ልጁ ለዐፄ ዳዊት እና ለዐፄ ዳዊት ልጆች፣ ለዐፄ ይስሐቅ እና ለዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ በተጻፉ የሙገሳ ግጥሞች መሆኑንም ልብ ይሏል፤ አዲስ ባህል አልነበረም ለማለት ነው።

ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ዘመናዊ ሥልጣኔ ወደተባለው ግብ በአፋጣኝ ለመድረስ መንቀሳቀስ፣ ለሀገር የነጻነት ህልውና መጠበቅ ወሳኝ መሆኑ ታምኖበት ነበር። ለዚህ መረጋገጥ ደግሞ፣ በልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች በቂ ዕውቀት የቀሰሙ ኢትዮጵያውያንን የማፍራቱ ተግባር ቁልፍ ጉዳይ ሆነ።

ስለዚህ፣ ከመስከረም 1934 ጀምሮ ከፋሺስት ወረራ አስቀድሞ የነበሩ ትምህርት ቤቶች እና ተጨማሪ ሌሎችም፣ በአዲስ አበባ እና በዋና ዋና የክፍላተ ሀገር ከተሞች ተከፈቱ። በዚህ ወቅት ግን፣ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ዕውቀት ለማስቀሰም እንጂ፣ እንደ ቅድመ ፋሺስት ወረራው ጊዜ የትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጡ፣ የውጭ አገር ቋንቋዎችን ማወቅን ብቻ ዐይነተኛ ግቡ ያደረገ አልነበረም። የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎችን በማስተማርና በማስተዋወቅ ለተማሪው የወደፊት የትምህርት ዘርፍ ምርጫ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነበር አቀራረቡ። ለምሳሌ፣ ቀደም ሲል የቁጥር ትምህርት ሲባል የነበረው እና በአሪትሜቲክ ላይ የሚያተኮር የነበረው ወደ አጠቃላይ ማቴማቲክስ (ዝርዝሮቹ አሪትሜቲክ፣ አራቱ መደብ፣ ዴሲማል፣ ፍራክሺን... ወዘተ ሳይቀሩ አልጀብራ፣ ጂኦሜትሪ፣ ትሪግኖሜትሪ) እና አጠቃላይ ሳይንስ (ዝርዝሮቹ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ)፣ የዓለም ጂኦግራፊና ታሪክ የሚተኮርባቸው የትምህርት ዐይነቶች ሆኑ። ቋንቋም ወደነዚህ መዝለቂያ ቁልፍ ተደረገ።

ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሆኑ (ወይም በሒደት ያንን እርከን የደረቡ) ትምህርት ቤቶች የተከሰቱትም በዚህ በ1930ዎቹ ወቅት ነበር[2]። ከእነዚህ መካከል ደግሞ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ዋናዎቹ፣ የዳግማዊ ምኒልክ፣ የተፈሪ መኮንን፣ የጄኔራል ዊንጌት እና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ (ኮተቤ) ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ በሐረር ደግሞ መድኃኔ ዓለም ነበር። በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ትምህርት ፈጽመው ከዚያ በላይ መቀጠል ለሚሹት፣ በአገር ውስጥ የተዘጋጀ ማስተማሪያ ቦታ ከ1943 በፊት ስላልነበረ፣ በኮሌጅ ደረጃ መማሪያ የትምህርት ተቋምን መኖር ሁኔታው የግድ ጠየቀ።

በሌላ በኩል እስከዚያን ጊዜ ድረስ፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሚባለው የትምህርት እርከን ወይም በወቅቱ የሚሰጠውን የመጨረሻ ደረጃ ትምህርት ከፈጸሙ ወጣት ኢትዮጵያውያን መካከል የተወሰኑቱ፣ ለከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በአንዳንድ ግለሰቦች ከፋይነት በየጊዜው ወደ ውጭ አገር ይላኩ ነበር። ለምሳሌ ፣ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ከርሳቸው ግዛት መጥተው ተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት ይማሩ ከነበሩት መካከል አራት ልጆች ለትምህርት ወደ ውጭ (ቤይሩት) መላካቸው በዘመኑ *የብርሃንና ሰላም* ጋዜጣ ተዘግቦ ይገኛል።

---

[2] *በኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከፈተው፣ ከአዲስ አበባ በስተ ምስራቅ ያኔ ገጠር የነበረውና ኮተቤ ይባል በነበረው ስፍራ በ1936 ዓ.ም. የተከፈተው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት ነበር።*

ይሁን እንጂ፣ በዚህ መልክ ወደ ውጭ አገር መላክ ብዛት ያለው የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት ዘመናት የሚፈጅ ከመሆኑም በላይ፣ ዝቅ ባለ ደረጃ የጀመሩ ሌሎች ትምህርት ቤቶችም እስከ 12ኛ እያደረሱ ጎራውን ስለ ተቀላቀሉ፣ 12ኛ ክፍል የሚፈጽመው ተማሪ ቁጥር በየዓመቱ እያደገ ስለሄደ፣ ከዐቅም አንጻር የማይቻል መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ።

ከነዚህም ሁሉ በላይ፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በየሀገሩ የትምህርት ሥርዐት ውስጥ መኖር፣ ያ ሀገር በልማት እንቅስቃሴው እምን ላይ እንዳለ አመልካችም ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ፣ ለኮሌጁ መከፈት ይኸም እንደ አንድ ዐቢይ ታሳቢ ነጥብ አልነበረም ማለት አይቻልም።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የተከፈተው ነጻነት በተመለሰ በ10ኛው ዓመት ላይ ነው። ስለዚህ፣ መጀመሪያ ላይ የነበረው የተማሪዎች ብዛት አነስተኛ ነበር። ወደ ውጭ ልኮ ከፍሎ ለማስተማር ሲሆን ቁጥሩ ብዙ ይምሰል እንጂ፣ ለአንድ የሀገር ውስጥ ተቋም ሲሆን ግን አናሳ አህዝ መሆኑ አልቀረም[3]።

እኛ፣ ማለትም ያኔ በሀገሪቱ ከነበሩት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተሰባስበን በ6ኛ ዙር ቅበላው በ1948፣ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ስንገባ፣ ይህ ሁኔታ እምብዛም ተለውጦ አልጠበቀንም። ምክንያቱም፣ እኛ ሰባ ያህል ወንድና ሴት ተማሪዎች ሆነን በመጀመሪያ ዓመት ተማሪነት ስንገባ፣ የኮሌጁን ተማሪ ጠቅላላ ቁጥር በእጥፍ ያህል እንዳሳደግነው ነበር ሲነገር ትዝ የሚለኝ። በሴት ተማሪዎች ረገድማ ከፍተኛ ልዩነት ነበር ያመጣነው። ምክንያቱም እኛ ከመግባታችን ቀደም ብሎ ኮሌጁ ሁለት ጊዜ ሲያስመርቅ፣በነዚያ ምሩቃን መካከል በ1947 የተመረቀች አንዲት ሴት ተማሪ ብቻ ስለነበረች ነው። ከኛ ቀድመው በ1948 በኮሌጅ የነበሩት ሴት ተማሪዎች፣ ሦስት የሁለተኛ ዓመት እና አንድ የሦስተኛ ዓመት፣ በድምሩ አራት ብቻ ነበሩ። ከኛ ጋር የገቡት ስምንት ስለነበሩ፣በ1948 የኮሌጅ የሴት ተማሪዎችን ጠቅላላ ቁጥር ከ4 ወደ 12 አሳደግነው። በ1948 እና በለጠቁት ዓመታትም፣ ወላጆቻቸው በሥራ ምክንያት በኢትዮጵያ የነበሩ፤ የተወሰኑ የውጭ አገር ሴት ተማሪዎች፣ ይኸን ቁጥር በየጊዜው ከፍ ያደርጉ ነበር።

ይህ የወንድና ሴት ተማሪዎች በኮሌጁ አንድ ጋ መማር፣ ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች እንግዳ ነገር ስለ ነበር፣ ዝግ ከነበረ ባህላችን ጋር ተደምሮ በዕለት ተለት ግንኙነታቸው ላይ የተወሰነ ተጽእኖ ነበረው። በአንጻራዊ ደረጃ፣ ከኮከበ ጽባሕ ቀ.ኃ.ሥ. ከመጣነው በቀር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም፣ በዚያን ጊዜ ያ ትምህርት ቤት ወንድና ሴት ተማሪዎች በአንድነት የሚማሩበት ትምህርት ቤት ነበረና ነው። ምናልባትም በዚህ ረገድ፣ ያኔ በሀገሪቱ ብቸኛው ትምህርት ቤት ሳይሆን የሚቀር አይመስለኝም።

---

[3] በ1943 ዓ.ም ሲከፈት የገቡት ተማሪዎች ቁጥር 21 ሲሆን፣ ሁሉም ወንዶች ነበሩ፤ መምህራኑም ዘጠኝ ነበሩ። Teshome Wagaw, *The Development of Higer Education and Social Change* (East Lansing, 1990), p. 72

ይህ የሚታየው፣ በያመቱ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች በሚደረገው የሚያዝያ 27 ቀን የነጻነት በዓል የአደባባይ ሰልፍ እና ለልደት በዓል ብስኩት፣ ሹራብና ብርቱካን ለመቀበል፣ የመለዮ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ተማሪዎች ሁሉ ተሰልፈው ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሲሄዱ ነበር።

ሌላው የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ያገናኝ የነበረው መድረክ ፣ በትምህርት ቤቶች መካከል በየዓመቱ ሲካሔድ የነበረው ልዩ ልዩ የስፓርት (በተለይ የአቴሌቲክስ) ውድድር ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ በየትምህርት ቤቶች የእግር ኳስ ቡድኖች በየጊዜው ይደረጉ የነበሩ ፉክክሮች ተጨማሪ አገናኝ መድረኮች ነበሩ።

በአጠቃላይ ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ገቢ ተማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን ጠቅሻለሁ። በተለይ የሴት ተማሪዎች ቁጥር በጣም ያነሰ ነበር። ለዚህም አንዱ ዐቢይ ምክንያት ጋብቻ ነበር ማለት ይቻላል። ከዚህም በላይ፣ ዕድሜያቸው ከፍ ካለ በኋላ፣ ሴቶች ትምህርታቸውን እንዲገፉበት የሚያበረታታ ሁኔታ አልነበረም።

እርግጥ ከእቴጌ መነን ተማሪ ቤት ሌላ፣ ሴቶች ብቻ የሚማሩባቸው በተለይ የሚሲዮን ተማሪ ቤቶች ነበሩ። እዚህ ላይ፣ ካቴድራል፣ የአሜሪካን ሚሺን እና ናዝሬት ትምህርት ቤቶች ይታወሱኛል። ሆኖም በዚያን ጊዜ ዋናው ለኮሌጁ የሴት ተማሪዎች ምንጭ አነሰም በዛም እቴጌ መነን ተማሪ ቤት ነበር ማለት ይቻላል።

ለወንዶች ተማሪዎች ቁጥር ማነስ የመጀመሪያው ምክንያት፣ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥቂት መሆናቸው እንደ ነበረ ተገልጿል። ከቁጥራቸው ማነስ በተጨማሪ ደግሞ፣ የነዚህ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር በአጠቃላይ እና በተለይም 12ኛ ክፍል የሚደርሱ ተማሪዎቻቸው ቁጥር አነስተኛ መሆኑ ነበር። ለምሳሌ፣ እኔን ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ያሳለፈኝ የኮከበ ጽባሕ ቀ.ኃ.ሥ. ትምህርት ቤት የከፍተኛ 2ኛ ደረጃን እርከን በ1944 በ34 ተማሪዎች ጀምሮ፣ የመጨረሻውን እርከን ያሟላው በ1947 ሲሆን፣ የ12ኛ ክፍሉ ተማሪዎች የነበርነው ብዛት ደግሞ 14 ብቻ ነበር።

ሁለተኛው፣ በዚያን ዘመን ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታ የሚያማልሉና የሚጠልፉ ዕድሎች በርካታ የነበሩ መሆናቸው ነበር። የአየር እና የባሕር ኃይል፣ የክብር ዘበኛ እና የፖሊስ ካዴትነት፣ የመምህርነትና ሌሎች የልዩ ልዩ የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች (ለምሳሌ፣ ባንክ፣ ቴሌ… ወዘተ) የሥልጠና ኮርሶች አጓጊ ነበሩ[4]። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪውን ከየደረሰበት እርከን የሚጠልፉና፣ ለሥራና ለደሞዝ ቶሎ በሚያቀርቡ በነዚህ ዕድሎች ሳቢያ፣ 12ኛን ለመፈጸም እንኳ የሚደርሱት ተማሪዎች ቁጥር እያነሰ የሚሔድ ነበር።

[4] ስለባንክ የስልጠና ተቋም በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኘውን የአቶ ተፈራ ደግፌን መጣጥፍ ይመለከቷል።

ከነዚህ ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ፣ በዘመኑ ‹‹ማትሪክ›› ይሰኝ የነበረው፣ ከእንግሊዝ አገር ይመጣ የነበረ፣ መደበኛ የ12ኛ መልቀቂያ ፈተና ነበር፡፡ እሱም ወደ ኮሌጅ የሚገባውን የተማሪ ቁጥር የመቀነስ ሚና ሳይኖረው አልቀረም፡፡

ተማሪው በሚወስዳቸው የራሱ ትምህርት ቤት እና የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ፈተናዎች ላይ፣ በተደራቢ ይኸኛው የተጨመረው፣ እንግሊዞች የፋሺስት ኢጣሊያን ጦር ለማባረር ሊያግዙን በመጡ ጊዜ፣ በኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዐት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ስለነበራቸው፣ ያን ሚና፣ ከዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ መከፈት ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ መነጠቃቸው እና በጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ብቻ በመወሰናቸው፣ ተቆጭተውና ተቆጥተው፣ ‹‹ለኮሌጁና ለምሩቆቹ ዕውቅና አንሰጥም›› በማለታቸው ነበር፤ የሚል ሐሜት በወቅቱ እንደ ነበረ መስማቴ ትዝ ይለኛል፡፡

እዚች ላይ አንድ ነጥብም መጨመር ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በትምህርት ሥርዐቱ ላይ በአጠቃላይ፣ እንግሊዞቹ የነበራቸው ምኖፓል ከተሰበረ እና በጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት አመራር ላይ ብቻ ከተገደበ በኋላ፣ የማንኛውም የውጭ መንግሥት ዜጎች ካንድ ትምህርት ቤት በላይ እንዲመሩና ዜጎቻቸውም ተሰባስበው እንዲሰማሩ አለመደረጉ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እንግሊዞች የያዙትን ሲይዙ፣ ተፈሪ መኮንንን ካናዳውያን፣ ኮከበ ጽባሕ ቀ.ኃ.ሥ.ን አሜሪካውያን፣… ወዘተ ተከፋፈሉት፡፡ በሌላውም መስክ እንዲሁ ተደረገ፡፡

የትምህርት ቤቶቹን ጉዳይ በሚመለከት ቁልፍ ሚና የተጫወቱት፣ በወቅቱ የገንዘብ ምክትል ሚኒስትር እና በተደራቢነት የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ተጠባባቂ ሚኒስትር የነበሩት፣ ክብር አቶ ይልማ ደሬሳና የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ያኔ ዋና ጸሐፊ የነበሩት እና የኢትዮጵያ ጸሐፌ-ታሪክ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የነበሩ መሆኑን መግለጽ ይገባኛል፡፡ እንግሊዞቹ ነገሩን እጃንሆይ ድረስ አድርሰውት ነበር፡፡ ሆኖም፣ ውሳኔው አልተለወጠም፡፡

ወደ መነሻዬ ስመለስ፣ መነሾው ምንም ሆነ ምን፣ ተማሪው አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ለመግባት እነዚህን መሰናክሎች ሁሉ መዝለል ግን ነበረበት፡፡

በ1948 ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ስገባ፣ ሁለት ሌሎች ኮሌጆችም ነበሩ፡፡ እነርሱም የምሕንድስና እና የሕንፃ ኮሌጆች ነበሩ፡፡ እንደሚታወቀው፣ ሁዋላ ሦስቱም የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ አካላት ሆነዋል፡፡ ዓለማያ ኮሌጅ አሁን አለበት ቦታ ያኔ ተከፍቶ የነበረ መሆኑን አላስታውስም[5]፡፡ የሦስተኛ ዓመት የእርሻ ኮሌጅ ተማሪዎች ከእኛ ጋር አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ያድሩ እንደነበረ ትዝ ይለኛል፡፡ በዚያን ዘመን፣ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ለክረምቱ ዕረፍት ተዘግተው ቆይተው የሚከፈቱት መስከረም 18 ቀን ነበር፡፡ መስከረም 18 እና ጥር 13 ቀን

[5] የአለማያ የእርሻ ኮሌጅ በጥቅምት 1947 ዓ.ም ማስተማር ጀመረ፤ ግንቦት 19 ቀን 1977 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከፍ ብሏል፡፡

ሁለቱ የማይነቃነቁ የሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች ሁሉ የሚከፈቱባቸው ቀናት ነበሩ፤ ከፋሲካ ዕረፍት በኋላ የሚመጣው ሦስተኛው የትምህርት ቤቶች መከፈቻ፣ ቀኑ በቁርጥ አይታወቅም ነበር እንጂ፣ ከ‹‹ከዳግማይ ተንሣይ›› ማግሥት የሚውለው ሰኞ ነበር። እነዚህ ቀናት፣ በተማሪዎች ዘንድ በጉጉት የሚጠበቁ ቀኖች ነበሩ።

ይሁን እንጂ፣ የ1948ቱን መስከረም 18 ቀን መድረስ ለመጠበቅ አላስቻለኝም ነበርና፤ የለንደኑን የጂ.ሲ.ኢ (ጀኔራል ሰርቲፊኬት ኦፍ ኤጁኬሽን) ፈተና ማለፌን ከትምህርት ቤቴ ሔጄ እንዳረጋገጥኩ፣ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ከመክፈቻው ቀን ቀድሜ በመሔድ እዚያ ገብቼ ማደር ለመጀመር ወሰንኩ። ከዚያ ቀደም የአዳሪ ተማሪ ቤት ገጠመኝ አልነበረኝምና፤ ለመግባት ቸኮልኩ።

ወደ ተማሪዎቹ ዲን ቢሮ ሔጄ ቀረብኩ። ከኔ ጋር አንድ ሌላ ተማሪም ነበር፡- ሥዩም ገብረ ሥላሴ የሚባል። ዲኑ ስማችንን ጠይቆን፣ የሆነ ዝርዝር ከተመለከተ በኋላ፣ ‹‹ኮሌጁ ገና አልተከፈተም፤ ስለዚህ፣አሁን ምንም አገልግሎት አይሰጥም። መኝታ ክፍል፣ አልጋ፣ አንሶላና የብርድልብስ ብቻ ልሰጣችሁ እችላለሁ። ማታ እስከ 12 ሰዓት ተኩል ግቢው መግባት አለባችሁ፤ መብራቱን ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ማጥፋት አለባችሁ፤...›› እያለ መተዳደሪያችንን አሳወቀን፤ በደስታ ፈነጠዝን።

መኝታ ያገኘሁበት ሕንፃ ገና አዲስ ነበር። ክፍሌ በሰሜን በኩል 8፣ በደቡብ በኩል ደግሞ 6 አልጋዎች የሚያዘረጉ፣ ሰፋ ሰፋ ያሉ ክፍሎች ያሉበት ፎቅ ላይ ነበር። ሌሎቹ ሕንፃዎች (ነባሮቹ) ባለ አንድ መኝታ ቤቶች ነበሩ - ላይም እታችም። አዲሱ ለካ ለ6ኛው ዙር ገቢ ተማሪዎች ታስቦ የተሠራ ኖሯል። በኋላ ተማሪ ሲመጣ መርካቶ ተባለ።

ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ በዚያን ጊዜ፣ሁለት ፋክልቲዎች ብቻ ነበሩት፡- ‹‹ፋክልቲ ኦፍ አርትስ›› እና ‹‹ፋክልቲ ኦፍ ሳይንስ›› የሚባሉ። በሳይንሱ ዘርፍ፣የምሕንድስና የሦስት ዓመት፣የባዩሎጂ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ነበሩ።

በአርት ፋክልቲ ውስጥ የሚጠቃለሉት የትምህርት ዐይነቶች በርካታ ነበሩ። ለምሳሌ፣እኛ በመጀመሪያው ዓመት ወደ 13 የሚጠጉ የትምህርት ዐይነቶችን መውሰዳችን ትዝ ይለኛል። ከነዚህ መካከል፣አንዳንዶቹ ለአንድ ወይም ለሁለት ተርም ነበር የሚሰጡት። ከነዚህ አጭር ኮርሶች መካከል፣ለምሳሌ፣የትምህርት ታሪክ፣ አንትሮፓሎጂ፣ ሶሲኦሎጂ እና አርኪኦሎጂ የአንዳንድ ተርም ሲሆኑ፣ ጥንታዊ ታሪክ (የሜሶፓታሚያ፣ የጥንታዊ ግብጽ፣ የሕንድና የቻይና)፣ እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ (2 ዓመት)፣ ጥበበ ቃላት[6]ና ፍልስፍና የየአራት ዓመታት ትምህርቶች ነበሩ። ፕሮግራሞቹ በርካታ የሆኑትን የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች በስፋት የሚያቅፍ ሆኖ፣ ተማሪውን ደህና አድርጎ ከነዚህ ሁሉ የሚያስተዋውቅ ነበር ማለት ይቻላል።

[6] ጥበበ ቃላት ከ«ስነ ጽሁፍ» ጋር ተመሳሳይ ጽንሰ ሀሳብ ነው።

ፈረንጆች ሊብራል ኤዱኬሽን የሚሉት ዐይነት ትምህርት ነበር፡፡ ወደ የሕዝብ አስተዳደር፣ የትምህርት፤ የሕግ፣ የሥነ መንግሥት፤ የታሪክ… ወዘተ የእውቀት ዘርፎች ለማምራት የሚያስችል ወይም የሚያመች ዐይነት አቀራረብ ነበረው፡፡

የኮሌጁ ምሩቃን በየሔዱበት አገርና በየመረጡት የዕውቀት ዘርፍ ስኬታማ ሆነው መመለስ፣ ስለ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ አካዳሚያዊ ብቃት ብዙ ሊነግር የሚችል ይመስለኛል፡፡

በበኩሌ በመደበኛው ትምህርትም ሆነ፣ በትምህርት-ተጓዳኝ[7] ተግባራት ላይ ያደረግሁዋቸው እንቅስቃሴዎች አርኪ ነበሩ፡፡ ገና ዘመናዊ ትምህርት ስጀምር፣ በክፍል ትምህርትና ከመምህራን በሚገኘው ሳይወሰኑ ‹‹በተጓዳኝ ራስን በማስተማር ላይ *መተማመን*›› የሚለውን እምነቴን አጠናክሬ ነበር፡፡ እንዲሁም፣ በትምህርት ገበታ ላይ *ፉክክሬ ከተማሪ ጋር ሳይሆን፣ ከሙሉ ማርክ ጋር ነው* የሚለውን አሰተሳሰቤን በአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ አዳበርኩና ያዝኩ፡፡ ስለዚህ ለኔ 40 አግኝቶ አንደኛ ከመሆን 95 አግኝቼ ዐሥረኛ መሆንን እመርጥ ነበር፡፡

የኮሌጁን ሕይወት የተሟላ የሚያደርጉት፣ ከትምህርት ሒደቱ በተጓዳኝ ይካሔዱ የነበሩት፣ ከቀጥታ-ትምህርት ውጭ የሆኑ፣ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ ተመሳሳይ የትምህርት-ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ያኔ በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ይካሔዱ ነበር፡፡ ሆኖም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ከነዚያ ላቅና ወሰብሰብ ያሉ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተማሪ መንግሥታት የመመሥረት ልማድ ረዘም ላለ ጊዜ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃዎች መከፈት ጀምሮ ሲካሔድ የቆየ ነበርና፣ኮሌጁም ሲከፈት ይኸው ቀጥሏል፡፡

እነዚህ እንቅስቃሴዎች፣በአእምሯዊና በአካላዊ እንቅስቃሴነት የሚመደቡ ነበሩ፡፡ መዝናናትንም፣ ዕውቀትና ልምድ መገብየትንም ያቀፉ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ባህላዊ በሚል ስያሜ ሥር ሲጠቃለሉ፣ የሁለተኛዎቹ ስፓርታዊ እንቅስቃሴ ሥር የሚመደቡ ነበሩ፡፡

እነዚህን ሁሉ የሚያደራጅ፣ የሚያስተባብርና የሚመራ፣ በተማሪዎቹ በራሳቸው በየዓመቱ መጀመሪያ የሚመረጥ፣ የተማሪዎች ምክር ቤት ነበር፡፡ ምክር ቤቱ ሁለት እርከን ነበረው ማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም፣ ለየስፖርት እና ለየባህላዊ እንቅስቃሴው ዐይነት ሁሉ አንድ ኘሬዚዳንትና አንድ ጸሐፊ ነበረው፡፡

ዋናዎቹ የምክር ቤቱ አጠቃላይ ኃላፊዎች ግን አምስት ነበሩ፡፡ እነርሱም፣ የተማሪዎች ምክር ቤት ኘሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ጸሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ የስፓርት ፕሬዚዳንት እና የባህል ኘሬዚዳንት የሚባሉት ሲሆኑ፣ እኔ በነበርኩበት ዘመን (1948-1951) በጥቅል የቅጽል ስማቸው፣‹‹ዘ ቢግ ፋይቭ›› (አምስቱ ታላላቆች)

[7] Extra- Curricular የሚለውን ቃል የሚመልስ ነው፡፡

ተብለው በተማሪው ይጠሩ ነበር። ይኸም፣ ከተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባላት የቅጽል ስያሜ የተኮረጀ ይመስለኛል።

የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ስፓርት ቀን በየዓመቱ ይከበር ነበር። ነገር ግን ከ1950 ጀምሮ፣በሁለቱም ዘርፍ የሚካሔደውን እንቅስቃሴ የሚወክል ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በአጭሩ የኮሌጅ ቀን ተብሎ እንዲከበር ተወሰነ። በዛው በ1950 ዓ.ም ስር ስፓርት ነክ ያልሆነ ፕሮግራምም ነበር፤ ይህም የጠለፋ ጋብቻ የውስጥ ቲያትር ነበር። ይህ ተውኔት በፈረስና በበቅሎ ጭምር የተተወነ ነበር!! አስቂኝ ነገሮች አልታጡበትም ነበር።

በነዚህ ዓመታዊ በዓላት ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ከመኳንቶቻቸውና ከሚኒስትሮቻቸው ጋር፣የውጭ ሀገራት አምባሳደሮችም ይገኙ ነበር።

ለለጠቀው ዓመት (ለ1951) ታስቦ የነበረው አድዋን የሚዘክር ቲያትር ፕሮግራሙ ላይ ለማቅረብ ነበረ። ተቃውሞ እንዳለበት ከቤተ መንግሥት ተደውሎ በጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ በስልክ መነገሩን፣መጨረሻ ሰዓት ላይ በተማሪዎቹ ዲን ለተማሪዎች ምክር ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ ለእኔ ለአሰፋው ዳምጤ (በዚያን ሰዓት ኘሬዝዳንቱ ሐጎስ ገብረ የሱስ ስላልነበረ፣ እኔ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ነበርኩና) ተነገረኝ። እኔ ያኔ የታየኝ ብቸኛ አማራጭ ቲያትሩን በግጥም ንባብ መተካት ነበር። ከሁለቱ የዘርፍ ኘሬዚዳንቶች፣ ማለትም፣ ከአሰፋው ደስታ (ሁዋላ ዶ/ር)፣ የስፓርት፣ ፣ከመክብብ ገበየሁ (ሁዋላ አምባሳደር)፣ የባህል እና ፋንታዬ ቢፍቱ (ገንዘብ ያዥ) ጋር ተመካክሬ ሌላ ቶሎ የሚደርስ አማራጭ ስላልተገኘ፣ ከተወሰነ ክርክር በኋላ የግጥም ንባቡ ጸና።

በበዓሉ ላይ የሚያነቡ ሦስት ግጥም አቅራቢዎች፣ ውድድር ተደርጎ፣1ኛ ተገኘ የተሻ ወርቅ፣ 2ኛ ስሙ አሁን የተዘነጋኝ፣‹‹ፍሥሐዬ›› ይመስለኛል ከቀድሞ መምህራን መካከል እና 3ኛ፣ አያሌው አሳዬ በመሆን አሸነፉ። በዓሉ ላይ ጃንሆይ እና በርካታ ተከትለው የመጡ ሹማምንትና ሌሎች እንግዶች በተሰበሰቡበት በአደባባይ አነበቡ። ሽልማትም አስቀድሞ እንደተወሰነው በየደረጃቸው ተሰጣቸው።

የወርቅ ሰዓት ሽልማቱን ሲሰጡት፣‹‹ጃንሆይ ለምን በእንደዚህ መፍቻ የሌለው ነገር ራስህን ታስጨንቃለህ አሉኝ›› ብሎ ተገኘ የተሻ ወርቅ ማታ በምግብ ቤት አዳራሽ በተደረገው ግብዣችን ላይ ነገረኝ። ከዚያ በሁዋላ፣ የግጥም ንባቡ የየኮሌጅ ቀኑ ዓመታዊ ባህል ሆነና፣ እያደር የፓለቲካ ድምፀቱም እያየለ ላመታት በመዝለቁ፣ ዛሬ ታሪክ ሆኗል።

ያን ለት፣ እኔም ‹‹ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ›› የሚል የተጻፈበት አንድ‹‹ፖርከር 51›› ብዕር እና እርሳስ ተሸለምኩ። እንዴትና በማን የተወሰነ እንደ ነበረ አላወቅሁም ነበር!

በዚህ በባህላዊ ዘርፍ ይካሔዱ ከነበሩ ሌሎች እንቅስቃሴዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥ፣የቲያትር፣የክርክር እና የመድረክ ንግግር ውድድሮች ጎላ ያሉት ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ በኢዮብ ላይ በተመሠረተ ተውኔት ውስጥ በመጫወቱ እና የተዋጣ ሆኖ ጃንሆይም በማየታቸው ሳቢያ ነበር፣ ተስፋዬ ገሠሠ ከሕግ ይልቅ ውጭ አገር ሔዶ ቲያትር ሊያጠና የበቃው፡፡ በመድረክ ንግግር ውድድር ደግሞ፣ ስብሐት ገብረ ግዚአብሔር፣ ከሌላው ሁሉ ሙያ የትምህርት ሙያ ይበልጣል በሚለው የውድድር ንግግሩ (በጃንሆይ ዳኝነት) አሸንፎ ነበር ከጃንሆይ የጅ ሰዓት ሽልማት ያገኘው[8]፡፡ በመደበኛ ዳኞች ውሳኔ መሠረት ሕግን ቀዳሚ አድርጎ የተናገረው ተስፋዬ ገሠሠ ነበር አንደኛ የወጣው የሚመስለኝ፡፡ ‹‹ለተማሪ ፊት ማሳየት ተገቢ አይደለም›› የሚል ፍልስፍና ያለውና ፊቱ የማይፈታ የነበረው የጁሪስፕሩደንስ አስተማሪያችን ዶክተር ክሩስኪ ይኸን ክፍል ውሰጥ ሲሰማ፣ ተስፋዬን ‹‹ምን ተናገርክ? የታላቁን የሮማ ዡሪስ የኡልፒያንን ቃል ጠቀስክላቸው፡- *ሱኡም ኩዊኬ ትሪቤሬ ኔሚኔም ሌዴሬ ፣ሌጌም ኦቤዲሬ* አልካቸው?›› ብሎ ጥርሱን ብልጭ ማድረጉና አባባሉ ብዙዎቻችንን እንዳሣቀን ትዝ ሲለኝ የሚኖር ነገር ነው[9]፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ አባል ሆኜ ከመደበኛው ትምህርት ኮርሶች ያልተናነሰ ጥቅም ያገኘሁባቸው ሁለት ማኅበሮች ነበሩ፡፡ እነርሱም፣ በዶክተር ሳማአን-ሐና ይመከርና ይደገፍ የነበረው፣ፓኤትሪ ሶሳይቲ (የሥነ ግጥም ማኅበር ወይም ክበብ) እና በሚስተር ሆይናስኪ መሪነት ይንቀሳቀስ የነበረው የኤትኖሎጂካል ሶሳይቲ ነበሩ፡፡ ዶክተር ሳማአን-ሐና ሁለተኛው መደበኛ የእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ መምህራችን ነበር፡፡ የመጀመሪያውና አይረሴ የእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ መምህራችን ሚስተር ቶማስ ዳዎንስ የሚባል ነበር፡፡ ከመምህሮቻችን መካከል የሚያስተምረው ዘርፍ ላይ መጽሐፍ ያኔ ያሳተመ (የእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ አጭር ታሪክ 1949) እርሱ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ሒሳዊ አቀራረቡ የእሱን ክፍል ተናፋቂ የሚያደርገው ነበር፡፡ በመምህራንም ዘንድ በጣም የተከበረ ምሁር ነበር፡፡

እንዲያውም አንዱ መምህራችን፣ተማሪ ቢሮው ሔዶ ስለ ሰጠው ማርክ ማነስ ሮሮ ሲያሰማው፣ ‹‹ሚስተር ዳዎንስ ስንት ሰጠህ?›› ነበር ዋና ጥያቄው፡፡ በእርሱም ትምህርት ከፍ ያለ ማርክ ለማግኘት፣በዳዎንስ የእንግሊዝኛ ጥበበ ቃለት ኮርስ ከፍ ያለ ማርክ የሚያገኝ መሆን ያለበት ያስመስለው ነበር፡፡ ይህ መምህር ያስተምረን የነበረው፣የሶሲዮሎጂ እና የፓለቲካል ሳይንስ ኮርሶችን ነበር፡፡

ወደ ዶክተር ሳማአን-ሐና ልመለስ፡፡ እርሱም እንደ ቶማስ ዳዎንስ ባይሆንም፣ ጎበዝ ነው የምንለው ካናዳዊ ጀዝዊት (ኢየሱሳዊ ሚሲዮን) አስተማሪያችን

---

[8] ስብሃት ገብረ እግዚአብሄርና ተስፋዬ ገሰሰ በኢትዮጵያ የስነጽሁፍና የኪነት አለም ውስጥ ሁለቱም በደራሲነት፣ ተስፋዬ ደግሞ በተጨማሪ በተዋናይነት፣ እውቅና ሊያገኙ ችለዋል፡፡
[9] ትርጉሙ፡-

ነበር፡፡ በዚያው በእንግሊዝኛ ጥበበ ቃላት ኮርስ ውስጥ የአሜሪካንንም ይዳስስ ነበር፡፡ ፍቅሩ ግን በተለይ ለቋንቋው ሥነ ግጥም ነበር፡፡ ከታወቁት የአሜሪካን ገጣምያን አንዱዋ የሆነችውን የኤሚሊ ዲክንሰንን ግጥሞች ያምልኮት ያህል ይወድ እንደነበረ ትዝ ይለኛል፡፡ እኛም የእንግሊዘኛ ግጥሞችን ዐውቀን በሥርዐት እንድናጣጥም እጅግ ይጣጣር፣ ይተጋም ነበር፡፡ ለዚህም ነው ክበቡ የተቋቋመው፡፡ እኛም እንድንጽፍ በእጅጉ ያበረታታን ነበር፡፡

እኔ በማውቀው ቋንቋ ያገኘሁትን ጽሑፍ ሁሉ የማንበብ ዝንባሌ ቀድሞውኑ ስለነበረኝ ደስተኛ ነበርኩ፡፡ በኋለኛው ሙከራ (በመጻፉ) ግን፣አንዳችም ነገር እንደማልፈይድ ባውቅም፣ አባል ሆኜ የቆየሁት የማነበውን ለማጣጣም የሚረዱ ቴክኒካዊ ቁምነገሮችን ክፍል ከምንማረው በተጨማሪ አገኝበት ነበርና ነው፡፡

በአባላት የመጻፍ ሙከራ ረገድ፣ሁለት ተማሪዎች ትዝ ይሉኛል፡፡ ሙከራውን እንዲ ያነብልን የተደረገው አንዱ ዐምደ ሚካኤል ካብቴ ነበር፡፡ ትዝ እንደሚለኝ የሦስት መስመር ግጥም ነበረች፤ ስለ መቃብር፡፡ ዶክተር ሳማን-ሐና በቃሉ ደግሚት አድናቆቱን ሲገልጽ ዛሬም ይታየኛል፡፡ ሁለተኛው፣ መስፍን ገብረ ቃል (ሁዋላ ጄኔራል) ነበር፡፡ ‹‹አይ አም አ ካፒቴን ኢን ሔል …››[10] በሚል መሥመር የሚጀምር ነበር፡፡ ኋላ ለውትድርና ትምህርት ወደ ሳንድኽርስት ከዓለማየሁ አስፋው ጋር ሔዱ ሲባል፣ በአግራሞት ትዝ ያለኝ ያ የግጥም ስንኝ ነበር!

በተጨማሪም፣ ሳማአን-ሐና ከምናነበው፣ ከምንሰማውና ከምናየው አእምሮአችንን የሚኮረኩሩ፣ እንዲሁም በሐሳባችን ብልጭ የሚሉ፣ ነገሮችን በማስታወሻ የመያዝን ባህል እንድናዳብር ያለማሰለስ ያሳስበን ነበር፡፡ ‹‹ዘወትር የኪስ ደብተርና ቁራጭ እርሳስ ከኪሳችሁ አይጥፋ ›› ማለትን ያዘወትር ነበር፡፡

ለዘለቄታው የጸና የግጥም ንባብና የማጣጣም ፍቅር (በተለይ የእንግሊዝኛዎቹን) ያሳደረብኝ የዚህ ክበብ ተሳትፎዬ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ የግጥምን ድርሰት የማክበርን ያህልም ደግሞ፣መጻፉንም እንዳልደፍር ያደረገኝ ይመስለኛል፡፡ ከነዚያ ከምርጦቹ ደረጃ አንጻር የኔዎቹ ሙከራዎች የትዬለሌ የሚርቁ ስለሆኑ፣እንኳን ለሌላ ዐይኖች ሊቀርቡ ለኔዎቹም የማይበቁ ነበሩና፣ ተቀድዶ መጣል ነበር ዕጣቸው፡፡ ከዚያም፣ ‹‹ጨርሶ አለመፈጠር››!

ያማርኛ ግጥሞችን ማንበብ ያስወደዱኝ ግን፣ የከበደ ሚካኤል ግጥሞች ነበሩ፡፡ በእስተርጅና ግጥሞች መጫጫር እንድሞክር ያደፋፈረኝም፣የዚሁ የብዕር ሰው የወጣትነቱ ዘመንና የበኵር ሥራው፣ *የብርሃን ሕሊና* መቅድም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ያው እኔም ወደ ዳግማይ ወጣትነት ዘመኔ እየሔድኩ አይደል!

ሁለተኛውና ሚስተር ሆይናስኪ ይመራው የነበረው፣ከላይ የጠቀስኩት ኤትኖሎ ጂካል ሶሳይቲ፣ሌላው ነዋሪ ቁምነገር ያስጨበጡኝ ገጠመኞች ያገኘሁበት ተሳትፎ ነበር፡፡ በኤትኖሎጂካል ሶሳይቲ አባልነቴ፣ ስለ *ዕቁብ* የጻፍኩት አጭር

[10] የሲኦል ካፒቴን ነኝ፡፡

ጥናታዊ ጽሑፍ፣ በዚህ ርእሰ ጉዳይ የተጻፈ የመጀመሪያው ጽሑፍ መሆኑን ዛሬ ተጠቅሶ ሳይ ከማገኘው እርካታ ያላነሰ፣ ስጽፈው ከሚስተር ስቴፈን ራይት ጋር ስለትርጉም ባደረግነው ውይይት መካከል፣ አንድ የትርጉም ጽሑፍ በትክክል የተተረጎመ መሆኑን ለማረጋገጥ መከተል ስለሚገባኝ መርህ የሰጠኝ ትምህርት ነበር። ይኸውም፣ በምንጭ ቋንቋው ውስጥ ያለውን ሃሳብ ሁሉ፣ በተረጎምክበት ቋንቋ ጽሑፍህ ውስጥ ወካይ መገለጫ ያደረግህ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ፣ የሚለው ነው። በጣም ግልፅና ቀላል ግን መሠረታዊ ነው፤ በግሌ እንደዋና የትርጉም ሥራ መርህ አድርጌው ስመራበት ኖሬያለሁ። አንድን የትርጉም ሥራ ለመፈተሻ ዓይነተኛ ዘዴ ይመስለኛል። በዚሁ ማኅበር በአንዱ የምሽት ስብሰባ ላይ ነበር፣ገና ለምርምር ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ንግግር ሊያደርግልን መጥቶ፣ዶናልድ ሌቪንን የተዋወቅነው። ንግግሩን በአማርኛ መጀመሩ ነበር ያነቃቃን። ከዚያ ወደ እንግሊዝኛ ንግግሩ ለመሸጋገር፣ ‹‹ንግግሬን ካማርኛ ይበልጥ በእንግሊዝኛ ማድረግ ይመቸኛል›› ነበር ያለው።

እንደሚታወቀው፣ የዚህ ወቅት የምርምሩ ውጤት፣ዛሬ በዓለም በብዙዎች በኢትዮጵያ ጉዳይ ምሁራን ዘንድ የታወቀው፣ *ሰምና ወርቅ* (ዋክስ ኤንድ ጎልድ) የሚለው መጽሐፉ ነበር።[11]

‹‹ከማርች 1960 በፊት አትክፈተው›› የሚል የእንግሊዝኛ ትይብ ያለበት ስምየለሽ ኤንቬሎኘ፣በማርች 1959 (እ.አ.አ) በመኝታ ቤቴ ክፍል በር ሥር ተሰዶ አገኘሁ። መጀመሪያ ላይ፣ ይህን እንቆቅልሽ ወዲያው ለመፍታት ዳዳኝ። ግን ጨክኜ ተውኩትና፣በዓመቱ እንግሊዝ አገር ኬምብሪጅ ዩኒቨርስቲ በሔድኩ በሰባተኛ ወሬ ከፍቼ ሳየው፣የዶናልድ ሌቪን ቃለ-መጠይቅ ነበር። ከአዲስ አበባ ከመልቀቁ በፊት፣ኤንቬሎፑን ካገኘሁት በኋላ የሱ መሆኑን ይንገረኝ አይንገረኝ አላወቅሁም። የተሰጠው ለ4ኛ ዓመቶች በሙሉ መስሎኝ የነበረው ትክክል የነበረ አለመሆኑን፣ዘመናት ቆይቶ ነበር ያወቅሁት። ያኔ ይህን ዐውቄ ቢሆን ኖሮ መልሴን እልክ እንደነበር አሁን ይሰማኛል።

የሆነው ሆኖ፣ጥያቄዎቹን በስፋት ለመመለስ ጀምሬ ግን ጨርሼ ሳልክ ቀረሁ። ዋና ሆነው የታዩኝ፣ሀገሬን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ፣በሃይማኖትና በፓለቲካ ረገድ የነበረኝ አመለካከት ተለውጦ እንደሆነና፣ከሆነ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ የሚጠይቅ ነበር።

ቃለ-መጠይቁ ባይላክም፣በርሱ ሳቢያ ስለነዚህና ሌሎችም ጉዳዮች ለረጅም ጊዜ እንዳሰላስል አድርጎኝ ነበር። እንዲያውም፣አምንባቸው የሚመስሉኝ ብዙ ነገሮች

---

[11] ይህ ሊቅ በአሜሪካን አገር እጅግ ታዋቂ ከሆኑት ዩኒቨርስቲዎች መካከል በአንዱ ውስጥ፣ ማለትም በቺካጎ ዩኒቨርስቲ ውስጥ፣ የሶስዮሎጂ ፕሮፌሰር ሆኖ ያገለገለና በምርምር ስራው አለም አቀፍ እውቅና ያገኘ ሊቅ ነው። *ሰምና ወርቅ* ሌላ ስፊ ተነባቢነት ያገኘና ምሁራዊ ተጽእኖም የፈጠረው መጽሀፉ፣ *Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society*፣ የተባለው ስራው ነው።

ለካ ዝም ብዬ በደፈናው የምላቸው እንጂ ውስጤ የማይቀበላቸው ኑረዋል፡፡ ገረመኝ!

የኤትኖሎጂካል ሶሳይቲ ታላቅ ጠቀሜታ በዕረፍት ወቅት አባላቱ ያደርጉዋቸው የነበሩ ጉዞዎች አስደሳችም አድማስ አስፊም መሆናቸው ነበር፡፡ በተለይም ለእኔ፣ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ከመግባቴ በፊት፣አንድ ጊዜ እመራው በነበረው፣ በወወክማው የወጣቶች ምንጭ ክበብ አባላት የሽርሽር ጉዞ አቃቂ ከመሔዴ እና፣ ወደ አሳደጉኝ የእናቴ እናት ቤት፣ ከአዲስ አበባ 25 ኪሎ ሜትር በስተምሥራቅ ከመመላለሴ በቀር፣ ከከተማው ወጥቼ ለማላውቀው ጥሩ አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

## ሁለት ጊዜ ጉዞ ወደ ጎጃም

ከነዚህ የኤትኖሎጂካል ሶሳየቲ የጉብኝትም ሆነ የጥናት የከተማ ውጪ ጉዞዎች፣ለእኔ አይረሴና በተከታዩ የሕይወት ጉዞዬ ላይ ተጽእኖ የነበረው፣ በ1949 በድኅረ ዐቢይ ጾም ዕረፍት ወቅት ወደ ጎጃም የተደረገው የጥናት ጉዞ ነበር፡፡ በእኔ በኩል ታቅዶ የነበረው የጥናት ርእስ *የጋብቻ ባህል በጎጃም* የሚል ነበር፡፡

ጉዟችን ከአዲስ አበባ እስከ ደብረ ማርቆስ በአውሮፕላን ነበር፡፡ በማግስቱ ከደብረ ማርቆስ እስከ ደምበጫ በግልጥ የኪራይ መኪና ሆኖ እዚያ ጥቂት አርፈን፣ ወደ ማረፊያችን ወደ መንገሻ ወርቅነህ አጎት ቤት፣ ወደ ታች ከባሊት የአምስት ሰዓት በላይ የእግር ጉዞ አድርገን ሲመሽ አካባቢው ደረስን፡፡

በሚስተር ሆይናስኪ መሪነት፣ ለጥናቱ የተሰማራነው፣ መንገሻ ወርቅነህ፣ አንዳርጋቸው ተስፋዬ፣ ተገኝ የተሻ ወርቅ እና እኔ ነበርን፡፡ የጥናቱ ጉዞ ውጤታማ የነበረ መሆኑን አላስታውስም፡፡

በራሴ ጥናት በኩል፣ የሰበሰብኩትን ማስታወሻ ስመለከተው አዲስ ወይም ከማውቀው ብዙም የተለየ አልመሰለኝም፡፡ ጥቂት ገርሞኝ የነበረው፣ በአረፍንበት ቤተሰብ ዘንድ *ሙሽሪት* ሲኗት የነበረች አንዲት ትንሽ ልጅ (12 ዓመቷ ነው ነበር ያለችኝ) ሁለተኛ ባልዋ ነው ሲባል መስማቴ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በልጅነት መዳር በተለይ የጎጃም ባህል የሚባል አልመሰለኝም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ የተለየ የምለው ነገር አላጋጠመኝም ነበር፡፡

ለዚሁ ጥናቴ ሳናግራቸው ከነበሩት ሰዎች መካከል በውይይቱ ወቅት የሚነግሩኝ፣ ለጥናቴ የሚጠቅሙ ከመሆናቸው ይልቅ፣ ለኔ እንግዳ እና እማላውቃቸው በመሆናቸው የያዝኩዋቸው ነበሩ፡፡ ከነዚህ መሀል፣ አንዱ ‹‹*ጥሩምቡሌ ነበርኩ*›› ብሎኝ፣ በዚያ መነሻ የተረከልኝ ነበር፡፡ ጣሊያኖች ሊቢያን በቅኝ ግዛትነት ይዘው ሲያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያውያን ተዋጊዎችን በውጊያው ላይ ማሰማራታቸውን ስሰማ በጣም ነበር የገረመኝ፡፡ ‹‹ጥሩምቡሌ›› የሚለውን ስያሜም ከትሪፖሊ ከተማ ስም ጋር መዛመዱ ታየኝ፡፡ ሌላው፣ ‹‹በንግስተ ሳባ ታሪክ ውስጥ የሚተረከው ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክ መወለዱ

ብቻ ነው። ነገር ግን፣ የርሱዋ ደንገጡርም ወንድ ልጅ ወልዳለች፤ ስሙ ዛገ የተባለ። ዛገ የጎጃም ነገሥታት አባት ነው›› ነበር ያለኝ። በሌላ በኩል ግን፣ ከዛጉዬም ጋር ያያይዘው ስለ ነበር፣ እውነትነት ካለበት ለዚህኛው የሚቀርብ መስሎኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ይሁንና፣ ይኸም ከዚያ ቀደም ያልሰማሁት አፈ ታሪክ ነበር።

በዚህ ጉዞ ላይ የገጠመን ትልቅ ድራማ ቅዳምን ከሚባል የቅዳሜ ገበያ ሔደን የሆነው ነገር ነበር። ገበያው ስፍራ ደርሰን ወዲያ ወዲህ ስንል፣ መሣሪያ የያዙ አራት ይሁኑ አምስት ሰዎች ድንገት መጥተው ሚስተር ሆይናስኪን ‹‹ሹም ዘንድ እናቀርበዋለን›› አሉ። ተደናገጥን፤ ያልጠበቅነው ነገር ነበር።

ሹም የተባለው፣ ካሳ የተባለ የአካባቢው የጎበዝ አለቃ ነው። ሽፍታና ሌባ-አድን ነው። ‹‹ማን ፈቀደለትና ነው ጣሊያን እዚህ ድረስ ይዛችሁ የመጣችሁት?›› አለ። በየፊናችን ስለ ጉዞአችን ዓላማ … ወዘተ ለማስረዳት ሞከርን።

ሆናይስኪ ግን ዝም ብለው ያስተውላሉ። መንገሻም ምንም መናገሩ አይታወሰኝም። እኔና አንዳርጋቸው ነበርን ለማስረዳት እምንጥረው። እሱ ሲናገር አንዱ፣ ‹‹ይኸ ደሞ በኛ አፍ ይናገራል፤ አዬኸው›› አለ። አንዳርጋቸው መነጽር አድርጎ ነበር። ምንአልባት ያኔ መነጽር ያደረገ ኢትዮጵያዊ አላዩ ነበር ይሆናል፤ ከዚያም እርሱም ተጠርጣሪ ሆነና መልስ ሰጪ እኔ ብቻ ሆንኩ።

‹‹አስሬ ወደ ማርቆስ ነው የምወስዳችሁ›› አለ።

በዚህ መካከል ሚስተር ሆይናስኪ፣ አንድ ያገር ግዛት ሚኒስቴር ደብዳቤ አውጥተው ሰጡት። መጀመሪያ ዘቅዝቆ (ማህተሙን ከላይ ወገን አድርጎ) ነበር ሲመለከተው የነበረው፤ ኂላ ሲነገረው ደንገጥ አለና፣ ከአጃቢዎቹ አንዱ ጮክ ብሎ እንዲያነብለት ወረቀቱን ሰጠውና ተነበበ። ችግራችንም በመጨረሻው በዚህ ተፈታ።

ከደብረ ማርቆስ ስንነሣም አንድ ቄስ ሾፌሩን ‹‹እባክህ እኔንም ስቀለኝ›› በማለት ለምነው አብረውን ደምበጫ ድረስ መጥተው ነበር። አስቀድመው ስለኛ ብዙ ጥያቄ ሲጠይቁና ሲያጠያይቁ ነበር። እንደሰማነው፣ ካንድ ሁለት ወር በፊት፣ ‹‹የዮሆቫ ምስክሮች ነን›› የሚሉ፣ ዎች ታወር ሚሺን የሚባል ድርጅት የላካቸው መጥተው፣ ባዕድ ሃይማኖት ሲሰብኩና ማርያምን ሲሳደቡ፣ ሕዝቡ ደብድቦ አባሯቸው ነበር። እኛም የመጣነው እንደዚያ ዓይነት ነገር ለማድረግ እንደ ሆነ ለማጣራት ኖሯል፣ ጥያቄና ክትትሉ። ይሁን እንጂ፣ ቅዳምን ገበያ ላይ የገጠመን ቀጥታ ግንኙነት የነበረው መሆኑን እጠራጠራለሁ።

ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን፣ መደበኛ ተግባራችንን ጀምረን የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኂላ፣ ለማህበራችን ከኬምብሪጅ ዩኒቬርሲቲ አንድ ደብዳቤ መጣ። ፍሬ ነገሩ፣ በሚለጥቀው የክረምት ወቅት፣ ስድስት የዩኒቬርሲቲውን ተማሪዎች የያዘ አንድ የቦታኒካል እና የዙኦሎጂካል የጥናት ቡድን፣ ለሁለት ወር በጎጃም ጥናት ለማድረግ ስለሚመጣ፣ አብረዋቸው የሚሔዱ ሁለት ፈቃደኛ የዩኒቬርሲቲ

ኮሌጅ ተማሪዎች ካሉ፣ እነርሱ ወጪውን ችለው ከነርሱ ጋር እንዲሔዱ የሚፈልጉ መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ስምንት አባላት ፈቃደኝነታችንን ገለጽንና፣ የማኅበሩ አመራርና አማካሪው እኔንና አንዳርጋቸውን መረጡን።

ጥናታቸውን ለማካሔድ ከመረጧቸው አካባቢዎች መካከል አንዳንዶቹ (ለምሳሌ የጮቄ ተራራ) አጋሚዶ (ሽፍታ/ወንበዴ) ያለባቸው ስለሆኑ ፣ አደገኛ ናቸው፤ የሚል ወሬም ነበር። በዚያን ጊዜ እኔ ይኸ ወሬ ምንም መስሎ አልተሰማኝም ነበር።

እኛ የኮሌጅ ተማሪዎች በነበርን ጊዜ የኪስ ገንዘብ እንድናገኝ፣ በልዩ ልዩ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች የክረምት ሥራ እንይዝ ነበር። (የመንግስት ተባበሩ ሳይኖርበት ይቀር ይሆን ብዬ አስቤያለሁ ያኔ)። ስለዚህ በቀደመው ክረምት፣ እኔም እንደሌሎቹ ጓደኞቼ ክረምት ሥራ (ለመጀመሪያ ጊዜ) አ. ቤስና ኩባንያ ከሚባለው፣ በዘመኑ በጣም ትልቅ የንግድ ድርጅት ዘንድ ሔጄ ጠይቄ ነበር። ያነጋገረኝ አንድ ሕንድ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ‹‹ሥራ የለንም›› እያለ ማቅማማቱ ትዝ ይለኛል። ሆኖም ብዙ ተነጋግረን ማስታወሻም ይዞ ነበር። በሌላ ቀን ተመልሼ እንድጠይቅ ነግሮኝም ነበር። እኔ ግን አልተመለስኩም፤ ምክንያቴ በከፊል እንደ እምቢታ ስለቆጠርኩት ነበር። ዋናው ግን፣ ሚስተር አርዲ የሚባለው የኮሎጁ አስተዳዳሪ እኔንና ሥዩም ገብረ ሥላሴን የክረምት ሥራ እና ደህና ደሞዝ ስለሰጠን ነበር። (ወሩ መጨረሻ ላይ - ሐምሌ ይመስለኛል - ቤስ ኩባንያ የተቀጠረ አንድ ተማሪ ይፈልግህ ነበር፤ ደሞዝህን ለምን አልወሰድክም? ናና ውሰድ ተብልሃል ይላል አሉኝ!! ገረመኝ፤ ያልሠራሁበትን ለመውሰድ ግን ፈቃደኛ አልነበርኩም።)

ስለዚህ፣ ለጎጃሙ ጉዞዬ የሚከፈለኝን፣ እንደዚያ (የ2ኛ) ዓመት የክረምት ሥራ ደሞዜ ቆጥሬ፣ ኬምብሪጆቹ ከእንግሊዝ አገር እስኪመጡ ጠበቅሁ። ጊዜው ሲደርስ፣ እኔ ብቻ ከአጥኚው ቡድን ጋር ወደ ጎጃም ተጓዝኩ። አንዳርጋቸው ‹‹የክረምት ሥራ›› ይዞ ኖሮ በዚያው ለመቀጠል ወስኖ የነበረ መሰለኝ።

ስድስቱ ተማሪዎች ከኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኮሌጆች ነበር የተሰባሰቡት። ስድስቱም እንደኔው፣ ሁለተኛ ዓመታቸውን ፈጽመው፣ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን 3ኛ ዓመት ገቢዎች ነበሩ፤ ለነሱ ግን ያ ዓመት (የኛ 1950) የመመረቂያቸውም ዓመት የሚሆን ነበር።

በአውሮፕላን ነበር ወደ ደብረ ማርቆስ የሔድነው፤ እዚያ ስንደርስ አሁንም እንደ ፋሲካው ሰሞን ጉዞዬ ያስተናገደን፣ የልማት ባንክ ባልደረባና የሲሪስ ኩባንያ ኃላፊ፣ አቶ ብሥራት ጀማነህ (ስሙን እንዳላሳሳትኩ ተስፋ አለኝ) ነበር። በመጀመሪያ ጉዞዬ ተዋውቀን ስለነበር፣ አሁን ለረጅም ጊዜ እንደሚተዋወቁ ሰዎች ነበር የሆንነው። ስለ ሀገሩና ስለ ሕዝቡ ጠባይ ብዙ ነበር የነገረን። አስፋላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ አገዘን።

የጠቅላይ ግዛቱ ምክትል እንደራሴ ከነበሩት ከፊታውራሪ ሰብስቤ ሽብሩ ዘንድ ነበር መጀመሪያ የቀረብነው። ኪው ጋርደን በሚባል ድርጅት የበላይ

ተቆጣጣሪነት፣ በዚያ አካባቢ ከሚገኙ የተክልና ዕፅዋት ዐይነቶች አንዳንዶቹን ይዘው እንደሚሄዱ… ዝርዝር አድርጎ የቡድኑ መሪ ኮሊን ሊኪ አስረዳ፡፡ ፊታውራሪውም አንዳንድ ጥያቄ ጠይቀው መልስ ተሰጠ፡፡ እኔም የትርጁማንነት ሥራዬን በዚህ መልክ ጀመርኩ፡፡

ከዚያ፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር እየተመካከሩ ወሰኑ - ከደብረ ማርቆስ ሁለት ፖሊሶች ለጥበቃ ተመድበው ከእኛ ጋር አብረው እንደሚሄዱ፣ በየምናርፍበት አቅራቢያ ከሚገኙ ፖሊሶች ሁለት ተጨማሪዎች እንደሚመደቡና፣ ማታ ማታ የአካባቢው ነጭ ለባሾች ከድንኳናችን ሰፈር እንደሚያድሩ ተነገረን፡፡

ፊታውራሪን ተሰናብተን ከቢሮአቸው እንደወጣን፣ ሁለት ሰዎች (የነበሩ ይመስለኛል) ወደኛ መጡና፣ «ተሰናብታችሁ ትሔዳላችሁ›› እያሉ በመቀባበል ተናገሩ፡፡ ይህንኑ ለነኮሊን ነገሪኳቸውና ወደሚወስዱን ቢሮ ሰዎቹን ተከተልናቸው፡፡ እንደገባን የእጅ ሰላምታ ከሰጡን በኋላ፣ ከሰባታችን በቀጥታ ማናገር የሚችሉት እኔኑ ስለሆነ ወደኔ እያዩ፣ ‹‹ምን ለመሥራት ነው የመጡት? ምንድር ነው የሚያጠኑት?›› ብለው ጠየቁኝ፡፡

እኔም ለሳቸው ትርጉም የሚሰጥ በመሰለኝ መንገድ ተናገርኩ፤ ‹‹ዋናው ትኩረታቸው በዚህ አካባቢ በዱር የሚገኙ ዕፀዋትን ለመመርመርና ሌላ ቦታ ከማይገኙት መካከል አንዳንድ ለዐይነት ለመውሰድ ነው›› ስል፣

‹‹ወስደው ምን ሊያደርጉት?›› አሉ ቀበል አድርገው፡፡

‹‹ለጥናት እንዲሆናቸው ነው፡፡ ለሰብል ጠር የሆነና ያልሆነውን ዓይነት አጥንተው ይለዩታል፡፡ ከነርሱ መካከል ይኸ አጭር ቀጭኑ ደግሞ ቢልሀርዝያ የሚባል በሽታ የሚያመጣው ቀንድ አውጣ በኩሬዎች ውስጥ መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ነው›› አልኩኝ፡፡ ከዚያ፣ ብዙም ሌላ ነገር ለማለት ወይም ለመጠየቅ የፈለጉ አልመሰለኝም፣ ተሰናብተን ወጣን፡፡

ከደብረ ማርቆስ ዕቃችንን በአህያ አስጭነን ወደ ጮቄ ተራራ አግጣጫ፣ መሊት ማርያም ወደምትገኝበት አካባቢ ወደ ስናን ወረዳ ነበር የመጀመሪያው እንቅስቃሴያችን፡፡ ስንደርስ ድንኳኖቻችንን ከፍ እና ጠፈፍ ያለ ቦታ ተካክለን ሰፈራችንን አበጀን፡፡ አንድ ትልቅ እና አንድ መለስ ያለ ሁለት ድንኳኖች ነበሩ፡፡ ትልቁ ውስጥ ሰባታችን እንተኛለን፤ ስንቅና ኮተታችንም እዚያው ውስጥ ነበር የሚቀመጠው፡፡ ሁለተኛው ለተከተሉን ፖሊሶች እና ከየአካባቢው ለሚጨመሩላቸው ሌሎች ፖሊሶች አገልግሎት የተመደበ ነበር፡፡

ከዚያ፣ በየለቱ ጧት ጧት እየተነሳን፣ በዚያ አካባቢ የሚኙትን ዕፀዋት ለመቃኘት፣ ከሠፈራችን በስድስቱም አግጣጫ እስከ የውሎ ገባ እርቀት ድረስ በእግር ጉዞ ማድረጉን ተያያዝነው፡፡ የተመረጡት ባለ አበባ ሆነ አበባየለሽ ዕፀዋት ደግሞ፣ በጥንቃቄ በልዩ ወፍራም ወረቀቶች መካከል እየተደረጉ ተጣብቀው (ሞንታጅ እየተደረጉ) እሽግ መስለው ይዘጋጁ ነበር፡፡ በዚህ መልክ ነበር እንግልጣር (እንግሊዝ) የገቡትም፡፡

ወደ ሁለት ሳምንት ግድም በዚህ መልክ ስናን ወረዳ ውስጥ ቆይተን፣ ድንኳኖቻችንን ነቅለን ወደ ጮቄ ተራራ አመራን። ተዳፋቱን ለመያያዝ ስንቃረብ፣ የሞላ ጅረት ጠበቀን። የሁለት ተዳፋት መሬቶች መገናኛ (መጋጠሚያ) ላይ ሆኖ፣ ወደ ታች እራቅ፣ ግን ጠበብ ያለ ወንዝ ነበረና ሁለቱ ግንገኖቹ በጣም የተራራቁ አልነበሩም። በመሆኑም ጊዜያዊ ድልድይ ሰርተን ተሻገርን። ጊዜያዊው ድልድይ ለአካባቢው ኑዋሪ መሸጋገሪያነት ቢያንስ ክረምቱ እስኪወጣ ሊያገለግል የሚችል ዓይነት ነበር። ደግሞም፣ የተጋደሙት ግንዶች ከዚያው የተገኙ ስለነበሩ ተገቢም ነው።

አቀበቱን እንደተያያዝነው፣ አፋቸውን ከፍተው ቀሩ። ለሁሉም ነገር አቃቂር አውጪ የነበረው ጆን ሊትጎ እንኳ በመደመም፣ ‹‹ለብሔራዊ አገልግሎት የእንግሊዝ ጦር አባል ሆኜ ከ24 ያላነሱ አገሮች አይቻለሁ። እንደዚህ ውብ አካባቢ ግን በሕይወቴ አይቼ አላውቅም›› አለ። ቆጨው መሰለኝ፣ ትንሽ ቆይቶ ‹‹ምን ያረጋል፤ ተፈጥሮ ይኸን መሰል ውብ መሬትና ወፍራም አፈር ሰጥታቸው ምንም ሳያረጉ በድህነት ይኖራሉ›› ሲል አከለበት። ለዚህ መልስ አልነበረኝምና ዝም አልኩኝ፤ አብዛኛውን ጊዜ በነገር እንያያዝ ነበር። ይኸኛው ግን የሚስተባበል አልነበረም።

ተራራው ሠንሠለት አናት ላይ ወጥተን ሠፈራችንን አመቻቸን። ብሩህ አየር ነበር። አጋሚዶ አገር እንደገባን ነበር የተቆጠረው። ምንም እንኳን እኔ ስለዚህ ጉዳይ የማወራው ከነርሱ ጋር ሳይሆን ከፖሊሶቹ ጋር ብቻ የነበረ ቢሆንም፣ እነርሱ አዲስ አበባ ሁሉ ነገር ተገልጾላቸው (ብሪፍድ ሆነው) እንደመጡ በኋላ ተገንዝቤያለሁ። ፖሊሶቹ ባገኙት መረጃ መሠረት የአጋሚዶዎቹ ቦታ እራቅ ያለ እና ወደ ሞጣ በኩል እንደ ሆነ፣ ሁለተኛ መንግስት አውቆት (ፖሊስ በመመደቡ) የመጡ በመሆኑ ለመተናኮል እንደማይፈልጉ፣ እና ሦስተኛ ለመተናኮል ቢፈልጉ እንኳ አሰልለውና ሰልለው ስለሚሆን፣ ለጊዜው ፍፁም ሰላም እንደሚሆን ነበር የተረዳሁት።

የሰፈርነው አራት መከራርር በሚባሉት፣ የጮቄ ተራራ አራት የተቀራረቡ የአናት ጉብታዎች (ጫፎች ወይም ራሶች) አቅራቢያ ስለሆነ፣ እነርሱ ላይ መውጣት ተቀዳሚው ተግባር ሆነ። በማግስቱ ጠዋት ይኸንኑ ለማድረግ ተነሳን። ከሁሉ አስቀድሞ ስም ተሠጣቸው፤ ማቲዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ ተባሉ።

ዮሐንስ በአንድ በኩል አገሬው ላዩ እየወጣ አርሶ ይዘራበታል — ገብስ። ስለዚህ፣ እርሱን መውጣት ቀላል ተደርጎ ስለታየ፣ በማቲዎስ እንጀምር ተባለ። በጣም አስቸጋሪ ነበር፤ ሌሎች ሁለቱ እንደዚህ ከበድ ያለ ጥረት የጠየቁን ነበሩ። በላያቸው የተገኙ ዕፅዋት በአንፃራዊ ደረጃ ብርቅ ተደርገው የተቆጠሩ ነበሩ፤ ከታወቀና ካርታ ላይ ከተመለከተ ቦታ ላይ በቅለው ስለተገኙ መሰለኝ።

ለአንድ ወር ያህል እዚያ ቆየን፤ እንደተለመደው በየአግጣጫው እየዞርን ዕፅዋት ስንሰበስብ እየዋልን። ዐልፎ ዐልፎ ግማሽ ቀን (በተለይ ከቀትር በኋላ) በሰፈር

እንውላለን፡፡ ለእረፍት ብቻ ሳይሆን አካባቢውን ጉም ያለብሰዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድፍን አድርጎ ማየት ከማይቻልበት ደረጃ ይደርሳል፡፡

አንድ ጊዜ እንደዚህ ዐይነት ችግር ውስጥ ገብቼ ነበር፡፡ ከድንኳኖቹ ብዙም አልራቅሁ ነበር፤ ከወደምስራቅ በኩል ተረተሩን ወረድ ብያለሁ፤ ጀምበር አዘቅዝቃለች፤ እኔ ከወደጥላው ወገን ነኝ፤ ድንገት ከየት መጣ ሳይባል ጉሙ ጀቦነኝ፣ ተነስቼ ቆሜ አካባቢዬን ለመማተር ብሞክር፣ አንድ ሜትር የሚሆን ድረስ ነበር መለየት የምችለው በጉሙ ውስጥ፡፡ ማዳመጥ ጀመርኩ፤ ቀደም ሲል ልብ ያላልኩት የፏፏቴ መሰል ድምፅ ከርቀት (ከታች በኩል) ተሰማኝ፡፡ ተምጫ የሚባው ትልቅ ወንዝ የሚመነጨው ከዚህ አካባቢ መሆኑን አይቻለሁ፤ ዐውቃለሁ፡፡ ስለዚህ፤ እሱን ወደ ቀኝ አድርጌ ፊቴን ስመልስ ወደ ድንኳኖቹ አግጣጫ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከቆምኩበት ቀጥታ ትይዩ ቦታ ላይ አልነበረምና ቀጥ ብዬ ብሔድ ሳልፈው እችላለሁ! ሆኖም ከፍ እያልኩ፣ በግምት ወደ ቀኝ እያደላሁ ስሔድ፣ ጉሙም ሳሳ እያለ ሔደ፡፡ ከዚያ ድምፅ ከበስተግራዬ ተሰማኝና ወደዚያ እያደላሁ መሔድ ጀመርኩ፡፡ ጉሙ ይበልጥ እየሳሳ ሔደ፣ ከ10 እስከ 15 ሜትር በጉሙ ውስጥ ማየት ይቻል ነበር፡፡ ድምፅ ባልሰማ ኖሮ ድንኳኑን በ10 ሜትር ወደ ግራ ትቼው ሳልፍ ነበር!

ሰፈር ከምንውልባቸው ግማሽ ቀኖች አንዱ፣ ‹‹የፖስታ ቀን›› ነበር፡፡ ከእንግሊዝ አገር ደብዳቤ ለባለደረቦቼ ሲላክ፣ መጀመሪያ እንግሊዝ ኤምባሲ ይደርሳል፤ ከዚያ ወደ ደብረ ማርቆስ ይላክና፣ ከማርቆስ ‹‹ፖስተኛ›› በየዐረፍንበት ይዞ ይመጣል፡፡ ሲመለስ ከኛ ደብዳቤ ይዞ ይሔዳል፡፡ ይኽ የመልዕክት ልውውጥ ያለአንዳች ሳንካ ሲከናወን ነበር፡፡

በዚህ መካከል፣ አንድ ጊዜ ሰኝን የሚባለውን አንድ ታላቅ ሳምንታዊ የሰኞ ገበያ ለማየት፣ ከጮቄ ወደታች በደብረ ማርቆስ አኳያ ወረድን፡፡ እውነትም እንደዝናው ትልቅ ነበር፡፡ የቁም ከብት ጭምር ሲገዛ እና ሲሸጥ አጋጥሞናል፡፡

እዚያ ገበያ ቦታ አንድ አስገራሚ ገጠመኝ ተከስቶ ነበር፡፡ የተወሰኑ ያገሬው ገበያተኞች ቀረቡኝና፣ ‹‹ዐረቂ-ዳግም ብንጋብዛቸው ነውር ይሆናል ወይ?›› አሉኝ፡፡ ‹‹እንግዳ መጋበዝ ምን ነውር አለው፤ እርግጥ፤ የማያውቁትን የሰው አገር የበሰለ ምግብና መጠጥ እንዳይደፍሩ መስማማታቸውን ሰምቼ ነበር፡፡ ለማንኛውም ልጠይቃቸው›› ብዬ መለስኩላቸው፡፡ ወዲያው በስጋት፣ ‹‹የዚህ አገር ዳግም የሚሰራው ከግብጦ ነው፤ ላለመዱት ኃይለኛ ነው ይላሉ›› አለኝ አንዱ፡፡ ስለግብዣውና ስለዳግሙ ነገርኳቸውና፣ ሊሞክሩት እንደሚችሉ ጠቆምኩ፡፡ እንደተለመደው ጆን ሊትኮ፣ ‹‹እንግሊዝ ከሚጠመቀው ጠንካራ የአልኮል መጠጥ የሚጠነክር ይኖራል ሊሉ ነው፤ ጎርደን ጂንን አላዩ›› አለ፡፡ ጣሊያኖች፣ አንዴ ቤንዚን ቢያጡ ከማርቆስ እስከ ደምበጫ በሱ መኪናቸውን ነድተውበታል፣ የሚለውን አፈ ታሪክ ተረክሁና፣ ይህ ማለት እንኳን የሰው ጭንቅላት የመኪና ሞተር ያዞራል ማለት እንደሚመስለኝ ተናገርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎቹ እየተቀባበሉ ነገሩን አናናቁት፡፡ ለጋባዦቹ ያሉትን ነገርኳቸው፡፡

ከዚያ ጆሮ በሌለው ስኒ እየተቀዳ ዳግሙ ታደላቸው። እኔ ያኔ አልኮል ቀምሼ ስለማላውቅ ታለፍኩ። ኢያን ስኒውን እንዳጋባ፣ ፊቱ ደም መሰለና ላብ አሰመጠው። ሁላችንም ተደናገጥን። ከዚያ ውሃ ውሃ ሆነ! የሚጠጣውም፣ ፊቱን የሚታጠብበትንም። የተቀሩት ድርሻቸውን ቢጨርሱም ለመድገም ግን የደፈረ አልነበረም። ድንጋጤው ካለፈ በኋላ፣ ከፈረንጁ አገር ኃይለኛ መጠጥ የግብጦ ዳግም መብለጡን በማስመስከራቸው፣ ገጠሬዎቹም ፈገግ ማለታቸው አልቀረም።

ድንኳን ውስጥ ስንሆን፣ በተለይ ማታ ማታ ስለብዙ ጉዳዮች እንጠያየቅ፣ እናወጋ እና እንከራከር ነበር። አቋሞቻችን መነሻችንን የሚያንፀባርቁ ነበሩ። እነሱ ሳንይንስና ቴክኖሎጂን ሲያነግሱ፣ ሃይማኖትን ያራክሡ ነበር። በእግዚአብሔር አናምንም ባዮችም ነበሩባቸው። እኔ ደግሞ የምጠይቃቸው፣ ‹‹ከጥንት እስከ ዛሬ የሰው ዘር ሕብረተሰቦች ሁሉ ለምን ሃይማኖት ነበራቸው? ዛሬም አላቸው! ሁለተኛ ሳይንስ መልስ ያላገኘላቸው አያሌ ነገሮች ስላሉ ሳይንስ እነርሱ እንደሚያስመስሉት ፍፁም አይደለም። ከዚህም በላይ የሚያለማውን ያህል አጥፊም ነው። ሄሮሽማንና ናጋሳኪን አስታውሱ›› ስል፣ ለመጨረሻው አባባሌ፣ ‹‹ጥፋቱ የሳይንቲስቱ ሳይሆን፣ የተጠቃሚውና የሰው ልጅ እኩይነት ነው›› ይላሉ። እኔም ፈጥኜ፣ ‹‹የሰው ልጅን የእኩይነት ዝንባሌ ማጥፋት ባይቻል እንኳን ማለዘቢያው፣ መቆጣጠሪያው ምንድርነው? ሃይማኖትና ሞራል አይደለምን?›› እንደሚታወቀው በእንደዚህ ዐይነቱ ክርክር አሸናፊም ተሸናፊም አይኖርም። እነርሱ የሳይንቲስቱን አቋም፣ እኔ ለሁለት ዓመት ዶክተር ሰምነር (የፍልስፍና መምህራችን) ሲግተን በነበረው ቶሚስቲክ ፍልስፍና የገባኝን ያህል እየታገዝኩ 6 ለ 1 የሆነ ክርክሬን በየአጋጣሚውና በየርእሰ ጉዳዩ ሳጧጡፍ ከረምኩ። የሚገርመው ነገር፣ እነዚህ ግልጽ እና እንደልብ ክርክሮች (አንዳንዴ መጯጯህ እና ኃይለ ቃልም የሚታከልባቸው) ይበልጥ እያቀራረቡን ሔዱ።

ይሁንና፣ የፍልሰታ ጾም መጣች። በምግብ ከእነሱ ተለየሁ። እስከዚያ ወቅት ድረስ፣ እነርሱ ከእንግሊዝ አገር ጭነው ያመጧቸውን የታሸጉ፣ እጅግ በርካታ ዐይነት ምግቦች እና በአካባቢው የምናገኘውን ዶሮ እና ዕንቁላል አብሬአቸው ስመገብ ነበረ- ከአሳማ ሥጋ ነክ ከሆኑ ነገሮች በስተቀር። አሁን ሁሉንም እርግፍ አድርጌ ተውኩ።

ፖሊሶቹና አገሬው ለካ ሲታዘበኝና ሲያማኝ ኖሯል። የአዲስ አበባ ሰው ሃይማኖት የለውም እያለ! ደግሞም፣ አንገቴ ላይ የታሰረ ምንም ክር አልነበረምና፣ ለተመልካች ለካ ይህም በራሱ ምስክር ኖሯል። እንጀራና ሽሮ ወጥ ከአካባቢው ካሉ ቤተሰቦች ይጎርፍ ጀመር። በቶሎ ማስቆም ነበረብኝ። ፖሊሶቹ እያገዙኝም የሚያልቅ አልነበረም።

‹‹እንጀራና ወጡ ቀርቶ፣ ቆሎ ቢሆንልኝ ብሏል›› ሲባል ጊዜማ ደግሞ፣ በስልቻ ይመጣ ጀመር! ከዚያ ድንችም እንደዚሁ። የመጣው እስኪያልቅ ሁለቱም

ዓይነት እንዲቆም ለማድረግ ትግል ነበር፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ለጋሽ የራሱን እንጂ ሌላው ምን አደረገ አይልም ነበርና ነው፡፡

ጉድ ተባለ!‹‹እኛ ማተብ የለውም እያልን ስናማ፣ እሱ ፍልሰታን በቆሎ ጿሚ ነው ለካ!›› ተባለልኝና ቁጭ፡፡ በጣም ነበር የደነቀኝ፣ ልቤም የተነካው፡፡ ወዳጆቼም በተለይ ከድንቹ ባያሌው ደረሳቸው፡፡ ቅቅሉ፣ጥብሱ በአትክልት ዘይት፡፡

በአንዱ ቀን ወሬያችን መካከል፣ በአሜሪካ እና በእንግሊዝ አገር ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች የኔ ምርጫዎች አራት አራት መሆናቸውን ነገርኩዋቸውና፣ ከአሜሪካ ምርጫዎቼ፣ ሃርቫርድ፤ ፕሪንስተን፤ ዬል እና ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲዎች ናቸው››አልኩዋቸውና ቆም አልኩ፡፡ እንደጠበቅሁት፣ ‹‹ከታላቁዋ ብሪታኒያስ?›› አሉኝ አንድ ሦስቱ፡፡

‹‹ኦክስፎርድ፤ኬምብሪጅ፣ ኤዲንበራና ለንደን ዩኒቨርሲቲዎች፡፡››

‹‹ታዲያ ለምን ኬምብሪጅን አትሞክርም?›› አለኝ ኮሊን ሊኪ፣ የቡድን መሪው፡፡ ‹‹እንዲያውም ለምን ኪንግስማን አትሆንም?›› አለኝና የራሱ ስለሆነው ኮሌጅ (ኪንግስ) የሙገሳ ቃላት ደረደረልኝ፡፡

ጆን ፍሌንሊ፣‹‹እርግጥ እንደ ኪንግስ ዕውቅ ቻፕል አይኑረው እንጂ በሌላው ነገር ክሌር ይሻላል›› አለ ፈገግ ብሎ፤ ኢየንም የራሱን ኮሌጅ፣‹‹ሞድሊን››ን መረጠልኝ፡፡ እንደዚህ ሲባባሉ፣ እኔ ልቤ በደስታ ውስጥ ውስጡን ቢፈነድቅም፣ ‹‹ገና ለዚያ መብቃቴ አሁን የሚታወቅ ስላልሆነ፣ ስለምርጫው ብዙ ማለቱ ያለ ጊዜው ይሆንብኛል›› ብዬ ወደ ሌላ ወግ ብንዛወርም፣ የኬምብሪጅ ነገር በልቤ ተተከለ፡፡

ከጮቄ ከመልቀቃችን ቀደም ብሎ እኔ፣ ጆን ሊትጎና ‹‹አጭሩ ቀጭኑ››በቡድኑ ውስጥ ብቸኛው አይሪሽ ‹‹ሐኪማችን›› (ስሙ ተዘነጋኝ) ወደ ኮባሊት ለመውረድ ተነሣን[12]፡፡ ረዘም ያለ ጉዞ ነበር፡፡ ወደ ሰፈራችን የምንመለሰው ከሦስት ቀናት በኋላ ነበር፡፡ ‹‹አጭሩ›› ከመንገድ ካንዱ ፖሊስ ጋር ሲመለስ፣ ሁለታችን ከሌላው ጋር ቀጥለን ኮባሊት ደረስን፡፡ ጉዞው ቀላል አልነበረም፡፡ ዝናብና የጅረቶች ሙላት በተለይ አውኮን ነበር፡፡

የኤትኖሎጂካል ሶሳይቲ አባላትን ባለፈው ጉዞ አስተናግደውን እነበሩት፤ እቀኛዝማች ካሴ እምሩ ቤት ሰተት ብለን ሔድን፡፡ ዕድለኛ ሆነን፣ ከደብረ ማርቆስ ገና ተመልሰው እቤት ደርሰው አገኘናቸው፡፡ ገና ሲያዩኝ በሩቁ ዐወቁኝ፡፡ጢሜ ግን ከዚያን ጊዜው የበለጠ በጣም ረዝሞ ነበር፡፡

‹‹ጮቄ ላይ ብዙ ፈረንጆች ድንኩዋን ተክለው፣ አካባቢውን ሲያስሱ ይውላሉ፤ አንድ የኛ ሰውም አብሮአቸው አለ›› ሲሉ ሰምቼ፣ ‹‹አዩ ያ አበሻ የተባለው

[12] የአየር ላንድ ተወላጅ ማለት ነው፡፡

ፊታውራሪ (እኔን ማለታቸው ነው) ቢሆን ኖሮ ምንም ቢሆን እዚች ሳይደርስ አይቀርም ነበር ስል ነበር።ይኸዋ እንዳልኩትም መጣህ›› አሉኝ፣ ከተሳሳምን በኋላ።

ጆን ሊትጎን አስተዋወቅሁዋቸው። ሰላምታ ሰጡት። አገሩ ወዴት እንደሁ ጠየቁት፤ ድንቅ አገር መሆኑን ነገሩቸው። ከዚያ ከኔ ጋር ወጋቸውን እንደ ቀጠሉ ራት መቅረቢያው ደረሰ።

ለጆን ሊትጎ ገበታ ለብቻው ተደረገለት። ከራት በኋላ፣ ያቀረበቺው ልጅ ጆን የበላበትን ዕቃ በጨርቅ ይዛ አነሣችና ለይታ አስቀመጠችው። ይህን ስታደርግ፣ ምንም እንግዳ ነገር የምታደርግ መስሎ አልታያትም። ምናልባት ከእኔና ከጆን በስተቀር ነገሩን ልብ ያለው ያለ አልመሰለኝም። (ጠበል ሳይረጭበት የማይበላበት መሆኑ ተነገረኝ ኋላ።)

በቀደመው ጉዞዋችን ጊዜ፣ ስለመጀመሪያው የፓርላማ ምርጫ (በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መሠረት) አልወዳደርም ብለው እንዲወዳደሩ አግባብቻቸው ነበር። አልተበገሩም ነበር። አሁን እንደቆጫቸው ነገሩኝ።

በማግስቱ ማለዳ ራቅ ያለ የሚሔዱበት የማይቀሩበት ጉዳይ ስለነበራቸው፣ሰንበትበት ብለን እንድንሔድ ሊያግባቡን ሞከሩ።ይኽን ሁለታችን የምንወስነው እንዳልሆነና፣ አለቃችን በሦስተኛው ቀን ሰፈር እንደሚጠብቀን ነገርኩዋቸው እና በጣም አዘኑ። ቢሆንም፣ በማግስቱም እዚያው ውለን እንደምናድር ነገርኩዋቸውና በመጠኑም ቢሆን ተጽናኑ። ጆን በአካባቢው የነበሩትን ዕፅዋት ሲመረመር፣ሲመዘግብና ሲለጥፍ ዋለ።

ቀኛዝማችም ከቀትር በኋላ መጥተው ስለነበር ብዙ አወጋን። ልቤን የነካኝ ነገር፣ በማግስቱ ጠዋት ሲሸኙኝ ያሉኝ ነገር ነበር። ‹‹ሰው የሚገጥመው ነገር አይታወቅም። ድንገት ባንድ ምክንያት የሰው ነፍስ በጅህ ቢያልፍ፣ ምንም ሳታመነታ፣ ብር ብለህ ወደዚህ ና፤ ማንም አያገኝህ›› ያሉኝ ነበር።ደግመን ሳንገናኝ ዐረፉ። ማረፋቸውን እንኳ የሰማሁት ብዙ ቆይቶ መሆኑ ሲቆጨኝ ይኖራል።

ከጮቄ ተነስተን፣ ደብረ ማርቆስን ወደ ጎን ትተን፣ ጉዞአችንን ወደ ታች ወደ ጥላትግን እና አነደድ ወደ ሚባሉት ወረዳዎች አደረግን። በዚህ ወቅት፣ ያ ቅዳሚን ገበያ ላይ፣ በሚስተር ሆይናስኪ ላይ ችግር ፈጥሮብን የነበረው የጎበዝ አለቃ አጅቦ ወስዶ፣ በአባይ ሸለቆ አካባቢ ለተለመደው የጎበዝ አለቃ እንዲያስረክበን ታዞ ኖሮ፣ ከነጭፍሮቹ መጥቶ ነበር።

አንድ በጣም ወደታች ርቆ ወደ አባይ በሚወርድ ወንዝ አጠገብ፣ ለድንኳን መትከያ አመቺ ስለነበረ እንግሊዞቹ ሰፈራችንን እዚያ ለማድረግ ሲጣደፉ፣ ከፖሊሶቹ አንዱ መጣና፣ ‹‹ይኸ ቦታ አይሆንም›› ብሎ ሹክ ይለኛል። ‹‹ለምን›› አልኩት። ‹‹ይህ ቦታ ቀድሞ ራስ ኃይሉ ሰይጣን ለመጎተት ሲመጡ

የሚያርፉበት ነው ይላሉ›› አለኝ፡፡ ‹‹ይኸን ምክንያት ልንሰጣቸው አንችልም›› አልኩትና ቅር እያለው ዝም አለ፡፡

ሌሊት ተኝተን ኃይለኛ አውሎ ንፋስ ተነሳ፡፡ ድንኳኖቹን ነቅሎ እንዳይወስድብን ብዙ ታገልን፡፡ ቆይቶ ንፋሱ ሳላንዳች አደጋ አለፈ፡፡ ማንም ምንም አይበል እንጂ፣ ፖሊሱ ያለውን በወቅቱ ሳናስበው አልቀረንም ነበር፣ ብዬ አስባለሁ፡፡ ያገሬው ሰዎች ግን፣ ምክንያቱ ምን እንደሆነ በርግጠኝነት አውቀዋል!

‹‹ዋናውን ይዘውታል›› ተባለ፡፡ ይህን ወሬ ስሰማ ድንኳናችን ለምን ጎብኚ እንደበዛበት ገባኝ፡፡ እንዲያውም አንዱ፣ ‹‹በዓይኔ በብረቱ አይቸዋለሁ፡፡ አንድ ቀንዱ ተሰብሯል፤ መላጣ ነው፡፡ ምን መስጠህ ብለው ቢጠይቁት (እንግሊዞቹን ማለታቸው ነው)፣ ከእነገሌ አውድማ ጤፍ ሳግዝ ነው አላቸው አሉ›› ብሎ ተናገረ፣ ተባለ፡፡

ይኽን ሁሉ ወሬ ጓደኞቼ አልሰሙም ነበር፤ ታች አባይ ወንዝ ደርሰን ከተመለስን በኋላ ወደ ደብረ ማርቆስ ተመለስን፡፡ ጻጉሜ ተጀምራለች፡፡ ደብረ ማርቆስ ላይ፣ ፊራውራሪ ሰብስቤ ራት ጋብዘው ሸኙን፡፡

አዲስ አበባ ስንደርስ የእንግሊዝ ኤምባሲ ግብዣ አደረግልን፡፡ ሁላችንም ጢማችንን አሳድገን ነበር፡፡ የኔ ወሬ ተነሳ፤ በቆሎ 15 ቀን ጾመ ተብሎ ተጽፎላቸው ኖሯል! ተሰግቶ የነበረው፣ እስከ ስድስት ጦሙን እየዋለ ከዚያ ቆሎ ብቻ በልቶ እያደረ እንዴት ይሆናል? ይታመማል፤ በጉዞ ይደክማል፣ እየተባለ ኖሯል፡፡ ይኽን ጎጃም ሳለን አልሰማሁም ነበርና፣ እዚህ በሌሎች መታወቄን አላውቅም ነበር! ለወሬ የሚበቃም ነገር አልመሰለኝም ነበር፡፡

ከዚያ፣ በዶክተር ማት አማካይነት፣ ጃንሆይ ዘንድ ቀረብን፡፡ ከመካከላችን አንደኛው አመመውና ቀረ፡፡ ስድስቶቻችን ጢሞቻችንን አንዝርገን ቀረብን፡፡ ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ነበሩ አቅራቢያችን፡፡ ፈረንጆቹን አስቀድሜ እኔ ወደኋላ ቀረት ብዬ ነበር፡፡ ጃንሆይ እነርሱን ጨብጠው እንደጨረሱ ለእኔም እጃቸውን ዘረጉልኝ፤ አመነታሁ፡፡ ጸሐፊ ትእዛዝ ‹‹ጨብጣቸው እንጂ›› ሲሉኝ በሹክሹክታ፣ በትክክል የሰማሁዋቸው መሆኔን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ብቻ ደመ ነፍሴን፣ ቀኝ እጄን በግራዬ ያዝኩና በቀኝ እጄ ጨበጥኳቸው፡፡

ኮሊን ሊኪ ስለጉዞአችን ነገራቸው፡፡ የገረመኝ ‹‹ጸጥታው አስተማማኝ አይደለም፤ ወደዚያ መሔድ አደገኛ ነው›› ተብለን ነበር፡፡ ‹‹ነገር ግን እኛ ተግባራችን በእግር መጓዝን የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ከጮቄ ተራራ እስከ አባይ ወንዝ ድረስ ለሁለት ወር ያህል ተጉዘናል፡፡ አንዳችም ችግር አልገጠመንም፤ በደረስንበት ሁሉ ሰዉ ሰላማዊና በወዳጅነት መንፈስ ነው የተመለከተን›› እያለ መናገሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ስለዚህ ነገር ማወቃቸውን የሚያመለክት ነገር አላየሁባቸውም ነበርና ነው፡፡

ጃንሆይም፣ ‹‹ዐልፎ ዐልፎ አንዳንድ ወስላታ ባይጠፋም ብዙ ችግር የለውም›› አሉ፡፡

እዚህ ላይ፣ ‹‹መታሰቢያ ነገር ብንሰጣቸውስ›› ብለው ጸሐፊ ትእዛዝን አማከሯቸው፤ እኛኛውም ‹‹ማለፊያ ነው›› አሉና፣ ስለ ወርቅ ሜዳልያዎች ተነጋገሩ፤ መካካለኛው ዐይነት እንዲመጣ አዘዙ፡፡

ጸሐፊ ትእዛዝ ይዘው እስኪመጡ፣ ኮሊን ስላየው መሬት ለምነትና ውበት እያዳነቀ መናገር ጀመረ፡፡ በአማርኛ ከተናገሩት ማስተርጎም ሊኖርብኝ ነው፣ እያልኩ ሳሰላስል፣ ጃንሆይ፣ በፈረንሳይ ተናጋሪ ስልት በእንግሊዘኛ መለሱለት፡፡ ‹‹አዎን፣ አገራችን ብዙ ለምና ውብ ቦታዎች አሉዋት፡፡ እንደ ሐረር፣ እንደ ጂማ ያሉ ...›› ገና እንዳሉ ጸሐፊ ትእዛዙ ደረሱ፡፡

አምስት ብቻ ስለነበርን ይዘው የመጡት ለእንግዶቹ ተሰጡ፡፡ ‹‹የሱስ?›› ሲሏቸው መልስ አልነበራቸውም፡፡ ‹‹ይምጣለት›› አሉ፡፡ በሩጫ ዓይነት ሔደው አመጡና፣ ለኔም ተሰጠኝ፡፡ ለሌሎቹ የጅ ሰላምታ ሲሰጡ እኔ ፈንጠር ብዬ እጅ ነስቼ ወጣሁ፡፡

ከኮሊ ሊኪ ጋር፣ አዲስ አበባን ከመልቀቁ በፊት፣ ስለ ኬምብሪጅ እና ኪንግስ ኮሌጅ የደብዳቤ ግንኙነት ለማድረግ ተነጋግረን ተሰነባበትን፡፡

## ጉዞ ወደ ሕንድ

በዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ተማሪነት ዘመኔ የሆነ ሌላው ትልቅ ቁም ነገር፣ የሃይማኖተ አበው፣ የኮሌጅ ተማሪዎች ማኅበር መመሥረትና፣ እኔም ከመሥራች አባሎቹ አንዱ መሆኔ ነበረ፡፡

የቅርብ ጓደኞቻችን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ሲለውጡ የማየት ቁጭት ያጫረው ቢሆንም፣ የማኅበሩ ዋና ዓላማ ግን ስለሃይማኖታችን ከዘልማድ የላቀ ዕውቀት ለማግኘት የተደረገ ጥረት ነበር፡፡ ዐይነተኛው መንገድም፣ ዘመናዊው ከፍተኛ ትምህርት በአማኝ ልቦና ውስጥ የሚያጭራቸውን ልዩ ልዩ እምነት ነክ የሆኑ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል፣ ጠለቅ ያለ ተዋሕዶአዊ የሃይማኖት ትምህርት ማግኘት ነበር፡፡ ለዚህም ግብ አጋዥ እንዲሆኑን የሔድነው ወደ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ነበር፡፡ በጥያቄያችን ተደስተው፣ አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅ መደቡልን፡፡ መምህሩም ለምን ዓላማ እንደሚያስተምሩን ጠንቅቀው በማወቃቸውና፣ ትምህርቱን በዚያ መንፈስ በማቀናበራቸው፣ ከተማሪው ጋር መልካም መግባባት ፈጥረው ነበር፡፡ በዚህም ሳቢያ በአዲስ አበባ በሚገኙት ሁለት ሌሎች ኮሌጆች የነበሩ እምነተ ተዋሕዶ ተማሪዎችም ተቀላቀሉንና፣ ማኅበሩ ኮሌጆች አቀፍ ሆነ፡፡

ሆኖም በአትላንቲክ ውቅያኖስ ከሚገኙት ደሴቶች አንዷ ትውልደ አፍሪካ ነዋሪዎች፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት አስተማሪ እንድትልክላቸው በጠየቁት መሠረት፣ የእኛ መምህር ተመርጠው ተላኩብንና ሌላ አስተማሪ ተተኩልን፡፡ አዲሱ መምህር ከመጀመሪያው የተለየ የአቀራረብ ፈሊጥ ነበራቸው፡፡ ሲያስተምሩ ማዝናናትን ለማከል አስበው በሚያቀርቧቸው ምሳሌዎች፣ አብዛኛውን ተማሪ የሚያስከፉ ስለነበሩ፣ የኮሌጁ ወኪል ነበርኩና

ለብፁዕ አባታችን እንዲለውጡልን አቤት ማለት ተገደድሁ። አቡኑም በምትካቸው አማርኛ የሚችሉ እና በጃንሆይ ልዩ ጽሕፈት ቤት የትርጉም ሥራ የሚያግዙ፣ የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባል የሆኑ መነኩሴ መደቡልን። ፖል ቬርጌስ የሚባሉ ነበሩ። (እኝህን ካህን፣ እንግሊዝ አገር ተማሪ ሳለሁ፣ በቤተ ክርስቲያናቸው የጵጵስና ሢመት ተሰጥቷቸው አግኝቻቸዋለሁ።)

በዚህ ማኅበር አባልነቴም ሳቢያ፣ በሕንድ አገር፣ ኬሬላ በሚባለው ክፍለ አገር ለተመሳሳይ ዓላማ እንደኛው በከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች የተቋቋመ ማኅበር ነበር። የወርቅ ኢዮቤልዩ ክብረ በዓሉን በሚያዚያ 1950 ያከብር ነበርና ነው፣ የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ (ፓትርያርክ) በጃንሆይ በኩል ጥሪውን የላኩት። እኔ (የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የሃይማኖት አበው ወኪል ወይም ተጠሪ) እና የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ኮሌጅ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት፣ ዘውድነህ ይምታቱ፣ የኢትዮጵያ ልኡካን ሆነን ተላክን።

ይኽ ከኢትዮጵያ ውጭ የመጀመሪያው ጊዜ ጉዞዬ ነበር። ከአዲስ አበባ ወደ ድሬድዋ የተጓዝነው ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን ከጧቱ በ1 ሰዓት ነበር። የምንበረው በዕቃ መጫኛ አውሮፕላን ነው ሲባል ደስተኛ አልነበርኩም። ሆኖም፣ ስለ ጉዞው ያደረብኝ ደስታ እና የበረራው ጊዜ አየር ምቹነት ይህንን የመከፋት ስሜት በውስጤ አላቆየውም። በስምጥ ሸለቆ እና በዚያ ውስጥ በአዋሽ ጠመዝማዛ መስመር ትርኢትም በጣም ተደስቼ ነበር። ዝነኛው የድሬድዋ ሙቀት ወላፈን፣ በሁለት ሰዓት አካባቢም ቢሆን፣ ገረፍ ሳያደርግ አልተወኝም ነበር። ያ ደግሞ፣ ስለ ጅቡቲው ሙቀት ይበልጥ አስግቶኝ የነበረ ቢሆንም፣ እዚያ ስንደርስ ግን ፈጽሞ እንደፈራሁት አልነበረም። ወደቡ ግን አድናቆትን አላሳደረብኝም ነበር። ኤደንም ከሞላ ጎደል የፈጠረብኝ ስሜት ተመሳሳይ ነበር። ሦስት ቦታ የተበታተነ ነገር ሆነብኝ፡- ክሬተር ኤደን፣ ስቲመር ፖይንት እና ሼክ ወይም አራብ ታወን። ሁሉም የሚገናኙበት፣ ዋናው ማዕከል የመጀመሪያው መሰለኝ። ሁለተኛው፣ ሻል ያለና እንግሊዞቹ መኖሪያ አካባቢ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። ሦስተኛው፣ ከባህሩ እራቅ ያለና ወደ ውስጥ ገባ ያለ ነው። ያገሬው ሕዝብ ከተማ ነው።

ያኔ ካስደነቁኝና ትዝ ከሚሉኝ ነገሮች መካከል አንዱ፣ ብዙ ሱቆች የኢትዮጵያ ገንዘብ ይቀበሉ የነበረ መሆኑ ነበር። አማርኛ ጥቂት ከሚችሉ፣ አቀላጥፈው እስከሚያውቁ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ማግኘቴ፣ ሌላው ነበር። በክሬተር ኤደን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባሳረፈን ሆቴል (ኤል ጋዚራ) ውስጥ፣ በመስተዋት ውስጥ ተደርገው ያየሁዋቸው የመሪዎች ፎቶዎችም፣ ትዝ ይሉኛል። መጀመሪያ ንግስት ኤልሳቤጥ ዳግማዊት (የቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ)፣ ከዚያ ቀጥሎ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኔህሩ፣ የፓኪስታኑ ሞሐመድ አሊ ጂናህ፣ የየመኑ ኢማም፣ የግብፁ ገማል አብዱል ናስርና ናጊብ።

ከኤደን ማታውን ወደ ቦምቤ (ሙምባይ) በረርን። በማግሥቱ አምስት ሰዓት ላይ ሳንታ ክሩዝ አውሮፕላን ማረፊያ ቦምቤ ደረስን። ከአውሮፕላን ላይ

እንዳየሁትም እውነትም በጣም ትልቅ ከተማ ነው፡፡ በከተማው የምናውቀው ሰው ስላልነበረ፣ ማንንም አልተጠባበቅንም ነበርና፣ አንድ ሰው ‹‹ዳምጤ!›› ሲል ስሰማ ጆሮዬን አላመንኩም፡፡ ባለ ንግድ- ሥራ የሆነው፣ በቦምቤ (ሙምባይ) የኢትዮጵያ የክብር ቆንሲል፣ ሚስተር ኢስማኤል ካንጋ ነበር፡፡ በመኪና ይዞን የከተማውን፣ የመንግሥትና የንግድ ማዕከል አሳየንና ወደ ቢሮው ወሰደን፤ ውጪ የከተማው ሙቀት ቃጠሎ ነበር! ጥቂት ዐረፍ አልን እና ቮልጋ ከሚባል ሆቴል ወስዶ ምሳ ጋበዘን፡፡ አብሮት ሲማ ኢላላ የሚባል ኢትዮጵያዊ ተማሪም ነበር፣ ወደ ማታ አውሮፕላን ጣቢያ ሲያደርሰን፡፡ ታጅ ማሃል ከሚባለው ትልቅ ሆቴል በሕንድ አየር መንገድ ኪሳራ አድረን፣ በማግስቱ እንድንበር ቀደም ሲል ጠይቀውን ነበር፡፡ ጃንሆይ ያረፉበት እንደነበረም ነግረውን ነበር፣ ለማግባባት፡፡ እንቸኩላለን ብለን ነበርና ነው፣ እንደምንም ቦታ ያገኙልንና፣ ወደ ማድራስ (ዛሬ ቼናይ) የበረርነው፡፡

በማድራስ አጭር ቆይታ ጊዜ፣ እንደ ጀብድ የቆጠርኩት እንግዳ ተግባሬ አይረሳኝም፡፡ ይኸውም የከተማውን ካርታ ገዝቼ፣ በአውቶቢስ ከተማውን ለማየት መድፈሬ ነበር፡፡ ሁለት ሙሉ ቀኖች ነበር የዋልነው፡፡

ከአየኋቸው ነገሮች የማይረሱኝ ደግሞ፣ ማድራስ ማሪና ቢች (መዝናኛ የባሕር ዳርቻ) ርዝመት፣ ስፋትና ውበት ነው፡፡ ‹‹በመላው ዓለም ካሉ የባሕር ዳርቻዎች በውበቱ ሁለተኛው ነው››፣ ብሎኝ ነበር አንዱ የዚያ ከተማ ነዋሪ በእርግጠኝነት፡፡ (እንደአጋጣሚ ሆኖ ልክ ከዐሥር ዓመታት በኋላ፣ የሪዮ ዲ ጃኒሮን ኮባ ካባና ቢች ሳይ፣ የማድራሱ ፈጽሞ የማይደረስበት መስሎ ተሰምቶኛል፡፡ ሰውየው አንደኛ ያደረገው የሳን ፍራንሲስኮን ነበር፡፡)

ሁለተኛው፣ የማሀተማ ጋንዲ መታሰቢያ ነው፡፡ ከየትም የመጡ፣ የማንኛውም ሃይማኖት ተከታዮች፣ በማንኛውም ቋንቋ የሚጸልዩበት፣ ልዩ ቦታ ነው፡፡ ዙሪያውን በዐምዶች የተከበበ ሰፋ ያለ፣ ጣሪያ የለሽ ክብ ሥፍራ ሲሆን፣ ከዋና መግቢው ግራና ቀኝ የሁለት ዝሆኖች ቅርፃ ቅርፆች ቆመዋል፡፡ ውስጥ፣ ከሁሉም የትላልቆቹ የሃይማኖቶች ቅዱስ መጻሕፍት ጥቅሶች አሉ፤ ከጋንዲ ንግግሮችም ጥቅሶች ተከትበዋል፡፡

ከማድራስ በባቡር ወደ ኮቲየም ነበር የሔድነው፡፡ የፓትርያርኩም መኖሪያ እና የጉባኤው መካሔጃም ቦታ በኮቴም ነበር፡፡ ወደ መንበረ ፓትርያርኩ ሔደን ሳለ፣ የኛን መገኘት ምክንያት በማድረግ ፓትርያርኩ አንድ ቀን እራሳቸው ቀደሱ፡፡ ከዚያ፣ በቆይታም አነጋገሩን፡፡ ‹‹ዐፄ ኃይለ ሥላሴም በሕይወት ያሉ ብቸኛው ኦርቶዶክሳዊ ንጉሠ ነገሥት ስለሆኑ፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ሁሉ፣ በቅዳሴያቸው ጊዜ ሁሉ ይጸልዩላቸዋል፤ ሁሌም ያስቧቸዋል›› አሉን፡፡

በራሳቸው ቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር እንዳለም ሳይገልጹልን አላለፉም፡፡ ከሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነበር ፓትርያርክ ጥንት ይሾም የነበረው፡፡ እ.አ.አ በ1900 ነበር፣ እራሳቸውን ችለው ፓትርያርክ መምረጥ የጀመሩት፡፡

በዚህ ሳቢያ ክፍፍል ተፈጥሮ እንደነበርና፣ የዚያ ችግር ውርስ ጨርሶ እንዳልጠፋና አብሮአቸው እንዳለ ገለጹልን፡፡

> ይባስ ብሎ ደግሞ የሕንድ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በገንዘብ ኃይል አማኞቻችንን ወደራሳቸው እየሳቡብን ነው፡፡ በተለይ ብርቱ አስተማሪ የሆኑትን ቀሳውስትና ዲያቆናት፡፡ ፕሮቴስታንቶቹ ደግሞ ከሁለታችንም ወደራሳቸው ለመሳብ ብርቱ ዘመቻ ያደርጋሉ፡፡ እኛ የክርስቲያኑ ቁጥር ትንሽ ነው፤ ያንኑ ወደ እኔ ልውሰድ እኔ ልውሰድ እየተባባልን ከምንሻኮት ይልቅ፣ ክርስቲያን ያልሆኑትን እያስተማርን ወደየራሳችን እንሳብና እናድናቸው ብንላቸውም አልሰሙንም አይሰሙንም›› እያሉ በሐዘኔታ ተናገሩ፡፡

የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ እንደ ኢትዮጵያዊቱዋ ሁሉ፣ በ4ኛው ምዕተ ዓመት፣ በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የተመሠረተች ናት፡፡ በመሆኑም፣ እውነተኛዋ የሕንድ ቤተክርስቲያ ተደርጋ ነው የምትቆጠረው፡፡ የካቶሊክ ሃይማኖት እዚያ አገር መጀመሪያ የገባው በጎዋ በኩል፣ በፖርቱጋል ሚስዮናውያን በ16ኛው ክፍለ ዘመን ላይ፣ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኑዋ ምሥረታ አንድ ሺ ዓመት በኋላ ነው ይላሉ፡፡ ፕሮቴስታንቶች ደግሞ፣ የመጡት በ19ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ነበር፡፡ የዚያች ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ገጠመኝ፣ ከኛዋ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት እንዳላቸው ተገንዝቤአለሁ፡፡

ፓትርያርኩ (ካቶሊኮስ ነው የሚባሉት) ከነገሩን ሁለቱን ነገሮች ገና እዚያው ሳለን አረጋገጥኩኝ፡፡ የመጀመሪያው የካቶሊኮቹን ነገር የሚመለከት ነበር፡፡ አንድ ቄስ ይመጡና፣ ‹‹እባክህ፣ ይህን የጅ ሰዓት ስትሔድ ሽጥልኝ፡፡ አንተ መንገድህ ላይ ኤደን ልትገዛ ትችላለህ›› ይሉኝና፣ የደቀቀ ሰዓት ያሳዩኛል፡፡ በዚህ ሳቢያ ነበር ስለሽኩቻቸው በዝርዝር ያወጉኝ፡፡ በዚህ ሳቢያ በተነሣ አምባ ጓሮ ነው፣ እርሳቸው ተደብድበው ሰዓቱ የተሰባበረባቸው፡፡

ሌላው የዚህ ጉዞ ገጠመኝ ፣ በኬራላ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ፣ በትሪበቫንድረም፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ኔህሩን ንግግር ለማድመጥ ታዳሚ የመሆን ዕድል ማግኘቴ ነበር፡፡ ኔህሩ ከልጃቸው ከኢንዲራ ጋንዲ ጋር ነበር ከቦታው የደረሱት፡፡ እኛ የውጭ አገር ጋዜጠኞች ተብለን ፊትለፊት ነበር ቦታ የተሰጠን፡፡ ታዳሚው እጅግ በብዙ ዐሥር ሺዎች ስለነበረ የደረሰው፣ የንግግር ቦታው ከባህሩ አካባቢ ሜዳ ላይ ነበር፡፡

አስተዋዋቂያቸው ሚስተር ናፑዲሪፓድ የኬራላ ኮሚኒስት ፓርቲ መሪ ነበሩ፡፡ ኔህሩ በረጅሙ ንግግራቸው፣ የሕንድን ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር፣ መመሪያውን ከውጪ የሚቀበል ነው ብለው ሲወርፉ፣ የሕንድን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን ካገራዊ የሕንድ የሃይማኖት ተቋማት አንዱ መሆኑን ጠቆም አድርገው ነበር፡፡ ንግግሩ ረጅም የነበረ የመሆኑን ያህል በርካታ አካባቢያዊና ሀገራዊ ጉዳዮች፣ ዓለምአቀፉንም ሳይቀር፣ ያነሱበት ነበር፡፡

ያንለት ማታ፣ በሌላ አጋጣሚ ልጃቸውን ኢንድራን በቅርብ ለማየት ቻልኩ። የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ ተጋብዘን፣ ከፊት መደዳ ተቀምጠን ነበር። ሙዚቃው ከመጀመሩ አስቀድሞ አጭር ንግግር እንዲያደርጉ ተጋብዘው፣ ከኛው መደዳ ሲነሱ ነበር መኖራቸውን ያወቅኩት። በኔህሩ ንግግር ወቅት ከማማው ሥር ፊትለፊታችን ተቀምጠው አይቼያቸው ስለነበር፣ አይጠፉኝም ነበር። ነገር ግን፣ እዚያ ቦታ ይኖራሉ ብዬ ካለመጠርጠሬም ሌላ፣ ብዙ ወይዛዝርት ስለነበሩም መጀመሪያ ላይ ልብ ብዬ አልተመለከትሁም ነበር።

በ1950 ከኢትዮጵያ ውጭ ያደረኩት ያ የሕንድ አገር ጉዞ፣ ትምህርታዊና ዐይን ከፋች ነበር። ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተመለስኩ በኋላ ስለዚህ ጉዞ ንግግር አድርጌ ነበር።

## የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ማኅበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴ

በየወቅቱ የሚወጣ፣ የዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ የተማሪዎች እትም እንዲኖር ለማድረግ ብዙ ጥረት ነበር። ነገር ግን፣ ከመነሻው አንሥቶ ሊዘልቅ የቻለ አንድም አልነበረም። ተጀምሮ መክሰም የብዙዎቹ ሙከራዎች ዕጣ ነበር። ሆኖም ለየተወሰነ ጊዜም ቢሆን እየሔዱ የቆሙ ጥቂቶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ *ዩ ሲ ኮልስ፣ ካምፐስ ስታር፣ ኒውስ ኤንድ ቪውስ* የሚባሉት የሚጠቀሱ ናቸው። በተለይም የመጨረሻው፣ የተሻለ ተንቀሳቅሶ፣ ውጤት አሳይቶ ለታሪክ ቅርስ ትቶ አልፏል።

በዚህ ረገድ፣ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥሩ ሙከራ ያደርጉ እንደ ነበር ትዝ ይለኛል። የኮተቤው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ይመስለኛል፣ *ስፓርክ* የሚል፣ ጄኔራል ዊንጌት *ቺንዲት*፣ ተፈሪ መኮንን ደግሞ፣ *ኤንሳይን* የሚሉ የተማሪ ‹‹ትይብ የተባዙ ጽሑፎች›› ነበሩ። እነዚህን ‹‹ትይብ ጋዜጦች ወይም መጽሔቶች›› ሌሎቻችን (የውጭ ተማሪዎች) የምናገኛቸው ወወክማ ነበር። የሐረር መድኅኔ ዓለሙን ጭምር። ወወክማ የማይናቅ ስብስብ ያለው ቤተ መጻሕፍትም ነበረው። ክበባትም ነበሩት። የወጣቶች ምንጭ ክበብ የሚባለው፣ በሒደት የኮከበ ጽባሕ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪዎች ክበብ ለመሆን በቅቶ ነበር።

በ1949 (ሁለተኛ ዓመቴ መነሻ ላይ) ከነዚህ መካከል፣ የባህል ፕሬዝዳንት የነበረው አክሊሉ ለማ፣ *ዩ.ሲ. ኮልስ* (UC Calls) የሚለውን ከዜና ይልቅ አስተያየት የሚያስተናግድ ሳምንታዊ ወረቀት እንዳዘጋጅ ይጠይቀኛል። በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ፣ የተባዛው ወረቀት ከምግብ ቤቱ በማስታወቂያ መለጠፊያው ሥር በተመደበው ጠረጴዛ ላይ በምሳ ሰዓት እንዲደርስ ለማድረግ ቀላል ፈተና አልነበረም። ምክንያቱም ተማሪው ለዚህ ጉዳይ ጽሑፍ ለማቅረብ ብዙም ተነሣሽነት የሚያሳይ አልነበረም። በቀደመው ዓመት የመዝናኛ ኮሚቴ (Social Entertainment Committee) ጸሐፊ ሳለሁ፣ ለግጥም ውድድር ተሳታፊ ሲጠየቅ የተሻለ ተሳተፎ ይታይ ነበር። ለዚህኛው ሲሆን ግን፣ በእጅጉ የቀዘቀዘ ነበር። ሰበቦቹና ምክንያቶቹ የተለያዩ ነበሩ።

ከነዚህ ዋናው ጥናት አለብኝ ሲሆን፣ አንዱ አንዴ በማሾፍ እንዳለኝ፣ ‹‹ይኽ ኤክስትራ ተብሏል እኮ!›› የሚል ፈሊጥ ነበር፡፡ በተለይ 3ኛ እና 4ኛ የደረሱት ከኮሌጁ ጓላ ስላለው ወደማሰብ ያዘነብሉ ነበር፡፡

ጥቂቶች ሴንሲቲቭ፣ ማለትም በተማሪው መካከል አላስፈላጊ መቃቃርን ሊያስከትሉ የሚችሉ፣ ጉዳዮች ላይ መጻፍ ካልቻልን የሚሉም አልጠፉም ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ ሃይማኖት መለወጥን (በዚያ ወቅት ጎልቶ ይታይ ነበርና) አስመልክቶ ስሜታዊ ጽሑፎችን በሚጋብዙ ጉዳዩች ላይ፣ ወይም የክፍል ጓደኛዬ የነበረው ዐወል አደም በኮተቤ ስለተሳተፈበት፣ ተማሪዎች ጎራ ለይተው ስለተደባደቡበት ሁኔታ የግሉን ትንተና እና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ መጻፍ መፈለጉ፣ እንደ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ሊቆጠር የሚችልና የሚበረታታ አልነበረም፡፡

አንዳንዶች ደግሞ፣ ስለሚጽፉባቸው አጠቃላይ ርእሶች፣ እውነተኛ አስተያየቶቻቸውን በስማቸው ለመጻፍ ፈቃደኛ የነበሩ አልነበሩምና፣ አለመጻፉን ይመርጡ ነበር፡፡ ይኽ ጓላ ካምፓስ ስታር የሚለው መውጣት ሲጀምር እና በብዕር ስም መጻፍ ሲቻል፣ የታየ ነገር ነበር፡፡ ይሁንና፣ በአዘጋጁና በጥቂት ተባባሪዎች በተደረጉ የጽሑፍ አስተዋጽኦዎች እስከ ትምህርት ዓመቱ መገባደጃ ዩ.ሲ ኮልስ እንደምንም ዘለቀ፡፡

በዚህና በሌላ ብዙ ትምህርታዊ በሆኑ ጉዳዩች ላይ የወወክማ ሚና መነሣት ይገባዋል፡፡ ከሁሉም ይበልጥ የወወክማ ዋና ሚና መድረክ ማዘጋጀት ነበር፡፡ መንግስቱ ለማ በ1948 ስለ አማርኛ ጥበበ ቃላት ስያሜና ምንነት፣ እንዲሁም በሀገራችን ስለ ሒስና ሐያሲ ያለመኖር ችግር በዚሁ መድረክ ላይ ነበር ሁለት ሰፊ ንግግሮች ያደረገው፡፡ (እዚህ ላይ፣ ሒስና ሐያሲ የሚሉትን ስያሜዎች በንግግሩ ውስጥ አለመጠቀሙ ሊጠቀስ ይገባል፡፡ ያኔ ገና አልተለመዱም ነበር፡፡) እንዲሁም፣ ልማት ለማጣጣም ሕዝብ እንዴት ቢደራጅ ይሻላል? በሚል ርእስ ዙሪያ ይፋዊ ክርክር በሁለት ተጻራሪ አቋሞች ዙሪያ እንደሚካሔድ በወቅቱ በአዲስ ዘመን ተዘግቦ ነበር፡፡ ይኸውም፣ መደራጀቱ በብሔረሰብ ወይስ በአካባቢ ነዋሪዎች አባልነት የሚል ነበር፡፡

ስለዚህ፣ በዚያን ዘመን ወወክማ የአንድ የማኅበራዊ ተቋምን ሚና የሚጫወት ነበር፡፡ ለዚህ፣ በተለይ ኢትዮጵያዊው እውነቱ በላይ እና የውጭ ዜጋው ሚስተር መርሊን ቢሾፕ፣ ለዘመኑ የአዲስ አበባ ፊደል ቀመስ የኀብረተሰብ ክፍል፣ ባለውለታ ነበሩ፡፡

ወደ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ስንመለስ፣ በየጊዜው የሁኔታዎችን ለውጥ እየተከተለ በመጉዋዝ ላይ ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር፣ ለወደፊቱ ለውጥ ያገዙ ሁነቶች የተከሰቱበት 1951 ጎልቶ ይመጣል፡፡ በዚህ ዓመት ሦስት ነገሮች ይከሰታሉ፡፡ መጀመሪያው፣ በመደበኛ ትምህርቱ ረገድ ሞደርን ቲንኪንግ (ወይም የዘመኑ አስተሳሰብ) የሚል ትምህርት፣ ሚኬሊዴስ በሚባል ዘረ ግሪክ ‹‹እጩ እየሱሳዊ›› መምህር መሰጠት ይጀምራል፡፡ በዚህ ኮርስ፣ አንደኛ፣ ለአራተኛ ዓመት ቶሚስቲክ ፊሎሶፊ እያለ ተማሪው የሚተርበውን መደበኛ የፍልስፍና

ትምህርት አስተማሪያችን ስማቸውን ማንሣት ጨርሶ የማይፈቅድላቸውን (ካነሣም በማጥላላት የሚያነሣቸውን) ፈላስፎች ሚኬሊዴስ እያነሣ ስለሰዎቹም፣ ስለ ሥራዎቻቸውም በክፍል ውስጥ በግልጽ መወያየት ተጀመረ፤ ከክፍል ውጪም የርስበርስ መከራከሪያ ሆኑ። ሁለተኛው፣ በዚያ ዓመት በተከበረው *የኮሌጅ ቀን* ላይ በአደባባይ የግጥም ንባብ የፕሮግራሙ አካል ሆኖ በመልካም አጋጣሚ ሳቢያ መግባት ነው። ሦስተኛው፣ በቂ ቁጥር ያላቸው ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች፣ የኮሌጅ ደረጃ ተማሪዎች በዚያ ዓመት መምጣት መጀመራቸው ነው። ይኸኛው ሰፋ ያለ አንድምታ የነበረው ነበር።

ጋና በ1949 ነጻነቷን ተቀዳጅታ፤ በለጠቀው ዓመት አክራ ላይ የ8 የአፍሪካ ነጻ መንግሥታትን የአርነት ንቅናቄ ታጋዮችን ያገናኘና ያቀራረበ ስብሰባ አካሄደች። እዚያ ስብሰባ ላይ የተገኘውን የኢትዮጵያ ተሳታፊ የልኡካን ቡድን የመሩት አቶ አበበ ረታ ሲሆኑ፣ በዋናነት ከልኡካኑ ጋር የንጉሡ ነገሥቱ የመጨረሻ ልጅ፣ ልዑል ሣህለ ሥላሴ፣ ሔደው ነበር።

ኢትዮጵያን በሚመለከት በዚህ ጉባኤ ላይ የተከሰተው ነገር፣ በየዓመቱ 50 የአፍሪካ ወጣቶች በኮሌጅ ደረጃ በኢትዮጵያ ለማስተማር የነጻ ትምህርት ዕድል ለተከታታይ አራት ዓመታት መሰጠቱ ነበር። ይህም ከ1951 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ሆነ፤ ከምሥራቅ እና ከምዕራብ አፍሪካ አገሮች ተማሪዎች መምጣት ጀመሩ። በዚህ በመጀመሪያው ቡድን ውስጥ አንዲት ሴት ከዛንዚባር ነበረች። (ያኔ ታንዛኒያ አልነበረችም፤ ታንጋኒካ እና ዛንዚባር የሚባሉ ሁለት አገሮች ነበሩ፤ ሁለቱም ገና የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶችም ነበሩ።)

ለኢትዮጵያውያኑም ለስኮላርሺፕ ተማሪዎችም የጠቀመ መስተጋብር ተፈጠረ። የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ አመራሮች ባይወዱትምና ብዙ የመለያያ ሙከራዎች ቢያደርጉም፣ ብዙም ውሎ ሳያድር ግንኙነቱ መተማመን ፈጥሮ ነበረ። በዚህ መሠረት በመጀመሪያው ዙር ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መካከል፣ የተወሰኑት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በ1951 ገቡ። በዚያን ጊዜ የተማሪዎች ምክር ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ ለመሆን ተወዳዳሪ ሆኜ ተመረጥኩ። ከአዲስ መጪዎች መካከል በተለይ ሮበርት ኦኡኮ እና ኦሞጊ ካሌብ የሚባሉት ኬንያውያንና ዴኒስ ኤጂንዱ የሚባል ናይጄርያዊ ተቀራርበውኝ ነበር።

በስኮላርሽፕ ተማሪዎቹና በኢትዮጵያውያኑ ተማሪዎች መካከል የቀረበ ግንኙነት እንዳይኖር፣ የኮሌጁ አስተዳደር ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ነበር። የኮሌጁ ተማሪ አባልነታቸው ይበልጥ እንዳይሰማቸው ለማድረግ፣ በሌሎች ኮሌጆች ካሉት ሌሎች የስኮላርሺፕ ተማሪዎች ጋር ሆነው፣ የራሳቸውን የአፍሪካ ተማሪዎች ክበብ እንዲያቋቁሙ እስከ ማድረግ ደርሰው ነበረ።

ሊያለያዩን ሲያደርጉት ከነበረው እኩይ ቅስቀሳ ውስጥ፣ *ኢትዮጵያውያኑ ተማሪዎች አይወዷችሁም፤ ረጅም ታሪክ አለን ብለው ስለሚኩራሩ ይንቋችኋል። እንዲያውም፣ ባሪያ ነው የሚሏችሁ* የሚል ዓይነት ነበር። ለዚህ ጉዳይ የጠቀማቸው፣ በቀደመው ዓመት በተባበሩት መንግሥታት የነጻ

ትምህርት ዕድል የተሰጠው፣ ከታንጋኒካ መጥቶ የነበረ ተማሪ ነበር። ሽባኒ ሺምቦ ማጎንጃ አማርኛ ያጠናና ጥቂት መስማት የሚችልም ነበር።

ይህን *ባሪያ ትሉናላችሁ* የሚል የውንጀላ ቅስቀሳ በኋላ የሰማሁት፣ በክስ እና በወቀሳ መልክ ከኦሞጊ ካሌብ አንደበት ነበር። ‹‹እኛ እናንተን ወንድሞቻችን እንላችኋለን። እናንተ ግን ባሪያ ትሉናላችሁ›› አለኝ አንድ ቀን ፀሐይ እየሞቅን ጫማችንን ስናስጠርግ።

ይኸን አባባል ለማስተባበል አልቃጣሁም። ይልቁንም፣ይህ እርስ በርሳችንም የምንባባለው ተራ ነገር መሆኑን ገለጽኩለት። ከአንድ አባትና እናት የሚወለዱ ወንድማማቾችና እትማማቾች ጭምር በቀልድም፣ ሆነ ብሎ ለመበሻሸቀም የሚባባሉት እንጂ የምር ነገር አይደለም። ባንጻሩምኮ ቀላ፣ ፈካ ያለው (የነጣው)፣ በነጫጭባነትና በሊጥ-ፊትነት ይተረባል አልኩት!! ስለዚህ ይኸ አባባል በሌሎች አገሮች አለ እንደሚባለው፣ በመርዘኛ ስሜት የተለወሰ አባባል እንዳይደለ ነበር፣ ላስረዳው የሞከርኩት።

ሌላው ኦሞጊን ያናድደው የነበረው ነገር፣ ‹‹እኔ ለናንተ የምነግረውን ምስጢር ነገር ወዲያው ለኮሌጁ አመራር ትነግሩብኛላችሁ። ወዲያው ደርሶ ተጠርቼ ይነገረኛል። ይኸንንም እንደማትወዱን እንደማስረጃ ይቀርብልኛል›› ነበር ያለኝ። እኔም፣ ጀዝዊቶቹ በተማሪው መካከል ያሰማሯው ሰላዮች እንዳሉና ሁላችንም እንሰለላለን ብለን እንደምናምን ገለጽኩለት። ‹‹ሚስጥርህ የወጣው ለተማሪው አመራር አባላት ከነገርከን ውስጥ ከሆነ፣ ይህ ሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ አንድ ዘዴ ሞክር›› አልኩት። ‹‹ምስጢር የምትለውን ነገር ለአንድ ሰው ብቻ ንገር። ለሁለት ሦስት ሰው መንገር አይሆንም- ለአንድ ሰው ብቻ ንገር›› አልኩት። በሳምንቱ ውስጥ ሰውዬውን እንደደረሰበት ነገረኝ። ‹‹ማን ነው?›› አላልኩትም። እሱ በገዛ ፈቃዱ ነገረኝ። አልተደነቅሁም ነበር። ገረመው።

አትወዱንም ስለሚለው ነገር በቀጥታ አስተባበልኩት። እንዲያውም እርሱ በግሉ በተማሪው ዘንድ ተወዳጅ (ፓፒዩላር) እንደሆነ ገልጬ፣ በሚለጥቀው ትምህርት ዘመን እኔ ለያዝኩት ቦታ (የተማሪ ምክር ቤቱ ጠቅላይ ጸሐፊነት) ቢወዳደር እንደሚመረጥ ነገርኩት። ከት ብሎ *ሥቆ*፣ የስኮላርሺፕ ተማሪዎችን እንደሆነ እንጂ የአንድ የኢትዮጵያ ተማሪ ድምፅ እንደማያገኝ ተናገረ። እኔም ብቻ ‹‹አንተ ሩጥና፣ ያኔ እናያለን›› ብዬው ወደየክፍላችን ለመግባት ተጣደፍን። በለጠቀው ዓመት በ1952፣ ኦሞጊ ካሌብ የዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ የተማሪዎች ምክር ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ ሆኖ ለመመረጥ መብቃቱን ሰማሁ።

በ1951 ሐምሌ *መጀመሪያ* ላይ፣ በኦሞጊ ካሌብ እና ዴኒስ ኤጂንዲ አስተባባሪነት የስኮላርሺፕ ተማሪዎቹ አዋጥተው፣ ዋሻ ይባልና በሲኒማ ኢትዮጵያ *ሥር* ይገኝ በነበረው ሬስቶራንት ባዘጋጁት እራት ላይ በክብር እንግድነት ተገኘሁ። አሞጋሽ ቃላትም፣ በተለይ ከኦሞጊ ካሌብና ዴኒስ ኢጂንዱ፣ ተሰንዝረውልኝ ነበር።

በ1951፣ የተማሪው ምክር ቤት አባላት፣ በሁለት ዓለማቀፍ የተማሪዎች ሰብሰባዎች መሳተፍ ነበረብን፡፡ የመጀመሪያው ጥሪ፣ ወደ ትምህርት ዓመቱ አጋማሽ ላይ የመጣው ከኮሴክ (Cosec= Coordinating Secretariat, International Students Association) ነበር፤ በሊማ (ፔሩ) በተካሔደው በዚህ ዓለማቀፍ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ የሔደውም፣ የተማሪዎች ምክር ቤት ፕሬዚደንት የነበረው ሐጎስ ገብረ የሱስ ነበር፡፡ ሁለተኛው እና የመላ አፍሪካ ሁለተኛ ጉባኤ ላይ ሁለት ልኡካን እንድንሳተፍ የተላከው ጥሪ ደግሞ፣ በትምህርት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ ነበር፡፡ በቱኒዝ ከተማ (ቱኒዝያ) ላይ በሚደረገው ስብሰባ ላይ እንድንሳተፍ እኔ የተማሪዎች ምክር ቤት ጠቅላይ ጸሐፊው እና የባህል ፕሬዝዳንቱ፣ መክብብ ገበየሁ፣ ተመርጠን ተላክን፡፡

ከዚህ ከ2ኛው ጉባኤ ገጠመኝ አንድ ነጥብ ጎልቶ ይወጣል፡፡ ይኸውም፣ ኋላ በሰፊው መድረክ ላይ የተስተዋለው፣ የሦስተኛውን ዓለም ወጣት የራስ የማድረግ ሽኩቻ መኖር በገሃድ መታየት ነበር ፡፡

ወደ ስብሰባው ለመሔድ በዝግጅት ላይ እያለሁ፣ ኮሌጅ ድረስ አንድ ሰው መጥቶ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ አለኝ፡፡ ጉዳዩ ወደ ጉባኤው ስሔድ፣ እግረ መንገዴን በስዊስ አገር ‹‹ኮ›› ከምትባል ከተማ ደርሼ እንድሔድ ለመጋበዝ ኖሮአል፡፡ አመስግኜ፣ ስመለስ እንጂ ስሔድ እንደማይመቸኝ ብገልጽ፣ ዋና ዓላማው ከስብሰባው በፊት እዚያ ቆይታ ማድረግ የሚፈለግ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ በዚህ ስገረም፣ ማንን አስፈቅዶ እንደ ነበረ አላስታውስም፣ በምግብ አዳራሹ አንድ ፊልም አሳየ፡፡ ፊልሙ አንድ ነውጠኛ የአርነት ንቅናቄ መሪ እንዴት ‹‹በሞራል ሪአርማመንት›› እገዛ ከትግሉ እንሚለዝብ የሚያሳይ ነበር፡፡ ለሰውዬው ያቀረብኩለት ጥያቄ፣ የሚለወጠው (የሚለዝበው)፣ ነጻ ለመውጣት የሚታገለው ጭቁን ነው፤ ጨቋኙስ? የሚል ነበር፡፡ ሰውዬውን ከፋው፡፡ የ‹‹ኮ›› ጉብኝት ጉዳይም በዚሁ አከተመ፡፡

ከዚያ በኋላ ወደቱኒዝ አዘገምን፡፡ በስብሰባው ላይ ወጣት የቱኒዝያ መንግሥት ባልደረቦች፣ ከቱኒዝያ ተማሪዎች አመራር ልኡካን ጋር ተቀይጠው ስብሰባውን ለመቆጣጠር ሲሞክሩ ይስተዋል ነበር፡፡ በዚህም እንቅስቃሴያቸው፣ በሁለተኛው ቀን ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት እንዲመራ ያልጄሪያን (ያኔ ገና ነጻ አልወጣችም ነበር) ተማሪዎች ልኡካን መሪ እንዲመረጥ አስደረጉ፡፡ ልክ የመክፈቻው ቀን መሪ የነበረው ናይጄሪያዊው ሊቀ መንበር እንዳደረገው፣ ይኸኛውም በተራው ስብሰባውን ሲመራ የመናገር ቅድሚያውን (እንደ ጥያቄው ቅደም ተከተል ሳይሆን) ለአረብ እና/ወይም የፈረንሳይ ተናጋሪ ለሆኑ ብቻ ይሰጥ ጀመር፡፡ ይኸም ከሌሎቹ ልኡካን አባላት ቅዋሜና ንትርክ በማስነሣቱ ፍሬ ያለው ነገር ሳይፈየድ ሁለተኛውም ቀን ተጠናቀቀ፡፡

ለሦስተኛው ቀን ሰብሳቢ በቀላሉ ለመምረጥ፣ የመጀመሪያ ሁለት ቀኖች ልምድ አላስቻሉም ነበርና የማይፈታ ችግር ተፈጠረ፡፡ ኋላ፣ በመራጭ ኮሚቴው ውስጥ የነበረ የአንዱ ልኡካን ቡድን መሪ (የየት አገር እንደሆነ ትዝ አይለኝም)

ኢትዮጵያን በእጩነት አቅርቦ የአብዛኛውን ድጋፍ አገኘ፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ ልኡካን በኩል፣ የተወሰኑም ቢሆኑ፣ ድምፀ ተአቅቦዎች (በድጋፍ እጃቸውን ያላሳዩ) ስላሉ ለመቀበል እንደሚቸገሩ ገለጹ፡፡ ነገር ግን፣ እንደገና ሲጠየቅ ሁሉም እጅ ስላሳየና፣ እንድያውም ለቀሪው ጊዜም የኢትዮጵያ ልኡካን መሪ እንዲቀጥል ስለተወሰነ፣፤ ሊቀ መንበርነቱን መቀበል ግድ ሆነ፡፡

ይሁን እንጂ፣ የነበረው ልዩነትና ግትርነት አንዳችም ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስችል አልነበረም፡፡ የተከሰቱት ልዩነቶች የሚከተለው መልክ ነበራቸው፡-

ሀ) እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችና ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች፣

ለ) አረብና ጥቁር አፍሪካዊነት፣

ሐ) ከነጻ አገርና ገና ነጻ ካልወጡ አገሮች መምጣት፣ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡ በመሆኑም፣ ስብሰባው፣ ምንም ሳይፈይድ ማለት ይቻላል፣ ተጠናቀቀ፡፡

ስለዚሁ ጉዳይ፣ በአንድ የቱኒዝያ ጋዜጣ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ልኡካን መሪነት እኔ ተጠይቄ የሰጠሁት ሒሳዊ አስተያየት ታትሞ ወጣ፡፡ እኛን ቃለ-መጠይቁ ታትሞ መውጣቱ ያስደነቀን፣ ለነገሮች አለመሳካት የቱኒዝያኖቹንም ሚና፣ ከአሽሙር ባለፈ አገላለጽ፣ በተማሪዎች ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ጭምር የሚተች በመሆኑ ነበር፡፡

ከዚህም ያላነሰ አስደማሚ የነበረው፣ የቻይና እና የሶቭየት ኅብረት ተማሪዎች ልኡካን በታዛቢነት መገኘታቸው ሳይሆን፣ ‹‹የዓለማቀፉ የተማሪዎች ማኅበር ወኪሎች ነን›› የሚሉ ሁለት የልኡካን ቡድኖችም (አንዱ [የኮሴክ] ከላይደን፣ ኔዘርላንድ እና ሌላው [የ International Union of Students] ከፕራግ፣ ቼኮስሎቫኪያ) በታዛቢነት መገኘታቸውና፣ እንዲሁም አራቱም፣ የኢትዮጵያን ልኡካን ቡድን ወደየአገራቸው አብረዋቸው እንዲሔዱ መጋበዛቸው ነበር!!

የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን በጊዜ ጥበት ሳቢያ የሁለቱን ሀገራት የተማሪዎች ወኪሎች ግብዣ ለመቀበል አለመቻሉን ገልጾ፣ ለሁለቱ የዓለማቀፍ ማኅበራት ልኡካን ደግሞ፣ ገለልተኛነቱን ለማሳየት፣ የሁለቱንም ግብዣ ተቀብሎ መጀመሪያ ወደ *ኢንተርናሺናል ዩኒዮን ኦቭ ስቲዩደንትስ* (IUS) ዋና ጽሕፈት ቤት መገኛ ወደነበረው ወደፕራግ ተጉዋዘ፡፡

የፕራግ ጉዞአችን በአየር መንገድ በኩል ችግር ነበረበት፡፡ ግን ከዚያ አስቀድሞ ሌላ እክል ነበረብን፡፡ ከቱኒዝ ሮማ የደረስን እለት ይሁን በማግሥቱ፣ የሕዝብ በዓል ነበር፡፡ ስለዚህ፣ የቼኮስሎቫኪያው ቆንስላ ዝግ የነበረ ከመሆኑም በላይ፣ የለጠቀው ቅዳሜና እሑድ ነበር፡፡ ሰኞ እለት ቆንስላው ስንሔድ ደግሞ፣ ለካ ፓስፖርታችን ‹‹ለምዕራብ አውሮፓ አገሮች ብቻ›› ኑሮአል የሚያገለግለው!! ወደ ምሥራቁ ክፍል ለመሔጃ አያገለግልም፡፡ ሆኖም፣ ቆንስላው ፓስፖርቱ ላይ ቪዛውን በማተም ፋንታ ልዩ ሰነድ በመስጠት ችግሩን እዚያው ፈታልን፡፡

ሆኖም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ተባባሪውም ቲ.ደብሊው.ኤም ወደ ምሥራቅ አውሮፓ አይበሩም ነበር። ስለዚህ፤ ቲኬቱ ለስዊስ አየር መንገድ መተላለፍ ነበረበት። ነገር ግን ቲኬቱን ለማስተላለፍ ሮማ የነበረው የቲደብልዩኤ አየር መንገድ ወኪል ፈቃደኛ አልነበረም። ‹‹የምትገቡት ኮሚዩኒስት አገር ስለሆነ፣ አንድ ነገር ብትሆኑ ኃላፊነቱን አንወስድም›› የሚል ብዙ የማስፈራራት ነገርም ነበረበት።

በዚያን ወቀት (ባልገልጸውም)፣ ስለኮሚዩኒስት አገሮች በአእምሮዬ የነበረው ምስል (በተለይ ለኮሌጅ ደረጃ ተማሪ) አስገራሚ ብቻ ሳይሆን፣ የሚያሳፍርም ነበር!! ከዜጋው አነስተኛ ቁጥር የሆኑ፣ ከአውሬ የማይለዩ አስፈሪ የፓርቲው አባላት ሕዝቡን በፍርሐት አስጨንቀው የሚያኖሩበት አገር ነበር የሚመስለኝ።

ይህ አመለካከት ከሁለት ምንጮች የተፈጠረ ነበር። አንዱ፣ አጋጣሚ ሆኖ በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪነቴ ጊዜ አንሥቶ ታይምን እና ኒውስዊክን (ብዙውን ጊዜ ለወራት ሳያሰልስ) ሰኞ ሰኞ በትኩሱ እያገኘሁ አነብ ነበር። ለዚህ ባውለታዬ፣ ዘጠነኛ ክፍል አብሮኝ ገብቶ የነበረና ጎረቤቴም፣ በአየር ማረፊያ የጤና ጥበቃ ወኪል ሆኖ መሥራት የጀመረው፣ ክፍሌ ግርማ ነበር። እነዚህን ሳምንታዊ መጽሔቶች በተከታታይና ለረጅም ጊዜ በመከታተሌ፣ ይህን አሉታዊ ምስል ለመቅረጽ የማይናቅ ሚና ነበራቸው።

ሁለተኛው፣ ከእምነቴ ነበር። የሃይማኖት አበው ማኅበርን ከመሠረቱት ተማሪዎችም አንዱ ነበርኩ እኮ። ስለዚህ፣ ‹‹ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር የለም›› የሚሉ ዐማርኛ የሚገባኝም የሚዋጥልኝም አልነበረም።

ይሁን እንጂ፣ የቲኬቱ ማስተላለፍ ጭቅጭቅ እልህ ውስጥ ከተተን። ራሳችን ኃላፊዎች ነን ብለን ድርቅ በማለታችን እና ቪዛም ስለነበረን ምንም ማድረግ አልቻለምና ፈቃዳችንን ፈጸመ።

በስዊስ አየር መንገድ ተጉዘን ዙሪክ ከምትባለው የስዊስ ከተማ ደርሰን ወረድን፤ ወደ ፕራግ የሚቀጥለው በረራ በማግሥቱ ማታ ስለነበረ ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ፕራግ ከተማ ገባን። የአዩኤስ ፕሬዚዳንት (ስሙ ተዘንግቶኛል) አውሮፕላን ጣቢያ ድረስ መጥቶ ኖሮ ተቀበለን። ትውልዱ ቼክ ነበር፤ አጠር ደልደል ያለ ባለ ወርቅማ ጸጉር። በርሱ መርሴዴስ ተሳፍረን እያወጋን ጉዞ ጀመርን።

ከአውሮፕላን ማረፊያው አካባቢ መራቅ ስንጀምር፣ ጨለማ ዋጠን። ጸጥ ያለ ጨለማ ነበር አካባቢያችንና፣ ሕዝቡ በየቤቱ ገብቶ ቆልፏል ማለት ነው፣ አልኩኝ ለራሴ። የመንገድ መብራት አይታይም። የተወሰኑ ደቂቃዎች ከነዳን በኋላ የመንገድ መብራቶች ማየት ጀመርን፤ እግረኛ ግን አይታይም። ሌሎች መኪኖችም ብዛት ባይኖራቸውም ይተላለፉ ጀመር። ወደ ከተማው መሀል ስንዘልቅ እግረኛም ማየት ቻልኩ። እነዚህ ወይ የተፈቀደላቸው፣ አለበለዚያም ኮሚኒስቶች ይሆናሉ - ለቁጥጥር የሚዞሩ! ብዬ አሰብኩ።

መኪናችን አንድ ትልቅ ሆቴል ዘንድ ደርሶ ወረድን፡፡ ይህ የገቢዎቹ አባላት መዝናኛ ቦታ መሆን አለበት አልኩ ለራሴ፡፡ ስንገባ አዳራሹ በሻንደሊዬ መብራት ብርሃን በብርሃን ነበር፡፡ በሚደሉ መቀመጫዎች ላይ ተቀምጠው ወንዶችና ሴቶች በየቡድን ሆነው እያወኩ፣ ልዩ ልዩ መጠጦች ከፊታቸው አኑረው ያወጋሉ፣ ያውካካሉ፣ ይዝናናሉ፡፡ ሁሉንም በመቃኘት አውሬዎቹን በዓይኔ ፈለግሁ፣ የምፈልጋቸውን የሚመስሉ አንድ አጣሁ!!

ጋባዦቻችን እና ሆቴሉ ቦታችንን አስያዙንና፣ የምንፈልገውን የምግብና የመጠጥም ሆነ የሌላ አገልግሎት ማዘዝ እንደምንችልና፣ ለነዚህ የሚቀርቡልንን ሰነዶች መፈረም ብቻ እንጂ ምንም መክፈል እንደማይጠበቅብን ገለጹልንና፣ ራታችንን ከበላን በኋላ፣ ወደ ፈለግንበት ቦታ ሊወስዱን ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹልን፡፡ ስለከተማው፣ እኛ ምንም የምናውቀው ነገር ስለሌለ እና ማታም ስለሆነ፣ እነርሱ ባወቁ እንዲያደርጉ ነገርናቸው፡፡

ከራት በኋላ፣ ‹‹ሰው ቀን ሲሰራ ውሎ ማታ እንዴት እንደሚዝናና ለማየት ከፈለጋችሁ›› ብለው ይዘውን አንድ ቦታ ሔዱ፡፡ ሰፊው አዳራሽ በሰው ጢም ብሏል፤ ከፊትለፊት መድረክ ነበረው፡፡ አንድ ሰው በቋንቋቸው ይናገራል፡፡ ሰዉ በንግግሩ መካከል በሳቅ ይንከተከታል፡፡ ስለሚለው ነገር፣ ጥቂት ሲተረጎምልኝ ሳይገርመኝ አልቀረም፤ ምክንያቱም፣ በሆነ ነገር ላይ አቃቂር ነገር ነበረበት- መንግሥትን ይነካል ብሎ መተርጎም የሚችል ዓይነት ነበርና ነው፡፡ አውሬዎቹን እዚህም ላገኛቸው አልቻልኩም፡፡

አንድ ሦስት ቦታዎች ለተወሰነ (ግን ለበቂ) ጊዜ፣ እየዞርን አየን፡፡ ተዝናናንም፡፡ በተለይ እመጨረሻው ቦታ ገብተን ትንሽ እንደቆየን፣ አንዱ የክር መሣሪያ የሚጫወት ሙዚቀኛ፣ *ቻርዳስ* የምትባለውን ተወዳጅ የቫዮሊን ድርሰት በድንገት መጫወት ጀመረ፡፡ ፍንደቃዬን መቆጣጠር ቀላል አልነበረም፡፡

በጉብኝታችን ወቅት ብዙ ነገር ከማየቴም ሌላ ስለአውሬዎቹ የነበረኝ ምስል እስከ ዘላለሙ ከአእምሮዬ ተወገደ፡፡ ሀገሪቱም፣ በኢንዱስትሪ ብዙ ወደ ፊት የሔደች መሆኑዋን፣ ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደብኝም ነበር፡፡

በዚህ መልክ የአይዩኤሱ የቼኮስሎቫኪያ ጎብኝት በሚያረካ ሁኔታ ሲገባደድ፣ የኮሴኩ ጉብኝት በአንፃሩ ግን ከሸፈ፡፡ ዋናው ችግር ቪዛ ያልነበረን ሲሆን፣ በዚህ ላይ እኛ ያለነው አምስተርዳም ሲሆን፣ ለቭሞር የተባለው የማህበሩ ደቡብ አፍሪካዊ ዋና ፀሐፊ ይሁን ፕሬዝዳንት (እረስቸዋለሁ) የነበረው ላይደን ከተማ ነበር፡፡ በዚህ ላይ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እዚያ የለም፡፡ የእንግሊዝ አገሩ አምባሳደራችን ነው የኔዘርላንዱም (በተደራቢ)፡፡

ለኢምግሬሽን ባለሥልጣኖቹ ደግሞ ዋናው ችግር፣ ከኮሚዩኒስት አገር ከፕራግ የመጣን መሆኑ ኖሩዋል፡፡ ነገር ግን፣ በራሳቸው አየር መንገድ *በኬ ኤል ኤም* ወደ አምስተርዳም የበረርነው በቀጥታ ሳይሆን፣ ዙሪክ ተመልሰን ውለን አድረን፣ ከዚያ ነበር፡፡ ሆኖም ለስዊስ ተመልሶ መግቢያ ፕራግ ባለው

ኮንስላቸው ቪዛ ስናስመታ ማህተማቸው ላይ ከ‹‹*ፖራሃ*›› የሚል ኖሮበታል!! ይሁን እንጂ፣ እኛ ስላጉላሉንና የራሳችንን ንጽህና ብቻ አይተን ተበሳጨን እንጂ፣ ከነሱ አንፃር ሆነን ብናየው ኖሮ ልክ ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፓስፖርታችን ከምዕራብ አውሮፓ ውጪ እንድንሔድ የማያስችል ሆኖ ሳለ፣ ቼኮቹ ያለአንዳች ማንገራገር ፈቅደው አስገቡን፡፡ የነርሱ ሰዎች ባንሆን ያስገቡን ኖሮአል? ብለው እነዚህኞቹ ቢያስቡ አያስገርምም ነበር፡፡

ስለዚህ በማግስቱ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ያለ ጥርጥር ወደ ምናገኝበት እና ካውሮፓም በጣም ወደ ምንርቅበት ወደ ካይሮ ጭኖ ወስዶ እንዲጥለን *ኬ ኤል ኤምን* አዘዙ፡፡ በካይሮ አንድ ሁለት ቀን ውለን አድረን ጉብኝት አደረግን፡፡ ከዚያ በቀጥታ ወደ አገራችን ተመለስን፡፡ ካይሮ ላይ ስለጉዞዬ በአጠቃላይ የጻፍኩበት ማስታወሻ ከሆቴሌ ተሰርቆብኝ ነበርና እየተበሳጨሁ ነበር የመጣሁት፡፡

ከነዚህ ሁሉ ገጠመኞች የተገኘው ግንዛቤ፣ ለራሱ ዓላማ እና ግብ የተመሠረተው የኢትዮጵያ ኮሌጆች ተማሪዎች ማኅበር፣ ወደፊት ወደግራና ወደቀኝ ሊስቡት የሚፈልጉ ኃይሎች እንደሚገጥሙት ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ‹‹ኮሌጆች ተማሪዎች›› ማኅበር ያልኩበት ምክንያት በ1951 መገባደጃ ላይ፣ የምሕንድስናንና የሕንፃ ኮሌጆችንም የሚያጠቃልል፣ ኮሌጆች አቀፍ የሆነ አንድ የተማሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ውጥን ነበርና ነው፡፡

ይሁንና፣ ከካይሮ አዲስ አበባ እንደገባሁ፣ የማጠፋው ብዙ ጊዜ አልነበረኝም፡፡ የብሪትሽ ካውንስል ኃላፊዎች በእግር በፈረስ ሲያስፈልጉኝ ነበር የደረስኩት፡፡ ምክንያቱም በዚያ ዓመት ትምህርቴን ጨርሼ ነበርና ነው፡፡ በዚያ ጊዜ ለከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የሚላኩት ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ወዲያውኑ ነበር፡፡ የኔ ምርጫ የእንግሊዙ ዝነኛ ዩኒቨርሲቲ ኬምብሪጅ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት በለንደን እሚደረግ አገር የማለማመጃ ፕሮግራም ስለነበረ ለዚያ ለመድረስ በጥድፊያ መነሳት ነበረብኝ፡፡

ስለዚህ፣ ውጭ አገር ለከፍተኛ ትምህርት ለሚሔዱ ተማሪዎች ልብስ ለመግዣ መንግሥት ይሰጥ የነበረውን 750 ብር ከትምህርት ሚኒስቴር ለመቀበል እንኳ ጊዜ ስላጠረኝ፣ ከአክስቴ (ያባቴ እህት) ተበድሬና ከሚኒስቴሩ እንዲቀበሉ ወክዬ መሔድ ግድ ሆነብኝ፡፡

## ትምህርት በእንግልጣር

በመስከረም 11 ቀን 1952፣ ስለ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ ከነበረኝ ፍቅርና መልካም ትዝታ ጋር፣ ከቀድሞው የአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ፣ ወደ እንግሊዝ አገር በቅድመ - ጄት አውሮፕላን በረርኩ። ከዚህ በላይ ወደገለጽኩት የቱኒዝ ጉባኤ የሔድኩትም በዚህ የበረራ መሥመር (አዲስ አበባ፣ አስመራ፣ ካርቱም፣ ካይሮ፣ አቴንና ሮማ) ስለነበር አሁን ሁለተኛ ጊዜዬ ነበር። ከሮማ ወደ ለንደን ያለው ጉዞ ብቻ ነበር አዲስ።

ለንደን ሂትሮው አውሮፕላን ማረፊያ ስደርስ፣ ሁለት ሰዎች ሲጠብቁኝ አገኘሁ። መጀመሪያ ያገኘኝ የብርቲሽ ካውንስል የላከው ሰው ነበር። ውስጥ ድረስ ገብቶ ተቀበለኝ። ከዚያ ከጉምሩክ ውጭ ደግሞ ኮሊን ሊኪ ገና ከሩቁ አይቶ ጠራኝ። ሁለቱ ተቀባዬቼ አይተዋወቁ ስለነበር፣ እኔ አስተዋዋቂ ሆንኩ።

ኮሊን በራሱ መኪና እሚፈለገው ቦታ ድረስ ለማድረስ ፈቃደኝነቱን ለብርቲሽ ካውንስሉ ወኪል ገልጾለት፣ አድራሻውን ከተረዳ በኋላ፣ በርሱ መኪና ወደ ማእከላዊ ምዕራብ ለንደን በረርን። የኮሊን አመጣጥ ሌላ ፕሮግራም መኖሩን ስላላወቀ በቀጥታ ወደ ኬምብሪጅ ወደ እናቱ ቤት ይዞኝ ለመሔድ ነበር። እሱም፣ አብረውት ጎጃም ሔደው የነበሩትም፣ ወደ ሥራ ዓለም መበታተናቸውን ነገረኝ። እርሱ ግን የኬምብሪጅ ከተማ ተወላጅ ስለሆነ ለጊዜው እዚያው እንደሆነም ገለጸልኝ። እንደዚህ እየተጫወትን፣ ባገር መለማመጃ ፕሮግራሙ ላይ የሚሳተፉ ወዳሉበት ቦታ አድርሶኝ፣ ፕሮግራሙ እንዳለቀ ወደ ኬምብሪጅ የምደርስበትን ቀንና ሰዓት ተነጋግረን፣ ወደ ኬምብሪጅ ተመለሰ።

በፕሮግራሙ ላይ የነበርነው ሁላችንም የብሪትሽ ካውንስል ስኮላርሺፕ የተሰጠን ስንሆን፣ የመጣንባቸው አገሮች ከእስያ፤ ከአፍሪካና ከላቲን አሜሪካ ነበር። የፕሮግራሙ ይዘት የገለጻዎችና የጉብኝቶች ስብጥር ነበር። የለንደንን ከተማ ልዩ ልዩ ስፍራዎች በመሪዎች አማካይነት ስንጎበኝ፣ እግረ መንገዱንም የትራንስፖርትና የመገናኛ አጠቃቀምን እየተለማመድን ነበር። የማለማመጃ ፕሮግራሙ ውስጥ የኬምብሪጅ ጉብኝት አንዱ ነበር። ኬምብሪጅ ስንደርስ ደግሞ፣ የኪንግስ ኮሌጅን ዝነኛ ቻፕል (ጸሎት ቤት) መጎብኘት አንዱ ጉዳይ ነበር። ስለዚህ፣ ገና ከመጀመሪያው አካባቢውንና ሁኔታዎቹን አይቼ በዕድለኛነቴ ተደሰትኩ።

ለእኔ የኬምብሪጅ ሕይወት እንደከተማው ውበት ያማረ ነበር የሆነልኝ። በትምህርት አሰጣጡ ረገድ፣ ከዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ እና ምናልባትም ከሌሎች ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች የሚለይበት አንድ ዋና ጉዳይ አለው። ይኸም እያንዳንዱ ተማሪ አንድ አንድ የራሱ አካዳሚያዊ ነፍስ አባት አለው። ቲዩተር ወይም ሱፐርቫይዘር ይሉታል። ወደ ትምህርት ክፍል መግባትን ማስታጎል፣ ወይም የፈለጉት ዘንድ ሔዶ አልፈለጉት ዘንድ አለመሄድ ይቻላል። የአካዳሚያዊ ነፍስ አባቱን ሳምንታዊ «ድርሰት» ግን ማስታጎል አይቻልም! የትምህርት አሰጣጡ መሠረት ነውና። የማጠናው "PPE" የሚባለው ሆኖ ትምህርቱ The Economics

Tripos የሚሰኝ ነበር። በምጣኔ ሀብት ሳይንስ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ሁለተኛ ዓመት ላይ ፖሊትክስን እና ሶስዮሎጂን ያካተተም ነበር።

እዚያ በነበርኩበት ጊዜ ሰር ዊንስተን ቸርችል፣ የቸርችል ኮሌጅን የመሠረት ድንጋይ ለማኖር መጥተው፣ በኔ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ ሲያልፉ ፎቶ ላነሣ ስል አንድ የእንግሊዝ የደህንነት ሠራተኛ መጥቶ ከፊቴ ተጋርጦ አፈጠጠብኝ። ሰውዬው ከማርጀታቸውም በላይ ደቦልቦል ያሉ ስለነበሩ፣ ገና ከመኪናው ለመውጣት ሲፍገመገሙ እንዳላነሳቸው ለማጨናገፍ መሰለኝ። እኔ አጉል አኳኋን ላይ እያሉ ለማንሳት አንዳችም ፍላጎት እንዳልነበረኝ አላወቀም።

በሌላ ጊዜ፣ ንግሥቲቱም እንዲሁ እኛ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ መጥተው በቅርብ አይቻቸው በፎቶ ከማያቸው ይበልጥ ጠና ያሉ ሴት መሆናቸውን አይቼ፣ መገረሜ ትዝ ይለኛል። ፈላስፋውን ቤርትራንድ ረሰልን ግን፣ በካም ወንዝ ላይ ሲንሳፈፍ ነበር ያየሁት። ከአድናቂዎቹ አንዱ ስለሆንኩ ደስ ነበር ያለኝ ሳየው። ያን ጊዜ ዘጠናው ውስጥ የነበረ መሰለኝ።

በኔ ኮሌጅ (ኪንግስ) ምሳና ቁርስ አሻ ቦታ መመገብ ይቻላል። እራት ግን በምግብ ቤት አዳራሽ (የኮሌጁ መሪና ሊቃውንቱም ባንድ ጥጋት ዝቅ አለች መድረክ ብጤ ላይ ይመገባሉ) ተገኝቶ መመገብ የትምህርቱ አካል ተደርጎ ስለሚቆጠር፣ መመገብ ግዴታ ነው። ሥነ ሥርዐቶችም አሉት።

ሌላው የዚህ ኮሌጅ የማይረሳ ገጽታ፣ ተማሪው የራሱ ምርጥ የመጻሕፍት ክምችት እንዲኖረው የሚበረታታበት ስልት ነው። ይኸውም፣ አንድ ተማሪ በአንድ ተርም ለመጻሕፍት መግዣ 12 ፓውንድ ካወጣ፣ 5 ፓውንድ ኮሌጁ ይጨምርለታል። ነገር ግን ተማሪው በዚያ ገንዘብ የሚገዛቸው መጻሕፍት በሚማረው ሳይሆን በሌላ ዕውቀት ዘርፍ ላይ እንዲሆን ይበረታታል።

በኬምብሪጅ ዩኒቬርሲቲ ያልነበረ ዐይነት ክበብ (ማኅበር) አልነበረም፤ የትምህርት፣ የጥበባት፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ... በውነቱ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ራስ ፈልጎ አባል የሚኮንባቸው ዐይነት ሲኖሩ፣ ሌሎች (ጥቂቶች) በግብዣ እንጂ፣ ራስ በመፈለግ አባል የማይኮንባቸው ነበሩ። ከነዚህ ያንዱ ለመሆን በቅቼ ነበር።

የኬምብሪጅ ዩኒቬርሲቲ የአፍሪካ ተማሪዎች ክበብም ነበር። በሁለተኛው ዓመቴ ፕሬዚደንትነት ተመርጬ ነበር። እንዲሁም የኢትዮጵያ ተማሪዎች በእንግሊዝ ሀገር ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆኜ ነበር።

በሄድኩበት ዓመት፣ ለገና ዕረፍት ሲዘጋ፣ ወደ ለንደን ሔድኩኝ። ብዙ ኢትዮጵያውያንም አገኘሁና ተዋወቅሁ። በወቅቱ አምባሳደሩ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን የነበሩ ሲሆን፣ የባህል አታሼው ጋሽ አበበ ከበደ ነበር።

### በሥራ ዓለም

ከሦስት ዓመታት የትምህርት ገበታ ቆይታ በኋላ፣ ከእንግሊዝ አገር ወደ ኢትዮጵያ መስከረም 21 ቀን 1955 ተመለስኩ። መመለሴን ለማሳወቅ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሔድኩ። ለሥራ የሚመድብህ የንግድና ኢንዱስትሪ

ሚኒስቴር ነው ተባልኩና፣ ወደዚያ የምወስደውን የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ደብዳቤ ለመውሰድ እንድመለስ አጭር ቀጠሮ ተሰጠኝ።

ከትምህርት አስደሳችና ጣፋጭ ዓለም ወደ እውነተኛው የጣጣ ዓለም ከመግባቴ በፊት፣ ለራሴ የአንድ ወር ዕረፍት ሰጥቼ ነበር። ደግሞም፣ ምናልባት እማልፈልገው ቦታ ማንም እንዲመድበኝ ስላልፈለኩ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሳልመለስ ቀረሁ። ፈልጌው የነበረው የ2ኛ ደረጃ መምህርነት ስምሪት ጉዳይ ገና ቀደም ሲል ስለ ከሸፈ፣ ዕረፍቴን እንደ ጨረስኩ የመምህርነቱን ጉዳይ ትቼ ወደ ሌላ ሥራ ሳተኩር ሐሳቤ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ላይ ነበር ያረፈው። የውጭ ጉዳዩን ነገር በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሳቢያ፣ ወዲያ ጣልኩና በልማት ባንክ ላይ አተኮርኩ። የትምህርት ቤት አብሮ አደጌ ንጉሴ ዘሪሁንም እዚያ መሆኑን ሰምቼ ሔጄ አማከርኩት። በርሱ አማካይነት ከዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ የመጀመሪያ ዙር ተማሪና ምሩቅ ከሆነው ከተሾመ ገብረ ማርያም ጋር ተዋወቅሁ። የባንኩ የሕግ ክፍል ኃላፊ ነበር።

ሆኖም፣ ባልጠበኩት አጋጣሚና ሁኔታ፣ ዓርብ ኅዳር 7 ቀን 1955፣ ጃንሆይ ዘንድ ቀርቤ፣ ኂላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት የተባለውን ተቋም ማቋቋም ተግባር ላይ ተመደብኩ። እውነቱን ለመናገር፣ አስቀድሞ ነገሩን ዐውቄው ቢሆን ኖሮ፣ ፈቅጄ የምገባበት ሁኔታ አልነበረም። የቤተ መንግሥቱን ሥርአት ቀርቶ፣ የቢሮክራሲውን እንኳ ገና በወሬ እየጠገብኩት ነበር እንጂ የማውቀው ዓለም አልነበረም። የሰማሁትም የሚስበኝ አልነበረምና።

ይሁንና፣ ‹‹ነገ በ 5 ሰዓት ይዘኸው ና ተብያለሁ›› ብሎ ሐሙስ በ11 ሰዓት ተኩል አቶ አበበ ከበደ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ዋና አስተዳዳሪ ሲነግረኝ፣ የሥራ ስምሪት ሐሳቤ ሁሉ ባልተጠበቀና እምቢ ሊባል በማይቻልበት አኳኋን ተቋጨ። አቶ አበበ ከበደ፣ ገና ተማሪ ሆኜ የማውቀውና የማከብረው፣ ለዓለሙ ሁሉ ቅን አሳቢና መንፈሳዊ ሰው ነበር። እኔን ለመጥቀምም እንዳደረገው አልጠራጠርም። ግን፣ አስቀድሞ ቢያማክረኝ ኖሮ እመርጥ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ አቶ ብለው፣ በልቤ ጋሼ እያልኩ ነው። በማግስቱም በቀጠሮዬ ሰዓት ተገኝቼ፣ ከጋሽ አበበ ጋር ከቢሮው ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት አመራን። እኔ ከርሱ ጋር ሰተት ብዬ ወደ ውስጥ የምዘልቅ መስሎኛል። ነገር ግን እንደዚያ አልሆነም።

ግቢው ውስጥ እንደ ገባን፣ ጥቂት ርቀት ከሔድን በኋላ አንድ ነጥብ ላይ ስንደርስ፣ አንድ ከልካይ አቆመንና ጋሽ አበበን ከነመኪናው ሲያሳልፈው፣ እኔ ወረድኩ። በግራችን በኩል ሰብሰብ ወዳሉ ሰዎች በጁ አመለከተኝና ሄጄ ቆምኩ። ሰልፍ አልነበረም፤ እንዲሁ እጅብ ብለው ነው የቆሙት። ባይኔ ስቃኝ አንድም የማውቀው ሰው እነርሱ መካከል አልነበረም። በጠቅላላ ሁኔታው እየተገረምኩ ዙሪያዬን ስቃኝ፣ ከኛ ጥቂት ከፍ ብሎ ደግሞ፣ ልክ እንደኛው ሌላ ስብስብ ታዬኝ። እሁለታችንም ዘንድ አንድ አንድ አስተናባሪ (አጋጅ፣ ከልካይ ወይም አጋፋሪ) ነበር።

ከላይ የሚጣራ ድምፅ  ተሰማና፣ የመከላከለኛው አስተናባሪ ወደኛ በኩል በስም ተጣራ፤ ከመካከላችን አንድ ሰው ተለቀቀና ሔደ፤ ግን ከበላያችን በኩል ካለው ስብስብ አላለፈም፡፡ ብዙም ሳልቆይ፣ የቀደሙኝንም ብዙዎች ቀድሜ፣ ሁለተኛውን ስብስብ ተቀላቀልኩ፡፡ እዚያ አንድ ከአውሮፓ የቴክኒክ ነገር አጥንቶ ከተመለሰ ወጣት ጋር ተዋወቅን፤ ቅብጥብጥ ብሏል፡፡

ድንገት ተከታትለን ተጠራንና በረንዳው ጋር ስንደርስ ‹‹እሱጋ ቆዩ›› ተባልን ፡፡ ወጣቱ መቅበጥበጡ በዛበት፤ የኔ ዝም ብሎ ነገሮችን ማስተዋል ምን እንደመሰለው አላውቅም፡፡ ብቻ፣ ‹‹ድንገት በጥያቄ ማፋጠጥ ይወዳሉ አሉ›› አለና ማስታወሻዎች ከኪሱ አውጥቶ፣ ልክ ፈተና እንደሚገባ ተማሪ፣ አንዴ አንዱን ቅጠል አንዴ ሌላውን ይመለካከት ገባ፡፡

ከዚያ ድንገት ተጠራሁና ደረጃውን ወጥቼ ከጋሽ አበበ ጋር እላይ ተገናኝቼ ወደ ውስጥ ገባን፡፡ ጃንሆይ ምን እንደተማርኩ ከጠየቁኝና ከመለስኩ በኋላ፣ ‹‹ነዋሪነት ያለው የሽልማት ድርጅት ለማቋቋም ካሰብን ቆይቷል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ቆየ፡፡ አሁን ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለማቋቋም ተነሥተናል፡፡ የአስጠራንህ ለዚህ ነው››አሉ፡፡

የሽልማቱ ድርጅት መቋቋም ትኩረት የሰጡት ጉዳይ ነበረና፣ ስለ ጥቃቅን ዝርዝር ሁሉ ይከታተሉ ነበር፡፡ ይህ የሆነው፣ ሊታሰብ ወይም ሊገመት እንደሚችለው፣ በግል ገንዘባቸው የሚያቋቁሙት ድርጅት ስለሆነ አልነበረም፤ ወይም አቃቂር አውጪዎች ማለት እንደሚወዱት፣ ለግል ዝናቸው ሲሉ አልነበረም፡፡ ይህም የሚታወቀው፣ የሽልማት ድርጅት በግል ገንዘባቸው ለማቋቋም የአነሣሣቸውን ምክንያት ስናስተውል ነው፡፡

አንድ ቀን ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ አሉን፤ ከጋሽ አበበና ከእኔ ሌላ ልዩ ጸሐፊያቸው አቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያምም ነበር፡-

> የኖቤልን የሰላም ሽልማት ልናገኝ ነበር፡፡ በአንድ ድምፅ ተበልጠን፣ የካናዳው ዕጩ ተሸለሙ፡፡ ይህን ስንሰማ ቆጨን፡፡ ደግሞም ምን የቀረብን የጎደለብን ነገር አለና ነው ብለን አሰብን፡፡ ግን፣ እኛን መጀመሪያ እንዲህ ከቆጨን ለሌላውማ … በማለት ሽልማት የሚያተጋ መሆኑ ተሰማን፤ እኛስ ለሀገራችን እንደዚህ የሚያተጋ የሽልማት ድርጅት ለምን አናቋቁምም ብለን ያሰብነው ያኔ ነው…ጊዜው ስላልደረሰ ቆየ፡፡ አሁን እግዚአብሔር ፈቅዶ ጊዜው ስለደረሰ ነው፡፡

አስቤውና ፈቅጄው የገባሁበት ሥራ የነበረ ባይሆንም፣ ከገባሁበት በኋላ ይህን ያህል አስቸጋሪ ሆኖ  አላገኘሁትም ነበር፡፡ እርግጥ፣ መጀመሪያ ላይ፣ ስለ እጅ አነሣስ፣ ጃንሆይ እንጂ ‹‹እሳቸው›› አለመባል … ወዘተ ዐይነት የሥነ-ስርዓት ጉዳዮች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ ነገሮች በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች የራሳቸውን አንጻራዊ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ውጤቶች ሆነው ነበር የሚሰሙኝ፡፡ እኔ ቁብ ባለኝ ነገርና እነሱ ቁምነገር በሚመስሏቸው ነገሮች መካከል ልዩነት ነበረ፡፡ በተለይ እኔ የምፈልገውና ሌሎች የሚፈልጉት የተለያየ

በመሆኑ ለግጭት የሚገፋፋኝ ነገር ብዙ አልነበረም፡፡ ይኸ ኋላም በቢሮክራሲው ውስጥ የቀጠለ ልዩነት ነበረ፡፡

ነገር ግን፣ በጃንሆይ ቀጥታ እይታ ሥር እና ከጋሽ አበበ ከበደ ጋር መሥራት ምንም አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ እንዲያውም አርኪ ነበር፡፡ የማቀርብላቸውን ማንኛውምን ማስታወሻ በዝርዝር አንብበው፣ ምን ጊዜም አስተያየትና ጥያቄ ይኖራቸዋል፡፡ በማስታወሻው ላይ፣ በቀይ ያመለክታሉ፤ ይጽፋሉ፡፡

እንደዚህ ያደርጉ የነበረው፣ የድርጅቱን ጉዳይ የተለየ አድርገው ያዩት ስለነበረ ሳይሆን፣ በማናቸውም ጉዳይ ቢሆን ያው ነበር፡፡ ለዚህ እንደ አብነት ሊቀርብ የሚችል ምሳሌ አለ፡፡ በአንድ ወቅት፣ ጸጋዬ ገብረ መድኅንን ቲያትር በኢትዮጵያ እንዴት እንዲሆን እንደሚያስብ ማስታወሻ አቅርብ ብለውት አቀረበ፡፡ ማስታወሻውን አይተው ሲመልሱለት ቀይ በቀይ ሆኖ ነበር - በአስተያየት እና በጥያቄ (ስለዚህ ጉዳይ እኛ እንዲህ ይሁን ብለን አዘን አልነበረም ታዲያ? የሚል ዐይነት)፡፡

እንዲሁም፣ የሽልማት ድርጅቱ ለተሸላሚው የሚሰጠውን በአንገት የሚጠለቀውን ሜዳሊያ እና የምስክር ወረቀት ለመወሰን፣ አንድ ቅዳሜ ቀን ጠዋት በደብረ ዘይት ቤተ መንግሥት ንድፉ እንዲቀርብ አዘዙ፡፡ ሠዓሊ አፈወርቅ ተክሌ እና እኔ ከሦስት ሰዓት ጥቂት ቀደም ብለን ደርሰን ግቡ ተብለን ስንገባ፣ እዚያ አለው ቢሯቸው ጠረጴዛ ላይ ከተከመሩ ፋይሎች መካከል መረጥ አድርገው አንዱን ሲመለከቱ አየሁ፡፡ የጀመሩትን ከፈጸሙ በኋላ፣ መነጽሩን አውልቀው አንዱ ፋይል ላይ አኑረው ተነሥተው ቆሙ፡፡ እንደ ቆሙ ዲዛይኖቹን ተመልክተው ከሠዓሊው ጋር ተነጋገሩና አስተያየታቸውን ሰጥተው አሰናበቱን፡፡

ጋሽ አበበ ከበደ በጣም ቀና እና ለሰው አሳቢ ነበር ብያለሁ፡፡ እርሱ የዚያ ሰፊ ደርጅት፣ የቀ.ኃ.ሥ. በጎ አድራጎት ድርጅት ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ ከሚያገኘው ደሞዝ የ50 ብር ብልጫ ያለው ደሞዝ ነበር ማስታወሻ አቅርቦ ያስፈቀደልኝ፣ ወደ ቢሮና ወደ ቤት መመላለሻ መኪናና ሾፌር ከቤተ መንግሥት ተመድቦልኝም ነበር፡፡ ነገር ግን፣ እኔ ነገሩ እጅግ ስለከበደኝ ከሳምንት በኋላ ይቅርብኝ ብዬ አስቀረሁ፡፡ በዚያን ሰሞን፣ ገና ከውጪ ለመጣ ምሩቅ፣ በሥራ እሰኪመደብ እቴጌ ሆቴል በነጻ የማረፍና ለመቋቋሚያ የሚሆን ገንዘብ (መጀመሪያ ላይ 5,000 ብር ያለ ወለድ ነበር) 2,000 ብር እና ከሞርጌጅ ባንክ በ 3.5% በሁለት ዓመት የሚከፈል ብድር የማግኘት መብት ነበረው፡፡ በዚህ ተጠቅሜ እና 2,000 ብር ተበድሬ ጨምሬ የራሴን መኪና ለመግዛት ወሰንኩ፡፡

ጋሽ አበበ ይህን ሲሰማ አልተስማማም፤ ገና የወር ደሞዝ ሳትበላ ዕዳ ውስጥ ትገባለህ? ነበር ያለኝ፡፡ ስለዚህ፣ መኪና መግዣ 10,000 ብር እንዲሰጠኝ ለጃንሆይ እንዳመለክት ጠይቆኝ ነበር፡፡ በምን አገልግሎቴ በማለት እምቢ ብዬ እኔ ባሰብኩት መንገድ አሳካሁ፡፡

*ሥራው* እየጣመኝና ወደ ውስጡ እየዘለቅሁ ሳለሁ፣ እንዲያውም የኖቤል ሽልማት ድርጅትን በመጎብኘት ላይ እያለሁ፣ አዲስ ክስተት መጠንሰስ ጀመረ። ከዚያ ጉብኝት ተመልሼ ብዙም ሳልቆይ፣ ወደ ሌላ መ/ቤት ትፈለጋለህ ተባለ። ይሁንና፣ በዚህ በሽልማት ድርጅት ምደባዬ ሳቢያ፣ ያልጠበቁኳቸውን ዕድሎች አገኘሁ።

1. በኢትዮጵያ ጥበባት ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩትን አብዛኛዎቹን ባለሙያዎች ለማወቅ እና ከአንዳንዶቹም ጋር በቅርብ ለመተዋወቅ በቃሁ። በሌሎቹም ሽልማት በሚሰጥባቸው ዘርፎች ስለተሰማሩ በተለይ ወጣት ባለሙያዎች የተሻለ ግንዛቤ አገኘሁ።
2. ከአልፍሬድ ኖቤል የሽልማት ድርጅት እና ኃላፊዎች፣ አንዳንድ የኮሚቴዎች አባላትን ለማነጋገር ቻልኩ። ስለሌሎች የተለያዩ ሽልማት ሰጪዎች ዜናዎች አገኘሁ።

በሥራዬም፣ የእይታዬ አድማስ ሰፋ ማለቱ አልቀረም። የቢሮ ሜራዎችም በርቀት ወላፈናቸው ደረሰኝ።

በገንዘብ ሚኒስትሩ ጠያቂነት፣ ሰኔ 15 ቀን 1955፣ *በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ማቋቋም* ተግባር ላይ በተሠማራሁ በሰባተኛ ወሬ፣ የሽልማት ድርጅቱ መቋቋም ይፋ ሊሆን አንድ ወር የሚያንስ ሲቀረው፣ በጽሕፈት ሚኒስቴር ደብዳቤ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተዛወርኩ። *መምሪያ ኃላፊ* ተደረግሁ።

በገንዘብ ሚኒስቴር *መጀመርያ* ላይ የገጠመኝ አስቂኝ ድራማ ነበር። የመዝገብ ቤት ዶሴ አከናዋኝ ፋይሎች ተሸክሞ መጣና፣ ‹‹ታይቷል ይቀመጥ ይበሉና ፓራፍ ያርጉልኝ›› ይለኛል። *መጀመርያ* ላይ ተናድጄ፣ ‹‹ለዚህ ነው እንዴ፣ እኔን ወደዚህ ለማዘወር ያ ሁሉ ሙግት ጃንሆይ ዘንድ ሦስት ጊዜ በሚኒስትሩ ተደረገ የተባለው?›› አልኩ በልቤ። ሆኖም፣ ፋይሎቹን ጠረጴዛዬ ላይ እንዲተዋቸው ነገርኩት። ከዚያ እኔን ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ለማዛወር በተደረገው ውይይት ላይ፣ የሚባለውን ያዳመጠ አንድ ከፍተኛ ባሥልጣን፤ ‹‹እኝህ ሰውዬ ይኸን ያህል እንዲዘዋወርላቸው ከፈለጉ፣ ምናልባት ለአንድ ትልቅ ቦታ አጭተውት ይሆናልና፣ የልጁን እንጀራ ለምን ትዘጋበታለህ? አሉኝ›› ብሎ ጋሽ አበበ ያለኝን ሳስታውስ፣ የባሰ ገረመኝ፤ እንቆቅልሽ ሆነብኝ።

ሌላም ነገር ታሰበኝ። የጽሕፈት ሚኒስቴር የዝውውር ደብዳቤ ደርሶኝ ወደ አዲሱ *መሥሪያ* ቤቴ የመጣሁ ሰሞን፣ ሚኒስትሩ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሮአቸው አነጋገሩኝ። ከዚያ ቀደም በዝናና በመልክ ብቻ ነበር በሩቅ የማውቃቸው። ከነገሩቸው ውስጥ ትኩረቴን ይበልጥ የሳበው፣ ‹‹በትምህርት ረገድ መልካም ተዘጋጅተሃል፤ አሁን ደሞ የቢሮክራሲውን አካሔድ መማር ይኖርብሃል›› የሚለው ነበር። በውስጤ ግን የነበረው አጸፋ፣ ‹‹እሱንማ ተምሮ መቀጠል ሳይሆን፣ ዐውቆ መቀየር ነው›› የሚለው ነበር። ይሁንና፣ ፍየል

ከመድረሱዋ ቅጠል መበጠሱዋ ዐይነት እንዳይሆንብኝ ረጋ ብሎ ማየትን ወሰንኩ።

የመዝገብ ቤቱ ዶሴ አከናዋኙ ከተዋቸው ፋይሎች መካከል አንዱን ገልጬ ማንበብ ጀመርኩ። ከአንድ ሚኒስቴር ለሌላ ሚኒስቴር ሲጻፍ ለገንዘብ ሚኒስቴር የተደረገ ግልባጭ እንጂ ቀጥታ የተጻፈ አይደለም። ከሥር ያሉትንም አንድ ሦስት አራት እንደዚሁ አነበብኩ። ግልባጮች ይሁኑ እንጂ ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ስለተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ታዲያ ለምን አንድ ዶሴ ውስጥ ሆኑ? አንድ ሁሉንም የሚያገናኝ ነገር መኖር አለበት። መቼም አለ ምክንያት አንድ ላይ አልሆኑም፣ አልኩ ለራሴ። እንደ መጽሐፍ ርእስ የዶሴውን ስም አየሁ። የሚያያዝበት ክር ለጊዜው አልታይህ አለኝ፤ ምናልባት ከፋይሉ መነሻ ጀምሬ ሁሉንም ባነብ ሊታየኝ ይችል ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ሆኖም፣ እርሱን ትቼ አንድ ሁለት ፋይሎችንም እንደዚሁ አደረግሁ። እንደ መጀመሪያው ሁሉ ግልባጮች የበዛባቸው ናቸው። ሆኖም፣ ገንዘብ ሚኒስቴር ለዚህ ወይም ለዚያ መሥሪያ ቤት የጻፋቸው ደብዳቤዎች ቀሪዎችም ነበሩባቸው።

በዚህ በዚህ ብዙ ጊዜ አሳልፌ ኖሮ፣ ከቢሮ መውጫ ሰዓት ደርሶ ኖሯል፤ የሰዎች ኮቴ በኮሪዶሩ ውስጥ በብዛት በመስማቴ ብቻ ሳይሆን፣ በመስኮት እንቅስቃሴም አየሁ። ሰዓቴ ለሰባት ጥቂት ቀረው ይላል። በዚያን ጊዜ (ክረምት 1955) የሥራ ሰዓት ጧት በ3 ስዓት ተገብቶ እስከ 7 ሰዓት፣ ከቀትር በኋላ በ9 ሰዓት ተገብቶ እስከ 12 ሰዓት ነበር የመንግሥት የሥራ ጊዜ። ከቀትር በኋላም፣ የጠዋቱን በመድገም የፋይል ክምሩን ጨረስኩና፣ የመጨረሻ የሆኑትን የየላይኞቹን የደብዳቤዎች ግልባጮች ግርጌ ‹‹ታይቷል›› እያልኩ፣ አዲስ በፈጠርኩት አጭር ፊርማ ምልክት እያደረኩ ጨረስኩኝ፤ ከሁሉም ወፍራም የሆነውን ፋይል ብቻ አስቀርቼ፣ ሌሎቹን በተላላኪ ወደ መዝገብ ቤት ላኩ።

ትንሽ ቆይቼ ዶሴ አከናዋኝ የተባለው ሰውዬ መጣ። ‹‹አንድ ፋይል ቀርቶዋል። አልጨረሱትም?›› አለኝ። መናደዱን ትቼ፣ ‹‹በጣም የሚፈለግ ነው እንዴ?›› አልኩት።

የፌዝ ቃናው ያመለጠው አልመሰለኝም። ‹‹አይ›› አለና ተቅለሰለሰ። ወዲያው፣ ‹‹ለማስታወስ ነው›› ብሎ ሊወጣ ከበሩ ላይ ሲደርስ፣ ‹‹አቶ አበበ›› አልኩት። አለበት ድርቅ ብሎ ቀረ። ወዲያው ግን አቤት አለና ወደ እኔ ቀልጠፍ ብሎ መጣ። ‹‹እነዚህን መሰል ዶሴዎች ብቻ ለእኔ እንድታቀርብ ብሎ ያዘዘህ ማነው?›› አልኩት። ‹‹የመዝገብ ቤት ሹሙ ናቸው፣ ታይቷል ይቀመጥ ብለው ምልክት እንዲያደርጉባቸው ነው ወደ ርስዎ የላኩኝ›› አለኝ። ‹‹እግዜር ይስጠልኝ›› አልኩትና ወጣ።

ውዬ ሳድር እንደሰማሁትና እንደተገነዘብኩት፣ አስተዳደሩ ብዙ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንን መቅጠር አይወድም። የነሱ በርከት ብሎ ተቀጥሮ ሥራ መልመድ፣ ለነባር ሠራተኞች እንደ የወደፊቱ አደጋ የሚታዩ ነበሩ። ከውጭ የሚመጡት

ደግሞ፣ የአገለገሉ የዱሮ ሹማምንት ተፎካካሪዎች ይሆናሉ፣ የሚል ትክክለኛ ሥጋት ነበር፡፡ ክፋቱ ግን፣ ሚኒስትሩ ሚኒስቴሩን በተማሩ ሰዎች ለመሙላት ይፈልጋሉ! ያም ሆነ ይህ፣ እኔ ወፍራሙን ፋይል ከዳር እስከ ጫፍ ለመውጣት ወስኜ ተነሣሁ፡፡ እውነቱን ለመናገር ብዙ ነገርም ተገነዘብኩበት፡፡

ጥቃቅን ሊባሉ ከሚችሉት መካከል፣ እንደ እናሳስባለን፣ እንገልጻለን፣ እና ስታውቃለን ያሉ፣ የበታች፣ የእኩያ እና የበላይ ድምፀት ያላቸው የደብዳቤ አዘጋጎች ነበሩ፡፡ ሌላው፣ የደብዳቤዎቹ ባህርይ አጠቃላይነት ሲሆን፣ አሻሚ ትርጉም ሊሰጣቸው ወይም ለመካድ የሚያመቹ መምሰል ነው፡፡ ‹‹በሕጉና በደንቡ *መሠረት እንዲፈጸም አስታውቃለሁ››* ሲል፣ የመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት ቁርጥ ያለ ትእዛዝን ሲያመለክቱ፣ የቀደመው ንኡስ ሐረግ ደግሞ ቁርጠኝነቱን ያረግበዋል፡፡

በዚህ መካከል፣ አንድ ቀን መለሎ የነበረው የሚኒስትሩ ተላላኪ መጥቶ፣ ‹‹ክቡርነታቸው ይምጡ ብለዋል›› አለኝ፡፡ አብሬው ሔድኩ፡፡

‹‹የጽሕፈት ሚኒስቴሩ ደብዳቤ ጉዳይ ከምን ደረሰ?›› አሉኝ፡፡

‹‹እኔ ምንም የደረሰኝ ነገር የለም፣ ጌታዬ›› አልኩኝ፡፡

ስለምን ጉዳይ የተጻፈ መሆኑን ነገሩኝና፣ ‹‹ስለዚህ ጉዳይ ምንም አታውቅም?›› አሉኝ፡፡

‹‹ስለ ደብዳቤውም ሆነ ስለጉዳዩ አሁን ገና ከክቡርነትዎ መስማቴ ነው›› አልኩኝ፡፡

‹‹ምክትል ሆነህ እንዴት አታውቅም?›› አሉ፣ ጥፋተኛ ነህ በሚል ድምፀትና ወደፊት አውቀህ መገኘት አለብህ በሚል አንድምታ፡፡ ከዚያ እጅ ነስቼ ወጣሁ፡፡ ነገሩ እየተደጋገመ፣ እሳቸው ቆጣ ቆጣ እያሉ ሲሔዱ ‹‹ጌታዬ እኔ ዘንድ የማይደርስን ነገር እንዴት ማወቅ እችላለሁ?›› አልኳቸው፡፡

‹‹እኔ የአንተ መዝገብ ቤት ልሁና›› አሉ፡፡

‹‹አንድ ደብዳቤ ከክቡርነትዎ ወይ ካለቃዬ ካልተመራልኝ ወይም መዝገብ ቤት ካልላከልኝ ምን ማድረግ እችላለሁ፤ መዝገብ ቤት የሚልክልኝ የታይቷል ይቀመጥ ደብዳቤዎች ነው የማውቀው፡፡ ለምሳሌ›› ስል፣

‹‹ተወው ሒድ ወደ ቢሮህ›› አሉና ወጣሁ፡፡

ከዚያ ሳምንታት ቀይቶ አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ቢሮዬን ከፍተው ዘው አሉ፡፡ እኔ አቀርቅሬ ፋይሎቼን እያጣጣምኩ ነበረ፤ ፈጥኜ አፈፍ አልኩ፡፡

‹‹ሲኒየር [ከፍተኛ] ረዳቶቼን ፈልጌ ቢሮአቸው አላገኝም፤ እንዴት ነው ሥራ የሚሠራው? ተፈሪን ፈለግሁት፣ ቢሮው የለም፡፡ ወልደ ማርያምን ፈለግሁት፣ የለም፡፡ …ያ የአንተ አለቃም የለም፡፡ ... ዲግሪ! ዲግሪ! … ይላሉ ግምባራቸው ላይ ለጥፈውት ይሒዱ፣ እርሱ ይሠራላቸው እንደሆነ..›› በሆነ ነገር ተበሳጭተዋል፡፡ እኔ ዝም ብዬ ቆምኩ፡፡ ቢሮው ውስጥ ጥቂት ጎርደድ ጎርደዱ

ካሉ በኋላ ወጡ፤ ከኋላቸው ተከተልኩ። ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት አመሩ…

የገንዘብ ሚኒስቴር የበጀት ኮሚቴ አባል እንድሆን መወሰኑ ከአስተዳደር ተጻፈልኝ። የዚህ ኮሚቴ ተግባር፣ ከየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርበውን የበጀት ጥያቄ በዝርዝር የሚመለከት፣ የየመሥሪያ ቤቶቹን የበጀት ጉዳይ ኃላፊዎች ጠርቶ እንዲያስረዱ እና እንዲያሳምኑ የሚጠይቅ፣ የዓመታዊው የመንግሥት የበጀት ዝግጅት ሒደት የመጀመሪያ ደረጃ አካል የነበረ ነው።

ከዚህም በላይ የተጠቃለለው ይህ ዓመታዊ የመንግሥት ልዩ ልዩ አካላት የበጀት ጥያቄ ሰነድ፣ ስለ መንግሥት የአስፈጻሚው ዘርፍ፣ በተለይም የጠያቂ ሚኒስቴሮችን አደረጃጀትና አወቃቀር ለማጥናት የሚያመች ገጽታ አለው። በተለይም ጥያቄዎቹን ለማስረዳት በሚጥሩበት ወቅት የሚገኘው መረጃ የማይገኝ ነው።

ከነዚህ ሁሉ ገጠመኞች ያስተዋልኩት አንድ ነገር፣ የመሥሪያ ቤቶችን አስተዳደሮች (ሠራተኞች፤ ገንዘብና ንብረት የማስተዳደር ሚና የተሰጣቸው)፣ ዘይትና ቅባት የመኪናን እንቅስቃሴ የማቀልጠፍ ሚና እንደሚጫወቱት ዐይነት እንዲያገለግሉ ቢፈጠሩም፣ እውነታው በተገላቢጦሽ ግን፣ የሥራው ባለቤት ከሆኑት ዋነኞቹ ዘርፎች ይልቅ ራሳቸውን የሚያስቀድሙ አዛዦች መሆናቸውን ነበር። ይኸም፣ አስተዳደር ለድርጅት ህልውና ሲባል ሳይሆን፣ ድርጅት ላስተዳደር ህልውና ሲባል የተፈጠረ የሚያስመስል ነበር።

ክቡር ሚኒስትሩ ድንገት ቢሮዬ መጥተው ከነበረበት ጊዜ በኋላ ወደ ቢሮአቸው አላስጠሩኝም። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን፣ ከበጀት ጥናት (ለኔ ግን ዶሴ ጥናት) ዋና ክፍል፣ ወደ ፋይናንስ፣ ክሬዲትና ኢንቬስትመንት ዋና ክፍል በምክትልነት ተዛወርኩ። አለቃዬ የገንዘብ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር እና የኢታብ (ኢኮኖሚክ ኤንድ ቴክኒካል አሲስታንስ ቦርድ) ዋና ጸሐፊ ነበር።

የበጀት ጥናት ዋና ክፍል ‹‹ሥራዬን›› ዮፍታሄ ከበደ የሚባለው የኮሌጅ ጓደኛችንና የኢታብ ወጣት ኢኮኖሚስት ተዛውሮ ተረከበ።

ዶሴ አከናዋኙ እንደለመደው ፋይሎቹን ተሸክሞ ይመጣና ‹‹ታይቶአል ይቀመጥ ብለው ምልክት ያርጉልኝ›› ይለዋል።

‹‹ለዚህ ነው ይህንን ያመጣህልኝ?›› ብሎ ይጠይቀዋል።

‹‹አዎን›› ይለዋል ዶሴ አከናዋኙ።

‹‹እንግዲያው፣ ታይቷል ይቀመጥ የሚል ማኅተም አሠራና እዚያው አንተው እያተምክ አስቀምጠው›› ይልና ያመጣውን ይዞ እንዲሔድ ያደርገዋል። ከዚያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ገንዘብ ሚኒስቴርን ለቆ ወጣ።

ኢታብ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የቴክኒክ (ማለትም፣ የባለሙያና የቁሳቁስ) እርዳታን ጉዳይ የሚመለከት ቋሚ የሚኒስትሮች ኮሚቴ (ወይም ቦርድ) ጽሕፈት ቤት መጠሪያ ነበር። ጽሕፈት ቤቱ ገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ለመገኘት የበቃው፣ የቦርዱ ሰብሳቢ የገንዘብ ሚኒስትሩ፣ ዋና ጸሐፊውም በገንዘብ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር ስለ ነበሩ ነበር።

እኔ የተዛወርኩበት ዋና ክፍል የገንዘብ ሚኒስቴር መደበኛ አካል የነበረ ነው። በርሱ እልቅና ሥር የነበርነው በርካታ ሠራተኞች ብንሆንም፣ እኔና አንድ ጸሐፊ ብቻ ነበርን የገንዘብ ሚኒስቴር ሠረተኞች እና ደሞዝተኞች የነበርነው። የተቀሩት፣ በፈረንጂኛ ምህፃረ ቃሉ ኢታብ (ኢኮኖሚክ አንድ ቴክኒካል አሲስታንስ ቦርድ) በመባል የሚታወቀው የሚኒስተሮች ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ተቀጣሪዎች ነበሩ። ረዳት ሚኒስትሩ ተሹሞ ሲዛወር፣ በእርሱ እግር አንድ ዋና ዲሬክተር፣ በሁለቱም ዘርፍ፣ ተተካ።

እኔ የተዛወርኩበት ዋና ክፍል ሁለት ኃላፊነቶች እና ከነሱ ጋር የተያያዙ ተግባራት ነበሩት። የመጀመርያውና ክፍሉ የሚታወቅበት የውጭ አገር የብድሮችን ሁኔታ መከታተል፣ መመዝገብ እና የዕዳዎቹ የዋና እና የወለድ ክፍያ በስምምነቱ መሠረት ወቅቱ ዝንፍ ሳይልና መቀጫ ሳያስከተል እንዲከፈል ማድረግ ነበር። ለዚህ ደግሞ፣ የየዓመቱ የዕዳ መክፈያ ገንዘብ በበጀት እንዲያዝ፣ በብሔራዊ ባንክም በኩል የውጭ ምንዛሪው በተፈለገው የውጭ ገንዘብ እንዲከፈል፣ ሁኔታዎችን እንዲያውቁ ማረጋገጥ ነበር።

የብድር ገንዘብ ዕዳዎቹን መዝግቦ ይይዝና በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉትን የመጻጻፍ ተግባራት ያከናውን የነበረው የሒሳብ ባለሙያ፣ ዜግነቱ እንግሊዛዊ፣ ዋና ምድቡ በእኛ ዋና ክፍል ሳይሆን በኢታብ ሆኖ አገኘሁት።

ሁለተኛው የዋና ክፍሉ ተግባር የመንግሥት ኢንቨስትመንት መከታተል ነበር። ይኸን አስመልክቶ ያለውን እንቅስቃሴ ለማወቅ ስሻ፣ ያገኘሁት አንዲት ፋይል ብቻ ነበር። ፋይሏም የያዘችው ሦስት ደብዳቤዎችን ብቻ ነበር። የመጀመሪያው ረዘም ካለ ጊዜ በፊት የተጻፈው የሚኒስትሩ ሲሆን፣ የመንግሥት ድርጅቶች አቋማቸውንና እንስቃሴዎቻቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለዋና ክፍሉ እንዲልኩ የሚያዝ ነበር። ሁለቱ ደግሞ ያን ጠቅሰው መረጃዎቹ እንዲላኩ የሚያሳስቡ በዋና ክፍሉ ኃላፊ የተጻፉ ነበሩ። ይኸን በተለይ የሚከታተል አልነበረም።

ይህ በእንዲህ እያለ፣ አይ.ኤም.ኤፍ (ማለትም፣ ኢንተርናሺናል ሞኔታሪ ፈንድ) የአባል አገራት የገንዘብ ሚኒስትሮችን እና የብሔራዊ ባንኮች ዝቅተኛ ደረጃ ኃላፊዎችን ማሠልጠኛ አዲስ ተቋም ከፍቶ ጥሪ አደረገ። ለዚያ ዓመት 21 ሰዎች ብቻ ማሠልጠን እንዳቀዱና፣ ከእያንዳንዱ አባል አገር ሁለት እጩዎች እንዲላኩ ተጠየቀ።

የኔ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኙት አንዱ ሆነ። በመጋቢት ወር 1957 ለመጀመሪያ ጊዜ የአትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጬ ዋሽንግተን ገባሁ። ከአፍሪካ

የሄድነው ሦስት ነበርን - ከኢትዮጵያ፣ ከግብጽና ከታንዛኒያ። በዚያን ወቅት፣ ኢትዮጵያ በአይኤምኤፍ ውስጥ፣ ምድቡዋ ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር ነበር።

ይህ የሆነበት መነሻ ታሪክ አለው። በ1946 (እ.አ.አ.) አይኤምኤፍ እና የዓለም ባንክ ሲቋቋሙ ከመሥራች አባላቱ ኢትዮጵያ አንዱዋ ነበረች። ያን ጊዜ ሌሎች ጥቂር እና ነጻ የአፍሪካ አገሮች አልነበሩም፤ ከላይቤሪያ በስተቀር። ለሁለቱ ሲባል ክፍል መመደብ አላመቸም ነበርና ነው፣ ኢትዮጵያን ከግብጽና ከሌሎች አረብ አገሮች ጋር፣ በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ አጠቃለሉዋት። ኋላ የአፍሪካ ክፍል ተከፍቶ እያለም፣ ኢትዮጵያ እዚያው እንድትቀጥል በኛው ወገን ተደረገ።

በአይ.ኤም.ኤፍ ቦርድ ላይ፣ አስፈጻሚ ዲሬክተርነት እና በተለዋጭ ዲሬክተርነትም ኢትዮጵያን የሚወክሉት ግብጻውያን ነበሩ! ኢትዮጵያ አንድ ጊዜ እንኳን፣ ዋናነቱ ቀርቶ ተለዋጭ ዲሬክተር መድባ አታውቅም ነበር!! ይሁንና በዚህ ወቅት የነበሩት ግብጻዊው አስፈጻሚ ዲሬክተር ሚስተር ዛኪ ስዓድ ነበሩ። ነባር የሆኑት እኚህ ሰው በድርጅቱ አመራር ዘንድ የተከበሩና ተደማጭነት ያላቸው ነበሩ።

በዚያን ወቅት ኢትዮጵያ ከድርጅቱ ጋር የነበራት ግንኙነት ጠንካራ ነበር፤ ምክንያቱም የተበዳሪ ጥገኝነት አልነበረባትም ነበርና ነው። ‹‹የአንቀጽ 14 ምክክር›› በሚባለው መሠረት ከድርጅቱ አንድ ቡድን ተልኮ፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በአጠቃላይ፣ የንግድን ሒደትና የገቢ ወጪ ንግድን፣ የውጭ ክፍያን ሚዛን በተለይ፣ አጥንቶ ዘገባ ለአስፈጻሚ ቦርዱ ያቀርባል። ለኢትዮጵያ መንግሥትም ይሰጣል።

የዚያ ዓመት የአንቀጽ 14 ምክክር ዘገባ ለአይ.ኤም.ኤፍ ቦርድ ሲቀርብ፣ በታዛቢነት እንድገኝ ተደርጎ ነበር። የኢትዮጵያ የዓለም ንግድና የክፍያ ሚዛን ሁኔታ ከነበርንበት ደረጃ አንጻር ችግር ጎልቶ የሚታይበት አልነበረም። በግንኙነታችን ጠንካራና ጤናማ አቋም ነበር። ይሁን እንጂ፣ ቦርዱ ላይ ሪፓርቱን አድምጦ አንዱ፣ (የነማን አገሮች ወካይ ዲሬክተር እንደ ነበረ አላወቅሁም)፣ ‹‹ሁኔታዋ ይህን የሚመስል ከሆነ፣ ለምን ኢትዮጵያ ከአንቀጽ 14 ወደ አንቀጽ 8 አትዛወርም?›› ያለው፣ በሆዴ እንዴ!! ነበር ያስባለኝ። ደግነቱ ዛኪ ሰዓድ ተገቢውን መልስ ሰጠ።

በተባለው ምድብ 8 ውስጥ የሚገቡት በዓለም ንግድ ውስጥ ያላቸው ጠንካራ አቋም ገንዘባቸውን ‹‹ኮንቨርቲብል መሆን የሚችል›› ያደረገው እንደ ጃፓንና ጀርመን ያሉት ነበሩ እንጂ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ወደ ውጪ የሚልኩትም ከውጪ የሚያስገቡትም ምርት ዋጋ በሌሎች የሚወሰን አገሮች አይደሉም። ስለዚህ፣ ንግግሩ የለበጣ መሆን አለበት! ነው ያልኩት ለራሴ።

ስለኮርሱ በደምሳሳው ሊባል የሚችለው፣ ስለፋይንስ አስተዳደር የገንዘብ ድርጅቱን አመለካከትና ፍልስፍና ለማሥረጽ የሚያግዙ ዐይነት አቀራረቦችና

ውይይቶች ነበር መስለው የተሰሙኝ፡፡ ከዚያ ውስጥ፣ አስደሳች የነበረው ፕሮግራም፣ በኒው ዮርክ በታላላቆቹ የዩኤስ ንግድ ባንኮች ዘንድ ያደረግናቸው የመተዋወቂያ ጉብኝቶች ነበሩ፡፡ በተለይ ደግሞ፣ በዚያ ባለው በዩኤስ ፌዴራል ሪዘርቭ ሲስተም ተቋም ያደረግነው ጉብኝት፡፡

በዓለም የገንዘብ ድርጅት ማኔጅመንት ውስጥ የኢትዮጵያ ዴስክ የሚባል ነበር፡፡ ስለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት የነበረው ስለነበር፣ ስለተቋሙ ከሱ ብዙ ተማርኩ፡፡ በዚያን ጊዜ፣ በኔ አስተያየት፣ ተቋሙ (የዓለም ገንዘብ ድርጅት) የልማት አጋዥ ሳይሆን ጎታችነቱ የሚያይል ነበር መስሎ የታየኝ፡፡

እዚያው እያለሁ የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ አቶ ብርሃኑ ድንቄ፣ ‹‹በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀቁ›› የሚል ዜና ወጣ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ኤምባሲ ስሔድ ሲተራመሱ ደረስኩ፡፡ በኋላ ጉዳይ ፈጻሚው ቢሮ ተሰባስበን እንወያይ ተብሎ እኔም ተቀላቀልኩ፤ የወታደራዊ ጉዳይ አታሼው ጀነራል አማን አንዶም ነበሩ፡፡ ቀደም ሲል ግጭት ተፈጥሮ ቢሮአቸውን ለቀው ነበር ሲባል ሰምቼ ነበር፡፡ ጄኔራሉን አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ኮሌጅ 4ኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ፣ *ኢትዮጵያን ሎው ኤንድ ኮንስቲቲዩሺን፣* በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ዐቃቤ ሕግ የነበረው አቶ በረከት ሀብተ ሥላሴ ሲያስተምረን፣ አብረውን ሲማሩ ለሰላምታ ያህል ዐውቃቸዋለሁ፡፡ ጉዳይ ፈጻሚው ዶክተር ጌታቸው አብዲ ነበር፡፡

ክቡር አቶ ብርሃኑ ድንቄ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ መጠራታቸውን ብቻ መግለጹ ይበቃል፡፡ የበተኑትን ወረቀት ለማስተባበል መመሪያ መጠየቅ ይሻላል፡፡ ይመለሱ የሚለው ጥሪ ሐቅ ስለሆነና፣ የኤምባሲው ኮፒ ለማስረጃነት ስላለ ችግር አይኖርም ተባለ፡፡

የዋሺንግተን ቆይታዬም እስከ ነሐሴ መጨረሻ ድረስ ነበር፡፡ ያን ፈጽሜ ወደ ኢትዮጵያ የተመለስኩት በለንደን፣ በፓሪስ እና በሮም የጥቂት ቀናት ቆይታ እያደረግሁ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ስደርስ፣ አሮጌው ዓመት ዐልፎ 1958 ጀምሮ ነበር፡፡

ዋሺንግተን ቆይቼ፣ በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ ድርጅቶች ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ላይ ለመገኘት የሚመጣውን የልኡካን ቡድን በአማካሪነት እንድቀላቀል ተወስኖ ቴሌግራም ተልኮ ኖሯል! የደረሰው ግን እኔ ወደ ለንደን ከበረርኩ በኋላ ነበር፡፡ መልካም እድል ስላመለጠኝ ወዳጆቼ ሲያዝኑልኝ፣ ሚኒስትሩ ዘንድ ስገባ ግን፣ ‹‹ያውሮፕላን ኪራይ ልታስወጣነው  የመጣኸው›› ብቻ ነበር ያሉት፡፡ እኔም፣ የሔድኩት ከባለቤቴ ጋር እንደነበረና፣ የተመለስነውም ሦስት ሆነን ስለነበረ፣ ብቆይም ኖሮ ወጪው አይቀር ነበር በማለት ተሰናብቼ ወጣሁ፡፡ ሌላ ግን አስደንቆኝ የነበረው ኢትዮጵያ የ1965 (1958) ሁለቱ ተቋማት የገዢዎች ቦርዶች ስብሰባ ሊቀመንበር የምትሆን የነበረ መሆኑን እዚያ ሆኜ አለመስማቴ ነበር፡፡

ስብሰባው ከመጀመሩ 10 ቀን ቀድመን ዋሺንግተን ገባን፡፡ ከባንኩ ወይም ከዩኤስኤ አይዲ ጋር ጉዳይ የነበራቸው ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው አያሌ

ሹማምንት እና የልማት ነክ ተቋማት ኃላፊዎች መጥተው ስለ ነበረ፣ በስብሰባው ሰሞን እዚያ አካባቢ የነበሩ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ቁጥር ቀላል አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ የዓመቱ ሊቀመንበር በመሆኗና፣ እኔም የኦፊሲየል ልኡካኑ አባል በመሆኔ፣ ከአውሮፕላን ቲኬት እስከ ውሎ አበሌና ሆቴል የከፈሉት ሁለቱ ተቋማት ነበሩ፡፡

ከዋሽንግተን እንደ ተመለስኩ፣ ወዲያው ይመስለኛል፤ የፋይናንስና ክሬዲት ዋና ክፍል አለቃዬ ተሾሞ ሔደ፡፡ በርሱ እግር ሰው ሳይተካ ቀረ፡፡ ትንሽ ጊዜ ካለፈ በኋላ፣ አንድ ቀን የተወሰንን ሰዎች (4?) ሚኒስትሩ ዘንድ ተጠርተን ቀረብንና፣ ‹‹ዲሬክተር ተብላችኋል›› አሉን፡፡ ለማንኛውም፣ እኔ እንደታየኝ፣ የክፍሉን ሥራ መሥራት ቀጠልኩ፡፡

የመጀመሪያው የተሳካ ሙከራዬ እንግሊዙን ከኢታብ ወደ ፋይናንስና ክሬዲት ማዘዋወር መቻሌ ነበር፡፡ እሱም በዝውውሩ ደስተኛ ነበር፡፡ ጥንቅቅ ያለ ሥራ ወዳድ ቻርተርድ አካውንታንት ነበር፡፡ ሆኖም ሪከርድ አያያዙን የሚረዳው ልምድ ያለው ሰው ከሌላ መሥሪያ ቤት እንዲዘዋወር አደረኩ፡፡ በሌላው ተግባሩም የሚያግዘው አንድ ወጣት ምሩቅ አደረግሁለት፡፡ ደስተኛ አልነበረም፤ ሆኖም ብርቱ የሥራ ሰው ስለ ነበረ አቃቂር ከማውጣት ያለፈ ችግር አልፈጠረም ነበር፡፡ ከሁለቱ ጋር ደግሞ የመጨረሻ ግባችን ምን እንደሆነ ተማመንን፡፡

ለመንግስት ኢንቨስትመንት ጉዳዮች ሥራ ብቻ አንድ ምሩቅ አስቀጥሬ መደብኩ፡፡ እየተመካከርን መረጃዎችን በመልክ በመልካቸው ለማሰባሰብ ተጣጣርን፡፡ እንግሊዙንም የሒሳብ ሰነዶች ትንተና ላይ እንዲያግዝ አሳተፍነው፡፡ በዚህ መሠረት ወደ 360 ሚሊዮን ብር በሚሆን ያህል ገንዘብ መንግስት ያቋቋማቸው ድርጅቶች መኖራቸውን በቅድሚያ ግምት ላይ ደረስን፡፡ ሆኖም ይኽ ገና ብዙ የማጥራት ተግባር የሚቀረውና ለአደባባይ የሚቀርብ አልነበረም፡፡ ወሬ ተሰምቶ የጥያቄ ደብዳቤዎች ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ በተቻለ እየተከላከልን ቀጠልን፡፡

በዚህ መካከል ዋና ዲሬክተር ተብዬ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ያልታሰበ ነገር ተከሰተ፡፡

## በዋሽንግተን ዲሲ ቢሮ መክፈት (1960-1964)

አምባሳደር ሆል፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር የነበሩት፣ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር በዐቃቤ ሰዓት ሲነጋገሩ፣ ‹‹በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ትብብር እርዳታ ሁኔታ የሚከታተል እና የሚያስተባብር ጽሕፈት ቤት ዩኤስ አሜሪካ በአዲስ አበባ ከፍታለች፡፡ ሆኖም፣ የኢኮኖሚ ትብብሩ እና የዕርዳታው ፍሰት ይበልጥ የተመቻቸ እንዲሆን፣ ኢትዮጵያም ይኽን የሚያስተባብር ሰው በዋሽንግተን ብትመድብ፣ በደብዳቤ በጽሕፈት ቤታችን በኩል ተጠይቆ መልስ እስኪደርስ ለመጠበቅ በአስቸኳይ

*ሊያነጋግሩን የሚችል ሰው እዚያው ይኖራልና፣ ነገሩ ይቀለጥፋል›› በማለት ያሳስባሉ፡፡*

*ንጉሠ ነገሥቱ ሐሳቡን ተቀብለው፣ ወዲያው የገንዘብ ሚኒስትሩን አስጠርተው ይነግሩዋቸዋል፡፡ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ይልማ ዴሬሳም፣ ስለ አስፈላጊነቱ መስማማት ብቻ ሳይሆን፣ ለዚህ የሚሆን ሰው እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ የአሰቡት ሰው ማን እንደሆነ ተጠይቀው ይናገራሉ፤ አስፋው ዳምጤ፡፡ ስለ ደረጃው ግን እንዲወሰንላቸው ይጠይቃሉ፡፡*

*በተነሣው ንግግር መካከል፣ እንዴት እና በማን እንደሆነ ባይታወቅም፣ ስለ አስፋው ጺም የሆነ ነገር ይወሳል፡፡ ይኸን ላውቅ የቻልኩት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር አስተዳደር ረዳት ሚኒስትሩ፣ ጥላሁን ምትኩ እየሣቀ፣ ‹‹ጢምህን እንዳትላጭ ተብለሃል›› ብሎኝ በዚህ ሳቢያ በተነሣው ውይይት ነበር፡፡*

*‹‹ክቡርነታቸው ከግቢ እንደመጡ አስጠርተውኝ፣ ‘ያን አስፋውን ጢምህን እንዳትላጨው በለው አሉኝ … ዋሺንግተን እንድትመደብ የተወሰነ መሰለኝ፣ ትንሽ ችግር የፈጠረው ደረጃህ ነገር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ውጭ ጉዳዮች ከነሱ ውጭ የሆነ ሰው በውጭ አገር ሲመደብ አይወዱም›› አለኝ፡፡ ይህን ያለው ከራሱ ልምድ ተነሥቶ ነበር፡፡ እሱም ክቡር አቶ ይልማ እዚያ አምባሳደር በነበሩበት ጊዜ ጸሐፊያቸው ሆኖ ሔዶ ነበርና ነው፡፡*

*ያንጊዜ እኔ ዋና ዲሬክተር ከሆንኩ ዋል አደር ብያለሁ፡፡*

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ አቶ ከተማ ይፍሩ፣ ተጠርተው ስለደረጃ ጉዳይ ሲጠየቁ ችግር አለብኝ ይላሉ፡፡ የአምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የ1957 ክዳት በኋላ፣ በዋሺንግተን የኢትዮጵያ አምባሳደር ባለመኖሩ፣ ኤምባሲው የሚመራው በ1ኛ ጸሐፊ ጉዳይ ፈጻሚነት ነበርና፣ ከዚያ በላይ ማዕረግ ያለው ሰው ችግር ይፈጥርብኛል ይላሉ፡፡*

*ይሁን እንጂ፣ እኔ ችግሩ አልታይ ይለኛል፡፡ ምክንያቱም እኔ የምሔደው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠራተኛነት አልነበረምና፡፡ ደግሞም፣ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከመከላከያ ሚኒስቴር የሚላኩ አታሼዎች ማዕረግ ከውጭ ጉዳይ ጋር ግንኙነት አልነበረውም፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ ክቡር ሚኒስትሩ በቃላቸው ነግረውኝ፣ በዋሺንግተን የገንዘብ ሚኒስቴር ተጠሪ የመሆኔ ደብዳቤ ሲደርሰኝ፣ ዝግጅቴን ጀመርኩ፡፡*

*ለመረጃ የሚያገለግሉ ጽሑፎችንና መጻሕፍትን ማሰባሰብ ጀመርኩ፤ ለምሳሌ የነጋሪት ጋዜጦችን፣ ከመነሻው ጀምሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ የወጡትን ጥራዞች በሙሉ፣ እንዲሁም አንድ አዲስ የዐማርኛ መተየቢያ መኪና ሥራ ማስኬጃ፣ የቢሮ ኪራይና ሥራ ማስኬጃ፣ ከዚያው የምትቀጠር አንዲት ጸሐፊን ደሞዝ፣ የሚያጠቃልል በጀት ሠርቼ ለሚኒስትሩ አቀረብኩ፡፡ ይህን ሳደርግ እግረ መንገዴን፣ የተባለው አገልግሎት በቁም ነገር የታሰበበት እና አስፈላጊነቱ የታመነበት መሆን እና አለመሆኑን ለመገመት እንዲያስችለኝም ነበር፡፡*

ይሁንና፣ ጉዳዩ ለበጀት ጉዳይ ዋና ኃላፊው ተመራ። እንደ ጠበቅሁት፣ ይዞት ዝም አለ። በማከያው እኔ ለተመደበው ተኪዬ፣ ለሙላቱ ካሳዬ የቀድሞውን ሥራዬን አስረከብሁ። ስለበጀት ምደባው ጭቅጭቅ ተነሥቶ ጉዳዩ ሚኒስትሩ ዘንድ ቀረበ። ‹‹ቢሮ ኤምባሲው ያገኛል፤ ጸሐፊዎችም ከአንድም ሦስት ስላሉና ሥራም ስለማይበዛባቸው ከነሱ አገልግሎት ያገኛል። ስለዚህ፣ በጀት መመደብ አያስፈልግም›› የሚል ሐሳብ አቀረበ።

እኔ፣ ‹‹በሰው ንብረትና ሠራተኛ ለማዘዝ ይቻላል?›› ብዬ አለማመኔንና፣ ‹‹በትብብር ልመና የመንግስት ሥራ እሠራለሁ ብዬ ለመሔድ ችግር መሆኑን›› ገለጽሁ።

ሚኒስትሩ፣ ‹‹ኤምባሲውን መጀመሪያም የገዛሁት እኔ ነኝ፤ ለ8 ዓመት አምባሳደር ሆኜም ዐውቀዋለሁ። የሚሰጡት የረባ ቢሮ አይኖርም። ይኸን ሰውዬ፣ በተለይ ኢንቬስተሮችን፣ ኤምባሲው አንድ ‹‹አቲክ›› ውስጥ ያነጋግር ነው እንዴ የምንለው፤ ፌር እንሁን እንጂ!›› ብለው ተናገሩና፣ ሁነኛ ቢሮም ጸሐፊም አስፈላጊ መሆኑን ቁርጥ አድርገው ገልጸው በዝርዝሩ ተስማምተን ቶሎ እንድሔድ አዘዙ።

ለማንም አልገለጽኩም ነበር እንጂ፣ በጀት ባስፈቅድም ኤምባሲው ውስጥ ለዘለቄታው ሊያሠራኝ የሚችል ሆኔታ ካለ፣ አስቀድሞውኑም ቢሮዬን እዚያው ውስጥ የማድረግና ገንዘቡን ከወጪነት የማዳን ዓላማ ነበረኝ። ስለዚህ ዋሺንግተን ስደርስ፣ ኤምባሲው ውስጥ ገባሁ። የተሰጠኝም ቢሮ የአምባሳደሩ ቢሮ ካለበት ወለል ላይ ከነበሩት ቢሮዎች አንዱ ነበር። ከነበሩት ቢሮዎች አንጻር ‹‹ደህና›› ከሚባሉት መሐል ነበር። እንዲያውም፣ ከሁለቱ አታሼዎች አንጻር ሲታይማ፣ ምርጥ ሊባል የሚገባው ነው። ቀደም ሲል፣ ሚኒስትሩ እንዳሉት የሁለቱ ሚኒስቴሮች (የትምህርትና የመከላከያ) አታሼዎች ቢሮ ሕንፃው አናት ላይ አቲክ ውስጥ ነበር የተሰጣቸው። ስለዚህ ከሁለቱ አንዱ ሰው ባይኖራቸውም ኖሮ የኔ ይሆን ነበር ማለት ነው! ብዬ ማሰቤ አልቀረም። ሆኖም፣ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቢሮዬን በዚያው አድርጌ ለመቆየት ወሰንሁ።

ቤተሰቤን ይዤ ስለነበር የሔድኩት፣ መኖሪያዬን በደቡብ ምዕራብ ዋሺንግተን አደረግሁ። ከዋሺንግተን ነዋሪ 80% ጥቁር አሜሪካውያን ነበሩ። አብዛኞዎቹ ነጭ ባለሀብቶችና የመንግሥት ሠራተኞችና ሹማምንት የሚኖሩት በቨርጂኒያና ሜሪላንድ ነበር።

አዲሱ ሥራዬን የጀመርኩት ወደ የዓለም ገንዘብ ድርጅት፣ ዓለም ባንክ እና ዩኤስ.ኤ.አይዲ ቀጠሮ እየጠበቅሁ መጀመሪያ *‹‹በኢትዮጵያ ዴስክ››* ላይ የተመደቡትን ግለሰቦች ለመተዋወቅ ጉብኝት (ወይም ከርተሲ ኮል) በማድረግ ነበር። በመጀመሪያው ተቋም ውስጥ፣ ከሦስት ዓመታት በፊት የነበረውና ተዋውቄው የነበረው፣ ጀርመኑ ፍራንትስ ድሬስ ሳይሆን፣ ማይክል ኒብሊንግ የሚባል አዲስ አሜሪካዊ ወጣት ነበር ያገኘሁት። (ይህ ሰው፣ በ1985

በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በነዋሪ ኃላፊ የሚመራ ቢሮ አይ ኤም ኤፍ በአዲስ አበባ ሲከፍት፣ የመጀመሪያው ኃላፊ ሆኖ መጥቶ የነበረው ነው።)

በዓለም ባንክ፣ ሆኔታው ጥቂት ለየት ይል የነበረው፣ የኢትዮጵያ ምድብ በአፍሪካ ክፍል ውስጥ መሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ፣ በባንኩ ቦርድ ውክልና ላይ እዚህም ሀገራችን አንዴም ሰው መድባ አታውቅም ነበር። በዚህ ወቅት ሚስተር ጋርባ የሚባል ናይጄሪያዊ ነበር ኢትዮጵያ የአለችበት የሃገራት ስብስብ ቦርድ ላይ የሚወከለው።

ስለነዚህ ድርጅቶች ጥቂት ገለጻ ማድረጉ ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ ሳይጠቅም አይቀርም።

እንደሚታወቀው፣ እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ወይም የገንዘብ ተቋማት፣ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ የዓለምን የንግድ ክፍያ ሁኔታ ሥርዓት ለማሲያዝ፣ እንዲሁም፣ በጦርነት የወደመውን በተለይ የአውሮፓ ኢኮኖሚን እንደገና ለመገንባትና የወደፊቱንም የልማት ጉዞ መንገድ ለማስያዝ ነበር የተመሠረቱት። የመጀመሪያው ተግባር አስፈጻሚ፣ የኢንተርናሽናል ሞኔታሪ ፈንድ (አይ. ኤም. ኤፍ.)፣ የሁለተኛው፣ ኢንተርናሺናል ባንክ ፎር ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ዲቨሎፕመንት (አይ.ቢ.አር.ዲ) ሆነው ተደራጁ። አወቃቀራቸው ግን ሁለቱም አንድ ዓይነት ስልት የሚከተል ነው።

ለነገሩ የድርጅቶቹ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) የመላ አባላቱ መዋጮ በመሆኑ፣ ድርጅቶቹ ንብረትነታቸው የአባላቱ ነው። ስለዚህ፣ የድርጅቶቹ የበላይ አካል በየዓመቱ የሚሰበሰበው የገዢዎች ቦርድ ነው። ገዢዎቹ ለባንኩ የአባል አገሩ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለፈንዱ የአባል አገሩ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ነው። እያንዳንዱ አስፈጻሚ ገዢ እርሱ በማይኖር ጊዜ በርሱ እግር ተተክቶ የሚሠራ፣ ተለዋጭ ገዢ አለው። የነዚህ ስብስብ ነው፣ ቦርድ ኦቭ ገቨርነርስ ተብሎ በየዓመቱ (2 ዓመት ዋሺንግተን፣ 3ኛው ስብሰባ የሚደረግበት አህጉርና አገር በተራ እየተመረጠ) የሚሰበሰበው። በቅርብ ሆኖ የድርጅቶቹን እንቅስቃሴ የሚከታተል ደግሞ፣ በቁጥር አነስ ያለ፣ አባላቱ ሁሉ የተወከሉበት የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች ቦርድ አለ።

ይሁን እንጂ፣ የድምፅ አቅም (ወይም ብዛት) በመዋጮ መጠን የተወሰነ ስለሆነ፣ ውክልናው ሁሉም እኩል አይደለም። ልክ እንደ ተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት፣ እነዚሁ አምስቱ ታላላቅ አገሮች እንዳንድ አስፈጻሚ ዲሬክተር በቀጥታ ሲሾሙ፣ የተቀሩት ደግሞ እየተሰባሰቡ አንድ ብቻ ይመርጣሉ አስፈጻሚ ቦርዱ ላይ በጋራ የሚወክላቸው። ምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ትገኝ የነበረበት ስብስብ ወደ 14 አገሮች የነበርን ሲሆን የሚኖረን ወካይ ግን አንድ ነበር።

ከዚህም በላይ፣ የባንኩ ፕሬዚደንት ምን ጊዜም አሜሪካዊ፣ የፈንዱ (የአይ.ኤም.ኤፍ) ማኔጂንግ ዲሬክተር አውሮፓዊ (መጀመሪያ ላይ በተከታታይ ፈረንሳዊ) ነበር የሚሆኑት።

የዓለም ባንክ አባል ለመሆን፣ አስቀድሞ የዓለም ገንዘብ ድርጅቱ አባል መሆን የግድ ነው፡፡ የሱ አባል ሳይሆኑ የዚያኛው አባል መሆን አይቻልም፡፡ ከባንኩ ጋር የተያያዙት ሁለት ድርጅቶች (አይዲኤ እና አይኤፍሲ) አባል ለመሆን ደግሞ አስቀድሞ የአይ.ቢ.አር.ዲ አባል መሆን ያስፈልጋል፡፡[13]

በዚህ መልክ እነዚህ ተቋማት በሙሉ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በነዚህ ተቋማት ውስጥ የኢትዮጵያን ጉዳይ በሚመለከት ከታች እስከ ላይ የሚያገባቸውና ወሳኞቹ እነ ማን እንደሆኑ ማጥናት ጀመርኩ፡፡

በመጀመሪያ ግን፣ ለዘለቄታው የመሥሪያ ቦታዬን ጉዳይ መቁረጥ አስፈለገ፡፡ ምክንያቱም፣ ቢሮዬ ቋሚ ስለሆነና የዘለቄታውን ሳስበው፣ወደፊት የሚተኩኝንም ሰዎች ነጻነት የሚመለከት ስለሆነ፣ ቦታ ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ በካሎራማ መንገድ ላይ ከሚገኘው ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጽሕፈት ቤት የማይርቅ አካባቢ፣ ኮኔክቲከት ጎዳና ላይ አዲስ ይሠራ ከነበረ ሕንፃ ላይ የተወሰኑ መረባ (ካሬ) ሜትሮች ወለል ተከራይቼ፣ አንድ ዋና ቢሮ፣አንድ ሰፊ የእንግዳ መቀበያና የጸሐፊ ቢሮ ፣ እንዲሁም፣ አንድ አገልግሎተ ብዙ ክፍል አስቀየድኩ፡፡

አንድ መኪናም ካለዱቤ በጥሬ ገንዘብ ገዛሁ፡፡ በሁሉም ቦታ ሻጮቹ የሚያበረታቱት ምንም ነገር ሲገዛ፣ ቃብድ ተከፍሎ በየወቅቱ በሚደረግ ክፍያ እንዲሆን ነው፡፡ በዚህ መልክ ሲሆን የበለጠ ጥቅም ያገኛሉና፤ ወለድ አለበታ!

እኔ ዋሽንግተን በተመደብኩበት ወቅት (1968 እ.አ.አ)፣ በአሜሪካ የፕሬዚደንታዊ ምርጫ የሚካሔድበት ዓመት ከመሆኑም በላይ፣ የቪየትናም ጦርነት ጉዳይ ያገሪቱን ዜጋ እያበጣበጠ እና ፖለቲካውን እየናጠ ነበር፡፡ ጠላት እየበረታ ግን ‹‹ወደድል ብርሃን እየተጓዝን ነው›› እየተባለ ተደጋግሞ በአሜሪካን ባለሥልጣናት ሲሰጥ የነበረው ተስፋ አሁን መረሳት የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ እንዲያውም እንደ ፈረንሳዮች ተዋርደን እንዳንወጣ የሚል ሥጋት በብዙዎች ዘንድ የበረታበት ጊዜ ነበር፡፡

ፕሬዚደንት ጆንሰን ከምርጫው ውድድር ራሳቸውን ያገለሉበት፣ የአሜሪካ የኒው ዮርክ ሴናተር የነበሩት የኬኔዲ ትልቁ ታናሽ ወንድም፣ ሴናተር ሮበርት ኬኔዲ ደግሞ ወደ ውድድሩ በይፋ የገቡበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህም በላይ፣ስለ ጥቁሮች መብት በሰላማዊ መንገድ ታጋይ የነበሩት፣ ሬቨረንድ ማርቲን ሉተር ኪንግ እና ሮበርት ኬኔዲ ተከታትለው የተገደሉበት ዓመትም ሆነ፡፡ በዚህ መሐል ነበር፣ የአሜሪካው የረጅም ጊዜ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት፣ ሚስተር ሮበርት ማክናማራ፤ የዓለም ባንክ ፕሬዚደንት ሆነው፣ እኔ ዋሽንግተን በደረስኩ በሁለተኛ ወሬ መገባደጃ ግድም ላይ የተሾሙት፡፡

ኮሚዩኒዝም የሚጸድቅበት ምቹ መሬት የኢኮኖሚ ድህነት መኖር ነው፣ በሚል እምነት ነው በጦር መሣሪያ መዋጋትን ትተው፣ በዚህ አስቸጋሪ (የኢኮኖሚ

[13] አይዲኤ የ International Development Association ምህጻረ ቃል ሲሆን አይኤፍሲ የInternational Finance Corporation ነው፡፡

ልማት) ግን ሲሳካ የተረጋገጠ የድል ጎዳና በሆነው ሜዳ ላይ ለመፋለም ሹመቱን የፈለጉት የሚል አሉቡዋልታ እንበለው ግምት በባንኩ አካባቢ ይሰማ ነበር።

ማክናማራ እንደ ተሾሙ፣ ለገንዘብ ሚኒስትሩ እንደ የኢትዮጵያ የባንክ ገዢነታቸው የደስታ መልእክት ቢላክ የሚል ማሳሰቢያ ላክሁ። ከተሾሙ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ እንደ ዓለም ባንክ ፕሬዚደንት የመጀመሪያ የአባል አገራት ጉብኝታቸውን፣ በዩጎዝላቪያ እና በኢትዮጵያ ለማድረግ መወሰናቸውን ሰማሁ። ከጉብኝቱ በፊት ለሚደረገውም ዝግጅት ኢትዮጵያን በሚመለከት እንድተባበራቸው ተጠየቅሁኝ። ስለ ኢትዮጵያ መረጃ ማቅረብ እና ስለ ኢትዮጵያ ማሳወቅ ተግባሬ ስለሆነ ችግር የሚፈጥር አልነበረም። እንዲያውም ግንኙነቴን ለማስፋት ይበልጥ በር ከፈተልኝ።

ከጉብኝቱ በሁዋላ፣ የባንኩ ፕሬዚደንት ስለሁለቱም የጎበኟቸው አገሮች የተሳሳተ ግምት እንደነበራቸው፣ በጉብኝቱ ወቅት ያልገመቱት የገጠማቸው መሆኑን ገለጹ። ዩጎዝላቪያ ጠብቀውት ከነበረው ይበልጥ በኢኮኖሚ የተራመደች፣ ኢትዮጵያ ደግሞ ከጠበቁት በላይ ኋላ የቀረች ሆነው ነበር ያገኙዋቸው። በኢትዮጵያ በቁንጮ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉት ሁሉ፣ ከሁለት በስተቀር፣ አንጋፋ ሰዎች መሆናቸውን ተናገሩ። ሕዝቡን፣ በተለይ ገበሬውን፣ ግን አደነቁ፤ ለምሳሌ፣ ገበሬዎቹን ሲያነጋግሩ ካንድ ጊዜ በላይ አስተርጉዋሚ መቀየራቸውን ተናገሩ፤ ምክንያቱም የሚነገራቸው ገበሬው ያለው ሳይሆን አስተርጉዋሚው ያበጃጀው ስለመሰላቸው ነበር። ነገር ግን፣ ደጋግመው እንዳዩት፣ የኢትዮጵያ ገበሬ ወግ አጥባቂና አዲስ ነገር የማይቀበል ሳይሆን፣ ለውጥ ተቀባይ ነው። በብዙ ነገር ንቃቱ ከተማረው የአሜሪካ ገበሬ የሚልቅ መሆኑን መታዘባቸውንም ገለጹ። ለኔ በወቅቱ የደረሰኝ አንድምታ፣ የኢትዮጵያ ችግር የአመራር ችግር ነው የሚል ነበር።

በዚህ መሐል አዲስ አበባ ሹምሽር መደረጉንና፣ ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ የገንዘብ ሚኒስትር ሆነው ሲሾሙ፣ የቀድሞው አለቃዬ አቶ ይልማ ዴሬሳ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ሆነው መሾማቸውን በዋሺንግተን ተሰማ። ሹመቱን የሰቱለት መስማታችን መጀመሪያ ላይ ገርሞኝ ነበር። ኋላ ሳስበው፤ ለካ ቀኑ በአሜሪካ ለእኛ የሚደርሰው 8 ሰዓት ያህል ዘግይቶ በመሆኑ ኖሩዋል።

ብዙም ሳይቆይ፣ ከአዲሱ የገንዘብ ሚኒስትር ቴሌክስ፣ በኤምባሲያችን በኩል፣ ደረሰኝ። ጉዳዩ፣ ለኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ከዓለም ባንክ ስለተጠየቀው ብድር፣ ከዓለም ባንክ ጋር ለመደራደር ከሚመጣው ቡድን ጋር ሆኼ ገንዘብ ሚኒስቴርን በመወከል እንድደራደር ኃላፊነት የሚሰጥ መልእክት ነበር። ስለ ፕሮጀክቱ፣ አዲስ አበባ ቢሮዬ ሳለሁ፣ አጠቃላይ ሐሳብ ቢኖረኝም፣ በተለይ የድርድሩ ይዘት ምን እንደሆነ የማውቀው ነገር አልነበረም። ሆኖም፣ ልኡካኑ የተሟሉ ሰነዶች ስለሚኖራቸውና ስለጉዳዩ አጠቃላይ ገለጻ እንደሚያደርጉልኝ ይታወቅ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እኔ እነርሱ እስኪመጡ

ከመጠበቅ አንዳንድ መረጃ ለመቃረም ወስኜ ወደ ዓለም ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ሔድኩ።

ሃንክ ጋስነር የሚባል አሜሪካዊ ወጣት ነበር የኢትዮጵያ፣ የሱማልያና የሱዳን ዴስክ ኃላፊ የነበረው። እሱ ዘንድ ቴሌክሴን ይዤ ሔድኩና፣ ኮፒው ደርሶት እንደሁ ጠየቅሁት። እንዳልደረሰውና ግን አንድ ቡድን ከአዲስ አበባ እንደሚመጣ ብቻ ማወቁን እየነገረኝ፣ ፋይሊንግ ካቤኔቱን ከፍቶ አንድ ፋይል አውጥቶ ይዞ ወደ ጠረጴዛው ተመለሰ። ከዚያ ፋይሉን ገልጦ ወረቀቶች እያገላበጠ፣ ‹‹የልኡካን አባላት እነማን እንደሆኑ ገና አልተገለጸልንም፤ በቅርቡ ሙሉ ዝርዝር ይደርሰናል ብዬ እገምታለሁ። በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ማን እንደሚሆን አሁን ዐወቅን›› አለና ‹‹የስምምነት ሰነዱን ረቂቅ ልከውልህ ካልሆነ እና ማየት ከፈለግህ›› ብሎ ፋይሉን አቀበለኝ። እኔም እያገላበጥሁ አንዳንድ ነገሮች ለመያዝ ሞከርኩ። ልኡኩ መጥቶ በተሳካ ሁኔታ ድርድሩ ተካሒዶ ተጠናቀቀ። አዲስ አበባም ሄዶ ሰነዱ ጸደቀ። በተጉዋዳኝ የቴሌኮሚዩኒኬሺን ብድር ድርድር ቀጥሎ ነበር። ለዚያም የኔ ቢሮ ድጋፍ ሰጪ ነበር።

ድርድሮቹ ተከታተሉ። የአውራ ጎደና፣ የትምህርት ሚኒስቴር… የሃንክ ጋስነር የሦስት ሀገሮች ጉዳዮችን የያዙ ፋይሎች ማከማቻው የነበረችው አንድ ፋይሊንግ ካቢኔ አልበቃችም ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥትና የተለያዩ ድርጅቶች የብድር እና የተዛማጅ ጉዳዮች ሰነዶችን ማኖሪያ፣ መጀመሪያ አንድ ቀጥሎ ሁለተኛ ፋይሊንግ ካቢኔቶች የሚያስፈልጋት ሆነ።

ትልቁ ለውጥ ግን የምንወስዳቸው ብድሮች ከአከፋፈልና ከጊዜ አንጻር እጅግ እየተለሳለሱ መሔድ ነበር። ቀደም ሲል ከዓለም ባንክ የወሰድናቸው ብድሮች በ6% ወለድና የ25 ዓመት የክፍያ ዘመን ነበር። አለም አቀፍ የልማት ማህበር (International Development Association ወይም አይዲኤ) ለደሀ አገሮች ተብሎ ከተቋቋመ በኋላም፣ ወሳጆቹ ከኛ የተሻሉ ናቸው የሚባሉ ነበሩ። ፈጽሞ የማይረሳኝ ለቱርክ 85 ሚሊዮን ባንድ ጊዜ ተሰጥቶ ያየሁት ነበር። ማንኛችን ነን የአ.ይ.ዲ.ኤ. ክሬዲት የሚገባን? ሁሌ ከሀንክ ጋር፣ እሱ ወሳኝ ባይሆንም፣ የማነሣው ነጥብ ነበር።

ውሎ አድሮ የአ.ይ.ዲ.ኤ. ክሬዲት ተጠቃሚዎች እየሆንን ሔድን፤ ለምሳሌ፣ እንደ መብራት ኃይል ያሉ ድርጅቶች ለዚህ ዐይነት ክሬዲት የሚታሰቡ አይደሉም። ነገር ግን፣ ዋናው ተበዳሪ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ጠበቅ ባለ ወለድና አጠር ባለ የመክፈያ ጊዜ ወደ እነዚህ ድርጅቶች የሚያቀብልበት አሠራር ተፈጠረ። በዚህ መልክ ነው የብድር ቅይጡ እንዲለሰልስ የሆነው።

የአሜሪካንን የግል ኢንቬስተሮች በመሳብ በኩል ግን አንዳች ስኬት አልነበረም ማለት ይቻላል። ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በቁም ነገር የሚፈልግ ሁነኛ ኢንቬስተር አንድ አልነበረም። ዋናው ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ሲያልፉ ምን ነገር እንዲሚከተል ማን ያውቃል የሚል ነበር የወቅቱ አስተሳሰብ። ለዘለቄታ የሚሆን ሥራ ለመጀመር፣ አሁን ለጊዜው ያለን የተረጋጋ የሚመስል ሁኔታ

ብቻ ሳይሆን፣ የወደፊት ዘላቂነቱም የሚያስተማምን መሆን አለበት። ያ ሳይኖር፣ የምንም ዐይነት ጠቃሚና አመቺ ማበረታቻዎች መኖር፣ ለሀገሩ ኢኮኖሚ ፋይዳ ያለው ሥራ መሥራት የሚችል ኢንቬስተርን መሳብ አይችልም። ስለመጻኢው ጊዜ ያለው ግንዛቤ መተማመንን የሚፈጥርበት ከሆነ፣ ከዚያ በኋላ ነው፣ የማበረታቻዎቹ ጥያቄ የሚታየው።

ከዚህ አንጻር አንድ አስከፊ ገጠመኝም ነበረኝ። ከሆነ የአሜሪካን ክፍለ ሀገር ደውሎ በቁምነገር ተቃጥረን መጣ፣ አንድ ኢንቬስተር ነኝ ባይ። መጥቶ ስንነጋገር ዳሎል ውስጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ነበር የፈለገው። ነውር ሆኖብኝ እንጂ በመጥረጊያ ባስወጣው ነበር ተገቢው። ዝም ብዬ ብቻ፣ ‹‹ይኸማ ፍጹም አይሆንም›› አልኩት።

አዲሱ ሚኒስትሬ፣ ጃንሆይ ለጉብኝት የመጡ ጊዜ አብሮ መጥቶ በነበረ ጊዜ፣ ቶሎ አዲስ አበባ እንድመለስ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ሁኔታዎች ስላላመቹ አልተቻለም ነበር።

በዚሁ ሥራዬ ይበልጥ ልምድና ግንኙነቶች በማበጀት ስተጋ አዲስ ነገር ተፈጠረ። ህዳር 19 ቀን 1964 ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እና የጽሕፈት ሚኒስትሩ፣ ከጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ በተጻፈ ደብዳቤ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር ሆኜ መሾሜን የሚገልጸውን ደብዳቤ ከማግኘቴ በፊት፤ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ከአቶ ማሞ ታደሰ የተላከ ይኸንኑ የሚገልጽ ቴሌግራም ደረሰኝ።

ቤተሰቤን፣ ባለቤቴንና ሦስት ልጆቼን በወሩ መጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ ልኬ እኔ ቆየሁ። ይህ የዋሽንግተን ቆይታ፣ ለኔና ለባለቤቴ ሁለተኛችን ነበረ። በመጀመሪያ ጊዜ (1957) የመጀመሪያ ልጃችን እዚያ ተወልዳ ነበር። ባሁኑ ደግሞ ሁለተኛ ሴት ልጃችን (1961) ተወልዳ ነበር። በመካከል ያለው ትልቁ ወንድ ልጃችን ኢትዮጵያ (1958) የተወለደ ነበር። ተኪዬ ሲመጣ አስረክቤ ለመሔድ መጠበቅ ነበረብኝ። ተኪዬ፣ ከሌላ መሥሪያ ቤት ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተዛውሮ የሚመጣው፣ ተፈራ ወልደ ሰማያት ነበር። ከወር በላይ ቆይቶ ደረሰ።

በጥር ወር አዲስ አበባ ተመለስኩ። ባልነበርኩባቸው አራት ዓመታት ውስጥ የከተማው ማኅበራዊ አየር የተለወጠ ይመስል ነበር።

በገቢዎች ዋና መምሪያ፣ በምክትልነት ተመድቤ ለተወሰኑ ወራት ሠራሁ፤ የገቢ መሥሪያ ቤቶቹም፣ ጉምሩክ፣ አገር ውስጥ ገቢ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ የቴምብር ቀረጥ እና የመሬት ግብርና የርሻ ታክስ መሥሪያ ቤቶች የነበሩ ሲሆኑ፣ ከጉምሩክ በቀር የተቀሩት በረዳት ሚኒስትሮች የሚመሩ ነበሩ። የዋና መምሪያ ኃላፊ ሚኒስትር ደ ኤታ ነበሩ።

1965 ላይ፣ የኤክሳይዝ ታክስ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ሆኜ ተመደብኩ። ዋናዎቹ የቀረጡ ገቢ ምንጮች ነዳጅ እና አልኮልና ያልኮል መጠጦች የነበሩ ሲሆን፣ ሌሎች ከሚያስገኙት የበዛ፣ እንደ ሹራብ፣ ጫማና የመሳሰሉ ዐይነቶች ነበሩ።

በነዳጅ የሚገኘው ገቢ፣ ዘመናዊ እርሻን (በትራክተር ማረስን) ለማበረታታት ተብሎ፣ 21 ሚሊዮን ብር ያህል፣ ከቀረጥ ነጻ መልክ በያመቱ ሳይገባ ይቀራል። ከነዚህ የቀረጥ ነጻ ነዳጅ ከሚያገኙ ገበሬዎች በእርሻ ታክስ የሚገኝ አልነበረም። ሚኒስቴሩ በዚህ ምክንያት ሁለቱን የሚያገናዝብ አሠራር ቀይሶ ነበርና አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል፤ ምክንያቱም እነዚህ ገበሬዎች ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሆነው ይገኛሉ። ከባድ የኃላፊነት ሥራ ያለባቸው ሰዎች በመሆናቸው ‹‹የሰንበት ቀን›› ገበሬዎች የሚል ስያሜም ተሰጥቷቸው ነበር።

ይሁንና፣ የቀረጥ ነጻውን የሚፈቅደው የኤክሳይዝ ታክስ መሥሪያ ቤት በመሆኑ፣ በመመሪያው መሠረት የርሻ ጥቅም ታክስ ለመክፈላቸው ማስረጃ ሲጠይቅ፣ ማቅረብ ያቅታቸዋል። ስለማይከፍሉ! ለመከልከል የበታች ሠራተኞች ስለሚፈሩ፣ ይህን ተግባር ኃላፊው መውሰድ ነበረበት። አብዛኛዎቹ ወዲያው ጃንሆይ ዘንድ ሔደው አቤት ማለት የሚችሉ ነበሩ። ደግነቱ የገንዘብ ሚኒስትሩ፣ አቶ ማሞ ታደሰ፣ የበታች ረዳቶቻቸውን አሳልፈው አይሰጡም ነበርና ሕጉን ማስከበር ተችሎ ነበር።

በመጨረሻም አዋጁ እንዲሻር ሐሳብ ቀርቦ ፓርላማ ብዙ ጉድ ሳይዝረጠረጥ አልቀረም ነበር።

በዚህ ወቅት፣ ከነዚህ የሰንበት ገበሬዎች በተቃራኒ፣ ዕውቀቱ የነበራቸው ወጣት የርሻ ባለሙያዎችም በመስኩ ነበሩ። እጅግ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነበሩ። ሆኖም፣ አብዮቱ መጣና ይህንንም ሳይለይ ደመሰሰው።

## በደራሲው የታተሙ ዋና ዋና ሥራዎች

### 1. የፈጠራ ሥራዎች

- *አንድ ለአምስት* (ዐቢይ ወግ)፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1980
- *ዘጠነኛው ዶሴ እና ቦዩ፣ እነሆ* - (የደራስያን ማኅበር የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ውስጥ የተካተቱ) አዲስ አበባ፣ 1980
- *ህጻኑ ይፍረድ እና ውለታ፣* (በመስኮብኛ ቋንቋ ተተርጉመው) *ዛግልያን ዘጎሪዞንት* (ከአድማስ ባሻገር) ሞስኮ፣ እ.አ.አ. 1986

### 2. ጥናታዊ ጽሑፎች

- «የሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ፣ አጭር ማስታወሻ»፣ *የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነጽሑፍ መጽሔት* (ቁ. 10 ልዩ እትም 1992)
- «ስለ ጥበበ ቃላዊ ሒስ»፣ *እፍታ* (መድበል ቁጥር አራት)፣ 1992
- «አንዳንድ ነጥቦች፣ ስለ አማርኛ ጥበበ ቃላት»
  - (1900-28)፣ *የካቲት መጽሔት* መስከረም - *ሚያዝያ* 1973
  - (1933-40)፣ *ጦቢያ* መጽሔት ግንቦት 1984 - *ሚያዝያ* 1985
  - (1940-50)፣ *ሰንደቅ* መጽሔት ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሀምሌ 1987፤ መስከረም 1988
  - (1950-60)፣ *ጦቢያ* መጽሔት፣ 1996
  - (1960-67)፣ *ጦቢያ* መጽሄት (ከመስረም እስከ መጋቢት 1997 ድረስ የወጣ ተከታታይ ጽሁፍ)
  - «አንዳንድ ነጥቦች ስለአቤ ጉበኛ ጽሁፎች» *የካቲት* መጽሄት ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ግንቦት 1974
  - «አንዳንድ ነጥቦች ስለሂስና ሃያስያን»፣ *የካቲት* መጽሄት ጥር 74፣ ታህሣሥ 75፣ መስከረም 76፣ ህዳር 1976
  - «ስለአሳታሚነት ሙያ» *የካቲት* መጽሄት ታህሳስ 1983
  - «አንዳንድ ነጥቦች ስለከበደ ሚካኤል የብዕር ፍሬዎች»፣ *ጦቢያ* መጽሄት ህዳር 1991
  - «ስለቤሳ ልብወለዶች ጥቂት ነጥቦች»፣ *ሰንደቅ* መጽሄት ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥር 1988

1. "Equb፧" *Ethnological Society Bulletin* (1958)
2. “Modern Amharic Literature, The 1st Phase, (1900-28 E.C.),” *Yekatit*, June 1981
3. “Modern Amharic Literature, Second Phase-I (1933-53)’ *Yekatit*, September 1981.
4. “Modern Amharic Literature, Phase II (1953-66)’’ *Yekatit*, December, 1981
5. “A ‘National’ Literature.’’ *Yekatit*, June 1982

# ተካ ኤገኖ፡- አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ተዋናይ

*በመኮንን ተገኝ*

ቀኛዝማች ተካ በአሁኑ ጊዜ ሰማንያኛ ዓመታቸውን የደፈኑ አረጋዊ ናቸው[1]:: አሁንም እንደ ትናንቱ ሁሉ ስራ በመስራት የሚያገኙትን እርካታ ላለማጣት ደፋ ቀና ሲሉ የሚውሉ፣ የንግድ ድርጅቶቻቸውን ለማስፋፋት አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመንደፍና ወደ ስራ በመተርጎም ላይ ያሉ ታታሪና ስኬታማ ነጋዴ ናቸው:: ባጭሩ ለቀኛዝማች ህይወት ማለት «መስራት መስራት አሁንም መስራት» ማለት ነው:: ብዙ በመስራት በጣም ብዙ ስራ መፍጠር ማለት ነው::

ቀኛዝማች ስለራሳቸው ሲናገሩ እንደሚሉት፣ «ከድህነት ዩኒቨርሲቲ የተመረቁ» ባለፀጋ ብቻ አይደሉም:: ቢያንስ፡-

1ኛ. በወቅቱ ኋላቀር አመለካከት የነበራቸው ሰዎች ነጋዴንና የእጅ ባለሙያውን አናንቀውና አሳንሰው በሚያዩበት ወቅት፣ ንግድን አቀላጥፎና በልጦ በመስራት፣ አስተሳሰባቸው የተሳሳተ መሆኑን ካስመሰከሩት ወጣት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች አንዱ ናቸው::

2ኛ. ከጥቃቅን የንግድ ዘርፍ በስተቀር፣ መላው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በውጭ የንግድ ሰዎች ቁጥጥር ስር በነበረበት ወቅት ከዝቅተኛ ደረጃ በመነሳት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እመርታ በማድረግ፣ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በመንግስት ድጋፍ ሳይሆን በግል ጥረታቸው ነፃ ለማውጣት ተቃርቦ የነበረው ወጣት የንግድ ማኅበረሰብ ቁንጮ አባል ናቸው::

እስከ አድዋ ድል ድረስ የነበረው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይ ደግሞ የደጋው ክርስቲያን፣ ከግብርና በስተቀር የጉልበት ሥራን እና ንግድን አሳንሶና አናንቆ የሚመለከት ነበር:: በዚህም የተነሳ የንግዱን ዘርፍ የተቆጣጠሩት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮያውያንና የውጭ አገር ነጋዴዎች ነበሩ:: ነጋዴዎችና የእጅ ስራ ባለሙያዎች ለህዝቡም ሆነ ለቤተመንግስት ሰዎች ከፍተኛ አገልግሎት ቢያበረክቱም፣ ከህብረተሰቡ የተገለሉ፣ በአብዛኛው ጊዜ ለጋብቻ የማይመጥኑ ተደርገው የሚቆጠሩ፣ በውትድርና ዓለም በመግባት አገራቸውን ለማገልገል የማይፈቀድላቸውና (በተለይ የእጅ ሞያ አዋቂዎች) የመሬት ባለቤትነት የተነፈጋቸው ነበሩ:: ከአድዋ ድል በኋላ አገሪቱ ከውጪው ዓለም ጋር ቀጥተኛና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ስትመሰርት ኋላቀር አመለካከቱ ቀስ በቀስ እየተፈረካከሰ መምጣት ጀመረ:: በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ - ጅቡቲ ምድር ባቡር ስራ ሲጀምር ከውጭ ወደ አገር ቤት የንግድ ዕቃዎችን በገፍ እንዲገቡ ያስቻለ ብቻ ሳይሆን፣ እግረ መንገዱን የካፒታሊስት ባሕል እና እሴቶች አብረው ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘልቁ ያደረገ ነበር:: በዚህ የተነሳም

---

[1] ይህ የእድሜ አሀዝ ጽሁፉ በተዘጋጀበት አመት (1999) የነበራቸውን እድሜ ይሰጣል::

የቤተመንግስት ሰዎች ከተራው ኢትዮጵያዊ ቀድመው በንግድ ዓለሙ ውስጥ ተሰማሩ:: የሚገርመው ደግሞ በዘመናዊው ንግድ ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የመጀመርያው የሆኑት ዳግማዊ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ነበሩ:: በመቀጠል ታላላቅ መሳፍንቶቻቸው ተከተሉ::

በወቅቱ ሕዝቡ ለነጋዴዎችና ለእጅ ስራ ባለሞያዎች ያሳይ የነበረው ንቀትና አሳንሶ የማየት ልክፍት ዳግማዊ ምኒልክ ለጀመሩት ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግ ፖሊሲ እንቅፋት እንደሚሆን ሲረዱ የሚከተለውን አዋጅ አወጡ:-

*ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ*
*ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ*
*ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ*

ከዚህ ቀድሞ ብረት ቢሠራ ጠይብ ሸማ ቢሠራ ሸማኔ ቢጽፍ ጠንቋይ ቤተክርስትያን ቢያገለግል ደብተራ እያላችሁ አርሶ ነጭ ከጥቁር አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ከዘውድ ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ እያላችሁ ነጋዴን ነግዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ቢገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ አጣቢ እያላችሁ ሰነፍ ብልትን እየተሳደበ አስቸገረ:: ቀድሞም ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ካዳምና ከሔዋን ነው እንጂ ሌላ ሁለተኛ ፍጥረት የለም ይህ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው አዳምንም «ብላዕ በሀፈ ገጽከ» ብሎታል ይህ ከቀረ ሁሉ ቦዘንተኛ ከሆነ መንግስት የለ አገር የለ በወዲያ አገር ግን ባውሮፓ ሁሉ አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ ነፍጥ ባቡር ቢሠራ መሐንዲስ እየተባለ እየተመሰገነ ሠራተኛውም ብዙ ይጨመርበታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም እናንተ ግን እንዲህ እየተሳደባችሁ ማረሻ የሚያሾል አሳጥታችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጉትና ልታጠፉት ነው::

እንግዲህ ግን እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው:: እንጂ ሌላውን መስደብ አይዶለም ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሠራል ሹምም አስረኽ ዓመት ለማስቀመጥ የሚቸግርኽ የሆነ እንደሆነ አስረኽ ወዲህ ስደድልኝ::

*ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻*[2]

ዓዋጁ እንዳሳየን ነጋዴና የእጅ ስራ ባለሞያዎች ባብዛኛው ሰው ይታዩ የነበረው እንደ «ሁለተኛ ፍጥረት» ነበር:: ጉዳዩን ለማሳጠር አንዲት ሴት ነገሩ ጭንቅ ቢላት ያለችውን ብንጠቅስ እንወዳለን:: ሴትዮዋ የጋብቻ ጥያቄ ይቀርብላታል:: ሆኖም ጥያቄውን ያቀረበው ሰው የማይመጥናት መስሎ ቢታያት

*አወይ ጉዴ*

*ሳግባሽ አለኝ ነጋዴ*

[2] ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር* (አዲስ አበባ፣ 1962)፣ ገጽ 421-2

አለች ይባላል፡፡ እንግዲህ እነ ቀኛዝማች ይህን ሁሉ ታግለው ስላሸነፉ ነው ያሁኑ ነጋዴ ጋብቻን ለመሰለ ታላቅ ጉዳይ የሚፈለግ ብቻ ሳይሆን ሰው ሁሉ ወዳጂ ጓደኛዬ ነው ብሎ ሊመካበት የሚጥረው፡፡

ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ በ1919 ዓ/ም ቡታጅራ አጠገብ በምትገኘው ኢሌ ተብላ በምትጠራ መንደር ተወለዱ፡፡ አባታቸው አቶ ኤገኖ ሽመቶ የመስቃን ጉራጌ ተወላጅ ሲሆኑ እናታቸው ወይዘሮ ደልጨሜ አሌዣ ደግሞ የክስታኔ ጉራጌ ነበሩ፡፡ እናታቸው ኢሌ ውስጥ በአነስተኛ ንግድ ውስጥ ተሰማርተው ነበር፡፡ ቀኛ ዝማች ስለእናታቸው የንግድ ተሳትፎ ከእናታቸው የሰሙትን ታሪክ በፍቅር ነው የሚያስታውሱት፡፡ ስለሁኔታው ሲናገሩ «እናቴ የዘጠኝ ወር ነብሰጡር ሆና ሌላ ጊዜ እንደምታደርገው ሁሉ ጠዋት ተነስታ ለንግድ ያዘጋጀችውን ቁሳቁስ ተሸክማ ገበያ ወረደች፡፡ ቀኑን ሙሉ ስትነግድ ውላ ዘጠኝ ጠገራ ብር አትርፋ ወደ ቤት ተመለሰች፡፡ ምሽት ላይ ወንድ ልጅ ተገላገለች ያን ልጅ ደግሞ ተካ ብላ ሰየመችው፡፡»

ያለ መታደል ሆኖ፣ ቀኛዝማች ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያሉ አባታቸውን በሞት ተነጠቁ፡፡ የአቶ ኤገኖ ሞት ለቤተሰቡ መበታተን ምክንያት ሆነ፡፡ እናታቸው ሌላ ባል ማግባታቸው ነው ነገሩን ሁሉ የበለጠ ያበላሸው፡፡ እልኸኛ ውና በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር መዋልን የማይወዱት ተካ ከናታቸው ጋር በመኖር በእንጀራ አባት ከመንገላታት በእድሜ ከኮሰሱት በኢኮኖሚ ከደቀቁት አያታቸው ጋር ለመኖር ቀያቸውን ጥለው ተሰደዱ፡፡

አያታቸው ቤት መኖር ጀምረው ብዙም ሳይቆዩ ሌላ ችግር ተፈጠረ፡፡ አባታቸው ሲሞቱ በውርስ የተገኘውን ሁሉ እንዲያስተዳድር አደራ የተሰጠው የታላቃቸው ታላቅ የሆነው ወንድማቸው በአጉል ሱስ ተጠመደ፡፡ ስራው በየቀኑ መረን የለቀቀ አልኮል መጠጣት ሆነ ፡፡ ውሎውም አዳሩም ከኮማሪቶች ጋር ሆነ፡፡ የመጠጥ ሱሱን ለማርካትና ኮማሪት ጓደኞቹን ለማስደሰት ሲል ንብረቱን መሸጥ ጀመረ፡፡ በመጨረሻ የእርሻ በሬዎችን ሲሸጥ በቤት ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ፡፡ አባታቸውን በሞት፣ እናታቸውን በእንጀራ አባት፣ የአባታቸውን ንብረት በወንድማቸው የተነጠቁት ተካ መግቢያ መውጪያው ጠበባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የመጣው ይምጣ በማለት ወደ አዲስ አበባ ለመሰደድ ቆረጡ፡፡

ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ሲጀምሩ መንገድ ላይ ከዚህ በፊት የሚያውቁት ሰው ይገጥማቸውና ሰውየው ከሱ ጋር ትንሽ ቆይተው እንዲሄዱ ይጋብዛቸዋል፡፡ ቀኛ ዝማችም ግብዣውን ተቀብለው ወደ ሰውየው ቤት አብረው ይሄዳሉ፡፡ ይህ አጋጣሚ የዕድሜ ልክ ትምህርት ያገኙበት ሆነ፡፡ በእንግድነት ባረፉበት መንደር ተስቦ ገብቶ ኖሮ ቀኛዝማች በበሽታው ተለከፉ፡፡ ወዲያው ሌሎች በበሽታው የተያዙ ሰዎች ገለል ወደ ሚደረጉበት አንድ ቤተክርስትያን ተወሰዱ፡፡ የወቅቱን አስከፊ ገጠመኝ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡፡ «በዛን ጊዜ ገና የ13 ዓመት ልጅ ስለነበርኩኝ በስፍራው በዕድሜ ትንሹና ይባስ ብሎ ደግሞ ዞር ብሎ የሚያይ የሚያስታምምና የሚያፅናና ዘመድ የሌለው ፍጡር እኔ ብቻ ነበርኩኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሌላው ሰው ሁሉ በሽታው እኔን ክፉኛ ስለጎዳኝ አብረውኝ የነበሩ በሽተኞች ሁሉ በኔ ተስፋ ቆረጡ፡፡ በሽተኛ በሞተ ቁጥር ሌሎች ከፍተኛ ዋይታ ያሰሙ ስለነበር የመንደሩ ሰው ሮጦ መጥቶ በመጀመርያ ይል የነበረው ውይ ያ ምስኪን ልጅ አረፈ ነበር፡፡ ያኔ በጣም የሰቀጠጠኝ ጉዳይ ያን ያህል ብቸኛ መሆኔ

ሲሆን ግርምት ያሳደረብኝ ደግሞ ለካስ ሞት ይህን ያህል ቅርብ ነው የሚል ሃሳብ ነበር። ከወረርሽኙ የተማርኩትና በኋላ ላይ በንግድ ህይወቴ እንደ ትልቅ ትምህርት የሆነኝ እንኳን ሌላ ሌላው ይቅርና ተስፋ ሳይቆርጡ በርትተው ከጣሩ ሞትንም ማሸነፍ እንደሚቻል ነው።»

ከወረርሽኙ እንደተረፉ በቀጥታ ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ አቀኑ። ቀኛዝማች ወደ አዲስ አበባ በሚጓዙበት ጊዜ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ከጣልያን ቁጥጥር ስር ነፃ የወጣች ብትሆንም አንዳንድ ሰዎች ዋናውን መንገድ ተከትለው በተጓዥ ላይ የስርቆትና የውንብድና ተግባር ይፈፅሙ ስለነበር ዋናውን መንገድ በመተው ተራራዎችን በማሳበር በአጨበር በኩል በማቋረጥ ነው ዋና ከተማው የደረሱት።

አዲስ አበባ ውስጥ ታላቅ ወንድማቸው የሆነው ደበላ ኤገኖ በልብስ ስፌት ሞያ ላይ የተሰማራ ስለነበር በቀጥታ መርካቶ በመሄድ አገኙት። ይህም የሆነው የልብስ ስፌት ሙያን በብዛት ይሰሩ የነበሩት ጉራጌዎች ስለነበሩ አንዱ የሌላውን አድራሻ ያውቅ ስለነበር ነው። ከወንድማቸው ጋር በተገናኙ ትንሽ ሰዓታት ውስጥ የአገር ቤት የልብ ጓደኛቸውን አርጋውን እዛው መርካቶ ውስጥ አገኙት። ምንም እንኳን ታላቅ ወንድማቸው ቀደም ሲል ስለንግድ ጥቅምና እሳቸውም ነጋዴ ቢሆኑ እንደሚሻላቸው የመከራቸው ቢሆንም እኩያቸው የሆነው አርጋው ስኬቱን እንደምሳሌ አድርጎ ሲያጫውታቸው በሃሳቡ ይበልጥ ተማረኩ። አርጋው ስለ ንግድ ጥቅም ሲያስረዳቸው «አሁን እኔ አምሳ ማርትሬዛ ያህል ገንዘብ ያጠራቀምኩት ስለነገድኩኝ ነው። በል እንካ ይቺን አንድ ማርትሬዛ ተቀበልና በቀጥታ ወደ ንግዱ ተሰማራ» አላቸው። ቀኛዝማችን ያኔ ያስደመማቸው «በእውነት አሁን እኔ እድሜዬን በሙሉ ብነግድ እንደ አርጋው አምሳ ማርትሬዛ አገኝ ይሆን?» የሚለው ሃሳብ ነው።

ደበላ የሰጣቸውን አንድ ማርትሬዛ አርጋው ከሰጣቸው አንድ ማርትሬዛ ጋር በመጨመር በነጋታው በጥዋቱ ዳቦ በመግዛት በየመንገዱ መሸጥ ጀመሩ። ገጠሬነታቸውን የተመለከቱ ልጆች አንድም የያዙት ዳቦ ጥራት የሌለው መሆኑን እያበሉ በርካሽ ለመግዛት ሲጥሩ ሲመች ደግሞ ገንዘባቸውን ለመንጠቅ ቢጣጣሩም እንደምንም ብለው የያዙትን ዳቦ ሸጠው ቤት ገቡ። ታዲያ ምን ያደርጋል በነጋታው ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩ ሰዎች እጅብ ብለው ቁማር ሲጫወቱ ሲመለከቱ እስቲ እኔም እድሌን ልሞክር ብለው ገብተው በቁማር ስለተበሉ ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ አስረክበው እጃቸውን አጨብጭበው ተመለሱ። በነጋታው እስከዛሬ ድረስ ሲያስታውሱት የሚያንገበግባቸውን ስራ ፈፀሙ። በህይወታቸው ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ የሌላ ሰው የደሞዝ ተቀጣሪ ሁነው ዋሉ። አንድ ጋዝ መሸጫ ቤት በጋዝ አከፋፋይነት በቀን አንድ ማርትሬዛ ተቆርጦላቸው ተቀጠሩ። አመሻሹ ላይ አንድ ማርትሬዛውን ዕንባ እየተናነቃቸው ተቀብለው ሁለተኛ ተቀጣሪ ሰራተኛ ላለመሆን ምለው ተገዝተው ወደቤት ተመለሱ።

በዛች አንድ ማርትሬዛ መርካቶ አሁን አዳራሽ በተሰራበት አካባቢ ከሚገኝ የአንድ ኢጣልያዊ ሸንኮራ ማከፋፈያ መጋዘን ሸንኮራ አገዳ በመግዛት ሌላ ሰፈር ይዘው በመሄድ በትንሽ በትንሹ እየቆራረጡ መቸርቸር ጀመሩ። ገበያው ደራላቸውና እየተመላለሱ ከመጋዘኑ ሸንኮራ አገዳ እየገዙ ሲቸረችሩ አርፍደው በረፋዱ ገበያ ብቻ ከ3 ማርትሬዛ በላይ አተረፉ። በትርፉና በስኬቱ የተደሰቱት ተካ ባላቸው ገንዘብ በሙሉ ሸንኮራ ገዝተው ወደ ተለመደው ቦታ አቀኑ። ሁኔታውን

አድፍጠው ይመለከቱ የነበሩ የከተማ ወሮበሎች እጅብ ብለው በመምጣት ለኔ ይህን ያህል ለኔ ደሞ ይህን ያህል በማለት ከከበቡአቸው በኋላ ሁሉም የቻለውን ያህል በመንጠቅ በተለያየ አቅጣጫ ሮጡ። በሁኔታው የተደናገጡት ተካ ሰውነታቸው ደነዘዘ። እንኳን ልጆቹን አሯሩጦ ለመያዝ መሞከር ይቅርና ዓይናቸውን ማመን እስኪያቅታቸው ድረስ ፈዘው ቀሩ። ይሄኔ በተደጋጋሚ በደረሰባቸው ኪሳራ ተደናግጠው ተስፋ እንደመቁረጥ ቢሉም እንደገና ራሳቸውን ካረጋጉ በኋላ አሁንም የመጣው ይመጣል እንጂ መነገዴን አላቋርጥም በማለት ለራሳቸው ቃል ገቡ። ይህ በአፍላ እድሜያቸው ያጋጠማቸው ወድቆ የመነሳት ትግል ኋላ ላይ ያጋጠማቸውን እክልና እንቅፋት በፅናት እየተቋቋሙ በማለፍ ስኬታማ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል።

እዚህ ላይ ያሁኑን የቀኛዝማችን ህይወት በጥሞና ለማየትና በንግድ ስኬታቸው ላይ ትምህርት አስተዋፅኦ አድርጓል ወይስ አላደረገም ብለን ለማመዛዘን ስለትምህርታቸው ደረጃ ትንሽ መልከት ማድረጉ አስፈላጊ ይመስለናል። የቀኛ ዝማች ተካ የትምህርት ደረጃ ከቤተ ክህነት ትምህርት የዘለለ አይደለም፤ ለዛውም ቢሆን በቅጡ አልተማሩትም። ቀኛዝማች ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አባታቸው ልጃቸውን በመያዝ እተካ ክርስትና አባት ቤት በመውሰድ ልጄን አስተምርልኝ በማለት ይሰጡዋቸዋል። የተካ የክርስትና አባት ደብተራ ሀይሉ በወቅቱ የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ገዢ የነበሩት የራስ ልዑል ሰገድ ፀሐፊ ነበሩ። ደብተራ ሀይሉ የሁለት ወንድና አንድ ሴት ልጅ አባት ቢሆኑም በወቅቱ ስለ ሴት ልጅ መማር ጥቅም አያውቁ ስለነበር ለሁለቱ ወንድ ልጆቻቸውና የክርስትና ልጃቸው ለሆኑት ለተካ እቤታቸው ውስጥ ዓለቃ ይስሀቅ የሚባሉ አስተማሪ ቀጠሩላቸው። ዓለቃ ይስሃቅ ጠንቃቃና ጎበዝ አስተማሪ ቢሆኑም የሃብታምም ይሁን የደሃ ልጅ ተማሪ እስከሆነ ድረስ ትምህርቱ የሚገለጥለት ሲለምን ነው ብለው ያምኑ ስለነበር፣ እንደ ሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የቆሎ ተማሪ ሁሉ ቀለባቸውን ከመንደሩ ነዋሪ ለምነው እንዲያገኙ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፉ። ለጉዳዩ አዲስ ያልሆኑት ደብተራ ሃይሉም በሃሳቡ ተስማሙ። ሦስቱም ልጆች እንደታዘዙት በልመና ያገኙትን እየተመገቡ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ከጊዜ በኋላም ከሁኔታው ጋር እየተላመዱ ሲመጡ ለምኖ መብላቱን እንደመደበኛ የተማሪ ህይወት ወሰዱት። ከዕለታት በአንዱ ቀን አቶ ኤገኖ ልጃቸውን ለማየት ደብተራ ሃይሉ ወደሚኖሩበት ከተማ ወረዱ። ኤገኖ ልጃቸው አቁማዳ ይዞ የሰው በር ላይ ቆሞ አገኙት። በነገሩ ግራ የተጋቡት አባት ምን እየሰራህ ነው ብለው ልጃቸውን ይጠይቃሉ። ልጅም በቤተ ክህነት ቀኖና ተማሪ ትምህርቱን እስኪጨርስ ድረስ ለምኖ መብላት አግባብ ስለሆነ ይህን እየፈፀምኩኝ ነው ይላሉ። አባት ግራ ይገባቸዋል። ቀኛዝማች ስለ ሁኔታው ሲያብራሩ «በጉራጌ ባህል ልመና በጣም የተጠላ ተግባር ስለሆነ አባቴ የምነግረውን ሁሉ አምኖ ለመቀበል አዳገተው። ይልቅዬ እኔን ከማድመጥ ልመና የሚለው ቃል ከመጠን በላይ ስላስቆጣው ንዴቱን ከኔ ለመደበቅ እስኪያቅተው ድረስ ፊቱ ልውጥውጥ አለ» ይላሉ። የልጃቸውን ማግባባት ወደ ጎን በመተው የልጃቸውን እጅ ጠፍረው በመያዝ ወደ ደብተራ ሃይሉ ቤት ገሰገሱ። እዛም እንደደረሱ «ደብተራ ሃይሉ ምነው ምን አጠፋሁ ምን በደልኩኝ ልጄን ዕውቀት አስተምርልኝ ብልህ ልመና ታስተምርብኝ» በማለት አምርረው ከተናገሩ በኋላ ልጃቸውን ይዘው ወደ መንደራቸው ተመለሱ። በዚች አጋጣሚ የቀኛዝማች የመማር ዕድል ተሰናከለ።

ወደ ወጣቱ ነጋዴ ተካ ኤገኖ የአዲስ አበባ እንቅስቃሴ ስንመለስ በኪሳራ ከተደመደመው የሸንኮራ አገዳ ችርቻሮ በመቀጠል በተለያዩ ጥቃቅን ንግዶች ላይ ከተሰማሩ በኋላ የተሸጋገሩት ወደ የገንዘብ ምንዛሬ ነው፡፡ ጣልያን ባልተመጣጠነ የጦር መሳሪያ ብልጫና በሕግ የተከለከለ የመርዝ ጭስ በመጠቀም በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ጊዜያዊ ድል በማግኘት የተወሰነውን የአገሪቱን ግዛት በተቆጣጠረበት አምስት ዓመታት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ በምኒልክ ብርና በማርትሬዛ ይካሄድ የነበረውን ግብይት በማስቆም ሊሬ በሚባለው የራሱ ገንዘብ እንዲተካ ማድረጉ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ከጣሊያን ወታደሮች፣ ከባንዳዎችና ከሴትኛ አዳሪዎች ሊሬ በመሰብሰብ በምኒልክ ብርና በማርትሬዛ ይመነዝሩት ነበር፡፡ ተካና እኩዮቻቸው ወደ ምንዛሬ ንግድ የተሰማሩት ግን ጣልያን ከኢትዮጵያ በሽንፈት ከተባረረች በኋላ ነበር፡፡

በዚህ የተነሳ እነ ቀኛዝማች በጥብቅ ይፈልጉ የነበረው የእንግሊዝ ጦር ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን በማገዝ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ይዞት የመጣውን የኢስት አፍሪካ ሽልንግን ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ከጣልያን ወረራ ራሷን ነፃ ብታወጣም ከ1933 እስከ 1937 ዓ.ም በነበሩት ዓመታት ለእርዳታ የመጣው የእንግሊዝ ጦር የተለያዩ ተልካሻ ምክንያቶችን በመፍጠር አገሪቱን በተዘዋዋሪ የቅኝ አስተዳደር ስር ለማቆየት ያላሰለሰ ጥረት ያደርግ ስለነበር ኢትዮጵያ የኔ የራሴ ነው የምትለው የመገበያያ ገንዘብና የፋይናንስ ተቋም አልነበራትም፡፡ ይህም ስለሆነ የእንግሊዝ ጦርና ከቅኝ ግዛቶቹ ያመጣቸው ወታደሮች ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያን አርሚ ተብሎ ይጠራ የነበረው የአገሪቱ መከላከያ ጦር ሳይቀር ደሞዙን ያገኝ የነበረው በኢስት አፍሪካ ሽልንግ ነበር፡፡ የእንግሊዝን ጦር ጨምሮ ቅኝ ግዛቱ ከነበሩ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከሕንድ፣ ከግብፅ፣ ከሱዳንና ከኬንያ ያመጣቸው ወታደሮች ያገር ውስጥ ምርቶችን በተለይ ደግሞ ለምግብ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ከኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች መግዛት ሲፈልጉ አገሬው የሚጠቀምበትን ማርትሬዛ ማግኘት ግድ ስለሆነ በቀጥታ ያመሩ የነበረው ወደ ገንዘብ መንዛሪዎቹ ነበር፡፡

ተካና እሳቸውን መሰል ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በገንዘብ ምንዛሬ ንግድ ላይ ይሰማሩ እንጂ በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው ንግዱን ከበላይ በመሆን ይቆጣጠሩ የነበሩት ሕንዶች ነበሩ፡፡ ታዲያ ሕንዶቹ ለግብይቱ የሚሆነውን አነስተኛ ገንዘብ ይዞ ለሚመጣ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ የያዘውን ገንዘብ በማርትሬዛ ለውጠው በመስጠት ሽልንጉን ማታ ይዞ መጥቶ እንዲያስረክባቸው ሲያደርጉ እንደ ቀኛ ዝማች ተካ ዓይነቱ ታማኝና ልምድ ያለው ንቁ ነው ለሚሉት ደግሞ አነስተኛ ገንዘብ ብድር በመስጠት እንዲነግድ ይረዱት ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ኪሳራ ገንዘብ አልባ የሆኑት ተካ ይህን ዕድል በመጠቀም ነበር ወደ ምንዛሬው ንግድ የገቡት፡፡ የገንዘብ ምንዛሬው ይካሄድ የነበረው በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ነበር፡፡ ንግዱ ይካሄድባቸው የነበሩት ዋና ዋናዎቹ ቦታዎች አዲስ አበባ እምብርት ላይ አሁን አራዳ ገበያ ተብሎ በሚጠራው (ፒያሳ) አካባቢ፣ ሜክሲኮ አደባባይና እስከ አሁን ድረስ መርካቶ ውስጥ ምንዛሬ ተራ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ነበር፡፡

በወቅቱ አንድ ኢስት አፍሪካ ሽልንግ በአፊሴል ይመነዘር የነበረው በአስር ማርትሬዛ ነበር፡፡ ነጋዴዎቹ ግን በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ በመመስረት አንዱን ሽልንግ በሰባት ማርትሬዛ መመንዘር ጀመሩ፡፡ በሽልንግ ደመወዛቸውን ተቀብለው ለምንዛሬ የሚመጡት የኢትዮጵያን አርሚ ወታደሮች በሁኔታው

በመቆጣት ድርጊቱን አይን እንዳወጣ ዝርፍያ ይቆጥሩታል። በዚህ የተነሳ መጀመሪያ ላይ በማስፈራራትና በንጥቅያ አንዱን ሽልንግ በአስር ማርትሬዣ ተመን መውሰድ ጀመሩ፤ ሆኖም ነጋዴዎቹ ራሳቸው ባወጡት ተመን ንግዱን ይቀጥላሉ። ነገር ግን፣ ወታደሮቹ እነሱ ባሉት ካልሆነ የግድያ ዛቻ መሰንዘር ይጀምራሉ። ከጥቂት ነጋዴዎች በስተቀር የተቀረው ፍንክች አልል አለ። የአብዛኛው ነጋዴ እምቢ ባይነትን እንደ ዐመፅ በመቁጠር ወታደሮቹ ጉዳዩን ለበላዮቻቸው ያሳውቃሉ። ጉዳዩ ንጉሠ ነገስቱ ድረስ ይሄዳል። በወቅቱ በተለያዩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች የተነሳ ጫና ስር የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት ተጨማሪ ጠላት ከማፍራት በማለት ይመስላል ከጦሩ ጋር በመወገን በእምቢተኛ ነጋዴዎች ላይ የጅራፍ ቅጣት ይወስናል። በዚህ የተነሳም ሶስት ነጋዴዎች ተይዘው ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ በጅራፍ ሲቀጡ እነ ቀኛዝማች ጎመን በጤና ብለው ንግዱን እርግፍ አድርገው ይተውታል። ተመሳሳይ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ ፊታቸውን ወደ ሌላ የንግድ ዘርፍ ለማዞር ወደ ንግድ ጥናት ይገባሉ።

አዲስ የንግድ ዓይነት ለማግኘት በማፈላለግ ላይ እያሉ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በከተማዋ በቁጥር ብዙ የሆኑትን የውጭ አገር ዜጎች በተለይ ደግሞ አብላጫውን የያዙት ጣልያኖች የሚፈልጉትን ቁሳቁስና አገልግሎት የሚያቀርቡ በቂ ሱቆች ስላልነበሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ተመልምለው በሱቅ በደረቴነትና በጫማ ጠራጊነት እንዲሰማሩ ተደረገ። ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ከቀረቡት መስፈርቶች ውስጥ በወቅቱ የሁሉም የውጭ ዜጎች መግባቢያ (Lingua Franca) የሆነውን ጣልያንኛ ቋንቋን መናገር የሚችልና ከዚህ በፊት በንግድ ስራ በመሰማራት በቂ ልምድ ያለው መሆን አስፈላጊ ነበር። ጣልያንኛን በበቂ ሁኔታ መናገር የሚችሉትና በቂ ልምድ የነበራቸው ተካ ውድድሩን በማለፍ ሲጋራ በማዞር ንግድ ላይ እንዲሰማሩ ከተመረጡት ሰባ አምስት ወጣቶች አንዱ ሆኑ። የተለያየ የሱቅ በደረቴነት የመነገድ ዕድል ቀርቦ ለምን ሲጋራ ማዞሩን እንደመረጡ ሲናገሩ፣ «ሲጋራ አዟሪነትን ከሌሎች አብልጬ የመረጥኩት በወቅቱ የበለጠ አትራፊ ንግድ እንደነበር አውቅ ስለነበር ነው» በማለት ያስረዳሉ። «በወቅቱ የመመረጥ ዕድሉን ያላገኙትም ሆነ በሌላ ሱቅ በደረቴነት ላይ የተሰማሩት ሁሉ የሲጋራ አዟሪነትን ትርፋማነት እየቆዩ ሲረዱት የንግድ ፈቃዳችንን እስከ ሁለት መቶ ማርትሬዣ ብር ለመግዛት ያግባቡን ነበር። ሆኖም ጣልያኖች ኢትዮጵያን ጥለው ሲሄዱ የሲጃራ ሱቅ በደረቴነት የማያዋጣ ሆነ። በዚህን ጊዜ ተካን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ንግዱን ትተው ወጡ። እንደ ሁሌው አንድ ንግድ አላዋጣ ሲል እንደሚያደርጉት ለትንሽ ጊዜ ላይ ታች በማለት የንግዱን ሁኔታ እያጠኑ ቆዩ። በመሃል ወደ አገር ቤት በመሄድ የመጀመሪያ ባለቤታቸውን አገቡ። ባለቤታቸውን ገጠር በመተው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ እንደገና ወደ ንግድ ዓለም ተመለሱ። ሆኖም የመጀመሪያው ትዳራቸው ዘላቂ መሆን አልቻል ብሎ በፍቺ ተጠናቀቀ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ዘመናዊ የአልኮል መጠጥን ወደ አገሪቱ በማስገባት ከሕዝቡ ጋር ያስተዋወቁት ግሪኮች እንደሆኑ ይታወቃል። በተለይ ደግሞ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ አልኮልን በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፋፋት ግሪኮች ቅድሚያውን ይይዛሉ። እነዚህ የግሪክ ነጋዴዎች የመጠጥ ንግዱ በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ የተገደበ ሳይሆን በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኙ ከተሞች ሁሉ

እንዲስፋፋ በነበራቸው ዓላማና በመሃላቸው በተፈጠረው ከፍተኛ ፉክክር የተነሳ ወኪል የሚሆኑአቸው አትዮጵያውያንን ወደ መመልመሉ አመሩ:: ከጋብቻ መልስ ስራ ፈተው የነበሩት ተካ አንድ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤት የነበረ ግሪካዊ ወኪል እንዲሆኑት ጥያቄ አቀረበላቸው:: ቀኛዝማችን በወኪልነት እንዲያገለግሉት የፈለጋቸው ኮስታስ አንቶኒኖስ የተባለ የአነስተኛ መጠጥ ፋብሪካ ባለቤት የነበረ ሰው ነው:: አንቶኒኖስ ባለ ዶሮ የተባለ የመጠጥ ፋብሪካ ነበረው::

ባለ ዶሮ በአገሪቱ አንደኛ ደረጃን ይዞ ከነበረው በኒኮላስ ፓፓሲኖስ ይመረት ከነበረው ባለ ፈረስ መጠጥ ቀጥሎ ሁለተኛው ነበር:: ኒኮላስ ፓፓሲኖስ ማለት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂና ዝነኛ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤት ለመሆን የበቃውን ታናሽ ወንድሙን ማለትም ኤልያስ ፓፓሲኖስን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ በመምጣት እንዲሰራ የጋበዘ ሰው ነው::

ወደ ተካና አንቶኒኖስ ጉዳይ ስንመለስ ግሪኩ ወኪሎቹን ወደ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወላይታ፣ ነቀምት፣ ጋሞጎፋ፣ አርሲና ወሎ ወደሚገኘው ካራቆሬ ሲልክ ቀኛ ዝማች ጅማ ሄደው እንዲነግዱ መደባቸው:: መጀመሪያ ላይ ተካ ጅማ በመመደባቸው ደስተኛ አልነበሩም:: እንደቀኛዝማች አመለካከት ምንም እንኳን ጅማን በአካል ተገኝተው ባያውቋትም በወሬ ይሰሙት እንደነበረው አብዛኛው የከተማው ነዋሪ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ስለሆነ ለአልኮል መጠጥ እጅግም ነው ባይ ነበሩ:: ሆኖም አንቶኒኖስ ስለጅማ ከተማና የመጠጥ ገበያው ከሳቸው የተሻለ የንግድ መረጃ ስለነበረው ቀኛዝማችን ያለመታከት በማግባባት ወደ ስፍራው እንዲሄዱ አደረገ:: በወቅቱ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤቶች በሆኑት ግሪኮች መሃከል በነበረው ከፍተኛ ፉክክር የተነሳ ወኪል የሚሆኑዋቸው ኢትዮጵያውያን በቂ ገንዘብ ሊኖራቸው እንደማይችሉ በመገንዘብ ታማኝና ቀልጣፋ ናቸው ላሉዋቸው መጠጡን በዱቤ ወስደው ከሸጡ በኋላ ገንዘቡን እንዲመልሱላቸው አመቺ ሁኔታ ይፈጥሩላቸዋል::

ታህሳስ 19 ቀን 1942 ዓ/ም የ23 ዓመቱ ወጣት ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ፣ ከዚህ በፊት ከወሬ በስተቀር አይተዋት ወደማያውቋትና በሳቸውና በከተማዋ እንዲሁም ባካባቢዋ ባሉ ቦታዎችና ነዋሪዎቿ ሁሉ በታሪክ ሲወሳ የሚኖር ገድል ለመስራት፣ ኮስታስ አንቶኒኖስ በዱቤ የሰጣቸውን ዘጠኝ መቶ ጠርሙስ ባለ ጆሮ የአልኮል መጠጥ (አንዱን በአንድ ብር ሂሳብ) የጣልያን ስሪት በሆነ ያረጀ የጭነት መኪና ሸክፈው ከሾፌሩ ጎን በመቀመጥ ጉዞአቸውን ሀ በማለት ከአዲስ አበባ ተነሱ:: እንደዛሬው በዘመናዊ አቅድ ባልተሰራና በወላለቀው የጅማ አዲስ አበባ መንገድ ባሮጌው መኪና እየተናጡ በድካም ዝለው ከሦስት ቀን በኋላ እኩለ ሌሊት ገደማ ጅማ ደረሱ:: በነጋታው ጅማ ከደረሱ በኋላ ነገሮች ሁሉ ከጠበቁት በላይ የተገላቢጦሽ ሆኖ ጠበቃቸው:: የከተማው ህዝብ እንደጠበቁት የአልኮል መጠጥን እርም ያለ ሳይሆን ከገመቱት በላይ የሚጎነጨው መሆኑን በዓይናቸው በብረቱ ተመለከቱ:: ይባስ ብሎ ድንጋጤ ውስጥ የከተታቸው፣ የተለያዩ የመጠጥ ምርቶችን በማከፋፈል የሚተዳደሩ የግሪክና የአርመን ነጋዴዎች ጅማ ውስጥ መከተማቸውን ሲያውቁ ነው:: ጅማ

ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ፋክክር በመፍራት ባቅራቢያው ወደ ሚገኝ ትንሽ ከተማ በመሄድ ያመጡትን መጠጥ መሸጥ እንዳለባቸው ወሰኑ፡፡

ከጅማ ጋር ስትወዳደር በጣም አነስተኛ ወደምትባለው አጋሮ ከተማ አፈገፈጉ፡፡ እዛም ቤት እሳት አለ እንደሚባለው ያልጠበቁዋቸው ሁለት ግሪኮች የከተማዋ መጠጥ አከፋፋዮች ሆነው ጠበቁአቸው፡፡ «ጉድ ነው አገሩ በሙሉ በውጭ ነጋዴዎች ተወሯል አይደል እንዴ?» አሉ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ጅማ በነበሩበት ወቅትና አሁን ደግሞ አጋሮ ውስጥ በታዘቡት ሆኔታ አገሬው ለነዚህ የውጭ ዜጎች ከፍተኛ ፍቅር ያለውና እምነትም የጣለባቸው ሆኖ ተሰማቸው፡፡ ተካ ያኔ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ወጣ ገባውን ማጥናት ጀመሩ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ የመጀመሪያው ግምታቸው ስህተት መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ አገሬው አማራጭ አጥቶ ነው እንጂ ከፈረንጆቹ ጋር የነበረው ትስስር ጥልቀት ያለው ሳይሆን ላይ ላዩን መሆኑን አረጋገጡ፡፡ በወቅቱ በአገሬውና በፈረንጅ ነጋዴዎች መሐል የነበረው ግንኙነት ምን ዓይነት እንደነበር ቀኛዝማች ባጭሩ እንዲህ ይገልጹታል፡-

1ኛ. አጋሮ ከተማ በመጠጥ ንግዱ ላይ የተሰማሩት ሁለቱ ግሪኮች በሚያገኙት ትርፍ የረኩ ስለነበር፣ በሌሎች፣ ተጨማሪ የንግድ ዘርፎች ላይ መሳተፍ ቀርቶ የያዙትንም ንግድ የማስፋፋት አዝማሚያ አልነበራቸውም፡፡

2ኛ. የግሪኮቹ የስራ ሰዓት እንደ ገበያው ሁኔታ የሚቀያየር ሳይሆን ዝንፍ የማይል ቋሚ ዓይነት ነው፡፡ ሱቆቹ ጠዋት በሶስት ሰዓት ተከፍተው ለምሳ በሰባት ሰዓት ላይ ይዘጋሉ፡፡ እንደገና በ9 ሰዓት ተከፍተው እስከ ምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡ በሰንበትና በበዓላት ይከፈታሉ ማለት ዘበት ነው፡፡ ሱቆቹ በተዘጉበት ጊዜ ደንበኞች መጠጥ ፈልገው ወደ ግሪኮቹ ቤት ቢሄዱ የሚሰጣቸው መልስ ሱቁ ክፍት ሲሆን ተመለስ የሚል አጭርና ግልፅ መልስ ነበር፡፡

3ኛ. ፈረንጆቹ ራሳቸውን ልዩ ፍጡራን አርገው ይቆጥሩ ስለነበር በግብይት ወቅት በነጋዴውና በደንበኛው መካከል ከሚደረገው ግንኙነት ውጭ የዘለለ ግንኙት ከአገሬው ጋር አልነበራቸውም፡፡ ፈረንጆቹ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከአገሬው ጋር ስላልፈጠሩ ራሳቸውን ያገለሉ ፍጡራን ነበሩ፡፡ አገሬው ጋር ተደባልቆ ከመተዋወቅ ይልቅ ትርፍ ጊዜያቸውን እርስ በርስ ካርታ በመጫወት ያባክኑ ነበር፡፡

ይህን ያስተዋሉት ተካ የመጀመሪያ እርምጃቸው ሱቃቸውን ቀኑን ሙሉ ክፍት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ደንበኛ እስከ መጣ ድረስ ምሽት ላይም ቢሆንም ለማስተናገድ ወሰኑ፡፡ በመቀጠል ከአገሬው ጋር መልካም ትስስር ማበጀት እንዳለባቸው በመገንዘብ ራሳቸውን ማስተዋወቅና ታዛዥ መሆናቸውን ማሳየት ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳን አጋሮ ከተማ ትንሽ ብትሆንም አካባቢውን የቡና አብቃይ አገር በመሆኑ አብዛኛው የከተማው ነዋሪም ይሁን ገበሬው በንፅፅር ከተቀረው የአገሪቱ ክፍል ጋር ሲተያይ የመግዛት አቅሙ ከፍተኛ ነበር፡፡ ሆኖም ትንሿ አጋሮ ትቅርና ጅማ ራስዋ አገሬው የሚፈልገውን ዘመናዊ እቃዎች የማቅረብ አቅም አልነበራቸውም፡፡ ይህን የተረዱት ተካ ያካባቢውን ባላባቶችና ታዋቂ

ሰዎችን ባገኙ ቁጥር አዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ስሄድ ምን ይዤላችሁ ልምጣ በማለት ይጠይቁ ጀመር፡፡

ያኔ አዲስ አበባ ካልሆነ በስተቀር በአካባቢዋ እንደልብ የማይገኙትና በነዋሪው ከፍተኛ ተፈላጊነት ከነበሩዋቸው ቁሳቁሶች መሃከል፡- ከወርቅ የተሰሩ የጣትና የጆሮ ጌጣጌጦች፣ የተወሰኑ አልባሳት፣ ዘመናዊ ጫማዎች፣ የቤት ዕቃዎች (ለምሳሌ የሸቦ አልጋ፣ ባለቀለበቱ በርሜል)፣ እንዲሁም የድንጋይ ወፍጮና በዘመናዊ ወፍጮ የተፈጨ በርበሬ አንዳንዶቹ ነበሩ፡፡ ነዋሪው እነዚህን ዕቃዎች ከአዲስ አበባ እንዲያመጡላቸው ቀኛዝማችን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ቢሆኑም አንዳንድ እክሎችም አላጡም፤ ለምሳሌ፣ አብዛኞዎቹ ነዋሪዎች ዘመናዊ ጫማ መጫማት ቢሹም ልካቸውን ወይም የእግራቸውን ቁጥር አያውቁም ነበር፡፡ የሚመጥናቸውን ጫማ በትክክል ለማምጣት ሲሉ ቀኛዝማች የደንበኛቸውን እግር ካርቶን ወረቀት ላይ በማስቀመጥ በስክርቢቶ የእግሩን ቅርፅ ወረቀቱ ላይ ከነደፉ በኋላ ወረቀቱ ላይ ስም በመፃፍ አዲስ አበባ ድረስ ተሸክመው መሄድ ነበረባቸው፡፡ ለጣት ቀለበት ፈላጊው ደግሞ የጣቱን ልክ ለማወቅ በጣቱ ዙሪያ ሽቦ በማሰር ከለኩ በኋላ ቋጠሮ በማበጀት መጠኑን ያውቁ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የያኔዋ አጋሮ እንኳን ሆስፒታልና ክሊንክም ስላልነበራት እምነትዋን የጣለችው ሳሙኤል በሚባሉ የልምድ የጤና ረዳት ነኝ በሚሉ ግለሰብ ላይ ነበር፡፡ እኝህ ሰው ቂጥኝ ያዘኝ ለሚል ሰው ሁሉ ፔንሲሊን የሰጡ በማስመሰል ወተት ይወጉ ነበር፡፡ ታካሚውም መርፌ በመወጋቱ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ የዳነ መስሎት ይደሰት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሲውል ሲያድር ከበሽታው አለመፈወሱን ሲያውቅ ማማረሩን ይቀጥላል፡፡ ይህን ሁኔታ ቀኛዝማች ከአገሬው ሰምተው ክትትል አድርገው እውነት መሆኑን ሲደርሱበት ሳሙኤልን ጠርተው ከወቀሱ በኋላ ዳግም እንዳይለምዳቸው በማስጠንቀቅ አዲስ አበባ ለስራ በሄዱ ቁጥር ፔንሲሊን ይዘውላቸው ይመጡ ጀመር፡፡ በእውነተኛው ፔንሲሊን ታክመው የዳኑት ሁሉ ፔንሲሊኑን ያመጡት ተካ መሆናቸውን ሲያውቁ የቀኛ ዝማች ውለታ ይሰማቸው ጀመር፡፡ አገሬው ከቂጥኝ በተጨማሪ ያስቸግረው ከነበረው በሽታዎች መሃከል ወባና ኮሶ ይገኙበት ነበር፡፡ ቀኛዝማች ለነዚህም የሚሆኑ መድኃኒት ከአዲስ አበባ እያመጡ ለሳሙኤል በሽያጭ ማቅረቡን ቀጠሉ፡፡ ሆኖም ነጋዴ ትርፍ ያለው ነገር ስለሚያማልለው የመድኃኒቶቹን ትርፋማነት ሲገነዘቡ ለሳሙኤል መሸጡን ትተው ሱቃቸው ውስጥ ራሳቸው ለደንበኞቻቸው መሸጥ ጀመሩ፡፡ አገሬው ከአዲስ አበባ ድረስ እቃ እንዲያመጡለት ሲጠይቅ ያለ ምንም የትራንስፖርት ክፍያ በማምጣት በቸገረው ጉዳይ ሁሉ ተሳታፊ በመሆናቸው የተነሳ ተካ የሚወደዱ ብቻ ሳይሆኑ የሚመለኩ አይነት ሰው ሆኑ፡፡

ቀኛዝማች ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ለስራ ያላቸው ከበሬታ ወደር የለውም፡፡ ከብዙዎቹ ባህሪዎቻቸው አንዱ ቀኛዝማች የሚታወቁበት በሰዓት ቀልድ የለም በሚለው አቋማቸው ነው፡፡ ስለ ሰዓት ያላቸውን ከበሬታ ሲገልጹ «እኔ ሰዓት ከሚሰርቅብኝ ሰው ገንዘብ የሚሰርቀኝን እመርጣለሁ» ይላሉ፡፡ ስለዚህም የቀኛ ዝማችን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ቤተሰባቸው ቀርቶ የጅማ ሰው ሁሉ ያውቀው ነበር ይባላል፡፡ ዕቃ ከአዲስ አበባ እንዲመጣለት የሚፈልግ ሰው መቼና በስንት ሰዓት ጅማ አይሮፕላን ጣቢያ ሄዶ እንደሚያገኛቸው ያውቅ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ

አየር መንገድ ትኬት ቢሮ ሳይቀር የቀኛዝማችን ቋሚ የጉዞ ኘሮግራም ስለሚያውቅ ትኬታቸውን ከመምጣታቸው በፊት አዘጋጅቶ ይጠብቃቸው ነበር።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው፣ በደንበኛው ፍላጎት ላይ የተመሰረተው የመገበያያ ሰዓታቸው፣ ለነዋሪው በሚሰጡት ከበሬታና ነፃ አገልግሎታቸው፣ ሁሉንም የንግድ እንቅስቃሴያቸውን በተጠና አደረጃጀትና ወቅቱንና ሰዓቱን ጠብቆ በሚካሄደው እንቅስቃሴያቸው፣ በአጋሮና በአካባቢው ገበሬዎች ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታን በማግኘታቸው በተጨማሪ እሰየው የኛ ልጅ በማለት ግሪኮቹን በመተው የሳቸው ደንበኛ እንዲሆን አስቻለው። አጋሮ ላይ ከተራ ወኪልነት ተነስተው የሩቅ ግባቸው የሆነውን የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከውጭ ነጋዴዎች ቁጥጥር ነፃ የማውጣት ትግልን ሀ ያሉት ተካ በሁለት ዓመት ውስጥ ዘመቻቸውን ጅማ ድረስ በመሄድ ለመግጠም በስነልቦናም ሆነ በገንዘብ ዝግጁ ሆኑ።

አጋሮ ላይ የፈጠሩት ዝና ቀድሞአቸው ጅማ ገብቶ ነበር። ሆኖም ተካ ሌላ ጉዳይ ገጠማቸው። አጋሮ ላይ ባገኙት ስኬትና ዝና ያልተደሰተው አንቶኒኖስ መተናኮሉን ይጀምራል። በአንድ ወቅት አቅመቢስና ልምድ የለሽ ወኪሉ የነበሩት ተካ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ ነጋዴ መሆናቸውን ሲያውቅና ብዙ ሰዎች ተካን አድንቀው መናገር ሲጀምሩ በተዘዋዋሪ የራሱን ድክመት የሚያሳይ መስሎ ተሰማው። በዚህን ጊዜ ተካን ለማክሰር የማይፈነቅለው ድንጋይ ጠፋ። አንዴ የነበረውን ከፍተኛ የሀብታምነት ዝና በመጠቀም ከሀብታም የውጭ ነጋዴዎች ጋር በሽርክና መስራትን እንደ ክብር ከሚመለከቱ አትዮጵያውያን ባለስልጣኖች ጋር በመተባበር ገንዘቤን ሰርቆኛል በማለት አዲስ አበባ ውስጥ አሳሰራቸው። ቀኛዝማች ምንም እንኳን ጥፋት እዳልሰሩ ቢያውቁም እስር ቤት ከመታሰር አጥፍቻለሁ በማለት ከእስር በመፈታት ንግዳቸውን መቀጠሉ የሚያዋጣ መሆኑን በማወቅ ይቅርታ በመጠየቅና የተባለውንም ገንዘብ እንደሚከፍሉ ቃል በመግባት ተፈቱ። ያሉትንም ፈፀሙ። አንቶኒኖስ አሁንም የአንድ እዚህ ግባ የማይባል ወጣት ኢትዮጵያዊ የንግድ ድልን በነጮች ላይ እንደተቃጣ ጥቃት በመቁጠር እሳት የላሰ ነጋዴ ነው የተባለ ግሪካዊ በመመልመል የሚያስፈልገውን ሁሉ ድጋፍ በመስጠት ጅማ ድረስ ላከባቸው። ሆኖም ግሪኩ የንግድ ችሎታ ሳያንሰው የካርታ ሱስ ስለነበረበት ጊዜውን ካርታ በመጫወት ሲያሳልፍ ጠንቃቃውና ስኬታማው ተካ በኪሳራ ጅማን ለቆ እንዲወጣ አደርጉት። ከስህተቱ አልማር ያለው አንቶኒኖስ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲከስር ቆይቶ በመጨረሻ ላይ በ1966 ዓ/ም አብዮት ሲነሳ ኢትዮጵያን ጥሎ ወደ አገሩ ቢመለስም እዛ በደረሰበት ችግር ራሱን ገደለ።

በ1945 ዓ/ም አካባቢ ጅማ ውስጥ የጠጅ ቤት ባለቤት የሆኑትንና ውቢቷን ወይዘሮ ደጊቱን በደመቀ ጋብቻ በማግባት ቀኛዝማች የእድሜ ልክ ትዳራቸውን መሠረቱ። ሁለቱም ተጋቢዎች ጅማ እምብርት ላይ የነበረውን ጠጅ ቤት ወደ ተካ ሆቴልነት ለወጡት። በዚህ ወቅት አጋሮ ላይ የጀመሩትን የውጭ ነጋዴዎችን ከመጠጥ ንግድ የማስወጣት ትግል ጅማ ላይ ቀጥለው ነቅነቅ የማይሉ የዘርፉ ቁጥር አንድ ነጋዴ ሆኑ።

በወቅቱ ጅማ ውስጥ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ያከፋፍሉ የነበሩት አንቶኔሊ እና ዳንኤሊ የተባሉ ጣልያኖች ነበሩ። ተካ እኔም ላከፋፍል ቢሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ

ቢራ ፋብሪካ ሃላፊዎች ልጅነታቸውን በመመልከት ከገንዘብም ገንዘብ ከችሎታም ችሎታ አይኖረውም በማለት ከለከሉአቸው:: ቆየት ብለው ግን የማከፋፈል ዕድሉን ሰጧቸው:: ከፈረንጆች ባነሰ ዋጋ በማከፋፈልና በዘመኑ አግባብ በነበራቸው የተለያዩ የብልጠት የማስታወቅያ ስራዎች በማሰራት ጣልያኖችንና በጅማ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበረውን መሎቲ ቢራን ከገበያ ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ከአዲስ አበባ እስከ ጐሬ፣ ከደሴ እስከ አሰብ፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ ደግሞ ጅቡቲን ጨምሮ ከድሬደዋ እስከ ጂጂጋ ያለውን የቢራ ንግድ ተቆጣጠሩት::

በማከፋፈልና የሆቴል ንግድ ዘርፍ በመግባት ከፍተኛ ሀብትና ንብረት ካፈሩ በኂላ ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ የንግድ ዘርፍ በመግባት የሚሸጡትን ዕቃ ወደ ማምረት ገቡ:: ከ1947 ገደማ ጀምሮ በጊቤ አካባቢ ላይ በቡና ተክል ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ ጀመሩ:: ስለ ዘመናዊ እርሻ ያላቸውን ልምድና ዕውቀት ውስኑነት በደንብ የሚያውቁት ተካ በዚህ የንግድ ዘርፍ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ሀብት እና እውቀት ያላቸውን ሰዎች አብረዋቸው እንዲሰሩ መገፋፋትና ማስተባበር ጀመሩ:: በዚህ የተነሳም በ1950 አካባቢ ጋላንቲኒ ከሚባል ጣልያናዊ ከበርቴና የሳሪስ ወይን ጠጅ ባለቤት ከነበረው አሌክሳንድራኪስ ከሚባል ግሪካዊ ጋር በመተባበር የአግሮ ኢንዱስትሪ ካምፓኒ መሠረቱ:: የካምፓኒውን መዋጮ የአንበሳውን ድርሻ የጨበጡ እንደመሆናቸው ድርጅቱ ተካ ኤገኖና ካምፓኒው በማለት ተሰየመ:: በ150,000 ብር የተቋቋመው ካምፓኒ ጌራ እና ዶዮ ላይ ከካፒታሉ የተወሰነ ገንዘብ በማውጣት 490 ሄክታር መሬት በመግዛት ስራውን ጀመረ::

በ1961 ዓ.ም የሸሪኮቻቸውን ዕጣ በሙሉ በመግዛት ካምፓኒውን የግላቸው አደረጉት:: ቢሆንም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የነበረውን አናስታሲዮ የተባለውን ጣልያናዊ በስራ በአስኪያጅነቱ እንዲቀጥል በማድረግ ስራውን ገፉበት:: ካምፓኒው 200 ቋሚ ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን በምርት ወቅት ተጨማሪ 600 ጊዚያዊ ሰራተኞችን ይቀጥር ነበር:: የቀኛዝማች እርሻ በወቅቱ በአካባቢው ከነበሩት የተለየና በእጅጉ የላቀ ነበር:: እርሻውን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል፡-

1ኛ እርሻው የተደራጀውና ይመራ የነበረው ዘመናዊ የእርሻ እንዱስትሪዎች መከተል ባለባቸው የፋይናንስ፣ የአስተዳደርና የቴክኒካዊ መስፈርቶችን በመሆኑ ነው::

2ኛ የእርሻው የአመራረት ጥራት በዘርፉ ኤክስፐርቶችና በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ዕውቀት ከነበረው የኦክሎሃማ ዩኒቨርስቲ ዕውቅና የተሰጠው ከመሆኑ በተጨማሪ ዩኒቨርስቲው በሙያው ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ምሁራን እና ተማሪዎች በመላክ በእርሻ ድርጅቱ ውስጥ ምርምር እንዲሰሩ በማድረጉ ነው::

3ኛ የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ብድር እንዲፈቅድ ሲፈለግ እንደ ሞዴል ዘመናዊ አግሮ ኢንዱስትሪ በመውሰድ የዓለም ባንክ ባለስልጣኖች ይጎበኙትና ይሁንታቸውን እንዲሰጡ መንግስት ይጠቀምበት የነበረ ድርጅት መሆኑ ነው::

4ኛ በአካባቢው ከነበሩት መሰል የእርሻ ካምፓኒዎች በተለየ መልኩ ምርታማና አትራፊ መሆን የቻለው በትንሽ ሰራተኛ ብዙ ማምረት በመቻሉ ነው፡፡ ይኸውም ካምፓኒው ለሰራተኛው የሚከፍለው ከመሰል ድርጅቶች ጋር ሲነጻጸር ትንሽ ነው፡፡ ሆኖም ሠራተኞች የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ያገኙ ስለነበር በሙሉ አቅማቸው ለማምረት ዝግጁ ነበሩ፡፡

ካምፓኒው ለሰራተኞች ይሰጥ ከነበሩት ጥቅማጥቅሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፦

1. ምቹ የመኖሪያ ቤቶችና የገላ መታጠቢያ የመሳሰሉ አቅርቦት ለሰራተኛው በነፃ ያቀርባል፡፡
2. መሰል ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው የበቆሎ ዱቄት ሲያቀርቡ፣ የቀኛዝማች ድርጅት ግን ለሰራተኞቹ እንጀራ በወጥ በማቅረብ ምግብ ለማዘጋጀት የሚያባክኑትን ጉልበት በመቆጠብ ስራ ላይ እንዲያውሉ ያደርግ ነበር፡፡
3. ሰራተኞች ጠንካራና የበለጠ አምራች እንዲሆኑ ለማድረግ ንጋት ላይ ከእንቅልፋቸው በመቀስቀስ የአካል አንቅስቃሴ ስፖርት እንዲሰሩ ይደረጉ ነበር፡፡
4. ሰራተኞች በአካባቢው ከፍተኛ የጤና ዕክል ይፈጥር በነበረው የወባ በሽታ ተጠቅተው ከስራ እንዳይስተጓጎሉበት በነፃ የወባ መከላከያ ያድል ነበር፡፡

ቀኛዝማች በደንብ የተደራጀ፣ የተሟላና የተቀላጠፈ አስተዳደር በመፍጠር ውጤታማ የእርሻ ድርጅት በማቋቋማቸው፣ በሌላ አነጋገር በምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ በዘመናዊነት ወደር የሌለው ሜካናይዝድ የእርሻ ካምፓኒ በማቋቋማቸው የተነሳ፣ በ1957 ዓ/ም በወቅቱ በአገሪቱ ከፍተኛ ክብርና ዝና የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የእርሻ ዘርፍ የወርቅ ሜዳልያ ለመሸለም በቅተዋል፡፡

በ1965 ዓ/ም ላይ ከጅማ ከተማ 73 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ጎጀብ አካባቢ የራስ መስፍን ሁለት ልጆችና የራስ መስፍን እህት ይዞታ የነበረውን 60 ጋሻ መሬት ገዙ፡፡ ይህ ለእርሻ የሚሆነውን ውኃ በቀላሉ ከጎጀብ ወንዝና በአካባቢው ከሚገኙ አራት ገባር ወንዞች ያገኝ የነበረ ለምና ምርታማ መሬት ነበር፡፡ በዚህ መሬት ላይ ቀኛዝማች ማምረት ከጀመሩት መካከል በቆሎ፣ በርበሬ፣ ጥጥ፣ አናናስ፣ ብርቱካን እና ሶያቢንስ ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ መጀመሪያ ላይ ከጣልያን ሽንኩራ አገዳ በመግዛት ሽንኩራ ቸርቻሪ የነበሩት፣ በመቀጠል የሕንድ ገንዘብ ምንዛሬ ተላላኪና የግሪክ መጠጥ ፋብሪካ ባለቤት ወኪል በመሆን ንግድንና ኢትዮጵያዊነትን በስኬት ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ሲታገሉ ያደጉት ተካ አጋሮና ጅማ የነበሩትን የውጭ ነጋዴዎች አሸንፎ ከንግድ ውጭ በማድረግ ያገኙትን ድል ድሬዳዋ ላይ በመድገም፣ የፈረንጅ ወኪል ከመሆን አልፈው ፈረንጅ ቀጥረው ማሰራትን እንደ ግብ

ሳይቆጥሩ፣ አገሪቱ ውስጥ በአግሮ እንዱስትሪው መስክ ከፍተኛ ዝና ካላቸው ከተንዳሆ ጥጥ ተክልና ከወንጂ ስኳር ጋር ለመወዳደር ቆርጠው ተነሱ፡፡ በዚህ የተነሳ ከአንድ የአሜሪካ የንግድ ድርጅት ጋር በመተባበር የታሸጉ የአናናስ ምርቶችን፣ የቲማቲም ድልህንና ጭማቂን የመሳሰሉ በማምረት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተዘጋጁ፡፡ ሆኖም ምን ይደረግ በ1967 መባቻ የደርግ መንግስት መጥቶ ባጭር የተቀጨ ጉዞ አደረገው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በ1964 ዓ/ም 800,000 ብር በማውጣት በጅማ ከተማ ታሪክ የመጀመሪያውን ዘመናዊ ሆቴል ከፍተዋል፡፡ ሆቴሉንም ለሚወዱአቸው ባለቤታቸው መታሰቢያ እንዲሆን ደጊቱ ሆቴል ብለው ሰይመውታል፡፡ ሆቴሉ ካሟላቸው ዘመናዊ ዕቃዎች በተጨማሪ እንደሳቸው ሁሉ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት (በስዕል ዘርፍ) አሸናፊ የነበረው፣ የሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ ስዕሎች ነበሩት፡፡

መጨረሻ በ1966 ዓ/ም ወታደሮች ስልጣን ሲይዙ ተካና እሳቸውን የመሰሉ፣ ጥረው ግረው ሀብት ያፈሩ፣ ለሞትና ለእስር ተዳረጉ፡፡ ድህነትን ታግለው ያሸነፉት ተካ፣ ኢትዮጵያዊነትን በወሬ ሳይሆን በተግባር ክብር ያላበሱት ተካ፣ በደርግ መንግሰት «የሰፊው ሕዝብ ጠላት»፣ «የጭቁኑ ደም መጣጭ»፣ «የኢምፔሪያሊዝም ቡችላ» ተብለው ዘብጥያ ወረዱ፡፡ ሁለት ጊዜ ታስረው ፍዳቸውን አዩ፡፡ እስር ቤት ውስጥ ስህተትህን አጋልጥ የሚለው ተደጋጋሚ ዛቻ ሲበዛባቸው «አዎ አንድ ስህተት ፈጽሜአለሁ፤ እሱም እኩዮቼ የሆኑት የውጭ ነጋዴዎች ሀብታቸውን ውጭ አገር ሲያከማቹ እኔ ግን አገሬ ነው በማለት እዚህ አስቀምጬ ለናንተ ማስረከቤ ነው» በማለት መለሱ፡፡ ቀኛዝማች የደርግ ዘመንን አጥብቀው የሚጠሉት፣ ሀብትና ንብረታቸውን ስለቀማቸው ብቻ ሳይሆን እንዳይሰሩ ስለከለከላቸውም ጭምር ነው፡፡

በእርግጥ ቀኛዝማች አብዮቱ እንደፈነዳ አልነበረም ለእስር የተዳረጉት፡፡ ያ ንግድን አቀላጥፎና ከሌሎች በልጦ በመገኘት ለከፍተኛ ስኬት ያበቃቸው ብሩህ አእምሮ በአደጋ ጊዜም እሳቸውን ለመታደግ ረድቶአቸዋል፡፡ በዚያ ወቅት እያንዳንዷን ሁኔታና እርምጃ በጥንቃቄና በብልሃት ያልተራመደ ታዋቂ ሰው ባልታሰበ ቅፅበት ህይወቱን የሚያጣበት አጋጣሚ ብዙ ስለነበረ፣ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ ንቁና ፈጣን መሆን የግድ ነበር፡፡ ቀኛዝማች ራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የወሰዱት እርምጃ ራሳቸውን ተስፋ የቆረጠና የቦዘነ ሰው አስመስሎ በመታየት ከጠላቶቻቸው ጥቃት ለማምለጥ ዘየዱ፡፡

ለዚህም ሲባል ወዳጃቸው ከሆኑት ከአቶ እየሱስ ወርቅ ዛፉ ፒፓ በመዋስ ትምባሆ ማጨስ ጀመሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቻይና አገር ስሪት የሆነና በወቅቱ የአብዮቱ ተከታዩች ያጠልቁት የነበረ ኮፍያ በማድረግና የታችኛው መደብ አባሎች ይለብሱት የነበሩትን ልብሶች በመልበስ ስራፈቱና ቦዘኔው በሚዝናኑባቸው ቦታዎች በመሄድ ቁማር በመጫወትና መጠጥ በመጠጣት ጊዜያቸውን ማሳለፍ ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳም በወቅቱ እንደጦር ይፈሩ የነበሩት የደርግ ባለስልጣኖችና ካድሬዎቻቸው «እሱኮ ተራማጅ ሆኖአል ጠጪም ብኩንም ሆኗል» በማለት ችላ አሏቸው፡፡

ይህ ዘዴያቸው ግን መዝለቅ የቻለው እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ነበር። በ1971 ዓ.ም. ከውርስ ከተረፈው ተካ ሆቴል ሰራተኞች ጋር በተፈጠረው የአሰሪና ሰራተኛ ውዝግብ የተነሳ ቀኛዝማች ችላ ብለዋቸው በነበሩት ባለስልጣናት ትኩረት ውስጥ ገቡ። ሠራተኞቻቸው ባቀረቡባቸው የተለያዩ የሃሰት ክሶች የተነሳ በቀጥታ ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። በወቅቱ የጅማ ክፍለ ሀገር የደርግ ተጠሪ የነበሩት ተሰማ በላይ "እስካሁን ድረስ ይህን የመሰለ አደገኛና በዝባዥ አድሃሪ ለእስርና ለቅጣት አለመብቃት አብዮታችን ከፈጸማቸው ስህተቶች አንዱ ነው። ተገቢው ምርመራ ተካሂዶበት የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ የአብዮቱን ደህንነትና የወዛደሩን መብት ማስከበር አለብን" በማለት ለበታቾቻቸው ትዕዛዝ አስተላለፉ።

ተሰማ በላይ ተካን የአብዮቱ አደገኛ ጠላት አድርጎ በማቅረብ የሞት ፍርድ እንዲፈፀምባቸው ለማድረግ የሃሰት ክሶችን አቀረቡ። ከቀረቡት ውንጀላዎች ውስጥ የራስ መስፍን ስለሺ ቤት ሲፈተሽ ምንም ዓይነት ገንዘብ ሳይገኝ በቀኛ ዝማች ቤት ውስጥ ግን ስምንት ሚሊዮን ብር ተደብቆ እንደተገኘ በማስመሰል ክስ መሰረቱ። ከዚህ በተጨማሪ አብዮቱን በትጥቅ ለመፋለም ቀኛዝማች ባላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ሶስት የጦር ሜዳ መሳሪያ በድብቅ አስቀምጠው እንደነበረና በፍተሻ እንደተገኘባቸው በማስመሰል ክስ መሠረቱ። "በአጠቃላይ የመደብ ጀርባው ሲታይ የወዛደሩን ላብና ጉልበት በመበዝበዝ ከፍተኛ ንብረት ያፈራ የአብዮቱ ቀንደኛ ጠላት ከመሆኑም በተጨማሪ አድሃርያን ያላቸውን ከመጠን ያለፈ ሃብትና ንብረት በአዋጁ መሰረት እንዲያስረክቡ ግዴታ እንዳለባቸው እያወቀ ከመጠን ያለፈ ሃብት በቤቱ ደብቋል፤ አብዮቱን በጦር መሣሪያ በመውጋት በብዙ ጓዶች መስዋእትነት የተገኘውን አብዮት ለመቀልበስ የተነሳ በዝባዥ ቡርዣዋ ስለሆነ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድበት አሳስባለሁ" በማለት ጓዶቻቸውን አሳመኑ።

ቀኛዝማች ተካ ግን ከሞት የታደጋቸውን ምስክርነትና ድጋፍ ያገኙት በምንም ዓይነት መልኩ ካልገመቱትና ካልጠበቁት ቁንጮ ባለስልጣን ነበር። ቀኛዝማችን ከሞት የታደጉት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ናቸው። ኮሎኔል መንግስቱ በቀጥታ ተሰማ በላይን በስልክ በማግኘት «ምንም ዓይነት እድፍ ያልተቀላቀለበት ኢትዮጵያዊ» ስለሆነ አደጋ ብታደርስበት ውርድ ከራሴ ነው በማለት ተግሳጽ የታከለበት ትዕዛዝ ስላስተላለፉ ነው ከእስር የተፈቱት። ቀኛ ዝማች ከኮሎኔል መንግስቱ ጋር ስለነበራቸው ትውውቅ ሲናገሩ «የኮሎኔሉ አጎት የሆኑት አስራት ወልዴ በተካ ጋባዥነት መኖሪያ ቤታቸው እራት ከሚጋበዙ ጥቂት ሰዎች አንዱ ነበሩ። የአስራት ወልዴ ወንድም ልጅ የሆኑት ወጣት መኮንኑ መንግስቱ ኃይለ ማርያምም ወደ ሰባት ጊዜ አጎታቸውን ተከትለው እየመጡ ተካ ቤት እራት ተጋብዘው ነበር።» መንግስቱ (ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም) የጅማ ሰው እንደመሆናቸው ስለቀኛዝማች ተካ ማንኛውም የከተማውና ያካባቢው ሰው ከሚያውቀው በተሻለ ሁኔታ እንዲያውቋቸው ያስቻላቸው በእራት ግብዣዎቹ ጊዜያት ከቀኛዝማች ጋር በአካል በመገናኘት እራት እየበሉ በእርጋታና በመዝናናት ባደረጓቸው ጭውውቶች የተነሳ ነው።

ቀኛዝማች ከእስር ተለቀው የኢህአዴግ መንግስት ደርግን ከስልጣን እስካስወገደበት ድረስ በነበሩት ዓመታት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያለ ስራ

ያሳልፉት የነበረው አዲስ አበባ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ነበር፡፡ በደረሰባቸው ከፍተኛ የንብረትና የሃብት ውርስና ባስከተለባቸው ከፍተኛ የህሊና ጠባሳና እስር ከምንም ነገር በላይ ከሚወዱት ስራ ፈጠራ ከመለያየታቸው የተነሳ አስራ ሰባቱን የአብዮት ዘመን  ከዓለም ጋር እንደተጣላ ሰው ከብዙ ነገሮች በመገለል በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንደ ቁም እስረኛ ሆነው አሳልፈውታል፡፡

ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ግን እንደ አዲስ ሀ በማለት በአዲስ ጉልበትና ከፍተኛ ፍላጎት የንግዱንና የስራ ፈጠራውን ዓለም ተቀላቀሉ፡፡ በፊት ወደለመዱትና ስኬታማ ወደሆኑበት የመጠጥ ማከፋፈል የንግድ ዘርፍ ፊታቸውን በመመለስ የበደሌ ቢራ አከፋፋይ ሆኑ፡፡ ሆኖም የበደሌ ፋብሪካ ሀላፊዎች ፈፀሙብኝ በሚሉት በደል የተነሳ በደረሰባቸው ኪሳራ ስራውን ተውት፡፡ በመቀጠል የቻይና ስሪት የሆነው የጂፋንግ መኪናዎች አስመጪ ሆኑ፡፡ ከቻይናዎቹ ጋር የተጀመረው ንግድም ስኬታማ ሳይሆን ቀረ፡፡ ቀኛዝማች ስለሁኔታው ሲናገሩ "በደሌዎች በደል ፈፅመውብኝ ከሰርኩ፡፡ ከቻይናዎች ጋር መስራት ደግሞ አዳጋች ነው፡፡ በመጨረሻ ሁለቱም በክርናቸው ስለደቆሱኝ በኪሳራ ንግዱን ዘጋሁ" ይላሉ፡፡

ሆኖም እንደሁሌው ወድቆ መነሳቱን ስለሚያውቁበት በአሁኑ ወቅት ስኬታማና ትርፋማ በሆነ ንግድ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ ጅማ ከተማ ውስጥ በቀላጤ ተወርሶ የነበረውን ደጊቱ ሆቴልን የኢህአዴግ መንግስት ሲመልስላቸው፣ ሆቴሉን እንደ አዲስ በማደራጀት፣ በማደስና አዳዲስ አገልግሎቶች እንዲሰጥ በማድረግ በከተማው ውስጥ ካሉት ትርፋማና ዘመናዊ ሆቴሎች ተርታ ለመሰለፍ አብቅተውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በደርግ መንግስት ያልተወረሰው ተካ ሆቴልም ስኬታማ ነው፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ ከ PVC የሚሰራ፣ ማለትም እንጨት መሰል የሆነ ለኮርኒስነትና፣ ክፍሎችን ለመከፋፈል የሚያገለግል ቁሳቁስ የሚያመርት ፋብሪካ በማቋቋም በኢንዱስትሪው የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተዋል፡፡ ቀኛዝማች አሁንም በዕድሜ ብዛት የጤና መታወክ ገጥሟቸው በሐኪም ትዕዛዝ እረፍት እንዲያደርጉ ቢነገራቸውም የሃይማኖትን ያህል ከሚያመልኩት ስራ ላለመነጠል ሲሉ የሐኪሙን ትዕዛዝ ችላ በማለት ቀኑን ሙሉ ፋብሪካቸው ውስጥ ደፋ ቀና ሲሉ ይውላሉ፡፡ ቀኛዝማች ሐኪም የነገራቸውን እንዲፈፅሙ ቢነገራቸው የሚሰጡት አጭር መልስ "እጄን ሳልንተራስ ከስራ የሚለየኝ የለም" የሚል ነው፡፡

# ክፍል ፫
# የተወረሱ ተግዳሮቶችን መቋቋም

# ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)

*ሺመልስ አዱኛ*

## *መግቢያ*

*ይህ ጽሁፍ የሚያተኩረው፣ በተለይ በ1966 ዓ.ም. በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን በተመሠረተ ጊዜ፣ አፍጥጦ የነበረውን የሕዝብ እልቂት ለመቋቋምና ከዛም በኋላ በተከታታይ የተከሰቱትን ረሀቦች ለማስቆም፣ የተደረጉ ጥረቶች ላይ ነው፡፡*

*ያም ሆኖ ግን ዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ከተቋቋመ ማግስት ጀምሮ በድርቅ ምክንያት የሚከሰተውን ችግር በዘላቂነት ለማስቆም ምን መደረግ አለበት፣ እንደገና ድርቅ ከተከሰተስ እንዴት መቋቋም አለብን፣ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ ሰፊ ጥናት አስጠንተናል፡፡ ጥናቱንም ለመተግበር ከዓለም ባንክ የዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት አስር ሚሊዮን ዶላር በብድር መልክ አግኝተን ነበር፡፡*

ስለዚህ የጽሁፌ የመጀመሪያው ክፍል የሚያተኩረው፣ የረሃብ ችግር አስገድዶት ቤት ንብረቱን ጥሎ ነፍሱን ለማዳን ዕርዳታ ፍለጋ የተሰደደውንና በየመጠለያ ጣቢያ የነበረውን ህዝብ፣ ነፍሱን አድኖ ተመልሶ እንዲቋቋም የተደረገው ጥረት ላይ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለረሀቡ ችግር የዘለቄታ መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ ይሆናል፡፡

## የድርቁ ችግር መከሠት (1965 ዓ.ም.)

*በ1965 ዓ.ም. በወሎና በትግራይ የተከሰተው ድርቅና ያስከተለው የሕዝብ እልቂት የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ከዳር እስከዳር ያነቃነቀና መዘዙም የአገሪቷን የመንግሥት አስተዳደር ያናጋ፣ ከፍተኛ የሕዝብ አመጽ ያስነሳና ሥርነቀል ለውጥ ያስከተለ ነበር፡፡*

በአገራችን ታሪክ የረሃብ እልቂት ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘግቦ የሚገኘው በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ሲሆን ይህም በመጽሐፈ ስንክሳር ውስጥ ነው፡፡ የድርቅ ቸነፈር ተደጋግሞ ሲደርስም ሕዝቦች በሚፈጽሙት ሀጢአትና በደል የተነሳ የሚከሰት የእግዚአብሔር ቁጣ ነበር ተብሎ በሰፊው ሲታመንበት ቆይቷል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚከተለው ረሃብ በወረርሽኝ በሽታ የታጀበ ስለነበረ ከፍተኛ ዕልቂት ያስከትል ነበር፡፡ በአፄ ምኒልክ መንግሥት የደረሰው ታላቁ ረሀብ (1880-1883) ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡

በድርቅ ምክንያት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከፍተኛ የከብት እልቂትም ይከተል ስለነበር በተለይ በአርብቶ አደሩ ሕዝብ ላይ በቶሎ የማይቀረፍ ከፍተኛ የችግር ጠባሳ ይተው ነበር። በከብት እልቂቱ ምክንያት አርሶ አደሩ ማረሻ በሬውን ሲያጣ፣ አርብቶ አደሩ ደግሞ ከብቱን ሲያጣ፣ የሁለቱም የኑሮው ዋልታ ስለሚናጋ ለዓመታት የሰው እጅ ለማየት ይገደዱ ነበር።

በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የአምበጣ መንጋና የተምች ወረርሽኝ ይመጣና የተዘራውን ሰብል እስከ ስሩ ስለሚላጨው፣ ዛፍና ቁጥቋጦውንም መለመላውን ስለሚያስቀረው ከባድ የረሃብ ቸነፈርና የከብት እልቂት ይከተል ነበር። በ1965 ዓመተ ምህረትና በተከተሉት ዓመታትም ከባድ የአንበጣ፣ የተምችና የፌንጣ ወረርሽኝ በስፋት ተከስቷል። ምንም እንኳን የምሥራቅ አፍሪቃ የአንበጣ መከላከያ ድርጅት ቢኖርም እንደልቡ ተዘዋውሮ መድኃኒቱን ለመርጨት፣ በአንድ በኩል የአምበጣ መፈልፈያ በሆኑት አካባቢዎች (ማለትም በምስራቅ በኦጋዴን፣ በሰሜን በኤርትራ) ይካሄዱ የነበሩት የእርስ በርስ ጦርነቶች እንቅፋት ሆነውበት ነበር፤ በሌላ በኩል አይሮፕላኖቹን ለመጠገንና ከአየር የሚረጨውን ፀረ አንበጣና ተምች መድኃኒት ለመግዛት የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን ስላልቻለ ድርጅቱ የታለመለትን ተግባር መፈጸም አልቻለም። አባል አገሮችም የመዋጮ ድርሻቸውን ስለማይከፍሉ ችግሩን አባብሶት ነበር።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነበር ተማሪው ለአያሌ አመታት «ደሃው ይናገራል» የሚለውንና የመሳሰሉትን ግጥሞች በመፃፍ (እና) የሕዝብን ችግር በመግለጽ ለለውጥና ለልማት ሲታገል፣ መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክርና ልዩ ልዩ የዲሞክራሲና የመብት ጥያቄዎችን በሰላማዊ ሰልፍ ሲገልጽ፣ በዩኒቨርሲቲ ሲያደርግ የነበረው የትምህርት ማቆም አድማና ሲከፍል የነበረው መስዋዕትነት እውን ሊሆን የተቃረበው። ያን ጊዜ ነበር የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብቅ ብሎ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" እያለ የለውጥ አጋፋሪ ሆኖ ግምባር ቀደም ሚና ለመጫወት የተነሳው።

በዚህ ጊዜ ነበር ጆናታን ድምብልቢ የሚባለው ጋዜጠኛ የተደበቀው ረሃብ (*"The Hidden Hunger"*) በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ፊልም በቴምስ ቴሌቭዥን ላይ በማቅረብ ይፋ ያደረገው። በዚህ ፊልሙ[1] አሰቃቂውን የወሎን የረሃብ ዕልቂት ከማሳየቱም በላይ፣ ፊልሙን ሲጀምር «በምዕራብ አፍሪቃ ከብቶች ሲያልቁ በኢትዮጵያ ግን ሰዎች እያለቁ ነው።» በማለት የዓለምን ሕዝብ በየቤቱ ገብቶ ልቡን ሰብሮታል።

---

[1] አዲስ የተቋቋመው የጦር ሃይሎች፣ የብሄራዊ ጦርና የፖሊስ ሰራዊት አስተባባሪ ደርግ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም. ምሽት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አሳይቶት በማግስቱ ለማድረግ ላቀደው አፄ ኃይለሥላሴን ከዙፋን የማውረድ እርምጃ የህዝቡን ስነልቦና አዘጋጅቶበታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ይህ ፊልም ትልቅ የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

**የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን (ዕማማኮ) መመስረት**

የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድ ካቢኔ ሥራ ለቆ ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ጠቅላይ ምኒስትር ሆነው ሲሾሙ ከተደረገው ሹመት መሐል የደጃዝማች ከበደ ተሰማ የግቢ ምኒስትርነትና የኔ የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነርነት ከመጀመሪያዎቹ መሐል ነበር። ይህም በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ነበር።[2]

እኔም በሃላፊነት እንድመራው የተቋቋመው የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኰሚሽን የተወለደው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባለች ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። በትዕዛዝ ቁጥር 93/1966 ነበር ኮሚሽኑ በሕግ የተቋቋመው። ሥራውም ሲጀመር ቀደም ሲል በእህል እጥረት ኰሚቴ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያንና ከዓለም የምግብ ኘሮግራም አለን ጆንስ፣ ከአትላንታ የበሽታ ቁጥጥር (CDC) አንድ ሐኪም፣ከዩኒሴፍ አንድ ስዊድናዊት ተባባሪ ባለሙያ በድምሩ ሰባት ሰዎች ብቻ ነበርን።[3] ቀደም ሲል መጥተው በወሎ ውስጥ የሚሠሩ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶች፣ ከየመሥሪያ ቤቱ የተውጣጡ ሠራተኞችና የክፍለ ሃገሩ እንደራሴና የአውራጃ አስተዳዳሪዎች በየወረዳውና መንገድ ዳር ባሉ ከተሞች ውስጥ መጠለያ ሰርተው እርዳታ በመስጠት ላይ ነበሩ። እነሱንም ማስተባበር ነበረብን።

በ1966 እና በ1967 ዓ.ም. ድርቁ በተከሰተበት ወቅት በተለይ በወሎ፣ በትግራይና በሰሜን ሸዋ ህዝቡ እየተሰደደ መንገድ ዳር ሲወጣ፣ የመጀመሪያው ጥረት የተደረገው በአስቸኳይ ህይወት አድን የሆነ ዕርዳታ መስጠት ነበር። እ.ኤ.አ. በኤፕሪል 13/1973 እህል ወደ ውጭ ሄዶ እንዳይሸጥ ታገደ። ለጅቡቲ ግን በፈቃድ ይላክ ነበር። በዚያን ወቅት በወሎ መጠለያ የነበረው ህዝብ ብዛት 280,000 እንደነበረ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት የተላከው ሪፖርት ሲያመለክት መንግስት ለዕርዳታ ሰጪዎች ያቀረበው የእህል ጥያቄ 60,000 ቶን ሲሆን ይህም የሚበቃው ለ200,000 ሰዎች ብቻ ነበር። በዚህ ጊዜ በወሎ 100,000 ሰዎች እንደሞቱ በወቅቱ የነበሩ መያዶች የሰጧቸው ሪፖርቶች ያመለክታሉ።

ሥራችንን ስንጀምር ያተኮርነው ነፍስ አድን ተልእኮ ላይ ስለነበር ሌትና ቀን መረባረብ ነበረብን። ከተለያዩ የዓለም ህዝቦች፣ ከመንግስታትና ከዓለም አቀፍ መያዶች ሰፊ እርዳታዎች አግኝተናል። እነዚህን ሁሉ ሀይሎች በማስተባበር ባደረግነው ጥረት በጀመርን በጥቂት ወራት ውስጥ የሰውን ማለቅ ለማስቆም ችለናል። በ1967 ዓ.ም. መሀከል ላይ ድርቁ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ውሎ ነበር። ይሁንና ዓመቱ ገና ሳያልቅ ድርቁ በሌሎች አካባቢዎች እንደገና ስለፈነዳ

[2] ሹመቱ የካቲት 25 ቀን 1966 ዓ.ም. ታውጆዋል፤ *አዲስ ዘመን* (የካቲት 26 ቀን 1996) ገጽ 1።
[3] «የእህል እጥረት ኮሚቴ» ታሪክ በሚከተለው መጽሀፍ ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል፦ ኃይለማርያም ሰይፉ ገብረ ሥላሴ፣ *የጥድፊያ ዘመናት - ረሃብና ቸነፈር፦ የታሪክ ማስታወሻ* (አዲስ አበባ፣ 2005)፣ ገጽ 40-59።

ችግራችንን አወሳሰበብን፡፡

ዕማማኮ እንደተቋቋመ 2,500,000 ብር የሚሆን ዕርዳታ ጠይቋል፡፡ በ1996 ዓ.ም መረጃ በሚገባ መሰብሰብ አስቸጋሪ ስለነበረ የደረስንበት ግምት የተራበው ህዝብ 400,000 ይሆናል የሚል ነበር፡፡ በ1967 ዓ.ም. ድርቁ በ11 ጠቅላይ ግዛቶች ተስፋፍቶ በነበረበት ወቅት አስተማማኝ መረጃ ሰብስበን የአደጋውን ስፋት እንደሚከተለው ገምተናል፡-

ሰንጠረዥ 1፡ በ1967 ለድርቅ የተጋለጠ ህዝብ ግምት

| ክፍለ ሀገር | የህዝብ ብዛት (በግምት) | ዕርዳታ ፈላጊ ህዝብ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ኤርትራ | 1,779,400 | 1,002,000 | 56.3% |
| ትግራይ | 1,993,600 | 963,000 | 48.5% |
| ወሎ | 2,456,400 | 956,000 | 38.7% |
| ጎንደር | 1,914,200 | 90,000 | 4.7% |
| ሸዋ | 4,584,800 | 70,000 | 1.5% |
| ሐረርጌ | 2,888,600 | 1,001,500 | 34.7% |
| ባሌ | 836,400 | 515,000 | 70.2% |
| ሲዳሞ | 2,560,600 | 270,000 | 10.5% |
| ጋሞ ጎፋ | 939,000 | 227,500 | 24.1% |
| ድምር | 1,995,300 | 5,161,280 | 25.9% |

እነዚህ አሀዞች በሚገባ እንደሚያሳዩት፣ የነፍስ አድን ስራው በቀላሉ የሚቆም አለመሆኑን ነበር፡፡ ስለዚህ ዕርዳታ የማደሉ ዘመቻ በስፋት ቀጠለ፡፡ አንዱን የድርቅ ዘመን ስንቋቋም ሌላ ድርቅና ረሀብ ሌላ ቦታ እየተከሰተ ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግረን ኖሯል፡፡ ይሁንና በዕርዳታ ሥራ ብቻ ተጠምደን የረጅም ጊዜ ራዕይ ከመንደፍ አልታቀብንም፡፡

እኔ በተሾምኩበት ወቅትና ከዚያም በኋላ አገራችን በታላቅ የአብዮት ነውጥ ውስጥ ስለነበረች መንግስት በብዙ አቅጣጫ ተወጥሮ ነበር፡፡ ይሁንና የመንግስት ከፍተኛ መሪዎች ለረሀቡ ትልቅ ትኩረት ስለሰጡት እኔ የምሰራውን ሥራ ይከታተሉና ያነቃቁኝ ነበር፡፡ በተሾምኩበት ዕለት አፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ ሰጥተው ባያነጋግሩኝም፣ ከጥቂት ቀን በኋላ አስጠርተውኝ፣ በስራው እንድገፋበት ከፍተኛ የማነቃቃት ንግግር

አድርገውልኝ ነበር። ከዚያ በኋላም በየጊዜው ማታ ማታ እቤቴ እየደወሉ እንቅስቃሴያችን እምን እንደደረሰና ምን ችግር እንዳጋጠመን ይጠይቁኝ ነበር። ምንም እንኳ ጊዜያቸው እጅግ የተጣበበ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸውም በሥራ ሰዓት በተቻለ መጠን በፈለግሁበት ሰዓት ላገኛቸው እንድችል ለረዳታቸው መመሪያ ሰጥተው ነበር። ማታ ማታም አስቸኳይ ጉዳይ ኖሮኝ ከፈለግሁዋቸው አልጋቸው አጠገብ ያለውን ቴሌፎን ቁጥር ሰጥተውኝ፣ በማንኛውም ሰዓት እንድደውል ፈቅደውልኝ ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች ለሥራዬ ቅልጥፍና ሰጥተውታል።

ደርግ ስልጣን ላይ በወጣበት ጊዜም ሌተና ጀነራል አማን አንዶምም ሆኑ ብራጋድየር ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ ለስራ ከፈለግኋቸው በረዳታቸው በሻምበል መለሰ ማሩ በኩል እያገኘኋቸው ውሳኔ በማግኘት ስሰራ ቆይቻለሁ። ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምም ስለስራዬ በመረዳትና በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጡኝ ነበር።

ከከፍተኛ መሪዎቻችንም ሆነ ከህዝቡ፣ ከዓለም አቀፍ ተቋማትም ሆነ ከመያዶች፣ ትልቅ ድጋፍ ቢኖረንም ችግሩ እጅግ ሰፊ ስለነበረ በቀላሉ የሚቀረፍ ሆኖ አላገኘ ነውም። እንዲያውም የመደጋገምና ባልተጠበቁ አካባቢዎች የመፈንዳት ባህርይም ያሳይ ነበር። ስለዚህ ችግሩን በቋሚነት ለመፍታት ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ ገና ከመጀመሪያው አሳሳቢ ሆኖ አግኝተነው ነበር።

**የኮሚሽኑ የትኩረት አቅጣጫ**

የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ሲቋቋም ቅድሚያ ተግባሩ አድርጎ የተነሳው ወገኖቻችንን ከሞት ማዳን ቢሆንም፣ በጊዜው በድርቅ መጎዳታቸው በይፋ ይነገር በነበረው በወሎና በትግራይ ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ የመልሶ ማቋቋም ሥራ እንዲከናወን፣ ከዓለም ባንክ ጋር በመነጋገር በተገኘ ድጋፍ፣ ወሎንና ትግራይን ከድርቅ መልሶ ለማቋቋም እንዲያስችል በጥቅምት 1967 - «*Drought Rehabilitation in Wollo and Tigray - Report of a Survey and Project Preparation Mission October - November 1974*» የተባለውን ጥናት በጥር 1967 እንዲቀርብ አድርጓል።

በዚህ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ትኩረቱ የእለት ዕርዳታ መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ ለረሃቡ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን በማወቅና ሁኔታውን ያባባሱ ምክንያቶችን በመመርመር የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ ነበረ። በዚህም መሠረት የሕዝብ እልቂትን ለማቆም በድርቁ ምክንያት ቀዬውን ለቆ በየመጠለያው ፈሶ የነበረው ሕዝብ ወደ ቤቱ እንዲመለስ፣ አመቺ የሆነውን አካባቢ ማረስና መዝራት እንዲችልና በልማት እንዲሠማራ፣ በሬ፣ ዘርና ማብሰያ ማቅረብና ሰብሉ እስኪደርስለት ድረስ ደግሞ የሚበላው እህል መስጠት፣ ራሱን እንዲችል የሚያግዙ ፕሮጀክቶች መንደፍና የረጅም ጊዜ

ፕሮጀክቶችን አሰባስቦ በባለቤት መሥሪያ ቤቶቻቸው በኩል በተግባር ላይ እንዲውሉ ብድርና እርዳታ እንዲገኝላቸው ማገዝ ነበር፡፡

***በሪፖርቱ መሰረት የረሀቡ ዋና ዋና ምክንያቶች፡-***

1. ለዘመናት ታይቶ የማይታወቅ ሀይለኛ ድርቅ መከሰት፣
2. ግዴለሽ የመሬት አጠቃቀም ያስከተለው የመሬት መበላትና መሸርሸር፣ አፈሩ ለእርሻ ምርታማ አለመሆን፣
3. የሕዝብ ቁጥር ማደግና ለየቤተሰቡ የሚደርሰው የመሬት መጠን እጅግ ማነሱና ከዚህም አነስተኛ ይዞታ የሚገኘው ሰብል አናሳ መሆኑ፣ የከብትም ቁጥር መጨመሩና የአካባቢው ግጦሽ መመናመኑ የአርብቶ አደሩን ኑሮ አስቸጋሪ ማድረጉ፣
4. የማያስተማምንና ኢፍትሃዊ የመሬት ይዞታ ሥርአት በምርታማነት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ናቸው፡፡

***ችግሩን ያባባሱት ታሳቢዎች፡-***

- የመገናኛ አለመመቻቸት፡- 1ኛ/ ምንም አይነት መረጃ የረሃቡ አደጋ ከደረሰበት አካባቢ ወደ ክፍለ ሃገሩ ዋና ከተማ አለመድረስ፣ 2ኛ/ ችግሩ ከታወቀ በኋላም መንገድ ባለመኖሩ ዕርዳታውን ለማድረስ ማስቸገሩ እና ከፍተኛ ዋጋ መጠየቁ፣
- የምግብ ዋስትና ክምችት በአገር ውስጥ አለመኖር፣ እህል ከውጪ እስኪመጣ ለመጠበቅ መገደድና በዚህም ምክንያት ረሃብ፣ በሽታና ሞት መከተሉ፣
- ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ ወስዶ ዕርዳታ በመጠየቅ ለተቸገረው ወገን አለመድረስ፣
- አውድ አመትና አመትባል በመብዛቱ ዘወትር ስለማይሰራ ባሉት የሥራ ቀናት ቶሎ ቶሎ ለማረስ ተጨማሪ በሬዎች ማስፈለጋቸው፣
- ሌሎችም ሁኔታውን ያባባሱ ምክንያቶች ከአሠራር ዘገምተኝነት ጀምሮ በርካታ ስለሆኑ በአስር አመት ውስጥ ሊወገዱ እንደማይችሉ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ችግሩ ከሰላሳ ዓመት በኋላ ዛሬም እንዳፈጠጠ ነው፡፡

***የመፍትሄ እርምጃዎች***

የመፍትሄ ሀሳቦቹ ዘላቂነት እንዲኖራቸው፣ ወቅታዊ መፍትሄ የሚሰጡ ፕሮጀክቶችን አቅዶ መፈጸም ብቻ ሳይሆን፣ የችግሩ ስር መሠረት በልማት ኋላ ቀርነት እንደመሆኑ መጠን አጠቃላይ አገር አቀፍ ፖሊሲ ተነድፎ በመገናኛ፣ በውሃ

ልማትና በመሬት አጠቀቀም አመርቂ እርምጃ በመውሰድ ፍትሃዊ የመሬት ይዞታ ለውጥ በማድረግ (እስከዛሬም ያልተፈታና አወዛጋቢ ጉዳይ) እና መልካም አስተዳደር በማቆም ችግሩን መቅረፍ ያስፈልጋል፤ የሚል ድምዳሜ ላይ ሪፖርቱ ደርሷል። ጥናቱም ችግሮቹን በስፋት ቢያቀርብም እዚህ ጽሁፍ ላይ አሳጥረን እናቀርባቸዋለን፡-

1. የድርቅ ችግር በሰላሳ፣ በአሥርና በአምስት አመት የሚያደርገውን መከሰት፣ ከአሲድ ዝናብ፣ ከመኪናዎች የሚወጣ ጭስ፣ ከምንጨፈጭፈው ደንና ከኦዞን ሽፋን መሸንቆር ጋር ተያይዞ ከሚመጣው በአሁኑ ጊዜ የጥናትና ምርምር ትኩረት የሆነው የዓለም እየሞቀች መሄድ (global warming) እስካለ ድረስ ልናቆመው አንችልም። ቢሆንም የድርቅን መከሰት መተንበይ እንድንችል ዘመናዊ የአየር ሁኔታ ትንበያ አቅም ካላቸው አገሮችና ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ልንዘጋጅ ይገባናል። በየአሥርና አምስት ዓመት ይደርስ የነበረው ችግር አሁን በእየሁለት አመቱና አንዳንድ አካባቢም በየአመቱ እንደሚደርስና በቀድሞው መንግሥት እስከ ስምንት ሚሊዮን የነበረው የተረጂ ቁጥር በ1995 እና 1996 እስከ 17 ሚሊዮን ሊደርስ እንደሚችል በአገሪቷ ከፍተኛ ባለሥልጣንና በቢ.ቢ.ሲ.ና በሲ.ኤን.ኤን ሲገለጥ ተደምጧል።

2. የመሬት አጠቃቀምን ችግር ለመፍታትም የተለያዩ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፤ በአፈር ጥበቃ፣ በደን ተከላ፣ በተሻለ አስተራረስ ዘዴ ምርታማነትን በማሳደግ፣ በተሻለ ዘርና በማዳበሪያ በመጠቀም ምርትን እስከ አምስት እጅ ለማሳደግ ስለሚቻል እነዚህን ዘዴዎች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ከተወሰነ መለኪያ በላይ ተዳፋትነት ያላቸውን አካባቢዎች ለዛፍ እንጂ ለእርሻ ሰብል አለማዋል፤ ለም አካባቢዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የተበላ አካባቢ ላይ ገንዘብና ጉልበት ከማፍሰስ ተቆጥቦ የሰብል ምርትን በማሳደግ ትርፍ አምራች አካባቢዎችን የምግብ ዋስትና ዋልታ ማድረግ ያስፈልጋል።

3. ሀ/ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ በግልጽ የሚታይ ሲሆን በ1946 ዓ.ም. 17 ሚሊዮን የነበረው በ1970 ዓ.ም ወደ 22 ሚሊዮን ከፍ ብሎ በ1997 ዓ.ም. 74 ሚሊዮን ደርሷል። ለዚህም መፍትሄው የቤተሰብ ምጣኔ ማድረግና የተጠናና አዋጪነቱ የተረጋገጠ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሠፈራ ፕሮግራም ማካሔድ ነው። ሠፈራ ውድ ስለሆነ (ወጪው በ1966 ዓ.ም. ግምት እንኳን በቤተሰብ አንድ ሺህ የአሜሪካን ብር ስለሆነ) በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። የሕዝብ ማስፈሩ ፕሮግራም ለተወሰነ ጊዜ ሊያገለግል ይችል እንደሆነ ነው እንጂ የሕዝብ ቁጥር ከ2.9% እስከ 3% እያደገ በሚሄድበት አገር ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። የአገሪቷን የቆዳ ስፋት በማየት በቂና አስተማማኝ የዝናብ መጠን በሌለበት ቦታ ሕዝብን

ማስፈር፣ የአካባቢውን ደንና ቁጥቋጦ አበላሽቶ አፈሩንም በአጭር ጊዜ ከለምነት ወደ በረሃማነት ስለሚለውጥ፣ ሕዝቡን ለቀጣይ ችግርና ረሃብ መዳረግ ይሆናል፡፡

ለ/ ለዘለቄታው ከአገሪቷና ከቤተሰቡ የኢኮኖሚ አቅም ጋር የሚጣጣም የቤተሰብ መጠን መኖር እንዳለበት ሕዝብን ማስተማርና ለሚፈልጉትም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በበቂ መጠንና በአመቺ ሥፍራ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔን በአስተማማኝነት ለማቅረብ የገጠር ልማት ፕሮግራሞችንና የጤና አገልግሎት ፕሮግራምን አቅርቦት አንድ ጋር መንደፍ ያስፈልጋል፡፡

የሕዝብን ቁጥር የመቆጣጠር ጠቀሜታን ከትምህርት ቤት ጀምሮ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ የኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከሚሰጡት ትምህርት ጋር ስለገጠር ልማት ፕሮግራም፣ ስለ እርሻ፣ ስለ ጤና፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ እንዲያስተምሩ ተደርጎ የአገሪቷ መሬትና ኢኮኖሚ ሊሸከም የሚችለውን የሕዝብ ቁጥር ያህል ብቻ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ ያም ሆኖ የአገሪቷን አጠቃላይ ልማት በአፋጣኝ በመከወን የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የሀይል ማመንጫን ክፍል ማራመድና ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡ ቀላል ለማይባል ህዝብ ሥራ ሰጥቶ የሚገኘው «ኢንፎርማል ሴክተር» ታግዞ ወደ መለስተኛ ኢንዱስትሪ፣ መለስተኛው ደግሞ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚያድጉበትን መንገድ በሥልጠና፣ በፍትሃዊ አስተዳደር፣ በብድርና በቴክኒክ ድጋፍ ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡

**የመሬት ይዞታ መሻሻል**

ከመነሻው ባለቤትነትን የማያረጋግጥና ኢፍትሃዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ሥርአት መስተካከል አለበት፡፡ በተጨማሪ የተሻሉ የእርሻ ዘዴዎች እውቀትና አስፈላጊ የእርሻ ግብአቶች ለምርታማነት በጣም፣ እጅግ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ የሚቀርቡበት መንገድ መፈለግ አለበት፡፡ ለዚህ ነው የጭሰኛውም ሆነ ትልቁ የሀብታም ይዞታ እኩል ተጎሳቁለው ሲገኙ በሌላ በኩል ደግሞ ለምነታቸው የተጠበቀና የተሻሉት የእርሻ መሬቶች ከሕዝብ ብዛት የተነሳ በየጊዜው እየተሸነሸኑ ከተበጣጠሱ የባለቤትነት መረጋገጥ ብቻውን መፍትሄ የማይሆነው፡፡ የርስት አገር ስሪት ባላቸው አካባቢዎች እንኳን መሬት ከትውልድ ወደትውልድ ስለሚከፋፈል ገበሬው የሚያርሰው የበሬ ግምባር የምታህል መሬት ስለሆነ አመርቂ ምርት አይገኝም፡፡ ገበሬው ሞፈር ዘመት ሄዶ የማያርስ ከሆነ ተገቢውን የቅርብ እንክብካቤ ለሰብሉ ሰጥቶ ምርታማነቱ አጥጋቢ እንዲሆን ማድረግ አዳጋች ነው፡፡[4]

[4] አንድ ገበሬ ከሚኖርበት ቀበሌ (ጎጥ) ሞፈር ቀንበሩን ተሸክሞ ራቅ ወደአለ አካባቢ ሄዶ ሲያርስ ሞፈር ዘመት ይባላል፤ ስራውን ለመጨረስ አርሶ አደሩ እዚያ እማሳው ላይ መዋል ማደር ያስፈልገዋል፡፡

በወቅቱ የነበረው የመሬት ይዞታ፣ የርስት አገርም ሆነ የጭሰኛና የገባር መሬት ያለበት ስርአትም ቢሆን፣ ተለውጦ ፍትሃዊና አስተማማኝ የመሬት ባለቤትነት ያረጋገጠ ይዞታ ቢመቻችም ምርታማነቱ የሚረጋገጠው፣

1. ተገቢ የሆኑ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ምርታማነት ላይ ያተኰሩ የልማት ቅድመ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ብቻ ሲሆን ዋናው የአጭር ጊዜ ቅድመ ሁኔታ የአፈር ጥበቃ ሲኖር ነው፡፡
2. እያንዳንዱ ገበሬ ሊያገኘው የሚችል የሠለጠነና ቋሚ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ መድኃኒት እና ብድር አቅርቦት አስተማማኝ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

**የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት፡-** ነሐሴ 29 ቀን 66 የወጣው የሕግ ትዕዛዝ 93/66 የአደጋ መከላከልንና ዝግጁነትን ጉዳይ ሲደነግግ ሠፈራንም እንደ አንድ ተግባር ጨምሮታል፡፡ እንዲሁም የዕለት ደራሽንና መልሶ ማቋቋምንም በሚመለከት ደንግጓል፡፡

የ1966 ዓ.ም. ድርቅ ያስከተለው የረሃብ ዕልቂት ሲከሰት የተደራጀ የአደጋ መከላከልና መልሶ የማቋቋም ዝግጁነት አልነበረም፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰው አጥኚ ቡድን ባሳሰበው መሠረት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ትምበያ፣ መገናኛ መንገድ፣ ማጓጓዣያ (ትራንስፖርት)፣ እህል ማከማቻ መጋዘኖችና ለአደጋ ጊዜ የሚውል መጠባበቂያ የእህል ክምችት በቅድሚያ ሊዘጋጁ የሚገባቸው ነገሮች ነበሩ፡፡

### መገናኛ

በአገራችን በተለይ የገጠር መንገዶች ባለመስፋፋታቸው እርዳታ ማድረሱ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው አፍላ ረሃብ በወሎና በትግራይ ሲከሰት በወሎ የነበረው የገጠር መንገድ 1,000 ኪሎ ሜትር ብቻ ሲሆን በትግራይ ደግሞ 3,000 ኪሎ ሜትር ብቻ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ የእርዳታ እህል ለማዳረስ ትግራይ የተሻለ አመቺነት ነበረው፡፡ በአስቸኳይ እንዲደርስ ተብሎ በተነደፈው ፕሮጀክት መሰረት በሦስት አመት ውስጥ በትግራይ ተጨማሪ 400 ኪሎ ሜትር በወሎ ደግሞ 600 ኪ.ሜትር መንገድ ተሰርቷል፡፡ በመንገድ ችግር ምክንያት በምዕራብ ጀርመን አየር ኃይል እህል ከሰማይ ይጣልላቸው የነበሩት ካበ ሃራና አረባቲ ቦራ የተባሉ አካባቢዎች በጀርመን እርዳታ መንገድ ሲሰራላቸው የቆቦ ላሊበላ መንገድ በቴር ደዞም ኔዘርላንድስ ሲሰራ እርዳታ ለማቅረብ ምቹ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ ሠፊ አገር ስለሆነች፣ በየጠቅላይ ግዛቱ የሚደርሰውን ችግር ለማወቅና የሚያስፈልገውን የዕርዳታ አይነትና መጠን አውቆ ለወገን ለመድረስ መረጃውን ማስተላለፊያ ስልክም ሆነ ሬዲዮ ባለመኖሩ ከባድ ችግር ነበር፡፡ ስለዚህ የሬዲዮ መገናኛ ማቋቋሙ አንገብጋቢ ጉዳይ ነበር፡፡ የሬዲዮ መገናኛዎች ማቋቋሙ ሥራ

ተፋጥኖ በ1977 ዓ.ም. 58 ቋሚ እና 26 መኪና ላይ የሚጠመዱ የሬዲዮ መገናኛ ዎች ስለተተከሉ የእርዳታ ሥራውን ለማከናወን ጥሩ እገዛ አድርጓል። ከዚህም የተነሳ ዕማማኮ ከፌርፌር (ደቡብ) እስከ ቃሮራ (ኤርትራ) በሬዲዮ መገናኘት ይችል ነበር።

## የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች (ትራንስፖርት)

በመቶ ሺ የሚቆጠረውን የእህል ኩንታል ለማጓጓዝ ትራንስፖርት ትልቁ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ ነው። የእርዳታ እህሉን ከዋና መንገዶች ተገንጥለው ወደ ውስጥ በሚገቡ እና በጥሩ ሁኔታ ባልተሰሩ በተለምዶ «ፒስታ» በሚባሉ መንገዶች ላይ ወስዶ እርዳታ የሚያደርስ የተሽከርካሪ አቅም አልነበረም። በምፅዋ፣ በአሰብና በጅቡቲ ተከማችቶ የነበረው እህል ቶሎ ቶሎ ሊጓጓዝ ባለመቻሉ በወቅቱ የነበሩ ጋዜጠኞች ሰባቱ የዕማማኮ ሠራተኞች ላይ ከባድ ወቀሳ ይሰነዝሩ ነበር። በከተማ ፖስታ ለማደልና ወደ አንዳንድ ስብሰባዎች ለመሄድ እንኳ የኮሚሽነሩ የግል መኪና ብቻ ነበር ያለው። በዚህ ጊዜ የጦር ሠራዊቱ መኪኖች የእርዳታ እህል እንዲያደርሱ ቢመደቡም፣ በጎማና በመለዋወጫ ችግር ምክንያት አመርቂ እገዛ ለማድረግ ስላልቻሉ፣ የአሜሪካ መንግሥት በትልልቅ የጭነት አይሮፕላኖች የመኪና ጐማዎችንና የተወሰኑ መለዋወጫ እቃዎችን በአፋጣኝ እንዲልክ ስለተደረገ፣ የሠራዊቱን መኪኖች መጠቀም ተችሏል።

የእንግሊዝ የውጪ ኢኮኖሚ ትብብር ምኒስትር ለነበሩት ለጁዲት ሃርት (Judith Hairt) ችግሩን ሳስረዳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እያንዳንዳቸው 50 ኩንታል የሚጭኑ ሃምሳ ቤድፎርድ መኪኖች በአይሮፕላን ተጭነው እንዲደርሱን አደረጉልን።

እያደርም የምዕራብ ጀርመንና የኢጣሊያን መንግሥታትም እገዛ አድርገዋል። የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና የአለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) ከዕማማኮ ጋር በመሆን የትራንስፖርትና የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮጀክት ሰርተው ለዕርዳታ ትራንስፖርት ተቋምና (Relief Transport) በተለይም ለስደተኞችና በአገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች ዕርዳታ የሚያቀርብ ተቋም (Transport Organisation for Relief) ፈጠሩ። እነዚህ ተቋማት በ1984 ዓ.ም. ላይ 1,547 ባለተሳቢ ተሽከርካሪዎችና ሥራውን ለማካሄድና መኪናዎቹን ለማሽከርከር 1,598 ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞች ነበራቸው።

በትራንስፖርት በኩል ጥቂት አውሮፕላኖችም ድርሻቱ ነበረው። ይህን ለማቋቋም የረዱን የኢትዮጵያ አየር ሃይልን በማቋቋም ብዙ አስተዋጽኦ የነበራቸውና በመጨረሻ እኔን ለሥራ ይዘውኝ ሄደው በሶማሌ ወራሪዎች የተገደሉት ካርል ጉስታፍ ፎን ሮዘን ሲሆኑ እሳቸውም የንትንቮርግን ጋዜጣ ኅትምበርግ ፖስት

ባደረገላቸው ድጋፍ አንድ ዲሲ ስሪ እና ሦስት Sab MI 15 የሚባሉ አነስተኛ አይሮፕላኖች ለድርጅቱ አስገዝተዋል፡፡ ውለታቸው ለዘላለም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በአይሮፕላን ዕርዳታ በማድረስ ላይ እያሉ ከተሰውት መሐል የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባልደረባ መቶ አለቃ ኃይሌ እና Christianson የሚባል የስዊድን ተወላጅ ይገኙበታል፡፡ የካርል ጉስታፍ ፎን ሮዘን ልጅ Eric Von Rosen ም ከባድ አደጋ ደርሶበት ሊተርፍ ችሏል፡፡ እነዚህ ሦስቱም አደጋዎች የደረሱት በጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት ነው፡፡

## የመጋዘንና የእህል ማከማቻ ቤቶች

ረሀቡ እንደደረሰ፣ ችግር ያለበት አካባቢ ዕርዳታ ለማስቀመጥ የተዘጋጀ መጋዘን ካለመኖሩ የተነሳ እህል የሚቀመጠው፣ ትምህርት ቤት አካባቢ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አጠገብ፣ ጊዜያዊ ጥርጊያ ማረፊያ አጠገብ ሲሆን እዚያው ማረፊያው ዳር በኘላስቲክ እየተሸፈነ ነበር፡፡ እህሉን ዝናብ እንዳያበላሸው መሸፈኛ የሚሆን ፕላስቲክ ከውጪ መምጣት ነበረበት፡፡ በዚህ በኩል የምዕራብ ጀርመን መንግሥት፣ Stern magazen እና የአሜሪካ መንግሥት ትልቅ ዕርዳታ አድርገዋል[5]፡፡ በ1984 ዓ.ም. የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን 3,538,690 ኩንታል የሚይዙ 353 መጋዘኖችና 112 ሳይሎዎች ሲኖሩት በአገሪቷ ልዩ ልዩ ክፍል ተሰራጭተው ይገኙ ነበር፡፡ ከነዚህ ማህል ትልቁ በ13 ሚሊዮን ብር የተሰራውና 1,000,000 ኩንታል የሚይዘው ከናዝሬት ከተማ ወጣ ብሎ ወደ ሶደሬ መሄጃ መንገድ ዳር ያለው ነው፡፡

የወሎ ጠቅላይ ግዛት 1,163,450 ኩንታል የሚይዙ የተለያዩ መጋዘኖች ነበረው፡፡ እነዚህ መጋዘኖች በአሥራ ሁለቱም የወሎ አውራጃዎች ሲገኙ ከዕማማኮ መጋዘኖች 1/3ኛዎቹ መሆናቸው ነው፡፡ ይህ የመጋዘን ይዞታ ተደላድሎ የተከፋፈለ ሳይሆን 735,750 ኩንታል የመያዝ አቅም የሚገኘው ኮምቦልቻና ደሴ ላይ ብቻ ነው፡፡

## የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት

የመጠባበቂያ እህል ክምችት የሚደረገው፣ ለድርቅ ሊጋለጡ የሚችሉ መሆናቸው በጥናትና ከአሁን በፊት በታወቁ ገጠመኞች የተረጋገጡ አካባቢዎችን ለመታደግ ሲሆን ዓላማውም ችግሩ ሲከሰት የሰው እልቂት ከመድረሱ በፊት ምግብ ማቅረብ እንዲያስችል ነው፡፡ ስለዚህ ገና በ1966 ዓ.ም. ዕማማኮ ሲመሰረት ነበር ጥናት ተዘጋጅቶ ለዕርዳታ ሰጪዎች የቀረበው፡፡ ነገር ግን ከስምንት ዓመት በኋላ በ1975

---

[5] እሽተርን መጽሄት (Stern Magazen) ምእራብ ጀርመን ውስጥ የሚገኝ፣ ከዋና ዋናዎቹ አንዱ የሆነ፣ መጽሄት ነው፡፡

ዓ.ም. ነበር ለእህል ክምችት የሚውለውን 120,000 ኩንታል የዓለም የምግብ ድርጅት የሰጠው:: ይህም የእህል ክምችት እስከ 1,800,000 ኩንታል ደርሶ ነበር:: ለረሃብ ይጋለጣሉ ተብሎ የሚገመቱትን በአስፈላጊ ጊዜ ለአምስት ወር ስለሚመግብ በዚያ ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ እህል በግዢም ሆነ በእርዳታ ስለሚመጣ የሰውን ህይወት ከህልፈት ለመታደግ ይቻላል በሚል ነበር:: 120,000 ኩንታል ግን ይህን ለማድረግ የሚያስችል አልነበረም:: ሁለተኛው ከባድ የረሃብ አደጋ ከአሥር ዓመት በኂላ በ1977 ዓ.ም. ሲከሰት የነበረው መጠባበቂያ 180,000 ኩንታል ብቻ ነበር:: ነገር ግን ወሎ ውስጥ 1,166,450 ኩንታል የሚይዝ ማከማቻ አቅም ነበረ:: ተጣጥረን ራሳችንን ካልቻልን ምን እና እንዴት መደረግ አለበት የሚለውን ማወቅ ብቻ አይጠቅምም:: አምርተንም ሆነ ገዝተን የሚያስተማምን የምግብ ዋስትና እንዲኖር የሚያስችል አቅም መገንባት ያስፈልጋል::

**የአደጋ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ**

ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን የድርቅ አደጋ ለመተንበይና የአደጋውን መጠን ለመገመት የሚችል ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን አግባብነት ያላቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ስብሰባ በመጥራት ስለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት እንዲያደርጉ የቴክኒክ ግብረሃይል አቋቁሞ፣ የቴክኒክ ሁኔታውን መርምሮ፣ ለአደጋ የተጋለጡ አካባቢዎችን ሁኔታ ለመተንበይ የሚያስችል ዘዴ ፈጥሮ፣ ሁኔታውን የሚከታተልና የሰዎችን የኒውትሪሽን ሁኔታ የሚያጠና አካል የሚቋቋምበትን ዘዴ እንዲያቀርብ አደረገ:: የተቋቋመውም ግብረሃይል ይህ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተቋም በእማማኮ ውስጥ እንዲቋቋም ሃሣብ ስለአቀረበ ይህ አሁን ያለው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በ1970 ተቋቁሞ ሥራውን ጀመረ::

የዚህ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም ዓላማው በድርቅ ምክንያት የሚከሰተው ረሃብ፣ የከፋ አደጋ ከማድረሱ በፊት ለመከላከልና ከደረሰም ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል መረጃ መስጠት ነው:: በዚህም መረጃ መሠረት፣ በተደጋጋሚ የሚጠቁትን አካባቢዎች ለይቶ በማወቅ ዘላቂ መፍትሄ በማቀድ የረሃብ እልቂት እንዳይደርስ መከላከል እንዲቻል ማድረግ ነው:: በተጨማሪ ችግሩ ቢከሰት እንኳ ለችግሩ የተጋለጠውን ሕዝብ ብዛት ለይቶ በማወቅ የሚያስፈልገውን የዕርዳታ መጠንና አይነት አዘጋጅቶ በአፋጣኝ መድረስ መቻል ነው:: የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም የሚከተሉት ዝርዝር ሃላፊነቶች ተሰጥተውታል፡-

1. የምግብ እጥረት የሚከሰትበትን አካባቢ፣ የእጥረቱን መጠንና በእህል እጥረቱ ለአደጋ የሚጋለጠውን ሕዝበ ቁጥር መተንበይ፣
2. የእህል እጥረት ያለበትን አካባቢና ትርፍ የሚመረትበትን አካባቢ ማወቅ፣ እጥረቱ የሕዝቡ መሠረታዊ ምግብ በሆነው የእህል የጥራጥሬና የቅባት እህል ዋጋ ላይ የሚያስከትለውን ሁኔታ መገመት፣

3. የሚከተለውን አደጋ ለመቋቋምና ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ሃሣብ ማቅረብ፣
2. የእህል እጥረትን ለመከላከል የዝግጁነት ክምችት የሚደረግበትንና በአስፈላጊ ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል መረጃ ማቅረብ፣
3. በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ የሆኑ ተባባሪ ድርጅቶችና አካላት ሊያተኩሩበት የሚገባውን አካባቢ በማመላከት ድርቅን ለመከላከል የሚያስችሉ የልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ማገዝ፡፡

በእማማኮ አስተባባሪነት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አካል የሆኑት ስምንት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ነበሩ፡፡ እነዚህም፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር፣ የማዕከላዊ እስታስትቲክስ ባለሥልጣን፣ የብሄራዊ የሜትሪዎሎጂ አገልግሎት ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የኒውትሪሽን ኢንስቲትዩት ናቸው፡፡

የዕማማኮ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የፕላን አገልግሎት አራት ክፍሎች ሲኖሩት ከነዚህ ሁለቱ በቀጥታ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ እነዚህም

1. የእስታትስቲክስና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ክፍል ሲሆን የዚህም ክፍል ሥራ ስለ ሰብል ምርት፣ ስለ ኒውትሪሽንና ስለከብቶች ሁኔታና የሰብልና የከብቶችን ዋጋ ጥናት በማድረግ የምግብ ስርጭት ይዘትን መከታተል ነው፡፡
2. የአደጋ ቅድመ ዝግጁነትና አጠቃላይ መረጃ ቡድን ሲሆን ስራውም ለአደጋ የተጋለጡትን አካባቢዎች ዝርዝር ጥናት በማዘጋጀትና ግምገማ በማድረግ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባውን የዝግጁነት ዕቅድ ማዘጋጀት ነው፡፡

የዚህ ፕሮግራም ሲስተም ሥራ የምግብ ሰብሎች በገበያ መገኘታቸውን የመለኪያ መስፈርት እንዲሆኑ የተመረጡት አመላካቾች ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን መከታተል ሲሆን ለውጦቹም ምግብ አቅርቦት ላይ ያላቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታ ማወቅና መዘገብ ነው፡፡ እነዚህ አመላካች ጠቋሚዎች (ኢንዲኬተሮች) በአብዛኛው የአቅርቦትና የፍጆታ ፍላጎት ላይ የሚከሰተውን የምርት ይዘት፣ የዝናብና የውሃ አቅርቦትን፣ የግጦሽ ሥፍራዎችን የመኖ ይዘት፣ የሕዝቡን የኒውትሪሽን አቋም እና የሕዝብን ፍልሰትና ከቦታ ቦታ የመንጓዝ ሁኔታ የሚመዝኑ ናቸው፡፡

ይህንንም ለማድረግ፣ ልዩ ልዩ የመረጃ አሀዞች ተሰባስበውና ወደ ሥራ ለመተርጎም የሚያስችል እቅድ እንዲሆኑ ተገናዝበውና ተሰልተው መቅረብ አለባቸው፡፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃን ለማዘጋጀት የአየርና የእርሻ ሁኔታን፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ መረጃዎችን ማሰባሰብና ሕዝቦች ችግርን ለመቋቋም የሚወስዷቸውን እርምጃዎችና ባህላዊ እሴቶችን የሚያካትቱ አሀዞችን ማቀናበር ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ የልዩ ልዩ ሙያ መስኮችን፣ መሥሪያ ቤቶችንና ድርጅቶችን ማካተቱ አስፈላጊ ነበር፡፡

*ለቅድመ ማስጠንቀቂያ ትንበያ የሚያስፈልጉት ግብአቶች በሙሉ ከልዩ ልዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችና ከአገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተሰባስበው በወቅቱ ሲደርሱ ጠቃሚና ነፍስ አድን ማስጠንቀቂያ ይሆናሉ፡፡*

*ከመንግሥት ቅድመ ማስጠንቀቂያ በተጨማሪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታትና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቡድን ጽሕፈት ቤት የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ያሰራጫሉ፡፡ የዓለም የምግብ ድርጅትም የሰብል ምርትን የሚያጠና ቡድን በመላክ የምግብ አቅርቦት ሁኔታን ያጠናል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1983/84 ዓ.ም. የዓለም የምግብ ድርጅት የሚያስፈልገውን የእህል መጠን ሳይሆን ሊጓጓዝ የሚችለውን ታሳቢ በማድረግ 125,000 ቶን እህል ብቻ በዕርዳታ ይጠየቅ በማለቱ በተፈጠረው ውዝግብ ጠቃሚ ጊዜ ሊባክንና የሰው ህይወት ሊጠፋ ችሎ ነበር፡፡ ይኸ ችግር በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ክፍሎች የጋራ ጥናት ለማድረግ የሚያስችላቸው ከሁሉም የተውጣጣ አጥኚ ቡድን በጋራ ስላሰማሩ በመጠኑም ቢሆን ተሻሽሏል፡፡*

*ይህ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅትን ትኩረት ስለሳበ ከታንዛንያ የክልል አስተዳዳሪዎችና የግብርና ባለሙያዎች መጥተው ጥናታዊ ጉብኝት በማድረግ ከኛ ልምድ እንዲማሩ አድርጓል፡፡ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያውም ምስጋናና አድናቆትን አግኝቷል፡፡*

**በኢትዮጵያ የአደጋ ምክንያቶችና የሚያስከትሏቸው ችግሮች**

*በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የሚደርሰውና ብዙውንም ሕዝብ የሚጎዳው ድርቅ ነው፡፡ በተለይ በተደጋጋሚ የሚጠቁት ከደጋው ክፍል ወሎ፣ ትግራይ፣ ኤርትራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ጎንደርና ጎጃም ሲሆኑ ከቆላማው ክፍል ሐረርጌ (ኦጋዴን)፣ ሲዳሞ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ባሌና አርሲ ነበሩ፡፡ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዛሬ አሥራ አንድ ጠቅላይ ግዛቶች ከባድ የድርቅ ችግር በተደጋጋሚ አጥቅቷቸዋል፡፡ በ1998 ዓ.ም. 7,923,150 ሕዝብ በድርቅ ምክንያት ለረሃብ ተጋልጦ ነበር፡፡*

*በ1979 አሰቃቂ ረሃብ ሲከሰት (መሐመድ አሚን በተለይ የኮረምን መጠለያ ካምፕ በፊልም በቀረጸበት ወቅት) ወደገበያ ቀርቦ የነበረው እህል ለወትሮው ከነበረው ጋር ሲተያይ 50% ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህ የእህል ዋጋ በጣም ናረ፡፡ ገበሬውም ሆነ ከብት አርቢው ለመኖር ሲል ይህንን ውድ እህል ሸማች ሆነ፡፡*

*በዚህ ጊዜ የታየውን የእህል ዋጋ ግሽበት (የዓመቱን አማካኝ ዋጋ በመውሰድ) እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡ የማሽላ ዋጋ በኩንታል 60 ብር የነበረው በ1976 ብር 121 ፣ 1978 ደግሞ ብር 177 ሲደርስ፣ ጤፍ በኩንታል በ1976 ብር 86 የነበረው፣ በ1977 ብር 167 ፣ በ1978 ብር 221 ደርሶ ነበር፡፡ እንዲሁም የገብስ ዋጋ በ1976 ብር 54 የነበረው በ1976 ብር 97፣ በ1998 ደግሞ ብር 139 ደረሰ፡፡ ይሄ ዋጋ ለገበሬውም ሆነ ለአርብቶ አደሩ ካቅሙ በላይ ስለነበረ ከብቱን፣ ጌጣጌጡንና ቅርሱን ለመሸጥ ተገደደ፡፡ ይህም አልበቃ ሲለው ወደ አዲስ አበባ፣ አስመራና ወደ ሌሎች*

መንገድ ዳር ወደ አሉ ከተሞች መሰደድ ጀመረ:: የመንገድ ዳር መጠለያ ጣበያዎች እንደገና ተቋቋሙ::

ምንም እንኳን የኮረም ጣቢያ ከ1975 ጀምሮ ቢኖርም ብዙዎቹ ጣቢያዎች ከ1977 ጀምሮ ነበር የተቋቋሙት:: ከጥር ጀምሮ በወር 2,000 ሰው ወደ ኮረም መመገቢያ ጣቢያ መጉረፍ ጀመረ:: በጥቅምት 1976 ዓ.ም. የባቲና የሀርቡ ጣቢያዎች እንደገና ሥራ ጀመሩ:: በጥር 1976 እና በየካቲት 1985 ሚሌ ላይም የመመገቢያ ጣቢያ ሥራ ጀመረ:: ወሎ ክፍለ ሀገር ውስጥ ድርቁ የከፋ ከመሆኑ የተነሳ በ1978 ከነበሩት 600,000 ተረጂዎች ግማሾቹ ከዚያው ነበሩ:: የድርቁ ሁኔታ እየከፋ በመምጣቱ ሚያዝያ 1978 በመጠለያ የነበረው ሕዝብ ብዛት 282,000 ደርሶ ነበር::

በዚህ ወቅት የሞቱ ሰዎች ቁጥር በሚገባ አልተመዘገበም:: በጣም የተጠቁት አውራጃዎች አምባሰል፣ ቃሉ፣ ራያና ቆቦ፣ አውሳና የጁ ሲሆኑ በ1977 እና በ1978 በመጠለያ ጣቢያ የሞቱት ሰዎች በግምት 60,000 ደርሶ ነበር:: ይህ አሃዝ መጠለያ ውስጥ ካለው 7% ሲሆን በአጠቃላይ የሞተው ሰው ቁጥር በትክክል ባይታወቅም ከ600.000 በላይ መሆኑ አያጠራጥርም:: በአማካይ በመጠለያ ከነበሩት መሀከል የሚሞቱት ቁጥር ከአንድ ሺው ሃያ አምስት ነበር::

ሰዎች ለሠፈራ እሚመለመሉበት የአምባሰል መቀበያ ጣቢያ ውስጥ 891 ሰዎች ሲሞቱ ለጉዞ በሚዘጋጁበት ጣቢያ 900 ሰዎች ስላለቁ ድምሩ 1,791 ደርሶ ነበር:: ይኸ ከአምባሰል ወደ ሰፈራ ከሄዱት መሐል 4.2% መሆኑ ነው:: በዚህ ስሌት መሰረት 372,298 ከሚሆኑት የወሎ ሰፋሪዎች መሀከል የሠፈራ ሕይወታቸውን ከመጀመራቸው በፊት 15,000 ያህል እንደሞቱ ይገመታል:: በጠቅላላ በወሎ ከ1966 እስከ 1978 ድረስ በረሃብ የሞተው ቁጥር 300,000 ይደርሳል የሚል ግምት አለ::

## የሞት ምክንያቶች

ተረጂዎቹ የሞቱበትን ምክንያት ለማወቅ ልዩ ልዩ ጥናቶች ተካሂደዋል:: ሁኔታውን ለመገንዘብ እንዲረዳ አንዳንዶቹን የጥናቶቹን ግኝቶች ማየቱ ይጠቅማል::

ወርልድ ቪዥን ሳንቃ ላይ ባደረገው ጥናት መሰረት ከሞቱት መሀከል 51% በተቅማጥ ሲሆን 11% በኒሞንያ ነበር:: በባቲ መጠለያ ከሞቱት 707 ሰዎች ማህል የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል በየካቲትና በመጋቢት 1978 ባደረገው ጥናት 47% የሚሆኑት በተቅማጥ፣ 22% በኒሞንያ፣ 19% በሃይድሬሽን፣ 4% በማልኒውትሪሽን እና 3% በወባ እንደሆነ አሳይቷል:: በዚህ መሠረት ተቅማጥ፣ ኒሞኒያና ኩፍኝ ከፍተኛ የሞት ምክንያቶች ሲሆኑ የምግብ ችግር ተከታዩ ምክንያት ነበር:: ከነዚህ በተጨማሪ እንደ ታይፈስ፣ ታይፎይድ (influenza)፣ ትኩሳት፣ ሚኒንጃይትስና ሂፐታይተስም በወሎ ከተከሰቱ የሞት ምክንያቶች መሀከል ይገኙበታል::

## የ1976 ድርቅና የሰብል መጥፋት ማስጠንቀቂያ

ከ1977 ጀምሮ በድርቅ ምክንያት ምርት አለመገኘቱ በተደጋጋሚ ተገልጾ ለዕርዳታ ሰጪዎች ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም ድጋፉ ይኸን ያህል አልነበረም፡፡ በአዲስ አበባ ላይ በ1974 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ባደረገው ስብሰባ ላይ የዕርዳታና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ድርቅ መጠቃቱዋን አስመልክቶ ጊዜያዊ ዕርዳታ ብቻ ሳይሆን የችግሩ መነሻ በልማት ኋላ ቀር መሆናችን መሆኑና በርሻ፣ በውሃ ሃብት ልማትና በመሬት ልማት አለመሟላት ስለነበረ ችግሩን መቅረፍ የሚያስችል የልማት ዕርዳታና ብድር ማስፈለጉን የሚገልጽ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርቦ ነበር፡፡

በመላው አገሪቱ የመኸር ዝናብ ከዘወትር መጠኑ ከግማሽ በታች መሆኑ በ1976 ዓ.ም. ሪፖርት ተደርጎ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ በብዙ አካባቢዎች አንዳንድ ከአመት አመት የሚፈሱ ወንዞችና ምንጮችም ደርቀዋል፡፡ አርብቶ አደሮችም ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ተሰደዱ፡፡ የዓመቱ የትምበያ ሪፖርት 5.2 ሚሊዮን ሕዝብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ገለጸ፡፡ ሁኔታው እያደር ተባብሶ የዕርዳታ ፈላጊው ቁጥር በታህሳስ 1976 ወደ 7,750,000 ከፍ ብሎ ነበር፡፡ ለዚህም የሚያስፈልገው የዕህል መጠን 1,504,775 ቶን ነበር፡፡ በመጋዘን የነበረውና ቃል የተገባለት እህል 220,490 ቶን ሲሆን የተጠየቀው ዕርዳታ 1,284,285 ነበር፡፡ ከተረጂው አንድ ሦስተኛው ማለት 2,587,420 ህዝብ የወሎ ህዝብ ነበር፡፡ የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅትም ባደረገው ግምት የእህል ሰብል በ25%፣ ጥራጥሬ በ30% እንደሚቀንስና 7.3 ሚሊዮን ቶን ከሚሆነው ምርት ከ1.7 እስከ 2 ሚሊዮን ቶን ምርት ስለቀነሰ ከ6.5 ሚሊዮን እስከ 8 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ ዕርዳታ እንደሚፈልግ ተገልጾ ነበር፡፡ ዕማማኮ ካቀረበው ሪፖርት ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ቢሆንም ባለው የወደብ ሁኔታና የትራንስፖርት አቅም ማነስ ምክንያት ሊጓጓዝ የሚችለው እህል ስላነሰ ዕርዳታ ሰጪዎቹ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት የኛን ጥናት እስኪያረጋግጡ በመቆየታቸው የሰው ሕይወት ማለፍን አስከተለ፡፡

### የችግሩ ገፈት ቀማሽ የወሎ ክፍለ ሃገር ህዝብ

በተለይ በ1976/77 ዓ.ም. በደረሰው ድርቅ ወሎን በጥልቀት መመልከቱ ችግሩን ለመገንዘብና ለወደፊት እርምጃችን ሊረዳ ይችላል፡፡ በሰሜን ምሥራቅ የሚገኘው የወሎ ክፍለ ሃገር አሥራ ሁለት አውራጃዎች ነበሩት፡፡ ክፍለ ሀገሩ በአብዛኛው ደጋ ነበር፡፡ ይሁንና በአውሳ አውራጃ የሚገኘው የደንከል ስምጥ ከባሕር ወለል በታች ነው፡፡ ስለዚህ፣ ክፍለ ሀገሩ በአገራችን የሚታወቁት ሦስቱም አየር ንብረቶች (ማለትም ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላ) ይገኙበታል፡፡

በአፋር ክልል ከሚገኘው አርብቶ አደር (ማለት ከአውሳ አውራጃ) በስተቀር ሌሎቹ የእህል ሰብል አምራች የሆኑ የገበሬዎች መኖሪያ ናቸው፡፡ የወሎን ለአደጋ

ተጋላጭነት ሁኔታ ያጠኑ ምሁራን የእርሻና የአካባቢውን የተክልና የእጽዋት ይዘት አካባቢዎችን (Agro-ecological zones) ሲከፋፍሉ ሁለት መስፈርቶችን በመጠቀም ነው:: (1) የእህል መብቀያውን ወቅት እርዝማኔ እና (2) ከባሕር ወለል በላይ ያለውን ከፍታ በመጠቀም ነው::

ከአውሳ በስተቀር በዝናብ በቀል እህል የሚተዳደሩትን አውራጃዎች የአፈር ጥልቀት በማጥናት ከ35 ሴንቲ ሜትር ያነሰ አፈር ያለው ከወሎ 90% ሲሆን የአገር አቀፍ አሃዝ ግን 35 መሆኑን አሳይተዋል:: ከላይ ካለው አፈር በያመቱ 1.3 ሴንቲ ሜትር እየታጠበ ይሄዳል:: እስከ 2010 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የአፈር መከላት ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል::

ሰንጠረዥ 2፣ የአፈር መከላት

| የአፈር ጥልቀት | 1985 | 2010 |
|---|---|---|
| ከ150 ሴሜ በላይ | 9% | 9% |
| 100 - 150 ሴሚ | 11% | 11% |
| 50 - 100 ሴሚ | 28% | 23% |
| 25 - 50 ሴሚ | 19% | 14% |
| 10 - 25 ሴሚ | 21% | 7% |
| 0 - 10 ሴሚ | 10% | 24% |
| ዲንጋያማ | 2% | 12% |

በ1977 ዓ.ም. የወሎ ሕዝብ ብዛት 3,609,918 ሲሆን በአማካይ በቤተሰብ በቃሉ 4.4፣ በዋግ፣ ላስታና አምባሰል 4.2፣ በዋድላ፣ ደላንታ፣ ራያና ቆቦ 4.1፤ በየጁ፣ አውሳ፣ ቦረናና ወረኢሉ 4.4ና በወረሂሙኑ 3.9 ሰው ይገኝበታል:: ከሕዝብ ቁጥር መብዛት የተነሳ ተራራውንና ምርታማ ያልሆነውንና አፈሩ የታጠበና በቂ ዝናብ የማይገኝበትን አካባቢ ጭምር ያርሳሉ:: ከዚህም የተነሳ መሬቱን በመከፋፈል ከሄክታር ያነሰና ሊያኖር የማያስችል መሬት ባለይዞታ ሆነዋል::

ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ከወሎ ሕዝብ ከፊሉ ተረጂ ሆኗል:: ከወሎ ሕዝብ በተከታታይ ዓመታት ተረጂ የነበረው በ1970 ዓ.ም. 24.3%፣ በ1971 ዓ.ም. 39.1%፣ በ1972 ዓ.ም. 36.4%፣ በ1973 14.4%፣ በ1974 ዓ.ም. 20.8%፣ በ1975 ዓ.ም. 31.1%፣ በ1976 ዓ.ም. 49.2%፣ በ1977 ዓ.ም. 61.1%፣ በ978 ዓ.ም. 40.1%፣ በ1979 8.3% እና በ1980 ዓ.ም. 20.9 ነበር:: ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው የወሎ ሕዝብ ለድርቅ የተጋለጠ መሆኑን ነው:: ከላይ በተጠቀሱት አስር አመታት የተጎዳው ሕዝብ

በአማካይ ከመቶ ሰላሳ ሁለት እጅ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በ1979 ዓ.ም. ወደ 8.3% ዝቅ ቢልም በዓመቱ ተመልሶ 20.8% ገባ፡፡

ወሎ በአብዛኛው ተራራማና መንገድም የሌለው ስለነበረ ችግር መኖሩ ከታወቀ የዕርዳታው እህል ክረምት ከመግባቱ በፊት አመቺ ቦታዎች ገብቶ መከማቸት አለበት፡፡ ከአዲስ አበባ መቀሌ እና ከኮምቦልቻ አሰብ ባሉት መንገዶች ዳር የአሉት ከተሞች በችግር ጊዜ የባላገሩ ህዝብ እርዳታ ፍለጋ ሄዶ የሚቀመጥባቸው ናቸው፡፡

## የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ ለማጠናቀር የተወሰደ እርምጃ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ በ1974 ዓ.ም. ዝቅተኛ ልማት ስላላቸው አገሮች ሁኔታ የተባበሩት መንግሥታት አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ ባደረገበት ወቅት ዕማማኮ ለዕለት ደራሽና ለዘለቄታ ልማት የሚያግዙ የቁሳቁስና የገንዘብ ዕርዳታ ጠይቆ ነበር፡፡ ከዚያም በመቀጠል በ1975 እና በ1976 ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበው ነበር፡፡ ቢሆንም ምላሹ አመርቂ አልነበረም፡፡

በ1977 ችግሩ ተባብሶ አርሶ አደሩ ቀዬውን ለቆ ምግብ ፍለጋ ተሰደደ፡፡ አርብቶ አደሩም ለራሱ ምግብ፣ ለከብቶቹ ግጦሽ፣ ፍለጋ ከብቱን እየነዳ በየአቅጣጫው ወደ ደጋው መጓዝ ጀመረ፡፡ በዚያን ጊዜ ዕርዳታ ሰጪዎች ዕርዳታ ፈላጊ ለነበረው 5.2 ሚሊዮን ሕዝብ ዕርዳታ ለመስጠት ቃል ቢገቡም ከአምስት ወር በኋላ እንኳን እርዳታው ሊደርስ አልቻለም፡፡ እንደገና አሁንም ችግሩ ተባብሶ በአገሪቱ በሙሉ የተረጂው ቁጥር 6,098,011 ሲደርስ፣ በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገቡት ተረጂዎች እንዳይሞቱ የአስቸኳይ የእርዳታ ጥያቄ ለ400,000 ቶን ቀረበ፡፡

ይህ ሁኔታ በራስ አቅም በቅድመ ማስጠንቀቂያ መሠረት፣ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ካልተቻለ፣ መንገዱና ተሽከርካሪው ኖሮ እርዳታው በወቅቱ በሚፈለግበት አካባቢ በመጋዘን ካልተከማቸ ጥሩ መረጃ መኖሩ ብቻ ችግሩን ሊፈታው አለመቻሉ ነው፡፡

### ራስን መቻል ቁልፍ ነው

ዕማማኮ ሲጨንቀው የመገናኛ ብዙሃንን በመጥራት ሁኔታውን ለአለም ሕዝብ እንዲያስረዱ ጋበዘ፡፡ በሰኔ 1970 ወይዘሮ ሁኔን ሎር ጋዳሽ በጀርመን ቴሌቪዥን ሪፖርት አቀረቡ፡፡ በቢቢሲም "Seeds of Despair" የሚባለውን ፊልም ቻርለስ ስቱዋርት አቀረበው፡፡ አራት ደቂቃ የሚቆየው መሐመድ አሚን ያነሳው ፊልምና ማይክል ቦርክ ገለጻ ያደረገበት ዜና በቢቢሲ ሲወጣ የችግሩ አስከፊነት በየሰው ቤት ገብቶ ታየ፡፡ የብዙዎችን ልብ ነካ፡፡ እነሱም የሚችሉትን ሰጥተው መንግሥቶቻቸውን ደግሞ እንዲረዱ ጫና ፈጠሩ፡፡ በተለይ የአንድ ቤተሰብ አባላት ያላቸውን ቤት ሸጠው ገንዘቡን በመለገሳቸው፣ የኢትዮጵያውያንን ነፍስ ለማዳን መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡

በ1977 ዓ.ም. በ10 ክፍለ ሃገሮች፣ በ64 አውራጃዎች፣ 283 የእህል ማደያ ጣቢያዎች እየሰሩ ነበር። በአመቱ በ68 አውራጃዎች እና በ310 ማደያ ጣቢያዎች ዕርዳታ መሥጠት ቀጠለ።

ዕርዳታ የሚሰጠው በድርቅ ለተጎዱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ በተስፋፋ ጦርነትና በእርስ በርስ ውጊያ ለሚፈናቀሉ፣ ከጅቡቲና ከሶማሌ ከስደትና ከምርኮ ወደ አገራቸው ለሚመለሱትም ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ከአራት መቶ ሺህ የሚበልጡ የሱዳንና የሶማሌ ስደተኞችንም የመርዳት ጫና ነበረ።

አስረኛውን የአብዮት በዓል ለማክበር በሚያደርገው ወጪና ዝግጅት ምክንያት ለችግሩ በቂ ትኩረት አልሰጠውም በማለት በወቅቱ በነበረው መንግሥት ላይም የሰላ ትችት ተሰነዘረበት። መንግሥት ከበአሉ ማግሥት ጀምሮ ሁኔታውን ለማስተካከል በወቅቱ መሪ ሰብሳቢነት ትልቅ ቡድን አቋቁሞ በውስጡም 12 ንዑሳን ኰሚቴዎች በከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሊቀመንበርነት አዋቀረ። እነዚህም የዕለት ዕርዳታ፣ የሎጂስቲክስና ትራንስፖርት፣ የሕዝብ ማስፈር፣ የእርሻ፣ የመንግሥት እርሻ፣ የኰንስትራክሽንና የውሃ ልማት፣ የፕላንና ፕሮግራም፣ የኢንስፔክሽንና የመረጃ፣ የፕሮፖጋንዳና የፀጥታ ኮሚቴዎች ነበሩ።

የተባበሩት መንግሥታትም ዕርዳታ የሚያስተባብር ኃላፊ በረዳት ዋና ፀሐፊ ደረጃ፣ በካምፑቺያ የነበረውን ችግር ለመፍታት በተደረገው እንቅስቃሴ የማስተባበር ልምድ የነበራቸውን የፊንላንድ ዲፕሎማት፣ ኩርት ያንሰንን ሾመ።

ሕዝብ ቀዬውን ለቆ በየመጠለያ ጣቢያው ተሰዶ ባለበት ወቅት (ሻለቃ ዳዊት የወቅቱ ኮሚሽነር ቀይ እምባ በተባለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት)፣እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1984 ዓ.ም. በየካቲት መጨረሻ በመጠለያና በእህል ማደያ ጣቢያዎች በየመንደሩ በሳምንት 10,000 ሰዎች ከመጋቢት በኋላ ከ16,000 እስከ 17,000 የሚሞትበት ሁኔታ ነበር። መንግስት፣ የተባበሩት መንግሥታትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መረባረብ ጀመሩ።

**የእለት ዕርዳታ ስርጭት**

አብዛኛው የአገራችን ክፍል የመንገድ መገናኛ ስለሌለው ዕርዳታ ማዳረሱ ፈታኝ ችግር ነበር። የትግራይ ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ልዑል ራስ መንገሻስዩም አውራጃን ካውራጃ ለማገናኘት ባደረጉት ጥረት (ጥርጊያም ቢሆኑ እንኳ) በተሰሩት መንገዶች ምክንያት በትግራይ ዕርዳታ የማሰራጨቱ ሥራ የተሻለ ነበር። በወሎ ከባድ የመንገድ ችግር ከመኖሩ የተነሳ፣ አብዛኛው እርዳታ የተከፋፈለው መንገድ ተከትሎ ባሉት ከተሞች ስለነበር፣ አብዛኛው በምዕራብ ያለው የደጋው ተራራማ አካባቢ በሚገባ አልተረዳም። ላስታ፣ ዋድላ፣ ደላንታና ቦረናን የመሳሰሉት አካባቢዎች መንገድ ስለሌላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች 62% የሚሆነውን የእርዳታ

እህል በ1985 ዓ.ም. ያከፋፈሉት በሦስቱ አውራጃዎች ማለት በአምባሰል፣ በየጁና በራያ ቆቦ ብቻ ነበር:: በነዚህ አውራጃዎች የነበሩት ተረጂዎች ዕርዳታ ከሚያስፈልገው ሕዝብ 34% ብቻ ነበሩ:: ይህ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ነበር:: ምክንያቱም በጥር 1985 ዕማማኮ ከተረጂው 68% ሲሸፍን ቢቆይም፣ ዕርዳታ ሰጪዎች አብዛኛውን ዕርዳታ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል ማሰራጨት ስለጀመሩ በታህሳስ 1985 የዕማማኮ ሽፋን 12% ብቻ ሆኖ ነበር:: የመሠረተ ልማት አውታር የሆነው መንገድ ካልተስፋፋ በድህነት ላይ የምናደርገው ጥረትም ሆነ ችግር ሲከሰት ለመርዳት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ ሊሆን አይችልም::

በ1984/85 በወሎ ዕርዳታ ከሚያስፈልገው 1,790,840 ከሚሆን ሕዝብ መሐል እርዳታ የደረሳቸው 1,447.282 ናቸው:: ይኸም የተሰራጨው በ21 መጠለያ ጣቢያዎች (የሠፈራ መጠለያዎችን ጨምሮ)፣ በ187 የእህል ማደያ ጣቢያዎች እና በ38 መመገቢያ ጣቢያዎች ሲሆን የተሰጣቸውም 414,357.77 ኩንታል እህል፣ 32,929.09 ኩንታል አልሚ ምግብና 2,100 ኩንታል የሚበላ ዘይት ነበር::

ይህን ዕርዳታ ለማድረስ ዕርዳታ ሰጪዎቹ ባላቸው የቢሮክራሲ መንተተ የተነሳ ፈታኝና አስጨናቂ መዘገይቶች ስለሚፈጠሩ ስምምነት የተደረገበት የምግብ ዕርዳታ ለተጠቃሚው ለመድረስ እስከ ሰባት ወር ይፈጅ ነበር::

## ሎጂስቲክስ

በየወደቦቻችን የነበረው የቢሮክራሲ አሠራር (ለምሳሌ ለአንድ ዕቃ እስከ 42 ፊርማዎች ማስፈለጉ) ለእርዳታ መዘግየት ተጨማሪ ምክንያት ነበር:: በተሽከርካሪም በኩል በየወሩ ሃምሳ መኪናዎች ያህል መሰናከላቸውና አራት ወይም ስድስቱም የመኪና እግር ላይ የሚገጠሙት ጎማዎች በአመት አራት ጊዜ በአዲስ መተካት ስለነበረባቸው፣ በጎማ እጦት ምክንያት መኪናዎች ለሥራ ዝግጁ አለመሆን ሌላው ችግር ነበር:: የምንጠቀምባቸው መኪናዎችም 47 ዓይነትና ከመቶ ሞዴል በላይ መሆናቸው በመለዋወጫ አቅርቦት በኩል ተጨማሪ ፈተና ነበር:: የመኪና ምርጫና በጥራት ተመርጠው አለመምጣት የሚያስከትለውን ችግር ለማስረዳት ያህል ከኩዌት በአስቸኳይ ከመጡት መቶ ተሽከርካሪዎች ከአመት በኋላ ሁሉም ሥራ ላይ ሊውሉ አለመቻላቸውን መገንዘቡ ብቻ በቂ ነው::

### በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የሚታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም መደራጀቱ በጣም ጠቃሚ ነው:: ጥቅሙ እርዳታ ለመጠየቅ የሚረዳ አሃዛዊ መረጃ ማግኘቱ ሳይሆን ሕዝቡ ያለበትን ሁኔታ አውቆ የሚያስፈልገውን መፍትሄ ለመቀየስ ማስቻሉ ነው::

ባለመታደል አቅም አጣን እንጂ፣ አቅም ብንገነባ ኖሮ፣ ራሳችን ራሳችንን እንድንረዳ የሚያግዘን መሣሪያ ነበር። የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት በመኸርም ሆነ በበልግ ያለውን የሰብል ሁኔታ በመተንተን በቂ ምርት እንዳለን ወይም እንደሌለን በወቅቱ ይገልጽ ነበር። ይህም ጠቃሚ ነበር።

በዚህም ሪፖርት የእህል እጥረቱን መጠን፣ እጥረቱ የደረሰበትን አካባቢና ምን ያህል ሰው የእህል አቅርቦት እንደሚፈልግ ያሳውቃል። በሪፖርቱ መሠረት የዝግጁነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በኛ አገር ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ በመውሰድ ፈንታ እርምጃውን ለመውሰድ የሚያስችሉንን መሣሪያዎች፣ እህል አልሚ ምግብ፣ የትራንስፖርት መኪና፣ ገንዘብ፣ ሥራ፣ ለውሃ ቁፋሮ፣ ለመስኖ ሥራ የልማት መሣሪያዎች ፣ ለመንገድ ወደ እርዳታ ሰጪዎች ለጥያቄ እንሄዳለን።

የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አቅማችን የተጠናከረ አይደለም። ለሱም ቢሆን ዕርዳታ ጠያቂዎች ነን። ጥሩ ዝናብ ዘነበም አልዘነበ፣ አሁን ባለን የማምረት አቅም፣ ለሸማችም ሆነ ለተረጂ መቅረብ ያለበትን የእህል መጠን ለማቅረብ፣ ወይም የምርት አቅማችንን ለማሻሻል፣ ወይም ከሌላ የልማት ሥራችን በምናገኘው ገንዘብ ሸምተን ለማቅረብ፣ ልዩ ጥረት ማድረግና መፍትሄ መፈለግ አለብን። ከመሠረቱ ላለው የእህል እጥረት (እስትራክቸራል ዴፊሲት ለምንለው) መፍትሄ መፈለግ አለብን።

በ1971 የእህል እጥረት በደረሰ ጊዜ፣ በጥናታችን መሠረት ሊኖረን ከሚገባው የመጠባበቂያ 180,000 ቶን ውስጥ የነበረን 18,000 ቶን (10%) ብቻ ነበር። ለትራንስፖርት ኪራይ፣ ለመኪና መግዣ፣ ለነዳጅና መለዋወጫ፣ እህሉን አጓጉዞ ለሕዝብ ለማድረስ 267,757,549 ብር ጥያቄ ለለጋሾች አቀረብን። ከቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በተገኘው መረጃ መሠረት በድርቁ ለሚጎዳው 7.75 ሚሊዮን ሕዝብ ለሕክምና ፍላጎት የሚያስፈልገንን 31,000,000.00 ብር ለማግኘት አሁንም ዕርዳታ ሰጪዎችን ጠይቀን መልስ መጠበቅ ነበረብን።

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሃዞች ጠቃሚ መረጃዎች ቢሆኑም ዝግጁነትን ማረጋገጥ በሌሎች ችሮታና በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነበር። ከኛ በኩል በቂ በጀት አልተመደበም። ለዓመታት የዕማማኮ በጀት እርዳታ ለማድረስ፣ ለመጫን፣ ለማውረድ እንኳን የማይበቃ በየዓመቱ 10,000,000.00 ብርና ለአንዳንድ የልማት ሥራዎች የሚሰጥ አነስተኛ ድጎማ ነበር። ስለዚህ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውጤት የሚኖረው ለዝግጁነት የሚረዳ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅም ሲኖር ብቻ መሆኑ ትልቅ ትምህርት ሊሆን ይገባል።

በ1977 ዓ.ም. የተከሰተው ከባድ ረሃብ የተባባሰው አስተማማኝነቱን የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት እያወቀው የኛን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ ሎጂስቲክሱ የላችሁም በሚል ስላንተተው ነው። በመጨረሻም፣ በመጠኑም ቢሆን ተግባራዊ

የሆነው እርዳታ የተገኘው የመገናኛ ብዙሃንና ሕዝቦች በመንግሥቶቻቸው ላይ በፈጠሩት ጫና እና እነቦብ ጊልዶፍ ተሰባስበው በዘመሩት መዝሙር ግፊት ነበር። ነገር ግን ባለው ሎጂስቲክስ ሊጓጓዝ የሚችለውን ያህል እንኳን እህል በወቅቱ ቢለቀቅ ኖሮ ብዙ ህይወት ይድን ነበር።

የሎጂስቲክስ ችግር መኖሩ የማይካድ ነው። በቅድመ ማስጠንቀቂያ መሠረትና አይ.ኤም.ኤፍ ባጠናው መሠረት ለዘጠኝ ወር የሚያስፈልገው እህል መጠን 912,212 ቶን ቢሆንም ዕርዳታ ማስተባበሪያ ይቻላል የሚለውን መጠን ገዝቶ ጥያቄውን በግማሽ ቀንሶ 450,000 ቶን ሲያደርገው የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO) እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) ግን 125,000 ቶን ላይ ረጉ። አሰብ ላይ ከመርከብ የማውረድ አቅማችን በቀን 2,846.5 ቶን ሲሆን ከወደብ የማንሳት ችሎታችን ደግሞ 2,585.6 ቶን ነበር። ስለዚህ ከመርከብ ወርዶ ማንሳት የማንችለው በቀን 260.9 ቶን በዓመት 93,912 ቶን ቢሆንም የዕማማኮ የችሎታ ግምት ወደ እውነቱ የተጠጋ ነበር። ለማንም መንግስት ቢሆን የራሱን ሕዝብ መመገብ አቅቶት በረሃብ ይሙቱ አይሙቱ ለሚለው ጥያቄ መልሱ በውጪ ሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ መሆኑ በጣም አሳሳቢና አጣብቂኝ ነው።

ለዚህ ነው በ1966 ዓ.ም. አስተማማኝ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ፕሮጀክት ሀሣብ የቀረበው። የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅትና የዓለም ምግብ ፕሮግራም ፈቃደኛ ሆነው እገዛ ሲጀምሩ በዕማማኮ ሥር ፕሮጄክቱ ተቋቋመ። የዚህ የአስቸኳይ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ፕሮጀክት ዓላማም:-

የተፈጥሮ አደጋ (ማለትም በአስከፊ ድርቅ፣ በፀረ-ሰብል ተባይ ወረርሽኝ ... እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊከሰት ስለሚችል) የዕህል ክምችቱ አመቺ (እስትራተጂክ) በሆኑ ሥፍራዎች ተቀምጦ በፍጥነት ሊደርስ የሚችል መሆን አለበት። ባልተጠበቀና ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ወይም በሰው ሠራሽ ችግሮች፣ ማለትም በጦርነት ወይም በመርከብ የተጫነ እህል በማዕበልና በሌላም ችግር ሲዘገይ የሚደርሰውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም እንዲቻል የታቀደ ነበር። የዕርዳታ ተስፋና የመግዛት አቅም ኖሯቸው ጊዜ በመግዛት ሕይወት ለማዳን ለሚሠሩ ድርጅቶች በብድር መልክ የሚሠራጭና ሊተካ የሚችል ክምችት መያዝ ነበር።

ይህም ዓላማ ለረሃብ የሚጋለጥ እስከ ሰባት ሚሊዮን ሊደርስ የሚችል ሕዝብ መጠን ያገናዘበና የሰው ሕይወት ሳያልፍ ተመጣጣኝ ዕርዳታ ከአምስት እስከ ሰባት ወር ውስጥ በማድረስ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የተቋቋመበትን ዓላማ ለመወጣት የሚያስችል የአደጋ ዝግጁነት ነበር። በዚያን ጊዜ በነበረው ሁኔታ መሠረት የተደረገው ጥናት የረጂዎችንም የመደገፍ አቅምና በጎ ፈቃድ ያገናዘበ ነበር። በ1967 ተጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ የሚከማቸው እህል 180,000 ቶን ይደርሳል። ለአደጋ ይጋለጣል ተብሎ የሚገመተው ሕዝብ ብዛት ከሰባት ሚሊዮን ስለማይበልጥና ሁሉም ባንድ ጊዜ ችግር ላይ ስለማይወድቁ የባሰበትን ሕዝብ ደረጃ

በደረጃ በመርዳት የሰው ህይወት ሳያልፍ ተጨማሪ እህል በግዢም ሆነ በዕርዳታ ይደርሳል ተብሎ የታሰበበትን ጊዜ ያገናዘበ ነበር፡፡ ይሁንና፣ አፈጻጸሙ እንደታሰበው አልነበረም፡፡

ምንም እንኳን የመጠባበቂያ እህል ክምችቱ ዘግይቶ ቢጀምርም ከዕርዳታ ሰጪዎች 42,500፣ ከመንግሥት ደግሞ 50,000 ቶን ስለተሰጠ የመጠባበቂያ ክምችቱ በ1980 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ 92,500 ቶን ደርሶ ነበር፡፡ በአገሪቱ በተደጋጋሚ ይደርስ በነበረው ድርቅና ረሃብ ምክንያት ለክምችቱ ቅድሚያ ተሰጥቶት የታቀደው 180,000 ቶን እንዲደርስ አለመደረጉ ብቻ ሳይሆን በየግዜው ለሚደርሰው አደጋ ከክምችቱ ወጪ የተደረገውም እህል በጊዜው ስለማይተካ የታሰበው ጣሪያ ሊደርስ አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በሰባት ዓመት ጊዜ ፕሮጀክቱ ሊያከማች የቻለው የዕቅዱን 51% ብቻ ነበር፡፡ በ1979 እና በ1980 ዓ.ም. የደረሰውን አስከፊ ድርቅ ለመቋቋም 46,500 ቶን እህል ወጥቶ በመታደሉ ብዙ ነፍስ ድኗል፡፡ ቢሆንም ለክፉ ቀን ሊኖረን የሚገባ የመጠባበቂያ ክምችት እህል 180,000 ቶን ሳይሆን 46,000 ቶን ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የመጠባበቂያ ክምችት እንዲኖረን ስናስብ ሊረዱ የሚችሉ ወገኖችን ድጋፋቸውን በተደጋጋሚ ጠይቀናል፡፡

የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ሀላፊነት በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የተጋለጡትን ወገኖች መርዳት ስለነበረ፣ ኮሚሽኑ ለሽማቂ ሕዝብ ሀላፊነት አልነበረበትም፡፡ በአብዮቱ ወቅት አያሌ ግብታዊ ውሳኔዎች ተወስደው ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሰቲትና በሁመራ የግል ሀብታቸውን በማፍሰስ በሰሊጥና በማሽላ እርሻ ተሰማርተው፣ የአገሪቱን የዕርሻ ምርታማነት በማሳደግ ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ቅስም የሚሰብር የውርስ አዋጅ ሲታወጅ በኃይል ስለመታቸው ትርፍ ሳይሆን ወጪያቸውን ለመመለስ እንኳን በማይችሉበት ሁኔታ የባንክ ባለዕዳ አድርጓቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በኤርትራ አሳሳቢ የረሃብ ሁኔታ እያንዣበበ ስለነበረ አንድ ኩንታል ማሽላ በ12 ብር ሂሳብ 250,000 ኩንታል በላይ ማሽላ ከነዚሁ ሰዎች በመግዛት ወደ ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንዲጓጓዝ በማድረግ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መምታት ተችሎ ነበር፡፡ አንዱ ወፍ ለም መሬት ለማልማት የወጣው ሀይል ሁለተኛው ወፍ በወንድማማች ጦርነት ከሃያ ኪሎሜትር በማይበልጥ ቀለበት ውስጥ ገብቶ ለነበረው ለአስመራ ከተማና ለየአውራጃዎቹ ሽማች ሕዝብ የሚቀርብ እህል በእህል ሰብል ገበያ በኩል ለሸማቹ፣ በዕማማኮ በኩል ለተረጂው ሕዝብ ማዳረስ መቻሉ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በቀጥታ ለክምችቱ የሚውለው እህል ከውጪ ቢመጣም ከላይ በጠቀስኩት ሁኔታ የሚገኘው እህል የአስቸኳይ ጊዜ መጠባበቂያ ክምችት እህል አጋዥ ነበር፡፡

የኤርትራን የእህል ስርጭት ካነሳሁ አልቀረ በአሊጊደር እና በተሰነይ አካባቢ በነበረው የባራቶሎ የጥጥ እርሻ ይመረት የነበረውን የጥጥ ምርት እርሻ ለማሰናከል የግድቡን ውሃ ወደ እርሻው የሚወስደውን የተሰካ በርሚል የሻቢያና ምናልባትም የጀብሃ ተዋጊዎች በጥይት ወንፊት አድርገውት የነበረውን በአዲስ በመተካት

ለትርፍ ቢፈለግ ጥጥ መትከል በገንዘብ አትራፊ ቢሆንም ሕዝብ ለማዳን ሲባል እማማኮ ማሽላ ዘርቶ ነበር ይሁንና በመዝራት ከዚህ የሚላከውን እህል ከተባበሩት መንግሥታት በተሰጠንና የተባበሩት መንግሥታትንም አርማ አድርገው በሚጓዙ መኪናዎች ጭነን ስናጉዋጉዝ ከእነ እህሉ ጀብሃና ሻቢያ ያቃጥሉዋቸው ነበር። ቢሆንም፣ ሕዝቡን ከሞት ለማዳን ከባድ ጥረት ተደርጓል።

በኤርትራ ጦርነት ጊዜ የወደመውን በኤላ በረድ የነበረውን የካሲያኒ ዴናኒይ የወይን እርሻና የኢላበረድ ወይን ፋብሪካን ሻቢያ ያጠፋውንና ያቃጠለውን እርሻም እንዲያንሰራራ ፋብሪካውም መልሶ ተቋቋሞ የወይኑም፣ የቲማቲም ድልህ ፋብሪካውም እንዲሠራ የከብት እርባታውንም ጥጆች ከካናዳ ድረስ በማምጣት እንደገና ወተትና አይብ እንዲያመርት በማድረግ ሰው ሰርቶ እንዲያድርና ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ ዕማማኮ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

በዚህ በአፍላ ጦርነት ወቅት ደቀመሐሪ የነበረውን የብስኩት ፋብሪካ ሻቢያ አቃጥሎትና አበላሽቶት የነበረውን ቤቱን በማደስ፣ መሣሪያውን በመተካት ሰዎች ሠርተው በልተው የሚያድሩበት እንዲሆን ለማድረግ ብዙ ተደክሟል።

በኤርትራ የሚኖሩ የአፋር ተወላጆች በዳህላቅ አካባቢ በአሳ ማጥመድ ሥራ ውስጥ እንዲገቡ፣ ከሉተራን ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን የዴንማርክ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር፣ ዘመናዊ አነስተኛ አሣ ማስገሪያ ጀልባዎችን መሥራት እንዲማሩ በናኩራ ትምህርት ቤት ከወዳጄ ከአቶ ካሣ ገብሬና በኤርትራ የእማማኮ ተወካይ ከነበረው ከመቶ አለቃ ብርሃኑ ጋር እና ከወረዳው አስተዳዳሪ ከአቶ ጠሀ ጋር እንዲሠራ ተደርጓል።

ከረን አካባቢ ጣሊያኖች ሠርተውት የነበረውን ግድብ አሸዋና ድንጋይ ሞልቶት ስለሞላው አሸዋውን በመጥረግ ግድቡን ሥራ ላይ በማዋል አትክልትና ፍራፍሬ እንዲመረት ተደርጓል። በምፅዋ ጦርነት የወደመውን ትምህርት ቤት መልሶ በመሥራት፣ የምድር ባቡር ጣቢያንና ሆስፒታሉን በማደስ፣ ከረን እንደገና ተመልሳ ነፍስ እንድትዘራ ተደርጓል።

በዚያን ወቅት እህል ሜዳ ላይ ይቀመጥ ስለነበረ ለወደፊቱ ደምበኛ መጋዘን መሥራት ትኩረት ተሰጥቶት ነበር። ይህም የእህል ክምችት የታሰበው በ10 ክፍላተ ሀገራት ቢሆንም ለጊዜው ዕማማኮ ማከማቻ በሠራባቸው በአሰብና በምጽዋ ወደቦች፣ በድሬዳዋ፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ በኮምቦልቻና በናዝሬት ብቻ ነበር።

በመጋዘን በኩል ለመጠባበቂያ ክምችት የራሱ መጋዘን ስላልነበረው በእህል ሰብል ገበያ ድርጅት ለማስቀመጥም በአንድ ቶን 33 ብር ያስከፍል ስለነበር አብዛኛው ክምችት የሚቀመጠው በእማማኮ መጋዘን ነበር።

የማከማቻ መጋዘን ያላቸው እማማኮና ግብርና ሚኒስቴር (በተለይ ኤፒድ) ከእማማኮ ጋር ከድርቁ ጋር በተያያዘ የመልሶ ማቋቋም ሥራ በጣምራ ይሠሩበት

በነበረበት ጊዜ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም እህል ማከማቻ መጋዘኖች ለድርቁ ተገኝቶ በነበረው ገንዘብ ስለተሠሩ በተለይ ዶ/ር ሰለሞን በኩረ (ለተወሰነ ጊዜ) እና የስዊድን ተወላጅ አማካሪዎች ፕሮፌሰር አይዛክሰንና ረዳታቸው ሚ/ር ሆኖበርግ (በኋላ የስዊድን አምሳደር ሆነው በኢትዮጵያ ያገለገሉት) ባደረጉት ጥረት የተሰሩ መጋዘኖች ስለነበሩ እማማኮ፣ እህል ሰብል ገበያ ድርጅትና ግብርና ሚኒስቴር ክምችት የመያዣ መጋዘኖች ነበሩአቸው። ከዚህም መሐል እማማኮ 3.3 ሚሊዮን ኩንታል የሚይዙ መጋዘኖች፣ እህል ሰብል ገበያ ድርጅት 6.3 ሚሊዮን ኩንታል የሚይዙ መጋዘኖች ነበሩዋቸው።

የእህል ክምችት ድርጅት በእማማኮ ሥር ሆኖ የኮሚቴ አባላት ከእማማኮ፣ ከግብርና ምኒስቴርና ከገንዘብ ምኒስቴር ተወጣጥተው ተደራጀ። የሙያ እገዛ እንዲያደርጉ የእማማኮ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የፕላን አገልግሎት ኃላፊ፣ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣ የብሔራዊ አስቸኳይ ጊዜ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ሥራ አስኪያጅና የዓለም የምግብ ፕሮግራም ተጠሪ ተመድበው ነበር።

የእህል ክምችቱን በማዘዋወርና በመለዋወጥ በኩል ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ዕማማኮና እሰገድ በቅርብ ይሠሩ ነበር። ለእርዳታ የሚሰጠውን በብድር በመስጠት አሮጌውን እህል በአዲስ ለመተካት ተሞክሯል። ከእህል ሰብል ገበያ ድርጅት ጋርም (በማበደር) የመለዋወጥ ተግባር ተፈጽሟል። ቢሆንም አሠራሩ በአብዛኛው በበጐ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንጂ የየድርጅቶቹ የሥራ ኃላፊነትና ድርሻ ተደርጎ ስላልተወሰደ አልፎ አልፎ ሥራው መጓተቱ አልቀረም። በተለይ የክምችቱ መጠን እየጨመረ ሲሄድ፣ ወጪና ጉልበት ስለሚጠይቅ፣ ችግሩ እየተባባሰ መሄዱ አልቀረም።

## የእህል ሰብል ገበያ ድርጅት

የእህል ሰብል ገበያ ድርጅት በ1969 ዓ.ም. ሲቋቋም ከዓላማዎቹ አንዱ ለችግር ጊዜ የሚሆን የመጠባበቂያ እህል መያዝ ነበር። ሆኖም ይህ የመጠባበቂያ ክምችት ትኩረት ተሰጥቶት መጠኑና ዓይነቱ ታውቆና ተለይቶ አልተከማቸም። ከዚህም የተነሳ ክምችት በመያዝ ለሚደርስበት ተጨማሪ ወጪ የሚያካክስበት ሁኔታም አልተገለጸም። በዚህ ሁኔታ ድርጅቱ ትኩረት ሰጥቶ የተንቀሳቀሰው ለሸማቹ እህል በማቅረብ ገበያውን ለማረጋጋት የሚያስችል የንግድ ሥራ ላይ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ አሳሳቢ የምግብ እጥረት ሲደርስ እገዛ ማድረጉ አልቀረም። በ1976/77 ዓ.ም. በደረሰው ድርቅ የተከሰተውን ረሃብ ለመቋቋም በተደረገው ጥረት ከለጋሾቹ ቃል የተገባለት እህል አገር እስኪገባ ድረስ 80,000 ቶን እህል በማበደር ጠቃሚ ድጋፍ አድርጓል።

ከአቅምና ከፍላጎት ጋር የተዛመደ አመርቂ የምግብ ክምችት እንዲኖረን የምግቦቹን አይነት ዝርዝር በጥናት ማዘጋጀት ያስፈልግ ነበር። ለክምችቱ ተግባራዊነት

ከዕርዳታ ብቻ ሳይሆን ከመንግሥትም በጀት መመደብና የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ሃላፊነታቸው ተገልጾ በሕግ እንዲያውቁት በማድረግ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እንዲመደቡ መደረግ ነበረበት።

በምግብ ዕርዳታ በኩል አቅም ያለው ሁሉ ሠርቶ ምግብም ሆነ ገንዘብ እንዲከፈለው እንጂ ምግብ በነፃ እንዳይሰጥ ቀደም ብሎ የተወሰነ ቢሆንም በሚገባ ተግባራዊ አልሆነም። ስለዚህ ከሕፃናት፣ ከአረጋውያንና አካለ ጎደሎ ሆነው መሥራት ከማይችሉት በስተቀር፣ ለሌሎች ምግብ በነፃ እንዳይሰጥ መደረጉ ሙሉ በሙሉ መረጋገጥ አልቻለም።

**የማስተባበር ተግባር**

በአገር አቀፍ ደረጃ ያለው አማካሪ ጉባዔ በጥሩ ሁኔታ ቢሠራም፣ አልፎ አልፎ የክፍለ ሀገር ባለሥልጣናትና የአውራጃ ኃላፊዎች ከተሰጠው መመሪያ ውጭ ጣልቃ በመግባት የዕማማኮን ሠራተኞች ውጥረት ውስጥ ይከቷቸው ነበር።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚያስተባብረው ክርስቲያን የእርዳታና የልማት ሥራ ድርጅት በረሀብ የተጠቃውን ህዝብ በማቋቋም በኩል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የረሃቡ ችግር በአስር ጠቅላይ ግዛት ተስፋፍቶ የነበረ ቢሆንም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመገናኛ ብዙሃንን ዜና ብቻ እየሰሙ ወሎና ትግራይ ብቻ ይሄዱ ስለነበረ፣ በየሳምንቱ አንድ የመመካከሪያ ስብሰባ ኮሚሽነሩ ይጠራ ስለነበረ፣ እዚያ ስብሰባ ላይ ችግሩ ስለተነገረ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየወሩ የሚወያዩበትና ሥራቸውን የሚያስተባብሩበት መድረክ እንዲያቋቁሙ ስምምነት ላይ ተደረሰና ኮሚሽነሩም ጭምር የሚገኝበት፣ የመያዶች መድረክ ተፈጠረ። ሲጀመር አብዛኞቹ የእምነት ነክ ድርጅቶች ስለነበሩ የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት (Christian Relief and Development Association) ይባል ነበር። አሁንም የሚጠራው በዚሁ ስሙ ነው።

**ኢማማኮ ከተባባሪ ድርጅቶች ጋር የሠራው የመልሶ ማቋቋም ተግባር**

የአገራችን መሠረታዊ ችግር በልማት ያለመጎልበት መሆኑ የታወቀ ነው። ከዚህም የተነሳ ዝናብ ባጠረ ቁጥር ረሃብ ይከሰታል። ገበሬውም ሆነ አርብቶ አደሩ እኩል ሽማችና እርዳታ ፈላጊ ይሆናል። የመጀመሪያው የመልሶ ማቋቋም እርምጃ የእርሻ በሬ ወይም የእጅ መሣሪያ መስጠት ነበር። በድርቅ የተጎዳው የወሎ ክፍለ ሀገር ውስጥ 344,393 አባወራዎች የሚያርሱት 172,196 ሄክታር መሬት ነበራቸው። ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ጥማድ በሬ ለመስጠት አቅም ስላልነበረ፣ አቀናጅተው እንዲያርሱ ለሁለት ቤተሰብ አንድ በሬ ለመስጠት ታቅዶ፣ የሚፈለገውን 106,861 የእርሻ በሬዎች ለመግዛት የሚያስፈልገው 37,401,550 ብር ነበር። ለሚታረሰውም

**መሬት የሚያስፈልገው 39,596.53 ኩንታል ዘርም ለሕዝብ ታደለ፡፡**

**በ1980 ዓ.ም ለልማት የተገኘው የእርዳታ ገንዘብ ሃምሳ ሚሊዮን ሲሆን 60 ከመቶ ከመያዶች፣37 ከመቶ ከመንግሥታትና 3 ከመቶ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ነበር፡፡ በ1978 ዓ.ም. ከእለት ዕርዳታ የተገኘው የገንዘብ መጠን የዚሁ አሥር እጥፍ ነበር፡፡**

**ለምሳሌ ያህል በ1976/77 እና በ1977/78 የተገኘው አጠቃላይ ዕርዳታ 1,525,899,310 ብር ነበር፤ ከዚህ መሓል በመንግሥት በኩል 584,412,542 ብር ሲገኝ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የተገኘው ዕርዳታ 941,486,768 ብር ሲሆን ከመንግስት ከተሰጠው ብር 35,774,226 ብልጫ ነበረው፡፡ ለዘላቂ ልማት የሚያገለግለው ዕርዳታ ለዕለት ደራሽ የዋለውን የዕርዳታ መጠን ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፡-**

ሠንጠረዥ 3፣ በዕማማኮና መንግሥታዊ ባልሆኑ

ድርጅቶች በኩል የተሠራጨ ዕርዳታ

| የዕርዳታው ዓይነት | መለኪያ | በመንግሥት በኩል የተሰጠ ዕርዳታ | | መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የተሰጠ ዕርዳታ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የቁጥሩመጠን | በብር | መጠን | በብር ሲተመን |
| እህል | በኩንታል | 9,311,780 | 383,719,480 | 8,585,550 | 452,160,492 |
| አልሚ ምግብ | በኩንታል | 598,800 | 62,770,011 | 2,089,900 | 270,280,343 |
| መኪና (የጭነት) | በቁጥር | 1,177 | 61,230,210 | 598 | 46,341,319 |
| የመኪና ተሳቢ | በቁጥር | 294 | 8,554,668 | 262 | 6,348,016 |
| ተሽከርካሪ | በቁጥር | 99 | 1,945,819 | 871 | 18,568,898 |
| መለዋወጫ ዕቃ | በቁጥር | | 8,985,080 | | 24,046,862 |
| የሕክምና መሣሪያ | በቁጥር | | 18,332,457 | | 17,479,722 |
| አልባሳት | በቁጥር | | 6,545,489 | | 36,927,879 |
| የእርሻ መሣሪያዎች | በቁጥር | | 114,316,863 | | 22,414,427 |
| የቤት ቁሳቁስ | በቁጥር | | 4,976,420 | | 2,906,304 |
| የግንባታ መሣሪያዎች | በቁጥር | | 11,429,437 | | 20,439,522 |
| ሌሎች | በቁጥር | | 1,606,608 | | 13,572,984 |
| ድምር | | | **684,412,542** | - | **941,486,768** |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ለጤና መሣሪያ መግዣ የዋለው በድምሩ ብር 35,812,179 የጤና አገልግሎት ለማሻሻል የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል:: ለጭነት መኪና፣ ለተሳቢ እና ለመለዋወጫ ዕቃዎች የተገኘው ዕርዳታ (ብር 160,703,110) በትራንስፖርት በኩል ያለውን አቅም በመገንባት ትልቅ ድጋፍ ነበር:: ቢሆንም አነስተኛ የመኪና ብዛት ለነበራቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለመለዋወጫ የተሰጣቸው ብር (24,046,862) ለዕማማኮ ከተሰጠው ብር (8,985,080) በ 15,061,782 ብር መብለጡ ያስተዛዝባል:: በተጨማሪም ለአነስተኛ ተሽከርካሪዎች በመያድ በኩል የተሰጠው ዕርዳታ ለመንግሥት ከተሰጠው ብር 16,623,079 መብለጡ ሌላው አጠያያቂ ሁኔታ ነው::

በዕርሻ መሣሪያዎች በኩል ብር 136,731,290 የሚገመት መሣሪያ መገኘቱ በእርሻ ልማት በኩል የሚደረገውን ጥረት ያጎለብት ነበር:: ስለዚህ ምንም እንኳን ለዘላቂ ልማት የነበረው ድጋፍ ከጊዜያዊ ዕርዳታ አኳያ ሲተያይ አነስተኛ ቢሆንም የበኩሉን የልማት አቅም ግንባታ አድርጓል::

### የመልሶ ማቋቋምና ራስን የመቻል እንቅስቃሴዎች

ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የእርሻ ልማት ሁኔታ በአይነትና በመጠን ተሻሽሎ በምግብ ራስ ካልተቻለ የማንወጣው አዙሪት ውስጥ እንገባለን:: በወቅቱ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረችው የኤርትራ፣ እንዲሁም የትግራይ፣ የወሎ፣ የጎንደርና የሰሜን ሸዋ ደን የተራቆተ ስለነበረ አፈሩ በሚያስደነግጥ መጠን እየታጠበ ነበር::

በወቅቱ ከዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ጋር የተደረገው ጥናት የሚከተለውን ሁኔታ ያሳያል:- ከሕዝባችን 85 በመቶ በተራራማዎች አካባቢ መኖሩን፣95 በመቶ የእርሻ መሬትና ከከብት ሃብታችን 2/3ኛው የሚገኘው በእዚሁ በደጋማ አካባቢ መሆኑንና ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴአችን 90 በመቶው ያህሉን ደጋሬ ክፍል ይኸው ደጋማ አካባቢ መሆኑ ነው:: ከደጋፊው 270,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ግማሹ አፈሩ የታጠበ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 20,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ያህሉ እህል ማብቀል የማይችል ነው:: ከዚህም የተነሳ 10,000,000 ገበሬዎች የሚያርሱት መሬት አልነበራቸውም:: ከጠቅላላው ደጋ መሬት በዓመት 1,900,000,000 ቶን ያህል አፈር እየታጠበ ሲሄድ ከታረሰው ክፍል ደግሞ 100,000 ቶን አፈር በዓመት ተጠርጎ ይሄዳል:: ይህን ሁኔታ የሚያባብሰው ደግሞ በፍጥነት እየጨመረ የሚሄደው የሕዝብ ቁጥር ነው::

በመልሶ ማቋቋም መርሃ ግብር በስፋት የተሠራው ለገበሬው የሠፈራ ሥራ፣ ለአርብቶ አደሩ ደግሞ ከብቱን የሚያግጠው መኖና ለከብት መጠጥ ያለውን ውሃ ማመቻቸት ነበር::

**ለአርብቶ አደሩ የመልሶ መቋቋም ተግባር**

ለአርብቶ አደሩ ከብቱ ሲያልቅ የርቢ ከብት መስጠትና የእንስሳት ጤንነት እንዲጠበቅ ክትባትና ሕክምና ማካሄድ ትልቁ ተግባር ነበር። በተለይ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብ በቦረና፣ በደቡብ ምሥራቅ (በኦጋዴን) የነበሩት የከብት ዕርባታ ፕሮጀክቶችን የሚያግዝ ዕርዳታ ተሰብስቦ አርብቶ አደሮች የኑሮ ዋስትና እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል። በአሊደጌ (አፋር ውስጥ) የመስኖ ግጦሽ ሙከራ፣ በአሬሮና በተልተሌ የውሃ ግድብ በአመቺ ቦታዎች በመሥራት የነበሩ ጅምሮች እንዲቀጥሉ ተደርጓል።

በገዋኔ፣ በዱብቲና በአሳይታ አርብቶ አደሩን ለማስፈር ጥረት ተደርጓል። በኦጋዴን ከጎዴ አንስቶ በቀላፎ፣ በሙስታሂልና በብሩኩል ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች እየተከናወኑ ነበር።

**የአርሶ አደሩ የመልሶ ማቋቋም ሥራና ሠፈራ**

በዓለም ባንክ ዕርዳታ ኮሚሽኑ ባደረገው ጥናት መሠረት ከዓለም ባንክ በተገኘ 10,000,000 ዶላር የሲሪንቃን ተፋሰስ ለማልማት በ1970 ዓ.ም. ሥራ ተጀመረ። የፕሮጀክቱ ስፋት 370 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን በውስጡ ያለውም 450,000 ሕዝብ በ33 ገበሬ ማኀበራት የተደራጀ ነው። የፕሮጀክቱ ዓላማ አካባቢውን ለመለወጥና የአፈሩንም ለምነት ለማደስና የአካባቢውን ደንና ቁጥቋጦ መልሶ ለማልበስ ነበር።

የልማቱ ሥራ እቅድ 1,183,834 ዛፎች ለመትከል፣ 18,595 ቦረቦሮችን ለመድፈን ፣ በሣር የተሸፈኑ የውሃ ቦዮችን ለመሥራት፣ ሦስት ግድቦችንና አምስት ኩሬዎችን ለመገንባት፣ ሁለት የውሃ አቅጣጫ መቀየሪያ ግድቦችን ለመገንባት፣ 58 ከሎ ሜትር የመኪና የእርከን ሥራ፣ 432 ኪሎ ሜትር እርከን፣ 35 ኪሎ ሜትር መንገድ፣ 435.5 ሜትር የመስኖ ቦይ፣ 2 ኪሎ ሜትር አፈር መጠበቂያ ግምብ ለወንዙ ለመሥራትነበር።

ሌላው የተፋሰስ ልማት በምዕራብ ጀርመን ዕርዳታ የተካሄደው የቆቦ አላማጣ ልማት አካል የሆነው የጎሊና ሆርማት ተፋሰስ ነው። ጎሊና ሆርማት ተፋሰስ ላይ 3,243 ኪሎ ሜትር የሚሆን በአፈር ጥበቃ ሥራ ተሠርቷል። 2,376,285 ዛፍ ተተክሏል። እንዲሁም 12 ባዮ ጋዝ፣ 38 የተሻሻሉ የገጠር ቤቶች ናሙና፣ 53 ኪሎ ሜትር መንገድና የወንዙን ፍሰት የሚለኩ ስድስት ሃይድሮ ሜትሮች ተተክለው ነበር። በተጨማሪም ለአካባቢው ገበሬ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥልጠና ሰጥተው ነበር።

እነዚህን የመሠሉት ፕሮጀክቶች በቀጣይነት ቢሠሩና በሌሎች ሥፍራዎችም ቢደገሙ እስጊውን የአየር ንብረት ለውጥ መግታትና ማሻሻል እንደሚቻል አቅጣጫ አሳይተዋል።

**የሠፈራ መርሃ ግብር**

የሠፈራ መርሃ ግብር በስፋት የተጀመረው በ1977 ዓ.ም የሠፈራ ባለሥልጣን በአዋጅ ከዕማማኮ ጋር ከተዋሃደ በኋላ ነው። መጀመሪያ በጅባትና ሜጫ አውራጃ ሀሮሌና በደሌ በሚባሉት ቀበሌዎች ሠፈራ በስፋት የተሠራ ሲሆን በ1977 ዓ.ም. ከወሎ 300,000 ሕዝብ ለማስፈር ተወስኖ እንቅስቃሴ ተጀመረ።

ሠፈራው ሁለት ዓይነት ሲሆን አንዱ ስግሰጋ ነበር - ማለትም ባሉ ገበሬ ማኅበሮች ውስጥ ሰፋሪዎችን በትርፍ ቦታ መሰግሰግ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ድንግሉ መሬት ላይ የሚደረገው ሰፋፊ ሠፈራ ነው።

ሠንጠረዥ 4፣ የሰፋሪዎች መኖሪያዎች ክልልና የሰፈሩበት ክልል

| የክልሉ መገኛ | የሠፋሪዎች መኖሪያዎች ክልልና የሠፋሪዎች ቁጥር | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከፋ | ኢሉባቦር | ሸዋ | ወለጋ | ጎንደር | ጐጃም | **ድምር** |
| ወሎ | 44,334 | 72,226 | - | 220,636 | - | 29,820 | **367,016** |
| ሸዋ | 6,514 | 29,322 | 6,149 | 11,279 | - | 54,977 | **108,241** |
| ጐንደር | - | - | - | - | 6,387 | - | **6,387** |
| ትግራይ | 21,982 | 46,367 | - | 21,367 | - | - | **89,716** |
| ጐጃም | - | - | - | - | - | 16,425 | **16,425** |
| ድምር | 72,830 | 147,915 | 6,149 | 253,282 | 6,387 | 101,222 | **587,785** |

በ1977/78 ከወሎ 376,298 ሰዎች እንዲሰፍሩ ተደረገ። ይህም በወሎ አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር 11.2 በመቶ መሆኑ ነው። ይህ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ሕዝብ የወሰደው መንገድ ካለበትና በቀላሉ ከሚደረሱ አውራጃዎች ነው።

**ሠፋሪዎች በአውራጃ**

ከእነዚህ ሠፋሪዎች ውስጥ 59 ከመቶ የሚሆኑት የሰፈሩት ወለጋ፣ 19 ከመቶ ኢሉባቡር፣ 14 ከመቶ ከፋ እና 8 ከመቶ ጎጃም ነው።

ሠንጠረዥ 5፣ የስግሰጋ ሠፈራ በክልል

| ክልል | የገበሬ ማኅበራት ቁጥር | አባወራ | | የቤተሰብ አባል | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | |
| ወለጋ | 724 | 267 | 28 | 57 | 887 | 1,239 |
| ኢሉባቦር | 428 | 23,464 | 3,872 | 25,614 | 37,172 | 90,122 |
| ከፋ | 155 | 13,828 | 2,685 | 23,479 | 36,827 | 76,819 |
| ድምር | **1307** | | **44,144** | | **124,036** | **168,180** |

- ሠፋሪዎችን ያዋጣ ክልል 62.4 በመቶ ከሸዋ፣ 18.4 በመቶ ከትግራይ፣
- የሠፈረበት ክልል 43.1 በመቶ ኢሉባቡር፣ 25.2 በመቶ ጎጃም፣ 17.2 በመቶ ከፋ፣ 12.4 ጎንደርና ሸዋ
- በትልልቅ ሠፈራ መርሃ ግብር ሞዴል እያንዳንዱ ሰፈራ ጣቢያ አምስት መቶ ቤተሰቦችን የሚያካትት ሲሆን የመሬት ድልደላውም እንደሚከተለው ነው:-

1. 1,000 ሄክታር በጋራ የሚታረስ
2. 200 ሄክታር ለደንና ለከብት ግጦሽ
3. 50 ሄክታር ለቤት መሥሪያና ለጓሮ አትክልት

በዚህ መሠረት አንድ ሠፈራ ጣቢያ 1,250 ሄክታር መሬት ይዞታ ያለው ነበር:: ሠፈራው አገልግሎቶችን አካቶ አዋጪ እንዲሆን አምስት ሠፈራ ጣቢያዎች በአንድነት መካተት አለባቸው:: የማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የጤናና የትምህርት ተቋማት ይመሰረታሉ:: የውሃ አገልግሎት ይሠራል:: በተጨማሪም መንገድ፣ መጋዘን፣ ክሊኒክ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ የእጅ ሥራና፣ የጥገና ክፍሎች ፣ የኅብረት ሱቅና ጽሕፈት ቤቶችም ይገነባሉ::

የሠፈራ መርሃ ግብርን ለመፈጸም የሚያስፈልገው ወጪ፣ ትራንስፖርትን ሳይጨምር እንኳን፣ ከፍተኛ ነው:: ለሰፈራ የወጣው ወጪ፣ የግንባታ ሥራዎችን፣ የጤናና የትምህርት ሚኒስትሮችና የውሃ ኮሚሽን ያወጡትን ሳይጨምር፣ ብር 564.4 ሚሊዮን ነበር::

የሕዝብ ማስፈር ሥራ በአፈጻጸም ስህተት ምክንያት ብዙ ወቀሳ ያስከተለና እርዳታ ሰጭዎችም እምብዛም ያልደገፉት ሥራ ነበር:: በመሠረቱ በጥናትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሠፈራ እንዲከናወን ከተጣበበውና ብጥስጣሽ ከሆነው የመሬት ይዞታ አካባቢ ወጥቶ ሰፋ ያለ እርሻ የሚገኝበት አካባቢ ሰዎች እንዲሄዱ ዕርዳታ ሰጪዎች ቢደግፉም አሰራሩን አልወደዱትም ነበር::

ዕማማኮ ከሠፋሪው መነሻና መድረሻ ቦታ ላይ ጥናት አካሂዶ የሚከተለው ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር፡-

1. መስፈር የሚፈልጉ ቢኖሩም የሰፋሪ ምልመላ በፈቃደኝነት አለመሆኑ፣ ለወረዳው የተመደበውን ኮታ ለመሙላት በግዴታ መሆኑ፣
2. ሠፋሪው የት እንደሚሄድ በሚገባ ሳይገለጽለት፣ ንብረቱን ለመሰብሰብና ዘመድ ለመሰናበት ጊዜ ሳይሰጠው ሠፈራ ጣቢያ ገብቶ እየተጠበቀ መቆየቱ፣
3. የሠፋሪ ምልመላ ምዝገባና የጉዞ ክንውኑም መልክ ያለው ስላልነበረ የቤተሰብ መለያየትና ልጆችና ወላጆች ተለያይተው ጠባቂ የሌላቸው ሕፃናት ሠፈራ ጣቢያ መገኘት፣
4. ከጉዞ በፊት ሰፋሪው እሚሰባሰብበት ጣቢያ የመጸዳጃ ሥፍራና፣ የሕክምና አገልግሎት አለመመቻቸት በፈጠረው ችግር በሽታና ሞት መከሰቱ በጉዞ ላይም የነበሩ ማረፊያ ጣቢያዎች ህመምተኞችንና የሚጠቡ ሕፃናትን ለማስተናገድ ዝግጅት አለመኖሩ፣
5. የሰፋሪው የወትሮ መኖሪያው አካባቢ ያለው አየር ንብረት ከሠፈረበት ልዩ በመሆኑ የተነሳ ሕመምተኛ መብዛቱ፣
6. የሰፈሩበት ቦታ በቂ የእርሻ መሬት አለመኖርና የመጠጥ ውሃ ባለመኖሩ ቤት አፍርሶ ሌላ ቦታ መጓጓዝ መኖሩ፣
7. ለእርሻ የሚያስፈልገው ዘርና መሣሪያ በወቅቱ ባለመቅረቡ የእርሻ ጊዜ መተጓጎሉ፣
8. የግል ይዞታ የለመዱ ገበሬዎች የኔ ነው የሚሉት ይዞታ አለመኖሩና ለጓሮ አትክልት የሚሰጠውም ተለይቶ አለመታወቁ፣ የግድየለሽነት ስሜት መፍጠሩና ለማምረት ያለው ፍላጎት መጥፋቱ... የመሳሰሉት ይገኝበታል፡፡

ከሰፈራ ቦታ ጠፍተው የሄዱትም ተጠይቀው የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው፡-

1. 30 ከመቶ የሚሆነው ሠፋሪ ሠፈራ የተላከው በግድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ቢሆንም በተራ ቁጥር ሦስት ካለው ጋር ሲተያይ አነስተኛ ይመስላል፡፡
2. ከሠፈሩበት ክልል ቀድሞ ወደነበሩበት ለጉብኝት እንኳን መሄድ አለመፍቀድና፣ ሠፈራው ባይስማማቸው ቀድሞ ወደነበሩበት ለመመለስ አለመቻሉ፣
3. 75 በመቶው ከቤተሰባቸው በመለየታቸው መሆኑን ይገልፃሉ (ይኼ ትንሽ የተጋነነ ይመስላል)፣
4. 67 በመቶው የተገባላቸው ቃል አለመፈጸሙን ገልጸዋል፤
5. የቤተ አምልኮ አለመኖርና የለመዱት የባሕል እና የኃይማኖት በአላት መዘንጋት፣

6. ሠፋሪዎች ስለሚሄዱበት አካባቢ መረጃ አለማግኘትና ካሉት የሠፈራ ጣቢያዎች መሐል የሚፈልጉትን መምረጥ አለመቻላቸው፡፡

ከአሁን ቀደም ሰዎች በፍላጎታቸው ካሉበት ወደ ሌላ እየሄዱ ደን መንጥረው ጎጆ ሠርተው በራሳቸው ይሰፍሩ ነበር፡፡ አሁን ግን ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ፣ በ1977 ብር 89,344,586፣ በ1978 ደግሞ ብር 106,080,499 ወጥቶ በምግብ፣ በቁሳቁስ፣ በርሻ መሣሪያ ታግዞም፣ ሠፈራን እየለቀቀ ይሄዳል፡፡ በ1977 ከነበረው ሰፋሪ፣ በ1981 ያለው ሰፋሪ ቁጥር በ100,000 ቀንሷል፡፡

**ዕማማኮ ያስጠናው የወሎና የትግራይ ፕሮጀክት ጥናቶች ግምገማ**

ዕማማኮ ከዓለም ባንክ ባገኘው ዕርዳታ በተደረገው የኘሮጀክቶች ግምገማ ወቅት ቀደም ሲል የተጠኑ ጥናቶችን በመመርመርና ተጨማሪ የኘሮጀክት ሃሳቦችን በማቅረብ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲሠሩ የቀረቡት ፕሮጀክቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የሥሪንቃ ተፋሰስ ጥበቃ፣
2. የማዕከላዊ ትግራይ ልማት የመሬትና የውሃ ሃብት ጥበቃ ጥናት በእንግሊዝ ዕርዳታ የሀንቲንግስ አማካሪ ቡድን (Huntings Consultants) ያጠናው፣
3. የታችኛው አዲያቦ ኘሮጀክት (በትግራይ) ከደጋው 12,000 ገበሬዎች ለማስፈር በዓለም ባንክ እርዳታ የተደረገ ጥናት፣
4. የወሎና የትግራይ ውሃ ልማት መሪ ዕቅድ፣
5. የወሎና የትግራይ የገጠር መንገዶች ሥራ መሪ እቅድ፡፡

**ሌሎች የአፈርና የውሃ ጥበቃና ልማት እቅዶች**

ከሌሎች ጥናቶች መሐከል በሥራ ቢውሉ በምግብ ራስን ለመቻል ያግዛሉ ተብለው ዕማማኮ ከሚከታተላቸው መሃከል፡-

1. በስግሪያ የተጠናው የዴዴሳ ልማትና አፈር ጥበቃ 500,000 ሄክታር የሚሸፍን፣
2. የጎዴ መስኖ እርሻ ቀደም ሲል በጃንሆይ ጊዜ በፈረንሳዩ ኩባንያ በሲኤም የተጠና፣
3. በአዋሽ ሸለቆ በግል ኩባንያዎች ይታረሱ የነበሩ መሬቶች ሲወረሱ በግብርና ሚኒስቴር ለሚታረሰውና አፋር አርብቶ አደር እንዲሠፍርበት የተደረገው ልማት፣
4. በፓዊ (መተከል) የተጀመሩት የሠፈራና የልማት ሥራዎች ይገኙ በታል፡፡

**የዕርዳታና የመልሶ ማቋቋም ሥራ ተዛምዶ**

የገጠር መሠረተ ልማት ቢዘረጋ፣ መብራትና ውሃ በገጠር እንዲገኝ ቢደረግ፣ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በሚገባ ቢደራጅና ዘመናዊ የምርት ስልትን ቢከተል፣ ዝናብ ባጠረ ቁጥር ረሃብን አያስከትልም ነበር በሚል መነሻ የዕርዳታ ማስተባበሪያን ተቋም ለማሻሻል ጥናት ተደርጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች፣ ማለትም ከፕላን ሚኒስቴር፣ ከዕማማኮ፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከውሃ ኮሚሽን፣ ከደን ልማት ባለሥልጣን የተውጣጣ ቡድን በእኔ መሪነት ሕንድና ቻይናን እንዲጎበኝ ታቅዶ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ሕንድ የሚሄደውን ቡድን መርቼ በመሄድ ከመንግሥት ባለሥልጣናት፣ በመስክ ከሚሠሩ በሳል ባለሙያዎችና ከገበሬዎች ጋር ውይይት አካሂደን መጥተናል፡፡ እኔ በሌላ አስቸኳይ ሥራ ምክንያት ባልሄድም፣ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ቻይና ሄደው ተመሳሳይ ተግባር ፈጽመው ከመጡ በኋላ፣ ለመንግሥት ሪፖርት ቀርቧል፡፡ በሪፖርቱም መሠረት ምኒስትሮች፣ ባለሙያዎች፣ መያዶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚገኙበት ስብሰባ ተደርጎ ከቻይናና ከሕንድ ምኒስትሮችና እንደ ዶ/ር ሰዋሚታን ያሉ ታዋቂ ባለሙያዎችም ሃሳብ ያቀረቡበት ውይይት ተደርጓል፡፡

በስብሰባው ውሳኔ መሠረትም የተባበሩት መንግሥታት የልማት ኘሮግራም አንድ በሳል ሕንዳዊ ባለሙያ በማቅረብ ደምብና ረቂቅ ሕግ እንዲያዘጋጅ ሆነ፡፡ ከዚህ በኋላ የመንግሥት ለውጥ ሆኖ ኢሕአድግ ሲመጣ፣ የዚህን ረቂቅ የተወሰኑትን በመመሪያ መልክ አውጥቶ፣ የቀድሞውን አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፸ ዓ.ም. ለውጦ፣ ቀድሞ የነበሩትን ኃላፊነቶች ቀንሶ፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንን አቋቁሞ፣ ኮሚሽነሩ ከዘጠኙ አካላት አንዱ ሆኖ፣ መንግሥት የሚሾመው ሊቀመንበር ያለው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ኮሚቴ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፹፯ ዓ.ም መቋቋሙን አሳውቋል፡፡

## ማጠቃለያ

የእርዳታ ማስተባበሪያ ሥራዬን በጀመርኩበት ዓመት የዓለም የምግብ ጉባዔ ሮም ላይ ተጠርቶ የድርቅና የረሃብ አሳሳቢነትን፣ ይልቁንም በሳህልና በኢትዮጵያ የደረሰውን የሰውና የከብት ዕልቂትን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የዓለም የምግብ ምክር ቤት የሚባል አዲስ ተቋም እንዲቋቋም ውሳኔ አሳለፈ፡፡ በዚህ ጉባዔ ላይ በወቅቱ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄኒሪ ኪሲንገር ከአሥር ዓመት በኋላ አንድም ልጅ እንደራበው ወደ መኝታው አይሄድም ብለው ነበር፡፡ ዛሬ ከሦስት አሠርት ዓመታት በኋላ፣ ልጆች እንደተራቡ ወደ መኝታቸው መሔድ ብቻ ሳይሆን፣ በረሃብ የሚሞቱትም ቁጥር ጨምሯል፡፡

ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ለመቻል በግድ በዝናብ ላይ ብቻ ከሚተማመን እርሻ

መላቀቅ አለብን፣ በማለት በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተደረጉ በአሜሪካ ቢሮ ኦፍ ሬክላማሽን ባለሙያዎችና በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የተጠኑ የአባይ ተፋሰስ፣ የግቤ፣ የኦሞና የዋቢ ሸበሌ ጥናቶች ሥራ ላይ አልዋሉም:: የተጀመሩ የልማት ሥራዎችም ሲቆሙ ሌሎች ደግሞ ሳይጀመሩ በእቅድ ብቻ ቀሩ:: እንደባለሙያዎች አስተያየት፣ በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት 5% ብቻ ሲሆን የለማው፣ ከውሃ ልናመነጭ ከምንችለው የመብራት ኃይል ደግሞ 2% ብቻ ነበር ማምረት የተቻለው::[6] ይህን የተፈጥሮ ሀብታችንን ተግባራዊ ለማድረግ የዓለም ባንክና ሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች፣ በተለይ በዓባይ ተፋሰስ የሚጠቀሙ አገሮችን ይጎዳል በሚል ሰበብ፣ ለመተባበር ዘገምተኛ ነበሩ:: ስለዚህ ዓባይን በጭልፋ አይቻልም:: የተባለውን አባባል ለውጠን አባይን በጭልፋ መቻሉን በገባር ወንዞቹ ላይ ባለን አቅም ሥራ በመጀመር በምግብ እራስን የመቻል ጉዞአችንን መጀመር አለብን::

ለዚህም መልካም ውጤት ሕዝቡ፣ ባለሙያውና መንግሥት መደማመጥና መናበብ መቻል አለባቸው:: መንግሥት ሕዝብን ካላዳመጠ፣ ለልማት የሚያመቹ የአስተዳደርና የሕግ ሥርዓቶች ካልተዘረጉና በሥራ ላይ ካልዋሉ ያሰብነው አይደርስም:: በየስብሰባው የሚነሱትን በጎ ሃሳቦችና ውሳኔዎችን ለመተግበር ጥሩ አስተዳደር፣ ግልፅነትና ለሕዝብ ተጠያቂነት በአስተማማኝ ሁኔታ ካልተረጋገጠ ከፍሬ ለመድረስ ያስቸግራል::

የአገራችን አንዱ ትልቅ ችግር የመንግሥት ለውጥ የመጣው፣ በምርጫ ሳይሆን በኃይል ስለሆነ፣ የተተኪው መንግሥት ትኩረት መቀመጫውን ለማደላደል ሲል ያለፈውን መንግሥት በመኮነን፣ የራሱን ሥራ አጉልቶ ለማሳየት በሚያደርገው ጥረት ኃይሉን መጨረሱ ነው:: ከዚህም የተነሳ ቀድሞ የተሠራው በጎ ሥራ ላይ መገንባት የለም፤ የተጀመረውንም አይጨርስም:: እንዲያውም ከእነአካቴው፣ የፊተኛው መንግሥት ላይ ያየውንና የኮነነውን ነውር መድገሙ ነው::

በ1966 ዕማማኮ ሲቋቋም የነበረው የፍትሃዊነትና የአስተማማኝ የመሬት ይዞታ ጉዳይ ዛሬም አልተፈታም፤ ዛሬም እያከራከረ ነው:: በእውነት በምግብ እራሳችንን ለመቻል ከፈለግን የተጠናውን ጥናት በመረጃ ላይ በተመረኰዘ ቅደም ተከተል መሥራት፣ የተጀመሩና በሥራ ላይ የነበሩትን ደግሞ መጨረስና ውጤት እንዲያስገኙ ማድረግ፣ የሁላችንም አገራዊ ግዴታና ኃላፊነት ነው::

[6] ይህ አሀዝ በአሁኑ ጊዜ እጅግ በጣም ተቀይሯል::

# በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት

*ጠና አበረ*

## *መግቢያ*

ዛሬ በዓለም ላይ ያለው የጤና አገልግሎት ሲታይ በጣም የተዛባ ነው፡፡ የበለጸጉ አገሮች፣ በተለይም ተላላፊ በሽታዎችንና ሌሎችንም የጤና ጠንቆችን በቁጥጥር ስር በማዋል፣ የሕዝባቸውን ጤንነት በመጠበቅ፣ የኑሮ ደረጃውን በይበልጥ እያሻሻሉ ናቸው፡፡ በመልማት ላይ ያሉ የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች ግን፣ ካለባቸው የድህነት ጫና በተጨማሪ፣ ለበርካታ ተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ በመሆናቸው፣ የኑሮ ደረጃቸው በየጊዜው እያሽቆለቆለ ይገኛል፡፡ በዚህ ሳቢያ ነፍሰጡሯ ሳትገላገል፣ ጨቅላው ሳያድግ፣ ወጣቱ ሳይጐለምስ፣ ጐልማሳው ሳይሸመግል፣ እንደቅጠል እየረገፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በታዳጊው ክፍለ ዓለም ከሚገኙት የጤና ጠንቆች መካከል የወባ በሽታ አንጋፋና በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው፡፡

### የወባ በሽታ መሠረታዊ ዕውነታዎች

ወባ በቀይ ደም ወይም በጉበት ውስጥ በጥገኝነት በሚኖሩ፣ በሚያድጉና በሚራቡ፣ በአጉሊ መነፅር (ማይክሮስኮፕ) ካልሆነ በስተቀር በዓይን የማይታዩ እና በእጅ የማይዳሰሱ፣ ኘላስሞድየም በመባል በሚታወቁ ረቂቅ ተህዋስያን አማካይነት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ የወባ በሽታ በአንዳንድ አካባቢዎች ንዳድ በመባል ይታወቃል፡፡ በተፈጥሮ በሰው አካል ውስጥ በመራባትና በማደግ ለበሽታው የሚያጋልጡት አራት የወባ ተህዋስያን ዝርያዎች ናቸው፡፡ እነሱም፡- ፕላስሞዲየም ፋልሲፓረም፣ ፕላስሞዲየም ቫይቫክስ፣ፕላስሞዲየም ማላሪዬ እና ኘላስሞዲየም ኦቫሌ ይባላሉ፡፡ ከነዚሁ የወባ ተህዋስያን ዝርያዎች መካከል በሃገራችን በዋናነት በህብረተሰቡ ላይ ጥቃት የሚያደርሱት ኘላስሞዲየም ፋልሲፓረምና ኘላስሞዲየም ቫይቫክስ የሚባሉት ናቸው፡፡

ተህዋስያኑ ያላቸው ቅርጽ፣ እድገት፣ የትውልድ ብዛት፣ ለመራባት የሚወስዱት የጊዜ ፍጆታ፣ የበሽታው የጥቃት መጠን፣ በሰው ላይ የሚያሳዩት የግርሻ አይነትና ወቅት፣ በመድኃኒቶች የመጠቃት ዝንባሌ፣ በአካል ውስጥ የሚያደርሱት የጉዳት ዓይነት፣ የተለያየ ነው፡፡

የወባ በሽታ የሚያስከትላቸው የጤና ጠንቆች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የቀይ ደም ህዋሳትን በማጥቃት፣ ለደም ማነስ የሚያጋልጥ ሲሆን፣ የአእምሮ መዳከም፣ ለጉበትና ለኩላሊት መታወክ፣ እና በአጠቃላይ ለአካል ጉስቁልናና ለሞት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በተለይም ፕላስሞዲየም ፋልሲፓረም የተባለው የወባ ዝርያ፣ በወቅቱ ተገቢው ሕክምና ካልተሰጠ በስተቀር፣ ለሞት አደጋ

ያጋልጣል:: የወባ በሽታ፣ በተለይ ነፍሰጡር ሴቶችንና እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን፣ በይበልጥ የሚያጠቃ ሲሆን፣ በቀላሉ ለአካል ጉስቁልናና ለሞት አደጋ ጭምር ያጋልጣል:: በተለይም አሁን ኤች አይ ቪ ኤድስ እየተስፋፋ በሄደበት ወቅትና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እየተጠናከረ በሚታይበት ጊዜ፣ እንዲሁም ከፍተኛ የምግብ ማነስና ያለመመጣጠን ችግር በሚታይበት ሁኔታ፣ የወባ በሽታ ከምንግዜውም የበለጠ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት አደጋ ሊያጋልጥ እንደሚችል የጥናት መረጃዎች ይጠቁማሉ::

**የወባ በሽታ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች**

- በሽተኛው ህመም ሲጀምረው ብርድ ብርድ የማለትና የማንቀጥቀጥ ስሜት ይከሰታል፣
- ጥርስ ማፋጨትና የሰውነት መወራጨት፣
- ጥቂት ቆይቶ የትኩሳትና የላብ መከሰት፣
- የምግብ ፍላጐት ያለመኖርና ቢመገቡም ማስመለስ፣
- ራስ ምታትና ውሃ ጥማት፣
- በጀርባና በአካል መገጣጠሚያዎች የቁርጥማት ስሜት መኖርና የመሳሰሉት ናቸው::

የወባ በሽታ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች የወባ ተህዋስያን በቀይ ደም ህዋሳት ውስጥ የሚያደርጉትን የዕድገትና የመራባት ኡደት ከጨረሱ በኂላ በመጨረሻ ከቀይ ደም ህዋሳት ውሰጥ በመውጣትና በመሰራጨት ሌሎች ጤነኛ የደም ህዋሳትን በሚያጠቁበት ጊዜ የሚከሰቱ ናቸው:: አንድ ሰው በወባ በሽታ በሚያዝበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ተመርምሮ አስፈላጊውን ሕክምና ካላገኘ በስተቀር፣ እንደወባው ዝርያ የሚለያይ ቢሆንም፣ በየሁለትና ሶስት ቀናት ያገረሻል:: የወባ በሽታ በደም ህዋሳት ላይ በሚያደርሰው ጥቃት ከሚከሰቱት ምልክቶች በተጨማሪ :-

- ደም ማነስ
- መገርጣት
- ክብደት መቀነስ
- የጣፊያ እብጠት እና የመሳሰሉት አዘወትረው የሚታዩ ምልክቶች ናቸው::

**የወባ በሽታ የመተላለፊያ መንገድ**

በአገራችን ከግንዛቤ ማነስና ከእምነት መዛባት የተነሣ የወባ በሽታ የበቆሎ አገዳና እሸት በመብላት እንደሚተላለፍ በአንዳንድ ቦታ ይታመናል:: ሆኖም ለዚህ ግምት መነሻው የበቆሎ አበባ በትንኝ መራቢያ ቦታዎች ላይ በሚረግፍበት ጊዜ ዕጮች በምግብነት ስለሚጠቀሙበትና የትንኝ ብዛት ስለሚጨምር ነው::

የወባ በሽታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፈው አነፎለስ በመባል በምትታወቀው እንስት የወባ አስተላላፊ ትንኝ አማካኝነት ብቻ ነው:: ትንኞች ሁሉ የወባ በሽታን የማያስተላለፉ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፣ የወባ በሽታ አስተላላፊ የሆነችው ትንኝ የምትጥለውን እንቁላል ለማዳበር ደም መመገብ ስለሚያስፈልጋት፣ በአጋጣሚ የወባ በሽታ ያለበትን ግለሰብ ደም ስትመጥ፣ በደሙ ውስጥ የሚገኙት የወባ በሽታ ተህዋስያን በትንኟ ሆድ ውስጥ ከ10-12 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በማደግ ቅርፃቸውን በመለዋወጥ ይራባሉ:: ከዚያም በኋላ፣ ትንኟ እንደገና ደም ለመመገብ ጤነኛን ሰው ስትነክስ፣ የምትመጠው ደም እንዳይጓጉል (እንዳይረጋ) በመጀመሪያ ምራቋን በምትረጭበት ጊዜ፣ ጥገኛ ተህዋስያኑም ከትንኟ የምራቅ ዕጢ ውስጥ ተቀላቅለው ከበሽተኛው ወደ ጤነኛ ው ሰው ይተላለፋሉ::

በጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ትንኟ ጥገኛ ተህዋስያኑን ስትተፋ ወዲያውኑ ህመም አይሰማም:: ህመምተኛው ምንም ዓይነት ስሜት ሳይሰማው የተለመደ ተግባሩን እያከናወነ ከ10-14 ቀናት ደህና ሆኖ ሊሰነብት ይችላል:: በነዚህ ቀናት ውስጥ በጉበቱ ውስጥ ተህዋስያኑ ገብተው ይራባሉ:: ተህዋስያኑ እድገታቸውን ጨርሰው ከጉበት ውስጥ በመውጣት ወደ ደም ቧንቧ በመሠራጨት ቀይ የደም ህዋሳትን ይወራሉ:: ይህም ክስተት በአራቱም የወባ ዝርያዎች የተለያየ ጊዜና ባህርይ ይኖረዋል:: ይህም የወባ በሽታ የመደላደያ ጊዜ ይባላል::

የወባ አስተላላፊ ትንኝ የምትራባው፣ በአብዛኛው ከዝናብ ወራት በኋላ በየአካባቢው ተጠራቅሞ በሚቆይ ውሃ ውስጥ ነው:: እንቁላሎቹ በውሃው ላይ ወደ እጭ ከተለወጡ በኋላ፣ እድገታቸውን ሲጨርሱ፣ ትንኞች በመሆን ከውሃው ላይ በረው ይሄዳሉ:: የወባ ትንኝ ከመራቢያው ቦታ እስከ ሁለት ኪ.ሜ በመብረር ሰውን ለመንደፍ ትችላለች:: የወባ ትንኝ ደም ለመመገብ የምትንቀሳቀሰው በምሽትና በሌሊት ወቅት ብቻ ነው::

**የወባ በሽታ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች**

የወባ በሽታ አስተላላፊ ትንኞች የሚራቡት በውሃ ውስጥ በመሆኑ፣ በሰዎች መኖሪያ አቅራቢያ የሚገኙትንና በጊዜያዊነት የሚፈጠሩትን የውሃ ኩሬዎች የአካባቢ ቁጥጥር በማድረግ ማድረቅ ወይም ማዳፈን፣ ወይም ያቆረ ውሃ ካለ ቦይ በመቅደድ ማፋሰስ ይቻላል:: ትንኞች እንዳይራቡ ለማድረግ የአካባቢ ቁጥጥር በሚደረግበት ጊዜ፣ የትንኞች መፈልፈያ የሆኑና አገልግሎት የማይሰጡ ሰው ሰራሽና የተጠፈጥሮ ጉድጓዶችን መሙላትና ማስተካከል፣ ረግረጋማ ቦታዎችን ቦይ በመቅደድ ውሃውን ማፋሰስ፣ ውሃ የሚመጡ እንደ ባህር ዛፍ የመሳሰሉ ተክሎችን መትከል፣ በደረቃማ ወራት የተቆራረጡና ኩሬ የፈጠሩ ወንዞችን በመጥረግ በፍጥነት እንዲፈሱ ማድረግ፣ የመስኖ አርጅኖችን መጥረግና ውስጣቸው የበቀሉ ሳሮችን ማጨድና ውሃውን ማፋሰስ፣ በቤት ውስጥና ውጭ የሚገኙ ውሃ የሚያቁቱ እንስራዎችን፣ በርሜሎችን፣ ቢርካዎችንና ጉድጓዶችን መክደን፣ በቤቶች ዙሪያ የተጣሉ አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ውሃ አቁረው የሚይዙ ሰባራ ቁሳቁሶችን ማስወገድ ያስፈልጋል::

ሌላው የመከላከያ እርምጃ ደግሞ፣ ሰፋፊ የውሃ ኩሬዎች ውስጥ የሚያድጉ እጮችን ለመግደል፣ የወባ ባለሙያዎችን በማማከር፣ የጸረ እጭ ኬሚካሎችን መርጨትና የተቃጠለ ዘይት በውሃ ላይ በማፍሰስ እጮቹ ታፍነው እንዲሞቱ ማድረግ ነው:: ይሁን እና ሊወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄና ሊያደርስ ስለሚችለው ጉዳት ምንጊዜም ቢሆን የባለሙያ ምክር መጠየቅ ወሳኝነት አለው::

የወባ ትንኝን ለመከላከል ዋንኛው ዘዴ የጸረ ትንኝ ኬሚካል (ዲዲቲ) መርጨት ስለሆነ፣ ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤቶችን ለመርጨት በሚመጡበት ጊዜ ነዋሪዎች ሁሉ በፈቃደኛነት ቤታቸውን ማስረጨት ይጠበቅባቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ በነፍስ ወከፍ ወይም በቤተሰብ ደረጃ በመድኃኒት የተነከረ የትንኝ መከላከያ አጐበር በአግባቡ መጠቀም ሌላው አማራጭ ነው:: ይሁን እንጂ ስለወባ ትንኝ መከላከያ አጐበር አጠቃቀም ከጤና ባለሙያዎች ተገቢውን ምክር ማግኘትና አዘውትሮ ተግባራዊ ማድረግ ይመረጣል:: ከሁሉም በላይ አንድ ሰው ወባማ በሆነ አካባቢ በሚታመምበት ጊዜ በፍጥነት በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጤና ድርጅት ወስዶ ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል::

## የወባ በሽታ የሥርጭት ሁኔታ

### የወባ በሽታ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ

የወባ በሽታ በሃገራችን ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎችም ክፍላተ አህጉር ተሰራጭቶ የሚገኝ በሽታ ነው:: ለምሳሌ፣ በአማካይ 107 አገሮችና አጎራባቾቻቸው ወባማ ናቸው:: 40% (2.4 ቢሊዮን) የሚሆነው የዓለም ህዝብ ለወባ በሽታ የተጋለጠ ነው፤ ከ300-500 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በየዓመቱ በወባ በሽታ እየተጠቃ ነው፤ 2.7 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በየዓመቱ በወባ በሽታ ምክንያት ይሞታል፤ በእያንዳንዱ ሰከንድ ውሰጥ 10 ሰዎች በወባ በሽታ ይያዛሉ፤ ነፍሰ ጡር ሴቶችና እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፣ እንዲሁም በምግብ ማነስና ያለመመጣጠን በሚመጣ በሽታ የተጠቁ ግለሰቦች በይበልጥ በወባ በሽታ ተጠቂ ናቸው::

### የአፍሪካ የወባ በሽታ ሁኔታ

በመሠረቱ የወባ በሽታ ከድህነት ጋር የተቆራኘ ነው:: የአፍሪካ አህጉር፣ በተለይም በስተደቡብ የሚገኙት ሃገራት፣ በአብዛኛው ድሆች ናቸው:: በመሆኑም፣ በአፍሪካ ውስጥ ከሚከሰተው የወባ በሽታ የሥርጭትና የሞት መጠን፣ 90% የሚሆነው ከሰሃራ በታች በሚገኙ አገሮች ነው፤ በዚሁ የዓለም ክፍል፣ በየዓመቱ 1 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በወባ በሽታ ምክንያት ይሞታል:: ከሚሞተው አንድ ሚሊዮን ሕዝብ መካከል፣ 25% የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው:: አፍሪካ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ በወባ በሽታ ምክንያት በየዓመቱ 12 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ እየደረሰባት ነው::

**የኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ገጽታ**

ኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ ከሚገኙት ሃገሮች መካከል፣ በድህነትና በኋላ ቀርነት በግንባር ቀደምነት የምትጠቀስ ሃገር ናት፡፡ የዚህም ዋናው ምክንያት በየጊዜው የሚከሰተው የምግብ እጥረት (ረሃብ) እና ከፍተኛ የተላላፊ በሽታዎች ጥቃት ነው፡፡ የወባ በሽታ ደግሞ በሃገራችን ዘመን ያስቆጠረ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግር መሆኑ ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪክ በርካታ ምዕተ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በ*18*ኛውና በ*19*ኛው ክፍለ ዘመን (በዘመነ መሳፍንት) ከፍተኛ ረሃብና ወረርሽኝ አዘውትሮ ይከሰት እንደነበር የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

የችግሩ መንስዔ በውል ባልታወቀበት ሁኔታ የኢንፍሉዌንዛ ወይም የወረርሽኝ በሽታ እየተባለ ይነገርለት ነበር፡፡ ሳይንሳዊ የምርምር ሂደቶች እየተጠናከሩ በሄዱ ቁጥር፣ የዚህ አደጋ ዋናው መንስኤ የወባ በሽታ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

**በኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታ ዘመናዊ ጥናት አጀማመር**

በኢትዮጵያ ውስጥ በሳይንስ የተደገፈ የወባ በሽታ የምርምር ጥናት የተጀመረው በጣሊያን ወረራ ጊዜ ነው፡፡ ከ*1929-1934* ድረስ የጣሊያን ተመራማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በወባ በሽታ ላይ የአሰሳ ጥናት አደረጉ፡፡ በ*1938*፣ *1945*፣ *1948* ተጨማሪ የአሰሳ ጥናት በእንግሊዞች ተካሄደ፤ በተለይም በሰር ጐርደን ኮቬል (Sir Gordon Covel) ፡፡ ከ*1946 - 1948* በጐንደር፣ በጣናና በባህርዳር አካባቢ በወባ በሽታ ምክንያት በርካታ ሰዎች እንደተጎዱ ጥናታዊ ዘገባዎች ያስረዳሉ፡፡ ከ*1948-1950* በኢትዮጵያ ውስጥ ዲዲቲ የተባለውን ጸረተባይ ኬሚካል በመጠቀም በወባ በሽታ ላይ የሙከራ ፕሮጀክት (Pilot Project) ተደረገ፡፡ የሙከራ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ በወባ በሽታ ተጠቂ በሆኑት በተመረጡ አካባቢዎች፣ ማለትም:-

1. በአዋሽ ሸለቆ - (በዓለም ጤና ድርጅትና በዩኒሴፍ ድጋፍ)፣
2. በቆቦ - ጨርጨር፣
3. በወሎ - ደንቢያ፣
4. በጐንደር እና በጋምቤላ፣ ቀደም ሲል ፖይንት ፎር ሲባል በነበረው ዛሬ ዩኤስ ኤይድ እየተባለ በሚጠራው የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ የሙከራ ፕሮጀክት (Pilot Project) ተካሄደ፡፡

በወባ በሽታ ላይ የሙከራ ጥናት በተደረገበት ጊዜ አንዳንድ መሠረታዊ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

እነርሱም፡-

- በከፍተኛ ደረጃ ወባማ የሆኑትን አካባቢዎች ካርታ በማንሳት መለየት፣
- የትንኝ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣
- የደም ናሙና መሰብሰብ፣ ደም መመርመርና ለወባ በሽታ ለተጋለጡ ህሙማን መድኃኒት መስጠት፣
- የመኖሪያ ቤቶችን ዲዲቲ በተባለው ጸረ ወባ ትንኝ መድኃኒት መርጨትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የሙከራ ፕሮጀክቱን (Pilot Project) ተግባራዊ ለማድረግ በተመረጡ ስፍራዎች ንኡስ ጣቢያዎች ተቋቁመው ነበር፡፡ እነርሱም፡- አዘዞ ንዑስ ጣቢያ (በጐንደር ክፍለ ሃገር)፣ አላማጣ ንዑስ ጣቢያ (በወሎ ክፍለ ሃገር)፣ ባህር ዳር ንዑስ ጣቢያ (በጐጃም ክፍለ ሃገር)፣ ጋምቤላ ንዑስ ጣቢያ (በኢሉባቦር ክፍለ ሃገር)፣ ኮምቦልቻ ንዑስ ጣቢያ (በወሎ ክፍለ ሃገር)፣ እና ናዝሬት ንዑስ ጣቢያ (በሸዋ ክፍለ ሃገር) ነበሩ፡፡

የሙከራ ፕሮጀክቱም ዲዲቲ የተባለውን ጸረ ትንኝ መድኃኒት በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ በመርጨት፣ የወባ በሽታን ስርጭት በመቀነስ ረገድ መልካም ውጤት አስገኝቶ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በ1958 ዓ.ም ታላቁ የወባ ወረርሽኝ በሀገራችን ተከሰተ፡፡ በወረርሽኙ፣ በስድስት ወራት ብቻ፣ 3,000,000 ሕዝብ (በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር 15% የሚሆነው) የተጠቃ ሲሆን፣ 150,000 (በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር 5% የሚሆነው) ለሞት አደጋ የተጋለጠበት ወቅት ነበር፡፡

## የኢትዮጵያ የወባ ማጥፊያ ድርጅት መቋቋም

ለኢትዮጵያ ወባ ማጥፊያ ድርጅት መቋቋም ምክንያት ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተደረገው የሙከራ ፕሮጀክት ውጤታማ በመሆኑ፣
- የተከሰተው ታላቁ የወባ ወረርሽኝ ያስከተለው አደጋ ከምንጊዜውም በላይ አሰቃቂ በመሆኑ፣
- በዘመኑ፣ በሌላው የዓለም ክፍል ጭምር፣ ወባን የማጥፋት ዘመቻ የተፋፋመበት ወቅት በመሆኑ፣
- ዓለም አቀፍ አጋሮቻችን የወባ በሽታን ለማጥፋት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁለገብ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ ሆነው በመገኘታቸው፣

- የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትም የወባ ማጥፊያ ኘሮግራም በሃገራችን እንዲቋቋም ፈቃደኛ በመሆኑ፣

የካቲት 21 ቀን 1951 ዓ.ም የወባ ማጥፊያ ድርጅት በኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግሥት ትዕዛዝ ቁጥር 22 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር እራሱን ችሎ ተቋቁመ::

## የወባ ማጥፊያ ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረው የወባ በሽታ ሥርጭት ሁኔታ

70% የሚሆነው የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ወባማ ነበር፤50% የሚሆነው ህዝብ ለወባ በሽታ የተጋለጠ ነበር፤ በ1958 ዓ.ም ታላቁ የወባ ወረርሽኝ ተከሰተ፤ ለምሳሌ፣ የወባ ማጥፊያ ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በወባ በሽታ በከፍተኛ ደረጃ ከተጠቁት አካባቢዎች አንዱ የሞጆ ከተማና ወረዳው ነበር:: በመሆኑም በወቅቱ የተከሰተውን የወባ በሽታ አደገኛነት ለማንጸባረቅ «ሞጆ አገሩ ቆንጆ፤ ሬሳ አይጠፋም ከጉጆ» ይባል ነበር፤ «የሞጆ ወባ ይገንድስህ!» እየተባለም የዕርግማን ቃል ይሰነዘር ነበር፤በወባ በሽታ ምክንያት ይደርስ በነበረው የአእምሮ ጉዳት የተነሳ «የቆላ ሰው ለምስክርነት አይበቃም» እየተባለም ይነገር ነበር::

## ብሔራዊ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ማሰልጠኛ ት/ቤት መቋቋም

በ1951፣ የወባ በሽታን ለማጥፋት አስፈላጊ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል ብሔራዊ የወባ ማሰልጠኛ ተቋም በናዝሬት ከተማ ተከፈተ::

በዚህ የማሠልጠኛ ማዕከል በርካታ የመስክ፣ የኦኘሬሽንና የካርታ ሥራ ቴክኒሽያኖች፣ የትንኝ ጥናት ቴክኒሽያኖች፣ የደም ጥናት ቴክኒሽያኖች (የላቦራቶሪ ቴክኒሺያኖች)፣ የወባ በሽታ ደም መርማሪዎች (Microscopists)፣ የጤና አጠባበቅና የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ሠልጥነው ተመርቀዋል::

የሰለጠኑት ባለሙያዎች በመስክ ሥራ በቂ ልምድ ካገኙ በኋላ ብቃት ያላቸው ተመርጠው የቴክኒኩን የመስክ ሥራ በኃላፊነት የሚመሩ ተቆጣጣሪዎች፣ በንኡስ ጣቢያ ደረጃ የአስተዳደሩን ሥራ በኃላፊነት የሚመሩ የንኡስ ጣቢያ ኃላፊዎች፣ የዋና መሥሪያ ቤቱንና የዓቢይ ጣቢያ ጽሕፈት ቤቶችን በኃላፊነት የሚመሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች ወደ ውጭ አገር ተልከው ስልጠና ተሰጥቷቸዋል:: በአጠቃላይ፣ የማሠልጠኛ ተቋሙ በሺህ የሚቆጠሩ ባለሙያዎችን አፍርቶ ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ የማሰልጠኛ ተቋሙ የታጠፈ በመሆኑ ባለሙያዎችን በመደበኛነት ማሰልጠን ካቋረጠ ረጅም ጊዜ ሆኖታል::

## የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ

የወባ ማጥፊያ ድርጅት ሥራውን በይፋ የጀመረው ንጉሰ ነገስቱ መጋቢት 1 ቀን 1951 ዓ.ም በሰጡት መሪ ቃል ነበር:: በወቅቱ የተላለፈውን መሪ ቃል፣ ለግንዛቤ ያመች ዘንድ፣ ከዚህ በታች ጠቅሰነዋል፡-

..... የወባ ማጥፋት ሥራ የሕዝቡን ርዳታ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ሕዝባችንም በሙሉ ልቡ ለዚህ ለተቀደሰ ሥራ ተባባሪ እንደሚሆን እምነት እንጥልበታለን። በተለይም ጠቅላይ ገዥዎች፤ እንደራሴዎች፤ የአውራጃና የወረዳ ገዥዎች፤ ባላባቶችና ምስለኔዎች፤ ጭቃሹሞች፤ የሕዝብ መሪ እንደመሆናቸው መጠን ከድርጅቱ ጋር በመተባበር ሕዝቡን እንዲያስተምሩና እንዲያበረታቱ አደራ የተጣለባቸው መሆኑን እንዲገነዘቡት ..... ያስፈልጋል።

በአገራችን ወባን ለማጥፋት የሚደረገው ትግል ጥሩ ውጤት እያስገኘ መሄዱን አይተናል። የጤና ጥበቃ ሚኒስትራችንና እናንተም የወባ ማጥፊያ ድርጅት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሕይወታችሁን ለወገናችሁ አገልግሎት ለማዋል ቆርጣችሁ ተነሥታችኋል። በሥራችሁ ብዙ ድካምና ፈተና እንደሚገጥማችሁ የታወቀ ነው። ቢሆንም የተቀበላችሁትን ኃላፊነት ተገንዝባችሁ ሐሳባችሁን ባለማዛባት ይህን የተቀደሰ ሥራ ፍጻሜ እንድታደርሱት ሁላችሁንም አደራ እንላችኋለን....እግዚአብሔር የተባረከ ሥራ ያድርገው።

**የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ የጊዜ ሰሌዳ**

በሃገራችን ታቅዶ የነበረው የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቀሴ በአራት የጊዜ ሰሌዳ የተከፈለ ነበር፦

1. የመዘጋጃ ጊዜ፣ 3 ዓመታት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ወቅት ፣ የካርታ ሥራ ዝግጅት ፣ ወባማ አካባቢዎችን መለየት፣ በተመረጡ አካባቢዎች የሚገኙ ቤቶች ሁሉ ካርታ እንዲነሱ ማድረግ፣ እና ለመኖሪያ ቤቶች ቁጥር መስጠት፣ የት እንዳሉ የማወቅና የመሳሰሉት ናቸው፤
2. የማጥቂያ ጊዜ ፣ 4 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የወባ ትንኞች የሚያርፉባቸው ቤቶች፣ ሕንፃዎች ወይም ሌሎች መጠለያዎች ሁሉ የጸረ ትንኝ መድኃኒት በመጠቀም በአግባቡ ይረጫሉ፤
3. የማጠናከሪያ ጊዜ ፣ 3 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት ወባ የሚተላለፍባቸውን ሥፍራዎች ለማወቅ የአሰሳ ጥናት ማድረግ፣ ለወባ በሽታ መንስዔ የሆኑትን ሁኔታዎች ሁሉ ማጥፋትና ይህ ወቅት ወባ በሽታ ተመልሶ እንዳያገረሽ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱ የሚረጋግጥበት ጊዜ ነው፤
4. የመጠባበቂያ ጊዜ ፣ 7 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የወባ በሽታ ሙሉ በሙሉ ከጠፋ በኋላ፣ ሥራውን ለመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ለማስረከብ የታቀደበት ጊዜ ነው።

| 1 | 2 | | | 3 | | 4 | | 5 | | | 6 | | | 7 | 8 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዓ.ም. | 1956 - 1958 | | | 1959 - 1960 | | 1961 - 1962 | | 1963 - 1964 | | 1965 | 1966 - 1968 | | | 1969 | 1970 - 1972 | | |
| አካባቢ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሀ | የመ | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ |
| ለ | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ |
| ሐ | | | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ |
| መ | | | | | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ |

**መፍቻ:-** የመ = የመዘጋጃ ጊዜ

የማ= የማጥቂያ ጊዜ

የማጠ = የማጠናከሪያ ጊዜ

የመቆ = የመቆጣጠሪያ ጊዜ

**የወባ ማጥፊያ ድርጅት የስራ እንቅስቃሴ ያስገኛቸው ውጤቶች**

በሙያ ዘርፉ በርካታ የሰለጠነ የሰው ኃይል አፍርቷል፤ የተጠናከረ ድርጅታዊ መዋቅርም እንደሚከተለው ፈጥሯል፡-

1 ዋና መ/ቤት - በአዲስ አበባ ፣14 አቢይ ጣቢያዎች - በየክፍለ ሃገሩ ፣ 5 መለስተኛ አብይ ጣቢያዎች (በተመረጡ ሥፍራዎች)፣50 ንዑሳን ጣቢያዎች በየአውራጃው፣ 20 የወባ ጤና ኬላዎች እና በአጠቃላይ 80 የሚሆኑ የወባ ጤና ተቋማት፣ ተቋቁመው የወባ በሽታን በማጥፋት ዘመቻ ላይ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡

ድርጅቱ በሰጠው አገልግሎት እንቅስቃሴ በተደረገባቸው በአካባቢ «ሀ» (A) ከ30-40% የነበረው የወባ በሽታ ጥቃት ወደ 5% እና ከዚያ በታች ዝቅ ብሎ ነበር፡፡ ይህ እርምጃ ባስገኘው ውጤት የወባ በሽታ የህብረተሰቡ አቢይ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ችግር እንዳይሆን አድርጎት ነበር፡፡

ከወባ በሽታ ነፃ በመሆናቸው የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርት ማዕከል የሆኑ አካባቢዎች አያሌ ነበሩ፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ፣ የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት፣ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ፣ የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ፣ የሁመራ እርሻ ልማት፣ የመተማ እርሻ ልማት፣

የባህርዳር ከተማ፣ የደምቢያና ፎገራ አካባቢዎች እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ።

**የአካባቢ ሀ ዓቢይ ጣቢያዎችና ንኡሳን ጣቢያዎች ስርጭት**

**1. አሥመራ ዓቢይ ጣቢያ**

አዲኡግሪ ንዑስ ጣቢያ
ከረን ንዑስ ጣቢያ
ምጽዋ » »
አቆርዳት » »
ባሬንቱ » »
ተሰነይ » »
ሁመራ » »

**2. መቀሌ ዓቢይ ጣቢያ**

መቀሌ ንዑስ ጣቢያ
ተምቤን » »
ሰቆጣ » »
አድዋ » »
ሽሬ እንዳስላሴ

**3. ጐንደር ዓቢይ ጣቢያ**

አዲስ ዘመን ንዑስ ጣቢያ
ደልሚ » »
አዲአርቃይ » »
አይከል » »
ሁመራ » »
ንፋስ መውጫ » »

**4. ደሴ (ኮምቦልቻ) ዓቢይ ጣቢያ**

ከምቦልቻ ንዑስ ጣቢያ
ሸዋ ሮቢት » »
ወልዲያ » »
አላማጣ » »

**5. ደብረማርቆስ ዓቢይ ጣቢያ**

ሞጣ ንዑስ ጣቢያ
ደብረማርቆስ » »
ቢቸና » »
መተከል » »

**5. ድሬዳዋ ዓቢይ ጣቢያ**

ድሬዳዋ ንዑስ ጣቢያ
ሐረር » »
ደደር » »
ሂርና » »
ሚኤሶ » »
በዴሳ » »
በደኖ » »
መቻራ » »

**6. ደብረዘይት ዓቢይ ጣቢያ**

የመጀመሪያው ዓቢይ ጣቢያ
ደብረዘይት ንዑስ ጣቢያ
ናዝሬት » »
አዋሽ » »
አዲስ አለም » »
(ወደ ኋላ ላይ ወደ ናዝሬት ዓቢይ ጣቢያ የተቀየረ)

***በአካባቢ «ለ» የተቋቋሙ ዓቢይና ንኡሳን ጣቢያዎች***

**1. ነቀምቴ ዓቢይ ጣቢያ**

ባኮ ንዑስ ጣቢያ
ነቀምቴ ንዑስ ጣቢያ
ጊምቢ » »
ጊዳ አያና » »

**2. ደምቢ ደሎ ዓቢይ ጣቢያ**

ጊዳሚ ንዑስ ጣቢያ
ዓለም ተፈሪ » »
አሶሳ » »
ቤጊ » »

**3. አዋሳ ዓቢይ ጣቢያ**

ያቤሎ ንዑስ ጣቢያ
ዲላ ንዑስ ጣቢያ
ሞያሌ » »
አዋሳ » »
ነጌሌ ቦረና » »
አላባ ቁሊቶ » »
አርባምንጭ (በኋላ ወደ ዓቢይ ጣቢያ ተለወጠ)

**4. ጅማ ዓቢይ ጣቢያ**

ጅማ ንዑስ ጣቢያ
ቡኖ በደሌ » »
ጋምቤላ » »
መቱ » »
ቦንጋ » »

*ከ1959-1963 ዓ.ም የማጥቂያ ጊዜ በአካባቢ "ሀ" ተጀምሮ በተከታታይ በአካባቢ "ለ" ተግባራዊ እንዲሆን ታቅዶ ነበር:: በአጠቃላይ የወባ ማጥፊያ ኘሮግራም በመላ ሃገሪቱ በ1980 ዓ.ም እንዲዳረስ ታስቦ ነበር:: ይሁንና የወባ ማጥፋቱ ኘ ሮግራም በአካባቢ "ሐ" እና "መ" ተግባራዊ ሳይሆን ኘሮግራሙ ተቋረጠ::*

**የኢትዮጵያ ወባ ማጥፊያ ድርጅትን የመሩ ኃላፊዎች የሚከተሉት ናቸው:-**

አቶ ሠይፈ ሚካኤል ዘለቀ (የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዳይሬክተር)፣ አቶ በቀለ ተገኝ (2ኛው ሥራ አስኪያጅ ) ፣ አቶ አመሐ እሸቴ (ሦስተኛው ሥራ አስኪያጅ) ፣ አቶ ኃይሉ መቼ (አራተኛ ሥራ አስኪያጅ) ፣አቶ ጥላሁን አበበ (አምስተኛ ሥራ አስኪያጅ) ፣አቶ የማነ ተክስተ (ስድስተኛ ሥራ አስኪያጅ) ፣ ዶ/ር አዋሽ ተ/ሃይማኖት የመጨረሻው ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ ከዚያ በኋላ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ወደ ወባ ቁጥጥር ኘሮግራም ተለውጧል::

**በወባ ማጥፊያ ድርጅት ላይ የተደረጉ መዋቅራዊ ለውጦች**

በ1962 ዓ.ም በዓለም ጤና ድርጅት ውሳኔ መሠረትና ሃገራችንም ስለተቀበለችው፣ የወባ ማጥፊያ ፕሮግራም ታጥፎ ወደ ወባ መቆጣጠሪያ ድርጅት ተቀየረ:: ከ1972-1978 ዓ.ም፣ የወባ መከላከያ ድርጅት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጤና አገልግሎት መምሪያ ሥር፣ የወባ መከላከያ ፕሮግራም በመባል በዋና ክፍልነት ዝቅ ብሎ በአዲስ መልክ ተዋቀረ:: ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ፣ የወባ መከላከያ ፕሮግራም ብሔራዊ የወባና ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች መከላከያ ድርጅት ተባለ:: አሁንም ቢሆን ድርጅቱ የሚጠራው የወባና ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች ቁጥጥር እየተባለ ነው:: ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች የሚባሉት:- ሽስቶሶሚያሲስ (ቢልሐርዚያ)፣ ሆንክስርኪያሲስ፣ የዕንቅልፍ በሽታ፣ ቆንጭር (ሌሽማኒያሲስ)፣ የጊኒ ወርም እና የወባ በሽታ ናቸው::

ድርጅቱ፣ የወባ በሽታን ጨምሮ፣ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ቬክተር ወለድ በሽታዎች ለመከላከል እቅድ ያወጣ ቢሆንም፣ ቢልሐርዚያ በተሰኘው በሽታ ላይ አንዳንድ መሠረታዊ እንቅስቃሴዎች ከመደረጋቸው በስተቀር፣ ተጨማሪ ሥራ

ስለመከናወኑ የተዘገበ መረጃ የለም:: ይልቁንም፣ ድርጅቱ ከአቅሙ በላይ ተለጥጦ በመዋቀሩ፣ የወባ በሽታንም፣ የታሰበውን ያህል፣ ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር ያስቻለ የሥራ እንቅስቃሴ አልነበረውም::

በየጊዜው በተደረገው የመዋቅር ለውጥ ምክንያት አብዛኛዎቹ ዓቢይ ጣቢያዎችና ንኡስ ጣቢያዎች ተዘጉ:: የሠለጠኑ ከፍተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ተበተኑ:: የወባ በሽታን የመከላከል ወይም የመቆጣጠር እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ተዳከመ:: በዚህ ሳቢያ በተደጋጋሚ አገር አቀፍ የወባ ወረርሽኝ እንደገና የተከሰተ ሲሆን ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል:: በ1966-67፣ በ1973-74፣ በ1983-84፣ በ1990-91፣ 1996-97 በአገር አቀፍ ደረጃ የወባ ወረርሽኝ ተከስቶ ከፍተኛ የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ አስከትሏል:: በርካታ ሕይወትም ጠፍቷል:: በመሆኑም፣ ይህ ሁኔታ ሲታይ፣ በየአምስት ዓመቱ የወባ ወረርሽኝ ሊከሰት እንደሚችል የጥናት መረጃዎች ያመለክታሉ::

**በወባ መከላከያ ድርጅት ላይ የተደረጉት መዋቅራዊ ለውጦች ያስከተሏቸው ችግሮች:-**

የወባ መከላከያ ድርጅት፣ በየጊዜው በተደረጉት መዋቅራዊ ለውጦች የተዳከመ ቢሆንም፣ የበሽታው የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ቀውስ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከሌላው የጤና አገልግሎት ጋር በውህደት እንዲቀላቀል መደረጉ፣ የሥራው እንቅስቃሴ የበለጠ እንዲዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ከሁሉም በላይ፣ በጤና ድርጅቶች የሚገኙ ባለሙያዎች ስለወባ በሽታ መሠረታዊ ግንዛቤ እንዳላቸው የማይካድ ቢሆንም፣ በተለይ ስለትንኝ ጥናት፣ ስለሌሎችም የወባ በሽታ የመስክ የሥራ እንቅስቃሴዎች ሥልጠና ሳይሰጥ ኃላፊነቱን እንዲሸከሙ መደረጉ፣ ካላቸው የሥራ ጫና ጋር ሊወጡት የማይችሉት ችግር ሆኖ በመገኘቱ፣ የመስክ የሥራ እንቅስቃሴው ከሞላ ጐደል መቋረጡ የማይታበል ነው::

ከዚያም በላይ፣ የተደረገው ድርጅታዊ ውህደት አካላዊ እንጅ ተግባራዊ ባለመሆኑ፣ የድርጅቱን መዋቅር፣ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና የንብረት ምንጮችን እንዲዳከሙ አድርጓል:: በአጠቃላይ ሲታይ፣ በቂ ጥናት ሳይደረግ ወይም የመሸጋገሪያ ጊዜ ሳይሰጥ፣ የተደረጉት ድርጅታዊ ለውጦች በኘሮግራሙ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል::

በመሠረቱ፣ ያልተማከለ አስተዳደር በየአካባቢው መንደር አቀፍና ህብረተሰቡን ያሳተፈ የወባ በሽታ ቁጥጥር ሥራን ለማጠናከርና ውጤት ለማስመዝገብ ጭምር የተሻለ እርምጃ ነው:: በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ ቀበሌዎችንና ወረዳዎችን በማጠናከር ተሳትፎውን ለማጎልበት አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል:: ነገር ግን የወባ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ዘርፈ ብዙና የባለሙያ ድጋፍ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ፣ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚያስቸግር ከነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል:: በመሆኑም:-

- በወባ ቁጥጥር ሥራ ላይ ያተኮረ ሥልጠና በማይሰጥበት በአሁኑ ጊዜ፣ በወረዳ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሟላት አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- በየወረዳው የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች (ሃኪሞች፣ ነርሶች፣ የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪዎች፣) ባላቸው ሙያ ላይ ስለወባ በሽታ የመስክ ሥራ፣ በተለይም ስለወባ አስተላላፊ ትንኞች ተጨማሪ ግንዛቤ ማግኘት ስለሚያስፈልጋቸው፣
- በየቀበሌው የሚመደቡ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችም የቅርብ ቁጥጥርና ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው፣
- የወባ በሽታ ከሚያስከትለው መጠነ ሰፊ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመከላከልና የመቆጣጠር እርምጃ ለመውሰድ የበለጠ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ በአሁኑ ጊዜ የወባ በሽታ ከሚያስከትለው ጫና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የወባ ቁጥጥር ሥራ ለመውሰድ አስቸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ በተለይ በየክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የበለጠ እንቅስቃሴ ቢደረግ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል።

### የወቅቱ የኢትዮጵያ የወባ ሁኔታ[1]

በሃገራችን፣ በአጠቃላይ ካለፉት 47 ዓመታት ጀምሮ የወባ በሽታን ለማጥፋት፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም፣ ዛሬም ቢሆን የወባ በሽታ ግንባር ቀደም የጤና ችግር፣ ከፍተኛ የህመምና የሞት ምክንያት፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ የሚያመጣ፣ እንዲሁም ለድህነታችን ዋንኛ ምክንያት ሆኖአል።

በመሆኑም፣ አሁን ባለንበት ወቅት ያለው የወባ በሽታ ሁኔታ ሲታይ:- 75% የሚሆነው የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት በወባ ጥቃት ስር ወድቆ ይገኛል፤ ከባህር ወለል በላይ እስከ 2000 ሜትር ድረስ ብቻ በሚገኙ አካባቢዎች ይደርስ የነበረው የበሽታው ጥቃት በአሁኑ ጊዜ እስከ 2300 ሜትር ድረስ እየተስፋፋ ነው፤ በሀገራችን የወባ በሽታ ግንባር ቀደም የህመምና የሞት ምክንያት እየሆነ ነው፤ በአማካይ ግምት 48 ሚሊዮን የሚሆነው ህዝብ (ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት 65%) ለወባ በሽታ ጥቃት፣ ተጋልጦ ይገኛል፤ ለተመላላሽ ህክምና ወደ ጤና ድርጅት ከሚሄዱት ህሙማን መካከል 16% የሚሆኑት የወባ ህመምተኞች ናቸው፤ ታመው በሆስፒታል ከሚተኙት መካከል 20% የሚሆኑት የወባ በሽታ ተጠቂዎች ናቸው፤ በሆስፒታል ተኝተው ከሚታከሙት ህመምተኞች መካከል 22% የሚሆኑት የሚሞቱት በወባ በሽታ ምክንያት ነው፤ ለምሳሌ በ1996 (2003) ዓ.ም በተከሰተው በሃገር አቀፍ የወባ በሽታ ወረርሽኝ ምክንያት፣ 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) የሚሆኑት ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት የተጠቁ

[1] ይህ ትንተና የተደረገው ወረቀቱ ለፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ስብሰባ እስከቀረበበት፣ እስከ ህዳር 1999 ድረስ፣ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ነው።

ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል 3,000 የሚሆኑት ሞተዋል፡፡ ይህ ወረርሽኝ የተከሰተው በ3,368 አካባቢዎችና በ200 ወረዳዎች ውስጥ ነበር፤ በየዓመቱ ከ4-5 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ በወባ በሽታ ምክንያት ይታመማል፡፡

**የወባ በሽታ የወደፊቱ ስጋት**

የወባ በሽታ፣ ከሚያስከትለው የጤና ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመከላከል እርምጃ እስካሁን ስላልተወሰደ፣ በአሁኑ ጊዜ እስከ 70% ማደጉ ይታወቃል፡፡ ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር፣ በተለይም በትንኝ ጥናትና ቁጥጥር በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩ ችግሩን አባብሶታል፡፡

ሌላው አዲሱ ክስተት፣ የወባ አስተላላፊ ትንኞች ጸረ ትንኝ መድኃኒትን እየተለማመዱት ስለመጡ ሲረጭባቸው በቀላሉ አይበገሩም፡፡ ሊተነበይ የማይችል የአየር ጠባይ፣ የስነምህዳርና የአካባቢ መለወጥ (ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና መጠነ ሠፊ የጐርፍ አደጋ በየአካባቢው መከሰት፣ ወዘተ)፣ ለወባ አስተላላፊ ትንኞች መራባት እና ለበሽታው ተህዋሲያን መተላለፍ ከምንጊዜው የበለጠ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡

በሠፈራና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች የወባ በሽታን የመቋቋም አቅሙ ዝቅተኛ የሆነው  የህብረተሰብ ክፍል፣ በብዛት ከደጋማው ወደ ቆላማው ክፍል ለሥራ ፍለጋ ሲንቀሳቀስ፣ ለበሽታው ተጋላጭ ይሆናል፡፡

የአነስተኛና የሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች በየአካባቢው መስፋፋት፣ የውሃ ማቆር ፕሮግራም በየአካባቢው መስፋፋት፣ አስቀድሞ ታስቦበት የመከላከያ እርምጃ ካልተወሰደ፣ የወባ ትንኝን እድገት ሊያባብሱ ይችላሉ፡፡

የኤች. አይ. ቪ. ኤይድስ ወረርሽኝ መከሰት፣ በሳንባ ነቀርሳ መስፋፋትና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች ህብረተሰቡ የወባ በሽታን ለመቋቋም ያለው የተፈጥሮ አቅም እየተዳከመ ስለሚሄድ የወባ በሽታ ለወደፊቱ አመርቂ የቁጥጥር እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር የበሽታው ጥቃት እየተባባሰ እንጂ እየተሻሻለ አይመጣም፡፡

***በአሁኑ ጊዜ የወባ በሽታን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች***

የወባ በሽታ እያስከተለ ካለው የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጫና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የወባ በሽታን የመቆጣጠር ወይም የመከላከል እርምጃ እየተወሰደ ነው ባይባልም፡- አጠቃላይ የጤና አገልግሎቱን ለማራመድ የጤና ፖሊሲ ወጥቷል፤ እያንዳንዱ ክልልም የራሱ የሆነ የአፈጻጸም ስልት በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገ ነው፤ የአምስት አመት ፕላንም ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ግሎባል ፈንድን ጨምሮ ከፍተኛ የውጭ እርዳታ መኖሩና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት ለመከላከሉ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው በሽታውን ለመከላከል፣ ብሎም ለማጥፋት፣ ይረዳል፡፡

***ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች***

አቢይ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍ:-

- ከየክልሉ ወጣት ተማሪዎች ተመልምለው በወባ በሽታ ቁጥጥር ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች በወባ በሽታ ላይ የምርምር ጥናት እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
- የወባ በሽታ ቁጥጥር የሥራ እንቅስቃሴ በዋና መሥሪያ ቤትና በክልሎች ደረጃ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ከፍተኛ ባለሙያዎች በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር እንዲሰለጥኑ ማድረግ፣
- ከተቻለ በመንግሥትና በግል የጤና ተቋማት፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በዩኒቨርስቲዎች ስለወባ በሽታ ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በዋና መሥሪያ ቤትም ሆነ በክልሎች ደረጃ የተጠናከረ የአስተዳደር መዋቅር እንዲኖረው ማድረግ፣
- መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እየተካሄደ ባለው የወባ ቁጥጥር ሥራ ተገቢውን ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

**የኢትዮጵያ የወባ መቆጣጠሪያ ባለሙያዎች ማኅበር መቋቋም**

የኢትዮጵያ የወባ መቆጣጠሪያ ባለሙያዎች ማኅበር መንግሥታዊ ያልሆነ፣ የፖለቲካ አመለካከት የሌለውና ለትርፍ ያልተቋቋመ የሙያ ማኅበር ነው። ማኅበሩ፣ በቀድሞው የወባ ማጥፊያ ባለሙያዎች መሥራች አባልነት፣ ሰኔ 21 ቀን 1994 ዓ.ም ከፍትህ ሚኒስቴር ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ፣ በይፋ ተቋቁሟል።

የማኅበሩ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ በአጋርነት በመሰለፍ የወባ በሽታ የኅብረተሰቡ ዓቢይ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግር እንዳይሆን የበኩሉን ጥረት ማድረግ ነው።

የማኅበሩ ዋና ራዕይ፣ የወባ በሽታ በኢትዮጵያ ውስጥ እያደረሰ ያለውን ጫና ለመቀነስና የኅብረተሰቡ ዓቢይ የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግር እንዳይሆን ማድረግ ነው። ከሁሉም በላይ፣ የወባ በሽታ ከድህነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፣ በወባማ አካባቢዎች ያለውን የድህነትና የወባ በሽታን የዑደት ቁርኝት እንዲቋረጥ ማድረግ ነው።

የማኅበሩ ተልዕኮ:- የወባ በሽታን በአመርቂ ሁኔታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የተቀናጀ መንደር አቀፍ የወባ በሽታ ቁጥጥር ስልት ለመቀየስ የሚያስችል ፕሮጀክት በሃገር አቀፍ ደረጃ ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ነው።

ማኅበሩ በአሁኑ ወቅት የወባ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ዘርፈ ብዙ እውቀት ያላቸውና የወባ በሽታን ጨምሮ በተለይም በጤና አጠባበቅ ዙሪያ ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ኤክስፐርቶች አሉት፡፡ አብዛኛዎቹ አባላት ከቀድሞው የኢትዮጵያ ወባ ማጥፊያ ማሠልጠኛ ተቋም የተመረቁና የወባ በሽታን በማጥፋትና በመከላከል ረገድ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉና በሙያ መስኩ በቂ የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው፡፡

ማኅበሩ፣ እነዚህንና እና ሌሎች የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማስተባበር፣ ከመንግስት አካላትም ጋር በመቀናጀት፣ መጠነ ሰፊ ጸረ ወባ ዘመቻ ያካሂዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

# የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም-ዓቀፋዊ ችግሮች

*ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ*

## *መግቢያ*

ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው፣ ለብዙ ሺህ ዓመታት የአባይ ወንዝ ዋና ተጠቃሚ የሆነችው ግብጽ፣ ከሱዳን በስተቀር፣ ሌሎቹን የላይኛውን የወንዙን ተፋሰስ አገሮች ሳታማክር በራስዋ ብቸኛ ውሳኔ፣ የአስዋንን ከፍተኛ ግድብ ፕሮጀክት በ 1947 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በ1955) ተግባራዊ ለማድረግ ከወሰደችው የተናጠል እርምጃ እስከ ኢትዮ - አሜሪካ ተራድኦ የአባይ ሸለቆ ጥናት መከናወን 1956 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. 1964) ድረስ፣ ባለው ዘመን ላይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ያላትን የተፋሰስ መብት መሠረት አድርጋ፣ የአባይን ውሀ ለራስዋ ጥቅም ለማዋል ከወሰነችበት ጊዜ ጀምሮ፣ ባለብዙ ፈርጅ የሆኑ ጥናቶች በአባይ ተፋሰስ ላይ አካሂዳለች፡፡ ከነዚህም አንዱ፣ የአሜሪካ-ኢትዮጵያ የአባይ ተፋሰስ ተራድኦ ጥናት የመስክ ተግባሩን ከ1949 እስከ 1954 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በ1957-1962) መካከል ባሉት ዓመታት አጠናቆ ስድስት አባሪዎች ያሉትን ዝርዝር ምርምሩን የያዘ መግለጫ በ1956 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ በ1964) አቅርቦአል፡፡ ይህ ጽሑፍ ከሚያተኩርበት ዘመን ወዲህም የአባይ ጉዳይ አሳሳቢነቱ ቀጥሎአል፡፡

በዚህ ገለጻ፣ ባንድ ዓቢይ ርእስ ተጠቃሎ የቀረበውን ጉዳይ፣ በሰባት ንዑሳን ርዕሶች ከፋፍዬ አቅርቤአለሁ፡-

1. የስያሜ ማስገንዘቢያ፣
2. መልክዓ ምድራዊ ጉዳዮች፣
3. የአባይን እድሜ ያህል የቆየ የአባይ ጉዳይ ታሪካዊ መሠረት፣
4. የአስዋን ከፍተኛ ግድብ ኢትዮጵያ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ለመቋቋም ኢትዮጵያ የወሰደቻቸው እርምጃዎች፣
5. ኢትዮጵያ አግባብነት ያላቸውን የራስዋን ፍላጎቶች ለማሙዋላት በአባይ ውሀ ለመጠቀም ላላት መብት አሜሪካ እውቅና እንድትሰጥ ፣ ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆ በምታካሂደው ምርምርና ጥናት እንድትረዳ፣ የውሃ ሃብትዋን ለማልማት የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን በማሠልጠን ረገድ ኢትዮጵያን እንድታገዝ፣ ከአሜሪካ ጋር የተደረጉት ውይይቶችና ስምምነት፣
6. በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ድርጅት መቋቋምና ለአባይ ተፋሰስ ጥናት የአሜሪካ ኢትዮጵያ የተራድኦ ፕሮግራም ያከናወነው ሥራ፣
7. መደምደሚያ፡፡

**የሥያሜ ማስገንዘቢያ**

በኢትዮጵያ አባይ እያልን የምንጠራውን ወንዝ፣ ወሰን ተሻግሮ ወደ ሱዳን ሲገባ ባሕር አል አዝራቅ (ሰማያዊ ባሕር) ወይንም ኒል እል እዝራቅ (ሰማያዊ ኒል) ይሉታል:: ከቪክቶሪያና ከኢኳቶርያ ሀይቆችና ወንዞች መንጭቶ በደቡብ ሱዳን ሲያቋርጥ ከኢትዮጵያ ከሚፈሰው ባሮ-አኮቦ (ሶባት) ወንዝ ጋር ከተቀላቀለ በኂላ ባሕር እል ጀበል ወይም ባሕር እል አብያድ ወይንም ኒል እል አብያድ (ነጭ ባሕር ወይንም ነጭ ኒል) ይባላል፤ ይህም ወንዝ ከአባይ ጋር ካርቱም ላይ ከተቀላቀለ በኋላ እል ባሕር (ባሕር) ወይንም እል ኒል ይባላል:: ይህ ወንዝ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሲፈስ በሱዳንና በግብፅ ወሰን አቅራቢያ በኢትዮጵያ ተከዜ፣ በኤርትራ ሰቲት፣ ከፍ ሲል ሱዳን ውስጥ አጥባራ፣ በመባል ከሚታወቀው ወንዝ ጋር ይቀላቀላል:: ከዚያም ግብፅን አቋርጦ ወደ ሜዲትራንያን ባህር ይገባል::

ግብፅ ሌላ ወንዝ ስለሌላት፣ ለዝናብም እምብዛ ያልታደለች በመሆኗ፣ የጥንቱ ግብፃውያን፣ በፈርዖኖች ዘመን፣ ወንዙን የሕይወት ምንጭ አድርገው በመቁጠር «ሃፒ» በሚል ስያሜ ያመልኩት ነበር::[1] በመጽሐፍ ቅዱስም (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ 2 ቁ 13) ፈለገ ግዮን (የግዮን ወንዝ) ተብሎ ይጠራል::ጥንታውያን ግሪኮችና ሮማውያን ኒሉስ ብለው ሠይመውታል::

በዘመናችን በኢትዮጵያ «ጥቁር አባይ» ፣ «ነጭ አባይ» የሚባሉት ስያሜዎች በተውሶ ያመጣናቸው ቃላት ናቸው:: ከኢትዮጵያ የሚመነጨው «አባይ» በመባል ስለሆነ የሚታወቀው በጽሑፌ «ጥቁር አባይ» የሚባለውን «አባይ»፣ «ነጭ አባይ» የሚባለውን «ነጭ ኒል»፣ ሁለቱ ከተቀላቀሉ I|F «ኒል» በማለት እለያቸዋለሁ::

**መልክዓ ምድራዊ ጉዳዮች**

የሚሲሲፒ ሚዙሪ ወንዝን በ100 ማይልስ ስለሚበልጠው የኒል ወንዝ በዓለም ረዥሙ ወንዝ ነው:: በአስዋን እንደተለካው በሰከንድ ከፍተኛ የሆነ የ13,500 ኪዩቢክ ሜትር የውሃ ፍሰት አለው:: በዓመት 90 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ፣ 140 ሚሊዮን ቶን አፈር ያጓጉዛል:: ወንዙ የሚያጓጉዘው አፈር ፣ ለሰው መኖሪያ ተስማሚ የሆነው የግብጽ መሬት፣ በየአንዳንዱ መቶ ዓመት፣ የ10 ሴንቲ ሜትር ከፍታ እንዲኖረው ያደርጋል ይባላል::

ለኒል አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ሁለቱ የውሃ ምንጮች፣ የኢኳቶርያል ሃይቆች አካባቢ እና የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች ናቸው:: የኢኳቶርያል ሃይቆች ፍሳሽ በማላካል አካባቢ ለነጭ ኒል የሚያበረክቱት የውሀ መጠን በያመቱ 15.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ነው:: አስዋን የሚደርሰው ጠቅላላ የውሃ ፍሰት በየዓመቱ 84 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ነው:: ከዚህ ውስጥ የኢኳቶርያል ሃይቆች አስተዋጽኦ 12 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ብቻ ነው:: በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ወንዞች አባይ፣ አጥባራ እና ሶባት (ባሮ - አኮቦ) በየዓመቱ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ 72

[1] Wallis E.A. Budge, *The Nile* (London, 1892), p. 45.

ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ነው፡፡ ይህም ከጠቅላላው የውሃ ፍሰት 86% በመቶ ገደማ መሆኑ ነው፡፡

ነጭ ኒል ለጠቅላላው ፍሰት ለሚያበረክተው አነስተኛ አስተዋፅኦ ዋናው ምክንያት በሱድ ላይ የሚከሰተው ከፍተኛ የሆነ የውሃ ትነት ነው፡፡ ወንዙ በደቡብ ማዕከላዊ ሱዳን ከፍተኛ የሆነ ረግረግ ፈጥሯል፡፡ ይህም ሁኔታ የወንዙን የውሃ ፍሰት በመቀነስ በአካባቢው በሚገኘው ሙቅ የአየር ፀባይ ምክንያት ውሃው ለከፍተኛ ትነት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

የአባይ ድርሻ 54 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአጥባራ ድርሻ 12.5 ቢሊዩን ኪውቢክ ሜትር ሲሆን፣ የባሮ-ሶባት ድርሻ ደግሞ 13.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ነው፡፡ ከሦስቱ በእጅጉ ትልቁ የሆነው አባይ፣ የጣና ሃይቅን እና ተፋፈሱን ጨምሮ፣ 324,430 ኪ.ሜትር ካሬ የሚሆን ቦታን ይሸፍናል፡፡ ይህ አካባቢ የኢትዮጵያ መሬት ከአራት አንድ እጅ መሆኑ ነው፡፡

የሶባት ወንዝ እንደ አኮቦ፣ ባሮ እና ፒቦርን የመሳሰሉ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ፣ ዋና ዋና ገባር ወንዞች አሉት፡፡ በዚሁ አካባቢ የዓመቱ የዝናብ መጠን ከ2000 ሚ.ሜትር በላይ ነው፡፡ ሶባት ከነጭ አባይ ጋር የሚገናኘው ከማላካል ደቡብ ነው፡፡ በሌላ በኩል የዲንደር እና የራሃድ ወንዞች ከአባይ ጋር የሚገናኙት በሰንአር እና በወድ መደኒ መካከል ነው፡፡

አጥባራ በኢትዮጵያ ተከዜ (ወይንም ሰቲት) እየተባለ የሚታወቀው፣ ከአባይ ሰሜን በላይ ወደ ሚገኘው ደጋማ አካባቢ ይፈሳል፡፡ ከጠቅላላው 112,400 ኪ.ሜትር ካሬ ፣ የተከዜ የውሃ ምንጭ አካባቢ የሚሸፍነው 68,800 ኪ.ሜትር ካሬ ይሆናል፡፡ ይህም ገባሪ ወንዞችን ሁሉ አንድ ላይ እንዲካተቱ ካደረግን ነው፡፡

በሶስቱ ወንዞች የሚጓጓዘው የአፈር መጠን ከ1,285 ቢሊዮን ቶንስ የማያንስ እንደሆነ ተገምቷል፡፡ በለም አፈር በእጅጉ የበለፀገው የግብፅ የወንዝ ዳርቻ ለዓመታዊው ማዳበሪያ የሚተማመነው በዓመታዊው የአባይ ጐርፍ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መጠኑ 5 ተኩል ሚሊዮን ኤከርስ (135,802.5 ኪ. ሜትር ካሬ) የሚሆነው የሚታረሰው መሬት ውሃ የሚያገኘውም ከዚሁ ከአባይ ከሚመጣው ጐርፍ ነው፡፡

አባይ በከፍተኛ ደረጃ በሚፈስበት ወቅት (በየሰከንዱ እስከ 10,000 ኪውቢክ ሜትር) ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ወደ ሜዲትራኒያን ባህር ይፈሳል፡፡ በዚህም ምክንያት የውሃው መጠን በእጅጉ ከፍ ብሎ ወደ ሃያ ጫማ ሲደርስ ነጭ ኒል ኦምዱርማን ላይ (በዚያን ወቅት ለጊዜው) እንዲታገድ ይደረጋል፡፡[2] በኦምዱርማን አካባቢ በተወሰነ ወቅት የሚገኘው የነጭ አባይ የውሃ መጠን በእጅጉ ከፍ ሲል ሃያ ጫማ ይሆናል፡፡

ግብፅ «የአባይ ስጦታ ናት» ይባላል፡፡ ይህ ሊካድ የማይችል ሃቅ ሆኖ፣ ውሃውን እና በአባይ ተጭኖ የሚመጣውን ብርቅ አፈር የሚጠቀሙት ወገኖች ሁል

[2] A.B. Thompson, "The Water Problem of Ethiopia and Neighboring Countries," *International Affairs* (Nov. 1935), p. 770.

ጊዜም በማያቋርጥ ስጋት ውስጥ ነው የኖሩት:: ይህም ፍርሃታቸው የውሃው ፍሰት አንድ ቀን በከፍተኛ ደረጃ ቢቀንስ፣ ወይንም የውሃው ፍሰት ወደ ሌላ አቅጣጫ ቢለወጥ፣ የግብፅን ህልውና ለማናጋት ይችላል በማለት ነው:: ውሃው በሚመነጭበት አካባቢ የኖሩት (በኢትዮጵያ እና በኑብያ፣ የአሁኗ ሱዳን) በግብፃዉያን ላይ ሁሉንም ዓይነት ተፅእኖ ለማድረግ ይህን ፍርሃት በተለያየ ጊዜ ተጠቅመውበታል::

**የአባይን ዕድሜ ያህል የቆየ የአባይ ጉዳይ ታሪካዊ መሠረት**

ሔሮዶቱስ «ግብጽ የአባይ ስጦታ ናት» የሚለውን አባባል ለዓለም ከማበርከቱ በፊት ይሄ በኢትዮጵያውያንና በግብጻውያን ዘንድ ታውቆ የቆየ ነገር ነበር:: አባይ በሚያጓጉዘው አፈር በረሃውን ወደ ለም የእርሻ መሬትነት ሲለውጠው ግብጾች ሰፊ መኸር ለመሰብሰብ ሲታደሉ፣ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ወንዙ ለምና ወዛም የነበረውን የሰሜን ኢትዮጵያን መሬት እያጠበና እያራቆተ፣ ሰው ወደ ማይኖርበት የጨረቃን የገረጣ አካባቢ ወደ ሚመስል ኮረብታማነትና ሸለቆነት ሲለውጠውና የመሬትነት ጠባዩን ጨርሶ ሲያጠፋው፣ ዝም ብለው ሲያስተውሉት ኖረዋል::

ግብጾች ስለተሰጣቸው ታላቅ በረከት የተለያዩ አማልክቶቻቸውን እያመሰገኑ፣ ግሪኮች «የጨረቃ ተራሮች» ብለው ከሚጠሩበት (አባይ ከሚመነጭበት) አካባቢ የሚመጣውን ውሃና አፈር ጥቅም ላይ እያዋሉ፣ በወንዙ ዳርቻ ታላቅ ሥልጣኔ ለመፍጠር ችለዋል:: ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ ሰፊ የእርሻ ለም መሬት ባለቤቶች የነበሩት የቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን በግብጾች ዕድል የሚቀኑበት ምክንያት አልነበራቸውም:: ይህም ስለተባለ፣ የአባይ ጉዳይ በዚያን ጊዜም ቢሆን ተነስቶ አያውቅም ነበር ማለት አይደለም::

በጥንታዊው ዘመን፣ የሚፈሰው የአባይ ውሃ መጠን በቀነሰ ቁጥር፣ ጉዳዩ አሳሳቢ እየሆነ መነሳቱን ከታሪክ እንረዳለን:: የግብጽ ባለሥልጣኖች አልፎ አልፎ የአባይ ወንዝ በምንጩ አካባቢ በሚደርስ ድርቅ ምክንያት የፍሳሹ መጠን የሚቀንስ መሆኑን ባለመጠርጠር፣ ኢትዮጵያውያን ውሃውን የዘጉት ወይም ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲፈስ ያደረጉት እየመሰላቸው፣ ውሃውን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ነገሥታት ዘንድ በየጊዜው መልእክተኞች ይልኩ ነበር::

ለምሳሌ፣ታሪክ ጸሐፊው የዓረብ ተወላጅ አል ማኪን፣ ድርጊቱ ከሆነበት ጊዜ ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ ሲጽፍ፣ በፋቲሚድ ሥርወ መንግሥት በሡልጣን አቡ ታምሊን አል ሙስታንዚር የአገዛዝ ዘመን (1036-1094) ግብጽ የሚደርሰው የውሃ ብዛት በ1089-1090 አካባቢ ቀነሰ:: በዚህ የተነሣ ሡልጣኑ ወዲያውኑ የግብጽ ቤተ ክርስትያንን ፓትርያርክ አባ ሚካኤልን ከፍ ያለ ገጸ በረከት አስይዞ፣ ኢትዮጵያውያን የተቋረጠውን የአባይን ወንዝ እንዲለቁ ለመለመን፣ ወደ ኢትዮጵያ ላካቸው:: ጉዞውም በ1092 እና በ1094 ዓ.ም. ማህል ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር:: የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አንድ ኮረብታ እንዲፈርስ ባዘዘ ጊዜ የውሃው መጠን በአንድ ሌሊት ሶስት ጫማ ከፍ ብሎ አደረ ሲል ተርኮአል:: በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉስ የዛጉዌው ይምርሃነ ክርስቶስ ነበር::

በ0ሥራ አራተኛው መቶ ዓመት የግብጽ የማምሉክ ሡልጣን፣ አል ናሲር ሙሐመድ ኢብን ቃላኡን፣ በርካታ አብያተ ክርስትያናት የማፍረሱና ክርስትያን የሆኑ ዜጎቹን በጽኑ የማሰቃየቱ ዜና ወደ ኢትዮጵያ ደርሶ ከፍ ያለ የኀዘን ስሜት መፍጠሩን፣ ማቅሪዚ የተባለው የመቅረብ (ሞሮኮ) ተወላጅ ታሪክ ጸሐፊ በወቅቱ ዘግቦአል:: በታሪኩ ስሙ ባይጠቀስም፣ ከ1380 እስከ 1412 የነገሠው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዳዊት አንድ የልዑካን ቡድን ወደ ግብጽ ልኮ፣ የአባይን ወንዝ ፍሳሽ ወደ ሌላ አቅጣጫ በማዞር የግብጽን ሕዝብ በረሐብ ለመፍጀት እንደሚችል፣ ለግብጹ መሪ በብርቱ ማስጠንቀቅያ ገልጾለት እንደ ነበር ጽፎአል::

ኢብን ፋድል አላህ አልዑማሪ የተባለ አንድ የግብጽ ቤተ መንግሥት ባለሟል *ማሳሊክ አል አብሳር ፊ ማምሊክ አል አምሳር* (ቀጥታ ትርጉሙ «የነገሥታት ምድር ቅኝት») በሚል ርእስ በዘመኑ ያስተዋለውን የተለያየ ነገር ጽፎ ነበር:: በዚህ መጽሐፉ ሐበሾች (ኢትዮጵያውያን) ወደ ግብጽ የሚፈሰውን አባይን እንደሚቆጣጠሩና ለግብጽ ሡልጣን ከበሬታ ሲሉ ብቻ ውሃው እንደተለመደው ወደዚያ እንዲፈስ የሚፈቅዱ መሆናቸውን ይናገራሉ ሲል ገልጾአል::[3]

ግብጾች የአባይ ፍሳሽ አንዳንዴ የሚያንስበትን እውነተኛ ምክንያት ለማወቅ ከቻሉ በኋላ ግን የፊት ጊዜ ጥርጣሬአቸው ተወግዶ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች እስከ 0ሥራ ስምንተኛው መቶ ዓመት ፍጻሜ ድረስ በሰላም ለመኖር ችለዋል:: ናፖሊዎን (ግብጽን ከያዘበት፣ ከ እ.አ.አ 1798 እስከ 1801) ከዚያም ሞሐመድ አሊ ፓሻ (1805-1849)፣ ሰዒድ ፓሻ (1854-1863)፣ ኸዲቭ ኢስማኤል (1863-1879) እና እንግሊዞች (1882-1921) በአገሩ በተከታታይ ሥልጣን ከያዙ በኋላ ነው ሁኔታው የተለወጠው::

በቱርክ ሡልጣን የግብጽ ገዢ ሆኖ የተሾመው ሞሐመድ አሊ ፓሻ የማምሉኮችን ሥልጣን ካስወገደ በኋላ ጠንካራ የሆነ ማእከላዊ መንግሥት አቋቋመ:: መስኖዎችና የውሃ ግድቦች በመሥራት በስፋት የልማት እቅዶች ማከናወን ጀመረ:: ዘመናዊ የሆነ የጦር ኃይል ካደራጀ በኋላ የአባይን ሸለቆ አካባቢ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ፈልጎ እስከ ኢትዮጵያና ዩጋንዳ ወሰን ድረስ ያለውን የሱዳንን መሬት በ1812 (1820 እ.ኤ.አ) ያዘ::

የሞሐመድ ዓሊ ልጅና ወራሽ ሰዒድ ፓሻ ቀይ ባሕርን ከኤውሮፓ፣ ከሕንድና ከሩቅ ምስራቅ ጋር የሚያገናኘውን፣ የስዌዝን መተላለፊያ እንዲሠራ ለፈረንሳዩ መሃንዲስ፣ ለፌርዲናን ደ ሌሴፕስ ፈቀደለት::

ኸዲቭ ኢስማኤል መላውን የአባይን ሸለቆ በግብጽ ይዞታ ሥር ለማድረግ የታቀደውን የአያቱን የሞሐመድ ዓሊን ዓላማ ተከትሎ በመጀመሪያ በ1865 ምጽዋንና ስዋኪምን ለመያዝ የቱርክን ሡልጣን ሕጋዊ ፈቃድ አገኘ:: ቀጥሎ ሶማልያንና ሐረርን በ1868 በጦር ኃይል በመያዝ ኢትዮጵያን ለመክበብ ቻለ::

[3] Gandfroy - Demomby, Iban Fadl Allah al-Umari, *Masalih al-Absar fi Mamalik al-Amsar*, (Paris, 1972).

*ከዚያም በኅዳር እና በመጋቢት ወር 1868 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ ወረራ አካሄደ።*

*በኢትዮጵያ በተደረጉት ዘመቻዎች በግብጽ ጦር ሠራዊት ላይ በተከታታይ በደረሰው ከባድ ሽንፈት ምክንያት ኰሎኔል አሕመድ ዑራቢና አብረውት ያሉት መኰንኖች ምጽዋ ላይ የተቃውሞ ንቅናቄ ጀምረው ወደ ግብጽ ከተመለሱ በኋላ በንቅናቄው ገፉበት። በግብጽ ለተፈጠረው ብሔራዊ እንቅስቃሴ ቀስቋሽ የሆነው ይህ የመኰንኖቹ ንቅናቄ በመጨረሻ የኸዲቭ ኢስማኤልን ያገዛዝ ዘመን ዕድሜ አሳጥሮት «ማሕሩሳ» በተባለችው መርከቡ ወደ ኢጣልያ ለመሰደድ አብቅቶታል። ይህም የሆነው እ.ኤ.አ. በ1882 ዓ.ም. ነበር። እንግሊዞች በግብጽ የስዌዝን የውሀ መተላለፊያና ሌሎችንም ተቅዋማትና የልማት እቅዶች ለመሥራት ከፍ ያለ ገንዘብ ያወጡበትን ጥቅማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ በዚህ የብጥብጥ ጊዜ እስክንድርያን በመድፍ ደበደቡ፤ ግብጽንም በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉ።*

*የመንግሥታትና የሥርወ መንግሥታት መምጣትና መሔድ ወይም መነሣትና መውደቅ በታሪክ ሂደት ውስጥ ሲታይ የኖረ ነገር ነው። ብዙ ሺህ ዓመት ዕድሜ የሚቆጥረው የኒል ጉዳይም በሸለቆው ውስጥ የሚገኙትን ሕዝቦች ግንኙነት በሚነካ መልኩ እንደዚሁ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ጉዳይ መሆኑም የማያጠራጥር ነው። የኒል ተፋሰስ አገሮችና መንግሥታት ከጥቅማቸው አንጻር ብቻ እያዩ የሚወስኑት ወይም የሚከተሉት ፖሊሲ በኒል ወንዝ ላይ አወዛጋቢ ሊሆን የሚችል ተጽእኖ ማስከተሉ የማይቀር ነው።*

*ከታሪክ እንደምንረዳው የተለያዩ የኢትዮጵያ ነገሥታት የአባይን አቅጣጫ እንለውጣለን ብለው በመዛት ግብጽ በክርስቲያኖች ላይ ከምትፈጽማቸው አንዳንድ የጭቆና ተግባራት እንድትቆጠብ ለማድረግ ተጠቅመውበታል።*

*እንዲሁም እንግሊዞች ሱዳንን ሲያስተዳድሩ ግብፅ እንድትኖር ወይንም እንድትንኮታኮት ለማድረግ ቁልፍ መሣሪያ በእጃቸው ነበራቸው። ለምሳሌ ኅዳር 24 1924 (እ.ኤ.አ) የእንግሊዝ ተወካይ በካይሮ በተገደለበት ወቅት ፣ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተሰጠው ማስጠንቀቂያ፣ በእንግሊዝ ሥር ያለው የሱዳን የጥምር አገዛዝ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሱዳን ውስጥ በገዚራ በተቋቋመው ድርጅት በመስኖ የሚለማው 300,000 ፋዳን (126,000 ሄክታር) ባልተወሰነ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ የእርሻው ማሳ ከፍ እንደሚል ለግብፅ አሳወቀ። ስለ ተሰጠው ማስጠንቀቂያ በፓርላማ በቀረበ ትችት፣ የእንግሊዝ መንግሥት ግብፅን በረሃብ በመቅጣት እጇን እንድትሰጥ ለማድረግ ይፈልጋል ወይ? የሚል ከፍተኛ ተቃውሞ ያዘለ ጥያቄ ተነሣ። በወቅቱ የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት በሰጡት መልስ ፍላጐቱ ይህ አይደለም በማለት ለአንግሎ - ግብፅ ትብብር ሁኔታ ታማኝ እና ፈቃደኛ የሆነ መንግሥት በግብፅ ካለ፣ ውሳኔው እንደሚሻርና ወደ ግብፅ የሚፈሰው ውሃ እንዳይቀንስ ከሱዳን ጋር ሁኔታዎች እንደሚመቻቹ፣ ለሚመለከተው ወገን ሁሉ ሁኔታውን ግልጽ አድርገዋል።*

*የኒል ሸለቆ ኅብረት የሚለው በሞሐመድ ዓሊ ፖሻ፣ በኬዲቭ ኢስማኤል እና በንጉሥ ፋሩክ የተነደፈው የግብጽ ዕቅድ፣እ.ኤ.አ በ1952 ከተከሰተው አብዮት በኋላ የሞሐመድ ዓሊ ሥርወ-መንግሥት አፍራሽ በሆኑት በፕሬዚዳንት ጀማል*

አብደል ናስር በከፍተኛ ደረጃ እንዲንቀሳቀስ ተደርጓል:: የኒል ሸለቆ ሀገሮች በግብፅ ተፅእኖ ሥር እንዲወድቁ ለማድረግ የተዘጋጀው ይህ ዕቅድ በየሃገሮቹ በሚገኙት ወገኖች ድጋፍ፣ በፀረ ኢምፔሪያሊዝም ፕሮፖጋንዳና ግብፅ እውን ለማድረግ በማትችለው በታንክ ኃይል ብቻውን ተፈጻሚ ሊሆን አለመቻሉ ሲታወቅ፣ ናስር ይህንን ዓላማ ትተው በምዕተ ዓመቱ የውሃ ማከማቻ ግንባታ ፕሮግራም እንዲተካ አደረጉ:: በዚህ ፕሮግራም መሠረት፣ በየ100 ዓመት ከሚከሰተው ድርቅ ግብፅን ለማዳን፣ ከፍተኛ መጠን ያለው የውሃ ማጠራቀሚያ ግድብ ለመሥራት ታቀደ::

በግብፅ፣ የኒልን ውሃ ሥርዓት ባለው መልኩ ለማጥናት እና የመስኖ ግብርናን ለማስፋፋት፣ እቅዶችን ማዘጋጀት የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው:: የኒልን ውሃ (ለመስኖ እና ለኃይል ማመንጫ) ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ጥናትና እቅድ የተካሄደው እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ እና 40ዎቹ አካባቢ ነው:: በዚህም መሠረት የምዕተ ዓመቱ የውሃ ማጠራቀሚያ የሚለው ፕሮግራም ተዘጋጀ:: በአንድ በኩል በታላቋ ብሪታኒያ እና በግብፅ መካከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በላይኛው የኒል ተፋሰስ አገሮች ቅኝ ገዢዎችና፣ እና በግብፅ መካከል እ.ኤ.አ ከ1891 እስከ በ1929 ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተደርገዋል:: እነዚህ ስምምነቶች ሁሉ የተዘጋጁት የኒል ውሃ፣ ለታችኞቹ የተፋሰሱ አገሮች በማያቋርጥ መልክ የሚፈስ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ነው::

ከእነዚህ ስምምነቶች አንደኛው እ.ኤ.አ ግንቦት 15 1902 የተፈረመው የአንግሎ-ኢትዮጵያ የወሰን ስምምነት ነው:: የዚሁ ስምምነት አንቀጽ 3፡-

> ግርማዊ ጃንሆይ አፄ ምኒልክ፣ ከግርማዊ ታላቋ የብሪታንያ መንግሥት እና ከሱዳን መንግሥት ጋር ስምምነት ሳያደርጉ፣ በጥቁር አባይ ፣ በጣና ሃይቅ እና በሶባት ላይ የወንዙን የውሃ ፍሰት የሚገድብ ምንም አይነት የግንባታ ሥራ አያካሂዱም፤ ወይንም ምንም አይነት የግንባታ ሥራ እንዲካሄድ አይፈቅዱም::[4] ሲል ደንግጓል::

ግብፅ እና ታላቋ ብሪታንያ በሱዳን ስም፣ ከላይኞቹ የኒል ተፋሰስ አገሮች ጋር ምንም ዓይነት ምክክር ሳያደርጉ፣ የኒልን ውሃ በመካከላቸው ለመከፋፈል ስምምነት ተፈራረሙ:: ታላቋ ብሪታንያ፣ በኮንዶሚኒየሙ ስም ሱዳንን ወክላ፣ ከግብፅ ጋር ግንቦት 7 1929 እ.ኤ.አ በተደረገው ስምምነት መሠረት፣ ለግብፅ በየአመቱ 48 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ተፈቀደላት:: ይህም የግብፅ ታሪካዊ መብት እንደሆነ ተደርጎ ተቆጠረ:: ሱዳን ደግሞ በየዓመቱ 4 ቢሊዩን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ብቻ እንድታገኝ ተፈቀደላት::

ግብፅ በየዓመቱ ከ60 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ በላይ የሚሻ፣ ከ3 ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት አልምታ፣ ለመስኖ እርሻ አውላለች:: ሱዳን ደግሞ በየዓመቱ 16 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ የሚሻ፣ 2 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን መሬት በመስኖ እንዲለማ አድርጋለች:: ሌሎቹ የተፋሰሱ አገሮች

---

[4] Sir Edward Herstlet, *The Map of Africa by Treaty*, Vol. 2 (London, 1976), p. 585.

እስካሁን ድረስ ጥቅም ላይ ያዋሉት ውሃ በእጅጉ ትንሽ ነው፣ ወይንም ለመስኖ ግብርና ውሃውን ጥቅም ላይ ለማዋል ያደረጉት ጥረት ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

የጣና ሃይቅን በተመለከተ፣ እ.ኤ.አ በ1925 ለተደረገው የአንግሎ-ኢጣሊያ ስምምነት የአፀፋ ምላሽ ለመስጠት፣ አዛዥ ወርቅነህ እሸቴ (ዶክተር ቻርልስ ማርቲን) ወደ አሜሪካ ተልከው ነበር። እርሳቸውም ከፕሬዚዳንት ኩሊጅ ጋር ተገናኝተው፣ ከኒውዮርኩ ጄ.ጂ. ኋይት ኤንጂንየሪንግ ኮርፕሬሽን ጋር ኅዳር 3 1927 እ.ኤ.አ ስምምነት ተፈራረሙ። የኋይት ኢንጂንየሪንግ ኮርፕሬሽን በራሱ ወጪ ግድብ እንዲሠራ፣ እንደዚሁም ውሃውን ለሱዳን በመሸጥ ትርፍ እንዲያገኝ እና ለኢትዮጵያ መንግሥትም የሮያሊቲ ክፍያ ለመፈፀም ተስማምቶ ነበር።

የጄጂ. ኋይት ኤንጂንየሪንግ ኮርፕሬሽን እ.ኤ.አ በ1930 እና 34 መካከል የጣና ሃይቅን ጥናት ሙሉ በሙሉ ከማጠናቀቁም በላይ፣ ግድቡ የሚገነባበትን ቦታም በሁለት የመስክ ጉዞዎች ጐብኝቷል። የግድቡ ወጪም ከ10-15 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚሆን ገምቶ ነበር። የግድቡ ፕሮጀክት ሳይከናወን ቀርቷል። የዚህም ዋናው ምክንያት፣ በአንድ በኩል በዲፕሎማሲው መስክ በብሪታኒያ እና በኢጣሊያ የተደረገው ግፊት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በወልወል የኢጣሊያ ወረራ ችግር ምክንያት ታኅሣሥ 1934 እ.ኤ.አ የተጀመረው የኢጣሊያ-ኢትዮጵያ ግጭት ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና አማካሪ የነበረው ጆን እስፔንሰር እንደፃፈው፡-

> ከ1945 እ.ኤ.አ ጀምሮ ግብፅ ምንም እንኳን ውጤት ባታገኝም ቅሉ የአባይ ውሃን ጉዳይ ለማንሳት ፈልጋ ነበር። ኢትዮጵያ የወንዞችዋን ውሃ በተመለከተ ለግብፅ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት በግብፅ በኩል ጠቀሜታ ያለው የአፀፋ አወንታዊ መልስ ሳይገኝ ከግብፅ ጋር ስምምነት ለማድረግ ምንም አይነት ፍላጐት አልነበራትም። ከዚህም በላይ በፖሪስ በተደረገው የሰላም ጉባኤ ኢትዮጵያ በኤርትራ ጉዳይ ባላት የይገባኛል ጥያቄ ላይ ግብፅ ተቃውሞ ማንሳቷ፣ እንደዚህ ያለው ድርድር እንዲካሄድ የሚረዳ አልነበረም። በዚህ የተነሳ የግብጽ ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል።[5]

### የአስዋን ከፍተኛ ግድብ ኢትዮጵያ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ለመቋቋም ኢትዮጵያ የወሰደቻቸው እርምጃዎች

ሊሠራ የታቀደው የአስዋን ከፍተኛ ግድብ ከወጪ አንጻር በጣም ከፍተኛ በመሆኑ፣ የዓለም ባንክ ጠቅላላውን ወጪ ለመሸፈን ያልተዘጋጀ መሆኑ ሲታወቅ፣ በቴክኒክ ረገድ ስምምነት ከተደረሰና የአሜሪካ እና የእንግሊዝ መንግሥታት ተጨማሪ እገዛ የሚያደርጉ ከሆነ፣ የዓለም ባንክም በበኩሉ ከወጪው ለመሳተፍ ዝግጁ እንደሚሆን አስታውቆ ነበር።

[5] John Spencer, *Ethiopia at Bay* (East Lansing, 1978), p. 188

*ግብፅ በሶቪየት የገንዘብ ወይንም የቴክኒክ እርዳታ እንዳትተማመን ለማድረግ የአሜሪካ እና የእንግሊዝ መንግሥታት በዕቅዱ ተካፋይ ለመሆን ፍላጐታቸውን በቀጥታ አሳይተው ነበር። ግን እነርሱ በጉዳዩ ላይ በገንዘብም ሆነ በፖለቲካ ረገድ የሚኖራቸው ተሳትፎ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንደሚሆን እና ግድቡ ከመሠራቱ በፊት ወደ ጐርፉ ውሃ ማከማቻ ሃይቅ የሚፈሰውን ውሃ ወደፊት እንዲቀንስ የሚያደርግ፣ የኒል ውሃን ጥቅም ላይ የሚያውል፣ የኢትዮጵያ ዕቅድ መኖር አለመኖሩን በቅድሚያ ለማወቅ ፍላጐት ነበራቸው። ይህ እጅግ ግዙፍ የሆነ ሃይቅ በሱዳን ወሰን የሚያቋርጠውን ውሃ ከማከማቸቱ በላይ፣ ከፍተኛ በሆነ የሱዳን መሬት ላይ ለዘለቄታው የሚንጣለል ነው። ሱዳን በዚህ ምክንያት ከግዛት አኳያ እና ለአቀደቻቸው የመስኖ ፕሮግራሞች ተጨማሪ ውሃ በማግኘቱ ረገድ ቀጥተኛ የሆነ ፍላጐት እንዳላት ገለጸች። የዓለም ባንክ የቀረበውን የግድብ ወጪ ለመሸፈን፣ በቅድመ ሁኔታነት የውሃውን ክፍፍል በተመለከተ፣ ሱዳን እና ግብፅ ያደረጉትን ስምምነት በሚያረካ መልኩ እንዳሻሻለው ተዘግቦ ነበር።*

*የግብፅ መንግሥት፣ በአስዋን ላይ የሚገነባው ከፍተኛ ግድብ፣ የግብፅን የውሃ ችግሮች በአንድ ትልቅ ፕሮጀክት አማካይነት ለመፍታት፣ በጣና ሃይቅ አፍ ላይ ወይንም በአባይ በታችኛው ክፍል የሚገነቡትን ግድቦች መቆጣጠርን ጨምሮ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ከስምምነት ለመድረስ እንደሚያስችለው ተማምኖ እንደ ነበር ይገመታል። የግብፅ መንግሥት፣ የዓለም ባንክ፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት የከፍተኛውን ግድብ ጠቅላላ ጉዳይ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር አለማንሣታቸው ይህንን አመለካከት ይደግፋል።*

*ወደ ግብፅ የሚፈሰው ውሃ እንዳይቀንስ ኢትዮጵያ የምትጠየቅ ከሆነ፣ በኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመው ግብረ-ሃይል እንደዚህ ያለው ጥያቄ ውድቅ መደረግ እንደሚገባው እና እንደዚሁም ያለምንም ጥርጥር የግድቡን ግንባታ የሚያዘገዩ ድርድሮች መደረግ እንደሚገባቸው፣ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ነበር። የናስር መንግሥት፣ ከግብፅ ውስጣዊ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች አንፃር ዕቅዱን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ያለበት በመሆኑ፣ እንደዚህ ያለው መዘግየት በግብፅ ላይ ብዙ ጣጣ እንደሚያስከትል ግልፅ ነበር። በተመሳሳይ መልኩ፣ አሜሪካ እና እንግሊዝ እንደዚህ ያለው ሁኔታ ከተከሰተ፣ ለግድቡ ግንባታ መዘግየት ኢትዮጵያን ተጠያቂ የሚያደርግ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ ስለማያጠራጥር፣ የዚህ ዓይነቱ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ግልፅ ነበር።*

*ከዓለም ባንክ፣ ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የሚደረጉት የገንዘብ ድርድሮች ተጠናቀው፣ የኢትዮጵያ ማረጋገጫ ሳይገኝና ኢትዮጵያ ውሃዋን በአግባቡ ለመጠቀም ባላት መብት መሠረት በጉዳዩ ላይ ላላት ተቃውሞ ኦፊሴላዊ ግንዛቤ ሳይወሰድ ግድቡ ቢገነባ፣ ኢትዮጵያ ነገሩን በዝምታ ለማሳለፍ እንደተስማማችና የአባይ ውሃን ፍሰት ለመቀነስ ምንም አይነት እርምጃ ከመውሰድ እንደምትቆጠብ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል። ይህ አደገኛ ነገር ሲሆን፣ ግብጽና ሱዳን ወደዚህ አቋም ዘንበል ማለታቸው አያጠራጥርም። ከዚህ ሁሉ በላይ፣ አሜሪካና እንግሊዝ ግድቡን ለመሥራት በሚያደርጉት የገንዘብ አስተዋጽኦና ግብጽ የምግብ ፍላጎትዋን ለሟሟላት ባለባት አጣዳፊ ሁኔታ፣*

በፓሊቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ረገድ ለመርዳት በሚያደርጉት ተሳትፎ መጠን የግብጽን አቋም ለመደገፍ ይገደዱ ይሆናል ተብሎ ተገመተ።

ጥያቄው ባጭሩ፣ ኢትዮጵያ ወንዞቿን በአግባቡ ለመጠቀም ያላትን መብት በወቅቱ መግለፅ ይገባት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነው። ጉዳዩ በመጀመሪያ ከሕግ አንፃር ሲጤን፣ ማንም ቢሆን መብቱን ለማስጠበቅ እርምጃ እንዲወስድ የሚያስገድደው ሁኔታ አልነበረም። በእርግጥ ጥያቄው ከግል የሕግ ሁኔታ፣ የግል የመሬት ባለቤቶችን የሚመለከት ከሆነ፣ የላይኛው ተፋሰስ የመሬት ባለቤት ግድብ ለመገንባት ዝግጅት ለሚያደርገው ለታችኛው ተፋሰስ የመሬት ባለቤት መብቱን ወይንም ተቃውሞውን ለመግለፅ አይገደድም። በሁለቱም፣ በዓለም-አቀፍ ሕግና በግል ሕግ መሠረታዊው ደንብ፣ ከጋራ ምንጭ የሚመነጨውን ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ፣ አግባብነት ባለው መልክ ተጠቅሞ ጥቅም ላይ የዋለውን ውሃ አግባብነት ባለው መልኩ ወደ ፈሳሹ ወንዝ እንዲመለስ ማድረግ ነው። ይህ መርህ፣ ለምሳሌ፣ በፖኪስታን እና በአፍጋኒስታን እና በህንድ መካከል ባሉት የውሃ ውዝግቦች ላይ ተቀባይነትን አግኝቷል።

እንደ እነዚህ ባሉት ሁኔታዎች፣ የበላይ ተፋሰስ ሀገርን መብትን ለመያዝ እና ለመጠበቅ በሕጉ ረገድ እንደዚህ ያለ ግዴታ የሌለ በመሆኑ፣ አንድ አገር ለበታች የተፋሰስ አገር ግልፅ የሆነ ተቃውሞ በማቅረብ ይህንኑ እንድታፀና ትገደዳለች። ስለዚህ ቀሪው ብቸኛው ጥያቄ፣ እንደዚህ ያለ ኦፊሴላዊ ተቃውሞ ከተግባራዊ ወይንም ከፖለቲካ ምክንያቶች አንፃር፣ አስፈላጊ ነው ወይ የሚለው ነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት ቢደረግ ኖሮ፣ ለሚወሰደው እርምጃ ወይንም የተቃውሞ መግለጫ፣ በሌላው ወገን ሊሰጥ የሚችለው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል። የዓለም ባንክ፣ ሱዳንን በተመለከተ እንደ ወሰደው ተመሳሳይ እርምጃ ሁሉ የኢትዮጵያን የውሃ ፍላጐት፣ የውሃ አጠቃቀም ፕሮግራሟን (የመስኖ ወዘተ) እንዲያረጋግጥ እና ኢትዮጵያ ግልፅ የሆኑ ማረጋገጫዎችን እንድትሰጥ፣ በኢትዮጵያ ላይ ተፅእኖ እንዲያደርግ ግፊት እንደሚደረግበት ምንም አይነት ጥርጣሬ አይኖርም። እንደዚሁም፣ ከኢትዮጵያ ጋር የሚደረሰውን መስማማት የግድቡን ወጪ ለመሸፈን በባንኩ በቅድመ ሁኔታነት እንዲቀመጥ መደረጉ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። ለግብፅ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነ ፕሮግራም እውን እንዳይደረግ በማያዣነት በመያዙ፣ የዓለም ባንክ በመላው ዓለም ሊደርስበት የሚችለውን ወቀሳ ለማስቀረት እንዲቻል፣ ኢትዮጵያ በወንዞቿ ላይ ለመጠቀም ያልተዘጋጀች፣ ይህንንም እውን ለማድረግ የማትችል ስለመሆኗ ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ከማንሳት አይቆጠብም። በተመሳሳይ መልኩ፣ ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ ዓላማ አኳያ፣ ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ማንኛቸውም መግለጫ፣ እነዚህ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ ተፅእኖ እንዲያደርጉ ያደርጋል። ማለትም፣ ኢትዮጵያ ከግብፅ እና ከሱዳን ጋር ስምምነት ላይ እንድትደርስ ተፅእኖ ያሳድራሉ።

ኢትዮጵያ ወጥመድ ውስጥ እንድትገባ ወይንም ማንኛቸውንም ግልፅ የሆነ መግለጫ እንድትሰጥ ተፅእኖ የሚደረግባት ከሆነ፣ በሱዳን ላይ ደርሶ የነበረው

ተመሳሳይ ሁኔታ ይደርስባታል:: የውሃ ፍላጐቷን በተመለከተ፣ መግለጫዎችን ሰጥታ ድርሻዋ እንዲጨመርላት ግብፅን መጠየቅ ይኖርባታል፤ ከግብፅ ጋር ለመደራደርም ዓለም- አቀፍ ባንክ በሚያደርግላት እርዳታ ላይ እንድትተማመን ያደርጋታል:: በሌላ በኩል፣ ኢትዮጵያ የዓለም ባንክ ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች የራሷን ውሃ በአግባቡ ለመጠቀም ከዓለም አቀፍ ህግ አኳያ ያላትን መብት ደጋግሞ በመግለፅ ብቻ ምላሽ የምትሰጥ ከሆነ፣ እንደዚሁም ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ ዲፕሎማሲያዊ ተፅእኖ የሚደረግባት ከሆነ፣ በመጨረሻ በአሁኑ ወቅት የውሃውን ፍሰት ሊቀንሱ የሚችሉ እና ውሃውን በከፍተኛ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችሉ ምንም አይነት እቅዶች የሉም ብላ ለመግለፅ ብትገደድ፣ ክብሯን የሚቀንስ ተግባር ይሆናል:: ከሁሉም በበለጠ ደግሞ፣ ከዚያ በኋላ በግልፅ ከታወቁት እና ከተገለፁት የግብፅ፣ የአሜሪካ እና የእንግሊዝ አቋሞች ጋር ልትጋፈጥ ትችላለች:: ማለትም፣ ሁሉም የኢትዮጵያ የወደፊት እቅድ ወደ ከፍተኛው ግድብ የሚደርሰውን የውሃ መጠን መንካት የለበትም በማለት ወይንም የዚሁ አንድምታ ያለው መልዕክት በማስተላለፍ፣ ሁሉም በጉዳዩ ላይ እጃቸውን የሚያስገቡ ይሆናሉ::

በአጠቃላይ፣ የታወቁትን ዲፕሎማሲያዊ ጥያቄዎች እና ግፊቶች በተመለከተ በራሷ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተግባራዊ እና ፖለቲካዊ ተጽእኖዎች ሲታዩ፣ ኢትዮጵያ በውሃው ላይ ለመጠቀም ያላትን መብት ከመግለጧ በፊት ቅድሚያ ዝግጅት ማከናወን እና እንደዚህ ያለ እርምጃ መውሰዱ አያስፈልግም ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሶ በዚሁ ተወሰነ::

* * *

በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ እና በዓለም ባንክ ተሳትፎ የአስዋንን ከፍተኛ የውሃ ግድብ ፕሮጀክት ለማገዝ የመጀመሪያ ደረጃ ስምምነት ላይ ተደርሷል የሚለው መግለጫ ሲሰማ፣ የኢትዮጵያን ሕጋዊ መብት ለማረጋገጥ የመጀመሪያው የአፀፋ እርምጃ፣ በጣና ሃይቅ ወይንም በጢስ አባይ መግቢያ ላይ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የሚያስችል ግድብ ለመገንባት የሚችል ተአማኒነት ያለው ኩባንያ በአስቸኳይ ማግኘት ነው የሚል አሳብ ቀረበ::

እኔ በወቅቱ፣ በምክትል ሚኒስትር ደረጃ፣ ሥራና መገናኛ ሚኒስቴርን እመራ ስለነበር፣ ናቪጋ ጣና እየተባለ ከሚጠራ የአገር ውስጥ የጣሊያን ኩባንያ ጋር በመተባበር፣ ባቲኞል በሚባል የፈረንሳይ ኩባንያ እንዲካሄድ ታቅዶ የነበረውን የጢስ አባይ ግድብ ሥራ እንድቆጣጠር፣ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ታዘዝኩ::

ለመነሻ በተደረገው ጥናት፣ በጣና ሃይቅ መግቢያ ላይ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያ መገንባቱ ምንም ዓይነት ተግባራዊ ጠቀሜታ የለውም የሚል አስተያየት መኖሩን ተረዳሁ:: በዚህ ቦታ ላይ የሚገነባ የኃይል ጣቢያ ከማናቸውም ሊታዩ ከሚችሉ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ማዕከላት በጣም የራቀ ነበር:: በተጨማሪም የኃይል ማመንጫው አቅም በጣም አነስተኛ ይሆናል:: እንደዚሁም በቂ የሆኑ

የቅድሚያ ጥናቶች ሳይደረጉ እና የጨረታ ውድድር ሳይደረግ፣ እንደዚህ ያለውን ከፍተኛ ፕሮጀክት መስጠቱ አግባብነት አይኖረውም፣ የሚል ሃሳብ አቀረብኩ:: በዚህም ምክንያት፣ በወቅቱ ዝነኛ የነበሩት ሃይድሮሎጂስት፣ ስዊድናዊው ፕሮፌሴር ሄልስትሮም ሃሳባቸውን እንዲያማክሩን አመጣናቸው:: በየካቲት ወር 1956 እ.ኤ.አ በአደረጉት ጉብኝት፣ ሄልስትሮም የሰጡት አስተያየት፣ ከባቲኞልና ከናቪጋ ጣና በቀረበው ሃሳብ ላይ የነበረውን ተቃውሞ የሚያረጋግጥ ነበር::

እንደ ሄልስትሮም አመለካከት ከሆነ፣ ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግንባታ በእጅጉ ተስማሚ የሚሆነው ከሃይቁ ርቆ በሚገኝ ቦታ ላይ ቢሆን ነው:: ከወንዙ አቅጣጫ ሲለካ፣ ከጣና ሃይቅ 325 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ከደብረ ማርቆስ በስተ ደቡብ በኩል ጥሩ የግድብ ቦታ እንዳለ በማረጋገጥ፣ የየቀኑን ጭነት ልዩነት ፍላጐት ለሚሟላት በሃይድሮ ኤሌትሪክ ጣቢያው ላይ አነስተኛ የውሃ ማጠራቀሚያ እንደሚያስፈልግ አሳሰቡ::

በሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫው ጣቢያ ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ውሃ በከፊል ከጣና ሃይቅ የሚመጣ ሲሆን፣ በከፊል ደግሞ በሐይቁ እና በኤሌክትሪክ ማመንጫው ጣቢያ መካከል ከሚገኘው ወንዝ ይገኛል:: ከሃይቁ መውጫ ላይ ያለው የውሃ ማሰባሰቢያ ቦታ በግምት 16,800 ኪ.ሜትር ካሬ ይሆናል:: እንደዚሁም፣ በመልካ ቀሎ ላይ በግምት 78,800 ኪ.ሜትር ካሬ ይሆናል::[6] ስለዚህ በሃይቁ እና በኃይል ማመንጫው ጣቢያ መካከል ያለው የውሃ ማመንጫ ቦታ 62,000 ኪ.ሜትር ካሬ ነው:: ወደ አዲስ አበባ የማስተላለፊያው መስመር ርዝመት 150 ኪ.ሜትር ብቻ ይሆናል ማለት ነው::

ወደ ኃይል ማመንጫው ጣቢያ የሚሄድ የተስተካከለ የውሃ ፍሰት ለማግኘት፣ የውሃ ማጠራቀሚያ ያስፈልጋል:: ይህ የውሃ ማጠራቀሚያ በጣና ሃይቅ አካባቢ የሚቋቋም እንደመሆኑ መጠን፣ ይህ ሃይቅ ለውሃ ማጠራቀሚያ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ይውላል ማለት ነው:: ለዚህ ዓላማ የሚያስፈልገው ውሃ ለመስኖ ከሚያስፈልግው ውሃ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፤ ማለትም፣ በበጋው ወራት የጣና ሃይቅ ለመስኖ ልማት እንደ ውሃ ማጠራቀሚያ ተደርጐ ያገለግላል:: በመጨረሻም፣ ለጐርፍ መከላከያ መጠነኛ የውሃ ማጠራቀሚያ መቀመጥ ይኖርበታል::

ቀደም ሲል በጣና ሃይቅ ላይ የተካሄዱት አብዛኛዎቹ ጥናቶች የተደረጉት በግብፅ እና በሱዳን በነበረው የእንግሊዝ አስተዳደር ጊዜ ነበር:: በ1902/03 እ.ኤ.አ የግብፅ ሥራ ሚኒስቴር ባልደረባ በነበረው በሲ. ኢ. ዱፑየስ (C.E. Dupius)፣ እንደዚሁም የአንግሎ-ግብፅ ሱዳን ጂኦሎጂስት በነበሩት በጂ. ደብሊዩ ግራሃም (G.W. Graham) እና በግብፅ መንግሥት የሥራ ሚኒስቴር የፊዚካል መምሪያ አባል በነበሩት አር.ፒ. ብላክ (R.P. Black) ከ1920-24 እ.ኤ.አ በነበረው ጊዜ

[6] መልካ ቀሎ አባይን ለመሻገር ከሚያመቹት ቦታዎች (መልካዎች) አንዱ ሲሆን፣ የሚገኘውም በምስራቅ ወለጋ ዞን ውስጥ በሊሙ ወረዳ ነው::

ተጠንቷል፡፡[7] እንደዚሁም በሜጀር አር. ኢ. ቺዝማን (R.E. Cheesman) የቅኝት ጥናት ተደርጎ ነበር፡፡[8] ጄጂ ኋይት ኢንጂንየሪንግ ኮርፖሬሽን (J.G White Inc.) የጣና ሃይቅን ቃኝቶ፣ የሃይቁን መውጫ ለመቆጣጠር እንዲቻል ግምት እንዲያቀርብ፣ በኢትዮጵያ መንግሥት ተጋብዞ የነበረው ድርጅት ከ1929-1934 እ.ኤ.አ አንዳንድ ጥናቶች አድርጓል፡፡[9] እንደዚሁም፣ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት በኤል.ፖንቴ ኮርቮ (L. Ponte Corvo) የጣናና የአባይ ጥናት ተካሂዷል፡፡[10]

እነዚህ ሁሉ ጥናቶች፣ የጣና ሃይቅ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለሚያደርግ ባለብዙ ፈርጅ ፕሮጀክት፣ በከፍተኛ ደረጃ ተስማሚ ሊሆን እንደሚችል አረጋግጠዋል፡-

1. ሃይቁን በመቆጣጠር እና የሃይቁን ከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ እጅግ በአየለ ሁኔታ ይከሰት የነበረውን የጐርፍ አደጋ ለመከላከል፣
2. ሃይቁን በመቆጣጠር ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያ የሚሆን የውሃ ማጠራቀሚያ በማስገኘቱ ረገድ ፣ ከዚህ በተጨማሪም ወደ ኃይል ማመንጫው የሚፈሰው ውሃ በበጋው ወራት እንዲጨምር ለማድረግ ያስችላል፤ በዚህም ምክንያት፣ በኃይል ማመንጫው ዓመቱን ሙሉ ውሃ እንዲገኝ ያስችላል፤
3. በአባይ ለውሃ ማጠራቀሚያ በእጅጉ ተስማሚ ከሆኑት ቦታዎች አንደኛው የሆነውን የጣና ሃይቅ በመቆጣጠር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ለመስኖ ዓላማ ውሃ ለማቅረብ ያስችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች እውን ለማድረግ በሃይቁ መውጫ ላይ መቆጣጠሪያ መገንባት ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሠረት የውሃውን ደረጃ ዝቅ ለማድረጉ ዓላማ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ለማንቀሳቀስ መቆጣጠሪያው በብረት በሮች የሚዘጉ መክፈቻዎች ሊኖሩት ያስፈልጋል፡፡

ቀደም ሲል በጣና ሃይቅ ላይ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች በወንዙ መሠረት አጋማሽ ላይ ዐሥር ኪ.ሜትር ርዝመት ያለው ጥልቅ የውስጥ ለውስጥ የውሃ ቦይ በመቆፈር ውሃ ከሃይቁ እንዲወጣ የሚል አስተያየት ቀርቧል፡፡

የሃይቁ የውሃ ማጠራቀሚያ አቅም እስከ ከፍታው ድረስ፣ ማለትም በሃይቁ የውሃ ደረጃ መካከል እስከ ከፍተኛው ዝቅተኛ ቦታ ድረስ ያለው መጠን 1 ተኩል ሜትር ሲሆን፣ ሊይዝ የሚችለው 4 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ

---

[7] William Garstin, *Report on the Basin of the Upper Nile* (Cairo, 1904); H.E. Hurst, R.P. Black and Y.M. Simaika, *The Nile Basin* Vol. VII (Cairo, 1946).
[8] R.E. Cheesman, *Lake Tana and the Blue Nile* (London, 1936)
[9] J.G. White, *Corporation Report on Lake Tana Outlet Works and the Ethiopian Highway from Addis Ababa to Lake Tana, 1933-1935.*
[10] L. Ponte Corvo, *Engineering Problems in Colonial Territories* (Rome, 1938); *idem, L'Africa Orientale Italiana ed il Nilo* (Roma, 1939).

ነው:: አንዳንዶቹ እንደ ገመቱት፣ የጣና ሃይቅ የውሃ ማጠራቀም አቅሙ እስከ 11 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ይደርሳል::

የኢትዮጵያን የተፋሰስ መብት በማረጋገጡ ሂደት የአባይን ተፋሰስ በሚገባ መርምሮ ለመስኖ ዓላማ የሚያስፈልገውን የውሃ መጠን መወሰኑ ዓይነተኛው ጉዳይ ስለሆነ፣ የባቲኞል - ናቪጋ ጣና የውሃ እቅድ ውድቅ ሆነ:: በተወሰነ ፕሮጀክት ላይ ከመሰማራት ይልቅ፣ ትኩረት መሰጠት የሚገባው ጉዳይ የሃይድሮሎጂ ጥናቶችን ለመጀመሩ እና የጥቁር አባይ ውሃ ተፋሰስ ጥናት ለማካሄዱ ተግባር እንዲሆን ተወሰነ::

**በዋሽንግተን የተደረገ ውይይት**

በ 1948 ዓ.ም. (በ1956 እ.ኤ.አ) የፀደይ ወቅት፣ ከዓለም ባንክ ጋር የሁለተኛውን የአውራ ጐዳና ብድር ለመደራደር፣ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላኖች መግዣና የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎች ማሠሪያ ከአሜሪካ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ብድር ለማግኘት፣ ወደ አሜሪካ መሄድ ነበረብኝ:: ከእኔ ጋር አብረው የተጓዙት ሚስተር ሮበርት እስኮት ሲሆኑ፣ ከእርሳቸውም ጋር ቀደም ሲል ከ4 ዓመታት በፊት (በ1943 ዓ.ም.) በሮማ ከኢጣሊያ ጋር የጦር ካሳ ድርድር ስናደርግ በቅርብ ሠርተን ነበር:: በዋሽንግተን ዲ. ሲ. ቆይታችን ወቅት የአባይን ጥያቄ በተመለከተ፣ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ለመወያየት አጋጣሚውን ተጠቀምኩ::

ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትርና የኦፕሬሽን ማስተባበሪያ ቦርድ ሊቀ መንበር፣ ከሚስተር ኸርበርት ሲ. ሁቨር (Harbert C. Hoover) ጁኒየር፣ ጋር በተደረገ ስብሰባ የአባይ ውሃን ለመጠቀም ኢትዮጵያ ያላትን ሕጋዊ መብት በመግለጽ የታች ተፋሰስ አገሮችን ፣ የግብፅ እና የሱዳንን ፍላጐት ለማሟላት፣ አሜሪካ ብትረዳም የአባይ ተፋሰስ የላይኞቹ ሀገራት ፍትሐዊ የሆነ የውሃ ድርሻ ለመጠቀም ያላቸውን መብት የአሜሪካ መንግሥት በግልፅ እውቅና ቢሰጥ ተገቢ ነው በማለት አስተያየት አቀረብኩ::

ሚስተር ሁቨር የተገለፁትን ሃሳቦች በአፅንኦት አዳምጠው፣ የቅርብ ምስራቅ፣ የደቡብ ኤስያ እና የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሆኑት፣ ከሚስተር ጆርጅ ቪ. አለን (George V. Alen) እና በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ዳይሬክተር ከሆኑት ከሚስተር ሊኦ ጂ. ሳየር (Leo G. Syr) ጋር በጉዳዩ ላይ በዝርዝር እንድወያይ አሳሰቡኝ::

በዚሁ መሠረት እኔና የሕግ አማካሪዬ ሚስተር ሮበርት ስኮት ለሁለት ሳምንታት ያህል ከሚስተር አለንና ከሚስተር ሳየር ጋር ለአያሌ ጊዜያት ተገናኘ ን:: በስብሰባችን መጨረሻ ላይ ሚስተር ሁቨር፣ ፕሬዚዳንት አይዘንሃወር ከፕሬስ ጋር በሚያካሂዱት ስብሰባ በአንደኛው ላይ የአሜሪካ መንግሥት ከፍተኛ ውን የአስዋን ግድብ ፕሮጀክት ሲያግዝ፣ ሱዳንን፣ ኢትዮጵያን፣ ኡጋንዳን ጨምሮ፣ ውሃቸው አስተዋፅኦ ለሚያደርገው ለላይኞቹ የተፋሰስ አገሮች መብትና ጥቅም እውቅና እንደሚሰጥ እንደሚገልፁ አስረዱኝ:: ከአራት ቀናት በኋላ ይህ ተስፋ ሊረጋገጥ ችሏል:: በመጨረሻም የአሜሪካ ማረጋገጫ በጽሑፍ

እንዲሰጠኝ ጥያቄ አቀረብኩ። ሚስተር ሁቨር ይህንኑ ሃሳቤን በፀጋ ተቀበሉት። በወቅቱ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበሩት፣ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ግንቦት 26 1956 እ.ኤ.አ የተፃፈውን የማረጋገጫ ደብዳቤ ሰጡኝ።[11]

ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ፣ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ኦፊሴላዊ ባልሆነ መልኩ ባደረግኩት ውይይት የተገኘውን ውጤት፣ ለግርማዊነታቸው እና ለካቢኔው ገለፅኩ። ከዚህም ጋር በማያያዝ፣ በሥራ ሚኒስቴር ሥር የውሃ ሃብት ልማት ድርጅት እንዲቋቋም ሃሳብ አቅርቤ የግርማዊነታቸውን እና የካቢኔውን ፈቃድ አገኘሁ።

በቅድሚያ፣ በአባይ ላይ ቀደም ሲል የተደረጉትን ጥናቶች ማሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ሙሴ ፕየር ፔትሪዲስን ለዚህ ስራ አጨሁዋቸው። እኒህ ሰው፣ የኢትዮጵያ ዜጋ የነበሩ፣ በትውልዳቸው ግሪካዊ የሆኑ፣ ከኢጣሊያን ወረራ በፊት በአንካራ የኢትዮጵያ ሌጋሽን ያገለገሉ፣ ለረጅም ጊዜ በግብፅ ነዋሪ የነበሩና በዚያ ወቅት በካይሮ የኢትዮጵያ ሌጋሽን በአታሼነት በማገልገል ላይ ስለነበሩ ለዚህ ሥራ እንዲረዱ አስፈቀድኩ። ፔትሪዲስ ስለ አባይ ጉዳይ በቂ እውቀት የነበራቸው ሰው ነበሩ። የውሃ ሃብትን በተመለከተ ቤተ መጻሕፍት አደራጁ፣ እንደዚሁም የአባይን ጥያቄ በተመለከተ ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶችን የሚገልጽ መጽሔት አዘጋጁ። ለውሃ ሃብት መምሪያ ክፍል ጥቂት መሐንዲሶችና ሠራተኞችም ተቀጠሩ።

የአባይ ውሃ፣ ለልማት ያለውን እምቅ ችሎታ በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ መሠረት ጥናት እንዲያካሂዱ፣ በ1952 እ.ኤ.አ የመጀመሪያ የአየር ጥናት ባካሄዱት ከሚስተር ቶም. ኤ. ክላርክ በቀረበ ሃሳብ መሠረት የአሜሪካ መንግሥት የአባይ ተፋሰስ ጥናትን ለማካሄድ እገዛ እንዲያደርግ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ ተገልጾልን ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ኦፊሴላዊ ጥያቄ ለአሜሪካ መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መደበኛ የግንኙነት መስመር አማካይነት እንዲቀርብ ተደረገ። የአሜሪካ መንግሥት ወዲያውኑ ተስማማ። በዚህም መሠረት ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት (USAID) ዳይሬክተር ጋር በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ስምምነት ፈረምኩ።

በሚቀጥለው ዓመት ወደ አሜሪካ ባደረግኩት ጉዞ የአሜሪካ የሬክላሜሽን ቢሮ ዋና መሥሪያ ቤትን እና የአሜሪካ የጠረፍ እና የጂኦደቲክ መሥሪያ ቤቶችን ጐበኘሁ። እነዚህ መስሪያ ቤቶች፣ ከአባይ ተፋሰስ ጥናት ጋር በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እና ምርምር አካሂደው ስለ ነበር፣ ወደ ፊት ለሚወሰደው የመርህ (የፖሊሲ) ውሳኔ ሊጠቅሙ የሚችሉ መረጃዎች እንዲያዘጋጁልን ተስማማን።

በሐምሌ 1948 ዓ.ም (1956 እ.ኤ.አ) ግብፅ ለሕዝባዊት ቻይና ሪፑብሊክ እውቅና በመስጠቷ ምክንያት እና በመስከረም 1955 እ.ኤ.አ ግብፅ ከቼክዝሎቫኪያ ጋር የጦር መሣሪያ ግዥ በመዋዋሏ በተፈጠረው ፀረ ኮሚኒስት ግፊት ምክንያት፣

[11] US Department of State, *Foreign Relations of the United States, 1955-1957, vol. XIII - Africa - National Security Council Report NSC 5615/1* (Washington, Nov. 19, 1956), pp. 335-339.

እንደዚሁም ጥጥ አምራች የሆኑ የአሜሪካን ግዛቶችን ከሚወክሉ ሴናተሮች እና የእስራኤል ደጋፊ በሆነው ቡድን በቀረበው አሉታዊ ተፅእኖ ምክንያት፣ የአሜሪካ መንግሥት ለግድቡ ግንባታ የገንዘብ እርዳታ ለመስጠት ገብቶት የነበረውን ቃል አጠፈ።

የአሜሪካ መንግሥት፣ ከከፍተኛ የአስዋን ግድብ ፕሮጀክት ተሳትፎ በሐምሌ ወር 1948 ዓ.ም. (1956 እ.ኤ.አ) ሲወጣ፣ የሰጠው ኦፊሴላዊ መግለጫ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፡-

> በግብፅ ጥያቄ መሠረት በታኅሣሥ ወር 1955 እ.ኤ.አ የአሜሪካ መንግሥት ከእንግሊዝ መንግሥት እና ከዓለም ባንክ ጋር በአስዋን የሚገኘ ውን የኒል ከፍተኛ ግድብ ግንባታ ለማገዝ ኅብረት ፈጥሮ ነበር። ይህ ፕሮጀክት በስፋቱ በጣም ግዙፍ ነው። የግንባታው ወጪ የአሜሪካ ዶላር 1,300,000,000 እንደሚፈጅ የተገመተ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 900,000,000 የአሜሪካ ዶላር በአገር ወስጥ ገንዘብ የሚወጣ ወጪ ነው። ጉዳዩ የግብፅን መብት እና ጥቅም የሚመለከት ብቻ ሳይሆን ሱዳንን፣ ኢትዮጵያን እና ኡጋንዳን ጨምሮ፣ ለውሃው አስተዋፅኣ የሚያደርጉ ሌሎች አገሮችንም፣ የሚያካትት ነው።
>
> በታኅሣሥ ወር የቀረበው የእርዳታ ጥያቄ፣ የግድቡን የመጀመሪያ ምዕራፎች ሥራ ለማካሄድ በአሜሪካ እና በእንግሊዝ ለግብፅ መንግሥት በእርዳታ መልክ ድጋፍ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ነበር። የሥራው ውጤት በግብፅ ብቻ የተወሰነ ነበር። ፕሮጀክቱን በአጠቃላይ ተግባራዊ ለማድረግ የአባይ ውሃ የመብት ጥያቄ አጥጋቢ በሆነ መልኩ ውሳኔ ማግኘትን የሚጠይቅ ነበር። ሌላው ዋናው ጉዳይ በሥራው አዋጭነት ላይ የነበረው ነው። ስለዚህ የአሜሪካ እርዳታ ሊሰጥ የሚችለው ግብፅ የኢኮኖሚ ሀብ**p ፟** በዚህ ሰፊ የግንባታ ፕሮግራም ላይ ለማዋል ፈቃደኛ እና ችሎታ ያላት ሁና ስትገኝ ነው።
>
> ባለፉት ሰባት ወራት ውስጥ የተከሰቱት ሁኔታዎች ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችሉ አልነበሩም። ከተፋሰሱ አገሮች ስምምነት አልተገኘ ም። በተጨማሪም ግብፅ፣ የፕሮጀክቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በቂ ሃብት በፕሮጀክቱ ላይ ለማዋል ያላት ብቃት፣ እርዳታው ከቀረበበት ጊዜ ይልቅ እያደር በይበልጥ አጠራጣሪ ሆነ። ስለዚህ፣ የአሜሪካ መንግሥት በፕሮጀክቱ መሳተፍ አዋጭነት የሌለው መሆኑን ደምድሟል።
>
> ይህ ውሳኔ፣የአሜሪካ መንግሥት ለግብፅ ሕዝብ እና መንግሥት ያለውን የወዳጅነት ግንኙነት በምንም መልኩ ቢሆን አለመለወጡን ያንፀባርቃል፤ ምንም የተለወጠ ነገር አለመኖሩንም ያሳያል።
>
> የአሜሪካ መንግሥት፣ የግብፅ ሕዝብ ማኅበራዊ ደህንነት እንዲረጋገጥ እና ለኒል ወንዝ ልማት ሥር የሰደደ ፍላጐት አለው። በተፋሰሱ አገሮች ጥያቄ መሠረት የአባይ የውሃ ሃብት በይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለክልሉ ሕዝቦች ጠቀሜታ ጥቅም ላይ እንዲውል ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንደሚገባው ጉዳዩን አግባብነት ባለው ወቅት ለማጤን ዝግጁ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ግብፅ የህዝቧን የኑሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለማሻሻል በምታደርገው ጥረት ለማገዝ ዝግጁ ነው። በዚህ መሠረት ከአሜሪካ ምክር ቤት ለተፈቀደው ገንዘብ አግባብነት

ባላቸው ድርጅቶች አማካይነት ለመወያየት ዝግጁ ነው ሲል ይደመድማል::[12]

ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ ፕሬዚዳንት ገማል አብደል ናስር የስዊዝ ካናል በግብፅ መንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውል አፀፋዊ እርምጃ ወሰዱ:: ይህም እርምጃ የእንግሊዝ እና የፈረንሳይን ዋና ዋና ጥቅሞች የነካ ነበር::

በኢትዮጵያ እና በግብፅ መካከል የነበረው ግንኙነት አሁንም በውጥረት ላይ ነበር:: በኅዳር ወር 1952 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ 1959)፣ የአስዋንን ግድብ ለመገንባት ዝግጅት በማድረግ ላይ የነበሩት ግብፃውያን፣ የኒል ውሃን በተመለከተ ከሱዳን ጋር አዲስ ስምምነት ፈረሙ:: ይህንንም ሲያደርጉ፣ ኢትዮጵያን ሳያስታውቁ ነው:: በተጨማሪም፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ በመስከረም 1950 ዓ.ም. (1957 እ.ኤ.አ.) ለኢትዮጵያ ጥቅም ተገቢውን ግምት አለመስጠት እንደ ትልቅ ጥፋት ተደርጐ ይቆጠራል በማለት የሰጡትን መግለጫ ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ ነው::

በ1929 እ.ኤ.አ ከሱዳን ጋር የተደረገው ስምምነት በአዲስ ድርድር ተሻሻለ:: እ.ኤ.አ በ1959፣ በግብፅ እና በሱዳን መካከል የተደረገው አዲሱ ስምምነት፣ ግብፅ የአስዋንን ከፍተኛ ግድብ እንድትገነባ ይፈቅዳል:: ይህም ግድብ 164 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ለማቆር የሚችል ነው:: በቦታው ላይ በረጅሙ ጊዜ የሚፈሰው ውሃ አማካይ ሁለት እጥፍ ይሆናል:: ስለዚህ ከትልቁ ግድብ የሚመነጨው 22 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ትርፍ ነው:: ከመጀመሪያው 48 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ላይ 7.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር እንዲጨመር ተደርጓል:: ስለዚህ የግብፅን ጠቅላላ ድርሻ 55.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ እንዲሆን ሲያደርግ፣ ለሱዳን ደግሞ፣ መጀመሪያ ከተፈቀደላት 4 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ላይ 14.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ስለሚጨምር፣ በአጠቃላይ 18.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ይደርሳታል::

ኢትዮጵያ የኒልን ውሃ ክፍፍል በተመለከተ፣ የግብፅን እና የሱዳንን የጋራ ስምምነት በመቃወም፣ ኒል የዓለም አቀፍ ወንዝ እንደመሆኑ መጠን፣ በኒል ሸለቆ የጋራ ባለሥልጣን አማካይነት በሰፊው እንዲለማ ሃሳብ አቀረበች:: በዚህ እንቅስቃሴም፣ ሁሉም የተፋሰሱ አገሮች መሳተፍ ይኖርባቸዋል ስትል ሃሳቧን ገለፀች:: ሊዮ ሲልበርማን የተባሉ የኦክስፎርድ ምሁር *የኢትዮጵያ ነገርን የማለዘብ ኃይል* በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጽሑፋቸው፡- «ኢትዮጵያ የተገለሉት የተፋሰሱ አፍሪካ ሀገሮች አፈ-ቀላጤ በመሆን ተግባሯን አከናውናለች:: በዚሁ ሀሳቧም ኒል ተፋሰስ ርዝመት የሚሸፍን ቴኒሲ ቫሌይ አውሶሪቲ (ቲቪኤ) አይነት ሃሳብ አቅርባለች::»[13] ሲሉ አስተያየታቸውን ገልጸዋል::

---

[12] United States, "Aswan High Dam," *Middle Eastern Affairs* (August-September 1956), pp. 298-299

[13] Leo Silberman, "Ethiopia: Power of Moderation," *The Middle East Journal,* Vol. 14 No 2 (1960), p.141. ቴኔሲ ቫሌይ አውሶሪቲ (Tennesse Valley Authority) እ.አ.አ. በ1933 ዓ.ም. የተቋቋመ መስሪያ ቤት ሲሆን ዋና ተግባሩም በታላቁ ቴኔሲ ወንዝ ላይና በሸለቆው ውስጥ የሚካሄደውን ልማት መምራት፣ ማስተባበርና መቆጣጠር ነው::

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ በቅኝ ግዛቶቹ (በኡጋንዳ፣ በኬኒያና በታንዛንያ) ስም ተገቢ ድርሻችንን በውሃው ለመጠቀም በስምምነት የመደራደር መብታችን የተጠበቀ ነው ሲል አስታወቀ::[14]

በአምባሳደር ሳሚር አህመድ በተዘጋጀ እና በግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ1978 እ.ኤ.አ «ግብፅ እና ኒል» በሚል አርእስት በታተመው መፅሐፍ ላይ በክልሉ በሚያልፈው ዓለም አቀፍ ወንዝ ላይ አንድ ሀገር ያላትን የማይገሰስ ሉዓላዊነት የሚደግፈውን በ1895 እ.ኤ.አ የወጣውን የሀርሞን ዶክትሪን[15] ከኮነነ በኋላ የወንዙ ውሃ ያለማቋረጥ እንዲፈስ በመጠየቅ ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

> ግብፅ ከፍተኛውን የአስዋንን ግድብ ለመገንባት ስትወስን አሁን ያሉትን ግጼታዎች በመወጣት የኒል ተፋሰስ ተባባሪዎችን አማክራለች:: በእርግጥም በጥሩ ጉረቤትነት መንፈስ መሠረት እና ከእነዚህ ሀገሮች ጋር ባላት የቆየ የወዳጅነት እና የትብብር ግንኙነት መሠረት ይህንኑ አድርጋለች::[16] የሚል ነበር::

ምንም እንኳን ለዚህ ከፍተኛ መርህ የከንፈር ሽንገላ ቢደረግም ቅሉ፣ ሁኔታው በትክክል ሲታይ ግብፅ ያማከረችው ሱዳንን ብቻ ነበር:: በዚህም መሠረት በ1959 እ.ኤ.አ የወጣውን አዲሱን የውሃ ስምምነት እንደገና እንዲስተካከል አድርጋለች:: ከሶቭየት ህብረት በተገኘ እርዳታ እና ብድር ከፍተኛውን የአስዋን የግድብ ፕሮጀክት በመገንባቱ ተግባር ከመሰማራቷ በፊት፣ ለኒል ሰማንያ አምስት ከመቶ (85 %) ያላነሰ ውሃ የምታበረክተውን ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ ሁሉንም ሌሎቹን የተፋሰስ አገሮች ከምንም አልቆጠረቻቸውም::

3,600 ሜትር ርዝማኔ፣ 110 ሜትር ከፍታ፣ 980 ሜትር መሠረትና 40 ሜትር ስፋት ያለው የአስዋን ግድብ የሚያመርተው የኃይል መጠን 2,100,000 ኪሎ ዋት ነው:: እንደዚሁም፣ ሰው ሠራሽ የሆነ መጠኑ 5,000 ኪሎ ሜትር ካሬ የሚሆን ቦታን የሚሸፍን ሃይቅ የዓለም ትልቁ የምህንድስና ውጤት የሆነው ግድብ ሊገነባ ችሏል::

* * *

የግብፅ ባለስልጣኖች፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ ላይ በገዥው ሥርወ-መንግሥት ላይ አመጾች እንዲነሣሡ ለማድረግ የታቀደ ፕሮፖጋንዳ እና የፖለቲካ መርሃ - ግብር ፕሮግራሞችን አካሂደዋል:: እነዚህ ከውጭ የሚሰነዘሩ ዛቻዎች፣ የኢትዮጵያ መንግሥትን ዓይነተኛ ድክመቶች በይበልጥ እንዲባባሱ አድርገዋል:: መንግሥቱ በኤርትራ እና በተለያዩ ስፍራዎች ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ

[14] B.K. Batstone, "The Utilization of the Nile Waters," *International and Comparative Law Quarterly*, Vol. 8, (July 1959), p. 558.

[15] US Attorney General Harmon's doctrine stems from the principle of Absolute Territorial Sovereignty which he invoked in 1895 in connection with US-Mexico dispute over the Rio Grande River.

[16] Egyptian White Book, *Egypt and the Nile* (Cairo, 1978), p. 30.

ገጥሞታል:: በዚህም መሠረት የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ከዚህ የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል፡-

> የአሜሪካ የፖለቲካ መርሃ-ግብር የኢትዮጵያውያንን የወደፊት እድላቸውን በተመለከተ እንደዚሁም በአካባቢያቸው የሚታዩ ክስተቶችን በተመለከተ ያደረባቸውን ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ለማለዘብ መሞከር ይኖርበታል:: ይህንንም የሚያደርገው ከዚህ በሚከተሉት ዘዴዎች አማካይነት ነው::
>
> - በቅርብ ምስራቅ እና በአፍሪካ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ላይ፣
> - በኒል ዓለም አቀፍ ልማት፣ እና
> - በሶማሌ ችግር ላይ፣ የጋራ ምክክር በማድረግ ይሆናል ሲል ወስኗል::

ኅዳር **19 1956** እ.ኤ.አ በአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት እንዲወሰዱ ከታቀዱ እርምጃች መካከል ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ የሚከተለውን ያካትታል:: «በማናቸውም የአባይ ሸለቆ ልማት ላይ የኢትዮጵያን ተሳትፎ መደገፍ እና በኢትዮጵያ የሚገኘው የአባይ ሸለቆ ክፍል እንዲጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸት»[17] አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል::

በሚቀጥለው ዓመት ምክትል ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን ኢትዮጵያን በጉበኙበት ወቅት ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት **12** ቀን **1957** እ.ኤ.አ ምክትል ፕሬዚዳንቱን ሲያነጋግሩ የአባይን ጉዳይ አንሥተውባቸው፣ ዩናይትድ ስቴትስ የአስዋንን ፕሮጀክት ለማገዝ ከግብፅ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ስምምነት ከማድረጓ በፊት እሳቸውን ባለማማከሩ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልፀዋል:: እንደዚሁም ከኒል ውሃ **85%** የሚሆነውን አስተዋፅኦ የምታደርገዋ ኢትዮጵያ በእርሻ እና በኢንዱስትሪ እያደገ የመጣውን ፍላጐቷን ለሟሟላት ከሁሉ በፊት አስፈላጊ የሆነውን ውሃ መጠቀም መቻል አለባት:: እነዚህኑ ፍላጐቶች ለሟሟላት የውሃ ማመንጫ እና ሌሎች ባራጆችን ለማጠናቀቅ የገንዘብ እርዳታ እንደሚያስፈልግ ንጉሠ ነገሥቱ ገልፀዋል::

ሚስተር ኒክሰን በበኩላቸው የአባይን ልማት በተመለከተ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ላቀረቡላቸው አስተያየት፣ «የኒል ጉዳይ የተለያዩ የተፋሰስ አገሮችን፣ ማለትም የግብፅን፣ የሱዳንን፣ የኢትዮጵያን፣ እንደዚሁም በኡጋንዳ ስም የእንግሊዝን ትብብር በማግኘት መፍትሔ ማግኘት ይኖርበታል»[18] ሲሉ አስተያየታቸውን ገልጸዋል::

የአሜሪካ ብሔራዊ ምክር ቤት ታኅሣሥ **30** ቀን **1960** እ.ኤ.አ (N.S.C **6028**) የአፍሪካ ቀንድን አስመልክቶ ባወጣው ረቂቅ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን አስፍሯል፡-

---

[17] US Department of State, *Foreign Relations of the United States 1955-1957, Vol. XIII - Africa Vol. XIII National Security Council.* Report, NSC 561 5/1 Nov 19, 1956 (Washington, 1959), pp. 335-339.

[18] *Ibid*

> *የኒል ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ ስምምነት እስካልተደረገ ድረስ ማናቸውም በኒል ወንዝ ላይ የሚደረጉ ለሌሎች ወገኖች የጠቀሜታ መብት ሊሰጡ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያ ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ሳይደረግ ቢፈፀሙ ኢትዮጵያ ውሃውን ወደፊት ለመጠቀም ላላት ዕቅድ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ይቆያል፣ ይህም አገሪቱ ከሱዳን እና ከግብፅ ጋር በሚኖራት ግንኙነት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ የገንዘብ እርዳታ በመስጠት ወይንም በሌላ መልኩ እንደ እነዚህ ባሉት ፕሮጀክቶች ላይ በሚሳተፍ በማናቸውም አገር ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል። የኢትዮጵያ መንግሥት በ1956 እ.ኤ.አ ከአሜሪካ መንግሥት በተሰጠው ኦፊሴላዊ ማረጋገጫ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ይተማመናል።*
>
> *የኢትዮጵያን ሕጋዊ መብት ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ሳይገኝ ምንም አይነት እርምጃ መወሰድ አይኖርበትም።*

**የብሔራዊ ደህንነት ሪፖርት በማጣቀሻ መልኩ ከዚህ የሚከተለውን ጨምሯል፦**

> *ይህ ማረጋገጫ እ.ኤ.አ ግንቦት 26፡1956 ከሚስተር ሁቨር ጁኒየር የአሜሪካ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በተፃፈው ደብዳቤ ላይ ተመልክቷል*[19]»። (*ማጣቃሻው የተወሰደው ከምንጩ ሰነድ ነው*)።

**የብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት *ታኅሣሥ* 30፡1960 እ.ኤ.አ ባወጣው *ሪፖርቱ* ላይ *የፖሊሲ መመሪያ* ብሎ ከዚህ እንደሚከተለው ይገልፃል፦**

> *ይህ መመሪያ* «*በተቻለ መጠን በኢትዮጵያ እና በሌሎች የተፋሰሱ አገሮች መካከል የኒልን ጉዳይ በተመለከተ በሚደረጉ ድርድሮች የአሜሪካ ተሳትፎ እንዳይኖር፤ከሁሉም በላይ አሜሪካ ማናቸውም የተፋሰስ አገር ያለውን አቋም እንደሚጋራ የሚያሳይ ሁኔታ ጨርሶ መፈጠር አይኖርበትም*» *የሚል* ነበር።[20]

**እ.ኤ.አ በ1961 *ሶሪያ* ከግብፅ ስትነጠል፣ ናስር በመላው አረብ ግንባር ዙሪያ የመጀመሪያው ሽንፈት ደረሰበት።**

**እ.ኤ.አ በመስከረም ወር 1962 የናስር ጦር የመን ገባ። የዚህም ዋና አላማ በሳዑዲ ከሚደገፉት የየመን ንጉሣውያን ኃይሎች ጋር አምስት ዓመት የቆየውን ጦርነት ለማካሄድ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ናስር በየመን የሚያገኘው ድል የሚያስከትለውን ጣጣ በእጅጉ ፈርተውት ነበር። ምክንያቱም የጦርነቱ ውጤት በሶማሊዎች እና በጅብሃ የኤርትራውያን ሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያስከትል በመሆኑ በሐምሌ ወር 1960 እ.ኤ.አ ነፃነቷን ያገኘችው ሶማሊያ በኦጋዴን ላይ የይገባኛል ጥያቄ አንስታ ነበር። ይህ ሁኔታ ናስር ጦር የመን ከመግባት ጋር ተደምሮ አፄ ኃይለ ሥላሴ የኤርትራን ፌዴሬሽን አፍርሰው ኤርትራን በኅዳር ወር 1962 እ.ኤ.አ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ ለማድረግ ገፋፋቸው።**

---

[19] US Department of State, *Foreign Relations of the United States 1958-1960, Africa Vol. XIV, National Security Council Report NSC 5028, Dec. 30,1960* (Washington DC 1992), p. 203.

[20] *Ibid,* p.210.

ፕሮፌሰር ሐጋይ ኤርሊክ እንደገለጹት ፦

> *በግንቦት ወር በ1955 ዓ.ም. (በ1963 እ.ኤ.አ.) የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ) በአዲስ አበባ በተመረቀበት ወቅት በኢትዮጵያ እና በግብፅ መካከል የነበረው ግንኙነት ባያሌው ሊሻሻል ቻለ። በሚቀጥለው ዓመት 1964 እ.ኤ.አ ናስር የአአድን የመሪዎች ስብሰባ በካይሮ አስተናገደ። በዚያ ስብሰባ ላይ የእያንዳንዱን አገር የግዛት አንድነት ሉዐላዊነት ማክበር የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓይነተኛ መርህ እንዲሆን ተወሰነ። ከዚያ በኋላ ናስር ለኤርትራ የነፃነት ግንባር (ጀብሃ) የሚያደርገውን እርዳታ አቆመ። በዚህም ምክንያት ግንባሩ በመካከለኛ ምስራቅ ያለውን ጽ/ቤት ከካይሮ ወደ ደማስቆስ ሶርያ ለማዛወር ተገደደ።[21]*

**ለአባይ ተፋሰስ ጥናት የኢትዮ አሜሪካ ተራድኦ ፕሮግራም**

የአባይ ተፋሰስ በዝርዝር ተመርምሮ፣ በዚሁ ጥናት መሠረት ሊመዘገብ፣ ሊገለጽ፣ ሊዘረዝር እና በካርታ ላይ ሊሠፍር ከመቻሉ በላይ፣ የሃይድሮሎጂክ እና የሜትሮሎጂካል ጣቢያ አውታሮች በጠቅላላ በተፋሰሱ ላይ እንዲቋቋሙ ተደርጓል። እውን ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶቹ ተለይተው እንዲጠኑ፣ የወጪያቸው ግምት እና በቅደም ተከተል የፕሮጀክቶቹ የአፈፃፀም ግዜም እንዲታወቅ ተደርጓል። የተፋሰሱ የአየር ፎቶግራፎች ሊዘጋጁ ችለዋል። እንደዚሁም የመጀመሪያ ደረጃ የጂኦደቲክ ጥናቶች ተከናውነዋል። የዚህም ዋና አላማ የሆሪዞንታል (የአግድሞሽ) እና ቨርቲካል (ዋልታ አውታር ቋሚ) መቆጣጠሪያዎችን ለማስገኘት ማስቻል ነው። የእነዚህም ዓላማ የተለያዩ ሚዛኖች ያሏቸውን ትክክለኛ ካርታዎች ለማዘጋጀት ነው።

ፕሮጀክቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ የተቋቋመውን የውሃ ሃብት መምሪያ የሚመሩ መሐንዲሶችና ቴክኒሺያኖች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል። እነዚህ መሐንዲሶችና ቴክኒሺያኖች ጥናቶችን እንዲያካሂዱ እና የሌሎች ወንዞች ተፋሰሶችን ሃብት እንዲያጤኑ በማቀድ ጭምር ነው። በአጠቃላይ ውሃን ለመቆጣጠር አስፈላጊ ለሚሆኑት የሃይድሮሊክ ሥራዎች አገሪቷ ኤክስፐርቶችን እንድታገኝ ይህንንም ሥራ ለኃይል ምርት፣ ለመስኖ ልማት፣ ለውሃ አቅርቦት ለማዋል እና እንደዚሁም ረሃብንና የምግብ እጦትን ለመዋጋቱ ተግባር በመጠኑ ለመርዳት ፈር ቀዳጅ በመሆን አስተዋጽኦ አድርጓል።

በአጠቃላይ የአባይ ጥናት ፈርጅ ብዙ ፕሮግራም ያለው ሲሆን፣ ከሁሉም በፊት የተዘጋጀው ከዚህ የሚከተሉትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነበር፦

1. የሃይድሮ ኤሌክትሪክ እና የመስኖ ልማቶችን በማጥናቱ፣ በመገምገሙ እና በማቀዱ ረገድ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ፣
2. የውሃ ሀብት የልማት ፕሮግራምን በማስተዳደሩ ረገድ የኢትዮጵያ መንግሥት የምህንድስና እና አስተዳደራዊ ድርጅት ለመፍጠር እና ለማቋቋም የሚያደርገውን ጥረት ለማገዝ ፣

[21] Haggai Erlich, *Ethiopia and the Middle East* (Boulder, Colorado, 1994), p. 138.

3. በአባይ ተፋሰስ ውስጥ ሊለሙ የሚችሉትን ዘርዝሮ ለማቅረብ እና በአጠቃላይም ይህንኑ ሀብት ለማልማት የሚያስችል ጠቅላላ እቅድ ለመንደፍ ፣
4. የኒልን ዓለም-አቀፍ ጥቅም በተመለከተ ውይይቶች በሚደረጉበት ወቅት አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ኢትዮጵያ ለማግኘት እንድትችል የሃይድሮሎጂክ ጣቢያዎች አውታርን ለማስገኘት ነው።

የአባይ ተፋሰስ ጥናት ፕሮግራም በኢትዮጵያ መሐንዲሶች እና ቴክነሺያኖች ተሳትፎ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው በሦስት የአሜሪካ ድርጅቶች ነበር። የጥናቱ ጠቅላላ ወጪ ወደ 10 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይጠጋ ነበር። ይህም ገንዘብ በእኩል ደረጃ የተዋጣው በሁለቱ መንግሥታት ነበር። ይህ ወጪ እያንዳንዱ መንግሥት ለራሱ ሠራተኞች የከፈለውን ደመወዝ እና የውሎ አበል አይጨምርም።

በጥናቱ ፕሮግራም የተሳተፉት ድርጅቶች፣ የአሜሪካ የጦር የመሃንዲስ ክፍል የካርታ አገልግሎት፣ (The Army Map Service of the US Army Corps of Engineers በመባል የሚታወቀው)፣ የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር የጠረፍ እና የጂኦዴቲክ ቅኝት ጥናት (The US Coast and Geodetic Survey of the Department of Commerce)፣ የአሜሪካ የአገር ውስጥ ሚኒስቴር የሬክላሜሽን ቢሮ (US Bureau of Reclamation) ናቸው። እያንዳንዱ ድርጅት ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ትብብር አስተዳደር (International Cooperation Administration of the State Department) ጋር በተደረገ ኮንትራት መሠረት በመስክ ላሰማራው ቡድን አመራርና እንደዚሁም ተግባራዊ ላደረገው እና ላወጣው የመጨረሻ ሪፖርት ማቅረብ ኃላፊ ነበር። የጦሩ የካርታ አገልግሎት ክፍል የአሜሪካ የአርሚ ኮር መሐንዲሶች የሚጠቀሙባቸውን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ካርታዎች ያዘጋጃል። የመሐንዲሶቹ ቡድን ከጐርፍ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ በሃይድሮሊክ ምህንድስና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው ነው። የአባይ ተፋሰስ የተለያዩ የግንኙነት ፎቶግራፎች በ1958 እ.ኤ.አ ጐሌታ ካሊፎርኒያ በሚገኘው በማርክ ኸርድ ኤርያል ሰርቬይዝ ሊዘጋጁ ችለዋል። አርሚ ማፕ ሰርቪስ 50,000 እና 20,000 ስኬል (ሚዛን) ያላቸውን የአየር ፎቶግራፎች ብቻ Ü∂≥ pG።

ፎቶ ሞዛይክ ፣ ፕላኒሜትሪክና ሌሎች አነስተኛ ካርታዎችን ለማዘጋጀት እንዲቻል አርሚ ማፕ ሰርቪስ ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ የፎቶ ግራማቲኩን መሣሪያና ያሠለጠናቸው ሠራተኞች ወደ ውሃ ሀብት ልማት እንዲዛወሩ አድርጓል።

እ.ኤ.አ መጋቢት 5 1957 በተደረገው ልዩ የአገልግሎት ስምምነት የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል ካለው የትብብር ፕሮግራም ጋር በተያያዘ የጂኦደሲ የቴክኒክ እርዳታ ለዓለም አቀፍ የትብብር አስተዳደር ለመስጠት ተስማምቶ ነበር። የአሜሪካ የባህር ጠረፍ እና የጂኦደቲክ ሰርቬይ ሥራዎቻቸውን 1957 እ.ኤ.አ መጨረሻ አካባቢ ጀምረው፣ በ1961 እ.ኤ.አ ለማጠናቀቅ ችለዋል።

የመስኩ ቡድን የአየር ፎቶግራፎችን በመጠቀም በፎቶግራሜትሪክ አማካይነት ካርታ ለመሥራት አስፈላጊ የሆኑትን ሆሪዞንታል እና ቨርቲካል ቁጥጥሮችን ለማደራጀት የጂኦደቲክ ጥናቶችን በኢትዮጵያ አካሂዷል፡፡

መላውን የአባይ ተፋሰስ የሚሸፍኑ ሆሪዞንታል (የአግድሞሽ) ቁጥጥሮች ለማድረግ የተቻለው የትሬያንጉሌሽን መስመር አውታሮችን እያንዳንዳቸው ከ30 ኪ.ሜትር ርዝመት በማይርቁ ቦታዎች ላይ በማቋቋም ነበር፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ ሁሉንም የተራራ ጫፎችን እና የኮረብታ ጫፎችን ለማገናኘት እና በመስመሮቹ መካከል ያለውን አንግል (ማዕዘን) ለመወሰን እንደዚሁም የጂኦደቲክ ሰርቬይ በመጠቀም እና ስሌቶችን በማካሄድ የመስመሮቹን ትክክለኛ ርዝመት ለማወቅ ነበር፡፡ ይህም ዘዴ እንደ መደበኛ ጥናት ሳይሆን የመሬት ከርቪቸር (ገፀ-ምድር እጥፈት) ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል የቨርቲካሉ ቁጥጥሮች ከባህር ከፍታ በላይ የሚገኙትን ትሬያንጉሌሽን ጣቢያዎች ትክክለኛ ከፍታ እና ሌሎች የቤንች ማርክ አውታሮችን ከፍታ ለመለየት አስችሏል፡፡ በዚህም መሠረት እነዚህ ከፍታዎች በፎቶ ግራሜትሪ አማካይነት የሚዘጋጁትን ካርታዎች የኮንቱር ከፍታዎች ለመወሰን ያስችላሉ፡፡ ሁለቱ የትሬያንግሎች መስመሮች እና የቤንች ማርክ ከፍታዎች የአባይ ተፋሰስን ካርታዎች ለማዘጋጀት መቆጣጠሪያዎችን የሚያስገኙ ከመሆናቸውም ሌላ የጂኦዶቲክ ሰርቬይን ወደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ለማራዘም እና በመሬት ላይ ለሚዘጋጁ አነስተኛ ካርታዎች በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ ነሐሴ 9 ቀን 1957 በተደረገ ልዩ የአገልግሎት ስምምነት መሠረት የዓለም አቀፍ ትብብር አስተዳደር (International Cooperation Administration, ICA) ከዩናይትድ እስቴትስ ዓለም - አቀፍ ልማት ድርጅት (US AID) ጋር በመተባበር የአሜሪካ የውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የሬክላሜሽን ቢሮ፣ የአባይ ተፋሰስን የተፈጥሮ ሀብት ጥናት በ1958 እ.ኤ.አ ጀመረ፡፡ በዚሁ መሠረት የመረጃው አሰባሰብ እና የመስክ ጥናቶች ሥራ በሰኔ 30፡1963 እ.ኤ.አ ሊገባደድ ችሏል፡፡

የሬክላሜሽን ቢሮ በኢትዮጵያ የአባይ መሬት እና የውሃ ሀብት በሚል ርዕስ የተዘጋጀ 314 ገጾች ያሉት ጥናት እ.ኤ.አ ነሐሴ 7፡1964 ሊያቀርብ ችሏል፡፡ ሪፖርቱ አንድ ዋና ቅጽ እና ስድስት አባሪዎች አሉት፡-

አባሪዎቹ፡- 1. ፕላን እና ግምት በሁለት ቅጾች፣ 2. ጂኦሎጂ፣ 3. ሃይድሮሎጂ፣ 4. የመሬት አመዳደብ 5. ኃይል፣ 6. የእርሻ እና ኢኮኖሚክስ በሚል አርዕስት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ሪፖርቱ በአሁኑ ወቅት ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ 433,754 ሄክታር መሬትን በመስኖ ለማልማት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይዘረዝራል፡፡ እንደዚሁም 8,660,000 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት የሚያስችሉ የኃይል ፕሮጀክቶችን ይገልፃል፡፡ ጥናቱ ኢትዮጵያ ያላትን የመሬት እና የውሃ ሃብት ዝርዝር ያቀርባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዋን ለማጠናከር እና የህዝቦቿን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚያግዝ የአጠቃላይ የልማት ዕቅድ የነደፈ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ 1969 እ.ኤ.አ ድረስ ለአባይ ተፋሰስ ጥናት ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ (ወደ 10 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ) ወጪ አድርጓል፡፡

ተፋሰሱ (ወይንም አባይ ውሃውን የሚያፈስበት አካባቢ) 200,000 ኪ.ሜትር ካሬ ወይንም የአገሪቱ ጠቅላላ ስፋት 1/6ኛ የሚያክለውን ይሸፍናል፡፡ በዚህ ተፋሰስ ውስጥ ውሃውን በመጠቀም ወይንም ባለመጠቀም ገና ወደፊት ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ ሃብቶች አሉ፡፡ ሀብቶቹ የሚያካትቱት የዋና ዋና ገባሮቹን እና የእነሱን ንዑስ ገባሮች ጭምር ነው፡፡ ዋና ዋና ገባሮች እንደ ደዴሳ ፣ ዳቡስ ፣ በለስ ፣ ፍንጫ፣ ጉደር፣ ሙገር ፣ በሽሎ እና ግልገል አባይ የመሳሰሉት በሚያልፉባቸው አካባቢዎች በመስኖ ሊለሙ የሚችሉ መሬቶችን ነው፡፡ እነዚህ መሬቶች የሚጠይቁት የመስኖ ውሃ በእጅጉ አነስተኛ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት የታችኞቹ የተፋሰስ አገሮችን ጠቀሜታ ሊጎዳ የማይችል ስለሆነ ይህን ያህል የሚያስጨንቃቸው ሊሆን አይገባም፡፡ ከውሃ እና ከመሬት ሃብት በተጨማሪ የደን ሃብቶችም አሉ፡፡ እንደዚሁም የተፈጥሮ እንስሳት ሃብቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም በደን ላይ የተመሠረቱ ታላላቅ ኢንዱስትሪዎችን ሊደግፉ ፣ የቱሪዝም እድገት ሊያግዙ የሚችሉ ናቸው፡፡የኢትዮጵያ ደን መውደም የዝናብ እጥረትን ስለሚያስከትል ጉዳቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለታችኞቹ ተፋሰስ አገሮች ጭምር በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ደን እንዲለማ በማድረግ በተለይ ግብፅና ሱዳን ሊተባበሩ ይገባል፡፡

የአባይ ተፋሰስ ጥናት ከተጠናቀቀ እና እንደዚሁም ተፋሰሱ ያለው ሃብት ከተዘረዘረ በኋላ፣ ለቅድመ ጥናት 33 ታላላቅ ፕሮጀክቶች ተለይተው እንዲታወቁ ተደርገው ነበር፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የፊንጫ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ፕሮጀክት ተግባራዊ ተደርጐ ጥቅም ላይ ሊውል ችሏል፡፡

ተለይተው እንዲታወቁ ከተደረጉት ታላላቅ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የጣና በለስ ፕሮጀክት ነበር፡፡ የጣና ሃይቅን ውሃ ወደ በለስ ወንዝ ለመሳብ 7 ኪ.ሜትር ርዝመት ያላቸው ቦዮችን፣ እንደዚሁም ከፍታው ከ2 ሜትር የማይበልጥ አነስተኛ ግድብ፣ በአባይ አፍ ላይ እንዲገነባ ያደርጋል፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ ውሃን ለማከማቸት እና ወደ ሃይቁ የሚገባውን የጐርፍ ውሃ ለመቆጣጠር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ በየደረጃው የሚገነቡ የተለያዩ የኃይል ማመንጫዎችን በሃይቁ ገፀ ምድር እና በበለስ ወንዝ መካከል ባለው 600 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን አናት ወይንም ራስ ለመጠቀም፣ እንደዚሁም በታችኛው በለስ እስከ 60,000 ሄክታር የሚደርስ የመስኖ ልማትን ለማከናወን ነው፡፡

የጣና በለስ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ በፋሽስት ቁጥጥር ስር በነበረችበት ወቅት አገሪቷ ያላትን የሃድሮ ኤሌክትሪክ ሃብት ባጠናው፣ በዝነኛው ኢጣሊያዊ ሃይድሮሊክ መሐንዲስ በፖንቴ ኮርቮ (Ponte Corvo) ተለይተው እንዲታወቁ ከተደረጉት ሶስት ፕሮጀክቶች አንደኛው ነው፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ የቦይ ፕሮጀክቶች የጣና ዲንደር እና የጣና ረሃድ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ጥናቱ በተደረገበት ወቅት ውድቅ እንዲሆኑ የተደረጉ ሲሆኑ፣ በእነርሱ ምትክ የተመረጠው ጣና በለስ ነበር፡፡ ምክንያቱም በቦይ ርዝማኔ ረገድ አጠር ያለ

ሲሆን፣ በቆላማው አካባቢ በመስኖ ሊለማ የሚችል ተስማሚ አካባቢ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

እ.ኤ.አ ከ1957-1962 በአሜሪካ የሬክላሜሽን ቢሮ እና በአሜሪካ የጠረፍ እና ጂኦዶቴክ (ኮስት አንድ ጂኦዴቲክ) መሥሪያ ቤቶች በኢትዮጵያ ተደርገው የነበሩት የሃይድሮሎጂካል ሰርቬዮች እና ጥናቶች የአባይ ተፋሰስን በማጥናት ብቻ የተወሰኑ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ጥናቶቹ ለኒል አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ሶባትን (አኮቦ - ባሮ) እና የተከዜ ወንዞችን የሚያካትቱ አልነበሩም፡፡

የአባይ ተፋሰስ ጥናት ለመስኖ እና ለውሃ ኃይል (ለሃይድሮ ፓወር) ልማት ሊውሉ ይችላሉ በማለት የተጠቆሙት 33 ዋና ዋና ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው የወጪ ግምትም አብሮ ተመልክቶ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የወጪው ግምት በአሁኑ ወቅት ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም ቅሉ፣ የውሃ ግድብ እና የውሃ ማጠራቀሚያ እንዲገነባባቸው፣ እንደዚሁም የውሃ ማከማቻ ስፍራ እንዲዘጋጅላቸው የተለዩት ቦታዎችና ለመስኖ ልማት እንዲውሉ ተለይተው የታወቁት ቦታዎች አሁንም አግባብነት ይኖራቸዋል፡፡

በአባይ ተፋሰስ በጠቅላላው በመስኖ እንዲለማ ተለይቶ የታወቀው የመሬት መጠን 433,745 ሄክታር ሲሆን፣ ይህንንም መሬት ለማልማት 6.3 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ያስፈልጋል፡፡ የውሃ ማጠራቀሚያ እንዲገነባላቸው ከተለዩት ቦታዎች 20 የሚሆኑት ግድቦች ከ100 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር በላይ የሚሆን ውሃ ለማጠራቀም የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በአባይ ወንዝ ላይ ዋና ዋና የውሃ ግድብ እንዲገነባባቸው የተለዩት አራቱ ዋና ቦታዎች ካራዶቢ፣ ሞቢል፣ መንዳያ እና የወሰን ፕሮጀክት ናቸው፡፡ አራቱ ግድቦች በጠቅላላ 51 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ለማከማቸት የሚችሉ ሲሆኑ፣ እነርሱም 25 ቢሊዮን ኪሎ ዋት በሰአት (kwh) የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ይችላሉ፡፡

የአባይ ተፋሰስን ለመመርመርና ለማጥናት እ.ኤ.አ ከ1957 እስከ 1962 ድረስ የተካሄደው የአሜሪካ እና የኢትዮጵያ የጋራ ፕሮግራም የታቀደው፣ ኢትዮጵያ ሃብቶቿን ለማልማት በአባይ ተፋሰስ ውስጥ ምን ያህል የመስኖ ውሃ እንደሚያስፈልጋት ለመወሰን ነበር፡፡ ፕሮግራሙ ስለ ውሃ አውዳሚ ባህሪያት እና ይህንንም መቆጣጠር አስፈላጊነት ግንዛቤን ፈጥሯል፡፡ ጥናቱ እንደዚሁ ውሃውን በተለያዩ መልኮች መቆጣጠር መሬትን ከአፈር ብክለት እና ከውድመት የሚከላከል ብቻ ሳይሆን አንድ ፕሮጀክት ከሚያስገኘው ባለብዙ ፈርጅ ጠቀሜታዎች (ለምሳሌ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ መስኖ፣ ውሃ ላይ መጓጓዣ [ናቪጌሽን]፣ መዝናናት፣ የአሣ እርባታ እና ከውሃ ማጠራቀሚያዎች ደግሞ እንደ ውሃ ማቆር የመሳሰሉት) ሊገኙ እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡

## መደምደሚያ

የኒል ተፋሰስን የሚያካትቱት የዐሥሩ አገሮች፡- ብሩንዲ፣ ግብፅ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬኒያ፣ ሩዋንዳ፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ እና ኮንጎ ዴሚክራቲክ ሪፑብሊክ (የቀድሞ ስሟ ዛየር) - ጠቅላላ የህዝብ መጠን፣ እ.ኤ.አ በ2004፣

***350,000,000 እንደሚደርስ ተገምቶ ነበር፡፡[22] በዓለም ባንክ ጥናት መሠረት ይኸው የህዝብ ቁጥር እ.ኤ.አ በ2050 ወደ 1,000,000,000 እንደሚጠጋ* ተµN p G፡፡**

***ግብፅ እና ሱዳን እ.ኤ.አ በ1959 በአደረጉት ስምምነት መሠረት ከኒል ውሃ የግብፅ ድርሻ 55.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ሲሆን፣ የሱዳን ድርሻ ደግሞ 18.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ሆኗል፡፡***

***በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከአባይ ውሃ የምትጠቀመው 0.6 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ብቻ ነው፡፡ ሌሎቹ የኒል ተፋሰስ አገሮች (ቡሩንዲ፣ ኤርትራ፣ ኬኒያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ ፣ ኡጋንዳ እና ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሬፑብሊክ [ዛየር]) በአጠቃላይ ከአባይ ውሃ የሚጠቀሙት 0.5 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ብቻ ነው፡፡***

***ሱዳን እና ግብፅ ደቡብ ሱዳን ውስጥ በሚገኘው ሱድ ከሚባለው ረግረጋማ አካባቢ በጋራ የሚቆፍሩት የጆንጉሌ ካናል ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ እያንዳንዳቸው ጥቂት ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ያገኛሉ፡፡ ግብፅ በየጊዜው እያደገ የመጣውን የሕዝቧን ፍላጐት ለማሟላት ያቀደችውን የአግድሞሽ የእርሻ ግብርና ማስፋፋት ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ ጀምራለች፡፡ ይህንንም የምታደርገው፣ እ.ኤ.አ በ1959 ከሱዳን ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት፣ የራሷ መብት አድርጋ በምትቆጥረው ውሃ ተማምና ነው፡፡***

***ከአስዋን ከፍተኛ ግድብ በተጨማሪ በሱዳን ውስጥ ሁለት ግድቦች ተገንብተዋል፡፡ እነዚህም በአባይ የሮዚየርስ ግድብ (3 ሚሊዮን ኪውቢክ ሜትር የመያዝ አቅም ያለው) እና በአትባራ ላይ የተገነባው የካስም ኤል ግርባ ግድብ (1.3 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ የመያዝ አቅም ያለው) ናቸው፡፡ በየዓመቱ ከኢትዮጵያ የሚፈሰው ጎርፍ ባለው ጨው አዘል ውሃ ምክንያት የመጀመሪያው የመያዝ አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ተደርጓል፡፡ ቀደም ሲል ከተገነቡት ሁለት ግድቦች ጋር ሱዳን በአሁኑ ወቅት አራት ግድቦች አሏት፡፡ እነዚህም በጠቅላላው 6.1 ቢሊዮን ሜትር ኪውቢክ ውሃ ያጠራቅማሉ፡፡ በተጨማሪ ሱዳን 1.9 ሚሊዮን ሄክታር በመስኖ የሚለማ የግብርና ፕሮግራም አላት፡፡ እንደዚሁም በአባይ ገባሮች ላይ በጠቅላላው 278 ሚሊዮን ዋት በዓመት ለማምረት የሚያስችል የሃይድሮ ኤሌክትሪክ የኃይል ጣቢያ ገንብታለች፡፡ በሱዳን በሱድ አካባቢ የሚደርሰውን የውሃ ብክነት ለመቋቋም የጆንገሌ ካናል ግንባታ እ.ኤ.አ በ1974 ተጀምሮ ነበር፡፡ በክልሉ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ግን የካናሉ ግንባታ እ.ኤ.አ በ1981 እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ በኢኳቶሪያል ሃይቆች አካባቢ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ካልተገነቡ የማስተላለፊያ ካናሎቹ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም፡፡***

***እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግብፅ 7 ሚሊዮን ፊዳን (ወይንም 3 ሚሊዮን ሄክታር) የሚሆን መሬት በመስኖ እንዲለማ አድርጋለች፡፡ ስለዚህ ከግድቡ የወጣውን ውሃ መልሶ መጠቀምን ጨምሮ በየአመቱ 65 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ለመስኖ ውሃ ትጠቀማለች፡፡ የአስዋን ከፍተኛው ግንብ 645 ሚሊዮን ሚሊ ዋት ሃይድሮ***

[22] በአሁኑ ወቅት፣ ደቡብ ሱዳን ራሷን የቻለች አገር ስለሆነች፣ የኒል ተፋሰስ አገሮች ቁጥር 11 ደርሷል፡፡

ኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም አለው፡፡[23] በታችኛው በረሃማ አካባቢዎች በትነት እና በመፍሰስ የሚባክነው ውሃ ግን እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

በተጨማሪ ግብፅ በጥር ወር 1989 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ Jan. 19, 1997) «ቶሽካ» ብለው በሠየሙት ዕቅድ ኻርጋ (Kharga)፣ ዳክላ (Dakhla) እና ፋራፍራ (Farafra) የተባሉትን በደቡብ ምሥራቅ የሚገኙትን በረሃማ ሥፍራዎች፣ እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ወደ ሲናይ አቅጣጫ «ሰላም» ተብሎ በተሠየመ ቦይ (ወይም ካናል) በስዌዝ ካናል ሥር ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ሰፊ በረሃ በመስኖ ለማልማት ወስናለች፡፡ እነኝህን ዕቅዶች በሃያ ዓመት ውስጥ በማከናወን በተጨማሪ አንድ ሚልዮን ሄክታር ገደማ እንዲኖራት ለማድረግ፣ ከሁለት ቢልዮን ዶላር ያላነሰ ወጭ እንደሚያስፈልግ በይፋ ታውቋል፡፡ ከዚህም እጅግ ከፍ ያለ ፣ እስከ 640 ቢልዮን ብር ወጭ በማድረግ፣ 16.2 ሚሊዮን ሕዝብ ለማስፈር የረጅም ጊዜ ዕቅድ ያላቸው መሆኑ ይሰማል፡፡ ግብፅ ከሱዳን ጋር እ.ኤ.አ በ1959 ባደረገችው ስምምነት መሠረት፣ የዓመት ድርሻዬ ነው ከምትለው 55.5 ቢልዮን ሜትር ኩብ ውሃ በላይ፣ 8 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በተጨማሪ እንደሚያስፈልጋት ይገመታል፡፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ1959 ከሱዳን ጋር ስትዋዋልም ሆነ አዲሶቹን ዕቅዶች ለመሥራት ስትወስን፣ ከሱዳን በቀር ለሌሎቹ ስምንቱ የኒል ተፋሰስ አገሮች ሳታስታውቅና ሳትስማማ በመሆኑ፣ የከረረ አለመግባባት እንዳያስከትል የሚያሰጋ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

በላይኛቹ የኒል ተፋሰስ አገሮች ውሃውን ጥቅም ላይ ማዋሉ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በኢኳቶሪያል ሃይቅ ተፋሰስ ወይንም በኢትዮጵያ ለመስኖ ግንባታ የሚደረግ ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ 150 ሚሊዮን ዋት ሃይድሮ ፖወር ለማምረት አቅም ያለው የኦወን ፏፏቴ ግድብ፣ ኡጋንዳ ከግብፅ ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት፣ ሊገነባ ችሏል፡፡ ይሄው ግድብ ለግብፅ የማያቋርጥ የመስኖ ውሃ የሚሰጥ ሲሆን፣ ለኡጋንዳም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት አስችሏል፡፡ በኢትዮጵያ የፍንጫዋ ግድብ በአባይ ገባሪ ወንዝ ላይ ተገንብቷል፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ የኃይል ማመንጫዋ ለማቅረብ እና ከረግረጉ ወደ ሸንኮራ አገዳው እርሻ የሚፈሰውን ውሃ ለመቆጣጠር ነው፡፡ የውሃ ማጠራቀሚያው 6 ሚሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ለማቆር የሚችል ሲሆን፣ በየዓመቱ 110 ሜጋ ዋት (M.W) ሃይድሮ ፖወር ለማመንጨት ይችላል፡፡

86% የሚሆነውን የአባይ ውሃ ለአስዋን ግድብ የምታቀርበው ኢትዮጵያ፣ የልማት ፍላጐቶቿን ለሟሟላት፣ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የሄደውን ሕዝቧን ለመመገብ ፣ እንደዚሁም ባለፉት አምስት ዐሠርት ዓመታት በአስከፊ ሁኔታ ያስተናገደችውን የድርቅ አደጋ ለመቋቋም፣ የአባይን ውሃ ጥቅም ላይ ማዋል ይኖርባታል፡፡

በቅርቡ በኢትዮጵያ የሸለቆዎች ልማት ባለሥልጣን በተደረገው ጥናት መሠረት፣ እ.ኤ.አ እስከ 2040 ድረስ የውሃ በጀት ተገምቷል፡፡ ይህም የሕዝብ

[23] ይህም 645 ሜጋ ዋት ይሆናል፤ የአስዋን ግድብ በአጠቃላይ 2,100 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሀይል ያመነጫል፡፡

*እድገት ግምቶችን፣ የእንስሳት ሀብት መጠንን፣ እና ለቤት፣ ለከተሞች፣ ለንግድና ለኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚያስፈልገውን የውሃ ፍላጐት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። በተጨማሪም በሶስቱ ሸለቆዎች፣ የአባይ፣ የተከዜ* (*ሰቲት*) *እና የሶባት* (*የባሮ አኮቦ*) *ተፋሰሶች፣ የሚገኘውን የውሃ ሃብት ግምት ውስጥ ያስገባል። በዚሁ ጥናት መሠረት በየዓመቱ ከእነዚህ ተፋሰሶች 57.8 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሀ ሊገኝ እንደሚችል እና እንደዚሁም መጠኑ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን በሸለቆዎቹ የሚገኘውን መሬት በመስኖ ለማልማት የሚያስፈልገው የውሃ መጠን 19 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር እንደሚሆን ተገምቷል። ከዚህ ውስጥ ግማሹ ለባሮ- አኮቦ ተፋሰስ እንዲውል ታቅዷል። የዚህም ዋናው ምክንያት በትነት እና በፍሰት ከፍተኛ የሆነ የውሃ ብክነት ስላለ ነው። በአባይ ተፋሰስ ይገኛል ተብሎ የተገመተው ውሃ 53.3 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ሲሆን፣ 0.84 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ለማልማት የሚያስፈልገው የውሃ መጠን 8.4 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር ውሃ ወይንም በተፋሰሱ ከሚገኘው በመቶ ዐሥራ አምስት* (*15* %) *ብቻ ነው።*

*ከአባይ ተፋሰስ፣ ከሶባት* (*ከባሮ - አኮቦ*) *እና ከተከዜ* (*ሰቲት*) *ሊመነጭ የሚችለው የኤሌክትሪክ ኃይል እጅግ ከፍተኛ ነው። በአባይ ተፋሰስ ብቻ፣ በዘጠኙ ገባሪ ወንዞች ላይ፣ ለኃይል ማመንጫ ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎች ተለይተዋል። ከእነዚህ ቦታዎች ላይ ሊገኝ የሚችለው የኤሌትሪክ ኃይል በየዓመቱ እስከ 48,970 ጂ. ደብሊዩ. ኤች* (G.W.H) *ይሆናል።*[24] *በባሮ አኮቦ ተፋሰስ ሦስት ግድቦች እንዲገነቡ ተለይተው ታውቀዋል። ከእነዚህም ግድቦች የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል በየዓመቱ 11,240 ጂ. ደብሊዩ. ኤች* (G.W.H) *ይሆናል። በተከዜ አንገረብ ጐአንግ ወንዞች ተፋሰስ ሊመነጭ የሚችለው የኤሌክትሪክ ኃይል በየዓመቱ 5910 ጂ. ደብሊዩ. ኤች* (G.W.H) *ነው። ድምሩ 66120 ጂ .ደብልዩ ኤች* (G.W.H) *ይሆናል። ግምቶቹም የተመሠረቱት ለኢትዮጵያ ወደ ፊት በሚያስፈልገው የኤሌክትሪክ ኃይል መሠረት ነው።*

*የተለያዩ የዓለም አቀፍ እውቅና ያገኙ ሊቃውንት ኢትዮጵያ ላይ ግድቦች፣ ውሃ ማከማቻ ሬዘርቭዋር ፣ በውሃ ኃይል የኤሌትሪክ ማመንጫ ቢሠራ በጠቅላላው ለኒል ተፋሰስ አገሮች፣ በተለይም ለግብፅ ፣ ለሱዳንና ለኢትዮጵያ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲሉ አስተያየታቸውን ገልጸዋል።*[25]

*የአባይ ተፋሰስ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረግ፣ በሌሎቹ የወንዝ ተፋሰሶች ውስጥ እንደሚገኙት ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ሁሉ፣ ያለ ምንም ጥርጥር አያሌ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሉት። ኢትዮጵያ ለ1000 አመታት አንፃራዊ ሰላም በሰፈነበት ሁኔታ በጉርብትና ከኖረችባቸው አጐራባች አገሮች ሕዝቦች ጋር አስፈላጊ ያልሆነ ውጥረት ሊኖር አይገባም። አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች (በቅርብ*

---

[24] *ጂ.ደብሊዩ ኤች* (GWL) *ጌጋዋት ሰአቶች* (Gigawatt Hours) *የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ምህጻረ ቃል ነው። አንድ* GWL *አንድ ቢሊዮን የዋት ሰአቶች ይሆናል፤ አንድ የኪሎዋት ሰአት* (Kilowatt Hours) *ማለት በአንድ ሰአት ውስጥ የጠፋው የኤሌክትሪክ ሀይል ማለት ነው።*

[25] *ያዕቆብ አርሳኖ፣* «*ግብፅ የሠሀራን በረሀ በአባይ ለማልማት የ40 ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት ዘርግታለች*»*፣ ሪፖርተር* (*የካቲት 1 ቀን 1997*).

ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ) በጣም ትላልቅ ናቸው:: አስፈላጊው ካፒታል ተገኝቶ ቢሠሩም፣ ለተፋሰሱ የታችኛዎቹ አገሮች ምንም ያህል የሚያስጨንቅ አይሆኑም:: የአባይን የውሃ ፍሰት ለመቀነስ የሚችሉት በጣም አነስተኛ በሆነ መልኩ ነው::

አሁን አሳሳቢና አንገብጋቢ የሆነው ጉዳይ አፈሩ በማያቋርጥ አኳኋን እየታጠበ በመሄዱ፣ የእርሻ ማሳዎች መውደም፣ እንደዚሁም በአባይ፣ በተከዜ እና በገባሮቻቸው ተፈጥሮአዊ ክስተት ምክንያት ትልቁ የአገሪቱ ክፍል በከፍተኛ ደረጃ ደኑ የመውደሙ ጉዳይ ነው::

አባይ እና ተከዜ የሚፈሱባቸው ትግራይ፣ ዋግ፣ ላስታ መካከለኛው የአማራ አካባቢ (በለሳ፣ጋይንት፣ ዋድላ፣ ደላንታ፣ ዳውንት፣ የጁ፣ ወረሂመኑ፣ አምባሰል፣ ወረኢሉ፣ ሳይንት፣ ቦረና፣ ጎጃም በከፊል)፣ የሰሜን ሸዋ አካባቢዎች (መንዝ፣ ተጉለት፣ መርሐቤቴ፣ ሞረት፣ ቡልጋ)፣ ወዘተ... ተመሳሳይ የመሬት ገጽታ ያሏቸው ናቸው:: ጠንካራ ኮረብታዎች፣ ጥልቅ የሆኑ የወንዞች ሸለቆዎች፣ ደን የሌለባቸው የታጠቡ ከፍታ ቦታዎች እና ምንም አይነት የእፀዋት ሽፋን የሌለባቸው ስፍራዎች ናቸው:: ሁሉም የሚያሳዩት በለምለሟ ኢትዮጵያ ውስጥ በረሃማነት በየጊዜው እየተስፋፋ የመጣ ክስተት መሆኑን ነው:: ህዝቦች በማያቋርጥ የበረሃማነት መስፋፋት ምክንያት ለሚከሰቱት ድርቅ እና ረሃብ ተጠቂ ሲሆኑ፣ ትላልቅ ወንዞች (እንደ በሽሎ፣ ወንጪት፣ ጀማ የመሳሰሉት)፣ ከአካባቢው በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀው የሚገኙት፣ ከከፍታው ቦታ ላይ የተረፈውን ማንኛቸውንም ነገር ሲያወድሙ ይተያሉ::

በዚህም ምክንያት ደን በመጥፋቱ ዝናብም ስለሚጠፋ ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳንና ግብፅ የሚፈሰው የውሃ መጠን መቀነሱ የማያጠራጥር ነው:: ስለዚህ በከፍተኛ ኮረብታማ አገሮች የሚኖረውን አብዛኛውን ሕዝብ ወደ ደልዳላ መሬት አሥፍሮ ኑሮውን እንዲያሻሽል፣ የነኙህ አውራጃዎች መሬት እንዲተነፍስና የደን ሽፋኑ እንዲመለስ የማድረግ ዕቅድ ለመተግበር፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን የውሃ ኤሌክትሪክ ኃይል ለመገንባት፣ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሱዳንና ለግብፅም ጠቃሚ ስለሆነ ኃላፊነቱ የጋራ ሊሆን ይገባል::

የኒል ተፋሰስ አገሮች በአለፉት ሠላሳ ዓመታት ትብብር ለመፍጠር እንደዚሁም ሁሉንም ተፋሰስ የሚያካትቱ የአሠራር ስልቶች ለተቀናጀና ለተዋሃደ ልማት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ትብብር እንዲካሄድ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል:: «ኒል 2002» የተባለው በቅርቡ ከተነደፋት ፕሮግራሞች አንደኛው ሲሆን፣ ይህም በኤክስፐርቶች እና በኒል ውሃ እና ልማት አንጻር በሚመለከታቸው የመንግሥት ሠራተኞች መካከል የበለጠ ግንዛቤ እና ትብብር እንዲኖር ለማስቻል ሲባል ነው::

ስለዚህም፣ አሁን ያሉትን እና ወደፊትም የሚከሰቱትን ችግሮች ለመቋቋም፣ በአለፈው ጊዜ የተደረጉ ስህተቶችን ለማረም፣ ሁሉም የአባይ ተፋሰስ አገሮች የጋራ ሃብታቸው የሆነውን ውሃ ለመጠቀም እና ለማልማት ሙሉ ተሳታፊዎች መሆን አለባቸው:: ጠንካራ እርምጃዎችን የመውሰድ ጊዜውም አሁን ነው::

በአለፈው ጊዜ የላይኞቹ የተፋሰሱ አገሮች ተረስተዋል:: ይህ ሁኔታ መቀጠል የለበትም:: ኢትየጵያ በተለይ በአለፉት ሃምሳ ዘመን በተደጋጋሚ በዝናብ

እጥረት እና በየጊዜው በሚከሰቱ የድርቅ ችግሮች ተጠቅታለች:: የደን መውደም፣ አፈር ታጥቦ መሄድ፣ በአባይ ተፋሰስ የሚገኙ ምንጮች እና ጅረቶች መድረቅ፣ እንደዚሁም በአጠቃላይ የሥነ-ምህዳር መበከል እና መውደም፣ የአባይ ውሃ ምንጭ በሆኑት አካባቢዎች በሚያስፈራ ሁኔታ ተስፋፍቷል:: እየተፋጠነ በመሄድ ላይም ይገኛል:: በሌላ በኩል በተፋሰሱ የታችኞቹ አገሮች ከፍተኛ የሆነ የውሃ ትነት እና ፍሰት፣ የአካባቢ ብክለት፣ የውሃ ብክነት እና እንደዚሁም ውሃውን በቅልጥፍና መጠቀም አለመቻል፣ አሳሳቢ ችግሮች እየሆኑ መጥተዋል::

መጠኑ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የሕዝብ የውሃ ፍላጐት ለሟሟላት፣ እንደዚሁም በአባይ፣ በአትባራ እና በባሮ አኮቦ (ሶባት) ወንዞች ላይ የውሃ ማጠራቀሚያዎች እና የውሃ ኃይል (የሃይድሮ ፖወር) ተቋማትን መገንባት ያለው ከፍተኛ እድል ከበረሃማው አካባቢ ይልቅ፣ በትነት ምክንያት የሚፈጠረው የውሃ እጥረት አነስተኛ በሆነበት ለደጋው አካባቢ በማድረግ እንደ እነዚህ ያሉትን ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: በኢትዮጵያ በጣና ሃይቅ አካባቢ አባይን የማገድ ሃሳብ ቀርቧል:: ይህም የሚጠፋውን በየዓመቱ 15 ቢሊዮን ኪውቢክ ሜትር የሚሆነውን ውሃ ለመከላከል ያስችላል:: ይህ ከሆነ የአባይ ዓመታዊ ፍሰት በመቶ አምስት (5%) ይሆናል:: በተጨማሪም በአስዋን ከፍተኛ ግድብ ምክንያት በታችኛው ሸለቆ ከተፈጠረው የናስር ሃይቅ ላይ በትነት እና በፍሰት የሚባክነውን ውሃ ሊቀንስ ይችላል:: እንደዚህ ያለውን እርምጃ ለመውሰድ በግብፅ እና በሱዳን ዘንድ ተቀባይነት ያለው አይመስልም:: ምክንያቱም በአባይ ውሃ ፍሰት ላይ ያላቸውን ብቸኛ ቁጥጥር ለማጣት ፈቃደኞች አይደሉምና::

በኒል ምንጭ ላይ የሚደርሰውን የተፈጥሮ ሃብት ብክለትና ጥፋት ለመቋቋም፣ በኢኳቶሪያል ሃይቅ አካባቢዎችና በኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች እንደዚህ ያለው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል:: ይህ ዓይነቱ እርምጃም መወሰድ የሚችለው በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ እና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ትብብር ነው::

የኒል ጉዳይ በግብጽና በኢትዮጵያ ግንኙነት ላይ ጥቁር ጥላ ከጣለበት እ.ኤ.አ ከ1950 ጀምሮ የሁለቱ አገሮች የዲፕሎማቲክ ልዑካን ወይም ተጠሪዎች በዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ሲገናኙ ፣ ምንም እንኳዋን የአባይ ጉዳይ በአእምሮአቸው የሚጉላላ፣ ወይም በማናቸውም ጊዜ በፊታቸው ድቅን ሊል የሚችል፣ ነገር ቢሆንም አንድም ጊዜ ሊያነሡት ፈልገው አያውቁም ነበር:: አባይ፣ በተለይ በግብጾች በኩል፣ ስሙ ፈጽሞ የሚነሣ ነገር አልነበረም:: የሁለቱ አገሮች መሪዎች፣ የግብፁ ፕሬዘዳንት ሙባረክና የኢትዮጵያው ፕሬዘዳንት መለስ ዜናዊ፣ እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 1993 ካይሮ ተገናኝተው ሁለቱ አገሮች አባይን ጨምሮ ለጋራ ጥቅም በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ለሚረዳዱበት ጥርጊያ በር የከፈተውን ስምምነት እስከተፈራረሙበት ጊዜ ድረስ፣ ይህ ሁኔታ ለ50 ዓመታት ያህል ቀጥሎ ነበር::

በስምምነቱ አንቀጽ 5 ላይ፣ "Each party shall refrain from engaging in any activity related to the Nile waters that may cause appreciable harm to the interest of any party" የሚለው ግብፅ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት እንዳይደርስ፣ ኢትዮጵያ

በአባይ ውሃ ከመጠቀም ትቆጠባለች፣ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት አሻሚ ሊሆን ይችላል:: ከፍ ያለ ጉዳት ለማድረስ ሆን ብሎ አለአግባብ የውሃውን የተፈጥሮ ሂደት ማዛባት በመሠረቱ በዓለም አቀፍ ሕግ የተከለከለ መሆኑ የታወቀ ነው:: ኢትዮጵያ የሕዝቧን ፍላጎት ለማሟላት በአባይ ፣ በተከዜ ፣ በባሮ አኮቦ ወንዞች በአግባቡ ብትጠቀም ግን ሕጉም ሆነ ስምምነቱ አያግዳትም::

በዚያ በሁለቱ መሪዎች ግንኙነት፣ ሁለቱን እሕትማማች አገሮች አስተሳስሮአቸው የኖረው የአባይ ወንዝ ጉዳይ፣ በሁለቱ አገሮች መካከል ተፈጥሮ በነበረው ፍጥጫ ምክንያት፣ ምንም ዓይነት ንግግር ያልተካሔደበት ረጂሙ የዝምታ ጊዜ አብቅቶ፣ የአባይ ጉዳይ ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚ ሊሆን በሚችል አኳ|ን በግልጽ ውይይት የሚደረግበትና የሚወሰንበት አዲስ የወዳጅነት መንፈስ ማንዣበቡ አንድ እርምጃ ነው:: የአባይ 2002 ጉባኤ፣ በተፋሰስ አገሮች የፖለቲካ መሪዎች ድጋፍ አስዋን (ግብፅ) ላይ እ.ኤ.አ. በ1993 ተጀምሮ፣ ለዘጠኝ ጊዜ በተለያዩ ሥፍራዎች በጠነከረ አኳ|ን መቀጠሉ ያስደስታል:: በቅርቡ አልፎ አልፎ በዜና እየተሰራጨ የምንሰማው ንትርክ ደግሞ በስምምነቱ ተስፋ ላይ ጥርጣሬን ይጥላል:: ዝነኛዋ ዘመናዊ ድምጻዊት እጅጋየሁ ሺባባው (ጂጂ)፣

> አባይ አባይ የበረሀው ሲሳይ
> አንተ ውሃ ቢጠሩህ አትሰማ
> ምን አስቀምጠሃል ከግብጦች ከተማ::
> ... አባይ ወንዛወንዙ
> ብዙ ነው መዘዙ::

ያለችውን ቅኝት ያስታውሳል::

የኒል ተፋሰስ የላይኞቹ አገሮች፣ የታችኞቹ የተፋሰስ አገሮችን ፍላጐት ማወቅ እና መቀበል ይኖርባቸዋል:: በተመሳሳይ መልኩ የተፋሰሱ የታችኞቹ አገሮች ለተፋሰሱ ለላይኛው አገሮች ፍላጐት ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል:: የዚህ ተፃራሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ ጥፋት እና አርቆ የማያስተውል መርህ (ፖሊሲ) ነው::

የአባይ ወንዝ በተለይ በግብጽ፣ በሱዳን እና በኢትዮጵያ መካከል የኅብረት ግንኘ -ነትን ፈጥሯል:: የእነዚህ የረጅም ታሪክ ባለቤት የሆኑት ሕዝቦች የአባይን ውሃ ለእልፍ አእላፍ ዘመናት ተጎንጭተዋል፤ እንደዚሁም ከአንድ አፈር የሚበቅሉ ሰብሎችን ተመግበዋል:: ስለዚህ የወደፊቱን ፈተናዎች ሊቋቋሟቸው እና የሕዝቦቻቸውን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚችሉት በትብብር እንጂ በፀብ እና በመናቆር አይደለም::

# ክፍል ፬
# የሴቶች እንቅስቃሴ

# የኢትዮጵያ ሴቶች በትምሕርትና በሥራ ዓለም
# (ከነፃነት እስከ አብዮት)

*እሌኒ መኩሪያ እና አለም ሰገድ ሀሩይ*

***መግቢያ***

**1.** ሴቶች፣ በርዕሱ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ፣ ምን አበረከቱ ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት፣ በቅድሚያ የዘመኑን ገፅታ የሚያስረዱ ዋና ተጽእኖዎችን (influences) በአጭሩ ማንሳቱ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሚከተለውን አቅርበናል፡፡

ሀ) በ1933 ዓ.ም. የ5 ዓመቱ የፋሺስት ኢጣልያ አገዛዝ በአገራችን አክትሞ ለቀጣዩ 33 ዓመት በአጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሳዊ አገዛዝ መንግሥት እንደገና ተቋቋመ፡፡

ለ) በዓለም ዙርያ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ያስከተለውን ከፍተኛ ውድመት መልሶ ለመገንባት የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በየአገራቸው፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች፡ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ከወንዶች ጎን ተሰማርተው ለአገራቸው ትልቅ አስተዋፆኦ ማበርከት የጀመሩበት ዘመን ነበር፡፡

እኛም አገር ይህ አስተሳሰብ በትንሹ ዘሩ ተዘራ፡፡ ያገራችን ሴቶች በዘመናዊ ስልጣኔ ሂደት ውስጥ፣ ጅምሮቻቸው እንዴት እንደነበር ለማስታወስ ያህል፣ እይታችንን ወደ አፄ ምኒልክ ዘመን እንመልሰው፤ ምክንያቱም በዚህ ዘመን ነው ዘመናዊ ስልጣኔን የሚያራምዱ መሠረታዊ አውታሮች ተዘርግተው የሴቶች የወደፊት እድልም ሂደቱ የተጀመረው፡፡ በዚህ ዘመን ነው ሴቶች፣ በጥቂቱም ቢሆን፣ የዘመናዊ ትምሕርት ዕድል ማግኘት የጀመሩት፡፡ በቀጣዩ የራስ ተፈሪ (ኋላ አፄ ኃይለ ሥላሴ) ዘመነ መንግሥት ዘመናዊ ስልጣኔ እየሰመረ ሲሄድ፣ አንዳንድ ሴቶችን፣ ከጓዳቸው የሚያስወጡ፣ ከትምሕርት ሌላ፣ ተጨማሪ በሮች ተከፈቱ፡፡ ለመጥቀስ ያህል፣ ወደ ውጭ አገር ለጉብኝት ሆነ ለመኖር እንዲሁም ለትምሕርት በመሄድ ከዘመናዊ አኗኗር ጋር የተቀሰሙ ልምዶችን መካፈል ተጀመረ፡፡ ባገር ውስጥ፣ ሴቶችን በሚመለከት እንቅስቃሴዎች ተጀመሩ፡፡

የውጪ አገር ጉዞን በሚመለከት፣ በቅድሚያ ግርማዊት እቴጌ መነን ገና በልእልትነታቸው ዘመን (በ1914 ዓ.ም.)፣ በኋላ ደግሞ ግርማዊት ከተባሉ ወዲያ በ1926 ዓ.ም.፣ ወደ እየሩሳሌም፣ ቴላቪቭ፣ ቤይሩት እና ሲሪያ ሲሄዱ፣ ከዚያም ቀጥሎ ኢትዮጵያ ከውጪ አገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠንከር ሲባል በፓሪስና በስዊስ አገር በባለሙሉ ስልጣን «ሚኒስትርነት» ማዕረግ የተሾሙት አምባሳደሮች፣ ራስ ጌታቸው አባተ በፓሪስ፣ በጅሮንድ ዘለቀ በስዊስ አገር ባለቤቶቻቸውን ይዘው ሄደዋል፡፡ እነኚህም፡ ወ/ሮ አስቴር መንገሻ (ፓሪስ፣

የመጀመሪያ የሴት መኪና ነጂ በኢትዮጵያ)፣ ወ/ሮ አዛለች ጎበና (በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሴቶች ጉዳይ ሚኒስትር በቤተ መንግሥት) ነበሩ:: ለትምሕርት ወደ ውጪ አገር የሄዱ የመጀመሪያዎቹ ልጅአገረዶች:- የግርማዊ ጃንሆይ ሴት ልጅ ጸኃይ ኃይለ ሥላሴ፣ የምስራች እምሩ፣ አምሳለ ህሩይ፣ ስንዱ ገብሩና የውብዳር (ኋላ እማሆይ ፅጌማሪያም) ይገኙበታል::

በጥቅሉ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እስኪወር ድረስ ሴቶችን በሚመለከት አበረታች ምልክቶች ታይተው ነበር፤ ዋነኛው ሴቶች በድርጅታዊ መልክ ተሰባስበው ወደሕብረተሰቡ መዝለቅ መጀመራቸው ነው:: የመጀመሪያው የሴቶች ድርጅት በ1927 ዓ.ም. በግርማዊት እቴጌ መነን ጠባቂነትና ከውጪ አገር በተመለሱት በልዕልት ፀኃይ ኃይለ ሥለሴ ፕሬዚዳንትነት ተቋቋመ:: ከመስረቱትም ወይዛዝርት መሀል: ቆንጅት አብነት፣ ቀፀላ ባልቻ፣ ቀፀላ ወርቅ ቱሉ፣ የምሥራች እምሩ፣ ወሰንየለሽ መንገሻ፣ ደብሪቱ ሳህሌ፣ ገነት ሕሩይ፣ ወይንሸት በየነ፣ አጸደና ሶንያ ባቢቼቭ፣ አዛለች ጎበና፣: አበባ ገብረ ሥላሴ፣ አሰለፈች ባቡ፣ አይዳ ሕሩይ፣ አሰገደች ኪሮሴ፣ አስቴር ወርቅነህ፣ አስካለ ግዛው፣ ሉሊት ተስፋዬ (ለብዙ ዓመታት ፕሬዚዳንቱ የነበሩ)፣ ጌጤ በዳኔ፣ አርበኛዋ ሸዋረገድ ገድሌ ይገኙበታል፡፡ ማሕበሩም በአዲስ አበባ የተቋቋመው የሴቶች በጎ አድራጎት ማሕበር ነው:: ካቋቋሙትም በኋላ ይህ ማሕበር በጦር ግንባር ለተሰለፉት ጀግኖች በልዩ ልዩ ሁኔታ የጦርነት ወቅት የሚያስፈልገውን እርዳታ ለማድረግ የመጀመሪያ አገልግሎት አበረከተ::

በዚሁ ወቅት ቀይ መስቀል ተቋቁሞ ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ አገልግሎት በመስጠት ከቀዳሚ ሴቶች አንዷ ነበሩ:: እንዲሁም በጦርነቱ አጥቢያ ከእቴጌ መነን ትምህርት ቤትና ከስዊድሽ ሚሽን የተውጣጡ ልጅ አገረዶችን እንግሊዛዊትዋ ሌዲ ኤዝሚ ባርትን (በወቅቱ የነበረው የእንግሊዝ ሚኒስትር ወይም አምባሳደር ባለቤት) አስተባብራ ለቁስለኛ የሚያስፈልገውን የቁስል መጠቅለያ (ባንዴጅ) እያዘጋጁ በማበርከት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

በዚሁ ወቅት፣ የውጪ አገር ሴቶችን ድጋፍ ለማግኘት፣ ግርማዊት እቴጌ መነን የመጀመሪያዋ ሴት ሬድዮ ተናጋሪ ሆነው፣ ለዓለም ሴቶች የድረሱልን ጥሪ አቅርበዋል:: የእንግሊዝኛውን ትርጉም ደግሞ ያቀረበችው የሐኪም ወርቅነህ ልጅ አስቴር ነበረች::

ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ፣ ያገራችን ሴቶች ቁጥር እየበዛ ከጓዳ ወደ አደባባይ ዘልቀው ለዘመናዊ ሕብረተሰቡና ሳገር እድገት አስተዋጽኦ ማድረግ የጀመሩበት ዘመን ነበር:: ስልጣኔ በንክኪ እንደሚዛመት ይታወቃል፡፡ ወደኋላ ትንሽ ብንመለስ፣ እንደሚታወቀው እኛ አገር የፋሺስት ኢጣሊያ መንግስት ለ5 ዓመት (ከ1928-1933 ዓ.ም.) ኢትዮጵያን በገዛበት ወቅት በተለይ በአዲስ አበባ የቆዩ ሴቶች ከጣሊያኖች ጋር በመተባበር ይሁን አልያም ኑሮን ለማሸነፍ፣ ጣሊያኖች በዙሪያቸው ስለነበሩ፣ በግርድና ሥራ በመሰማራት፣ ታላላቅ የሆኑ ሹማምንቶቹን በማስተናገድ፣ ባዝማሪነት የተሰማሩ ሴቶች በዝማሬ በማስደሰትና በማጫወት፣ በጥቅሉ እነዚህ ሴቶች ከጣሊያኖች ጋር ባሳለፉት ዓመታት፣

በማየት፣ በመስማት፣ ኑሮአቸውን በመካፈል፣ የዘመናዊ ኑሮ ተጽእኖ (influence) አድሮባቸዋል። ይህም የታየው በአለባበስ ለውጥ፣ በተለያየ የጠጉር አበጣጠር፣ በቤት አያያዝ፣ በንግድም ሥራ በመሰመራታቸው ነው። እንደሚታወቀው በዚሁ ዘመን የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ በጣም አይሎ ሳለ፣ ሙዚቃ በሽክላ ቀረፃ ሥራ ተቋቁሞ ነበር። አዝማሪዎችም ሹማምንቶችን እንዲያሞግሱ ይገደዱ ነበር። ነገር ግን አዝማሪዎቻችንን ማን ይችላቸዋል? ለምሳሌ ንጋትዋ ከልካይ የጣሊያኑን ንጉሥ ቪክቶሪዮ አማኑኤልን እንድታሞግስ ትታዘዛለች። እሷም ባንድ በኩል እያሞገሰች በሰምና ወርቅ ተጠቅማ ለበላዩ አማኑኤል ክብሩንና ሞገሱን አሳለፈች። ዘመናዊ ስልጣኔና ባሕላዊ ዘይቤ እንዲህ ያለ ውጤት ያስገኛል።

በዚህ ወቅት ደግሞ፣ አገር ውስጥ ሆነው፣ የጣሊያን ንኪኪ ሳያድርባቸው፣ በዱር በጫካው ሆነው፣ ለነፃነት ሲታገሉ የቆዩ አርበኛ ሴቶችም ነበሩ። ለምሳሌ ከታወቁት ሌላ፣ እናት አርበኞች እታገኝ ኃይሌ እና ዘነበች ወልደየስ ይገኛሉ። አርበኛዋ ዘነበች ምንም እንኳዋን የ15 ዓመት ወጣት ብትሆንም በአምስት ዓመቱ የሽምቅ ትግል መውዜርዋን ታጥቃ ከባለቤትዋ ጋር ዘምታለች። በይፋትና በቡልጋ መሀል በምትገኝ ቦታ ላይ ማሽላ ውስጥ የጨበጣ ውጊያ ሲካሄድ ባለቤትዋ አጠገብዋ ሲሞቱ «ገዳዩን በመግደሌ የባለቤቴን፣ የወገኖቼን ደም ተበቅያለሁ» ብላ ተናግራለች። ስለ ሌላው ትውስትዋ ስትናገር ደግሞ፣ «አንድ ቀን ልብሳችንን አጥበን እንዳሰጣን የጠላት ጦር ደረሰብን። በእለቱ የታጠቅሁት አንዲት ቁምጣ ነበረች፤ ይህቺን ቁምጣ ያለ ልዋጭ ሁለት ዓመት ለብሻትአለሁ።» በትግሉም ወቅት ሌሎች ሴቶች አብረዋት ነበሩ። ከምታስታውሳቸው መሀል፡- አየለች ዮሴፍ፣ ጎርፍዋ ሠይፉ እና ልክየለሽ በያን ጥቂቶቹ ናቸው። የአርበኛ ዘነበች የጀግንነት አገልግሎት በዚህ አላበቃም፡- «አገር ሰላም ሆኖ ነፃነታችንን ለማብሰር የአንድ ሻለቃ አዛዥ ሆኜ ሲዳሞ ክፍል ሀገር ገባሁ። ስላደረግሁትም አስተዋጽኦ የአርበኝነት የድል ኮከብ ሊሻንና ባለ 5 ዓመት የድል ኮከብ ተሸልሜአለሁ» ብላ ነበር። እንዲሁም አርበኛ ዘነበች ሴቶች አርበኞችን አሰባስባ እውቅና እንዲያገኙ 150 አባላት የነበረውን የአዲስ አበባ የእናት አርበኞች ማሕበርን ከአቋቋሙት መሀል ነበረች።[1]

በጦርነት የተዋጉና የወደቁ የጦር መሪዎች ልጆችና ሚስቶች በዚሁ በአምስት ዐመት ወቅት በስደተኝነት ውጪ ሄደው ነበር። ከነሱ መሀል ንጉሱን ተከትለው ወደ እንግሊዝ አገር የሄዱት ልጆች ልዕልት ፀሀይ፣የራስ ደስታ ዳምጠው ባለቤት ልእልት ተናኘ ወርቅና ልጆቻቸው፡ አይዳ፣ ሒሩት፣ ሰብለ ሲሆኑ ወደ እየሩሳሌም በስደት ከሄዱት መሀል ደግሞ የአልጋ ወራሽ ሴት ልጅ እጅጋየሁ

[1] *አዲስ ሕይወት* (በአኢሴማ. ማዕከላዊ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ የሚታተም) ቅፅ 8፣ ቁጥር 26፣ 1981፣ ገጽ 9

*አስፋው ወሰንና የራስ ደስታ ዳምጠው የመጨረሻ ሴት ልጅ ሶፊያ ይገኙበታል። የአርበኛው የደጃዝማች አበበ ዳምጠው ባለቤት ወሰንየለሽ መንገሻ እና ልጆቻቸው፣ ሙሉ እመቤት አበበ (የራስ ብሩ ባለቤት) እና ልጃቸው ፍቅርተ ብሩ፣ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ (በኋላ የአልጋወራሽ ባለቤት)፣ እና ወ/ሮ አክሎግ አበበ፣ የራስ እምሩ ባለቤት፣ ወ/ሮ ጽጌ ማሪያም (በኋላ ልዕልት) እስከ 8 ልጆቻቸው (ሴቶቹ:- የምሥራች፣ ማርታ፣ ሒሩት፣ ዮዲት፣ ዕሌኒ፣ ሩፋኤል፣ ማሚዩ፣) ከተሰደዱት መሀከል ነበሩ።*

*በዚሁ ዘመን ወደ ጣሊያን አገር በእስር ሴቶች ተወሰደው ነበር (በአንድ ወቅት ወ/ሮ ስንዱ እንዳሉት ወደ 30 የሚሆኑ ነበሩ)፤ ከነሱም መሀል የከንቲባ ገብሩ ባለቤት ወ/ሮ ካሣዬ የለምቱ ከነ ልጆቻቸው (ብርሃኔ፣ ስንዱ፣ ደስታ፣ ጽጌ፣ ገነት)፣ የሀኪም ወርቅነህ እሸቴ ባለቤት ወ/ሮ ቀጸላ ወርቅ ቱሉ ከ6 ልጆቻቸው ጋር (አስቴር፣ ኤልሳቤጥ፣ ሳራ፣ ርብቃ፣ ሶስና/ሱዚ እና ያሳደጉዋት የእህታቸው ልጅ ሮማን ወርቀ ኮርማ)፣ እንዲሁም የብላቴን ጌታ ሕሩይ ሴት ልጅ ገነት ሕሩይ እና የደጃዝማች በዛብህ ባለቤት ወ/ሮ ድንቅነሽ ተፈሪ፣ የደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል ባለቤት ወ/ሮ አፀደ ባቢቼቭ እና ሴት ልጆቻቸው (አማረችና ማርታ) ይገኙበታል። ብዙ ሴቶች ደግሞ በእስር ወደ ሱማሌያ ተወስደው የስቃይ ኑሮ የኖሩ ነበሩ። እንዲሁም ወደ አምስት ሌሎች ጎረቤት ሀገሮች፣ ማለትም ኬንያ፣ ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ ግብጽ፣ እና ማደጋስካር ከሄዱት ስደተኞች መሀል ሴቶች ነበሩ። በአጠቃላይ እነዚህ ሴቶች ከዘመናዊ ስልጣኔ አንድ አንድ ነገር ቀስመው በመመለስ ለቤተሰቦቻቸው ሆነ ለወገኖቻቸው አካፍለዋል።*

*ከ1933 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ ዘመናዊ እድገት እየዳበረ ሄዶ፣ ያገራችን የተማሩ ሴቶች ቁጥር እየበዛ ከጓዳ ወደ አደባባይ ዘልቀው ለሕብረተሰቡና ለአገር እድገት አስተዋጽኦ አድርገዋል። ዘመኑ ለሴቶች ዘመናዊ የትምህርት እድል ተከፍቶ ከጓዳ ወደ ሕብረተሰብ እንዲዘልቁ ያስቻላቸው ዘመን በመሆኑ፣ ላገር ልማትና እድገት አስተዋጽኦ ማበርከት የጀመሩበት ዘመን ነበር።*

*ከነፃነት መልስ ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግስት እንደገና ተቋቁሞ በ1966 ዓ.ም. እስከተጠናቀቀበት ድረስ ለሴቶች ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ ነበር። በ1952 ዓ.ም. በወጣው ሕገ መንግስት ውስጥ ስለ ሰው መብቶች በተመዘገበው ክፍል የጾታን ልዩነት የሚያስቀር አንቀፅ ተካቷል። በመጀመሪያ ከእንግሊዝ አገርና ከእየሩሳሌም ተምረው ከመጡት ወጣት ስደተኞች መሀከል ከፍተኛ ትምሕርት እድል በማግኘት ወደ ውጪ የሄዱና አገር ውስጥ የተማሩም ነበሩ። ሁሉም ተምረው ሲመለሱ ሞያተኞች በመሆናቸው በዚሁ ሙያቸው ተሰማርተው የመጀመሪያ ሴት ባለሙያዎች ሁነው ያልተቆጠበ አገልግሎት ሰጥተዋል።*

*በመንግሥት ሆኑ በግል ትምህርት ቤቶች: (በተለይ በሀይማኖት ድርጅቶች የተቋቋሙ) በአዲስ አበባና በክፍለ ሀገር ከተሞች: ሴቶች ከወንዶች ጎን እንዲማሩ ሁኔታዎች ተመቻቹ። ትምሕርት ሲጨርሱ በሺዎች የሚቆጠሩ የተማሩ ሴቶች አገልግሎት ሊሰጡ ወደ እሚችሉበት ሥራ ተሰማሩ።*

ሜሪ ታደሰ እና ሚሚ ወልደማሪያም፣ ሂሩትና ዮዲት እምሩ፣ ገነት ኤፍሬም፣ ወይንሸት በሻህ ውረድ የሚገኙበት በጠቅላላው 25 የሚሆኑ ሴቶች ወደ ግብፅና ቤይሩት ተልከው ነበር[2]፡፡ ሌሎች ደግሞ በሚቀጥሉት ዓመታት ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካና ኤስያ ለከፍተኛ ትምህርት እየተላኩ አገራቸው ተመልሰው በተማሩት እውቀት ማገልገል ጀመሩ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በአገር ውስጥ በተቋቋሙት ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ሴት ተማሪዎች እንዲካፈሉ በማበረታታት፣ በሞያ ማሰልጠኛ ተቋማት በማሰልጠን፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች በአስተማሪነት፣ በነርስነት፣ በፀሀፊነት፣ በባልትና፣ በዕደጥበብ ሙያ፣ በሙዚቃ፣ በዘፋኝነት፣ በሰአሊነት፣ በአይሮፕላን በረራ ጉዞ አስተናጋጅነት፣ በልብስ ሰፊነት እየሰሩ አያሌ አስተዋጽኦ ለሀገር አበርክተዋል፡፡

እንዲሁም፣ ቁጥራቸው ያነሰም ቢሆንም፣ በሕግ፣ በሳይንስ፣ በእርሻ፣ በህክምና፣ በአርኪተክቸር፣ በኢንጅኔሬንግ፣ በፕላን፣ መስኮች እንዲያገለግሉ የነጻነት ጉህ ከቀደደበት ጊዜ አንስቶ፣ ወጣት ሴቶች ከወንዶቹ ጋር ለትምህርት ወደውጭ ተልከዋል፡፡ እንዲሁም የማታ ትምሕርት በተጀመረበት ወቅት የሴት ተማሪዎች ቁጥር እየበዛ በመሄዱ፣ አበረታች አቅጣጫ ይዞ ነበር፡፡

የሴቶች ተሳትፎና አገልግሎት በአዲስ አበባ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን፡ ቀስ በቀስ፡ ወደ ክፍለ አገር ከተሞችና አካባቢዎች ተዛምቶ፣ በዘመኑ በርከት ያሉ ሴቶችን ከጓዳ ወደ አደባባይ አውጥቶ በትኩስ ሀይላቸው የተቻላቸውን ለሕብረተሰቡና፡ ለቤተሰብ እድገት ማበርከት ጀመሩ፡፡

በፖለቲካ አንፃር፣ የሴቶችን ተሳትፎ ስንመለከት፣ አንድ አንድ ሁኔታዎች እንደሚያመለክቱት፣ ከንጉሣዊ ቤተሰብ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ድረስ፣ በስውር ሆነ በይፋ ሴቶች በፓለቲካ መሳተፍ የጀመሩበት ዘመን ነበር፡፡

በንጉሱ አካባቢ የነበረውን የፓለቲካ ሁኔታ በሚመለከት፣ የንጉሱ ታላቅ ሴት ልጅ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃይለ ሥላሴ ትልቅ ተሰሚነት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ፣ የልዑል አልጋወራሽ ባለቤትና የአርበኛው ሜ/ጄነራል አበበ ዳምጠው ልጅ መንፈሰ ብርቱ መሆናቸው እየተሰማ ከወሬም አልፎ በታሕሳስ 1953 ዓ.ም በተከናወነው መፈንቅለ መንግሥት የተጫወቱት ሚና ቀላል እንዳልነበረ ይገመታል፡፡

---

[2] እነዚህ ልጃገረዶች በልሂቃን ቤተሰቦች ውስጥ የተወለዱ ነበሩ፤ ሜሪ ታደሰ፣ የአቶ ታደሰ መሸሻ ልጅ ሲሆኑ፣ አቶ ታደሰም እስከጣልያን ወረራ ድረስ የአፄ ኃይለሥላሴ ልዩ ረዳት (ጸሀፊ) ነበሩ፤ ወንድማቸው፣አቶ ማሞም ሆኑ እሳቸው፣ በሚኒስቴርነት ኢትዮጵያን እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ለአያሌ አመታት አገልግለዋል፡፡ የሚሚ ወልደማርያም አባት የተለያዩ ከፍተኛ የስልጣን ቦታዎች ይዘው አገራቸውን ካገለገሉ በኂላ፣ ጣልያን ኢትዮጵያን ሊወር ሲቃረብ በፈረንሣይ የኢትዮጵያ አምባሳደር (በሚኒስትር ማዕረግ) ሆነው ነበር፡፡ ሁለቱም ቤተሰቦች ካቶሊኮች ነበሩ፡፡ ሂሩትና ዮዲት የታወቁት የልዑል ራስ እምሩ ልጆች ሲሆኑ፣ ገነት ደግሞ የብዙ ዘመኑ ዲፕሎማት የብላቴን ጌታ ኤፍሬም ተወልደ መድህን ልጅ ነበሩ፡፡ የወይንሸት አባት፣ የአፄ ኃይለሥላሴ የቅርብ ረዳት ነበሩ፡፡ የብላታ ሎሬንዞ ታእዛዝ ልጅም የዚሁ ቡድን አባል ነበረች፡፡

በሕብረተሰቡ የነበረውን የፓለቲካ ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ከየወረዳው ወደፓርለማ ተመርጠው የመጡ ሴቶች አገርን በሚመለከት በሚካሂዱት የፓለቲካ ውይይቶች በመካፈል ድርሻቸውን አበርክተዋል።

የፓለቲካ ትኩረታችንን ወደ ዩኒቨርስቲና ወደ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስናዞር ደግሞ፣ በተለይ በ60ዎቹ፣ የሀገር ፓለቲካና ኢኮኖሚ አሳሳቢ ደረጃ በመድረሱ በተማሪዎች አካባቢ ንቅናቄዎች ሲከሰቱ በመሀላቸው ሴት ወጣቶች ተካፍለዋል።

## ሴቶች ሳገር እድገት በዘመኑ ምን እንዳበረከቱ መጠነኛ ዝርዝር፡-

*ማ? ምን? መቼ? በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ባመቸ መንገድ ተዘርዝሮ እንደሚከተለው ቀርቧል። የቀረቡት ማስረጃዎች ለናሙና ያህል ናቸው።*

**በትምህርት ዘርፍ - ከሞግዚትነት እስከ ትምህርት ቤት ባለቤትነት፡**

(ሀ) በዘመኑ ልጅ አገረዶች ለብቻቸው ከቤት ውጪ ማደር ያልተለመደ በመሆኑ፣ የሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤቶች ሲቋቋሙ በሞግዚትነት የሚሠሩ ልጅ አገረዶችን የግል ንጽህና አጠባበቅ፣ ወዘተ... የሚቆጣጠሩ ሞግዚቶች ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ለምሳሌ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አደዬ ኪዳን፡ አደዬ አመቴ እና አደዬ ጎመሽ ገብረ እስታቲዮስ ይገኙበታል። (አደይ ጎመሽ የሚገርመው በባለቤታቸው ስም ነበር የሚጠሩት፤ ያባታቸው ስም ወልደ ሚካኤል ነበር።)

(ለ) በፊደል አስተማሪነትና በሞግዚትነት- ወይዘሮ በፍቃዷ እና ወይዘሮ ሮማን በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት የአማርኛ ጽሕፈት አስተማሪ ነበሩ (በዚያን ዘመን የፊደልና የንባብ አስተማሪዎች የተለያዩ ነበሩ)።

የጅምናስቲክ አስተማሪ ጀንበር የሚባሉ እና ጽዮን አንዶም ነበሩ። ከዚያም በኋላ በ2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ጋር አብረው ትምሕርት መካፈል ሲጀምሩ ተጨማሪ የጤና ነክ ቁጥጥር በማድረግ፡ ተገቢውን እንክብካቤና ምክር በመስጠት በሞግዚትነት የሚቆጣጠሩና የሚያገለግሉ ሴቶች ነበሩ። በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሱፐርቫይዘርነት የትምሕርት ቤት ሠራተኞችን በመቆጣጠር ትርሲት አበበ ነበሩ።

(ሐ) በመንግሥትና፡ በሀይማኖት ትምሕርት ተቋም፡ በአዲስ አበባም ሆነ በክፍለ ሀገር ከተሞች፡ ቁጥራቸው ከፍ ያለ ሴቶች ባንደኛ ደረጃ አስተማሪነት ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል።

ለናሙና ያህል ትምህርት ለሴቶች ሆነ ለወንዶች በተለያየ አቅጣጫ እንዲጠናከር ካበረከቱት ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፡- በእንግልዝኛ ትምህርት፡ በናዝሬት ትምህርት ቤት፡- ዕሌኒ እምሩ፤ ኪሮስ ሀብቱ፤ በ2ኛ ደረጃ አስተማሪነት፡ (አመሃ ደስታ ትምህርት ቤት) ወይንሸት በሻውረድ ይገኙበታል።

(መ) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪነት፡- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በ1954 ወደ ሙሉ ዩኒቨርስቲ ካደገ በኋላ የሴት መምህራን ቁጥር እየጨመረ ሄደ፤ እንዲሁም የሴት ተማሪዎች፡፡ በተለይ በሶሻል ወርክ ትምህርት ክፍል ትምህርቱ ተማሪዎችን ወደ ችግር የበዛባቸው የከተማ ክልሎች ለጥናታዊ ሥራ በመላክና ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ከመምህሮቻቸው ጋራ በመማከር ሁለቱም ወገኖች - ማለት ተማሪዎቹና መምህሮቹ - ለአካባቢ ችግሮች ተግባራዊ መፍትሄ እንዲኖር ግልጽ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

በሶሻል ወርክ ትምሕርት በመምሕርነት ከተሰማሩት ሴቶች መሐል፡- ሂሩት እምሩ፡ የሶሻል ሳይንስና አንትሮፖሎጂ መምሕር፣ አልማዝ እሸቴ፡- የሳይኮሎጂ መምሕር በተለይ በትምሕርትና በእድገት ሳይኮሎጂ (Education & Development Psychology ) መምህር አሳሰቡ፣ ፊያሜታ ፕሮታ የሶሻል ወርክ መምህር ነበሩ፡፡[3]

በሌላ ትምሕርት የተሰማሩ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች አገልግሎታቸውን በመጥቀስ በትምሕርት ዲፓርትመንት ረዳት ፕሮፌሰር፡- መዐዛ በቀለ ኒፓን፣ በባዮሎጂ (ባዮ ኬሚስትሪ)፡- ጫልቱ ግፋወሰን፣ ሙሉእመቤት ምትኩ፡- በአካውንቲንግ እና በቢዝነስ ፋክልቲ ምስራቅ ኤሊያስ በመምህርነት አገልግለዋል፡፡

ከአስተማሪነት ባሻገር የሥራ ሃላፊነት በመጋራት አገልግሎት የሰጡም ነበሩ፡ በዩኒቨርሲቲ መዝገብ፡ ክፍል፡- የሺእመቤት እማኙ፡ የክፍሉ ምክትል አስተዳዳሪ አረጋሽ ገብረ ሥላሴ፡- በኤክስቴንሽን ክፍል ደግሞ ዲን አለሚቱ ነበሩ፡፡

(ሠ) የትምሕርት ቤት ዳይሬክተርነት፡- የውጪ አገር ሰዎች ትምህርት ቤቶችን ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ ቀስ በቀስ ያገር ተወላጆች የዳይሬክተር ሀላፊነት ወስደው አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሴት ተማሪዎች መሰረታዊ አስተዳደግ እንዲኖራችው አድርገዋል፡፡ ከነኚህ ዳይረክተሮች መሀል በእቴጌ መነን ት/ቤት፡- እመቤት ሂሩት ደስታ፣ ስንዱ ገብሩና የሺሀረግ አበበ ይገኙበታል፡፡

እመቤት ሂሩትን እና ስንዱ ገብሩን አንዳንድ ተማሪዎች ሲያስታውሱአቸው እንዲህ ብለዋል፡፡ በተለይ ልዕልት ሂሩት እንግሊዝ አገር ያከማቹትን እውቀት ለተማሪዎቻቸው ለማካፈል ብዙ ይጥሩ ነበር፡፡ በዚህ አክዋያ የእንግሊዝ ግጥም ደራሲያኖችን (እንደ ሼሊ፣ ዊልየም ብሌክ፣ ወዘተ) ያስተምሩ ነበር፡፡ በወቅቱ ተማሪዎቹ ግራ ቢገባቸውም በጊዜ ብዛት አንዳንዶቹ እየወደዱት ሄደዋል፡፡ በደግነታቸውና ለሁሉም በሚሰጡት አክባሪ ጠባያቸው በሁሉም ዘንደ ይወደዱ ነበር፡፡ ወይዘሮ ስንዱ ደግሞ በዳይሬክተርነታቸው የሚታወቁት፣ ልጆቹ በስነስርአት እንዲያድጉ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀሙ ስለ ነበር ነው፡፡ እንዲሁም

[3] ፊያሜታ ፕሮታ፣ በሁዋላ ላይ ታዋቂው የስነጽሁፍ ሰው፣ በአሉ ግርማ በጻፈው ዝነኛው ኦሮማይ ልብወለድ ውስጥ ለሳሳት ዋና ገጸ ባህርይ በሞዴልነት ወይም በመነሻነት የተጠቀመባቸው ወጣት ሴት ናቸው፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ውስጥ ከበአሉ ቀድመው ገብተዋል፡፡ ስለዚህ፣ “ፊያሜታ” የበአሉ ታላቅ ወይም ሲንየር ነበሩ፡፡

በተለይ በሚደርሱት ትያትሮች ለተማሪዎች መድረክ እየፈጠሩ የትያትር ፍቅር እንዲዳብር አድርገዋል፡፡

ከዚህም አልፎ፣ ተማሪዎቻቸው ስለ አካባቢአቸው እንዲያውቁ ያበረታቱ ነበር፡፡ ለምሳሌ አንድዋ ተማሪ (በተራዋ ከዓመታት በኋላ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የሆነችው) ወ/ሮ የሺሀረግ አበበ፡ ከጎጃም ከፍለ ሀገር መጥታ አንደ ቀን ቢሮአቸው ቀርባ ጋዜጣ ማንበብ እፈልጋለሁ ብላ ስትጠይቃቸው ተገርመው በመጀመሪያ ትኩር ብለው ካስተዋልዋት በኋላ ጋዜጣ በየጊዜው እንዲቀርብላት እንዳደረጉ ታስታውሳለች፡፡

(ረ) የግል ትምህርት ቤቶች መቋቋም ሲጀምሩ ደግሞ በባለቤትነት፡- እመቤት ሶፊያ ደስታ (የመዋዕለ ሕፃናትና የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)፣ ወ/ሮ ሕይወት መንገሻ፡ (የመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት) ይጠቀሳሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሴቶች በጎ ሥራ አገልግሎት በ1952 ዓ.ም በመካከለኛ ወረዳ የሠፈር ትምህርት ቤት ሲከፍት ሥር አመራር ፕሬዚደንት ወ/ሮ ዘውዲቱ አምባቸው ሲሆኑ ትምህርት ቤቱ እስከ 4ኛ ክፍል 401 ተማሪዎች ነበሩት፤ በሀይማኖት ድርጅት ከተቋቋሙት የግል ትምህርት ቤቶች፣ የአሜሪካን ሚሽን ትምህርት ቤት ርዕሰ መምሕር ወ/ሮ ኤልሣቤጥ ካሮርሳ ይገኙበታል፡፡ እሳቸውም ሴቶች በትምሕርት እንዲታነጹና ከወንዶች ያላነሰ ትምሕርት እንዲያገኙ ጥረዋል፡፡

እነዚህን ለናሙና አቀረብናቸው እንጂ ሌሎች ስማቸው ያልተጠቀሱ ብዙ እህቶች በትምህርት ዘርፍ አስተዋጽኦ ያደረጉ እንዳሉ አይዘነጋም፡፡ እዚህ እንዲካተት የፈለግነው ትምሕርት ሚኒስቴር ከአሜሪካን ተራድኦ ድርጅት ጋር በመተባበር የመጡትና በየክፍለ ሀገሩ የተሰማሩት የሴት ሰላም ጓድ አስተማሪዎች (Peace Corps) በራሳቸው እውቀት ተመክተው በባእድ አገር በሥራ ተሠማርተው በማየታቸው ለአገር ወጣት ሴቶች ከጓዳና ከማጀት ወደ አደባባይ እንዲወጡ ምሳሌና አርአያ ሆነውላቸዋል፡፡ እንዲሁም ወጣት ሴቶችን ወደ አውሮፓና አሜሪካ ለትምሕርትም ሆነ ለጉብኝት በመላክ ተነቃቅተው በመመለስ ለሴቶች ለወደፊቱ የዘመናዊ ስልጣኔ፣ እድገትና ለፓለቲካ ሂደቱ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

## በጤና ጥበቃና በህክምና ዘርፍ የሴቶች አገልግሎት

ዘመናዊ የጤና አገልግሎት በሰፊው ወደሕብረተሰቡ እስኪዘልቅ ድረስ አገልግሎቱ በዘልማድ በተገኘው ዘዴ ይከናወን ነበር፡፡ በዚህ አክዋያ የሴቶች አገልግሎት ሰፊ ነበር፡፡ በተለይ የቤተሰብን ጤና በሚመለከት፣ ባዋላጅነት ሴቶችን በሚያጠቁ በሽታዎች ወዘተ. . . አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ከብዙዎቹ የአንዷን ስም ለመጥቀስ ያህል ወ/ሮ አሰለፈች ነብሴ የተባሉ በዚህ ዘመን በሰላሌ አውራጃ በፈረስ እየተዘዋወሩ ሁለገብ ነፃ የጤና አገልግሎት በመስጠት ታውቀዋል፡፡ ባሁኑ አጠራር በመጠኑ፡ የParamedical አገልግሎት ይሰጡ ነበር ማለት ነው፡፡

*በነርስነት፡-* በዚህ ዘመን፡ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ክፍለ ሀገር ከተሞች በተቋቋሙት ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች፣ ሴቶች በነርስነት (በመንግሥትና በሀይማኖት ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች፣ በቀይ መስቀል) ከፍ ያለ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በመንግሥት በኩል በመጀምሪያ በያመቱ እስከ 50 ነርሶች፣ በኂላም ከመቶ በላይ፣ እየሰለጠኑ ወደ አገልግሎት ይሰማሩ ነበር፡፡ ከዚያም በላይ ለሀላፊነት ሥራ ብቁ እንዲሆኑና የውጪ አገር ባለሙያዎችን እንዲተኩ ለማድረግ ውጪ አገር እንዲሰለጥኑ ቁጥራቸው ውስን የሆኑ ሴቶች ወደ ዩጋንዳ፣ ወደ እስራኤልና ወደ ሊባኖስ ተልከው፣ በነርስነት ሰልጥነው በሜትረንነት አገልግለዋል፡፡

ከነዚህም መሐል የመጀመሪያዎቹ ፈር ቀዳጆች፡- ሲስተር ጥሩወርቅ፣ ሲስተር ተናኜ ደርቤ፣ ሲስተር አስቴር አያና፣ ሲስተር ጌጤ ኃይለማሪያም እና ሲስተር አሰገደች አሰፋ ይገኙበታል፡፡

ስዊድን አገር በነርስነት ሰልጥነው አገልግሎት ከሰጡት መሀከል፡-- ሲስተር ኢትዮጵያ፣ ሲሰተር ሸዋረገድ፣ ሲስተር ብፅዒቱ ባይሩ እና ሲሰተር የሺ አስፋው ይጠቀሳሉ፡፡

*በሜትረንነት የተሰማሩ* - ዩጋንዳ የሚገኘው ማካሬሬ ዩኒቨርስቲ ሰልጥነው ከተመለሱት መሐከል፣ በመጀመሪያ በአጤ ሚኒልክ ሆስፒታል በተራ የሜትረን ሥራ እየተለማመዱ፣ ከዚያም በልዩ ልዩ ሆስፒታሎች በሜትረንነት ያገለገሉ፡- ሲስተር ጫማሽ ወርቅ ስዩም፣ ሲስተር ሙሉ ዳባ፣ ሲስተር አስናቀች ገብሬ፣ ሲስተር አበራሽ ተርፋ፣ ሲስተር ላቀች ተፈሪ ነበሩ፡፡

እንግሊዝ አገር ሰልጥነው ከተመለሱ በኂላ፣ አገራቸውን በሜትረንነት የሚከተሉት ሁለት ሴቶች አገልግለዋል፡፡ ሲስተር ሥርጉት ሥነ ጊዮርጊስ (በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል፣ ያሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል)፣ ሲስተር ጥሩወርቅ አስፋው (በልዕልት ጸሐይ ሆስፒታልና በጋንዲ ሆስፒታል)፣ ሲስተር ምህረት ጳውሎስ (የቀድሞው ፓለስታይን ግዛት የአሁኑ እስራኤል ሰልጥና ተመልሳለች) የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትን የጤና ክፍል አቋቁማ ብዙ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ ከቤይሩት (ሊባኖስ) ከተመለሱት መሃል ሲስተር ሸዋረገድ እና ሲስተር ተናኜ ደርቤ ይገኙበታል፡፡ ሲስተር ተናኜ ባለ ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ ስትሆን በልዕልት ጸሐይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል የነርስ ትምህርት ቤት አስተማሪ ነበረች፡፡

በተጨማሪ ልዩ ሞያ ካላቸው ሐኪሞች ጎን በመቆም አገልግሎት ከሰጡት መሐል፡- በአይን ህክምና፡- ሲስተር ኬንያ፣ ባዋላጅነትና በቀዶ ጥገና ሲስተር ሮማን አለማየሁ፣ በሕፃናት ክሊኒክ (Paediatric Clinic) ሲስተር እጅጋየሁ ዱሬሳ፣ በቀይ መስቀል፡- ሲስተር ሙሉ እመቤት ፋሪስ፣ በኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ሲስተር እጅግአየሁ ነጋ፣ በልዕልት ጸሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል የተቋቋመው የደም ባንክ (Blood Bank) እንግሊዝ አገር ተምራ የተረከበቺው

ሲስተር አየለች ነበሩበት፡፡ ቀላል የሕክምናን ሙያ አሠልጣኝ የነበረች ሲስተር ዘነበችወርቅ ለገሠ ትገኛለች፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ነርሶች፣ አሁን ለናሙና ያቀረብናቸው ናቸው እንጂ፣ ሌሎች ብዙ መኖራቸው አይካድም፡፡

*በጤና መኮንንነት፡-* በጎንደር ከተማ የጤና ኮሌጅ (ያሁኑ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ) በተቋቋመው የጤና መኰንኖች ስልጠና፣ በያመቱ ለ5 ዓመት ያህል፣ እስከ 50 ሴቶች እየሰለጠኑ ለገጠሩ ሕዝብ የጤና አገልግሎት በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ከነዚህም መሀል፣ ከፍተኛ ውጤት በማምጣቷ ሲስተር አዳነች ኪዳነ ማርያም፣ የትምህርት ዕድል በውጪ አገር በማግኘቷ በጤና ጥበቃ አስተዳዳሪነት የዶክትሬት ማእረግ ይዛ ከአገለገለች በኋላ የተጠቀሰው ዘመን አልፎ በኢህአዴግ መንግስት የመጀመሪያዋ የሴት ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ለመሆን በቅታለች፡፡

*በሐኪምነት፡-* ዶ/ር ውዳድ ኪዳነ ማርያም፡ ቤይሩት (ሊባኖስ) ሰልጥነው የመጀመሪያዋ የሴት ሀኪም በመሆን በማህፀን ህክምና፣ በሥጋ ደዌ በሽታ አማካሪነት፣ በኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአስተዳዳሪነት፣ እንዲሁም በተሰማሩበት ሥራ ሁሉ ከፍ ያለ አገልግሎት ላገር አበርክተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህክምና ፋክልቲ የመጀመሪያ ምሩቅ ሆነው አገልግሎት የጀመሩ ደግሞ ዶክተር ፍሰሃ ገብረወልድ ነበሩ፡፡

በትምሕርትና በጤና ላይ ያተኮርንበት ምክንያት በተለይ መሠረታዊ የእድገት ዘርፎች በመሆናቸው ስለሆነና ሴቶች ከጅምሩ በሰፊው አስተዋጽኦ ያበረከቱዋቸው ዘርፎችም በመሆናችው ነው፡፡

## በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች (ከፅዳት ሠራተኛ እስከ ሚንስትር ዴታ) ሴቶች ያበረከቱት አስተዋጽኦ

ሴቶች በመንግሥት ሥራ በይፋ ተሳትፈው መሥራት የጀመሩት በዚህ ዘመን ነበር፡፡ በጽዳት ጥበቃ፣ ሻይና ቡና በማቅረብ፣ በፀሀፊነት መሰረታዊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም አልፎ፡ ሙያቸው በሚፈቅደው በተለያየ ደረጃ፡ በሙያም ሆነ በሹመት ተመድበው አገልግለዋል፡፡

### በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር

አንዳንድ ሴቶች በተለያየ ክፍል በረዳትነት አገልግለዋል፡፡ ይህ እንዳለ ሲሆን አምባሳደር ዮዲት እምሩ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በአፍሪካ ክፍልና በተባበሩት መንግስታት ክፍል እንዲሁም በውጭ አገር በዲፕሎማትነት ለብዙ ዓመት አገልግለው የሚኒስትር ዴታ ማዕረግ ደርሰው ድርሻቸውን አበርክተዋል፡፡ ወይዘሪት ኢትዮጵያ ሐረጎት ደግሞ የሚኒስትሩን የአፍሪካን ክፍል በመምራት

ሠርተዋል:: እንዲሁም ወይዘሮ ማርታ ገብረፃዲቅ የፓስፖርት ክፍል ሹም ነበሩ::

**በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

በጤና ነክ ሥራ በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች ከሚንስቴሩ መሥሪያ ቤት ውጪ አገልግሎት የሚሰጡ ሲኖሩ፣ በሚኒስቴሩ ውስጥ ወይዘሮ ሶፍያ አብርሀም በምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ በውጪ ድርጅቶች ሥራ የክፍል ሓላፊ ሁነው፣ እንዲሁም ሲስተር ሰንበቱ ገብሩ የነርሶች ክፍል ሓላፊ ሆነው ለበርካታ ዓመታት አገልግሎት አበርክተዋል::

በጤና ጥበቃና በስዊድን መንግሥት ተራድኦ፣ በልእልት ፀሐይ ሆስፒታል (ያሁኑ ጦር ሓይሎች ሆስፒታል) በተቋቋመው የሕፃናት ምግብ ምርምር ተቋም፣ ወይዘሮ አበባ ኅበዜ፡ በሙያቸው በምግብ አመጋገብ ሳይንስ አገልግሎት ለመስጠት (Nutrition) የመጀመሪያ በመሆን፡ በዚሁ ሞያ ተሰማርተው ለሕፃናት የተሟላ አመጋገብ ጥናት አድርገው እንደ ፋፋ ያሉ ምግቦች እንዲዘጋጁ በማድረግ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: እንዲሁም ያገራችንን ምግቦች፣ በተመረመረ ሁኔታ፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ መጽሐፍ እንዲታተም በማድረግ የተመጣጠነ ጤናማ አመጋገብን በሚመለከት ሕብረተሰቡ እንዲረዳ እድርገዋል::

**በትምሕርት ሚኒስቴር**

ዘመኑ ሴቶች ትምህርት እንዲያገኙ ሙከራ የተጀመረበት ነበር:: ይህንንም በመመልከት፣ መንግሥት ሴቶችን በተለያየ የትምህርት ዘርፍ (ባገር ውስጥም ሆነ በውጭ) በማሰልጠን በትምህርት ምኒስቴር እየተመደቡ ሰፊ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል:: ከነዚህም መሀል:-

ሀ. ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ- ምክትል ሚንስትርነት ደረጃ ደርሰው በትምህርትና ባህል ነክ ጉዳዮች መምርያ ኃላፊ ሆነው ካበረከቱት የተለያየ አገልግሎት መሀል የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት እንዲቋቋም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: እንዲሁም የስነ ጥበብ ትምህርት ቤት እንዲስፋፋ ጥረዋል::

ለ. ወ/ት አፀደ ካህሳይ- በሚኒስቴሩ ውስጥ የ2ተኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ክፍል ኃላፊ ሆነው በመምራት የትምህርት ቤቶች ሂደት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መምሪያዎች በማዘጋጀት ሠርተዋል::

ሐ. ወ/ሮ መና የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች ክፍልን በመቆጣጠር ሠርተዋል::

መ. ዶ/ር መአዛ በቀለ፣ ወ/ሮ ገነት ዘሪሁን እና ወ/ሮ አንጄሊና ማንጎ በስርዓተ - ትምሕርት ክፍል ለልዩ ልዩ የትምህርት ቤት ደረጃዎች ተስማሚ የሆነ ሥርዓተ ትምሕርት በመንደፍ አገልግሎት ሰጥተዋል[4]፡፡

ሰ. የሴቶች ተሳትፎ በተግባረ እድ ሥራ እንዲበረታታ በማለት በትምሕርት ሚኒስቴር ውስጥ የቴክኒክ ክፍል ተቋቁሞ (Technical Vocational Education for Girls) ወ/ሮ ሰብለወንጌል የሸዋሉል ይመሩት ነበረ፡፡

ረ. ወ/ት የሺ ተፈሪ የጥናትና የስታቲስቲክስ ሹም ሆነው ለትምሕርት ሂደት ለሚረዱ ማስረጃዎች በማሰባሰብ አገልግለዋል፡፡

ሠ. ትምሕርት የእድገት መሠረት በመሆኑ እድሉ በተቻለ መጠን በሰፊው እንዲዳረስ በማድረግ በትምሕርት ሚኒስቴር (በእንግሊዞች ተራድኦ) የተቋቋመው መገናኛ ብዙሀን ማዕከል በአዲስ አበባና በተወሰኑ ያገሪቱ ክፍለ ሀገራት ላሉ ተማሪዎችና ላልተማሩ ጎልማሶች፣ ጠቃሚ ትምሕርት በማሰራጨት ማዕከሉ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ወ/ሮ ራሄል መኩሪያና ወ/ሮ ሮዛ ገብረ ሥላሴ (የትምሕርት ነክ ፕሮግራም አዘጋጆች) አስተዋጽኦቸው ከፍ ያለ ነበር፡፡

በትምሕርት ሚኒስቴር ውስጥ ስማቸው የተጠቀሱትና ያልተጠቀሱትም ሴት ሠራተኞች ጭምር ባገራችን ትምሕርት ስርዓትና ግንባታ ሥራ በመሳተፋቸው የሥራ ድርሻቸው ቀላል አለመሆኑን እናስመዘግባለን፡፡

*በፕሮፓጋንዳ ሚኒስቴር--ማስታወቂያ ሚኒስቴር፡፡* በማስረጃ ሥርጭት ሥራ (Information Dissemination) ከፀሀፊነት እስከ ቴሌቪዢን ፕሮግራም አዘጋጅነት ሴቶች ያበረከቱት አስተዋጽኦ፡፡

ከጣሊያኖች በተወረሰው አሠራር በፕሮፓጋንዳ ሚኒስቴርነት ተሰይሞ ይታወቅ የነበረው ከጥቂት ዓመታት በኋላ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተብሎ ነበር፡፡ ሴቶች በዚሁ ሚኒስቴር በማስረጃ ሥርጭት ሥራ መሠረታዊ አገልግሎት የሰጡበት ዘመን ሲሆን አንዳንዱን ከዚህ ቀጥሎ እንጠቅሳለን፡-

*በሬድዮ ዜና አቅራቢነት* በአማርኛ ዜና አቅራቢነት በ1940 ዓ.ም. ቅድሚያ የያዘችው ሮማነወርቅ ካሳሁን ነበረች፡፡ ይህ የሆነው ሴቶች ዜና አንባቢነት እንዲሰሩ በቢ.ቢ.ሲ. ከመፈቀዱ በፊት ነበር፡፡ ቀጥሎ ዕሌኒ ፈጠነ እና አሰገደች ይበርታ፡ ይገኙበታል፡፡ የውጪ አገር ቋንቋ ስርጭት ሲስፋፋ በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ዜና ዓለምሰገድ ሕሩይ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ደግሞ ታቦቷ ወልደ

---

[4] ዶ/ር መአዛ በቀለ፣ ኢትዮጵያዊ ያገቡና ኢትዮጵያዊ ስም የወሰዱ፣ የጃሜይካ ተወላጅ ነበሩ፤ ሙሉ ስማቸውም፣ መአዛ በቀለ ኒፓን ነበር፡፡ ለዶክትሬት ዲግሪ ያቀረቡት ጥናት እጅግ ጠቃሚ ስለነበረ እስከዛሬ ድረስ በማጣቀሺያነትና (ለምርምር) በመነሻነት ሲያገለግል ቆይቷል፡- ይህም ጥናትም ታትሟል፡- Maaza Bekele, *A Study of Modern Education in Ethiopia* (New york Colmbia University, Teachers College, 1966)

ሚካኤል፣ ነፃነት አስፋው፣ ማርታ አማረና፡ ዕሌኒ መኩሪያ በዚሁ ሞያ አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም በዜና አገልግሎት ውስጥ ትርንጎ አርጋው ነበረች፡፡

*በፕሮግራም አዘጋጅነት-* የሮማነ ወርቅ ካሳሁንን ፈለግ በመከተል፡ ሴት ፕሮግራም አዘጋጆች ለህብረተሰብ አድማጮች ወቅታዊ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ያቀርቡ ነበር፡፡ በዚህም ሥራ ከተሰማሩት መሀከል፣ አሰገደች ይበርታ፣ አልማዝ ደጀኔ፣ አስቴር ሞገስ ነበሩበት፡፡ አሰገደች ይበርታ፣ «*ሴቶች በአደባባይ*» በተባለው ፕሮግራም የታወቁ ሴቶችን ታሪክ በማስረጃ እየደገፈች ታስተዋውቅ ነበር፡፡ ሌሎች ደግሞ (እንደ አልማዝ ደጀኔና አስቴር ሞገስ) በሙዚቃ ፕሮግራም ዝግጅት አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታቦቷ ወልደ ሚካኤል፣ ነጻነት አስፋው፣ ማርታ አማረ፣ ዕሌኒ መኩሪያ ነበሩ፡፡ በምንመለከተው ዘመን በኢትዮጵያ ድምጽ ሬድዮ በልዩ ልዩ ያገር ቋንቋዎች አለታዊ ስርጭት ተጀምሮ ነበር፡፡ ቋንቋዎቹም አፋርኛ፣ ሱማሊኛና አረብኛ ነበሩ፡፡ በእነኚህ ክፍሎች ውስጥ (ለምሳሌ በሶማሊኛ ፕሮግራም) ኒምኦ አሊ ሲጠቀሱ፣ የሱማሊኛ ክፍል፣ እንደ አማርኛው ክፍል፣ የራሱ ኦርኬስትራ ነበረው[5]፡፡ ከሙዚቀኞች መሀል የታወቁት ድምጻውያን ማሪያን እና ሀዋ ነበሩ፡፡

እንዲሁም በ1958 በተቋቋመው በብሥራተ ወንጌል ሬድዮ ጣቢያ፣ በእንግሊዝኛ ዓለምሰገድ ሕሩይና ዕሌኒ መኩሪያ ነበሩ፡፡ በፈረንሳይኛ ዜና አቅራቢ ጸዳለ ወርቁ ነበረች፡፡ በብስራተ ወንጌል ሥር በሚተዳደረው የምሥራች ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ ደግሞ፡- በአማርኛ ፍቅርተ ሀይሌ፣ በኦሮምኛ ማርታ ነመራና ማርታ ኩምሳ፣ በትግሪኛ ደግሞ ብርሀን ተድላ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

*በሬድዮ ፕሮግራም አሰልጣኝነት* ሬድዮ ፕሮግራም ጥራት እንዲኖረው በመታመኑ በብሥራተ ወንጌል ውስጥ ፕሮግራም አዘጋጆችን ማሰልጠን የተጀመረበት ዘመን ነበር፡፡ በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በህንድ አገሮች ጭምር እየተዘዋወሩ ያሰለጥኑ የነበሩት ወ/ሮ ዓለም ሰገድ ሕሩይ ነበሩ፡፡

*የሙዚቃና ዶክዩመንት ቤት* (Transcription Library) የተደራጀ የሙዚቃና የዶክዩመንት ቤት ከጅምሩ የተዘጋጀው በጣቢያው ሴቶች ነበር፡፡ ዕሌኒ መኩሪያ በሬድዮ ኢትዮጵያ በሙዚቃ ክፍል ሥር በሚገኘው ቤተ መጻሕፍት (Transcription Library) ኃላፊ ሆነው ከ ወ/ሮ አለሚቱ ይበርታ፣ ወ/ሮ ጸጋዬ ወ/መድህን፣ ከሉሊት ተስፋዬ ጋር በመሆን በማደራጀት፣ ወ/ሮ ምሕረት ሳሙኤል፣ ወ/ሮ ሣራ ጽጌ፣ ወ/ሮ ሞገሳ አበበ ደግሞ በብሥራተ ወንጌል ራድዮ ጣቢያ፣ በየምሥራች ድምፅ ደግሞ ወ/ሮ ብርክት ተክለ ሚካኤል አገልግለዋል፡፡

---

[5] ይህ አረፍተ ነገር ለአሁን ዘመን አንባቢ ግር ሊል ይችላል፡፡ በዚያን ጊዜ፣ በሬዲዮ ሙዚቃ የሚተላለፈው ሙዚቀኞቹ ከነመሳሪያቸው ጣቢያው ድረስ በመሄድ ሲተውኑ ነበር፤ ስለዚህ እያንዳንዱ የሬዲዮ ጣቢያ የራሱ ኦርኬስትራ ያስፈልገው ነበር፡፡

*በጋዜጠኝነት* በሴቶች አካባቢ ያሉ ሁኔታዎችን ጽፎ በማሳወቅ፣ ማበረታቻ ጽሑፎች በማቅረብ፣ ማንነታቸውን ለሕብረተሰቡ በማሳወቅና ምን እንዳበረከቱ በመግለጽ ሴቶች በጋዜጠኝነት ሥራ መካፈል የጀመሩት በዚሁ ዘመን ነበር:: ከነዚህም አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል:- በአማርኛው እለታዊ ጋዜጣ *አዲስ ዘመን* ዕሌኒ ፈጠነ፣ ፍቅርተ ሓይሌ፣ ብዙ ወንድምአገኘሁ ይገኛሉ:: በእንግሊዝኛው እለታዊ ጋዜጣ *ኢትዮጲያን ሄራልድ* (Ethiopian Herald) ደግሞ: ጥሩወርቅ ዳዊት፣ ሶፊያ ይልማ ይጠቀሳሉ::

ዕሌኒ ፈጠነ በጋዜጠኝነት ሥራዋ ሰፊ አገልግሎት ሰጥታለች:: ጠቃሚነቱ እስከዛሬ ዘልቋል:: ለምሳሌ *በአዲስ ዘመን* እለታዊ ጋዜጣ የሚወጣው ሳምታዊ የጽሁፎቿ ስብስብ: ሴቶችን በሚመለከት ጉዳይ፣ ጥሩ የምርምር ምንጭ ሊሆን ይችላል::

ፍቅርተ ሀይሌና ብዙ ወንድም አገኘሁ በዘመኑ በጋዜጠኝነት ሥራ የቆዩ ባይሆኑም: ለኢንቬስትጌቲቭ ዘገባ (investigative reporting) ፣ የጋዜጠኝነት ዘዴ ተጠቅሞ ድብቅ የሆነ ሁኔታን ፈልፍሎ በማውጣት፣ ለአንባቢያን በማሳወቅ፣ አበረታች አገልግሎት ሰጥተዋል:: ለመጥቀስ ያህል ፍቅርተ ሃይሌ በንግድ ትምህርት ቤት ውስጥ በማታ ትምሕርት የነበረ የድብብቆሽ ሥራ አለ በማለት፣ በተማሪነት ተመዝግባ የተመለከተችውን *አዲስ ዘመን* ጋዜጣ ላይ በመጻፍ ዕሁፏ ከሥራ መሰናበቻ ምክንያት ሆኗል::

ብዙ ወንድም አገኘሁ ደግሞ አንዳንድ ወጣት ሴቶች (በማደንዘዣ እጽ አጠቃቀም ጭምር) ሕይወታቸው መባከኑን የሚያስረዳ ጽሁፍ፣ ለጥቂት ግዜ አብራቸው በመኖር፣ በጽሁፏ ችግሩ በአንባቢያን እንዲታወቅ በማድረጓ የወጣት ሴቶች ኑሮ ወደ አሳዛኝ ውድቀት እንዳያመራ አድርጋለች::

*በቴሌቪዥን የሴቶች አገልግሎት* - ቴሌቪዢን ባገራችን በ1957 ዓ.ም. ሲቋቋም ከሠራተኞቹ መሀከል በርከት ያሉ ሴቶች ነበሩ:: አብዛኛዎቹ በፕሮግራም አስተናጋጅነት የሚሠሩ ሲሆኑ፣ ሀ ብሎ ሲጀመር ጀምሮ ዕሌኒ መኩሪያ በእንግሊዝኛ (ለተወሰነ ጊዜም በአማርኛ) ፕሮግራም አዘጋጅነት እና በዜና አቅራቢነት ተሰማርታለች:: ከዚያም ሌላ የፊልም ክፍል ኀላፊ በመሆን ቤተ መጻህፍቱን አቋቁማለች:: ሆኖም ገነት በርሄ የላቀ አገልግሎት ያበረከተችው ለሴቶች አዲስ መድረክ በመጀመር *«ከማጀት ወደ አደባባይ»* በተሰኘው ሳምንታዊ ፕሮግራም ነው:: ብዙሀኑን ሴቶች ከማጀት ወደ አደባባይ እንዲወጡ የሚያነቃቃ ፕሮግራም ነበር::

እንግዲህ፣ ባጭሩ እንደተመለከትነው፣ ሴቶች በዘመኑ በነበረው የማስረጃ ስርጭት ሥራ ሁለገብ አስተዋጽኦ ከማድረጋቸውም በላይ ለሥራው መሠረታዊ እድገት እንዳበረከቱ ጥርጥር የለውም::

### *ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር*

የሕዝብ ኑሮ እንዲሻሻልና እንዲጠናከር በማለት የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር በዚሁ ዘመን ተቋቁሞ ስለነበር በተለይ የሴቶች ኑሮ በመላው አገር እንዲሻሻል በማሰብ፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ (ከአብዮት በሁዋላ አዲስ አበባ) ዩኒቨርስቲ እና ከውጪ አገር የተመለሱ ሴት ምሩቃን ሙሉ አገልግሎት ሰጥተዋል። ከነኚህም መሀከል ለናሙና የሚጠቀሱ፡- ወ/ሮ ወይንሸት በሻህውረድ፣ ወ/ሮ እህተ መገርሣ፣ እና ወ/ሮ ወደርየለሽ ከበደ ናቸው። መሥሪያ ቤቱ ባካሄዳቸው ዘመቻዎች ብዙ ሴቶች እንዲጠቀሙ ተደርገዋል። «ኑሮ በዘዴ» በማለት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉ በገጠርና በከተማ ለሚኖሩ ኑዋሪዎች በመሥሪያ ቤቱ በተደረገው ጥረት ብዙ ሴቶች ተጠቅመዋል።

### *በፍርድ ሚኒስቴር*

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋክልቲ ተቋቁሞ በተጠናከረበት ወቅት ሴቶች መሳተፍ ጀምረው በሕግ ትምሕርት ከተመረቁ በኂላ በዳኝነትና በጥብቅና ሥራ ተሠማርተው ነበር። ከመጀመሪያዎቹ ዳኞችና ጠበቆች መሀል የተከበሩ በልዩ ወርቅ ገብረመስቀል (የመጀመሪያዋ ሴት ዳኛ)፣ **ወ/ሮ ንጋት** (ጠበቃ) ይገኙበታል። ይህ እንዲህ እንዳለ በፍርድ ቤት ደጃፍ የጽሕፈትና የምክር አገልግሎት ከሚሰጡት መሀል አብዛኛዎቹ ሴቶች ሲሆኑ አገልግሎታቸውም መረሳት የለበትም።

### *የጦር (የመከላከያ) ሚኒስቴር*

ምንም እንኳን በጦር ሜዳ የሴቶች ተሳትፎ፣ ስንቅ መሰነቅ፣ የተጎዱትን ማስታመም፣ ሁሌ ያለ ቢሆንም፣ በጣሊያን ወረራ ጊዜ በአርበኝነት የታወቁ ሴቶች መኖራቸውን እያስታወስን ስማቸው እንደገነነው አርበኞች፣ እንደ ከበደች ሥዩም፣ ሸዋረገድ ገድሌ እና ልክየለሽ በያን ባይታወቅም፤ እነ ወርቅነሽ ሲሳይ (በቡልጋ) ማንያህልሻል ጎብተሚካኤል (በአርሲ)፣ እታገኝ እሸቴ (በጋሞጎፋ)፣ ሲጠቀሱ፣ እንዲሁም ከ20 የበለጡ የሴት አርበኞች ስም በወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን *«የሕይወት ጓደኛ»* መጽሐፍ ውስጥ ተዘርዝሯል።

በዘመኑ በጦር ሚኒስቴር ሥር የተመሠረተው የጦር ሠራዊት ክፍልና የመንግሥት ቤት ጥበቃ የሚያስተዳድር የክብር ዘበኛ ክፍል፡ ሴት ወታደሮች በተለያየ የሥራ መስክ እየሰለጠኑ በሰላም ጊዜ ሆነ በጦር ሜዳ አገልግሎት ይሰጡ ነበር።

ለመጥቀስ ያህል፣ በዘመኑ በኮሪያና በኮንጎ በተካሄዱት ጦርነቶች፣ ኢትዮጵያ የጦር ድጋፍ በመስጠትዋ፣ ሴት ወታደሮች የቃኘው ሻለቃ ጦር አባል በመሆን ተካፍለዋል። ከነዚህም መሀከል በኮንጎ የዘመቱት ሲሰተሮች፡- ሮማን አለማየሁ፣ ፀሀይቱ ደስታ፣ ዜናዊት አየለና የሻለቃ ማዕረግ ያገኙት ደግሞ ሻለቃ አስቴር አያና እና ሻለቃ ብርቅነሽ ከበደ ሲሆኑ ሁሉም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የክብር ኮከብ ሜዳልያ ተሸልማዋል።

## በአገር ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ

ከጽዳትና ከጸሐፊነት ሥራ ሌላ፣ በዚህ ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደረው የፖሊስ ሰራዊት ውስጥ፣ ሴት ፓሊሶች በየክፍለሀገሩ ተሰማርተው አገልግሎት ይሰጡ ነበር:: በተጨማሪም በሬድዮና በጋዜጣ፣ የሕብረተሰቡን ፀጥታ በሚመለከት፣ ፕሮግራምና ጽሁፎች በማቅረብ አገልግሎት ያበረክቱ ነበር:: በትራፊክ ሥራም ያገለግሉ ነበር።

የመጀመሪያው ምርጫ ቦርድ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ስር ሲቋቋም (በ1950 ዓ.ም.) በአመራረጥ ዙሪያ ያሉትን ሁኔታዎችና ግዴታዎች ለመራጮች በማሳወቅ፣ በሕዝብ ግንኙነት ወ/ሮ አልማዝ ፋሲካ ከሥራ ጓደኞቻቸው ጋር በመሥራት፣ የተመራጮች ሃላፊነት ምን እንደሆነ ለሕዝቡ በማስተማር ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: እንደሚታወቀው በየ4 ዓመቱ ምርጫ ይካሄድ ነበር።

ይሄም የሚያረጋግጠው፣ በ40 ሣንቲም ይሸጥ የነበረው ታማኙ *አዲስ ሪፖርተር* መፅሄት እንደዘገበው፣ በመጀመሪያው በ1950 ዓም ምርጫ ወደ 4 ሚሊዮን የቀረቡ መራጮች ሲመዘገቡ በምርጫ የተካፈሉት ከ2 ሚሊዮን ተኩል በላይ ይገመታሉ። ለ3ተኛው ዙር ደግሞ 5 ሚሊዮን ሲመዘገቡ፣ የመራጮች ቁጥር ወደ 3 ሚሊዮን ተጠግቷል።

## በትራንስፖርት ሚኒስቴርና በአውራ ጎዳና ባለሥልጣን የሴቶች ተሳትፎ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ በዘመኑ ብቸኛ ሆኖ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የሴቶች ተሳትፎ ከእድገቱ ጋር አብሮ አድጓል። በአስተዳደር ሥራ ከተካፈሉት መሀከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን፡ የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዋና ጸሀፊ፣ ወ/ሮ ጸሀይ አባይነህ የሬዘርቬሽንና ሺያጭ ክፍል ዳይሬክተር፣ ወ/ሮ ኩላ ዜርቮስ፡ በሬዘርቬሽንና ቲኬቲንግ ክፍል ተመድበው ለአየር መንገዱ ሰፊ አገልግሎት ሰጥተዋል::

በመስተንግዶ፣ ከበረራ በፊትና በበረራ ላይ በሚከናወኑ ሥራዎች ደግሞ የአየር መንገድ ሴት አስተናጋጅዎች ማራኪ በሆነ አቀራረባቸው፣ በትእግስታቸው፣ (ወደርየለሽ ሆኖ በመገኘቱ) አየር መንገዱ ተወዳጅነት እንዲኖረው ሰፊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ከእነኚህ ፈር ቀዳጅ አስተናጋጆች መሀከል የሺ ምሕረቱ፡ አይኔ አበባና፡ ሚሊዮን አብዲሳ ይገኙበታል።

የአየር መንገዱን የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ክፍል በመምራት ወ/ሮ የሺ ታፈሰ በምክትል ሥራ አስኪያጅ ደረጃ አገልግለዋል:: ደግሞ፣ በአውሮፕላን አብራሪነት የመጀመሪያዋ ሴት፣ ወ/ሮ አሰገደች አሰፋ ሲሆኑ፣ እንዲሁም ወ/ሮ ሙሉእመቤት እምሩ ይጠቀሳሉ::

በአውራ ጎዳና ባለስልጣን መስሪያ ቤት ደግሞ ሲቪል ኢንጂኒየር ብርቅነሽ አስፋው፡ በመሀንዲስ የዲዛይን ክፍል እስከ ኃላፊት በመስራት ፈር ቀዳጅ ሆነው አገልግለዋል::

የማመላለሻ ሚኒስቴር በገንዘብ በኩል የተለያዩ ዋና ዋና ክፍሎች እና ልዩ ልዩ ቅርንጫፎች ሲኖሩት የገቢን፣ የወጪንና የቲኬት ማደያውን ክፍል ያጠቃልላል። የዚህ ክፍል ሥራ አስኪያጅ (ዲፓርትመንት ማኔጀር) ወ/ሮ ቀለምወርቅ ደነቀ ነበሩ።

***በቴሌኮሚዩኒኬሽን የሴቶች ተሳትፎ፤-***

በቴሌኮሚዩኒኬሽን ዙሪያ፡ በመንግስትና በግል መሥሪያ ቤቶች ሴቶች በስልከኝነት ሥራ በሰፊው ተሰማርተው፡ (በክፍለ ሀገር ከተሞች ጭምር፡ ተቀጥረው) ያገለገሉበት ዘመን ነበር።

በከፍተኛ ማዕረግ የሚገኙም ነበሩ። ለመጥቀስ ያህል፣ ወ/ሮ መንበረ ካሣ ትምሕርቷን በዩንቨርስቲ በዲግሪ ካጠናቀቀች በሁዋላ የአስተዳደር መኮንን ነበረች፤ወ/ሮ ሰፊያ ይልማ ደግሞ የማስታወቂያ ክፍል ሹም ነበረች።

***የሴቶች ተሳትፎ በባንክና በኢንሹራንስ ሥራ፡-***

የብሄራዊ ባንክ፡ ከተቋቋመ ጀምሮ፣ ሴቶች በእድገቱ አብረው ተጉዘዋል። ከዩኒቨርስቲና ከንግድ ትምህርት ቤት የተመረቁ፣ በባንክ እየተቀጠሩ፣ ከጸሐፊነት እስከ ክፍል አስተዳዳሪነት ሰርተዋል። ከባንክ ሥራ እድገት ጋር የሴት ተቀጣሪዎች እየበዙ ሄዱ። በብሄራዊ ባንክና በንግድ ባንክ ቅርንጫፎች እንዲሁም በተቋቋሙት የግል ባንኮች የአስተዳዳሪነት ሥራ በመስራት ባንኮቹ ለሚሰጡት አገልግሎት የሴቶች ተሳትፎ እስካዛሬ በሰፊው ቀጥሏል።

ከነኚህም ለናሙና ያህል ለመጥቀስ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቀለጠፈ አገልግሎት ሲያበረክቱ ከነበሩት መሀከል ወ/ሮ ይጋርዱ አለማየሁ ይገኙበታል። እዚህ ሳንጠቅስ የማናልፈው ከነባሮቹ መሀል ደግሞ፡ ወ/ሮ አክሎግ አበበ፣ ወ/ሮ ሊያ ወርቅህ እና ወ/ሮ አስቴር ወርቅነህ ይገኙበታል። ወ/ሮ አስቴርም በውጪ አገር ግንኙነት ክፍል፣ በዋና ፀሐፊነት፣ ከ1940ዎቹ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጡረታቸው ድረስ፣ በአረአያነት (በተለይ ለሴቶች)፣ ሙሉ አገልግሎት አበርክተዋል። በጥር ወር 1963 ዓም ጡረታ ሲወጡ፣ ለዚሁ ለቅን አገልግሎታቸው ልዩ ሜዳልያና ስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

## በፓርላማ የሴቶች ተሳትፎ፡-

በፓርላማ የነበረው የሴቶች ውክልና፣ ምንም እንኳን የሴት አባሎቹ ቁጥር ከወንዶቹ በጣም ቢያንስም፣ አበረታች አቅጣጫ ይዞ ነበር። የተመራጮች ዋስትና ብር 1,000 ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ቢሆንም የሴት ድምጽ በመድረክ መሰማት ባልተለመደበት ዘመን፣ ሴቶች በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን የእኩልነት መብት በመመርኮዝ፡ ከአዲስ አበባ ልዩ ልዩ ወረዳዎች፣ እንደ ወ/ሮ ቀፀላ በላቸው፣ ወ/ሮ አየለች መሸሻ፣ ወ/ሮ ሳራ ገብረየስ፣ ወ/ሮ አንቀጽ ሳህሌ፣ እና ወ/ሮ አልማዝ አጥናፍ ሰገድ፣ ወጣቷ የከፋ ክፍለሀገር የሊሙ ወረዳ እንደራሴ ወ/ሮ ራብያ አብድልቃድር፣ ለፓርላማ

አባልነት ተወዳድረው በማሸነፍ ወደተቋሙ ስለገቡ፣ የሴቶችን መብቶች ለማራመድ ለፓርላማ በማቅረብ፣ በቀጣዩ ዘመናት የሴቶች መብት እንዲጠበቅ ለተካሄዱ ክርክሮች በር ከፋች ሆነው አገልግለዋል።

እዚህ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ የፓርለማ ሴት አባሎች ናቸው። በ1950 ዓ.ም ከአዲስ አበባ አውራጃ ከተመረጡ የፓርለማ አባሎች መሀከል ሁለት ሴቶች ነበሩ። እነሱም ወ/ሮ ቀጸላ በላቸው ከገፈርሳ ወረዳ ግዛት ከ7 እጩዎች መሀል እና ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ከእንጦጦ ወረዳ ግዛት እጩዎች መሀከል ነበሩ።

በዚሁ ዓመት በሌላ ወቅት ደግሞ ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ የግራ ምክትል ፕሬዚደንት በመሆን ተመርጠዋል። በዚህ ወቅት ንግግር ሲያደርጉ፣ «ለዚህ ከፍተኛ ቦታ ሴት ናት፣ አትችልም፣ ሳትሉ ስለመረጣችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናሁ። ይህ እድል ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሴቶች እንደተሰጠ የሚቆጠር ስለሆነ፣ ያደረጋችሁትን ምርጫ፣ ያስተያየታችሁን ከፍተኛነት ይመሰክራል።» ብለው ነበር። ወ/ሮ ቀጸላ በግላቸው ደግሞ በ1951 ዓም ለውጪ ጉዳይ ኮሚቴ አባል ተመርጠው ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል።[6]

ሆኖም፣ ከፓርላማ ታሪክ ጋር አብሮ የሚወሳው የወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ትግል ነው። ከ1942 ዓ.ም. ጀምሮ ስለ ሴቶች መብት ረጅም ልምድ አካብተው፣ የሕግ መወሰኛ ምክትል ፕሬዚደንት ሆነው ለሀገር እድገትና የሴቶች መብት እንዲጠበቅ ድምጻቸውን በማስተጋባት ፈር ቀዳጅ ሆነው አገርን በቅን አገልግለዋል።

እንዲያውም ገና ለምርጫ ሲቆሙ ነው የንግግር ችሎታቸውን ያሳወቁት። ለምሳሌ፣ በምረጡኝ ቅስቀሳ ጊዜ አንድ ጠያቂ እንዴት ነው እናንተ ሴቶች ሳትለፉበት የመመረጥ መብት ያገኛችሁት ብሎ ሲጠይቃቸው፣ ለመሆኑ እናንተ ወንዶች ምን ሠርታችሁ ነው መብቱን ያገኛችሁት? ብለው መልሰውለታል። በዚህን ጊዜ ጠያቂው ዝም አለ፤ መልሳቸውም በጭብጨባ ተሸኘ።

## በንግድ ዓለም፣ ከእንጀራ ሻጭነት፣ መንገድ ቸርቻሪነት እስከ ምግብ ቤትና መጠነኛ ሆቴሎች ባለቤትነት፣

በጎጆአቸው ሁነው እንጀራ ጋግረው መሸጥ የተጀመረበት ዘመን ነበር። በዚህ ንግድ ብዙ ሴቶች ተሰማርተው፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሰጥተዋል። እንጀራ ጋግረው ወደ ውጪ ለኤክስፓርት በመላክ ፈር ቀዳጅ የሆኑት ወ/ሮ ላቀች ተክለ ኃዋርያት ከባህል ምግባችን መሰረታዊ የሆነውን

---

[6] ከበደ እንግዳ ሰው፣ *የምክር ቤታችን ዕድል፣ ከልጅነት እስከ እውቀት* (አዲስ አበባ፣ 1953 ዓ.ም.)፣ ገጽ 53-66።

እንጀራ፡ ድሬዳዋ እየጋገሩ ወደ ጂቡቲ በመላክ ምግቡ ውጪ አገር እንዲታወቅ አድርገዋል።

እንዲሁም፣ በተመሳሳይ ዓላማ፣ አያሌ ሴቶች በየእለቱ በጉልት ገበያ፣ በገጠር ደግሞ በገበያ ቀን ተሰማርተው፣ ከማለዳ እስከ ምሽት፣ በብርድም፣ በፀሀይም ቃጠሎ፣ በመንገድ ዳር እንደ አትክልት፣ ጥራጥሬ፣ ቅመማ ቅመም፣ የፈትል ምርቶች ወዘተ፡- የመሳሰሉትን ውጤቶች በመሸጥ ቤተሰብአቸውንና ገበያተኞችን አገልግለዋል፤ አሁንም እያገለገሉ ነው።

ያገሩን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሚመለከት፣ በአዲስ አበባና በክፍለ ሀገሮች በተቋቋሙት ፋብሪካዎች፣ ሴቶች በተለያዩ የፋብሪካ ሥራዎች በመካፈል አገልግሎት መስጠት የጀመሩበት ዘመን ነበር። በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ቡና በመፈልፈል፣ በሽቶ ፋብሪካ ወዘተ፣ የመጠጥ ፋብሪካዎች ምርቶቻቸውን በገበያ በሰፊው ከማዋላቸው በፊት፣ ሴቶች በዘልማድ ባገኙት ሞያ ጠጁን፣ ጠላውን፣ ካቲካላውንና የመሳሰሉትን ያገር መጠጦች በማሰናዳትና በንግድ ተሰማርተው በማሰራጨት አገልግሎት ይሰጡ ነበር።

ዘመናዊ አኗኗርን መከተል የሚገፉፉ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ከቤት ውጪ የመብላት ባሕልን አስከተለ። በርከት ያሉ ሴቶች የንግድ ምግብ ቤት በማቋቋም በዚህ ሥራ ተሰማርተው ነበር። የሳንድዊችን አመጋገብ ለወጣቶች በማስተዋወቅ ሁለት ሴቶች፣ ወ/ሮ ታየች በየነና፡ ሲስተር ሰንበቱ ገብሩ፣ በ4 ኪሎና በንግድ ትምህርት ቤት አካባቢ፣ የሳንድዊች ቤት በማቋቋም፡ ከእንጀራ ውጪ ቀላል ምግብ ወጣቱ የሚያገኝበት መንገድ በመክፈት አገልግለዋል። በተጨማሪ የውጪ አገር እንግዶች ከሚያስተናግድ ምግብ ቤት አንዱ የወ/ሮ አሰገደች ወልዴ ሰፊ አገልግሎት በመስጠቱ ሳይጠቀስ አያልፍም። እንዲሁም፡- የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት እያደገ በመሄዱ፣ የማደሪያ ችግር ለማቃለል ሲባል ከተሠሩት መጠነኛ ሆቴሎች መሐከል በባለቤትነት በሴቶች ተይዘው አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ።

የሚገርመው ደግሞ «የነጻነት ሆቴል» ባለቤቶች ሁለት እህትማማቾች፣ በቀለች ሞገስና ሂሩት ሞገስ፣ ሆቴሉ እስከ 300 እንግዶች የሚያስተናግድ፣ በየቀኑ ልዩ ልዩ አይነት ምግቦች የሚያቀርብና ለሠርግና ለልዩ ልዩ ትላልቅ መስተንግዶ በትዕዛዝ የሚያዘጋጅ ሆቴል ነበር።

ቱሪስቶች በሚያዘወትሩት ታሪካዊው ላሊበላ ከተማ ደግሞ Seven Olives *«ሰቨን ኦሊቭስ»* የተባለ የመጀመሪያ የግል አነስተኛ ሆቴል በእመቤት ሂሩት ደስታ ተቋቁሞ በተለይ ለውጪ አገር ጎብኝዎች አገልግሎት መስጠት ጀምሮ ነበር።

የአዲስ አበባ ነዋሬዎች ቁጥር እያደገ ሲሄድ የቤት ችግር መኖሩን የተገነዘቡ ወ/ሮ ሙሲሊሃ በሺር፣ ከስደት እንደተመለሱ፣ የኢንዱስትሪ ማህበር አባል ሆነው፣ ትናንሽ ቤቶች እየሰሩ ማከራየት፣ እንዲሁም ሁለት ታላላቅ ሱቆች፣ (አንዱ መርካቶ ሌላው ቸርችል ጎዳና ላይ) ሠርተው በንግድ ዘርፍ

አስተዋፅኦዋቸው ተመስግኖ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የወርቅ ሜዳልያ ተሸልመዋል፡፡

ሴቶች በአገር ልብስ ንግድ ተሰማርተው ንግዱ የተስፋፋበት ዘመን ነብር፡፡ አንዳንዶቹ ቤታቸው ሆነው በመፍተል፣ ፈትላቸውንም ለሸያጭ በማቅረብ፣ በጥልፍ እያሳመሩ እየሠሩ፡ ያገር ልብስ ሽያጭ እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡ ነገር ግን ከሁሉም በላይ በልብስ ጥራትና ውበት ያገር ወግ በመከተል ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወ/ሮ ጽዮን ሚካኤል አንዶም ሲሆኑ፣ እስከዛሬ ድረስ፣ (በ86 ዓመታቸው) የሚሠሯቸው ልዩ ልዩ የአገር ልብሶች ተወዳጅነታቸው ቀጥሏል፡፡[7]

በሌላ በኩል ደግሞ፤ ላገር ውጤት ተቆርቁራ፣ ያገር ውጤቶች ከውጪ አገር ከሚመጡት የሕጻናት ልብሶች ጋር ሊወዳደሩ ይችላሉ በሚል አስተሳሰብ ተነሳስታ በመሐል ከተማ ገበያ አዳራሽ ውስጥ የታወቀ የሕጻናት ልብስ ሰፊና የሕጻናት ሽቀጥ ነጋዴ የነበረችው፡- ወ/ሮ ፀኃይ ኃይሌ በፈር ቀዳጅነት ልትጠቀስ ይገባል፡፡

በእደ ጥበብ ንግድ፡ የእደ ጥበብ ሥራ፣ ከባህል ጋር ተያይዞ የመጣ በመሆኑ፣ ሴቶች በመጥለፍ፣ በሸክላ ሥራ፣ በአለላ ሥፌት እና በልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎች ውጤታቸውን ለገበያ ማዋል ጀመሩ፡፡ ከእደ ጥበብ ስልጠና ማዕከሎች እንደ *እቴጌ መነን እደ ጥበብ ትምሕርት ቤት*፣ እንዲሁም በሀይማኖትና በበጎ ሥራ አድራጎት ድርጅቶች በተቋቋሙ ማዕከሎች፣ ሴቶች ጭምር ማሰልጠን ጀምረው፣ የበለጠ ጥራት ያላቸው የተለያዩ እደ ጥበብ ውጤቶች፣ እንደ ምንጣፎች፣ የሽመና ውጤቶች (አሻንጉሊቶች፣ የጥልፍ፤ የሹራብ ሥራዎች ወዘተ...) ላገርና ለውጪ አገር ገበያተኞች እንዲውሉ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ለምሳሌ - በተለይ የታወቀው የሐረር አለላ ስፌት ተወዳጅነት በማትረፉ፣ ሙያውም ወደ ልዩ ልዩ ክፍለ አገሮች ስለተዛመተ በዚሁ ሙያ ለተሰማሩ ሴቶች የገቢ ምንጭ ሆኗል፡፡

ሙያቸውን ለወጣቱ በማስተላለፍ የሚታወቁት ወ/ሮ አሻ አብዱል ራህማን 13 ቋሚ ሠራተኞችና፡ ሌሎች በብዛት የሚሠሩ የቁርጥ ሠራተኞች እያስተዳደሩ፣ የኢትዮጵያን ባህል የያዙ እቃዎች፣ እንደ ጋሻና ጦር የተሠሩ ላንቲካዎች፣ ለምግብ ማቅረቢያ የሚያገለግሉ የአለላ ስፌቶች፣ ከእንጨት የተቀረጹ፣ ከዛጎል፡ ከጨሌና ከሸክላ የተሠሩ ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ የእደ ጥበብ እቃዎች ያመርቱ ነበር፡፡ እሳቸው ካረፉም በኋላ ሴት ልጆቻቸው ተረክበው ያካሂዱት ነበር፡፡ በአሻንጉሊት ሥራ ደግሞ ጃፓን አገር ባገኙት ዘመናዊ ሙያ በመጠቀም ወ/ት ፀኃይ ዮሐንስ ማራኪ የሆኑና በባሕላዊ አለባበስ ያጌጡ አሻንጉሊቶች በመሥራት እውቅና አግኝታ ነበር፡፡

[7] ይህ እድሜ፣ ጽሁፉ ለኤፍ.ኤስ.ኤስ ስብሰባ በቀረበበት አመት (1999) ወ/ሮ ጽዮን የነበራቸው ነው፡፡

በግል እርሻ መሰማራት የተጀመረው በዚሁ ዘመን ነበር። በእርሻ ሥራ ከተሰማሩት ሴቶች መሀከል ለናሙና ያህል፡- በዶሮ እርባታና ሽያጭ ከነባሮቹ መሀከል ወ/ሮ ላቀች ሕሩይ ይገኙበታል። እንዲሁም ሰፋ ባለ ንግድ በተያያዘ ዘመናዊ የዶሮና የእንቁላል እርባታና ሽያጭ፡ ወ/ሮ ለምለም (በብሾፍቱ) እና ወ/ሮ ውዳሴ መብራቱ (በግርማዊነታቸው ሽልማት ያገኙት) ይገኙበታል። በከብት እርባታና በወተት ሽያጭ እነ ወ/ሮ አክሎግ አበበ ተሰማርተው ነበሩ። ከበቆሎ አምራቾች አንድዋ ወ/ሮ ታየች በየነ ሲሆኑ፣ ቡና በሰፊው አምርተው ወደ ገበያ ከሚያውሉ ሴቶች አንድዋ ወ/ሮ ሶስና (ሱዚ) ወርቅነህ ሲሆኑ፡ ሴቶች እንዲበረታቱ አድርገዋል።

የቡና እርሻ በብዛት በወንዶች የተያዘ በመሆኑ ወ/ሮ ሱዚ ሱሪአቸውን ለብሰው፣ ቀበቶአቸውን ታጥቀው በድፍረት ተሰማርተው ነበር። እንዲያውም አንድ ቀን አዋሳኛቸው ቡና አምራች ወሰን ለመግፋት መሳሪያውን ይዞ ሲንጎራደድባቸው ውሎ እሳቸውም እያፏጩ እየተንጎራደዱ ተከታተሉት። ለማስደንገጥ መሳሪያውን ይዞ ሲጠጋቸው እሳቸው ደግሞ የታጠቁትን ሽጉጥ ገለጥ አደረጉ፤ ከዚህ በሁዋላ ማንነታቸውን አስከብረው የእርሻ ሥራቸውን ለብዙ ዘመን ቀጠሉ።

በቤት ግንባታ ሥራ ውስጥ የተሣተፉ ሴቶች ምን አበረከቱ? በዘመኑ ዘመናዊ የግል መኖሪያ ቤቶችና ታላላቅ ሕንፃዎች፣ የሆቴሎች ግንባታ፣ በተለይ በአዲስ አበባ መሠራት ሲጀመር፣ በሕንፃ ግንባታ ሥራ የንግድ ተቋራጮች ተሳትፈው እያሉ ከሠራተኞቻቸው መሐከል ሕንፃ ኮሌጅ የተመረቁ ሴት መሀንዲሶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ ያሁኑን ማዘጋጃ ቤት ተቋራጭ ሆኖ የሠራው የሜዜዲሚ ኩባኒያ ሲሆን ወ/ት ማምዬ እምሩና ወ/ሮ ትደነቂአለሽ አበበ (ከሌሎች ባለሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር) በማዘጋጃ ቤት ንድፍ ሥራ ላይ ላይ ተሰማርተው አገልግለዋል።

በፋርማሲነት፡ የመድሀኒት ሽያጭ በግል ፋርማሲ መሸጥ የተጀመረው በዚሁ ዘመን ነበር። ሴቶቹም በዚህ ንግድ የተሰማሩ ነበሩ። ከነዚህም መሀከል ወ/ሮ ሮማን ጎበዜ (ቤይሩት ተምረው የተመለሱ) ይገኙበታል። እንዲሁም ከመጀመሪያዎቹ ከ ዩኒቨርሲቲ በፋርማሲ ትምሕርት የተመረቁት ኢትዮጵያዊት ወ/ሮ ሀርሚየን ናልባንዲያን ይገኙበታል።

ሴቶች በንግድ ዓለም ያበረከቱት አስተዋጽኦ አርዕስት ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎች በጣም ብዙዎች መኖራቸው አይካድም።

## ሴቶች ተደራጅተው የሰጡት አገልግሎት

በዘመኑ በነበረው ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ሴቶችን አሰባስቦ ድርጅታዊ አሠራር በማስለመድ፣ለዘመናዊ ሕብረተሰብ ዕድገት እንዲውል የተደረገው በቅድምያ በበጎ ፈቃደኝነት የተመሰረተው *የኢትዮጵያ ሴቶች በጎ አድራጎት ማህበር* ሲሆን፣ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፣ የተቋቋመው በእቴጌ መነን ጠባቂነትና በልዕልት ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ ፕሬዚዳንትነት፣ በ1927 ዓ.ም. ከጣሊያን ወረራ

በፊት ነበር:: ኋላ፣ ደግሞ በልዕልት ተናኘወርቅ የበላይነትና መሪነት ለሴቶች አበረታችና ጠቃሚ ትምህርትና አገልግሎት ሰጥቷል::

እኛ ወደ እምንመለከተው ዘመን ስንመለስ (ማለትም ከነጻነት በኋላ) በ6 ክፍለ አገር ዋና ከተሞች ውስጥ ቅርንጫፎች ተቋቁመው በዓላማው ተሰልፈዋል:: ከማሕበሩም ዓላማዎች መሀከል:- በአንድ በኩል ሴት አባሎች ያላቸውን ሞያ- ለሌላቸው እንዲያካፍሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶችን አሰልጥኖ ወደ ሕብረተሰብ ዘልቀው በሰለጠኑበት ሞያቸው እንዲያገለግሉ ማድረግ ነበር:: ዋናው አገልግሎታቸው ግን *«ችግረኞችን፣ በሽተኞችን፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶችን መርዳት እናት አባት ያጡ ሕፃናት አጠባበቅና፡ የችግር ኑሮ የሚሻሻልበትን ዘዴ ለመሥራት::»* ሲሆን ይህንን ዓላማ በመከተል የችግረኞች ልጆች እየተማሩ የሚያድጉበት *የትንሳኤ ብርሀን ትምህርት ቤትን* እና በተጨማሪ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ረዳትነት *የልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ክሊኒክን* አቋቁመው ያካሂዱ ነበር::

ይህ የሴቶች በጎ *ሥራ* ማሕበር የሚተዳደረው ከአባሎቹ በሚያገኘው እርዳታና መዋጮ፣ ከአሜሪካን መንግስት ተራድኦ ድርጅት በሚያገኘው ልገሳ፣ በየዓመቱ በሚያካሂደው ባዛር፣ በሎተሪ ሽያጭ ወዘተ፣ ሲሆን በተለይ ለገቢ ማስገኛ ተብሎ በመሀል ከተማ የተቋቋመው *የአዲስ አበባ ምግብ ቤት* ባለሙያዋ ወ/ሮ ቀፀላ በላቸው ያገር ምግብ ባለሙያዎችን አሰባስበው ይመሩት የነበረውና፡ በአገርና በውጪ አገር ሰዎች ተወዳጅ የሆነው ነበር:: ይህ *የአዲስ አበባ ሬስቶራንት፣* ምንም እንክዋን ቢወረስም፣ በአሁኑ ዘመን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል::

በዚሁ ማሕበር በሚካሄደው የሴቶች የሞያ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ወ/ሮ ድንቅነሽ ፈይሳ ለብዙ ዓመት በርዕሰ መምህርት ሲያገለግሉ፣ ወ/ሮ አዳነችና ወ/ሮ ራቢያ አብድል ቃድር ባስተማሪነት፣ ወ/ሮ ሉሌ ተስፋዬ በአስተዳዳሪነት፣ በትጋታቸው፣ በችሎታቸው፣ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል::

ሌላው ሳይጠቀስ የማይቀረው የሴቶች ማሕበር በጦር ኃይሎችና በፓሊስ ሰራዊት መኮንኖች ሚስቶች የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ማሕበር ነው:: ከዓላማው ጥቂቶቹን ለመጥቀስ:- አባቶቻቸው በጦር ሜዳ ለሞቱባቸው፣ አባትና እናት ለሌላቸው ሕጻናት በትምሕርትና በዕድገት አስፈላጊውን እርዳታ ማድረግ፣ ባሎቻቸው በጦር ሜዳ የሞቱባቸውን ሴቶች በማናቸውም ረገድ መርዳት፣ ያላገቡ መኮንኖች በጦር ሜዳ ሲቀሩ፣ ለቤተሰቦቻቸው እርዳታ ማበርከትን ይጨምራል:: ግንቦት 15 ቀን 1956 ዓ. ም ይህ የበጎ አድራጎት ማሕበር ሲቋቋም ጀምሮ ለብዙ ዓመታት ለዓላማው መስዋእት በመሆን በትጋት በዋና ፕሬዚደንትነት ያገለገሉት ወ/ሮ ደስታ ገብሩ ነበሩ::

ሌሎች የሴቶች ድርጅቶች ምን አበርክተዋል? የሀይማኖት ድርጅቶች ማለት የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክና የመካነ እየሱስ ቤተ ክርስትያኖች ሴቶችን በየበኩላቸው አሰባስበው በማደራጀት በተለያየ የእደ ጥበብ ሙያ በማሰልጠን፣ የስልጠና

ውጤታቸውን ወደ ገበያ በማዋል፣ ለአካባቢያቸው ሕብረተሰብ አገልግለዋል:: በአገልግሎታቸው ከሚታወቁት አንደኛዋ እማሆይ ጻድቃን የሚባሉ በደብረ ሊባኖስ እና በደብረ ጽጌ ገዳማት በሚገኘውና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጎ አድራጎት ማህበር ስር የተቋቋመውን ክሊኒክ የሚያካሂዱ ነበሩ::

እዚህ ላይ የማይታለፈው ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ (የቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ባለቤት) በግል ሀብታቸው እናት አባት ለሌላቸው ልጆች በረጲ መኖሪያና ትምህርት ቤት አቋቁመው ልጆቹን በፍቅርና በእንክብካቤ እያስተማሩ ያሳድጉ ነበር[8]::

እንዲሁም የወጣቶች ሴቶች ክርስትያን ማህበር *(ወሴክማ)* በ1953 ዓ.ም. ሲቋቋም፣ ወጣት ሴቶችን አሰባስቦ በማሕበራዊ ኑሮ እድገት ላይ በማተኮር፣ ጠቃሚ አገልግሎት ይሰጥ ነበር:: ለብዙ ዓመታት ዋና ፀሐፊ በመሆን ያገለገሉት ወ/ሮ እህተ መገርሣ ሲሆኑ፡ ከቀድሞው *የወሴክማ* ፕሬዚዳንቶች መሀከል ደግሞ ልዕልት ማሕጸንተ ሀብተ ማሪያም፣ አንዷና የመጀመሪያዋ ነበሩ[9]:: ሌላዋ ብዙ አስተዋጽኦ ለወሴክማ ስኬታማነት ያበረከቱት ወ/ሮ ውድነሽ አምሳሉ ነበሩ:: እንዲሁም:- «ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ወርቅነህ ወሴክማ በአገራችን እንዲቋቋምና ብዙ ጠቃሚ ፕሮግራሞችን እንዲመራ ካደረጉት ጥቂት ሰዎች አንጋፋዋ ነበሩ:» ይላል የወሴክማ መጽሄት:: ስለ ፕሮግራሞቹም በሰፊው ይተነትናል:-ከነኚህም መሀከል: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:-

- የጎልማሶች ትምሕርት፣ ዓለም አቀፍ የምግብ አሠራር፣ የሰውነት ማጠንከሪያ፣ ለችግረኛ ቤተሰብ ልጆች ማቆያ (የመዋዕለ ሕፃናት) ሲሆኑ፣ በተጨማሪ:-
- መደበኛ ተምሕርት ያቋረጡ ወጣት ሴቶችን ለሕፃናት ትምሕርት ቤት እንዲያገለግሉ በማሰልጠን፣
- ከ2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የወደቁትን ወጣቶች የሁለት ዓመት ስፌት ስልጠና በመስጠት ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ እና፣
- አረጋውያን ሴቶችን የእጅ ጥበብ በማስተማር የምርት ውጤታቸውን እዚያው በመሸጥ ገቢ እንዲያገኙ ማድረግን ይመሳስላል:: ሆኖም በምንመለከተው ዘመን መጨረሻ ላይ (1966 ዓም) እንደሌሎቹ የተጠቀሱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሁሉ፣ ይህም ማህበር ተቀጨ::

[8] በዚህ በተባለው ጊዜ፣ ረጲ ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ በሚወስደው መንገድ ላይ፣ ከከተማው ትንሽ ወጣ ያለ፣ ከመንገዱ በስተቀኝ የሚገኝ፣ ኮረብታ ነው፤ በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ረጲን ማካተተት ብቻ ሳይሆን ፣ ከዚያ አልፎ የሰበታ ከተማ ወሰን ደርሷል።

[9] ልዕልት ማህጸንተ ሀብተማርያም፣ የታላቁ የወለጋ ባለባቶች ቤተሰብ ከሆኑት፣ ከደጃዝማች ሀብተማርያም ገብረ እግዚአብሄር ይወለዳሉ፤ የአፄ ኃይለሥላሴ የመጨረሻ ልጅ የነበሩትን ልዑል ሳህለ ሥላሴን አግብተው አንድ ልጅ (ልዑል ኤርምያስን) ወልደዋል።

## በዓለም አቀፍና በአፍሪካ ደርጅቶች የተሠማሩ ሴቶች ምን እንዳበረከቱ

በዚህ ዘመን፣ ማለትም በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና ኢትዮጵያ ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት ሥር የሚተዳደር የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) ሴት ሠራተኞች ከጅምሩ በሥራው ተሳታፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ብዙዎቹም ውጪ አገር ተምረው ከተመለሱት መሐከል ነበሩ፡፡ ከነዚህ መሀከል በነባርነት ካገለገሉት ለናሙና ለመጥቀስ ያህል፡- ወ/ሮ ተክላ በላቸው፣ ወ/ሮ አልማዝ ተድላ፣ ወ/ሮ ዕሌኒ ኪዳኔ (በፋይናንስ ክፍል ረዳት ሃላፊ)፣ ወ/ሮ ሚሚ ወ/ማርያም (ባስተዳደር ክፍል)፣ ወ/ሮ ምስራቅ ተፈራ (በእርሻ ክፍል ውስጥ) አገልግለዋል፡፡ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ደግሞ ወ/ሮ ትርሲት አካለወርቅ የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ ፀሐፊ፣ እንዲሁም በድርጅቱ የፐሬስና የፕሮቶኮል ክፍል የማስታወቂያ መኰንን (Information Officer)፣ የመጀመሪያዋ የነበረቺው ወ/ሮ ሒሩት በፍቃዱ፣ በዶክመንቴሽን ክፍል ደግሞ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ሀይለ ማሪያም ሁሉም በየፊናቸው አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በዚህም ዘመን በተባበሩት መንግሥታት ሥር ከሚተዳደሩት እንደ የአለም የጤና ድርጅት (World Health organization, WHO)፣ ዩኔስኮ (UNESCO) ያሉት ቅርንጫፎቻቸውን በአዲስ አበባ አቋቁመው በጤና፣ በትምሕርት፣ በባህል ጉዳዮች ላይ አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡ በዚህም ወቅት ዩኔስኮ (UNESCO) ቢሮውን በሃላፊነት ከመሩት መሀከል ወ/ሮ ተክአ ዘርኤ ከዩኔስኮ (UNESCO) ፕሮግራሞች አንዱ የገጠር ሴቶች ኑሮ የሚሻሻልበት ፕሮግራም ሲሆን፣ በማጀቴ (ወሎ ክፍለ ሀገር) የተካሄደውን ፕሮግራም ወ/ት ሂሩት እምሩ (ከሌሎች ሥራ ጓደኞቻቸው ጋር) በበጎ ፈቃደኛነት የገጠር ሴቶችን በማስተማር አገልግለዋል፡፡

የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽንና የአፍሪካ አንድነት ማህበር ሥራቸው እየተስፋፋ ሲሄድ፣ የተለያዩ ክፍሎች ሲቋቋሙና ሲጠናከሩ፣ የሴት ሠራተኞች በሞያተኛ ነትና በጸሐፊነት ቁጥራቸው ጨምሮ ማገልገል የጀመሩበት ዘመን ነበር፡፡

## የሴቶች ተሳትፎ በደራሲነትና በሌላም አይነት የጽሁፍ ዝግጅት

በዘመኑ በሴቶች የተፃፉ መጽሐፎች ሁለት ዓይነት ነበሩ፡፡ አንደኛው የስነጽሁፍ ድርሰት፣ ሁለተኛው ደግሞ ባልትና ወይም ሙያ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምድብ በተርጓሚነት የሚገኙት ወ/ሮ ሣራ ወርቅነህ ሲሆኑ በ1933 ዓ.ም *«ማዕበል»* የተሰኘ የዊልያም ሼክስፒርን ትያትር በማሳጠርና የተዋንያኖቹን ስም የአማራ ስም በማድረግ *በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት* አሳትመው ነበር፡፡ ሆኖም የቀደምትነት ቦታ የያዙት ሴት ደራሲያን ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን እና ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ናቸው፡፡ *«የሕይወት ጓደኛ»* በሚል ርዕስ ወ/ሮ ሮማነ ወርቅ ካሣሁን በ1947 ዓ.ም. በንግድ ማተሚያ ቤት አሳትመዋል፡፡ በዚህ መጽሐፋቸው ውስጥ ሴቶችን በሚመለከት ብዙ አርዕስት ዳስሰዋል፡- ስለ ጥንትና ዘመናዊ ሴት፣ ስለ ቁንጅና ምስጢር፣ ስለ የኑሮ ጓደኛ

አመራረጥ፣ ስለ አማትና ምራት፣ ወዘተ። አርአያ ስለሚሆኑ አያሌ ኢትዮጵያዊ ሴቶች ታሪክ በአጭሩ አካተዋል።

ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ከ 21 በላይ መጻሕፍትና ድርሰቶች አበርክተዋል። ከነዚህ መሀል አንዱ «*የልቤ መጽሐፍ*» በሚል ስያሜ በጥር ወር 1939 ዓ.ም. የተደረሰውን የመጀመሪያውን መጽሐፋቸውን በ1942 ዓ.ም. በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አሳትመዋል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ድርሰትና ሁለት ትያትሮች (ድራማዎች) ሲገኙ፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለተሰው ወጣት ሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆንና ለወደፊት ወጣቶች ያገር ፍቅርን ማዳበሪያ እንዲሆን የታተመ ነው ይላሉ። ድርሰቶቹ ለመድረክ የተዘጋጁ በመሆናቸው የመጀመሪያ የመድረክ ጽሁፍ ሴት ደራሲ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፡ በእቴጌ መነን ት/ቤት ቲያትሩ እንዲታይ በማድረጋቸው፡ በወጣት ሴቶች ዘንድ የተዋንያን ሞያ ተወዳጅነት እንዲኖረው ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

እንዲሁም፣ ሁለቱም ደራሲያን በጽሑፎቻቸው፣ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን *ማህደረ ጥበብ እና ትዳር በዘዴ፣* ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ *የልቤ መጽሐፍ* እንዲሁም በስድ ንባብ፣ በግጥምና በትያትር መልክ ለሴት ደራስያንና በድራማ መልክ የተደረሰውም፣ ለሴት ተዋንያን በር ከፋች ምሳሌዎች ሆነዋል።

በዚሁ ዘመን በባልትና ሞያቸው የታወቁት ሴቶች በየበኩላቸው የባልትና መጽሐፍ ጽፈው ያካበቱትን የባልትና እውቀት እንዳይጠፋ በማለት፡ ያላቸውን ሙያ ለትውልድ እንዲተላለፍ አድርገዋል። ከነኚህ ውስጥ ወ/ሮ መቅደስ ወርቅ ዘለቀ *«የሙያ ምንጭ ለወጣቶች ማሳሰቢያ»* በሚል ርዕስ በ1941 ዓ.ም. 301 የምግብ አይነቶችን አሠራር የያዘ አሳትመዋል። በ1953 ዓ.ም. ደግሞ ወ/ሮ ሸዋንግዢው በላይ 91 የምግብ አይነቶችን አሠራር የሚያስረዳ «*ጥንታዊው የሴቶች ሞያ፡ - ከዘመናዊ የተዋሀደ*» በሚል ርዕስ አሳትመዋል። በዚህ መጽሀፍ መቅድም ውስጥ ደራሲዋ ወ/ሮ ሸዋንግዢው እንዲህ ይላሉ፡-

> *ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብኩበት ምክንያት ቀድሞ ለነበረው ለእናቶቻችን ሞያ መታሰቢያ ለዛሬው ላዲሱ ዘመንና ለሚመጣው ትውልድ መማሪያና መምሪያ ሆኖ ጥንታዊውንና ሐዲሱን የኢትዮጵያ ሙያ፡ መሠረቱን አያይዞ እያጸናው እንዲሄድ፣ የዕውቀቱንም ብርሃን በተወራራሽነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ድንቅና ምስጉን የሆነ ሥራው በረጅም ዕድሜ ታውቆ ለመኖር እንዲችል ይሆን ዘንድ በማለት ነው*[10]።

ይላሉ። ይህም ሐሳብ በተጠቀሱት 3 መጽሐፎች ውስጥ ይንጸባረቃል። ሶስተኛዋ ደራሲ ልዕልት ጽጌማሪያም ወልደ ሩፋኤል ሲሆኑ እሳቸውም *«የእናቶች ሙያ»* በሚል ርዕስ በ1957 ዓ.ም. ያሳተሙት ነው። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የ251 የምግብና የቅመማ ቅመሞችን አሠራር አቅርበዋል።

---

[10] ሸዋንግዢው በላይ፣ *ጥንታዊው የሴቶች ሞያ - ከዘመናዊው የተዋሀደ* (አዲስ አበባ፣ 1953 እንደገና 1962)

## የሴቶች ተሳትፎ በኪነ ጥበብና በሰዓሊነት

በሰዓሊነት፡- ዘመናዊ መንገድ በመከተል፣ ሴት ሰአሊዎች ብቅ ያሉት በዚሁ ዘመን ሲሆን ይኸውም የስነጥበብ ትምህርት ቤት ከተቋቋመ በኋላ ነበር፡፡ ውጪ አገር ተምረው የተመለሱት ወ/ሮ ማርታ ነሲቡ ሰዓሊ ከመሆናቸውም በላይ ለልጆች መጽሐፍ ስእላዊ ድጋፍ በመንደፍ በዚሁ ሞያ የሴት ፈር ቀዳጅ ሆነው አበርክተዋል፡፡ ያገርና የውጪ አገር ባህል አስተዋጽኦ ላበረከቱት ተቀዳሚ ሰዎች ለተማሪዎች፣ ለማሳወቅ ትምሕርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር «የቀለም ሰዎች» በሚል አርእስት በ1951 ዓም አሳትሟል፡፡ ሰአሊት ማርታ ነሲቡ ስለ ውጪ አገር የስነ ጥበብ ሰዎች የዳበረ እውቀት ስለነበራት ከሰለሞን ሪኖ ጋር የድጋፍ ስዕሎች ሠርተዋል፡፡ ለዚሁ መጽሐፍ ወ/ሮ መዐዛ በቀለ ታሪኮችን አሰባስበዋል፡፡

የሥነ ጥበብ መጀመሪያ ምሩቅ የነበረችው ሰአሊት ደስታ ሐጎስ ስትሆን ትምህርት ቤቱ ሲስፋፋ ለሴት ሰአሊዎች ፈለግ ሆናለች፡፡ እንዲሁም ሰአሊት ቀፀላ አጥናፍ ከተመርቁ በኋላ ውጪ አገር ሄደው (ፓላንድ) በሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል፡ ተመልሰው በእቴጌ መነን እደ ጥበበ ት/ቤት ያስተምሩ ነበር፡፡ ሰአሊ ደስታ ሐጎስ ደግሞ አከታትላ የስእል ትርኢቶች በማሳየት ለወጣት ሰአሊዎች አርአያ ሆናለች፡፡ በአንድ ወቅት ባሳየችው ትርኢት፣ አንዱ ስእልዋ የክርስቶስን የስቅለት ስቃይ የሚያመለክት ሲሆን፣ ስቃዩን ለመጋራት በሚል ስሜት የራስዋን ደም ተጠቅማ በመሳልዋ የተመልካቹን ቀልብ ስባለች፡፡

በሙዚቃ ዓለም፡- ዘመናዊውን መንገድ በመከተል ሴት ሙዚቀኞች ብቅ እያሉ ብዙ አስተዋጽኦ ያበረከቱበት ዘመን ነበር፡፡ በፒያኖ አጨዋወታቸውና በፒያኖ ድርሰታቸው በቅድምያ የታወቁት እማሆይ ጽጌ ማሪያም ገብሩ ናቸው[11]፡፡ እሳቸውም ሙዚቃዊ ድርሰቶቻቸውን በትዝታና በኦርቶዶክስ ዜማ ተመርኩዘው በዘመናዊ ስልት በማቅረባቸው ላገር እና ለዓለም ሙዚቃ አፍቃሪዎች ጊዜ የማይሽረውን ስሜት የሚቀሰቅሱ ድርሰቶቻቸውን በመጫወት እየተደነቁ ይኖራሉ፡፡

በፒያኖ አስተማሪነት ከታወቁት የመጀመርያዋ ሴት ደግሞ ልጆች እና ወጣት ሴቶች ወደ ፒያኖ ፍቅር እንዲያመሩ ያደረጉት ወ/ሮ አስቴር ገብረ ማሪያም ይጠቀሳሉ፡፡

ያገር ዘፈን ባሕሎችና ከዚያው ጋር የተዛመዱ ውዝዋዜዎች በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት አግኝተው በእውቅና እንዲተላለፉ በማድረግ ትልቅ ሚና ያበረከቱት በዘመኑ በከተማ የተገኙ ዘፋኞች ሲሆኑ፣ የሴቶች ድርሻ ቀላል አልነበረም፡፡ በተለይ ሀገር ፍቅር ማሕበር ከተቋቋመ በኋላ ከነ ንጋትዋ ከልካይ፣ ከእነ ዘራፌ

[11] እዚህ መጣጥፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱት፣ እማሆይ ጽጌ ማርያም፣ የወይዘሮ ስንዱ ገብሩና የወይዘሮ ደስታ ገብሩ እህት ነበሩ፤ አባታቸውም ታዋቂው ከንቲባ ገብሩ ደስታ ነበሩ፡፡

(አልያም እታገኘሁ ሀይሌ) ጀምሮ፣ ዘመኑ ሴት ዘፋኞችን ከድብቅ ጠጅ ቤት አዝማሪነት አውጥቶ እያበረታታ የሄደበት ነበር:: ባልተለመደበት ዘመን የዳንስ አስተማሪ ጭምር የነበረችው ሴት ዘፋኝ ሜሪ አርምዴ በክራሯ፣ በጎርናና ድምጽዋና በማራኪ ግጥሞችዋ ብዙዎችን ማርካለች:: ሴት ዘፋኞች ተገቢውን ድጋፍ በማጣታቸው ኑሮአቸው ስለሚቆረቁዝ ሜሪ አርምዴ በጣም ታዝን ነበር:: በተለይ ከውጭ አገር ሴት ዘፋኞች ጋር ሁኔታውን ስታመዛዝን:: ባንድ ወቅት ይህ ሁኔታ ከፊትዋ ድቅን አለባት:: የደቡብ አፍሪካዋ ታዋቂ ዘፋኝ ማርየም ማኬባ አዲስ አበባ መጥታ ራት ጋብዛት ነበር፤ እስዋም አጸፋውን ለመመለስ ፈልጋ፣ የመኖሪያ ቤትዋ ድህነት ስላሳፈራት፣ የት እንደምትጋብዛት ተጨነቀች:: በአጋጣሚ ከሚያደንቁዋት ሰዎች አንዱ አፓርትመንቱን እንድትጠቀምበት ፈቀደላት:: በየቦታው ፎቶዋን እቤቱ ውስጥ ተክታ የሱዋ መሆኑን በማሳመን ተደስተው ከማኬባ ጋር ራት ከበሉ በኋላ፣ መደናቀፊያ ነገር መጣ:: መጸዳጃ ቤቱ የት እንደሆነ ጠፋት::

ዘመኑ ብዙ ሴት ዘፋኞች አፍርቶ ነበር፤ ዘመናዊዎቹ ብዙነሽ በቀለና ሂሩት በቀለ ከክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ፣ ጠለላ ከበደ እና ፍቅርተ ደሳለኝ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኦርኬስትራ ወዘተ:-- በመድረክ መታየት የጀመሩበት ወቅት ነበር:: ኋላ ደግሞ በለጋ ወጣትነታቸው ተመልምለው ሀገር ፍቅር ቲያትር ውስጥ የተጫወቱ እንደ አሰለፈች አሽኔ፣ እንደ ዘነበች ታደሰ (ስሜትዋን በሙሉ በመድረክ ላይ የምታንጸባርቅና ተመልካችን በሙሉ የምትቀሰቅስ ስለነበረች ጃንሆይ ጭራ ቀረሽ ብለው የሰየሙዋት)፣ እንደ አስናቀች ወርቁ ከነ ክራሯ፣ ዘፋኖቻቸውንና ውዝዋዜአቸውን ጭምር በመድረክ እያሳዩ መዝናናት በሕዝብ ዘንድ አስለመዱ:: ልምድም እያካበቱ ሄዱ:: በተለይ ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ በቴሌቪዥን እያሳዩ ተመልካችን ማረኩ፤ አስደነቁ:: በዚሁ ዘመን ነበር ኦርኬስትራ ኢትዮጵያ በሚል ስያሜ የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ የባሕል የሙዚቃ መሳሪያዎች እና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃና ውዝዋዜ አሰባስቦ በመድረክና በቴሌቪዥን ማስተዋውቅ የተጀመረው:: ከወላይታ የመጣች የዚህ ኦርኬስትራ አባል የነበረች በማሚቴ ስም የምትታወቀው አልማዝ፣ ውዝዋዜዋ ጭንቅላትዋን፣ አንገትዋን፣ ወገብዋን፣ እግሮችዋን፣ ሰውነትዋን በሙሉ (አንድም የሰውነትዋ አካል ሳይቀር) በማንቀሳቀስና በብሄረ ሰብዋ ሙዚቃ እየተመራች በመጨፈር አድናቆትን አትርፋ ነበር:: እንዲሁም አዲስ አበባ ያገር መናሀርያ በመሆንዋ ከየክፍለ ሀገሩ የሴት ዘፋኞች (እንደ ጸሀይቱ ባራኪና አምለሰት አባይ) እዚሁ አዲስ አበባ እውቅና አግኝተው ማዝናናት ጀምረው ነበር:: አንዳንዶቹም ከዚያም አልፈው (እንደ ጭራ ቀረሽ፣ እንደ አስናቀች ወርቁ እና እንደ ጠለላ ከበደ) በተዋንያንነት መካፈል ጀምረው በሕዝቡ ዘንድ የትያትር ማየትና ማድነቅ ፍቅር እንዲበረታታ አስተዋጽኦ አበርክተዋል::

አርቲስት ሰላማዊት ገብረ ሥላሤ በሙያዋ ምክንያት ከባለቤትዋ ጋር ተፋትታ ነበር:: ይህ የሚያሳየው በሕብረተሰቡ ዘንድ ለአርቲስቶች የቱን ያህል ዝቅተኛ አመለካከት እንደነበረ ነው:: ሆኖም በራስዋ አንደበት እንደተናገረችው:- «የካቲት የሰማእታት ቀንን ምክንየት በማድረግ ኦልምትኩም ብዬ ኦልዋሽም የማለውን

ቲአትር ያቀረብን ለት ተዋበችን ሆኜ ነበር የተጫወትኩት፡፡ ንጉስ ነገስቱ ገብተው አይተው ስለተደሰቱ ተዋንያኑን ቤተ መንግሥት ድረስ አስጠርተው ጋበዙን፡፡ እኔም የአንገት ወርቅ ከእጃቸው ተሸለምኩኝ» ብላለች፡፡ ለጥቆም፣ «[ባለቤቴም] በጋዜጣ ላይ ወጥቶ ሲየዩና በራሺያ፣ በሱዳን፣ በዩጋንዳ ባህላችንን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ጊዜያት እየተገጋዘኩ መሥራቴን በማየታቸው አዝማሪነትም ለካ እንዲህ አይነት ክብር አለው *ፈረንጅ ሀገር ድረስ ያስኬዳል* ብለው ለመታረቅ ቢለምኑኝ በጣም አበሳጭተውኝ ስለነበር በተራዬ አሻፈረኝ ብዬ እንደተጣላን ቀረን፡፡» ብላ አውስታለች፡፡[12]

በመጨረሻ ድንቅዋ ድምጻዊና ረቂቅዋ ገጣሚ ንጋትዋ ከልካይ (የማትጠልቀው ጀንበር) ሐምሌ *19 1998* ዓ.ም. በ*108* ዓመታቸው ከማረፋቸው *1* ዓመት በፊት ለአገልግሎታቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ተሰጥቷቸው ነበር፡፡

ለመሆኑ ያለ ሴት ዘፋኝ፣ ያለ ሴት እስክስታ ወራጅ፣ ያለ ሴት የአገር ባሕል ጭፈራ፣ ያለሴት ተዋንያን የተሟላ መዝናናት ይገኛል ወይ? ሴቶች እንደ አደይ አበባ መፍካት የጀመሩበት ዘመን ነበር፡፡

[12] *ገነት* (በሴቶች ጉዳይ ለይ የሚያተኩር በግል የሚታተም ወርሐዊ መጽሔት) ሐምሌ *1985* ቅፅ *1* ቁጥር *5*፣ ገጽ *21*

## *መደምደሚያ*

ዘመኑ የዘመናዊነት ዕድገት ጅምር የታየበት በመሆኑ፡ በቅድምያ ዕድል አግኝተው ከጓዳ የወጡ ሴቶች በየፊናቸው፣ በየሞያቸው፣ በትኩስ ኃይላቸው፣ ተጠቅመው ላገርና ለሕብረተሰብ ምን ያህል እንዳበረከቱ ከሞላ ጎደል፡ በብልጭታ አቅርበናል።

በመጨረሻም መግለጥ እምንፈልገው፣ የቀረበው የሴቶች ዝርዝር ለናሙና ያህል የቀረበ ነው እንጂ በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች በይፋ ከጓዳ ወደ አደባበይ ወጥተው በትኩስ ሀይላአቸው ተጠቅመው ላገር አጠቃላይ ግንባታ እድገት አበርክተው ለመጭዎች ሴቶች ከማጀት ወደ አደባባይ እንዲወጡ አመቻችተዋል ብለን እናምናለን። የኦሊምፒክን ባሕል ምሳሌ በመጠቀም ሴቶች፡ በዘመኑ አቀጣጥለው ያበሩት ችቦ በቀጣይ ዘመን ለመጡት ሴቶች ተላልፏል።

# ክፍል ፫
# አቅድን መጀመር

# የኢኮኖሚ ፕላን በኢትዮጵያ መቼና እንዴት ተጀመረ?

*አሸናፊ ሺፈራው*

## የታሪክ ማስታወሻ

የዛሬ አንድ መቶ ዓመት አካባቢ የኢትዮጵያ ማንነት እና የንጉሠ ነገሥቷ የዳግማዊ ምኒልክ ገናናነት የዓለም ሕብረተሰብ መነጋገሪያ ነበር:: በአገር ውስጥ እምዬ ምኒልክ አገራቸውን አረጋግተው አስተዳደሩን ለማሻሻል ጥረት በማድረግ ላይ ነበሩ:: ብዙ የማሻሻል እቅዶችና ጅማሮዎች ታይተዋል::

በዚሁ ጊዜ የአፄ ምኒሊክ ጤናቸው ታውኮ አቤት ሲውሉ፣ የመንግስታቸው ሽግግር አላማ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከወሎው መስፍንና ከሴት ልጃቸው የሚወለደው ኢያሱ ሚካኤል ወራሴ መንግሥታቸው መሆኑን ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ አስታወቁ:: መስፍኑም እራሱን እስኪችል ሞግዚት መርጠው የመንግሥት ሽግግሩ በሰላም እንዲተላለፍ ተናዘው መሳፍንቱንና መኳንንቱን ቃል አስገቧቸው::

አፄ ምኒልክ ሰላማዊ የመንግስት ሽግግር ለልማትና እድገት ወሳኝ መሆኑን፣ ጠንቅቀው ያወቁ መሪ ነበሩ ብንል ማጋነን አይሆንም:: አፄ ምኒልክ ለዚህ ሰላማዊ ሽግግር ቀደም ብለው ያሰቡበትና ያመቻቹ ይመስላል:: ተቀናቃኝ ሊሆኑ ይችላሉ የሚሏቸውን መሳፍንት ወይ አሳምነዋቸዋል፤ አለበለዚያ በፍርድ አስወግደዋቸዋል:: በዘመኑ የነበሩት የምኒልክ መሳፍንትና መኳንንት እያንዳንዳቸው እንደትላልቅ ተቋም የሚቆጠሩ፣ ታማኝና ለንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር የነበራቸው ስለነበሩ ምርጫውን የተቀበሉት በደስታ ነበር:: በዘመኑ የነበሩት ፊታውራሪ ሐብተጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ ራስ ቢትወደድ ተሰማ፣ ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ፣ በጅሮንድ ይገዙ ... ወዘተ ኃይልም ስልጣንም ነበራቸው:: ቢሆንም እነዚህ የአፄ ምኒልክ ታማኝ መሳፍንትና መኳንንት ናደውና (ልጅ እያሱ) መሐላቸውን አፈረሱ ሲባል የሐይማኖትና የሐገር ጉዳይ ስለሆነባቸው አቡኑ ከመሐላቸው እንዲፈቷቸው አድርገዋል፤ ልጅ ኢያሱን ከስልጣን አወረዷቸው:: የምኒልክን ቃል በሙሉ ላለመሻርና በሕዝብ ዘንድም ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ወ/ሮ ዘውዲቱ ምኒልክን አንግሠው፣ ራስ ተፈሪ መኮንንን አልጋ ወራሽ አድርገው ንግሥትን እንዲረዱ መርጠው ሾሟቸው:: በዚህ ውሳኔያቸው የመንግስቱንም ሰላማዊ ሽግግር ለማረጋገጥ በቁ::

ራስ ተፈሪ መኮንን፣ ለዚህ ምርጫ ያበቃቸው፣ ለዙፋኑ የነበራቸው ቅርበት ሳይሆን፣ በዘመኑ ከነበሩት መሳፍንት በአስተሳሰባቸውና በአሳዩት የአስተዳደር ችሎታቸው፣ አስተዋይ፣ ብልህና መንፈሰ ጠንካራ መሆናቸው ነበር:: የነበሩት የአባታቸው ዘመዶችና አሽከሮች ከምኒልክ መሳፍንትና መኳንንት ጋር የነበራቸው መልካም ግንኙነት ሚዛኑ ወደ ተፈሪ እንዲያዘነብል መርዳታቸው አያጠራጥርም:: በተጨማሪ፣ ራስ ተፈሪ ከአባታቸው የወረሱት ሀብት ከዘመኑ መሳፍንት የተለዩ ያደርጋቸዋል::

ስለዚህ ብዙዎቻችን እንደምናስበውና እንደምንገምተው ሳይሆን፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመንገሥት የበቁ በምርጫ እንጂ በውርስ ወይም ይገባኛል በማለት አይደለም።

በዘመኑ ለዙፋኑ ቅርበት ያላቸው ይገባናል ሊሉ የሚችሉ መሳፍንቶች ነበሩ። ነገር ግን፣ በጊዜው ከነበሩት የምኒልክ ታማኝ መሳፍንትና መኳንንት ቃል ውጪ በኃይል መንግስት ለመያዝ የሞከረ የለም። ኃይሉም ዝግጅቱም አልነበራቸውም። ይህ ሲባል ግን በራስ ተፈሪ ሹመት ተቃውሞ አልነበረም ማለት አይደለም። መርጠው ስልጣን ላይ ያወጧቸው መሳፍንትና መኳንንት ሳይቀሩ በየግላቸው በሥራ ላይ ሲያዩዋቸው ቅሬታ ነበራቸው። ስልጣንንም አስተባብሮ፣ አሳምኖ የሚሽራቸው አልነበረም። መሻር ግን ይቻል ነበር።

የልጅ ኢያሱ ወገኖች ራስ ተፈሪን ከስልጣን ለማውረድ ብዙ ጥረዋል። አባታቸው ጦር አንስተዋል። ግድያ ሁሉ ተሞክሯል። በዘመኑ ራስ ተፈሪን የሚተካ ብቁና የተሻለ የአመራር ችሎታ ለኢትዮጵያ የወደፊት መሻሻል አላማ ያለው ተወዳዳሪ መስፍን አልታየም። በዛሬው አነጋገር ራስ ተፈሪ ተራማጅ የሚባሉ መሪ ነበሩ። ለብዙ ዘመን በኢትዮጵያ የተንሰራፋውን የፊውዳል ሥርዓት የማስወገድ አላማ የነበራቸው መሪ ነበሩ። የኢትዮጵያ ነፃነትና ሉአላዊነት የሚከበረው ኢትዮጵያ የዓለም ሕብረተሰብ አባል ስትሆን ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ። ከብዙ ትግል በኋላም መሳፍንቱንም መኳንንቱንና የሃይማኖት አባቶችን አግባብተው፣ አሳምነው፣ ኢትዮጵያ የአለም መንግሥታት አባል እንድትሆን አበቋት። አባል ለመሆን የሚጠየቀውን የመልካም አስተዳደርና የሰው ልጅ መብት ማክበር ግዴታንም ቀስ በቀስ ሥራ ላይ እንዲውል በሕግ እንዲወሰን አደረጉ። የባሪያ ንግድን እና የባሪያ ስርዓትን አስቀሩ።

ለሰው ልጅ መሻሻልና ለሐገር ልማት፣ ትምህርት ወሳኝ መሆኑን ገና ከመጀመሪያው በመገንዘብ እውን ለማድረግ ጥረዋል። ወጣቶች ትምህርት ቤት ገብተው ወይም ውጪ ሐገር ሔደው እንዲማሩ አድርገዋል፤ አበረታተዋል። በአንድ ወቅት መሳፍንቱንና መኳንንቱን ከልጆቻቸው መርጠው ውጪ ሐገር ሔደው እንዲማሩ አንድ አንድ ልጅ እንዲሰጧቸው ጠይቀው ብዙዎቹ ያቀረቡት ልጆቻቸውን ሳይሆን ያሽከሮቻቸውን ልጆች ነበር። ለምሳሌ ከኛ ቤተሰብ ውስጥ በዚህ ጊዜ ተመርጦ የተሰጠው የባሻ አደፍርስ ልጅ አለመወርቅ ውጪ ሒዶ ተምሮ ዶክተር ሆኖ አንቱ ተብሎ መጣ። የመሳፍንቱ ልጆች ግን እድሉ ተሰጥቷቸው የማወቅ፣ የመማርና የመመራመር ተካፋይ ሳይሆኑ ቀሩ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአገር መከላከያና ፀጥታ በኩልም የትምህርት አስፈላጊነትን በመገንዘብ፣ በሐገር ውስጥ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ከውጪ አስተማሪዎች መጥተው ማሰልጠን ተጀመረ። ከነሱ ማህል እየተመለመሉ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት የተላኩ ነበሩ። ይህ ሁሉ የተፈሪ መኮንን አላማና ፍላጐት ነበር።

እነዚህ በሐገር ውስጥ እና ወደ ውጪ እየተላኩ የተማሩትና የሰለጠኑት የኢትዮጵያ ልጆች፣ ትምህርታቸውን እየጨረሱ ሀገራቸውን ለማገልገል ሲጀምሩ ነበር የጣሊያን ፋሺስት መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ያነሳው። የጣሊያን ወታደርም የኢትዮጵያን ጦር ጥሶ ወደ መሐል ሀገር ሲገሰግሥ

ከመርዝ ጋዝ ጪስና ከዘመናዊ መሣሪያ ጭፍጨፋ የተረፈው የኢትዮጵያ ወታደር ነበር ለአምስት ዓመት ጣሊያንን በአገር ውስጥና በውጪ ሀገር ሲታገል የቆየው፡፡

ለዚህ የአርበኝነት ትግል ጥንካሬ ከሰጠው ነገር ውስጥ በዘመኑ ንግርት እየተባለ የሚጠራው በባህታውያንና በመንፈሳዊ አባቶች የሚነገረው አንዱ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ፈርሶ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ተሰደዱ ሲባል፣ ሕዝቡ አዝኖ በየቤተክርስቲያኑ ሲጸልይ፣ በአጋጣሚ ለሴት አያቴ አንድ ደብረሊባኖስ መነኩሴ (ባሕታዊ) አይዞሽ አትዘኚ ንጉሡ ከአምስት ዓመት በኋላ በጒጃም በኩል ተመልሰው ይመጣሉ ብሎ ነገራቸው፡፡ ይህን ንግርት፤ ወግ ነውና ለወዳጆቻቸውና ለወገኖቻቸው ተናገሩ፡፡ ለጊዜው ፍቼ ተሹሞ የመጣው የጣሊያን ተሿሚ (ኢትዮጵያዊ) ባለ ስልጣን ንግርቱን ሰምቶ ለአለቆቹ ነግሮ አያቴ ከነልጆቻቸው ታሰሩና የነገረሽን ሰው ስም አውጪ ተብለው ባለመናገራቸው ከፍ ያለ ስቃይ ደረሰባቸው፡፡ በመጨረሻም ጠዋት እንዲገደሉ ተወስኖ ማታውኑ በአንድ ከፍተኛ የጣሊያን ባለሥልጣን ዘንድ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ሰውነታቸውን ገልጠው የደረሰባቸውን ኢሰብአዊ ግርፍያ ለባለሥልጣኑ አሳዩት፡፡ በተአምር፣ የሞት ውሳኔው ተነስቶ ለሦስት ዓመት በደናኒ (ሱማሊያ)፣ ከልጆቻቸው ጋር ታስረው ተፈተዋል፡፡

በዚህ ጊዜ የጣሊያን ጦር የነበሩትን ትምህርት ቤቶች ዘግቶ የተማሩትን ሲቪልና የጦር መኮንኖች እያሳደደ ፈጃቸው፡፡

## የሉአላዊነትና የነፃነት ትግል (1933-41)

በ1932 ዓ.ም (በታሪክ አጋጣሚ) ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር፣ እንግሊዝ ደጀኑዋን ነፃ ለማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኢጣሊያን ጦር ማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ አገኘችው፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ ከጠላት ወረራ ነፃ ለመውጣት የመጀመሪያ ሆነች፡፡ በዚህ ጊዜ ከእነኛ ውጪ ሐገርና በሐገር ውስጥ ከተማሩት ብርቅዬ ልጆችዋ ውስጥ ብዙዎቹ ተገድለዋል፡፡ የተረፉ ቢኖሩ አንዳንድ በሐገር ውስጥ በአርበኝነትና እንዲሁም በውጪ በስደት ያሉት ነበሩ፡፡ ሆኖም ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የመልካም አገልግሎት መነሻ ሆነዋታል፡፡

ከድል በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የመጀመሪያ ትግል የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ሕልውና ማረጋገጥ ነበር፡፡ እንግሊዞች ኢትዮጵያን «ከጠላት የተያዘ ግዛት» ብለው በመሰየም ለማስተዳደር ፍላጐት ነበራቸው፡፡ ከዚህ የእንግሊዝ ሤራ ለመውጣት ከፍተኛ ትዕግስት፣ ሥልትና ቆራጥነት ይጠይቅ ነበር፡፡ ከዚያም፣ በዓለም መድረክ የምታቀርበው የይግባኝ ጥያቄ (የኤርትራና ሱማሊያ) ነበር፡፡ ለዚህ ትግል ከተረፏት የተማሩ ልጆቿ እንዲሳተፉ መመደብ ነበረባት፡፡ ስለዚህም በሐገር ውስጥ ለሚደረገው የእድገትና የመሻሻል ጥረት አስተዋጽኦ ማድረግ አልቻሉም፡፡

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ የፓለቲካና የአስተዳደር መዋቅሮች በሙሉ ፈራርሰው ስለነበር ሁሉም እንደገና የሚቋቋሙ ነበሩ፡፡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶች፣ የጤናና የኢኮኖሚ ልማት ተቋማት መገንባት ነበረባቸው፡፡ የመቋቋሙን ጥረት በጣም ፈታኝ ያደረገው፣ ያለእርዳታ በራሷ አቅም ብዙ መተግበሩ ነበር፡፡ ለመቋቋሚያ ኢትዮጵያ፣ ከእንግሊዝ መንግሥት ከጠየቀችው አስራ ሁለት

*ሚሊዮን የስተርሊንግ ፓውንድ ውስጥ የተሰጠችው ሁለት ሚሊዮን ፓውንድ ብቻ ነበር፡፡*

**ግንቦት 2 ቀን 1933 ዓ.ም የተሾሙ የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች**

1. *ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው (በኋላ ራስ ቢትወደድ) የአገር ግዛት ሚኒስትር፣*
2. *ራስ አበበ አረጋይ የጦር ሚኒስትር፣*
3. *አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ (በኋላ ፀሐፊ ትዕዛዝ) የጽህፈት ሚኒስትር፣*
4. *አቶ ሎሬንሶ ታዕዛዝ (በኋላ ብላቴን ጌታ) የፍርድ ሚኒስቴር፣*
5. *አቶ አየለ ገብሬ (በኋላ ብላቴን ጌታ) የፍርድ ሚኒስቴር፣*
6. *አቶ መኮንን ደስታ የትምህርት ሚኒስቴር (አቶ መኮንን የሀርቫርድ ዮኒቨርሲቲ ምሩቅ)፣*
7. *አቶ ገብረእግዚአብሔር ፍራንሷ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣*
8. *አቶ መኮንን ሐብተወልድ የንግድና ገንዘብ ሚኒስትር፣*
9. *ፊታውራሪ ታፈሰ ኃብተሚካኤል የፓስታ ሚኒስትር፣*

*ንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ማቋቋማቸውንም ለሚመለከተው ሁሉ አስታወቁ፡፡ ከዚህ በተከታታይ የሚኒስትሮችን ስልጣንና ተግባር የሚገልጽ እንዲሁም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ወጣ፡፡ በአገር አስተዳደር በኩል ኢትዮጵያ በ12 አውራጃዎች፣ በ60 ወረዳዎችና በ339 ምክትል ወረዳዎች ተከፋፍላ የክፍለ ሀገር አስተዳደር ተቋቋመ፡፡ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እየተከፈላቸው እንዲሠሩ ተደረገ፡፡ ግብር በቀጥታ ለመንግሥት ግምጃ ቤት እንዲከፈል ሆነ፡፡ በጉልበትና በልዩ ልዩ አገልግሎት ለመንግስት ባለሥልጣን ይሰጥ የነበረው ቀረ፡፡ የመንግሥት አስተዳደር አንድ ወጥ በሆነ ማዕከላዊ መንግስት እንዲተዳደር መሠረት ተጣለ፡፡*

*የጣሊያን ወረራ፣ የነበሩትን ፊውዳሎችና ሥርዓቱን፣ ከመሠረቱ አናግቶት ነበር፡፡ የሰብአዊ መብት መከበር፣ በተለይ የባሪያ ንግድና ባርነት፣ ከጦርነቱ በፊት በአዋጅ የተከለከለ ቢሆንም፣ በሥራ ሙሉ በሙሉ የተተረጐመው ከጦርነቱ በኋላ ነው፡፡ እነዚያ ትላልቅ፤ እንደተቀዋም የሚቆጠሩት የምኒሊክ መኳንንትና መሳፍንት በጦርነቱ፣ ወይም በዕድሜ ወይም በሞት ከመድረኩ ተገለዋል፡፡ የተረፉትም ቢሆኑ፣ የኃይል አሰላለፉ ከግለሰቦች ወደ ማዕከላዊ መንግሥት በማዘንበሉ፣ ሕዝቡም ፍላጐቱን ለማርካት፣ ችግሩን ለመፍታት፣ በበለጠ የሚመለከተው ወደ ማዕከላዊ መንግሥት ስለነበር፣ ተሰሚነታቸው ተዳከመ፡፡*

*በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያም በዓለም ደረጃ ሉአላዊነትዋን አሳወቀች፡፡ በአርበኞቿ መስዋዕትነትና በንጉሠ ነገሥቱ አመራር ጽናት ኢትዮጵያ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት የአሸናፊዎቹ ጐራ (አላይድ ፓወረስ) አባል ሆነች፡፡ በ1938 ለንደን በተደረገ ስብሰባ ላይ በጦርነቱ ለደረሰው ጥፋት የጣሊያንን መንግሥት የጦር ካሳ እንዲከፍል አስፈረደች፡፡*

ከድል በኋላም፣ በመጀመሪያዎቹ ሰባት አመታት (1933-41 ዓ.ም)፣ አዲሱ የኢትዮጵያ መንግሥት የአስተዳደር መዋቅር ተዘረጋ። አዳዲስ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች ተከፈቱ። በእርሻ፣ በማዕድን፣ በኢንዱስትሪ፣ ለወደፊት መሠረት የሚሆን ጥናትና ምርምር ተጀመረ።

በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ እንደገና ስትቋቋም የነበረውን ሁኔታ ማገናዘብ እንዲቻል፣ የመንግሥቱን የገቢ ሁኔታ ማየት በቂ ነው፤ በ1943 ዓ.ም የመንግሥቱ ገቢ ብር 28 ሚሊዮን ብቻ ነበር። በ1946 ብር 60 ሚሊዮን ደርሶ ነበር።

## የልማት ትግልና የሥራ ፕሮግራም (1942-48)

በሚቀጥሉት ሰባት አመታት፣ ማለትም ከ1942-1948 ዓ.ም፣ የኢትዮጵያን የልማት አቅጣጫ መተለም የተጀመረበት ነበር ማለት ይቻላል። የኢኮኖሚና የሶሺያል ልማት መስሪያ ቤቶች፣ በተጀመሩ ጥናቶች ውጤት መሠረት፣ የሥራ ፕሮግራማቸውን ይቀይሱ ጀመር። በዚህ ጊዜ የተደረጉት ጥናቶችና የሥራ ፕሮግራሞች የሚሰሩት በውጪ ሀገር ዜጐች ነበር። ለከፍተኛ ትምህርት የተላኩት መመለስ የጀመሩትም በዚህ ጊዜ ነበር። በእኔ እድሜ ክልል ውስጥ የነበርነው ገና በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ትምህርት ቤት ነበርን። በዚህ ጊዜ ነበር አንዳንድ የመንግስት ሥራዎች ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ እየወጡ እራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ የተደረገው። ለምሳሌ አውራ ጐዳና ባለስልጣን በ1945 ዓ.ም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1942 ዓ.ም.፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በ1944 ዓ.ም፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለስልጣን በ19--- ዓ.ም፣ ተቋቋሙ። እነዚህ መስሪያ ቤቶች የሚመሩት በውጪ ዜጐች ነበር። ድርጅቶቹን ለመምራት በቂ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን አልነበሩም። ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመለሱት ወጣት ባለሙያዎች በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በየትምህርታቸው እየተመደቡ ከውጪ ሥራ መሪዎች ጋር በተባባሪነት፣ በምክትልነት ወይም በረዳትነት እንዲሰሩ ተደረገ።

መንግሥት እነዚህን መስሪያ ቤቶች የሚቆጣጠረው አግባብ ያለው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት የበላይ ሹም በሊቀመንበርነት በሚመራው ቦርድ ነበር።

በየድርጅቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ጨምሮ የተደረጉት ጥናቶች በሥራ ፕሮግራም መተርጐም ጀምረው ነበር። ከነዚህም አንዳንዱን ለመጥቀስ፡-

- የ10 ዓመት የኢንዱስትሪ ኘሮግራም በአሜሪካ ቴክኒካል የኘሮጀክት ተልዕኮ ተዘጋጅቶ በከፊል በሥራ ላይ ውሏል፤
- በእርሻና በከብት ዕርባታ ዘርፍ ምርት ለማሳደግና ምርምር ለማድረግ የሚያስችል ኘሮግራም በአሜሪካን (ፖይንት-4) አቀነባባሪነት ተጀምሮ ነበር፤
- የደን ሀብትን ለማልማትና ለማሻሻል በእርሻ ሚኒስቴር የተጀመረ ሙከራ ነበር፤

- የአውራ ጐዳና የአራት ዓመት የማሻሻልና የማስፋፋት ፕሮግራም ተነድፎ ነበር፤
- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽንን የ3 ዓመት የማሻሻያና የማስፋፋት ፕሮግራም ተነድፎ ነበር፤
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደተቋቋመ፣ የአገር ውስጥ አውሮኘላን ማረፊያ ጣቢያ የማሰራት ፕሮግራም ተጀምሮ የአየር መጓጓዣ አገልግሎት እንዲስፋፋ ሆነ፤
- ወደ ውጪ የሚላከውን ቡና ጥራቱን ማሻሻያ ኘሮግራም ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ዋለ፤
- የአሰብ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት ጥናት የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነበር፤
- ለተቀነባበረው የውሃ ሀብት ልማት ኘሮግራም የአባይና የዋቢ ሸበሌ ሸለቆ ጥናቶች ተጀመሩ፤
- በትምህርት ዘርፍ የ10 ዓመት የትምህርት ማስፋፊያ ኘሮግራም በአሜሪካ ኤክስፐርቶች ተነድፎ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ ለብዙ ዘመናት የትምህርት ሚኒስቴሩን ሥልጣን የያዙት ንጉሡ ነገሥቱ ነበሩ፡፡ እኔ እንደማስታውሰው፣ በእኔ የእድሜ ክልል ለነበሩ ከአንደኛ ክፍል ጀምሬ ዮኒቨርቲ ኮሌጅ ገብቼ ወደ ውጪ ሐገር እስክሄድ ድረስ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከኔ ተለይተውኝ አያውቁም፡፡ በየአመቱ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ፣ በየክፍሉ ከአንደኛ እስከ 3ኛ የሚወጡ ተማሪዎች ታላቁ ቤተ መንግሥት እየሔድን እንሸለማለን፡፡ ሁለተኛ ደረጃና ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሆነን፣ በዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ፍራፍሬ ይዘው ይጐበኙናል፡፡ ምግባችንን፣ ጤንነታችንን ይጠይቃሉ፤ ይቆጣጠራሉ፡፡ እንዲሁም በሙሉ እስኮላርሺኘ ወደ ውጭ ስንሔድ ትምህርት ሚኒስትሩ ዘንድ ቀርበን እንሰናበታለን፡፡ ስንመለስ እንደዚሁ ቀርበን በየመስሪያ ቤቱ እንመደባለን፡፡ የአዲስ አበባን ኑሮ እስክንለምድና ከተመደብንበት መስሪያ ቤት ደመወዝ እስክናገኝ ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወጪ ሆቴል እንድንቀመጥ ይደረጋል፡፡ አሁን ስመለከተው ይህ ሁሉ የሚደረግልን እንክብካቤ ከማበረታታት ባሻገር ሞራላችንን፣ የኑሮ ደረጃችንን እንድንጠብቅ አስችሎናል፡፡ ያኔ የሚከፈለን ደመወዝ፣ ለመቋቋሚያ የሚሰጠን ብድር ብቁ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የ6 ወር ደመወዝ አንድ አዲስ ቮልስዋገን ይገዛል፡፡
- በተጨማሪም ለወደፊት የልማት ኘሮግራም መነሻ የሚሆን ምርምርና ጥናት በየክፍሉ ይካሄድ ነበር፡፡ በማዕድን፣ በውሃ ሀብት፣ በእርሻና በደን ሀብት፣ በኃይል ማመንጫ፣ በአሣ ሐብት ልማት፣ በአዲስ አበባ መሪ ፕላን፣ በትምህርትና በጤና ወዘተ...በተጨማሪ አዲሱ የዓለም መንግስታት ማህበር እንደተቋቋመ የመጀመሪያውን ሐገር አቀፍ ጥናት ያደረገው በኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ ነበር፡፡

## የልማት ፕላን በኢትዮጵያ መቼና እንዴት ተጀመረ?

የልማት ፕላንን በየሥራ ክፍሉ ከሚዘጋጀውና በተናጠል በሥራ ላይ ከሚውለው ፕሮግራም የተለየ የሚያደርገው የየሥራ ክፍሉን ቅደም ተከተልና አሰራር የጠበቀ አጠቃላይ መሆኑ ነው:: በዚህ መልክ የሚዘጋጀው ፕላን በጣም የታወቀው በማዕከላዊነት መንግሥት ሁሉንም የሥራ ክልሎች በቀጥታ በሚቆጣጠረውና በሥራ ላይ ለማዋልም ሙሉ ኃላፊነት ባለው በኮሙኒስት ሀገሮች የሚነደፈው ፕላን ነው:: ኮሚኒስት ባልሆኑ ሀገሮች የሚዘጋጀው ፕላን እንደሀገሩ የፖለቲካ አቋምና ፍላጐት፣ የልማት አቅጣጫ አመልካች ወይም የልማት ፖሊሲ መሠረት ሆኖ ሊዘጋጅ ይችላል::

የተቀነባበረና አጠቃላይ የሆነ የልማት ፕላን ለማዘጋጀት መረጃ ወሳኝ ነው:: የሀገሩ ሕዝብ ቁጥር፣ ምጣኔ ሀብት፣ የሥራ ውጤት፣ ገቢ ወዘተ...መረጃ መኖር አለበት::

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በ1947/48 ዓ.ም አጠቃላይና የተቀነባበረ የአምስት ዓመት የልማት ፕላን ለማዘጋጀት ሲወስን መነሻው ምንና ማን ነበር? ስንል ቀጥተኛ መልስ ለመስጠት ያዳግታል:: ስለሆነም ኘላኑ በማን እርዳታ እንደተዘጋጀ ስለማውቅ መቼና የት እንደተወሰነ እገልጻለሁ::

በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለዚህ ፕላን አነሳሺው ማን ነበር? ስንል፤ ከንጉሠ ነገሥቱ ሌላ ማንንም አናይም። ጉዳዩ ወደ ዩጐዝላቪያ ከመኬዱ በፊት የታሰበበት ቢሆን ኖሮ ማስታወሻ ያቀረበው ሰው አብሮ ይሔድ ነበር። በኋላም ሥራውን (ጥናቱን) የሚከታተለው እሱ ይሆን ነበር:: በዚያን ጊዜ ይህን ባለሥልጣን አናየውም:: ከጃንሆይ ጋር አብረው የሄዱት፣ ጄኔራል አቢይ አበበ፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አቶ አክሊሉ ሐብተወልድ ነበሩ:: በዚያ ጊዜ ሁሉንም የመንግሥት ጉዳይ የሚያስተባብሩት ንጉሠ ነገሥቱ ነበሩ:: በዚህም ሚኒስትሮች በየሳምንቱ አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ የአቃቢ ሰዓት የሚባል የውይይት ጊዜ ከንጉሥ ነገሥቱ ጋር ነበራቸው::

### የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን

#### *ዝግጅት*

ፕላኑን ያዘጋጀው 11 ከፍተኛ የዩጐዝላቪያ ኘሮፌሰሮችንና የኢትዮጵያ ባለሥልጣኞችን ያቀፈ ቡድን ነበር::[1] እንደሰማሁት፣ ኤክስፐርቶቹ በሀገር ውስጥ እየተዘዋወሩ ዝርዝር የኢኮኖሚ ጥናትና አሰሳ ያደረጉት በምስጢር ነበር። ለዚህ ሥራ ባልደረባቸውም የክብር ዘበኛ ነበር።

ፕላን ሲዘጋጅ በመሠረቱ ለአፈጻጸሙም ሆነ ለተቀባይነቱ ግልጽ መሆንና ሕብረተሰቡን በጠቅላላ የሚያሳትፍ መሆን አለበት:: ታዲያ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፕላን ሲዘጋጅ ለምን ምስጢር ሆነ ይባል ይሆናል:: እኔ

[1] እነዚህ የዩጎዝላቭያ ኤክስፐርቶች የመጡት፣ አፄ ኃይለሥላሴ እ.አ.አ. በ1954 ዓ.ም. ዩጎዝላቭያን ሲጐበኙ፣ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ነበር። እነሱም የተሰጣቸው ሀላፊነት ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ሁሉ ማድረግና ከዚያም በኋላ ፕላኑን ማዘጋጀት ነበር።

እንደምገምተው በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ገለልተኛ ነኝ ብትልም ወዳጅነቷና ረዳቶቿ የምዕራብ ሐገሮችና እነሱ የሚቆጣጠሩት ተቋማት ናቸው:: ስለዚህ አንደኛ ከመጀመሪያው ዝግጅቱ ይፋ ቢሆን የወዳጆቿን ተቃውሞና ጥያቄ ላለማስነሳት፣ ሁለተኛ አዘጋጆቹ ዩጐዝላቪያውያን (የኮሚኒስት ጐራ አባል) ስለሆኑ ቅሬታና ጥርጣሬ እንዳያስከትል በማሰብ ነው::

**የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ኘላን ዝግጅት መዋቅር:-**
***የሚኒስትሮች ኮሚቴ (ቦርድ) አባሎች***

1. ክቡር አቶ አበበ ረታ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ሰብሳቢ፣
2. ክቡር ባላምባራስ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል (በኂላ ብላቴን ጌታ) የእርሻ ሚኒስትር ዴታ፣
3. ክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ የንግድና የኢንዱስትሪ ምኒስቴር ምክትል ሚኒስትር አባል፣
4. ክቡር አቶ ምናሴ ለማ በገንዘብ ሚኒስትር ምክትል ሚኒስትር፣ አባል (ክቡር አቶ ምናሴ ለማ፣ በካይሮ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ምሩቅ፤ ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የብሔራዊ ባንክ ቦርድ ሰብሳቢ)፣
5. ክቡር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ስላሴ የሥራ ሚኒስቴር አባል፣ (ክቡር ደጃዝማች ዘውዴ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ በታሪክ ዶክትሬት፣ ደራሲ የፍርድ ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፣ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሆነው ያገለገሉ)፣
6. ክቡር ልጅ ሚካኤል እምሩ፣ በመከላከያ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር፣ (ክቡር ልጅ ሚካኤል የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሩቅ)፣

በኤክስፐርት ደረጃ ከዩጐዝላቪያና የኢትዮጵያ ኤክስፐርቶች በቅንጅት እንዲሠሩ ተደረገ::[2]

***የመጀመሪያውን ፕላን ያዘጋጁ የዩጐዝላቭያ ኤክስፐርቶች***

- ሚስተር ቦርቮይ ዮሊች የፌዴራል የፕላን ቢሮ ምክትል ዲሬክተርና በቤልግሬድ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚ ፕሮፌሰር፣
- ሚስተር ሚላን ሚሴሪች፣ በቤልግሬድ የፌዴራል ፕላን ቢሮ የመንግሥት አማካሪ፣
- ኢንጅኒየር ብራኒስላቭ ሚሎሳቭሌዬቪች፤ በቤልግሬድ ዩኒቨርሲቲ በእርሻ ፋኩሊቲ ፕሮፌሰር፣
- ኢንጂኒየር ዲሻን ላሊዮሹች በቤልግሬድ ዩኒቨርሲቲ የእርሻ ፋኩሊቲ ፕሮፌሰር፣

[2] እነዚህም ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ከዩጐዝላቭያ በኩል 11 ሲሆኑ ከኢትዮጵያ በኩል ደግሞ 10 ነበሩ::

- ኢንጂኒየር ሜቲይ ክሌይድንስት በሉብሊያና በውሃ ሀይል (ሀይድሮ ኢነርጂ) ኢኒስቲትዩት አማካሪ፣
- ኢንጂኒየር ደኒስ የሊንስ፣ የሊብሊያና የጂኦሎጂ/ ኢኒስቲቲዩት ዳይሬክተር፣
- ሚስተር ጆንዚ ሴንቼች፤ ሉብሊያና የማዕድን ቴክንሺያን፣
- ኢንጂኒየር ፖሌ ቬሊ ሚሉቲኖች በቤልግሬድ የፌደራል ፕላን ቢሮ አማካሪ፣
- ኢንጂኒየር ቪሊሚር ሚሉቲኖቪች በቤልግሬድ ዩኒቨርሲቲ በኢንጂነሪንግ ፋኩሊቲ ፕሮፌሰር፣
- ሚስትር ፍራንዮ ራክኒች፣ በቤልግሬድ የኢኮኖሚክስ ኢንስቲትዩት አባልና ፋኩሊቲ ፕሮፌሰር፣
- ሚስተር ፍራንንዮ ራክኒች፣ በቤልግሬድ የኢኮኖሚክ ኢንስቲትዩት አባልና፣
- አራት ትርጉም ሰራተኞችና በኢትዮጵያ በኩል የሚከተሉት ኤክስፐርቶች ነበሩ፡-

***የመጀመሪያውን ፕላን ከዩጎዝላቪያኖች ጋር ሆነው ያዘጋጁ ኤክስፐርቶች***

- አቶ መአዛ ወርቅነህ፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር፣
- አቶ አርአያ እቁበ እግዚ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዋና ዲሬክተር፣
- አቶ ንጋቱ ወልደ ጊዮርጊስ ደስታ፣ በእርሻ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር፣
- አቶ መኩሪያ ወልደ ሥላሴ፣ በእርሻ ሚኒስቴር ዲሬክተር፣
- አቶ ሀብቱ እሼቴ፣ በእርሻ ሚኒስቴር ዲሬክተር፣
- እንጂኒየር በቀለ ማሞ፣ በማእድን ቦርድ ምክትል ዲሬክተር፣
- አቶ አስፋው ደምሴ በገንዘብ ሚኒስቴር ምክትል ዲሬክተር፣
- አቶ በላይ አባይ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣
- አቶ አባተ መንከና ከሥራ ሚኒስቴር፣
- ካፒቴን አሰፋ እረኛው ከክብር ዘበኛ፡፡

በዩጐዝላቭ ኤክስፐርቶች ተዘጋጅቶ የቀረበውን የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ፕላን በኢትዮጵያ ወገን የተመለከቱት ኢትዮጵያ የመደበቻቸው አስሩ ኤክስፐርቶች ነበሩ፡፡ ፕላኑ ሲዘጋጅ የየመስሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ የሥራ ፕሮግራም ከመካተቱ ሌላ በዝግጅቱ የመስሪያ ቤቶች ተሳትፎ የነበረ አይመስልም፡፡ በዝግጅቱ ተካፋይ (ተባባሪ) እንዲሆኑ የተመረጡት ወጣት ኤክስፐርቶች ከአምስት መስሪያ ቤቶች ብቻ የተውጣጡ ነበሩ፡፡ ከሶሻያል መስሪያ ቤቶች ማንም አልነበረም፡፡ እንዲሁም እራሳቸውን ችለው ከተቋቋሙት፣

በመጀመሪያው ፕላን የኢንቨስትመንት አመዳደብ ቅድሚያ የተሰጣቸው፣ መስሪያ ቤቶች እንኳ አልተወከሉም፡፡ ለምሳሌ፣ አውራ ጐዳና፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ወዘተ..፡፡ ይህ የተደረገው፣ ምናልባት የነዚህ መስሪያ ቤቶች ሥራ መሪዎች የውጭ ሀገር ዜጐች ስለሆኑ፤ የዝግጅቱን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ ተብሎ ይሆናል፡፡ ለዚህ ከፍተኛ ዝግጅትና ተሳትፎ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሰብሳቢ እንዲሆን፣ በኋላም ለፕላኒንግ ቦርድ ጽህፈት ቤት የቅርብ ተከታታይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው፣ ስለፕላን በጊዜው የነበረው ግንዛቤ፣ በተለይ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ፣ ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር የተያያዘ ተደርጐ በማሰብ ይሆናል የሚል ግምት ይሰጣል፡፡

ለመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን የተደረገው ጥናትና አሰሳ፣ በተለይ መረጃ እጦት ያስከተለውን ችግር አጥኝዎቹ በሚገባ አመልክተዋል፡፡ ሆኖም ፕላን በጠቅላላ የነበረውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታና ወደፊት የሚኖረውን የእድገት አቅጣጫ በሚገባ ያመለክታል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ምናልባት ከኢኮኖሚው ዝቅተኛ የእድገት ደረጃና ኋላቀርነት አንፃር፣ ችግርና መፍትሔው አይሻማም ብሎ ከማሰብ የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ያኔ ለተነሱት መሠረታዊ ችግሮች የተሰጡት መፍትሔዎች ዛሬም፣ ከ50 ዓመት በኋላ፣ በአንዳንድ የኤኮኖሚው ሴክተሮች ውስጥ ላሉ ችግሮች መፍትሔ ሆነው ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ በማዕድን አሰሳና ውጤት፣ የኢንዱስትሪ ውጤት ኋላቀርነት ዛሬም አለ፡፡ በዚህ ጊዜ አዘጋጅዎቹ ስለ ገጠማቸው ችግርና ተዘጋጅቶ ስለቀረበው ፕላን አስተማማኝነት ሲገልጹ፣ «የቀረበው ፕላን የቅርብ ጊዜን የልማት አቅጣጫ የሚቀጥልና የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ወደ ተፋጠነ የኢኮኖሚ ልማትና ወደ ተሻለ የወደፊት እድገት የሚመራ ዘዴ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ እድገት በቀላሉ የሚደረስበት፣ የልማቱ ፍሬም የሚደረሰው ደረጃ በደረጃ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዘመናዊ ለማድረግ ከመሰናክሎች ሁሉ ከባዶቹ በቂ የኢንቨስትመንት ገንዘብ አለመገኘቱና ፕላኑን ሥራ ላይ የሚያውል በቂ የተማረ የሰው ሀይል አለመኖሩ ናቸው፡፡ ሦስቱ ፕላኖች፣ ከሁሉም በላይ ከባዱ መሰናክል የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን እጥረት መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ብዙ ገንዘብ እንኳ አስፈላጊ ሆኖ ከብዙ ፍለጋ በኋላ ቢገኝም፣ ፕላኑ ባመለከተው፣ ቅድሚያ ለተሰጣቸው የሥራ ክፍሎች እና ፕሮግራሞች ሳይደርስ መቅረቱ ትልቁ ችግራችን ነበር፤ ይህም የሆነው በሰው ሀይል እጥረት ነበር፡፡

### *አላማና ግብ*

የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ዓላማና ግብ ከመነደፉ በፊት፣ በጊዜው ያለውን የኢኮኖሚ ይዘት አስቀድሞ መገምገም፣ የወደፊቱን የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫና እድገትን የሚያነሳሱ ክንዋኔዎች መተንተን አስፈላጊ ነበር፡፡ ስለሆነም የወደፊቱ የኢኮኖሚ ልማት የሚወሰነው ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ሀብት፣ በህዝቧ ታታሪነትና ፍጆታውን ገትቶ ለኢንቨስትመት ሀብት ማካበት ሲችል ነው፡፡

የዛሬ 50 ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 19 ሚሊዮን ነበር፡፡ በእርሻ መሬት በኩል ያለው ለእርሻ ተስማሚ የሆነው መሬት ብዛት በ3ተኛው ፕላን ተለውጧል፡፡ 83 ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የታረሰው 10.13 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ መሆኑ ተገምቷል፡፡ ይህም ማለት ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ የእርሻ መሬት ጥበት አልነበራትም፡፡ ይህ መሬት፣ ባለው ቴክኖሎጂ ቢያንስ እያደገ በመሄዱ ያለውን ህዝብ የምግብ ፍላጐት ማርካት ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ይህን ሁኔታ ታሳቢና መሠረት በማድረግ ነበር ግቦቹን የወጠነው፡፡ በአነስተኛ ኢንቨስትመንት፣ ባለው ቴክኖሎጂ፣ አንዳንድ የእርሻ ዘዴዎችንና የእርሻ መሣሪያዎችን በማሻሻል፣ የተሻለ የሰብል ዘር በመምረጥ፣ የገበሬውን የእርሻ ምርት ከፍ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ እንደነበር ሁሉም ተስማምተውበታል፡፡ ለተፋጠነ ልማት የተቀነባበረ፣ የታወቀና ያልተቋረጠ፣ ተከታታይ የሆነ የልማት ፖሊሲ ማራመድ አስፈላጊነቱ ተጠቁሟል፡፡ ስለዚህ በኘላኑ የተመለከተው የኢንቨስትመንት ወጪ፣ እንዲሁም ፓሊሲዎቹና መመሪያዎቹ ስራ ላይ ከዋሉ የሚከተሉትን አጠቃላይ ውጤቶችን እንደሚያስገኙ ተመልክቷል፡-

**የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ዋና ዋና ግቦች**

| ተ.ቁ | | 1947 | 1949 | 1954 | - |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከእረሻ ውጪ የሚኖረው ሕዝብ | - | - | 2.1 | - |
| 2 | ጠቅላላ ብሔራዊ ገቢ በሚሊዮን ብር | 1,686 | 1,801 | 12,841 | 16 |
| 3 | ጠቅላላ የእርሻ ውጤት በሚሊዮን ብር | 1294 | - | 1495 | 11 |
| 4 | ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ውጤት በሚሊዮን ብር | 125 | 280 | 588 | 21 0 |
| 5 | አማካኝ አመታዊ እድገት | 2-2.5 | - | 3.7 | 3.7 |
| 6 | አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢ በብር | 89 | 91 | 100 | |
| 7 | የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ከእርሻ የሚገኝ በቶን | 13,00 | 2,200 | 5,800 | - |
| | • ጥጥ | 62,500 | 62,500 | 112,500 | |
| | • ሸንኮራ አገዳ | 282,900 | 275,300 | 316,400 | |
| | • ሌሎች ሰብሎች | 497,000 | 526,000 | 601,000 | |
| | • ሥጋ የታረደ | | | | |
| 8 | የውጪ ንግድ (የተላከ) በሚሊዮን ብር | 154 | 182 | 228 | - |
| | • ቡና | 85 | 110 | 143 | |
| | • የዘይት /እህልና ውጤታቸው | 16 | 15 | 16 | |
| | • የበግና የበሬ ቆዳ | 15 | 17 | 20 | |

በዋና ዋናዎቹ ክፍላተ ኢኮኖሚ የተመለከቱትን ግቦች በአጭሩ ለማመልከት እሞክራለሁ፡፡

**እርሻ**

የመጀመሪያው የአምስት አመት ፕላን የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ፣ ፖሊሲውና መመሪያው የወጣው ከፕላኑ ዋና አላማዎች ጋር በማጣጣም ነበር፡፡ ለዚህም በአምስት አመት ውስጥ ከፍ ያለ የእርሻ ምርት፣ በተለይ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት የሚመረቱ ሰብሎች ለማቅረብ አስፈላጊው እርምጃ ሁሉ መወሰድ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ይህም፡-

- የገበሬውን ምርታማነት፣ በሄክታር የምርት ውጤቱን በማሳደግና ጥራቱን በማሻሻል፣ የአስተራረስ ዘዴን እንዲሁም የእርሻ መሣሪያ (ባለው ቴክኖሎጂ) በማሻሻል፣ ማሳደግ፣
- በከብት እርባታ በኩል ለገበያ የሚቀርበውን የከብት ብዛት ከፍ ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍና አገልግሎቱን አስተባብሮ መስጠት፣
- ባልተያዘ የእርሻ መሬት ላይ ሰው በማስፈር ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያ ከፍ ያለ ሰብል እንዲቀርብ ማድረግ፣
- ለዚህ እቅድ ማስፈፀሚያ ተመጣጣኝ የሆነ በተቀላጠፉ ድርጅቶችና በሰለጠኑ የእርሻ ተጠሪዎች የተደገፈ፡-
    - የኤክስቴንሽን አገልግሎት መፍጠር፣
    - የተሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችና ምርጥ ምርት ለገበሬ ማቅረብ፣
    - የሰብል ተባዮችንና በሽታን መከላከል፣
    - የከብት በሽታን ደረጃ በደረጃ ማጥፋት፣
    - የከብት የገበያ አቅርቦት አገልግሎት ማደራጀት፣
    - የእርሻ ምርምር አገልግሎት ማቋቋም፣
- መደበኛና ልዩ የእርሻ ማሰልጠኛ ተቋማት ተቋቁመው ለፕላኑ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል እንዲያሰለጥኑ ማድረግ የሚለውን ተግባራዊ ማድረግ ነበሩ፡፡

በእርሻ በኩል የተመደበው ወጪና የሰው ሀይል አነስተኛ ነው ቢባልም፣ በፕላኑ በተመለከተው መሠረት ቢፈፀም፣ በተከታታይ ለሚቀጥለው ዘመን ጭምር የሚደረገው የተፋጠነና የተጠናከረ ልማት መሠረት እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

ፕላኑ ከዚህ በላይ አልፎ አልፎ እንደተጠቀሰው፣ በእርሻው ዘርፍ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፣ አገልግሎቶች እንዲሰጡ አመልክቷል፡፡ ግን በዘመኑ በእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ በየደረጃው የነበሩ ሠራተኞች፣ የግልና የመንግስት እርሻ ነክ ተቋማት፣ ገበሬው የዚህን የእርሻ መሪ ሀሳብ በሚገባ እንዲረዳ ምን አድርገዋል? ለማስፈፀምስ ምን ያህል ሙከራ አድርገዋል? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ይህ የዘመኑ ፕላን አፈፃፀም ግምገማ በሚቀርብበት ጊዜ የምንነጋገርበት ይሆናል፡፡

**የደን ልማትና እቅድ**

በአንደኛው የአምስት አመት ፐላን መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያ ያለው የደን ሀብት ወደ 30 ሚሊዮን ሄክታር እንደሚደርስ ተገምቷል። ደን ለማገዶና ለቤት መስሪያ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ከማስፈለጉ ሌላ ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተጠቁሟል።

ኢትዮጵያ ያላትን ደኖች ጠብቃ ማቆየትና ባዶ የሆነውን መሬት በደን መሸፈን ቅድሚያ የሚሰጠው እርምጃ መሆኑ ከ50 ዓመት በፊት ጀምሮ ታውቋል፤ ተነግሮናል። በጊዜው የቀረበው ዕቅድ:-

- ያሉትን ደኖች ዝርዝር አውጥቶ ድንበራቸውን አረጋግጦ መጠበቅ፣
- በተጋለጡ አካባቢ የዛፍ ችግኝ ተከላ ተጠናክሮ መቀጠል፣
- የጥበቃ አገልግሎት፣ ደን የሚንከባከቡና የሚያስተዋውቁ ተቋማት ማደራጀትና ማቋቋም፣
- አስፈላጊውን የደን ሰራተኛ ለማሰልጠን የደን ትምህርት ቤት ማቋቋም፣
- ከፍ ያለ የማገዶ እጥረት ስላለ ለማገዶ የሚያገለግል የተክል ዘር መርጦ መትከል፣ ማስፈለጉ ተገልጿል።

**የማዕድን ክፍል**

የመጀመሪያው አምስት ዓመት ኘላን በማዕድን ልማት ያመለከታቸው ስራዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- አሁን ከሚመረቱ ማዕድናት ጋር ተጠናክሮና ተሻሽሎ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- የአዳዲስ ማዕድናት ፍለጋና አሰሳ ምልክት በተገኘው ማዕድን ላይ እንዲያተኩር፣ በተለይ የድንጋይ ከሰልና የብረት ማዕድን ለኢንዱስትሪ መስፋፋት አስፈላጊ ስለሆነ ፍለጋው ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣
- ከፍተኛው የማዕድን ፍለጋ ወጪ በውጭ ሀገር የግል ኢንቨስትመንት የሚሸፈን ሲሆን ይህም ለዘይት፣ ለብረት፣ ለመዳብ ፍለጋና አሰሳ ስለሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ፣
- የሐገር ውስጥ ባለሐብቶችን በማዕድን ፍለጋና ማውጣት ላይ እንዲሳተፉ በሚቻለው ሁሉ መርዳት፣ ብድር በመስጠት የታክስና የታሪፍ ቅነሳ በማድረግ፣ ከተቻለም ቀጥታ ዕርዳታ መስጠት ይኖርበታል፤ የሚሉ መሰረተ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል።

**ኤሌክትሪክ ኃይል**

በ1948 ዓ.ም በመንግስት የኤሌክትሪክ ማመንጫ የሚወጣው የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በጣም ዝቅ ያለ ነበር። በዚሁ ዘመን በነዳጅ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል 51% ሽፋን ሲኖረው በውሃ የሚመነጨው 49% ብቻ ነበር።

ከጠቅላላው በመንግስት ከሚመነጨው ኤሌክትሪክ (197,000 ሚ.ኪ.ዋ)[3] የኢንዱስትሪ ፍጆታ 52,000 ሚ.ኪ.ዋ.ስ ብቻ ነበር። ይህ ዝቅተኛ የኤክትሪክ ኃይል ለኢኮኖሚው ልማት፣ በተለይ ለኢንዱስትሪው ኋላ ቀርነት፣ ዋናው ምክንያት ነበር ተብሏል። ኢትዮጵያ ካላት ከፍተኛ የውሀ ኤሌክትሪክ አቅም፣ የምትጠቀመው 0.5% ብቻ መሆኑ ተገልጿል።

ፕላኑ ኢትዮጵያ ከውሃ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ያላትን አቅም በመገንዘብ፣ ወደፊት የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መሠረቱ ከውሃ መሆኑን ቢያመለክትም፣ በዚህ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከጊዜና ወጪ አኳያ ከነዳጅ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መቀጠል እንዳለበት አመልክቷል። የነዳጅ ዋጋ በጣም ዝቅ ባለበት ጊዜ እንኳን፣ በውሀ የሚመነጨው ኤሌክትሪክ ዋጋ አንድ ስድስተኛ ሲሆን፣ 1/3 በነዳጅ ከሚመነጨው ነበር።

በአምስት አመት ውስጥ በሚደረገው የኤሌክትሪክ ኃይል ኢንቨስትመንት በነዳጅ ለሚመነጨው ሀይል ብር 43.3 ሚሊዮን፣ በውሀ ለሚመነጨው ብር 26.5 ሚሊዮን ቀሪው ብር 11.7 ሚሊዮን ደግሞ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማሰራጫ መስመሮች መዘርጊያና እድሳት ነበር። በዚህም ወጪ በ1954 ዓ.ም 67.047 ኪ.ዋ. የሚደርስ ኤለክትሪክ ማመንጫ ኃይል እንዲገነባ ታቅዷል።

በፕላኑ ዘመን ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደው ከፍተኛው ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ቆቃ ሲሆን ይህም ጣቢያ 43,200 ኪሎ ዋት እንደሚያመነጭ ታቅዷል[4]። የዚህ ማመንጫ ጣቢያ መጠናቀቅና ከቆቃ አዲስ አበባና ከቆቃ ድሬዳዋ የሚዘረጉት የማሰራጫ መስመሮች መጠናቀቅ፣ ለታቀደው የኢንዱስትሪ ልማት በቅድሚያ አስፈላጊ ነበር።

የቆቃ ማመንጫ ጣቢያና የማሰራጫው መስመሮች የግንባታ ወጪ ከተያዘው የኤሌክትሪክ ኢንቨስትመንት 73.6% ድርሻ ነበረው።

**የፋብሪካ ልማት ግቦች**

በአንደኛው የአምስት ዓመት ፕላን መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያ የነበሩት ፋብሪካዎች 172 ሲሆኑ፣ 90% የሚሆኑት በእርሻ ውጤት ላይ የተመሰረቱ ነበሩ። በ1947 ዓ.ም እነዚህ ፋብሪካዎች 12,300 ሰራተኞች ነበሯቸው። የፋብሪካዎች ምርት በዚያን ጊዜ ብር 40 ሚሊዮን ደርሷል። ፋብሪካዎቹ በብዛትም፣ በመጠንም፣ በአይነትም፣ አነስተኛና ኢትዮጵያ ካላት ገበያና ጥሬ ሀብት ጋር ሲመዛዘኑ ተመጣጣኝ አልነበሩም።

በኢትዮጵያ የተቋቋሙት ፋብሪካዎች ከሌላ ተመሳሳይ ሀገሮች ጋር ሲመዛዘኑ የተለየ የሚያደርገው አብዛኛዎቹ የሌሎቹ ሀገሮች ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ወደውጭ ለመላክ ሲሆን (Export Oriented ሲሆኑ)፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙት ግን አብዛኞቹ አቅርቦታቸው ለሀገር ውስጥ ገበያ ነበር።

---

[3] ይህ ወደ ሜጋ ዋት ሲቀየር 197 ይሆናል፤ ምክንያቱም፣ አንድ ሜጋ ዋት 1,000 ኪሎ ዋት ነው።

[4] ይህ 43.2 ሜጋ ዋት ይሆናል፤ በጊዜው ትልቅ ግድብ ነበር።

እንዲያውም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከአሁን ከተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች፣ ለውጭ ሀገር ገበያ ብቻ ተብለው የተቋቋሙት በጣም ጥቂት ናቸው::

ለኢትዮጵያ ፋብሪካ ልማት ኋላቀርነት የተሰጠው ምክንያት በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት አለመኖር፣ የአገር ውስጥ ካፒታል አለመኖርና የኢንተርፕረነርስ ውሱንነት መሆኑ ተጠቁሟል:: በዚህ በኩል ፕላኑ የነዚህን አገልግሎቶች አቅርቦት ከሞላ ጐደል እንዲመቻች አድርጓል::

የፋብሪካ ግንባታ በመሠረቱ ለግል ባለሀብቶች ቢተውም፣ መንግሥት አንዳንድ ለአጠቃላይ እድገት አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ኢንዱስትሪዎች በቀጥታ በባለቤትነት ለብቻው ወይም በህብረት ያቋቁማል:: የግል ጥረቱን ለማበረታታት ምቹ የሆነ ፓሊሲ፣ የባንክ ብድርና የታሪፍ ከለላ እንደሚሰጥ ታቅዷል:: በፕላኑ እንዲቋቋሙ የተጠቆሙት ፋብሪካዎች አስፈላጊው ጥሬ እቃ አገር ውስጥ የሚመረት፣ ገበያው የታወቀና የተረጋገጠ፣ ዕቃዎቹን ከውጭ ወደ ሀገር በመግባት የታወቁ፣ መጠናቸው አነስተኛና መካከለኛ፣ አሰራራቸው (ቴክኖሎጂው) ቀላል ስለሆኑ ለማቋቋም አስቸጋሪ አይሆኑም የሚል ግምት ነበር::

በዚህም መሠረት ለፋብሪካ ግንባታ ከያዘው የኢንቨስትመንት ወጭ ውስጥ 65% ከሐገር ውስጥ፣ ቀሪው 35% ከውጪ የግል ኢንቨስትመንት እንደሚገኝ ታሳቢ ተደርጐ ነበር:: ፋብሪካ ለማቋቋም ከበጀት የተያዘው ብር 13.1 ሚሊዮን ብቻ ነበር:: (ብር 6 ማሊዮን ከመንግስት ካዝና ወጪ የሚሆን ሲሆን 7.1 ሚሊዮን ከጦር ካሣ የሚገኝ ነው::)

**ሠንጠረዥ 2:- የፋብሪካ የኢንቨስትመንት ወጪ አመዳደብ**

| | በሚሊዮን ብር |
|---|---|
| ለጨርቃ ጨርቅ | **20.3** |
| ለምግብ ማዘጋጃ ፋብሪካ | **20.3** |
| ለቆዳና ጫማ | **2.5** |
| ለእንጨት ማዘጋጃና የህንጻ ዕቃ | **3.7** |
| ለብረታብረት ፋብሪካ | **2.6** |
| ለሌሎች (ኬሚካል፣ ሕትመት፣ እደጥበብ፣ ወዘተ...) | **7.0** |
| ለጥናትና ምርምር | **1.0** |
| ድምር | **57.4** |

በፋብሪካው ግንባታ ከፍተኛውን የኢንቨስትመንት ወጪ የያዙት ጨርቃጨርቅና ምግብ ማዘጋጃ ፋብሪካዎች ናቸው (72%):: የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ መቋቋም የጥጥ ፍላጎትን ከፍ ስለሚያደርግ፣ ጥጥ በአገር ውስጥ እንዲመረት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል የሚል ዕቅድ ነበር::

በምግብ ፋብሪካ በኩል ከሚደረገው ኢንቨስትመንት፣ 70% የሚወጣው ለስኳር ፋብሪካ ማስፋፊያ ይሆናል፤ ይህም የሐገር ውስጥ የስኳር አቅርቦትን ከ16 ሺህ

ቶን በፕላኑ መጨረሻ ወደ 36 ሺህ ቶን ያደርሰዋል ተብሎ ተገምቷል፡፡ ሌሎቹ ፋብሪካዎች የታቀዱት፣ ምርቶቻቸው ከውጭ የሚገቡትን የፍጆታ እቃዎች እንዲተኩ ነበር፡፡ ይህም Important substitution ስትራተጂ የሚባለው ነው፡፡

በዚህ የፋብሪካ የልማት ዕቅድ፣ የሀገር ውስጥ ፋብሪካ ውጤት በ1947 ዓ.ም ከነበረው ብር 61.7 ሚሊዮን በፕላን መጨረሻ ወደ ብር 175.5 ሚሊዮን ያድጋል ተብሎ ተይዟል፡፡ የፕላን ፋብሪካ ውጤት ግብ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፤ ጨርቃ ጨርቅ ከ3.5 ሚሊዮን ካሬ ሜትር ወደ 21 ሚሊዮን ካሬ ሜትር፣ ቆዳ ከ 860 ቶን ወደ 2,150 ቶን፣ ጫማ ከ80,000 ወደ 300,000፣ ስኳር ከ15,000 ወደ 35,000 ቶን (በ1962)፣ ለማድረስ ታቅዶ ነበር፡፡ በዚህ የፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ የሠራተኛውን ቁጥር በ1947 ዓ.ም ከነበረው 18,000 ወደ 28,000 ከፍ እንደሚያደርገው ተገምቷል፡፡

### ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን

የትራንስፖርትና ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ከፍላጐቱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ወደኋላ የቀረ ስለሆነ ለማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት መሰናክል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ለክፍለ ኢኮኖሚው ቅድሚያ ተሰጥቷል፡፡ ከጠቅላላው የአምስት ዓመት ኢንቨስትመንት ወጪ፣ 45% ለዚሁ ክፍል ተመድቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡- የትራንስፖርትና የኮሙኒኬሽን ኢንቨስትመንት ወጪ አመዳደብ**

| ተ.ቁ | | በሚሊዮን ብር |
|---|---|---|
| 1. | ለአዲስ መንገድ ሥራና ለጥገና | 120 |
| 2. | ለተሽከርካሪ መኪና መግዣና ለጥገና መሣሪያ መግዣ | 18.0 |
| 3. | መለዋወጫ | 6.0 |
| 4. | ለባቡር ሐዲድ ኘሮጀክት | 24 |
| 5. | የአሰብ ወደብ ግንባታ | 47.5 |
| 6. | የአየር ትራንስፖርትን ማስፋፊያና ዘመናዊ ለማድረግ | 10.0 |
| 7. | የቴሌኮሙኒኬሽን | 4.5 |
| | ድምር | 230.00 |

ሀ. ለመንገድ ሥራና ጥገና ብር 120 ሚሊዮን ሲመደብ፣ እቅዱ ከ1,500-2 000 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ ለመሥራት ሲሆን፣ የሀገሪቱን የመንገድ ጥገና አገልግሎት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማደራጀትም ነበር፡፡

ለ. ለአሰብ ወደብ የተመደበው፣ የወደቡን የማስተናገድ አቅም በዓመት ከፍ ለማድረግ፣ 12,000 ካሬ ሜትር መጋዘን ለማሰራት፣ 1,000 ሜትር የሚሆን የመርከብ መቀበያ (ማቆሚያ) ለመገንባት ነበር፡፡

ሐ. ለአየር አገልግሎት የተመደበው ብር 45.7 ሚሊዮን ሲሆን፣ ግማሹ አዲስ አይሮፕላን ለመግዛትና ቀሪው የአየር መንገዱን አገልግሎት ለማስፋፋትና ዘመናዊ ለማድረግ፣ የአየር ማረፊያ ሜዳዎችን አሻሽሎ ለመገንባት፣ በየጣቢያው ያሉትን የጥገናና የአይሮፕላን ማስተናገጃ መሣሪያዎች ለማሟላት ነበር፡፡

**መ. ለቴሌኮሙኒኬሽን የተመደበው ብር 10 ሚሊዮን አገልግሎቱን ለማሻሻልና ለማስፋፊያ ነበር::**

**ትምህርት**

**ትምህርት፣ ምንም እንኳን ብልጭታው ከኢጣሊያን ወረራ በፊት ቢታይም፣ በዘመናዊ መልኩ፣ በሥርአት ተደራጅቶ ስርጭቱ ከዋናው ከተማ ወጥቶ፣ በጠቅላይ ግዛቶች የተስፋፋው ከ1933 ዓ.ም በኋላ ነው:: ከመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ዝግጅት ቀደም ብሎ፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ ፕሮግራም መመሪያ ተዘጋጅቶላቸው፣ ሥራ ላይ ከዋሉት አገልግሎቶች ውስጥ፣ ትምህርት የመጀመሪያው ነው:: በ1948 ዓ.ም የነበረው የተማሪዎች ብዛት፣ የክፍል ብዛትና አማካኝ የተማሪ ብዛት እንደሚከተለው ነው:-**

**ሠንጠረዥ 4:- የ1948 የተማሪዎች፣ የክፍልና አማካኝ የተማሪ ብዛት**

| | መለኪያ | የተማሪ ብዛት | የክፍል ብዛት | አማካኝ የተማሪ ቁ. በክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ክፍል | በቁጥር | 44,675 | 732 | 61 |
| 2ኛ ክፍል | | 18,229 | 497 | 36 |
| 3ኛ ክፍል | | 10,736 | - | - |
| 4ኛ ክፍል | | 6,806 | 261 | 26 |
| ከአንደኛ ክ/4ኛ የደረሰው | መቶኛ | - | - | - |
| 5ተኛ | በቁጥር | 4,184 | 185 | 23 |
| 6ተኛ | | 2,845 | 139 | 20 |
| 7ተኛ | | 2,300 | 117 | 19 |
| 8ተኛ | | 1,896 | 94 | 20 |
| ከ5ተኛ ክ/8ተኛ የደረሰ | መቶኛ | - | - | - |
| 9ተኛ | | 1,301 | 42 | 31 |
| 10ተኛ | | 935 | 31 | 30 |
| 11ተኛ | | 494 | 21 | 24 |
| 12ተኛ | | 310 | 20 | 16 |

**የመጀመሪያው አምስት ዓመት ፕላን ሲዘጋጅ የትምህርት አደረጃጀት፣ አንደኛ ደረጃ፣ ከ1 እስከ 4 ክፍል፣ መካከለኛ ደረጃ ከ5-8 ክፍል፣ ሁለተኛ ደረጃ፣ ከ9-12 ክፍል ነበር:: ከዘጠነኛ ክፍል እስከ 12ኛ የሚደርሰው ተማሪ 18% ብቻ ነበር :: በዚህም ምክንያት፣ የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ተማሪ የሚስተናገዱት፣ ካላቸው አቅም በታች ስለሆነ፣ በፕላኑ ዘመን የዝቅተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት እንደሚያስፈልጋቸው ተጠቁሟል:: በፕላኑ የቀረበው መፍትሔ በፕላኑ መጨረሻ ዓመት የአንደኛ ደረጃን ተማሪ ቁጥር 212 200 ማድረስ፣**

*የ8ተኛ ክፍልን የተማሪ ቁጥር ወደ* 3,200 *ማሳደግ፣ እንዲሁም ተመርቆ የሚወጣውን የአስተማሪ ብዛት (በ1954 ዓ.ም) ከ321 ወደ 960 ከፍ ማድረግ ነበር::*

*ይህ እርምጃ፣ በፕላኑ ዘመን የታየውን የቴክኒሺያን እጥረት፣ ለሚቀጥለው ፕላን ያሻሽላል የሚል ተስፋም ተደርጓል:: በዲግሪ የሚመረቀውን የሰው ኃይል አስመልክቶ ከዶክተሮችና ከከፍተኛ መሐንዲሶች በስተቀር የሀገሪቷ ፍላጐት ከሐገር ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች በሚመረቁትና ከውጪ በሚመለሱት እንደሚሸፈን ተመልክቷል::*

**የገጠር ልማት ኘሮግራም**

*በዚህ አርዕስት የታቀደው በውል ያልታወቀ ቢሆንም፣ በመንግሥት በኩል በባለቤትነት የሚመራው ተቋም ገና ያልተቋቋመ ቢሆንም፣ የሕዝብ ተሳትፎና መተባበር ለአጠቃላይ ልማት ምን ያህል ወሳኝ መሆኑን ለማስታወስ የተያዘ ነው:: በገጠርና በትናንሽ ከተማዎች ለሚካሄዱ ሥራዎች ከመንግስት በዕርዳታ መልክ የሚሰጥ ብር 25.0 ሚሊዮን ተመድቧል:: በዚህ የፐላን ጥቆማ መሰረት የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ተቋቋሞ ሥራውን እንዲያስተባብር ተደርጓል:: ክቡር አቶ አካለወርቅ ሐብተወልድ የመጀመሪያው ሚኒስትር ነበሩ::*

*እንደሚታወቀው፣ ወዲያው ታዋቂው የክቡር ዘበኛ አዛዥ፣ በኋላም የልዩ ካቢኔ ኤታ ማዦር ሹም የነበሩት፣ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ሚኒስትር ሆኑ:: የህዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስትር አላማ በብሔራዊ ደረጃ ሲታይ በጣም ከፍ ያለና አንቱ የሚያሰኝ ስራ ነበር::*

*ሚኒስትሩ ግን መስሪያ ቤቱን በሚገባ አደራጅተው፣ ቁልፍ የሆኑ ኤክስፐርቶች አስመጡ:: በማከታተል የኢትዮጵያን ወጣቶች ለትምህርት ወደህንድ ላኩ:: በዚህ ሥራ ከሰለጠኑት ወጣቶች ውስጥ እነ አቶ ሺመልስ አዱኛን፣ አቶ መሰለንና ስዩም ገብረ እግዚአብሄርን (በሁዋላ ዶክተር)፣ አቶ አበራ ምልቶታልን የመሰሉ ነበሩበት:: እስራኤልም ልከው እንዲሰለጥኑ አድርገዋል:: በእንደዚህ ያለ ወኔና እልህ ስራቸውን ሲሰሩ ነው ጄኔራል ሙሉጌታ በጄኔራል መንግሥቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ የተገደሉት*[5]*:: የመስሪያ ቤቱ እቅድ እንደጀመረ ሊያድግ አልቻለም::*

**ፖሊሲና አስተዳደር**

*ፕላኑ ፖሊሲና አስተዳደር በሚለው ክፍል ስለፕላኑ ይዘትና ምንነት ፣ ስለኢኮኖሚክ ፖሊሲ አላማና መሳሪያነት፣ እንዲሁም ስለመንግስት አስተዳደር አመልክቷል:: ፕላኑን ለማስፈፀም የመንግስት አስተዳደር፣ መሻሻልና ቀልጣፋነት ወሳኝ መሆኑን ቢገለፅም፣ ስለሚወሰደው የማሻሻል እርምጃ ፣ ስለሚያስፈልጉት ለውጦችና መሻሻል በፕላኑ አልተመለከተም:: ይሁንና፣*

---

[5] በታህሳስ 1953 *የተሞከረው መፈንቅለ መንግስት ሲከሽፍ፣ መንግስቱና ገርማሜ ንዋይ በጥበቃ ስር ያደረጓቸውን ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች ረሽነው ከቤተ መንግስት ሸሹ፤ ከነዚህም ሰለባዎች አንዱ፣ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ነበሩ::*

ቁልፍ ናቸው በሚባሉ የስራ ክፍሎችና ለፕላኑ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን መሻሻሎችና አዳዲስ ድርጅቶች ጠቁሟል:: ለምሳሌ፣

- በእርሻ ሚኒስቴር ስር ስለሚቋቋመው ኤክስቴንሽን አገልግሎት ወሳኝነት፣
- በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውስጥ ስለሚኖረው የምርምርና የጥናት ክፍል፣
- በስራ ሚኒስቴር ውስጥ ስለሚቋቋመው የውኃ ሀብት ድርጅት (ኤጀንሲ)፣
- ስለእስታቲስቲክ ድርጅት መቋቋም አስፈላጊነት፣
- ስለ መንግስት ሰራተኛ መብትና ግዴታ፣
- ፕላኑን ስራ ላይ ለማዋል ስለሚያስፈልገው መዋቅር፣ በየክፍሉ መሰጠት ስለአለባቸው አገልግሎቶች::

ሌላው ግን በሂደት እየታየ እንደሚሻሻል፣ እንደሚለውጥ ታሳቢ በማድረግ አልፎታል:: የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን በሚታወጅበት ጊዜ የፕላኑ ዝግጅትና የአፈጻጸም መዋቅር አብሮ ለህዝብ ተገልጿል::

## *የመጀመሪያው አምስት ዓመት ፕላን ውጤት*

የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ጊዜ ተፈፅሞ ምን ተሠራ? ምንስ ለሐገር የሚጠቅም ውጤት ተገኘ? በምንልበት ጊዜ ብዙ ነገር ማገናዘብ ይኖርብናል:: ፕላን ሥራ ላይ ማዋል ስንል ምን ማለታችን ነው? ፕላኖች ሁሉ በአንድ መሰረት ላይ ተመርኩዘው ክንዋኔን ይተነብያሉ፤ ከዚያ ትንበያችን ወይም ግምታችን ትክክል ነበር ወይ? ብለን ጠይቀን መመለስ እንችላለን:: ግን ከመጀመሪያው ይህን ትንበያውን ራሱን አስመልክቶ መጠየቅ የሚገባው ሌላም ጉዳይ አለ፤ ሥራ ላይ የሚውል የፕላን ትንበያ ነበር ወይ? ብለን ልንጠይቅም እንችላለን:: ይህ ደግሞ፣ ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት፣ እንደፕላኑ አቀራረጽ፣ አስገዳጅነትና አመልካችነት ፣ እንደመረጃው አስተማማኝነት ይወሰናል:: በቂና አስተማማኝ መረጃ ካለ፣ ፕላኑን እራሱን፣ ውስጣዊ ባህርዩንና የልዩ ልዩ ክፍሎቹን ተዛማጅነት ከመነሻ መፈተሽ ይችላል:: ነገር ግን የተሟላ መረጃ በሌለበት፣ የፕላኑ አስገዳጅነት ባልተረጋገጠበት፣ ስለፕላኑ ስራ ላይ መዋልና አለመዋል ምን መነጋገር ያስፈልጋል ማለት ይቻላል::

ፕላን አዘጋጆች እንደሚሉት፣ «ፕላን አንድን የተገለጸ ፍላጎትን አውቆ በሥራ ላይ የማዋል ሂደት ነው::» ስለዚህ፣ የዚሁ የማስፈጸም ሂደት ከመጀመሪያው፣ በሁለተኛው፣ ከሁለተኛው በሶስተኛው ወዘተ እንዴት ነበር? እየተሳካ ነው ወይ የመጣው? ወይስ አይደለም? በሚል አስተሳሰብ ካልሔድን ውስጡን በአንድ ፕላን ግምገማ አናየውም:: እንዲያውም ተስፋ እንዳያስቆርጠን መጠንቀቅ አለብን::

እኔ፣ በአንድ አጋጣሚ እንዳዳመጥኩት፣ ስለ አዋሽ ሸለቆ ንግግር ሲደረግ፣ ስለልማቱ የነበረው አንዱ ጠንካራ ሀሳብ ልማቱ ለውጭ ሀገር አልሚዎች ይሰጥ የሚል ነበር፤ በእኔ በኩል ደግሞ፣ የአዋሽ ሸለቆ ለኢትዮጵያ ምንም

ተቀናቃኝ የሌለበት (በውሃ አጠቃቀም ማለቴ ነው)፣ አቀማመጡ ማእከላዊ የሆነ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶቹ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ፣ መገናኛ ወዘተ የተመቻቸበት ብቸኛ መልክአምድር ነው። ታድያ ይሄ እንዴት ለውጭ ዓለም ይሰጣል? በማለት ለሚኒስትሩ ያቀረብኩት ማስታወሻ ትዝ ይለኛል። የአዋሽ ሸለቆ ልማት በፍጹም ለውጭ ዜጎች መሰጠት የለበትም፤ እንዲያውም፣ በብቸኝነት ለኢትዮጵያ ልጆች ተመድቦ በወቅቱ የሙያ ክሂሎትም የሀብት ሀይልም ከሌላቸው፣ መንግሥት ተምረው ተመራምረው እስከሚደርሱ መንግስት መጠበቅ አለበት የሚል ሃሣብ ነበር ያቀረብኩት። አሁን አስተሳሰቤ አክራሪ እንደነበር ይሰማኛል።

ዋናው ነገር ልማት በማንኛውም ሁኔታ ከሚቀር ቢጀመር ይጠቅማል። በሂደት የማይሻሻል፣ የማይለወጥ ነገር የለም። ስለአዋሽ ሸለቆ ልማት በጊዜው ለሀሳቡ ደጋፊ ባላገኝም፣ በሂደት ግን ወደ ሸለቆው ልማት ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዲገቡ ግፊት ተደርጓል። የውጪ ኢንቨስተሮችም ገብተዋል። በመንግስት በኩልም፣ የዚያን አካባቢ አርብቶ አደር ሕዝብ ወደ ቀዋሚ እርሻ እንዲገባ ለማበረታታት፣ ልዩ የሙከራ ፕሮጀክት በአዋሽ ሸለቆ ባለስልጣን ተቀርጾ ስራ ላይ ውሏል። ለአንድ አርብቶ አደር አባ ወራ 4 ሄክታር ውሃ ገብ መሬት በዘመናዊ እርሻ እንዲያርስ፣ የሚያስፈልገው ሁሉ ድጋፍ፣ ከልማት ወጪ ጀምሮ ሥራውን እስከማካሄድ ድረስ በባለስልጣኑ ሀላፊነት ተዘጋጅቶ እየታረሰ፣ ትርፉ ለተመረጠው አርብቶ አደር ይሰጥ ነበር። ቀስ በቀስ አርብቶ አደሩ ከተመልካችነት ወደ ተሳታፊነት እየተለወጠ መጥቶ ነበር። ስለዚህ በሂደት ሁሉ ነገር ይለወጣል፤ ይሻሻላል።

በአለፈው 30-40 ዓመት (በእኛ እድሜ) እንኳ ብዙ ነገር አይተናል፣ አሳልፈናል። በሸለቆው በልማት የተሰማሩት ሁሉም (የሀገሩም፣ የውጭውም ኢንቨስተሮች) በደርግ መዳፍ ተጨፍልቀዋል። ሸለቆውም የመንግስት ንብረት ሆነ ተብሏል። ይህ እራሱ ያኔ ያላየሁት አንድ የሂደት ለውጥ ነው።

ስለዚህ ስለፕላን ሥራ ላይ መዋል ስንነጋገር፣ የፕላኑን ይዘትና በዝግጅቱ ላይ ያለውን ችግር ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን በተጨባጭ ባየናቸው፣ በተወሰዱና ባልተወሰዱ እርምጃዎችና ጥረቶች፣ የፕላኑን ዋና ዋና ፕሮግራሞች ሥራ ላይ ውለዋል አልዋሉም ለማለት ይቻል ይመስለኛል።

በዚህም መሰረት፣ የመጀመሪያው የአምስት አመት ፕላን ጉልህ ውጤቶችን በማነጻጸር ለመግለጽ እሞክራለሁ።

በአጠቃላይ ሲታይ፣ ውጤቱ ከፍ ያለ የፕላን አፈጻጸምን ያመለክታል:: ለኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ተብሎ በፕላኑ የተመለከተው በ24 ከፍ ብሎ ወጥቷል:: ይደረስበታል ተብሎ የታቀደው 3.7 እድገት 3.2 መድረሱ ተገምቷል:: የውጪ ንግዱ እድገት በኘላኑ እንደተተነበየው ነው:: እንዲሁም የማዕከላዊ መንግስት ገቢ በሐገር ውስጥ በብር 14 ሚሊዮን ከታቀደው በላይ ሆኖ ተገኝቷል::

የኢንቨስትመንት ወጪ በሁሉም ክፍል (ከሶሽያል አገልግሎት በስተቀር) የወጣው ከዕቅድ በላይ ነው:: በሚከተለው ሠንጠረዥ እንደተመከተው፣ ከፕላን በተጨማሪ፣ ኢንቨስትመንት የተደረገው በቤት ሥራ፣ በትራንስፖርትና በመገናኛ ነው:: በነዚህ ክፍሎች የተደረገው ወጪ ለውጤት እድገት በቀጥታ ስለማይረዳ የብሔራዊ ገቢ ቅነሳ አንዱ ምክንያት ነበር:: የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮግራም በዕቅዱ መሠረት ተፈጽሟል:: ለማዕድን የወጣው ከዕቅዱ ከፍ ቢልም ፍለጋውና አሰሳው ውጤት አላስገኘም:: የፋብሪካ ኢንቨስትመንት ከዕቅድ በላይ ቢሆንም የታሰበው የውጤት ዕቅድ ገቢ በ33 ዝቅ ብሏል:: ፋብሪካዎች ተሰርተዋል፤ ይሁን እንጅ ውጤታቸው ገና አልታየም:: ለዚህ ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያውያን ኢንተርፕርነርስ ያላቸውን ገንዘብ የፋብሪካ መስሪያ ቤት ላይ ማዋልን መርጠዋል:: ይህ የኢንቨስትመንት ወጪ የሚያመለክተን ገንዘብ ቢኖረንም፣ ያለን አስተያየትና ዝግጅት አነስተኛ ስለሆነ፣ የፋብሪካ ግንባታ ከሚያስገኘው ጥቅም ተካፋይ ሳንሆን ቀርተናል::

ሰንጠረዥ 5:- የኢንቨስትመንት ወጪ

| ተ.ቁ | የሥራ ክፍል | ፕላን | የተደረሰበት | ማመዛዘኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እርሻና ደን | 92.1 | 109.9 | 120 |
| 2 | ማዕድን ኃይልና ኢንዱስትሪ | 138.0 | 159.8 | 111 |
| 3 | ትራንስፖርትና መገናኛ | 240.0 | 287.3 | 120 |
| 4 | ሶሺያል አገልግሎት | 57.0 | 39.0 | 68 |
| 5 | መኖሪያ ቤት | 122.5 | 206.8 | 169 |
| 6 | ሌሎች | 24.0 | 36.8 | 153 |

በማስተባበር በኩል የታየው አርኪ አይደለም:: የማኔጀሮች እጥረት፣ የልማት አስተናጋጅ ድርጅቶች አለመቋቋም፣ ፍጻሜውን አዘግይቷል:: በሚቀጥለው ፕላን ዘመን በሁሉም ክፍል፣ (አስተዳደሩ፣ የእርሻውና የንግዱ ክፍል... ወዘተ).. ለተሻለ አፈጻጸም የተሻለ የተዘጋጁ ይሆናሉ የሚል ተስፋ ነበር::

በትምህርት በኩል፣ ተፈላጊው ድጋፍና የሰለጠነ የሰው ሀይል ቢኖረንኑሮ፣ በዚህ በአንደኛው ፕላን ጊዜ ከታየው የተሻለ ውጤት እንደምናሳይ ጥርጥር የለውም:: ይህ የተማረ የሰው ሀይል እጥረት በዚያን ጊዜ በሁሉም የመንግስት አስተዳደር ውስጥ ጐልቶ የሚታይ ነበር:: የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በጀት ለተፈቀደላቸው ቦታ እንኳን ሰራተኛ መቅጠር አስቸጋሪ ነበር:: ተመራቂዎች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ የሚመጡት ብዙ አማራጭ ስለነበራቸው የሚቀጠሩት በምርጫቸው ነው:: የመንግሥት መስሪያ ቤቶች

ጠቅላላ አደረጃጀታቸውንና ሥራቸውን ያላሻሻሉት በከፍተኛ ደረጃ ሰራተኞች ለመቅጠር ያስቸግራቸው ነበር፡፡ እኔ ከተማሪ ቤት (ከውጪ) ስመጣ ለመግባት የፈለግሁት ገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ልማት ባንክ ነበር፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴር ሥራ ስጀምር ደግሞ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር መግባት የፈለግሁት ከከተማ ውጪ የአንድ ጠቅላይ ግዛት የፋይናንስ ሀላፊ ሆኜ ለመስራት ነበር፡፡ ይህ ፍላጐቴ እራሱ ጥያቄ አስነሳ፤ ለምን ፈለገ ተባለ፡፡ ከዚያ ሁለተኛ ምርጫዬ ልማት ባንክ ስለነበር፣ የባንኩን ማኔጀር ሙሴ አቤል የተባሉትን ቀጠሮ ይዤ ሳነጋግራቸው ማንነቴንና ትምህርቴን ካረጋገጡ በኋላ ለመቅጠር ደስ ስላላቸው እሱንም ተውኩት፡፡ ከዚያ በኋላ ሳጠያይቅ የፕላን ጽህፈት ቤት እንዳለ ሲነገረኝ ስለ መንግስትና ስለ ሐገሪቱ ፋይናንስ አጠቃላይ ግንዛቤ አገኝበታለሁ በማለት ወደ ጽህፈት ቤቱ ሄጄ ለመቀጠር በቃሁ፡፡ ስለዚህ የአገሪቱን የፋይናንስ አጠቃላይ እንቅስቃሴ የመመልከት እድል አገኘሁ፡፡ ምርጫ ነበረኝ፣ እማልፈልግበት እንጂ የምፈልግበት ቦታ አልተቀጠርኩም፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ዋና ዋና ግቦች**

| ተ.ቁ | | ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት | መለኪያ በሺ | 1947 | 1949 | 1954 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | ከዚህ ከእርሻ ውጤት | በሺ | | | 2,100 |
| 2. | | ጠቅላላ ብሔራዊ ገቢ | በሚሊዮን ብር | 1,686 | 1,801 | 2,841 |
| 3. | | ጠቅላላ የእርሻ ውጤት ገቢ | በሚሊዮን ብር | 1,294 | | 1,495 |
| 4. | | ጠቅላላ ኢንዱስትሪው | በሚሊዮን ብር | 125 | 280 | 588 |
| 5. | | አማካኝ አመታዊ እድገት | በመቶኛ | 2.0-2.5 | | 3.7 |
| 6. | | የፋብሪካ ጥሬ እቃ | | | | |
| | 6.1 | ጥጥ | በመቶኛ | 1,300 | 2,200 | 5,800 |
| | 6.2 | ሸንኮራ አገዳ | በመቶኛ | 62,500 | 62,500 | 112,500 |
| | 6.3 | ሌሎች ሰብሎች | በመቶኛ | 282,900 | 275,300 | 316,400 |
| | 6.4 | ሥጋ የታረደ | በመቶኛ | 497,000 | 526,00 | 601,000 |
| 7. | | የውጭ ንግድ | በሚሊዮን ብር | 154 | 182 | 228 |
| | 7.1 | ቡና | በሚሊዮን ብር | 85 | 110 | 143 |
| | 7.2 | የዘይት እህልና ውጤታቸው | በሚሊዮን ብር | 16 | 15 | 16 |
| | 7.3 | የበግና የፍየል ቆዳ | በሚሊዮን ብር | 15 | 17 | 20 |

**ሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን**

***ዝግጅት***

የሁለተኛው አምስት ዓመት ፕላን የተዘጋጀው እንደመጀመሪያው በዩጐዝላቭ ኢክስፐርቶች እርዳታ ነው፡፡ በፕላኒንግ ቦርድ ጽህፈት ቤት ውስጥ በየዋና ዋና ክፍሉ (በእርሻ፣ በማዕድን፣ በኢንዱስትሪ፣ ወዘተ) የዩጐዝላቭ

ኤክስፐርቶች ስለነበሩ፣ ከየክፍሉ ሠራተኞች ኤክስፐርቶች ጋር የየመሥሪያ ቤቱን አቅድ አዘጋጁ:: ከዚያ በፕላኒንግ ጽህፈት ቤት በየዘርፉ ፕላን ይነድፉና ፕላኑን ለማዋሀድና አጠቃላይ ግቡን ለመወሰን ከፍተኛ የፕላን ኤክስፐርቶች መጥተው ረቂቅ ፕላኑን አንድ ጋር ካዋሃዱ በሁዋላ ለፕላኒግ ቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርበዋል::

የሁለተኛው ፕላን የተዘጋጀው በዚህ ዓይነት ሲሆን፣ ከመጀመሪያው ፕላን የሚለየው የሚኒስቴርና የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዝግጅቱ በቀጥታ ተካፋይ መሆናቸው ነው::

### የ20 ዓመት መሪ ፕላን

ሌላው የሁለተኛው ፕላን ከመጀመሪያ የሚለየው «የረጅም ጊዜ የኤኮኖሚ ልማት» የሚል ርዕስ ታክሎበት የ20 ዓመት የኢኮኖሚ እድገት ትንበያ (Projection) መካተቱ ነው:: በዚህ ትንበያ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት በመጀመሪያው ፕላን መጨረሻ ከተደረሰበት 3.4 %፣ በአምስተኛው ፕላን አማካኝ እድገቱ 5.8 % ይደርሳል የሚል ነበር::

በዚህም መሠረት ያጠቃላይ የሀገር ውስጥ ውጤት (GDP) ከተደረሰበት ብር 2,130 ሚሊዮን በአምስተኛው ፕላን ብር 5,650 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተመልክቷል:: የዚህ ትንበያ የዋና ዋና ኢኮኖሚ ዘርፍ ውጤት በሰንጠረዥ ተመልክቷል:: በዚህ ትንበያ የአምስት አመት የልማት ውጤት በመጀመሪያው ዓምስት ዓመት ከወጣው ብር 8,39 ሚሊዮን በአምስተኛው ፕላን ብር 5,039 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተመልክቷል:: በተጨማሪም፣ ይህ እቅድ ግቡን ከመታ ኢትዮጵያ ከውጪ ሀገር የሚያስፈልጋት ዕርዳታ እየቀነሰ ይሄዳል የሚል የምስራችም ይዟል:: ዛሬ ይህ ጊዜ ካለፈ 24 ዓመቱ ነው::

### የሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ግቦች

የሁለተኛው የአምስት አመት ፕላን ቅድሚያ የሰጠው ለእርሻ ሲሆን፣ አጠቃላይ ግቡ በመጀመሪያው ፕላን ከተመለከተው ብዙ የተለያየ አይደለም:: በእርሻው ዘርፍ የገበሬውን ምርታማነት አሳድጐ፣ ለተጨማሪው ህዝብ ምግብ፣ የኢንዱስትሪ ተጨማሪ ጥሬ ዕቃ እና ወደ ውጪ የሚላኩ የእርሻ ውጤቶች ማሳደግ የሚል ነው:: እንዲሁም ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፓርትና መገናኛ በተመሳሳይ መልኩ የመጀመሪያውን የአምስት አመት ፕላን ግቦች ተመርኩዞ የወጣ ስለሆነ እንደገና አልገልጸውም::

በትምህርት በኩል በ1959 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ቁጥር 331,000 ለማድረስ፣ የሁለተኛ ደረጃ 40,500፣ የልዩ ልዩ የሙያ ትምህርት ቤቶችን ምሩቆች (ቴክኒሺያኖች) 11,679 ለማድረግ፣ የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች፣ ደግሞ በፕላኑ ዘመን የሚያስፈልጉትን 1,839 ለማድረስ ታቅዶ ነበር:: የመደበኛ የሆስፒታል አልጋ ቁጥር 9,700፣ የስጋ ደዌ 6,250፣ በ1959 ለማድረግ ታቅዷል:: የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል የወባ ማጥፋት ፕሮቪዥን ተቀባይ በ1959 ዓ.ም በወባ ጥበቃ አካባቢ ሽፋኑን በዘዴ ለማድረስ ታስቦ ነበር። በዚያን ጊዜ በወባ የሚጠቃው ሕዝብ ብዛት 10 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል:: ይህ

*የወባ ማጥፊያ ፕሮግራም የተጀመረው በአሜሪካን እርዳታ ሲሆን የእርዳታው መጠን በመጀመሪያ ዓመታት ከፍ ብሎ በያመቱ እየተቀነሰ የኢትዮጵያ መንግሥት በ1964 ገደማ ወጪውን ሙሉ በሙሉ እንደሚሸፍን ስምምነት ተደርጐ ነበር፡፡*

*ሌላው በዋናነት የተመለከተው፣ በአስተዳደር ቅልጥፍና ማነስና በልማት መዋቅሮች አለመስተካከል ምክንያት በመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን አፈጻጸም ላይ የደረሱት በሁለተኛው ፕላን የሚከተሉት እርምጃዎች መሰናክሎችን ለማስወገድ እንዲወሰዱ ታቅዷል፡፡*

*ሀ. ፕላኑን ለማስፈጸም፣ ለመከታተልና ዝርዝር ፕላኖች ለማዘጋጀት በየልማት ሚኒስትሮች ውስጥ የልማትና የእስታትስቲክስ ክፍሎች እንዲቋቋሙ፣*

*ለ. የፕሮዳክቶች ጥናቶች አቀራረብ ግምገማ በቂ ስላልሆነ ይህን የሚያከናውን የቴክኒካልና የእርሻ ኤጀንሲ እንዲቋቋም፣*

*ሐ. የገንዘብ ቁጥጥር ስርጭትና ብድርን በተመለከተ የኢትዮጵያ ባንክ በሁለት ተከፍሎ ብሔራዊ ባንክ እና የንግድ ባንክ ተብሎ እንዲቋቋምና በተጨማሪ ለአነስተኛና ለመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ የሚሰጥ የኢንቨስትመንት ባንክ እንዲቋቋም፣*

*መ. ልማቱን ለማስተባበርና ለማስተዋወቅ በየጠቅላይ ግዛቱ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት እና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሪ የኢንዱስትሪ (ፋብሪካ) አስተዋዋቂ ቢሮ እንዲቋቋም፣*

*ሠ. የልማቱን ሥራ እና የመንግሥት አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግና ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ አዳዲስ የመንግሥት ድርጅቶች (እንደ መብራት ኃይልና ቴሌኮሚኒኬሽን ወዘተ የሚባሉ) እንዲቋቋሙ፣ እንዲሁም የገጠር መንገድ፣ ትምህርትና የጤና አገልግሎቶች የማቅረብ ኃላፊነት ለጠቅላይ ግዛቶች እንዲሰጥ፣*

*ረ. የኤኮኖሚውን እንቅስቃሴ ለመደገፍና ወደፊት ለማራመድ፣ የተለያዩ ህጐች እንዲወጡ፣ የአሰሪና የሠራተኛን ግንኙነት የሚደነግግ ህግ እንዲታወጅ፣ እንዲሁም፣ የመንግሥት ሰራተኛን መብትና ግዴታ የሚያብራራና የሚደነግግ ህግ እንዲወጣ፣*

*ሠ. የፕላኑን አፈጻጸም፣ በሚገባ ለመከታተል፣ ለማስፈጸምና ለመስራት የፕላን መዋቅሩን ማሻሻልና ቀልጣፋ ማድረግ፣ አሁን ባለው የፕላን መዋቅር አጠቃላይ እንቅስቃሴውን የሚከታተሉ በስድስቱ የፕላን ኮሚቴዎች፣ የኢንቨስትመንት፣ የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የመሬት ይዞታና የሕግ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ተመልክቷል፡፡*

*የሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ግቦች ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ የአፋጻጸሙም መዋቅሮች ጊዜውና ሁኔታው እየታየ መሻሻል እንዲደረግባቸው ማስፈለጉ ተመልክቷል፡፡*

**የሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ውጤት፣**

በጠቅላላው የሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን አፈጻጸም ሲታይ፣ ጽንሰ ሀሳቡን ሆነ ጥቅሙንና አስፈላጊነቱን በሚመለከት የመንግስት ባለሥልጣኑም፣ ሠራተኛውም፣ ሕዝቡም ከመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን የተሻለ ግንዛቤ ነበረው:: መሥሪያ ቤቶች በየዓመቱ በጀት ሲጠይቁ እቅዱ በአምስቱ ዓመት ፕላን የተመለከተ መሆኑን በመጥቀስ ማስፈጸሚያ መጠየቅ ጀመሩ:: እንዲሁም ሕግ ሲረቀቅ፣ መግቢያው ውስጥ በአምስት ዓመት ፕላን ውስጥ የተመለከተ መሆኑ በምስክርነት ይጠቀስ ጀመረ::

የፕላኑን አፈጻጸምና የውጤቱን አሐዝ ስንመለከት የሐገር ውስጥ የሥራ ውጤት (GDP) በፕላኑ ከተመለከተው በብር 950 ሚሊዮን ከፍ ያለ ነበር:: አማካኝ እድገቱም በፕላን ከተመለከተው 4.3% 4.6% መድረሱ ተመልክቷል:: በልማት ወጪ በኩል፣ በጠቅላላው በአምስቱ ዓመት ይወጣል ተብሎ ከተተመነው ብር 233 ሚሊዮን ከፍ ብሎ ወጥቷል:: የልማቱ ወጪ በእርሻና በሶሺያል አገልግሎት፣ በተከታታይ 41% እና 51% ብቻ ሲፈጸም፣ በሌሎቹ ክፍላተ ኢኮኖሚ ከፍ ባለ መቶኛ ከፕላኑ በላይ ወጪ ሆኑዋል:: በተለይ ለመኖርያ ቤት ግንባታ የወጣው በፕላን ከተመለከተው 87% ከፍ ያለ ነበር::

የእያንዳንዱ ዘርፍ የሥራ ውጤት፣ በተለይ በፋብሪካ እየተፈበረኩ የተመረቱትን ዕቃዎች እድገት ስናይ፣ ከፍ ያለ ቢሆንም በፕላን ከታቀደው የተዛባ ነው:: ለምሳሌ የኤክስፓርት ፋብሪካዎች ውጤት ከፕላን ከታቀደው በጣም ዝቅ ያለ ሲሆን በፕላን የታሰቡት ፋብሪካዎች አልተቋቋሙም፤ ለፋብሪካዎች አስፈላጊው ጥሪ እቃ እንደታሰበው ከሐገር ውስጥ ሳይሆን የመጣው ከውጪ ነበር::

ከማዕድን ዘርፉ ይገኛሉ ተብሎ የታቀዱትና የፋብሪካ ጥሬ እቃ ይሆናሉ ወይም ወደ ውጪ ይላካሉ የተባሉ ማዕድኖች ሳይወጡ፣ ሳይስፋፉ ቀርተዋል:: በዚህም ምክንያት የማዕድን ዘርፍ ውጤት አፈጻጸም በጣም ዝቅ ያለ ነበር:: በዋነኛነት ታቅዶ የነበረው የፖታሽ ምርት (1,050,000 ቶን) ፋብሪካው ስላልተቋቋመ ሳይገኝ ቀርቷል:: ስለሆነም ለማዕድን አሰሳና ፍለጋ የወጣው ገንዘብ ከእቅድ በላይ ነበር::

በትምህርት ዘርፍ በአንደኛ፣ በሁለተኛና በከፍተኛ ትምህርት ቤቶች የተመዘገበው የተማሪው ብዛት ከዕቅድ በላይ ቢሆንም፣ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጥራቱ፣ ይዘቱና ስርጭቱ (በከተማና በገጠር) ፣ እንዲሁም የአስተማሪው ብቃት ዝቅተኛ መሆኑ ተገልጿል:: በዚህም ምክንያት ብዙ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ:: ለምሳሌ ከአንደኛ ክፍል ወደ ሁለተኛ ክፍል የሚዘዋወሩት 45 % ብቻ ነበሩ:: በገጠር ብዙ ክፍሎች በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር በጣም ከፍ ያለ ነበር:: በሁለተኛ ደረጃ የተማሪው ብዛት ከዕቅዱ በጣም ከፍ ያለ ሲሆን ውጤቱ ግን ዝቅ ያለ ነበር:: በቂ ተማሪዎች በ12ተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ላይ ለመቀመጥ አይደርሱም ነበር:: ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች በቂ ተማሪዎች ባለማግኘታቸው ያላቸውን መሳሪያ፣ ቋሚ ንብረትና ድርጅት በአግባቡ መጠቀም አልቻሉም::

በልማት አስተዳደር፣ በመዋቅር ማሻሻል፣ ማስተባበርና አመራር ዘርፍ በሁለተኛው ፕላን የተመለከቱት አብዛኛዎቹ ቢቋቋሙም፣ ለማስፈጸም በቂ ድጋፍ አልሰጡም፤ ለማስፈጸሙ በቂ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲቋቋሙ ከተባለው ውስጥ የፕላንና እስታትስቲክስ ክፍል ይገኙበታል፤ የፕሮጀክት ጥናት ቴክኒካል ኤጀንሲ ተቋቁሟል፤ በገንዘብ ቁጥጥር፣ ስርጭትና ብድር በኩል የብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንክ፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ባንክ እራሳቸውን ችለው ተቋቁመዋል፤ የሠራተኛና የአሰሪ አዋጅ መጥቷል፤ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ ኮሚሽን አዋጅ ወጥቶ መስሪያ ቤቱ ተቋቁመዋል፤ የፕላን መዋቅሩ ጽህፈት ቤት የሁለተኛው ፕላን አጋማሽ ላይ ወደ ሚንስቴር ደረጃ ከፍ ብሎ የማስተባበሩን፣ የመምራቱን፣ የዝግጅቱን እና የማስፈጸሙን ሥራ ከሌሎች የልማት መሥሪያ ቤቶች ጐን በአቻነት እንዲመራ ተደርጓል:: በአጠቃላይ፣ የሁለተኛውን የአምስት አመት ፕላን አፈጻጸም ስንመለከት የተገኘው እድገትና መሻሻል ምን ያህሉ የፕላኑ ቀጥተኛ ውጤት ናቸው ብሎ መመዘን ያስቸግራል:: ሆኖም፣ ፕላኑ ብዙውን ግንዛቤ፣ ፍላጐትና ለልማት ተነሳሺነትን ፈጥሯል፤ በተለይ በመንግሥት የልማት ሚኒስትሮችና መስሪያ ቤቶች ግንዛቤ ፈጥሯል:: ፕላን ባይኖረን የተደረሰበት የልማት ውጤት፣ የተደረገው መሻሻል ይኖር ነበር ማለት አይቻልም::

**ሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን**

***ዝግጅት፤***

የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ዝግጅት ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ፕላኖች በጣም የተለየ ነበር:: የሶስተኛው ፕላን ሲዘጋጅ የየመሥሪያ ቤቱ ደረጃና አቋዋም የተሻለ ነበር:: የመጀመሪያውና የሁለተኛው ፕላን ሲዘጋጅ የፕላኒንግ ቦርድ ጽሕፈት ቤትን የመራው በረዳት ሚኒስቴር ደረጃ የነበረ ያልታወቀና ያልተሞከረ ወጣት ነበር:: በዚህም ምክንያት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችንና የኤጀንሲ ኃላፊዎችን ለማስተባበር ችግር ነበር:: በዚህ ላይ፣ ስለፕላኖቹ ግንዛቤ የነበራቸው ከፍተኛ ባለስልጣኖች ናቸው:: በመሀከለኛና ከዚያ በታች የነበሩ ሠራተኞች ፕላኑ ከሥራቸው ጋር የነበረውን ትስስርና አስፈላጊነት በሚገባ የተገነዘቡት አይመስሉም ነበር::

የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ዝግጅትና አመራር የተከናወነው የፕላን መስሪያ ቤት ወደ ሚኒስቴር ደረጃ ከፍ ብሎ የታወቁ ሚኒስቴር በመሾም ነበር:: በየመስሪያ ቤቱም፣ የፕላንና የእስታቲስቲክስ ክፍል በሚኒስትሩ ጽህፈት ቤት ስር እንዲቋቋም በመደረጉ የፕላን ክፍል ሀላፊው ከሠራተኛው ሙሉ ትብብርና ተስማሚነት እንዲኖረው አድርጓል:: የመስሪያ ቤቱንም ፕላንና ፕ ሮግራም አስተባብረውና አዘጋጅተው ማቅረብ ችለዋል::

የክፍላተ ሀገር ፕላንና ፕሮግራም በሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር አስተባባሪነት፣ የግል ድርጅቶችና ነጋዴዎች ደግሞ በነጋዴዎች ምክር ቤት አማካኝነት፣ በዝግጅቱ ተካፋይ ሆነዋል:: ከየመሥሪያ ቤቱና ከመንግሥትና ከግል ድርጅቶች ተዘጋጅቶ የሚላከው ፕላንና ፕሮግራም ወደ ፕላን ሚኒስቴር

እየተላከ በሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የኘላን ሚኒስትሮች አባል ለሆኑበት የፕላን ኮሚቴ ቀርቦ ውይይት ተደርጐበት የዘርፍ ፕሮግራም ይዘጋጃል፡፡

አብዛኞቹ፣ ለፕላን መስሪያ ቤት የሚቀርቡት፣ የየመስሪያ ቤቱ ፕላኖችና ፕሮግራሞች በፕላን ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በተላከው የፕላን ዝግጅት መመሪያ መሠረት ሲሆኑ አልፎ አልፎ አቅራቢዎቹ ባላቸው ልምድ መሠረት የሚቀርቡ በጊዜው የነበረውን የሥራ አፈጻጸም ብሂል የማያንጸባርቁም ነበሩ፡፡ የፕላን ዝግጅት መመሪያው ማንኛውም ለማስፈጸም የሚዋቀር ድርጅት የሚሠራው ሥራ ተለይቶ፣ ውጤቱ ወይም አገልግሎቱ ተሰልቶ መቅረብ አለበት ይባላል፡፡ ለምሳሌ የሚሠራው መንገድ እንደሆነ በኪሎሜትር እና በጊዜ ተለይቶ፣ አገልግሎት ሰጪ ከሆነ የሚሰራው ለስንት ሰው በቀን በሳምንት ተወስኖ እንዲቀርብ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም ከአንድ መስሪያ ቤት የተላከውን አንድ የግንባታ ሥራ የሚሰሩ መሀንዲሶች፣ ቀያሾች፣ ግንበኞች፣ አናጢዎች ያለው ድርጅት ከነሙሉ መሣሪያና ተሽከርካሪ ጋር አንድ ጊዜ ቀርቦ ስለነበር የመስሪያ ቤቱን ሀላፊ ጠርተን ፕሮዤው የሚሠራው ሥራ ግንባታው የት አለ ብለን ስንጠይቅ «አይ የናንተ ነገር!! እሱንማ እኔ የት አውቀዋለሁ! ይህን ድርጅት ያዋቀሩት ንጉሠ ነገሥቱ ጠርተው እንደዚህ ያለ ግንባታ (ድልድይ፣ ቤት፣ ከተማ፣ ወዘተ...) ሥራ ስባል ያንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም የሚያስችል ድርጅት ነው ያቀረብኩት» አለን፡፡

ይህ የዘርፉ የተወሰነው ፕሮግራም በፕላን ሚኒስቴር ኢክስፐርቶችና በዓለም ባንክ አማካኝነት ተቀጥረው በመጡ ከፍተኛ ኢክስፐርቶች አስተባባሪነት የኘላኑ ውስጣዊ ውህደት ተጠብቆ የየዘርፉ ግቦችና እድገቱ ተወስኖ ረቂቅ ኘላኑ ይዘጋጃል፡፡ ይህም በየደረጃው ከኘላን ኮሚቴ እስከ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮበት ተሻሽሎና ተስተካክሎ እንዲፀድቅ ሆኑዋል፡፡ የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ካለፉት ሁለት ፕላኖች በተሻለ ዝግጅት ከታች ወደላይ የመጣ መስሪያ ቤቱ በልዩ ልዩ ደረጃ ባሉ ሠራተኞች የተሻለ ዕውቀትና ግንዛቤ የነበረው የፕላን ዝግጅት ነበር፡፡

**የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ግቦች**

የሶስተኛው የአምስት ዓመት ግቦችና አላማዎች በአሀዝ ሲተረጐሙ ምን እንደሚመስሉ አጠቃላይ ስዕል መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ጠቅላላ የሥራ ውጤት (GDP) ከ1960 ዓ.ም ከነበረው ብር 3,575 ሚሊዮን በ1965 ዓ.ም ብር 4,779 ሚሊዮን እንዲደርስ፣ አማካኝ የአምስት ዓመት እድገት ራእይ የሆነ የነፍስ ወከፍ ገቢው በ1965 ዓ.ም ብር 181.0 እንዲደርስ፣ ተመልክቷል፡፡ የወደፊት እድገቱን አስተማማኝ የሚያደርገው ከእርሻው ዘርፍ የሚገኘው የተፋጠነ እድገት መሆኑ ታምኖበታል፤ አጠቃላይ የእርሻ ውጤት ዕድገት የ3 % ዕድገት፣ ገንዘብ ነክ የሆነው 5-7%፣ ገንዘብ ነክ ያልሆነው፣ ገበሬው ለራሱ የሚያመርተው የእርሻ ውጤት 1.8% እድገት ሲኖረው ነው፡፡ በሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ ከ10% በላይ የሆነ እድገት (በኢንዱስትሪ 15.8% ትራንስፓርት ንግድ ወዘተ... 16.5%) እንደሚያስመዘግቡ በማሰብ ነው፡፡

*በሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን፣ የእርሻው ፕሮግራም ግልጽ የሆነ የአትኩሮት ለውጥ አድርጓል፡፡ ከአነስተኛ ገበሬው ከእጅ ወደ አፍ እርሻ ይልቅ በትላልቅና ዘመናዊ እርሻ ላይ እንዲተኮር ታቅዷል፡፡ ለምሳሌ የእርሻን የልማት ወጪ አመዳደብ ስንመለከት ለእርሻ ከተመደበው ብር 312 ሚሊዮን ገንዘብ ነክ ወጪ ብር 209 ሚሊዮን (63%) የተመደበው ለትላልቅ ዘመናዊ እርሻዎች ሲሆን ከፍተኛው ወጪ የተያዘው ብር 864.4 ሚሊዮን (30.2%) ለኢንዱስትሪ ነው፤ ብር 565 ሚሊዮን ለፋብሪካና ለእጅ ጥበብ፣ ብር 179.4 ሚሊዮን ለማዕድን፣ ብር 120 ሚሊዮን ለኤሌክትሪክ ነበር፤ በትምህርት በኩል ግቡ በ1965 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ ተማሪን ቁጥር 616,000 ለማድረስ (18% አንደኛ ደረጃ መግባት ከሚገባቸው ሲሆን ) በጤና በኩል እንደ ሳምባ ነቀርሳ፣ ፈንጣጣ፣ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የመሳሰሉትን በልዩ ፕሮግራም ለመከላከል ነው፡፡ የጤና ጣቢያንና የክሊኒኮችን ቁጥር በእጥፍ ለማሳደግ ታቅዶ ነበር፡፡*

*ወባ፣ ለልማቱ ጥረት ከፍተኛ ጠንቅ ስለሆነና ከ11 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚሆነው የወባ ወረርሽኝ ባለበት አካባቢ ስለሚኖር፣ ልዩ የወባ ማጥፊያ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ከ1959 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ውሏል፤ የኘሮግራሙ አላማ በሚቀጥሉት 12 እስከ 15 ዓመታት የወባ ወረርሺኝን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ነበር፡፡ በሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ውስጥ የወባ ጠንቅ ባለባቸው ሁሉም ቦታዎች የማጥፋት ፕሮግራሙ ይካሄዳል፡፡ በሰሜንና ማዕከላዊ (ሀ) እንዲሁም በማዕከላዊና ምዕራባዊ (ለ) ክፍላተ ሀገር የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ጊዜ ይጀመራል፡፡ ይህ የወባ ማጥፊያ ፕሮግራም ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ፕሮግራሙን ማቋረጥ በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያስከትል በየደረጃው ተገልጾና ታምኖበት የተጀመረ ነው፡፡ ፕሮግራሙም እንዳይቋረጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለመፈጸም መንግሥት በቁርጠኝነት ተቀብሎ፣ ቅድሚያ ሰጥቶ፣ በመፈጸም ላይ ነበር፡፡ እንደተፈራው መንግስት ካቋረጣቸው የጤና ፕሮግራሞች አንዱ የወባ ማጥፊያ ፕሮግራምን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በሕዝቡ ላይ የደረሰው ጉዳትና እልቂት እስካሁን ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ቀጥሏል፡፡*

*ከነዚህ ግቦችና አላማዎች በተጨማሪ በሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን አፈጻጸም ላይ የታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን መፍትሔዎች አስቀምጧል፤ በሁሉም ክፍላተ ኢኮኖሚዎች (የየዓመቱን የመደበኛና የልማት ውጤት ጨምሮ) ዝርዝር ፕሮግራም በፕላኑ ተመልክቷል፡፡ ሁሉንም የተመለከቱትን እቅዶች ማስፈጸም የማን ሀላፊነት እንደሆነ ተለይቶ ዝርዝሩ በፕላኑ ውስጥ "ምድብ ሥራና ሀላፊነት" በሚል ምዕራፍ ስር ተካቷል፡፡ የፕሮግራሙ ጥናትና አፈጻጸም በጊዜ ተለይቶ ማን ምን መቼ መፈጸምና ማቅረብ እንዳለበት ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡ ለምሳሌ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለዩኒቨርስቲ እንዲፈጽሙ ተመልክተው ከነበሩት ኃላፊነቶች አንዳንዶቹን እጠቅሳለሁ፡፡*

**ሰንጠረዥ 7፡- ከትምህርት ሚኒስቴር ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የተሰጡ ስራዎች**

| የሥራ ዓይነት | የሚጀመርበት ጊዜ | የተጠቀሰበት ሥፍራ | |
|---|---|---|---|
| | | ምዕራፍ | ምንባብ ገጽ |
| ሀ. የትምህርት ሥነ-ምግባር ሚኒስቴር | | | |
| 1. አስተዳደርና የሥነ አመራር አንድ ብሔራዊ የአማርኛ ቋንቋ ጥናት አካል መፍጠር | 1962 | 16 | 49 |
| 2. ሕግ | | | |
| የመንግሥት ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ለመቆጣጠር የሚያስችል ሕግ ማዘጋጀት | 1962 | 17 | 41 |
| 3. ምርምር ጥናት | | | |
| በፈተና እየወደቁ ስለሚወጡት ተማሪዎች ችግር ጥናት ማድረግና የማስወገጃ ጊዜውን ማቅረብ | 1962 | 16 | 52 |
| 1. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ | | | |
| 2. አስተዳደር የሥራ አመራር | 1962 | 16 | 95 |
| ለ. አንድ ኘላን የሚያደርግ ክፍል ማቋቋም | | | |
| 2. ምርምር ጥናት | | | |
| ሀ. የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ ከብሔራዊ ፍላጐት ጋር ተስማሚ እንዲሆን ማድረግ | 1961-62 | 16 | 27 |

እንዲሁም 9 የሚሆኑ ልዩ ልዩ የሥራ መመሪያዎች (ለምሳሌ:- ስለፕላን ዝግጅት መመሪያ፣ የልማት ወጪ መመሪያ፣ የሰው ጉልበት ሀይል መመሪያ፣ የቀበሌ ልማት መመሪያ፣ ወዘተ...) ተዘርዝረው በፕላኑ ውስጥ ተካተዋል:: የሁለተኛውን አምስት ዓመት ፕላን ለማስፈጸም የነበረው ችግር የሚከናወኑት ሥራዎች በአጠቃላይ እንጂ በዝርዝር አለመጠቀሳቸው ሲሆን ፕሮግራሙ ተጀምሮ ስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ባለመወሰኑ ምክንያት ለመከታተል አልተቻለም ነበር:: ይህን ለማረም በሶስተኛው ፕላን ውስጥ በሥራ ውጤት በኩልም ከያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚጠየቀው የሥራ ውጤት በገንዘብና በድርጅት ተለይቶ በዝርዝር ስለተመለከተ ሐላፊነቱ ግልጽ ነበር::

ለምሳሌ:- የእርሻውን ፕሮግራም ስንመለከት፣ ለማስፈጸም ኃላፊነቱ የተጣለው በእርሻ ሚኒስቴር ላይ ስለሆነ የመስሪያ ቤቱ መዋቅር ተስተካክሎ መቋቋም እንዳለበት ተመልክቷል:: ትላልቅ እርሻዎች እና የኮኦፕሬቲቭ እርሻዎች እንዲቋቋሙ ቅድመ ዝግጅቱ ተመልክቷል፤ በሰለጠነ ሠራተኛ በኩልም እንዲሁ የሚያስፈልጉት ተለይተው ለጐደለው የሥልጠና ፕሮግራም በየልማት ድርጅቱ እየተሰጠ እንዲያሟሉ ተመልክቷል::

በሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ውስጥ የየዘርፉ ግቦች በዝርዝርና በግልጽ ተመልክተዋል:: እንዴት እንደሚተገበሩ በተቻለ መጠን በዝርዝር ስለተገለጹ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ፕላን ዘመን የተከሰቱትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚቻለው ሁሉ ተገልጿል::

*ሶስቱ ፕላኖች የተዘጋጁትና ለአፈጻጸማቸውም የሚያስተባብረውና የሚገመግመው ተቋም በሂደት ልዩ ልዩ ስም (ጽሕፈት ቤት፣ ሚኒስቴር፣ ኮሚሽን) ቢሰጠውም ተቋሙ ስላልተለወጠ፣ ፕላኖችም ሳይቋረጡ ተከታታይ ስለነበሩ፣ በሁሉም ደረጃ ለማሻሻል ታዋቂ እየሆነ የፕላን ጥቅሙ እየጐላ እንዲሄድ አስችሏል፡፡*

**የሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ውጤት፣**

*የሶስተኛው ፕላን ውጤት፣ አፈጻጸሙንና ያጋጠመውን ችግር ስንመለከት በአሁኑ ጊዜ በአሀዝ አመሳክሮ በመጀመርያው ሁለት ፕላኖች እንደተመለከተው ማቅረብ አልተቻለም፤ በ1966 ደርግ ባካሄደው የመንግሥት ግልበጣ መረጃዎች በጊዜው አልተሰበሰቡም፤ የነበሩትም አልተገኙም፡፡ የሶስተኛው ፕላን አፈጻጸም ተገምግሞ የአራተኛው ፕላን ረቂቅ እንደተዘጋጀ ቢታወቅም ረቂቅ ፕላኑን ማግኘት አልተቻለም፡፡*

*ከ1960 - 66 ስለነበረው የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ አጠቃላይ እስታቲክስ መስሪያ ቤት ያቀናበረውን መረጃ ስንመለከት በ1965 ዓ.ም ባጠቃላይ የተደረሰበት የእድገት ደረጃ በሁለተኛው ፕላን ከተደረሰበት* 4.6% *በታች እንደነበር ይጠቁማል፤ የእርሻ ውጤት በ1965 እና 1966 በነበረው ድርቅ የተነሳ ዝቅ ያለ ነበር፤ በጠቅላላ የኢንዱስትሪው ውጤት እንደታሰበው ከፍ ያለ እደገት ቢያሳይም፣ በፋብሪካ--- ሚሊዮን--- ኤሌክትሪክ--- የማዕድን ውጤት በፓታሽ ፋብሪካ አለመቋቋም ብር--- ብቻ ነበር፡፡*

*በሶሽያል አገልግሎት የ1965/66 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የነበሩት--- ነበሩ፣ በኘላኑ የተመለከተው--- ነበር፡፡ በመጨረሻ ጠቅላላ ሥራ ውጤት* (GDP) *ብር 4,643 ሚሊዮን ደርሷል፤ የነፍስ ወከፍ ገቢ ብር 192,7 ነበር፤ እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች የቀረቡት በጊዜው በነበረው ዋጋ ስለሆነ ከፕላኑ ጋር ማነፃፀር አይቻልም፡፡*

***መደምደሚያ***

*በኢትዮጵያ ተጀምሮ የነበረው የመሥራት ባህል፣ አዲስ የመንግሥት ባህል፣ የመንግሥትን አሠራር ቀልጣፋ በማድረግ፣ በማስተባበርና በማሟላት በልማት እንቅስቃሴው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ ያለፉትን ሦስት ፕላኖች ለማዘጋጀትና ሥራ ላይ ለማዋል በተደረገው ሙከራ የተቀናጀ የልማት ፕሮግራም ምን ዓይነት ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል የመንግሥት ባለሥልጣናትና ሠራተኞች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዳገኙ አያጠራጥርም፡፡ በፕላን ዝግጅቱም ተካፋይነታቸው እየተሻሻለ መጥቶ በሦስተኛው ፕላን (በፕሮግራም ቀረጻውም ሆነ በዝግጅቱ) ሙሉ ተካፋይ ነበሩ፡፡*

*የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አሠራራቸውንና የሥራ ክፍፍሉን፣ ሳይደራረብ ቀልጣፋና አንድ ወጥ ለማድረግ፣ ፕላኑን በቀጣይነት እንዲፈጸሙ አስችሏል፡፡ እንዲሁም ለልማቱ እንቅስቃሴ ያስፈልጋሉ፣ ይረዳሉ፣ የተባሉ ድርጅቶችና፣ መስሪያ ቤቶች እንዲቋቋሙ እና አስፈላጊዎቹ ሕጐች እንዲቀረጹ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፡- በፋይናንስ አስተዳደር ብሔራዊ ባንክ፣*

ንግድ ባንክ፣ የኢንቨስትመንት ባንክ በማለት ተለያይተው ተቋቁመዋል:: የሀገር ውስጥ ኢንሹራንስ ድርጅቶች ተጀምረዋል:: የተሟላ የሕግ ከለላና ሥርዓት ለልማት ማስፈለጉን በመጠቆም የንግድ፣ የፍትሐ-ብሔር፣ የወንጀለኛ መቅጫ፣ የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ፣ የመንግሥት ሠራተኛ አስተዳደር፣ የደመወዝ ደረጃ (እስኬል)፣ የጡረታ እንዲሁም በየዘርፉ የማበረታቻና የአስተዳደር (እንደ ቴክኒክ ድርጅት ያሉ፣) በእርሻ፣ በሆቴልና ቱሪዝም፣ በኢንዱስትሪ ከፍተኛ ጥናቶች በማካሄድ ፋብሪካ (አዲስ ጐማ ፋብሪካ፣ የሸራና የጫማ ፋብሪካ)፣ በታሪካዊ ሥፍራዎች የተሠሩ ሆቴሎች (በባሕር ዳር፣ በጐንደር፣ በላሊበላ፣ በአክሱም፣ በጋምቤላ) ተሠርተዋል::

የየመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችም ለሚሰጡት አገልግሎትና ለሚያካሒዷቸው ፕሮጀዎች፣ ለሚያስፈልጓቸው ሠራተኞች፣ በጀት የሚወሰነው በፕላን በተመለከተው መሠረት መሆኑን እየተረዱ ሲሔዱ፣ ለፕላን ያላቸው ግንዛቤና እምነት ከፍ አለ፤ በመንግሥት ደረጃም የሚሰጠውን አገልግሎትና፣ የሚፈጸመውን ፕሮግራም ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና የሥራ ውጤቱንና እድገቱን እያነፃፀረ ለመለካት ፕላን አመቺ መሣሪያ መሆኑ እየታወቀ መጣ:: የልማት እንቅስቃሴውን፣ ችግሩን፣ ያለውን ጉድለት፣ ለወዳጅ መንግሥታት፣ ለዓለም አቀፍ እርዳታ ድርጅቶች ለማስረዳት፣ ድጋፍ ለመጠየቅ ፕላን የአንድ ሀገር ፍላጐትና ጥረት ማስረጃ መሆኑን ሁሉም ተረዳ::

በተጨማሪም፣ ሦስቱ ፕላኖች በተከታታይ ሳይቋረጡ በመዘጋጀታቸው የመጀመሪያው ለሁለተኛው፣ የሁለተኛው ለሦስተኛው የማሻሻያ በትር፣ የችግር መፍቻ ቁልፍ ሆነው ነበር:: አንዱ ፕላን አልቆ ሌላው ሲጀምር፣ ለደረሰው ጉድለት፣ ላጋጠመው ችግር ግልጽ የሆነ ነቀፌታና ሂስ ለመንግስትና ለአስፈጻሚው ክፍል ስለሚቀርቡ ለመረዳት፣ ለመታረም እድል ሰጥቷል:: በዚህም ምክንያት በፕላን እና በፕሮግራም መሥራት ልማትን፣ እድገትን ማፍጠን እንደሚያስችል መንግሥትና ባለስልጣኖች እየተገነዘቡ መጡ:: በአስር ዓመታት ውስጥ ስለልማትና እድገት በአንድ መንግሥት ቢሮክራሲ ውስጥ እንደዚህ ያለ ግንዛቤ መፍጠር ቀላል አልነበረም:: እንዲሁም በሚቀጥሉት ፕላኖች ተመሳሳይ ግንዛቤ በስፋት በሕዝቡ፣ በነጋዴውና በገበሬው ዘንድ ለመፍጠርና ተባባሪነታቸውንም በመቀስቀስ፣ ልማቱን ወደ ቀዬው በመውሰድ፣ እይታውን ማስፋት፣ መለወጥ ይቻላል የሚል ተስፋ ነበር::

ስለሆነም በ1966 ዓ.ም የተደረገው የመንግስት ለውጥ ያለፈውን የልማት ጥረት፣ ሙከራ፣ የታየውን የእድገት ጮራ ከመንግሥት ሥርዓቱ ጋር አድሐሪ ብሎ በመፈረጅ፣ ተራማጅ በሚባል ስርነቀል አስተሳሰብና ሥርዓት እንዲለወጥ አደረገ:: ለውጡ ባስከተለውም የፖለቲካ ግብግብና የማሕበራዊ ሥርዓት መናጋት የሕዝቡ ልማትና እድገት ትኩረት ሳያገኝ ቀረ::

# የአውራጃና የጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ሪፎርም (1955-1966)፡- የግል ትዝታዎች

*ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረወልድ*

## መግቢያ

በዛሬው ዕለት ለዚህ ለተከበረው ጉባኤ ንግግር እንዳደረግ ተጋብዤ የነበረው «የጠቅላይ ግዛትና የአውራጃ አስተዳደር ሪፎርም ከነፃነት እስከ አብዮት» በሚል ርዕስ ላይ ነበር። ነገር ግን መንግሥታዊ በሆነ የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማራሁት ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እስከተገለልኩበት እስከ 1967 ዓ.ም ስለሆነ ተካፋይ ባልሆንኩበትና በማላውቀው ከ1933 እስከ 1944 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተፈጸሙትን ለመናገር ያዳግተኛል። ስለዚህ ተካፋይ በሆንኩባቸውና አንዳንድ መረጃዎች ባገኘሁባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ መናገር እንዲፈቅድልኝ የጋበዙኝን ፈቃድ ጠይቄ ስለፈቀዱልኝ በዛሬው ቀን የምዘግብላችሁ ከ1944 እስከ 1967 ዓ.ም ተካፋይ የሆንኩባቸውንና ከዚያ በፊት ያሉትን አንዳንድ በአጋጣሚ መረጃ ያገኘሁላቸውን የአስተዳደር ሪፎርሞችና የልማት ሥራዎች ነው።

እላይ በተጠቀሰው ርዕስ ሥር ሊነገሩ የሚችሉ ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች ቢኖሩም ንግግር እንዳደርግ በተወሰነልኝ ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ለመናገር ጊዜው ስለማይበቃኝ የምነግራችሁ ዋና ዋናዎቹን ብቻ ነው። በመሆኑም ንግግሬ ወዝ ያጣና ይደርቅባችሁዋል ብዬ እሰጋለሁ። እንዳልኩት ንግግሬ ወዝ ካጣና ከደረቀባችሁ ችግሩን ያስከተለው የጊዜው ማጠር ነውና ወደፊት ከልጅነቴ ጀምሮ እስከ ሰማንያው ማብቂያ ዕድሜዬ ያለፍኩባቸውን የሕይወት ውጣ ውረዶችና ትዝታዎች በዝርዝር የመጻፍ ዓላማ ስላለኝ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ዓላማዬ ከተሳካልኝና መጽሐፉ ከተጻፈ የዛሬውን ያልተሟላውንና ወዝ አጥቶ የደረቀባችሁን ንግግሬን የምትካሱበት እንቅልፍና እህል ውሀ የሚያስረሳ መጽሐፍ ይሆናል ብዬ ስለማምን ሁላችንም ያ መጽሀፍ እውን እስኪሆን በተስፋ እንድንጠብቅ በትህትና እለምናለሁ። እንግዲህ ወደ ርዕሱ ከመግባቴ በፊት፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለትውልዴ፣ ስለ ልጅነት ኑሮዬና ከትምህርት ወደ ሕዝብ አገልግሎት ሥራ ዓለም እስከተሸጋገርኩበት ያሉትን ባጭሩ እገልጻለሁ።

## ትውልድ፣ የልጅነት ኑሮና ትምህርት

እኔ ወልደሰማዕት ገብረወልድ በልጅነት ዕድሜዬ ውስጥ ሆኜ አባቴ ወጣ ባሉ ቁጥር የጦር መሣሪያዎቻቸውንና የጸሎት መጻሕፍቶቻቸውን እያገላበጥኩ ማየት እወድ ስለነበር፣ የአባቴን የጸሎት መጻሕፍት ሳገላብጥ የአንድ እህቴ፣

የሦስት ወንድሞቼና የእኔ የልደት ቀናት የተጻፈበት በብራና የተጻፈ መዝሙረ ዳዊት አየሁ፣ የልደት ቀኔ ሐምሌ 19 ቀን 1917 ዓ.ም ነበር፡፡

አባቴ ግራዝማች ገብረወልድ ዋልተንጉሥ ባየ፣ እናቴ ወይዘሮ አየለች ወልደየሱስ ሀሰን ይባላሉ፡፡ አባቴ የተወለዱት በሐረር ጠቅላይ ግዛት ሐረር ከተማ ከግንቡ ውጪ «አደሬ ጢቆ» በሚባለው ቦታ ሲሆን እናቴም የተወለዱት በዚያው ጠቅላይ ግዛት «ጨለንቆ» ከተማ ነው፡፡ የአባቴ ወላጆች ትውልድ ልዩ ቦታ፣ የወንድ አያቴ መርሀቤቴ፣ የሴት አያቴ እንሳሮ ሲሆን፣ የእናቴ ወላጆች ትውልድ ቦታ ደግሞ የወንድ አያቴ ጠራ የሴት አያቴ መንዝ ልዩ ቦታው ዶባ ነው፡፡ አያቶቼ፣ ከየትውልድ ቦታቸው ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤልን ተከትለው ወደ ሐረር ጠቅላይ ግዛት ከሔዱ በኋላ ፣ የእሳቸው አሽከሮችና ወታደሮች ሆነው ይኖሩ ነበር፡፡ ልዑል ራስ መኮንን ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ፣ አያቶቼ ከባድ ሀዘን ስለደረሰባቸው በሐረር ከተማ መኖራቸውን ትተው እዚያው ጠቅላይ ግዛት ወደአሉት ርስቶቻቸው ሄደው መኖር ጀመሩ፡፡ የእናቴ ወላጆች በዚያው ጠቅላይ ግዛት ጨርጨር አውራጃ ርስታቸው ወደሚገኝበት «ገውደው» ወደሚባለው ቦታ ሄዱ፡፡ የአባቴ አባት፣ አቶ ዋልተንጉሥ ባየ በ«ውላቂጊ» ወረዳ የሚገኘው የልዑል ራስ መኮንን ርስተ ጉልት ሹም ሆነው ከቆዩ በኋላ የልዑል ራስ መኮንን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ሀዘን ስለጸናባቸው ሥራቸውን ለቀው በዚያው ጨርጨር አውራጃ ርሥታቸው ወደሚገኝበት «ቦረማ ጢቃ» ሔደው በቀን አንድ ጊዜ እህል ውሀ እየቀመሱ በጾም በጸሎት ሲኖሩ ጠላት ኢትዮጵያን ከወረረ በኋላ በተደረገው ጦርነት ልጃቸውን ቀኛዝማች ዋጋዬ ዋልተንጉሥን ማርኮ ወደመቃዲሾ ወስዶ ስለገደለባቸው በሀዘን ላይ ሀዘን ተደራርቦባቸው በ1929 ዓ.ም ባልና ሚስቱ በአንድ ሳምንት ውስጥ ተከታትለው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡

አባቴ ሕጻን ሆነው፣ በዚያን ጊዜ በነበረው ባህል መሠረት መንፈሳዊ አባት ተቀጥሮላቸው፣ ዳዊት ደግመው፣ ቅዳሴ ተምረው፣ በዲቁና ሲያገለግሉ፣ ሕፃኑ የወደፊቱ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አባታቸው ልዑል ራስ መኮንን ሐረር ከተማ ባቋዋቋሙት ሆስፒታል ሀኪም የነበረ ዶክተር ቢታሊያንና ኢትዮጵያዊው አባ ሳሙኤል ፈረንሳይኛ ሲያስተምሩዋቸው አባቴ እያዩ፣ ይኸንኑ ትምህርት ለመማር ይጉዋጉ ስለነበረ፣ ድሬ ደዋ ከተማ በሚገኘው ሚሲዮናዊ ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር፣ ከወላጆቻቸው እየጠፉ ወደ ድሬ ደዋ ይኮበልሉ ነበር፡፡ ወላጆቻቸው ልጃችን ይኮተልክብናል ብለው ስለሰጉ አባቴ ከጠፉበት እየተያዙ እንዲመለሱ ይደረጉ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ አባቴ ወደ ድሬዳዋ መኮብለላቸውን ስላላቋረጡ፣ አባታቸው ተቸግረው በእግራቸው እግረ ሙቅ እስከማጥለቅ ደርሰው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉና በዲቁና ሲያገለግሉ፣ የተመኙትን ዘመናዊ ትምህርት ሳይማሩ፣ በልጅነታቸው የመንግሥት ሥራ ያዙ፡፡ በዚያን ዘመን ለወታደር በየወሩ እንደደሞዝ የሚሰጠው እህል ስለነበር፣ አባቴ ሥራ የጀመሩት የወታደር ቀለብ ሰፋሪ ሆነው ነው፡፡ የወታደሮች ቀለብ ሰፋሪ ሆነው ሲሠሩ ባሳዩት የሥራ ትጋትና ታማኝነት፣ ዕድገት አግኝተው የወታደር ቀለብ

ሰፋሪዎች ተቆጣጣሪ ሆነው ተሾሙ። በዚህም ሥራ ላይ ሆነው ሲሠሩ፣ የሥራ ትጋታቸውና ታማኝነታቸው ብቻ ሳይሆን ቀደም ብለው ሥራውን ይሠሩት ከነበሩት ታላላቆቻቸው የበለጠ፣ ሠራተኞችን እየተቆጣጠሩ የማሠራትና ሕዝብን የማስተዳደር፣ ከዕድሜያቸው በላይ የሆነ ጠባይ ስለታየባቸው ገና በልጅነታቸው የበዴሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም ሆኑ። ወላጆቻቸው ልጃችን የልጅ አዋቂ ሆነልን ብለው፣ ገና ሃያኛው ዕድሜ እንደጀመሩ፣ አጋቧቸውና ትዳር ያዙ።

ሁለቱም፣ የወላጆቼ ወላጅ ቤተሰቦች፣ ልዑል ራስ መኮንንን ሲያገለግሉ በቅርብ ይተዋወቁ ስለነበር፣ እላይ እንደተጠቀሰው፣ አባቴ የበዴሳ ማዘጋጃ ቤት ሹም በነበሩበት ጊዜ ሃያኛው ዕድሜያቸውን ሲጀምሩ፣ እናቴ አስራ አምስት ዓመት ሲሆናቸው፣ አጋብተዋቸው፣ በሞት የተለዩትን አንድ እህቴን፣ ሁለት ወንድሞቼንና አሁን በሕይወት የምንገኘውን፣ የአራት ዓመት ታላቁን ሰብስቤንና እኔን፣ በጠቅላላው አምስት ልጆች ወልደው አባቴ በመቶ ሰባት ዓመታቸው እናቴ በመቶ ሶስት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አባቴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ዕድሜያቸው ስለገፋ ወይም ታመው ሳይሆን፣ ሰፊ ታሪክ ባለው ሁኔታ የታህሣስ ሚካኤልን ፀዲቅ ቆርሰው ለጠበልተኞቹ ቡራኬውን ካደሉ በኋላ ለእጃቸው ውሀ እንዲያመጡላቸው ጠይቀውና ታጥበው፣ ከዚያን ሰአት ጀምሮ እህል ውሀ እንዳይቀርብላቸው አደረጉ። እህል ውሀ ሳይመገቡ በሔዱ ቁጥር ድካም ሲሰማቸው አይቼ፣ «ስለመድሃኒዓለም ተውኝ» እያሉ ሲማጠኑኝ፣ እስካሁን የሚቆጨኝ ጉሉኮዝ እንዲሰጣቸው በማድረግ የፈጸምኩት ስህተት ነው። ያም ሆነ ይህ ለህዳር 12 አጥቢያ፣ አሥራ ሁለት ሰአት ገደማ ላይ፣ መመገብ ባቆሙ ልክ በአንድ ወር አርፈው፣ በዚያው በየወሩ በሚዘክሩት የቅዱስ ሚካኤል እለት ህዳር 12 ቀን 1987 ዓ.ም የካ ደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን (አዲስ አበባ) አፅማቸው አረፈ።

የወላጆቼ የበኩር ልጅ በሕጻንነቱ ከሞተባቸው በኋላ፣ ቀጥሎ የተወለደችውን ሴት ልጃቸውን፣ ያደግድጉን፣ በጣም ያፈቅሩዋት ስለነበር እማማ ብለው ይጠሯት ነበር። አባቴ በልጅነታቸው ለመማር ጓጉተው የነበሩትን ዘመናዊ ትምህርት ልጆቻቸው እንዲማሩ ይፈልጉ ስለነበር፣ በጣም የሚያፈቅሯትን ያደግድጉን በዚያን፣ ሕጻን ልጅን ለትምህርት ከቤተሰብ ለይቶ ለብዙ ዓመታት ማቆየት ባልተለመደበት ዘመን ገና በአምስት ዓመት እድሜዋ፣ አሰበ ተፈሪ ከተማ ይገኝ የነበረው የሙሴ አንቷን የካቶሊክ ሚሲዮን አዳሪ ትምህርት ቤት አስገቧት። ህጻኗ በነበረችበት ትምህርት ቤት ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ስትጨርስ፣ ትምህርት ቤቱ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ልኳት ትማር ነበር። ጣልያን ኢትዮጵያን በ1928 ዓ.ም. ወርሮ በተደረገው ጦርነት በሰሜን ግምባር ተሰልፎ የነበረው ጦር መረታቱና መሪው፣ አፄ ኃይለሥላሴም፣ ወደአዲስ አበባ መመለሳቸው ስለተሰማ፣ወደ ጦር ግንባር ለመሔድ ተዘጋጅቶ ትእዛዝ ይጠባበቅ የነበረው የጨርጨር አውራጃ ጦርና ሕዝቡ ተደናግጠው ግራ

ተጋቡ። ይህ አስደንጋጭ ሁኔታ ሲፈጠር የእናቴ አባት አቶ ወልደየሱስ ወደ አዲስ አበባ በባቡር ገስግሰው ያደግድጉን ወደ ውላቁኒ አመጡዋትና ከወላጆቹዋና ከወንድሞቿ ጋር ቀላቀሉዋት።

ያደግድጉ፣ ከአዲስ አበባ መጥታ ከእኛ ጋር ስትኖር፣ እንደ ብርቅ ዐይን ዐይኑዋን እናያት ነበር። አማርኛዋ ስለሚኮላተፍና ለእኛ እንግዳ የሆነ ቁዋንቁዋ እየቀላቀለች ስለምትናገር እንስቅ ስለነበር ታኮርፍና ዝም ስትል አንዳንዴም ብድግ ብላ «ኮሾ-ሜርድ» እያለች እጆቹዋን እያወናጨፈች ስትቆጣ፣ የተቆጣች መሆኑዋ ቢገባንም፣ የምትናገራቸው እንግዳ ቃላት የባሰውን ስለሚያስቁን ጥላን ትሔዳለች። ምግብ ሲቀርብልንም፣ እያማተበች በማናውቀው ቁዋንቁዋ ስትጸልይ፣ ስትተኛም ተንበርክካ እንደዚሁ ስለምታደርግ እንደኛው ሰው መስላ ትታየን እንጂ የምታደርገው ሁሉ በቤተሰቡ ውስጥ የተለየች ፍጡር ሆና እንድትታይ አድርጓት ነበር። በዚያን ዘመን፣ በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ ካቶሊክ ሲባል እንደ ከሀዲ ተደርጎ ይቆጠር ስለነበረ፣ እናቴ ከሳቸው ያልተሻለ አስተያየት የሌላቸውን ንስሀ አባታቸውን ጠርተው ልጄ ኮትልካለች ብለው እያለቀሱ አባቴን አሳምነዋቸው ያደግድጉ መጽሐፈ ቁደር እንድትጠመቅ ማድረጋቸው ትዝ ይለኛል።

ታላላቆቼ የተወለዱት አባቴ የበዴሳ ማዘጋጃ ቤት ሹም በነበሩበት ጊዜ ወላጆቻቸው ይኖሩበት በነበረው፣ ከበዴሳ ከተማ ማዶው ላይ በሚገኘው ቦረማ ጢቃ ተብሎ የሚጠራው ቦታ ሲሆን፣ እኔ ግን የተወለድኩት አባቴ ከበዴሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹምነት የአሰበ ተፈሪ ከተማ ዙሪያ የጭሮ ወረዳ ገዢና የፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው የጭሮን ወረዳ ሲያስተዳድሩ ከቦረማ ጢቃ አሰበ ተፈሪ ከተማ እንደመጡ ነው። ያደግድጉ ሙሴ አንቷን አዳሪ ትምህርት ቤት ገብታ እንድትማር ሲያደርጉ፣ ለታላቅ ወንድሜ ለሰብስቤ አንድ መንፈሳዊ አባት ቀጥረውለት ያስተምሩት ነበር። እኔም ፊደል መቁጠሪያ ዕድሜዬ ሲደርስ፣ ታላቅ ወንድሜን ያስተምሩ የነበሩት መንፈሳዊ አባት እኔንም ፊደል መቁጠር እንዳስጀመሩኝ፣ አባቴ ከጭሮ ወረዳ ገዢነት ተነስተው የመሰላ ወረዳ ገዢና የፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ስለተዛወሩ፣ ፊደል ሳለይ ወደ መሰላ ወረዳ ሔድን። መሰላ በነበርንበት ጊዜ፣ አባቴ ለብዙ ጊዜ ከቤት እየተለዩና ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ጫካ ገብተው ሕዝቡን ያስቸግሩ የነበሩትን ሽፍቶች ሲያድኑና ሕዝቡ ሰላም እንዲያገኝ ሲያደርጉ፣ ልጆቻቸው እንዲማሩ የሚጉዋጉ ቢሆንም ስለልጆቻቸው ትምህርት የማሰብ ጊዜ ስላልነበራቸው መሰላ ወረዳ ስንኖር አስተማሪ አልተቀጠረልንም ነበር። አባቴ ወደ መሰላ ወረዳ የተላኩበትን ተግባር ፈጽመው ሕዝቡ ሰላም ሲያገኝና አስተዳደሩ ሲቃና፣ ከወረዳው ተነሱና የውላኒ ወረዳ ገዢ፣ የፍርድ ቤት ዳኛና የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ርሥተ ጉልት ሹም ሆነው ተሾሙ። መሰላ ወረዳ ስንኖር የተወለደው የመጨረሻው ልጃቸው ታናሽ ወንድሜ ቀፀላ በተወለደ በጥቂት ወራት ውስጥ ወደ ውላቁኒ ወረዳ መጣንና ወረዳው ዋና ከተማ «ፉኛን ዲሞ» መኖር ጀመርን።

ፉኛን ዲሞ፣ ከምዕራብ ሰሜን በኩል «አርባ ረከቴ» የምትባለው ጠባብ መተላለፊያ የምትገኝበት ተረተር ጋር የተያያዘ ሌላ ተረተር መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ኮረብታ ላይ የምትገኝ፣ መንደር ናት። ይህች መንደር ወረዳ ገዢው የሚኖርባት የወረዳው ዋና ከተማ ናት። ኮረብታው ዙሪያውን ለጥ ባለ ሰፊ የማሽላ እርሻ በተንጣለለበት ሜዳ የተከበበ ሲሆን፣ ከኮረብታው በስተደቡብ ከሚገኘው፣ በሊና ተብሎ ከሚጠራው፣ ሰፊ ሜዳ መካከል ትልቅ ምንጭ ይፈልቃል። ምንጩ እየወረደ ሲሔድ ወንዝ ይሆንና ሜዳው እንዳለቀ በሚገኘው ውላቂኒ ተብሎ በሚጠራው ሸለቆ ውስጥ ይወርዳል። ወንዙ በዳርና ዳር የሚገኙትን የቡና፣ የሙዝ፣ የብርቱካን፣ የትርንጎ፣ የሸንኮራ አገዳና ሌሎች ተክሎች መስኖ እርሻ እያጠጣ ሲያልፍ፣ ሌሎች ምንጮች እየተቀላቀሉ ያጎለበቱትና ትልቅ ወንዝ ይሆናል፤ ይህ ትልቅ ወንዝ ወደ ደቡብ እየፈሰሰ ዝቅ ሲል በሌላ ሸለቆ ከሰሜን ወደደቡብ ከሚፈሰው ሌላ ወንዝ ጋር ይቀላቀልና ጋሌቲ የሚባለውን ትልቅ ጅረት ፈጥረው ጅረቱም ወደ ደቡብ ምዕራብ ይተማል።

❋❋❋

*ከዚህ በሁዋላ ደጃዝማች ወልደሰማእት ትምህርት ቤት ገብተው፣ ትምህርታቸውን ደረጃ በደረጃ እየተከታተሉ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ይገባሉ። ቀጥሎም ወደቤይሩት ተልከው ጥናታቸውን ከአጠናቀቁ በሁዋላ፣ በአገር ግዛት ሚኒስቴርና በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የሀላፊነት ቦታ ይዘው ያገለግላሉ። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ይመደባሉ። በዚህ ስራ ላይ እያሉ በድንገት ወደ ወላይታ አውራጃ ይዛወራሉ፤ አላማውም የግዛቱ ገዢ ሆነው የአውራጃውን አስተዳደር እንዲያሻሽሉ እና ልማት እንዲያፋጥኑ ነበር። ትርክታቸው የሹመት ዜናቸውን እንዴት እንደሰሙት በማቅረብ ይጀምራል።*

***አርታኢው***

❋❋❋

መስከረም 19 ቀን 1955 ዓ.ም ሦስት ሰአት ገደማ ይመስለኛል ከቤተ መንግሥት ስልክ ተደወለና እዮቤልዩ ቤተ መንግሥት እንድገኝ ተነገረኝ። ንጉሠ ነገሥቱ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚንስቴር ሥራ ላይ ዐይናቸውን ጥለውበት ስለነበር፣ ከማንኛውም መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ለሥራችን የምንፈልጋቸውን ሠራተኞች ጠይቀን የማዛወር መብት ተሰጥቶን እናዛውር ነበር። በዚህ ምክንያት ሌሎቹን መሥሪያ ቤቶች እያዳከሙ አንዱን ማጎልበት ተገቢ አይደለም የሚል ሀሜት ስለነበረ፣ ይህን ሀሜት ማክሸፍ እንዲቻል የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴርን ዓላማ፣ ያከናወናቸውን ሥራዎች፣ በስእልና በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጥና የሚያሳምን ኤግዚቢሽን እንድናዘጋጅ ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኙበት እንዲታይ ታዘን ስለነበረ የኤግዚቢሽኑን ማዘጋጀት ኃላፊነት

ለእኔ ተሰጥቶኝ ነበር። ይህ የኤግዚቢሽን ዝግጅት እምን ላይ እንደደረሰ ንጉሠ ነገሥቱ በየጊዜው እያስጠሩኝ ይጠይቁኝ ስለነበረ፣ ወደ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ስጠራ፣ ለዚሁ ጉዳይ መስሎኝ ይኸንኑ የሚያስረዱ የተጠቀለሉ ወረቀቶችን ይዤ ሔድኩ።

መሥሪያ ቤታችን ከቤተመንግሥቱ ብዙም ስለማይርቅ እንደተጠራሁ ወዲያው ስለሔድኩ እንደኔው (ለሹመትም ይሁን ለሽረት) ከተጠሩት ሁሉ ቀደም ብዬ ደረስኩና ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ለሥራ ስለተጠራሁ እንዲያቀርቡኝ እልፍኝ አስከልካዮቹን ጠየቅሁዋቸው። እሺ ጠብቅ እያሉኝ ጊዜው እየዘገዬ በሔደ ቁጥር የማይመስሉኝና (ከጥቂቶቹ በስተቀር) የማላውቃቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ሔደ፤ የተሰበሰቡት ሰዎች ስለሹመት ሲወያዩ ሰማሁዋቸው። አንዳንዶቹ የሚያውቁኝ «አንተም ለሹመት ተጠራህ? ኃይለኛ ሆነኸባቸዋል? ወዴት ሊልኩህ ይሆን? እዚያው እገርማሜ ቦታ እንዳይሆን [ወላይታዎች] ኃይለኞች ናቸው ተጠንቀቅ!» በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኙበት ሚኒስትሮቻቸው የሚያዩት ኤግዚቢሽን የማዘጋጀት ኃላፊነት ተሰጥቶኝ ኤግዚቢሽኑን በማዘጋጀት ላይ እያለሁ ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር እነሳለሁ የሚል ጥርጣሬ አላደረብኝም ነበር። ያም ሆነ ይህ፣ ሹመትና ሽረቱ የሚነገርበት ጊዜ ደረሰና መጀመሪያ በጠቅላይ ግዛት እንደራሴነትና ከአውራጃ ደረጃ በላይ ያሉ ተሹዋሚዎች አንድ በአንድ እየተጠሩ ጠቅላይ ሚኒስቴሩና በታዛቢነት የሚገኙት ሚኒስቴሮች በተገኙበት ሹመታቸው ወይም ሽረታቸው እየተነገራቸው ሲወጡና ሲሳሳሙ ሳይ እንደቆየሁ ተራዬ ደረሰና ተጠራሁ። አንድ ስሙም መልኩም ትዝ የማይለኝ ሰው እየመራኝ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ትልቁ ሕንጻ ፊት ለፊት ሰሜን ምሥራቅ በኩል የሚገኝ በሣር የተከፈከፈ እልፍኝ መሳይ ቤት ውስጥ ገባሁ።

ወደ እልፍኙ ውስጥ ስገባ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሀከል ላይ፣ በግራና በቀኛቸው ሚኒስትሮች፣ ቆመው አየሁና ገብቼ ፊታቸው እንደቆምኩ ሳቅ አሉና «በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ [ወላይታ] አውራጃ ገዢ ሆነህ ተሾመሀል» ብለው የተሻርኩበትን ዜና ካበሰሩኝ በኋላ ሊጨብጡኝ እጃቸውን ወደ እኔ ሲዘረጉ ሰውነቴ ተለዋወጠና ያለሁበት ጠፋኝ። የዘረጉትን እጃቸውን ሳልነካ ገላምጫቸው ወጣሁና ከቤተ መንግሥቱ በስተሰሜን በሚገኘው አጥር በር ወጥቼ አጥሩን ተጠግታ ቆማ ወደነበረችው መኪናዬ ስሔድ ያ ለሹመት ስጠራ እየመራ ወደ ሻሪዎቼ ባለሥልጣኖች ያቀረበኝ ሰው «አቶ ወልደሰማያት ትጠራለህ ተመለስ» እያለ ከኋላዬ ሲሮጥ መኪናዬ ውስጥ ገባሁና አስነስቼ ወደ ቢሮዬም ወደ ቤቴም ሳይሆን ወደ ኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር እንዋኝበት ወደ ነበረው ወደ ለገጣፎ ወንዝ በፍጥነት እየነዳሁ ሔድኩ።

እቦታው ላይ እንደደረስኩ መኪናዬን ከዋናው ቤት ጉዋሮ አቁሜ ሠራተኞቹን «ላርፍ ስለምፈልግ እተኛለሁና በር እየመታችሁ እንዳታስቸግሩኝ» ብያቸው

የመኝታ ክፍል ሰጡኝና ገብቼ ከውስጥ ቆልፌ ተኛሁ። እጅግ በጣም አናዶኝ የነበረውና ባለሥልጣኖቹን ገላምጩ መውጣት ደረጃ ላይ ያደረሰኝ፣ እንዲሁም ከተሹዋሚዎችም ሆኑ ከተሻሪዎች ጋር ሆኜ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርቤ እጅ መንሳትና ከንጉሠ ነገሥቱ ምክርም ሆነ መመሪያ መቀበል የሚገባኝን ረግጩ መኮብለል ደረጃ ላይ ያደረሰኝ ምክንያት መሻሬ ቆጭቶኝ ሳይሆን ቀደም ብሎ ከምድር ጦር መሀንዲስ መምሪያ ጋር በግል መግባባት ቡልደዞሮችና ግሬደሮች ከነቴክኒሺያኖቹ አግኝቼ ከኤረር ገዋኔ ያለውን አዲስ መንገድ በማሠራት ላይ እያለሁ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው አሳስበው በእኔ ኃላፊነት ኤግዚቢሽን በመዘጋጀት ላይ እያለ የአስተዳደር ሪፎርም ስራ ለአገር እድገት የሚበጅ የሁለት ኮሚቴዎች አባል እና የሦስተኛው ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኜ በመሥራት ላይ እያለሁ፣ ሚኒስትሩና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተባብረው ከሥራዬ ላይ ማስነሳት መቻላቸው ነበር። ሁኔታው ከፍ ያለ እልህ ውስጥ ስላስገባኝ ከቤተ መንግሥቱ ግቢ ወጥቼ መኪናዬ ውስጥ ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ እያለቀስኩ ነበር ለገጣፎ ወንዝ ዳር እምትገኘው አነስተኛ ሆቴል የደረስኩት። ለገጣፎ ደርሼ እመኝታ ክፍሌም ከገባሁ በኋላ ማልቀሴን ቀጥዬ ማታ ራቴን፣ በማግስቱም ምሳዬንና ማታ ራቴን፣ ሳልበላ አልፎ አልፎ እያሸለበኝ፣ ስነቃ እያለቀስኩ ሁለት ሌሊትና አንድ ቀን ተግማሽ ቆየሁ።

በቆየሁ ቁጥር ቁጣዬ እየበረደልኝና እልሄ ለማመዛዘንና ለማስተዋል ቦታ እየለቀቀ ስለሔደ፣ የምሠራው ለአገሬና ለወገኔ እድገት እንጂ ለራሴ ጥቅም ስላልሆነ ለምን እኔ ያሰብኩት ካልሆነ ብዬ እዚህ ከፍተኛ እልህ ውስጥ እገባለሁ የሚል ሃሳብ አደረብኝ። ይልቁንም አዲስ አበባ ከተማ ያሉትን ቤተሰቦቼንና ዘመዶቼን በጣም የሚያስቡልኝንና የሚጨነቁልኝን አሰበ ተፈሪ ያሉትን ወላጆቼን ከፍተኛ ጭንቀት ላይ በመጣሌ ተጸጸትኩና ወደ ቤቴ ለመመለስ ወሰንኩ። ለአንድ ቀን ከግማሽና ለሁለት ሌሊትና ለአንድ ረፋድ ቀን «ከሸፈትኩበት» ከለገጣፎ ወንዝ ዳር ጎስቋላ የገጠር ሆቴል ሰው ሁሉ ወደየሥራው ሔዶ ብዙም ሰው በመንገድ ላይ በማይታይበት ሰአት ላይ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

## ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረብኩና ጥልቅ ምክርና ግሳጼም ተሰጠኝ፦

ከቤተ መንግሥት ግቢ በርሬ ከወጣሁበትና ከአዲስ አበባ ከተማ ከጠፋሁበት ሰአት ጀምሮ በመንግሥት በኩል ለፖሊስ፣ በቤተሰቤ በኩል ለዘመድ ሁሉ ተነግሮ በአራት መአዘን ተፈልጌ ስላልተገኘሁ ቤተሰቦቼ ሞቱዋል የሚል ጥርጣሬ አድሮባቸው ሀዘን እንደተቀመጡ፣ ቤቴ ስደርስ የሞተው ሰው ስለተነሳላቸው እልልታው ቀለጠ። እንግዳ ቤት ብዙ ሀዘነተኞች ተቀምጠው ስላየሁ ወደ መኝታ ቤት ገባሁና ጥቂት እንዳረፍኩ እመቤት ሆይ ሂሩት ደስታ (አሁን ልዕልት) ከጠፋሁበት መመለሴን ማን እንደነገራቸውና እንደላካቸው አላውቅም እቤቴ መጥተው፣ «ንጉሠ ነገሥቱ ስለሚፈልጉህ እንሒድ» አሉኝ። በዚያን ሰአት ንዴቴ የበረደልኝና ራሴን ገዝቼ የተረጋጋሁ ስለነበርኩ እምቢ

ማለት ደረጃ ላይ አልነበርኩምና እሺ ብዬ አብሬያቸው ሔድኩና ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረብኩ፡፡

በዚያን እለት፣ ማለት በተሾምኩ በሦስተኛው ቀን፣ መስከረም 21 ቀን 1955 ዓ.ም እና ከአሥር ዓመት ገደማ በኂላ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆኜ በተሾምኩ ማግስት፣ ህዳር 6 ቀን 1964 ዓ.ም፣ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት በቀረብኩባቸው ሁለት ቀናት ከንጉሠ ነገሥቱ ያገኘሁት ሰፊ ትምህርታዊ ምክር ቀደም ብሎ የነበረኝን ለአገርና ለወገን ዕድገት በርትቶ የመሥራት ፍቅር የሚያጠናክርልኝ ነበር፡፡ እንዲሁም ከቀድሞውም የበለጠ ኢትዮጵያ ያለችበትን አስጊ ሁኔታ የተረዳሁትና ለአገሬ፣ ለወገኔ የነበረኝ ፍቅር ከቀድሞ የበለጠ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ለሰላማቸው፣ ለአንድነታቸውና ለብልጽግናቸው መስዋዕት መሆን እንደሚያስፈልግ የተማርኩባቸው የተቀደሱ ቀናት ነበሩ፡፡ ደሃይቱ አገሩ ኢትዮጵያ ያስተማረችው ትውልድ የራሱን ጥቅም እርግፍ አድርጎ በመተው ለአገሩ ለኢትዮጵያና ለወገኑ ለኢትዮጵያውያን ሰላም፣ አንድነትና ብልጽግና ሌት ተቀን መሥራት እንደሚያስፈልገው በነዚያ በተቀደሱት ሁለት ቀናት ንጉሠ ነገሥቱ የሰጠኝ ሰፊ ምክር ስላስገነዘበኝ ከዚያን በኂላ የሠራሁት መልካም ውጤት ያለው ሥራ ቀስቃሽ (ካታሊስት) የሆነኝና እስካሁን የአገርና የወገን ማገልገል ጉዳይ ሲነሳ የሚቀሰቅሰኝና የሚያቁነጠንጠኝ ያ በአእምሮዬ የተቀረጸውና ባህል ሆኖ ከእኔ ጋር የሚኖረው የንጉሠ ነገሥቱ ሰፊ ምክር ስለሆነ የተቀደሰው ስማቸዉ ዘለዓለማዊ ሆኖ እንዲኖር እመኛለሁ፡፡

ከንጉሠ ነገሥቱ ምክር ባገኘሁባቸው በነዚያ ሁለት ቀናት (መስከረም 21 ቀን 1955 ዓ.ም እና ህዳር 6 ቀን 1964 ዓ.ም) የተናገሩትን ሁሉ መጥቀስ ራሱ አንድ መጽሐፍ መጻፍ ስለሚሆንና አንዱን ጠቅሶ ሌላውን መተውም ስለሚያስቸግር ጥቂቱን ለምሳሌ ያህል ለማስፈር እወዳለሁ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያን ለመምራት ከእግዚአብሔር አደራ ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ሌት ከቀን ለአገር ሰላም ለሕዝባቸው ብልጽግናና ለኢትዮጵያ እድገት ለዓለም ሰላም ጭምር ጥረት በማድረግ ድርሻቸውን የተወጡትና በመወጣትም ላይ መሆናቸውን ተናግረው የኢትዮጵያ አጎራባች አገሮችና ኃያላን መንግሥታት ጭምር በኃይማኖት፣ በኤኮኖሚና በፖለቲካ ጥቅማቸው ምክንያት የኢትዮጵያንና የሕዝቧን እድገትና አንድነት የማይፈልጉ ስለሆኑ ውስብስብ የሆኑ ከባድ ችግሮች እንዳሉባት የሀገሮቹን ስምና በኢትዮጵያ ላይ የፈጸሚቸውንና በመፈጸም ላይ የሚገኙትን ችግሮች እንደምሳሌ እየጠቀሱ ገለጡልኝ፡፡ ንግግራቸውን በመቀጠል ለትምህርት መስፋፋት ሌትና ቀን የሚጥሩት፣ እነዚህን በኢትዮጵያ ላይ ከየአቅጣጫው የተጋረጡባትን ችግሮች ለመቋቋም የሚቻለው በጥበብና ተግቶ በመሥራት ስለሆነ በትምህርት ላይ ማተኮራቸውን ገልጠው እነዚያ ጥረው ግረው ያስተማሩዋቸው ወጣቶች የግል ጥቅማቸውን እርግፍ አድርገው በመተው ራሳቸውን ለሀገራቸውና ለወገናቸው አንድነት ደህንነትና ዕድገት መስዋዕት በማድረግ በቅንነት፣ በታማኝነትና

በህብረት ተግተው የሠሩ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ተናግረው ሳልበሳጭ በርትቼ እንድሠራ አገራችን ጠላቶቿን መቋቋም እንድትችል እኛ ወጣቶቹ ምን ማድረግ እንደሚገባን ሲናገሩ ህዋሳቴ ሁሉ በውስጤ ሲንቀሳቀሱና ለሀገሬና ለወገኔ የማገልገል ፍላጎቴ ልገልጥበት የምችልባቸው ቃላት ማግኘት በማልችለው በከፍተኛ ደረጃ ጨመረና አቁነጠነጠኝ፡፡

ስለኔ ሲናገሩ ሐረር ጠቅላይ ግዛት ሆኜ የሠራሁዋቸውንና ለእርሻ ልማት ስለሚሰጠው ብድር ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ከጓደኞቼ ጋር በቀረብንበት እለት ሳልፈራ በድፍረት በተናገርኩትና ክቡር አቶ መኮንን ባዘጋጁት ለጭሰኞች ብድር በሚሰጥበት ሰነድ ባለመስማማቴ ምክንያት ክቡር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ሃሳቤን ወደውት አብሪያቸው እንድሠራ ጠይቀዋቸው ከሐረር መምጣቴንና በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የሠራኋቸው ሥራዎች መልካም መሆናቸውን ሲነግሩኝ ለካስ በቅንነት አደርግ የነበረው ሩጫ ታውቆልኛል የሚል ስሜት አሳደረብኝና ስለፈጸምኳቸው ተግባሮች መልካምነት የነበረኝን ጥርጣሬ አስወገደልኝ፡፡ ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ተነስቼ የወላይታ አውራጃ ገዢ እንድሆን፣ በሌሎች በኩል ግፊት ቢኖርም፣ በንጉሠ ነገሥቱ በኩል ያለው ሃሳብ ግን ቀና መሆኑንና የበለጠ ነፃነት አግኝቼ መሥራት እንድችል ራሳቸው በመፈለጋቸው እንጂ በተቃዋሚዎቼ ግፊት ብቻ አለመሆኑን፣ ተናግረው የአውራጃውም ደረጃ ከጠቅላይ ግዛት የማያንስና ቀደም ብሎም የታወቁ ደጃዝማቾች የሚሾሙበት አገር መሆኑን ገለጹልኝ፡፡ ስለአውራጃው ሲናገሩ፣

> *ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ አስተዳደር ሥር የነበሩ ግዛቶች በስተኋላ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ማዕከላዊው መንግሥት ተዳክሞ ጠቅላይ ግዛቶቹ እያፈነገጡ የየራሳቸው ግዛት ፈጥረው ስለነበረ አጼ ምኒልክ [ወላይታ] ዙሪያ ያሉትን ሁሉ እንደ ቀድሞው በኢትዮጵያ አስተዳደር ሥር ሲያደርጓቸው ጦና ቢመክሩትም እምቢ ስላለ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ተናደው ራሳቸው ዘምተው ወታደሩን 'የማረከውን ሸጥ ለውጥ' ብለው ስለፈቀዱለትና እስካሁንም መልካም አስተዳዳሪ ባለማግኘቱ ጭምር ቂም ይዞ፣ ኢትዮጵያዊነቱ የማይሰማው ስለሆነ፣ ሕዝቡ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝና ኢትዮጵያዊነት እንዲሰማው እንዳደርግ የመረጡኝ መሆኑን አረጋገጡልኝ፡፡ የአውራጃ አስተዳደሩን ሥራ እያስታዋልኩ እንድሠራ ሲመክሩኝ ገርማሜን አነሱና 'ገርማሜ እንዳንተው እዚህ አልስማማ ስላለ መክረንና የጠየቀንን ሁሉ ሰጥተነው እንዲያስተዳድር ብንልከው የማይገቡ ተግባሮችን ፈጽሞ ሕዝቡን ስላጋጨው እኛ ሳናነሳው ሕዝቡ ራሱ አባረረው፡፡ የአስተዳደር ሥራ ሲሠራ የሕዝብ ባህል መለወጥ ጥቅም ቢኖረውም፣ ባንድ ጊዜ እንለውጥ ቢባል ለጊዜው የባለጊዜዎችን ጥቅም ስለሚነካና ስለሚያስቀይማቸው እንቅፋት ይፈጥራልና ትልቁንም ትንሹንም እህ እያሉና እያማከሩ መሥራት ነው፡፡ የራስን ጥቅም ትቶ ለዚያው ለሕዝቡ ጥቅም የሚሆን ሥራ ከተሠራ ጥቅሙ የተነካውም ቢሆን ይሸነፋል፡፡*

በማለት ሁሉንም ለመጥቀስ ሰፊ ጊዜና ቦታ የሚጠይቁ በጣም ጠቃሚ ጉዳዮችን እያነሱ ከመከሩኝ በኋላ በመጨረሻ ላይ ትእዛዛቸውን ረግጬ በመሔዴ በፈጸምኩት ከባድ ጥፋት ይቅርታ የተደረገልኝ ስለሆነ ወደታዘዝኩበት በቶሎ ሔጄ አውራጃውን እንዳይና ለሥራዬ የሚያስፈልገኝን ጠቅላይ ግዛቱንና የአገር ግዛት ሚኒስቴርን ጠይቄ ካልፈጸመልኝ ቀርቤ እንዳመለክት ነግረውኝ እጅ ነስቼ ወጣሁ። ከዚያ ቀን በኋላ አንድ ቀን በፈጸምኩዋቸው የአስተዳደር ሪፎርሞች ተከስሼ፣ በሌላ ቀን፣ ደግሞ እንድፈጽም የተጠየኩት ከባድ ጉዳይ ስህተት ያለበት ስለሆነ ጉዳዩን ሳልፈጽም ስህተቱን እንዲታረም ለማመልከት ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርቤአለሁ። ከሁለቱ ቀናት በስተቀር ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሳልቀርብ ኖሬ፣ በመጋቢት ወር 1957 ዓ.ም ለአንድ ሳምንት ያህል የወላይታን አውራጃ ለመጎብኘት ወደ አውራጃው እስከመጡበት ቀን ድረስ፣ ሥራዬን በሙሉ ልብ በቅንነትና በትጋት ስሠራ ቆየሁ።

ወደ አውራጃው ከመሔዴ በፊት አንዳንድ የልማት መሥሪያ ቤቶችን አነጋገርኩ። ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ስወጣ የሔድኩት ወደ ቤቴ አልነበረም። ያን እለትና በማግስቱ ወደ ልማት መሥሪያ ቤቶች እየተዘዋወርኩ ማነጋገርና እርዳታ መጠየቅ ጀመርኩ። እየተዘዋወርኩ ያነጋገርኳቸውና እርዳታ የጠየቅኋቸው የልማት መሥሪያ ቤቶች፣ አውራ ጎዳና ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ መብራት ኃይልና ሌሎችም መሥሪያ ቤቶች ነበሩ። የማውቃቸውንም የማላውቃቸውንም ባለሥልጣኖች እየተዘዋወርኩ ሳነጋግር በተለይ በቤተ መንግሥት የፈጸምኩት የድፍረት ተግባርና ከዚያም በፊት የበላዩን ምክትል ሚኒስትር ቀጣ እየተባለ ይናፈስ የነበረው አሉባልታ በአድር ባዮች እና ሆድ አምላኮች ዘንድ ጋጠ ወጥ አስመስሎኝ ነበርና ፊታቸውን ያጨፈገጉብኝ ቢኖሩም በደስታና በስሜት ከልባቸው አስበው ሊረዱኝ ደስታቸውን የገለጡልኝና ያበረታቱኝም ነበሩ። በተለይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተፈራ ደግፌንና የቴሌኮሚኒኬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በትሩ አድማሴን ሳነጋግራቸው የነበራቸው ቅን አስተያየትና (ቀጥሎ) የፈጸሙዋቸው እጅግ መልካም ተግባሮች (ሁሉም በየቦታው የሚገለጽ ቢሆንም) እንደነሱ ያሉ ባለሥለጣኖች የልማት መሥሪያ ቤቶችን ቢመሩ ኢትዮጵያ እዚህ ደረጃ ላይ ባልተገኘች ነበር በማለት ያለኝን ከፍ ያለ አክብሮት እገልጥላቸዋለሁ። እነዚህን ሁለት ባለስልጣኖች ሳነጋግራቸው፣ አቶ ተፈራ ደግፌ በዚያኑ ሰሞን አንድ የሶዶን ከተማና የአካባቢውን የንግድ እንቅስቃሴ አጥንቶ የሚመለስ ቡድን የሚልኩ መሆኑን ሲገልጡልኝ፣ የቴሌኮሚኒኬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በትሩ አድማሴ ደግሞ አቶ በየነ ደስታንና አቶ ግርማ (ሁለቱም የክፍል ኃላፊዎች) ይዘው በዚያኑ ሰሞን ወደ አውራጃው አብሬያቸው ሔጄ ሁኔታውን አጥንተው መመለስ እንደሚችሉ ገልጠውልኝ አብረን ለመሔድ ተስማማን።

በትምህርት ቤትም ሆነ በሌላ የሥራ ቦታ ቀደም ብለን የማንተዋወቀው ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተን ያነጋገርኳቸው እነዚህ ሁለት ባለስልጣኖች ለአገራቸውና ለወገናቸው ዕድገት ያላቸውን ከፍ ያለ ፍላጎትና ቅን አስተሳሰብ የሚገልጽ በመሆኑ እስካሁን ትዝ ባለኝ ቁጥር እያስደነቀኝና እያስደሰተኝ በጣም አከብራቸዋለሁ፡፡

## አገር ጎብኚ እንግዶች መስለን የሶዶን ከተማ ከአቶ በትሩ አድማሴ ጋር ጎበኘን፡-

ከአቶ በትሩ አድማሴ ጋር ከተነጋገርን ከጥቂት ቀናት በኋላ ከመሥሪያ ቤታቸው አቶ በየነ ደስታንና አቶ ግርማን አስከትለው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አቶ በላይ ብናልፈውን ጨምረን ወደ ሶዶ ተጉዋዝን፡፡ በዚያን ጊዜ መንገዱ አያመችም ነበርና ከአዲስ አበባ ጠዋት ተነስተን ሻሸመኔ በቀለ ሞላ ሆቴል አድረን በማግስቱ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ገደማ ላይ ከሻሸመኔ ተነስተን ቀደም ብሎ የነበረውን የበጋ ጥርጊያ መንገድ ወደ በጋ ከክረምት የሚያገለግል የጠጠር መንገድ ለመለወጥ የአውራጎዳና ባለሥልጣን ከሻሸመኔ ወደ ሶዶ በመሥራት ላይ የሚገኘውን አንድ መቶ ሰላሳ ኪሎሜትር ጥርጊያ መንገድ ተያያዝነውና ጠዋት አራት ሰአት ገደማ ሶዶ ከተማ ገባን፡፡ ሶዶ ከተማ እንደገባን ማንነታችንን ሳንገልጥ ተላላፊ አገር ጐብኚዎች መስለን ከተማዋን እየተዘዋወርን ሁላችንም በየበኩላችን የምንፈልገውን ለማወቅ ነዋሪዎችንና ነጋዴዎችን እያነጋገርን እስከ ሰባት ሰአት ጎበኘን፡፡

የሶዶ ከተማ ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በፊት የተቆረቆች ከኢትዮጵያ የቀድሞ ከተሞች አንዷ ናት፡፡ ከተማዋ፣ በበጋ ወራት ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር የሚያገናኛት ጥንት በሰው ጉልበት የተሠራ የመኪና ጥርጊያ መንገድ እና እንዲሁም ከአዲስ አበባ ከሆሳዕና ከጅንካ በበጋ ወራት ብቻ በሳምንት አንድ ቀን የሚያገናኛት የአየር ግንኙነት አላት፡፡ የሬዲዮ ቴሌፎንም ሆነ የስልክ መስመር የላትም፡፡ እንዲሁም የከተማው ነዋሪ በከተማው መካከል በሚገኘው ሸለቆ ውስጥ በሚገኙ ሁለት (በበጋ ወራት) ጭል ጭል በሚሉ የተበከሉ ምንጮች የሚጠቀሙ ሲሆን በተለይ በበጋ ወራት ከባድ የውሀ ችግር ያለባት ከተማ ነበረች፡፡ ከተማዋ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት የሌላት ብትሆንም የሚደንቀው እዚያች በጣም የተጎሳቆለች አነስተኛ ጥንታዊ ከተማ ውስጥ አንድ ትልቅ በዲዝል ጀነሬተር የሚሠራ በአክሲዮን የተቋቋመ የደረቅ ቡና መፈልፈያ ድርጅት አለ፡፡ እጅግ ኋላ ቀር የሆነ ያለመድሃኒትና ያለመሠረታዊ የህክምና መሣሪያዎች በአንድ ክፍል ደሳሳ ቤት ውስጥ በአንድ የራሱን ጤና መጠበቅ በተሳነው ድሬሰር የሚካሔድ የመንግስት ክሊኒክ በአንጻሩ ደግሞ በስመ ጥሩው በሊጋባ በየነ አባ ሰብስብ ስም የሚጠራ አሠራሩ አዲስ አበባ የሚገኘውን የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሚያስታውስ የስብሰባ አዳራሽ የአስተማሪዎች ማረፊያና የቤተ መጻህፍት ክፍሎች ያሉት በጥርብ ድንጋይ የተሠራ አንድ

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዚያች ጎስቋላ ጥንታዊ ከተማ ውስጥ መገኘቱ ያስደንቃል። ከከተማዋ በስተ ምስራቅ አንድ ኪሎሜትር ተኩል ያህል ራቅ ብሎ የሚገኘው ከጠላት ወረራ በፊት የተቋቋመ የሱዳን ኢንቴሪየር ሚሲዮን ሆስፒታል በአንድ አሜሪካዊ ዶክተርና በአራት ያህል ነርሶች እየተካሔደ፣ ከሲዳሞና ከጋሞጎፋ ድረስ ለሚመጡ ህሙማን አገልግሎት ይሰጣል። የሶዶ ከተማ ለጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት፣ ለኩሎ ኮንታ፣ ለከንባታና ለሀዲያ እና ለደራሳ አውራጃዎች አማካይ ቦታ በመሆኗ የቡና፣ የቅቤ፣ የቡሉኮ፣ የስጋ ከብት፣ የቆዳ የሌጦና የዝንጅብል ንግድ የሚካሔድባት ኢትዮጵያውያን፣ ህንድ፣ አረብና ግሪክ ነባር ነጋዴዎች ይገኙባታል።

ያችን ጥንታዊ ከተማ እየተዘዋወርን፣ ወንዱንም፣ ሴቱንም፣ ልጆችንም እያነጋገርን ያደረግነው ጉብኝት ማንነታችንን ሳንገልጥ ስለከተማዋ ለማወቅ የምንፈልግ ተላላፊ አገር ጎብኚ መንገደኞች መስለን መሆኑን ቀደም ብሎ ጠቅሼያለሁ፤ በተለይ ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በከተማዋ ነዋሪ የሆኑና ስለአውራጃው ሕዝብና የመንግሥት ሠራተኞች ማን ምን እንደሆነ ጥርጥር አድርገው የሚያውቁትን ግሪካዊ አዛውንት «ሙሴ ቆስታን» በሰፊው አነጋግረን፣ ስለአውራጃው ሕዝብ ከቀድሞ ጀምሮ ስለነበሩት አውራጃ ገዢዎችና ሠራተኞች ግንዛቤ አገኘን። አዛውንቱ አረቂ ጭምር የሚነግዱ ስለሆኑ፣ እንግዶችን በየደረጃቸው የሚያስተናግዱባቸው የመጎንጫ ጓዳዎች ስላሉዋቸው፣ ከእንግዶቻቸው ጋር እያወጉ፣ በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያን በፊት ስለነበሩት የአውራጃ ገዢዎች የመንግሥት ሠራተኞች የያዝነውን የዶሮ ወጥ የአገልግል ፍትፍት (የቤት ጠጅ) ምሳ አብረን እየተጋበዝን በሰፊው አወጉን። አዲስ ስለተሾምኩት ስለእኔም ከተባራሪ ወሬ የሰሙትን ያህል በመጠኑ ነገሩን። በከተማው እየተዘዋወርንና በተለይም ከአዛውንቱ ከሙሴ ቆስታ መረጃዎችን ካጠናቀርን በኋላ እላይ ወደተጠቀሰው ከከተማዋ በስተ ምስራቅ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው (በስተኋላ እንደተረዳሁት) ከጤና አገልግሎት ይልቅ በወንጌል ስብከት ላይ ተሰማርቶ ወደ ነበረው ሱዳን ኢንቴሪየር ሚሲዮን ሆስፒታል ሔድን።

አሜሪካዊ ሚሲዮናውያኑም፣ በአውራጃው ውስጥ በሚዘዋወሩት ወንጌል ሰባኪዎቻቸው አማካይነት፣ ከሙሴ ቆስታ ይበልጥ እንጂ የማያንስ ስለሕዝቡና የመንግሥት ሠራተኞች አሠራር ስለሚያውቁ፣ ስለአውራጃው፣ ስለሕዝቡና ስለመንግሥት ሠራተኞች አሠራር ሁኔታ በጥያቄና መልስ ማንነታችንን ሳይጠራጠሩ ክፉውንም በጎውንም አጫወቱን። በዚህ ሁኔታ ለማወቅ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ከሞላ ጎደል ካወቅን በኋላ ወደሻሸመኔ ለመመለስ ስንነሳ ከእኔ በፊት ስለነበሩት አውራጃ ገዢና ስለእኔም ያውቁ እንደሆነ አቶ በትሩ ሚሲዮናውያኑን ጠይቀዋቸው የነገሩን ነገር ስለነበረ የእኔን ማንነት ሳንገልጥላቸው ተሰናብተናቸው ብንሔድ ወደ አውራጃው በኦፊሴል ስሔድ አውራጃ አስተዳዳሪነቴን ሲያውቁ መልካም አይሆንምና ማንነትክን እናሳውቃቸው ብለው አቶ በትሩ አድማሴ የኔን ማንነት ሲነግሯቸው

ከመቅጽበት ሁኔታው ሁሉ ተለወጠና በጣም ተደናግጠው እየተርበተበቱ ወደቤታቸው እንድንገባና ሻይ እንድንጋበዝ አጥብቀው ጠየቁን። መንገዱ መጥፎ ስለሆነና ጊዜውም እየመሸ ስለሔደ ሻሸመኔ ገብተን ማደር ስላለብን ይቅርታ ጠይቀን ወደ ሻሸመኔ ተጓዝንና ከምሽቱ ሦስት ሰአት ገደማ በቀለ ሞላ ሆቴል አደርን።

ከዚህ በላይ በተገለጠው ሁኔታ የሶዶን ከተማ ጎብኝተን ስለከተማዋና ንግድ እንቅስቃሴዋ፣ ስለመንግሥት ሠራተኞች አሠራርና ስለሕዝቡ ለከተማዋ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑት አገልግሎቶችና ከሻሸመኔ ወደ ሶዶ ከተማ ስንሔድና ስንመለስ የአውራጃውን ሰሜናዊ ክፍል ግራና ቀኝ ተመልክተን ስለአውራጃው ተፈጥሯዊ ሁኔታ መጠነኛ ግንዛቤ አግኝተን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። አዲስ አበባ እንደተመለስን ወደ አውራጃው በኦፊሴል ሔጄ ለሥራዬ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማጥናትና ወደ አዲስ አበባ እንደገና ተመልሼ ለማሟላት ዝግጅት ጀመርኩ።

## በኦፊሴል ወደ አውራጃ ሔጄ ሥራ ለመጀመር ዝግጅት ጀመርኩ፡-

ከእነ አቶ በትሩ አድማሴ ጋር የሶዶን ከተማ ጎብኝተን ወደ አዲስ አበባ የተመለስን እለት ምሽቱንና ሌሊቱን ጭምር ወደ አውራጃው ሔጄ የምሠራቸውን እያሰላሰልኩ የሶዶን ከተማ ተዘዋውረን ስንጎበኝ እንዲሁም ከሻሸመኔ ወደ ሶዶ ከተማ ስንሔድና ስንመለስ የአውራጃውን ሰሜናዊ ክፍል ተመልክቼ በተገነዘብኩት ላይ ተመሥርቼ ሰባ ሰባት የአስተዳደር ሪፎርሞችንና የልማት ሥራዎችን ዝርዝር ስመዘግብ አደርኩ። በዚህ ሁኔታ ሌሊቱን እንቅልፍ ሳይወስደኝ መቼ በነጋ እያልኩ አደርኩና ጠዋት ወደ ቢሮ ሥራ የመግቢያው ሦስት ሰአት ሳይደርስ ወደ አገር ግዛት ሚኒስቴር ሔድኩ።

አገር ግዛት ሚኒስቴር ስደርስ ቀደም ብለው ከገቡት ተላላኪዎች ውስጥ አንዱን የአስተዳደር ዋና ዲሬክተር የነበሩት ፊታውራሪ ታፈሰ ጠብቄን ቢሮ ጠየቅሁትና ቢሮዋቸውን ሲያሳየኝ በር ላይ ተቀምጬ ለመጠበቅ ብሞክር ተላላኪያቸው ተራ ባለጉዳይ መስየው በር ላይ ተቀምጦ መጠበቅ እንደማይቻል ነግሮኝና እልፍ ብዬ እንድጠብቅ ጠየቀኝ። ለግል ጉዳዬ ሳይሆን ለሥራ የምፈልጋቸው መሆኔንና ማንነቴን ስገልጥለት ትቶኝ ሔደ። ተላላኪው ትቶኝ የሔደው ዋና ዲሬክተሩ ቢሮዋቸው በር ሳይደርሱ ለመንገር ፈልጎ ኖሮ ነግሯቸው ተከታትለው ሲመጡ በር ላይ ተቀምጬ አዩኝ። እየተዛባ ይወራ የነበረውን የበላዬን ምክትል ሚኒስትር የቀጣሁ ደፋር ሰው መሆኔን ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የተሻርኩ እለትም በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት የፈጸምኩት ድፍረትና ከአዲስ አበባም መጥፋቴ እየተጋነነ እየተዛባ ተነዝቶ ስለነበረ የኔ እቢሮዋቸው በር ላይ ተቀምጦ መጠበቅ ፊታውራሪ ታፈሰን ገርሞዋቸው ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት አላውቅም ሲያዩኝ ደነገጡና ቆም ብለው ምን ነው? አሉኝ። «ላነጋግርዎት ፈልጌ ነው» አልኳቸውና አስከትለውኝ ቢሯቸው ገባን። ገብተን

*እንደተቀመጥን የወላይታ አውራጃ ገዢ ሆኜ መሾሜን ሳይሰሙ እንዳልቀሩ ገልጬ አገር ግዛት መዝገብ ቤት የሚገኘውን ስለአውራጃውና ስለሠራተኞቹ ለማጥናትና ለማወቅ ስለምፈልግ ስለአውራጃው የሚገልጹ ሰነዶችንና የሠራተኞች የግል ማህደራቸውን ከመዝገብ ቤት ሳላወጣ እዚያው ሆኜ እንዳጠና እንዲፈቀድልኝ፣ እሳቸውም ስለአውራጃው የሚያውቁትን ያህል ጊዜ ሰጥተውኝ እንዲያስጠኑኝ ከአገር ግዛት ጀምሮ የጠቅላይ ግዛቶች፣ የአውራጃ፣ የወረዳና የምክትል ወረዳ ደንቦችንና በየጊዜው የተላለፉትን ትእዛዞችና መመሪያዎች ተገልብጠውና ተጠርዘው እንዲሰጡኝ፣ እንዲሁም ከአውራጃው ዋናው ባላባት ከፊታውራሪ ደስታ ጦና ጀምሮ በሕግ መወሰኛና በሕግ መምሪያ (በፓርላማው) ውስጥ ያሉትን ባላባቶችና ሌሎችም ካሉ እቢሮዋቸው ድረስ እንዲመጡ ጋብዘው እንዲያስተዋውቁኝና ስለአውራጃው አስተዳደርና ልማት እንዲያወያዩን ጠየቅኳቸው። ባቀረብኩላቸው ጥያቄዎች በጣም ተደስተውና ተገርመው እስካሁን ጠቅላይ ገዢዎችም ሆኑ አውራ ገዢዎች ሲሾሙ ስለራሳቸው ጉዳይ እንጂ ስለሚሠሩት ሥራ ጠይቀዋቸው ስለማያውቁ እኔ ያቀረብኳቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢና የሚያስደስቱ መሆናቸውን ገልጠውልኝ ሁሉንም እንደሚፈጽሙልኝ ቃል ገብተው አበረታቱኝ። ከመለያየታችን በፊት የሹመቱ እለት የፈጸምኩትና ከአዲስ አበባ ከተማም መጥፋቴ ተጋኖ የተወራው እውነት መሆኑን ጠየቁኝ። ተጋኖ የተወራውን ሳይሆን ያደረኩትን ስነግራቸው እንደድሮው ቢሆን ይኸም ቢሆን የሚያስገርፍ፣ በዚያን ጊዜም ቢያንስ የሚያስግዝ፣ መሆኑን ገልጠውልኝ፣ ለወደፊቱ እንዳልዳፈርና እንዳልቀጣ መክረውኝ ተለያየን።*

*ከፊታውራሪ ታፈሰ ጠብቄ ጋር ተገናኝቼና ተዋውቄ ጥያቄ ካቀረብኩላቸው ቀን ማግስት ጀምሮ መዝገብ ቤት እየገባሁ፣ የአውራጃ ግዛቱን ሠራተኞች ስም የሥራ መደባቸውን፣ የሕይወት ታሪካቸውንና ሌላውንም በየግል ማሕደራቸው ማግኘት የቻልኩትን ጠቃሚ መረጃዎች ማስታወሻ እየያዝኩ አጠናሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላም፣ የተገኙትን ያህል ደንቦችና ትእዛዞች ተጠርዘው ተሰጡኝ። በፓርላሜንት (በሕግ መምሪያና በሕግ መወሰኛ) ያሉትን ሰዎች ፊታውራሪ ታፈሰ እቢሮዋቸው ጋብዘው ለግማሽ ቀን ያህል ስብሰባ አድርገን ስለአውራጃ ግዛቱ አስተዳደር መሻሻልና ልማት ተወያየን። በዚህ ሁኔታ በአገር ግዛት ሚኒስቴር የተጠቀሱትንና ሌሎች ጉዳዮች ካጠናሁና መረጃዎችንም ሰብስቤ ካጠናቀቅኩ በኋላ፣ በተጨማሪ በየልማት ሚኒስትሮችና ድርጅቶች እየተዘዋወርኩ አነጋገርኩ። ካነጋገርኳቸው መስሪያ ቤቶች ውስጥ ፊታቸውን ካዞሩብኝ (እንደ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ያሉት) በስተቀር፣ ሌሎቹ ከሞላ ጎደል በአርኪ ሁኔታ አነጋገሩኝ። በተለይ ቴሌኮሚኒኬሽንና ባንክ የመጀመሪያዎቹ አጥኚ ቡድኖች ወደ አውራጃው ለመሔድ መመደባቸውን ስለገለጡልኝ ለአውራጃው ልማት እንደተመኘሁት መልክ ሊይዝልኝ እንደሚችል ፍንጭ አገኘሁና ደስ አለኝ።*

## ለአጭር ጊዜ ጥናት በኦፊሴል ወደ ሶዶ ከተማ ሔድኩ፡-

የአውራጃውን ጽህፈት ቤት ሥራ ለማከናወንና የአስተዳደር ሪፎርም ለማድረግ፣ እንዲሁም የልማት ሥራዎችን ለመሥራት፣ የአውራጃው ጽህፈት ቤትና የምኖርበት ቤት ለሥራና ለኑሮ (በዝቅተኛ ደረጃ እንኳዋን ቢሆን) አመቺ መሆናቸውን ለማየት እና ሁኔታውን እንደገና አጥንቼ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስና የሚቻለውን ያህል ማሟላት እንድችል በኦፊሴል ወደ ሶዶ ከተማ ተጓዝኩ፡፡

ቀደም ብሎ ከእነ አቶ በትሩ አድማሴ ጋር ባደረግነው ምስጢራዊ ጉብኝት ወቅት የአውራጃ ገዢው መኖሪያ ቤት የትኛው እንደሆነ አውቀው ስለነበረ፣ ሶዶ ከተማ ስደርስ፣ ሰው መጠየቅ ሳያስፈልገኝ፣ ከተማው መግቢያ ላይ አውራ ጎደናው ዳር ወደሚገኘው የአውራጃው ገዢ መኖሪያ ቤት በቀጥታ ሔድኩ፡፡ በሩ ላይ ስደርስ መኖሪያ ቤቱን የሚጠብቁ ፖሊሶች ማንነቴን ሲያውቁ፣ የአጥሩን በር ከፈቱልኝና ግቢው ውስጥ ገብቼ፣ ወደ አንድ ጎን አዘንብላ ለመውደቅ ጥቂት የቀራት የመኪና መጠለያ ውስጥ መኪናዬን አቆምኩና አብረውኝ የነበሩ ወንድና ሴት ሠራተኞች ፖሊሶች እየረዷቸው፣ እቃ ሲያወርዱ፣ የቤቱ ቁልፍ እማን ዘንድ እንደሆነ ስጠይቅ፣ የአውራጃው ዋና ጸሀፊ ዘንድ ስለሆነ ቁልፉን ይዞ እንዲመጣ የተላከበት መሆኑን፣ አንዱ ፖሊስ ነገረኝ፡፡

በአገር ግዛት ሚኒስቴር መዝገብ ቤት ያለውን የአውራጃውን የሠራተኞች የግል ማህደር ሳጠና የአውራጃው ዋና ጸሀፊ ስም አቶ ከበደ ብርሃኔ ስለሚል ሐረር ጠቅላይ ግዛት የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዲሬክተር ሆኜ ስሠራ የእኔ መረጃ ሠራተኛ ነኝ እያለ ሲያጭበረብር ተደርሶበት ብቻ ሳይሆን በእንደዚህ ያለ የማጭበርበር ሥራው ክቡር እንደራሴውም ደርሰውበት ከሥራ የተባረረው አቶ ከበደ ብርሃኔ ይሆን ወይስ ስመ ሞክሼ ነው በሚል ተጠራጥሬ እዛው አገር ግዛት ሚኒስቴር ከፔርሶኔል ክፍል ስጠይቅ ያው የማውቀው ከበደ ብርሃኔ እንደሆነ አረጋግጬ ስለነበረ መምጣቱን ስጠባበቅ ቆየሁ፡፡ ይህ በአጭበርባሪነት ተወንጅሎ ከሥራ የተባረረ ሰው ከእኔ ጋር የሚሠራ ሰው መሆኑ ብቻ ሳይሆን የምኖርበትን ቤት ቁልፍ በመያዙና ከአውራጃው ሠራተኞች ውስጥ መጀመሪያ የማገኘው ሰው ሆኖ በመገኘቱ ድንጋጤም ጭንቀትም አደረብኝና ሃሳብ ውስጥ ገብቼ ሳወጣና ሳወርድ ከቁመቱ ማጠር በስተቀር በፍጹም ያ የማውቀውን ከበደ ብርሃኔን የማይመስል በጣም ወፍራምና ፊቱ ያወለወለ መኩዋንንት የቤቱን በር ቁልፍ መክፈቻ ይዞ መጣ፡፡ እንደደረሰና እንዳየኝ እጅ ነስቶ ጫማ ለመሳም ከጅሎት እንደማጎንበስ ብሎ ሲጠጋኝ ወደኋላዬ ፈግፈግ እንደማለት አልኩና በሁኔታዬ ያሰበውን እንዲፈጽም የማልፈልግ መሆኔን ሲያውቅ በደፈናው ሰላምታ ሰጥቶኝ ወደ በሩ ሔደና ከፈተ፡፡

በሩ እንደተከፈተ አብረውኝ የሔዱት ሠራተኞቼ ፖሊሶችና የአውራጃው ዋና ጸሀፊ እየተረባረቡ መስኮቶችን ከፍተው ከውጪ ቅጠል በመቁረጥ ጭምር ከአዲስ አበባ ይዘነው በሔድነው የቤት ወለል መጥረጊያ ቤቱን ሲያጸዱ እኔ

እመኪና ውስጥ ገባሁና ሳነባብብ ቤቱን አጽድተው እንደጨረሱ እቃችን ገባና ፖሊሶች ወደ ጥበቃ ሥራቸው ሔዱ። አቶ ከበደ ብርሃኔ እጅግ ጮሌና አጭበርባሪ መሆኑን ስለማውቅ ምን እንደማደርግ በማውጣትና በማውረድ ላይ እንዳለሁ ወደ እኔ መጣና እቤት ገብቼ እንዳርፍ ጠይቶኝ ወደ ቤት ስገባ እሱም ተከትሎኝ ገባና የምፈልገውን እንዳዘው ጠየቀኝ። በጠዋት ቢሮ ስለምገባ በአውራጃው ውስጥ የሚገኙትን ሠራተኞች፣ የየሚኒስቴሩ ተጠሪዎችና የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ በሦስት ሰአት አውራጃው ጽሕፈት ቤት ቢሮ እንዲገኙና እንድንተዋወቅ እኔ ግን በሁለት ሰአት ቢሮ ስለምገባ የጽሕፈት ቤት ሠራተኞችን ከአገር ግዛት መዝገብ ቤት ከየግል ማህደራቸው እንዳጠናሁት ስማቸውንና የሥራ መደባቸውን እየጠቀስኩ ቀደም ብለው ገብተው እንድንተዋወቅ ለሁሉም እንዲነግራቸው መመሪያ ሰጠሁት። የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ስምና ሥራ እንዴት ሊያውቅ ቻለ እነሱን ካወቀ እኔንም ሳያውቀኝ አልቀረም ብሎ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት አላውቅም ደንገጥ ሲል ተመለከትኩት። ሠራተኞቹ በዚያኑ እለት እቤት መጥተው እጅ እንዲነሱና እንዲተዋወቁ ፈልጎ እያቅማማ መጠየቅ ሲቃጣው ቆጣ ብዬ በዚያን እለትም ሆነ በሌላ በማንኛውም ቀን ለሥራ ጉዳይም ሆነ በሌላ ምክንያት እመኖሪያ ቤቴ ግቢ ማንም ሰው እንዲገባ የማልፈቅድ መሆኔንና ይኸንኑ ግቢውን ለሚጠብቁ ፖሊሶች ትእዛዝ የምሰጥ መሆኔን ገልጬለት የግቢውን ጠባቂ ፖሊሶች አላፊ እንዲጠራልኝ ነግሬው ጠራው። በሥራ አመካኝቶም ሆነ በሌላ ሁኔታ ሠራተኛም ሆነ ባለጉዳይ እመኖሪያ ቤቴ ግቢ እንዳይገባ ዋናው ጸሀፊ ፊት ግቢውን ለሚጠብቁ ፖሊሶች ኃላፊ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቼ ዋናው ጸሀፊ እጅ ነስቶ ፖሊሱ ሰላምታ ሰጥቶ ሔዱ። እኔም የማውቀው ከበደ ብርሃኔ መሆኑን ለራሱም ሆነ ለሌሎች ሳልናገር ለጥቂት ወራት አብረን ስንሠራ ቆየን።

የአውራጃው ገዢ መኖሪያ ቤት ጠላት በዕቅድ በሸክላ ዕጡብ የሠራው ስለሆነ እየተጠገነ በጽዳት ቢያዝ ለዚያ ገጠር ከተማ ቀርቶ መጠነኛ ቤተሰብ ላለው በአዲስ አበባ ለሚኖር ባለሥልጣን የማያንስ ነው። ቤቱ ሁለት መኝታ ክፍሎች ሳሎንና የማዕድ ሁለት የተያያዙ ክፍሎች የመጸዳጃና የወጥቤት ሁለት ክፍሎችና አንድ ከወጥቤቱ ጋር የተያያዘ አነስተኛ የወጥቤት እቃና የምግብ ጥሬ እቃዎች ግምጃ ቤት አሉት። በተገለጠው ሁኔታ በእቅድ በዕጡብ ግንብ የተሠራው ይህ ቤት በጥገናና ጽዳት እጦት በሚያሳዝን ሁኔታ ተጎሳቁሏል። የቤቱ ጣሪያ ኮርኒስ ውስጡ የሌሊት ወፎች መራቢያ ሆኖ ግርግዳዎቹ ተቀራርፈው በጣውላ የተሠራው ወለል እንጨቱ የጣውላነቱን መልክ ለውጦና ተፈነቃቅሎ ቤቱ በአጠቃላይ ጉስቁልቁል ብሎ ሳየው የመኖሪያ ቤት ችግር ይገጥመኛል ብዬ ደንገጥ ማለቴ አልቀረም። መጸዳጃ ቤት የሚገኙት የገላ መታጠቢያ ገንዳ (ባኞ) የእጅ መታጠቢያው (ሲንክ)፣ እዳሪ መውጫው ሳሕን ነጭነታቸውን ለውጠው ወደቡናማነት ተለውጠዋል። የተሰባበሩና የተበጣጠሱ የሳሎንና የማዕድ ቤት እቃዎች ተወነጋግረው ተቀምጠዋል። ወጥቤቱ ባዶ ሲሆን ግድግዳው ላይ ያሉት ርዝራዥ ቧንቧዎች ቀደም ብሎ ወጥቤቱ የተሟላ

እቃዎች እንደነበሩት ያመለክታሉ። እኛ ኢትዮጵያውያን እጅ ከገባ በኋላ ግን ምንም ጥገና አለማድረጋችን ብቻ ሳይሆን አለአግባብ ስለተጠቀምንበት ቤቱ የሰው መኖሪያነቱን ለውጦ የሌሊት ወፎች መራቢያ እንዲሆን አድርገን በውስጡ የሚገኙትን እቃዎች አውድመን ለዓይነት የቀሩትም ለብዙ ጊዜ ጽዳታቸው ስለተጓደለ ቀለማቸውን ለውጠውና ተሰባብረው ምንነታቸውም እንዳይታወቅ አድርገናቸዋል። የሚገርመው በዚህ ሁኔታ የተጎሳቆለ ቤት በትልቁ የመኝታ ክፍል ውስጥ ፍራሹ የተሠራበት ጥጥ ጉዋጉሎ ይጉርበጥበጥና ጨርቁ የወየበና የተበላሻ ይሁን እንጂ አልጋው የሞዝቮልድ ድርጅት ከባህር ማዶ እያስመጣ ይሸጠው የነበረ የቤተሰብ ሰፊ አልጋ በጥሩ ሁኔታ መገኘቱ ነው። ይህን የተጎሳቆለ ቤት አሳድሼ የቤት እቃዎቹንም ቀስ በቀስ በአዲስ እየተካሁ ሳሚላ ቀደም ብሎ የነበረውን ይህን አልጋ ሳልለውጥ እስከመጨረሻው ተጠቅሜበታለሁ።

የቤቱ ጣሪያ ኮርኒስ ውስጥ የተከማቸው የሌሊት ወፎች ኩስና ሽንታቸው ትንፋግ እቤት ውስጥ መቀመጥ ስለማያስችል በረንዳ ላይ ተቀምጬ ማስታወሻዬን ሳሚላ መሽና ወደ ቤት ገባሁ። ሠራተኞቹ በቡታ ጋዝ የሚሠራውን መብራት ለኩሰውት ክፍሎቹ ከመተንፈጋቸው በስተቀር እንግዳ ቤቱና ማዕድ ቤቱ ጥሩ ብርሀን አግኝተዋል። ፖሊሶች ከአቅራቢያው ወንዝ በበርሜል እያስገፉ ያስመጡልን ውሃ በመጸዳጃ ቤትና ወጥቤት በየባልዲው ተሞልቷል። ውሀው ከአዲስ አበባ የቧንቧ ውሀ ጋር ሲመዛዘን መልኩም ሆነ ንጽህናው ቅር የሚያሰኝ ከመሆኑ በስተቀር በውሀ በኩል ለጊዜው አልተቸገርንም። ለሦስት ቀን ያህል የሚበቃ እንጀራ ወጥና አንድ አገልግል ፍትፍት አለን። ሳይበላሹ የሚቆዩ ለሳምንታት የሚበቁን ቆሎ ዳቦ የቅቤና የማር ጭኮና ቅይጥ ቆሎ ደረቅ ምግቦች የአምቦ ውሀና ለስላሳ መጠጦች ይዘን ስለሔድን ለጥናት ሶዶ ከተማ ለሁለት ሳምንት ያህል ስንቆይ በምግብ በኩል ችግር አልገጠመንም። ገጥሞን የነበረው ችግር የቤቱ ጣሪያ ኮርኒስ ውስጥ የተራቡት የሌሊት ወፎች ኩስና ሽንት ትንፋግ ፍሊት ቢረጭም አልበግረው ማለቱና ለዐይን ሲይዝ ጀምሮ የሌሊት ወፎቹ ከጣሪያው ሲወጡና ሲገቡ የሚሰማው ኩዋኩዋታና አስቀያሚ ሲጥ ሲጥ የሚል ያይጥ ድምጽ ዓይነት ድምጽ መተኛት ቀርቶ ቤት ውስጥ መቀመጥም የሚያስጠላ መሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ ቤቱ ተከፍቶ ከተጠራረገና እቤት ገብቼ እተዘዋወርኩ ክፍሎቹን ከተመለከትኩ በኋላ ከቤት ወጣሁና እበረንዳው ላይ ተቀምጬ ቀደም ብዬ የጀመርኩትን ማስታወሻ እያየሁና እራቴንም እዚያው ቀማምሼ እዚያው እስከ ውድቅት ቆይቼ ወደ መኝታ ቤት ገባሁና ተኛሁ። ከሻሸመኔ ሶዶ ያለው መንገድ በጣም ያንገላታ ስለነበር አልጋ ላይ ጥቂት ስገላበጥ እንደቆየሁ ምን ጊዜ እንደወሰደኝ ሳላውቅ ትንፋጉን የሚያሸንፍ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለና ከጎኔ ሳልገላበጥ አድሬ እንደልማዴ አሥራ አንድ ሰአት ገደማ ነቃሁ። ወደ መጸዳጃ ቤት ገብቼ ተጠዳዳሁና በጣሳ ከባልዲ ውስጥ ውሀ እየጨለፍኩ ታጥቤና ልብሴን ለብሼ ስጨርስ አሥራ ሁለት ሰአት ገደማ ሆነና ወገግ አለ። ከቤት

ወጥቼ ግቢው ውስጥ እየተዘዋወርኩ ሳይ በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ ማስታወሻዎቼን እየተመለከትኩና የአቶ ከበደ ብርሃኔን ነገር ሳሰላስል ሁለት ሰአት ሆነና ከመኖሪያ ቤቱ ሃምሳ ሜትር ያህል ወደሚርቀው አውራጃው ጽሕፈት ቤት ሔድኩ፡፡

አውራጃው ጽሕፈት ቤት ስደርስ የጽህፈት ቤት ሠራተኞች እጽህፈት ቤቱ በር ላይ ግራና ቀኝ ቆመው ይጠብቁኝ ስለነበር ስደርስ በአቶ ከበደ ብርሃኔ አስተናባሪነት ተዋወቅኩና በእሱው እየተመራሁ መጠነኛ ስፋት ያለው የአውራጃው ገዢ ቢሮ ገባሁ፡፡ ቀና ብዬ ሳይ የክፍሉ ግርግዳ ከፍ ያለ በመሆኑ ረጅም መጥረጊያ አጥተው ይሁን ወይም ጠጋ ብሎ የሚያየው ሰው ጠፍቶ እንደሆነ ሳላውቅም በኮርኒሱና በግርግዳው መገናኛ ዙሪያውን የሸረሪት ድር ግጥም ብሎበት መራቢያቸው ሆኗል፡፡ ቁጥራቸው ስድስት ያህል የሚሆኑት ሠራተኞች ገቡና እንደቆምኩ ጥቂት ከተወያየን በኋላ የየሚኒስቴሩን ተጠሪዎች ለመተዋወቅና ለማነጋገር የቀጠርኳቸው ስለሆነ ከነሱ ጋር ስጨርስ በየሥራቸው ላይ እንዳሉ በቢሯቸው እየተዘዋወርኩ የማያቸውና የማነጋግራቸው መሆኔን ገልጬላቸው አሰናበትኳቸው፡፡

ሦስት ሰአት ደረሰና የየሚኒስቴሩ ተጠሪዎች ስለመጡ ገቡና አሁንም በአቶ ከበደ ብርሃኔ አስተናጋጅነት ተዋወቅን፡፡ ባደረግነው ውይይት የመጣሁት አጭር ጥናት አድርጌ ለመመለስ መሆኑን ገለጥኩላቸው፤ እኔ የምፈጽምላቸው ጉዳይ እንዳላቸው ስለሥራቸውም ዋና ዋናዎቹን እንዲገልጡልኝ ጠይቄያቸው ጥሩ ትምህርት ያገኙሁበት ረጅም ሰአት የፈጀ ውይይት አድርገን አሰናበትኳቸው፡፡ ወዲያው ሦስት ጠባብ ክፍሎች ውስጥ የሚሠሩትን የጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች በየሥራ ክፍላቸው እየተዘዋወርኩ ስለ ሥራቸውና በሥራቸው ላይ ስለሚገጥሙዋቸው ችግሮች እንዲገልጡልኝ ለየብቻቸው እየጠየኩ በሰፊው አነጋገርኳቸውና ከሞላ ጎደል በጽህፈት ቤቱ ስላሉ ዋና ዋና ችግሮች አወቅሁ፡፡ ለምሳሌ የጽህፈት ቤቱ የዓመት የሥራ ማስኬጃ ሦስት መቶ ብር ያህል ስለሆነ ከባለጉዳይ የወረቀትና የፋይል መግዣ ገንዘብ እየተጠየቀ ወይም ይዞ እንዲመጣ እየተደረገ እንደሚስተናገድ ተነገረኝ፡፡ ይህ ሁኔታ በደርግም ሆነ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት በአዲስ አበባ ከተማ ሳይቀር በአንዳንድ መሥሪያቤቶች እስካሁን የሚፈጸም ሲሆን ይህ አሠራር ባለጉዳይን ለመበዝበዣ በር የሚከፍት ብቻ ሳይሆን ጉዳዮች ቶሎ እንዳይፈጸሙ የሚያደርግና ባለጉዳይን የሚያጉላላ ነው፡፡

ሌላው ችግር በገጠር ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ጭምር በዚያን ዘመንና አሁንም በአንዳንድ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ያለው የባለጉዳዮችን ጉዳዮች የያዙ ፋይሎች መደርደሪያ ላይ ሳይሆን በየግርግዳው ሥር ቦታ ሲጠፋ ወለል ላይ ጭምር ተመሰቃቅለው ስለሚቀመጡ ማህደሩን ቶሎ አግኝቶ ባለጉዳዮችን ማስተናገድ ስለማይቻል ይህን ምክንያት በማድረግ ባለጉዳዮችን ሆን ብሎ ለማጉላላት ወይም እጁን እንዲዘረጋ ለማድረግ ጥሩ ምክንያት ነው፡፡በየክፍሉ

እየተዘዋወርኩ የአውራጃውን ጽህፈት ቤት ሠራተኞች በሥራቸው ላይ እንዳሉ ሳነጋግራቸው እንደተጠቀሱት ያሉ ችግሮችና ሌሎችንም ለሥራ ቅልጥፍና እንቅፋት የሚሆኑ ሠራተኞች ሆን ብለው ባለጉዳዮችን ለማጉላላት በር የሚከፍቱላቸው ወይም ባለጉዳዩ እጁን እንዲዘረጋላቸው የሚያደርጉትን ብዙዎቹ በቀላሉ ሊሻሻሉ የሚችሉ የጽህፈት ቤቱን ዋና ዋና ችግሮች ምናልባት ከሁለት ሰአት በማይበልጥበት ጊዜ ውስጥ መረዳት ቻልኩ።

የየሚኒስቴሩ ተጠሪዎችንም ሆነ የአውራጃውን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ሳነጋግር የቤቱ ጣሪያ ኮርኒስ ውስጡን መኖሪያና መራቢያ ያደረጉት የሊት ወፎች ኩስና ሽንት ትንፋግ ከመኖሪያ ቤቱ በበለጠ ሁኔታ ስለሚተነፍግ የየሚኒስቴሩ ተጠሪዎችንና የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ባነጋገርኩበት ወቅት ጣልቃ እያስገባሁ ለምን ወፎቹን እንዳላስወገዷቸው ስጠይቃቸው ይሰጡኝ የነበረው መልስ ወፎቹን ማስወገድ የማይቻል በመሆኑ ከሊ.ጋባ በየነ አባ ሰብስብ ትምህርት ቤት በስተቀር በከተማው ውስጥ በሚገኙት መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የሌሊት ወፎች በየጣሪያው ውስጥ እየተራቡ ከባድ ችግር መፍጠራቸውን ነገሩኝ። ካሰቡበት ለዚህ ችግር መፍትሄ ማግኘት ስለሚችሉ የተገነዘብኩት ሠራተኞቹ ምን ያህል ለሥራ ግዴለሽ እንደሆኑ ስለሆነ ሥራ ስጀምር መጀመሪያ የሌሊት ወፎቹን እንዴት በቀላሉ ማስወገድ እንደሚቻል የማሳያቸውና ለሥራ ምን ያህል ግዴለሽ እንደሆኑ እንዲገነዘቡት ስለማድረግ በሃሳቤ አቅጄ ቆየሁ።

ያ በሊ.ጋባ በየነ አባሰብስብ ስም የአዲስ አበባውን የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ከሚያስታውሰው በጥሩ ሁኔታ በጥርብ ድንጋይ ከተሠራው ትምህርት ቤት በስተቀር በሶዶ ከተማ የሚገኙት የአውራጃው ጽህፈት ቤት የፍርድ ቤት ግምጃ ቤትና የፖሊስ ጣቢያ ጽሕፈት ቤቶች እንደ አውራጃ መኖሪያ ቤት ሁሉ ጠላት በሸክላ እጡብ በዕቅድ የሠራቸው ሕንጻዎች ናቸው። እነዚህ ሕንጻዎች በየጊዜው መጠነኛ ጥገናና ጥበቃ ቢደረግላቸው ለምሳሌ ከሌሊት ወፎች መራቢያነት ቢጠበቁ እነዚህ በመፈራረስ ላይ የሚገኙ ሕንጻዎች አዲስ አበባ ከሚገኙት መሥሪያ ቤቶች ሕንጻዎች የማይተናነሱ ናቸው። በማግሥቱና በሚቀጥሉት ቀናት ወረዳና ምክትል ወረዳ ገዢዎች እያስጠራሁ ሶዶ ከተማ የሚገኙትን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ወህኒ ቤት እየተዘዋወርኩ ከጎበኘሁና ሠራተኞቹን አነጋግሬ ጥናት ካደረግኩ በኋላ ወደፊት በአውራጃው ለምፈጽማቸው የአስተዳደር ሪፎርሞችና የልማት ሥራዎች መሠረት ስለሚሆኑኝና መጀመሪያ ስለምፈጽማቸው ሥራዎች ግንዛቤ አግኝቼ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

## ስለሚሟሉልኝና ስለምፈጽማቸው ሥራዎች ማስታወሻ አቀረብኩ፡-

ከሶዶ ከተማ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለስኩ በዚያን ጊዜ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ጠቅላይ ገዢና የግርማዊነታቸው የኤርትራ ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ

የነበሩት ክቡር ራስ አንዳርጋቸው መሣይ የሚኖሩት አዲስ አበባ ከተማ ስለነበረ በመጀመሪያ ምስጢራዊና በሁለተኛው አጭር የጥናት ኦፊሴላዊ ጉብኝቶች ስለተገነዘብኩትና እንዲሁም በጣም አስፈላጊ ስለሆኑት ለአውራጃው ጽሕፈት ቤት ለመኖሪያ ቤቴና ለብዙ ጊዜ ጥገና ሳይደረግለት ቆይቶ በጣም ለተጎዳው ላንድ ሮቨር መኪና ማደሻ ሦስት ሺህ ብር ያህል እንዲሰጠኝ እንዲሁም ወደፊት ልሠራቸው ካቀድኳቸው የአስተዳደር ሪፎርሞችና የልማት ሥራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ማስታወሻ አቀረብኩላቸው፡፡ ስለእድሳቱ ገንዘብ ለአገር ግዛት ሚኒስቴር ማስታወሻ እንዳቀርብና እሳቸውም በማስፈጸሙ በኩል የሚረዱኝ መሆናቸውን ነግረውኝ ሃሳባቸውን በጽሁፍና በፊርማቸው እንዲያሰፍሩበት ባቀረብኩላቸው የአስተዳደር ሪፎርምና የልማት ሥራዎች ማስታወሻ በየገጾቹ በቀኝ በኩል ባለው አምድ ክፍት ቦታ ላይ ቆራጥና ወሳኝ መሆናቸውን በሚገልጡ ቃላት «ተስማምቻለሁ ይህን የሚቃወም ቢኖር ኢትዮጵያዊ አይደለም» የሚሉና በሌሎች ተመሳሳይ ቃላት ባቀረብኩዋቸው ሀሳቦች በሙሉ ተስማምተውና ፊርመው በማግሥቱ ማስታወሻውን መልሰው ሰጡኝ፡፡ ውሳኔያቸውን ሳየው እኛ በአስተዳደር ጎታችነታችውና ኋላ ቀር አስተሳሰባቸው የሚታሙት ለካስ ቆራጥ ውሳኔ ሰጪ ኖረዋል በማለት በሀሜት እሰማቸው የነበረውን የተዛባ አስተያየት ለወጥኩ፡፡ ይህ አጋጣሚ በአንጻሩ ያስተማረኝ ትጉህ ሠራተኛ አገር ወዳድና ተራማጅ ለመምሰል የበላዮቻቸውን የሚያሙ ግን ሥሩ ሲሉዋቸው ግራ የሚገባቸው ሰነፎች በአፍ እንጂ ሆዳቸው ከሞላ ስለአገራቸውና ወገናቸው ዕድገት ግድ የሌላቸው አስተሳሰባቸው በተማሪ ቤት ከተነገራቸው ወይም ካነበቡት የቀነጫጨቡትን ጥራዝ ነጠቅ አስተሳሰብ በቃል ከመናገር በስተቀር እውነተኛው አስተሳሰባቸው ግን ኋላ ቀርና ባዶ የሆነውን ሀሜተኞች እንድታዘባቸው አድርጎኛል፡፡ ለክቡር ራስ አንዳርጋቸው ባቀረብኩት ማስታወሻ እንዲስማሙ ከጠየቅኳቸው የአስተዳደር ሪፎርሞችና የልማት ሥራዎች ውስጥ ለምሳሌ ጠቅላይ ግዛቱና አገር ግዛት ሚኒስቴር ደርሶ ሳይፈቅድ ለጭሰኞች ርስት እንድሰጥ፣ ከአውራጃው ውጪ ጭምር ጭሰኞች እያመጣሁ ከአውራጃው ተወላጆች ጋር እያሰባጠርኩ እንዳሰፍር፣ ለሕዝቡ አስተዳደር በሚያመች ሁኔታ ጥናት እያደረግኩ ወረዳዎችን ከወረዳ፣ ምክትል ወረዳዎችን ከምክትል ወረዳ እየቀላቀልኩና እየከፋፈልኩ እንድመድባቸው እድሜያቸው የገፋውን በጡረታ፣ ሌሎች ምንም ችሎታ የሌላቸውን በአርበኝነት፣ በአገር ተወላጅነትና በልዩ ልዩ አገልግሎት ምክንያት በወረዳና ምክትል ወረዳ ገዢነት የተመደቡትን በጡረታ እስኪገለሉ ደሞዛቸውን እያገኙ እንዲቀመጡና ካሉት ሠራተኞች ውስጥ የተሻሉትን እየመደብኩ እንድሠራ የሚሉ በዚያን ጊዜ እንኳን አውራጃ ገዢዎች ጠቅላይ ገዢዎች ለማድረግ የማይሞክሩትን ለሰሚው እንግዳና አስደንጋጭ የነበሩትን ጉዳዮች ለጠቅላይ ገዢው ማስታወሻ አቅርቤ ሁሉም አዎንታዊ መልስ አገኙ፡፡

ለጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ማስታወሻ አቅርቤ የሚያበረታታ መልስ ካገኘሁ በኋላ የሐረር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ በነበሩበት ጊዜ አይጥና ድመት ሆነን ለኖርነው

አሁን የአገር ግዛት ሚኒስትር ለሆኑት ክቡር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ ከጠቅላይ ግዛት እንደራሴ እንደተነገረኝ ስለእድሳት ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ጉዳዮች ጨምሬ እንዲፈጽሙልኝ ማስታወሻ አቀረብኩላቸው፡፡ እምቢ ለማለት ምንም ምክንያት የማያገኙለትን ለመኪናና ለቤት ማደሻ የጠየቅኩትን ከዚያው ከአውራጃው ሠራተኞች ደሞዝ ተመላሽ የሆነውን ገንዘብ እንድጠቀምበት ፈቅደው ለቀሩት ጥያቄዎች ፊታቸውን አዞሩብኝ፡፡ ለምሳሌ የሚንስቴሩ የቢሮ ዕቃዎች በአዲስ እየተለወጡ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ትልቁ ሕንጻ በስተምዕራብ የሚገኘው አሁን ተሻሽሎ ቪዛ መስጫ የሆነው ቤት ዙሪያውን ያለው ረጅም በረንዳ ላይ ተቀምጠው መተላለፊያውን ከዘጉት አሮጌ የቢሮ እቃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ እንዲሰጡኝ የሶዶን ከተማ ማሻሻል እንዲያመቸኝ የማዘጋጃ ቤቱን ሥራ ከኔ በፊት እንደነበሩት አውራጃ ገዢ ደርቤ እየሠራሁ ለሱ የሚከፈለው አበል ለእኔም እንዲከፈለኝ ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችና ሌሎችም ሲሆኑ ሁሉንም ሳይቀበሉኝ ቀሩ፡፡ የማዘጋጃ ቤቱን ሥራ ግን እንድሠራ ተስማምተው ስለአበሉ ግን ወልደሰማዕት አዲስ አበባ ሆኖ ያገኝ የነበረውን በቂ አበልና ደሞዝ ይዞ ወደ አውራጃው ስለሔደ የቀድሞው አውራጃ ገዢ ከማዘጋጃ ቤቱ ያገኝ የነበረው ተመላሽ እንዲሆን ጽፈው ለእኔ ግልባጭ አደረጉልኝ፡፡ አገር ግዛት ሚኒስቴር በረንዳ ላይ ተጥለው መተላለፊያ የዘጉትንና ፀሐይና የክረምት ዝናብ ወጨፎ እየተፈራረቁባቸው በመውደም ላይ የሚገኙት አሮጌዎቹ የቢሮ እቃዎች በሀራጅ ተሸጠው ገንዘቡ ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ይሆናል የሚል ምክንያት ሰጥተው ከለከሉኝ፡፡ እነዚያ እቃዎች ለብዙ ዓመታት በረንዳ ላይ ተከማችተውና ሰዎች እንደልባቸው እንዳይተላለፉ አውከው የክረምት ዝናብ ወጨፎና የጠዋት ፀሐይ ሲፈራረቅባቸው ኖረው እንደተባለው በሀራጅ ሳይሸጡ ባክነዋል፡፡

ለክቡር የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ባቀረብኩት ማስታወሻ የተፈቀደልኝን የደሞዝ ተመላሽ ገንዘብ ሚኒስቴር በበኩሉ እንዲፈቅድልኝና ለአውራጃው ግምጃ ቤት ትእዛዝ እንዲያስተላልፍልኝ እየተከታተልኩ በተጨማሪ ከሻሸመኔ ከተማ ወደ ሶዶ ከተማ ያለውን የበጋ ጥርጊያ መንገድ በጋ ከክረምት እንዲያገለግል ወደ ጠጠር መንገድ መለወጥ የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን ይሠራው የነበረው የጥርጊያው ሥራ አላባ ቁሊቶ ደርሶ ስለነበረ ሥራው እንዲፋጠን ልረዳ የምችልበት ነገር እንዳለ ለማነጋገር ከየሚኒስቴሩ ጋር በመፈራረስ ላይ የሚገኙት ሠራተኞቻቸው ለሚገለገሉባቸው ሕንጻዎች መጠነኛ የማደሻ ገንዘብ እንዲሰጡኝ በበጀት ተይዘው ያልተመደቡ ሠራተኞች ከዚያው ከአውራጃው አወዳድረን ሠራተኞችን መቅጠር እንዲፈቀድልን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአንድ ግሪካዊ ይመራ ከነበረው የተስቦ በሽታ መከላከያ ላቀድኩት የሕዝብ ማስፈር ሥራ የሚያገለግሉ በእርዳታ መጥተው መጋዘኑን ያጨናነቁ የወባ የተቅማጥና ሌሎች ልዩ ልዩ መድሃኒቶች እንዲሰጡኝ የእርሻ ልማት ለማካሔድ እንዲያመች የዓለም ማያ ኮሌጅ የአውራጃውን የእርሻ መሬት አፈር ምርመራ እንዲያደርግልኝ በስዊድናዊው ሚስተር ኖርበርግና በምክትላቸው አቶ ናይግዚ

ገብረመድህን የሚካሔደው ሕንጻ ኮሌጅ ለቤት ሥራ የሚያገለግሉ የሸክላ አፈሮችንና የመጠጥ ውሀ ማሻሻል ሕንጻ ኮሌጅ ጥናት እንዲያካሒድ በአቶ ሀብቱ እሸቴ የሚመራው ማዕከላዊ ስታቲስቲክ መሥሪያ ቤት ለአውራጃው ሕዝብ ቆጠራ የሚያገለግል ፎርም እንዲሰጠኝና ወደአውራጃው ለጥቂት ቀናት አሰልጣኞችን ልኮ የአውራጃውን ሠራተኞች አስተማሪዎችንና ተማሪዎችን ስለሕዝብ ቆጠራው ፎርም እንዲያሰለጥንልን በአቶ ደምሰው እሰየው ይካሔድ የነበረው አዲስ ተቋዋቁሞና ሠራተኞችን አሰልጥኖ ያለ ሥራ የተቀመጡት የካርታ ሥራ ባለሙያዎች በአቶ አሰፋ መንገሻ የሚመራው የውሀ ልማት የካርታ ስራ ባለሙያዎች ጋር ተባብረው የአውራጃውን ካርታ እንዲያነሱልን ከትንባሆ ሞኖፖል እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን ከየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ከየልማት ድርጅቶች ጋር ስነጋገርና ሳመቻች አዲስ አበባ ቆየሁ። በተጨማሪ መንግሥት ማሟላት የሚገባው ቢሆንም በባለሥልጣኖቹ በጎ ፈቃድ ማጣትና በዚያን ጊዜም በነበረው የመንግሥት የገንዘብ አቅም ማጣት ምክንያት እንዲያሟሉልኝ ማድረግ ያልቻልኩትንና ለኑሮዬና ለሥራዬ የግድ የሚያስፈልጉኝን እኔ ሳሟላ ቆየሁ። በዚህ ሁኔታ ከተዘጋጀሁ በኋላ ቀደም ብሎ የማውቀውን የአገሩ ተወላጅ የተዘነጋኝን የቤት እድሳት ባለሙያዎች አስከትዬ ወደ ሶዶ ተመልሼ ሔድኩና ሥራ ጀመርኩ።

## ለሥራ ተዘጋጅቼ ወደ ወላይታ ሶዶ ከተማ ሔድኩና ሥራ ጀመርኩ፡-

የወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪ ከሆንኩበት ከመስከረም 19 ቀን እስከ ታህሳስ ወር መጀመሪያ 1955 ዓ.ም ባለው ሁለት ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ ያህል ወደ አውራጃው ሔጄ በመጀመሪያው ጉዞዬ አንድ ቀን ለጥቂት ሰአታት በሁለተኛው ጉዞዬ ለወር ያህል በሶዶ ከተማ እየቆየሁ ጥናት ካደረኩና ሌላውን ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ ቆይቼ በታህሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ ወደ አውራጃው ሔድኩና ሥራ ጀመርኩ።

ሶዶ ከተማ እንደደረስኩ ቀደም አድርጌ በላኳቸውና እኔም ይዤያቸው በሔድኩት ለቤት ጥገና የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች አብረውኝ የሔዱት የቤት እድሳት ባለሙያዎች መጀመሪያ የመኖሪያ ቤቴን ከዚያ የአውራጃውን ጽህፈት ቤት እንዲያድሱ አመቻቸሁላቸውና እኔ ስለአውራጃው የጀመርኩትን ጥናት እያካሔድኩ የአስተዳደሩን የእለት ተለት ሥራና የማሻሻል ሥራ ከልማቱ ሥራዎች ጋር ተያያዝኩት።

ቀደም ብሎ ወደ አውራጃው በሔድኩበት ጊዜ የተዋወቅኳቸውና ለጥቂት ሰአታት የተወያየነው በሶዶ ከተማ ከሚገኙት ከአውራጃ ግዛቱ ጽህፈት ቤት ሠራተኞች የወረዳና ምክትል ወረዳ ገዢዎችና የየሚኒስቴሩ ተጠሪዎች ጋር ብቻ ስለነበረ ከከተማውና የአውራጃው ነዋሪዎች የታወቁ የአገር ሽማግሌዎች ጋር መተዋወቅና መወያየት ስለሚያስፈልግ እንዲጠሩ አደረግኩ። በአውራጃ ግዛቱ ውስጥ ያሉት የመንግሥት ሠራተኞች ዳኞች የሀገር ሽማግሌዎች

በተገኙበት በሶዶ ከተማ በሚገኘው በሊጋባ በየነ አባሰብስብ ትምህርት ቤት እንዲሰበሰቡ አድርጌ ካልተዋወቅኩዋቸው ጋር ከተዋወቅኩ በኋላ ስለ አውራጃው መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትእ ሥራ አፈጻጸምና ስለምንፈጽማቸው የልማት ሥራዎች ያለኝን ዓላማ በሰፊው ገለጥኩላቸው። በዚያን የሕዝብ ስብሰባ እለት የዚያን ዓይነቱ ስብሰባ ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ለተስብሳቢዎቹ እንግዳ ሆኖባቸው እንዳልቀረ የምገምተው «እኛ የመንግሥት ሠራተኞች ሁላችንም ተባብረን ሕዝቡ መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝና የኑሮ ደረጃውን ማሻሻል እንዲችል በቅንነትና በታማኝነት እናገለግለው። እኛ የመንግሥት ሠራተኞች የሕዝቡ አገልጋዮች እንጂ ተገልጋዮች አይደለንም። የሕዝብ የኑሮ ደረጃ የሚያድገው መንግሥት በሚፈጽማቸው አንዳንድ የልማት ሥራዎች ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ በራሱ ጥረት ራሱን በራሱ መርዳት ሲችል ነው። ሕዝቡ ይህን ጥረት ማድረግ የሚችለው መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝ ሲደረግ ነው።» የሚሉ አረፍተ ነገሮችን ማእከል ያደረገ ስለአስተዳደር ስለፍትህና ስለልማት ያደረኩት ሰፊ ንግግር ሳይሆን አልቀረም።

በአውራጃ በወረዳና በምክትል ወረዳ ጽሕፈት ቤቶች የምንገኝ የሕዝብ አገልጋዮች ባለጉዳዮችን እንድናገለግል በሰጠሁት መመሪያ ባለጉዳዮች ሲመጡ በትህትና ተቀብለን የመጡበትን ጉዳይ በቅንነት ወዲያው ፈጽመን እንዲሔዱ እንድናደርግ፤ ስለአሠራሩም ደንብ የሚዘጋጅና በተጨማሪ የሥራው አካሔድ እየታየ እንደሁኔታው በየጊዜው መመሪያ የሚሰጥ መሆኑን ገልጬ ወደ ጽህፈት ቤት የሚመጡ ባለጉዳዮች ወዲያው ጉዳያቸው ሊፈጸም ሲችል ቢዘገይባቸው ቀጠሮ ቢሰጣቸው ያልሆነ ቀላጤ ተጽፎላቸው ቢመላለሱ የተጻፈላቸውን ደብዳቤ መዝገብ ቤት የሚመጡ ባለጉዳዮች ቢመላለሱ የተጻፈላቸውን ደብዳቤ መዝገብ ቤት ወዲያው ወጪ አድርጎ ባይሰጣቸው ባለጉዳዮችን ካጉላላው ሠራተኛ ወይም ሠራተኞች ከደሞዛቸው ለተበዳዮቹ ኪሳራ እንደሚቆረጥላቸውና እንደጥፋቱም ሁኔታ ተጨማሪ ቅጣት እንደሚፈጸም አጠንክሬ ነገርኳቸው።

በዚያን እለት ስብሰባ ሌላው ለተሰብሳቢዎቹ እንግዳ ሳይሆንባቸው ያልቀረው ጉዳይ ስለግብር አከፋፈል የሰጠሁት መመሪያ ሳይሆን አልቀረም። ግብር ከፋዩ ግብሩን እንዲከፍል አዋጁ የሚያዘው ከየካቲት ወር ጀምሮ እስከ ሰኔ ሰላሳ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን ይህን አዋጅ ሽሬ ሕዝቡ ግብሩን መክፈል ያለበት ገንዘብ ማግኘት በሚችልበት ቅቤውን ማሩን እሸቱንና የመሳሰሉትን ሸጦ ገንዘብ በሚያገኝበት ከመስከረም ወር ጀምሮ እንጂ የእርሻ ውጤቱን ካሚጠጣና ለሌሎች አገልግሎቶች አውሎ ገንዘቡን ከጨረሰ ከየካቲት ወር ጀምሮ አይደለምና ወደፊት ግብር ከፋዮች ከመስከረም ወር ጀምሮ እንዲስተናገዱ መመሪያ ሰጠሁ። ከዚህ መመሪያ ጋር በማያያዝ ግብር ከፋዩ በብዛት መጥቶ ለአንድ ሰው ገንዘብ መቀበል ጫና በሚሆንበት ጊዜ ከእኔ ጀምሮ ግብር ከፋዩን እንድናስተናግድና ግብር ከፋዩ እንደመጣ ሳይጉላላ ወዲያው ግብሩን ከፍሎ ወደየሥራው እንዲሔድ። በዚህ ሁኔታ ግብር ከፋዩ ሳይስተናገድ ቀርቶ ቢጉላላ

በግብር ተቀባይ ሠራተኞች ላይ ኪሳራ የማስከፍልና ሌላም ከባድ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ስናገር ተከፍተው ፊታቸውን ጨፍግገው መቀመጫቸውን ግራና ቀኝ የሚያሹ ተደስተው ፈገግታ የሚያሳዩና ከመቀመጫቸው በላይ ወደኋላና ወደፊት የሚናጡ እንደነበሩ ከመድረኩ ላይ ሆኜ እመለከት ነበር፡፡

በፖሊስና በፍርድ ቤቶች በኩል [በወላይታ] አውራጃ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በአዲስ አበባ ከተማ ጭምር ሕዝቡ እንደሚጉላላ ጠቅሼ ፖሊሶች የሕግ ማስከበር ሥልጣናቸውን አላግባብ እየተጠቀሙ ሰዎችን ያለወንጀላቸው እንዳይዙ ሰዎች በደል ተፈጽሞባቸው ወይም ጉዳት ደርሶባቸው ለማመልከት ሲቀርቡ ፖሊስ የተበዳዮች ቀድሞ ደራሽና ወገን ስለሆነ በአግባቡ ጉዳያቸውን እንዲፈጽሙላቸው እንጂ በቀጠሮ አላግባብ በማስተናገድና እጃቸውን እንዲዘረጉ በማድረግ ተበድለው የሚመጡትን ሰዎች ተጨማሪ በደል እንዳያደርሱባቸው በየጊዜው በየፖሊስ ጣቢያዎች በድንገት እየደረስኩ የፖሊስ የእለት ሁኔታ መዝገቦችንና የእስር ቤቶችን የማይና ከአርባ ስምንት ሰአት በላይ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የተሳሩ እንዳሉ የምቆጣጠር መሆኔን ስቆጣጠር አላግባብ የተፈጸመ ነገር ባገኝ በዚያው አውራጃው በጠቅላይ ግዛቱና አዲስ አበባ ጠቅላይ ፖሊስ ጽ/ቤት ድረስ ጥፋቱ ተገልጦ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን፣እንደጥፋቱ ሁኔታ አይቼ ጥፋተኛው ፖሊስ እኔ በማስተዳድርበት አውራጃ እንዳይሠራ ከአውራጃው እንዲወጣ እስከሚደርስ እርምጃ እንደምወስድ ተናገርኩ፡፡ በፍርድ ቤት በኩል መፈጸም ስለሚገባቸው የፍትህ ርትዕ አሰጣጥ ቀጠሮ ዳኞች ሳያበዙ የሕዝቡን ጉዳይ እያዩ ፍትህ ርትዕ መሠረት ያደረገ ውሳኔ እንዲሰጡ እኔም አልፎ አልፎ እያስቻልኩ ዳኝነት የማይና እኔ ባላስቻልኩበት ጉዳይ አቤቱታ ሲቀርብልኝም ሆነ ሳይቀርብልኝ ዳኞች የሰጡዋቸውን ውሳኔዎች ማህደሮች እያስቀረብኩ የማጠናና አላግባብ የተሰጡትን ውሳኔዎች ከእኔ ሥልጣን በላይ የሆኑትን ለፍርድ ሚኒስቴር እየላኩ እንዲታዩና በዳኛው ላይ አስተያየት የሚሰጥና እርምጃ የሚወሰድ ስለሆነ ዳኞች ሕዝቡን በትክክል እንዲያገለግሉ በሰፊው መመሪያ ሰጠሁ፡፡

ከዚህ በላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ከሕዝብ ጋር በየእለቱ ግንኙነት ካላቸውና አገልግሎት ለሚሰጡ የመንግሥት ሠራተኞች ብቻ ሳይሆን ለሊጋባ በየነ አባሰብስብ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና አስተማሪዎች መመሪያ ሰጥቼ በአጠቃላይ ጊዜ ባገሁ ቁጥር በየመሥሪያ ቤቶቻቸው እየተዘዋወርኩና ድንገት እየደረስኩ ሥራቸውን የማይ መሆኔን በመግለጥና ሕዝብ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ እኛ የሕዝብ አገልጋዮች ማድረግ የሚገባንን ነገሮች በመግለጥ በአውራጃ አስተዳዳሪነቴ የምፈጽማቸው ምን እንደሚመስሉ በሰፊው አስረዳኋቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ በዚያን እለት በተደረገው ስብሰባ የሰጠሁት መመሪያና በተካሔደው ውይይት ከመንግሥት ሠራተኞችና ከሀገር ሽማግሌዎች መተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት እኛ የሕዝብ አገልጋዮች ሥራችንን በምን ሁኔታ መፈጸምና ሕዝብን ማገልገል የሚገባን በምን ሁኔታ እንዲሆን

*እንደምፈልግ ሁሉም ፍንጭ እንዲያገኝ አደረኩ። በዚያን ቀን ያደረኩት ንግግርና የሰጠሁኋቸው መመሪያዎች ሕዝቡን ግራ ሳያጋቡት አልቀሩም። ይኸውም ሁሉም በሹክሹክታ ሰምቶ የነበረው ከአለቃዬ ጀምሮ እስከንጉሠ ነገሥቱ ተጣልቼ በግዞት ወደ አውራጃው እንደተላኩ ሲሆን በዚያን ቀን ስብሰባ ግን የምናገረውና የምሰጠው መመሪያ ልዩ ሥልጣን ተሰጥቶኝ አውራጃ ግዛቱን በምፈልገው ዓይነት እንዳስተዳደር ሥልጣን እንደተሰጠኝ ዓይነት ሆኜ መታየቴ ነው።*

*ከዚያን ቀን ጠቅላላ ስብሰባ በኋላ በአውራጃው ግዛት ጽሕፈት ቤት ተቀምጬ ባለጉዳዮችን እያነጋገርኩ ጉዳያቸውን መፈጸምና ደብዳቤዎችን መፈረም ውስጥ አልገባሁም። እድሜ ለላንድ ሮቨር መንገድ እያሠራሁ ጭምር በየወረዳው እየተዘዋወርኩ የመንግሥት ሠራተኞችን ያገር ሽማግሌዎችን እያነጋገርኩና ከኔ በፊት በነበረው አሠራር አንዳንድ ጠቅላይ ግዛትና ከዚያም አገር ግዛት ሚኒስቴር ካልደረሱ ይፈጸሙ ያልነበሩትን የመሬት ለጭሰኞች መስጠትና ሌሎች የአስተዳደር ሥራዎች እየፈጸምኩ ጥቂት ሳምንታት የፈጀ የወረዳዎች ጉብኝት አደረኩና ስለአውራጃው ያለኝን ግንዛቤ ማጠናከር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ በእኔ ላይ ያለውን የመልካም አስተዳደር እምነት እንዲያድርበት አደረኩ። በተለይ አገር ግዛት ሚኒስቴር ካልደረሰ ይፈጸም ያልነበረውን እንደ መሬት ለጭሰኞች መስጠት ጉዳይ ባለጉዳዩ አውራጃ ግዛቱ ጽህፈት ቤት እንኳን ሳይደርስ እዛው ባለበት ወረዳ ሲፈጸምለት በሕዝቡ በኩል በኔ ላይ ወዲያው ከፍ ያለ እምነት እንዲያድርበት ያደረገ ሲሆን የሕዝቡን እጅ ማየት በለመዱ በመንግሥት ሠራተኞች ላይ ግን ድንጋጤ ያስከተለና ስቅጥጥ ብለው ሕዝቡን በመልካም ሁኔታ ከማገልገል በስተቀር አማራጭ እንደሌላቸው ያደረጋቸው ሳይሆን አልቀረም።*

*ከአውራጃ ከተማ ሶዶ ውጪ በየወረዳው የሚገኙትን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እየተዘዋወርኩ ከጎበኘሁና የሕዝቡን ጉዳዮች እዚያው ሕዝቡ ባለበት ከፈጸምኩ በኋላ በሶዶ ከተማ በአውራጃው ጽህፈት ቤትና በሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጽህፈት ቤቶች ላይ አተኮርኩ። ከዚያው አውራጃ ደሞዝ ተመላሽ ለቤት ማደሻና ለመኪና መጠገኛ ተሰጥቶኝ በነበረ ጥቂት ገንዘብ ላይ በረዳት ሚኒስትርነቴ አገኝ የነበረውን ስምንት መቶ ብር ደሞዝና አንድ መቶ ሰባ ብር አላዋንስ ለቤት ሠራተኞች ደሞዝ ጨምሮ በወር ከሁለት መቶ ብር በላይ ስለማይጠይቀኝ የቀረውን እጅግ በጣም መጎሳቆል ብቻ ሳይሆን የሌሊት ወፎች መራቢያና በመፈራረስ ላይ የነበሩትን መኖሪያ ቤቴን የአውራጃውን ጽሕፈት ቤት የፍርድ ቤቱን የግምጃ ቤቱን ማዘጋጃ ቤቱንና የፖሊስ ጽህፈት ቤቶችን አንዱን ከሌላው ሳለይ በእኩል ደረጃ ከአዲስ አበባ ይገዬያቸው በሔድኩት የጥገና ቁሳቁሶችና ባለሙያዎች በአውራጃው ወህኒ ቤት በሚገኙ የሕግ እስረኞች የጉልበት ሥራ እገዛ በሶዶ ከተማ ሳይሆን በዋና ከተማው በአዲስ አበባ ከተማ እንኳ ዐይን በሚስቡ ሁኔታ በሶዶ ከተማ የሚኙትን ጽሕፈት ቤቶች ሁሉ አሳደስኩ። የጽህፈት ቤቶቹ እድሳት በሚካሔድበትና*

እድሳቱም ካለቀ በኋላ ለሠራተኛውም ሆነ ለሕዝቡ እንግዳ ነገር ስለሆነባቸው የከተማው ነዋሪ ብቻ ሳይሆን ከየወረዳው ጭምር አንዳንድ ሰዎች እየመጡ በማየት በወሬ እንደሰሙት ተግቴ ወደ አውራጃው የተላኩ ሳይሆን ልዩ ሥልጣንና ለሥራ በርከት ያለ ገንዘብ ተሰጥቶኝ እንደመጣሁ ዓይነት አድርገው ሳይቆጥሩት አልቀሩም። ስለዚህ መልካም አስተዳደር አጥተው የተበደሉት ሲፈነድቁ በሕዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጠው ይንደላቀቁ የነበሩት በሊጋባ ቤየነ አባሰብስብ ትምህርት ቤት በተደረገው ታላቅ ስብሰባ ያደረኩት ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ንግግር ተግቴ ወደ አውራጃው መላኬን ለመሸፋፈን ያደረግኩት ንግግር መስሏቸው የነበሩት ከአገር ግዛት ሚኒስቴርና ከሌላም ቦታ እንደደረሳቸው ተባራሪ ወሬ አለመሆኑ ግልጽ እየሆነላቸው ስለመጣ ሰቅጠጥ ማለት ብቻ ሳይሆን ግራ መጋባታቸው እንዳልቀረ አምናለሁ።

ከዚህ በላይ የተነገሩትን ከታህሣሥ ወር መጀመሪያዎቹ ቀናት እስከ ጥር ወር መጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት 1955 ዓ.ም ውስጥ ፈጽሜ በወላሞ አውራጃ ከዘጠኝ ዓመት በላይ ስኖር ሃይማኖታዊ የሕዝብ በዓላት ያከበርኩበት የመጀመሪያና የመጨረሻው የሆነውን ጥር 12 ቀን 1955 ዓ.ም የጥምቀት በዓል አከበርኩ። በጥምቀት በዓል ላይ ተገኝቼ የካህናት ማሸብሸብ ተፈጽሞ ታቦቱ ጉዞ ሊጀምር ሲል አንድ ቢጫ ጨርቅ ያሸረጡ ከዳሌያቸው እስከ ደረታቸው ሰንሰለት የጠመጠሙና የበግ ደበሎ የደረቡ ስጋቸው አልቆ አጥንቶቻቸውን በቆዳቸው ውስጥ አልፎ ማየትና ለይቶ መቁጠር የሚቻል መነኩሴ ከቆሙበት ከታቦቱ በስተኋላ ፈንጠር ብለው ወጡና መሀል ላይ ቆመው ቀኝ እጃቸውን ወደ አራቱ ማዕዘናት እያመለከቱ ያውጁ ጀመር። ወደ ምስራቅ ዞረው በእጃቸው እያመለከቱ «[በወላይታ] ሕዝብ እልል በል አስተዳዳሪ መጣልህ» ወደ ሰሜን ዞረው በእጃቸው እያመለከቱ «[በወላይታ] ሕዝብ እልል በል ዳኛ መጣልህ» ወደ ምዕራብ ዞረው በእጃቸው እያመለከቱ «[በወላይታ] ሕዝብ እልል በል መሐንዲስ መጣልህ» ወደ ደቡብ ዞረው በእጃቸው እያመለከቱ «የወላሞ ሕዝብ እልል በል ሐኪም መጣልህ» እያሉ ለሕዝቡ የሚሰጡትን ትእዛዝ ሴቱ እየተቀበለ እልልታውን ካቀለጠው በኋላ መነኩሴው ታቦቱ ጉዞ እንዲጀምር አዘዙና ጉዞ ተጀመረ።

በመነኩሴው አዋጅ ግራ ተጋብቼ ታቦታቱን አጅበን ከምንጓዘው የመንግሥት ባለስልጣኖች ውስጥ የፖሊስ አዛዡን ኮሎኔል ወደእኔ ጠቅሼ ሲቀርበኝ መነኩሴው ጤነኛ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ሥራቸውስ ምን እንደሆነ ጠየቅኩት። መነኩሴው አባ መላኩ (ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱሥ አቡነ ተክለሐይማኖት) ተብለው እንደሚጠሩና በመጓዝ ላይ ወደምንገኝበት በደብረ መንክራት አቡነ ተክለሐይማኖት ገዳም የሚኖሩ በአውራጃው ውስጥ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚመሩ በሁሉም ሰው በእስላሞችና በሌሎች የሐይማኖቶች ተከታዮች ጭምር ሳይቀር የተከበሩና አልፎ አልፎ የሚታያቸውን እንደዚያኑ እለት ሕዝብ በተሰበሰበበትና በገበያ ላይ የሚያውጁ መሆናቸውን ነገረኝ። ነገሩን

በመቀጠል ለያን እለት የተናገሩትም ስለእኔ መሆኑንና በእኔ ላይ ሕዝቡ እምነት እንዲያድርበት የሚያደርግ ስለሆነ ወደፊት ለምሠራው መንገድ ያመቻቸልኝና በጣም ጥሩ መሆኑን ሲነግረኝ ነገሩ ገርሞኝ በዚያን እለት በጉዞ ላይ እንዳለን የነገረኝን በጉዞ ላይ እንዳለን አሰላሰልኩት እንጂ ከዚያ በኋላ አንድ ቀን ከመኰንኑ ጋር በስብሰባ ላይ እስከተገናኘንበት ቀን ድረስ አላጤንኩትም ነበር፡፡

## የአስተዳደር ሪፎርምና የልማት ሥራዎች ጎን ለጎን ማካሔድ ተጀመረ፡-

እስካሁን በተገለጠው ሁኔታ ከሠራተኛውና ከሕዝብ ጋር ስተዋወቅ በተደረገው ስብሰባ ላይ ስለአስተዳደር አፈጻጸምና የልማት ሥራዎች ዓላማዬን ገልጬ የቤቶች እንድሳትም ከተፈጸመና ለመግቢያ ያህል በየወረዳው እየተዘዋወርኩ አንዳንድ ሥራዎችን ካከናወንኩ በኋላ የቱን አስቀድሜ የቱን እንደማስከትል ግራ የሚገባኝን ብዙ ሥራዎችን ባንድ ላይ ጎን ለጎን ማካሔድ ጀመርኩ፡፡ ባደረኩት የሕዝብ ስብሰባና በሌሎች አጋጣሚዎች ሁሉ አሜሪካን ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ቤይሩት ስማር በነበረችኝ አጭር የበጋ የእረፍት ጊዜ ቱርክን ስጎበኝ ያየሁትን የሕዝብ የልማት እንቅስቃሴና በነሐሴ ወር 1950 ዓ.ም ከትምህርት ወደ አገሬ ስመለስ እግረ መንገዴን በመቋቋም ላይ የነበረችውን እስራኤልን ስጎበኝ ከሕጻን እስከ ያፈጀ ሽማግሌ የእስራኤል ሕዝብ አገሩን ለልማት የኑሮ ደረጃውን ለማሳደግ ሁሉም ባለው ሙሉ አቅም በኅብረትና በተናጠል ተግቶ ሲሠራ ብቻ መሆኑን በመግለጥ ያየሁትን እንደ ምሳሌ እየጠቀስኩ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ አስረዳሁ፡፡ እኛም እንደዚህ ተባብረን ብንሠራ የሚለው ምኞት በአእምሮዬ ሲጉላላ የኖረውና አንድ ሕዝብ ከፈለገና ቆርጦ በመነሳት ተባብሮና ጠንክሮ ከሠራ የኑሮ ደረጃውን ከፍ ማድረግና አገሩን ማበልጸግ ይቻላል የሚለው ጠንካራ እምነቴ ዘወትር በጆሮዬ ሲያቃጭልና በአእምሮዬ ሲጉላላ ኖሮ ምኞቴንና እምነቴን በሥራ ለመተርጎም አጋጣሚ ስላገኘሁ በጋለ መንፈስ ቆርጬ ተነሳሁና ይኸንኑ በመግለጥ ሕዝቡን ለሥራ ቀሰቀስኩት፡፡

### *ሕዝብ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ ጥረት ተደረገ፡-*

ወደ አውራጃው ሔጄ ሥራዬን የጀመርኩት የመልካም አስተዳደርና የፍትህ ርትዕ ማስፈንና የልማት ሥራዎችን ጎን ለጎን በማካሔድ ቢሆንም እንደሚታወቀው ለዘላቂ የአገር ዕድገትና ለሕዝብ ብልጽግና መሠረቱ ሕዝብ መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝ ማድረግ ስለሆነ መጀመሪያ ላይ የልማት ሥራዎችንም እየሠራሁ ያተኮርኩት ሕዝቡ መልካም አስተዳደርን እንዲያገኝ ማድረግ ላይ ነበር፡፡

የወረዳዎችንና የምክትል ወረዳዎችን ሥራና ለሕዝብ የሚሰጡትን አገልግሎት በየቦታው በመገኘት ጭምር ሳጠና ቆይቼ በልማቱ ክፍል የሚገለጠው የአውራጃው ካርታ ተዘጋጅቶ እንዳለቀ እንደ ቀድሞው የባላባቶችን ክልል በመከተል ሳይሆን ለአስተዳደሩና ሕዝቡ ከመንግሥት ሊያገኝ በሚገባው አገልግሎት አመችነት መሠረት ቆይቶ ክስ ያስከተለብኝን አሥራ ሁለቱን

ምክትል ወረዳዎች ሰርገፎ የነበሩትን አምስት ወረዳዎች ወደ ሰባት ከፍ በማድረግ ወሰናቸውን በካርታም በምድርም ላይ እንዲከለሉ አደረኩ። ለባለርስቶች ከመንግሥት መሬት ንጣፍ እየሰጠሁ ለአስተዳደሩና ለከተማው ዕድገት አመች በሆኑ ቦታዎች አዳዲስ የወረዳ ዋና ከተሞችን ቆረቆርኩና ከተሞቹ በስተኋላ ከስዊድን ሉንድ ዩኒቨርስቲ በመጡ የከተማ ፕላን ባለሙያዎች ተጠንተው ማስተር ፕላናቸው እስኪሠራ በሕንጻ ኮሌጅ ባለሙያዎች በአቶ በለጠ ሀብታሙና በሚስተር ፎግልቪክ እየተጠኑ ጊዜያዊ ማስተር ፕላን ተዘጋጀላቸው።

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የአውራጃ ገዢው ቢሮ ተሰነጣጥቆ ለመፍረስ የቃጣው ከመሆኑም በላይ ኮርኒሱ ውስጥ የተራቡት የሌሊት ወፎች ኩስና ሽንት ትንፋግ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እክፍሉ ውስጥ መቀመጥና ባለጉዳዮች ማነጋገር ስለማያስችል ቤቱ ቢጠገንና ወፎቹ እንዲወገዱ ቢደረግም ለቢሮነት አመች ሆኖ ስላላገኘሁት ዝንጀሮ መጀመሪያ የመቀመጫዬን እንዳለችው ሁሉ በዚህ በቀላሉ ላስወግደው በምችለው መሰናክል ምክንያት ሥራዬ እንዳይታጎል ቢሮዬን ማመቻቸት አስፈለገኝ፤ እንዲሁም ለባለጉዳዮች መጉላላትና የጽህፈት ቤቱን የየእለቱ ሥራዎች በቅልጥፍና ማካሔድ እንቅፋት የሚሆነው አንዱ ዋናው ምክንያት የሰነዶች ማከማቻ መዝገብ ቤት በሥርአት አለመደራጀት ስለሆነ ለመዝገብ ቤት ሥራ አመች የሆነና አቡዋራ ቅመው በየግርግዳው ሥርና ሜዳ ላይ ተመሳቅለው የተቀመጡትን ሰነዶች በሥርአት ማስቀመጥ የሚያስችል ክፍል እንዲኖር ማድረግ ነበር።

ስለዚህ በየእለቱ የጽህፈት ቤቱን ሥራዎችን በመልካም ሁኔታ ለመፈጸምና እኔም ሆንኩ የጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች ባለጉዳዮች በመልካም ሁኔታ ለማስተናገድና የአስተዳደሩን ሥራ ለማቃናት እላይ የተጠቀሱትን ሁለት ክፍሎች አመች በሆነ ሁኔታ ማደራጀት ስለሚያስፈልግ ከጽህፈት ቤቱ ሕንጻ በሰሜን በኩል ከሕንጻው ግርግዳ ጋር አያይዞ አንድ እስከ ሃያ ሰዎች በስብሰባ ማስተናገድ የሚያስችል የአውራጃው አስተዳዳሪ ቢሮና ሁለተኛ አንድ የመዝገብ ቤት ሰነዶች ማቀፊያዎች የሚቀመጡባቸው መደርደሪያዎች በግርግዳዎቹ ዙሪያ ማቆም የሚያስችልና ሠራተኞች እንደልባቸው እየተንቀሳቀሱ ሊሠሩ የሚያስችላቸው ለመዝገብ ቤት የሚያገለግል ክፍል እነዚህ ሁለት ክፍሎች ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሠሩ ተደረገ። ለአውራጃው አስተዳዳሪ የተሠራው ክፍል አንድ ለአውራጃው አስተዳዳሪ፣ ሁለተኛው ለስብሰባ የሚያገለግሉ ሁለት ጠረጴዛዎችና ለሃያ ያህል ተሰብሳቢዎች የሚበቁ ወንበሮች እንዲኖሩት ተደርጎ የአውራጃው አስተዳዳሪ ቢሮ ተሟላ። ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ስሠራ መዝገብ ቤቱ በተደራጀው መሠረት በዚያው መልክ የአውራጃው መዝገብ ቤት እንዲደራጅ ተደረገና አቡዋራ ቅመው በየግርግዳውና በየሜዳው ላይ ተመሰቃቅለው ተቀምጠው የነበሩት ሰነዶች በየማህደራቸው ሆነው ሥርአት ይዘው ተደረደሩ።

ከዚህ በላይ እንደተነገረው ክፍሎቹን ለመሥራትና እቃዎቹን ለማሟላት ገንዘብና የመዝገብ ቤቱን ሰነዶች በዘመናዊ መልክ ሥርአት ለማስያዝ የመዝገብ ቤት ሰነዶች አቀማመጥ ባለሙያ እንደሚያስፈልጉ ግልጽ ነው። የገንዘብና የሙያ ድሀ የሆኑትን ኢትዮጵያ አገራችንና ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ከልብ በመነጨ ፍላጎት ለማገልገል የተነሳ ሰው የግል ገንዘቡን ያካበተውን ሙያና ጊዜውን ብቻ ሳይሆን ካስፈለገ ሕይወቱንም ጭምር ለዚያው ቆርጦ ለተነሳበት አገልግሎት መስዋዕት ካላደረገ ያ የተቀደሰ ዓላማው እንደማይፈጸምለት እስካሁንም ያለኝ የማያወላውል እምነቴ ስለሆነ የተጠቀሱትን ሁለት ክፍሎች ለማሠራት እቃዎቹን ለማሟላት ገንዘብም ሆነ ሙያው አልቸገረኝም። ይኸውም ሙያውን የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር መዝገብ ቤት በዘመናዊ መልክ ያደራጁትን ባለሙያዎች ሥራ ስከታተል ከሁለትና ሦስት ሰአት በላይ የማይወስደውን መዝገብ ቤት የማደራጀትና ሠራተኞችን የማሰልጠን ቀላሉን ሙያ አካብቼ ስለነበረ በገንዘብ በኩል በዚያን ሪዜ ለወላይታ ሶዶ ላልተንደላቀቀ ኑሮዬ በወር ከሁለት መቶ ብር የበለጠ የወር ወጪ ስላላስፈለገኝ ወደ አንድ ሺህ ብር ይጠጋ ከነበረው የወር ደሞዜና አበሌ የሚተርፈውን የባንክ የቁጠባ ሂሳብ ደብተር ያደረኩት የአገሬንና የወገኔን አገልግሎት ስለነበረ የመዝገብ ቤት ማደራጀትና ሠራተኞችን የማሰልጠን ሙያውም ሆነ ክፍሎቹን ለመሥራትና ለማሟላት ገንዘብ አልቸገረኝም ነበር።

በዚህ ሁኔታ ተጨማሪ ሁለት ክፍሎች ስለተሠሩና ስለተሟሉ ለነበሩት ሠራተኞች ብቻ ሳይሆን ለተጨማሪ ሠራተኞች ጭምር የሚበቁ ክፍሎች ተገኙ። እንዲሁም ለጽህፈት ቤት ቀልጣፋ አሠራር ማነቆ የሚሆነውና ለባለጉዳዮች መጉላላት አንዱ ዋናው ምክንያት የመዝገብ ቤት ሰነዶች አለመደራጀትና ሰነዶች ሲፈለጉ ቶሎ አለመገኘታቸው ስለሆነ የአንድን ጉዳይና የባለጉዳይን ማህደር ለማግኘት ቀናት ጭምር ያስፈልግ የነበረው ችግር ተወገደና በደቂቃዎች ውስጥ የጉዳዮችን ማህደር ማግኘት ስለተቻለ ባለጉዳዮችን በቅልጥፍና ማስተናገድ ተቻለ።

የጽህፈት ቤት ሥራዎችን ለማቀላጠፍና ባለጉዳዮች መልካምና ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስፈልጉት እላይ የተገለጡት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችንም የጽህፈት ቤት አሠራሮች ማሻሻል ያስፈልግ ነበር። አንድ ባለጉዳይ ወደ ጽህፈት ቤት መጥቶ ሲያመለክት ጉዳዩ ደብዳቤ መጻፍ የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ቀጠሮ ሳይሰጠው ወዲያው ደብዳቤ እንዲጻፍና የተጻፈው ደብዳቤ ለባለጉዳዩ እንዳይሰጥ የሚያደርግ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ወዲያው ተፈርሞና ከመዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለባለጉዳዩ ደብዳቤ ተሰጥቶት እንዲሸኝ ምክንያት ኖሮ ደብዳቤው ለባለጉዳዩ የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ መዝገብ ቤቱ ደብዳቤውን በዚያው ሰአት ውስጥ ወጪ አድርጎ ለባለአድራሻው ሳይዘገይ እንዲደርስ እንዲደረግ ባለጉዳዩ ሲያመለክት ውሳኔ ሰጥቶ ደብዳቤውን የሚፈርመው ሰው የሚሰጠው ውሳኔ የጉዳዩ አፈጻጸም የግድ የደብዳቤ መጻጻፍ የሚያስፈልግ ሆኖ ካልተገኘ ጉዳዩ ባንድ ውሳኔና ደብዳቤ እንዲፈጸም ጉዳዩ

ባንድ ውሳኔና ደብዳቤ መፈጸም ሲችል ባለጉዳዩን የሚያመላልስ ውሳኔ እንዳይሰጥ ሌሎችንም አንድ ባለጉዳይ ወደ ጽህፈት ቤት መጥቶ ሲያመለክት ቀልጣፋ አገልግሎት አግኝቶ ወደ ሥራው እንዲሔድ ለዋናው ጽህፈት ቤት ብቻ ሳይሆን ለወረዳዎችም ጭምር መመሪያ ተሰጠ፡፡ ከተፈጥሮ ችሎታ ማነስና በአንዳንድ አስገዳጅ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር በመመሪያው መሠረት ሳይፈጸም ቀርቶ ባለጉዳዩን ያጉላላ ሠራተኛ ከደሞዙ ለባለጉዳዩ ኪሳራ እንዲከፍለው ስለሚደረግ ባለጉዳዮች ነገ ተመለስ ደብዳቤ ለመጻፍ ጊዜ በማጥፋት የተጻፈ ደብዳቤ ወዲያው ወጪ አድርጎ ባለመስጠት ቀላጤ በማመላለስ ባለጉዳይን የሚያጉላላ የጽህፈት ቤት አሠራር እንዲወገድ ስለተደረገና ሕዝብ የመልካም አስተዳደርን ጣዕም መቅመስ ስለጀመረ በአስተዳደሩ ላይ እምነት እያደረበት ሔደና መተባበርና የልማት ሥራዎችን ያንቀሳቅስ ጀመር፡፡

በዚያን ጊዜ የድንጋይ ዳቦ ዘመን ስለነበረ የኑሮ ውድነት ባይኖርም በመንግሥት የኤኮኖሚ አቅም ማነስ ምክንያት የሠራተኞች ደሞዝ በጣም አነስተኛ ስለነበረ ሠራተኞች ይህን ምክንያት አድርገው እንዳሁኑ ዘመን ለመንደላቀቅ ፈልገው ባለጉዳዮችን አይዝረፉ እንጂ የባለጉዳዮችን እጅ የሚመለከቱ ስለነበሩ ያ የባለጉዳዮችን እጅ ለመመልከት ምንም መንገድ የማይከፍትላቸው መመሪያ ሲሰጠውና በተለይ ከዚያችው አነስተኛ ደሞዛቸው ላይ ለባለጉዳይ ኪሳራ እንዲከፍሉ መደረጉ ሳይከብዳቸው እንዳልቀረ ይሰማኝ ነበር፡፡ በስተኋላ ግን የሠራተኞች ደሞዝ በመጠኑ እንዲያድግ ስለተደረገና በተለይ የወረዳ ሠራተኞች አዲስ በተቆረቆሩ ከተሞች ቦታ በነጻ እያገኙ ቤት ሠርተው እንዲያከራዩ ስለተደረገና የመልካም አስተዳደር ሥራ የባለጉዳዮችን ቁጥር በጣም ስለቀነሰው በሠራተኞች ላይ የነበረው የሥራ ጫና በዚያው መጠን ስለቀነሰ ሠራተኞች በመጠኑም ቢሆን ተክሰዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ ያም ሆነ ይህ የሕዝብ አገልጋዮች ሕዝብ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ አገር እንዲያድግና ሕዝብ እንዲበለጽግ መስዋዕት መሆን ከስጋ ፍላጎት መሟላት የበለጠ የሚያረካ መሆኑን ስለማምን በአውራጃው እድገትና በሕዝቡ መልካም አስተዳደርና ዕድገት ማግኘት ሠራተኞቹ እንደ እኔው ይረካሉ የሚል እምነት ቢኖረኝም አሠራሬ ጨከን ያለ እንደነበረ ይሰማኝ ነበር፡፡ ይልቁንም ቅዳሜና እሁድ በመንግሥታዊም ሆነ በሃይማኖታዊ የበዓላት ቀናት ጭምር በተለይ አውራጃው ጽህፈት ቤት ለባለጉዳዮች ክፍት ሆኖ ስለሚያገለግል እንዲሁም ጠዋት ከአንድ ሰአት ጀምሮ አንዳንዴም ከዚያ በፊት ቢሮ እገባ ስለነበረ ሠራተኞች ከእኔ ቀድመው ቢሮ መግባት ስለነበረባቸው የአውራጃውን ጽህፈት ቤት ሠራተኞች በጣም ተጭኜያቸው ስለነበረ የከፈሉት መስዋዕትነት ለአገራቸውና ለወገናቸው ዕድገት ቢሆንም እግዚአብሔር ዋጋቸውን ለልጆቻቸው ጭምር እንደሚከፍላቸው አምናለሁ፡፡ በወላይታ አውራጃ የተፈጸሙ መልካም ሥራዎች ካሉ በሠራተኞች ከፍተኛ ጥረትና መስዋዕትነት ጭምር መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እየመሰከርኩና

ከልብ እያመሰገንኩ ለአገራቸውና ለወገናቸው ዕድገት በፈጸሙት መስዋዕትነት ሊኮሩና ሊረኩ ይገባቸዋል፡፡

በአስተዳደር ሥራ የቢሮ ሥራዎች እንዲቀላጠፉና ባለጉዳዮች መልካም አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የጽህፈት ቤት መደራጀትና ጥርት ያለ የአሠራር መመሪያ መኖር ብቻውን በቂ ስላልሆነ መመሪያውን ሥራ ላይ የሚያውሉት ሠራተኞች ለየተመደቡበት ሥራ ከሞላ ጎደል እንኳዋ ቢሆን ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልግ ነበር፡፡ በመሆኑም በአውራጃው ጽህፈት ቤት በአምስት ወረዳና በአሥራ ሁለት ምክትል ወረዳ ግዘቶች ተመድበው ሕዝብን የሚያገለግሉ ሠራተኞችን መመልከት ያስፈልግ ነበር፡፡ በአውራጃው ጽህፈት ቤት ያሉት ሠራተኞች አንዳንድ የሥራ መደብ ለውጥ ከተደረገ ለተመደቡበት ሥራ ከሞላ ጎደል የሚያውሉ ሲሆን አንዱ ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የነበረው ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ተባሮ ባልታወቀ ምክንያት የአውራጃው ግዛት ዋና ጸሀፊ ሆኖ ያገኘሁት አቶ ከበደ ብርሃኔ በተደጋጋሚ ቢመከርና ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ጠባዩንም ሆነ ለሕዝብ የሚሰጠውን አገልግሎት በተለይ የባለጉዳዮችን እጅ በማየት በኩል ያለው ጠባዩን ስላላሻሻለ ከአውራጃው ተባረረና በምትኩ እዚያው የአውራጃው ጽህፈት ቤት ይሠራ የነበረ የባለጉዳዮችን እጅ በማየት ጠባይ የሚጠረጠር ሆኖም በምክር ጠባዩን የሚያሻሽል ስለሆነና የጽህፈት ቤቱ አሠራር መመሪያም የማያፈናፍነው በመሆኑ አቶ (በሁዋላ ግራዝማች) ታደሰ ወልደየስ የአቶ ከበደ ብርሃኔን ቦታ እንዲይዝ ተደረገ፡፡ ለመልካም አስተዳደር ይበጀል ተብለው የተሰጡት መመሪያዎች በየወረዳውም ጭምር ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ስለሚያስፈልግ አንዳንድ ሠራተኞችን የሚያስቀይም ሌሎቹን የሚያስደስት ቆራጥ እርምጃ መውሰድ አስፈልጎ ነበር፡፡ በወረዳና በምክትል ወረዳ አስተዳደሪነት ከተመደቡት ሠራተኞች ውስጥ አብዛኞቹ ከጠላት ወረራ በፊት ጀምሮ በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ ላይ ተመድበው ሲሠሩ የኖሩና በአምስቱ የጠላት ወረራ ዘመን ደግሞ በዱር በገደሉ እየተንከራተቱ ጠላትን ይፋለሙ የነበሩ አርበኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሠራተኞች በተመደቡበት ሥራ ላይ ሆነው ለሕዝብ መልካም አስተዳደር ታስቦ የተሰጠውን መመሪያ ለመፈጸም ችሎታቸውም ሆነ ዕድሜያቸው የማይፈቅድላቸው ስነበረ ከ1910 ዓ.ም ጀምሮ በወታደርነት ሲያገለግሉ ኖረው ጠላት ኢትዮጵያን ሲወር የአምስት ዓመት አርበኛ የነበሩትንና ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በወረዳ ገዢነት ሲሠሩ የቆዩትን እንደነ ግራዝማች መንግሥቱ ይሻል ያሉትን አርበኞች ያስፎከራና ጠብመንጃ ያስጎተተ እርምጃ መውሰድ አስፈልጎ ነበር፡፡ ይኸውም በ1955 ዓ.ም የታወጀውንና ገና በሥራ ላይ ያልዋለውን የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ምክንያት በማድረግ ሁለት የወረዳ ሰባት የምክትል ወረዳ ገዢዎችንና አንድ የምክትል ወረዳ ግዛት ጸሀፊ በድምሩ አሥር ዕድሜያቸው የገፋና ለሕዝብ መልካም አስተዳደር ይበጃል ተብሎ የተሰጠውን መመሪያ ለመፈጸም የማይችሉትን ሠራተኞች ከሥራቸው ላይ እንዲነሱና የጡረታ አበላቸዉ እስኪወሰንላቸው

ሙሉ ደሞዛቸውን እያገኙ እንዲቆዩ ማድረግ አስፈልጎ ነበር፡፡ በእነዚህ ከሥራቸው ላይ እንዲነሱ የተደረጉ ሠራተኞች የጡረታ አበላቸው እስኪወሰንላቸውና ደሞዛቸው ነፃ ሆኖ ለሚተኩዋቸው ሠራተኞች መክፈል እስኪቻል እዚያው በየወረዳውና ምክትል ወረዳው የነበሩት ሠራተኞች እንደየችሎታቸው ተመርጠው የነበራቸውን ደሞዝ እንደያዙ በእድገትና በዝውውር በተነሱት ሠራተኞች ምትክ ተደለደሉ፡፡ የወሰድኩት እርምጃ የበላይ ባለስልጣኖችንም ውሳኔ ይጠይቅ ስለነበረ ጥያቄ አቅርቤ መልስ እስካገኝ ብጠብቅ ሲጉዋተት ወራቶች ሳይሆን ዓመታትም የሚጠይቅና ሥራዬን የሚያደናቅፍ ስለሆነ የወሰድኩት እርምጃ መሰማቱ ስላልቀረ ለጊዜው የደካሞች ጉምጉምታና ሊመቱኝ ምክንያት ፈልገው ይጠባበቁ በነበሩ ባለስልጣኖች ዘንድ መፈራገጥ የእነግራዝማች መንግሥቴ ይሻልን ቀረርቶና ጠብመንጃ መጎተት ያስከተለ ቢሆንም የወሰድኩት እርምጃ ለሕዝብ መልካም አገልግሎት የሚጠቅምና ሠራተኞችንም የማይጎዳ ስለበረ ለመቃረን የተፈራገጡት ሁሉ እህ እያሉ ቀሩ እንጂ ሥራዬ አልተደናቀፈም፡፡

በአውራጃውና ወረዳ ጽህፈት ቤቶች ማደራጀትና ባለጉዳዮች መልካም አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የተፈጸሙ ሥራዎች እላይ የተገለጡት ብቻ ሳይሆኑ ለአገር ልማት ለወገን ዕድገትና ለመልካም አስተዳደር መሠረት የሆኑ ሌሎች ብዙ ተግባሮች በየጊዜው ተፈጽመዋል፡፡ ሕዝብ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ ለማድረግ መመሪያ አውጥቶና ሠራተኞችን ደልድሎ መቀመጥ ብቻውን የተፈለገውን ያህል ውጤት ስለማያስገኝ በየወረዳው እየተዘዋወሩና በድንገት እየደረሱ ሠራተኞች በተሰጠው መመሪያ መሠረት የሚሠሩና ባለጉዳዮችን በመልካም ሁኔታ የሚስተናገዱ መሆናቸውን ማየትና መቆጣጠር አንድ ባለጉዳይ ተበደልኩ ብሎ ሲያመለክት ቢሮ ተቀምጦ ደብደቤ መጻጻፍ ሳይሆን ወዲያው መኪና አስነስቶ ተበደልኩ ባዩን ይዞ እቦታው ላይ በመድረስ የተፈጸመውን በደል አጣርቶ እርምጃ መውሰድ በየወረዳው እየተዘዋወሩ የአስተዳደር በደል እንዳለ ሴት ወንዱን መንገደኛውን ሳይቀር እያነጋገሩ የሕዝብን ትርታ ማዳመጡ ያስፈልግ ነበር፡፡ ፍጹም ባይሆንም በዚህ ሁኔታ ሕዝብ ከሞላ ጎደል መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ ጥረት ስለተደረገ ሕዝቡ በአስተዳደሩ ላይ ሙሉ እምነት አድሮበት ስለነበረ አድርግ የሚባለውን የሚያደርገው ለራሴ ጥቅም ነው እያለ ይፈጽም ስለነበረ ራሱን በራሱ በመርዳት ባደረገው ጥረት ብዙ መልካም የልማት ሥራዎችን ስለሠራ ይህ የሕዝቡ ጥረት ከኢትዮጵያውን አልፎ አውሮፓውያንና አሜሪካውንያንን አስደንቆ እቦታው ላይ እየተገኙ የተፈጸሙትን ለማየት ሌሎቹም ለማጥናት ወደ አውጃው እየመጡ ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን እኔንም ጭምር እንድመሰገን አድርጎኛል፡፡

### *ሕዝብ ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝና ደኅንነቱ እንዲጠበቅ ጥረት ተደረገ፦*

የሕዝብ መልካም አስተዳደር የሚሟላው ደህንነቱ እንዲጠበቅና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝ ሲደረግ ነው፡፡ እንዳሁኑ ዘመን ባይሆንም በዚያን ዘመን በፖሊስና

በፍርድ ቤት በኩል የፍትህ መጓደል እንደነበረ ይታወቃል። የነበረውን የሕዝብ ደኅንነት አለመጠበቅና የፍትህ ርትዕ መጓደል ለማስቀረትና ሕዝቡ የተሟላ መልካም አስተዳደር እንዲያገኝ ለማድረግ በዚያን ዘመን አውራጃ ገዢው በሕግ የአውራጃው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ስለነበረ በዚህ ሕጋዊ ሥልጣኑ በችሎት ተሰይሞ ማስቻል ስለሚችል በሳምንት ሁለት ቀን ማክሰኞና ሐሙስ እያስቻልኩ ዳኝነት በማየት ለዳኞችና ለአቃቤ ሕግ አባላት ቀጠሮ እንዳያበዙና ጉዳዮችን በሕግ እንዲፈጽሙ ምክርና አስተዳደራዊ መመሪያ በመስጠት የሕግ ጠበቆች ለሀሰተኞች እየቆሙ ሁለቱንም ወገን ተከራካሪዎች በደል እንዳያደርሱባቸው ምክር፣ መመሪያና ማስጠንቀቂያ በመስጠት በተለይም ሕዝቡ ነገር ትቶ በልማት ላይ እንዲያተኩር በየአጋጣሚው ሁሉ ምክር በመስጠትና በመቀስቀስ የወንጀልም ሆነ የፍትሀብሔር ክርክሮች በመቶ ዘጠና ስለቀነሱ የአውራጃውና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ከሰአት በኂላ የማያስችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰው እንደነበረ አስታውሳለሁ። የአውራጃው ፍትህ ርትዕ ሁኔታና የሕዝብ ደኅንነት መጠበቅ እዚህ መልካም ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ያስቻሉትን በአጠቃላይ የተነገሩትን ለአድማጭ ዘርዘር አድርጎ መናገር የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

እላይ እንደተጠቀሰው ሕዝቡ በፍርድ ቤት ቀጠሮ ብዛት በመመላለስና ፍትህ ርትዕ በማጣት እንዳይበደል ለማድረግ እኔ በነበረኝ የአውራጃው ፍርድ ቤት ፕሬዚዴትነት ሕጋዊ ሥልጣን በሳምንት ሁለት ቀን እያስቻልኩ ዳኝነት ማየት ጀመርኩ። ቀን ሳስችል የማያቸውን ፋይሎች ቀደም ብሎ ከፍርድ ቤት እያስመጣሁ ከፍትሀብሔርና ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች ጋር እያገናዘብኩ ፋይሎቹን ሌሊት ሳጠና አድርና የመሀል ዳኛ ሆኜ ሳስችል የአውራጃው ፍርድ ቤት መልክ እየያዘ ሔደ። የአውራጃው ፍርድ ቤት መልክ እየያዘ መምጣቱ በየወረዳው ፍርድ ቤቶች ተዘግተው የተፈረዱ በይግባኝ ወደ አውራጃው እየመጡ የተዛቡት ውሳኔዎች መቃናት ብቻ ሳይሆን ቀጠሮ የሚያንዛዙትንና ፍርድ የሚያዛቡትን የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ወቀሳና ምክር ስለሚሰጣቸው ሰቅጠጥ ማለት ጀመሩና የአውራጃው ፍርድ ቤት መቃናት የወረዳ ፍርድ ቤቶችንም መቃናት አስከተለ። በዚህ ሁኔታ የፍርድ ቤት ሥራ እየተቃና ሲሔድ እግዚአብሔር በቀላሉ እንዲፈቱ ያደረጋቸው ሁለት ችግሮች ተደቀኑብኝ አንደኛው ችግር የአውራጃው ገዢ ባሉበት ጉዴዩ የታይልኝ የሚለው የባለጉዳይ ቁጥር ስለበዛ ከሁለት ቀን በላይ ማስቻል ለምፈጽማቸው የአስተዳደርና የልማት ሥራዎች የማውለውን ጊዜ ስለሚያጣብብኝ በሳምንት ከሁለት ቀን በላይ ማስቻል አለመቻሌ ሲሆን ሁለተኛው ለጊዜው ችግር መስሎ ይከሰት እንጂ የአውራጃውን ቀና የፍርድ አፈጻጸም በመቶ ዘጠና ያሻሻለው ጊዜያዊ ችግር ነበር። ይኸውም ዳኞች ተስማምተው ፍርድ ካልሰጡ ፍርዱ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ስለሆነ ከግራና ከቀኜ ተቀምጠው የሚያስችሉት ሁለት ዳኞች ብዙ ጊዜ አብረን በማስቻላችን አወቅኩህ ናቅኩህ ነገር ሆነና ሁለቱ ተባብረው በድምፅ ብልጫ ፍትህ ለማጉዋደል መሞከራቸው ነበር። ሁለት ወፎችን ባንድ ድንጋይ መግደል ከሚባለውም በላይ ሦስት ወፎችን ባንድ ድንጋይ ለመግደል

የሚያስችል አንደኛ በድምፅ ብልጫ ፍትህ ለማጓደል የተዶለተውን ለአንዴና ለመጨረሻ ለማክሸፍ፣ ሁለተኛ ወደፊት ዳኞች የተከራካሪዎችን እጅ ሳያዩ ያለ አድሎ ትክክለኛውን ፍትህ እየሰጡ እንዲያስችሉ የሚያደርግ ሦስተኛ ዳኞች ትክክለኛ ፍርድ እየሰጡ የሚያስችሉ ከሆነ የእኔን በሳምንት ሁለት ቀን ማስቻል ስለሚያስቀር በችሎት ላይ የማውላቸውን ሁለት ቀኖች ለሌሎች ሥራዎች ማዋል እንድችል ማድረግ የሚያስችለኝ ክስተት እግዚአብሔር ፈጠረልኝ።

የተፈጠረው ክስተት በተለይ ጠምጣሚውና የባለጉዳዮችን እጅ ማየት የተጠናወታቸው በቀኝ ተቀምጠው የሚያስችሉት የአውራጃው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቱ አቶ አዳሙ ስለነበሩ ከአውራጃው ሔደው እንድገላገላቸው ሁለተኛ በሔዱበት ቦታም እርኩስ አመላቸውን ምርር ብለው እንዲተውት የሚያደርጋቸው ዳኞች እኔን ያየህ ተቀጣ የሚያሰኛቸውና ፍርድ ሳያዛቡ እንዲያስችሉ የሚያደርግ ነበር፡- ነገሩ እንዲህ ነው፡ በሽማ መሬት ከሚከራከሩት ሁለት ወንድማማቾች አንዱ በሀሰት የሚከራከረው በቀኝ ተቀምጠው ለሚያስችሉት የፍርድ ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ለአቶ አዳሙ ጠቀም አድርጎ እጁን ስለዘረጋላቸው ለሱ አድልተው በድምፅ ብልጫ ለመፍረድ በግራዬ በኩል ተቀምጦ የሚያስችለውን ሦስተኛውን ዳኛ ያግባቡት መሆናቸውን አረጋገጥኩ። ወጥመዱን እስካመቻች ጉዳዩ በቀጠሮ እንዲተላለፍ አድርጌ ተበዳዩን በስውር ጠራሁትና ለማንም እንዳይናገር አስጠንቅቄ አስር ብር ሰጥቼው አንድ ሙክት ገዝቶ ሳይመሽ ከሰጣቸው ስለሚያርዱት በጣም ከመሸ በኋላ ለአቶ አዳሙ እንዲሰጣቸው አደረኩ። ያንኑ እለት ማታ ምክንያቱን ሳልገልጥ የአውራጃውን ፖሊስ አዛዥ፣ የየሚኒስቴሩን ተጠሪዎችና ሁለት በከተማው ውስጥ የታወቁ ያገር ሽማግሌዎችን ጠዋት ከአሥራ ሁለት ሰአት በፊት ለብርቱ ጉዳይ የምፈልጋቸው መሆኔን ገልጬ አውራጃው ግዛት ጽህፈት ቤት እንዲገኙ አደረግኩ። የተቀጠሩት ሰዎች ምን ከባድ ችግር ተፈጠረ ብለው ለማወቅ ስለጓጉ ሁሉም ከቀጠሮው ሰአት በፊት ቀደም ብለው ተገኙና ጉዳዩን ሳልገልጥላቸው አስከትዬ ወደ አቶ አዳሙ መኖሪያ ቤት አመራሁ። ተከታዮቼ ወዴት እንደምንሔድ ለምንስ ጉዳይ እንደሆነ ሳያውቁ እየተንሻካሾኩ ተከትለውኝ ወደ አራዳ በሚወስደው ጎዳና ተጉዘን በማዘጋጃ ቤቱ ዝቅ ብሎ ከምትገኘዋ ወንዝ ሻገር እንዳልን በስተቀኝ የሚገኘው አቶ አዳሙ ቤት ስንደርስ ወደ ቀኝ ተገነጠልኩና የወንጀለኛውን ቤት የአጥሩን በር የቆርቆሮ መዝጊያ በኃይል ስደበድብ ያስከተልኳቸው ባለስልጣኖች አሁንም ግራ ተጋብተው ተደናግጠዋል። የአጠር በር መደብደብ የሰማ አሽከር ከጓሮ በኩል ብቅ ብሎ የአውራጃው ባለስልጣኖች በሙሉ በር ላይ ቆመው ሲያይ በሩን ሳይከፍት ወደ ኋላው ተመለሰ። ወዲያው አቶ አዳሙ በዚያን ፒጃማ መልበስ ባልተለመደበት ዘመን ብሉኮዋቸውን እንዳጣፉ ብቅ አሉና ሙክቱን ማታ እሳቸው ሳያውቁ ለአሽከራቸው ማን ሰጥቶት እንደሔደ የማያውቁ መሆናቸውን ሌሎችንም መማጠኛ ቃላት እየወተወቱ ሲወራጩ የተጣፋው ቡሉኮ እየተነጠለ ከፊል ብልታቸውን ሲያሳይ ልብስ ለመልበስ እንኳን ጊዜ ሳይሰጣቸው በሁለት

*ፖሊሶች ታጅበው የአሥር ብር የደለበ ሙክት እየጐተቱ በከተማው ውስጥ እንዲያልፉ ተደረገ። ደግነቱ ጊዜው በጣም ማለዳ ስለነበረ ብዙም ሰው አላያቸውም፤ ይህ ክስተት በብርቱ ምስጢር እንዲያዝ በማድረግ ዳኞችንና ፖሊሶችን በቢሮዬ ሰብስቤ ምክርና ማስጠንቀቂያ በሰጠሁበት እለት ወሬውን ለአባሎቻቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ እንዲሆናቸው ከሚያነሱት በስተቀር በምስጢር እንዲያዝና ለሕዝብ እንዳይሰራጭ አስጠነቀቅኩ። የዚህ ለዳኞችና ለፖሊሶች ትልቅ መቀጣጫ ሆኖ የፍርድ ቤቶችንና የፖሊሶችን አሠራር በጣም እንዲቃና ያደረገው ጉዳይ በምስጢር እንዲያዝ ቢደረግም እየሾለከ መውጣቱ ስላልቀረ በይፋ አይወራ እንጂ እውነት ነው ውሸት እየተባለ በሹክሹክታ እንደተረተ መነገሩ አልቀረም።*

*እላይ ባጭሩ የተገለጠው ታሪክ ረጅም ስለሆነ ዝርዝሩን መናገር ብዙም ጥቅም ስለሌለው በአጠቃላይ በተነገረው አብቅቼ መደምደሚያውን ባጭሩ ልንገራችሁ፡- የአቶ አዳሙን ጉዳይ ለጠቅላይ ግዛቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳላሳውቅ የፍርድ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ከነበሩት ከክቡር ፊታውራሪ አበበ ገብሬ ጋር በምስጢር ተነጋግረን የአቶ አዳሙ ወንጀል እንደተሸፈነ ያው ብዙም ሰው ሳያያቸው በማለዳ ቡልኮ እንደለበሱ በከተማ መካከል በግ የጎተቱት ቅጣት በቂ ሆኖ ወደ ጋምቤላ እንዲዛወሩ ተደረገ። በየጊዜው ለዳኞችና ለፖሊሶች ሕዝቡን በቅንነትና በፍትህ እንዲያገለግሉ በሚሰጠው ምክርና መመሪያ ላይ በአቶ አዳሙ ላይ የተወሰደው እርምጃ ተጨማሪ ሆኖ የአውራጃውን የፍትህ ሥርአት አቃንቶታል ብዬ አምናለሁ። ለኔም ለመጀመሪያው አንድ ዓመት ተኩል ያህል በሳምንት ሁለት ቀን በዳኝነት እቀመጥ የነበረውን ስላስቀረልኝ ጊዜውን ለአስተዳደርና ልማት ሥራዎች ማዋል አስችሎኛል። በእንደዚህ ባሉ የተወሰዱ ልዩ ልዩ እርምጃዎች በአውራጃው ፍትህ ርትዕ እየሰፈነ ስለሔደና ሕዝቡ ነገር ትቶ ራሱን በራሱ ለመርዳትና ኑሮውን ለማሻሻል በልማት ሥራ ላይ እያተከረ ስለሔደ እላይ እንደጠቀስኩት የፍርድ ቤቶች ሥራ በጣም እየተቃለለ ስለሔደ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የአውራጃው ፍርድ ቤቶች ከሰአት በኋላ የማያስችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር።*

*በሥራ ምክንያት ከፍተኛ ጠብ ላይ ደርሰን እንጉዋሸም የነበርነው ሰዎች በአውራጃ ገዢነት ስም ከአዲስ አበባ ወደ ወላይታ አውራጃ እንድባረር ሲያደርጉ ግራ ተጋብቼ ሥራ እንዳልሠራ አድርገው ለማስወቀስ ብዙ መሰናክሎችን አጥምደውብኝ ነበር። አንደኛው መሰናክል እኔ ወደ አውራጃው እንደተጋዝኩ ቀደም ብሎ ለአውራጃው ተመድበው ይሠሩ ከነበሩት አንድ መቶ ሃምሳ የፖሊስ አባላት ውስጥ ሃምሳውን ወደ ሌላ አዛውረው በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ በብዛት ወንጀል በመፈጸም ይታማ የነበረውን የወላይታ ሕዝብ በመቶ የፖሊስ አባላት ብቻ ሰላሙና ንብረቱ እንዲጠበቅ ማድረግ ስለማይቻል ሕዝቡ ሰላም አጥቶና ችግር ተፈጥሮ ከመሔዱ እንዲህ አደረገ አሰኝቶ ማስወቀስ ይህን ዐይን ያወጣ ደባ ስለፈጸሙብኝ ለበላይ ብጮህም የሚሰማኝ አጣሁ። ይህን ችግር ለማቃለል አንድ መቶ ባለማደሪያ ነጭ ለባሾች ቀጥሬና አሰልጥኜ የሕዝቡን ደኅንነትና*

ንብረት በመጠበቅ በኩል ፖሊሶችን እንዲረዱ ለማድረግ የጠየኩትም አልተፈቀደልኝም። ስለዚህ አቶ ገርማሜ ነዋይ ሕዝቡ ራሱን በራሱ ደኅንነቱንና ንብረቱን መጠበቅ እንዲችል «ሰንተርያ» የሚል ስም የተሰጠው የጥበቃ ሥርአት ፈጥሮ የነበረው ሥራ እሱ ከሔደ በኋላ ተቋዋርጦ ስለነበረ በተጠናከረ ሥርአት ባለው መልክ እንዲቋቋምና የሕዝቡን ደህንነትና ንብረት በመጠበቅ ለፖሊስ ረዳት ሆኖ እንዲሠራ አደረኩ። ይኸውም ከየአቅጣጫው የሚመጡ መንገዶች የሚገናኙባቸው አማካይ መስቀለኛ መንገዶች ላይ ቤቶች እየተሠሩ በአንድ የጥበቃ ቦታ ከአካባቢው ነዋሪዎች የተውጣጡ አሥር ሰዎች ለአርባ ስምንት ሰአት ተመድበው ተላላፊዎችን እየተመለከቱና የሚጠረጥሩትን ሰው አቁመው እየጠየቁ እንዲቆጣጠሩ ከአሥሩ ጠባቂዎች ውስጥ አምስቱ በየአካባቢያቸው መንደሮች እየተዘዋወሩ የነዋሪውን ሰላም እንዲጠብቁ ወንጀል ሲያጋጥማቸው ወዲያው ወደ ወረዳው ፖሊስ ወስደው ከነመረጃው እንዲያስረክቡ የሚያደርጉ «ሰንተርያዎች» (ቃፊሮች) ተቋቁመው ከፖሊስ ጥበቃ በተሻለ ሁኔታ የሕዝቡን ሰላምና ንብረት ይጠብቁ ጀመር። እነዚህ ሰንተርያዎች ሥራቸውን በሚገባ መሥራታቸውን በቅርብ እንዲቆጣጠሩዋቸው በቅርባቸው ለሚገኙት ቀበሌ ተጠሪዎች ጭቃ ሹሞችና ወረዳ ገዢዎች መመሪያ መስጠት ብቻ ሳይሆን እራሴ በአውራጃው ውስጥ እየተዘዋወርኩና በድንገት እየደረስኩ በመቆጣጠር ሕዝብ ራሱን በራሱ ደኅንነቱንና ንብረቱን እንዲጠብቅ ስለተደረገ ወደ አውራጃው እንደሔድኩ አንድ ሦስተኛው የፖሊስ ኃይል እንዲቀነስ የተደረገው ደባ መክሸፍ ብቻ ሳይሆን ደባውን ለማክሸፍ የተወሰደው እርምጃ ከፖሊስ አባላት በበለጠ ሁኔታ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ተገኝና የሴረኞችን ቅስም ሰብሮ አሳፈራቸው።

በአውራጃው ውስጥ በሚፈጸሙ ወንጀሎች በኩል ከፍተኛ ድርሻ የነበረው በየአካባቢው በብዛት የተቋቋሙት ገበያዎች ወደ ማታ ከአሥራ አንድ ሰአት ጀምሮ ሌሊቱን ሙሉ ደርተው ስለሚያድሩ በገበያውና ከገበያ ወደየቤታቸው ሲመለሱ በየመንገዱ በመጠጥ ኃይል እየተደፋፈሩና በሌሊት ጭለማ እየታገዙ የሚፈጸሙት ልዩ ልዩ ወንጀሎች ነበሩ። በእነዚህ በየአካባቢው በብዛት በተቋቋሙትና ሌሊቱን ሙሉ ደርተው በሚያድሩ ገበያዎች በርካታ ሰንጋዎች እየታረዱ ገበያተኛው ሥጋ እየበላ ካቲካላና የአገር ባህል መጠጥ «ቦርዴ» እየጠጣ በመስከር እስከ ግድያ የሚያደርሱ አምባጉዋሮዎች እየተነሱ፣ ሴቶች እየተደፈሩ፣ ደካሞች እየተዘረፉ፣ ቂርሾ የነበራቸው ሰዎች የተቃራኒዎቻቸውን ቤቶች እያቃጠሉ የሚፈጠሩት ልዩ ልዩ ወንጀሎች በርካታ ነበሩ። የገበያዎች ሌሊቱን ሙሉ ደርቶ ማደር በጨለማ ለመገበያየትም ሆነ ለተጠቀሱት ወንጀሎች መፈጸም የሚያመች በመሆኑ ገበያዎች ቀን ከማለዳ ጀምሮ እስከ አሥራ አንድ ሰአት ብቻ እንዲደሩና ከአሥር ሰአት ጀምሮ ገበያተኞች ወደየቤታቸው መመለስ እንዲጀምሩና በአሥራ አንድ ሰአት ገበያው እንዲበተን ተወስኖ ውሳኔውን እንዲያስፈጽሙ ለወረዳ አስተዳዳሪዎች መመሪያ ተላለፈ። ወረዳ አስተዳዳሪዎች በበኩላቸው ለጭቃ ሹሞችና ለቀበሌ ተጠሪዎች

መመሪያውን አስተላልፈው ጥብቅ ቁጥጥር ተጀመረ፡፡ ይህን ለብዙ ዘመን የቆየ የሕዝብ ባህል ባጭር ጊዜ ውስጥ ማስቀረቱ ያስቸገረ ቢሆንም በመጨረሻው ሕዝቡ ቀን በብርሃን መገበያየቱን እየለመደው ስለሔደ በወላይታ አውራጃ በተለይ የቤት ማቃጠል በኢትዮጵያ ውስጣ በጣም ከፍተኛ የነበረው ወንጀል ጠፍቶ ነበር፡፡ የሌሊት ገበያ እንዲቀር ከተደረገ በኋላ በአጠቃላይ የአውራጃው የወንጀል ሥራ ከሌሎች ከተወሰዱ የወንጀል ሥራዎች መካከል እርምጃዎች ጋር ተዳምሮ በአውራጃው ውስጥ ይፈጸሙ የነበሩት ልዩ ልዩ ወንጀሎች በመቶ ዘጠና ቀነሱና ያ በጠቅላይ ግዛቱ ከሚገኙት አውራጃዎች ሁሉ በበለጠ በወንጀል ሥራው ከፍተኛነት ይጠቀስ የነበረው የወላይታ አውራጃ በወንጀል ሥራው ከፍተኝነት ሳይሆን ከጠቅላይ ግዛቱ አልፎ በአገር ደረጃ በከፍተኛ የልማት ሥራ እንቅስቃሴው የሚታወቅ ሆነና እስካሁን እንደተገለጠው የሕዝቡም መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ ከሞላ ጎደል ሊሟላለት ችሏል፡፡

## የልማት ሥራዎች እንቅስቃሴ

የሕዝባዊ መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ ማግኘት እና ዘላቂ የልማት ሥራዎች የማይለያዩና የሚደጋገፉ ተግባሮች ስለሆኑ ከዚህ በላይ በወላይታ አውራጃ ሕዝቡ መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝ ጥረት ሲደረግ የሕዝቡም የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችም ይፈጸሙ ነበር፡፡ ስለዚህ ከዚህ በላይ የተገለጡት ሕዝቡ መልካም አስተዳደርና ፍትህ ርትዕ እንዲያገኝ የተደረጉት ጥረቶችና ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተላቸው በየርዕሳቸው ተለይተው የሚነገሩት የልማት ሥራዎች ሁሉም ባንድ ላይ ጎን ለጎን ይካሔዱ ነበር እንጂ ጊዜ ተለይቶላቸው በቅደም ተከተል የተፈጸሙ አለመሆናቸውን ላስታውስ እፈልጋለሁ፡፡

### *አውራጃው ካርታ ተነሳና የሕዝብና የቤት ቆጠራ ተካሔደ፡-*

በአውራጃው ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ለማካሔድ የአውራጃውን ቆዳ ስፋት፣ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የአፈሩን ዓይነትና አጠቃቀም የመሬት ሥሪትና ይዞታ እንዲሁም የሕዝቡ ቁጥጥርና አሰፋፈር በቅድሚያ ማወቅ የሚያስፈልጉ ስለሆነ እነዚህን ለልማት መሠረት የሆኑ ነገሮች እንዲታወቁ ማድረግ አስፈላጊ ነበር፡፡ ስለዚህ ወደ አውራጃው ሔጄ ሥራ ከመጀመሬ በፊት የተጠቀሱት ሥራዎች የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ የልማት ድርጅት የበላይ ባለሥልጣኖች ወደ ወላይታ አውራጃ እንድሔድ እንደታዘዝኩ ወደ አውራጃው ከመሔዴ በፊት የተጠቀሱት ሥራዎች የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ የልማት ድርጅት የበላይ ባለሥልጣኖች ወደ አውራጃው ከመሔዴ በፊት አነጋግሬያቸው እንደነበር ቀደም ብዬ ገልጫለሁ፡፡ ባለስልጣኖቹን ሳነጋግር ተስፋ በሰጡኝ መሠረት ለካርታው ሥራ የሚያስፈልገውን የአየር ፎቶግራፍ ከአውራ ጎዳና ባለስልጣን ካገኘሁ በኋላ የካርታ ሥራ ባለሙያዎች ከውሀ ሐብት ልማት ድርጅትና ከካርታ ሥራ ኢኒስቲትዩት ለካርታ ሥራ ከሚያስፈልጋቸው መሣሪያዎች ጋር

ተልከውልኝ የወረዳ አስተዳዳሪዎች ከአጠገባቸው ሳይለዩ በሕዝቡ ጉልበት እየተረዱ እኔም በየጊዜው በሥራቸው ላይ እየተገኘሁ በማበረታታት ሥራቸውን በቅልጥፍና ማካሔድ ጀመሩ።

እነዚያ ወደ አውራጃው የተላኩት የካርታ ሥራ ባለሙያዎች በዚያን ጊዜ በነበረው የሠራተኞች በአገር ፍቅር በተመሠረተ የሥራ ትጋት ሌት ተቀን ሠርተው የአውራጃውን ካርታ ማንሳት ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቀቁ። የካርታውን ሥራ እንዳጠናቀቁ የነበሩት አሥራ ሁለት ወረዳዎች ተሰርዘው ሦስቱ ወረዳዎች ወደ ሰባት ከፍ ብለው እንዲደለደሉ አጥንተን ስለነበረ አንዱ ወረዳ ከሌላ ወረዳ የሚዋሰንበትን ጭምር በትክክል አውራጃው ካርታ ላይ እንዲሰፍርና በመሬት ላይ እንዲከለል አደርጉልን። ባለሙያዎቹ በዚህ ሁኔታ ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የውሀ ልማት ድርጅት በዕርዳታ ብዙ የቅየሳ መሣሪያዎች (ቴዎዶላይቶች፣ ጃሎዎችና ባለሃምሳና ሰላሳ ሜትር ጥቅል ሜትሮች) መጋዘናቸውን ያጨናነቁት መሆኑን ግምጃ ቤቱ ውስጥ ገብቼ ያየሁት ስለነበረ የውሀ ልማት ባለሙያዎች ወደ አውራጃው ይዘዋቸው የሔዱትን የቅየሳ መሣሪያዎች እዛው ለአውራጃው ግዛት የልማት ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ትተው እንዲሔዱ ስላደረኩ የባለሙያዎቹ ኃላፊ የነበሩት እስካሁን ባዩኝ ቁጥር «ባገለገልን መሣሪያዎቻችንን ነጥቀህ አባረርከን» እያሉ በውስጠ ወይራ ቀልድ እየወቀሱኝ እንሳሳቃለን። ያም ሆነ ይህ ባለሙያዎቹ ጥለውልን የሔዱዋቸው የቅየሳ መሣሪያዎች ከአውራጃው አልፈው ለጠቅላይ ግዛቱ የልማት ሥራዎች ከፍ ያለ አገልግሎት ሲሰጡ ኖረዋል።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው የአውራጃው ካርታ ሥራ ሲካሔድ የአውራጃው ሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ዝግጅት ይካሔድ ስለነበረ የካርታው ሥራ እንዳለቀ የሕዝብና የቤት ቆጠራው ሥራ ተጀመረ። ከማእከላዊ ስታቲስቲክስ ዋና መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቶ ሐብቱ እሸቴ ጋር ተነጋግሬ ያገኘሁትን የሕዝብ ቆጠራ ፎርም አሞላል ለማጥናት ብቃትና ወጣትነት ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞች አስተማሪዎችና በአስተማሪዎች የተመረጡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መሥሪያ ቤት በተላኩልን አሰልጣኞች የፎርሙን አሞላል አጠኑ። ሰልጣኞቹ በአዲሱ ካርታ የወረዳ ድልድሎች መሠረት በቡድን እየተከፋፈሉና የቡድን መሪ እየተደረገላቸው ወረዳ ገዢዎች ጭቃ ሹሞች፣ የቀበሌ ተጠሪዎች፣ የአውራጃውን ቀበሌዎች የሚያውቁ የአገር ሽማግሌዎች ተመድበውላቸው የየቡድኑ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ክልል በካርታ ላይ ተከለለና መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ለሦስት ቀናት ተዘግተው ቆጠራው ተጀመረ። የማዕከላዊ ስታቲስቲክ መሥሪያ ቤት ከሰጠን ፎርሞች በስተቀር ሌላ ወጪ ሳያስፈልግ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሥራና ማቀነባበሩም ጭምር ሦስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስለተጠናቀቀ ጉድ ተባለ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ለልማት ሥራዎች መሠረት የሆኑትን የአውራጃው ካርታ እንዲዘጋጅ፣ የሕዝብና የቤት ቆጠራ እንዲካሔድ ለማድረግ የተባበሩት

መንግሥታት የልማት ድርጅቶች ምንም እንኳን ያደረጉልን ትብብር የጋራ የአገር ልማት ቢሆንም አስገዳጅ ነገር ሳይኖርባቸው በፈቃደኝነት፣ በቅንነትና በአገር ዕድገት ወዳድነታቸው የፈጸሟቸው ስለሆነ በአውራጃው ለተፈጸሙ የልማት ሥራዎች መሠረት በሆኑት መልካም ተግባሮች ስለተባበሩን የአውራጃው ሕዝብም ሆነ እኔ ባለውለታዎች መሆናችንን እየገለጽን ስናመሰግናቸው እንኖራለን፡፡

### የሬዲዮ ቴሌፎን ከዚያም የስልክ አገልግሎት ጀመረ፡-

ቀደም ብሎ እንደገለጥኩት ከለገጣፎ የአርባ ስምንት ሰአት ሽፍትነት ተመልሼ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ከቀረብኩና ምክርና ግሳጼ ከተሰጠኝ በኋላ አንዳንድ የልማት መሥሪያ ቤቶችን አነጋግሬ ከቴሌኮሚኒኬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በትሩ አድማሴ ጋር አውራጃውን ኦፊሴል ያልሆነ ጉብኝት አድርገን መመለሳችን ይታወሳል፡፡ አቶ በትሩ ወደ አውራጃው አስከትለዋቸው ከሔዱት የቴክኒክ ክፍል ኃላፊዎች ጋር ካደረጉት ጥናት በተጨማሪ አከታትለው ወደ አውራጃው የላኩዋቸው አጥኚዎች ሥራ ተጠናቶ የሬዲዮ ቴሌፎን ማስገባት እንዲቻል ቤት እንድንሰጣቸው ጠየቁን፡፡ ወደአውራጃው እንደሔድኩ ካሳደስኩት የማዘጋጃ ቤት ጽህፈት ቤት ሠራተኞች አሸጋሽገን ሁለት ክፍል ሰጠናቸውና የሬዲዮ ቴሌፎን አገልግሎት ተጀመረ፡፡ ለንግድ ሥራም ሆነ ለሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ከአውራጃው ውጪ መገናኘት ችግሮአቸው የነበሩት የአውራጃው ነጋዴዎችና ሕዝብ ከአዲስ አበባና የመገናኛ አገልግሎት ካላቸው የኢትዮጵያ ከተሞች ጋር ለመገናኘት ተራ የሚጠብቁት የማዘጋጃ ቤቱን ጽህፈት ቤት ግቢ አጨናነቁት፡፡

የሬዲዮ ቴሌፎን አገልግሎት ከተቋቋመ በኋላ የአውራጃው ሕዝብ የቴሌፎን አገልግሎት ፍላጐት በተደረገው ጥናት ከትልቅ ከተማ የማያንስ በጣም ብዙ ስልክ በየቤታቸው እንዲገባላቸው የሚፈልጉ ሰዎች ስለተገኙ ሬዲዮ ቴሌፎን ከተቋቋመ በኋላ ወዲያው ከሻሸመኔ የስልክ መስመር መዘርጋት ተጀመረና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሥራው ተጠናቆ የአውራጃው ሕዝብ የስልክ ተጠቃሚ ሆነ፡፡ መጀመሪያ የሬዲዮ ቴሌፎን መቋቋም፣ ቀጥሎም የስልክ አገለግልግት መጀመር የአውራጃውን የልማት እንቅስቃሴ ከማንኛውም ነገር ሁሉ ይበልጥ ያፋጠነው ስለሆነ «የወላይታ ልማት በአቶ በትሩ አድማሴና በረዳቶቻቸው እርዳታ ተሳካ» እያልን ባለውለታዎቻቸው መሆናችንን በመግለጥ ስናመሰግናቸው እንኖራለን፡፡

### የባንክ አገልግሎት ሥራ ተጀመረ፡-

የወላይታን አውራጃ ከመኀብኘቴ በፊት በቀደምትነት ካነጋገርኳቸው የልማት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች ውስጥ እንደ አቶ በትሩ አድማሴ ሁሉ አቶ ተፈራ ደግፌንም አነጋግሬ ነበር፡፡ ለመርዳት በገቡልኝ መሠረት ወደ አውራጃው አጥኚ ቡድን ልከው ጥናቱ የተጠናቀቀ ስለሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የራሱን ቤት

እስኪሠራ ለባንክ አገልግሎት የሚያመች ሦስት ክፍል ቤት እንዲፈለግላቸው ጠየቁኝ። ስለዚህ በጥድፊያ ከአሠራነው የአውራጃ ግምጃ ቤት ጽህፈት ቤት ሕንፃ የጠየቁትን ሦስት ክፍሎች ሰጠናቸውና ሥራ ጀምረው የሶዶ ከተማ ነጋዴዎችና በአጠቃላይ የአውራጃው ሕዝብ የባንክ አገልግሎት ማግኘት ጀመረ።

ባንኩ ሥራ ሲጀምር ያገኘነው ጥቅም ከሚሰጠው የባንክ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በዚያ ለሥራ የምናውለው ገንዘብ ብርቅ በሆነበት ዘመን ለሰጠናቸው ሦስት ክፍል ቤቶች ጠቀም ያለ የወር ኪራይ ሲከፍሉን ቆይተው ነበር። በኋላም የራሳቸውን ቤት ሠርተው ሲወጡ በኪራይ ይጠቀሙባቸው በነበሩት ክፍሎች ውስጥ የነበሩት ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን ዘመናዊ የቢሮ እቃዎች ሰጥተውን ክፍሎቹን አድሰው ስላስረከቡን የአውራጃውን ግምጃ ቤት በዘመናዊ የቢሮ እቃዎች አሸበረቁልን። ለዚህ የማይረሳ እጥፍ ድርብ ውለታቸው አቶ ተፈራ ደግፌን ስናመሰግናቸው እንኖራለን።

***የየብስና የአየር መገናኛ አገልግሎቶች ተሻሻሉ፡-***

እላይ ከተገለጡት ከባንክና የስልክ መገናኛ አገልግሎቶች በተጨማሪ ለአውራጃው ልማትና የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በቅድሚያ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ሥራዎች ውስጥ የየብስና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች መኖር ናቸው። ስለዚህ የወረዳዎችን ዋና ከተሞች ከአውራጃው ከተማ ሶዶ እንዲሁም የወረዳዎችን ከተሞች አንዱን ከሌላው የሚያገናኙ ሌላው ቢቀር በበጋ ወራት እንደልብ የሚያገለግሉ ጥርጊያ መንገዶች እንዲኖሩ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ የየብስና የአየር መገናኛን አገልግሎት ጥቅም ሕዝቡ እንዲያውቅና በመንገድ ሥራ ላይ እንዲተባበርና እንዲረባረብ ማድረግ ያስፈልግ ነበር።

ስለዚህ በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ሕዝቡን በመሰብሰብ እንዲሁም በሚደረጉ ሌሎች ስብሰባዎች ሁሉ ሴቱም ወንዱም ሕጻን ሽማግሌ ሳይቀር በመኪና መንገዶች ሥራ ላይ እንዲረባረቡና የየወረዳው ሕዝብ በፉክክር መልክ እንዲሠራ ምክርና መመሪያ ተሰጠ። በየሥራ ቦታው እየተገኘሁ ከወረዳና ምክትል ወረዳ አስተዳዳሪዎች ጋር ሆነን እንደመሀንዲስ መንገድ እየቀየስን የእንጨት ድልድዮችን አሠራር እያሳየን ወደ አውራጃው የሔድኩበት 1955 ዓ.ም ሳያልቅ የወረዳ ዋና ከተማዎች ሁሉ ከአውራጃው ከተማ ከሶዶ በምቹ ጥርጊያ የመኪና መንገድ ተገናኙ። በላንድ ሮቨር ሳይሆን የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ሳላስረክብ ወደ አውራጃው ይገኙ የነበረው ... በሔድኩት ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ በሰርቪስነት እንድገለገልባት አስገዝተውልኝ በነበረች ቮክስ ቫጎን አውቶሞቢል ወደየወረዳው እየተሽከረከርኩ በየወረዳውና በየቀበሌው የሚካሔዱትን የአስተዳደርም ሆነ የልማት ሥራዎች ድንገት እየደረስኩ መቆጣጠርና ማበረታታት ቻልኩ። በልማት ሥራዎች እርዳታ ለማድረግ ወደ አውራጃው የሚመጡ በየወረዳዎችና በየቀበሌዎች እንደልባቸው እየተዘዋወሩ

ማየትና ማጥናት ስለቻሉ ሥራቸው እየተቃናላቸው ውጤት የሚያስገኝ ሆነ። ገበሬው ሶዶ ከተማ ድረስ ሳይንገላታ በየወረዳው ዋና ከተማ ገበያዎች ምርቱን እያቀረበ ሸጦ ተመልሶ አቤቱ ማደር ቻለ። የሶዶና የወረዳ ከተሞች በመንገድ መገናኘት የአስተዳደሩ ሥራ እንዲቃና የንግዱ እንቅስቃሴ እንዲፋጠን በአጠቃላይ የሁሉንም ኅብረተሰብ ክፍል ሥራ እንዲቃናና ጥቅም እንዲያገኝ አደረገው።

ሕዝብ በጉልበት የመንገድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የነበረው እስከ 1957 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የመንገዱ ሥራ ደረጃ ከፍ አለና ሕዝቡ ራሱን በራሱ በመርዳት የሚፈጽማቸውን የልማት ሥራዎች ጥቅም ስለተረዳ የመንግሥት ግብር ሲከፍል ለልማት በዓመት እንደችሎታው ካንድ እስከ ሦስት ብር ይከፍል በነበረው የልማት ገንዘብ የመንገድ ሥራ መሣሪያዎች ተገዙና የመንገዱ ሥራ ከሰው ጉልበት ወደ መንገድ መስሪያ መሣሪያዎች ተሸጋገረና የመንገዱም ሥራ ጥራት ተሻሻለ። መንገዶቹ የውሀ መውረጃ ቦይና የሲሚንቶ ቱቦ ፉካዎች ያላቸው አንደንዶቹ የተፈጥሮ ጠጠር የለበሱና በጋ ከክረምት የሚያገለግሉ የብረት ድልድዮች የተዘረጋላቸ ደረጃቸው ከፍ ያለ ሆነ። ለኢንቬስተሮች የሚያገለግሉ ሰው አልሰፈረባቸው ለሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች የሚያመቹ ድንግል መሬቶች በሚገኙባቸው የብላቴን ወንዝ ሸለቆና የአባያ ሐይቅ ዳርቻ በጋ ከክረምት የሚያገለግሉ የመኪና መንገዶች ተሠሩና ብላቴን ወንዝ ላይ የብረት ድልድይ ተዘረጋ። ይህን ለልማት አመች የሆነ ቅድመ ዝግጅት የተመለከቱ አትክልትና ፍራፍሬ እያመረቱ ወደ አውሮፓ የሚልኩና ለአገር ውስጥ ፋብሪካዎች ጥጥ የሚያመርቱ ሁለት ትላልቅ የውጪና አራት መካከለኛ ኢትዮጵያውያን ኢንቬስተሮች የእርሻ ልማት ይሠሩ ስለነበረ በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ለአውራጃው ሕዝብ ሰፊ የስራ እድል ከፍተው ስለነበረ ሕዝቡ በየአመቱ ለልማት ይከፍል የነበረው በጣም አነስተኛ የልማት ገንዘብ በሺህ የሚቆጠር ብር ሆኖ ተመልሶለታል። የአውራጃው የመንገድ ሥራ የልማት ክፍል በጣም ተጠናክሮ ስለነበረ በመንገድ እጦት በጣም ለተቸገሩ ለጎረቤት አውራጃዎች እርዳታ መስጠት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር።

በየብስ በኩል ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት እላይ እንደተገለጠው ከሰው ጉልበት ወደ መንገድ መስሪያ መሣሪያዎች ተሸጋግሮ ከፍ ያለ ጥቅም መስጠት ደረጃ ለይ የደረሰ ሲሆን የአየር መገናኛውም እንደዚሁ በተሳካ ሁኔታ ተፈጽሟል። የሶዶ ከተማ ከጠላት ወረራ በፊት ጀምሮ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ታገኝ ነበር። ሆኖም የአይሮፕላን ማረፊያው በበጋ ብቻ የሚያገለግል የተፈጥሮ የከብቶች ማጋጫ ረባዳ ሜዳ ስለነበረ አገልግሎቱ ውሱን ነው። በሳምንት አንድ ቀን በሚያደርገው በረራ የአይሮፕላኑ ማረፊያ ሰአት ሲደርስ ለዚሁ ሥራ የተመደቡ ዘበኞች ሜዳው ላይ የሚግጡትን የቀንድና የጋማ ከብቶች ማስወጣትና ተመልሰው ወደ ሜዳው እንዳይገቡ መከላከል ነበረባቸው። ከሰኔ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ህዳር ወር ባለው የክረምት ወራት ያ ረባዳ ሜዳ የዝናብ ውሀ ስለሚሞላ የአየር አገልግሎቱ ይቋረጥ ነበር። ስለዚህ

የአየር አገልግሎቱ በጋ ከክረምት ማገልገል ብቻ ሳይሆን በሳምንት የሚያደርገውን በረራ ቀናት ከፍ ማድረግ እንዲችል ለእንስሳትም ሆነ ለሰው ዝግ የሆነ ወደፊት ሜዳው ተስፋፍቶ ለትልልቅ የአይሮፕላኖች ማረፊያ ማገልገል የሚችል የአይሮፕላን ሜዳ ቦታ ተመረጠ። አዲስ የተመረጠው የአይሮፕለን ማሳረፊያ ቦታ በአውራጃዋ ሕዝብ የጉልበት ሥራ ሜዳው ተደልድሎና አምሮ ከተዘጋጀ በኋላ የኢትዮጵያ የአየር መንገድ እንዲረከብ ተደረገ። ድርጅቱ ሜዳውን ተረክቦ እስካሁን ያልተለወጠውን ለደረቅ ጣቢያዎች ባዘጋጀው ፕላን መሠረት ለቢሮ ለዘበኞችና ለእቃ መጋዘን የሚያገለግሉ ክፍሎች ያሉት ቤት ሠርቶ በሳምንት የሚያደርገውን በረራ ቀናት ጨምሮ አገልግሎት በጋ ከክረምት መስጠት ጀመረና ሕዝቡ አስተማማኝ የሆነ የአየር በረራ ተጠቃሚ ሆነ።

## የከተሞች ልማት እንቅስቃሴ

አውራጃው በሰባት ወረዳዎች ተደልድሎ ለከተሞች መስፋፋትና ለወረዳው ሕዝብ አገልግሎት አማካይ በሆኑ ቦታዎች የወረዳ ከተሞች መቆርቆራቸውን ቀደም ብሎ ተናግሬያለሁ። እነዚያ አዲስ የተቆረቆሩ ከተሞችና በተለይ የአውራጃው ዋና ከተማ ሶዶ በጥናት ላይ የተመሠረተ ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶላቸው ለከተማዎቹ ነዋሪዎች የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ ከሌሎቹ የልማት ሥራዎች ጋር ጎን ለጐን የወረዳ ከተሞች ማስተር ፕላን ጥናትና ዝግጅት ይካሔድ ነበር።

የወረዳ ዋና ከተሞች ማስተር ፕላን ጥናት የተጀመረው አውራጃው በሰባት ወረዳዎች ተደልድሎ የወረዳ ዋና ከተሞች ከተቆረቆሩ በኋላ ሲሆን የሶዶ ከተማ ማስተር ፕላን ጥናት ግን የተጀመረውና የተጠናቀቀው ቀደም ብሎ ነው። በአገር ግዛት ሚኒስቴር የማዘጋጃ ቤቶች ክፍል ይተዳደሩ የነበሩት የጠቅላይ የአውራጃና የወረዳ ግዛቶች ዋና ከተሞችን ማልማት እንዲቻል ጥናት እያካሔዱ ማስተር ፕላን እንዲያዘጋጁ ከእስራኤል የመጡ ባለሙያዎች ለጥናታቸው የሚያስፈልጉዋቸው ዕቅድና ዕቅዱን ለመፈጸም መሣሪያዎችና የሰው ኃይል እስኪዘጋጁላቸው በአገር ግዛት ሚኒስቴር የማዘጋጃ ቤቶች አስተዳደር ክፍል ያለ ሥራ ተቀምጠው ነበር። በዚህ እድል ለመጠቀም የባለሙያዎቹ መሪ የነበሩትን ሚስተር ፓቬልን እንዲረዱኝ በግል አነጋግሬ አዎንታዊ መልስ ስላገኘሁ ባለሙያዎቹ ወደ ሶዶ ከተማ ሔደው ከተማዋን እንዲያጠኑና ማስተር ፕላን እንዲያዘጋጁልኝ የክፍሉ ኃላፊ የነበሩትን አቶ አልፍሬድ ሻፊን አነጋግሬ ባለሙያዎቹ ወደ አውራጃው ተላኩልኝ። ቀደም ብሎ እንደተገለጠው የውሀ ልማት ድርጅትና የካርታ ሥራ ኢንስቲቲውት ሠራተኞች የአውራጃውን ካርታ ሲሠሩ ለከተማ ማስተር ፕላን ዝግጅት አስፈላጊ የሆነው የቶፖግራፊ ካርታ ሠርተውት ስለነበረ እነሚስተር ፓቬል ወደ ሶዶ ሲሔዱ ለከተማው ማስተር ፕላን ጥናትና ዝግጅት የሚያስፈልጋቸው ከባዱ የቶቶግራፊ ካርታ ሥራ ተዘጋጅቶ ስለጠበቃቸው የከተማውን ማስተር ፕላን ለማዘጋጀት

*የሚያስፈልጉዋቸውን ሌሎች መረጃዎች ለመሰብሰብ የሶዶን ከተማ እየተዘዋወሩ ከማጥናት በስተቀር ችግር አልገጠማቸውም። ስለዚህ ለማስተር ፕላኑ ሥራ የሚፈልጓቸውን መረጃዎች ሰብስበው ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ የሶዶን ከተማ ዘመናዊ ማስተር ፕላን ባጭር ጊዜ ውስጥ አዘጋጅተው በኦፊሴል ተላከልኝ።*

*የኢትዮጵያን የምድር ጦር የመሀንዲስ መመሪያ በማሰልጠን ላይ የነበረው ማግ የሚባለው የአሜሪካን መንግሥት ድርጅት ርዳታ በሰጣቸው የመንገድ ሥራ መሣሪያዎች የሰለጠኑ ወታደሮች መለማመጃ ቦታ ስለሚፈልጉ ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር በነበርኩበት ጊዜ ከክፍሉ ጋር ተነጋግሬ ከኤረር ገዋኔ አዲስ የመኪና መንገድ እሠራ እንደነበር ቀደም ብዬ ተናግሬያለሁ። አሁንም የምድር ጦር መሐንዲስ ክፍልን ርዳታ ጠየኩና ከኛም በመጠኑ በታከለበት በራሳቸው ነዳጅና አበል በእስራኤላውያኑ ባለሙያዎች በተዘጋጀው ማስተር ፕላን መሠረት የሶዶን ከተማ ሰፋፊ መንገዶችን መክፈትና ማስተካከል ተጀመረ። መቼም የልማት ሥራ ሲካሔድ ሁሉን ቀይቶ የሚጠቅም መሆኑ ቢታወቅም ለጊዜው አንዳንድ ሰዎችን መጉዳቱ አይቀርምና መንገዶች ሲከፈቱ በጊዜው የአንዳንድ ሰዎችን ሮሮ ዘግይቶ ደግሞ በፍርድ ቤት መከሰስ ያስከተለብኝን የአርባ የሰላሳና የሀያ ሜትር ስፋት ያላቸው መንገዶችን መክፈት ሥራ ተጠናቀቀ።*

*የምድር ጦር መሀንዲስ ክፍል የመንገድ ሥራ መሣሪያዎች የሶዶን ከተማ መንገዶች መክፈት ሥራ ሲጨርሱ ቆላና ሞቃት በሆነ ቀበሌ የሚገኘውን አበላ የሕዝብ ማስፈር ተጀምሮ የሚካሔድበትን ቀበሌ የደን ምንጣሮና የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና ከአበላ እስከ አባያ ሀይቅ ለመዝናኛ የታቀዱት ፍል ውሀዎች እስከሚገኙበት ያለውን ጎዳና እንዲከፍቱ ተላኩ። ያለእረፍት እንዲሠሩ በኔ በኩል የነበረባቸው የስራ ጫና በተለይ ደግሞ ከከተማ መራቃቸውና ትኩስ እንጀራ እየበሉና ማታ ማታም ከሚዝናኑበት የሶዶ ከተማ ተለይተው በጣም ሞቃት በሆነ አካባቢ በድንኳዋን ውስጥ መኖር ወታደሮችን አስመርሩዋቸው ኖሯል። እኔ ሳላውቀው ከመሥሪያ ቤታቸው ጋር ተጻጽፈው ወደ አደስ አበባ ለመመለስ አስፈቅደው ኖሮ የመሰነባበቻ ግብዣ እንኳ ሳናደርግላቸውና የምስጋና ሸኚ ደብዳቤ ሳልሰጣቸው ምን ጊዜ ከአውራጃው እንደወጡ ሳይታወቅና ሳይታዩ ጨለማ ለብሰው ከአውራጃው በመውጣት አዲስ አበባ መሥሪያ ቤታቸው መመለሳቸውን ሰማሁ። መቼም ሠራተኞቹን የላከልኝ መሥሪያ ቤት ሳይፈቅድ ቡለደዘሮችንና ግሬደሮችን የሚጭኑ ሎው ቤድ ተሽከርካሪዎች ተልከው መሣሪያዎችን ጭነው ወታደሮቹ ጨለማ ለብሰው ሊመለሱ እንደማይችሉ ስላወቅሁ ለአውራጃው ልማት ብዙ አስተዋጽኦ ያደረጉ ስለሆነ ሽልማትና የመሸኛ ግብዣ ሳናደርግላቸው በመመለሳቸው እኔ ብቻ ሳልሆን የአውራጃው ሕዝብ ጭምር ያዘነ መሆኑን በመግለጥ ለየግላቸውና ለመሥሪያ ቤቱ የምስጋና ደብዳቤ ጽፌ ላኩ።*

እላይ የተገለጠው የሶዶ ከተማ ማስተር ፕላን በመዘጋጀት ላይ እንዳለ ለከተማው እድገት የሚያስፈልጉ ሌሎችም የልማት ሥራዎች ይካሔዱ ነበር። ለአንድ ከተማ ነዋሪ በተለይ የንጹህ ውሀ እንዲያገኝ ማድረግ ቀደምትነት ሊሰጠው እንደሚገባ ይታወቃል። ስለዚህ በተለይ በበጋ ወራት ይከሰት የነበረውን የሶዶ ከተማ ከባድ የውሀ ችግር ማቃለል ያስፈልግ ነበር። ይህን ሥራ ከመጀመራችን በፊት የከተማው ነዋሪዎች የንጹህ ውሀ አገልግሎት እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ በተለይ በሕጻናቱ ላይ ምን ያህል የጤና መሻሻል እንደሚያስከትል ማወቅ እንዲቻል በአሜሪካ መንግሥት ርዳታ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአማካሪነት ይሠሩ የነበሩትን የጤና ባለሙያዎች ከእነዶክተር ኪንግና ሚስተር ኤልደር ጋር ተነጋግሬ ወደ አውራጃው መጥተው የሶዶ ከተማን ነዋሪ በተለይ የሕጻናቱን ጤና እግዲያጠኑልኝ ጠየቅሁዋቸው። ጥያቄውን በደስታ ተቀብለው በላቦራቶሪ መሣሪያ የሚታገዙ የቴክኒሺያኖች ቡድን ይዘው ወደ ሶዶ ከተማ መጡና የሶዶን ከተማ ነዋሪዎች በተለይ የሕጻናቱን ጤና ሁኔታ አጠኑልን። እንዲሁም በሕንጻ ኮሌጅ ምክትል አስተዳዳሪ በአቶ ናይግዚ ገብረመድህን የሚመራ የመሐንዲሶች ቡድን በከተማው አካባቢ የሚገኙትን ምንጮች ስላጠናልን ለከተማው የቡዋንቡዋ ውሀ ለማስገባት የቀረን የውሀ ቧንቧዎችና የቧንቧውን መስመር የሚዘረጋ ባለሙያ ማግኘት ነበር።

ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር በነበርኩበት ጊዜ ለዕድገት ጣቢያዎች ውሀ ለማስገባት በእርዳታ አግኝተናቸው ከነበሩት የውሀ ቧንቧዎች ውስጥ መጠናቸው ከሚያስፈልጉን በላይ ስለሆኑ ለጊዜው አያስፈልጉም ተብለው የተቀመጡ የውሀ ቧንቧዎች መኖራቸውንና ማስቀመጫ ቦታ ጠፍቶ ተቸግረን እንደነበረ ስለማውቅ ከመሥሪያ ቤቱ ጋር ተነጋግሬ የስጦታ ያህል በሆነ አነስተኛ ዋጋ የውሀ ቧንቧዎቹን ማግኘት ቻልኩ። ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር በተገኙት የውሀ ቧንቧዎች ላይ በነዶክተር ኪንግ አማካይነት በእርዳታ የተገኙት የውሀ ቧንቧዎች ተጨምረው ከአዲስ አበባ ያስመጣሁት ቧንቧ መስመር መዘርጋት ባለሙያ አቶ አባተ በሕግ እስረኞች የጉልበት ሥራ እየታገዘ ለሶዶ ከተማ ነዋሪዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ የንጹህ ውሀ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደረገ። የሶዶ ከተማ ነዋሪዎች የንጹህ ውሀ ማግኘት ከጀመሩ ከጥቂት ወራት በኋላ እነዶክተር ኪንግ የነዋሪውን ሕዝብ ጤና ሁኔታ እንደገና ሲያጠኑ በተለይ የሕጻናቱ ጤና በጣም ተሻሽሎ ስለተገኘ ለከተማ ነዋሪዎች ንጹህ ውሀ ለጤና መሻሻል ጭምር የሚጠቅም መሆኑ ተረጋገጠ።

የሶዶ ከተማ ማስተር ፕላን ከተማውን በመኖሪያ ቤቶች በመስሪያ ቤቶች፣ በኢንዱስትሪና በገበያ ወዘተ ዞኖች ከፋፍሎ በዘመናዊ መልክ የተዘጋጀ ስለሆነ በማስተር ፕላኑ መሠረት በኢንዱስትሪና በገበያ ዞን በዚያን ዘመን ዘመናዊ ናቸው የሚባሉ የገበያ አዳራሾችና የቡና መጋዘኖች ተሠሩ። በተለይ የቡና መጋዘኖቹ ቡናን በንጽህና ለማከማቸት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው ተብሎ በቡና ቦርድ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩት አቶ ለማ ፍሬውና የመሥሪያ ቤቱ

*ሠራተኞች ተጎብኝቶ ምስጋናና አድናቆት አግኝቷል። በማስተር ፕላኑ መሠረት በግልጽ በታ የተቋቋሙት የገበያ ቦታና ሱቆች ቀደም ብሎ ምርቱን ወደ ገበያ ይዞ የሚመጣውን ገበሬ በየጉዋዳቸው እያስገቡ በፈለጉ ዋጋ ይነጥቁት የነበሩትን ነጋዴዎች ጥቅም ስላስቀረው በእነዚያ ነጋዴዎች በኩል ለብዙ ጊዜ ያልተቋረጠ አቤቱታና እስከ ጠቅላይ ሚንስትር ጽሕፈት ቤት የደረሰ እኔን የመወንጀል አቤቱታ አስከትሎ ነበር። የከተማው ማስተር ፕላን መዘጋጀት ያስከተለው ጥቅም ማስተር ፕላኑ አልቆ መንገዶች እንደተከፈቱ የገበያ አዳራሾችና ሱቆች፣ ዘመናዊ ሆቴሎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገለግሎት የሚሰጥበትና የሠራተኞች ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶች ከአነስተኛነቱ በስተቀር ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በሌሎች ከተሞች የማይገኝ ዘመናዊ ቄራ በዚያን ዘመን ከአነስተኛ የገጠር ሆስፒታል የሚወዳደር ትልቅ የጤና ጣቢያ ሕንጻ፣ ባንድ ጊዜ ሦስት መቶ የሚያስተናግድ ከአስራ አምስት ሺህ በላይ ልዩ ልዩ መጻህፍትና ኢንሳይክሎፒዲያዎች ያሉት የተሟላ ቤተ መጻህፍት ወመዘክርና ባህላዊ ሙዚየም፣ ሦስት ሺህ ሰዎች የሚያስተናግድ በፊሊፕስ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አረፈ ዐይኔ አብረሃ መሪነት የተዘጋጀ የድምጽ መቅረጫና ማጉያ፣ ለቲያትርና ፊልም ማሳያ መድረክ «ስቴጅ» ያለው የስብሰባ አዳራሽ፣ በሕንጻ ኮሌጅ የተሠሩ ሞዴል መኖሪያ ቤቶች ወዘተ በየጊዜው እየተሠሩ ያቺ ጠባብ የእግር መንገዶች የሚገኙባት በሰንሰል የተዋጠች ጥንታዊ የሶዶ ከተማ የዘመናዊ ከተማ መልክ እያገኘች ሔደች።*

*እላይ ባጠቃላይ በተገለጠው ሁኔታ የሶዶ ከተማ ልማት ሲካሔድ ግርማዊ ቀደማዊ ኃይለሥላሴ ባለስልጣኖቻቸውን አስከትለው በመጋቢት ወር* 1957 *ዓ.ም ለአንድ ሳምንት አውራጃውን ሲጎበኙ እሳቸውም ሆኑ ያስከተሏቸው ባለስልጣኖች ፊቱን አዙሮብን ስለነበረው የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን ተገርመው ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ወዳጄ ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ወደ ሶዶ ከተማ ተጠርተው የንጉሠ ነገሥቱ ወቀሳና የመኳንንቱ ትችት ደርሶባቸዋል። ሆኖም ከወቀሳውና ትችቱ በኋላም ቢሆን የሶዶ ከተማ የኤሌክትሪክ መብራት ያገኘችው ከአንድ ዓመት በኋላ በ*1958 *አብዛኛውን ጊዜ የማይሠራ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ዲዝል ሞተር ተተክሎላት ስለነበር የቡና መፈልፈያዎች የእንጨትና ብረት ሥራ ድርጅቶችና ወፍጮዎች ያንቀሳቅሱ የነበሩት ባለኢንዱስትሪዎች በየግላቸው በተከሉዋቸው ዲዝል ሞተሮች ነበር። ይህን ሁኔታ የተመለከቱ የውጭ አገር ተወላጆች ሳይቀሩ ታዝበው ሥልጣኑ በእነኝሁ ፊታቸውን ባዞሩብን ሰዎች እጅ ስለሆነ ማሰናከላቸው የማይቀር ቢሆንም ይህን ደባ የተመለከቱት በልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ይረዱኝ የነበሩት የስዊድኑ ሲዳ ሰዎች ተገርመው ለአውራጃው ከተሞች ብቻ ሳይሆን ለመንደሮች ጭምር የሚያገለግል የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ በእርዳታ ለመሥራት የአጀራን ታሪካዊ ፏዋፏቴ ማጥናት ጀምረው ነበር።*

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የአውራጃው ካርታ ተነስቶ አውራጃው በሰባት ወረዳዎች ከተከለለ በኋላ ለከተማ መስፋፋትና ለሕዝብ አማካይ በሆነበት ቦታ የወረዳ ከተሞች ተቆርቁረው፣ መጀመሪያ የሕንጻ ኮሌጅ የከተማ ማስተር ፕላን ጥናት ባለሙያዎች እነሚስተር ፎግሊቪክ በኢትዮጵያውያኖቹ በእነ አቶ ታደሰ ቸኮልና አቶ በለጠ ሀብታሙ እየተረዱ የወረዳ ከተሞች ማስተር ፕላን በጥድፊያ ማጥናትና ማዘጋጀት ጀምረው ሥራቸውን አጠናቀቁ። በተዘጋጀው ማስተር ፕላን መሠረት መንገዶች ተከፍተው የከተሞቹን ልማት ለማካሔድ ተመቻቹ። ሕዝቡ ራሱን በራሱ ለመርዳት ያደርግ የነበረውን የልማት እንቅስቃሴ ጥቅም እየተገነዘበ የመጣበት ጊዜ ስለነበረ ከራሱ አልፎ መንግሥት ሊሠራው የሚገባውንም ጭምር መፈጸም ደረጃ ላይ ደረሰ። ይኸውም በየከተማዎቹ ለሕዝብ የአስተዳደር አገልግሎት መስጫ ምቹ የሆኑ እያንዳንዳቸው አምስት ክፍል ያላቸው የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የፍርድ ቤት ግምጃ ቤት ፖሊስ ጣቢያ ጽህፈት ቤቶች ክሊኒክና ወህኒ ቤት መንግሥት ምንም ሳያወጣ በሕዝቡ እርዳታ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተሠሩ። በየወረዳው የተሠሩት ጽህፈት ቤቶች አሠራርና የክፍሎች ብዛት ምናልባትም እስካሁንም በሌላ አውራጃዎች የሚገኙ የወረዳ ሳይሆን የአውራጃ ጽህፈት ቤቶችም የሚወዳደሩዋቸው አይመስለኝም። የመንግሥት ጽሕፈት ቤቶች በተገለጠው ሁኔታ ሲሠሩ በየወረዳ ከተሞች አንዳንድ ቤተ መጻህፍት የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ቢሮ የተማሪዎች ማረፊያና የአስተማሪዎችና የተማሪዎች መጸዳጃ ክፍሎች ያሉት የተሟላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግማሹን ሕዝቡ ግማሹን የስዊድኑ ሲዳ ባወጡት ገንዘብ ተሠሩ።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ትምህርት ቤቶች እላይ በተነገረው ሁኔታ በየወረዳው ሲሠሩ በሕንጻ ኮሌጅ አርክቴክቶች የተዘጋጁ ለመኖሪያ፣ ለሱቅ፣ ለኢንዱስትሪ ወዘተ የሚያገለግሉ የቤት ፕላኖች በነጻ እየታደሉና አሠራራቸው ቁጥጥር እየተደረገ በየከተሞቹ ግለሰቦች የቤቶች ሥራ እያጣደፉ ስለሔዱ በተለይ የአረካ፣ የሁምቦና የቦዲቲ ከተሞች ባጭር ጊዜ ውስጥ አድገው ደረጁ። ለቦዲቲ ከተማ በሕንጻ ኮሌጅ እርዳታ ውሀ የገባለት ሲሆን ለቀሩት የወረዳ ከተሞች ሕዝቡ ለልማት ባወጣው ገንዘብ በቂ የውሃ ቡዋንቧዎች ተገዝተው ሁለት ከተሞች ሲቀሩ የቀሩት ከተሞች የቧንቧ ውሀ ገባላቸው። ለቀሩትም ሁለት ከተሞች የቧንቧ ውሀ እንዲገባላቸው ዝግጅት ሲደረግ ወደ ወለጋ ስለተዘዋወርኩ የውሀ ቧንቧዎቹ አውራጃው ግምጃ ቤት ተከማችተው ስለነበረ እነዚያም ሁለቱ ከተሞች የቧንቧዋ ውሀ ሳይገባላቸው እንዳልቀረ አምናለሁ።

### የእርሻ ልማትና የሕዝብ ሰፈራ እንቅስቃሴ፦

በዚያን ወደ ወላይታ አውራጃ በተዛዝኩበት ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመቶ ዘጠና አምስቱ ያህል ኑሮውን የመሠረተው በእርሻ ላይ ስለነበረ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ለእርሻ ሥራ ትኩረት መስጠት ያስፈልግ ነበር። ስለዚህ የእርሻን ሥራ በጥናት ላይ በተመሠረተ ዕቅድ ማካሔድ አስፈላጊ ስለሆነ

መጀመሪያ የአውራጃው የእርሻ መሬት አፈር ለምነት ሁኔታ መጠናት ስለሚገባው የዓለም ማያ የእርሻ ኮሌጅ እንዲያጠናልኝ ጠይቄ ከሰባቱም ወረዳዎች የእርሻ መሬት የአፈር ናሙናዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደምንችል መመሪያ ሰጥተውን ናሙናዎቹን ሰብስበን ስለላክንላቸው መርምረው ውጤቱን ላኩልን፡፡

በየቀበሌው ያሉት የአውራጃው የእርሻ መሬት ለምነት ሁኔታ ከታወቁ በኋላ እንዳሁኑ በደፈናው ለገበሬው ማዳበሪያ እየሸጡ በማንኛውም የአፈር ዓይነት ማንኛውንም የማዳበሪያ ዓይነት በመጠቀም መሬቱንና ገበሬውን ማደህየት ሳይሆን ማዳበሪያ የሚያስፈልገውንና የማያስፈልገውን ብቻ ሳይሆን የትኛውም ክፍል አፈር ምን ዓይነት ማዳበሪያ እንደሚያስፈልገው ታወቀ፡፡ ከግብርና ሚኒስቴር በመነጋገር ስለማዳበሪያ አጠቃቀምና የተሻሻለ የአስተራረስ ዘዴ የሚያስተምሩ በአምቦና በጂማ እርሻ ኮሌጆች የሰለጠኑ የእርሻ ባለሙያዎች በተለይ የተገኙትን ያህል የወላይታ ተወላጆች እነ ንጋቶ በደቾ፣ ደሳለኝ ታንጋንና የሌሎች ክፍል ተወላጆች ለሰባቱም ወረዳዎች እንዲመደቡልኝ አደረግኩ፡፡ በዚያን ጊዜ የእርሻ ሚኒስቴር ከውጪ ማዳበሪያ እያስመጣ ገበሬው በማዳበሪያ መጠቀም እንዲለምድ በራሱ ትራንስፖርት እቦታው ድረስ በመውሰድ ለገበሬው በነጻ ያድል ስለነበረ ማዳበሪያ እንዲላክልኝ ጠይቄ የተላከልኝን ማዳበሪያ የተመደቡልኝ የእርሻ ባለሙያዎች በዓለም ማያ የእርሻ ኮሌጅ ጥናት መሠረት የትኛው የማዳበሪያ ዓይነት ለየትኛው የአፈር ዓይነት እንደሚውል እየተለየ በማዳበሪያ መጠቀምና በተሻሻለ አስተራረስ ዘዴ የእርሻ ባለሙያዎቹ ገበሬው የተሻለ ምርት ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ ያስተምሩት ጀመር፡፡

በተሻሻለ የእህል ዘር መጠቀም በዚያን ጊዜ ገና ያልተጀመረና ከግብርና ሚኒስቴር የተሻሻለ የእህል ዘር ማግኘት ስለማይቻል በአዲስ አበባ ከተማ ከአራዳ ፖስታ ቤት አካባቢ የሚገኘው አትክልት ተራ ኢጣሊያዊ የአትክልት የአደንጉዋሬና የቦቆሎ ምርጥ ዘሮች ከውጪ አገርና ከአስመራ እያስመጣ ይሸጥ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ኪሎ የአገር ውስጥ ቦቆሎ በአሥር ሳንቲም ይሸጥ የነበረውን ጣሊያኑ ከውጪ ያስመጣውን ምርጥ የበቆሎ ዘር አንዱን ኪሎ በአንድ ብር ይሸጥ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙም ሰው ስለ ምርጥ ዘር ስለማይገነዘብ ከኢጣሊያው ብዙም የሚገዛው ደንበኛ ባይኖረውም እኛ በየአመቱ ከአንድ መቶ እስከ ሁለት መቶ ኪሎ ግራም የምንገዛው ደንበኞቹ ስለነበርን ባየን ቁጥር ፊቱ እየፈካ ከውጪ ስለሚያስመጣው የበቆሎ ዘር ምርጥነት እስኪሰለች ያወጋን ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ አንዱ ኪሎ በቆሎ በአንድ ብር ይሸጥ ከነበረው ከኢጣሊያኑ ይልቅ የተጠቀሙት ዘሩን ገዝተን የምናድላቸው የወላይታ ገበሬዎች ነበሩ፡፡ በወረዳ አስተዳዳሪዎች አማካይነት ምርጡን የበቆሎ ዘር ለጎበዝ ገበሬዎች ፍሬዎቹ በቁጥር የተሰጧቸው እሸቱን ሳይበሉ አድርቀው ለዘር እንዲያቆዩዋቸው መመሪያ በመስጠት በሦስት ዓመት ውስጥ ምርጡ የበቆሎ ዘር አውራጃውን አዳርሶት ከፍ ያለ ጥቅም ሊሰጥ ችሏል፡፡ በአውራጃው

የሚገኘው የማሽላ ዘር ምርቱ በጣም አነስተኛ ስለሆነ ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ከጨርጨር አውራጃ ምርታቸው በጣም ከፍ ያለ የሙገር የፈንዲሻና ሌሎች የማሽላ ዘሮች አስመጥቼ እንደ ምርጥ የበቆሎው ዘር ለጎበዝ ገበሬዎች ተከፋፍለው ተዘሩ። ሆኖም የሐረር ጠቅላይ ግዛት የማሽላ ዘሮች ጮርቃ ከሚሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ሌሊት እየተነሱ ወፍ ካልተከላከሉላቸው በስተቀር በወፎች ስለሚበሉ ምርት ማግኘት አይቻልም። የወላይታ ገበሬ ሌሊት ተነስቶ ወፍ የመጠበቅ የእርሻ ባህል ስለሌለው ለማስተዋወቅ ሞክሬ የነበረው ከፍ ያለ ምርት ሊያስገኙ ይችሉ የነበሩት የጨርጨር ማሽላ ዘሮች በወፍ ስለተበሉ ጥረቱ ሳይሳካ ቀረ።

ገበሬው የኑሮ ደረጃውን እንዲያሻሽል ከተፈለገ ማተኮር የሚያስፈልገው የምግብ ሰብሎችን በማምረት ላይ ብቻ ሳይሆን ተሽጠው ከምግብ ሰብል የተሻለ ዋጋ የሚያስገኙ ለፋብሪካ ምርት አገልግሎት የሚውሉ ሰብሎችን ማምረት ላይ ጭምር ሲሰማራ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ትንባሆ ሞኖፖል ለሚያመርታቸው ሲጋራዎች ከውጪ የሚያስመጣቸውን ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን የትንባሆ ቅጠሎች ከአዋሳ ከተማ ዳር ደቡብ ምስራቅ ላይ ማምረት ጀምሮ ነበር። ይህንኑ ተመልክተን የትንባሆ ሞኖፖል በሚፈልገው ዓይነት ገበሬዎች የትንባሆ ቅጠል ማምረት እንዲችሉ የሚያሰለጥኑ ባለሙያዎች መሥሪያ ቤቱ እንዲልክልን የድርጅቱን ዋናሥራ አስኪያጅ የትምህርት ቤት ወዳጄን ሚቹን አቶ በቀለ ትንሳኤን ጠይቀን አንድ ዩጎዝላቪያዊ የትንባሆ ተክል ባለሙያ ወደ አውራጃው ልኮ ጥናት አደረገ። አውራጃው ለትንባሆ ቅጠል ምርት አመች መሆኑን ባለሙያው ስላረጋገጠ ገበሬዎችን የሚያሰለጥኑ ባለሙያዎችና የትንባሆውን ዘር ላከልን። የትንባሆ ቅጠል ምርት ከፍ ያለ ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ ገበሬው ለትንባሆ ምርቱ ብቻ ሳይሆን ለጥራቱም ሽልማት የሚያገኝበት ስለሆነ ጥራት ያለው ከፍ ያለ የትንባሆ ቅጠል ለማምረት እየተወዳደረ ገበሬውም ሆነ የትንባሆ ሞኖፖል ሊጠቀም ቻለ። በዚህ ሁኔታ ይመረት የነበረው የትንባሆ ቅጠል ምርት ከፍ ያለ ስለነበረ ትንባሆ ሞኖፖል ምርቱን የሚያከማችባቸው መጋዘኖች እንዲሰራ መሬት ሰጥተነው በቦዲቲና በሶዶ ከተማዎች ዳር ላይ ያሰራቸው የትንባሆ ቅጠል ማከማቻ ትላልቅ መጋዘኖች የትንባሆ ቅጠል ተከማችቶባቸው ይሁን ወይም ባዷቸውን እስካሁን እንዳሉ አውቃለሁ።

በአውራጃው ትንባሆ ሞኖፖል ያካሒድ የነበረው የትንባሆ ቅጠል ማምረት ልማት ለገበሬዎች የትንባሆ ዘር እያደለ ገበሬዎች የሚያመርቱትን የትንባሆ ቅጠል መግዛት ብቻ አለነበረም። ወደፊት በሚገለጡት በኢንቬስተሮች በሚካሔዱት ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች በሚገኙበት በብላቴን ወንዝ ሸለቆ የትንባሆ ሞኖፖልም አሥር ጋሻ መሬት ተረክቦ ራሱ ዘመናዊ የትንባሆ እርሻ ልማት በማካሔድ ከውጪ ያስመጣው የነበረውን ቨርጂኒያ የሚባለውን የትንባሆ ቅጠል ያመርት ነበር። ቅጠሉን ማምረት ብቻ ሳይሆን የትንባሆውን ቅጠል የሚያደርቅና ለሲጋራ የሚያዘጋጅ ፋብሪካን በብዙ ሚሊዮን ብር እዚያ በብላቴን ወንዝ ሸለቆ እርሻው ላይ አቋቋሙ። ከውጪ ያመጣ የነበረውን

የትንባሆ ቅጠል ባገር ውስጥ ያመርት ስለነበረ ለአውራጃው ሕዝብ ተጨማሪ የሥራ እድል ማስገኘቱ ብቻ ሳይሆን በአውራጃው ይካሔድ የነበረ የእርሻ ልማት ለአገር እድገትም አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችል አድርጎታል፡፡

በዚያን ጊዜ የነበረውን ገቢ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች እንደለውዝ (ኦቾሎኒ) ሰብሎችንም በተለይ የአበላ ሰፋሪዎች እያመረቱ ለገበያ ያቀርቡ ነበር፡፡ እንዲሁም እርሻ ሚኒስቴር ከእስራኤል ያመጣ ከነበረው ምርጥ የጥጥ ዘር ለሰፋሪዎቹ በማደል ሰፋሪዎቹ ጥጥ እያመረቱና በኅብረት እያከማቹ ለአዲስ አበባ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፣ ከበርበሬ የሚሠራ የሚታሸጉ ምግቦችን ማቅለሚያ በፋብሪካ ያመርት ለነበረው ካላማዙ ስፓይስ ኩባንያ የበርበሬ ምርት በማቅረብ ሰፋሪዎች ያገኙት የነበረው ገቢ ከእለት ጉርሳቸውና የዓመት ልብሳቸው አልፎ ባንክ ገንዘብ ማስቀመጥ ደረጃ አድርሷቸዋል፡፡

በአውራጃው ሰላጣ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ቀይ ሥርና የመሳሰሉት የቅጠላ ቅጠል ተክሎች በፍጹም የማይታወቁ ነበር፡፡ አሚራን ከሚባለው የእስራኤል ኩባንያና ያ ምርጥ የበቆሎ ዘር ይሸጥልን ከነበረው የኢጣልያ ተወላጅ የምግብ ቅጠላ ቅጠልና ሥራ ስር ተክሎች ዘር እየገዛን ለጎበዝ ገበሬዎች በማደል እላይ እንደ ተገለጡት ገንዘብ ሰብሎች (የካሽ ሰብሎች) ከፍ ያለ ዋጋ አያግኙበት እንጂ ተክሎችን ለአውራጃው ሕዝብ ለማስተዋወቅና ለገበያም እየቀረቡ መጠነኛ ገቢ አስገኝተውበታል፡፡

በግለሰብ ገበሬዎች ደረጃ በአውራጃው ስለ እርሻ ልማት እንዲንቀሳቀሱ ይደረግ የነበረው እስካሁን በአጠቃላይ የተገለጠው ሌሎችም ሲሆን በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች የሚካሔዱ በአምስት፣ በአሥር፣ በሀምሳና በመቶ ጋሻ መሬት ላይ ስድስት ዘመናዊ የእርሻ ልማት ሥራዎች ተቋቁመው ይካሔዱ ነበር፡፡ እነዚህ ዘመናዊ እርሻዎች የሚገኙት በብላቴን ሸለቆ ከአበላ የሕዝብ ማስፈር ቀበሌ ተነስቶ በአባያ ሀይቅና ወባማ የብላቴን ሸለቆ አቋርጦ በዳሞት ወይዴ ወረዳ በኩል ሶዶ ከተማ የሚገጥመው በጋ ከክረምት በሚያገለግለው መንገድ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች ሊቋቋሙ የቻሉት ቀደም ብሎ እንደጠቀስኩት የአውራጃው ሕዝብ ባወጣው የልማት ገንዘበ በተገዙ የመንገድ ሥራ መሣሪያዎች በጋ ከክረምት የሚያገለግል መንገድና ብላቴን ወንዝ ላይ በሠራነው የብረት ድልድይ ምክንያት እንደልባቸው በጋ ከክረምት ወደ እርሻ ቦታቸው መግባትና መውጣት በመቻላቸው ላይ ነው፡፡ እነዚህ ዘመናዊ እርሻዎች ለአውራጃው ሕዝብ ሰፊ የሥራ እድል ማስገኘት ብቻ ሳይሆን ለውጪ ገበያ ያቀርቡት በነበረው የእርሻ ምርት በአገር ደረጃ ከፍ ያለ ጥቅም ያስገኙ ስለነበረ ሕዝቡ ለራሱ አውራጃ ብቻ ሳይሆን ለአገር ዕድገት ጭምር አስተዋጽኦ ማድረጉን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

በወላይታ አውራጃ በቦሎሶ ወረዳ ዋና ከተማ አረካ ድንበር ላይ በሚገኘው ዱቦ የካቶሊክ ሚሲዮን ኃላፊ አባ ሄንሪ ተፀንሶ በሶዶ ዙሪያ ተወልዶ ሥራውን የጀመረውና ቀስ በቀስ ሰባቱንም የወላይታ ወረዳዎች ካደረሰ በኋላ በአሁኑ ጊዜ

በአዲስ አበባ ከተማ በቅሎ ሰፈር ራስ በሠራው ቤቶች ውስጥ ሆኖ ሁለገብ የልማት ሥራዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያካሒደው ትልቁና የመጀመሪያው አገር በቀል የእርዳታ ድርጅት «አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ» መጀመሪያ የተመሠረተው በወላይታ ነው፡፡ የዚህን አገር በቀል የእርዳታ ድርጅት አስደናቂ አጀማመር ለመግለጥ መጽሐፍ ስለሚያስፈልግ ለወደፊቱ ትቼ ባጭሩ ይህ አገር በቀል ድርጅት ሲፀነስ ከሌሎች የልማት ሥራዎች በተለይ በእርሻ ልማት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ያደርግ ስለነበረ ለአውራጃው የእርሻ ልማት አስተዋጽኦ አድርገዋል በማለት አልፈዋል፡፡

የወላይታ አውራጃ ሕዝብ ራሱን በራሱ በመርዳት ያደርግ የነበረው የእርሻ ልማት እንቅስቃሴ ዝና ከአገር አልፎ በውጪ አገሮች ጭምር ስለተሰማና ትኩረት ስለሳበ ይኸንኑ እቦታው ላይ ተገኝቶ ለማየት ወደ አውራጃው ይመጡ ከነበሩት ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች መካከል አንዱ የዓለም ባንክ ፕሬዚዴንት የነበሩት ሚስተር ሮበርት ማክነማራ ረዳቶቻቸውን አስከትለው በተለይ አበላ የሕዝብ ሰፈራ ቀበሌን ጐብኝተዋል፡፡ በአውራጃው ይካሔዱ የነበሩ የእርሻ ልማትና የሕዝብ ማስፈር ሥራ በመንግሥት ቢታገዝ የኢትዮጵያን ገበሬ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነት ማላቀቅ ይቻላል የሚል እምነት ስላደረባቸው ይኸንኑ ለኢትዮጵያ መንግሥት ገልጸው ይህን ተግባር ለሚፈጽም ድርጅት ማቋዋቋዋሚያ ከዓለም ባንክ በረጅም ጊዜ የሚከፈል ብድር በመፍቀድ «የወላይታ አውራጃ የእርሻ ልማት ድርጅት (በእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃሉ፣ ዋዱ- Welayta Agricultural Development Unit, WADU-) ተቋቁሞ ነበር፡፡ አንድን ዓላማ ግብ ለማድረስ ድርጅት ማቋቋም የሚያስፈልግ ቢሆንም ዓላማው ግቡን እንዲመታ ለማድረግ የሚያስፈልገው አማራጭ የማይገኝለት ዋናው የግል ጥቅማቸውን እርግፍ አርገው ትተው ለአገራቸውና ለወገናቸው ጊዜያቸውን ኃይላቸውን ችሎታቸውንና ካስፈለገ ገንዘባቸውን መስዋዕት የሚያደርጉ ድርጅቱን የሚመሩ ሲኖሩ ብቻ ስለሆነ ሳይሆን ቀረና እንደታሰበው ዓላማው እንኳን ለሌሎች የኢትዮጵያ ገበሬዎች ዕድገት ውሎ ጥቅም መስጠት ይቅርና ለዚያው የወላይታ አውራጃ ሕዝብ ጥቅም ሳይሰጥ ፈርሶ ከዓለም ባንክ የተገኘው ብድር የኢትዮጵያ ሕዝብ እዳ ሆኖ ቀርቷል፡፡

### *የሕዝብ ሰፈራ እንቅስቃሴ፡-*

በወላይታ አውራጃ ይካሔድ የነበረው የሕዝብ ማስፈር ሥራ ቀደም ብሎ አጋጣሚ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ የጻፍኩት ቢሆንም የራሱ ርዕስ ኖሮት ቢገለጽ የሚጠቅም ሆኖ ስላገኘሁት በራሱ ርዕስ ሥር ጥቂት ለየት ያለ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡-

ሁለት ወፎች ባንድ ድንጋይ እንደሚባለው ሁሉ አንደኛ ጭሰኞች የራሳቸው መሬት ኖሯቸው ከጭሰኝነት እንዲላቀቁ፣ ሁለተኛ ሁሉም ገበሬ የራሱ የእርሻ መሬት ኖሮት የእርሻ ልማት በማካሔድ እንደሚነገርላት ኢትዮጵያን የእህል

ጎተራ (የዳቦ ቅርጫት) ማድረግ የሚለው ምኞት በየጊዜው ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላይ ግዛቶችን ሲጎበኙ ቅስቀሳ ቢያደርጉና በኋላም ጭሰኞች ግማሽ ጋሻ መሬት በርስትነት እየተሰጣቸው የእርሻ ልማት እንዲያካሒዱ የ1945 ዓ.ም. ቢታወጅም አሁንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች እንደታሰበው ጭሰኞች የራሳቸው ርስት እንዲያገኙ የማድረጉና የእርሻ ልማቱም እንደተፈለገው ሊሳካ አልቻለም፡፡ ኢትዮጵያውያንን ከጭሰኝነት የማላቀቅና የእርሻ ልማት በማካሔድ ኢትዮጵያን የእህል ጎተራ ማድረግ የሚለው የተቀደሰ ዓላማ የሚተው ስላልሆነ ይህን ዓላማ እውን ለማድረግ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ጭሰኞችን በኅብረት እያሰፈረ የእርሻ ልማት ለማካሔድ ዕቅድ ነድፎ ሥራ ጀምሮ ነበር፡፡ ሚኒስቴሩ በብዙ የዩጎዝላቭ ኤክስፐርቶች እየታገዘ ሥራ እንደጀመረ በታህሳሱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ሥራውን የሚመሩት ሚኒስቴር ተገደሉና ሌላ ሥራውን የማይደግፉ ሚኒስትር ተሾሙ፡፡ ከእኝህ የተጀመረው ዓላማ ከሚቃወሙና ሥራውን ካዳከሙት ባለስልጣንና አጋሮቻቸው ጋር ተጋጭቼ ወደ ወላይታ አውራጃ ስሔድ በሕዝብ ማስፈር ዓላማ አጥብቄ አምን ስለነበረ ወደ አውራጃው እንደሔድኩ መጀመሪያ ሥራዬ ካደረኳቸው ውስጥ አንዱ የሕዝብ ማስፈር ሥራ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው የሕዝብ ሰፈራን ዕቅድ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ስለሚያስፈልጉት የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ዝግጅት መናገር ጊዜና ቦታ ስለሚጠይቁ እነዚህን ትቼ በወላይታ አውራጃ በ«አበላ» እና በ«በኦሞ ሽለቆ በሌ» በሁለቱ ቀበሌዎች ስለተካሔዱት የሕዝብ ሰፈራዎች ዓላማዎችና ውጤታቸው ባጭሩ እነግራችኋለሁ፡፡

በአበላ ቀበሌ የተካሔደው የሕዝብ ሰፈራ ዓላማ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ታቅዶ የነበረው በጣም ያስጎመጅ የነበረው ጭሰኞች በኅብረት ሰፍረው በኅብረት አርሰው ከፍ ያለ ምርት እንዲያገኙና ለቀለብ ከሚያውሉት የተረፈውን በጋራ እየሸጡም ለሌሎች ለኑሮ አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች እያዋሉ እንዲጠቀሙ አገሪቱም ከፍ ያለ የእህል ክምችት እንዲኖራት ለማድረግ የሚለውን ዓላማ እሥራ ላይ ለማዋል ነው፡፡ ሌላው የእኔ ዓላማ ለአገር ዕድገት ጠንቅ የሆነውን የመለያየትን ስሜት አጥፍቶ አንድ ዓላማ ያለው ኅብረተሰብ መፍጠር እንዲቻል ልዩ ልዩ ጎሳዎች ባንድ ለይ ሰፍረው የመጠላላትና የመናናቅ መንፈስ አስወግደው አንዱ ከሌላው እየተማረና እየተዋወቀ እየተጋባ ወዘተ አገሩን የሚያሳድግ ጠንካራ አንድ ኢትዮጵያዊ ባህል መፍጠር የሚል ነው፡፡ የዚህን ዓላማ እውነትነት ለማወቅ ከኤርትራ፣ ከትግራይ፣ ከወሎ ዋግና ላስታ፣ ከሰሜን ሸዋ ልዩ ልዩ ቦታዎች፣ ከጉጂ (ኦሮሞ) ያሰባሰብኳዋቸውን ጭሰኞች ከወላይታዎች ጋር እያሰባጠርኩ ነበር ያስፈርኳቸው፡፡ በአበላ የተካሔደው ሰፈራ በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የታቀደው ጭሰኞች በጋራ መሬት ተሰጥቷቸውና ሰፍረው በጋራ አርሰው፣ በጋራ አምርተው ማከማቸትና በጋራ መጠቀም የሚለው ኮሚኒስታዊ ዕቅድ በሰፋሪዎቹ ፍጹም የተጠላና የማይሠራ መሆኑን የተገነዘብኩ ሲሆን ልዩ ልዩ ጎሳዎች አሰባጥሮ በማስፈር ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ባህል መፍጠር የሚለው ዓላማ ግን እውነትነት ያለው

መሆኑን ፍንጭ አገኘሁ። ሁለተኛው በኦሞ ሸለቆ በበሌ ቀበሌ የተካሔደው የሕዝብ ሰፈራ ሁለት ዓላማዎች ያለው ነበር። አንደኛው ዓላማ አንድ ጎሳ ከሌሎች ጎሳዎች ሳይቀላቀል ቢኖር የመሻሻሉ ሒደት ቢማርም እንኳዋ ዘገምተኛ ይሆናል ወይም ባለበት ይዳክራል የሚለውን ሃሳብ ለማወቅ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ በአንድ አካባቢ በባለርስቶች መሬት ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ጭሰኞች በሙሉ አስነስቶ በሌላ ቦታ ከመንግሥት መሬት በርስትነት እየሰጡ ቢያሰፍሯቸው ጭሰኞቻቸው ለቀው የሔዱባቸው ባለርስቶች ራሳቸው ማረስ ከሚችሉት ውጪ ያለውን መሬት ገዢ ካገኙ በመሸጥ ገዢ ካላገኙ ለመንግሥት በግብረ ጠልነት ይለቁታል። ስለዚህ መንግሥት ጭሰኞችን ከአንድ አካባቢ በሙሉ ከባለርስቶች መሬት ላይ እያስነሳ ራሱ ከሚያዝበት ርስት እየሰጡ ቢያሰፍሯቸው ቀስ በቀስ ኮሽ ሳይል በሰላማዊ መንገድ መንግሥት የሚታማበትን የጭሰኞች ችግር ሊፈታው ይችላል የሚሉትን ሁለት ሃሳቦቼን እውነትነት ላረጋግጥ ችያለሁ።

ባጭሩ ለማጠቃለል የጋራ መሬትን በጋራ አርሶ በጋራ አምርቶ መጠቀም የሚለው በአበላ የተጀመረው የሕዝብ ሰፈራ ሀሳብ ማስገደድ ቢጨመርበትም ሰፋሪው እንዲበተን ያደረገው ሲሆን እየተሰባጠሩ የሰፈሩት ልዩ ልዩ ጎሳዎች ከፍ ያለ መሻሻል ማሳየት ብቻ ሳይሆን ደርግ የግል ንብረትን ሲሰርዝ ባይበተኑ ኖሮ የባህል ውኅደትም እየታየ ሔዶ ነበር። በአንድ አካባቢ ከባለርስቶች ርስት ላይ ተነስተው በኦሞ ሸለቆ በበሌ ቀበሌ የሰፈሩ የወላይታ ተወላጆች የሰፈራው መሬትና የሕዝቡ ስርጭት ከአበላ የተሻለ ቢሆንም ምንም መሻሻል ሳያሳዩ የኖሩ ሲሆን ከርስታቸው ላይ ጭሰኞቹ በሙሉ የተነሱባቸው ባለርስቶች እነ ባላንባራስ ከፎ አለንጎ ብዙም ሳይቆዩና ሳያንገራግሩ እቢሮዬ ድረስ መጥተው በማነጋገር ከነበራቸው መሬት ውስጥ በስጦታ ለመንግሥት ለቀናል በማለት በማስረከባቸው አንድ ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ሳይደባለቅ ተለይቶ የሚኖር ጎሳ እድገቱ ዘገምተኛ ወይም መሻሻል አያሳይም የሚለውና በሰላማዊ መንገድ የጭሰኞችን ችግር መፍታት ይቻላል የሚለውን ሁለቱንም ሃሳቦቼን ለማረጋገጥ ችያለሁ።

በወላይታ አውራጃ በአባያ ሐይቅ አካባቢ በአበላና በኦሞ ሸለቆ በበሌ ሁለት ቀበሌዎች የተካሔዱት የጭሰኞች ሰፈራ ጭሰኞች የራሳቸው መሬት እያገኙ እንዲሰፍሩ ለማድረግ ቢሆንም በተጨማሪ እላይ ባጭሩና በአጠቃላይ የተነገሩትን በመጽሐፍ ደረጃ መገለጥ የሚገባቸውን ሃሳቦች ለማረጋገጥ ጭምር ነበር።

### *የትምህርት ማስፋፋት እንቅስቃሴ፦*

በአውራጃው ይካሔድ የነበረው የትምህርት እንቅስቃሴ ፈጣንና የሚያረካ ነበር ማለት ይቻላል። ቀደም ብሎ በወላይታ አውራጃ ይገኙ የነበሩት ትምህርት ቤቶች እንደቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። አጋጣሚ

ሆኖ ባገኘሁት ቦታ ሁሉ የጠቀስኩት በሶዶ ከተማ የሚገኘው በአዲስ አበባው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ቅርጽ በጥርብ ድንጋይ የታነጸው የሊጋባ በየነ አባ ሰብስብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ሌሎች ከመኖር የማይቆጠሩ በአጣናና በሣር ክዳን ተወነጋግረው የተሠሩ በደሳሳ ጎጆ ውስጥ የሚገኙ አራት በአጠቃላይ አምስት የመንግሥት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአውራጃው ውስጥ ይገኙ ነበር። በተጨማሪ በሶዶ ከተማ ምስራቅ ላይ የሚገኘው የሱዳን ኢንቴሪየር ሚሲዮን የወንጌልን ትርጉም ሳያውቁ ሐይማኖት እንዲያስፋፉ እንዲሁም ሕዝብን በህክምና እያጉዋጉ ለመሳብ ወንጌልና የተበከሉ መድሃኒት መስጫ መርፌዎች ጎን ለጎን አስቀምጠው በሽተኛው ሲመጣ በትውልድ ቁንቁዋው ወንጌል ከተነበበለት በኋላ በዚያ በተበከለ መድሃኒት መስጫ መርፌ ጭኑን የሚያቆስሉት የዶክተር ስም የሚሰጣቸው ማንበብ እንዲችሉ የሚማሩበት በስም አራተኛ ክፍል ድረስ የሚያስተምር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ በዱቦ ቀበሌ የካቶሊክ ሚሲዮን ወንጌል ሳይሆን ሳይንስ ጭምር እስከ አምስተኛ ክፍል የሚያስተምር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባጠቃላይ ሁለት አንደኛ ደረጃ ሚሲዮናዊ ትምህርት ቤቶች ይገኙ ነበር።

ሕዝቡ በቀሩት የልማት ሥራዎች ላይ ያደርግ እንደነበረው ብርቱ እንቅስቃሴ ሁሉ በትምህርት መስፋፋትም ላይ ብርቱ እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረውን መንግሥትም ሆነ ሌሎች እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ተገንዝበውለት ርዳታ ስላረጉ እስከ 1962 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አንድ ከፍተኛ አጠቃላይ (ኮንምፕርሄንሲቭ) ሁለተኛ ደረጃ ሦስት መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዘጠኝ አንደኛ ደረጃ በድምሩ አሥራ ሦስት የመንግሥት አንድ መለስተኛና ሁለተኛ ደረጃና ሃያ ሦስት አንደኛ ደረጃ በድምሩ ሃያ አራት የኢ.ኦ.ቤተ ክርስቲያንና አምስት አንደኛ ደረጃ የሚሲዮን በአጠቃላይ በአውራጃው የሚገኙት ትምህርት ቤቶች ከሰባት ወደ አርባ ሦስት ትምህርት ቤቶች ከፍ ብለው ነበር። በአውራጃው የትምህርት ቤቶች መስፋፋት በተለይ የሶዶ ከተማ ከጋሞ ጎፍና ከሲዳሞ ጠቅላይ ግዛቶች እንዲሁም ከከንባታና ሃዲያ አውራጃ የሚመጡ ተማሪዎች ማዕከል ሆና ታገለግል ስለነበረ በወላይታ አውራጃ የተደረገው የትምህርት መስፋፋት የተጠቀሙት ወላይታዎች ብቻ ሳይሆኑ የተጠቀሡት ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃ ጭምር ነበሩ።

### *የጤና አገልግሎት እንቅስቃሴና መስፋፋት፡-*

ወደ ወላይታ አውራጃ ስሔድ ያየሁት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አለኝ ከሚል የለኝም ማለቱ ይሻለው የነበረ ክሊኒክ ያሳፍራል። ወደ አውራጃው እንደሔድኩ ከጎበኘኋቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ይኸው በሶዶ ከተማ ለስሙ ክሊኒክ ተብሎ ይጠራ የነበረውን የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው። ክሊኒኩ የተቋቋመው ለህመምተኞች የህክምና አገልግሎት መስጫ አንድ የፊት ለፊትና ሁለተኛው የድሬሰር ነኝ ባዩ መኝታ ጉዋዳ ያለው የግርግዳው ጭቃ ምርግ ረጋግፎ በጭላንጭሎቹ ውጭውን

ማየት የሚያስችል የአሥር ብር ኪራይ ቤት ውስጥ ነው፡፡ በመጠጥ ይሁን በማድያት ፊቱ የበለጠ የመነጀከና እጅጌው የነተበ ጋውን የለበሰ ድሬሰር በድንገት ወደ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ የሚያይ ሰው ድሬሰሩ ታሞ ለእርዳታ የመጣ ሕመምተኛ እንጂ ህመምተኞችን የሚረዳው ድሬሰር ነው ብሎ ለመናገር ይጠራጠራል፡፡

ባንድ በኩል የሚገኘውን የቤቱን ግርግዳ ተደግፎ የሚገኘው ከሳጥን እንጨት ተወናግሮ የተሠራ የመድሃኒት መደርደሪያ ላይ አንድ ሁለት የወረቀት ፓኮዎች እጥቅም ላይ የዋሉ መድሃኒት መስጫዎች፣ ባዶ ብልቃጦች፣ አቧራ የቃሙ ጥጥና ፋሻ ጨርቅ፣ ጎዶሎ ጠርሙስ፣ አልክሆል፣ ሌሎችም ካሉ የማይቆጠሩ ቁሳቁሶች መደርደሪያው ላይ ተበታትነው እንደተቀመጡ ሲታዩ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሶዶ ከተማ አንድ ክሊኒክ አቋቁሜያለሁ ለማለት ያህል እንጂ ከተቋቋመ ጀምሮ ዘወር ብሎ እንዳላየው የቤቱ፣ የድሬሰሩና ያ ከሳጥን እንጨት ተወናግሮ የተሠራው መደርደሪያ ቁልጭ አድርገው ይመሰክራሉ፡፡ ድሬሰሩም ሲጠየቅ የገለጠው ይሄንኑ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ደሞዙና አሥር የቤት ኪራይ ሦስትና አራት ወር እየዘገየ የሚላክለትና ለዓመት የሚመደቡለትን በጣም አነስተኛ የህክምና መስጫ መድሃኒቶች ወደ አዲስ አበባ ሔዶ በደጅ ጥናት የሚያገኝ መሆኑን ለማስመሰል ይሁን እውነቱን በምሬት የጤና ባለስልጣኖችን ፍርድ አቅርቦ በገንዘብ ሳይሆን በጅራፍ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይኸንኑ በቀልድ መልክ ለሚቼ ለወዳጄ ለአቶ ዮሐንስ ጽጌ ስነግረው እንደማኩረፍ ብሎኝ ብዙ ነገሮች ሊበላሹብኝ ነበር፡፡

መጀመሪያ ወደ ወላይታ አውራጃ ስሔድ ሕዝቡ በመንግሥት በኩል ያገኝ የነበረው የጤና አገልግሎት እላይ እንደተጠቀሰው ሲሆን፣ ከ1955 ዓ.ም. ጀምሮ ሕዝቡ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ባደረገው የልማት እንቅስቃሴና መንግሥት ባደረገው እርዳታ እስከ 1962 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አንድ ትልቅ ከገጠር ሆስፒታል የማያንስ ከፍተኛ የጤና ጣቢያ፣ ሰባት የተሟሉ ክሊኒኮች ተቋቁመው ሕዝቡ የተሟላም ባይሆን ከቀድሞው በጣም የተሻለ የጤና አገልግሎት ማግኘት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ በተጨማሪ በሶዶ ሱዳን ኢንቴሪየር ሚሲዮን ሆስፒታል ላይ በተደረገው ጫናና ሆስፒታሉ ከውጪ እርዳታ እንዲያገኝ ለእርዳታ ሰጪ በተጻፈለት የድጋፍ ደብዳቤ ከውጪ ባገኘው እርዳታና በራሱም ጥረት በተሠሩት ተጨማሪ የህሙማን መኝታና የህክምና መስጫ ክፍሎች ተስፋፍቶ ከወንጌል ትምህርት ይልቅ በህክምና አገልግሎት ላይ በማተኮሩና በጣም የታወቁ ዶክተሮችና አዳዲስ የህክምና መሣሪያዎች እያስመጣ ለአውራጃው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ለሚመጡ ሕመምተኞች ጭምር ከፍ ያለ አገልግሎት መስጠት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡

### *የልማት ሥራዎች ይካሔዱ የነበረበት ሁኔታ፡-*

*እንኳን ትልቁንና የተቀደሰውን አገር እንዲያድግና ወገን እንዲበለጽግ ለማድረግ የሚሠራ ሰፊ ሥራ ይቅርና አንድን አነስተኛ ዕቅድ እንኳን እንደታቀደው ተፈጽሞ ጥሩ ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው ብዬ እዚህ ላይ ስናገር ይህን መስዋዕት የሚለውን ቃል እስከአሁን በየክፍሉ ደጋግሜ የተናገርኩት ስለሆነ አዳማጩን ያሰለቻል ብዬ ብሰጋም አስፈላጊ ቃል ነውና እዚህም ላይ እናገረዋለሁ፡፡*

*እስካሁን በየክፍሉ የተገለጡት በወላይታ አውራጃ የተፈጸሙት የልማት ሥራዎች በሕዝቡና በአውራጃው ውስጥ በማንኛውም ክፍል በሚገኙት ከተላላኪ እስከ እኔ ባሉት የመንግሥት ሠራተኞች ከባድ መስዋዕትነት የተፈጸሙ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ሰባቱ የሳምንት ቀናት የሥራ ቀናችን ነበሩ፡፡ መንግሥታዊ እና ሐይማኖታዊ በዓላት ሁሉም የሥራ ቀናታችን ስለነበሩ አናከብራቸውም፤ አይከበሩም፡፡ ከአንዱ ቀን ሃያ አራት ሰአቶች ውስጥ የአጭር ጊዜ የእንቅልፍ ሰአቶች ተቀንሰው የቀሩት የሥራ ሰአቶቻችን ነበሩ፡፡ ስለእኔ ስነግራችሁ የቀረውም እንደእኔው አንዳንዱም ከእኔ ከበድ ባለ ሁኔታ ጊዜውን ለሥራ ይሰዋ እንደነበረ ስለምትገነዘቡት እኔን እንደምሳሌ አድርጌ እነግራችኋለሁ፡፡ ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰአት ገደማ እነቃና እስከ አሥራ ሁለት ሰአትና አንዳንዴም እስከ ተኩል ስድበሰበስ ቆይቼ ቢሮ እገባለሁ፡፡ ያቆጠቆጠ ሪዝ የማጽዳትና ቁርስም ሆነ ምሳ የመብላት ልማድ አልነበረም፡፡ ሪዝ አለማጽዳቱ የኩባውን ፊደል ካስትሮን፣ ቁርስና ምሳ ያለመብላቱ ደግሞ በማያስርብ ክኒን ይኖራል የሚሉ ስሞች አስገኝተውልኝ ነበር፡፡ በኪኒን የመኖሩ ነገር በውጪ አገር ሰዎች ዘንድ ጭምር በሰፊው ተነግሮ ስለነበረ ሰሜን አሜሪካን ስኀበኝ ሜሪ ላንድ በሚገኘው በትልቁ የባህር ኃይል ኔቫል ሆስፒታል ስታከም የምውጠው የማያስርብ ክኒን ምን ዓይነት እንደሆነ ሊያክሙኝ ተሰብስበው የነበሩት የየሙያው ሀኪሞች ሲጠይቁኝ ኢትዮጵያን ከድህነት የሚያወጣ «መስዋዕትነት» የሚባል ክኒን ነው ስላቸው የተገረሙም የተደናገጡም ነበሩ፡፡*

*በማለዳ ተነስቼ ቢሮ ስገባ ሠራተኞች ከእኔ ቀድመው ቢሮ መግባት ስለነበረባቸው የሚከተሉኝ የፖሊስ አባላትም እንዲሁ ስለሚያደርጉ እቢሮ የምቆየው እስከ ሁለት ቢበዛ ሦስት ሰአት ስለሆነ ባለጉዳዮችም በማለዳ ቢሮ መገኘት ስለሚያስፈልጋቸው ከቢሮ ወጥቼ በወረዳዎቹ ወደሚገኙ የልማት ቀበሌዎች ስዘዋወር ውዬ ከምሽቱ ሦስትና አንዳንዴም አራት ሰአት ወደ ቤት ስለምገባ አብረውኝ የሚውሉት ሕዝቡም ሠራተኛውም እንደኔው ማልደው የሚነሱ ከእኔው ጋር ስለሚውሉ ሕዝቡም ሆነ ሠራተኞች የቁርስም ሆነ የምሳለ ልምድ እንዳልነበራቸው ትገነዘባላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ጠዋት በማለዳ ሲወጣ ልጆች በእንቅልፍ ላይ ስለሆኑ ከምሽቱ ሦስትና አራት ሰአት ወደ ቤት ሲመለሱ ልጆች ስለሚተኙ አባትና ልጆች*

መረሳሳት ደረጃ እንደሚደርሱ ግልጽ ነው፡፡ እዚህ ላይ እንደ ሰው ተፈጥሮ ሁኔታ የሚያስቅ፣ የሚያስደነግጥ፣ ሲብስም የሚያስለቅስ የሆነውን ነገር ልንገራችሁ፡፡ አንዳንድ ቀን ለጉብኝት ወይም ለሥራ ወደ አውራጃው እንግዶች ሲመጡ እንደ እንግዳው ሁኔታ ምሳ ወይም እራት ስጋብዝ ልጆቼ በፊደል ካስትሮነቴ መልክ ያዩኝ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ለሥራ መጥቼ ሪዜን አጽድቼው ስለነበረ ወደ ቤቴ ስመለስ እንግዳ ቤት ትልቁ ሶፋ ላይ እንደተቀመጥኩ ከእነዚያ አባትነቴን ረስተው ከነበሩት እውጪ ከሚጫወቱት ልጆቼ አንዱ ዳዊት የሚባለው ሲሮጥ መጥቶ ከእኔ ራቅ ብሎ ሶፋው ላይ ተቀመጠና ቀስ እያለ ተጠግቶ ጭኔን ጎንተል በማድረግ አባትነቴ ሳይሆን ያ አንዳንድ ቀን የሚያየው ሪዛም ሰው ትዝ ብሎት «አንተ አባባ! ያ ጢም ያለው አባባ የት ሔደ!?» ሐዘኑ ለሥራ ከማደርገው መሩዋሩዋጥ ባይለየኝም ለጊዜ አስለቅሶኛል፡፡

እንግዲህ እናትን አድማጮች ልትገነዘቡት የሚገባው እስካሁን በአጠቃላይ የተገለጡት በወላይታ አውራጃ የተፈጸሙት የልማት ሥራዎች በሕዝቡና ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ የነበሩ የሕዝብ አገልጋዮች የየግል ጥቅማቸውን እርግፍ አድርገው ትተው በቅንነት፣ በታማኝነትና በኅብረት ሙሉውን ጊዜያቸውን፣ ኃይላቸውንና እውቀታቸውን፣ ሲያስፈልግም የግል ገንዘባቸውንና ሕይወታቸውን መስዋዕት በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ጥንታዊቷንና ባለታሪኳን ኢትዮጵያችንን ከምትገኝበት የድህነት አረንቋ መንጥቆ ማውጣት የሚቻለው ይህ ትውልድ ይህን አማራጭ የማይገኝለትን መስዋዕትነት ሲከፍል ብቻ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባዋል፡፡

### *ካጋጠሙኝ ብዙ ችግሮች ውስጥ ሁለቱን እንደምሳሌ፡-*

የእንቅፋቱና የችግሩ መጠንና ብርታት ይበላለጥ እንጂ ማንኛውም ሥራ ሲካሔድ እንቅፋትና ችግር ሳያጋጥሙት ሥራው አልጋ ባልጋ ሆኖ እንደማይፈጸም ታውቃላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለሆነም እስካሁን የተነገሩትን በወላይታ አውራጃ የተፈጸሙ የልማት ሥራዎች ስናካሂድ በየጊዜው መሰናክሎችና ችግሮች ገጥመውኝ ነበር፡፡ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ ገጥመውኝ ከነበሩት ችግሮች ውስጥ ሁለቱ ከበድ ያሉ ነበሩ፡፡ ይኸውም በአቶ ገርማሜ ነዋይ ላይ ሕዝብ አነሳስተው ወደ አውራጃው በሔደ ዘጠኝ ወራት ዕድሜው ከአውራጃው እንዲወጣ እንዳደረጉት ሁሉ በእኔም ላይ በዚያው ሁኔታ ሕዝብን አነሳስቶ ከአውራጃው እንድባረር ለማድረግ ከሁለት ክፍሎች ከባድ ጥረት ተደርጎ ነበር፡፡ ሆኖም እነኝህን ሁለት ከባድ ችግሮች እንዳላየ እያየሁና እንደልሰማሁ እግዚአብሔር በቸረኝ ትዕግስት፣ ልበ ሙሉነትና ድፍረት ችግሮቹን ተቋቁሜ፣ ሁለቱም ክፍሎች ለእኔ ባጠመዱት ወጥመድ እራሳቸው እየተጠመዱ መዋረዳቸውን ዝርዝሩን ወደፊቱ ትቼ አጠቃላዩን እነግራችኋለሁ፡፡

በንግግሬ መጀመሪያ ላይ እንደገለጽኩላችሁ የፓርላማ አባሎች ሆነው በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩትን የአውራጃው ባላባቶች የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ፊታውራሪ ታፈሰ ጠብቄ እቢሯቸው ጠርተው ካስተዋወቁን በኂላ ለግማሽ ቀን ያህል ስለአውራጃው የአስተዳደር የፍትህና የልማት ሥራዎች መሻሻል ተባብረን እንድንሠራ ስንነጋገር በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለኝን አቋም ባላባቶቹ አውቀው የተግባባን መስሎኝ ወደ አውራጃው በመጡ ቁጥር ክብራቸውን ጠብቄ እያነጋገርኂቸው አሰናብታቸዋለሁ። ይሁን እንጂ ማንም ይሁን ማን፣ ሕገ መንግስቱም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች የማይፈቅዱትን፣ ከሕዝብ ጥቅም ውጪ የሆኑ ድርጊቶችን፣ እንዳይፈጽሙ ጥብቅ መመሪያ ሰጥቼ ስነበረ ከባላባቶች ጋር የሚያጋጨን ነገር ተፈጠረ። ይኸውም ባላባቶች በተለይ ዋናው ባላባት ፊታውራሪ ደስታ ፍስሀ አውራጃውን በረገጡ ቁጥር የአውራጃው ሕዝብ እንደየችሎታው በጢስ ከሃምሳ ሳንቲም እስከ አንድ ብር በጭቃ ሹሞችና ቀበሌ ተጠሪዎች አማካይነት እያወጣ የሚሰጠውን ያለ ሕግ በሕዝብ ላይ የተጣለውን ቀረጥ የሰጠሁት ጥብቅ መመሪያ ስለሚያግድ በአዲስ አበባ ከተማ ለመንደላቀቂያ በየጊዜው ያገኙት የነበረው ብዙ ሺህ ብር ተቋረጠ። ባላባቶቹ የነልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ምልጃ ጭምር የማይበግረኝ መሆኑን ቀደም ብለው ተገንዝበው ስለነበረ መጀመሪያ አቶ ገርማሜ ነዋይን ከአውራጃው ባባረሩበት ዘዴ ተጠቅመው እኔንም ለማባረር ዶለቱ። የሕዝብን ትርታ የሚቀሰቅስ ዘዴ ፈጥረውና ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች እያመጣሁ አበላ ማስፈር የጀመርኩትን መነሻ በማድረግ «ወልደሰማዕት ከአውራጃው ውጪ ሰዎች እያመጣ ርስታችሁን ሊነቅላችሁ ነው» በማለትና በመካሔድ ላይ በነበረው ሪፎርም ጥቅማችን ይነካብናል ብለው የሚጠራጠሩትንም በመቀስቀስ የሶዶን ከተማ በየነጋው በሰከረ ፈረስ ያጥለቀልቁት ጀመር። የሽብር ፕሮፓጋንዳቸው ለቤተሰቦቼ ጭምር በሚደርስ ሁኔታ ይካሔድ ስለነበረ መኖሪያ ቤቴ በዋናው አውራ ጉዳና ላይ ስለሆነ ከቤተሰቦቼ ውስጥ አንዷ ወጥና ጠጅዋ እጅ የሚያስቀረጥምና ምራቅ የሚያስውጠው «ባሱዬ» የፈረሰኞቹን በየቀኑ ወደ ሶዶ ከተማ መጉረፍ ስላየች ሽብሩ አስደንግጧት በልብ ድካም ወድቃ ሱዳን ኢንቴሪየር ሆስፒታል ተወስዳ እንደበረ ማታ ወደ ቤት ስመለስ የተነገረኝ ትዝ ይለኛል። እኔ ግን በዚያን ጊዜ ምንም እንኳ በአዲስ አበባዎቹ አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ዘንድ ወደ አውራጃው እንደግዞት የተላኩ ሆኖ ቢቆጠርም ሕዝብ ያለምክንያት አምጾ በአንድ የአውራጃው ከፍተኛ ባለሥልጣን ላይ አደጋ ቢያደርስ ያ ሕዝብ ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቀው ሕዝቡም ደፍሮ አደገኛ ችግር እንደማያደርስብኝ ስለማወቅ አሽባሪዎቹ በሰከረ ፈረስ ወደ ሶዶ ከተማ ሲጎርፉ በመካከላቸው አያለፍኩና እንዳላየ እያየኂቸው በላንድ ሮቨሬ ከሶዶ ከተማ ወጥቼ በየወረዳዎቹ ቀበሌዎች ይካሔዱ ወደነበሩት የልማት ሥራዎች እየሔድኩ እዚያው ውዬ ማታ በምሽት ወደ ቤቴ እመለሳለሁ።

ሴረኞቹ ድፍረቴንና ልበሙሉነቴን ተገንዝበው፣ በሴራቸው የማልበገርና ወጥመዳቸው እንዳልያዘላቸው ሲገነዘቡ፣ ተስፋ ቆርጠው ባገር ላይ ሴራ

ጠንስሰው በወላይታ አካባቢ ለሚገኙት ለጋሞ ጎፋ ለኢሉባቦር፣ ለከፋና ለሌላ ክፍል ባላባቶች «ሱማሌ እንኳ ሽርጡዋን ሳትፈታ--..እኛ ግን--» የሚል ቃል በማከል ደብዳቤ እየጻፉ ቅስቀሳ ጀምረው ኖሮ ደብዳቤው የደረሳቸው «እኛ የለንበትም ልብ አድርጉ--» በማለት የተጻፈላቸውን ለመንግሥት ሰጥተዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ ምንም የሰማሁት ነገር ስለሌለ አገር ደግ ነው ብዬ በሶዶ ከተማም ሆነ በየወረዳው እየተዘዋወርኩና በተለይ ቅስቀሳ ለማካሔድ ምክንያት ያደረጉዋቸውን ከአውራጃው ውጪ እያመጣሁ በአበላ ቀበሌ ያሰፈርኳቸውን አዘውትሬ እየጎበኘሁና የልማት ሥራዬን ስሠራ ጉዳዩን የሚያጣራ ቡድን ሶዶ ከተማ ገብቶ ሥራውን ጀመረ። አጣሪው ቡድን እኔን አንድ ቀን ለሁለት ሰአት ያህል ከማነጋገሩ በስተቀር በሌላ ጊዜ ሳንገናኝ ሥራውን አጠናቆ ሔደ። በዚህ ሁኔታ ንቅናቄው ከሽፎ ወንጀለኞቹ ፍርድ ቤት ቀርበው ከአስራ አምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ተፈርዶባቸው ወህኒ መግባታቸውን በኋላም ምን ያህል ወህኒ ቤት እንደቆዩ አላውቅም ምህረት ተደርጎላቸው መፈታታቸውን ሰማሁ። እኔም እስከመጨረሻው ከወላይታ ሕዝብ ጋር እንደ አባትና ልጅ እንደወንድማማች ተፋቅረን የልማት ሥራዎች ስንሠራ ቆይተናል። ከአውራጃው ወደ ወለጋ ስሔድም ድል ያለ ድግስ አዘጋጅቶ ነጋሪት እያስጎሰመ ለባለቤቴ ጥምዝ ወርቅ ለእኔ እስካሁን የምገለግልባትን መኪና ሸልሞ ሸኝቶኛል። አሁንም ምስሌን በትልቁ አስቀርጾ በአውራጃው ሚዚዬም ሰቅሎ እያስታወሰኝ ስለሆነ ውለታውን የማይረሳ ለሌሎችም ምሳሌ የሚሆን ታላቅ ሕዝብ ስለሆነ አመሰግነዋለሁ።

ከዚህ በላይ የተገለጠው ችግር እንደተነገረው ባጭሩ የሚገለጥ ስላልሆነ ሂደቱ እያሳቀ የሚያዝናና ቁምነገሮችንም የሚያስተምር ስለሆነ ወደፊት ዝርዝሩን እጽፋለሁ የሚል ሃሳብ አለኝ። ገጥሞኝ የነበረው ሌላው ችግር እንደዚሁ ሕዝብን በኔ ላይ የሚቀሰቅስና በተለይ ሕዝቡ ተባብሮ የሚሠራውን የመንገድ ሥራ እንዲቋረጥና ከመስከረም ጀምሮ ግብሩን ይከፍል የነበረውን እንዳይከፍል ለማድረግ ነበር። ይህ ሴራ የተጠነሰሰው የሚገርመው በሕዝብ ወገንነታቸው ከታወቁትና በዘመኑ በተራማጅነታቸው ብዙ ከተነገረላቸው እላይ ከተጠቀሱት ባላባቶች ጋር እሳትና ጭድ ከነበሩት የንጉሠ ነገሥቱም ወዳጅ ከነበሩት ከፊታውራሪ በካሎ መሆኑ ነበር።

በወላይታ አውራጃ እንደባህል ሆኖ ገበያዎች የሚደሩት ቀን ሳይሆን ሌሊት መሆናቸውንና አብዛኛው ወንጀል ይፈጸም የነበረው በገባዮች ሌሊት መድራት ምክንያት መሆኑን ቀደም ብሎ መግለጤን አስታውሳለሁ። ስለገበያ ገጥሞኝ የነበረው ሌላው ችግር በተለይ የታወቁ እንደነ ፊታውራሪ በካሎ ያሉ ሰዎች በርስታቸው ላይ ገበያ እያቋቋቋሙ ከገበያተኛው ቀረጥ መሰብሰባቸው ነው። እንደሚታወቀው ያሁኑ እንጃ እንጂ በዚያን ዘመን መንግሥት እንኳን ከሕዝብ ቀረጥ የሚሰበስበው ገንዘብ ሚኒስቴር የሚያዘጋጀውን ሕግ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ተነጋግሮበት ከዚያም ለፓርላማ ቀርቦ ሲያሳልፈው ንጉሠ ነገሥተ ዘንድ ቀርቦ በነጋሪት ጋዜጣ ሕግ ሆኖ ሲታወጅ ነው እንጂ እንኳን ግለሰቦች

*መንግሥትም ከሕዝብ ቀረጥ መሰብሰብ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ እነፊታውራሪ በካሎ በዳሞት ጋሌ ወረዳ ሸንቶ በሚባለው ቀበሌ በሚገኘው ርስታቸው ላይ ገበያ አቋቁመው «ሸንቶ ቦጋለ ዋለሉ ገበያ» በሚል ርዕስ ካርኒ አሳትመው ከቦረዴ (ባህላዊ መጠጥ) ሻጭ ላይ ሳይቀር ከገበያተኛው ላይ የሚሰበስቡትን ቀረጥ ሌሎቹም በዚሁ ሁኔታ ተመሳሳይ ሕገ ወጥ ቀረጥ የሚሰበስቡትን የሚያግድ ጥብቅ መመሪያ ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ወረዳ ገዢዎች ጭቃ ሹሞችና የቀበሌ ተጠሪዎች እንዲቆጣጠሩ አደረኩ፡፡ በዚህ ቦታ ትምህርት ቤትም ከፍተው የአካባቢውን ሕጻናት ያስተምሩ ስለነበረ ይኸንኑ በጎ ሥራቸውን በማስታከክ ገበያውን ያቋቋሙት ሕዝቡን ለመርዳት ብለው እንጂ ለራሳቸው ጥቅም ለማግኘት አለመሆኑንና ጥቅም ሊያገኙበት የሚችሉትን መሬት ለትምህርት ቤትና ለገበያ ያዋሉት መሆናቸውን እየገለጡ ቢጽፉልኝና የፓርላሜንቱ ፕሬዚዳንት የነበሩትን ክቡር ሌተና ጀኔራል አቢይ አበበን አማላጅ ቢልኩም የማልበገር መሆኔን ሲገነዘቡ ወገኔ ነው የሚሉትን ሰፊ የወላይታ ሕዝብ መቀስቀስ ጀመሩ፡፡ ሕገ መንግሥቱን እየጠቀሱ መብትን አስከብር ይህን አድርግ ያን አታድርግ በማለት ለሕዝቡ የሚጽፉትን ለኔ የሚልኩልኝን የደረሰኝን እንዳልደረሰኝ ሆኜና እንደማላውቅ ሆኜ የልማት ሥራዬን ማጧጧፍ ቀጠልኩ፡፡*

*ሴረኛው አተኩረውበት የነበረው በተለይ መጀመሪያ ላይ ሕዝቡ በጉልበት ይሠራው የነበረውን መንገድ እንዳይሠራና ከመስከረም ጀምሮ ግብሩን እንዲከፍል በሰጠሁት መመሪያ መሠረት ሳይሆን አዋጁ በሚያዘው እስከ የካቲት ቆይቶ እንዲከፍል ለማድረግ ነበር፡፡ ሆኖም ሕዝቡ የሚሠራው መንገድና ግብሩንም እንደቀድሞው ምንም መንገላታት ሳይደርስበት ገንዘብ በሚያገኝበት ከመስከረም ወር ጀምሮ መክፈሉ በሁለቱም በኩል ከፍ ያለ ጥቅም ያገኘባቸው መሆኑን ስለተገነዘበ ለፊታውራሪ በካሎ ቅስቀሳ እንደኔው ጆሮ ሳይሰጥ የልማቱን ሥራ ማጧጧፍ ቀጠለ፡፡ ይሁን እንጂ የመንግሥት ለውጥ ሆኖ ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁለት ክፍል ሴረኞች ደጋፊዎችና ተወላጆች ለመበቀል ሴራ ጀምረው ሳይሳካላቸው ቀረ፡፡ ሴራውም ባለሥልጣኖች ሁሉ ሲታሰሩ ባለመታሰሬ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ የነበሩት ሴረኞች ከልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴና ከልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ጋር ስሜን ሦስተኛ አድርገው በዩኒቨርስቲው ግቢ ወረቀት ለጥፈው ወልደሰማዕት ካልታሰረ ዕድገት በኅብረት ዘመቻ አንሔድም እስከማለት ደርሰው ሌሎቹ ደግሞ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ሥልጣን እንደያዘ በራሱ ላይ እሳት የሚጭር መሆኑን ሳይገነዘብ በቀድሞው ባለሥልጣኖች ላይ ቀስቅሶት አገር ሲታመስ በዚህ እድል ተጠቅመው በጋዜጣ በሌብነት ወንጅለውኝ ነበር፡፡ እስካሁን በጣም የሚደንቀኝ እግዚብሔር ሁሉንም በሰላም ያሳለፈልኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መሪ ሆነው ቅስቀሳ ያካሒዱብኝ የነበሩት ሁሉ ለእኔ የተመኙትን መታሰርና ሞት በተከታታይ እራሳቸው ጽዋውን እየቀመሱ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ ዓለም መለየታቸው ነው፡፡*

## የአገር ውስጥና የውጪ እንግዶች የልማት ጉብኝት

*ግርማዊ ቀደማዊ ኃይለሥላሴ ሁለት ጊዜ ወደ አውራጃው መጥተው አንዴ ሳምንት ያህል በሁለተኛው አራት ቀን በአውራጃው ቆይተው ወረዳዎቹንና የልማት ቀበሌዎችን በዝርዝር የጐበኙ ሲሆን ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በስተቀር ሚንስትሮችና ከፍተኛ ባለስልጣኖች በየጊዜው ወደ አውራጃው እየመጡ ጐብኝተዋል፡፡*

*የአውራጃውን የልማት እንቅስቃሴ ለአጭር ጊዜ ለመጎተት ሌሎቹ ደግሞ እዚያው ተቀምጠው ለማጥናት አንዳንዶቹም በካኪ ለባሽነቴ በኮምኒስትነት የሚጠረጥሩኝ ለጥናት የመጡ እያስመሰሉ የሚሰልሉኝ ብዙ የውጪ አገር ሰዎች ወደ አውራጃው ይመጡ ነበር፡፡ ለስለላ የመጡትን ትቼ ከቀሩትን ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ውስጥ ቀደም ብሎ ነግሪያችሁ የነበሩት የሥራ ረዳቶቻቸውና ባለቤታቸውን አስከትለው የመጡት የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ሚስተር ሮበርት ማክነማራ ሃያ አምስት ያህል የሚሆኑ የስዊድን የፓርላማ አባላት የስዊድን የውጪ እርዳታ (ሲዳ) ዲሬክተር ሚስተር ሚሻኒክ፣ ፋኦ ልማቱን እንዲያጠና ልኮት የነበረው ቡድን መሪ ዶክተር አሊ ኤልቶም ሁለት ወር አውራጃው ተቀምጠው የከተማዎችንና የገጠር ልማት ጥናት ያካሔዱት የስዊድኑ ሉንድ ዩኒቨርስቲ በፕሮፌሰር ኦኬሶን የተመራው የፕሮፌሰሮችና የመጨረሻ ዓመት ተመራቂ ተማሪዎች ቡድን ወዘተ ናቸው፡፡ ወደ አውራጃው እየመጡ የጐበኙ ስለነበሩት እንግዶች በአጠቃላይ ይህን ያህል ከነገርኳዋችሁ በኋላ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ እንዴት ሁለት ጊዜ ወደ አውራጃው መጥተው ለብዙ ቀናት በአውራጃው ቆይተው ሊጎበኙ እንደቻሉ ባጭሩ እነግራችሁኋለሁ፡፡*

*ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በአውራጃው ይካሔድ የነበረው የልማት እንቅስቃሴ ይታይ የነበረው ለውጥ በቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎችና በውጪ አገሮችም ጭምር እየተሰማ ስለሔደ እውነትነቱን በትክክል ለማወቅ ተፈልጎ ይሁን በሌላ ምክንያት አላውቅም ሰዎቹ ተራ የሲቪል ልብስ ለብሰውና ሲቪል ታርጋ በለጠፈች ላንድ ሮቨር መኪና ሆነው የጠቅላይ ፖሊስ ባልደረባ በአንድ ኮሎኔል መኮንን የሚመራ ቡድን ጎብኚ መስለው አውራጃዋን በዝርዝር አጥንተው ለክፍፍላቸው ያቀረቡት ሪፖርት ለአገር ግዛት ሚኒስቴር ከዚያም ለንጉሠ ነገሥቱ ይደርሳል፡፡ ኮሎኔሉ እንዳቀረቡት ሪፖርት ባይሆንም ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም ብለው መስማታቸው ስለማይቀር ሪፖርቱ እንደቀረበላቸው ወደ አውራጃው መጥተው በዝርዝር ለመጎብኘትና የሰሙትን ለማረጋገጥ ሳይሆን አይቀርም ወደ አውራጃው የሚመጡ መሆናቸው ይነገረኛል፡፡ ለዝግጅት በቂ ጊዜ ባይኖረኝም ከአዲስ አበባ ጭምር ሊያግዙኝ በመጡ ወዳጆቼና በተለይ የአውራጃው ሕዝብ ሠራተኞች አስተማሪዎች ሳይቀሩ ባደረጉት ርብርብ ለንጉሠ ነገሥቱ በጣም የሚያስደስት ዝግጅትና አቀባበል አደረግንላቸው፡፡*

*ንጉሠ ነገሥቱ በአውራጃው በቆዩበት የአምስት ቀናት ጉብኝታቸው እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ አብረዋቸው የነበሩት መሳፍንቶች መኳዋንንቶችና ሚኒስትሮች በጣም*

ተደስተው ስለነበረ ለሕዝቡና ለሠራተኞች ከፍ ያለ ምስጋና እኔን ደግሞ «እኛ ብድርህን መክፈል አንችልም እግዚአብሔር ብድርህን ይክፈልህ» ብለው በማመስገንና በመመረቅ የኒሻን ሽልማትና የማዕረግ ስም እንዲሰጣቸው ያቀረብኳቸው ሁሉም ተሰጣቸው። ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ የተዘነጉ ሰዎች እንዳሉ እንድሰጣቸው መዳሊያዎች እንዲሰጡኝ አዘዙልኝ።

በ1957 ዓ.ም. በአውራጃው ይካሔድ የነበረውን የአስተዳደር ሪፎርምና የልማት እንቅስቃሴ አጥንቶ ሪፖርት ለማቅረብ ወደ አውራጃው መጥተው የነበሩት የጠቅላይ ፖሊስ ባልደረባ ኮሎኔል (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ፋንታ---ባህዳር ወር 1965 ዓ.ም. ወደ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ስሔድ በምስጢር ሪፖርቱንና ጠቅላይ ፖሊስ ለአገር ግዛት የጻፈውን ደብደቤ ሲሰጠኝ ማንነታቸውን አወቅኩ።

## መደምደሚያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት መጣጥፎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የተለያዩ የኤኮኖሚ ተቋማት እንደተገነቡ ይተርካሉ፤ የግንባታው ሂደትም አንዱ ካንዱ ልዩነት ቢኖረውም፣ ተመሳሳይነትም ነበረው። የመጀመሪያው ተመሳሳይ ገጽታ ተቋማቱ የውጭ የሰው ሀይል፣ አንዳንዴም የውጭ ድርጅት ላይ፣ በመንተራስ መታቀዳቸው፣ መገንባታቸው እና ለመጀመሪያዎቹ አያሌ አመታት በነዚሁ የውጭ ሰዎች መካሄዳቸውና መመራታቸው ነው። በአንድ የውጭ ሀይል ላይ መቆም አደጋ እንዳለው ገና በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ ትልቅ ግንዛቤ ስለነበረ፣ ከአንድ ሀገር በላይ ወዳጅ ማፍራት የተለመደ የዲፕሎማሲ እና የውጭ ግንኙነት መርህ ሆኖ ቆይቷል፤ በተቋም ግንባታ ታሪክም የተንጸባረቀው ይኸው ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአሜሪካን ኩባንያ ሲሰጥ ቴሌን የማቋቋሙና የማካሄዱ ሀላፊነት ግን የተሰጠው ለስዊድኖች ነበር። በዚህ በኩል ከቅኝ ሀገሮች ልምድ በእጅጉ ይለያል። እዚያ ሁሉም ነገር የሚሰራው በቅኝ አድራጊው ሀገር ተወላጆች ነበር፤ ይህም ቅኝ የነበረችው አገር፣ ከነጻነት በሁዋላም ቢሆን ፣ የቅኝ አድራጊዋ ጥግ ሆና እንድትቆይ ከሚያስገድዷት መረቦች አንዱ ነበር።

በኤኮኖሚው ውስጥም ይኸው ሁኔታ ይንጸባረቃል። እንደሚታወቀው፣ አፄ ምኒልክ ሆነ ብለው ባንያኖችን (የህንድ እና የፓኪስታን ተወላጆችን)፣ የአርመን፣ የግሪክ፣ የየመን (አረብ) ተወላጆችን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በንግድ ስራ፣ ወይም ሙያቸውን በመሸጥ (ለምሳሌ፣ በአናጢነት፣ በእንጨት ስራ፣ በህክምና፣ በመሀንዲስነት ወዘተ)፣ ቢቻልም ፋብሪካ በማቆም፣ በመጨረሻም መንግስትን በማገልገል ስራ ላይ እንዲሰማሩ ያነቃቁ ነበር፤ በዚህ የተነሳ ከ19ነኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ የውጭ ዜጐች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በተለይ በንግዱ ዘርፍ በስፋት ተሳትፈዋል፤ ጥሪትም አካብተዋል። በመለወጥ ላይ በነበረው ዘመናዊ ኤኮኖሚ ውስጥ የበላይነት አግኝተዋል፤ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እጅግ ጥቂት ነበሩ።

ይህ "ፖሊሲ" መነሻ ምክንያት ነበረው፤ ከ19ነኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ጀምሮ ኢትዮጵያ በሯን ለለውጥ ሀይሎች ሰፋ አድርጋ ስትከፍት፣ ካጋጠሟት ተግዳሮቶች መሀከል አንዱ፣ ዘመናዊ የነጋዴ ክፍል አለመኖር ነበር። ይህንን ክፍተት ለመሸፈን የውጭ ሰዎችን ማስገባት አስፈላጊ ሆነ። የለውጡ ሂደት እየሰፋ ሄዶ ወደ 1940ዎቹ ስንመጣ፣ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች እና የቢዝነስ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፤ በዚህ ጊዜ መንግስት ለሀገር ተወላጆች ልዩ አትኩሮት በመስጠት ያተጋ ነበር፤ አላማውም የካፒታል ባለቤት የሆነ ብሄራዊ የኢኮኖሚ መደብ ፈጥሮ ባእዳኑን መተካት ነበር።

ይህ ጉዳይ በዝርዝር ቢቀረብ ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ይወድ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉም አልተዘለለም፤ የተካ ኤገኖ ታሪክ ውስጥ በአግድሞሽ ይጠቀሳል። ከዚህ ሌላ፣ የውጭ ባለሙያዎችንና ባእዳን ማኔጀሮችን በኢትዮጵያውያን

መተካት እቅድ ነበር። በእንግሊዝኛ Ethiopianization ይባል ነበር። Ethiopianization እንደ ፖሊሲ ተይዞ በ1950ዎቹና 60ዎቹ ይሰራበት ነበር።

እዚህ መጽሀፍ ውስጥ ታሪካቸው የቀረበው ተቋማት እንዴት Ethiopianization እንዳካሄዱም በየቦታው ተጠቅሷል። አንዳንዴ ትግል ይጠይቅ እንደነበርም ተጽፏል። “ፖሊሲው” ግን በጥቂት መስሪያ ቤቶች የታጠረ እንዳልሆነ ለማሳየት የንግዱንና የቢዝነሱን ክፍል በማንሳት ቀደም ብሎ ጠቁሜአለሁ። በመንግስት ደረጃም በስፋት ተግባር ላይ ውሏል። ሁለት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይበቃል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከፈተው በ1936 ዓ.ም. አዲስ አበባ ኮተቤ የተባለው አካባቢ ነበር፤ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል መልኩ፣ ትምህርት ቤቱ የተቋቋመውና የሚመራው በፈረንጆች ነበር፤ መምህራኑ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ፈረንጆች ነበሩ፤ ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱም  በውጭ ሰዎች የተያዙ ነበሩ፤ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲውም ሲከፈቱ፣ ሁኔታው አንድ አይነት ነበር። ይህ ሁኔታ፣ ወጣት ኢትዮጵያውያውን ከዩኒቨርሲቲዎች (ከውጭም ሆነ ከአገር ውስጥ) እየተመረቁ ወደስራው አለም መግባት እስኪ ጀምሩ ድረስ ነው። ከ1940ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ Ethiopianization ስለተካሄደ፣ በአስር አመት ውስጥ (በ1950ዎቹ መጨረሻ) ብዙዎቹ የትምህርት ተቋማት (ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ጭምር) በኢትዮጵያውያን እንዲመሩ ሆኗል፤ መምህራንን መተካቱ ግን በጣም ረዘም ያለ ጊዜ ወስዷል። ሌላው ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የህክምና ዘርፉ ነበር። በዚህም መስክ እንዲሁ የውጭ ሙያተኞች ደረጃ በደረጃ በኢትዮጵያውያን ተተክተዋል። የአፍሪካ ሀገሮች ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ በብዛት ነጻ ሲወጡ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቋቁሞ አዲስ አበባን የጽህፈት ቤቱ መቀመጫ ስላረጋት፣ የአፍሪካ ዲፕሎማቶች በብዛት ይመጡ ነበር። ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያዩ፣ ከሚያስደንቋቸው ነገሮች አንዱ፣ እዚህ ሀገር ብዙ የቴክኒካዊ ስራዎች በኢትዮጵያውያን መሰራታቸው ነው። ይህንን ስሜት ማንዴላ በመጽሀፉ ውስጥ፣ ለትጥቅ ትግል ስልጠና ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ የተመለከተውን በሚገልጽበት ጊዜ ቆንጆ አድርጐ ስሜቱን ገልጿል።

የተቋማት ግንባታ ሌላው ገጽታ የጥራትና የደረጃ ጉዳይ ነው። በዚህም በኩል፣ የመንግስት አቀራረብ ለሁሉም ድርጅቶች ተመሳሳይ ነበር። የተቋም ግንባታው ፕሮጀክት አሀዱ ተብሎ ሲጀመር አንስቶ፣ የላቀ ደረጃ ያለው ድርጅት ለመገንባት ጥረት ተደርጓል። እዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት ምዕራፎች ይኸንኑ ሀቅ በተደጋጋሚ ያሳያሉ። በዚህ የተነሳ፣ ድርጅቶች ሲወለዱ አንስቶ “የፈረንጅ መስሪያ ቤት” ይመስሉ ነበር። ቅልጥፍናቸው፣ የቢሮአቸው “መልክ” ራሱ፣ የሰራተኞቹ ሁኔታ (ካለባበሳቸው አንስቶ እስከ ስራ ባህላቸው ድረስ)፣ አለም አቀፍ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ይደረግ ነበር። ሰራተኞቹም በመስሪያ ቤታቸው፣ በሥራቸውና በሙያቸው እጅግ ይኮሩ ነበር፤ በሌላ አነጋገር፣ ትልቅ

espirit de corps ነበራቸው፡፡ ይህ ስሜት በዚህ መጽሀፍ መጣጥፎችም ውስጥ ይንጸባረቃል፤ ህብረተሰቡም በበኩሉ ታላቅ አክብሮት ነበረው፡፡

ይህ ማለት የተቋም ግንባታው ሁልጊዜም በሰዓቱ ወይም በተገቢው መንገድ ተካሂዷል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ተቋማት መመስረት ከሚገባቸው ጊዜ እጅግ ዘግይተው ስለተቋቋሙ የተደቀኑባቸውን ተግዳሮቶች መወጣት ሲያስቸግራቸው እናያለን፡፡ ለዚህም እጅግ ጥሩ ምሳሌ ድርቅን ለመቋቋም በ1966 የተመሰረተው የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋምያ ኮሚሽን ነው፤ ይህ መስሪያ ቤት እጅግ የዘገየ ተቋም ነበር፡፡ በ1940ዎቹና በ1950ዎቹ በአገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ድርቅ ተከስቶ ህዝብን በፈጀ ወቅት መመስረት ነበረበት፤ ነገር ግን አልሆነም፤ ስለዚህም፣ መዘዙ ሀገርንም ሆነ መንግስትን ብዙ ዋጋ አስከፈለ፡፡

ይህ መጽሀፍ ከነጻነት እስከ አብዮት የነበሩት ሶስት አሰርቶች የተቋም ግንባታ አሰርቶች ሊባሉ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ አሰርት (በ1930ዎቹና 40ዎቹ) በየጊዜው አዳዲስ ተቋም ይፈጠር ስለነበር በህዝብ ዘንድም የፈጣን ለውጥ ዘመን ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ እዚህ ውስጥ የተካተቱት መጣጥፎች ያንንም ስሜት በመጠኑም ቢሆን ያሳያሉ፤ ያንጸባርቃሉ ማለት ይቻላል፡፡ ተቋማቱ፣ በጥራት እና አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ አኳኋን መገንባታቸው፣ ቀጣይነት ላለው ልማት መሰረት እየተጣለ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

***አርታኢው***

# ስለ ደራሲዎቹ

***መኰንን ተገኝ፡-*** በታሪክ የትምህርት ዘርፍ በባችለርና በማስተርስ ዲግሪ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) የሰለጠኑ ባለሙያ ሲሆኑ፣ በአሁኑ ወቅት የታሪክ ተመራማሪ ናቸው፡፡

**ስምረት *መድሃኔ* (ኮሎኔል)፡-** በአየር ሀይል ውስጥ የኮሎኔል ማዕረግ እስኪደርሱ ካገለገሉ በኋላ፣ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ተዛውረው በፓይለትነትና በስራ አስፈጻሚነት ሰርተዋል፤ በሚኒስቴርነትም አገራቸውን አገልግለዋል፡፡

**ሺመልስ *አዱኛ፡-*** ለብዙ አመታት የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽንን መርተዋል፤ በዚህም ጊዜ፣ ባሳዩት ከፍተኛ የአመራር ብቃት፣ ብሄራዊና አለም አቀፋዊ እውቅና አግኝተዋል፡፡ አሁን በጡረታ ላይ ናቸው፡፡

**ሺፈራው በቀለ፡-** በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ታሪክ ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት፣ *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፡- በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች* (አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ 2004) የተሰኘ መጽሀፍ አርታኢ ሆነው አሳትመዋል፡፡

**በትሩ አድማሴ፡-** በመሃንዲስነትና በአመራር ደረጃ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽንን ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ ባለሙያ ናቸው፡፡

**ተፈራ ደግፌ፡-** ግምባር ቀደሙን ኢትዮጵያዊ ባንከር የማያውቅ የዕድገት ጥናት ምሁር ይኖራል ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ ከብዙ ዓመታት የባንክ አገልግሎትና በደርግ እስር ቤት የአያሌ አመታት የእስር እንግልት በኋላ ወደውጭ ሄደው በከፍተኛ የባንክ አመራር ሥራ ላይ ለተለያዩ ዓለማቀፋዊና ብሄራዊ የባንክ ተቋማት አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

**ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ፡-** የታወቁ የግል ኢንቨስተር ነበሩ፡፡ ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ተነስተው ከፍ ያለ ካፒታል ለማንቀሳቀስ የቻሉ ሰው ናቸው፡፡

**አምባሳደር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፡-** አብዛኛው የሙያ ዕድሜያቸውን ያሳለፉት በማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነበር፡፡ በዚሁ ሥራቸውም ምክንያት ሠራተኞችን በሚመለከት የወጡ ደንቦችንና ተቋሞችን (የሠራተኛ ማህበራትንና የሠራተኛ ፍ/ቤቶችን) ተከታትለዋል፡፡ የአስተዳደር ለውጥንም በሚመለከት በሰፊው ሰርተዋል፡፡ በኋላ ላይ መንግሥት ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዛውሮአቸው በአምባሳደርነትም አገልግለዋል፡፡

**ነጋሽ ገብረማርያም፡-** በጆርናሊዝም ሰልጥነው ከአሜሪካ ከተመለሱ በሁዋላ በጋዜጠኝነት ሙያ ተሰማርተው ሰርተዋል፤ በዚህም ትልቅ እውቅና እና ተከባሪነት አግኝተዋል።

**እሌኒ መኩሪያ፡-** በጋዜጠኝነታቸውና ስለሴቶች በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በነበራቸው ተሳትፎ ታዋቂ ናቸው።

**አሸናፊ ሺፈራው፡-** የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ፣ በገንዘብ ሚኒስቴርና በፕላኒንግ ኮሚሽን በተለያዩ ከፍተኛ የሀላፊነት ቦታዎች፣ አብዮቱ እስኪፈነዳ ድረስ፣ አገራቸውን አገልግለዋል።

**አስፋው ዳምጤ፡-** ታዋቂው ደራሲ፣ ገጣሚና ሀያሲ፣ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑበት መስክ ኤኮኖሚክስ ሲሆን፣ ለብዙ አመታት በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ በተለያዩ ከፍተኛ የሀላፊነት ቦታዎች አገልግለዋል፤ ከዚያ በሁዋላ በመጻህፍት አርታኢነት በኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅትና በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ ሰርተዋል።

**ከበደ ፍሬ ሰንበት፡-** ጡረታ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በአመራር ደረጃ አገራቸውን ለረጅም ዓመታት አገልግለዋል።

**ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረ ወልድ፡-** በሀገራችን ታዋቂነት ያገኙት የወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ሥራ ላይ ባዋሏቸው የአስተዳደር ለውጦች ነው። ከዚያም የጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ በመሆን የተለያየ ለውጥ በሥራ ላይ አውለዋል።

**ዓለምሰገድ ኀሩይ፡-** በጋዜጠኝነት ለብዙ ዓመታት ሰርተዋል፤ ሰፊ አስተዋጽኦም አድርገዋል፤ በአሁኑ ወቅት በጡረታ ላይ ይገኛሉ።

**ዘውዴ ገብረ ሥላሴ (ዶ/ር ደጃዝማች)፡-** በታሪክ ሙያ የሰለጠኑና በተለያዩ ከፍተኛ የሀላፊነት ቦታዎች በመቀመጥ አገራቸውን ያገለገሉ ሰው ነበሩ። ጽሁፋቸውን በኤፍ. ኤስ. ኤስ የውይይት መድረክ ካቀረቡ ከጥቂት አመታት በኋላ አርፈዋል።

**ጠና አበረ፡-** ጡረታ እስከወጡበት ድረስ በወባ መከላከያ ድርጅት ውስጥ በተለያየ የሥልጣን እርከን ላይ በመሆን ሠርተዋል። ከዚያም የወባን መስፋፋት በሚመለከት፣ በልዩ ልዩ መንገድ (ማህበር በማቋቋም፣ ትምህርት በመስጠት፣ ወዘተ...)፣ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን፣ የመከላከል ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

**ጥሩነህ ዜና (አምባሳደር)፡-** አብዛኛውን የስራ ዘመናቸውን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲያሳልፉ እስከ አምባሳደርነት ደረጃ ደርሰዋል፤ በአሁኑ ጊዜ የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር ሆነው አገራቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ።